# ሕግ መንግሥታዊነት
# እና
# የሐሳብ ነጻነት
# በኢትዮጵያ

ግንቦት 2005

በዞን ዘጠኝ

# መግቢያ

ዞን ዘጠኝ የአራማጆች እና ጦማሪዎች ኢ-መደበኛ ቡድን ነው፡፡ ቡድኑ በአብዛኛው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በጦማሩ አስተያየቶችንና ትንታኔዎችን በማስፈር እና በየሦስት ወሩ የበይነመረብ ዘመቻ በማካሄድ የአራማጅነት ሥራ ይሠራል፡፡ ከተመሠረተ ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ ሦስት ዘመቻዎችን (በሕገ መንግሥቱ ይከበር፣ የሐሳብ ነጻነት ይከበር፣ እና የሰላማዊ ሰልፍ ይከበር በሚል) ያካሄደ ሲሆን ከ150 በላይ ጽሑፎችንም በጦማሩ በኩል አስተናግዷል፡፡

ከነዚህ ጦማሮች መካከል አብዛኛዎቹን በዚህ ጥራዝ ውስጥ ያዘጋጀናቸው ሲሆን፣ በወጡበት ቅደም ተከተል ከማዘጋጀት ይልቅ በየርዕሰ ጉዳዩ በማሰባሰብ አንባቢ በመረጠው ርዕስ ላይ አትኩሮ እንዲያነብ በማድረግ አሰናድተነዋል፡፡ ይህንን በምናደርግበት ሰዓት የዞን ዘጠኝ አባላት የጻፉትን በሙሉ ስማቸውን ሳንጠቅስ ያስተናገድን ቢሆንም፣ ከሌሎች ሰዎች ተልከውልን በጦማራችን ያስተናገድናቸውን ጽሑፎች ጸሐፊዎች ግን ገልፀናል፡፡

ጽሑፎቹ በተለያዩ ጊዜ የተጻፉ እንደመሆናቸውና የተጻፉበት ጊዜንም የሚያንፀባርቁ በመሆናቸው ብሎም ጦማሩ ላይ የሰፈሩበትን መልክ ሳንቀይር የሰበሰብናቸው በመሆኑ ያለፈባቸው ነገሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፤ በተጨማሪም ጥቃቅን የአርትኦት እንከኖች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ አንባቢዎች፣ እነዚህን ክፍተቶች እየሞሉ እንዲያነቡ ከይቅርታጋ እንጠይቃለን፡፡

ጽሑፎቹን ሰብስበን በኤሌክትሮኒክ ኮፒ ማስቀመጥ ያስፈለገን፣ ለወደፊቱ ማነፃፀሪያ ይሆናሉ ብለን በማመናችን መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

መልካም ንባብ!

Email: zone9ners@gmail.com
Twitter: @zone9ners

# ማውጫ

## የሕግ የበላይነት


ሕገ መንግሥታዊነት ....................................................................1
ግልጽ ደብዳቤ ለጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ....................................4
ሕግ ምርኩዝ ነው ዱላ? ...................................................................7
ሰብኣዊ መብቶች፣ ሕገ-መንግሥቱ እና መንግሥት ........................................10
የቴሌኮም ማጭበርበር ሕጉ አወዛጋቢነት .....................................................12
ግልጽ ደብዳቤ ለአቶ ደብረፅዮን ገ/ሚካኤል እና ለአቶ በረከት ስምኦን ........................16
መብት በአደባባይ ........................................................................19
የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የመውጣት መብቶች ..............................................22
ሳንሱር እና ሕግ፡ ከትናንት እስከዛሬ ......................................................23
እስርቤቶቻችንና ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች ..................................................27


## የመለስ አገዛዝ


የመለስ ዜናዊ ፲ ታላላቅ የአፍ ወለምታዎች ...................................................31
የሁለት 'ሚኒስትሮች' ወግ ..................................................................33
ጠቅላያችን የማን ናቸው? ....................................................................34
የመለስ ዜናዊ 'ሀሁ' በስልጣን ጎዳና ............................................................37
መለስ ወደ ውጭ - መለስ ከውጭ ...........................................................40
መለስ ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያውያን .....................................................44
ማን ሥልጣን ላይ ተወለደና? ...............................................................46
ከመለስ በኊላ! ............................................................................48
ምናልባት፣ ምናልባት… ከመለስ በኊላስ? ...................................................51
ባልቻን ፍለጋ ................................................................................54
የመለስ ሞት ለምክር ቤቱ ምኑ ነው? ........................................................56
ስለ ግለሰብ ማሰብ ይብቃን! ..................................................................58
የእኛ ጀግንነት ..............................................................................60
የመለስ ውርስ እና ራዕይ ....................................................................63
ስለጠቅላይ ሚንስቴር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ፡ ያልተባሉና ያልተነገሩ ..........................67
ቤተመንግሥቱ ኃይለማርያምን የሚያሠራ ይሆን? ............................................70
ዘመቻ ገለአድ ................................................................................73

## ተቃዋሚዎች


"መክሸፍ" እንደተቃዋሚ ፓርቲዎች ....... 76

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችና የመደራደር አቅማቸው (ክፍል 1) ....... 80

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የመደራደር አቅም (ሁለት) ....... 83

ተቃዋሚን በአንድ የመፈረጅ ጣጣ ....... 88

'ተቃዋሚ' ስንል ....... 90

ተቃዋሚውን ማን ገደለው? ....... 93


## የብሔር ፖለቲካ


የካምፓስ ተማሪዎች የጎሳ ግጭት፤ ከመነሻው እስከ መድረሻው ....... 96

ትግራይ እና ሕወሓት ምንና ምን ናቸው? ....... 102

የዘር ፖለቲካ አዳላጭነት ....... 105

ፎንቱ ፎኒፍ ሪፊታ ጄናን ኢቲሌን ጂቢቻ ቲ ካቴ
("ስጋ ለስጋ ይደነግጣል ቢባል ጥጃ እንኳ በቁርበት ደነገጠች") ....... 107

እንሄዳለን - አትሄዱም ....... 110


## ምጣኔ ሀብት


GTP የት አደረሰን? ....... 114

ነጻነት እና ዳቦ ....... 117

ሳንሱር ዋጋ ያስከፍላል ....... 120


## ትምህርት


ትምህርት… ወዴት ዘመም ዘመም? ....... 122

የትምህርት ጥራት ነገር (ክፍል አንድ) ....... 127

የትምህርት ጥራት ነገር (ክፍል ኹለት) ....... 130

ስለምንስ ከምሁራን መካከል ትፈልጉኛላችሁ?! ....... 133

የዩንቨርስቲው ምኅዳር ....... 136

ምሁርነት እና ምሁር ....... 140


## ማኅበራዊ


አንባቢውን ኢትዮጵያዊ ፍለጋ ....... 142

ስደትና ፍቅር ....... 146

‹‹ሕዝብ›› ምንድን ነው? ....................150
የሴቶች ወጪ <=> የወንዶች ገቢ ....................152
የትችት ባሕላችንን ብንተቸውስ? ....................154
አፋዊነት… (Sweet Talk) ....................157
ባርነት በዘመን ሲዋጅ? ....................160
ዳያስፖራው ጽንፈኛ ወይስ ተስፈኛ? ....................162
የእነርሱ እና የእኛ ሕዳሴ ....................167
“ጠንቅቆ” የመጻፍና አለመጻፍ ጉዳይ ....................170
የፍርሐት ዘመን ....................171
ወጣት ሴት የመሆን ጣጣ ....................173
ወጣት ወንድ የመሆን ጣጣ ....................176
ስለ ወንድና ሴት የመጻፍ ጣጣ ....................179
ልፈራ የሚገባኝ “ሕይወቴን ያለክብር እንዳልመራ” ነዉ እንጂ “ክብር የተነፈገዉ ሕይወቴን እንዳላጣ አይደለም፡፡” ....................181
ሕፃናትና ኢትዮጵያችን ....................183
የቀለም ልዩነት(መድልኦ) በአገራችን ኢትዮጵያ ....................185
የደሞዝ Vs. የጠብሽ* ሰሞን ....................188
ከተሜውን ናፍቆት ....................191
አንድ እሁድን በማረሚያ ቤት… ....................194
ኢትዮጵያውያን ፍቅር ያውቃሉ? ....................197
ሴት የመሆን ጥቅሞችና መታደሎች ....................200
የቅድመ ምርመራ ቅድመ ምርመራ ....................203
የስደተኛው ማስታወሻ ከአውሮፓ ....................205

## ሃይማኖት

ኹለት ዓይን፣ ኹለት ዕይታ ....................209
የዓለም ሃይማኖቶች እና ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ....................213
መጅሊሱን ከውስጥ ስንመለከተው ....................217

## የጉዞ ማስታወሻ

የጉዞ ማስታወሻ፤ መቐለን በአንድ ቀን ....................221

የጉዞ ማስታወሻ፤ ሥልጣኔ ወደላይ እና ወደታች ....................................................223
የጉዞ ማስታወሻ የቀሰቀሰው የጉዞ ማስታወሻ ከታሪካችን ታሪክ ምጸቶችና ቁጭቶች ጋር!...229
አክሱምን ወላይታ አገኘሁት!!! (የአርባ ምንጭ ጉዞ ማስታወሻዬ) ....................................233
ፎቶግራፍ የሌለው የጉዞ ማስታወሻ.....................................................................239

## መጽሐፍት

መጽሐፍ፤ ከወዴት አለህ?.................................................................................243
የቃሊቲው መንግሥትን እኔ እንዳነበብኩት ...........................................................245
የ"ኢሕአዴግ ቀይ እስክሪብቶ"ን እኔ እንደወደድኩት… .............................................248
ዋኤል ጎኒም ኢትዮጵያዊ ቢሆን ኖሮ…? ...........................................................250

## የጎረቤት አገር ፖለቲካ

እኛና ሶማሊያ ..................................................................................................252
አንድ ለመንገድ፡- ከካምፖሎጀው ፍጥጫ ማግስት..............................................255
ኬንያ ከነጻነት እስከ ነጻ ምርጫ ..........................................................................257
የውኃ-ፖለቲካ እና የአባይ ጉዳዮች፡ ወፍ በረር ቅኝት ...........................................262

## እግር ኳስ

የኢትዮጵያ የእግር ኳስ ቡድን የአዲስ ጉዞ ጅማሬ .............................................268
እግርኳሳችንና ተግዳሮቶቹ… .............................................................................271
ስለግብ ጠባቂዎች እስኪ እንነጋገር .....................................................................274
የዓለም ዋንጫው ለኢትዮጵያ ምኗ ነው?..............................................................276

## ነጻ ሐሳብና ሚዲያ

ቀዩ መስመር ...................................................................................................281
"መክሸፍ" እንደ ኢትዮጵያ ሚዲያ - መጽሔቶች ...................................................283
የግል ፕሬሱ ለአቅመ አማራጭነት ብቁ ነውን? ....................................................286
ድምፃችን ይሰማ!.............................................................................................290
ልማታዊ ጋዜጠኛነት ወይስ ይሁንታን ማምረት? ...................................................293
እንዴት እንደመጥ?............................................................................................297
ዳኛቸውና ገዢ ሐሳቦቹ ....................................................................................299
"አራማጅነት" በኢትዮጵያ ...............................................................................302

ነጻ ሐሳብ የማያውቁት ኤፍኤሞቻችን ........ 306
የበይነመረብ ደህንነት (Internet Security) አንድምታዎች! ........ 308

## ሌሎች

የያዘን አባዜ ........ 311
የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሞያዎች ማኅበር ዛሬ ........ 313
ፖካ ዮኬ፣ IDIOT PROOF — ETHIOPIA ........ 315
የኪራይ ሰብሳቢ ማዕበል ........ 317
አባይን መልሱልኝ! ........ 320
የኛ ኃይል ........ 323
ከሞቱ ዜና ጋር በተያያዘ ........ 325
የታክሲ ሰልፍ መጀመሪያውና መጨረሻው ........ 327
የታክሲዎቻችን ነገር ........ 329
‘ሰንደቁ’ ላይ ያለው ‘ዓላማ’ ........ 331
በኢትዮጵያ የቡድን አመራር ተጀምሯል? ........ 334
የቀይ ለባሾቹ ውሎና አዳር ........ 336
ሁለት ማስታወሻዎች ለኢሕአዴግ ........ 339
“የተዘነጉት እስረኞች” እና የተዘነጋው የቤተሰቦቻቸው ስቃይ ........ 342
Development in Silence, Democracy’s unbecoming! ........ 344

## ለውጥ

ኢሕአዴግ ሥልጣኑን በምርጫ ይለቃል? ........ 347
አብዮት ወይስ አዝጋሚ-ለውጥ? ........ 350
ለውጥን መቋቋም እና መፍራት ........ 354
የሥርዐት ለውጥ እና ሃይማኖቶች ........ 357
1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት እና የነጻ ማኅበራት ፋይዳ ........ 361

# ሕገ መንግሥታዊነት

የፈረንሳዩ ንጉስ ልዊ 17ኛ የአምባገነንነት መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ስልጣኑን ሲያስረግጥም 'I am the State' በማለት ነው፡፡ አዎ ልዊ 17ኛ የአምባገነንነትን መጨረሻ ጫፍ አሳውቆናል፡፡ ‹ሀገር የእኔ፤ እኔም ሀገር› ብሎ ማወጁ ‹የፈለኩትን ማድረግ እችላለሁ፣ ፈላጬም ቆራጬም እኔ ነኝ!› እንዲል አደርጎታል፡፡

እንግዲህ በተለየዩ ሀገራት የመንግስት አካላትን ስልጣን በሕግ መገደብ አስፈላጊ የሆነት ዋነኛ ምክንያት እንዲሃ ያለውን ልቅ የስልጣን ምኞት ለማለዘብ ነው፡፡ ሕገ መንግስት ደግሞ ስልጣንን ለመገደብ ተብለው ከሚቀመጡ ገደቦች አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ግን ሕገ መንግስት መኖሩ ብቻ ባለስልጣኖችን ስርዓት ለማሲያዝ ይበቃልን?

## ሕገ መንግሥታዊነት ስንል

ሕገ መንግስታዊነት መነሻውም መድረሻውም ሕገ መንግስቱ ነው፡፡ የሕገ መንግስታዊት ፅንሰ ሀሳብም ከሕገ መንግስት ፅንሰ ሀሳብ ጋር አብሮ የዳበረ ሀሳብ ነው፡፡ Walton Hamilton የተባሉት የህግ ባለሙያ ሕገ መንግስታዊነትን ሲያብራሩ "Constitutionalism is the name given to trust which men to repose in the power of words engrossed on parchment to keep the government in order." ማለትም ‹‹ሕገ መንግስታዊነት ሰዎች በፅሁፍ ለተቀመጡት እና መንግስትን ስርዓት ለሚያስገቡት ቃላቶች የሚሰጡት እምነት ነው፡፡›› በማለት ነው፡፡ በጥቅሉም ሕገ መንግስታዊነት ስንል ሕገ መንግስቱን ተግባራዊ ማድረገ ማለታችን ነው፡፡ ከዚህ መሰረታዊ ሀሳብም ሁለት አንኳር ጉዳዮችን ማውጣት እንችላለን፡

*እምነት (Trust)*

እምነት ሰዎች በሕገ መንግስቱ ተማምነው እና ሕገ መንግስቱን እንደ ድጋፍ አድርገው በስርዓቱ ውስጥ የሚኖሩበት ተስፋ ነው፡፡ ሰዎች ሕገ መንግስቱን የሚያከብሩት ሌሎችም እንደኔ ሕገ መንግስቱን ያከብሩታል፤ አናከብርም ቢሉ እንኳን መንግስት ይሄን አመኔታየን ያስከብርልኛል ብለው ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ በሕገ መንግስቱ የተቀመጡት ቃላት በስርዓቱ ያላቸውን አመኔታና በሕግ መንግስቱ ላይ ያላቸውን መመካት ገላጭ ነው፡፡ ተበዳይ ‹ኧረ በሕግ አምላክ› ብሎ መብቱን ሲጠይቅ፤ በዳይ (መንግስትም ሆነ ግለሰብ) ሕግን አስታውሶ እራሱን ከተግባሩ ሲገታ፤ ይሄ ነው ዜጎች በሕጉ ላይ ያላቸው እምነት፡፡ ‹ሕጉን አምኝ› እንዲሉ፡፡

*መንግስትን ልክ ማስገባትና መገደብ (Limited and Restrained Government)*

ሌላው የሕገ መንግስታዊነት ዋነኛ ግብ እና ዓላማ፤ መንግስትን በሕግ በተሰጠው ማዕቀፍ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ እና ከተሰተው የስልጣን ገደብ ውጭ ዝንፍ እንዳይል እንደ መቆጣጠሪያነት ማገልገሉ ነው፡፡ በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር መንግስት የዜጎች ይሁንታ ውጤት እንደመሆኑ መጠን፤ ይሄ ይሁንታም በሕገ መንግስቱ የተገለፀ እና በሕገ መንግስታዊነት የሚተረጎም ነው፡፡ ዜጎች መንግሰታቸውን ሲያበጁ ያንተ ስለጣን እስከዚህ ነው፤ ከዚህ በላይ መጓዝ አትችልም ብለው በሕግ ለክተው ስልጣኑን ለመንግስት ይነግሩታል፤ መንግስትም በተሰመረለት ክበብ ውስጥ ይጫወታል፤ ያኔም ሕገ መንግስታዊነት አለ እንላለን፡፡ ስልጣኑ ተገድቦ ሕግን የሚተገብር መንግስትም (Limited Government) የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ዋነኛ ምሰሶ ነው፡፡

## ሕገ መንግሥቱ ስለ ሕገ መንግሥታዊነት

የማንኛውም ሀገር ሕገ መንግሥት በመሠረታዊነት ባለ ሁለት ጫፍ (Double Edged) ነው፡፡ በአንድ በኩል ለዜጎች እና ለመንግሥት መብት ይሰጣል፣ ግዴታም ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ መብቶች እና ግዴታዎች እንዴት መሬት ይነካሉ፣ በማን ይፈፀማሉ ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ እንግዲህ ሕገ መንግስታዊነትን በዚህ በሁለተኛው ጫፍ ላይ ቆሞ እናየዋለን ማለት ነው፡፡

### ሕገ መንግሥት ያለ ሕገ መንግሥታዊነት

ሕገ መንግስታዊነት ዘመናት በጨመሩ ቁጥር አብሮ እያደገ የመጣ ሀሳብ ሲሆን አሁን ባለው መሰረታዊ መግባባትም ሕገ መንገግስታዊነት ማለት መንግስትን እንደ መገደቢያ መሳሪያ፣ የፈላጭ ቆራጭነት ተቃራኒ (The Antithesis of Authoritarianism) እንዲሁም የአሉታዊው አምባገነንነት አዎንታዊ ፀር ተደርጎ የሚወሰድ ሰፊ ሀሳብ ነው፡፡ አዎ ሕገ መንግስት የሕግ የበላይነት ዋነኛ መሰረት ነው፡፡ ነገር ግን ሕገ መንገስታዊነት በሌለበት ሕገ መንግስት ከወረቀት ላይ ነብርነት አይዘልም፤ አስፈላጊነቱም እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ ለዚህ ጥሩ ማነፃፀሪያ የሚሆኑን የ1923ቱ የኢትዮጵያ ሕገ መንገስት እና የ1947ቱ የተሻሻለው ሕገ መንግስት ናቸው፡፡ የ1923ቱ ሕገ መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው መሬቱም፣ ሕዝቡም ሕጉም የንጉሰ ነገስቱ ነው ብሎ ፍፁማዊ እኔ ሀገር ነኝን (I am the State) ይሰብካል፤ በሕግ መግዛት (Rule By Law) እንጅ ለሕግ መገዛት (Rule of Law) ፈፅሙ ያልተፈቀደ እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡ ይሄ ሕገ መንግስት ወደ መሬት ወረደም አልወረደም ለዜጎች የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡

በሌላ በኩል የተሻሻለው 1947ቱ ሕገ መንግስት ደግሞ 20 የሚበልጡ አንቀፆችን፤ መምረጥ እና መመረጥን መብት ጨምሮ ለዜጎች የተሰጡ መብቶችን ለመደንገግ አውሏቸዋል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያዊያን ህይወት መሻሻል አለመቻሉ ለንጉሱ ስርዓት ውድቀት ዋነኛ መነሻው ነበር፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ሕገ መንግስታዊነት አለመኖሩ ነው፡፡ እናም ሕገ መንግስታዊነት ከሌለ የሕገ መንግስት መኖር በህግ መግዛትን እንጅ ለሕግ መገዛትን አያመጣም፤ ጥቅሙም አይታይም፡፡

### ሕገ መንግሥታዊነት 'በልማታዊት' ኢትዮጵያ

የአምስተርዳሙ ነዋሪ እና በኢትዮጵያ ላይ እጅግ ብዙ ጥናቶችን እና ምርምሮችን ያደረጉት ፕሮፌሰር ጆን አብኒክ 'Ethiopia Ethnicity and Constitutionalism in the Contemporary Ethiopia' ባሉትና የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት (የኢፌድሪ ሕገ መንግስት) ላይ ባተኮረው ፅሁፋቸው "When reading the constitution it is also notable that how far the proclaimed text s removed from the actual practice of the political culture and social relations in." በማለት ‹ሕገ መንግስት ወዲያ፤ ተግባር ወዲህን› ያዜሙልናል፡፡

እንደ ፕሮፌሰር ጆን አብኒክ ሁሉ በዛ ያሉ የምዕራብ የሰብዓዊ ተቋማት፣ የተለያዩ መንግስታት እንዲሁም የተለያዩ ኢትዮጵያዊያን ሕገ መንግስቱና እና መሬት ላይ ያለው እውነታ እጅግ ይለያያል እናም ኢህአዴግ በእጁ ያለውን ሕገ መንግስት ያክብር እያሉ ይማፀናሉ፡፡

### ሕገ መንግሥቱን ማን ያክብረው?

የኢፌድሪ ሕገ መንግስት አንዳንድ አካላት እንደ አፍራሽ ሰነድ ቢመለከቱም አለም ዓቀፍ የሰብዓዊ ስምምነቶችን ሙሉ ለሙሉ መቀበሉ፤ እንዲሁም ከአጠቃላይ ከአንቀፆቹ ሲሶ (30 አንቀፆች) ያህሉን ለዜጎች መብትን ለመዘርዘር እና ለመስጠት ማዋሉን ስንመለከት፤ ሀገሪቱ ዘመናዊ የሕገ መንግስት ስርዓት ውስጥ ከገባች ጊዜ ጀምሮ የዜጎችን መብት በተሻለ ደረጃ በመለገሱ ረገድ ትልቅ እምርታን ያሳየ ሕገ መንግስት እንደሆነ እንድንረዳ ያደርገናል፡፡ ታዲያ ይህ ሁሉ መብት በሽ የሆነበት ሕገ መንግስት ምነው ተቃውሞ በዛበት; ብለን ስንጠይቅ፤ መልሳችን ‹ሕገ መንግስታዊነት› የሚል ነው፡፡

የኢፌድሪ ሕገ መንግስትም ሕገ መንግስታዊነት ወሳኝ እና ዋነኛ የስርዓት አካል አድርጎ በመውሰድ በተለያዩ አንቀፆቹ ሕገ መንግስቱ እንዲከበረና ሕገ መንገስታዊነት እንዲሰፍን ያስገድዳል፡፡
በጥቅሉ በአንቀፅ 9 ንዑስ ቁጥር 3 ላይ ‹‹ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግስት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌሎች ማሕበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው ሕገ መንግስቱን ማስከበርና ለሕግ ተገዥ የመሆን ሀላፊነት አለባቸው፡፡›› በማለት ሁሉም ዜጋ ላይ ግዴታን ይጥላል፡፡

እንዲሁም በተለየ ሁኔታ የተለያዩ አካላትን ሕገ መንግስታዊነት ይስን ዘንድ እንዲሰሩ ያስገድዳል አንቀፅ 13 ንዑስ ቁጥር 1 ላይ ‹‹በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌደራል መንግስትና እና የክልል ህግ አውጭ፣ ሕግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካላት በዚህ ምዕራፍ (በሕገ መንግስቱ ምዕራፍ ሶስት የተካተቱትን መብቶች እና ግዴታዎችን ለማለት ነው) ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፡፡››፣ አንቀፅ 51 ንዑስ ቁጥር 1 ላይ

‹‹የፌደራሉ መንግስት ሕገ መንግስቱን ይከላከላል፣ ይጠብቃል፡፡›› ብሎ ያስቀምጣል፡፡ አንቀፅ 74 ንዑስ ቁጥር 13 ላይ ‹‹ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሕገ መንግስቱን ያከብራል፤ ያስከብራል፡፡›› በማለት ጠቅላይ ሚኒስትሩን የሕገ መንግስታዊ ግዴታ ተወጭ ያደርገዋል እንዲሁም አንቀፅ 87 ንዑስ ቁጥር 4 ‹‹የመከላከያ ሰራዊቱ በማናቸውም ጊዜ ለሕገ መንግስቱ ተገዥ ይሆናል፡፡›› በማለት የመከላከያ ሰራዊቱ ለሕገ መንግስቱ በመገዛት ሕገ መንግስታዊነትን ያሰፍን ዘንድ ያስገድደዋል፡፡

እንግዲህ ሕገ መንግስታዊነት ይኖር ዘንድ እኒህ ሁሉ ግዴታዎች በሕገ መንግስቱ ተቀምጠው ነው፤ መንግስት ‹የምን ሕገ መንግስት› በማለት የመብት ጥሰቶች እና ኢ-ሕገመንግስዊነት አሰፍኗል ተብሎ እየተነገረ ያለው፡፡

**ሕገ መንግሥታዊነት እንደ አጀንዳ**

ኢሕአዴግ ከምርጫ ዘጠና ሰባት ወዲህ በተቃዋሚው ጎራ ላይ ከለጠፋቸው ታፔላዎች አንዷ ‹የቫይማር ሪፐብሊክ (Weimar Republic) ናፍቆት› ትሰኛለች፡፡ በአጭሩ ሀሳቡ ከአንደኛው የአለም ጦርነት በኋላ የነአዶልፍ ሂትለር The Third Reich እስኪመሰረት ድረስ የነበረችው ጀርመንን ለማመላከት ሲሆን፤ ኢህአዴግ ሀሳቡን ሲያስቀምጥም ‹‹ተቃዎሚዎች እንደ ድህረ የመጀመሪያው የአለም ጦርነቷ የቫይማር ሪፐብሊክ ኢህአዴግን በማድከም ወደ ቫይማር ሪፐብሊክነት ቀይረው፤ በመጨረሻም ሒትለር የየቫይማር ሪፐብሊክን ግሩም ሕገ መንግስት ቀዳዶ እንደጣለው ሁሉ እነዚህ ተቃዋሚዎችም የኢፌድሪ ሕገ መንግስትን ቀዳደው ለመጣል የተዘጋጁ ናቸው›› እያለ በተለያዩ ሰነዶቹ ላይ ትችቶቹን ያቀርባል፡፡

ተቃዋሚው ጎራ ‹የሕገ መንግስት ይሻሻል› ጥያቄውን እንደ ያዘ ሕገ መንግስታዊነት እንዲሰፍን ቢተጋ ኢህአዴግን አጀንዳ ከማሳጣትም አልፎ ‹ሒትለር መጣብህ› ከሚል አለቅጥ የሚጮህ ኢህአዴግዊ ጅራፍ እራሱን ይጠብቃል፡፡ ለዜጎችም ቀላል እና የሕግ ጥልፍፎሽ ውስጥ የማያስገባ የመብት ጥያቄ መሆን ይችላል፤ **ሕገ መንግሥታዊነት ይስፈን - ሕገ መንግሥቱ ይከበር** እንደማለት፡፡

# ግልጽ ደብዳቤ ለጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ

**ጉዳዩ፡- ሕገ መንግሥቱ በመንግሥት እንዲከበር ስለመጠየቅ**

የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር፣

ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 74 ላይ የጠቅላይ ሚኒስትርን ሥልጣን እና ተግባር ሲደነግግ፥ ቁጥር 13 ላይ "[ጠቅላይ ሚኒስትሩ] ሕገ መንግሥቱን ያከብራል፣ ያስከብራል" ይላል። ትንሽ ከፍ ብሎ ደግሞ በቁጥር 8 ላይ "የመስተዳድሩን ሥራ አፈጻጸምና ብቃት ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ የሆኑ የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል" ይላል።

እናም እርስዎ በቅርቡ አመራሩን የተረከቡት መንግሥት በተለያዩ መንገዶች ሕገ መንግሥቱን በመጣስ የመቃወም፣ የመደራጀትና ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን እንደወንጀለኝነት እንዲፈሩ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እያደረገ በመሆኑ እና በውጤቱም ብዙ ንጹሐን ዜጎች በሠላማዊ ትግል ተስፋ እየቆረጡ እንዲሳደዱ፣ በፖለቲካው ውስጥ ተሳትፎ እንዳያደርጉ፣ "አሸባሪ" ድርጅቶችን እንዲቀላቀሉ እያስገደደ መሆኑን በመታዘቤ ይህንን ግልጽ ደብዳቤ ልጽፍልዎ ተገድጃለሁ።

አገራችን ኢትዮጵያ የኢሕአዴግ ብቻ ያልሆነችውን ያክል እርስዎም በጠቅላይ ሚኒስትሩ መንበር ላይ እስካሉ ድረስ በእኩልነት እና በቅንነት የሚያገለግሉት የኢሕአዴግ ወዳጆችን ብቻ ሳይሆን የኢሕአዴግ ነቃፊዎችንም ጭምር እንደሆነ ይዘነጋዎታል ብዬ ስለማልገምት ላስታውሶት አልደፍርም፤ ነገር ግን በተለያዩ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች የተተበተበች ድሀ አገር ውስጥ የሚኖር ገዢ ፓርቲ ከደጋፊዎቹ ይልቅ ተቃዋሚዎች ሊኖሩት እንደሚችል መገመት ጥልቅ ምርምር ማድረግ አይጠይቅም። ይህንን የምናገረው ሕዝብ ሆኜ በሕዝብ ውስጥ የሚነገረውንና የሕዝብን ብሶት እየኖርኩኝ በማየቴ ነው።

ከላይ ከጠቀስኩት እውነት በሚጻረር መልኩ ግን ከላይ እስከታች ድረስ በተዘረጋው የመንግሥት ስርዓት ውስጥ በኃላፊነት የተመደቡ ባለሥልጣናት፣ አስፈጻሚዎች እና የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች በአገሪቱ ተቃዋሚ የሌለ እስከሚመስል ድረስ ከሰብኣዊ እስከ ቡድን መብቶችን በመጣስ እና በማፈራረስ በገዛ አገራችን የሁለተኛ ዜግነት ስሜት እንዲሰማን እያደረጉን ይገኛል። በግሌ መንግሥት እና ሹመኞቹ መብትን ለማፈን የሚያወጣውን ወጪ ሕገመንግሥቱን ለማክበር ቢያወጡት አገሪቱ እውነተኛ ለውጥ ታስመዘግባለች ብዬ አምናለሁ።

የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር፣

ሕገ መንግሥቱ በመንግሥት እየተጣሰ ነው ስል ያለምክንያት አለመሆኑን ጥቂት ምሳሌዎችን በመጥቀስ እንዳስረዳ ይፍቀዱልኝ፡-

- አንቀጽ 10 (2) - "የዜጎች እና የሕዝቦች ሰብኣዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ።"

**እውነታው፡-** ሕግ አስከባሪ ፖሊሶች የግለሰቦችን ሰብኣዊ መብት በአደባባይ ይጥሳሉ፣ ሰዎች በፖለቲካዊ አመለካከታቸው ማኅበራዊ፣ ስነልቦናዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ውስጥ የሚገቡበት አጋጣሚ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ነው።

- አንቀጽ 12 (1) - "የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት"

**እውነታው፡-** የተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለየትኛውም የግል መገናኛ ብዙኃን በራቸውን ዘግተው ጥያቄ የሚያስነሱ ጉዳዮች ላይ ሕዝቡ መልስ ከማግኘት ይልቅ በአሉባልታዎች ቅብብል እንዲደናበር ተጨማሪ እንቅፋት እየሆኑ ነው።

- አንቀጽ 20 (3) - "[የተከሰሱ ሰዎች] በፍርድ ሒደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር፣ በምስክርነት እንዲቀርቡ ያለመገደድ መብት አላቸው"

**እውነታው፡-** በመንግሥት የሚተዳደሩት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ እና ባለሥልጣናትም ጭምር፣ በተለያዩ ጊዜ ክስ የተመሰረተባቸውንም ያልተመሰረተባቸውንም ጋዜጠኞች እና ሌሎችም ተቃዋሚዎች ያውም ‹‹በሽብርተኝነት›› የመወንጀላቸው ነገር የማያቋርጥ የዕለት ተዕለት ድራማ እየሆነ መጥቷል።

- አንቀጽ 21 (2) - "[የታሰሩ ሰዎች] ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሃይማኖት መሪዎቻቸው ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኟቸውም ዕድል የማግኘት መብት አላቸው"

እውነታው፦የማረሚያ ቤት ኃላፊዎች የፈለጉትን ሰው ጠያቂ እንዳይኖረው፣ ወይም የሚጠይቁትን ሰዎች ማንነት የመገደብ ሥራ በገዛ ፍቃዳቸው በየጊዜው እየፈጸሙ ይገኛሉ፡፡ እንደምሳሌም ከዚህ ቀደም ብርቱኳን ሚዴቅሳ በታሰረችበት ወቅት ጠያቂዎች እንዳይጎበኟት ሲከለከሉ በፍርድ ቤት ክስ መስርታ እና በፍርድ ቤቱ መብቷ ተፈቅዶ አልተከበረላትም፤ አሁንም የ18 ዓመት የእስር ፍርድ ላይ የሚገኘውን ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን ለመጠየቅ የሚችሉት ቤተሰቦቹ ብቻ እንዲሆኑ አላግባብ በማረሚያ ቤቱ ጥበቆች ተደርጓል፡፡

- አንቀጽ 29 (2) - "ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሐሳቡን የመግለጽ ነጻነት አለው፡፡ ይህ ነጻነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ውስን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሐሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነጻነቶችን ያካትታል፡፡"

እውነታው፦ ይህ አንቀጽ በአሁኑ ሰዓት በገደል ጫፍ ላይ ቆሟል፡፡ ጋዜጦች ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ እየታገዱ ነው፤ ማተሚያ ቤቶች በተለይ የፖለቲካ ጋዜጦችን እየመረጡ እንዳያትሙ በመንግሥት ባለሥልጣናት ጫና እየደረሰባቸው ነው፣ ድረገጾች እና ጦማሮች ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይነበቡ እየተደረገ ነው፡፡

- አንቀጽ 29 (5) - "በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም የመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙኃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ያደርጋል፡፡"

እውነታው፦ የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት እና የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በመንግሥት የሚተዳደሩ ድርጅቶች ሆነው ሳሉ የገዢውን ሐሳብ ብቻ የሚያንፀባርቁ፣ በአንድ ወገን ዘመም ይዘቶቻቸውና የሕዝብን እውነታ በማፈን የሚታወቁ መገናኛ ብዙኃን ሆነዋል፡፡

- አንቀጽ 40 (4) - "የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመ[ፈ]ነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡፡"

እውነታው፦ በልማት ሰበብ በተለይም በጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ኦሮሚያ እና ሌሎችም ክልሎች ለውጭ አገር ዜጎች ለግብርና በሚከራዩ መሬቶች ላይ ነዋሪ የነበሩ ዜጎች በተደጋጋሚ እንዲፈናቀሉ እና ከትውልድ ቀያቸው ርቀው እንዲሰፍሩ እየተደረገ እንደሆኑ ብዙ ብሶቶች ገሃድ እየሆኑ ነው፡፡

- አንቀጽ 79 (2) - "በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛውም የመንግሥት አካል፣ ከማንኛውም ባለሥልጣን ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተጽዕኖ ነጻ ነው፡፡..."

እውነታው፦ ፍርድ ቤቶች ነጻነት ላይ ሕዝቡ ያለው እምነት ከዕለት ዕለት እየተሸረሸረ ነው፡፡ ነጻ ፍርድ ቤቶች አሉ ብሎ የሚያምን እየጠፋ ነው፡፡ ቀደም ብዬ የጠቀስኳት ብርቱኳን ሚዴቅሳ ዳኛ በነበረችበት ወቅት በዋስትና የፈታቻቸው አቶ ስዬ አብርሃ ከፍርድ ቤት ትዕዛዝ ውጪ መታሰራቸው ለዚህ የፍርድ ቤቶች ነጻነት ችግር ጥሩ ምሳሌ ይሆናል፡፡

- አንቀጽ 87 (1) - "የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦች እና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተ ይሆናል፡፡"

እውነታው፦ ይሄ እውነት ነው በሚለው ላይ የሚስማሙ ሰዎች ማግኘት ይቸግራል፡፡ ሠራዊቱ በአናሳ ብሔር አባላት የበላይነት እንደተያዘ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ ይባስ ብሎ ችግሩን ቀስበቀስ ለመቅረፍ ሲሞከር አይስተዋልም፡፡ እንዲያውም እርስዎ ተጠባባቂ ጠቅላይ ሚኒስትር በነበሩበት ወቅት ከተሾሙ 34 ጄኔራሎች ውስጥ 29ኙ የአንድ ብሔር አባላት መሆናቸው ጥያቄው አጋግሎታል፡፡

- አንቀጽ 89 (2) - "መንግሥት የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት፡፡"

እውነታው፦ ዛሬ ዛሬ በሀብታሞች እና ድሆች መካከል ያለው የኢኮኖሚ ልዩነት እጅግ እየተጋነነ መጥቷል፡፡ ዜጎች ሀብት ለማፍራት እኩል ዕድል አላቸው ብለው የሚያምኑ እጅግ ጥቂቶች ናቸው፡፡ ስደተኛ ወጣቶች በድንበር እያሳበሩ ለሞት እስከመጋለጥ የሚደርሱት ድህነት እየገፋቸው ነው፡፡ ጉዳዩ በጣም የከፋ ቢሆንም መንግሥት ይህንን ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚሠራው ሥራ አይታይም፡፡

- አንቀጽ 89 (6) - "የሀገር ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት መንግሥት ሕዝቡን በየደረጃው ማሳተፍ አለበት፡፡ የሕዝቡንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት፡፡"

**እውነታው፡-** በአገራችን አዋጆች ከወጡ በኋላ ማሳወቅ እንጂ የሚመለከታቸው አካላት ረቂቁን በማውጣት ቀርቶ፣ የወጣው ረቂቅ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ የሚደረግበት ልምድ ፈፅሞ አልተዘረጋም። በከተማ ቤቶች ሊዝ አዋጅ ላይ የነበረው ከፍተኛ ግራ መጋባት እና ቅሬታም ለዚህ ጥሩ የቅርብ ጊዜ ምሳሌ ነው።

- አንቀጽ 89 (8) - "*መንግሥት የሠራተኛውን ሕዝብ ጤንነት፣ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት።*"

**እውነታው፡-** *ሠራተኛው የሕዝብ ክፍል ወር ጠብቆ በሚያገኛት ምንዳ ለመኖር በሚያደርገው መፍጨርጨር የኑሮ ውድነት መስዋዕት እየሆነ ነው። መንግሥት ላለፉት ዐሥር በየጊዜው እያሻቀበ የመጣውን የዋጋ ግሸበት ለመቆጣጠር ለማዋል ሥር ነቀል እርምጃ አልወሰደም። በዚህም የሠራተኛው ሕዝብ ደህንነት አደጋ ላይ ተንጠልጥሏል።*

- አንቀጽ 102 (6) - "*በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነጻና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኛነት እንዲካሄድ ከማንኛውም ተጽእኖ ነጻ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል።*"

**እውነታው፡-** *የምርጫ ቦርድ ነጻነት ከአከራካሪነት ድኖ አያውቅም። እንዲያውም አሁን እንኳን መጪውን የአዲስ አበባ ከተማ ምርጫ አስመልክቶ 34 የተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫ ቦርድ ነጻነት ላይ ጥያቄ እንዳላቸው ተናግረዋል። አጥጋቢ መልስ ግን እስካሁን አልተሰጣቸውም።*

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፣

ከላይ በጠቃቀስኳቸው አንቀጾች ላይ ብቻ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የደረሱትን ሕገ መንግሥታዊ ጥሰቶች ዘርዝሮ ለመጨረስ በጣም ይከብዳል። መንግሥትዎ ሁሉንም ሕዝቦች በእኩል መንገድ ማገልገል ቢኖርበትም እኩል እያገለገለ ነው ብዬ ግን አላምንም። ሰብአዊ መብት አያያዝ እየተሻሻለ ሳይሆን እያሽቆለቆለ እንደመጣ ዓለም አቀፍ ሪፖርቶች ይመሰክራሉ፣ መንግሥት ግልጽነት ይጎድለዋል፣ የገዢው ፓርቲ ነቃፊዎች እንደወንጀለኛ የሚቆጠሩበት አጋጣሚ በዝቷል፣ ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት ገደል አፋፍ ላይ ቆሟል፣ የመንግስት መገናኛ ብዙሐን ለገዢው ፓርቲ ወገንተኝነት ያሳያሉ፣ አርሶ አደሮች ከቀያቸው የሚፈናቀሉት ያለ ፈቃዳቸው እንደሆነ የሚያመላክቱ መረጃዎች አሉ፣ ፍርድ ቤቶች ከፖለቲካዊ ተጽዕኖ ነጻ ናቸው የሚለውን የሚያምነው የሕዝብ ቁጥር እየተመናመነ ነው፣ የመከላከያ ሠራዊቱ ከአንድ ብሔር ተዋፅኦ የመገንባት ነገር ጥርጣሬ ውስጥ ወድቋል፣ የኢኮኖሚያችን ስርዓት ለሁሉም እኩል ዕድል አልሰጠም የሚሉ ጥያቄዎች እየተነሱ ነው፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ምርጫ ቦርድ ነጻ ነው በሚለው ላይ የማይስማሙ ወገኖች በዝተዋል።

እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች እና ችግሮች የተከሰቱት የመንግሥት ኃላፊዎች ሕገ መንግሥቱን ለማክበር ቁርጠኝነት ስለሚያንሳቸው ነው። የመንግሥት ኃላፊዎች ሕገ መንግሥቱን በቁርጠኝነት ባለማክበራቸው ሳቢያ ሌሎችም ዜጎች ሕገ መንግሥቱ ላይ ያላቸው ጠንካራ እምነት እንዲሸረሸር እያደረገ ነው። ስለሆነም የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የጉዳዩን አንገብጋቢነት በመረዳት ሕገ መንግሥቱን የማስከበር ቆራጥ ዘመቻ በአስቸኳይ እንዲጀምሩ እለምንዎታለሁ።

ከሕገ መንግሥቱ አክባሪዎች አንዱ፣

# ሕግ ምርኩዝ ነው ዱላ?

ሕዝብ አብሮ ሲኖር ግጭት ሊያስወግደው የማይችለው ነገር ነው። የሰዎች የእርስ በእርስ ግንኙነት እስካለ ድረስ ግጭት አለ። በግጭቱ ጉልበተኛው አሸንፎ ተሸናፊውን እንደፈለገ ይቀጣል ማለት ነው። ይህ እንግዲህ እንግሊዛዊው የስነ መንግስት ሊቅ Thomas Hobbes ‘State of Nature’ የሚለው ወይም ጉልበተኛ የሚገዛበት ደካማ የሚጠቃበት እና Hobbes “ life is solitary, poor, nasty, brutish, and short” ብሎ የገለፀው ሀሳባዊ አለም ነው።

ይህ እንዳይሆን ህዝብ ስምምነት ላይ ደረሰ ይሄንም ስምምነት በልቦናው ፈረመ ‘መንግስት’ የሚባልም አካል መሰረተ። ይህ አካልም ከህዝቡ ጉልበት ተቀንሶ ጉልበተኛን ይቀጣ ዘንድ ተሰጠው እንዲሁም ይህ መብት እንዳለው ሁሉ የህዝቡን ሰላም የማስጠበቅም ግዴታ ተሰጠው። ማን ? መንግስት የተባለው አካል።

ታዲያ መንግስት በጦር በጎራዴ ብቻ ሰላምን አያስጠብቅም ይልቅስ ሰላማዊ መሳሪያውን ይመዛል ይሄም መሳሪያ የመንግስት ህግ ነው። ህዝቡም ያከብረው ዘንድ ይወዳል ወይም ይገደዳል። ስለዚህ የመንግስት ህግ ማለት መንግስት ህዝብ ከራሱ የተፈጥሮ ስልጣን ቀንሶ መንግስት ለተሰኘው አካል ስለሰጠው መንግስቱ ይሄን የህዝብ አደራ ለመጠበቅ የሚቀርብ በትር ነው።

በመሰረቱ የኢትዮጵያም ታሪክ በዚህ የመንግስት ህልዮት ይገዛል። ነገሩ የሚበላሸው መንግስት የተባለው አካል የህዝብን አደራ በልቶ ሌላ ዳቦ መጋገር ሲጀምር ነው። የህዝቡን ዳቦ በልቶ የራሱን ሽልጦ ሲያነጉት ነው መከራው።

መንግስታት በተቀያየሩ ቁጥር የህዝብን ሰላም እና ጥቅም ለመስጠበቅ ህግ ያወጣሉ፣ ይከለክላሉ፣ ያስጠብቃሉ። ይሄም እውነት በጠነከረ ሁኔታ አሁን ባለንባት ኢትዮጵያ ገዝፎ ይታያል።

ለምሳሌ ኢህአዴግ ስልጣን ይዞ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ከፀደቀበት ህዳር 1987 ዓ.ም ወዲህ፡

- ወደ 750 የሚደርሱ አዋጆች፣
- ከ200 በላይ ደንቦች፣
- በሽዎች የሚቆጠሩ መመሪያዎች ወጥተዋል።

እነዚህ ሕጎች በአጠቃላይ መብትን ማስጠበቂያና ግዴታን መስጫ ናቸው። እንደ ሁሉም የህግ ባህሪያት። አስገራሚ የሚሆነው ጉዳይ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ የሚወጡ ህጎች ብርታት እና ሀይል ነው።

የፕረስ ሕጉ አዋጅ ቁጥር 590/2000፣ የሙያ ማኅበራት ሕግ አዋጅ ቁጥር 620/2000፣ የፀረ-ሽብር ህግ አዋጅ ቁጥር 652/2001፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ህግ አዋጅ ቁጥር 662/2001፣ የሊዝ ህግ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ብለን የዋነኛዎቹን ብርቱ ህጎች መዘርዘር ይቻላል። ከነዚህ በተጨማሪ ደግሞ በረቂቅ ደረጃ ያለ የሁሉንም ሰው በር ሊያንኳኳ የሚችል አዲስ የህግ ረቂቅ የቴሌኮም ህግ በሂደት ላይ ይገኛል።

እንግዲህ ለጨዋታችን ይሄን ረቂቅ ህግ ከፀረ-ሽብር ሕጉ ጋር አብረን እንመልከተው፡-

- ማሞ እና ብሪቱ አዲስ ሙሽራዎች ሲሆኑ የፍቅራቸው ሙቀት አልበርድላቸው ብሎ የሚያደርጉትን አሳጥቷቸዋል:: ለዚህም ይመስላል ማሞ ህዝብ ይወቀው፣ ይመልከተው ብሎ ከብሪቱ ጋር ሲቃበጡ እና የጭናቸው ፍም በጋለበት ወቅት እያደረጉት ያሉትን ድርጊት ምስል የፌስቡክ ገፁ ላይ የለጠፈው። ግማሾቹ ጓደኞቹ ምነው ማሞ! ሲሉት ግማሾቹ ደግሞ ኧረ ማሚሻ ቀወጥሽው ሎል ምናምን ብውለታል።
- በአዲሱ ረቂቅ የቴሌኮም አዋጅ አንቀፅ 6 መሰረት ማንኛውም ሰው ፀያፍ የሆነ ነገርን ማንኛውንም የቴሌኮም መሳሪያ ተጠቅሞ ለህዝብ ያሳወቀ ከሆነ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 640 የተደነገገው ቅጣት እንዳለ ሁኖ ከ 3 — 8 ዓመት ያስቀጣል። እንግዲህ ህጉ ከፀደቀ አቶ ማሞንም መልካም የእስር ወቅት ለማለት እንገደዳለን እንዲሁም ሞቶ በክር መታሰር ነው ክፉ ስምንት ዓመት እማ ስምንት ቀን ናት ብለን ለማፅናናት እንወዳለን።
- አያንቱ የዩንቨርስቲ ትምህርቷን ጨርሳ በአንድ የመንግስት ድርጅት ውስጥ ተቀጥራ ለሁለት ዓመታት ካገለገለች በኋላ በአንድ የምስራቅ አውሮፓ ሀገር ነጻ የትምህርት ዕድል ታገኛለች። ማንነቷን እና የቋንቋ ችሎታዎን ለማረጋገጥ በሚል ዩንቨርስቲው አያንቱን በ Skype ለሚደረግ የ30 ደቂቃ ቃለ መጠይቅ

ይጋብዛታል፡፡ አያንቱም በተቀጠረችበት ሰዓት ሰፈር ውስጥ የሚገኝ አንድ ኢንተርኔት ካፌ ውስጥ ተገኝታ ቃለ ምልልሱንም በድል ተወጣለች፡፡ የማረጋጋጫ ደብዳቤም ይደርሳታል፡፡

በአዲሱ የቴሌኮም አዋጅ አንቀፅ 10 ንኡስ ቁጥር 4 መሰረት ማንም ሰው እያወቀም ሆነ በቸልተኝነት በኢንተርኔት የሚደረግን የስልክ ወይም የፋክስ ጥሪ ያደረገ ከሆነ ከ3 ወራት እስከ ሁለት ዓመት የሚደርስ ቅጣት ይቀጣል፡፡ እንግዲህ ይህ ረቂቅ አዋጅ ከወጣ እህት አያንቱ ወደ ትምህርት ከመሄድ ይልቅ ወደ እስር ቤት መሄዷ እውን ይሆናል፡፡

## እሱ እንዳለው ያ ሎሬቱ

- ዳርጌ ፌስቡክ ላይ ነው ውሎ አዳሩ፡፡ የሆነ ቀን ነሽጥ ሲያደርገው "አልሻባብ ድሬዳዋን ተቆጣጠረ ይሄም የጫትን ዋጋ ሊያንረው ይችላል" ብሎ ይለጥፋል:: በጉዳዩ የተደናገጡት ፌስቡካዊያን ጩኸታቸውን ያሰማሉ፡፡

በፀረ ሽብር ሕጉ ማኝኛውንም የሽብር ድርጅት መደገፍ እንዲሁም ህዝብን ሊያሽብሩ የሚችሉ መረጃዎችን የለቀቀ አሁን ደግሞ በረቂቁ የቴሌኮም አዋጅ ማንኛውንም የቴሌኮሚኒኬሽን መሳሪያ ተጠቅሞ አሸባሪ መልዕክት ያስተላለፈ ሰው እስከ 8 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እንደሚቀጣ ተደንግጓል፡፡

እንግዲህ ዳርጌም የዚሁ አንቀፅ ተሸላሚ ነው ማለት ነው፡፡ በርግጥ ዳርጌ "ጽሑፉን የጻፍኩት ጓደኞቼን አስደንግጬ April the Fool ለማለት ነው" እንደሚል አይጠረጠርም፡፡

Thomas Hobbes ከመቃብር ቀና ብሎ ይሄን ቢመለከት የስነ መንግስት ትንታኔውን ያሻሽለው ይሆን ወይስ Sometimes, the state of nature can be the case even if there is a Law, since an unjust law is not a law at all" ይላል? እኛም መንግስት ከሕዝብ ኃይል ተቀናንሶ የተሰጠውን በትር አደራውን ሳይሆን ሌላ ነገር ሲጠብቅበት ባየን ጊዜ Is Rule by law a Rule of Law? ብለን እንጠይቃለን::

# ሰብኣዊ መብቶች፣ ሕገ-መንግሥቱ እና መንግሥት

ሰሞኑን የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን የማዳመጥ ፍቃደኝነት ካሳያችሁ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ከሕገ -መንግሥቱ መጽደቅ ጋር ተያይዞ ለአንድ ሳምንት እየተከበረ ይገኛል፡፡ በትምህርት ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደግሞ በዓሉ ለቀናት (ለአንድ ሳምንት) እንዲከበር ተወስኗል፡፡ ይህ ሕገ መንግሥቱ የጸደቀበትን ቀን ተከትሎ ለ7ተኛ ጊዜ የሚከበረው በዓል ሕገ መንግሥቱ ያጎናጸፋቸው መብቶች ብሎ ብዙዎቹ ብሔር ብሔረሰብ ላይ ያተኮሩ መብቶችን ሲያነሳ ሌሎቹን ደሞ ከተግባራዊነታቸው አለያይቶ ለብቻቸው ያስተዋውቃቸዋል፡፡

የኢፌድሪ ሕገ መንግሥት በሶስተኛው ምእራፍ መሰረታዊ መብቶች እና ነጻነቶች ብሎ በተለምዶ ሰብአዊ እና ሲቪል መብቶች የምንላቸውን ያስቀምጣል፡፡ በክፍል አንድ በ15 አንቀጾች ሰብኣዊ መብቶች የተቀመጡ ሲሆን በዚሁ ምዕራፍ ክፍል ሁለት ዴሞክራሲያዊ መብቶች ስር16 አንቀጾች ተካተዋል፡፡ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተቱት መብቶች ከጥቂቶቹ (አንቀጽ 39 ለዚህ ምሳሌ ነው) በስተቀር በዓለም አቀፍ ደረጃ ሕገ መንግሥቱን ሰብኣዊ መብቶች ጉዳይ ላይ ትኩረት የሰጠ እና የተለየ ያደርጉታል፡፡

ወደ ተግባሩ ሲመጣ ባለፉት 18 ዓመታት ከጽሑፉ ጋር በፍጹም የማይገናኙ ብዙ የተግባር ጥሰቶችን አንደግለሰብም እንደ አገርም አስተናግደናል፡፡ ከነዚህ መካከል አንዳንዶቹ ግልጽ ጥሰቶች አስተዳደራዊ ይምሰሉ እንጂ በባሕሪያቸው በሕገ መንግሥቱ የተቀመጡትን የሰብኣዊ መብት ድንጋጌዎች በግልጽ የሚቃረኑ ከመሆናቸውም ባሻገር በተለያዩ የመንግስት አካላት በመጣሳቸው እንደቁምነገር እንደማይቆጠሩ ያሳያል፡፡

## የተናቁ አንቀጾች

በምዕራፍ ሦስት ክፍል አንድ በሰብኣዊ መብት ክፍል ከተደነገጉት ዐሥራ አምስት (15) አንቀጾች መካከል ቢያንስ ዐሥራ ሁለቱ በግልጽ በተደጋጋሚ በመንግስት ተጥሰዋል፡፡ ከነዚህ መካከል አንዳንዶቹ ድንጋጌዎች ሊያከብሩዋቸው በሚገቡ የመንግስት አካላት ዘንድ እንደ ቅንጦት ሲቆጠሩ ሌሎቹ ደግሞ በአፈጻጸም ወለምታ ይታሻሉ፡፡

የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 15 ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብቱን አረጋግጦ በሕግ ካልተደነገገ በስተቀር ሕይወቱን እንደማያጣ ይናገራል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ሕጻናት እና ወጣቶች ሳይቀር በየመንገዱ ሲገደሉ ምስክር የሆንበት ጊዜ ቅርብ ትዝታ ነው፡፡ ይህንን ዓይነት ዜጎች ሕይወታቸውን በሕግ ባልተደነገገ ሁኔታ ማጣት እንደ አንድ ሰብኣዊ መብት ጥሰት ሳይሆን እንደ የአንድ ሰሞን የፓለቲካ አለመረጋጋት ውጤት ብቻ መቆጠሩ፣ የኦጋዴን ጭፍጨፋን ዓይነት የብዙ ሰዎች ሕይወት ያለምንም ሕጋዊ ድንጋጌ የተቀጠፈበትን የመብት ጥሰት በዝምታ መታለፉ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 15 መናቅ ውጤት ነው፡፡

የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 16 ማንም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ ሕጋዊ ከለላ ቢሰጠውም ይህንን የመብት ጥሰት በዋናነት የሚፈጽሙት ሕግ አስከባሪዎቹ የመንግስት አካላት ናቸው፡፡ ከመንገድ ላይ አንስቶ እስከ ሕጋዊ የፓሊስ ጣቢያዎች ድረስ ያለምንም ማቅማማት እንደሥራም ጭምር ቆጥረው ከፍተኛ የአካል ጉዳት የሚያደርሱት እነዚሁ የመንግስት አካላት ናቸው፡፡ (ይህ አንግዲህ በደህንነት ነኝ ባይ አባላት እና በስርዓቱ ተጠቃሚዎች የሚፈፀመውን የአካል ጉዳት ሳንጨምር ነው፤) ይህ ከማንኛውም አካላዊ የአካል ጉዳት የመጠበቅ መብት በራሱ በመንግሥት ማረሚያ ቤቶች እንኳን መከበር አቅቷቸው የተለያዩ እስረኞች በተለያየ ወቅት የሚደርስባቸውን የአካል ጉዳት ለአደባባይ ሲያቀርቡ መስማት ለሕግ አስፈጻሚ አካላት የተለመደ እና እርምጃ ያልተወሰደበት የመብት ጥሰት ነው፡፡ የቅርብ ጊዜዎቹን የአንዱአለም አራጌን እና ዘሪሁን ገ/እግዜያብሔር በእስረኞች የደረሰባቸውን ከፍተኛ የአካል ጉዳት እና ማረሚያ ቤት ውስጥ ተቀምጠው እንኳን ያጡትን የአንቀጽ 16 ሕጋዊ ከለላ ማስታወስ ይቻላል፡፡ ዜጎች ክስ ሳይቀርብባቸው እና ሳይፈረድባቸው እንደማይታሰሩ አንቀጽ 17 ቢደነግግም በተቃራኒው ግን ለረዥም አመት ሳይፈረድባቸው ሕይወታቸውን በእስር ቤት የሆኑ ዜጎች ቁጥር መንግሥት የሚታማበት ሰብኣዊ መብት አያያዝ ነው፡፡

በሕግ ጥበቃ ስር ያሉ ሰዎችን መብትን አስመልክቶ ሕገ መንግሥቱ በቤተሰቦቻቸው በሃይማኖት አባቶች እና በወዳጅ ጓደኞቻቸው መጎብኘት መብት እንዳላቸው ቢደነግግም በተቃራኒው ግን የተለያዩ "የፓለቲካ እስረኞችን" ማግኘት መጠየቅ እና ማናገር የማረሚያ ቤቶች ቸርነት ሲሆን ‹‹ኧረ ተው ሕገ መንግሥቱን አክብሩ›› የሚል የሕግም ሆነ የመንግሥት አካል አልተገኘም፡፡ ወ/ት ብርቱካ ሚደቅሳን ማየት (ከእናቷ እና ከልጇ) በስተቀር ፍጹም የማይፈቀድ የነበረ ሲሆን ዛሬ ደግሞ እነእስክንድርንና አንዱአለምን መጠየቅ አለመፈቀዱ እንደትክክለኛ

አስተዳደራዊ አሠራር ተቆጥሯል። ከፓሲስ ጣቢያ እስከ ቃሊቲ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ መናቅ የመንግሥት ተቋማት ቋሚ አሠራር አካል ሆኗል። (ጠያቂዎችን ሳይቀር ኢ-ሰብኣዊ በሆነ መንገድ እንደሚያስተናግዱ ለማየት ለአንድ ቀን ወደ እነዚህ አካላት ጎራ ማለት ይበቃል።)

በተደጋጋሚ ሲጣስ የቆየው የሃይማኖት የእምነት እና የአመለካከት ነጻነት መብት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 27 በግልጽ ተቀምጧል። ይህ አንቀጽ ነጻ የሃይማኖት፣ ትምህርት እና አስተዳደር ተቋማትን በነጻነት ስለማቋቋም እና ትምህርቶችን ስለማስተማር ቢፈቅድም በተቃራኒው ላለፉት 8 ወራት አካባቢ የሚታየው የሙስሊም ኢትዮጵያውያን ጥያቄ ለአንቀጹ መናቅ ትልቅ ምሳሌ ሆኖ መጠቀስ ይችላል። (ይህ እንግዲህ የሌሎች ሃይማኖት ተቋማት ነጻነት ዙሪያ ያሉትን ብዙ ጥያቄዎች ሳናነሳ ካለፍን ነው።)

በዴሞክራሲያዊ መብቶች ተርታ ከተመደቡት ውስጥ አንቀጽ 29 የአመለካከት ሐሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት የመጀመሪያው ነው። ይህ አንቀጽ መኖሩ ራሱ አጠራጣሪ እስኪመስል ድረስ ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ በመንግሥት ተጥሷል። የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የሐሳብ መግለጽ መብትን "በማንኛውም የሕትመት እና የስነ ጥበብ መልክ በመረጠው ማሰራጫ ማስተላለፍ" እንደሚችል ይናገራል። በተቃራኒው የተለያዩ የሕትመት ውጤቶች ቁጥር ቀን ከቀን እየቀነሰ ለመጥፋት አዝማሚያ ላይ ሲደደርስ አገራችን ከዋናዎቹ የኢንተርኔት አጋጅ አገሮች አንዷ ነች። የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ደግሞ በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያለ የመገናኛ ብዙኃን የተለያዩ አስተያየቶችን የሚያስተናግድ እንዲሆን ያስገድዳል። (አንባቢያን ኢቲቪን ካሰባችሁ አንቀጽ 29 ምን ያህል እንደተናቀ ትረዳላችሁ።)

አንቀጽ 30 የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ እና የአቤቱታ መብትን ቢያረጋግጥም በተግባር ግን ሰላማዊ ሰልፍን አገራችን ውስጥ ማሰብ መንግሥት ላይ እንደማሴር ታላቅ ወንጀል ከተቆጠረ ዓመታት አልፈዋል። (የመጨረሻዎቹ የሚያዚያ 1997 ሰልፎች እንኳ በፎቶ ከቀሩ ስንት ዓመት ሆናቸው?) ሰላማዊ ሰልፍ በሕገ መንግሥቱ የተሰጠ መብት መሆኑን የማያስታውሱ የመንግሥት ባለስልጣናት ያሉባት ኢትዮጵያ የተለያዩ ሕገ መንግስታዊ የመሰብሰብ መብትን በተግባር ለመተግበር የባለሥልጣን ይሁንታን እና ችሮታን (ማስፈራራት፣ ፍቃድ መቀማት…) የምትፈልገው አዲስ አበባ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 30 ከናቀች ቆይታለች።

## አንቀጾች እንዴት ይናቃሉ?

በተለምዶ የአፈጻጸም እንጂ የፖሊሲ ችግር የለብኝም የሚለው የኢሕአዴግ መንግሥት ሕገ መንግሥቱ ላይ ያሉ የመብት ጥሰቶችን ግን በአፈጻጸም ደረጃም ሲቀበል አይታይም። የመሻሻል ዕድሉን ጠባብ የሚያደርገው አንዱ የመንግሥት ችግር ሕገ መንግሥታዊ መብቶች በተደጋጋሚ መጣሳቸውን አለማመኑ ነው። ይህንን ተከትሎ ለተለያዩ ኃላፊነት ላለባቸው አስተዳደራዊ ሰዎች የሚሰጠው ቅጥ ያጣ ታማኝነትን መሠረት ያደረገ ስልጣን አንቀጾችን በቀላሉ እንዲጣሱ ይረዳል። ከሕገ መንግሥቱ በላይ የፓርቲ የበላይነትን የሚያስቀድመው የኢሕአዴግ መንግሥት የፓርቲ ስልጣኑን እና ታማኝነቱን ካረጋገጠ ሕገ መንግሥቱን ማክበር እና አለማክበሩ የመንግሥት ስልጣን መስፈርት አለመሆኑ የቀድሞ ጠ/ሚኒስተርም ቢሆን ያገጋገጡት ሐቅ ነው።

ሌላው ሕገ መንግሥቱ ላይ የተጠቀሱትን መብቶች በግልጽ የሚጣሱባቸው መንገዶች አንዱ ያለምንም ማቅማማት ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረኑ ሕጎችን ማውጣት እና ተግባራዊ ማድረግ ነው። ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት አዋጅ፣ የተሻሻለው የፕሬስ አዋጅ እና የፀረ-ሽብርተኛነት ሕጉ ይጠቀሳሉ። እነዚህ አዋጆች በሕገ መንግሥቱ የተሰጡ መብቶችን ከመሸራረፋቸውም በላይ ገለልተኛ ተቋማት መብቶችን እንዳያስተዋውቁ ያደረጉና እና ዜጎች ስለሕገ መንግሥታዊ መብቶቻቸው እንዲያውቁ የሚደረጉ ጥረቶችን የገደሉ ናቸው።

ዜጎች ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን የሚያስከብሩባቸው ሁኔታዎች የሚመቻቹት መብቶቻውን በደምብ እንዲያውቁና እንዲጠይቁ በማበረታታት ቢሆንም መንግሥት ከስርዓተ ትምህርት ጀምሮ እስከተቋማት ድረስ የመብት ማስተዋወቂያና መጠየቂያ መንገዶቹን ከመገደቡም ባለፈ ሌሎች ተቋማት ተመሳሳይ ኃላፊነት እንዳይወጡ ኢ-ሕገ መንግስታዊ አዋጆችን መጠቀሙ የመብቶችን ጉዳይ አትኩሮት እንዳያገኝ እና በጠያቂዎቻቸውም ዘንድ እንደቅንጦት እንዲታዩ ምክንያት ሆኗል።

## የሕገ መንግሥቱ አንቀጾች እንዲከበሩ - መፍትሄው

*መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት መብቶችን ማስተዋወቅ እንዲችሉ ሕገ መንግሥታዊ መብቶቻቸው፡፡ የመንግሥት ባለሥልጣናት የዜጎችን ሕገ መንግሥታዊ መብት እንደችሮታ ሳይሆን እንደ ግዴታቸው ይቁጠሩ፡፡ ይከበሩ፡፡ መንግሥት ራሱ ሕገ መንግሥቱን ያክብር፡፡*

# የቴሌኮም ማጭበርበር ሕጉ አወዛጋቢነት

የቴሌኮም ማጭበርበር ሕጉ አወዛጋቢነት የሚጀምረው ‹‹አዋጁ ፀድቋል፣ አልፀደቀም?›› የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ስንጀምር ነው፡፡ አዲስ አድማስ ጋዜጣ በግንቦት 18፤ 2004 እትሙ ‹‹አዋጁ ፀድቋል›› ብሎ ቢዘግብም ለገዢው ፓርቲ በሚወግኑ ጽሁፎቹ የሚታወቀው ጦማሪ ዳንኤል ብርሃነ ደግሞ ገና ‹‹የመጀመሪያውን የንባብ ደረጃ ማለፉ ነው›› ይላል፡፡ ፍኖተ ነፃነትም በበኩሉ በሰኔ 12፤ 2004 እትሙ ‹‹ፍርሀት የወለደው የቴሌ አፋኝ ረቂቅ ሕግ›› ባሰኘው ጽሁፉ ገና ረቂቁ በፓርላማ እንደቀረበ ነገር ግን ከፓርላማችን ያለፈ ልምድ መረዳት እንደሚቻለው ‹‹የቀናት ጉዳይ ነው እንጂ መጽደቁ እንደማይቀር›› ያትታል፡፡

በአገራችን ረቂቅ ሕጎች የሚመለከተው ሕዝብ’ጋ በግልፅ ሳይደርሱ በጭምጭምታ ይቆዩና ድንገት በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው ሕግ የመሆናቸው የተለመደ ድራማ በዚህ ረቂቅ አዋጅ ይለወጣል ብሎ መገመት ሞኝነት ነው፡፡ ይሄም ጽሁፍ በጭምጭምታው እውነታነት እና በረቂቅ ሕጉ ዙሪያ መጠነኛ ትንታኔ ይሰጣል፡፡

በቃሉ ኃይሉ (ስሙ ለዚህ ጽሁፍ ሲባል የተቀየረ) በስካይፕ የሚያወራው ከሚናፍቃቸውና ባሕር ማዶ ከሚኖሩ፣ እሱን ለማግኘት ኮምፒዩተር ላይ ቁጭ ብለው ከሚጠብቁት ጓደኞቹ’ጋ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ‹‹እኔ እስከማስታውሰው ድረስ›› አለ ለዞን ዘጠኝ አስተያየቱን ‹‹እኔ እስከማስታውሰው ድረስ፤ ምንም ዓይነት ሕግ ሲወጣ ብወደውም ብጠላውም እታዘዝለት ነበር፡፡ አሁን ግን በስካይፕ ማውራት ሕገ-ወጥ ከሆነ ከጓደኞቼ እና ከሕጉ መምረጥ ሊኖርብኝ ነው፡፡ ጓደኞቼን ከሕጉ የማስበልጥበት ምክንያት እስካሁን አይታየኝም፡፡›› በቃሉ ይህንን የተናገረው አዋጁ ስካይፕ መጠቀምን በወንጀልነት ፈርጆታል የሚለውን ወሬ ከሰማ በኂላ ነው፡፡

‹‹የቴሌኮም ማጭበርበር አዋጁ›› ከስያሜውና ከትርጉም ክፍሉ ውጪ 18 አንቀጾች ብቻ አሉት፡፡ በሕገ-ወጥ መንገድ ስልክ ማስደወልም ሆነ ሌሎች የቴሌኮም አገልግሎቶችን ያለ ኢትዮ ቴሌኮም እውቅና መስጠት የማይቻል መሆኑ ድሮም በሕግ የተደነገገ ቢሆንም አሁን የዚህ አዋጅ መውጣት አስፈላጊ የሆነው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በማሕበራዊ ደረገጾች ላይ እያደገ የመጣውን ፀረ-አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊነት ለመገደብ እንደሆነ ብዙዎች መጠራጠር ጀምረዋል፡፡ የአዋጁ መግቢያ ላይም እንዲህ የሚል ይነበባል፡፡ ‹‹…የቴሌኮም ማጭበርበር ከኤኮኖሚ ኪሳራውም ባሻገር ዋና የደህንነት ስጋት በመሆኑ…›› ህግ አውጪው በረቂቅ አዋጁ ከኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ባለፈ ለሃገር ደህንነት ማሰቡን በግልጽ ይናገራል፡፤(በዚህ ጽሁፍ ውስጥ አዋጁ የተጣቀሰው ከእንግሊዝኛው ቅጂ ሲሆን ትርጉሙ የዞን ዘጠኝ ነው፡፡)

ኢሕአዴግ ለአብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚያደርገው ቅጥ ያጣ ጥበቃ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ትችቶቹን በሐሳብ ማሸነፍ እንዳቃተው ያሳብቃል፡፡ በጥቅሉ የመረጃ መረብን እና በዋናነት ማሕበራዊ ድረገጾችን ማዕከል አድርገው የሚንቀሳቀሱት የመረጃ ምንጮች እንደ ዶ/ር ዳኛቸው አባባል ‹‹የመረጃ ኦና.›› (Information Vacuum) ለመፍጠርና አውራ ፓርቲው ‹የሕዝብ› መገናኛ ብዙሐንን በመጠቀም የሚያጮኻቸው ወደአንድ አስተሳሰብ ያዘነበሉ መረጃዎች ለሚፈጥሯቸው የገደል ማሚቱ ድምጾች እንቅፋት ሆነዋል፡፡

## ከቻይና ምን መማር?

‘ሪፖርተርስ ዊዝ አውት ቦርደርስ’ የተባለ የጋዜጠኞች ድንበር የለሽ ቡድን ቻይናን ‹ከኢንተርኔት ጠላቶች› አንዷ እንደሆነች ያስቀምጣታል፡፡ የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ ልኡካን ቡድን ደግሞ በአዲስ አበባ ለሚገኘው አቻው — ኢሕአዴግ በብዙሐን መገናኛ እና ኢንተርኔት አስተዳደር ዙሪያ ያካበተውን ልምድ አካፍሎ ተመለሰው በቅርብ ጊዜ እንደሆነ በገዢው ፓርቲ ድረገጽ ላይ የሰፈረው ዜና ያስረዳል፡፡

ቻይና ‹‹የምዕራቡ ዓለም የመረጃ ነፃነት ባሕል የአገሬን ባሕል ያጠፋል›› በሚል ስም ለበርካታ ብዙሐን መገናኛ በሯን ዘግታለች፡፡ ለቻይና ብቻ ተብሎ የተዘጋጀው ጉግል አንዳንድ የኮሙኒስት ፓርቲን የሚያስቀይሙ ቃላቶችን እንዳይፈልግ ተደርጎ በልኳ ተሰፍቶላታል፡፡ ፌስቡክና ትዊተርም ታግደዋል፡፡

የቻይና የፍቅር ልጅ የሆነችው ሃገራችን ከቻይና በቀሰመችው ልምድና ቴክኖሎጂ የቪኦኤና የዶቼቬሌን ሬዲዮ ጣቢያ ማፈኗን መንግስቷ አምኗል፡፡ በርካታ ድረገጾችም ታግደዋል፡፡ አንድ የዞን ዘጠኝ አባል በግሉ ባደረገው ቅኝት 65 ነፃ ድረአምባዎች፣ 14 የፓርቲ እና ለፓርቲ የሚወግኑ ድረአምባዎች፣ 37 ጦማሮች፣ 7 የበይነመረብ ሬዲዮና ቴሌቪዥኖች እና 37 የፌስቡክ ቡድን ገጾች በኢትዮጵያ እንዳይነበቡ መደረጋቸውን አረጋግጧል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ነው አዲሱ አዋጅ በመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ አርቃቂነት ለፓርላማ የቀረበው፡፡ ‹አዲሱ አዋጅ ምን ዓይነት በቀላሉ ትርጉማቸው ሊጠመዘዝ የሚችሉ አንቀጾች አሉት? የማሕበራዊ ድረገጽ እንቅስቃሴዎችን እንዴት ያውካቸዋል? ሐሳብን በነፃ ከመግለጽ መብት አንጻርስ አዋጁ እንዴት ይታያል? ስካይፕና ጉግል ቶክን የመሳሰሉት በVoice over Internet Protocol (VoIP) የሚጠቀሙ አገልግሎቶችን ሕገወጥ ያደርጋቸው ይሆን?› የሚሉ ጥያቄዎችን የሚያጭሩ እና ለማብራሪያ ክፍት የሆኑ አንቀጾችን ከዚህ በታች እንጠቃቅሳለን፡፡

## አወዛጋቢዎቹ አንቀጾች

በአዋጁ ክፍል አንድ በተለዩ ቃላት ትርጉሞች ላይ የሚከተሉትን ያስቀምጣል፡፡ አንቀጽ 2 ላይ ‹‹የቴሌኮሙኒኬሽን ቁሳቁስ ማለት ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የዋለ ወይም ሊውል የታቀደ ዕቃ፤ መገጣጠሚያ (accessories) እና ሶፍትዌሮችን ጨምሮ ማለት ነው፡፡›› ይላል፡፡ አንቀጽ 1 ላይ ‹የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት› የሚለውን ሲተረጉም በኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚቀርቡ ጽሁፎች እና ምስሎች ከአገልግሎቱ እንደሚካተቱ ጠቁሟል፡፡ ሶፍትዌሮችን በዚህ ትርጉም ውስጥ በማካተት የተከታይ አንቀጾችን ትርጉም በዚያ መልክ እንድናይ ያስገድደናል፡፡

ክፍል ሁለት፣ አንቀጽ 3 ‹‹ሚኒስትሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመምከር የትኞቹ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁሳቁሶች፣ አምራቾች፣ ገጣጣሚዎች፣ አስመጪዎች ፈቃድ እንደማይሹ ይገልጻል፤ ደንብ ያበጃል›› ይላል፡፡ ይህም በሚኒስትሩ (ሚኒስትሩ የሚባለው የኢንፎርሜሽን እና ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፡፡) ያልተዘረዘሩ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፣ ተጠቃሚውን በወንጀልነት እስከ 4 ዓመት ፅኑ እስራት እና እስከ 40,000 ብር በሚደርስ ቅጣት፣ አስመጪ እና አከፋፋይ ድርጅቶችን ደግሞ ‹‹..ከ10 እስከ 15 ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከ100,000ብር እስከ 150,000 ብር የሚደርስ ቅጣት..›› ሊያስከትልበት እንደሚችል ረቂቁ ይደነግጋል፡፡

የዚህ አንቀጽ ለትርጉም ክፍት መሆን የምንጠቀምባቸው የበይነመረብ ማሰሻዎች (Internet browsers)፣ ሶፍትዌሮች (skype, google talk…)፣ የስልክ ቀፎዎች (blackberry, iPhone, Android ስልኮች፣ ወዘተ…)፣ እና ሌሎችም ዓይነት በሚኒስትሩ ይወሰናሉ፣ ካልተወሰኑ ደግሞ ለመጠቀም ፈቃድ ያስፈልጋል የሚል አንድምታ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡(የጆሮ ማዳመጫ /head set/ የተጠቀመ ሰው ያልተፈቀደ መሳሪያ ገጣጥሞ ተጠቀመ ቢባል ሊስቀጣው ነው ማለት ነው እስከሚል የተለጠጠ ትርጉም ድረስ ሊወስደን ሁሉ ይችላል፡)

አንቀጽ 6(1) ደግሞ ‹‹ማንም የቴሌኮም መረብን ወይም መሳሪያን በመጠቀም በፀረሽብርተኝነት አዋጅ 652/2001 መሰረት የሽብር መልዕክት ቢያሰራጭ ወይም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሰረት የሚያስጠይቅ አጸያፊ መልዕክት ቢያሰራጭ… ከ3 እስከ 8 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከ30,000 እስከ 80,000 ብር ድረስ ይቀጣል›› ይላል፡፡በዚህ አንቀጽ የተጠቀሰውን ወንጀል መፈጸም በዚህ ህግ ቢካታትም ባይካተትም ማስጠየቁ የማይቀር ሆኖ ሳለ በድጋሚ የተለየ ሽፋን መስጠቱ የህጉን አስፈላጊነት እንድንጠይቅ ያስገድደናል፡፡

አንቀጽ 13 ‹‹የቴሌኮም ማጭበርበርን ለመከላከል፣ ለመመርመርና ለመቆጣጠር ብሔራዊ የቴክኒክ ሥራ ቡድን ከሚመለከታቸው አካላት ተውጣጥቶ ይቋቋማል፡፡››

አንቀጽ 14 ‹‹ፖሊስ የቴሌኮም ማጭበርበር ተከስቷል ወይም ሊከሰት ይችላል ብሎ ባመነ ጊዜ ከፍርድ ቤት የብርበራ ፈቃድ መጠየቅ ይችላል፡፡›› ይህም የአንድ ሰው የስልክ ንግግር፣ አጭር የጽሁፍ መልዕክቶች፣ የኢሜይል መልዕክት ልውውጦች እንደአስፈላጊነታቸው የሚበረበሩበትን የሕግ አግባብ ይሰጣል ማለት ነው፡፡ መንግስት የኢንተርኔት አጠቃቀምን በተመለከተ ለአገሪቱ ደህንነት የሚያሰጉ ነገሮች ካሉ መቆጣጠር አለበት የሚለው ነጥብ ላይ መስማማት ቢቻልም የግለሰቦችን ነፃነት በተራ ፍራቻ ማሳጣት ግን ከሰብአዊ መብት ጥሰት ውስጥ ሊመደብ ይችላል፡፡

ህጉ በአጠቃላይ ካሉበት መሰረታዊ ገደቦች (limitations) መካከል ዋና ዋናዎቹ የግለሰቦችን ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት በሃገር ደህንነት ስም መንጠቁ፣ ለትርጉም ክፍት የሆኑ ሰፋፊ ሃሳቦችን ማጠቃለሉ እንዲሁም የህጉን አስፈላጊነት በሚገባ ሊያሳምን አለመቻሉ ናቸው፡፡

ከሌሎች የተለመዱ ሕጎች በተለየ የማስረጃ ሁኔታን የዳሰሰው ይህ አዋጅ ለወትሮ ከምንጠቀምባቸው የማስረጃ አይነቶች በተጨማሪ ተቀባይነት ያላቸውን ተጨማሪ የማስረጃ አይነቶች ይጨምራል፡፡ይህ ከመሰረታዊ ሰብአዊ መብት ጥበቃ ጋር እና ከመሰረታዊ የወንጀል ሕግ ጋር መታረቁ ያልተገጋገጠ የማስረጃ ስርአት በህጉ ትግበራ ወቅት ታርሞ ይተገበራል ማለት ዘበት ነው፡፡

ከኢንተርኔት ወደ ስልክ መደወልን፣ ያልተፈቀዱ ሶፍትዌሮችን መጠቀምን፣ እንዲሁም የጽሁፎችን ይዘትን በብዙ ከሚወቀሰው የጸረ ሽብርተኝነት ህግ ጋር ማቀላቀሉ ህጉን ከተጸፈበት በላይ አላማ እንዳለው ሌላ ምስክር ነው፡፡ ወደ ስልክ መደወል እና ማስደወልን የሚከለክለው የህጉ አንቀፅ አስር ከተከለከሉ ሶፍት ዌሮች ጋር ተደምሮ የኢንተርኔት የድምጽ ንግግርን ወደ ወንጀልነት ይቀይረዋል፡፡

## VoIP (Skype, Google Talk…) በሚኒስትሩ ይፈቀዱ ይሆን?

የቀድሞዋ አዲስ ነገር መራጌ ኤዲተር መስፍን ነጋሽ በፌስቡክ ገጹ ላይ ‹Promote then criminalize!› በሚል ርዕስ ባሰፈረው አጭር የስዕል ማብራሪያ ላይ (ምስሉ እዚህ ጦማር መግቢያ ላይ ይታያል) ከሁለት ቀን በፊት በሚኒስትሩ ድረገጽ ላይ VoIPን (Voice over Internet Protocolን) የሚያስተዋውቅ ይዘት ያለው መልዕክት ተለጥፎ እንዳገኘ (ያ ገጽ አሁን በሌላ ይዘት ተተክቷል) በምስል አዘጋጅቶ እና የመጀመሪያው መስመር ላይ "ስለ VoIP ሰምታችሁ የማታውቁ ከሆነ የረዥም ርቀት የስልክ ጥሪዎችን የምታደርጉበትን መንገድ ለመቀየር ተዘጋጁ" የሚል ነገር እንዳነበበ ጠቅሶ ጽፎ ነበር፡፡ መስፍን ነጋሽ ይህንን ሁኔታ ከረቂቅ አዋጁ አንፃር በመታዘብ አገልግሎቱን እያስተዋወቁ፣ ተጠቃሚዎቹን ወንጀለኛ ከማድረግ የተቀነባበረ ሴራ ለይቶ እንደማያየው ተናግሯል፡፡

የሚኒስተሩ ድረገጽ በፍጥነት በሌላ ጽሁፍ መተካቱ አዋጁ እውነትም VoIP ኢላማ አድርጎ ተነስቷል ብሎ ለመጠርጠር እንደ አንድ ግብአት ሊቆጠር ይችላል፡፡ በሌላ በኩል እ.ኤ.አ. በ2002 የቴሌሴንተር አገልግሎት ፈቃድን በተመለከተ በወጣው መመሪያ አንቀጽ 13(2) ላይ VoIP (ከኮምፒዩተር ወደ ኮምፒዩተር የሚደረግ የድምጽ ግንኙነት ጨምሮ /ስካይፕን ያካትታል/) የተከለከለ ቢሆንም እስካሁን ድረስ የተለያዩ ኢንተርኔት ካፌዎች ስካይፕን በይፋ ሲጠቀሙ እንጂ በወንጀል ሲከሰሱ የታየበት አንድም መረጃ የለም፡፡ ሌላው ቀርቶ ኢቴቪ የሕዳሴው ግድብን አንደኛ ዓመት አስመልክቶ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ በስካይፕ ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል እያለ ሲያስተዋውቅ መክረሙ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡

በመሆኑም መመሪያው እያለ፣ የፀረ-ሽብርተኝነቱም ሆነ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ እያሉ አዲሱ ‹የቴሌኮም ማጭበርበር አዋጅ› እዚያ የተካተቱትን ሕግጋት ደግሞ መውጣቱ ያስፈለገበት ምክንያት ግልጽ አለመሆን የእነዚህን የቴክኖሎጂ ውጤቶች መስፋፋት ተከትሎ እያደገ የመጣውን ሐሳብን በነፃ የመግለጽ መብት ለማፈን የተወሰደ እርምጃ ነው የሚለውን መላምት ያጠናክረዋል፡፡ ለዚህም እንደዋቢ መጥቀስ የሚቻለው በረቂቁ ላይ ‹‹መንግስት በሕዝቡ አመኔታ እንዲያጣ የሚያደርግ…››፣ ‹‹… አፀያፊ ጽሁፎች›› የሚሉ አሻሚ እና ሰፊ ትርጉም የሚኖራቸውን ሐረጎች መጠቀሙ የአዋጁ ኢላማ በተለይ ማሕበራዊ ድረገጾች ላይ በሚደረጉ የግል ሐሳብን በነፃ የመግለጽ መብት ላይ ያነጣጠረ ነው በሚል ለስጋት የሚጥሉ ሆነዋል፡፡

ሚኒስትሩ VoIPን ከሚከለከሉ አገልግሎቶች መካከል እንደሚያስቀምጣቸው ለመጠርጠር የሚያበቃ ሌላም ምክንያት አለ — የገዢው ፓርቲ የቅርብ ሚዲያ እና "ህግ አውጪው" በመባል የሚታማው ሬድዮ ፋና፡፡ የዜና መጽሄት በተሰኘው ፕሮግራሙ ሬዲዮ ፋና የረቂቅ አዋጁ መንፈስ ሁሉንም ዓይነት VoIPን የሚጠቀሙ አገልግሎቶችን ለማገድ የወጣ እንደሆነ ፍንጭ ይሰጣል:: በተለይ (በፕሮግራሙ ላይ) አንድ የምክር ቤት አባል የአዋጁን አስፈላጊነት ለማስረዳት ሲናገሩ ኢትዮ ቴሌኮም እንደስካይፕ ያሉ በኢንተርኔት ስልክ የማስደወያ ሶፍትዌሮችን በሕግም ሆነ በቴክኖሎጂ ቁጥጥር ስር ማድረግ እንዳለበት አስረድተዋል:: አዲሱ የቴሌኮም አዋጅ ረቂቅ ደግሞ ለቴሌ ይህን ሕጋዊ ዳራ ይፈጥርለታል::

አዋጁ ከኢትዮ ቴሌኮምም በላይ በድብቅ የኢንተርኔት ማጥለል (Internet filtration) ሥራ በመስራት የሚታማውን የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲን (INSAን) ነፃ ያወጣዋል — የረቂቁ አንቀጽ 13 ‹የቴክኒክ የሥራ ቡድን›መቋቋም የሚለው ከለላ በማስቀመጥ፡፡

ባሳለፍነው ሳምንት እየተዘዋወርን ያነጋገርናቸው ጥቂት የኢንተርኔት ካፌ አገልግሎት ሰጪዎች ከወዲሁ (አዋጁ ከመጽደቁ እና በነጋሪት ጋዜጣ ከመውጣቱ በፊት) የስካይፕ እና ማንኛውንም የድምጽ (Voice over IP) አገልግሎት መስጠት ማቆማቸውን ለመረዳት ችለናል፡፡

ዳንኤል ብርሃነ ከላይ ባጣቀስነው ጦማሩ ላይ ‹‹ስካይፕ በሕግ እንደማይታገድ የጥብቅና ባርኔጣዬን አስይዤ እወራረዳለሁ›› ሲል ከተከራከረው በተቃራኒ መደምደም እንደሚቻለው፣ አዋጁ አሁን አሁን እያቆጠቆጠ የመጣው በበይነመረብ ላይ ሐሳብን በነፃ የመግጽ ፍላጎት ላይ ክፉ ጥላ መጣሉ ነው፡፡ እንዲያውም አንዳንዶች የአዋጁ ብቸኛ ዓላማም ይኸው ነው ሲሉ ጥርጣሬያቸውን ከወዲሁ እየገለፁ ነው፡፡ ውጤቱን ለማየት ግን አዋጁ (በፓርላማ ክርክር እና የጋለ ውይይት?) ፀድቆ የተግባር እርምጃው እስኪጀመር ጥቂት ወራት ብቻ መታገስ በቂ ይሆናል፡፡

# ግልጽ ደብዳቤ ለአቶ ደብረፅዮን ገ/ሚካኤል እና ለአቶ በረከት ስምኦን

ለተከበሩ አቶ ደብረፅዮን ገ/ሚካኤል፤ የኮሙኒኬሽን እና ኢንፎርሜሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር፣
ለተከበሩ አቶ በረከት ስምኦን፤ በሚኒስትር ማዕረግ፣ የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ፣

ከ20 ዓመታት በፊት ፓርቲዎቻችሁ - ሕወሓትም ሆነ ብአዴን - ብዙ የኢትዮጵያ ልጆች ሕይወታቸውን የገበሩለትን ጦርነት ያካሔዱት፥ ኢትዮጵያውያን ‹‹ጀርባቸውን ሳይመለከቱ›› በነጻነት አመለካከታቸውን እና ሐሳባቸውን እንዲያንፀባርቁ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ብዙዎች ደማቸውን ያፈሰሱለት፣ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ የተሰየመለት (አንቀጽ 29) ‹‹የአመለካከት እና ሐሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት›› ከኢትዮጵያውያን እጅ ቀስ በቀስ አፈትልኮ እየወጣ መሆኑ ቢያሳስበኝ ይህንን ግልጽ ደብዳቤ ለመጻፍ ተገደድኩ፡፡

ደብዳቤዬን መስመር ለማስያዝ እንዲመቸኝ ከኔ የተሻለ የምትረዱትን ነገር በማስታወስ ልጀምር፡፡ ኢትዮጵያ ከ80 ሚሊዮን የሚልቁ ሕዝቦች፣ ከ80 የሚልቁ ብሔሮች እና ብሔረሰቦች፣ በርካታ ሃይማኖቶች፣ እምነቶች እና ባሕሎች ያሏት አገር ናት፡፡ ሁሉም የየራሱ የሆነ ነገሮችን የሚረዳበት መንገድ ያለው ይህ ብዝኃ-ሕዝብ በፓርላማ ውስጥ ባለ አንድ ፓርቲ ሙሉ ድምፅ እና አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል አማራጭ ሐሳብ ብቻ ሊወከል ፈፅሞ አይችልም፤ ስለዚህ ሕዝቦች ሐሳባቸውን በነጻ የሚገልፁበት ሌሎች አማራጮች ያስፈልጓቸዋል፡፡ እነዚህ አማራጮች ጋዜጣና መጽሔቶችን፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥኖችን እንዲሁም አዲሱ ብዙኃን መገናኛ (new media) በመባል የሚታወቀውን በበይነመረብ ላይ ባሉ ድረአምባዎች፣ ጦማሮች እና ማኅበራዊ አውታሮች ላይ ዜጎች የሚያሰፍሯቸውን አስተያየቶች እና ሐሳቦች ያካትታል፡፡

በአሁኑ ወቅት በርካታ በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያወሩ መጽሔቶች እና ጥቂት የማይባሉ የስፖርት ጋዜጦች ለሕዝብ የሚደርሱ ቢሆንም፣ ማዕከላዊ ትኩረታቸውን ፖለቲካ አድርገው የሚጽፉ ሳምንታዊ ጋዜጦች ቁጥር ግን እየተመናመነ መጥቶ ከ10 በታች ሆኗል፤ ከነርሱም ውስጥ ገሚሱ ከተመሰረቱ 5 ዓመት የማይሞላቸው ሲሆን እንደሌሎቹ ከዚህ በፊት በተለያዩ ምክንያቶች ከስመው እንደቀሩት እልፍ ጋዜጦች መጥፋታቸው አይቀርም የሚል ስጋት አለኝ፡፡ ይህ እንግዲህ የፕሬስ ነጻነት በአገራችን ከተጀመረበት ጊዜ አንጻር ሲታይ በየቀኑ ሁለት፣ ሦስት ጋዜጦች ከሚወጡበት እና የተለያዩ ሐሳቦች ከሚንሸራሸሩበት፣ በቀን ምንም ነጻ ጋዜጣ ላይወጣ ወደሚችልበት (ሰኞ እና ኀሙስን መጥቀስ ይቻላል) ጊዜ ዝቅ ብለናል ማለት ነው፡፡

ሁለት የግል ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎች ያሉ ሲሆን አንዱ ትኩረቱን ከማኅበራዊ ጉዳዮች ሳያርቅ፣ ብዙዎች እንደሚሉት ‹‹ከመንግሥት ጋር ሳይጋጭ›› ለመዝለቅ እየሞከረ ሲሆን ሌላኛው ሙሉ ለሙሉ የሚያንፀባርቀው የገዢውን ፓርቲ ሐሳብ እና ርዕዮተ ዓለም ብቻ በመሆኑ አማራጭ ድምፅ ብሎ ለመጥራት ከባድ ነው፡፡ በተጨማሪም፤ አንድም የግል ቴሌቪዥን እስካሁን አልተፈቀደም፡፡

ሕገ-መንግሥቱ በአንቀጽ 29 (5) ላይ *‹‹በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙኃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል፡፡››* ብሎ ቢደነግግም በተግባር የሚታየው እውነታ ግን ተቃራኒው ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የሚያሰራጫቸው አራት ቴሌቪዥኖች፣ የኢትዮጵያ ሬዲዮ እና ኤፍ ኤም 97.1 እንዲሁም የኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ የሚያሳትማቸው ጋዜጦች በሙሉ ለገዢው ፓርቲ የሚወግኑ፣ ተቃራኒ ሐሳብ የሚያመነጩ ወገኖችን የሚያፍኑ እና ፍርደገምድል የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ መሆናቸውን ማንም ከሕዝብ የወጣ መንገደኛ አስቁመው ቢጠይቁት ይመሰክራል፡፡

አዲሱ ብዙኃን መገናኛን በመጠቀም የሚቀርቡ ዜናዎች እና መረጃዎች ቀልጣፋ እና በቀላሉ የመሰራጨት አቅም ያላቸው ቢሆኑም፤ መንግሥት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለዘርፉ ትኩረት ባለመስጠቱ በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የሚጽፉ፣ ራሳቸውን የድረገጽ ዜና እና መረጃ አገልግሎት ለመስጠት በሕጋዊ መንገድ ያስመዘገቡ ያገር ውስጥ የሚዲያ ተቋማት የሉም፡፡ ይሁን እንጂ በውጭ አገር የሚኖሩ ዜጎቻችን የመሠረቷቸው በርካታ ድረገጾች እና አገር ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንም በትርፍ ሰዓት ሊጽፉባቸው የመሠረቷቸው በርካታ ጦማሮች አሉ፡፡ እነዚህ የሕዝብ አስተያየቶች፣ እና አማራጭ ምክረሐሳቦች የሚንጸባረቁባቸው ጦማሮች እንኳንስ መንግሥትጋ ደርሰው ለስህተቶቹ የእርምት እርምጃ እና ለብሶቶቹም ምላሽ ሊሰ’ጥባቸው ቀርቶ ከጸሐፊው በቀር ኢትዮጵያ ውስጥ ላለ አንድም ዜጋ ሳይደርሱ እንዲቀር ድረገጾቹ ከስር፣ ከስር እየታገዱ ይገኛሉ፡፡

ክቡራን ሚኒስትሮች፣

ኢትዮ-ቴሌኮም ‹‹ኢትዮጵያን ከመጪው ዘመን ጋር የማገናኘት›› ሕልሙን የሚፈፅመው በተቀላጠፈ እና ነጻ የመረጃና ተግባቦት አገልግሎት እንጂ በከፊል በተገደበ ተግባር ሊሆን አይችልም፡፡ የብሮድካስት አገልግሎት የገዢው ፓርቲን አቋም ብቻ ለይቶ እያሰራጨ ሕዝቡን በአንድ አስተሳሰብ ብቻ ለመቅረፅ የሚያደርገው ሙከራ ከስነምግባርም ሆነ ስለወደፊቷ ኢትዮጵያ ከሚያስብ ሕሊና አንጻር ተገቢ አይደለም፡፡

መንግሥት የፕሬስ ነጻነቱን የሚያፍንባቸው በርካታ መንገዶች ናቸው፡፡ በብሮድካስት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የሕትመት ፈቃድ ለማውጣት የሚሄዱ የድርጅት ወኪሎች በፖለቲካዊ አመለካከታቸው ምክንያት ይከለከላሉ ወይም ተሰላችተው እንዲቀሩ ተከታታይ እና የተራዘሙ ቀጠሮዎች የሚሰጥበት አስተዳደራዊ በደል ይደርስባቸዋል፤ (የቀድሞው ‹አውራምባ ታይምስ› ጋዜጠኞች ተሰብስበው የመሠረቱት አሳታሚ በዚህ መንገድ አዲስ ጋዜጣ ማሳተም ሳይችል ቀርቷል)፡፡ ማተሚያ ቤቶችም ቢሆኑ ፈቃድ የተሰጣቸውን ጋዜጦች ‹‹በበላይ አካላት ትዕዛዝ›› እንዳይታተሙ ያግዳሉ፤ (የፍትሕ ጋዜጣን እግድ መጥቀስ ይቻላል)፡፡ አዲስታይምስ መጽሔትም በብሮድካስቱ ባለሥልጣን ፈቃዱ እንዳይታደስ ተከልክሏል፡፡ በመንግሥት በጀት የሚተዳደረው ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሳንሱር የሚከለክለውን የሕገ-መንግሥት አንቀጽ (29/3/ሀ) የሚጋፋ የሥራ ውል ያስፈርማል፤ ሌላኛው የመንግሥት ይዞታ ቦሌ ማተሚያ ቤትም በተመሳሳይ መንገድ አንድ ማኅበራዊ ጉዳይ ላይ እና ሌሎች የስፖርት ጋዜጦችን ብቻ ይዞ የፖለቲካ ጋዜጦችን ‹‹ሥራ ይበዛብኛል›› በሚል ሰበብ እንዳይታተም ያደርጋል፡፡

ጥቂት የማይባሉ የግል ማተሚያ ቤቶች ያሉ ቢሆንም፣ ሁሉም ሊባል በሚቻል መልኩ አንድን ጋዜጣ ለአንዴ ብቻ ካተሙ በኂላ ደግመው አያስተናግዱም፡፡ ይህም የሚሆነው ‹‹በመንግሥት ወይም ባለሥልጣናት ጫና›› እንደሆነ አሳታሚዎቹ በተደጋጋሚ የገለጹት ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም በላይ፣ ጋዜጠኞች እየታሰሩ ነው፤ ሌሎችም በመንግሥት አካላት ጫና አገራቸውን እየለቀቁ ለመሰደድ ተገደዋል፡፡  ይሄ ደግሞ በቀሪዎቹ ጋዜጠኞች ላይ ራሳቸውን እና ሐሳባቸውን ሳንሱር እንዲያደርጉ፣ ዜጎች በየተገናኙበት ብሶታቸውን ‹ሌላ ሰው ሰማኝ አልሰማኝ› በሚል ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው በሹክሹክታ እንዲያወሩ የሚያደርግ ፍርሐት ውስጥ ከትቷቸዋል፡፡

ብዙ ጋዜጦች በታገዱበት እና ቀሪዎቹም ‹‹መንግሥትን የማያስከፉ›› ይዘቶች ላይ በሚያተኩሩበት በዚህ ጊዜ ዜጎች ብሶታቸውን የሚተነፍሱበት እና መረጃዎችን የሚያገኙባቸውን ሌሎች አማራጮች መፈለጋቸው የማይቀር ነው፡፡ ለዚህም ነው በተለያዩ የድረአምባ ጦማሮች እና የማኅበራዊ አውታሮች ላይ የውይይት መድረኮችን የሚከፍቱት፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ማኅበራዊ አውታሮችም በኢትዮጵያ እንዳይነበቡ እየታገዱ ነው፡፡ ለእገዳው የተለያዩ ኃላፊነቱን ሊወስዱ የሚችሉ ቢሮዎች ቢኖሩም፣ ዋናው ግን የተሌኮም አገልግሎቱን በብቸኝነት የሚመራው ኢትዮ-ቴሌኮም ነው፡፡

የኢትዮ-ቴሌኮም የመረጃ ማጥለል ሥራ፣ በግል ባደረግነው የማጣራት ሙከራ ብቻ ከ200 በላይ ድረአምባዎችን እና ጦማሮችን በኢትዮጵያ እንዳይነበቡ አግዷል፡፡ ይህ እገዳ ሲደረግ ምንም የተሰጠ መግለጫ ባይኖርም መንግሥትን ‹‹የሚያስቀይሙ›› ሥራዎች ላይ መሆኑ በግልጽ ያስታውቃል፡፡ ሌላው ቀርቶ፣ ዓለም አቀፎቹ የሲኤንኤን፣ ቪኦኤ እና አልጀዚራ ድረአምባዎች በተለያዩ ጊዜ ባቀረቡት መረጃ ምክንያት የመዘጋት እና እንደገና የመከፈት ዕጣ ቀምሰዋል፡፡ ይህንን የተመለከተ ዜጋ ምናልባት የሚታገዱት የመረጃ ምንጮች ለሕዝብ ደኅንነት የሚያሰጉ መረጃዎችን የያዙ ይሆናል ብሎ ሊያስብ ይችላል፤ ነገር ግን የሚታገዱትን ገጾች መረጃ ላነበበ እውነታው አያሻማም፤ ገጾቹ የሚያቀርቡት መረጃ እና ዕውቀት ቢሆንም መንግሥት ላይ ያላቸውን ተቃውሞ/ትችት ግን የማይሸሽጉ ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ በኢትዮጵያ ለማኅበረሰብ ደህንነት የማይበጁ፣ ከሕዝቡ ባሕልና ወግ ጋር የማይሄዱ የሚባሉትን የልቅ ወሲብ ቪዲዮ እና ምስል የሚያቀርቡ ድረገጾች - አንዳቸውም አለመታገዳቸው ሌሎቹ ድረአምባዎች የሚታገዱት ለማኅበረሰቡ ታስቦ እንዳልሆነ መልዕክት ይሰጣል፡፡

ስለዚህ ክቡራን ሚኒስትሮች፣

መንግሥት የዜጎችን ሐሳቦች፣ ጋዜጦች እና ጦማሮች በተደራጀ መልኩ እያሰሰ እና እያነበበ የሕዝቦችን ብሶት እና ችግር ተረድቶ ለመፍትሔው መረባረብ ሲኖርበት፣ ዜጎች መረጃዎቹን እንዳያወጡ እንቅፋት መሆንን ከመረጠ በየት በኩል ኃላፊነት የሚሰማው ማኅበረሰብ መፍጠር ይቻለዋል? መንግሥት በምሳሌነት የማያሳየውን ሥርዓት ከሕዝቡ እንዴት መጠበቅ ይቻለዋል?

እንግዲህ እነዚህን ጥያቄዎቼን በቅን ልቦና ተረድታችሁ ለጥያቄዎቼ ሁሉ መልስ እንደምትሰጡኝ በማመን የሕገ-መንግሥቱን አንቀጽ 29 (2) በመጥቀስ ደብዳቤዬን እቋጫለሁ፡-

*‹‹ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሐሳቡን የመግለጽ ነጻነት አለው፡፡ ይህ ነጻነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሐሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነጻነቶችን ያካትታል፡፡››*

ሕገ-መንግሥቱ ይከበር፤ የአመለካከትና ሐሳብን በነጻነት የመያዝና የመግለጽ መብት ይከበር!

ሐሳባቸውን የመግለጽ ነጻነታቸውን ከተነፈጉት ዜጎች አንዱ፣

# መብት በአደባባይ

ሰዎች ይሰበሰባሉ፣ አደባባይም ይቀመጣሉ፣ መብታቸውንም ይጠይቃሉ፤ ፖሊሲ ይቀየር ዘንድ ይጮኻሉ፣ ግፍ ይቆም ዘንድ ከፍ ያለ ድምፃቸውን ያሰማሉ፣ አደባባይ እንደወጡ በዛው ውለው ሊያድሩም ይችላሉ፣ አቤቱታ በተለያየ መንገድም ያሰባስባሉ፣ የሚመለከተውን አካልም መፍትሄ እንዲሰጥ ይጠይቃሉ። ይህ ተግባር ሰላማዊ በሆነ እና ሕግን በአከበረ መንገድ ሲከናወን ሰላማዊ ሰልፍ ይባላል። ጥያቄዎች ግን ይከተላሉ፤ ሰዎች ለምን ወደ አደባባይ ይወጣሉ? ለምን በሕግ የተቋቋሙ እንደ ፍርድ ቤት ያሉ ተቋማትን አይጠቀሙም? ለምን በመረጧቸው አካላት አማካኝነት አቤቱታቸውን አያቀርቡም? ለምን የሚመለከተውን አስተዳደር አካል (Administrative Body) በቀጥታ ሄደው አይጠይቁም? ኧረ ለመሆኑ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረገስ ውጤታማ ነውን? የሚሉ ጥያቄዎች ተከትለው ይነሳሉ።

## ሰላማዊ ሰልፍ ለምን?

ከ20ኛው ክፍለዘመን ታላላቅ የታሪክ ሊቃውንት መካከል የሚጠቀሰው እንግሊዛዊው የታሪክ ሊቅ Eric Hobsbawm 'Interesting Times: A Twentieth-Century Life' ባለው መፅሃፉ የሰላማዊ ሰለፍን ሀሴት ሲገልፅ፡ *"Next to sex, the activity combining bodily experience and intense emotion to the highest degree is the participation in a mass demonstration at a time of great public exaltation."*

በማለት የሰልፍ አካል መሆን ደስታው የበዛ እንደሆነ፤ ከወሲባዊ እርካታ ጋር አንፃፅሮ ይገልፀዋል።

በዚህ የኤሪክ ሆብስባውም ሀሳብ በመንደርደር ሰዎች ለምን ሰላማዊ ሰልፍ ይወጣሉ/ መውጣት ይፈልጋሉ? የሚሉትን ጉዳይ እንመለክት።

## ዴሞክራሲ!

ከሁሉም በፊት ሀሳብን ለማስተጋባት አደባባይ መውጣትንም ሆነ በአደባባይ መሰብሰብን ዋጋ የሚሰጠው ዲሞክራሲ ነው። ሰዎች ሀሳባቸውን አደባባይ ወጥተው ሲለፁ የስርዓት የኔነትን (Legitimate regime)፤ እንዲሁም የዲሞክራሲውን መጠናከር (Democratic Consolidation) ገላጭ መሆኑ ነው። ለዛም ነው ዲሞክራሲ መኖር እና ዲሞክራሲን መሻት ዋነኛው ወደ አደባባይ የመውጣት ምክንያት የሚሆነው።

## የብዙኃን አመራር - የህዳጣን መብት

ከዲሞክራሲያዊ ስርዓት ዋነኛ ምሰሶዎች መካከል አንዱ የብዙሃኑ አገዛዝ፤ የህዳጣኑ መብት (Majority Rule - Minority Rights) የተሰኘው ነው። ይሄም ማለት ብዙሃኑ የመረጡት እንደ ህግ ሆኖ ይገዛል፤ ስርዓቱም በነሱ ፍላጎት መሰረት ይሆናል፤ ይሄንም በተወካዮቻቸው አማካኝነት ያካሂዱታል፤ ነገር ግን የብዙሃኑ ሕግ ገዥ ቢሆንም፤ በህዳጣኑ መብት ላይ ጉዳት ማምጣት የለበትም ወይም የብዙሃኑ ስርዓት የህዳጣኑን መሰረታዊ መብቶች መንካት የለበትም የሚል ነው። በዚህ መሃል ህዳጣኑ በብዙሃኑ ፍላጎት የወጣውን ሕግ እያከበሩ፤ ነገር ግን ያልተስማሙበትን ህግ፣ ስርዓት እና ፓሊሲ ይቀየር ዘንድ ድምፃቸውን ሊያሰሙ ይችላሉ።

እናም አደባባይ በመውጣት ሀሳባቸው ሀይል እንዲኖረው በማድረግ ፤ መብታቸው ይሰፋ ዘንድ መናገር የህዳጣኑ ሕጉን የሚገዳደሩበት አንዱ አካሄድ ነው።

እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች አሁን ባለንባት ኢትዮጵያ ወሳኝ ቦታን ይይዛሉ። የፖለቲካ ምህዳሩ እና አጠቃላይ የሀገሪቱ እንቅስቃሴዎች በአንድ ግዙፍ የፖለቲካ ፓርቲ እጅ ባሉበት በዚህ ወቅት፤ ህዳጣኑ የሚጮሁበት መድረክ በእጅጉ የጠበበ ከመሆኑ ጋር ተዋህዶ እነዚህ አካላት በአደባባይ ድምፃቸውን ያሰሙ ዘንድ አደባባዩን ይፈልጉታል።

## Non — Justiciability

አንድ ሰው ተበደልኩ ብሎ ሲያስብ፣ እና የመብት ጥሰት ደረሰብኝ ብሎ ሲያምን ጉዳዩን ለፍርድ ቤት አቅርቦ መፍትሄ ማግኘት እንደሚችል ዲሞክራሲያዊ ስርዓቶች የሚቀበሉት መሰረታዊ የመብት ማስፈፀሚያ መንገድ ነው። እነዚህም መብቶች የፍርድ ይሁንታን ያገኙ መብቶች (Justiciable Rights) ይባላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ መብቶቹ እንደ መብት በሕግ የተከበሩ ቢሆንም፤ በተለያዩ ምክንያቶች እነዚህን መብቶች በፍርድ ቤት ጠይቆ ማስፈፀም ላይቻል ይችላል። ለምሳሌ የኢፌድሪ ሕገ መንግስት በአንቀፅ 43 ላይ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የዘላቂ ልማት መብት ተጠቃሚ መሆን እነዳለባቸው እንዲሆኑ ፤ ነገር ግን አሁን ባለው ሁኔታ ይህ መብት አልተከበረልኝም ብሎ በፍርድ ቤት ማስፈፀም አይቻልም፤ ምክንያቱ የሀገሪቱ ኢኮኖሚን ግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን መንግስት ይህ መብት ይከበር ዘንድ በርትቶ መስራት እንደሚጠበቅበት በሕገ መንግስቱ ተገልጿል። እናም መንግሰት ይሄን ግዴታውን እየተወጣ አይደለም ብሎ ያሰበ ኢትዮጵያዊ አደባባይ በመውጣት በመንግስት ላይ ጫና ማሳደር ሊፈልግ ይችላል፤ ሕጉም ይፈቅድለታል። ይሄም አካሄድ ዜጎች ሰላማዊ ሰልፍን በፍርድ ይሁንታ ላልተሰጣቸው መብቶች (Non-Justiciable Rights) እንደ ማስፈፀሚያነት ሊተቀሙበት ችላሉ እንደማለት ነው።

## እነማን ሰላማዊ ሰልፍ ይውጡ? ምንስ ያገኛሉ?

በዋናናት የሰላማዊ ሰልፍ መውጣትን ውጤታማነት የሚያውቀው ሰልፉን የተሳተፈው ሰው ነው። ለዛም ነው በመግቢያችን የጠቀስነው የኤሪክ ሆብስባውም ጉዳዩን ከወሲባዊ እርካታ ጋር ያመሳሰለው። ነገር ግን ይህ ሰላማዊ ታቀውሞም/ድጋፍ የሌሎቹን መብት የሚጥስ መሆን የለበትም። የሌሎቹን መብት መጣስ በሚጀምርበት ወቅት የሞራል የበላይነቱን እና ሕጋዊነቱን ያጣል፤ ስኬቱም ይከሽፋል። እናም አደባባይ ለድጋፍ/ተቃውሞ የሚወጣ ህዝብ የሰላማዊ ሰልፍ አስኳል የሆነውን ሰላማዊነትን (Peaceful nature) መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል።

እነዚህ ሰልፈኞች ምን ሊያገኙ ነው አደባባይ የወጡት የሚለው ተያያዥ ጥያቄን ስናይ ደግሞ፤ ከላይ የጠቀስነው ስርኣቱ ለኤም ከለላ ይሰጣል ከሚለው ጥቅል ለዲሞክራሲው ከሚሰጥ ይሁንታ (Legitimacy) ጀምሮ ተሳታፊዎች እንዲነቃቁ ማሳቻሉ፤ የሰልፉ አካላት አንድነትን እንዲያዳብሩ እና መፍትሄ በጋራ እንዲሹ (Promotion of a sense of solidarity) ፤ እንዲሁም የተነሱበት አላማ ገዝፎ እንዲታይ (To increase the visibility of the cause) እና ምላሽም በተሻለ መንገድ እንዲያገኝ ያስችላል።

## የመንግሥት ግዴታ

መንግስትስ ሚናው ምን ሊሆን ይገባል? የሚለው ጥያቄም ወሳኝ ነው። በመጀመሪያ መንግስት የብዙሃኑን ህግ ለማስጠበቅ፤ የህዳጣኑን መብት ደግሞ ለማክበር ነው የተቀመጠው ካልን፤ ከብዙሃኑም ሆነ ከህዳጣኑም ወገን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሰልፍ እወጣለሁ የሚልን አካል ባለመከልከል ግዴታውን መወጣት ይኖርበታል። የዘመናዊ ህገ መንግስቶች መሰረት Yሆነው የአሜሪካ ሕገ መንግስት በመጀመሪያው ማሻሻያው ይሄን ግዴታ በፌደራሉ መንግስት ላይ ይጥላል። ሰዎች ምንም አይነት ስብሰባ ለማድረግ በሰላማዊ መልኩ መሰብሰባቸውን እና ጉዳታቸውን ለመግለጽ የሚያደርጉትን ማንኛውንም አይነት ሰላማዊ የአቤቱታ መግለጫ መንገድ የሚከለክል ህግ መንግስት ማውጣት አይችልም ብሎ ያፀናዋል።

የዚህ አይነት መንግስት በመብቱ ጣልቃ እንዳይገባ የሚከለክሉ ህጎች መብቱን ተፈጥሮዊ (Inherent) መሆን ግምት ውስጥ የሚያስገቡ ናቸው። ዜጎች መብቱን ያገኙት ከህግ ሳይሆን ከተፈጥሯቸው ነው፤ መንግስት ደግሞ በተፈጥሮዊ መብታቸው ላይ ጣልቃ መግባት አይችልም በማለት መንግስት ራሱን ጣልቃ ከመግባት እንዲያቅብ የሚያስገድዱ መብቶች ናቸው።

የኢፌድሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 30 ላይ ይሄን መብት እንደ ተፈጥሮዊ መብት (Human Rights) ባይቆጥረውም፤ በዲሞክራሲያዊ መብትነት (Democratic Rights) ተቀብሎ መብቱን ለዜጎች ይሰጣል፤ በተዘዋዋሪም (A contrario) ይሄን መብት የሚፃረሩ ማንኛውም አይነት ተግባር ሊኖር እንደማይችል ይገልፃል። በሰላማዊ መንገድ የመሰለፍ እና የመሰብሰብ መብትን በተመለከተ በመንግስት በኩል ያለው ዋነኛ ግዴታ፤ መብቱን የሚፃረር ምንም አይነት ህግ ከማውጣት መቆጠብ እና በተግባርም መብቱን ለዜጎች መተው ነው።

ከዚህ የመታቀብ አሉታዊ ግዴታ (Obligation to refrain) በተጨማሪ፤ በሰላማዊ መንገድ የመሰለፍ እና የመሰብሰብ መብትን ከማስከበር አንፃር ከመንግስት የሚጠበቅ አዎንታዊ ግዴታም (Positive obligation) አለ፤ የዜጎችን ደህንነት እና ፀጥታ ማስከበር፡፡ ይህ ግዴታ በዋነኛነት የሚመነጨው ከመንግስት-ዜጎች ማህበራዊ ውል (Social Contract) ነው፡፡ መንግስት የዜጎች ተወካይ ሁኖ ሲቀመጥ፤ ዋነኛው ስራው የዜጎችን ፀጥታ እና ደህንነት ማስከበር ነው፡፡ እናም ዜጎች በሰላማዊ መንገድ የመሰለፍ እና የመሰብሰብ መብታቸውን ሲጠቀሙ መንግስት ደህንነታቸውን ማስከበር ይኖርበታል፡፡ ይህ ግዴታ በሁለት መንገድ ጠቃሚ ሆኖ ይገኛል፤ የመጀመሪያው በሰላማዊ መንገድ አደባባይ የወጡትን ዜጎች (ምን አልባትም ህዳጣኑን) ደህንነት ከመጠበቅ አኳያ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሰልፉ ላይ ያልተሳተፉ ዜጎችን (ምን አልባትም ብዙሃኑን) ከምንም አይነት የደህንነት ስጋት ነፃ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህም በሰላማዊ መንገድ የመሰለፍ እና የመሰብሰብ መብትን ከማስጠበቅ አኳያ የመንግስት ግዴታዎች በሁለት ትይዩ ይቀመጣሉ፤ መብቱን የሚፃረር ሕግ ባለማውጣት እና የመብቱ ተጠቃሚዎችን ከለላ በመስጠት፡፡

በመግቢያችን የጠቀስነው ኤሪክ ሆብስባውም የሰላማዊ ሰልፍ ፅኑ ባህሪ እንዲህ ገልፆ ይጨርሳል:-

*‹‹Unlike sex, which is essentially individual, it [Mass Demonstration] is by its nature collective...and it can be prolonged for hours....It implies some physical action--marching, chanting slogans, singing – through which the merger of the individual in the mass, which is the essence of the collective experience, finds expression."*

# የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የመውጣት መብቶች

በ[ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም]

በሥራ ላይ አለ የሚባለው በ1987 ዓ.ም. የወጣው ሕገ መንግሥት አንቀጽ 30ና 31 የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት፣ የመደራጀት መብት ይደነግጋሉ፤ ነገር ግን ሁለቱም አንቀጾች ግን እያሉ መፍረሻውን ወይም ማርከሻውን አብረው ይገልጻሉ፤ እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው ነው፡ይህ ዘዴ በአጼ ኃይለ ሥላሴም ሆነ በደርግ ሕገ መንግሥቶች ውስጥ የሚታይ ነበር።

የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የመውጣት መብቶች የሕዝቡን ስሜትና ፈቃድ ለማወቅ ለሚፈልግ መንግሥት የእነዚህ መብቶች በተግባር መዋል በጣም ፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም መንግሥትንና ሕዝብን ያቀራርባሉ፤ የእነዚህ መብቶች መታፈን የሚያሳየው በመንግሥት ፋንታ አገዛዝ መኖሩንና ሕዝቡን ያለፈቃዱ በኃይል ብቻ የሚገዛ መሆኑን ነው።

አንቀጽ 30‹‹ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፤›› ከአለ በኋላ ‹‹ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ፤›› በማለት የአንቀጹን ዋና ርእስ ያደበዝዘዋል፤ ያውም ምንም ትርጉም በሌለው ማመካኛ ነው፤ እግዚአብሔር ያሳያችሁ መሠረታዊ የሆነ የዴሞክራሲ ማሙያዎች የሆኑትን የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍን የማድረግ መብት ‹‹ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ›› በሚል በተምታታና ግልጽ ባልሆነ አስተሳሰብ ዋናውን መብት ለመገደብ ‹‹ሕጋዊ›› የሚመስል ማመካኛ ፈጠሩ፤ በዚህም ምክንያት በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉ የሚመስሉት አንቀጾች በተግባር ታግተዋል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመሰብሰብም ሆነ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ መትረየስንና ክላሽን የሚጋርድና የሚከላከል ጥላ ያስፈልጋል፤ እነዚህ የሕገ መንግሥቱ አንቀጾች ከሥራ ውጭ በመሆናቸው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበርና የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ወደአለመኖር ተሸጋግረዋል።

አሁን ደግሞ በፖሊቲካ ፓርቲዎች ላይ ጭቆናውና አፈናው እየበረታ በመሄዱ ፖሊቲካ ፓርቲዎች ሕዝባዊ ስብሰባ የሚያደርጉበት አዳራሽ (የግልም ሆነ የመንግሥት) ማግኘት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰናል፤ በሰላማዊ ሰልፍም አገዛዙ መሳቂያና መሳለቂያ ሆኖአል፤ ለግራዚያኒ በኢጣልያ የሚሠራውን ሐውልት ለመቃወም ጥቂት ዜጎች በስድስት ኪሎ ቢሰበሰቡ ፖሊሶችና የደኅንነት ነጭ ለባሾች እየደበደቡ ይዘው፣ አንድ ቀን አስረው በበነጋታው በዋስ ለቀዋቸዋል፤ በፋሺስት ኢጣልያ ላይ ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት ካልተፈቀደ ለምን ይፈቀዳል?

በዚህ ሁሉ ላይ ጋዜጠኞችን ሽብርተኞች እያሉ ወደወህኒ ቤት በመወርወር ጋዜጠኞች ሁሉ አንድም ወደስደት አንድም ወደወህኒ እየገቡ ነጻ ጋዜጣ እየጠፋ ነው፤ ስለዚህም በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ሁለገብ አፈና ሰፍኖአል ለማለት ይቻላል።

በኢትዮጵያ ሕዝቡ ቤቱ ሲፈርስ፣ መሬቱን ሲነጠቅ፣ ከኑሮው እየተፈናቀለ ሲባረር፣ ፍትሕ ሲጠፋ፣ ክብሩንና ኩራተን ተገፎ በያገሩ ሲሰደድና ውርደት ሲደርስበት ተሰብስቦ ለመወያየት መብት የለውም፤ በተናጠል እንባውን እያፈሰሰ ወደአምላኩ ማመልከት ልማድ ሆኖአል፤ በአገዛዙ ወንበር ላይ የተቀመጡት እግዚአብሔር የኢትዮጵያን ሕዝብ ግፍ የማያይ፣ ጩኸቱንም የማይሰማ ይመስላቸዋል፤ አግዚአብሔር ግን ሁሉንም ይመዘግባል፤ ለንስሐ የሰጣቸው ጊዜ ሲያበቃ ፍርዱን ለእያንዳንዱ ይሰጣል፤ ያን ጊዜ ኃይልም፣ ሀብትም፣ ሥልጣንም የሕዝብ ይሆናል።

# ሳንሱር እና ሕግ፡ ከትናንት እስከዛሬ

የሰው ልጅ ሐሳቡን ለሌላው መግለጽ መጀመሩ ሰዎች የጋራ ባሕርያትን ይዘው ወደ አዲስ ስልጣኔ፣ ወደ አዲስ ሕይወት እንዲወጣ አድርጎታል። ነገር ግን የዚህ ትስስር ድንበር የለሽ መሆን ጉዳት አለው በማለት፣ በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ ምክንያቶች መረጃን የመለዋወጡ ሂደት ገደብ እንዲኖረው ይደረጋል። ገደብ እንዲደረግ የሚያስገድዱት ዋነኛ ምክንያቶች ሦስቱን ዋነኛ ተቋማት መጠበቅ በሚል ሐሳብ ስር ይጠቃለል።

እነዚህም ተቋማት ቤተሰብ፣ ቤተ እምነት እና ቤተ መንግሥት ናቸው። ቤተሰብን መጠበቅ ስንል ቤተሰብ የኅብረተሰብ መሠረት በመሆኑ ቤተሰብን እና ስርዓቱን የሚጎዱ ነገሮች (Obscene) በአደባባይ እንዳይኖሩ ማድረግ ማለታችን ነው። ቤተ እምነትን የሚያጎድፉ ነገሮችም (Blasphemous) እንዲሁ:: እንዲሁም በሦስተኛነት በሕግ የተዘረጋውን ስርዓት ለመጠበቅ ሲባል ሲሆን ይሄም የግደባ ሂደት ሳንሱር (Censorship) ይባላል።

## የሕግ ማዕቀፉ እና ልምዱ ምን ይላል?

ከላይ የጠቀስናቸውን ሦስት ተቋማት ከመጠበቅ አንፃር የተለያዩ ሀገሮች የተለያየ የህግ ማዕቀፍ ዘርግተው ጥበቃ ያደርጋሉ። ከጥንታዊቷ ሮም እስከ የዘመናችን ነጻ እና ለዘብተኛ (Liberal) ሀገሮች ድረስ በተለያዩ ምክንያቶች በመነሳት የሐሳብ ዝውውርን በሕግ ሲገድቡ ነበር፣ አሁንም ይገድባሉ። ነገር ግን የሕግ ገደቡ ያለ አግባብ ተለጥጦ የግለሰቦችን መብት መግፈፍ ሲጀምር ያኔ የገደቡ ስህተት ይጀምራል። ለምሳሌ የሮማን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከመካከለኛው ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ ለተከታዮቹ 500 ዓመታት፣ አብዛኛውን የሳይንስት አስተምህሮቶች (የጋሊሊዮን መሬት በፀሐይ ዙሪያ ትሽከረከራለችን የሚል እሳቤን ጨምሮ) እንደ የኑፋቄ ትምህርት (Heresy) በመቁጠር፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ ምንም ዓይነት ስርጭት እንዳይደረግ በማለት በሕግ ገድባ ቆይታለች፣ ሕጉንም የተላለፉትን ከእስራት እስከሞት ትቀጣ ነበር። ይሄም የተደረገው የሕግ ገደብ የሳይንሱን ዕድገት አቀጭጮት ነበር። በጥቅሉ አሁን ባለው አለም አቀፍ እሳቤ ሐሳብን ማሰራጨት ሙሉ ለሙሉ የተፈቀደ መብት (Absolute Right) እንዳልሆነ ጥቅል ስምምነት ቢኖርም፣ ገደቡ ከየት ይጀምር የሚለው ግን አከራካሪ ነው።

## ምኑ ይገደብ?

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ሊገደብ የሚገባው መብት የትኛው መሆን አለበት የሚለው ሐሳብ ስምምነት ላይ ያልተደረሰበት ጉዳይ ነው። ነገር ግን እንደ ኀልዮት ሊቃውንት የተለያየ ሐሳብ ይሰነዝራሉ። መንግሥት ራሱን እንደ ጠባቂ እና ሁሉን አድራጊ (state as Big Brother) በማድረግ ይህ የተፈቀደ ነው፣ ይህ ደግሞ የተከለከለ ነው የሚል ከሆነ የዜጎችን መብት ሊያቀጭጭ ይችላል የሚለው እሳቤ አንዱ ነው። ይህም - ይሄን ብትናገር፣ ብትጽፍ፣ ብታሰራጭ ዋ! - ማለት ሳንሱር በማስፈራራት (Censorship through intimidation) የሚለው ሐሳብ ነው። ሊቃውንቱም ይህ መሆን የሌለበት ነገር ነው ይላሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት እንደ የኅብረተሰቡ ተወካይነቱ (As agent of the Society) ኅብረተሰቡ የማይቀበላቸውን ነገሮች በሕግ መገደቡ ተገቢ ነው የሚለውን ሐሳብ እናገኛለን። ይህም ማለት መንግሥት እና ኅብረተሰቡ በሚገደበው ነገር ላይ ስምምነት አላቸው እንደማለት ነው - Censorship through consensus። ይሄም የኅብረተሰቡን የሞራል እሴቶች የሚፃረሩ ጉዳዮች ላይ ገደብ መጣሉ ተገቢ ነው ወደሚለው ሐሳብ ያደርሰናል።

ስንጠቀልለውም በቀዳሚነት (As a Rule) ሐሳብን የመግለጽ ገደብ አይኑር፣ ነገር ግን ኅብረተሰቡ ላይ ጉዳት ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮች ላይ ገደብ ማድረግ ይገባል ወደሚለው ድምዳሜ እንደርሳለን።

## ገደብ በኢትዮጵያ (Censorship In Ethiopia)

የተጻፈ ሕግ በሀገራችን መተግበር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በጣሊያን ወረራ ጭምር በፖለቲካ ቢሮ አማካኝነት ቁጥጥር የነበረ ቢሆንም ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት ላይ ገደብ በማድረግ ቀዳሚነቱን የያዘው፣ የ1935ት ዓመተ ምህረቱ "የቴአትርና የሲኒማ አደራረግን ስለመመርመር" የወጣው አዋጅ ቁጥር 37/1935 ነው።

በርግጥ ነገር ግን ለሳንሱር መሠረት የሆነው የሕግ ማዕቀፍ የተዘረጋው ከወረራው መቀልበስ በኋላ በወጣው አዋጅ ነው፡፡ በዚህ ‹ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን ለመመርመር በወጣ አዋጅ› አንቀጽ 4 መሰረት፡ ‹‹ማንኛውንም ፊልም፣ ቲያትር እና ሪቪው ይህንም የመሰለ የልዩ ልዩ ጨዋታ ሁሉ የጨዋታ መርማሪ ሳይመረምራቸው ለሕዝብ እንዲታዩ ማቅረብ አይቻልም›› በማለት ይደነግግ ነበር፡፡ አስከትሎም አንቀጽ 7 ላይ ‹‹የጨዋታ መርማሪው ‹‹ማንኛውንም ፊልም፣ ቲያትር እና ሪቪው ይህንም የመሰለ የልዩ ልዩ ጨዋታ ሕዝብ ይየው ወይም አይየው ብሎ የሚወስን የሕዝብን ፀጥታና ንፅህና (ብልግና የሌለበት መሆኑን) አይቶ ነው፡፡›› በማለት የገደቡ ምክንያት ደህንነት እና ንፅህናን መጠበቅ እንደሆነ ቢነገረንም፤ ስርዓቱን የሚያስኮርፉ ማናቸውም ድምፆችን ለመገደብ እንደ መሳሪያ ተደርጎ ይሠራበት ነበር፡፡ ይህ ሕግ  ንጉሡ ከሥልጣን እስከ ወረዱበት ዘመን ድረስ ዘልቆ ከስርዓቱ ጋር አብሮ ከሰመ፡፡

ደርግ ወደስልጣን በመጣበት የመጀመሪያ የሽኩቻ ዓመታት ገደቦቹ ላልተው ነበሩ ቢሆንም፤ ስልጣኑን አጥብቆ ሲይዝ ግን የበለጠ አክርሮ የተለያዩ አዋጆችን እና ደንቦችን እያከታተለ ያወጣ ጀመር፡፡ ኅብረተሰባዊነትን ይቃወማሉ ያላቸውን ሐሳቦችም በኅብረተሰባዊነት ስም እየማለ ሲያሻው በሕግ አሊያም በጉልበት ‹ሐሳብ የሚታሰብ እንጅ የሚነገር አይደለም› (You can thought anything but, you can't express it) በሚል ብሂል ሳንሱርን አክርሮ ይሰራበት ነበር፡፡

በንጉሡ እና በወታደራዊው መንግሥት ስርዓቶች ወቅት የነበረውን ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ከሎሬት ፀጋዬ ገብረመድኅን ግፍ የበለጠ የሚነግረን የለም፡፡ ሎሬት ፀጋየ እንዲህ ይላሉ፡-

*"ከፃፍኳቸው 41 ቴአትሮች ውስጥ (ከተረጐምኳቸውና በእንግሊዝኛም ከፃፍኳቸው ጭምር)፣ ዐሥራ ሁለቱን ሳንሱር ሙሉ በሙሉ አግዶብኛል፡፡ ሃያ አንዱን ቆራርጦብኛል፡፡ ሦስቱን ግማሽ ለግማሽ ጐራርዶብኛል፡፡ አራቱ ግን ገና ለመድረክ [አልቀረቡም] ከሦስቱ የሥነ ግጥም መጻሕፍቶቼ ውስጥ (ሁለቱ ገና አልታተሙም)፣ በሠላሳ ሰባት ነጠላ ዝርዝር ግጥሞቼ ምክንያት፣ የሳንሱር ቢሮ፣ የፀጥታው ክፍል ቢሮና የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቢሮ ከፍተኛ ሹማምንት ገስፀውኛል፡፡ ቀጥተውኛል፡፡ ዝተውብኛል፡፡ በአንዲት "ጆሮ ገድፍ" በምትባል ትንሽ ቴአትር ምክንያት የጃንሆይ መንግሥት ፀጥታ ቢሮ፣ ለሃያ አራት ሰዓት በቁጥጥር ስር አውሎኛል"*

## ‹ሳንሱር ደህና ሰንብች›

የደርግ ስርዓት መገርሰስ ካመጣቸው መሠረታዊ ለውጦች አንዱ ሐሳብን በነጻነት የመግለጸ መብት መከበሩ ነው፡፡ የሳንሱር ቢሮም መዘጋቱ፡፡ ለዚህም መብት የመጀመሪያ ከለላ የሆነው የ1983 ዓ.ም የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር ነው፡፡ ቻርተሩ በአንቀጽ አንድ ዓለም አቀፉ የሰብኣዊ መብት ደንጋጌ (Universal Declaration of Human Right) ያለምንም ገደብ ለኢትዮጵያዊያን ተግባራዊ የሚደረግ ሰነድ መሆኑን ከደነገገ በኋላ በተለይም እያንዳንዱ ግለሰብ የእምነት፣ ሐሳብን መግለጽ፣ የመደራጀት መብት አለው›› በማለት ይደነግጋል፡፡ ይሄንም ተከትሎ 1985ቱ የፕሬስ ሕግ መውጣት ሀገሪቱ ሐሳብን የመግለጽ መብትን ያለገደብ ለማክበር ቆርጣ መነሳቷን አመላካች ሆነ፡፡

ለዚህ ነጻነት ሕገ መንግሥታዊ ድጋፍ ለመስጠት በማሰብም በ1987 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ፡ ‹‹ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል፡፡›› በማለት በአመለካከት ደረጃ ምንም ዓይነት ገደብ እንደሌለ አስረግጦ ሲያበቃ፤ በተመሳሳይ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ደግሞ ‹‹ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሐሳቡን የመግለጽ ነጻነት አለው፡፡ ይህ ነጻነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሐሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነጻነቶችን የካትታል፡፡›› ብሎ መብቱን ያሰፋዋል፡፡ እንዲሁም በዚሁ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 3 ላይ ‹‹የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ ነው፡፡›› በማለት ነፃነትን በሰፊው ያውጃል፡፡ ነገር ግን ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት በሕግ ገደብ ሊደረግበት እንደሚችል አንቀፁ ያትታል፡፡

## ‹ሳንሱር እንደገና›!?

እነዚህ ሁሉ መብቶች በሰፊው በሕግ ከለላ ማግኘታቸው ኢሕአዴግ ሥልጣን በያዘበት የመጀመሪያው ዐሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደ ትልቅ እምርታ የሚታይ ሲሆን ይሄንም ተከትሎ በሀገሪቱ ውስጥ የፕሬስ መስፋፋት እንዲሁም ሐሳብ መግለጫ ሜዳው መስፋት አሳይቷል፡፡ የተለያዩ መጽሔቶች ጋዜጦች እና የስነጽሑፍ ሥራዎች (መጽሐፍትን ጨምሮ) ስርጭትም በሚታይ ሁኔታ መስፋፋት ጀመረ፡፡ ይህ ሁኔታ ያልሰከነ በመሆኑ የሚታማውን የቅድመ 97 የፕሬስ ዘመን የሚጨምር ሲሆን ለዓመታት በቋሚነት የቆዩትን እንደነ ጦቢያና ጦማር የመሳሰሉትን የሕትመት ውጤቶችን ይዞ ዘልቋል፡፡ የምርጫ 97 ውጤት ደም አፋሳሽ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መንግሥት በጉዳዩ ላይ የፕሬስ ተቋማት ሰራተኞችን እና ጋዜጠኞችን ማሰሩን አስከትሎ ጠበቅ ያለ አቋም መያዝ ጀመረ፡፡

## አዋጆቹ

ከምርጫ 97 በሁዋላ ምንም እንኳን የወንጀል ሕጉ ሐሳብን ከመግለጽ ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ ወንጀሎች እንደሚያስቀጡ ቢደነግግም ከዚህ በተጨማሪ ጋዜጠኞችን የሚጫኑ ቅጣቶችን በማከል ከብዙ አተካራ በኋላ የመገናኛ ብዙኃን እና የመረጃ ነጻነት አዋጅ ሕግን አፀደቀ፡፡ ከብዙ አካላትም በዋነኛነት ከጋዜጠኖች ሕጉ አፋኝ እና ሕገ መንግሥቱንም የሚፃረር መሆኑን በመግለጽ ተቃውሞ መሰማት ጀመረ፡፡

በማስከተልም አወዛጋቢው የፀረ-ሽብር ሕግ ለፓርላማ ቀርቦ ፀደቀ፡፡ የመገናኛ ብዙኃን እና የመረጃ ነጻነት አዋጅ እንዲሁም የፀረ-ሽብር ሕጉ ሐሳብን ከመገደብ (Censorship) ጋር ያላቸው ተዛምዶ በዋነኛነት ተዘዋዋሪ ነው፡፡ ይሄም ማለት የመገናኛ ብዙኃን እና የመረጃ ነጻነት አዋጅ ያስቀመጠው እስከ አንድ መቶ ሽሕ ብር የሚደርስ ቅጣት አቅመ ደካማውን ፕሬስ በአንዴ ከገበያ ውጭ ሊያደርገው ስለሚችል ጋዜጠኞች ራሳቸውን እንዲገድቡ (Self Censorship) የሚያስችል መሆኑ፤ እንዲሁም የፀረ-ሽብር ሕጉ ግልጽ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎችን ጭምር በሽብር ተግባርነት የሚፈርጅ መሆኑ ዜጎች ራሳቸውን እንዲገድቡ እና ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን አሳልፈው እንዲሰጡ ማድረጉ ነው፡፡ ይሄም በሕግ ቋንቋ ‹Chilling Effect› ወይም ‹ስጋት ለበስ ቅልበሳ› የሚባለው ነው፡፡ ይህም ማለት ዜጎች ቅጣትን በመፍራት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን ከመጠቀም ወደኋላ ማድረግ (discouragement of the legitimate exercise of a constitutional right) ነው፡፡

እነዚህ ቀጥተኛ ያልሁኑ የራስን ግደባ ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ መንግሥታዊ ተቋማት ‹የሥራ ውል› በሚል መጠሪያ፤ ለሕትመት የሚበቁ ጽሑፎችን በመርማሪ አስመርምረን ነው የምናትመው ማለታቸው፤ ጉዳዩን ከማባስም አልፎ በሕገ መንግሥት በግልጽ የተከለከለውን ሳንሱር በእጅ አዙር እየመጣ ነው እንዴ? ብለን እንድንጠይቅ ያስገድደናል፡፡

ከነዚህ ሕጎች እና ደንቦች በተጨማሪ እያደገ የመጣውን የድረ-ገጽ ተጠቃሚ ቁጥር መሠረት በሚያደርግ መልኩ ከምርጫ 97 ወዲህ ትክክለኛ ቁጥራቸውን ማወቅ የማንችላቸው ድረገጾች በኢትዮጵያ ብቸኛ የቴሌኮምኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ በሆነው በኢትዮቴሌኮም ሰርቨር እንዳይታዩ የሆኑ ሲሆን፤ ይሄም እገዳ (Censorship) ከአረቡ ዓለም መነቃቃት በኋላ እጅግ ተባብሶ በመቀጠል እንደ አልጀዚራ ያሉትን ዓለማቀፍ የዜና አውታሮችን ከማገድ ጀምሮ፤ የግለሰቦችን የማኅበራዊ ድረ-ገጽ አድራሻ እስከማፈን ቀጥሏል፡፡ (ከዚህ ጋርተያይዞ የዞን 9ኝን የጦማሮች ምን ጻፉ ጽሁፍ እዚህ ይመልከቱ) መንግሥት ለዚህ እና ከእገዳ ጋር ለተያያዙ ጥያቄዎች የሚሰጠው ምላሽ፤ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮን መንግሥታቸው ሀገሪቱን ከማረጋጋት አኳያ ማፈኑን እና የአፈና አቅማችን እያጠናከርን ነው ከማለታቸው በስተቀር፤ በደፈናው ‹እኔ አላገድኩም› የሚል ነው ፡፡(በተለይ የተለያዩ የፌስቡክ ገጾች እና ጦማሮችን የመዝጋት ልምድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተባባሰ መጥቶ የአቤ ቶክቻው የግል ፊስቡክ ገጽ፣ የዞን ዘጠኝ የፌስ ቡክ ገጽ እና ጦማር፣ ድምጻችን ይሰማ እንዲሁም በቀዳሚነት የተዘጋው የቀድሞው አዲስ ነገር ጋዜጣ የፌስ ቡክ ገጽ ይታወሳሉ፡፡)

ስናጠቃልልም የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት በግልጽ እገዳን እና አፈናን (Censorship) ከመከልከሉም በተጨማሪ፤ ኢትዮጵያዊያን መረጃ የማግኘት መብታቸው በሰፊው የተከበረላቸው መሆኑን ያትታል፤ ነገር ግን በተለይም ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ መንግሥት በሚያወጣቸው ሕጎች እንዲሁም ከሕግ ውጭ በሆኑ አካሄዶች እነዚህን መብቶች እያጠበባቸው እና እየገፋቸው እንደሆነ እውነታዎች ያሳያሉ፡፡ ይሄም በሀገሪቱ አንድ ዓይነት አስተሳሰብ (Singular Discourse) እንዲኖር መፈለጉም የዜጎችን በሕገ መንግሥት የተሰጠ መብት፤ በአዋጅ መንጠቅና

ግፋም ሲል በጉልበት ወደመቀማት እየመራው ነው የሚለውን እሳቤ አጉልቶታል፡፡ ነገር ግን የBen Shahn ፖስተር “You have not converted a man because you have silenced him." ይለናል፡፡

# እስር ቤቶቻችን በሕገ-መንግሥት ወይንስ በ‹‹ሕገ-አራዊት››?

## እስርቤቶቻችንና ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች

በጌታቸው ሺፈራው

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትን እንዲጸድቅ በበላይነት የመሩት አቶ መለስና አቶ ሌንጮ ለታ መሆናቸው ይነገርላቸዋል፡፡ ይህ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ጉዳይ ቀጥተኛ ተሳታፊ ባልሆኑት የተገንጣይ መሪዎች ጠንሳሽነት የጸደቀው ሕገ መንግሥት ለአገር ሉኣላዊነት፣ አንድነትና ታሪክ ክብር የሌለው ቢሆንም ዓለማቀፋዊ የሰብኣዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አጠቃልሏል፡፡ ሆኖም እነዚህ ሰብኣዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለእርዳታ ማሰባሰቢያ የተቀመጡ እንጂ ወደመሬት ወርደው ተግባራዊ መሆና ባለመቻላቸው የይስሙላህ ሕግ ሆኗል፡፡ ከሕገ መንግሥቱ ይልቅ የገዥዎች ጊዜያዊ ሥልጣን ጥቅም ለማስጠበቅ በየጊዜው ትርጉሙ የሚቀያየረው የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ‹‹መርሕ›› ሕዝብ ላይ የተጫነ ገዥ ሕግ ከሆነ ሰነባብቷል፡፡ ይህን ስርዓት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ‹‹ሕገ አራዊት›› ሲሉ ይገልጹታል፡፡ በዚህ ስርዓት ሕዝብ በሕግ ስም እንጂ በሕግ የሚዳኝበት አጋጣሚ አይታይም፡፡ ብዙዎቹ በዚህ ስርዓት ያለውን የኢትዮጵያን ሕዝብም የታሰረ፣ ታስሮ የተፈታና ለወደፊት የሚታሰር እያሉ በቀልድ መልክ በሦስት የእስራት ምድብ ያስቀምጡታል፡፡ እንደ እኔ ሌላ አራተኛ ምድብም ሊካተት ይገባዋል፡፡ ይኸኛው እንደ ሦስቱ ምድቦች የአካል ጉዳትና ሰብኣዊ መብት ጥሰት የማይደርስበት ሕገመንግሥቱን አጽድቆ ራሱ የሚጥሰው አሳሪው ክፍል ነው፡፡ ይህ አሳሪው የኅብረተሰብ ክፍል በአካል ያልታሰረና ስርዓቱ እስካለ ድረስ በአካል ሊታሰርበት የሚችለው አጋጣሚ ጠባብ ቢሆንም የአዕምሮ እስረኛ ነው፡፡

ኢሕአዴግ እየዘመረለት የሚገኘው አቶ መለስና በእኩል ደረጃ የሚያወግዘው ‹‹አሸባሪው›› አቶ ሌንጮ ያጸደቁት ሕገ-መንግሥት ኢትዮጵያውያን ታሳሪዎች ምቹ ሁኔታ እንዲመቻችላቸው በርካታ አንቀጾችን አስቀምጧል፡፡ ለአብነት ያህል አንቀጽ 19 (2) የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ‹‹የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይንም ማንኛውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም፡፡ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡›› ቢልም በተለያዩ ጊዜያት የተሰሩ የፕሮፖጋንዳ ፊልሞች ላይ ‹‹እማኝነታቸውን›› የሰጡ ታሳሪዎች የሚሰጡት ቃል በኃይል የተደረገ መሆኑ እየተነገረ ነው፡፡

መጋቢት 8/2005

ይህን እውነታ እሁድ መጋቢት 8/2005 ‹‹ለማርሻል ግራዚያኒ ክብር መስጠት የአባቶቻችንን መስዋዕትነት ማራከስ ነው›› በሚል የተደረገ ሰላማዊ ሰልፍ ተከትሎ እኔና ጉዋደኞቼ በታሰርንበት ወቅት ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ አንድ ታሳሪ ከአንድ ጊዜ በላይ ቃል መስጠት እንዳለበት የሚገልጽ የሕግ አሠራር ባይኖርም ከሶስት እስከ አራት ጊዜ ቃል እንድንሰጥ ተደርገናል፡፡

በመጀመሪያው ዙር ሁሉም ሕገ መንግሥቱ ‹‹ሰጥቶኛል›› ያለውን መብት ተጠቅሞ ‹‹ቃል አልሰጥም›› ብሎ ፊርማውን አስቀምጦ ወጣ፡፡ በዚህ የተደናገጡት መርማሪዎች አንዳንዶቹን ቃል እንዲሰጡ ቢያባብሉም ሊሳካላቸው አልቻለም፡፡ በታጎርንበት ጣቢያም ሆነ በሌሎቹ ጣቢያዎች የፖሊስ አባል መሆናቸው ያልታወቀውና ከመጀመሪያው ጀምሮ ሰልፉን የበጠበጡት ‹‹ኮማንደር›› ግን ‹‹ይህ ፒቲሽን በመሆኑ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል›› በሚል መርማሪዎች የቻሉትን ሁሉ ተጠቅመው ቃል እንዲቀበሉን ትዕዛዝ አስተላልፈዋል፡፡ ሆኖም ሁሉም ታሳሪዎች ቃል ሳይሰጡ ቀሩ፡፡ ይህን ተከትሎም የይስሙላህ ሕገ መንግሥቱ ተግባር ላይ የዋለው ለተወሰኑ ደቂቃዎች ብቻ ሆነ፡፡

ቃል አንሰጥም ካልንበት ወቅት በኋላ ለጥቂት ጊዜ ጠፍተው የቆዩት ‹‹ኮማንደር›› ታሳሪዎች በእየተራ ፎቶ ግራፍና ቪዲዮ እየተቀረጹ ሌላ ተጨማሪ ቃል እንዲሰጡ አደረጉ፡፡ ይህን ምርመራ የሚያከናውኑት ፖሊሶች ሳይሆኑ ደህንነቶች በመሆናቸው ቃል አልሰጥም የሚለው መብት አይሰራም፡፡ ተመርማሪው ገና ከመግባቱ ስድብና ዘለፋ ይገጥመዋል፡፡ ከእነኮማንደር በሚደርስ ቅድሚያ ፍረጃ አንዳንዶቹ ለቃል ከመግባታቸው ዱላ ጠብቋቸዋል፡፡ አብዛኛዎቹ ወጣቶች ብሄራቸውን ሲጠየቁ ‹‹ኢትዮጵያዊ›› በማለታቸው ዱላና ዱላ ቀረሽ ስድብና ዘለፋ ገጥሟቸዋል፡፡ አንዲት የሰማያዊ ፓርቲ አመራር ወጣት ከደህንነቶቹ በደረሰባት ድብደባና አስጸያፊ ዘለፋ እራት መብላት አልቻለችም፡፡የባሰው ደሞ ቅዳሜ መጋቢት 7 ቅስቀሳ ላይ እያሉ የታሰሩ ወጣቶች የደረሰባቸው ከፍተኛ

ድብደባ ነው፡፡ ተክለሀይማኖት አካባቢ ታስረው የነበሩት መካከል አንደኛው ብሔሩን ‹‹ኢትዮጵያዊ›› በማለቱ ይመረምረው የነበረው ደኅንነት ከመደብደብ አልፎ በሽጉጥ አስፈራርቶ መረጃ እንደጠየቀው አውግቶኛል፡፡ ቃል ስንሰጥ ከተጠየቅናቸው ጥያቄዎች በተጨማሪ የኢሜልና የፌስ ቡክ አድራሻና የይለፍ ቃል በግድ ተቀብለውናል፡፡ ‹‹በምርመራው›› በ1997 ዓ/ም ማንን እንደመረጥን ተጠይቀናል፡፡ መልሱን ከመመለሳችን በፊት ደኅንነቶቹ ራሳቸው ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ መምረጣችንን ያለ ጥርጥር እየነገሩ ‹‹አፍራሽነታችን›› የቆየ መሆኑን ለማስገንዘብ ሞክረዋል፡፡ ይህ ሁሉ የሚደረገው ለሕዝብ ይቆማል በሚባለው ፖሊስ ተቋም ግቢ ውስጥ ሲሆን ፖሊስ በደኅንነቶች የሚሰጠው ክብር ለታሳሪዎች ከሚሰጠው የሚለይ አይደለም፡፡

## የተያዙ ሰዎች አያያዝ በፓሊስ ጣቢያዎች

ተግባር ላይ መዋል ያልቻለው ሕገ መንግሥት አንቀጽ አንቀጽ 17(1) ‹‹ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብአዊ ከሆነ ወይንም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይንም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው›› ቢልም የሚፈጸመው ግን በተቃራኒው ነው፡፡ ስርዓቱ ለይስሙላህ ከሚጠቀምበት ሕገ-መንግሥት በተቃራኒ ‹‹በሕገ አራዊቱ›› እንደሚመራ በደንብ የተረዳሁት ለማሳላቸት ተብሎም ይሁን ለሌላ ዓላማ ከፖሊስ ጣቢያ ፖሊስ ጣቢያ ሲያዟዙሩን ካመሹ በኋላ ከለሌቱ አምስት ሰዓት ገደማ ቀጨኔ አካባቢ በሚገኘው ወረዳ 9 ፖሊስ ጣቢያ ከገባን በኋላ ነው፡፡ ከታሰርነንበት ጊዜ ጀምሮ በሆነ ባልሆነው በዚህ የወረዳ 9 ጣቢያ በተደጋጋሚ የታሰሩ የባለራዕይ ወጣት አመራሮች እንደተለመደው ለመቀጣጫ ወደዚሁ ጣቢያ ሊወስዱን እንደሚችሉ በእርግጠኝነት ይናገሩ ነበር፡፡ ማታ ላይ ሁላችንም ወደጣቢያው እንድንሄድ ተፈልጎ የነበረ ቢሆንም ቀድሞ በመሙላቱ የተወሰኑት ጃን ሜዳ አካባቢ ባለው የማዘዣ ጣቢያ እንዲያድሩ ተደርገዋል፡፡

በወረዳ 9 ሦስት በአራት የሆነች ጠባብ ክፍል ውስጥ እድሜያቸው 15 አመት የማይበልጥ ህጻናትን ጨምሮ 37 ሰው እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ በእርግጥ ይህ ክፍል እስከ 50 ሰው የሚይዝበት አጋጣሚ እንዳለ ታሳሪዎቹ ነግረውኛል፡፡ በክፍሉ ወስጥ በተነጠፈው ቆሻሻ የወለል ምንጣፍ ላይ ሰው በሰው ላይ ተኝቷል፡፡ ሙቀቱ ከፍተኛ በመሆኑ ብዙዎቹ ራቁታቸውን ናቸው፡፡ አስተባባሪዎቹ ከፖሊስ ቦታ እንዲፈልጉልን በተላለፈላቸው ትዕዛዝ መሠረት በዚህ መተላለፊያ በሌለው ቤት ውስጥ ለመቀመጫ ያህል ቦታ ሰጡን፡፡ ታሳሪ ወጣቶቹም የያዝነውን ገንዘብ እንድናስረክባቸው ጠየቁን፡፡ ተከትሎም ሳንቲም ሳይቀር ያለንን ገንዘብ በሙሉ ተቀብለውናል፡፡ይህ ታዲያ እኛ ወጣቶቹ ላይ ብቻ ሳይሆን ከእድሜ የገፉትም ላይ ተግባራዊ የሆነ ውስጣዊ የታሳሪዎች ህግ መሆኑን ሰምተናል፡፡እንዳስተዋልኩት ከሆነ ይህ ቤት ሰው እንደሰው የማይቆጠርበት ዘግናኝ ቤት ነው፡፡ በዚህ ሰዎች እንደሰው በማይቆጠሩበት ቤት ውስጥ ሰው ሊማር የሚችለው ጭካኔን ብቻ ነው፡፡ እንደገባንም የገጠመኝ ይህ ነው፡፡ በግድግዳው ላይ የተጻፉት ጽሑፎችም የሚያሳዩት ጨካኝ በሆኑት ታሳሪዎች ላይ የሚደርስባቸውን በደል ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ግድግዳው ላይ የተጻፉ ጽሑፎች እስረኞቹ ያለምንም ጥፋት መታሰራቸውን የሚገልጹ ናቸው፡፡ በተለይ ‹‹አገሬ ሆይ ወንድ አይወለድብሽ››፣ ‹‹በደልን ለማን ይነግሩታል››፣ ‹‹አይ ስቃይ››፣ ‹‹ገሃነብ ከመግባት በምን ይለያል››፣‹‹ሰው እንዴለለኝ›› የሚሉት ግድግዳው ላይ የተጻፉ ጽሑፎች የእስረኞችን ምሬት ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ፡፡ በዚህ በደል የተሞላበት እስር ቤት የሚገኙት አብዛኛዎቹ ታሳሪዎች ከጨካኝነታቸው ባሻገር የአእምሮ ችግርና ተስፋ መቁረጥ የሚስተዋልባቸው ናቸው፡፡ በቀጨኔውና በሌሎቹ በተዘዋወርንባቸው ለሰው የማይመቹ እስር ቤቶች ውስጥ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በተደጋጋሚ እንደሚታሰሩ በየግድግዳው የተጻፉት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ስም ዝርዝር ምስክር ነው፡፡ በእነዚህ ጨካኝ ቤቶች የሚገኙ እስረኞች ከስርዓቱ እንደሚሻሉ ግን እየቆዩም ቢሆን አሳይተውናል፡፡ በምን እንደታሰርን በነገርናቸው ወቅት ለእኛ የነበራቸው አመለካከት ተቀየረ፡፡ ቀደም ብለው ተደራርበው ተኝተው የነበሩትን በማስነሳት ሰፋ ብሎ ለማስቀመጥ የሚያስችል ቦታን እንድንተኛበት አመቻቹልን፡፡ እስረኞች ጫማና ልብሳቸውን ጨብጠው ነው የሚተኙት፡፡ አልፎ አልፎ ዘመድ ያመጣላቸውን ምግብም ከልብስና ጫማቸው ጋር መደበቅ የግድ ይላቸዋል፡፡ አንድ እስረኛ ሊቀርብለት የሚገባውን ምግብ ባይቀርብልንም የታሰርንበትን ምክንያት ዘግይተው ያወቁት ያች ጠባብ ቤት ውስጥ የሚገኙ እስረኞች በርህራሄ ከጓደኞቻቸው የደበቁትንና ለራሳቸው የቆጠቡትን ቆሎና ጁስ ለእኛ አቅርበውልናል፡፡ በተለይ እነ ዶክተር ያቆብ በእስረኞች ዘንድ ይታወቁ ስለነበር በሌላኛው ክፍል ውስጥ መታሰራቸውን ስንነግራቸው በስርዓቱ ላይ ያማረሩት ብዙዎቹ ናቸው፡፡ ከአንገቱ በላይ ካለው የሰውነት ክፍሉ ውጭ ቀሪው ሰውነቱ ላይ ጓደኞቹ የተኙበት አንድ ወታደር ዶክተር ያቆብና ኢ/ር ይልቃል በቀጣዩ ክፍል መታሰራቸውን ሲሳማ ‹‹ይች ግፈኛ አገር!›› ብሎ እንደገና ተኛ፡፡ ሌላኛው አዛውንት ‹‹ምሁሮቿን ሞባይል ሰርቀው ከተያዙ ሕጻናት ጋር ወለል ላይ እንደዚህ የምታስር አገር የት ትገኛለች?›› ለሚል ጥያቄያቸው መልስ ሳይጠብቁ ‹‹የኢትዮጵያ ምሁራን ክብር ቦታና ፓስፖርት እንደልባቸው ከሚሰጣቸው የሶማሊያ ስደተኞች ያነሰ ሆነ፡፡ አገራችን የጠላት እንጂ የዜጎቿ መኖሪያ አልሆነችም፡፡›› ብለው ተናገሩ፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ የተሻለ ጥንቃቄ ሲደረግለት ያየሁት ሽንት የሚሸናበት የጀሪካን ቅዳጅ ብቻ ነው፡፡ ይህ ጀሪካን ማንም እንዳይጫነው ጥንቃቄ የሚደረግለት ብቸኛው ታሳሪ ነው፡፡ ይህንም የሚያደርጉት ተደራርበው የተኙት እስረኞች የሽንት ማጠራቀሚያውን በሀይል ሲገፉት አሊያም በእንቅልፍ ልባቸው ሲወጡበት በተደጋጋሚ እየተደፋ ቤቱ ስለሚበላሽ ነው፡፡ የሰው ትንፋሽ እና በየቦታው የሚጨሰው ሲጋራ የክፍሉ ሌላኛው አስከፊ ገጽታ ነው፡፡ አብዛኛው እስረኛ ቀን የተወሰነች ሰዓት ተኝቶ ለሌቱን ሌሎች እስረኞች እንዳይጫኑት እየተከላከለ ቁጭ ብሎ ያድራል፡፡ አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርቦ ያደረው አብዛኛው እስረኛ በጠባቧ ግቢ ውስጥ ‹‹ሊዝናና›› ሲወጣ ቁጭ ብለው ያደሩት መተኛት ይጀምራሉ፡፡ ሆኖም በየደቂቃው በቆጠራና በሌላ ምክንያት እስረኞች ወደክፍል እንዲመለሱ ስለሚደረግ ሌሊት ከሚደርስባቸው ያልተለየ ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡ አንድ ሰው ከፍ ያለ ድምጽ በማሰማቱ አሊያም የመውጫ ሰዓት ደርሶ ፖሊስ ውጣ ሳይለው ሊወጣ በመሞከሩ ክፍሉ እንደገና በቅጣት ተቆልፎ ቤቱ ወስጥ ያለው ሁሉም ሰው አብሮ ይቀጣል፡፡

ዝቅተኛ ካድሬዎች ከሙቶ በላይ እስረኛ ከሚታጨቅበት የቀጨኔው እስር ቤት የተሻለ ስፋት ያለው የቀበሌ ቤት፣ ኮምደሚኒየምና ቪላ ባለቤቶች ናቸው፡፡ ከፍ ያለ ስልጣን ያላቸው ፖለቲከኞች፣ ዘመዶቻቸው፣ የደኅንነት ኃላፊዎች፣ ወታደራዊ አመራሮችና የመሳሰሉት ደግሞ ከሚኖሩባቸው ዘመናዊ ቤቶች በተጨማሪ በሽዎች ብር የሚያከራዩትን ቤት በሕዝብ ገንዘብ ገንብተዋል፡፡ ለሥልጣኑ ሲል ሰዎችን ማሰቃየት አንዱ ስልት ነውና በህግ ጥፋተኝነታቸው ያልተረጋገጠ ታሳሪዎች ወለል ላይ እግራቸውን ዘርግተው የሚተኙበት እስር ቤት ለመገንባት ፍላጎት ያለው አይመስልም፡፡ልንቃወመው ወጥተን በስርዓቱ ድጋፍ ያገኘው የፋሽስት ስርዓት እንኳ በሞቃዲሾና ሮም ቁም ስቅል ያሳዩትን ወገኖቻችንን ያጉርበት የነበረው እስር ቤት አሁን አዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙት በተለየ ሰው በቅጡ ሊያስተኛ የሚችል እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡

## እንዳያውቅ የተደረገው የሕዝብ ፖሊስ

ፖሊሶች ሕግ እንዲያውቁ አይደረግም፡፡ ሰላማዊ ሰልፉ ከመበተኑ ጀምሮ እስከተፈታንበት ጊዜ ድረስ ሰላማዊ ሰልፍ የመውጣት መብት በሕገመንግሥቱ መደንገጉን የሚያውቁ ፖሊሶች አላጋጠሙኝም፡፡ ሁሉም ይህ መብት ከፓርቲው የሚሰገስ አድርገው የሚቆጥሩ ናቸው፡፡ ሕግ እንዳያውቁ ተደርገው እንጂ ለአገራቸው ሕዝብ የተለየ ጥላቻ ኖሯቸው እንዳልሆነ ግን ዓላማውና ሕጉ ሲገባቸው ከእኛ ጎን ቆመው አበረታትተውናል፡፡ በተለይ አመራሮቻቸው ከነገሯቸው በተቃራኒ በፖሊሶች ላይ ግርታ የተፈጠረው በአንድ የፖሊስ መኪና እንደ ሸንኩርት ከሰው ላይ ሰው ጭነው ወደ ጣቢያ ሲወስዱን በመደብደባቸው ይሽማቀቃሉ ተብለው የተገመቱት ወጣቶች፡-

‹‹ተከብረሽ የኖርሽው በአባቶቻችን ደም፣ በአባቶቻችን ደም፣
እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም፣ ያስደፈረሽ ይውደም!››

እያሉ ሲጨፍሩ ነው፡፡ ሰባራ ባቡር አካባቢ በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ባረፍንበት ወቅት ሁሉም ሰው እስረኛ ሳይሆን ለሌላ ዓላማ የተገናኘ ያህል ልዩ ስሜት ውስጥ ነበር፡፡ ፖሊሶችንና ‹‹ኮማንደሩን›› ስለሕግ ያስረዳል፡፡ ስለአገሩ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይዘምራል፡፡ ኢሕአዴግን ይተቻል፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን የታሰርነውን ለማየት ወደጣቢያው ለመግባት ሙከራ ሲያደርጉ ፖሊስ ሲያስመልሳቸው ሁሉም ለእርሳቸው ክብር ከመቆም በጭብጨባ ክብራቸውን ገለጸላቸው፡፡ በወጣቶቹ ላይ መሽማቀቅና የጥፋተኝነት መንፈስ መመልከት ያልቻሉት ፖሊሶች ይበልጡት ተደናገጡ፡፡ ‹‹ኮማንደሩ›› እና አንዳንድ አመራሮች ደግሞ በመናደዳቸው ጨኸታችንን እንድንቀንስ በተደጋጋሚ ወቀሳ ያደርሱብን ነበር፡፡ ይህን ባለመሳካቱም በቪዲዮ ቀረጻ ተጀመረ፡፡ በወቅቱ ግን ለማሸማቀቅ በሞከሩት አካላት ላይ ይበልጥ ያናደደና ፖሊሶቹ ከእኛው ጋር እንዲሆኑ ያደረገ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ በወቅቱ ከወጣቱ ተለይተው ተቀምጠው የነበሩት እነ ዶ/ር ያቆብ፣ ኢ/ር ይልቃል፣ አቶ ታዲዮስና ሌሎችም በመጨመራቸው ድምፃችን ከፍ ብሎ መሰማት ጀምሯል፡፡ ለማሸማቀቂያነት የታሰበው ቪዲዮ መቅረጽ ሲጀመርም፡፡

‹‹ተከብረሽ የኖርሽው በአባቶቻችን ደም፣ በአባቶቻችን ደም፣
እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም፣ ያስደፈረሽ ይውደም!›› እንደገና ተዘመረ፡፡

እኛን ለመጠበቅና ለማስቀረጽ ፊት ለፊታችን መሳሪያና ዱላ ይዘው የተኮለኮሉት ፖሊሶች ከመገረም አልፈው በስሜት አብረውን ዘምረዋል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ፖሊሶቹ የጠየቅናቸውን ነገር ለማቅረብ ቀናኢ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ከተነገራቸው ባሻገር ሌላ አዎንታዊ ዓላማ ይዘን መነሳታችንን ማረጋገጥ የሚያስችላቸውን ጥያቄ በጓደኝነት መንፈስ ይጠይቁን ነበር፡፡ በኮማንደሩ ትዕዛዝ ከፖሊስ ጣቢያ ፖሊስ ጣቢያ ሲያንከራትቱንም ጠባቂ

ፖሊሶች ያጅቡን የነበረው ያለ መሳሪያ ነበር፡፡ ስልኮቻችን በመያዛቸው ከቤተሰብ ጋር መገናኘት እንደምንችል በማወቃቸውም ባለ አንስተኛ ደሞዝተኞቹ ፖሊሶች በራሳቸው ጥያቄ ብዙ ሰው ወደቤተሰብ እንዲደውል ተባብረዋል፡፡ እንደኛ ጾማቸውን ውለው የእረፍት ጊዜያቸው ሲደርስ የተለዩን በኀደኛና ዘመድ ስሜት ነው፡፡

## የመለስ ዜናዊ ፲ ታላላቅ የአፍ ወለምታዎች

የዞን ዘጠኝ ነዋሪዎች የሆኑት በፈቃዱ ዘ ኃይሉ **የመለስ ዜናዊ 'ሀሁ' በስልጣን ጎዳና** እንዲሁም ዘላለም ክብረት**መለስ ወደ ውጭ - መለስ ከውጭ** በሚል ርዕስ ሁለት ጦማሮች አስነብበውናል። ይህም ስለጠቅላያችን የጤና ሁኔታ ከነበረው ውዝግብ መለስ ብለን ሌሎች ሁኔታዎች እንድንቃኝ ዕድል ሰጥቶናል ።ዛሬ ቀኑ ቅዳሜ ነው፤ እስኪትንሽ ቅዳሜ ቅዳሜ የሚሸት ነገር እያወራን ዘና እንበል በሚል ደግሞ ይችን ጽሑፍ ከ**ዱራሜ ዶት ኮም** ያገኘነውን የጠቅላያችንን አስር ታላላቅ የአፍ ወለምታዎች ፣ በዚህ ንግግራቸው የተገረመው አብዛኛው ሰው ወደሚሰማው ቋንቋ እንደወረደ ተርጉመን ለአደባባይ አውለነዋል።

፩. በ1983 ዓ.ም. በለንደኑ ጉባዔ በኢህአዴግ ታርጋ የተሰባሰቡት ቡድኖች የፓርቲያቸው ህወሓት ተቀጥላ እንደሚሆኑ ለአሜሪካና ብሪታኒያ ባለስልጣናት አረዷቸው።ብሪታኒያውያኑ ይህንን በተቃወሙ ጊዜ ቁጣቸው በግልጽ የሚታየው አቶ መለስ እንዲህ አሉ።

***"አንድ ነገር ግልጽ ላድርግ ፤ ከጉባዔው በኋላ ኢህአዴግ የሚባል መንግስት አይኖረንም።"***

፪. በ1985/6 ዓ.ም. ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ያላቸውን እይታ በአንድ ቃለ መጠይቅ ማብቂያ ላይ እንዲያካፍሉ ከአንድ ዘጋቢ ለቀረበላቸው ጥያቄ አቶ መለስ እንዲህ ሲሉ መለሱ።

***"የኢትዮጵያ ዕድሜ መቶ ዓመት ብቻ ነው ፤ከዚህ በቀር ሌላ የሚያወሩት ራሳቸውን በተረት ተረት እያሞኙ ነው።"***

፫. በ1986/7 ዓ.ም. አስመራ ከተማ ውስጥ ለአንድ የውጭ ሀገር ጋዜጠኛ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ስለ ኤርትራው ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቅ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል።

***"ከኢሳይያስ ጋር አንድ ሰዓት ማሳለፍ፣ 10 መጽሐፍ ከማንበብ በላይ ልበብሩህ፣ አዋቂ እና ተጠቃሚ ያደርጋል።"***

፬. ለአምስት አስርት ዓመታት የኢትዮጵያን ታሪክ ካጠኑት ፕሮፌሰር ዶናልድ ሌቪን ጋር በ1989 ዓ.ም. በነበራቸው ወይይት ከምንሊክ ወረራ በፊት ኢትዮጵያ የምትባል አንዲት አገር እንዳልነበረች ተናገሩ።ይህ የበለጠ አጽንኦት ለመስጠት ሲሞክሩ እንዲህ አሉ።

***"ትግሬዎች የአክሱም አላቸው ፤ ይህ ለጉራጌ ምኑ ነው? አገዎች ላሊበላ አላቸው ፤ ይህ ለኦሮሞ ምኑ ነው? ጎንደሬዎች ቤተ መንግስት አላቸው፤ ይህ ለወላይታ ምኑ ነው?"***

፭. ለመንግስት ሚዲያዎች በሰጡት አንድ ቃለ መጠይቅ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ከጨርቅነት የዘለለ ምንም እንዳልሆነ ተናገረዋል።

***"ባንዲራ የጨርቅ ቁራጭ ነው"***

፮. በ1990 ዓ.ም. ሰማኒያ ሺ የሚደርሱ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ኤርትራውያንን ሀብት ንብረታቸውን ቀምተው ኢ-ሰብዐዊ በሆነ መልኩ ከሀገር ካስወጡ በኃላ ለፓርላማው እንዲህ አሉ።

***"የአይናቸው ቀለም ካላማረን ፣ ከሀገራችን የማባረር መብት አለን።"***

፯. በ1993 ዓ.ም. ልጇ ወደ ኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ዘምቶ አለመመለሱ ያሳሰባት እናት ልጇ ወዴት እንዳለ መለስ ዜናዊን አጥብቃ ጠየቀች።በጥያቄዋ ድምጸት የተበሳጩት አቶ መለስ እንዲህ ሲሉ መለሱ።

***"ሴትዮ፣ ልጅሽ በስድስት ወራት ወደቤቱ ካልተመለሰ ፣ መልሱን ታውቂዋለሽ።"***

፰. በ1997 ዓ.ም. ምርጫን ተከትሎ በተካሄደው ህዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ በጠቅላያችን ትዕዛዝ 193 ያልታጠቁ ንጹሐን ዜጎች በአዲስ አበባ እንዲገደሉ ትዕዛዝ ሲሠጡ የትግራዋይ ተወላጅ ለሆነው ለታማኛቸው ጄኔራል ሳሞራ አማራዎችን ለማለት አህዮች የሚለውን ቃል ተጠቅሟል።

***"እነዚህ አህያ አማራዎች ትምህርት ያስፈልጋቸዋል።ሰላማዊና ሃይማኖተኛ የሚሆኑት ክላሽንኮቭ ስትደግንባቸው ብቻ ነው።"***

፬. ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ የከሸፈ ፣ ተከተታይ ወረራ  በ1998 ዓ.ም. በሱማሊያ መሬት ላይ መሬት ያዛ በነበረበት ሰዓት ለ ኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ አላማቸው የኢስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረትን ለማንበርከክ ሳይሆን በዚያ የሌሉትን በሱማሊያ የሚገኙት የኤርትራ ወታደሮች ለማሰደድ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

***"እያጠቃን ያለነው  በሱማሌ ወይዛዝርት ቀሚስ ስር የተሸሸጉ የኤርትራ ኃይሎችን ብቻ ነው፡፡"***

፭. በ2002 ዓ.ም. ከሊቢያው አምባገነን ሙዐመር ጋዳፊ ጋር ስለ ሁለትዮሽ ግንኙነት በሚወያዩበት ጊዜ አቶ መለስ እንዲህ አሉ፡፡

***"እኔ የመናዊ ነኝ ፤ የመናዊ እንደሆንኩኝ አውቃለው ፤ ሁላችንም የመናውያን ነን፡፡ ከነገሥታቱ ቤተሰብ በቀር ሁላችንም አረብ ነን፡፡"***

# የሁለት 'ሚኒስትሮች' ወግ

ወግን *‹‹ሥርዐት ደንብ ወይም የተደረገውን ታሪክ ማውጋት መተረክ ፣ ለሹሞች ለአለቃ ለቄስ ገበዝ የሚሰጥ ወይም የነፍስ አባት የሙት ልብስን አልጋን ዋንጫን መግፈፍ፡፡››* ብሎ ከሳቴ ብረሃን የአማርኛ መዝገበ ቃላት ይፈታዋል፡፡

እኛም ከዚህ ትርጉም ውስጥ *‹‹የተደረገውን ታሪክ ማውጋት መተረክ››* የሚለውን ተከትለን የሁለት መሪዎችን/ጠቅላዮችን ጨዋታ እንጫዋወታለን፡፡

Twitter በተባለው የማህበራዊ ድረ ገፅ እስከ ፈረንጆቹ 2012 ድረስ ከ 140 ሚሊየን በላይ ግለሰቦች ተመዝግበው ስለተለያዩ ጉዳዮች ሃሳባቸውን ያካፍላሉ በተከታዮቻቸውም (Followers) ምላሽ እና አስተያየት ያገኛሉ እነርሱም የፈለጉትን ሰው መከተል (Follow) ይችላሉ፡፡

ከነዚህ መራጆች (Twitterati) መካከልም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ @MelesZenawi እና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ @HailemariamD እንደሚገኙበት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰምተናል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ Twitterን የተቀላቀሉት ከ3 ዓመት በፊት ማለትም April 9/2009 እንደሆነ የTwitter ታሪካቸው ያስረዳል፡፡ በመጀመሪያ ያደረጉት Tweetም "Just had some of my favorite Shiro. Thank You Chef" የሚል ሲሆን፡፡ ይህችም Tweet በተለያዩ ግለሰቦችም ዘንድ የተለያየ አንድምታ የምትፈጥር ሆናለች፡፡

- አንዳንዶች *‹‹እንዴ ስለ ምግባቸው ማውራታቸው ከፖለቲከኝነት ይልቅ Holywoodian መሰሉ እኮ››*ሲሉ፣
- *‹‹የለም የለም እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ከድሃ ቤተሰብ ተወልደው በድህነት እንደማደጋቸው እርሳቸውም ሽሮ እየበሉ ኑሮን እንደሚገፉት ያመላክታል››* ይላሉ ሌሎች፣
- ከፓርቲው አካባቢ የሚመስሉ ሰዎች ደግሞ *‹‹እኛ በአበል እና በመሳሰሉት ወጭዎች በመደገፍ ቀይ-ክትፎ እንቆርጣለን እርሳቸው ሽሮ ነው ምግባቸው አቤት መስዋዕትነት!››* ሲሉ ይደመጣሉ፡፡

የሆነ ሆኖ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህችን አነጋጋሪ Tweet ካደረጉ በኋላ ለሁለት ዓመታት ከTwitter መንደር ጥፍት ብለው ከርመው በ April 2011 ነው ብቅ የሚሉት፡፡ ለመጥፋታቸው ዋነኛው ምክንያት አሁን ካለው የፓርቲያቸው የፓርላማ መቀመጫ ብዛት ጋር ስናስበው ግልፅ ይሆንልናል፡፡ በዛን ወቅት እርሳቸው በምርጫ ዝግጅት እና ወከባ ውስጥ ነበሩ ብለንም መደምደም ያስችለናል፡፡ ፍሬውም 99.6 በመቶ የፓርላማ ወንበር፡፡

የነTwtter ሚና ከፍተኛ እንደነበር የታየበት የአረቡ አለም ፀደይ (The Arab Spring) ፍሬ ካፈራና ሁሉም በየጓዳው መደንገጥ በያዘበት ሰሞን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ብቅ ብለው ጥቅም ላይ ስላልዋለው 3 ሚሊየን ሄክታር መሬታችን፣ ስለ ህዳሴው ግድብ ተስፋና መከራ፣ ስለ የተለያዩ እርዳታዎች፣ ስለውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ የግንቦት 20 እንኳን አደረሳችሁ መልእክት ወዘተ tweet ያደርጉና 'የሆሊውድ' መንፈሳቸው እንደገና ሲቆሰቆስ፡፡

"I wanted to upload photos of this moments but the twitter app on this iphone is not letting me do it, maybe its [it's] the network" እንዲሁም "here are some photos I promised…" ብለው ጥያቄ ያጭሩብናል፣ ይሄ ነገር እንዴት ነው? ያስብሉናል፡፡

- የApple ምርት የሆነውን iphone መጠቀማቸው ጠዋት ማታ ከሚከሱት ኒዮ ሊበራሊዝም አቀንቃኞች ጋር የጓዳ ግንኙነት አላቸው እንዴ? ሲያስብለን፣
- "…maybe its [It's] the network" ሲሉ ደግሞ *‹‹ለካ ቴሌ ቤተሰቦቹንም አሰመርሯል እያልን ብለው ብለው "Ethio Telecom SUCKS" እንዳይሉ እንፈራለን፡፡››*
- ለማንኛውም ግን ቆይተውም ቢሆን የለጠፉልንን ፎቶ ስናይ *‹‹ፎቶ አንሺነት ምንኛ መታደል ነው!››*ያስብለናል፡፡
- ወደኋላ እንመለስ እና በሜይ 30/ 2011 ፓርቲያቸው ስልጣን የያዘበትን ሀያኛ አመት ካከበረ ከሁለት ቀናት በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ "Welcome to twitter @HailemariamD" በማለት የምክትል

ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝን ወደ Twitter መምጣት ያበስሩናል እንደገናም በሌላ ትዊታቸው "Follow the deputy PM & FM of #Ethiopia" ይላሉ። ታዲያ ይሄስ ምን ሹክ ይለናል?

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ *‹‹ስልጣን ልለቅ ነው። ኦ ይቅርታ ፓርቲየ ያሳደገህን ድርጅት ጥለህ የት ልትሄድ አርፈህ ተቀመጥ አለኝ››* እያሉ ብዙ ዓመታትን ቆይተዋል። በቅርብ ደግሞ 'መተካካት' በተባለው የፓርቲያቸው ስትራቴጅ አማካኝነት የአሁኑ የምርጫ ወቅት (2002-2007) የመጨረሻቸው እንደሆነ እና ከ2007 ዓ.ም በኋላ በጠቅላይ ሚኒስትርነት እንደማይቀጥሉ እየገለፁ ይገኛሉ።

እና እርሳቸውን ማን ይተካቸዋል? ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ምላሾች እየተሰጡ ናቸው። ከቀዳሚዎቹ መልሶች አንዱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ሀይለማርያም ደሳለኝ ሊሆኑ ይችላሉ የሚለው ሲሆን ከላይ ከተጠቀሱት ትዊቶችም ወደዚህ ያዘነብላሉ።

"Welcome to twitter @HailemariamD" ሲሉ *‹‹ወደ መንበሩ እንኳን ደህና መጣህ››* እንደማለት ነው። "Follow the deputy PM & FM of #Ethiopia" ሲሉ ደግሞ *‹‹ህዝቤ ሆይ በስርዓት እንዳኖርኩህ አሁንም ይህን ስርዓት የሚያስቀጥልልህ የምወደው ልጅ ይህ ነው፣ ለእርሱም ተገዙ››* ማለታቸው ነው የሚሉ 'ተንታኞች' ተበራክተዋል።

በሌላ በኩል ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ ወደ Twitter አለም ከገቡ ከአንድ ዓመት በላይ የሆናቸው ቢሆንም እስከ አሁን ያደረጓት አንድ እራሷን የቻለች Tweet ብቻ ናት። እሷም "Happy Birthday @meleszenawi" የምትል ስትሆን ይሄ ምላሻቸውም፡፡

*‹‹መልካም ልደት፣ ተቀብያለሁ እርስዋን ያኑርልኝ፣ እናት ሸህ ልጅ ትውለድ ስሙንም መለስ ትበለው የሚል እጅ መንሻ ነው››* የሚል ትርጉም ተሰጥቶት የሽግግሩ ወሬ እየጦፈ ይገኛል። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስም በምላሻቸው "Thank You Hailemaram ! I appreciate all the best wishes" ይላሉ። ይህ የቤተዘመድ ወግ የማያስቀናው ከቶ ማን ነው?

እውን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ "Follow the deputy PM & FM of #Ethiopia" እንዳሉት በትረ ስልጣኑን ለተከታያቸው ያስረክቡ ይሆን? መልሳችን አዎ ከሆነ ያሰጀመሩትን ግድብ ሳያስጨርሱ ወዴት ነው? የሚለውም ከባድ ጥያቄ ነው።

# ጠቅላያችን የማን ናቸው?

ሰሞኑን የጠቅላያችን ጤና በጽኑዕ መቃወስ የሚያወሱ ጭምጭምታዎች ከተለያየ አቅጣጫ እየተናፈሱ ይገኛሉ፡፡አንዳንዶቹ እንደውም ስለ ድህረ መለስ ኢትዮጵያ እና ስለተተኪዎች የምር መነጋገር ይዘዋል፡፡እንደው አያድርገውና! ድንገት ጸጥ ቢሉ መቃብራቸው ላይ የሚነበብ አጭር የህይወት ታሪካቸውን የመጻፍ ሃላፊነት ቢሰጠን ምን እናደርግ ይሆን? አንድ የኔ ብጤ ተርታ ሰው ቢሆን ብዙም አያስቸግርም፡፡ የእርሳቸው ለመጻፍ ግን የህይወት ታሪክ እና ሌላውን መደበኛ ታሪክ (history and biography) ማጣቀስ ተገቢ ነው:: ለዚህ ደግሞ ሁነኛው የትምህርት ዘርፍ የስነ ማኅበረሰብ ጥናት (sociology ) ነው፡፡

እንደ የስነ ማኅበረሰብ ጥናት ባለሙያዎች ትንታኔ ሰው በዕለት ተዕለት ጉዳዮቹ ወስጥ የተለያዩ ማኅበራዊ ማነቆዎች ያጋጥሙታል፡፡አንድ ማእከላዊ ሰው (average person) እነዚህ ያገጠሙትን እክሎች(traps) አልፎ የግሉን ችግሮች ከትልቁ ስዕል (ከሚኖርበት ማኅበረሰብ ፣ ከዓለም ታሪክ) ጋር ለማያያዝ ይከብደዋል፡፡ ከዚህ ይልቅ ከራሱ ትንሽ ዓለም (መንደር ፣ ጎሳ ፣ ት/ቤት ፣ መ/ቤት) አንጻር መረዳት ይቀናዋል፡፡ ጥቂቶች ነገር ግን የመንፈስ ልዕልና (quality of mind) ያላቸው ግላዊ ጉዳዮችን ከማኅበረሰብ ጋር አጣምሮ ለማየት የሚያስችል ማኅበረሰባዊ ነጽሮት (Sociological imagination) አላቸው፡፡

ስነ ማኅበረሰባዊ ነጽሮት ብዙ ፍሬዎች አሉት፡፡ የራስን የህይወት ልምድ ከታሪክ አጋጣሚና ከማኅበረሰባዊ መዋቅሮች ጋር በማገናኘት እድል ፈንታ ጽዋ ተርታን ለመለካት ይጠቅማል፡፡ እንዲሁም በማኅበረሰብ ውስጥ የራስን ሚና መለየትና ራስን ለአንድ ስፍራ ለማጨት ያስችላል፡፡ በዚህ ዘርፈ ብዙ ማኅበረሰብ ውስጥ የኔ ስፍራ የት ነው? የሚለውንም ጥያቄ ለመመለስ የሚደረግም ሐሰሳ ነው፡፡ በዚህ ነጽሮት ተጠቅመው የራሳቸውን፣ የቤተሰባቸውን፣ የመንደራቸውን ችግር የፈቱ ሰዎች 'የራሳቸው ናቸው' ለማለት ይከብዳል፡፡ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ የፈጠሩት ደግሞ የሁሉ ሰው (global citizen or cosmopolitan person) ተብለው ይጠራሉ፡፡ በእኛም ማኅበረሰብ ውስጥ እንደዚህ ህዝበ አዳም የኔ የሚላቸው አልፎ አልፎ ይታያሉ፡፡ በየእደሩ፣ በዕቁብና በጽዋ ማኅበራት ከማዕከላዊነት አልፈው ከቤተሰባቸው በላይ ለአከባቢያቸው ማኅበረሰብ የሚተጉ ሰዎች አልጠፉም፡፡ እንደዛሬ የመቅለል ዘመን ሳይመጣ፣ የረባ ሚኒስቴር ሳይጠፋ በፊት በዓለም አቀፍ ተቋማት በማገልገልም የዓለምን ህዝብ የጠቀሙ ጠንካራ ዲፕሎማቶችም ነበሩን፡፡ እንግዲህ ይህን መሰረት አድርገን ነው የጠቅላያችንን አጭር የህይወት ታሪክ ለመጻፍ ጥረት የምናደርገው፡፡ በነጽሮታቸው መጠን ለማኅበረሰባቸው ባበረከቱት አስተዋጽኦና ይህን ተከትሎ ከማኅበረሰቡ የሚሰጥ "የኔ ነህ ፣ጀግናዬ ነህ፣" ከሚል ማዕረግ፡፡ በአንድ ቃለ መጠይቅ ወ/ሮ አዜብ መስፍን ስለጠቅላያችን ጭንቅላት ምጥቀት ሲናገሩ "ገንዘብ ለማግኘት ብፈልግ እርሱን ከዚህ አስወጥቼ ሌላ ስራ እንዲሰራ ነው የማደርገው" ማለታቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንዳይሆንብን እርሱን ትተን በርዕሰ መንግስትነት ለሁለት አሥርት ዓመታት ካስተዳደሯት ኢትዮጵያ ተነስተን 'የኢትዮጵያ ናቸው/ አይደሉም ?' ብለን እንጠይቃለን፡፡

## የኢትዮጵያ

ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን እርሳቸውን የኔ ብለው ለመቀበል ይቸገራሉ፡፡ በግድ አስገድደው ያንተ ነኝ ካላሉት በቀር ሁሉም እርሳቸውን መሪዬ ናቸው ብሎ ለመቀበል አይፈልግም፡፡ እርግጥ ነው ሙሉ ወጣትነታቸውን በጫካ ያሳለፉት አቶ መለስ የኢትዮጵያን የወደፊት እጣ የመወሰን "እምዬ መለስ" ተብሎ የመጠራት ብዙ እድል በእጃቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያን የሚያዩበት መነጽር በእጅጉ ስለተንሸዋረረ የኔ የሚያስብል ግብር ሳይኖራችው ሁለት አሥር ዓመታት አለፉ፡፡ ታሪኳን ወደ ሰማንያ አመት፣ ባንዲራዋን ወደጨርቅነት፣ ልጆቿን ለርሀብ እና ለስደት የዳረገ በመሆናቸው ከኢትዮጵያ ማህጸን የተፈጠሩ፣ አፈሯን ፈጭተው ያደጉ ስለመሆናቸው ብዙዎች እንዲጠራጠሩ አድርጓቸዋል፡፡ የሚጠበቅባቸውን አለመፈጸማቸው ሳያንስ የሀገሪቷን መጻዒ ተስፋ እንዳይፋፉ ምሁራንን የሌሉበት፣ ጋዜጠኞች የሚታሰሩበት ማድረጋቸው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ሆድና ጀርባ ያደርጋቸዋል፡፡ በአጠቃላይ በፓርቲያቸው ካድሬዎች አገላለጽ አቶ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ የማይሆኑበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

## የትግራይ

በወርሃ የካቲት በ1968 ዓ.ም. የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት(ት.ህ.ነ.ኣ.ድ) የትግሉን መግለጫ ባሰፈረበት የመጀመሪያ እትሙ የትግላቸው ዐብይ ምክንያት ከቀን ቀን እየተባባሰ የሚሄደው የኢኮኖሚ ብዝበዛ በሰፊው

የትግራይ ሕዝብ (ትግርኛ ተናጋሪዎች፣ አፋር (ጠልጠል)፣ አገው ፣ ሳሆ፣ ኩናማ ወ.ዘ.ተ.) ላይ ድሕነት ርሃብና ውርደት እየተደደጋገመ እንዲደርስ በማድረጉ የሥራ ማጣት ችግር ሽርሙጥናና ስደትን ማስከተሉ መሆኑን ያትታል፡፡ ይህ ያልጠራ ንደፈ ሐሳብ ብዙዎቹን በማጓጓቱ ብዙዎቹ የትግራይ እናቶች ልጆቻቸውን ገብረዋል፡፡ ይህ ግን እነአደይን በብዙ ከተሞች እጃቸውን ለምጽዋት ከመዘርጋት አላዳናቸውም፡፡ በስደትና በሴተኛ አዳሪነትም የራሳቸውን ድርሻ ያነሳሉ፡፡ አንዳንዶች ስርዓቱ ለትግራይ ተወላጆች የተለየ ጥቀማ ጥቅም እንደሰገኘ ሽንጣቸውን ገትረው ቢከራከሩም በእለት ተዕለት የሚያጋጥመን እውነታ ይህን አይነግረንም፡፡ በጭንጋፉ ስርዓተ ትምህርት ያለፉ፤ እጅግ ተስፋ አስቆራጭ በሆነው የኑሮ ውድነት የሚዳክሩ የትግራይ ተወላጅ ወዳጆቼ በዙሪዬ በከበቡኝ ጊዜ ደግሞ ይበልጥ ሰውየው የትግራይ ናቸው ለማለት ይከብደኛል፡፡ እርግጥ ነው እርሳቸውም ቢሆኑ ብሔራቸውን ሲጠየቁ ‹‹እኔ በእሳት ተፈትኖ ካለፈው የትግራይ ሕዝብ ነው የወጣሁት›› ቢሉም ትግራይ የኔ አትላቸውም፡፡

ባላባታዊ መደብ በመደብነት እንዳይኖር ቢዋደቁም አሁንም ኢትዮጵያ (ትግራይ) ጥቂቶች የሚምነሽነሹባት ሆናለች፡፡ ወሰን አልባ ርሃብ እና እርዛቱን ለመቋቋም የትግራይ ክልል እየተረዱ ዜጎች ዛሬም የሴፍቲ ኔት መርሐግብር ተጠቃሚ ናቸው፡፡ ይህ ያንገበገበው ትግራዋይ ዘለዓለማዊ ኢትዮጵያዊ እንዲህ እያለ ማንጎራጎር ከጀመረ ሰነባበተ፡፡ ለየካቲት 11 ብዙሓት አኖታት ኣብሻያት ወይድማ አዬታት ..ንዘላዓለም ዘይምሎሱ መንእሰያት ህባተን ይኹን ደኣምብር ንውሕዳት ህይወት ቁማርተኛታት ሸሻይ ኾይና አላ፡፡

## የቀዳማዊቷ

አቶ መለስ የልጆቻቸው ናቸው ለማለትም አያስደፍርም፡፡ እርግጥ ነው የፈለጉትን እንደሚበሉ፣ ያሻቸው ነገር እንደማይጎልባቸውም ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ይህን አንድ የመርካቶ ነጋዴም ያደርገዋል፡፡ ጋዜጠኛና የፖለቲካ ተንታኝ ዐብይ ተክለማሪያም የጠቅላያችን በአንድ ቃለ መጠይቅ ስለልጃቸው ሰመሃል መለስ ዜናዊ አስረስ “ልጆት በአደባባይ ፖለቲካ ህይወት እንድትሳተፍ ይመኛሉ?” ለሚል ጥያቄ የሰጡትን “እንደ ዕድል ሆኖ እኔ ስለእርሷ አልወስንም ነገር ግን መወሰን ብችል ከዚህ ዓይነት ህይወት (ከፖለቲካ) ራቂ ብዬ እመክራት ነበር፡፡” የሚል መልስ ተከትሎ ‘የአባት ውርስ’ በሚል ጽሑፉ ጠቅላያችን ልጃቸው ወደ ቦለቲካ እንዳትገባ አንደ ጥሩ አባት የከለከሉበትን ምክንያት ከተነተነ በኋላ አለመግባቷ ከዚህ እንደማያድናት አስረግጦ እንዲህ ይላል፡፡

“የኢትዮጵያ ፖለቲካ አደገኛ ቢሆን፣ ውስን ቢሆን፣ ክብረ ቢስነት ቢበዛበትም እንኳ በክፉልም ቢሆን አቶ መለስ ራሳቸው ተጠያቂ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ሰመሃል ፖለቲከኛም ሆናም ሆነ ሳትሆን የምታልፍበት ሁኔታ የአባት ውርስ እንጂ የተፈጥሮ እና የአምላክ እዳ አይደለም፡፡”

**አዲስ ነገር ጋዜጣ 2ኛ ዓመት ቁጥር 101 መስከረም 16/2000**

ይህ ከወዳጅ ከዘመድ ከሀገር ልጅ የማያኖር የአባት ውርስ ስንገነዘብ ጠቅላያችንን የልጆቻቸው እዳ እንጂ መኩሪያ እንዳልሆኑ እንረዳለን፡፡ከነርሱ ይልቅ ቀዳማይቷ እመቤት አዜብ መስፍን የኔ ቢሏቸው ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ስርዓት እንደርሳቸው የተመቸው የለም፡፡ ከጅማ እስከ መተማ እንደሚነግዱ፣ Boeing 777 ለመሸመት የሚያስችል አቅም እንዳላቸው፣ ለጌጣጌጥ መግዣ ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር በላይ እንደሚያወጡም ብዙዎቻችን ሰምተናል፡፡ እነዚህን እውነት አዘል ሀሜቶች ያደመጠ ሰው የሰውዬውን አጭር የህይወት ታሪክ ቢጽፍ እንዲህ የሚል ይመስለኛል፡፡

“ወዲ ዜናዊ ምንም ያልነበራትን የወልቃይት ጠገዴ ኮረዳ ከምንም አንስተው ለብዙ አመታት ተዋግተው ፣ ላይ ወጥተው ታች ወርደው፣ ቀን እረፍት ሌት እንቅልፍ አጥተው፣ ቢሊኒየር ለማድረግ ባደረጉት ግብግብ ለደም ካንሰር፣ ለጭንቅላት እጢና ለከፍተኛ ጭንቀት በመዳረጋቸው በተወለዱ...”

ይሄስ ማርያምን ደስ አይልም ፤ እባክዎ የመጨረሻውን ምዕራፍ ያሳምሩት፡፡ ህመም እስክንድር ነጋን በማሰር፣ ብራሰልስ በመመላለስ አይድንም፡፡ ንስሐ ይፈልጋል፤ መመለስ ይፈልጋል ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መታረቅ፣ ከትግራይ ህዝብ ጋር መታረቅ፣ ከአዲሱ ትውልድ ጋር መታረቅ ይፈልጋል፡፡ የሚያድግ ልጅ አይጥላኝ አይደል የሚል የኢትዮጵያ ሰው፡፡

# የመለስ ዜናዊ 'ሀሁ' በስልጣን ጎዳና

**መለስ ዜናዊ (የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር)**
**ልደት፦ ሚያዝያ 30፣ 1947**
**የኅወሓት ሊቀመንበርነት፦ ከ1981 ጀምሮ**
**የኢሕአዴግ ሊቀመንበርነት፦ ከ1981 ጀምሮ**
**የኢትዮጵያ ፕሬዚደንት፦ ከ1983 — 1987**
**የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር - ከ1987 - አሁን**

"ብልቡ ዝሸፈተ ምመልሲ ይብለን" ይባላል በትግርኛ፤ 'በልቡ የሸፈተን የሚመልሰው የለም' እንደማለት!

## የታሪኩ መጀመሪያ

የሕወኀት ወላጅ ከሆነው ማገብት (ማኅበር ገስገስቲ ብሔረ ትግራይ) መስራች አባላት አንዱ የሆኑት አረጋዊ በርኸ *(ከነፃ አውጪ ታጋይነት ወደምሁርነት የተሸጋገሩ ስደተኛ ምሁር ናቸው፤)* The Origin of The Trigray People's Liberation Front በሚለው ጥናታቸው ላይ እንዳሰፈሩት መጀመሪያ ትግራዋይ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ሕብረት ተፈጠረ፡፡ የኅብረቱ አባላት ከሆኑት ውስጥ መለስ ተክሌ እና አባይ ፀሃዬ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ማሕበሩ አርታኢ ቡድንን ይመሩ ነበር፡፡ የኅብረቱ ዋነኛ ዓላማ ለትግራይ ሕዝቦች ፖለቲካዊ ንቃት ማጎናፀፍ ብቻ ስለነበር፣ ከዚያ የተሻለ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ እንዲችል በሚል ማገብት ተወለደ፡፡ ማገብት የኅወሓት ወላጅ እናት ነው፡፡

ማገብት ሕወሓትን ከመመስረቱ በፊት ከኅግሓኤ (ሕዝባዊ ግምባር ሓርነት ኤርትራ) ጋር የሥራ ግንኙነት መስርቶ ነበር፤ *(ስሙም ከዚያው የተገኘ ይመስላል፡፡)* መለስ ከኅወሓት፣ ጥቂት ቀደምት አባላት አንዱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ መጽሐፍት እንደሚተርኩት መለስ ዜናዊ እና አቦይ ስብሓት የኅወሓት መስራች ሳይሆኑ፣ ከተመሰረተ ጥቂት ወራት በኋላ ትግሉን የተቀላቀሉ መሆናቸውን A Political History of the Tigray People's Liberation Front (1975-1991): Revolt, Ideology and Mobilisation in Ethiopia በተሰኘው የዶክትሬት ድግሪ ማሟያ ጽሑፋቸው ላይ አረጋዊ በርኸ ጽፈዋል፡፡

መለስ ዜናዊ (የያኔው ለገሠ ዜናዊ) የሕክምና ሳይንስ ትምህርታቸውን አቋርጠው ሽምቅ ተዋጊነትን የመረጡት በተለይ የትግራይን፣ ብሎም የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን ነፃነት በመናፈቅ እንደሆነ ድርሳናት ይተርካሉ፡፡ ይሁን እንጂ ገና ትግሉ ከመጀመሩ በፊት መስራቾቹ የተመቻቸ ጊዜ ሲጠብቁ መለስ የደረሱበት ጠፍቶ ነበር፡፡ ከአንድ ወር በኋላ ግን በኤርትራ፣ የእናታቸው መንደር ከሆነችው አዲ ቋላ ተገኝተዋል፡፡ እንዲህ እያለ፣ እያለ ከዓመታት በኋላ ማርክሲስት-ሌኒኒስት ሊግ ኦቭ ትግራይ (ማሌሊት) ከኅውሓት ጎን ለጎን ተፈጠረ፤ ይህ ሊግ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊውን ርዕዮተ ዓለም እና የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል የምትለዋ ሐረግን በማኒፌስቶው የያዘ ሲሆን በዚህ ግራ ዘመም እና እስካሁንም ድረስ ተፅዕኖው እንዳለ በሚነገርለት የማሌሊት ፖለቲካ ውስጥ የመለስ ዜናዊ ሚና በእጅጉ የጎላ እንደነበር ይነገራል፡፡

የመለስ ዜናዊ ስልጣን የጀመረው እ.ኤ.አ. በ1979 ኅወሓት የመጀመሪያውን የድርጅት ቻርት ሲያወጣ ነው - የፕሮፓጋንዳ ክፍሉ *(ክፍሊ ፖለቲካ)*፣ የአባይ ፀሃዬ ምክትል በመሆን፡፡ ይህ ማዕረግ ምናልባትም ብዙ የሚነገርለትን የመለስን አንደበተ ርዕቱነትን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ሹመት ነበር፡፡

### የአቢዮታዊ ዲሞክራሲ አመጣጥ

መለስ እስካሁን ድረስ በቅጡ "መፍታት ወይም መበየን" የሚችል ሰው አልተገኘም የሚባልለትን አብዮታዊ ዲሞክራሲን ለኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ብቸኛው ዲሞክራሲያዊ ርዕዮተ ዓለም ነው ሲሉ የሚከራከሩት ‹የአብዮታዊ ዲሞክራሲ› ሰያሚም ሆነ ፈጣሪ ራሳቸው መለስ ስለሆኑ ነው በሚል በተደጋጋሚ ያሳማቸዋል፡፡ አረጋዊ በርኸ እንደሚተርኩት ‹ሕዳር 1978 መለስ ዜናዊ "አፈላላይጥና ኣብ ግልፂ መድረክ ንክሪብ" ('ልዩነታችንን በግልፅ መድረክ እንነጋገር') የሚል ርዕስ ያለው ጽሑፍ ጻፉ፡፡ ይህንን ሌሎችን በግልጽነት መተቸት ነው የተባለለትን ጽሑፍ ተከትሎ እና የሌኒንን 'Bourgeois Democracy and the Proletarian Dictatorship' የተሰኘ ጥናት መሠረት አድርገው አቢዮታዊ ዴሞክራሲ በራሳቸው በመለስ ዜናዊ ተፈጥሯል፡፡

መለስ ዜናዊ የኅወሓት አመራሮች ኮሚቴ ውስጥ በ1971፣ የሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ውስጥ ደግሞ በ1975 ለመግባት ችለዋል። ትልቁን ስልጣን ማለትም የኅወሓትን ሊቀመንበርነት ማግኘት የቻሉት የዛሬ 23 ዓመት (በ1981) ከስብሓት ነጋ መሆኑ ይታወሳል። ቀድሞም ቢሆን የአመራሮችን የስልጣን ዕድሜ ገደብ የሚገድብ መመሪያ የሌለው ኅወሓት በመለስ ዜናዊ የ21 ዓመታት አመራርም ተተኪ መሪ ሊያገኝ አልቻለም። ይልቁንም መለስ ዜናዊ ከ10 ዓመት አመራር በኋላ በመልካም ፈቃድ ስልጣናቸውን ካስረከቧቸው አቦይ ስብሓት የተማሩት ነገር እንዳለ በተግባር አላሳዩም። እንዲያውም በፓርቲው መካከል የተፈጠረው ልዩነት የፈጠረላቸውን ዕድል ተጠቅመው አሁን ፓርቲው ውስጥ ያላቸውን የሁሉ ባለቤትነት መብት እና ስልጣን ስብሓት ነጋ ያኔ ከነበራቸው ስልጣን በእጅጉ የበለጠ እንደሆነ ብዙዎች ይናገራሉ።

የሦስት ልጆች አባት ለመሆን የበቁት አቶ መለስ ዜናዊ፣ የኅወሓትም የኢሕአዲግም ሊቀመንበር ሆነው ከ23 ዓመታት በላይ አሳልፈዋል። እስከዛሬ በ21 ዓመት የኢሕአዴግ ኢትዮጵያን የማስተዳደር ሥራ ውስጥም ትልቁን ስልጣን የያዙት እርሳቸው ብቻ ናቸው። *(4 ዓመታት በሽግግር መንግስቱ ፕሬዚደንትነት እና 17 ዓመታት በጠቅላይ ሚኒስቴርነት።)*

## የመለስ ፈተና እና አስተላለፍ

መለስ ዜናዊ የስልጣን ዘመናቸው አልጋ ባልጋ ነበር ማለት አይቻልም። ከሁሉም የበለጠ ፈተና ገጥሟቸው የነበረው ግን መለስ እነስዬ የገቡበትን አዘቅት ለማጣጣል *ቦናፓርቲዝም* ሲሉ የጠሩት የኅወሓት መከፋፈል *(ሕንፍሽፍሽ)* እና ምርጫ 1997 ሳይጠቀሱ የማይታለፉት ናቸው። *ቦናፓርቲዝም* ለኅወሓት የመጀመሪያው የመከፋፈል አደጋ አልነበረም፣ የመጀመሪያው *ሕንፍሽፍሽ* በሚል የሚታወሰውና በትግሉ ወቅት ተከስቶ የነበረው ገበሬ ታጋዮች፣ ተማሪ መሪዎቻቸውን ለማስወገድ የሞከሩበት መከፋፈል ይቀድመዋል። ሆኖም በመለስ የስልጣን ሕልውና ላይ በዋናነት ጥላውን ያጠላው *የ1993ቱ ሕንፍሽፍሽ* ነበር።

በተለይም በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት *(ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር የሩቅ ዝምድና አላቸው የሚባሉት)* ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ በኤርትራ ላይ ቆራጥ እርምጃ ለመውሰድ ባለመፈለጋቸው ተከስቶ የነበረው ግጭት ተጋግሎ፣ የኅወሓትን ሕልውና እና የመለስ ዜናዊን ስልጣን አደጋ ላይ ከጣለ በኋላ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተቃራኒያቸውን የእነአቶ ተወልደ ቡድን አጀንዳ ተነጥለው የወጡት እንደሚሉት *"በመስረቅና የራሳቸው በማስመሰል"* ድሉ በእጃቸው እንዲገባ ለማድረግ ችለዋል። ምንም እንኳን የዚህ ታሪክ አተናተን እስካሁንም ድረስ ሁለቱንም ቡድኖች የሚያግባባ ደረጃ ላይ ባይደርስም እርሱን ተከትሎ በሙስና አቶ ስዬን ማሳሰሩ፣ የአቶ ተወልደ ድምጽ መጥፋቱ መለስ ዜናዊ ለስልጣን ያላቸውን ቀናኢነት ትዝብት ውስጥ የጣለ ነበር።

ከዚህ የኅወሓት መከፋፈል በኋላ፣ መለስን ይፎካከሩ የነበሩት የሕወሓት አባላት እነስዬ፣ ገብሩ አስራት እና አስገደ በመወገዳቸው ያለአንድም ተቀናቃኝ በብቸኝነት የስልጣን መንበሩ ላይ ተደላደሉበት። ቀድሞውንም ቢሆን የሌሎቹ የኢሕአዲግ አባል ፓርቲዎች የኅወሓት ተገዢነት የሚታሙ በመሆኑ ከዚያ ውስጥ እርሳቸውን የሚፎካከር ግለሰብ አልነበረም ማለት ይቻላል።

ከዚያ በኋላ፣ በራሳቸው በጠቅላይ ሚኒስትሩ "እንከን አልባ" እንደሚሆን የተነገረለት ምርጫ 97ትን ተከትሎ የተነሳው አለመግባባት እና ሕዝባዊ ተቃውሞ፣ ሌላው የመለስን መንበር የነቀነቀ አጋጣሚ ነበር። ይሁንና መንግስታቸው ባመነው ብቻ በ200 ወጣቶች ሞትና፣ በተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች (ጋዜጠኞችን ጨምሮ) እስር ተቋጭቷል። ከዚህ አጋጣሚ በኋላ መለስ እንደግለሰብም ሆነ የሚመሩት ኢሕአዲግ እንደፓርቲ ስልጣን በምርጫ የማስረከባቸውን ነገር በጥያቄ የሚያዩት አልጠፉም።እነዚህ አካላትየአውራ ፓርቲ ኀልዮት እና የ40 ዓመት ዕቅዶቹን የመሳሰሉ የፓርቲ ሰነዶችን በዐብይ ምሳሌነት ያነሳሉ።

መለስ ከኅወሓት መከፋፈል በኋላ ተቀናቃኞቻቸውን በሙሉ በመኮርኮም ላይ ተሰማርተው ቆይተዋል በሚል የሰብአዊ መብት ተሚጋቶች እና ተቃዋሚዎች ሲወቅሱዋቸው ይደመጣል። ከዚህም በተጨማሪ በውስጠ ፓርቲ የመቀናቀን አቅም ያላቸውን አባላትንም ቢሆን ዕድል በመንፈግ ይታማሉ። ለአብነትም የአዲስ አበባ ከንቲባ ሆነው ባገለገሉበት ወቅት ከማንኛውም የኢሕአዲግ/ኅውሓት ባለስልጣን በላይ ተቀባይነት አግኝተው የነበሩትን እና አሁን ፓርቲው የሚኩራራባቸውን ኮንዲሚኒዬም ቤቶችና ጥቃቅንና አነስተኛ ፕሮጀክቶች ያስጀመሩትን አርከበ ዕቁባይን

መጥቀስ ይቻላል፡፡ መለስ የአርከበ ዕቁባይን ሥራ “ቀለም የመቀባት ሥራ” ሲሉ አጣጥለውት ነበር የሚሉ የውስጥ አዋቂ ወጎችም አልጠፉም፡፡

ዊኪሊክስ በቅርቡ ይፋ ባደረገው መረጃ ደግሞ፣ የዛሬ ሦስት ዓመት በተካሄደ የኅወሓት የሊቀመንበር ምርጫ**መለስ ሳይሆኑ አርከበ ዕቁባይ** ተመርጠው እንደነበር ያትታል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ መሰሉ ጫና ብዙ ፈተና ያለፉት አርከበ የምርጫውን ውጤት እና የተመረጡበትን ስልጣን አለመቀበላቸውን ጠቅሰው የአሜሪካ አምባሳደር ጽፈዋል፡፡ ‹መለስ ከኃላፊነታቸው ይልቅ ስልጣናቸውን ይወዱ ነበር ወይ?› የሚለው ክርክር ከላይ የተጠቀሱትን ጨምሮ በተለያየ ወቅቶች በታዩ እርምጃዎቻቸው ለመደምደም ከባድ አይሆንም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ብዙ ካልተጠቀሱትም ሆነ ጭራሹኑ ካልተነኩት ብዙ ታሪኩች ትዝታ በመነሳት ሊቀናቀኗቸው የሚችሉትን ሁሉ ገለል በማድረግ የፓርቲያቸውን ፖለቲካዊ መሪ የመፍጠር ኃላፊነት ሳይቀር ከንቱ በማስቀረት ‹የማን ይተካቸው እና የአትሄድብን› አጀንዳ የፓርቲው ታላቅ ጉዳይ እንዲሆን ማድረጋቸው ለትዝብት ዳርጓቸዋል፡፡

በዚህ ስልጣንን ለብቻ የመቆጣጠር ታሪክ ኪሳራ አለ ከተባለ የከሰረው ፓርቲው እና አገሪቱ ብቻ ሳይሆኑ፣ ራሳቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩም ጭምር ይሆናሉ፡፡ ጠ/ሚ መለስ ወጣትነታቸውን የሰዉለት የ17 ዓመት ትግል ሕዝብን የስልጣን ባለቤት የማድረግ ሕልም ነው ቢባልም፣ ከታገሉበት ዓመታት በላይ ስልጣን ላይ በመቆየት እና ለቦታው የሚመጥን ተተኪ ባለማፍራት የታገሉትን አምባገነናዊ ስርዓት በእጅ አዙር አምጥተውታል ብለው የሚሟገቱ ጥቂቶች አይደሉም፡፡፡

አረጋዊ በርኸ በጦርነት እና በትግል ወቅት ጥሩ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ የሚያደርግ ሰው (activist) በቀላሉ የእንቅስቃሴው መሪ ተደርጎ የመመረጥ እድል እንደሚኖረው ጠቅሰው፣ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የተመረጡ መሪዎችን ለማስወገድ ግን ራሱን የቻለ፣ ሌላ ከፍተኛ ትግል እንደሚጠይቅ ከላይ በተጠቀስው የዶክትሬት ማሟያ ጽሑፋቸው ተናግረዋል፡፡ መለስ ዜናዊ፣ ኢሳያስ አፈወርቂን እና ዮዎሪ ሙሴቪኒን የዚህ ሁነኛ ምሳሌ ሲሉም ጠቅሰዋቸዋል፡፡

እንግዲህ አሁን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በጠና እንደታመሙ ከበቂ በላይ ዜናዎች አረጋግጠዋል፡፡ በጽሁፌ መግቢያ ላይ የተዋስኩትን አባባል፣ አረጋዊ በርኸ የተጠቀሙበት የኅወሓትን ከዜሮ ተነስቶ ለድል መብቃትን ለመዘከር ቢሆንም፣ እኔ ግን በተቃራኒው ልዋሳቸው እወደድኩ፡፡ እንደቡድኖች ሁሉ ግለሰቦችም በልባቸው የሚወስኑት ነገር ይኖራቸዋልና መለስም ለዚህ ሁሉ ጠቅላይ ገዢነት ያበቃቸው በልባቸው የነበረው የመምራት ፍላጎት ነው - እውነትም ‹በልቡ የሸፈተን የሚመልሰው የለም!› እንዲሉ - ለስልጣንም ቢሆን!!!

# መለስ ወደ ውጭ - መለስ ከውጭ

መጋቢት 25/1982 ዓ.ም ዋሽንግተን ዲሲ 14ኛው መንገድ ቦታውም የህወሀት ፅ/ቤት፡፡ አንድ ያለማቋም ሲጋራ የሚያጨሱ፣ በፅ/ቤቱ በባዶ እግራቸው ዘና ብለው ቁጭ ያሉ፣ እንግሊዘኛቸው የሚያምር በኢትዮጵያዊ የንግግር ዘይቤ የተካኑ ወጣት ከቀድሞው የCIA ኤጀንት እንዲሁም አፋቃሬ ኢትዮጵያዊው (Ethiopianist) ፖል ሄንዝ ጋር ለውይይት ቁጭ ብለዋል፡፡ በንግግራቸው መጀመሪያም ወጣ ቱ ፖል ሄንዝን እንዲህ ሲሉ ጠየቁት፡

‹‹አንተ የፃፍካቸውን ብዙ ነገሮች አንብቢያለሁ በሁሉም ነገሮችህ እስማማለሁ ነገር ግን ለምን ማራክሲስቶች እያልክ ትጠራናለህ?››

## ፖል ሄንዝም

‹‹ምክንያቱም እናንተ እራሳችሁን ማርክሲስቶች ነን እያላችሁ ስለምትጠሩ ነው፡፡ አልባኒያን እንደ ሞዴል አድርገን የተቀበልን ነን ትላላችሁ፡፡ ለስታሊንም የተለየ ፍቅር እንዳላችሁ ሪፖርቶች ያሳያሉ‹‹ ይሏቸዋል፡፡

ወጣቱ ቀበል አድርገው: ‹‹እኛ ማርክሲስት-ሌኒኒስት እንቅስቃሴዎች አይደለንም፣ በትግራይም ማርክሲዝም እና ሌኒኒዝምን ተግባራዊ አናደርግም፡፡ አዎ አንዳንድ አባላት ማርክሲስት ሌኒኒስት ሊሆኑ ይችላሉ እኔም በተማሪነት ዘመኔ ነበርኩ፣ አሁን ግን አለም ላይ ምን እየተካሄደ እንዳለ እናውቃለን፣ የውጭ ርዕዮተ አለምም ለኛ መፍትሄ ይሆናል ብለን አናምንም፣ የራሳችን ባህል እና ወግ የጠበቀ ስርዓት መፍትሄ ነው ብለን እናምናለን›› በማለት ተኮት ኩተው ያደጉበትን ማርክሲዝም በካፒታሊዝሙ አለም መሪ ዋና ከተማ ቀበሩት::

የያኔው ወጣት የዛሬው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ናቸው::

## ታዳጊው መለስ

ካርል ማርክስ 'የግል ሀብት የህብረተሰብ ችግር ነው፣ ሀብታም ደግሞ የህብረተሰቡ ሳንካ ነው' ማለቱን እጅግ በጣም ትክክለኛ ሀሳብ ነው ብሏል ያ ትውልድ ፡፡ የዊንጌቱ መለስም ዩንቨርስቲ ሲገቡ ይሄን ሀሳብ በልቦናቸው አዋሉት፡፡ የሀብታሞች መንግስት ነው ያሉትን ንጉሳዊ ስርዓትም ከጓደቻቸው ጋር በጩኸት አፈረሱት፡፡ የንጉሱ ስርዓት መገርሰስ ግን ለመለስ በቂ አልነበረም ይልቅስ ወደ ስልጣን የቀረበው ወታደራዊ መንግስት የትግራይን ህዝብ ጥያቄ አልመለሰም እንዲያውም የትግራይ ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ተገንጥሎ የራሱን ሀገር መመስረት አለበት፣ ሌኒን እና ስታሊም የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ለጭቁኑ ህዝብ ዋነኛ የነፃነት መሳሪያ ነው ይላሉ ብለው በማመን ተኻህትን ተቀላቀሉ በተኻህት የመጀመሪያ ማንፌስቶም 'ነጻ ትግራይን' ለመመስረት ከጓደቻቸው ጋር ተስማሙ የማንፌስቶውንም መዝጊያ ‹‹ኢም ፔሪያሊዝም ይንኮታኮታል›› በማለት የምዕራቡን ካፒታሊስት ስርዓት አጣጣሉ፡፡ የቀድሞው ተጋድሎ ሓርነት ሕዝቢ ትግራይ (ተሓህት) የበኋላው ህወሀት በትግል አስር አመታትን ካሳለፈ በኋላ አቶ መለስ ወደ ስልጣን ማማ የሚያወጣቸውን አንድ መንገድ ቀየሱ በህወሀት ውስጥ አንድ ተጨማሪ ሊግን ማቋቋም ሊጉንም ማርክሲስት ሌኒኒስት ሊግ ኦፍ ትግራይ (ማሌሊት) አሉት ሊቀመንበርነቱንም ተቆናጠጡ፡፡

## መለስ በትግል ወቅት

እንግዲህ አቶ መለስ ከተማሪነት ጊዜያቸው ጀምሮ ደርግ እስከ ወደቀበት ጊዜ ድረስ ለአለማቀፉ ህብረተሰብ የነበራቸው አስተሳሰብ በካቲታሊስት-ሶሻሊስት ንጽርኦተ አለም (World Outlook) አስተሳሰብ የተቃኘ ነበር፡፡

የአለም ጭቁን ህዝቦች ነፃ የሚወጡት የግል ሀብት ሲጠፋ (On the abolishing of Private property) ነው የብሄሮችን ነፃነት በቡድን መብት አስተሳሰብ አማካይነት መመለስ አለበት፣ ይሄም በሩሲያ መሪነት የምስራቁ አለም ርዕዮት ስለሆነ ለምስራቁ ጎራ መልካም አመለካከት ነበራቸው:: በመጨረሻም የአልባንያን ሶሻሊዝምም እንደ ትክክለኛ ሞዴል በመውሰድ የሀገሪቱ አዳኝ አድርገው ተቀበሉ የያኔው መለስ፡፡

## ከቀብር መለስ

ከላይ በመግቢያችን እንደጠቀስነው አቶ መለስ በዋሽንግተን ቆይታቸው ማርክሲስትነታቸውን ቀብረዋል፡፡መለስ ማርክሲስትነታቸውን ከቀበሩ በኋላ ደርግ ወደቀ፣ የሀገሪቱን አመራርነትም ተረከቡ፣ ፍቅራቸውንም ከምእራቡ አለም ጋር አደረጉ፡፡ ምእራቡ አለም ሀገሪቱን ከህዝብ ብዛቷ አንፃር እንዲሁም የአፍሪካ ቀንድ ማዕከል መሆኗን ከአካባቢው መረጋጋት ጋር ብሎም ለመካከለኛው ምስራቅ የወደብ መቆጣጠሪያ (Light House) አድርጎ ማሰቡ ግንኙነቱን ከኢትዮጵያ ጋር ለማጠናከሩ ጠቃሚ ሆኖ ሊያገኘው ችሏል፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ የፀረ-ሽብር ትግሉ (War on Terror) እና የኢትዮጵያ የሱማሊያ ጎረቤት መሆን ኢትዮጵያን እንደ ጠቃሚ አጋር ለማየት አስቻለው አለማቀፉን ህብረተሰብ፡፡

አቶ መለስም ይሄን የአለም አቀፉ ህብረተሰብ በተለይም የምዕራቡን ፍላጎት የተረዱ ይመስላሉ፡፡ ለዛም ነው ‹‹ሁሌም ከእናንተ ጋር ነን›› ብለው ምዕራቡን በፍቅር የከተቡት፡፡ በዛ ላይ የንግግር ተሰጥኦአቸው (Oratory) ታክሎበት የምእራቡን አይን እንዲያማልሉ አስችሏቸዋል፡፡

## የG-20 ስብሰባ ሶል ፣ ደቡብ ኮሪያ

የቀድሞው የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ቶኒ ብሌር በአንድ ወቅት የአፍሪካ ተራማጅ መሪዎች (The New Progressive Leaders of Africa) ዝርዝራቸው ውስጥ መለስን ከቀዳሚዎቹ ስፍራ አሰልፈዋቸዋል፡፡

በዚህ የጫጉላ ወቅት መለስ ሁሌ ከምእራቡ አለም ጋር የሚነ ያታርካቸው ጉዳይ የሰብዓዊ መብት አያያዝ እና ከአለማቀፍ የገንዘብ ተቋማት (Bretton Woods Institution) የሚቀርብላቸው ጥያቄ ነው፡፡ ሰዎች ያለአግባብ ይታሰራሉ፣ ዲሞክራሲንም አስረዋል፣ ህግና ስርዓት ፈረሰ ወ.ዘ.ተ ይሏቸዋል የሰብዓዊ ተቋማቱ በሌላ በኩል ደግሞ አለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማቱ የፋይናንስ ተቋማትን ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት አድርጉ፣ ሞኖፖሊዮችን ለቀቅ አድርጉ፣ የኢኮኖሚውን አወቃቀር አስተካክሉ (Structural Adjustment) ወ.ዘ.ተ ይሏቸዋል፡፡ በዚህ ሁሉ ጊዜ የመለስ መልስ ለዘብተኛ ነበር፡፡ ዲሞክራሲን በቻልነው መጠን እያሳደግነው ነው፣ ህገመንግስቱን እያስፈፀምነው ነው በርግጥ በአፈፃፀም ደረጃ አንዳንድ ጥቃቅን ችግሮች ይከሰታሉ እነሱም በቀጣይ የማስፈፀም አቅማችን ስናዳብር የሚስተካከሉ ናቸው እያሉ የሰብአዊ ተቋማቱን ቁጣ ለማብረድ ይጥሩ ነበር እንዲሁም ጊዜው ገና ነው፣ ልማታችንን ተደራሽ ካደረግን በኋላ ለግል ባለሀብቶች ኢኮኖሚው ሙሉ ለሙሉ ክፍት ይሆናል እያሉ የምዕራቡን አለም በተስፋ ፈገግ ያስብሉት ነበር መለስ በዚህ 14 ዓመት በዘለቀ የምዕራቡ አለም ፍቅራቸው ዘመን፡፡

## መለስ እንደገና፣ ከቀለም አብዮት እሰከ ኒዮ ሊብራሊዝም

ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም አዲስ አበባ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ወንበሮች በሙሉ ጭንቀት በወረራቸው የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሀላፊዎች እና ሰራተኞች ተሞልቷል፡፡ ሁሉም በያለበት አዲስ ስለተረቀቀው የማህበራት እና ሲቪል ሶሳይቲ አዋጅ መንፈስ ላይ ይወያያል፡፡ የውይይቱ ዋነኛ ማጠንጠኛዎችም ሁለት አንቀፆች ናቸው፡፡ ‹‹ከ10 በመቶ በላይ አመታዊ ባጀቱን ከውጭ ለጋሽ የሚቀበል ማንኛውም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በፓለቲካዊ አድቮኬሲ ስራ እንዲሁም ትኩስ (Sensitive) የሆኑ የማህበረሰቡ አካላት ጋር የተያያዘ ስራ መስራት አይችልም›› የሚለው እና ‹ሁሉም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከበጀታቸው ከ30 በመቶ ያልበለጠውን ገንዘብ ብቻ ነው ለስራ ማስኬጃ ማዋል የሚችሉት›› የሚሉት አንቀፆች የታዳሚውን ቀልብ ስበዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስም የእነዚህን ሁለት ጉዳዮች ምንነት ለማስረዳት ነው በቦታው የተገኙት፡፡ ንግግራቸውንም እንዲህ ሲሉ በጠንከሩ ቃላት ጀመሩ፡

‹‹ገንዘብ ከውጭ፣ ሰው ከሀገር ውስጥ በመደባለቅ ኢትዮጵያዊ ሲቪል ሶሳይቲ መፍጠር አይቻልም፡፡ከጡጦ በሚንቆረቆር ገንዘብ ዲሞክራሲ ይኖራል ለማለት የማይቻል ነው፡፡ በዲሞክራሲ ተዋናይ ለመሆን የውጭ ገንዘብ ያስፈልጋል የሚለው አባባል አደገኛ ድንቁርና ወይም ስድብ ነው፡፡ በውጭ ገንዘብ የሚደረግ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ተንጦ ቅቤ አይወጣውም፡፡›› በማስከተልም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተደናግጦ የሚመለከታቸውን ታዳሚ እያማተሩ ‹‹በሞግዚት ዲሞክራቲክ መሆን አይቻልም፡፡በኢትዮጵያም ሆነ በሌላ ሀገር ዲሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደር እና ሰብዓዊ መብት በጡጦ ሊጠባ አይቻልም፡፡ ጡጦ ካላስፈለገው ባለጡጦ አያስፈልገውም፡፡በውጭ ገንዘብ እና አይዲያ

ላይ የተመሰረተ የዲሞክራሲ እድገት በእባብ አንቁላል ላይ የተመሰረተ ርቢ ማለት ነው፡፡የማይመለከታችሁ ቢላዋ ይዛችሁ እሰው አንገት አካባቢ እስካላሽከረከራችሁ ድረስ መስራት ትችላላችሁ፡፡ ቀይ መስመሯን ስትሻገሩ የጨዋታው ህግ ይቀየራል፡፡ በቢላዋ ጉዳይ ጥያቄ ወይም ኮምፕሮማይዝ የለም፡፡››

ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለዚህ ዛቻ መሰል ንግግር ያበቃቸው ምንድን ነው? ብለን ስንጠይቅ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አለማቀፋዊ ፍቅር እንደገና ምዕራቡን አለም እንደተፋታ ለማየት እንችላለን፡፡ ኢህአዴግ እንደ ፓርቲ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ እንደ አንድ የፓርቲ መሪ ግለሰብ ምርጫ 97ን ተምረንበታል ይላሉ፡፡ ከቀዳሚዎቹ የምርጫ 97 ትምህርቶች መካከል የሲቪል ሶሳይቲው ሚና መሆኑ ምርጫውን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የተከታተለ ሁሉ የሚስተው ጉዳይ አይደለም፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትሩ እና በፓርቲቸው እምነትም ሲቪል ሶሳይቲው ውጭ ሁነው በሚዘውሩት እና የራሳቸው የተለየ አጀንዳ ባላቸው ሀይሎች እየተደገፈ ተቃዋሚዎቹን በጭፍን ረድቷል ይሄ እርዳታም መንግስትን በምርጫ ከማስወገድ ባለፈም በህዝባዊ አመጽ ወይም በተለምዶ ቀለም አብዮት ተብሎ በሚጠራው እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባንድ ወቅት 'የቅጠላ ቅጠል' አብዮት ብለው ያሾፉበት እና በምስራቅ አውሮፓ ተሞክሮ የታየውን አይነት ለውጥ እስከማካሄድ ድረስ ይዘልቃል ባይ ናቸው፡፡ ለዚህም ዋነኞቹ አንቀሳቃሾች አንዳንድ የምዕራብ ሀይላት ናቸው በማለት መለስ ስልጣን በመያዛቸው ዋዜማ የተጋቡትን የምዕራብ ፍቅር ተጣሉት፣ አኮረፉት፡፡

ይባስ ብሎ በዛው በመጋቢት 2000 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ፅሁፋቸውን የመጀመሪያ ድራፍት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስብሰባ አዳራሽ ለውይይት አቀረቡ፡፡ የፅሁፋቸው ዋነኛ ማጠንጠኛም የምዕራቡን አለም ፖለቲካል-ኢኮኖሚ በማጣጣል ለአፍሪካ የሚበጃት ከምስራቁ ተሞክሮ መውሰድ ነው በማለት እነ ደቡብ ኮሪያን፣ ቻይናን እና ሲንጋፖርን እየጠቀሱ አዲስ ወዳጅ ፍለጋ ፊታቸውን ከምዕራቡ አለም መለስ አድርገው ወደ ምስራቁ ማማተር ያዙ፡፡ ማርክሲስቶች ኢምቴሪያሊዝም ይውደም ባሉበት ድምፀት መለስም ኒዮ ሊብራሊዝም ይውደም ማለትን አዘወተሩ፡፡

## ግለሰቡ መለስ

መለስ አቋማቸውን ሕዝቡ ላይ ካሰረፁ በኋላ በግላቸው ስብእናቸውን ለመገንባት መሯሯጣቸው አልቀረም፡፡ ለዚህም ዋነኛ ተጠቃሽ የሚሆነው የጠቅላይ ሚኒስትሩ አፍሪካን ይወክላሉ፣ ልዕለ-ሰብነት አላቸው የሚለውን አመለካከት በአለማቀፉ ህብረተሰብ ውስጥ ሊተክሉ መቻላቸው ነው፡፡

ወደስልጣን እንደገቡ በርቀት ትምህርት ከእንግሊዙ ኦፕን ዩንቨርስቲ በቢዝነስ አዲሚንስትሬሽን የማስተርስ ዲግሪ ሲይዙ ዩንቨርስቲው የመለስን ውጤት ‹‹One of the best result in Open University's History›› ሲል ነበር የገለፀው፡፡ በማስከተልም ከሮተርዳሙ ኢራስመስ ዩንቨርስቲ ሌላ ማስተርስ በኢኮኖሚክስ በመያዝ ስብዕናቸውን ያዳበሩ ሲሆን እንደ ጆሴፍ ስቲግሊትዝ እና ጀፍሪ ሳክስ ከመሳሰሉ ትልልቅ ስብእናዎች ጋር በመሻረክ እንዲሁም ፈጣን እና ቀልጣፍነታቸውን በመጠቀም ለአለማቀፉ ህብረተሰብ መለስ እንደ ታላቅ ምሁር ሁነው ቀርበዋል:: ለዚህም ትክክለኛ አመላካች የሚሆንልን የእንግሊዝ የአለምአቀፍ ልማት ሀላፊ የነበሩት ክሌር ሾርት በአንድ ወቅት ስለ መለስ ሲናገሩ፡ 'the most intelligent politician I've met anywhere in the world'. በማለት ነበር፡፡ ይህ የመለስ ስብእና በተለይም በአፍሪካ መሪዎች ዘንድ ጎልቶ የሚንፀባረቅ ምስል ነው፡፡ ለዛም ይመስላል አፍሪካን በመወከል መለስ ቅድሚውያን የሚይዙት፡፡

## የመለስ ካሮት እና ዱላ

ይህ ከላይ ተጠቀሰው ፅሁፍ የሮያል አፍሪካ ሶሳይቲ ሊቀመንበር የሆኑት ሪቻርድ ዳውደን መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን እንዴት እየመሯት ነው? (How Meles Zenawi Rules Ethiopia?) ያሉት ፅሁፋቻው መግቢያ ነው፡፡

መለስ አለማቀፉን ህብረተሰብ ሲቀርቡ ተለሳልሰው ይቀርባሉ፣ቃል ይገባሉ፣ ጊዜ ስጡን ይላሉ ነገሩ ከረር ሲልባቸው ዱላቸውን ይመዙና እኛ ለማንም የውጭ ሀይል አንንበረከክም ብትፈልጉ በሊማሊሞ ማቋረጥ ትችላልችሁ እያሉ ሊያስፈራሩ ይሞክራሉ፡፡ ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው ምርጫ 2002 ነው፡

መለስ ከቻይናው ፕሬዘደንት ሁጅን ታኦ ጋር በቻይና አፍሪካ የትብብር ፎረም ላይ፡-

‹‹ምርጫው ከመካሄዱ በፊት ከአለም አቀፍ ዲሞክራሲ ተቋማት ቃል በቃል የተገለበጠ የምርጫ ስነምግባር ደንብ አለ በሱ ላይ እንፈራረም እና ምርጫውን በሰላም እናስኪደው›› አሉ በፓርቲያቸው አማካኝነት። ‹‹አይ ምህዳሩ እንዲህ በጠበበት ሁኔታ ስለ ስነምግባር ማውራት ከባድ ነው መጀመሪያ ምህዳሩን ለቀቅ ያድርጉት›› ሲባሉ አሻፈረኝ አሉና ምርጫ አካሄዱ ውጤቱንም አለማቀፉ ህብረተሰብ እንደማይቀበለው ባወቁ ጊዜ አለማቀፉን ህብረተሰብ በተለይም የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ተቋማትን የሚያወግዝ ሰልፍ በመላው ኢትየጵያ ጠሩ 'NO, to TROJAN HORSE' የሚል የእንግሊዘኛ መፈክር አሸክመውም ካሮቱን አልበላም ያለውን አለማቀፉ ህብረተሰብ በዱላ ዳሰስ አደረጉት።

አለማቀፉ ህብረተሰብም በአካባቢው ካለው ሌሎች ፍላጉት አንፃር መለስን በድፍረት ተው ማለት አልፈለገም ከላይ የጠቀስናቸው ሪቻርድ ዳውደን አንድ የአሜሪካን ዲፕሎማትን ጠቅሰው ‹‹ይህ የሙባረክ አባዜ (Mubarak Syndrome) ነው›› ይላሉ ማለትም “We only talked to Mubarak about Egypt’s role in the region, never about what was happening inside Egypt. It’s the same with Ethiopia.” ።

## መለስ ለነገ

ከማርክሲዝም ወደ ካፒታሊዝም (በእርሳቸው ቋንቋ ወደ ነጭ ካፒታሊዝም) ከዛም ምንነቱን ያልለየለት 'የልማታዊ መንግስት' ርእዮተአለም አራማጅ ነኝ እያሉ ያሉት መለስ የሀገሪቱን የውጭ ፖሊሲዎች በግል ፍላጎታቸው ስር አድርገዋል ይሏቸዋል ተችዎቻቸው። ለምን እንዲህ አደረክ ሲባሉ የሚያኮርፉት መለስ የግል ወዳጆቻቸው የኢትዮጵያ ወዳጆች እንዲሆኑ ነው ጥረታቸው እንጅ ሀገራዊ ጥቅምን(National Interest) ያገናዘበ አይደለምም ሌላው ትችት ነው። እንግዲህ መለስ ስልጣን አስረ ከቡ እንበልና የመለስ የውጭ ግንኙነት ውርስ (Legacy) ምን ሊሆን ይችላል?

## መለስ ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያውያን

ኢትዮጵያ ድፍን የ25 ብር ኖት የላትም፤ ሆኖም ሊዘጋጅላት ነው ብለን እናስብ:: በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍተኛ ተጽእኖ ፈጣሪ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው መሪዎች ምስላቸው በዚህ የብር ኖት ላይ ታትሞ እንዲወጣ ቢፈለግ፣ ኢትዮጵያውያንን የሚያስማሙ መሪዎች አሉን? አቶ መለስስ ለዚህ ማዕረግ በስንቱ ኢትዮጵያዊ ይታጩ ይሆን? ብለን ብንጠይቅ:: መልሱ አዳጋች ነው:: እንደበለፀጉት ሀገሮች ነጻ የሆነ የሕዝብ አስተያየት የሚሰበስብ የሚዲያም ሆነ የህዝብ ግንኙነት ድርጅት በሌለበት እንደ ኢትዮጵያ ባለ ሀገር አቶ መለስን አብዛኛው ሕዝብ ‹ይወዳቸዋል› ወይም ‹ይጠላቸዋል› ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይከብዳል:: እንደ አፄ ምንሊክ ወይም እንደ አፄ ኃይለስላሴ የኢትዮጵያዊያንን አስተያየት በተለያየ መስመር እንደማይበታትኑ መናገር ግን አይከብድም:: ከሕዝብ ዕይታ ከተሰወሩ ወዲህ እንኳን፣ ስለጠቅላይ ሚንስትሩ በየማህበራዊ ድረገጾች እና በየጦማሮቹ የሚጻፉት ጽሁፎች የተቃውሞ እና የድጋፍ በማለት ለሁለት መክፈል ይቻላል:: ለመሆኑ አቶ መለስ በኢትዮጵያ እና በኢትዮጵያውያን እንዴት ይታያሉ?

ባልደራባዬ አቤል ጠቅላያችን የማን ናቸው? ብሎ በጠየቀበት ጦማሩ ‹‹ኢትዮጵያውያን እርሳቸውን የኔ ብለው ለመቀበል ይቸገራሉ፤ በግድ አስገድደው ያንተ ነኝ ካላሉት በቀር ሁሉም እርሳቸውን መሪዬ ናቸው ብሎ ለመቀበል አይፈልግም›› ይለናል:: ነገር ግን ባለፉት ሃያ አንድ ዓመታት የኢሕአዲግ የፊት ገጽ ሆነው የቆዩት አቶ መለስን ኢትዮጵያውያን እንዴት ያዩዋቸዋል የሚለውን ለመረዳት የኢሕአዲግን የአስተዳደር ስረዓት በቅጡ መረዳት ያስፈልጋል::

ኢሕአዲግ በቁመናው ሀገር አቀፍ የፖለቲካ ድርጅት ቢመስልም ሊቀመንበሩ አቶ መለስ ዜናዊ በጠና ታመዋል የሚል ወሬ ሲናፈስ በፓርቲው አባላት መንደር የሚስተዋለው አለመረጋጋት ብሎም የሚወራው የስልጣን ሽኩቻ የኢሕአዴግን ሀገር አቀፍነት ሳይሆን በአቶ መለስ ዜናዊ ሙሉ ቁጥጥር ስር የወደቀ ፓርቲ መሆኑን የተለያዩ ተንታኞች ይናገራሉ:: አቶ መለስ እና ደጋፊዎቻቸው ኢትዮጵያን በአዲስ መንገድ ለመስራት መንገድ ጀምረናል ብለው ቢናገሩም ከተቀናቃኞቻቸው እና ተቃዋሚዎቻቸው ግን ቀድሞ ከነበሩት የኢትዮጵያውያን የአገዛዝ ስርዓቶች ምንም የተለያ ነገር እንዳላመጡ ይባሱንም ሀገሪቱ የነበራትን መልካም እሴቶች እንዲሸረሽሩ ምክንያት ሆነዋል ብለው ይወቅሷቸዋል::

በቅርቡ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ የአቶ መለስን የሃያ አንድ አመት አስተዳደር ስርዓት በማስመልከት በሰማያዊ ፓርቲ ጋባዥነት ባደረጉትን ንግግር ላይ የአቶ መለስን ስርዓት ከበፊት ስርዓቶች ጋር በማነፃፀር ተናግረዋል:: እንደ ዶክተር ዳኛቸው አገላለፅ የዐፄ ኃይለሥላሴ የፈረስ ስም “ጠቅል” ነበር:: ስርዓታቸውና የፈረሳቸው ስም የተዋሃደ ነበር:: ፈረሱን ተምሳሌታዊ ያደርጋሉ “ጠቅል” ሲሉ ፍፁማዊ ስርዓት (Absolute State) እየፈጠሩ ነበር:: የስሜኑን ባላባቶች ተራ በተራ በፖለቲካ ካሸነፉ በኋላ “ጠቅል” ነው የሆኑት:: እንደ ዐፄ ቴዎድሮስ “አገር በእጄ” ነው ያሉት:: ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ቢያንስ ግልፅ ነበሩ:: የአቶ መለስ ስርዓት ግን ለየት ያለ “የጠቅልነት”(“Absolutism”) ባህሪ የሚስተዋልበት መሆኑን አስረድተዋል:: ይህ የአቶ መለስ ስርዓት ለየት ያለ “የጠቅልነት”(“Absolutism”) ባህሪ ያለው ሲሆን ምንም ዐይነት ተቀናቃኝ ኃይል የማያስተናግድ እና የተደራጀውንም ሆነ ያልተደራጀውን የማይታገስ ፍፁማዊ ነው:: በተጨማሪም የአቶ መለስን የኢሕአዲግ አገዛዝ የዴሞክራሲ ማዕከላዊነት (Centralized Democracy) የሚተገብር ነው ብለው ገልፀውታል::

### የመለስ ፊት ደጋግ ስጦታዎቸ ለኢትዮጵያ

አቶ መለስ ዜናዊ በሰብዓዊ መብት አያያዝ እና በሌሎች በርካታ ጉዳዮች የሰላ ሂስ ቢሰነዘርባቸውም በደጋፊዎቻውም ሆነ በተቃዋሚዎቻቸው ዘንድ የሚመሰገኑበት ደጋግ ተግባራት አሏቸው:: ከነዚህ በቀዳሚነት የሚነሳው ፍትሐዊ አይደለም ቢባልም የኢኮኖሚ እድገቱ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ በቀድሞዎቹ የሊቢያው መሪ ሞአመር ጋዳፊ እና በሴኔጋሉ መሪ አብዱላሂ ዋዴ የአፍሪካ ሕብረትን መቀመጫ ከአዲስ አበባ ወደ ሀገራቸው ለመውሰድ የተለያዩ ማባበያዎችን በመጠቀም ቢሞክሩም በአቶ መለስ አንደበተ ርቱዕነት ተሸንፈው የኅብረቱ መቀመጫ ከታሪካዊ ቦታው ሳይነሳ ቀርቷል:: ነገር ግን ዘግይተዋል አልያም ለፖለቲካ ፍጆታ አውለውታል ተብለው ቢታሙም የታላቁ የአባይ ግድብ ስራ ጅማሮም ሌላው አቶ መለስ ሊታወሱበት የሚችሉበት ደግ ተግባራቸው እንደሆነ ብዙዎች ይመሰክሩላቸዋል:: አቶ መለስ በተለያዩ ዓለምአቀፍ ስብሰባዎች የኢትዮጵያን

አልፎም የአፍሪካን ጉዳዮች በማስረዳት የአፍሪካ መሪ የሚል ስያሜ እንዳተረፉ ከተለያዩ ጽሁፎች መረዳት ይቻላል::

## መለስ ለኢትዮጵያ ንፍገት እና ክፋት

‹‹አንድ ሺሕ አራት መቶ ማይልስ የሚያህል የውኃ ጠረፍ ካስረከብን በኋላ አራት መቶ ኩንታል ድንች ለማያመርት ቦታ ከ50 እስከ 60 ሺሕ ወጣት በጦርነት ገብረናል›› ይላሉ ዶ/ር ዳኛቸው አሠፋ የኤርትራ መገንጠልን ተከትሎ ሀገሪቱ ወደብ አልባ መሆኗን እና ሁለት ዓመት የቆየውን የኢትዮ ኤርትራን ጦርነት ክስረት በአንድ ላይ ለማውሳት:: ይህ እንግዲህ የአቶ መለስን ንፍገት እና ክፋት ለማውሳት ተችዎቻቸው በቀዳሚነት የሚያነሱት ተግባራቸው ነው:: በስምም ቢሆን ሕገ መንግስታዊ ስርዓት አቋቁመው በሕገ መንግስቱ ላይ የተዘረዘሩትን ሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሸራርፈዋል፤ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጡ መብቶችን የሚደፈጥጡ አዋጆችን አውጥተው የዜጎችን መብት ገፈዋል የሚሉ ሂሶችም ከአቶ መለስ ተቃዋሚዎች ተዘውትረው የሚደመጡ ትችቶቻቸው ናቸው::

ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ Diciphering Meles Zenawi's haterade to Ethiopia በሚለው አንድ በቅርቡ ባሳተሙት ጽሑፋቸው ‹ኢትዮጵያን ሳይወዱ ኢትዮጵያን ያስተዳደሩ ብቸኛ መሪ› በሚል በአቶ መለስ ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶችን ባጠናከሩበት ጽሑፋቸው አቶ መለስ ሀገራቸውን የማይወዱበትን ምክንያት የተለያዩ የስነልቦና ኀልዮቶች በማንሳት አስረድተዋል:: በብሔር ብሔረሰቦች መብት መረጋገጥ ስም በርካታ የብሔር ሥራ ፈጣሪዎች (Ethnic entrepreneurs) በየሰፈሩ እንዲፈለፈሉ ምክንያት ሆነዋል የሚል ትችትም ከአቶ መለስ ስም ጋር በተደጋጋሚ የሚነሳ ጉዳይ ነው:: አቶ መለስ አንደበተ ርቱዕ እንደሆኑ በደጋፊዎቻቸው ቢመሰከርላቸውም ሌሎች ግን ‹በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የነበሩ የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካዮችን በማንጓጠጥ እና አግባብ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ይናገራሉ፤ ይህም ከአንደበተ ርቱዕነት አቅም ማጣት የሚመነጭ ነው› በማለት በተቃራኒው ይተቿቸዋል:: የኢትዮጵያ ታሪክ ለነገሥታቱ የሚወግን ታሪክ በመባል በሚዛናዊነት በተለያዩ ወገኖች ይወቀሳል፡፡ ቀጣዩ የኢትዮጵያ ታሪክስ፣ ከመቶ ዓመታት በኋላ የአቶ መለስን ታሪክ እንዴት ያስታውሰው ይሆን?

## ማን ሥልጣን ላይ ተወለደና?

Murder at 1600 ዊስሊ ስናይፐስ (Wisely Snipes) የተሰኘ ጥቁር አሜሪካዊ የሚተውንበት ልብ አንጠልጣይ ፊልም መጠሪያ ነው - Murder at 1600፡፡ 1600 (Sixteen hundred) የአሜሪካ ፕሬዝዳንቶች መኖሪያ የሆነው ዋይት ሀውስን በር ይዞ የሚያልፈው መንገድ መጠሪያ ነው፡፡

ፊልሙ የሚያጠነጥነው ስናይፐስ ዋይት ሀውስ ውስጥ ተገድላ የተገኘች ሴትን ነፍሰ ገዳይ እና የአማሟት ሁኔታ ለማጣራት በሚያደርገው ውጣ ውረድ ላይ ነው፡፡ ነፍሰ ገዳዩን ለማግኘት ስናይፐስ በሚያደርገው ክትትል በግድያው የፕሬዝዳንቱ እጅ እንዳለበት የሚጠቁሙ የጥርጣሬ መረጃዎች ያገኛል፤ ይህ ያልተዋጠላቸው የፕሬዝዳንቱ ቺፍ ኦፍ ስታፍ ስናይፐስን ደውለው ያስጠሩትና የዋሽንግተንን ማስታወሻ ሃውልት አሻግሮ የሚያሳየው ፓርክ ውስጥ የጠዋት ስፖርት እየሰሩ ስናይፐስን የክትትሉን ትኩረት ወደ ሌላ ተጠርጣሪዎች እንዲያዞር ወይንም ከነጭራሹ ቢተወው እንደሚሻል ለማስረዳት ይሞክራሉ፡፡ ስናይፐስ ግን የሚመለስ አልሆነም፤ እንደውም መረጃዎች የጠቆሙት ሰው እና ስልጣን ድረስ እንደሚሄድ አስረግጦ ይነግራቸዋል፡፡ ይህን ጊዜ ቺፉ ቆጣ ብለው ‹‹ፕሬዝዳንትነቱ ተቋም ነው (ግለሰብ አይደለም) እዛ እንድትደርስ አልፈቅድልህም›› ይሉታል፡፡

## ሥልጣን ተቋማዊ (Institutionalized) ሲሆን ምን ማለት ነው

በታዳጊ ሀገራት ያሉ የመንግስት የአስፈፃሚ ቅርንጫፍ አናት ላይ የሚገኙ ባለስልጣናት ብዙ ጊዜ ሲፈፅሙ/ሲፈፅሙ ሲሞክሩ ከምናያቸው የፖለቲካ ቅሌቶች መካከል ስልጣን ላይ ለተጨማሪ ዓመታት ለመቆየት ሕገመንግስቱን ማሻሻል (ሴኔጋል እና ቬንዙዌላ የቅርብ ምሳሌዎች ናቸው)፣ ምርጫ ማጭርበርበር (ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ዚንባቡዌ)፣ በምርጫ ቢሸነፉም ስልጣን አለቅም ማለት (ኮትዲቩዋር) ይገኙበታል፡፡ እነዚህን የመሰሉ አሳፋሪ ድርጊቶች የሚፈፅሙት ታዲያ ስልጣንን የሚያዩት እንደህዝብን ማገልገያ መሳርያ ሳይሆን እስከ እለተ ሞታቸው የፈለጉትን እየፈለጡና እየቆረጡ የሚኖሩበት የግል ንብረታቸው አድርገው ስለሆነ ነው፡፡ ማቲያስ ባሰዶው እና አሌክሳንደር ስትሮህ የተባሉ የማህበራዊ ሳይንስ ጥናት ባለሙያዎች *የፖለቲካፓርቲዎች ተቋማዊነት በታዳጊ ሀገራት በፌተሹበት ጥናት* ተቋማዊነትን ሲተረጉሙ *‹ድርጅቶች እሴቶችን የሚመርጡበት እና ቀጣይነትን የሚያረጋግጡበት ሂደት ነው›* ሲሉ ይገልፁታል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደማንኛውም ድርጅት ትውልድ ተሻጋሪነታቸውን ለማረጋገጥ ግልፅ የሆነ ስልጣንን (ቢያንስ ፓርቲ ውስጥ) ለተተኪዎች የሚያስተላልፉበት መመሪያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህንንም ሽግግር የሚያበረታታ ስልጣን ህዝብን ማገልገያ መሳሪያ ብቻ እንደሆነ የሚያረጋግጥ የውስጠ ፓርቲ እሴት ያስፈልጋል፡፡ ኃላፊነትን ለመረከብ በጥሩ ሁኔታ የተኮተኮተ ተተኪ ማዘጋጀት እና ተተኪውም ብቁ መሆኑ ሲረጋገጥ ስልጣን (የፓርቲውንም ይሁን የሀገር) ማስረከብን አማራጭ የሌለው ምርጫ የሚያደርግ ባህል መፍጠርን ያካትታል ማለት ነው - ተቋማዊነት፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ማድረግ ያልቻለ እንደ ትልቅ ውድቀት የሚቆጠርበት በተለይም ስልጣን አልለቅም ብሎ ችክ ማለትን አሳፋሪ የሚያደርግ እሴት መፍጠር ወሳኝ ነው፡፡

## አምባገነኖች እና ተቋማዊነት!

*"What would I do if I leave the Presidency? Chop Onions?" Hosni Mubarak*

ከላይ እንደ ተጠቀሰው አምባገነኖች ስልጣን ላይ ለመቆየት ምንም ከማድረግ ወደኋላ አይሉም፤ ድርጊታቸው ምንም ያክል አሳፋሪ ቢሆንም፡፡ አንባገነኖች እራሳቸውን ብቸኛ ነፃ አውጪ፣ ሰላም አስከባሪ፣ አልሚ …ወ.ዘ.ተ አድርገው ነው የሚቆጥሩት ወይም እንዲቆጠሩ የሚፈልጉት፡፡ ለዚህም ነው መልካም ስራ በመስራት ትንሽም ቢሆን ህዝባዊ ተቀባይነት የሚያገኙ ሰዎችን ከኃላፊነታቸው ዞር ከማድረግ አንስቶ ‹‹በህጋዊ›› እርምጃም ከጨዋታ ውጪ የሚያደርጓቸው፡፡ ሰዎች በአምባገነኑ ጥርስ ውስጥ ለመግባት የሚጠበቅባቸው ጥሩ ስራ ሰርተው በህዝብ ዘንድ ጥሩ ስም እና አመኔታ መገንባት ብቻ ነው፤ የአምባገነኑ ፓርቲ ወይንም ጎሳ አባል፣ አብሮ አደግ፣ ወይንም የተፎካካሪ ፓርቲ አባል መሆን ልዩነት ያለው የሚከተለው ቅጣት ላይ ነው እንጂ ህዝብ እንዲወደውና አመኔታ እንዲጣልበት የሚፈቀደው ለአምባገነኑ ለእራሱ ብቻ ነው፡፡ አምባገነኖች በወዳጅ ሀገሮችም ዘንድ እንደብቸኛ የወዳጅነቱ ጠባቂ ሆነው መቅረብ ነው የሚፈልጉት - እነሱ ከሌሉወ ዳጅነቱ ገደል እንደሚገባ፡፡

ይህን ትንተና ለመደገፍ የቀድሞ የግብፅ ፕሬዝዳንት የነበሩትን ሆስኒ ሙባረክ እና የሊቢያ መሪ የነበሩትን ሙአመር ቃዳፊን ማየት ይበቃል፡፡ ሁለቱ መሪዎች በየሀገራቸው ለረጅም (ከሦስት አሥርት ዓመታት በላይ)

በስልጣን የቆዩ ሲሆን ሀገሮቻቸው የሚያስፈልጋቸው ዴሞክራሲ ከምዕራቡ ዓለም ለየት ያለ እንደሆነ ሲሰብኩ የኖሩ ነበሩ። የአረቡ ዓለም ፀደይን ተከትሎ ሁለቱም ስልጣናቸው አደጋ ላይ ሲወድቅ የተለመደውን የአምባገነኖች ብሔራዊ መዝሙር ነበር የዘመሩት፤ እስከዛሬ እኔ ሆኜ ነው እንጂ ይህች ሀገር በብዙ ችግሮች የተተበተበች ናት፣ ያለ እኔም በቀጥታ የእርስ በእርስ ጦርነት ነው የምትታመሰው፣ በኋላ ሙባረክ/ቃዳፊ ምን በደለን የምትሉበት ቀን ይመጣል የሚል አንድምታ ያለው ንግግር ነበር የሚያቀርቡት - የሚሰማቸው አላገኙም እንጂ። የሚገርመው ከጥቃቅን የማስዋቢያ ለውጦች በስተቀር የሁሉም አምባገነኖች ክርክር አንድ ነው - የእናት ሆድ ዥንጉርጉር የሚለው አባባል ለአምባገነኖች የሚሰራ አይመስልም። በስተመጨረሻ መውደቂያቸው ሲቃረብ አምባገነኖች የሀገሪቷን ችግሮች አጋንነው ሲደረድሩ ለሃያና ሠላሳ ዓመት በአመራራቸው ስር ስለነበረች ሀገር ሳይሆን ስለሌላ መልካሙዋን ማንሳት ስለማይፈልጓት ፀበኛ ሀገር የሚያወሩ ነው የሚመስለው።

አምባገነኖች ሁልጊዜም ቢሆን እንደስልጡን መሪ መታየት ይፈልጋሉ። ጎልማሳ እያሉ ስልጣን እንደያዙ ምንም የማይወጣለት ብሔር ብሔረሰቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል የሚያጎናፅፍ ሕገመንግስት ሲያፀድቁ እና በሀገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ ሊባል የሚችል ህዝባዊ ምርጫ ሲያካሂዱ የተሰጣቸውን የ‹‹ተራማጅ››ነት ዝና ስልጣን ላይ ከድፍን ሃያ ዓመት በላይ ከቆዩ በኋላ በልማታዊነት እንደገና ዝናዋን መልሰው ሊጎናፀፉ ይፈልጋሉ። አንድ አሁን በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊ የምጣኔ ሃብት ባለሙያ በመጽሐፋቸው እንዳሰፈሩት አምባገነኖች እራሳቸውን ለማሞኘት የሚሄዱትን ርቀት አሳንሶ መመልከት በርግጠኝነት መሳሳት ነው።

## ከአንባገነኖችበኋላስ

አምባገነኖች የፖለቲካ ስልጣንን የግል ንብረታቸው አድርገው በመመልታቸው ተተኪ ማዘጋጀት ይቅርና ሊተኩ ይችላሉ የሚባሉትን ሰዎች ብቻ አይደለም ሐሳቡንም ጭምር ማጥፋት ከተቻላቸው ይሞክሩታል። ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው አንባገነኖች እራሳቸውን እና እራሳቸውን ብቻ ለሀገሪቱ አማራጭ የሌለው ምርጫ አድርገው፤ እኔ ከሌለሁ ምንም አይኖርም በሚል ስልታዊ የፍራቻ ድባብ ውስጥ የሚመሩት ሀገር ዜጎች ሁሉ እንዲገቡ በማድረግ የስልጣናቸውን እድሜ ማራዘም ነው ግባቸው። እንደሳቸው ማነው አቻችሎ የሚገዛን እሳቸው ባይኖሩ እኮ እስከዛሬም አልቀን ነበር ብለን እንድናስብ ነው የሚፈለገው፤ ስለሆነ ሳይሆን ለዓላማቸው ስለሚረዳቸው ብቻ።

### ወደገደለው

አቶ መለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ አልተወለዱም። ፈጣሪም እሳቸውን ብቻ ለቦታው የሚመጥኑ አድርጎ እንዳልሰራቸው ምስክር ከራሳቸው ሌላ የሚያስፈልገን አይመስለኝም። እንደውም

- አስፈራርቶ እና በጠብ-መንጃ ተማምኖ ከሚገዛን ልምድ ያለው አምባገነን አንድ ሀገራዊ ራዕይ ፈጥሮ የሚመራን ጀማሪ ይሻለናል፣
- ተቃዋሚዎችንና ጋዜጠኞችን ሳስር እና ሳንገላታ አያገባችሁም፣ ገንዘባችሁን በሊማሊሞ በኩል ይዛችሁ መሄድ ትችላላችሁ፤ ሃያ አንድ ዓመት ማሸነፍ ያቃተን የምግብ እህል ተረጂዎች ጉዳይ ግን የጋራችን ነው ብሎ ሀገሪቷን ከሚያዋርድ መሪ በግልፅ ቋሚ የውጭ እገዛ የምንፈልግበትን ሀገራዊ ጉዳይ ለይቶ ከሁሉም ወዳጅ ሀገራት ጋር ተስማምቶ የሚሰራ መሪ ይሻለናል፣
- ስልጣን ላይ ለመቆየት ንፁሀን ዜጎችን ከሚገድል/ከሚያስገድል ይህን ተግባር እፈፅማለሁ፣ ሀገሪቷን ከእህል ተረጂነት አላቅቃለሁ አለበለዚያ ግን ስልጣን የናንተ ነውና እለቃለሁ የሚል፣ ብሎም የሚፈፅም መሪ ይሻለናል።

# ከመለስ በኋላ!

በዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና መምህር እና ከጥቂት የአደባባይ ምሁራን አንዱ የሆነውን ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋን አነጋግረን ስለወቅቱ ማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች የተለያዩ ሐሳቦችን ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ አሁን ደግሞ የአቶ መለስን 'ድንገተኛ!?' ሞት ተከትሎ በድኅረ-መለስ አትዮጵያና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ እንደተለመደው ገዢ ሐሳቦቹን ሰጥቶናል፡፡ መልካም ንባብ

## የመርዶው ሕዝባዊ ምላሽ

እንደሚታወቀው ለሀያ አንድ ዓመታት በሙሉ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥኑን መስኮት አጣበው ይዘውት የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ መለስ ዜናዊ ናቸው፡፡ እንዲሁም በከፍተኛ ሁኔታ ተክለ ስብዕናቸውና ስራቸው በሚዲያው ሲገነባላቸው የቆዩት ጠቅላይ ሚኒስተር በድንገት የህይወታቸውን ህልፈት ህዝቡ ሲሰማ ድንጋጤና ሀዘን ፈጠሮበታል፡፡ ይህንንም የህዝብ ሀዘን በሁለት አቅጣጫ ልናየው እንችላለን፡፡ የመጀመሪያው አስከሬናቸው ከውጭ ሀገር በገባበት ምሽት ከተጠበቀው በላይ ህዝብ ወጥቶ ብሶቱን እና ሀዘኑን የገለፀበት ነው፡፡ ምናልባትም ህዝብ ላሳየው የሐዘን ጎርፍ አንድ ወሳኝ የሆነ ነገር መገንዘብ የምንችለው ህዝቡ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ፓርቲው ከሚያራምደው የጎሳና የነገድ ፖለቲካ ውጪ እንደአንድ ኢትዮጵያዊና እንደግለሰብ አይቶ እንዳዘነላቸው መረዳት አያስቸግርም፡፡ በተጨማሪም እሳቸው በህይወት እያሉ ለያይተው ያዩት ህዝብ ሲሞቱ ግን እርስ በርስ ሳይለያይ በህይወት እያሉ ያላያያዙትን ህዝብ በሞታቸው ሊያያይዙት ችለዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ እየተመለከትን ያለነው የህዝቡን ስሜት ለፖለቲካ ግብአታቸው ለመጠቀም ስትራቴጂ ነድፈው፣ በተደራጀ መልኩ እንቅስቃሴ ውስጥ መግባታቸውን ነው፡፡ ከዚህም አኳያ መንግስት ሊያደርግ የሚፈልገው አቶ መለስ ኖረም አልኖረም ህዝቡ የስርዐቱን መቀጠል እንደፈለገና ተቀባይነትም እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡ ይህንንም ለመተግበር በብሔራዊ የቀብር ስነ ስርዓት አስፈጻሚው ኮሚቴ ስም የህዝቡን ስሜት ወደፈለጉት አቅጣጫ ተቆጣጥሮ ለማዞር የሚያስችል ኮሚቴ ተቋቋሞ በስራ ላይ እያየነው ነው፡፡ በመሆኑም መልስ አዘል ጥያቄ በማቅረብ ህዝቡ እንዲናገር በማድረግ፣ በየሰፈሩ ድንኳን በመትከል፣ በካዴሬዎች አማካኝነት በየመስሪያ ቤቱ መመሪያ በመስጠት ወዘተ… የህዝቡን ስሜት ለፖለቲካ ግብዐት እየተጠቀሙበት ይገኛል፡፡ ለማጠቃለልም ብዙ ሐዘንተኞች የተጀመረው ፕሮጀክት ከፍፃሜ እንዲደርስ በርግጥ ቢጠይቁም የመንግስት ኮሚቴ እንደተመኘው የኢሕአዴግን ስርዓት ቅጥያ ሲጠይቁ አልተደመጡም፡፡ ምን አልባትም ህዝቡ በፕሮጀክት እና በስርዐት መካከል ያለውን ልዩነት የተረዳ ይመስላል፡፡

## የሥልጣን ሽግግር

የድኅረ መለስ መንግሥት ምን ዓይነት የፖለቲካ መንገድ እንደሚይዝ ከመተንተናችን በፊት ወደኋላ መለስ ብለን ከቅርብ ታሪካችን እና ከፖለቲካ አንጻር ጥቂት በእንበል፡፡

### ሀ. ከታሪክ ማሕደር

በዶ/ር ሌቪንን "Wax and Gold" የተሰኘው መጽሐፍ ገጽ 152 ላይ እንዲህ ይላል፡፡

*"Successors to the throne were not determined according to fixed rule like primogeniture. Membership in the Solomonian line was normally a prerequisite……Usually however there were several legitimate candidates for the position and the absence of fixed procedures for choosing among the meant that the death of an emperor was often a time of confusion and political improvisation."*

*"የመንበሩ ወራሾች በተደነገገ ቋሚ መመሪያ አልነበረም የሚወሰኑት፡፡ በሰለሞናዊ ስርወ መንግስት መስመር ውስጥ አባል መሆን በጥቅሉ እንደቅድመ ሁኔታ የተቀመጠ ነው… በተለምዶ፣ ምንም እንኳን ቦታውን የሚመጥኑ ብዙ ሕጋዊ (ሰለሞናዊ) እጩዎች ቢኖሩም፣ አንዱን ለመምረጥ የሚያስችል ውሱን መስፈርት ባለመኖሩ የንጉሠነገሥት ሞት ሁልጊዜም ውዥንብር እና ፖለቲካዊ ጥበብን ይጠይቃል፡፡" (ትርጉም የዞን ዘጠኝ)*

በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ሰላማዊና ሕጋዊ የሆነ የስልጣን ሽግግር በአብዛኛው ተካሄዶ አያውቅም። እንደ ዕውቁ ሶሾሎጂስት አገላለጽ ይህም የሆነበት ምክንያት፡-

- አንደኛ የስልጣን ሽግግር ህጉ በደንብ አለመቀመጡ፣
- ሁለተኛ ስልጣን ለመያዝ (ዘውድ ለመጫን) የሰለሞናዊ ስርወ-መንግስት የግዴታ ተወላጅ መሆንና፣
- በአንድ ጊዜ ከሰለሞናዊው ስርወ መንግስት ተወላጅ የሚሆኑ ብዙ ተወዳዳሪዎች ለቦታው ብቁ ሆነው መገኘታቸው ነው፤

በመሆኑም ወደ ኢህአዴግ ዘወር በምንልበት ጊዜ ከላይ የጠቀስናቸው ታሪካዊ ክፍተቶች ዛሬም እንደትላንቱ ኢህአዴግም የዘረጋው ስርዓት አልተሻገራቸውም። ይህንንም ስንል በሕገ መንግስቱ ላይ በግልጽ የሰፈረ ቋሚ የስልጣን ሽግግር ህግ የለም። በተጨማሪም ትላንት ዘውድ ለመጫን የሰለሞናዊው የዘር ሀረግ አስፈላጊ እንደነበረው አሁን ደግሞ ስልጣን ለመጨበጥ የኢህአዴግ አመራር መሆን የግድ ነው። በመሆኑም ለሰለሞናዊው የሽግግር ጥያቄም ሆነ ለአሁኑ ጊዜ በርካታ ተቀራራቢ ዕጩዎች ወይም ተወዳዳሪዎች መኖራቸው ሽግግሩን ውስብስብ እና አስቸጋሪ አድርጎታል።

**ለ. ከፓለቲካ ዳራ**

አሁን ለተነሳው የሽግግር ጥያቄ መልስ ለማግኘት የጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ አመራር ምን አይነት መልክ የያዘ ነበር የሚለውን ማወቅ ይገባናል፤ ምክንያቱም በየትኛውም የዓለማችን ክፍል እንደሚታየው የስርዓቱ ዲሞክራሲያዊ ወይንም ኢ-ዲሞክራሲያዊ መሆን በስልጣን ሽግግሩም ላይ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ምንአልባት ይህንን ሐሳብ የበለጠ ለማብራራት የሀኛያው ክፍለ ዘመን የፓለቲካ ፍልስፍና መምህርት ከነበረችው ሐና አረንት (Hanna Arendt) ትንሽ እንውሰድ።

እንደ ሐና አረንት አመለካከት የዴሞክራሲያዊ ስርዓት አገዛዝ የ'ስልጣን መርህ' (authority principle) ሲከተል ኢ-ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ በአንጻሩ ደግሞ በ'መሪ መርህ' (leadership principle) ይተዳደራል። በ'ስልጣን መርሕ' የስልጣን ተዋረዱና ክፍፍሉ በሀገሪቱ ህግ በዝርዝርና በግልጽ ተለይቶ ይቀመጣል። በሌላ በኩል በ'መሪ መርሕ' የሚታዳደሩ ሀገሮች ግን ይህን በተመለከተ የስልጣን ተዋረድ የላቸውም። ስልጣኑ ተጠቃሎ በመሪው እጅ ይገኛል። ከመሪው ቀጥሎ ሁለተኛ የሚባል ለይስሙላ ይቀመጣል እንጂ መሪው አንድ ነገር ቢሆን በሁለተኛ ደረጃ የተሰየመው ሰው ይተካዋል ማለት አይደለም። ለማጠቃለል የሀና አረንት አቀራረብ የሚያስተምረን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ማለት ከ'መሪ መርህ' ወደ 'ስልጣን መርህ' መሸጋገር ማለት ነው። በኢትዮጵያ ሕገ መንግስታዊ ሰርዓት ሲዘረጋ ይህ ታስቦ ቢሆንም የዲሞክሪያሲያችን ጨቅላነት የመሪዉን ጫንቃ መሸከም ስላቀታት ዴሞክራሲው በአጭሩ ተቀጭቶ በ'መሪ መርህ' ለመመራት በቅተናል።

## ድኅረ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ (Post; Capital 'P' or Small 'p')

የእንግሊዘኛውን 'post' የሚለውን ቃል ለሁለት ከፍለን ብንመለከተው ለትንተናችን ያመቸናል። ካፒታል 'ፒ' እና ስሞል 'ፒ' ብለን እንከፍለዋለን። ካፒታል 'ፒ' ተጠቅመን ድኅረ (Post) ስንል consequential መሰረታዊ የለውጥ ሂደቶችን ያካተተ ማለት ሲሆን ባንፃሩ ደግሞ ስሞል 'ፒ' ስንጠቀም መሰረታዊ ያልሆነና ፋይዳ ያለው ለውጥና ሽግግር የማይታይበት ሆኖ እናገኛዋለን። ለምሳሌ በአረብ ሀገራት በቅርቡ የተነሳው አብዮት መሰረታዊ የስርዓት ለውጥ ስላስከተለ ካፒታል 'ፒ' ነው። በሌላ በኩል ከአንዋር ሳዳት ወደ ሙባረክ የነበረው ሽግግር ግን ምንም ዓይነት የስርዓት ለውጥ ስላልታየበት ስሞል 'ፒ' ነው።

ከሁሉ አስቀድሞ ከላይ በትንሹ ልንጠቅሰው እንዳሰብነው አሁን አመራር ላይ ያሉት ባለስልጣናት የድኅረ መለስን ስርዓት እንዳለ እንዲቀጥል እና ሽግግሩም ስሞል ፒ' እንዲሆን ይፈልጋሉ። ለዚህም ነው አስቀድመው "የፓርላማ አባላቱን በአስቸኳይ ሰብስበን አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን ከጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስቴርነት ወደ ቋሚ ጠቅላይ ሚኒስቴርነት እንለውጣለን" የሚል ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡት።

መንግስት እንዳሰበው የስርዓቱ ሕልውና በምንም መልኩ ጥያቄ ውስጥ የገባ እንዳልሆነ በየጊዜው የሚነግረን ቢሆንም ብዙ የአደጋ ቀጠናዎች እንዳሉ ግን እየተገነዘብን ከላይ ወደ አነሳነው ወደ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ መመረጥ ፖለቲካ አንድምታ ላይ እንመለስ።

ከአቶ ኃይለማርያም ምርጫ ዙሪያ ሁለት ጥያቄዎች ማንሳት እንችላለን። አንደኛ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የኢህአዴግ መሪዎች 'የስልጣናችን ምንጭ (legitimacy) የሚፈልቀው በትጥቅ ትግሉ ውስጥ በከፈልነው መስዋዕትነትን' ሲሉ ቆይተው በዚህ ጎዳና ያላለፈ ሰው መምረጣቸው፤ ሁለተኛ ደግሞ ሌሎች አንጋፋ ፓርቲዎች እያሉ ኢህአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኂላ የተመሰረተ ፓርቲ አባል መሆናቸው ስለሳቸው ሳይሆን በግንባሩ የፖለቲካ ህይወት ወሳኝ ሚናን ስለሚጫወቱት አካሎች የሚነግረን ነገር አለ።

ይህንን ለመረዳት ከሁለት ዓመት በፊት ከኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር መካከል አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ እንዴት የምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴርነትን ሹመት እንዳገኙ ማስታወስ ይገባናል። በዚህ ወቅት ፓርቲው በመተካካት ጥያቄ እና በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ጤና መቃወስ ምክንያት ተወጥሮ ነበር። በዚህም ጊዜ በጣም የሚያስገርመውና የሚያስደምመው የህወሓት ልሂቃን ሁለት አማራጭ ይዘው ቀረቡ። አንደኛ በአገሪቱ ላይ ዴሞክራሲ እንዳይቀጭጭ ከተፈለገ እና እኛ የምንወክለው የሕዝብ ቁጥር አነስተኛ ስለሆነ የጠቅላይ ሚኒስቴሩን ቦታ ከብአዴን እና ኦህዴድ ብንመርጥ የግንባራችንን የኃይል ሚዛን ስለሚያዛባው በኛ በኩል ተቀባይነት የለውም የሚል ሐሳብ አቀረቡ። ሁለተኛ የጠቅላይ ሚኒስቴሩን ጽ/ቤት ለሦስት ወይንም ለሁለት በመክፈል የስልጣን ክምችቱን (premiership ) ብናሰራጨው የተሻለ ይሆናል አሉ። በመሆኑም የመጀመሪያው ሐሳብ በግንባሩ ተቀባይነት በማግኘቱ ከሁለቱ ብዙኃን ፓርቲ ውጪ የሆነ ሰው በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴርነት ለመምረጥ በቅተዋል። ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ ሀገሪቱን ለሌሎች ስጋቶች ስለሚያጋልጣት ተቀባይነት አላገኘም።

አሁን ለጊዜው የሀገሪቱ የፖለቲካ አቅጣጫ ወይም የሽግግር ሁኔታ ካፒታል 'ፒ' ወይንም ስሞል 'ፒ' ይሆናል ለማለት አስቸጋሪ ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ አራት ዐበይት ወቅታዊ ጉዳዮች አሉ።

1. የአቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የፖለቲካ ደረጃ አጠያያቂነት በራሳቸው አመራር እንዳይሄዱ ሰርዓቱ የማይፈቅድላቸው በመሆኑ፣
2. የኦሮሚያ ክልል ፕሬዘዳንት አቶ አለማየሁ አቶምሳ ቦታ በህመም ምክንያት ክፍተት በመፍጠሩ እና ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚነሳው ውዝግብ፣
3. በኢትዮጵያ ሙስሊሞች እና በመንግስት መካከል የተነሳው ውዝግብ እልባት አለማግኘት፣
4. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ህልፈት ተከትሎ ቀጣዩን ፓትርያርክ የመምረጥ ሂደት

## መደምደሚያ

እንደሚታወቀው ኢህአዴግን የሚያዋቅሩት የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉም እኩል ናቸው ቢባልም በኦርዌሊያን (George Orwell) አነጋገር "ሁሉም ፓርቲዎች እኩል ናቸው አንዳንድ ፓርቲዎች ግን የበለጠ እኩል ናቸው" እንዳለው ልክ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ባላነሰ የህወሓት ሊቀመንበር ቦታ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ህይወት ላይ ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው አጠያያቂ አይደለም። ይሄ ፓርቲ የበላይነት እና የገዢ ስፍራውን ለረጅም ጊዜ ማስቀጠል ይፈልጋል። ይሄንን ለመተግበር አሁን ለማደረግ እንደተፈለገው ከሌላ (ማለትም ብዙኃን ቁጥር ከሌለው) ፓርቲ በመሾም አሊያም ከራሱ ፓርቲ ሰው መልምሎ በማቅረብ በምንም መልኩ የስልጣን ባለቤትነቱን ለማረጋገጥ ይፈልጋል።

# ምናልባት፣ ምናልባት… ከመለስ በኋላስ?

የመንግሥት ኮምንኬሽን ጉዳዮች በነገሩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ቢሞክርም የአቶ መለስን "ቀላል ህመም" ከማመን ይልቅ አሁንም ኢትዮጵያ በዚሁ ዜና እውነትነት እና ውሸትነት ዙሪያ እየተናጠች ትገኛለች - የሚያሳምን እና የተረጋገጠ መረጃ የሚሰጥ እስካሁን አልተገኘም እንጂ! ‹‹ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ታመዋል፣ ኧረ እንዲያውም ሞተዋል፣ አይ… መዳከም ነው እንጂ ደህና ናቸው… ወ.ዘ.ተ›› የሚሉ መላምቶች አሁንም በየፌናው ይሰነዘራሉ፡፡ ይህ ዜና እየተናፈሰ ባለበት በዚህ የውጥረት ሰሞን አንድ የመንግስት ኃላፊ ወጥቶ ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት ረዥም ጊዜ መውሰዱ መንግስትን ትዝብት ላይ ቢጥለውም ከአቶ በረከት መግለጫ በኋላ ደግሞ የመረጃው ትክክለኛነት ለማመን እንኳን ሳይሞክሩ፣ ብዙዎች በተከታዩ የድኅረ መለስ ዘመን ላይ እያወሩ ይገኛሉ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ (እንደ ኮምንኬሽን ሚኒስትሩ ንግግር ቀላሉን ያርግላቸውና) ከዚህ በኋላ አገሪቱን መምራት የማይችሉበት ሁኔታ ቢፈጠር ቀጥሎ ምን ይከሰት ይሆን?›› የሚለው ልብ አንጠልጣይ ጥያቄም በተለያዩ ሰዎች እና አካላት ዘንድ የመወያያ አጀንዳ እየሆነ ይገኛል፡፡

## የአቶ መለስ አለመኖር…

የሕወሓት ‹‹የነፍስ አባት›› አቦይ ስብሃት ነጋ በቅርቡ ከቪኦኤ ጋር በነበራቸው ንግግር የአቶ መለስን በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት አለመኖር አቃለው ሃገሪቷ በአመራር ደረጃ የሚያጋጥማት ክፍተት እንደማይኖር ተናግረዋል፡፡ ይህ እንግዲህ ከአንድ የበታች አመራር ካድሬ የተሰጠ ሐሳብ ቢሆን ኖሮ ‹‹የፓርቲውን እና የመንግስትን አሠራር ያልተረዳ፣ የዋህ፣ ልማታዊ›› ብለን እናልፈው ነበር፡፡ ጉዳዩን የተናገሩት ግን የፓርቲው ከፍተኛ ተጽእኖ ፈጣሪ እነደመሆናቸው መጠን የመለስ አለመኖርን ክፍተት ለመረዳት የመረጃ እጥረት አለባቸው ተብሎ አይታሰብም፡፡ በሌላ በኩል ክፍተቱ ቢኖርም እንኳን፣ አቦይ ስብሓት ክፍተት አለ ብለው እንዲሉ መጠበቅ የዋህነት ነው፡፡

የአቶ መለስ ስልጣን ለረዥም ዓመታት ተለጥጦ መቆየቱም ብዙም የሚያወያይ እና የሚያከራክር አይደለም፡፡ በተለይ በተለይ በአሁኑ ወቅት በዋናነት የሚታዩትን የመንግስት ዋና ዋና ዕቅዶች (የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን እና የግድብ ግንባታውን ጨምሮ) አርቃቂ እና ባለቤት እንደሆኑ ይነገራል፡፡ የዚህ "ከአቅም በላይ የተንጠራራ" ዕቅድ አፈጻጸምን ያለሳቸው ማሰብ ትንሽ አስቸጋሪ ይመስላል፡፡ በተለያዩ ሚኒስትር መስሪያ ቤቶች አሠራር እና አፈጻጸም ላይ ጠንካራ እጃቸው በተደጋጋሚ ይገባል፣ ለውሳኔም ይቃጣሉ ተብለው የሚታሙት አቶ መለስ ከቤሮክራሲው መጥፋታቸው የሚታይ ክፍተት መፍጠሩም የማይቀር ነው፡፡ ለኢኮኖሚያዊ ትንታኔው፣ለመንግስት ስህተቶች መከላከሉ፣ ለልማትና ጥፋቱ ማብራሪያ ባለፉት አሥር ዓመታት በብቸኝነት ብቅ የሚሉት መለስ አለመኖራቸው፣ "የፋጡማን አለመኖር" ያህል ነው ብሎ በቀላሉ ማለፍ ለማንም የፖለቲካ ንቃት ላለው ኢትዮጵያዊ የሚዋጥ አይመስልም፡፡ ሌላው ቀርቶ በሕጋዊው የፍትህ ስርዓት የማይፈቱ የሚመስሉ ጉዳዮችን የመጨረሻ እልባት የመስጠት ድረስ ስልጣን ያላቸው አቶ መለስ መሆናቸው እየታወቀ ይህ ለዓመታት የተገነባን "ሁሉ ያገባኛል" ስብዕና አለመኖር የሚፈጥረው ክፍተት የሚካድ አይደለም፡፡

ታዲያ ይህንን ሁሉ ጫና ጠቅልለው የያዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ድንገት ሳይዘጋጁ እና ሳያዘጋጁ ከመድረኩ ድንገት ድርግም ማለታቸው ከወደፊቱ የአገሪቷ መጻኢ ጊዜ ጋር ቢገናኝ ስህተት ነው ማለት አይቻልም፡፡

### ሕገ መንግሥታዊው መንገድ

አንዳንዶች የኢፌድሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 75/1/ለ ‹ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖር ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤› የሚለውን እየጠቀሱ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን ቀጣዩ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርገው ያስባሉ፤ በዚሁ አንቀጽ መሠረት ሕገ መንግስቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሌሉበት ሁኔታ ሁሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተክተው እንደሚሰሩ ያናገራል፡፡ የዚህን አንቀጽ ተፈጻሚነት ደረጃ በግልጽ በሕገ መንግስቱ ባይቀመጥም ጉዳዩን በተመለከተ የተሻለ የሕግ አግባብ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው የአገሪቱ ሕግም ይህ ብቻ ነው፡፡ በተቃራኒው ይህንን የሕገ መንግስቱን አንቀጽ በሚነካ እና ክፍተቱን መጠቀም በሚመስል መልኩ የኀወሓት "የነፍስ አባት" አቦይ ስብሓት ነጋ በጉዳዩ ዙሪያ ስልጣኑን ለፓርላማው የሰጠ እና አዲስ ምርጫን ያገናዘበ የ"ተረጋጉ!" መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ አቦይ በዚሁ የአሜሪካ ድምጽ የሬዲዮ ጣቢያ ንግግራቸው የአቶ መለስ መኖር እና አለመኖር

የሚያመጣው ችግር እንደሌለ እና ተተኪ መምረጥ የፓርላማው ኃላፊነት መሆኑን ነው አጽንኦት ሰጥተው ነው የተናገሩት፡፡

ጥቂቶች በተጻፈው (የቀረበ) ሕግ መሰረት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን የወደፊቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናሉ ብለው ቢገምቱም ብዙዎች ግን ይህ የገዢው ፓርቲን ብሎም የኅወሓትን ባሕሪ የማያውቁ እና ያልተረዱ የዋሆች ግምት ነው ብለው ይተቹታል፡፡ እንደ ተቺዎቹ አባባል ከሆነ በቀድሞው የኅወሓት ክፍፍል ወቅት ሚናቸው ከደጋፊነት ባልተሻለ ሁኔታ የነበረው አባል ፓርቲዎች አሁን በአጠቃላይ የኀወሓት የበላይነት የሚታይበትን ሁኔታ ተቀይሮ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ ለአቶ ኃይለማርያምም ሆነ ለሌላ አባል ፓርቲ አመራር ይሰጣል ማለት ዘበት ነው፡፡በዚህ ሐሳብ የሚስማሙት ተቺዎች ተከታይ ቦታውንም ሆነ ውስጣዊ ትግሉን ወደ መገመት ሲመጣ ነገሩን ከውጭ በማየት ብቻ ተከታዩ የመሪ ምርጫ ምን እንደሚመስል ለመገመት ይቸገራሉ፡፡

## የአቦይ ስብሃት መንገድ

በፓርቲው ውስጥ ባላቸው ቦታ እና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለሚዲያ ቅርብ በመሆን የሚታወቁት አባት ስብሃት ነጋ የስልጣን መተካቱን ነገር አስመልክተው የሰጡት ምላሽ የማይሆን፣ የማይባል እና ሌሎች የአጋር አመራሮችን ገሸሽ ያደረገ የሚመስል አካሄድ ይታይበታል፡፡ አቦይ ከየት እንዳመጡት በማይታወቀው ሕግ ተመስርተው አብላጫ ድምጽ ያለውን ፓርቲ አዲስ እጩ የማቅረብ ስልጣን ሰጥተው ሲያበቁ የተለዩ ሐሳቦች አፍልቆ የማያውቀውን ፓርላማ የአዲሱ ጠ/ሚኒስትር መራጭ ያደርጉታል፡፡ ነገሩ ጠንካራ የሕግ ድጋፍ ያለው ባይመስልም ከእስከዛሬው የኢህአዴግ/ኅወሓት ህጋዊነት ባህሪይ በመነሳት በዚህ መንገድ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሊመጣ የማይችልበት ምንም ምክንያት የለም ብሎ መደምደምን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

በእርግጥ የአቦይ ስብሃት መንገድ ተግባራዊ ለመሆን የውስጠ ፓርቲ ትግሉ እና የእርሳቸው የኃይል ሚዛን ወሳኝ ጉዳዮች ይሆናሉ፡፡

## የሕወሓት ምናልባትም የኢሕአዴግ መንገድ

ይህ መንገድ ለመገመት የሚከብደው ጉዳዩ የውስጠ ፓርቲ ትግል ስለሆነ ብቻ ሳይሆን እንደ ከዚህ በፊቶቹ ታውቀው የወጡ ልዩነቶች በፓርቲው በቅርብ ጊዜ ባለመታየቱም ጭምር ነው፡፡ ሁሉም ውሳኔ እና አመራር ከላይ ወደ ታች በሆነበት የኢሕአዲግ አሰራር ግለሰቦች ለአመራር ያላቸውን ፍላጎት እና ዝግጁነት የማሳየት ዕድል አልነበራቸውም፡፡ በተሻለ አፈፃፀም የሚታወቁትም ቢሆኑ "ከአቶ መለስ ጋር መሥራትን መባረክ ነው" እያሉ ወደሰብአዊ አምልኮ በተጠጋ አድንቆት ከማደናነቅ ውጪ ራሳቸውን በተመጣጣኝ ቦታ ያለ ሥራ አስፈጻሚ እና ዕጩ ተተኪ አድርገው ያቀረቡበት ጊዜ የለም፡፡ በዚህ የአመራር ክፍተት ላይ የውስጠ ፓርቲ ቁርሾ እና "ከእኛ በላይ ለአሳር" አስተሳሰብ ተጨምሮበት የሚቀጥለውን ተተኪ መገመቱን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

ከቅርብ ሰዎች ተገኙ የተባሉት መረጃዎችም የሚያሳዩት ገና ካሁኑ ለሁለት የተከፈሉ እና ለቦታው ራሳቸውን ያጩ ጎራዎች መኖራቸውን ብቻ ነው፡፡ የተባለው መረጃ እውነት ሆኖ የትኛውም ውስጠ ፓርቲ ቡድን ቢያሸንፍ እንኳን አዲሱ እጩ ወደ ስልጣን የሚመጣበትን መንገድ የፓርቲዎቹ ሕግጋቶች የሚመልሱት ጥያቄ አይመስልም፡፡ የፓርቲ መሪዎቹን የቆይታ ጊዜ የማይገድብ የፓርቲ ሕገ ደንብ እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ የሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት ምን ዓይነት ስልቶች እንደሚመጡ መገመት አስቸጋሪ ነው፡፡ ጉዳዩ በተለያየ አተያይ የተወሳሰበ ቢመስልም የትኛውንም ነገር ያስከፍል እንጂ የኅወሓትን የፓርቲ የበላይነት አረጋግጦ የሚጠናቀቅ እንደሚሆን የብዙዎች ግምት ነው፡፡ በእርግጥ ይህ አዲስ መሪ የማምጣት ትግል የውስጠ ፓርቲ መረጋጋት ላይም የራሱን ተጽዕኖ መፍጠሩ የማይቀር ነው፡፡ አቶ መለስ ለዓመታት የገነቡትን እምነት እና በየሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ቢሮ መግለጫ ላይ ሳይቀር የሚከሰት ስብእና ማጣት፣ የአባላትን በራስ መተማመን መጉዳቱ የማይቀር ነው፡፡ በተለይ በተለይ እንደኢሕአዲግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አባላት ባሉበት ፓርቲ ውስጥ የመረጋጋቱ ሁኔታ ጊዜ የሚወስድ ይሆናል፡፡ ይህ የውስጠ ፓርቲ መረጋጋት እና መለስን የሚተካ አዲስ ምሰሶ የማቆም ሥራ ከፓርቲው ውጪ ለሆኑ የፓለቲካ እንቅስቃሴዎች አዲስ ዕድል ይከፍት ይሆናል የሚሉ ግምቶችንም ፈጥሯል፡፡

## የተቃዋሚዎች እና የሌሎች የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች መንገድ

በደካማነቱ እና በተስፋ አስቆራጭነቱ የሚታማው የተቃዋሚው ጎራ በዚህ አዲስ ምዕራፍ ውስጥ የሚኖረው ሚና ብዙም ከፍተኛ ላይሆን ይችላል፡፡ በተለይ በተለይ በማኅበረሰብ ደረጃ በምርጫ ዋዜማ ላይ የሚገናኙት (ለዚህ ምክንያቶቹ ብዙ ቢሆኑም) 91 ፓርቲዎች በእንደዚህ ዓይነት የአመራር ክፍተት ወቅት የሚኖራቸው ሚና ላይ ዝግጅት አላደረጉም ብሎ መደምደም ከባድ አይሆንም፡፡ የፓርቲዎች ከሕዝቡ ጋር በቅጡ አለመገናኘት እና አለመተዋወቅ ለስልጣን ሽግግሩ ከሚታሰቡት አካላት መካከል የመጨረሻዎቹ አድርጎዋቸዋል፡፡ የራሳቸውን ህልውና በማቆየት እና ባለማቆየት ላይ የተጠመዱት እነዚህ አካላት የተሻለ የስልጣን ዕድል ያለው አካል የሚመጸውታቸውን የፖለቲካ ምህዳር ከመጠበቅ ውጪ አማራጭ ያላቸው አይመስሉም፡፡

ይህ የአመራር ክፍተት አሉ እየተባሉ የሚጠሩትን አገር ውስጥ ከሚገኙት ፓርቲዎች ውጪ ያሉ የተለያዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችም ቢሆን፣ አሁን ባላቸው በግልፅ የማይታይ እና የማይነገር የፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ ተመርኩዞ ወደ ላይ ብቅ ይላሉ ብሎ ማሰብ ዘበት ነው፡፡ (ክፍተቱ ለተለያዩ እንቅስቃሴዎች የተወሰነ ዕድል መስጠቱ የማይቀር ቢሆንም!)

## ድኅረ መለስ

አገሪትዋ አሁን ካለችበት የፓለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና ተያያዥ አጣብቂኝ ሁኔታዎች ላይ የአቶ መለስ መጥፋት ተጨምሮበት ጉዳዩን ከድጡ ወደማጡ እንዳያሸጋግግረው የሰጉ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ በቀጣዩ አመራር ወቅት አሁን ትታይ የነበረችውንም የፓለቲካ ምህዳር ጠራርጎ ማጥፋት አዝማሚያ አሁኑኑ እየታየ ነው የሚሉ ክርክሮችም እየበረከቱ ነው፡፡ ቁርጡ ሳይታወቅ ገና፣ ከሰሞኑን በፍትህ ጋዜጣ ላይ የተወሰደው ግራ የሚያጋባ “ሕጋዊ” እርምጃ የድኅረ መለስ ውጤት ተደርጎ መወሰድ ጀምሯል፡፡ በቅርቡ የተወሰደውንም የሙስሊሞችን ጥያቄ በኃይል የመፍታት አዝማሚያ የዚሁ ምሳሌ ሊሆን ይችላል፡፡

ጠቅልሎ ስልጣንን የማስተዳደር ክህሎት የማጣት ችግር የሚመስለው ይህ እርምጃ ለካ ጠቅላይነት ስልጣን ብቻ ሳይሆን ክህሎትም (የአምባገነንነት ክህሎት እንበለው እንዴ?) የሚጠይቅ ነው የሚያስብል ሆኗል፡፡ አዲሱ አመራር ቢያንስ ሁሉን አቀፍ ስልጣን መያዙን እስኪያረጋግጥ እና እስኪለማመድ ድረስ እንኳን ቢሆን ተመሳሳይ እርምጃዎች የማይበረክቱበት ምንም ምክንያት የለም፡፡

በአቶ መለስ፣ በቋሚነት ያለመኖር ዋና ተግዳሮቱ ወይም ዕድሉ የሚሆነው መጀመሪያ ለፓርቲው ለራሱ ለኢሕአዴግ ነው፡፡ ፓርቲው የአቶ መለስን አለመኖር እንደ ዕድል በመጠቀም ቢያንስ የሚታማበትን የአንድ ግለሰብ አምባገነንነት እና አመራር ወደ ቡድን አመራር እና እውነተኛ መተካካት ሊቀይረው የሚችልበት እድል አለ፡፡ ይህንን ዕድል በሚገባ ከተጠቀመ ኢሕአዲግ ቀስ በቀስ የቡድን ሐሳቦችን ወደማንሸራሸር እና የሐሳብ ልዩነቶችን ወደሚያስተናግድ ፓርቲነት ሊቀየር ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ በፓርቲው ውስጥ ታፍነው የቆዩ ሐሳቦችን ለንግግር እና ለትግበራ የማምጣት ዕድል ይኖረዋል፡፡

በተቃራኒው ከፓርቲው የቀድሞ ልምዶች በመነሳት የዴሞክራሲ ባህሉ ዝቅተኛ በመሆኑ ጭራሽ ወደባሰ የውስጠ ፓርቲ ችግር ባይገባም እንኳን ባለበት ሁኔታ የመጨረሻ ውጤቱ የጠቅላዩን መቀየር ብቻ ይሆናል የሚሉ ግምቶች አሉ፡፡ ምናልባት የመለስ ግለሰባዊ ግዙፍነት ከዚህ በባሰ ሁኔታ ተጽዕኖ አሳርፎ ከነበረ ደግሞ ፓርቲውን የተለየ ሐሳብ እያራመዱ፣ በአቶ መለስ ምስሶነት ጥላ ስር ብቻ የነበሩ አካላት ከአቶ መለስ አለመኖር ጋር ተያይዞ ራሳቸውን በማግለል የአዲስ ቡድኖች የመፈጠር ዕድልም ሊኖር ይችላል የሚሉ መላምቶች በስሱ ይሰማሉ፡፡ (ምንም እንኳን የዚህ ሁኔታ መፈጠር ዕድል ጠባብ ቢመስልም፡፡) ኢሕአዲግ የአቶ መለስ ስብዕና ብቻ ከፓርቲው ጋር ያጠጋጋቸው መለስን አትንኩብን ፓርቲውን ግን እንደፈለጋችሁ ብለው መለስ ላይ እምነት ያሳደሩ ከፓርቲ ፓለቲካ ውጪ ያሉ አካላትን ይዞ የመቀጠሉ ጉዳይም ሌላው የድኅረ መለስ ጊዜ ጥያቄ ነው፡፡ ብዙዎቹ እንደሚገምቱት ጉዳዩ በውስጠ ፓርቲ ትግል ጠቅላይን ለጠቅላይ በመተካት ብቻ የኢሕአዲግን ግዙፍነት በመጠበቅ ከተጠናቀቀ የወደፊትዋ ኢትዮጵያ አዝማሚያ ለመሻሻል እድል የሌለው ሊመስል ይችላል፡፡

በዚህ መሀል፣ እንደሕዝብ - የአቶ መለስን የውጪ ተክለ ስብዕና የሚተካ ጠንካራ ሰው ማምጣት የሚጠበቅበት አዲሱ አመራር በዕድሉ ተጠቅሞ የፓርቲውን የዲሞክራሲ ባህል መለወጥ ካልቻለ የአቶ መለስን ዓይነት ሌላ ሰው፣ በዘዴ ሁሉን የመጠቅለል ክህሎት እስኪያዳብር ድረስ ‹‹የአንባገነንነት መለማመጃ ልንሆን ይሆን እንዴ?›› የሚል ጥያቄ ከወዲሁ ማንሳቱ አስፈላጊ ነው፡፡

# ባልቻን ፍለጋ

የመድፍ አረር አካባቢውን አጥኖታል፣ ጎራዴ ይብለጨለጫል፣ የደም ወንዝ ይጎርፋል። አዎ ይህ ጥቁር ጦር ቀላል እንዳልሆነ እየታየ ነው። ያ የበጋ ሰማይ ደምን አየ መሰለኝ ክፉኛ ቀልቷል። በቀላ ሰማይ ስር ጦርን እንደ ብዕር ደምን እንደ ቀለም አድርገው ጀግኖች ታሪክ ይፅፋሉ። ታሪክን በመክተቡ መሀል ለጥቁሮቹ ጀግኖች አንድ አስደንጋጭ ነገር አጋጠማቸው። ከመሪዎቻቸው አንዱ የሆኑት ከጠዋቱ 3 ሰዓት ገደማ ፊትአውራሪ ገበየሁ ተሰው። ወላድ በድባብ ትሂድ ገበየሁን ያጣ ጦር አልተበተነም ባልቻን የሚያክል መሪ አግኝቷልና። ደጃዝማች ባልቻም መድፉን እንደ ቀላል ያገላብጠው ጀመር። ይሄን የታዘበ አዝማሪም።

*<<ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ፣*
*መድፍ አገላባጭ፣ ብቻ ለብቻ።>>*

ብሎ ተቀኘ። ምስጋና ለባልቻ፣ ምስጋና ለገበየሁ ያ ጥቁር ጦር ጠላቱን ድል ነሳ፣ አዲስ ታሪክም ፃፈ። የካቲት 23/1888 ዓ.ም አድዋ ኢትዮጵያ።

## ዛሬ ገበየሁ

አዎ እነ ገበየሁ እነ ባልቻ ታሪክ ከጻፉ ድፍን አንድ ምእተ ዓመት ሊሞላቸው 5 ዓመታት ብቻ ነው የቀረው ወቅቱም 1983 ዓ.ም ውልደቱ በታሪካዊዋ አድዋ የሆነ፣ ራሰ በሀ፣ ቀጭን-አጭር መሪ ነገሰ ኢትዮጵያን ሊያስተዳድር። የቀድሞው ፕሬዘደንት ያሁኑ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ። መለስ እንደ ገበየሁ ከፊት ሆነው ህዝቡን ወደ ድል ወይስ ወደ ገደል መሩት?ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተለያዩ መልሶች ናቸው የሚሰጡት።
ባንድ ወገን ‹‹ነፃነትን ያለገደብ ሰጠ፣ ድንቅ እና ውብ ህገ-መንግስት ለህዝቡ አስረከበ፣ ሀገሪቱን በልማት ጎዳና ትንዝ ዘንድ አረር በማይሸትበት፣ጎራዴ በማይብለጨለጭበት የልማት መንገድ መርተዋታል፣ ማን እንደ እርሳቸው? ማን እንደ መለስ?›› በማለት ‹‹ወዲ ወሊደሙ መለስ በልዩ›› (ልጅ ወልደሽ ስሙን መለስ በይው) እያለ መለስ ለህዝቡ ከመሪም በላይ ናቸውን ሲሰበክ፣ ‹‹ይቀጥል ሊቁ ሰው ጥበብ የተካነው›› እያለ ንጉስ ሆይ ሽህ ዓመት ይንገሱ፣ ዙፋንዎት ይፅና፣ አመራርዎት ይቅናን ይዘምራል።

በሌላ ወገን ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በማይወዳት መሪ እየተመራች ነው፣ 'ባንዲራን ጨርቅ' ያለ የቅርስን ዋጋ ያሳነሰ፣ 'ኮሮጆ የሚያስገለብጥ'፣ ህግ ደንታ የማይሰጠው ህግ ሰሪ ህግ አፈራሽ በአጠቃላይ ምሉዕ በኩሉሄ የሆነ መሪ ከቶ ለምኔ? እርሱ የወረደ እለት ስለቴን አስገባለሁ፣ እሱ የሞተ እለት ፈጣሪ የህዝቡን እንባ አይቷል ማለት ነው እያለ ይተቻል።

አዎ ! ዛሬ 'ገበየሁ' ፈተናቸው ብዙ ነው። አዎ ! ዛሬ 'ገበየሁ' 'ጠላትን' ለመዋጋት ጦር ሜዳ መሄድ አላስፈለጋቸውም ያሉበት ቦታ ድረስ ይሰማቸዋል የመድፍ ጩኸት፣አይናቸው ላይ ያብረቀርቃል የጎራዴው ስለት፣ በዓይነ ህሊናቸው ይታያቸዋል ደም የቀደደው ቦይ ። በርግጥ 'ገበየሁ' ዛሬ ግለሰብ ብቻ ሳይሆኑ ስርዓትም ናቸው ቢባል አያስገርምም። በርግጥም መድፉን ብቻቸውን አገላብጠውታል።

የሆነ ሆኖ በአሁኑ ወቅትም 'ገበየሁ' የት እንዳሉ በትክክል ማወቅ አልተቻለም። ጓዶቻቸው ‹‹ሥራ ጫና ነበረባቸው አሁን እያረፉ ነው›› ሲሉ ህዝቡ ‹‹ድሮስ ብቻቸውን ህዝብን የሚያክል ነገር እያገላበጡ ምነው አይደክሙ?›› ይላል። እንዲሁም የ አለፉ ዘመናትን ሲያስታውስ።

*ደከመኝ ሰለቸኝ፣ እረፍት የማያውቀው፣*
*አብዮታዊ መሪ፣ ጓድ መንግስቱ ነው።*

ተብሎ ለመንግስቱ-ኮመኒስቱ የተዘመረውን መዝሙር ይታወሰዋል።

በተቃራኒው ደግሞ ‹‹አይ 'ገበየሁ' ለዘላለሙ አሸልበዋል የስልጣን ሽኩቻውም በበታቾቻቸው መካከል ጡፏል›› የሚል መረጃ ይሰማል።

የትኛው መረጃ እንደሚጨበት ማወቅ አልተቻለም። ለማንኛውም ጨዋታችን እንዲሞቅ እንዲህ እናስብ። ከእንግዲህ 'ገበየሁ' በህወይት ኖሩም አልኖሩም ወደስልጣን አይመለሱም ስለዚህም የገበየሁን ተኪ 'ባልቻን' እንፈልግ።

## 'ባልቻን' ፍለጋ

'ገበየሁን' ይተካ ዘንድ 'ባልቻን' እንፈልጋለን፡፡ መጀመሪያ 'ባልቻ' ሊኖርባቸው የሚችሉትን ቦታዎች እናስስ እስኪ፡፡

1. *- 'በመስዋዕትነት ከተገኘው ሕገ መንግሥት'*

ከሌሎች ሀገሮች ህገ መንግስቶች በተለየ የኢፌድሪ ህገ-መንግስት ገበየሁ ቢሞት የባልቻ መገኛ የት እንደሆነ በግልፅ አይጠቁምም፡፡ ይልቅስ ህገ መንግስቱ ገበየሁ ‹በማይኖር ጊዜ› በሚል ጥቅል አጠራር ምክትሉ 'የባልቻን' ድርሻ ይወርሳል ይላል፡፡ ይህ ህገመንግስታዊ አንቀፅ ለትርጉም ክፍት ነው፡፡ 'ገበየሁ' ከስራ ለአጭር ጊዜ ሲርቅ ነው ብቻ ነው ተብሎ ሊተረጎምም ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አይ 'ገበየሁ' በሞተም ጊዜ ተክቶ ሊሰራ ይችላል ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ እንግዲህ 'ባልቻን' ከህጋዊ መስመር አገኘን የሚሉም ከሁለተኛው ትርጉም የተነሳ መሆን አለባቸው፡፡ አሁን ካለው ድባብ በመነሳት ይህ የመሆን ዕድሉ ዝቅተኛ ይመስላል፡፡ ቢሆን እንኳን እንደ 'ገበየሁ' ህዝቡን ብቻውን ማገላበጡ ያጠራጥራል፡፡

2. *- 'ጀኔራል ባልቻ'*

እነሆ 'ባልቻን' ፍለጋ የጦር ካምፕ ውስጥ ነን 'ባልቻን' በግልፅ ለማየት ግን አልተቻለም፡፡ በርግጥም 'ባልቻን' ከጦር ካምፕ የምናገኘው ከሆነ ግን ጉዳዩ ያስፈራል፡፡ ቢያስፈራም ግን 'ባልቻ' በጦር ካምፕ ውስጥ መሽጎ ሊሆን ይችላል፡፡ የተገኘ እለት 'ጀኔራል ባልቻ' ሀገሪቱን በአንድ እግሯ አቆሚት መባሉ የማይቀር ነው፡፡

3. *- 'ባልቻን' ከቤተ መንግስት*

ሌላው ጥርጣሬያችን 'ባልቻን' እዛው 'የገበየሁ' ቤተ-መንግስት ውስጥ ልናገኛቸው እንችላለን የሚለው ነው፡፡ አይሆንም አይባልም፡፡ ሴቱ-ወንዱ የቤተ መንግስት ባለሟል ድንገት ‹‹ባልቻ ነኝ እኮ፤ስለምን ርቃችሁ ትፈልጉኛላችሁ፤ እዚሁ ቤተመንግስት ነበርኩ እኮ›› ሊል ይችላል፡፡ ‹‹ሹመት በተርታ፣ ስጋ በገበታ››ን እየተረተ ‹‹የሞትንም እኛ፤ ያለንም እኛን›› እያለ ሊያሳውጅ ይችላል 'ባልቻ' ከቤተ መንግሥት፡፡

4. *-'ባልቻን' ከምድረበዳ*

በርግጥም 'ባልቻን' ከምድረበዳ ያልነው 'ከተቃዋሚው' ጎራ ይመጣ ይሆን የሚለውን ግምታችን ነው፡፡ ዲያስፖራ ተቃዋሚው መግለጫ፣ ኮምኒኬ ወ.ዘ.ተ በማውጣት ዱብ ዱብ እያለ እራሱን እያሟሟቀ ይገኛል፡፡ መቸም 'ባልቻ' 'አትላንቲክን' ወይም 'ሚድትራኒያንን' አለዚያም 'መረብ' ወንዝን አቋርጦ ሊመጣ ይችላል ማለት ከባድ ነው! ኧረ በጣም ከባድ ነው፡፡ በሌላ ጎኑ ሀገር ውስጥ ያለውን ተቃዋሚ ስናይ አሁን ባለበት ሁኔታ ጀኔራሎቹ፣ ይሆኑ ወይስ ከቤተ መንግስት እያለ ከመገመት ውጭ ያው በምድረበዳ እየተንከራተተ ነው፡፡ እናም አንድ ነገር ላይ እርግጠኛ መሆን እንችላለን አዎ 'ባልቻን' በምድረ በዳ መፈለግ ከንቱ ልፋት ነው፡፡

የሆነ ሆኖ 'የገበየሁ' ዘመን እያለቀ ይመስላል፡፡ 'የባልቻን' መምጫ ግን ማወቅ አልተቻለም፡፡ ቢመጣስ እንደ 'ገበየሁ' ብቻውን ህዝቡን ያገላብጠዋል የሚለውም ሌላ ጥያቄ ነው፡፡

# የመለስ ሞት ለምክር ቤቱ ምኑ ነው?

የኢፌድሪ ሕገ መንግስት ከፀደቀ የፊታችን ህዳር 29 ዓ.ም 17ኛ ዓመት የልደት በዓሉን ያከብራል፡፡ ይህ ኢትዮጵያ ካየቻቸው ቀዳሚ ሕገ መንግስቶች በተሻለ መጠን ሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የሚቸረው እና የሀገሪቱ የበላይ ሕግ፤ ከያዛቸው አንቀፆች መካከል የመንግስቱን አይነት የሚደነግገው ክፍል በአንቀፅ 45 ላይ ምክር ቤታዊ ዲሞክራሲ (Parliamentarian Democracy) እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ አያይዞም የተዘረጋው ስርዓት ፌደራላዊ እንደሆነና፤ ይሄም አወቃቀር በ9 ክልሎች እና በአንድ ፌደራል / ማዕከላዊ መንግስት የተደለደለ መሆኑን ያስቀምጣል፡፡ እንዲሁም የፌደራሉ ምክርቤት ሁለት የተለያዩ አካላትን ያቀፈ እንደሆነ ገልፆ፤ እነዚህም አካላት ዋነኛ ተግባሩ ሕግ ማውጣት የሆነውን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ዋነኛ ተግባሩ ሕገ መንግስቱን መተርጎም የሆነውን የፌደሬሽን ምክር ቤት ናቸው፡፡

በማስከተልም ከሁለቱ የፌደራሉ ምክር ቤቶች አንዱ የሆነው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ‹‹…የሥራ ጊዜ ከመስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ሰኞ እስከ ሰኔ ሰላሳ ነው›› በማለት የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 58 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሰረት የፊታችን ሰኞ መስከረም 28/2004 ዓ.ም የኢፌድሪ ሕገ መንግስት ከፀደቀ ወዲህ ለ4ኛ ጊዜ የተመረጠው ምክር ቤት 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑን ይጀምራል ማለት ነው፡፡

አሁን ሥራ የሚጀምረው ምክር ቤት ከቀዳሚዎቹ ምክር ቤቶች የሚለየው ባለፉት 4 ምክር ቤቶች አባል የነበሩት እና በምክር ቤቱም ጉልህ ሚና የነበራቸውን የቀድሞውን የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ሳያካትት መከፈቱ ይሆናል፡፡ መለስ ለምክር ቤቱ፣ ምክር ቤቱ ለአቶ መለስ ምን እና ምን ነበሩ?

## ምክር ቤቱ ያለ መለስ፤ ምን ሆነ?

በኢፌድሪ ሕገ መንግስት መሰረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ካሉበት ዋነኛ ግዴታዎች መካከል ‹‹ስለ ሀገሪቱ ሁኔታ፣ በመንግስት ስለተከናወኑ ተግባራትና ስለወደፊት ዕቅዶች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በየወቅቱ ሪፖርት ማቅረብ›› አንዱ ነው፡፡ አቶ መለስም በ17 ዓመት የጠቅላይ ሚኒስትርነት ዘመናቸው (የኢፌድሪ ሕገ መንግስት ከፀደቀበት ጊዜ ወዲህ) ይሄን ተግባር ሲያከናውኑ ነበር፡፡ ነገር ግን የጤናቸው ሁኔታ ጥሩ አይደለም ተብሎ ከአደባባይ ከጠፉበት ካለፈው ሰኔ አጋማሽ ጀምሮ ህልፈታቸው በመንግስት እስከ ተነገረበት የነሃሴ ወር አጋማሽ ድረስ ከዚህ ተግባራቸው ርቀው ነበር፡፡

በዚህም መሰረት በሕገ መንግስቱ የተቀመጠው እና አስገዳጅ የሆነው የምክር ቤቱ የስራ ማጠናቀቂያ ሰኔ ሰላሳ ሊከበር አልቻለም ነበር (የእንግሊዘኛው የሕገ መንግስቱ ቅጅ አንቀፅ 58 ንዑስ ቁጥር 2 The annual session of the House *shall*… end on the 30th day of the Ethiopian month of Sene በማለት አስገዳጅ እንደሆነ ይነግረናል)፡፡ ምንም እንኳን ምክር ቤቱ የሥራ ጊዜየን ያራዘምኩት ከእርሳቸው መታመም ጋር በተያያዘ አይደለም ቢልም፡፡ አቶ መለስ የሌሉበት ምክር ቤት የምክር ቤቱን የሥራ ዘመን ማጠናቀቂያ ሕገ መንግስቱ ካስቀመጠው ቀን በላይ በማራዘም፤ የሕገ መንግስት ጥሰት ፈፅሟል ይላሉ የቀድሞው የኢትዩጵያ ፕሬዘደንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፡፡

ሌላው ምክር ቤቱ ያለ መለስ ምን የተለየ ነገር አደረገ? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው በምክር ቤቱ የ17 ዓመት ታሪክ ውስጥ የአስቸኳይ ስብሰባ የተጠራው ሁለት ጊዜ ብቻ ሲሆን፤ ሁለቱንም ጊዜ ባሳለፍናቸው ሶስት ወራት ውስጥ ነው ያካሄደው፡፡ የመጀመሪያው የቴሌኮምንኬሽን አዋጁን ለማፅደቅ፣ በሀምሌ ወር 2004 ዓ.ም አጋማሽ ሲሆን፤ ሁለተኛውን ደግሞ መስከረም 11/2005 ዓ.ም የአዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር እና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሹመት ለማፅደቅ ነበር፡፡ ይሄም ምክር ቤቱ ከመለስ በኋላ ምነው አስቸኮለው? እንድንል ይጋብዘናል፡፡

## Economics 101ን ማን ያስተምራል?

አቶ መለስ ዜናዊ በሞት በመለየታቸው የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ ብቻ ሳይሆን አስረክበው ያለፉት፤ የምክር ቤቱን የመሪነት ሚናም ነው፡፡ መለስ በምክር ቤት ውስጥ በምጣኔ ሀብት ጉዳዮች ላይ አብዝተው ተከራካሪ እና ዝርዝር ማብራሪያዎችን ሰጭ እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ በተለይም በሶስተኛው ሀገር ዓቀፍ ምርጫ የተቃዋሚዎች ቁጥር በእጅጉ ከፍ ማለቱን ተከትሎ፤ መለስም የሚጠየቁት ጥያቄ እና ፈተናቸው በዛው ልክ ከፍ ብሎ ነበር፡፡

በሀገሪቱ የኑሮ ውድነት አሳሳቢ እየሆነ ነው፣ የዋጋ ግሽበትም ጣሪያ ነክቷል መንግስትዎ ምን ሊያደርግ አስቧል? ተብለው ሲጠየቁ፡፡ ማብራሪያቸውን የሰዋሰው ግድፈት በማረም ‹‹Fiscal እንጅ Physical አይደለም›› በማለት ይጀምሩ ነበር ኢኮኖሚስቱ መለስ፤ ለትዝብት በሚዳርግ መልኩ፡፡ አስከትለውም አዳም ስሚዝን ምክር ቤት ውስጥ እንደ እማኝ በመጥራት ‹‹የነፃ ገበያ መርሆዎችን አልጣስንም፣ ስሚዝንም አላስከፋንም፣ የኢትዮጵያ ገበሬም ስሚዝን አንብቦ ባያውቀውም በፖሊሲዎቻችን አስተዋውቀነዋል›› እያሉ ማስተማር ከዘወትር የምክር ቤት ተግባሮቻቸው አንዱ ነበር፡፡

ስለ ፍላጎት እና አቅርቦት ግንኙነት ትንታኔ በማቅረብ መንግስታቸው በኢኮኖሚው ላይ ለተፈጠረው ችግር ተጠያቂ እንዳልሆነና ተጠያቂዎቹ ‘ዓለማቀፍ ኅብረተሰብ’፣ እንዲሁም ‘የመንግሥት ሌቦች’ ናቸው እስከማለትም ይደርሳል የመለስ የምጣኔ ሀብት ምክር ቤታዊ ገለፃቸው፡፡ስለ ምጣኔ ሀብት በምክር ቤት ቀርበው ማብራሪያ ከማብዛታቸው የተነሳ፤ ማብራሪያቸውን በቴሌቪዥን በቀጥታ የሚመለከተው ህዝብ በቅርቡ በኢኮኖሚክስ ዲፕሎማ ወይም የምስክር ወረቀት ማግኘቱ አይቀርም ተብሎ ይቀለድም ተጀምሮ ነበር፡፡

እንግዲህ መለስ ከዚህ በኋላ ኢኮኖሚክስ በምክር ቤት ያስተምሩ ዘንድ የህይወት ህግ አልፈቀደም፡፡ አዲሱ ተመራጭ ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ የአቶ መለስን ቦታ ተክተዋል፡፡ አቶ ሃይለማርያም የመለስን የምክር ቤት ትምህርት ይቀጥሉበታል( አላማየ የመለስን ውርስ ማስቀጠል ነው ማለታቸውን ልብ ይሏል) ወይስ አይቀጥሉበትም? የሚለው በጊዜ ሂደት የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡

## በፓርላማው ብቸኛ ተቆጭ

አቶ መለስ በምክር ቤቱ ተገኙ ማለት ምክር ቤቱ ሞቅ ያለ ድባብ አለው፣ ማለትም ሌላው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ መለስ በምክር ቤት ሲገኙ ‘ከተቃዋሚ ፓርቲዎች’ እስከ ‘ተራ ወንጀለኞች’፣ ‘ከአለማቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች’ እስከ ‘አለማቀፍ የሰብዓዊ ተሚጋች ድርጅቶች’፣ ‘ከኢህአዴግ አባላት’ እስከ ‘መንግስት ሰራተኛው’ ድረስ መለስ የማይወርፉት አካል አልነበረም፡፡

‘ቆሻሻ’፣ ‘ያበዱ ውሾች’፣ ‘ኪራይ ሰብሳቢ’፣ ‘የመንግስት ሌባ’፣ ‘እነ ጭር ሲል አልወድሞች’ ወ.ዘ.ተ እያሉ የስድብ መአት የሚያዥጎደጉዱት መለስ፤ ማንንም አካል ከመገላመጥ አይመለሱም ነበር፡፡ ይሄም አንዳንዶች የሰውየውን ስብእና በመጥፎ መልኩ እንዲመለከቷቸው አድርጓቸው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ አንድነት መድረክ የአመራር አባል እና የቀድሞው የኢትዮጵያ ምክር ቤት አባል የነበሩት ዶ/ር መረራ ጉዲና ‹‹አቶ መለስን እንዴት ያስታውሷቸዋል?›› ተብለው በአውስትራሊያው SBS ራዲዮ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ‹‹አቶ መለስን የማስታውሳቸው በፓርላማው ውስጥ ብቸኛው ተቆጭ እንደነበሩ ነው፡፡›› ብለዋል፡፡ ይህ እንግዲህ የመለስ የምክር ቤት ቆይታ ውርስ ነው፡፡ አቶ ሃይለማርያም በምክር ቤት እንዴት ይሆናሉ? ጊዜ ጌታ ነው መልሱ፡፡

## ‹‹ሳቃቸው መች ያስተኛል››

መለስን በምክርቤት የዋሉ እለት ምክር ቤቱ ከፍጥጫም ባለፈ ሳቅ እና ተረት ልማዱ ነበር፡፡ ከኤዞፕ እስከ አለቃ ገብረ ሀና ተረቶች በመለስ እያነሱ የምክር ቤት አባላትን ሲያስፈግጉ ነበር የሚውሉት፤ መለስ፡፡ በየመሃሉ የሚጥሏቸውም ቃላት ከማስከፋት አልፈው አንዳንዴ ፈገግም ያሰኛሉ፡፡ ባጭሩ መለስ በምክር ቤት የተገኙ እለት የምክር ቤት አባላት ሳቂታዎች ነበሩ፡፡

በምክር ቤቱ እንቅልፋቸውን በመተኛት ታዋቂ የነበሩ አንድ የምክር ቤት አባል ‹‹ምንድነው; ምክርቤት የገቡት ለመተኛት ነው እንዴ›› ተብለው ሲጠየቁ፡፡ ‹‹ኢጭ እንተኛስ ብንል ሳቃቸው መች ያስተኛል›› አሉ ተብሎ እስከ መቀለድም ተደርሷል፡፡ አቶ ሃይለማርያም እኒህን ‘እንቅልፋም’ አባል ከእንቅልፍ እየቀሰቀሱ ያማርሯቸዋል ወይስ ‘በሰላም እንዲተኙ’ ይፈቅዱላቸዋል? ጊዜን ማየት መልካም ይሆናል፡፡

# ስለ ግለሰብ ማሰብ ይብቃን!

አገራችን ወዴት እየሄደች ነው? ቀጣዩስ እጣ ፈንታችንስ ምን ይሆን? ይህ የሰማኒያ ሚሊዮን ሕዝብ ጥያቄ ነው። ጠቅላያች በእግዜር እጅ ከመያዛቸው በፊት፣ እራሳቸው የሃገሪቱ ብቸኛ ፈላጭ ቆራጭ ሆነው ገዝተውናልና ለኛ ለዜጎች በጊዜያችን የሚመጥነንና የሚገባን ነገሮችን ሳስብ ግን ለብዙዎቹ ጥፋቶች ተጠያቂ አደርጋቸዋለሁ፤ የስልጣን ጥም እና ሕዝብን (ያውም 80 ሚሊዮን) የግል ቤተ ሙከራ ማድረግ፣ ጊዜን እና የሃገርን ንብረት ያላገናዘበ የሙከራ አመራር እና አገዛዝ በፓለቲካውም ሆነ በሞያ ሃላፊነቶች ላይ የፈጀውን ይፍጅ በሚባልበት ሥራና ትክክለኛነቱን ጥናት ያላረጋገጠው እውቀት በመተግበር ለሀገር ሃብት መባከን ምክንያት እንደሆነ ሲያነታርክ ቆይቷል። ይህ አካሄድ አንዳንዶቹን ባለስልጣኖቻችንን ባለጠጋ አድርጎ እኛን (እና ሃገራችንን) በፀጉራችን ልክ በእዳ ዘፍቆናል።

በፊት በፊት በጎሳዎች መሃከል የሚፈጠሩ ግጭቶች የሚፈቱት በሽማግሌዎች ነበር ዛሬ ዛሬ መፍትሄ የሚያገኙት በፌዴራል ፖሊስ ሆኗል። (ይህንን የተለመደውን እና ውጤታማውን መፍትሄ በመተው መፍትሄ የሚመስለውን ጊዜያዊ ማደንዘዣ በሂደት እንደዚህ ዓይነት ግጭቶችን መፍትሄ የምናገኘው በጠመንጃ አፈሙዝ ብቻ እንዲሆን በማድረግ በመነጋገር ላይ የተመሰረተ የነበረው በአፈሙዝ ፍርሃት ብቻ እንዲሆን አድርጎታል።

## የአቶ መለስ መገኛ?

አቶ መለስ አልምተዋል፤ አቶ መለስ አጥፍተዋል ቢከፋም ቢለማም እኔ የእርሳቸው አድናቂ ባልሆንም የሚያደንቋቸውን ሰዎች ሐሳብ ግን ማኮስመን አልፈልግም። ቀጣዩ እጣ ፋንታችን ግን ሁላችንንም ሊያሳስበንና ነገሮችን በጥንቃቄና በማስተዋል ልንመለከት ይገባል። ሁላችንም እናልፋለን፤ አገራችን ግን አገር ሆና ትቀጥል ዘንድ ሁላችንም ግዴታ አለብን። ይህቺ አገር የምስኪኑም፣ የቱጃሩም፣ የሆዳሙም፣ የሃቀኛውም፣ የሁሉም ሃገር ነች ነገሮችን ግን ጥሩ ይሆኑ ዘንድ ሁላችንም ግዴታ አለብን።

ብዙ ነገር በምታስቡበት ሰዓት ከኛ በተሻለ መንገዶችን ሊመሩን የሚገቡ አዋቂዎች ፋና ወጊ መሆን ተስኗቸው የእግዜርን እጅ የራሳቸው አስመስለው ወደ አራት ኪሎ እያሳዩን ነው - መለስን ያስታመሙት እነርሱ ይመስል። ታዝበናል መፍትሄው ምን ይሁን?

በአንድ ሠው ላይ መንጠላጠል (ለሃገርም ሆነ ለድርጅት አዋጭ አይደለም)። መለስን እንደ ብቸኛ አዳኛችን አድርገን እርሳቸውን ብቻ ማሰብ እርሳቸው ራሳቸውን በገነቡበት መንገድ እንደመሸነፍ ነው፤ እንደርሳቸው ያለ ከወዴት ይገኛልም ብሎ መጠየቅ፣ እንደርሳቸው ያለ አምባገነን እንደ መናፈቅ ነው። አሁንም ስለግለሰቦች ከማሰብ መውጣት መጀመር ያለብን ይመስለኛል። ማሰብ ያለብን ነጻ መሆን ስለሚገባቸው የፍትህ አካላት፣ ስለ ገለልተኛ ምርጫ ቦርድ እና በመፈቃቀድና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ አገርን እና ሕዝብን እንጂ ግለሰብን አይደለም። እነዚህ እና የመሳሰሉት ተቋማት ብቃታቸውና ነጻነታቸው ከተረጋገጠ የመምራቱ ጉዳይ ክልሎች በዙር እንኳን ቢያደርጉት መሠረቱ የማይናድ ይሆናል በግለሰብ ላይ ያልተመሰረተ ነውና።

የሰሞኑን ሁኔታ ስታዘበው፣ የሃገራችን ሁኔታ መስቀለኛ መንገድ ላይ ያለ ይመስለኛል። ነገሮች እየተከናወኑ ያሉት በሕግ ሳይሆን በጠመንጃ ነው። ለዚህም ምሳሌ የሚሆነው የፍትህ ጋዜጣ በሰበብ አስባቡ መታገድና የሙስሊም ኢትየጵያውያን ሰላማዊ እንቅስቃሴ መሪዎች መታሰር ነው። ይህ ደግሞ የሚያሳየው ጉልበተኛ ጭንቅ ውስጥ ሲገባ የሚወስዳቸው እርምጃዎች ምን ያህል አስጊ እነደሆኑ ነው። ያለንበት ሁኔታ ብዙ ባሰብኩበት ቁጥር ፍርሃቴንም ያንረዋል፤ ነገር ግን ይህ አስገራሚ የሆነና ለትንቢት የማይመቸው ሕዝብ ወደ ሚያጠፋን መስመር ባለመሄድ እንደምንድን ሳስብ ተስፋዬ ይለመልማል እንደ ኢህአዴግ ሥራማ ቢሆን ኖሮ?!...

ዜጎች ለውጥን ለመቀበል ፍርሃት ሊያድርባቸው ይችላል። በኦክቶበር ወር ላይ በዚሁ ጉዳይ በሊቢያ ተደርጎ የነበረው ጥናት እንደሚያሳየው መጠይቁ ከቀረበላቸው 2000 ዜጎች ውስጥ 69 በመቶ የሚሆኑት የአንድን ሰው አስተዳደር (ከዲሞክራሲ አምባገነንትን) መርጠዋል። በሶሪያም የበሽር ደጋፊዎች ምክንያታቸው የአንድን ሰው አገዛዝ በመደገፋቸው ሳይሆን ግራ የተጋቡና እርስ በርሳቸው እንኳን ያልተግባቡት ተቃዋሚዎች የአሜሪካ ተላላኪ ሆነዋል። አገሪቷንም ወደ አልተፈለገ እልቂት ይወስዷታል በሚል ነው አሁንም ከበሽር የወገኑት። እኛም በታሪካችን የማይታለፉ የሚመስሉትን አልፈናል፣ የሚገባንን ለውጥ መሻት ግን ከጊዜያችን ጋር መሄድ ነው።

አለበለዚያ አምባገነኖች በሚቆፍሩልን ጉድጓድ ‹‹ካለነርሱማ ይህች አገር ተስፋ የላትም እያልን›› መፍሰስ ብቻ ነው መጨረሻችን፡፡

ከመለስ ሌላ ማሰብ አለመቻል እንደ ሃገርም እንደ ግለሰብም በራሱ ያሳፍራል፡፡ ኢህአዴግ ምሁራንን እውቅና መንሳትና በፍርሃት ውስጥ ቀብሮ ሃገሪቷን የእርሱ ብቻ ያለበት አስመስሏታል በሚለው የምንስማማው ብዙዎች ነን፡፡ (ሃገሪቷን የተቆጣጠረ ሰሞን ያባረራቸውን ምሁራን አስቡ) ተተኪዎችን ስናስብ በሙያቸውና በብቃታቸው እንጂ በተንኮል፣ በጠመንጃ፣ በ‹‹የፈጀውን ይፍጅ›› በጆትና በ'try and error' ፕሮፓጋንዳ እንዲሁም ጊዜውና የአለም ባንክ ገፍተው ባመጡት ለውጥ መሆን የለበትም፡፡ ለመሪነትም ባይሆን በቅርብ ከምናውቃቸው ብንነሳ የአዲስ አበባ ባለአደራ ቦርድ ከንቲባ የነበሩት አቶ ብርሃኔ ደሬሳን ማን እንደዛ ይሰራሉ ብሎ ጠብቆ ነበር? አቶ አርከበ ሙሉ ነጻነቱ ቢሰጣቸው ኖሮስ ለሥራው ብቁ አልነበሩምን?፣ በዶ/ር እሌኒ፣ በኤርምያስ አመልጋስ ማን ያልተደመመ አለ? ሌሎችን ኢህአዴግ አዳፍኗቸው ነው እንጂ ሕግ ያለበት ሃገር ቢሆንና ሁሉም በነጻነት መስራት ቢችል ስንት ተአምር ባየን ነበር፡፡ አሁንም ተተኪ ማን አለ በሚል ጥያቄ ማንም አምባገነን እንዲሆንብን መፍቀድ የለብንም፡፡ በ‹ሃገር ፍቅር›ና በ‹ልማት› ስም የተጠቀለልነው ይበቃናል፤ ስለ ነጻ ተቋማት እንጂ ስለግለሰብ ማሰብ ይበቃናል፡፡

ጆሴፍ ስታሊን በጊዜው ራሽያን ከጀርመን ወረራ ታድጓታል፡፡ ከዛም አልፎ በርሊን ድረስ ሄዶ ጀርመንን አደብ አስገዝቷል፡፡ በዚህም ራሺያ የዓለም ሃያልነቷን አስመስክራለች፡፡ ከዛም የተሳካ የተባለውን የኒውክሌር ባለቤት እንድትሆን አስችሏታል፡፡ እኛ አገር እንደ እድሜ ማራዘሚያ ካርድ እንደ ተመዘዘው GTP ስታሊንም Great Plan for the Transformation of Nature ነበረው፡፡ እርሱም እንደማንኛውም አምባገነን የራሱን ስብዕና አጉልቷል፡፡ አንዳንዶች የሁለተኛው የዓለም ጦርነትን ብቻውን ያሸነፈ እስከማለት ሁሉ ደርሰዋል፡፡ እኛጋስ ‹አባይን የደፈረ› አይደል እያልን ያለነው? አሁን ባለንበት ጊዜ ዓለም ለስታሊን የተደበላለቀ ስሜት አለው፡፡ አንዳንዶች አንባገነንና ነፍሰ ገዳይ ሲሉ ሌሎች በጊዜው ሊኖር የሚገባው መሪ ነበር ይላሉ፤ አንዳንዶች አሁንም ይናፍቋቸዋል፡፡ እኛስ?

ስናጠቃልል የራሽያው Pravda እንዲህ ይል ነበር ‹‹*Stalin was the greatest agriculturalist, philologist, geneticist, political scientist and military commander*›› እኛ ደግሞ ተውሰንም ቢሆን እንዲህ እንላለን፣
"No matter how experienced leaders are, no matter what knowledge and talents they possess, they cannot succeed in replacing the whole collective. The most important principle is that decisions should be based on the experience of many, should be the fruit of collective creation."

"መሪዎች ምንም ዓይነት ልምድ ቢኖራቸው፣ ምንም ዓይነት ዕውቀት እና ክህሎት ቢኖራቸው፣ ሁሉንም ጠቅለው በመተካት ሊሳካላቸው ግን አይችልም፡፡ እጅግ ጠቃሚው መርኅ፣ ሕዝባዊ ውሳኔዎች የጋራ ልምድን መሰረት ያደረገ እንዲሁም የጋራ ፈጠራ ፍሬዎች መሆን ይገባቸዋል፡፡"

# የእኛ ጀግንነት

ጀግንነት እና እኛ ኢትዮጵያውያን ከተያያዝን የማንላቀቅ ለሌሎችም ስንሸልመው የኖርን የጀግንነት ወራጅ ሕዝቦች ነን፡፡ ከጀግንነት ጋር ጥልቅ ፍቅር ውስጥ የወደቅን ሕዝቦች መሆናችንን ለማሳየት የታሪክን ምስክርነት መጠየቅ አያስፈልግም፡፡

በቅርብ ጊዜዎች እንኳን ጀግንነትን ለብዙዎች ስንሸልም ተመልክተናል፡፡ በቅርቡ ደግሞ የልማት ጀግንነት ለገበሬዎች እና ድህነትን ድል ላደረጉ ሁሉ ሲሰጥ የነበረ ስያሜም ሆኖም ነበር፡፡ ኢትዮጵያውያን በዘመናችን ከድፍረት ጋር የተያያዘ ጀግንነትን ስለምናደንቅ እና ስለምናበረታታ ጥንት ጥንት የጦር ሜዳ ጀግነነትን አሁን ደሞ የተለየ ድፍረትን በጀግንነት ምሳሌነት ከመጥቀስ ባሻገር የሚያግባባን የጋራ ትርጉም ያለው አይመስልም፡፡

## ሰሞኑ እና ጀግንነት

የቀድሞው ጠ/ሚር አቶ መለስ ዜናዊ (ነፍሳቸውን ይማርና) ከሞታቸው ጋር ተያይዞ በሰሞኑን ጀግንነትን የመሾም ታሪካችን ውስጥ ከፍተኛ ስፍራን የያዙ መስለዋል፡፡ በእርግጥ በጥቂት ፖስተሮች እና ህትመቶች ላይ ይታይ የነበረው የአቶ መለስ የጀግና ስፍራ ከሞታቸው በኋላ በእርግጠኝነት እና በስፋት በሁሉም ቦታ እና ሁኔታ እየታየ ነው፡፡ ህልፈታቸው ከተሰማበት ማግስት አንስቶ ስራ የጀመረው የፕሮፖጋንዳ ማሽንም አገራዊ ሃዘኑን ለፖርቲ ስብእና ግንባታ መጠቀም መሆኑ በሚያስታውቅ ሁኔታ የጀግናው ሞት ምን ያህል እንዳሳዘነን ሊያሳየን ሞክሯል፡፡ ይህ የሚዲያው ተግባር እና ተያያዥ ሕዝባዊ ምላሾችን አስመልክቶ ውይይቱ ለሌላ ጊዜ ይቆየንና የአቶ መለስን ጀግና ያስባሉ ጉዳዮችን በትኩረት ብንመለከት ቢያንስ ቢያንስ ጀግና ባሰኛቸው ነገር ላይ መነጋገር የወደፊት ጀግኖቻችንን ሹመት በአትኩሮት ለማየት ይረዳን ይሆናል፡፡

## ልማታዊ መሪ (የግድብ እና የመንገድ አባት)

አቶ መለስ ዜናዊ የመንግስትን ስልጣን ከተረከቡ ከ1983 ጀምሮ የተለያዩ የመሰረተ ልማት ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ መንግስታቸው ከሚታወቅበት ጉዳዮች አንዱ መንገዶች እና ህንፃዎች በብዛት መገንባታቸው ነው፡፡ ይህ የመንግስት ስኬት በተለይ ካለፉት መንግስታት ጋር ሲነጻጸር የሚያስመሰግነው ቢሆንም መንገድ የሰራልን መሪያችን ጀግና ነው የሚያስብል ድምዳሜ ላይ ማድረሱን እጠራጠራለሁ፡፡ ለነገሩ ፓርቲውም ቢሆን ስለስኬቶቹ ሲጠየቅ መጀመሪያ የሚያነሳው መንገድን ስለጥፋቶቹም ሲወቀስ መልሶ የሚያነሳው መከላከያ ያው የመንገድ እና የህንፃዎች ግንባታን ነው፡፡ በቅርብ "የአባይ መደፈር" ነገሩን ወደዚያ ወሰደው እንጂ ላለፉት 20 ዓመታት ፓርቲያቸው የመንገድ ግንባታን ግብር የሚሰበስብ መንግስት ኃላፊነት ያልሆነ ይመስል ለተለያየ ፕሮፖጋንዳ ሲጠቀምበት ከርሟል፡፡

ግብር ከፋይ ሕዝብ መንገድ ሲሰራለት እነደችሮታ እንዲቆጥረው ሲደሰኮር መክረሙን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ የአባይ ፕሮጀክት መጀመርን ሙሉ ዕውቅናን ለጠ/ሚኒስትሩ መስጠት የጥረታቸው የሚገባ ዋጋ ነው:: (ይህ እንግዲህ የመነሻ ዓላማውን፣ የፕጀክቱን ስኬታማት ዕድሎች፣... የመሳሰሉትን ክርክሮች ሳይጨምር ነው፡፡) ይህ የሚገባው ዕውቅና እንዳለ ሆኖ ነገር ግን የመንግስት ኃላፊነቶቹን የሚወጣ መሪን ኃላፊነትህን ስለተወጣህ ጀግና ነህ ብሎ ማወደስ የለመደብን፣ የማጋነን እና በነፈሰበት የመንፈስ ዘይቤ ውጤት ይመስላል፡፡ የአባይን የመገደብ ፕሮጀክት ብቻውን ለሚች ጠ/ሚር ተገቢ ዕውቅና ቢሰጣቸውም ሌሎቹን ልማታዊ ቅጥያዎች መንግስታዊ ኃላፊነታቸው/ሥራቸው መሆኑን ባንረሳ ጥሩ ነው፡፡

ልማቱ ከተነሳ አይቀር በልቶ ማደር ብርቅ የሆነባቸው የከተማ ነዋሪዎች፣ የቤት ኪራይ እና የደሞዝ መጠን አንድ የሆነበት ጊዜ፣ ትራንስፓርት ችግር የሚያስለቅስበት ወቅት፣ የኑሮ ውድነቱን መቋቋም ያልተቻለበት ዘመን የእርሳቸው አመራር ውጤት መሆኑንም መዘንጋት አያስፈልገንም፡፡

## የኢትዮጵያ/የአፍሪካ ተወካይ

ኢቴቪ፣ መስሎቹ እና ሐዘንተኞቹ በተደጋጋሚ ያነሱት የነበረው የአቶ መለስ የመጀመሪያ ሰሞን የጀግነት መገለጫ በአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ዙሪያ ያደረጉት ንግግር ነው፡፡ እውነቱን እንነጋገር ከተባለ አቶ መለስ ስለአገራቸው በቅንነት እና እንደመሪ በሚያኮራ መልኩ የተናገሩት ብቸኛ ንግግር ይሄ ነወ ለማለት እደፍራለሁ:: ኢቴቪም ቢሆን

የአገር መሪ እንዳጣን ሊያስታውሰን ሲሞክር ደጋግሞ ሲያሳየን የነበረው ይሁንኑ ንግግር ነበር፡፡ ከዚያ ውጪ ያለውን የአቶ መለስን ስብዕና ሰስናስታውስ ደጋግሞ የሚታወሰኝ "ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች" ተያያዥ ጉዳዮች እና ከእሳት የተፈተነ ብሔር መምጣታቸውን በኩራት የተናገሩበት ንግግራቸውም ጭምር ነው፡፡

አፍሪካ ህብረት እና ኢትዮጵያ በአፍሪካ ያላት ቦታ ዛሬ በመለስ ዘመን ያገኘነው አዲስ ቦታ አይደለም፡፡ (አቶ መለስም ቀደም ሲል በገለጽኩት ንግግራቸው ላይ ይህንን ያምናሉ)፡፡ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ህብረት (በቀድሞ አፍሪካ አንድነት) ውስጥ የነበራትን ቦታ ይዛ እንድትቀጥል ማድረጋቸው እንደ አንድ መሪ የሚያስመሰግናቸው ቢሆንም ጀግና የሚያስብል ማዕረግ ግን የሚያላብስ አልነበረም፡፡ እንደውም እንደአለመታደል ሆኖ ነው እንጂ "በየስብሰባው የሚዞር መሪ" ያላት አገር ተብሎ ከመታወቅ ይልቅ በፈጣን የዴሞክራሲ ስርአት እና ተያያዥ ፍሬዎቹን የሚያጣጥሙ ሕዝቦች አገር ተብሎ መታወቅ ይበልጥ ያምርብን ነበር፡፡

የአቶ መለስ አለም አቀፍ የተግባቦት ችሎታ የማይካድ ቢሆንም የግል ስብእናቸውን ገንብቶ እኛን ለኢቴቪ ፕሮፖጋንዳ ከመዳረግ ውጪ እንደ አገር ኢትዮጵያን የጨመረላት ነገር ያለ አይመስለኝም፡፡ እንደውም ይህ የተግባቦት ችሎታቸው የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እና ጭቆናን ለመደበቅ እነደመሳሪያ ሆኖ ማገልገሉን አናንሳ ካልን ነው፡፡ ከአፍሪካ መሪዎች በተሻለ የማሳመን ችሎታቸው የሚታወቁትን አቶ መለስን አፍሪካ ተወካይ አድርጋ ብትመርጥ አይገርምም፡፡ የአፍሪካ መሪዎች ብዙዎቹ አምባገነኖች ናቸው፡፡ ሕዝቦቻቸውን በማማረር በሚታወቁ የአፍሪካ መሪዎች መካከል በሙስና እና በመልካም አስተዳደር እጦት ሕዝቦቻቸውን የሚያስቃዩ መሪዎችን መወከል የምርጦች ምርጥ መሆን አይደለም፡፡ አቶ መለስ የዴሞክራሲያዊ አገራትና የሚኮራባቸው ስኬታማዎች መሪዎች ተወካይ አልነበሩም፡፡ ኢትዮጵያን እንደ ሃገር በየአመቱ ብዙ ሺህ ሰዎች የሚሰደዱባት፣ በየአገሩ እየሞቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎችዋን በየቀኑ የምትቀበል አገር መሆንዋን የአቶ መለስ ተወካይነት አላስቀረውም፡፡ ምክንያቱም ይህ በእርሳቸው አስተዳደር ዘመን ኢትዮጵያ ያለችበት እውነታ ነውና!

## የዴሞክራሲያ አባት/የአንድነት አባት

ይህንን ወደቀልድነት የሚያደላ የአቶ መለስ ቅጥያ ጀግንነት የሰማሁት ከኢቲቪ እና መሰሎቹ ነበር፡፡ እንደሰማሁት መጀመሪያ የተሰማኝ የነበረው "የዴሞክራሲን እና የአንድነትን ትርጉም ለመረዳት ምን ያስፈልገናል ወይስ አይገባቸውም ተብለን ይሄን ያሕል ተንቀን ነው" የሚል ጥያቄ ነበር፡፡ አንዳንዴ ሳስበው አቶ መለስን በግል ከየትኛውም ሚዲያ ውጪ ብናጨዋውታቸው ራሳቸው የአንድነት እና የዴሞክራሲ አባት ነኝ የሚሉ አይመስለኝም፡፡ ዴሞክራሲ ሒደት ነው ብለው ይሸፋፍኑት ይሆናል እንጂ፡፡

አቶ መለስ የዴሞክራሲን ማስፈን ፍላጎት እና ተግባራዊነት የተቀላቀለባቸው መሪ ነበሩ፡፡ (ይህንን ለመረዳት ሕገ መንግስቱን እና ተግባራዊውን ሁኔታ ማወዳደር ይበቃል) የፓርቲያቸውም ሆነ የግለሰብ ባህሪያቸው ዴምክራሲን እሴታቸው አድርጎ አይቶ የሚያውቅ አይመስለኝም፡፡ አለማቀፋዊ ተቀባይነትን ለማግኘት ከሚሞክሩ የጨዋታ ምርጫና ሚዲያ ውጪ የተቃውሞ ድምጾች መገለጫም ሆነ ቁጥር ቀን በቀን እየቀነሰ ሄዶ አሁን ዜጎች መንግስትን የምትተቸች ትንሽ ንግግር እንኳን ሲያደርጉ አካባቢያቸውን ዞር ዞር ብለው ለማየት እና ድምጻቸውን ለመቀነስ የተገደዱበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡ ይህ እንግዲህ የአቶ መለስን የ1997ቱን የኢትዮጵያን የሰላማዊ ዴምክሲያዊ ሽግግር ዕድል የገደሉበትን፣ ነፍስ ያስጠፉበትን ተግባራቸውን እንርሳ ካልን ነው፡፡

የአቶ መለስ መንግስት ባለፉት 21 ዓመታት ከፈጠራቸው ታላላቅ ጠንካራ አገራዊ ጥፋቶች መካከል አንዱ እንደአገር ልዮነቶቻችን ላይ አንድናተኩር የመደረጋችን ስትራቴጂ ነው፡፡ ይህ የሃይማኖት እና የብሔር ልዩነትን በዕውቅና እና መብት መስጠት ሽፋን በማስፋፋት የማንነታችን መነሻ ኢትዮጵያዊነት መሆኑን የረሳንበት ደረጃ ላይ አድርሶናል ለማለት እደፍራለሁ፡፡ ይህ በጋራ መሃከል ላይ እስከንመጣ ድረስ የሚቆይ አገራዊ የቤት ሥራ የአቶ መለስ አመራር ውጤት ሆኖ እያለ አቶ መለስን የአንድነት አባት ማለት፣ በሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲከኛ እስረኞች ያሉባትን ሃገር፣ የፓለቲካ ስደተኞች የበዙባትን ሃገር፣ ሽምግልና የፓለቲካ እስረኞችን ለማስፈታት መቀለጃ እና መሳሪያ በሆነበት ዘመን፣ አቶ መለስን የዴሞክራሲ አባት አድርጎ መሳል በሕዝቦች ላይ መቀለድ ነው፡፡

## እንደበተ ርቱዕ?

የአቶ መለስ እንደበተ ርቱዕነት ሰሞኑን አንዱ የጀግንነታቸው ምክንያት ሆኖ ተገልጧል፤ (ለነገሩ ወደ በኋላ ትንሽ ደበዘዘ እንጂ የድሮም ዝናቸው መሰረት እንደበተርዕቱነት ነበር)፡፡ በእርግጥ አቶ መለስ ሐሳባቸውን በመግለጽ በኩል ጠንካራ ነበሩ፡፡ ሐሳባቸውን የሚገልጹበት መንገድ እና ሁኔታ ቢለያይም (ፓርላማ ላይ ሌላ፣ ከአገር ውስጥ

ጋዜጠኞች ጋር ሌላ፣ ከሃገር ውጪ ስብሰባ ላይ ሌላ፤ የአገር ውስጥ ስብበሳ ላይ ሌላ) በራስ መተማመን መንፈስ ሐሳባቸውን ከመግለጽ ተቆጥበው አያውቁም ነበር፡፡ በሃገር ውስጥ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ግን አቶ መለስ የመሪነት ስልጣናቸውን እንደፈለጉ ለመናገር መሳሪያ አድርገው ተጠቅመውበታል የሚል እምነት አለኝ፡፡

አቶ ለመለስ በፓርላማ ይጠየቃሉ እንደፈለጉት ይመልሳሉ፤ እርሳቸው ለመለሱት መልስ ክርክር እና ተጨማሪ ምላሽ የመስጫ ጊዜ ኖሮ ስለማያውቅ ከማስካካት ባለፈ የክርክራቸውን ቀሽምነትን እና ጥሩነት ከሌሎች ጋር በመከራከር ተፈትኖ አያውቅም፡፡ በዚህ ብዙ ዕድሎች የሰጠን ምርጫ 97 እንኳን እርሳቸውን በአደባባይ ሲከራከሩ ሊያሳየን አልቻለም ነበር፡፡ በተለይ በአገር ውስጥ ጉዳዮች ዙሪያ የአቶ መለስ አንደበት አንድም ቀን ለክርክር ቀርቦ አያውቅም፡፡ እሳቸው ይናገራሉ ሌሎች ያዳምጣሉ፡፡ እንደውም ሞታቸው የሚቆጨው ከአንድም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ጋር ለቀጥታ ክርክር ቀርበው ሳይከራከሩ በመቅረታቸውም ጭምር ነው፡፡ የአቶ መለስ አንደበተ ርቱዕነት በዓለም አቀፍ መድረኮች የሚመሰከርለት ቢሆንም እንደ ኢትዮጵያዊ ምስክር ሆነን እና አፋችንን ሞልተን እናወራለት ዘንድ እሳቸው ብቻ ሲናገሩ መክረማቸው ቀርቶ በአገራዊ ውይይቶች ከሌሎች ጋር ሲያወሩ፣ ሲወያዩ እና ሲከራከሩ የማየት እድሉ ቢኖረን ይህንን የጀግንነታቸው መገለጫ አንደበተ ርቱዕነታቸውን ነው ብለን አፋችንን ሞልተን እናወራ ነበር፡፡

ለእኔ በግሌ አቶ መለስ የምኮራባቸው ጥሩ መሪ አልነበሩም፡፡ እዚህ ቅሬታ ላይ የሰሞኑን ቅጥ ያጣ ፕሮፖጋንዳ ሲጨመርበት ደግሞ እንደ ሰው ያዘንኩትን ሐዘን በኢቴቪ እና በመሰሎቹ እንዳልቀማ ጥረት ሳደርግ ቆይቻለሁ፡፡ ሐዘኑን ፓለቲካ ሲያደርጉብን ከርመው እኛ ፓለቲካዊ ስናደርገው የሚወቅሱን ካሉ ለአቶ መለስ ማዘን እና ፕሮፖጋንዳውን ባለመቀላቀል እንዲረዱኝ ለማስታወስ እወዳለሁ፡፡ አልታደልንም እንጂ ኢቴቪን ወደ አንድ ጽንፍ ሲጎትተን የሚያመጣጥንልን ሌላ ሚዲያ ቢኖረን ኖሮ በዚህ ሐሳብ ዙሪያ ለመነጋገርም አንነሳም ነበር፡፡

አቶ መለስ ታታሪ፣ ለአላማቸው ጽኑ፣ ጠንካራ ሰራተኛ፣ የፓርያቸው ምሰሶ ነበሩ፡፡ የእርሳቸው ዓይነት አንድ ሁለት ሰው አንደተተኪ እንኳን ሳያበቁ ማለፋቸው የአመራራቸውን ድክመት ያሳያል፡፡ እርሳቸው የጥቂት ዓመታት መሪ ቢሆኑ ኖሮ በቂ ጊዜ ሳይኖራቸው ነው ብለን እናስተባብልላቸው ነበር ነገር ግን ከ30 ዓመት በላይ በመሩት ፓርቲ ውስጥ ለሚተካቸው መጥፋት መልሶ ራሳቸውን ተጠያቂ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚሁ አጋጣሚ የሰሞኑን የመንግስት ባለስልጣናት አቶ መለስን ሲያወድሱ የፓርቲያቸውን ባዶ ሜዳ መቅረትም እየነገሩን ነበር፡፡ የአቶ መለስ ታታሪነት አንጂ ተተኪ ያለመኖር ታሪክ የሚኮራበት መሆን አልነበረበትም፡፡

ለታታሪው ኢትዮጵያዊ አቶ መለስ ዜናዊ ነፍስ ይማር፡፡ በፕሮፖጋንዳ ብዛት ራሳቸውን እያጠፉ ላሉት ኢቴቪና ዘመድ አዝማድ ሚዲያዎችም ነፍስ ይማር!

# የመለስ ውርስ እና ራዕይ

ሰሞኑን በመስቀል አደባባይ ሳልፍ የአዲስ አበባን 125ተኛ አመት አከባበር አስመልክቶ (የበአሉ አከባበር ራሱ ሌላ ጽሁፍ ይወጣዋል) አዲስ ቅርጻ ቅርጾች ተቀምጠው ተመልክቼ ነበር፡፡ እነዚህ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾች (125 የሚል ጽሁፍ ሌላ 31 የሚል ምን ለማለት እንደሆነ ለመረዳት ጊዜ የፈጀብኝ ሌላ ጽሁፍ የቀድሞው መሪ አቶ መለስ ፎቶ በእያንዳንዳቸው ላይ የተቀመጠባቸው ሌሎች ቅርጾች) ከሌላ ጊዜው በተጨማሪ የመለስን መንፈስ በአደባባዩ ሞልተውታል፡፡ በትልልቅ ባነሮች ብቻ ይታይ የነበረው የሟች ጠ/ሚኒስትሩ መስቀል አደባባይ ላይ መገኘት አሁን አደባባዩን መሬት ሞልቶታል፡፡ይህ በመስቀል አደባባይ እና በመላው አዲስ አበባ የሚታዩት የመለስ ምስሎችሁሉም ማለት ይቻላል ውርሳቸውን ለማስቀጠል እና ራእያቸው ስለማሳካት የሚያወሩ ናቸው፡፡ በእርግጥ ጥቂት መንፈሳዊ መልእክት መሰል መልእክት የያዙ ጽሁፎችም አልጠፉም( "ለህዝብ የተፈጠረ ለህዝብ የኖረ እና ለህዝብ የሞተ…"ከነዚህ ውስጥ ይጠቀሳል)

የአቶ መለስ ሞት በይፋ ከታመነበት ጊዜ አንስቶም ከፓስተሮች ጀምሮ እስከ ፓርላማው ውይይት ድረስ የሚነሳው ቃል ራእይ እና ውርስ(ሌጋሲ) ሆኗል፡፡ አገሪቷም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ራእይን የማሳካት ታላቅ የማሃላ ስነ ስርአት ላይ ያለች ይመስል ከሩጫ እስከ ቢሮ ስራ ከእንጀራ መጋገር እና ዝቅተኛ የስራ መስኮች ጀምሮ እስከ ታላላቅ ቦታዎች ተተኪ አመራሮች ድረስ "የእናሳካለን መሃላ"ን ስራችን አድርገን ይዘነዋል፡፡ የማይተማመን ባልጀራ ………ነገር ነው ብለን መደምደማችንን ብንተወው እንኳን ሁላችንም የምንግባባበት የአቶ መለስ ውርስ እና ራእይ አለ ወይ የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይሆናል፡፡

## የውርስ እና ራዕይ ስብከት

አቶ መለስ ሞት በፊት ሲያቆጠቁጥ የነበረው ግለሰባዊ ገጽታ ግንባታቸው ተጠናክሮ ከሞታቸው በኂላ በሁሉም የመንግስት ሚዲያዎች አልፋና ኦሜጋ ሁሉን ቻይ ሆነው ቀርበዋል፡፡ በከፍተኛ የመንግስት አመራር ደረጃ ሳይቀር ከእርሳቸው ውጪ የሚሰራ ምንም ነገር እንዳልነበር ሲነገረን ከርሞአል፡፡ይህ የሃዘን ማግስት የሟች ገጽታ ግንባታ ደረጃውን በፍጥነት በማሳደግ ራእይህን እናሳካለን ውርስህን እናስቀጥላለን ወደሚል አገራዊ መሃላም ተቀይሯል፡፡ ይህ የራእይ እና የውርስ ማስቀጠል ማሃላ እና ስብከት ከተባበሩት መንግስታት ስብሰባ እስከ ፓርላማ፣ ከዜና እስከ ወረዳዎች አመራር ንግግር ሳይቀር ሲነገር እና ሲወራ ነበር፡፡ ሚዲያውም የካድሬዎችን ንግግር ቅርጽ በማስያዝ የራሱን ሚና ሲወጣ ነበር፡፡ ኢቲቪ እንኳን ከዜናው ጀርባ ታላቁን መሪ ካስቀመጠ ስንት ጊዜው?ለዛውም "ታላቁ አባታችን መከረን ……"ከሚል ጽሁፍ ጋር!!

## "የጠቅላይ ሚኒስትራችን ጠ/ሚኒስትር"

በሚዲያው መሪነት በታላላቅ ባለስልጣናት ፊትአውራሪነት ሲመራ የነበረው የውርስ እና ራእይ ስብከት ሌላ ጠ/ሚኒስትር መተካታችንን ማስታወስን ራሱ ነውር ሲያደርገው ተመልክተናል፡፡ በስህተት የቀድሞው ጠ/ሚኒስተር የሚሉ የነበሩ የከተማው ፓስተሮች እንኳን በፍጥነት ጠ/ሚኒስተር በሚለው የአቶ መለስ "ዘላለማዊ ማእረግ" ተተክተዋል፡፡ ዘንድሮም ሞታቸው ከስልጣናቸው እንዳስወገዳቸው ማመን ያቃታቸው ሚዲያዎች የቀድሞን የሚል ቃል ለመጠቀም አልደፈሩም፡፡ አንደውም አዲሱ ጠ/ሚኒስትር በፓርላማ ንግግራቸው አቶ መለስን "ክቡር ጠ/ሚኒስትራችን" በማለት ደጋግመው በመጥራት ጠቅላይ ሚኒስትራችን ሌላ ጠ/ሚኒስትር እንዳላቸው በይፋ አጠናክረው ነግረውናል፡፡ ይህ መለስን ከመሪነት ቦታ ለማንሳት ያለመፈለግ አባዜ በዚህ አያያዙ ከቀጠለ ከቀናት እና በአላት ስያሜነት ባለፈ የአቶ ለመስን ውርስና ራእይ ምንነት ሳንጠይቅ እንድንቀር እንዳያደርገን ያሰጋል፡፡

## የአቶ መለስ ራዕይ

ለመሆኑ ባለራእዩ መሪ" ራእያቸው ምን ነበር የሚለወን ጥያቄ ለራሴ ሳነሳ የሚታወሰኝ ትልቅ እቅድ እና ራእይ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ እንዲሁ ስጠረጥር ግን የእርሳቸው ራእይ አሳኪዎች ሊያነሱዋቸው የሚችሉዋቸው ነገሮች ከምስላቸው ጀርባ ያለው የህዳሴው ግድብ ፕሮጀክት እና የባቡር መስመር ዝርጋታው እንዲሁም የመንግስት እቅድ ሆኖ የምናውቀው(ከህልፈታቸው በኂላ ሙሉ ለሙሉ የእርሳቸው እቅድ የሆነው) የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ይመስሉኛል፡፡ከእነዚህ ላይ ከተጨመረ የሚጨመረው መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገሮች ተርታ እንድንመደብ ያደረጉት ጥረት እየተባለ የሚወራው አወዛጋቢውን የኢኮኖሚ እድገት የማስቀጠል ወሬ ነው፡፡ እነዚህ የመንግስትን ፕሮጀክት እና የግለሰብን ራእይ ማቀላቀል ጉዳዩች ወደጎን ትተን ብናስበው እንኳን

ማንኛውም በጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታ የተቀመጠ መሪ ሊያደርግ የሚገባውን የመንግስትን ስራ የመምራት የማቀድ እና የማስፈጸም ስራ እንደ ራእይ ማሰቡ አልተዋጠልኝም።አቶ መለስ ላለፉት 21 አመታት አገዛዛቸውም ቢሆን አገራችን ብለው ጠርተዋት የማያውቋትን ኢትዮጲያን በምግብ ዋስትና ራስን ስለማስቻል በተለያየ ጊዜ ከተናገሩት ውጪ (እርሱም መንግስታዊ ሃላፊነት እንጂ ራእይ ሊሆን አይችልም) ስለወደፊትዋ ኢትዮጲያ የሚታወስ ራዕይ ማስቀመጣቸውን እጠራጠራለሁ።

ምንም እንኳን አቶ ለመለስ ታላቅ መሪ ለመባል የመፈለግ ራእይ ሊኖራቸው እንደሚችል ብዙዎች ቢጠረጥሩም እንደ እኔ እንደእኔ የአቶ መለስ ራእይ ከዚያም በተጨማሪ በዋናነት የራሳቸውን እና የፓርቲያቸውን የስልጣን ዘመን ማስቀጠል እንደነበር ይሰማኛል። ከላይ የዘረዘርኳቸው የማንኛውም መንግስት ሃላፊነቶችን ማከናወን የተለመደ የመንግስት ተግባር ቢሆንም የተለየ እመርታ ስናሳይ እንደከረምን እና አስደናቂ አገራዊ ለውጥ ላይ እንዳለን ተደርጎ ሲቆጠር አስተውያለሁ። ባቡር ለመስራት ያሰቡ ግድብ ለመገንባት ያቀዱ እና የመንግስትን እቅድ ያወጡ መሪዎች ባለራእይ ሲባሉ ሰምተን የማናውቀውም የመንግስት ስራቸውን መስራታቸው ባለራእይ ስለማያሰኛቸው ብቻ ነው።(አቶ መለስ እንኳን ደሞዙን ሰልጣኑን እና ስሙን ለያዙት ስራ ቀርቶ ባለቤታቸውን ለማገዝ ለኤፈርትስ ሲያቅዱ አልነበር አንዴ?) እኔ በግሌ ብጠየቅ አቶ መለስ ራእይ የፓርቲያቸውን አገዛዝ እና የስልጣን እድሜ ማራዘም፣ሞተው እንኳን "የቀድሞው" ለማለት ለመድፈር ያልቻለ የእርሳቸው አምላኪ የፓርቲ ስርአትን ማጠናከር፣ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ የራስን ገጽታ መገንባት እንዲሁም የመድብለ ፓርቲ ስርአት እና የነጻ ፕሬስን በማንኛውም ሁኔታ እንዳይኖር ማድረግ የመሳሰሉት ናቸው።አቶ መለስ ያለሟት ኢትዮጲያ ሲቪል ማህበረሰብ የማይኖርባት ሰብአዊ መብት የማይወራባት ጋዜጠኞች በተሰጣቸው ልክ ብቻ የሚንቀሳቀሱባት ግልጽ ቀይ መስመር የተሰመረባት ነበረች። የራእይ ማሳካት ማሃላችን እነዚህንም አብሮ እንደሚጨምር ማስተዋሉ አስፈላጊ ነው።

## የአቶ መለስ ውርስ

አቶ መለስ ለ21 አመት አገር እንደመግዛታቸው የሚያስቀሩት ውርስ ያስለመዱት ስርአት የፈጠሩት አካሄድ መኖሩ አይቀሬ ነው።ጥያቄው ውርሳቸውን ምንድነው ማስቀጠሉስ ለማን ይበጃል ውርሱስ ምንድነው የሚለው ነው?

## ቁጣ እና ንቀት - ውርስ 1

ከአቶ መለስ ውርሶች አንዱ እና ሁሌም ከእርሳቸው ጋር ተያይዞ የሚታሰበኝ ማንንም ቢሆን ከመቆጣት ያለመመለሳቸው ጉዳይ ነው። ይህ ማንንም አልፈራም አባዜ ከፓርላማ አንስቶ እስከ ጋዜጠኞች የሚነሱ ጥያቄዎች መልስ እስከመስጠት ድረስ ይታያል።አቶ መለስ በፓላማም ሆነ ጥያቄ በሚመልሱበት ወቅት ተቃዋሚዎችን ያስፈራራሉ፣ህዝቡን ንቀት በሚመስል መልኩ አግባብ ዛቻዎችን ሲያሰሙ ይስተዋላሉ። ማንኛውንም እርሳቸው ያሉትን መንገድ የማይደግፍ የመሰላቸው አካል ላይ ዘለፋን ያሰማሉ። ይህ የአቶ መለስ ውርስ ነው። ውርሱን እናስቀጥላለን ስንል ደሞ ተተኪው ጠ/ሚኒስትርን ተሳዳቢ በንቀት ተናጋሪ እና በፓርላማው በስተቀኝ በኩል በዛቻ ጣቶቹን የሚያወዛውዝ ይሁን እያልን መሆኑ ነው ማለት ነው።

## በድን ፓርላማ - ውርስ 2

አቶ መለስ ያወረሱን ሌላው ነገር አሳፋሪ እና በድኑ ብቻ የሚንቀሳቀስ ፓርላማ ነው።ይህ የአገሪቷን ህዝብ ወክያለሁ የሚል ፓርላማ የማይናገር የማይሰማ የሃሳብ ልዩነት የማይታሰብበት ከመሆኑም በላይ በበድንነቱ የማያፍር ግን የሚያሳፍር ፓርላማ የአቶ መለስ ውርስ ነው። ይህ "የታላቁ መሪ" ውርስ ፓርላማ ለመልካም ምኞት መግለጫ የሚያላግጥ፣ ላልተቀለደ ቀልድ የሚስቅ፣ የመስማት እና መናገር እንዲሁም ማሰብ የተሳናቸው ስብስብ ከመምሰሉም በላይ በታየ ቁጥር የሚያሸማቅቅ ብሄራዊ ሀፍረት ነው። (እግዜር ይስጣቸውና በአፍሪካ እና በአለም መድረክ የሚያኮራ ፓርላም ብለው ዜና ነግረውን አለማወቃቸው ያስመሰግናቸዋል) የአቶ መለስን ውርስ ሳይበረዝ እና ሳይከለስ ማስቀጠል ይህንን በድን ፓርላማ ይዞ መንቀሳቀስን ይጨምራል።

## የምርጫ ድራማ - ውርስ 3

ምርጫ የሚባለውን ሃሳብ ወደ ድራማ እና ቀልድነት ብሎም ወደ አገራዊ ጨዋታ የቀየርነው፣ ከተስፋ ምንጭነት ወደ አገራዊ ኪሳራነት የለወጥነውም በዚሁ በአቶ መለስ አገዛዝ ዘመን ነው። ይህ "ምርጫ የሚሉት ጨዋታ ምን ያደርጋል?" ወደሚል አገራዊ አስተሳሰብንም ያመጣነው በዚሁ ዘመን ላይ ነው። የአቶ መለስን ውርስ ስናስቀጥል ምርጫን የማጨበርበሪያ እና የአለም አቀድ ድጋፍ ማግኛ መድረክ ከመሆኑ ውጪ ለማሰብ ያለመቻላችንንም አብረን እናስቀጥላለን ማለት ነው።

## የወረቀት የመድብለ ፓርቲ ስነ ስርአት - ውርስ 4

የመድብለ ፓርቲ ስርአት በኢትዮጲያ የወረቀት ብቻ እንዲሆን ያደረጉት አቶ መለስ ናቸው። የተቃዋሚን ፓርቲን መምራት እና በተለመዱ መንገዶች ማህበረሰቡን መድረስ የማይቻልባት ጠንካራ ተቃዋሚ ማግኘት ምኞት የሆነባት ኢትዮጲያ መፈጠር የአቶ ለመለስ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። እንኳን በተቃዋሚ ፓርቲ ደረጃ ቀርቶ በኢህአዴግ ስርአት ውስጥ እንኳን የአጋር ፓርቲዎችን በነጻ የመቆም መብት የማይታሰብ መሆኑም የእርሳቸው አመራር ውጤት ነው። የግለሰቦችን አቅም ተጠቅሞ ውስጠ ፓርቲ አቅሙን ያላጠናከረው ኢህአዴግ ዛሬ በመሪው ሞት ብዙ ነገር እንዳጣ ሲያወራ ይስተዋላል። የአንድ ግለሰብ አቅም እና ገጽታ ግንባታ የሚያሳስበው የአንድ ፓርቲ ረዥም ዘመን አገዛዝን ለማጠናከር የሚሰራው፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መኖር የሚያሰጋው፣ አጋር ፓርቲዎች ልዩነት ሳይኖራቸው እንዲገዙ የሚያደርገው አሃዳዊ ስርአት የአቶ መለስ ውርስ ነው።

## የተሽመደመዱ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት - ውርስ 5

የህዝብ አግልግሎት ተቋማት አገልግሎት ተሽመድምዶ "አገልግሎት ለመሆኑ አለ?" በሚያስብል ደረጃ የ የምትገኘው አገራችን የአቶ መለስ አመራር ውጤት ናት።በ21 አመታት አገዛዛቸው አቶ መለስ ደካማ አገልግሎት ሰጪውን ኢትዮ ቴሌኮምን፣ በቋሚነት መብራት ማቋረጥ ስራው የሚመስለውን የኢትዮጲያ መብራት ሃይል ኮርፖሬሽንን አውርሰውን አልፈዋል።እነዚህ የተሽመደመዱ ተቋማት ምሳሌዎች ጠቀስን እንጂ ደንበኛ የሚያስለቅሱ የመንግስት ተቋማት የኚሁ መሪ ውርስ ናቸው። እንግዲህ ይህንንም ማስቀጠላችን ነው ማለት ነው?

## የተቀላቀሉ ፓርቲ እና መንግስት - ውርስ 6

በደንብ ያልተነገረለት እና በሚገርም ሁኔታ ልዩነቱን ማሳየት የማይቻለው የፓርቲ እና የመንግስት መጋባትም የአቶ መለስ ውርስ ነው። በየትኛውም የመንግስት ስራዎች ውስጥ የፓርቲ አገልጋዮችን ማየት የማይገርምበት የመንግስት ሃብት ለአንድ ፓርቲ ግላጋሎት ሲውል ሃይ ባይ የሌለበት ስርአት አቶ መለስ የፈጠሩት ስርአት ነው።የህዝብ ሃብት በማንአለብኝነት የሚጠፋበት ስርአት የአቶ መለስ ውርስ ነው።ከውርሱ መቀጠል ጋር ተያይዞ እንግዲህ ኢህአዴግ የመንግስትን ሃብት እንደፈለገ ሲጠቀም እንዲኖር መፍቀዳችን ነው ማለት ነው።

## ሊሞት አንድ ሐሙስ የቀረው የግል ሚዲያ እና ለውሸት ቆርጦ የተነሳ የመንግስት ሚዲያ - ውርስ 7

መንግስትን የሚተች፣የሚያስተምር አቅጣጫ የሚጠቁም የግል ሚዲያ ኢትዮጲያ ውስጥ የሚታገሱት ነገር እንዳይሆን የተደረገው በአቶ መለስ የአገዛዝ ዘመን ሲሆን እስካሁንም ውርሳቸው ሆኖ ተተኪዎቻቸው እያስቀጠሉት ይገኛል።ይህ ምንም አይነት ትችት ያለመታገስ ባህሪይ የአገሪቷን የህትመት ሚዲያ በየቀኑ የሚሞት እና ጠራርጎ ሊጠፋ አንድ ሃሙስ የቀረው ሆኗል። ጋዜጠኞችን የሚያሰድደው፣ የሚያስር እንዲሁም ለህይወታቸው የሚያሰጋ(በአለም አቀፍ ደረጃ የመሰከረለት) ስርአት የአቶ መለስ ውጤት ሲሆን ይህንንም እንግዲህ ልናስቀጥል መሆኑ ነው።

## ሰብኣዊ መብትን የማያወሩ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት - ውርስ 8

ስለሰብአዊ መብት ማውራት እንደሃጥያት የሚቆጠርባት ኢትዮጲያ የአቶ መለስ ዘመን ላይም ለውጥ አላሳየችም። ድሮም በነጻነት መደራጀት የማይፈቀድላቸው የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ከ1997 በኋላ ደግሞ በጠቅላላው ሰብአዊ መብት ደህና ሰንብት እንዲሉ ተገደዋል። በነጻነት መደራጀት የምኞት ጥያቄ እንደሆነ የሚቆጠርባት "ዳቦ

ቅድሚያ" ተብሎ ሰብአዊነት የተረሳባትን ኢትዮጲያ አቶ መለስ ውርስ ስትሆን እናስቀጥላለን ብለን ስንምል ይህንንም ጨምረን መሆኑ ነው፡፡

## የፍርሐት ትውልድ - ውርስ 9

ፍርሃት የግል ባህሪያችን ሆኖ የቀረበት ይህ ዘመን የአቶ መለስ ውርስ ነው፡፡ በትንሹ እንኳን ሃሳባችንን መግለጽ የምንፈራበት፣ ሰዎች ሃሳባቸውን በነጻነት ሲገልጹ የምናሳቅቅ ሰዎች የተፈጠርነው በእነዚሁ 21 አመታት ነው፡፡ በተለይ ባለፉት ጥቂት አመታት በአቶ መለስ ስብእና ግንባታ ልክ እያደገ የመጣው የፍርሃት መጠን ማህበረሰቡን የፍርሃት ማህበረሰብ ለማለት እስክንደፍር ድረስ ተጋኗል፡፡ይህንንም ማስቀጠል ማሃላው ውስጥ መጠቃለሉን አለመርሳትም ጥሩ ነው፡፡

## የኑሮ ውድነት እና የከተማ ድህነት - ውርስ 10

ቀን ከቀን የሚሻሻል የማይመስል ልብ የሚሰብር እና የከፋ የከተማ ድህነት የኑሮ ውድነት፣ የእለትን ጉርስን የማግኘት ትግል፣በደሃውና በሃብታሙ መካከል የሚታይ ከፍተኛ የኑሮ ልዩነትም ቢሆን የአቶ መለስ ውርስ ነው፡፡መጓጓዥ አገልግሎት ችግርን መፍታት ያቃተው አሰራር ትራንስፓርት ማግኘት እድል እንደሆነ የሚቆጠርበት ከተማ ከአቶ መለስ የተረከብናቸው ውርሶቻችን ናቸው፡፡

ራእይ እና ውርስን የማስቀጠል መሃላው ቢለይልን ብናውቀው እና ብንረዳው ቢያንስ ለሚዛናዊነት ይረዳናል፡፡ካልሆነም እኔ ከጠቀስኩት ውጪ ሌላ ውርስ እና ሌላ ራእይ የሚጨምር ካለ ለመስማት ዝግጁ ነኝ፡፡

# ስለጠቅላይ ሚንስቴር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ፡ ያልተባሉና ያልተነገሩ

**በቀድሞ ተማሪያቸው**

## I. መግቢያ፡-

የጠቅላይ ሚንስተር አቶ መለስ ዜናዊ ድንገተኛ ሞት ተከትሎ የአቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ያልተጠበቀና ያልታሰበ ወደስልጣን መምጣት ብዙዎችን ያስገረመ ጉዳይ ሲሆን ይህንንም ተከትሎ የዚች ሃገር ጉዳይ ያገባኛል ያሉ ብዙ ግለሰቦች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት እና ሌሎችም የሳቸው ሹመት ለሃገሪቱ ጥሩ አጋጣሚ ሊሆን እንደሚችልና ምናልባትም ፈጣሪ ለዚች ሃገር ለውጥ ያስቀመጣቸው ሊሆኑ ሁሉ እንደሚችሉ ተስፋ አድርገውባቸዋል፡፡ እኔም ከነዚህ ወገኖች አንዱ ነኝ፡፡

ስለ ጠቅላይ ሚንስተር ኃይለማርያም ደሳለኝ በተለያዩ ድህረገጾችና ጋዜጦች ብዙ የተባሉና የተጻፉ ሲሆን አብዛኞቹ የሳቸውን በጎና ጥሩ ጎኖች የሚዳስሱ ናቸው፡፡ ከዚህም መካከል ሰውየውን ጥሩ ሃይማኖተኛና፣ ፈርሀ እግዚአብሔር ያላቸው፣ የመልካም ስነምግባር ባለቤት፣ ቅንና ተንኮል የሌለባቸው፣ ጥሩ አስተማሪና አስተዳዳሪ የነበሩ፣ ቤተሰባቸውን የሚወዱና የሚያከብሩ፣ ሰውን የማይጎዱ፣ ምንም አይነት ሱስ የሌለባቸውና ሙስናን የሚጸየፉ ወዘተ... የሚሉ ናቸው፡፡ እኔም ከሞላ ጎደል በነዚህ የሰውየው ባህሪያቶች እና ገለጻዎች እስማማለሁ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሰሞኑን በፋርቹን ጋዜጣ እና በቪኦኤ ራዲዮ ጣቢያ በአርባ ምንጭ የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት (አሁን አርባ ምንጭ ዩንቨርስቲ) ሁለት የቀድሞ የስራ ባልደረቦቻቸው (መምህራን የነበሩት ዶክተር ዮሴፍና ዶክተር ስለሺ በቀለ) እና አንድ የቀድሞ ተማሪ (አቶ ኤርሚያስ) ስለዚሁ ጉዳይ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ እነዚህም አስተያየቶች ስለ አቶ ኃይለማርያም ጠንካራና በጎ ጎኖች የሚያወሱ ሲሆኑ አሁንም የዚህ ፅሑፍ ጸሐፊ ከሞላ ጎደል በተሰጡት አስተያየቶች ይስማማባቸዋል፡፡

እንደማንኛውም ዜጋ እና የርሳቸው የቀድሞ ተማሪ በአቶ ኃይለማርያም ሹመት እኔም በበኩሌ ከመገረምም አልፌ ከተደሰቱና የለውጥ ጭላንጭል ከተያቸው ወገኖች ውስጥ አንዱ ነኝ፡፡ ከባለሙያነታቸውም፣ የአካደሚ ሰው ከመሆናቸው፣ በቅርብም ቢሆን በፖለቲካውና በመንግስት ስልጣን ከነበራቸው ተሳትፎ እና ልምድ እንዲሁም ከዳራቸው /Background/ አንጻር ይቺን ሃገር ሊመሩ፣ ሰላም እና ለውጥ ሊያመጡና ሊያሳድጉ ይችላሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ከዚህም አንጻር ይህንን ጽሑፍ በዚህ ሰዓት መጻፍ አልፈለኩም ነበር፡፡ ነገር ግን በምዕራቡ ዓለምም እንደተለመደው አንድ መሪ ወደስልጣን ሲመጣ ለዚያውም የዘጠና ሚሊዮን ህዝብ መሪ ቀርቶ እያንዳንዱ በጎና ደካማ ጎን ከልጅነት ጀምሮ አስተዳደጉና ገጠመኙ ባህሪና የሥራ ፀባይ በአጠቃላይ የህይወት ታሪኩ በደንብ ተደርጎ እንደሚዳሰስና ትንተና እንደሚሰጥበት እናውቃለን፡፡

እኔም የዚህ ጽሑፍ ጻሐፊ አቶ ኃይለማርያምን ከ1985-1989 ዓ.ም ለአምስት አመታት ያህል በተማሪነት የማውቃቸው ስሆን ከላይ ከዘረዘርኳቸው በብዙ ሰዎች ከተባሉት በጎ ጎኖች ውጭ ያሉትን እና በተለያዩ ሚዲያዎች ብዙ ያልተነገሩትነና ያልተባሉትን ለመጻፍ እወዳለሁ፡፡

## II. የአቶ ኃይለማርያም ወደ አካዳሚክ ስልጣን አመጣጥ፡-

አቶ ኃይለማርያም የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በ1984 ዓ.ም ከፊላንድ ታምፒር /Tampere/ ዩኒቨርስቲ በውሃና አካባቢ (ሳኒተሪ) ምህንድስና /Water & Environmental (Sanitary) Engineering/ ይዘው እንደተመለሱ በወቅቱ በአርባ ምንጭ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ዲን በነበሩት እና በ1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት ደግሞ የኢዴፓ ሊቀመንበር እና የቅንጅት ፓርቲ ም/ሊቀመንበር በነበሩት በዶክተር አድማሱ ገበየሁ ረዳት ሬጅስትራር ሆነው ተሹመዋል፡፡

በዚያን ጊዜ የኢንስቲትዩቱ ሬጅስትራር የነበሩት የስታስቲክስ ምሩቅ የሆኑት አቶ የማነ ናቸው (አሁን በሕይወት የሉም)፡፡ እንደ አቶ ኃይለማርያም በተመሳሳይ ጊዜ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ከእንግሊዝ ሀገር ይዘው የመጡት አቶ አባቡ ተክለማርያም (አሁን ዶክተርና በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ) እና አቶ ስለሺ በቀለ ( አሁን ዶክተርና አፍሪካ ህብረት ውስጥ የሚሰሩ) በምክትል ዲንነት እና በምርምርና ህትመት /Research & Publication/ አስተባባሪነት

በቅደም ተከተል ተሹመዋል፡፡ ይህ ሹመት በወቅቱ ረዳት ሬጅስትራር ለነበሩት ለአቶ ኃይለማርያም ስላልተዋጠላቸው ቅሬታን ፈጥሮባቸዋል፡፡ አንድም በትምህርት ደረጃም ሆነ በሥራ ልምዳቸው /Seniority/ ከማይበልጧቸው የሚያንስ ሹመት ማግኘታቸው ሲሆን ሌላው ደግሞ የብሔር አድልዎ ተደርጎብኛል በሚል ስሜት ነው፡፡ ዶክተር አድማሱ የሚፈልጋቸውንና የራሱን ብሔር ተወላጆች (አማራ) ሲሾም እኔ ከደቡብ አካባቢ ስለሆኩ ጎደቶኛል በሚል ስሜት መሆኑ ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አቶኃይለማርያም ዶክተር አድማሱ ከኢንስቲትዩቱ የሚነሳበትን መላና ዘዴ ይፈልጉ ነበር፡፡ በኋላም በታህሳስ ወር 1985 ዓ.ም በወቅቱ የተ.መ.ድ ዋና ፀሐፊ የነበሩት ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሪ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ተከትሎ በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች በተነሳው የተማሪዎች አመጽ ዶክተር አድማሱ አመጹን ደግፈሃል እና አበረታተሃል በሚል ምክንያት ከዲንነቱና ከሃላፊነቱ ተንስቷል፡፡ አመጹን ከማይደግፉ ተማሪዎች ኢንፎርሜሽን በመውሰድና ለደህነንትና ፖሊስ አካላት በማቀበል (ዶክተር አድማሱ ለአንድ ቀን ታስሮ ነበር) ዶ/ሩ ከቦታው እንዲነሳና እንዲባረር ያደረጉት አቶ ኃይለማርያም እና በወቅቱ የኢንስቲትዩቱ አስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ የነበረ አንድ የህወሀት አባል ናቸው፡፡

በዶክተር አድማሱ ምትክ በወቅቱ ምክትል ዲን የነበሩት አቶ አባቡ ተጠባባቂ ዲን ሆነው ሲሾሙ አቶ ሃለማርያም ደግሞ ምክትል ዲን ሆኑ፡፡አሁን የአቶ ኃይለማርያም ዋናው የስልጣን ግልበጣ ሴራ ይጀምራል፡፡ አቶ አባቡ ለትምህርታዊ ወርክሾፕ ወደ እንግሊዝ ሃገር በሄዱበት ጊዜ አቶ ኃይለማርያም በሰሜን ኦሞ ዞን እና በክልሉ ባለስልጣናትና ቁልፍ የፖለቲካ ሰዎች በመታገዝ እሳቸው የአካባቢው ብሔር ተወላጅ እያሉ እንዴት የሌላ ብሔር (አማራ) ሰው ስልጣን ይይዛል ብለው ሎቢ /Lobby/ በማስደርግና በተደረገ ማግባባት ወ/ሮ ገነት ዘውዴ (በወቅቱ የትምህርት ሚኒስትር) አቶ አባቡን በማውረድ አቶ ኃይለማርያምን የኢንስቲትዩቱ ዲን ያደርጎቸዋል፡፡ ይህም የሆነው አቶ አባቡ በውጪ ሃገር በነበሩበት ጊዜ ሲሆን ወደ ኢንስቲትዩቱ ግቢም እንደተመለሱ ስብዕናቸውን በሚነካ መልኩ በአንድ ቀን ውስጥ በኃላፊነት ይዘውት የነበረውን መኪና እንዲያስረክቡና የዲኑን መኖሪያ ቤትም ለቀው እንዲወጡ በቀደሞ ምክትላቸው በአቶ ሃይለማርያም ታዘው ነበር፡፡ ይህም አቶ ሃይለማርያም ምን ያህል ሥልጣን እንደሚወዱና ለሥልጣን ጓጉተው እንደነበር ያሳያል፡፡

በነገራችን ላይ አቶ ሃይለማርያም ፖለቲከኛ ለመሆን ያሰቡትም፣ ግኝኙነትም የጀመሩት፣ ወደ ፖለቲካ ውስጥም የገቡት በዚሁ አጋጣሚ ነበር፡፡ ይህም ማለት ማለትም በኢንስቲትዩቱ ውስጥ ያለውን የስልጣን ፍትጊያ ለማሸነፍ እና ዲንም ለመሆን ከነበራቸው ፍላጎትና እሱንም በድል ለመወጣት ከደቡብ ፓርቲ (ደኢህዴን) ድጋፍ ለማግኘት ብለው ነበር፡፡ በተጨማሪም የዞኑና የክልል ፖለቲከኞች አቶ ኃይለማርያም የዲንነቱን ቦታ እንዲያገኙ በወቅቱ እጅግ ከፍተኛ ድጋፍ አድርገውላቸዋል፡፡ ስለዚህ አቶ ኃይለማርያምን ፖለቲካ ውስጥ ያስገባቸው ዋናው ምክንያት እና ዛሬ ለደረሱበትም ትልቅ ቦታ መነሻ የሆነው ያ የኢንስቲትዩቱ ዲን የመሆን ፍላጎታቸው ነበር ማለት ይቻላል፡፡

## III. የአቶ ኃይለማርያም የአመራር መንፈስ

የኢንስቲትዩቱ ዲን ከሆኑ በኋላ ስልጣናቸውን በደንብ ለማደላደል የሚፈልጓቸውንና የሚቀርቧቸውን ሰዎች በተዋረድ ይሾሙም ነበር፡፡ አቶ ኃይለማርያም የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ መሆናቸው የሚታወቅ ሲሆን አባል የሆኑበት ቤተክርስቲያን ግን ከዋነኞቹ ወንጌላዊ አብያተክርስቲያናት ለየት ያለና በሦስቱ ስላሴዎች የማያምን የኢትዮጵያ ሃዋርያ (Apostolic) ቤተክርስቲን (በተለምዶ only Jesus የሚባሉት) ነው፡፡ እናም በወቅቱ ስልጣን ሲሰጡ የሃዋርያ ቤተክርስቲያን አማኝ ካለ ቅድሚያ ይሰጡና ያዳሉ ነበር፡፡ እርሳቸውም አብዛኛውን ጊዜ የሚያስተምሩት የ/Water supply & West Engineering /ኮርስ ሲሆን እኔም በእሳቸው ሁለት ኮርስ ተምሬአለሁ፡፡ በጣም ጎበዝና ጥሩ የአካደሚክ ዕውቀት የነበራቸው ሰው እንደሆኑ ልመሰክርላቸው እወዳለሁ፡፡ ነገር ግን አንድ የማልክደው ሀቅ ቢኖር በአስተዳደጋቸው ይሁን፣ ከአሁን በፊት በደረሰባቸው ነገር ለሰሜን አካባቢ ሰው (በተለይ ለአማራ ብሔር ተወላጆች) ትንሽም ቢሆን ጥላቻ ነበራቸው፡፡ ምዕራባውያን የበታችነት ስሜት(ኢንፌሪየሪቲ ኮምፐሌክስ) እሚሉት አይነት ነገር ይሰማቸው ነበር፡፡ ይህንንም በተለያየ አጋጣሚ ያንጸባርቁት ነበር፡፡ ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ የቀድሞ ገዢዎች፣ ሰሜነኞች፣ ጨቋኞች እያሉ የጨቆኞና የተጨቋኝ አይነት ክርክር /Argument/ ያበዙ ነበር፡፡ በተጨማሪም በአስተዳደራቸው ጊዜም ቢሆን የተወሰነ አምባገነንነት ይታይባቸው ነበር፡፡ ሌላው ደግሞ በኢንስቲትዩቱ ባህል መሰረት በየአመቱ ከ1-3ኛ ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ለረዳት አስተማሪነት ይቀጠራሉ፡፡ አቶ ኃይለማርያም ዲን ከሆኑ በኋላ ግን መቀጠር ያለበት እሳቸው ከሚፈልጉት ብሔር ውጪ ከሆነ በተለያየ ዘዴ እንዳይቀጠሩ ያደርጉ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ብዙ እዛው ቀርተው ማስተማር የነበረባቸውና ዛሬ ትልቅ ቦታ የደረሱ የቀድሞ ተማሪዎች ምስክር ናቸው፡፡ ይህም ምን ያህል አቶ ሃይለማርያም እርሳቸው ጨቋኝ ነበሩ ከሚሏቸው ብሄሮች ጋር ችግር እንደነበረባቸው ያሳያል፡፡

በተጨማሪም አቶ ኃይለማርያም ዲን በነበሩበት ወቅት መታየትም የሚፈልጉ ሰው ነበሩ፡፡ በተቻላቸው መጠን ዜና ሊሆን የሚችል ነገር እየሰሩ በተለያየ አጋጣሚ ስማቸውንና አርባምንጭ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትን በኢቲቪና በሬዲዮ እንዲታወቅ ያደርጉ ነበር፡፡ ይሄም በደቡብ ፓርቲና በመንግስት ባለሥልጣናት አይን ውስጥ እንዲገቡና ለፓርቲው ከፍተኛ ሃላፊነት እንዲመለመሉ አድርጓቸዋል፡፡ ከዚያም በኋላ ነው የደቡብ ክልል ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው የተሾሙት እና የፓርቲውም ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የሆኑት፡፡

## IV. አቶ ኃይለማርያም ያለፉባቸው ፈተናዎችና ያጋጠሟቸው ተግዳራቶች

አቶ ኃይለማርያም በህይወታቸው ፈጽሞ ሊረሱት የማይችሉትና ምናልባትም እግዚአብሔር ረድቷቸው የተወጡት፣ ያን ወቅት በብቃት ባያልፉ ኖሮ ይቅርና የቀድሞ የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት ከዚያም አልፎ የአሁኑ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሊሆኑ ቀርቶ ከመምህርነት ሙያቸውና (ነገር ግን ዶክትሬታቸውን ሊይዚ ይችሉ ይሆን እንጄ) ከአርባ ምንጭ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አይወጡም ነበር የሚያስብል አንድ ተግዳሮት ደርሶባቸው ነበር፡፡ እሱም በ1988 ዓ.ም ሁለተኛ ሴሚስተር መጀመሪያ አካባቢ በኢንስቲትዩቱ የተነሳው የተማሪዎች አመጽ ነው፡፡ ይህም አመጽ በዚያን ወቅት በነበረው የአቶ ሃይለማርያም አስተዳደራዊና የኢንስቲትዩቱ አካዳሚካዊ ችግሮች ላይ ተንተርሶ የተቀሰቀሰ ሲሆን አቶ ኃይለማርያምን፣ ምክትላቸውን እና የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊውን ከስልጣን እንዲለቁ የሚጠይቅ ነበር፡፡

በወቅቱ ተማሪዎች በፖሊስ ተንገላተዋል፡፡ ከ20 የማያንሱ በተማሪ የተመረጡ መሪዎች ለ21 ቀን በአርባ ምንጭ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ እስርቤት ታስረዋል፡፡ አቶ ኃይለማርያም የዞኑን አስተዳዳሪና ፖሊስ ሃላፊ እያመጡ የተማሪ መሪዎችን አስፈራርተዋል፡፡ የተማሪዎቹን ህጋዊና አግባብ ያለውን ጥያቄን በማጣመም ተማሪዎቹ ምንም ዓይነት ችግር የለባቸውም፣ ችግራቸው ሌላ ብሔር (ወላይታ) አይገዛንም፣ ዲን አይሆንም ብለው ነው በማለት ተማሪውን ከአካባቢው ህበረተሰብ ጋር ለማጣላትና ለማጋጨት ሞክረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪው በረብሻው ምክንያት ግቢውን ለቆ ሲወጣ እንኳን የከተማው ህዝብ እንዳይተባበረው አድረገዋል፡፡ ተማሪው ከግቢው ወጥቶ ወደ አካባቢው ከሄደ ከአንድ ሳምንት በኋላ ትምህርት ሚኒስቴር በሚዲያ ጥሪ አድርጎ ተማሪዎቹ ተመልሰው ወደ ግቢ እንዲገቡ ከተደረገ በኋላ፣ ከትምህርት ሚኒስቴር ዶክተር ተክለሃይማኖትን (በዚያን ጊዜ ምክትል ትምህርት ሚኒስትር) መጥተው ተማሪውን አወያይተውና አረጋግተው ትምህርት እንዲጀመር ሲደርግ፣ የተማሪውን ጥያቄ ባልመለሰ መልኩ ምንም አይነት የኢንስቲትዩቱ ባለስልጣን አቶ ሃይለማርያምን ጨምሮ እርምጃ ሳይወሰድባቸው በስልጣን እንዲቆዩና እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ የዛሬው ጠቅላይ ሚኒስትር ታላቅ ባለውለታ ምናልባትም ዶክተር ተክለሃይማኖት ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ወቅቱ ብዙ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ያምጹ የነበረበት ጊዜ ሲሆን ትምህርት ሚኒስቴር ከሞላ ጎደላ የተማሪዎቹን ጥያቄ ለመመለስ የየግቢውን ዲኖችና ፕሬዝዳንቶች ያነሳበት ጊዜ ነበር፡፡ ለምሳሌ ወ/ሮ ገነት ዘውዴ አዳማ ድረስ ሄደው በተማሪዎች ጥያቄ መሰረት የናዝሬት ቴክኒክ ኮሌጅ ዲንን በወቅቱ ከሃላፊነት አንስተዋል፡፡ አቶ ኃይለማርያም ግን ያን ማዕበል በዶክተር ተክለሃይማኖት እገዛና ትብብር አልፈዋል፡፡ ማን ያውቃል ፈጣሪ ይህን ትልቅ ቦታና ስልጣን ስላየላቸው ይሆን?

ከዚህ በተረፈ በተማሪዎች ረበሻ ወቅት አቶ ሃይለማርያም ከስልጣን እንዲወርዱ በጣም ሲጥርና ተማሪዎችን ሲያስተባብር የነበረ አንድ የተማሪዎች መሪ እንደነገረኝ ተማሪው ትምህርቱን ጨርሶ ተመርቆ ከወጣ በኋላ ውጪ አገር የትምህርት እድል ለማግኛት የድጋፍ ደብዳቤ /Recommendation Letter/ እንዲጽፉለት ሲጠይቃቸው ተማሪው ባደረገው ነገር ምንም ቂም ሳይዙና ቅር ሳይላቸው በደስታ ጥሩ የድጋፍ ደብዳቤ ጽፈውለት በዚያም መሰረት በውጪ ሃገር እስኮላር ሽፕ አግኝቶ 2ኛ ድግሪውን ተምሮ እንደመጣ አጫውቶኛል፡፡

## V. ማጠቃለያ

ከዚያ በኃላ በነበሩ ጥቂት አመታት አቶ ኃይለማርያም በኢንስቲትዩቱ ውስጥ ያላቸውን የሥልጣን ማዕከል ያደላደሉበትና በመሀልም እሳቸውን ከአካዳሚክ ሀላፊነት ወደ ፖለቲከኛነት የሚወስዳቸውን ሽግግር የፈጸሙበት ወቅት ነበር፡፡ የተማሪዎቹም አመጽ ከተደረገ ከ3 ዓመት በኋላ አቶ ሃይለማርያምን ዛሬ ወደ ደረሱበትን ስልጣን ትልቅ ቦታ አንድ ብለው ወደጀመሩበት የስልጣን ጉዞ ወደ ደቡብ ክልል ምክትል ፕሬዝዳንት ቢሮ ተሹመው ሄዱ፡፡ ከሐዋሳው ሹመት በኋላ የቆዩበት ሁኔታና ወደአዲስ አበባ ጠቅላይ ሚንስቴር ቢሮ እንዴት ሊመጡ እንደቻሉ እንደቻሉ ከዚያም አሁን እስከተሸሙበት ቁጥር አንድ የሀገሪቱ የሥልጣን እርከን እንዴት እንደደረሱ በዛም ያለፉባቸውን ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ደግሞ ሌላ እንደ እኔ ለማየትና ለመታዘብ እድሉ የገጠመው ሰው ከዚህ ይቀጥልበት፡፡

# ቤተመንግሥቱ ኃይለማርያምን የሚያሠራ ይሆን?

ነብዩ ኃይሉ

ላለፉት 21 ዓመታት የምኒሊክ ቤተመንግሥት ለአንድና ለሁለት ቀን ግፋ ሲልም ለአንድ ሳምንት ካልሆነ ጌታውን አጥቷቸው አያውቅም፡፡ አቶ መለስ በግንቦት ወር በቡድን ስምንት ጉባኤ ከተካፈሉ በኋላ ግን ማንንም አምነው የማይርቁትን ቤተመንግስት በህመም ምክንያት ትተው ብራስልስ ከረሙ፡፡ ህመማቸው እና አማልክቱ ጨክነውም ዳግም ወደ ምኒሊክ ቤተ መንግስት በቁማቸው ሳይመለሱ ቀሩ፡፡ እናም ቤተመንግስቱ ላለፉት ሦስት ወራት ኦና ሆኗል፡፡

አገሪቱን ማን የት ተቀምጦ እንደሚመራት ብዙም ግልጽ ባይሆንም፣ ኃለማርያም ደሳለኝ በተጠባባቂነት አገሪቱን እየመሩ እንደሆነ ሲገለፅ ሰንብቷል፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ባለፈው አርብ መስከረም 4 ተጀምሮ ቅዳሜ መስከረም 5 ቀን 2005 ዓ.ም የተጠናቀቀው የገዢው አብዮታዊ ፓርቲ ምክር ቤት ስብሰባ አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝን በሚቄ ሊቀመንበሩ ምትክ ቢያስቀምጥም፣ ሰውየው እስከወሩ ማገባደጃ ቃለ መሀላ ፈፅመው ወደ ቤተመንግስት አይገቡም፡፡(በዚህ ሳምንት መጨረሻም ይሆናል የሚልም ግምት አለ) ሁኔታው ኢህአዴግ ኃይለማርያምን ቤተመንግስት ከማስገባቱ በፊት ማጠናቀቅ የፈለገው ስራ እንዳለ አመላካች ነው፡፡

ኢህአዴግ ከ21 ዓመት በኋላ ከህወሓት ውጪ የሆነን ግለሰብ ለፓርቲው ሊቀመንበርነት በመሾሙ በፓርቲው የውስጥ ፖለቲካዊ የኃይል አሰላለፍ ላይ ለውጥ መጥቷል ለማለት ያስችላል? የአቶ ኃይለማርያም ፖለቲካዊ ተክለ ስብዕናስ እንደ መሪ ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚያስችይሆን? ለእነዚህ ጥያቄዎች ቀጣዩ ፅሁፍ ምላሽ ለመስጠት ይሞክራል፡፡

## የኢሕአዴግ የኃይል አሰላለፍ ለውጥ አሳይቶ ይሆን?

ኢህአዴግ ላለፉት አመታት ከህወሓት ተፅእኖ ስር ተለይቶ አያውቅም፡፡ የአራት ፓርቲዎች ስብስብነቱም አፋዊ ከመሆን ያለፈ አልነበረም፡፡ ህወሓት ያቀደው፣ ህውሓት ያቦካውና የጋገረውን ተቀብሎ ከማስተጋባት ውጪ ህወሓትን የሚገዳደር አንድም አባል ድርጅት ያልነበረው ኢህአዴግ፣ ለህወሓት አንደኛ፣ ለብአዴን ሁለተኛ፣ ለኦህዴድ ሦስተኛ እንዲሁም ለደኢህዴን የአራተኛነት ደረጃ የሰጠ ውስጣዊ የኃይል አሰላለፍ ነበረው ተብሎ ሲታማ ከርሞአል፡፡

የህወሓትም ሆነ የኢህአዴግ ጭንቅላት ተደርገው የሚወሰዱት መለስ ዜናዊ ከሞቱ በኋላ ግን የኢህአዴግ ውስጣዊ የኃይል አሰላለፍ እንዲቀያየር የሚያስገድድ ሁኔታ ተከሰተ፡፡ ለፓርቲው ቅርብ የሆኑ ወገኖች እንደሚገልፁት ህወሓት በአቶ መለስ ላይ ከተገቢው በላይ በመተማመን ተተኪ ሰው ባለማዘጋጀቱ በኢህአዴግ ውስጥ የነበረውን ተፅእኖ በቀላሉ ለማጣት ተገዷል፡፡ ብአዴን ውስጥ አዳዲስ ፊቶች በፊት እንዲመጡ ባይደረግም ቅሉ ፓርቲው ከአቶ መለስ በኋላ አለቅነቱ ለኔ ይገባኛል የሚል የተሳካ እንቅስቃሴ ማድረጉንም እነዚሁ ወገኖች ያስረዳሉ፡፡ ኦህዴዶች በስልጣን ሽኩቻ ላይ ብዙም አልተሳተፉም፤ ከብአዴን ጋር የነበራቸውን ዘመን ያስቆጠረ የመቀናቀን አዝማሚያ ላለማድረግ የተገደዱ ይመስላል፡፡ አሁን ከሞላ ጐደል ኢህአዴግ ውስጥ ብአዴን ጠንከር ያለ ባይሆንም መግባባት ለመፍጠር የሚያስችል የበላይነት ይዟል፡፡ ኢህአዴግ መንግስት እንዲመሰርት የሚያስችለውን ትልቁን የፓርላማ መቀመጫ የሚያዋጣው ኦህዴድ ሀገሪቱ ያላትን ሁለት ከፍተኛ የስልጣን ማዕረጐች ለማግኘት አለመቻሉ አስገራሚ ባይሆንም በፓርቲው ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመካከለኛ አመራር ላይ እየተጠናከረ ከመጣው በኢህአዴግ ውስጥ ስልጣን ይገባናል የሚል ጥያቄ አንፃር የኦህዴድ አመራሮች ፈተና ውስጥ መግባታቸው አይቀሬ ነው፡፡ ደኢህዴን አቶ ኃይለ ማርያምን ስላስመረጠ ብቻ በኢህአዴግ ውስጥ ያለውን ደረጃ በማሻሻል የበላይነቱን አረጋገጠ ለማለት ባይቻልም ተጠቃሚነቱን አረጋግጧል ለማለት ግን ያስደፍራል፡፡

ይህ በሲቪል አስተዳደር ላይ የተደረገ የአሰላለፍ ለውጥ ሁሉን አቀፍ እንደሆነ ተደርጐ ከተወሰደ እና የህወሓት የበላይነት እንዳበቃለት ከተቆጠረ ግን ስህተት ላይ መጣሉ አይቀርም፡፡ ይህ ስህተት የገዢውን አብዮታዊ ፓርቲ ትክክለኛ ማንነት ካለመረዳት ይመጣል፡፡ በተግባር እንደሚታየው ኢህአዴግ ፍፁማዊ አምባገነንነቱን ለማስጠበቅ የተለያዩ ክንፎችን ዘርግቷል፡፡ አንደኛው የሲቪል አስተዳደር ክንፍ ሲሆን ሁለተኛው ወታደራዊና የደህንነት ክፍል ሲሆን ሦስተኛው የፓርቲውን ኢኮኖሚያዊ የበላይነት የሚያሳየው የንግዱ ክንፍ ነው፡፡ እነዚህ ክንፎች አመጣጥ ነው በሁሉም የበላይነቱን ተቆናጠው የነበሩት ህውሓቶች የመለስን ሞት ተከትሎ ከሌሎቹ ኢህአዴጋውያ በበለጠ ስልጣን በማጣት ስሜት ዙሪያው ቢጨልምባቸውም ኢህአዴግ ግን አሁንም ከቁጥጥራቸው ውጪ አይደለም፡፡

በኢንዶውመንት ስም ባቋዋቋሟቸው የንግድ ድርጅቶች [ህውሓቶች] የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የመዘወር አቅም አላቸው፡፡ የህውሓቶች ዋስትና ይህ ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም በኢህአዴግ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ላይ ከፍተኛ ድርሻ ያለውንና ስርዓቱ እንደ አፈና መሳሪያነት የሚጠቀምበትን ወታደራዊና የደህንነት ኃይል በበላይነት መቆጣጠራቸው ለህወሓቶች በሲቪል አስተዳደሩ ያጡትን የኃይል ሚዛን ያስጠብቅላቸዋል፡፡

በቅርቡ ይፋ የተደረገው ወታደራዊ ሹመት ወትሮም በብሔር ስብጥር ፍትሀዊነት ማጣት የሚታማውን የሀገሪቱ የመከላከያ ሰራዊት የከፍተኛ መኮንንነት ስፍራዎች የህውሓት ሰዎች በበላይነት እንዲቆጣጠሩት ተጨማሪ ሀይል ሰጥቷቸዋል፡፡ ይህ እርምጃ ህውሓቶች ያለብዙ ፍትጊያ ሲቪል አስተዳደሩን እንዲለቁ የተሰጣቸው ማስተማመኛ መሆኑን ለመረዳት አይከብድም፡፡ በብሔር ስብጥሩ ከፍተኛ አለመመጣጠን የታየበት ወታደራዊ ሹመት ኃይለማርያም ቤተመንግስት ከመግባታቸው በፊት በጥድፊያ መደረጉ እና በትግራይ ክልል ብዙሀን መገናኛዎች እየተላለፈ ካለው “ሶስተኛውን የወያኔ እንቅስቃሴ እንጀምራለን” የሚል አንድምታ ካለው መልእክት ጋር ሲዳመር የኢህአዴግ የውስጥ ሽኩቻ ሀገሪቱን ለትርምስ እንዳይዳርጋት ያሰጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አቶ ኃይለማርያም በሚያዋቅሩት ካቢኔ ውስጥም ሆነ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በአማካሪነት ደረጃ ለህውሃቶች ሁነኛ ቦታዎች እንደተዘጋጀላቸው ቃል መገባቱን ከታማኝ ምጮች የተገኙ መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ ይህ ደግሞ ህውሓቶች ጠቅላይ ሚኒስትሩን በቅርብ ርቀት ለመቆጣጠር የሚያስችላቸው እንደሚሆን ይገመታል፡፡ እዚህ ጋር ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ኃይለማርያም ምን ያክል በዙሪያቸው ያለውን የኃይል ሚዛን ትግል አልፈው በራሳቸው ውሳኔ ሰጪነት መስራት ይችላሉ? የሚለው ነው፡፡

## ኃይለማርያም እና ኢሕአዴግ

አቶ ኃይለማርያም በኢህአዴግ ውስጥ የጐላ ደርሻ ካላቸው ግለሰቦች ተርታ የተሰለፉት ከሁለት አመት በፊት የኢህአዴግ ምክትል ሊቀመንበር እንዲሆኑ ሲመረጡ ነበር፡፡ ሰውየው ከአስተዳደር ጋር የተገናኙ ስራዎች ላይ ረጅም አመት የመስራት ልምድ ቢኖራቸውም ከፖለቲካ ተክለ ሰብዕናቸው ይልቅ (technocrat) ገራገር የቴክኒክ ሰውነታቸው ያመዝናል፡፡ ይህንን የሚያረጋግጠውም ከሁለት አመት በፊት በምክትል ጠ/ሚኒስትርነትና ውጪ ጉዳይ ሚኒስትርነት ሲሾሙ “ስራው ላይ ልምድ ስለሌለዎት ለመስራት አይቸገሩም ወይ?” ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት ማላሽ “ከቅርብ አለቃዬ[ከአቶ መለስ] ምክር እየጠየኩ እሰራለሁ” ማለታቸው ነው፡፡ የያኔው ገራገር ፖለቲከኛ ኃይለማርያም ደሳለኝ ዛሬም ፖለቲካዊ ብስለት ያገኙ አይመስሉም፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ሞት ተከትሎ በሰጧቸው አስተያየቶች መለስን በምንም አይነት ሁኔታ መተካት እንደማይችሉ ጠቅሰው ሀገሪቱን “በጋራ” ለመምራት እንደሚጥሩ ተናግረዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ለአንድ ፖለቲከኛ አስፈላጊና ወሳኝ የሆነው በራስ የመተማመንና ራስን ተፎካካሪ አድርጐ የማቅረብ ብቃት ጨርሶ እንደሌላቸው ነው፡፡ ፖለቲካ፣ መተጋገዝ፣ መተባበርና መመካከርን የሚጠይቅ የጋራ ስራ ቢሆንም፣ ሁልጊዜም ቆራጥነትና በራስ የመተማመን ግላዊ ጥንካሬን የግድ ይላል፡፡

የኢትዮጵያ ህገመንግስት ስልጣንን ሁሉ አከማችቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሰጣል፡፡ በመሆኑም አቶ ኃይለማርያም ህገመንግስቱ ሳይሳሻሻል “በጋራ” አመራር ለመስጠት መዘጋጀታቸው የሚያዛልቅ የብልህ ውሳኔ አይመስልም፡፡ “በጋራ” የሚወስኑትም ከማን ጋር እንደሆነ ብዙም ግልጽ አይደለም፡፡ ኢህአዴግ ከነበረው የወንጀልና የመብት ጥሰት ታሪክ እና አሁንም ሊወስዳቸው በሚችላቸው አደገኛ እርምጃዎች ፈጠነም ዘገየ በፍትህ ፊት የሚዳኝ ስርአት ከመሆኑ አንፃር አቶ ኃይለማርያም “በጋራ” ውሳኔ ለመስጠት መዘጋጀታቸው የኋላ ኋላ ጦስ ተቀባይ ሊያደርጋቸውም ይችላል፡፡ አምባገነንና ወንጀለኛ ስርዓትን መምራት የሚያስከፍለውን ዋጋ ሳያገናዝቡ “መለስ የጀመሩትን” እንደሚያስቀጥሉ ቃል መግባታቸው ከቀደመው የአቶ መለስ አገዛዝ ያልተሻለ አገዛዝ እንደሚኖራቸው አያጠያይቅም፡፡

የሦስተኛው አለም ፖለቲካ በአብዛኛው በጠንካራ አመራር (Bold leadership) ላይ የመመስረት ታሪክ እንደመያዙ፣ ኢህአዴግ ከጅምሩ በሴራ የታሸ ፖለቲካን ከማዘውተሩ እና የኢትዮጵያ ወቅታዊ ፖለቲካዊ ውጥረት ላይ ያለ ከመሆኑ አንጻር የአቶ ኃይለማርያም ፖለቲካዊ ተክለ ስብዕና ፈተና ውስጥ መግባታቸውን ለመገንዘብ አያስቸግርም፡፡

## የኃይለማርያም ፈተናዎች

ኢህአዴግ አቶ ኃይለማርያምን ወደ ፊት ያመጣበት ሂደት በፓርቲው የጋራ መግባባት ላይ የተመሰረተ ቢሆንም የኦህዴድ ተመጣጣኝ ቦታ አለማግኘት እንዲሁም የደህንነትና የወታደራዊ ስልጣኖች ተከማችተው ለህወሓት መሰጠታቸው ጊዜ ጠብቀው እንደሚፈነዱ ቦንቦች የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

ኦህዴድ በአቶ ኃይለማርያም ካቢኔ የሚሰጠው ቦታ በአመራሮቹና በፓርቲው መካከለኛ አመራሮች መካከል እየተባባሰ ያለውን አለመግባባት ሊያረግበው የሚችል አይመስልም፡፡ በመሆኑም ኦህዴድ ከስድስት ወር በኋላ በሚደረገው የኢህአዴግ ጠቅላላ ጉባኤ ምን አይነት አቋም እንደሚወስድ ለመገመት አስቸጋሪ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ህገመንግስት ለጠ/ሚኒስትሩ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥነት ስልጣንን ያጎናፅፋል፡፡ አቶ ኃይለማርያም ከመከላከያ ሰራዊቱ አዛዦች ጋር ቅርበት ያላቸው ያለመሆኑ፣ የህውሓት ከኢህአዴግ ኃላፊነት መራቅን ተከትሎ ፖለቲካዊ ውሳኔዎችን በወታደራዊና በደህንነት መዋቅር የመቃወም አዝማሚያ ሊከሰት የመቻሉ አጋጣሚ አይኖርም ማለት የማይቻል ነው፡፡

አለም አቀፉ ማህበረሰብ የኃይለማርያምን ወደ ማማው መውጣት እንደ በጐ ጅማሮ መቁጠሩ የማይቀር ቢሆንም ሰውየው በቂ ዲፕሎማሲያዊ እውቀትና የዳበረ ልምድ ያላቸው ስላልሆኑ የአቶ መለስን ያክል የፋይናንስ ድጋፍ በማግኘት ስራቸው በመቆም ላይ ያሉትን የአባይ ግድብንና ሌሎች ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ለማስቀጠል መቸገራቸው የማይቀር ነው፡፡

ኢትዮጵያ ያለችበት የአፍሪካ ቀንድ ቀጠና ያልተረጋጋና በርስ በርስ ጦርነቶች እንዲሁም በተጐራባች ሀገሮች መሀከል በቋፍ ላይ ባሉ ግጭቶች የተወጠረ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥም ነፍጥ ያነገቱና በጐረቤት ሀገራት የሚደገፉ ቡድኖች የመኖራቸው ጉዳይ፣ የኢትዮጵያ ጦር ሱማሌ ውስጥ ከመገኘቱና ከኤርትራ ጋር ካለው ወታደራዊ ፍጥጫ ጋር ሲዳበል በየትኛው ወቅት ምን ሊከሰት እንደሚችል ለመተንበይ አስቸጋሪ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያለው ከቁጥጥር ውጪ የሆነ የዋጋ ግሽበት እና ከፍተኛ የስራ አጥ ቁጥር፣ በአፈና እና በግድያ ያልበረደው የኢትዮጵያውያን የነፃነትና የመብት ጥያቄ እንዲሁም የኢህአዴግ መንግስት በሃይማኖት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የመግባት አባዜ ያስጀመረው የሙስሊሞች የተደራጀ ተቃውሞ ትክክለኛ ምላሽ የማያገኙ ከሆነ ሊያቀጣጥሉ የሚችሉት ስርአቱ በምንም አይነት መንገድ ሊወጣው የማይችለው ህዝባዊ ንቅናቄ ሊፈጥር እንደሚችል ለመገመት ነብይነት ግድ አይልም፡፡

ከላይ ከተብራሩት ተጨባጭ ፈተናዎች አንፃር የምኒሊክ ቤተመንግስት ለአቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የምቾት ስፍራ ሊሆንላቸው የሚችል አይመስልም፡፡

# ዘመቻ ገለአድ

በታምራት ተስፋዬ

ሰከንዶች ደቂቃን፣ ደቂቃ ሰዓትን፣ ሰዓት ቀናትን እየፈጠሩ ይኸው ዛሬ ላይ ደረስን።

ዛሬ ትላንት አይደለም፤ ትላንት የዓለምን ሁኔታ ለመተንበይ የነቢይነትን ሚና መጫወት አይጠበቅብንም ነበር። ትላንት የዓለም ሁኔታ በአዝጋሚ ለውጥ ውስጥ ከመሆኑም በላይ ዓለም ለስር ነቀል ለውጥ የተጋለጠች አልነበረም። ዛሬ ሁሉ ነገር ከመለወጡ የተነሳ ነገን ለመተንበይ የማይቻልበት ሁኔታ ላይ ተደርሷል። የማትጨበጠውን ዓለም ለመረዳት ሀገራችን ባለፉት ሦስት ወራት ያሳለፈውን ሁኔታ ማሰብ ብቻ በቂ ነው። ለዛሬም የሰሞኑ ዓቢይ ክስተት የሆነውን ፖለቲካዊ ለውጥ እስኪ ትንሽ አብረን እንየው።

በነገራችን ላይ ገለአድ ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰ የተራራ ስም ሲሆን ጌዴዮን ደፋር እና ፈሪ ወታደሩን የለየበት ቦታ ነው። እንደሚታወቀው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ከሰሞኑ ኳታር ደሃ ላይ ሰንብተው ተመልሰዋል። ከዓመታቶች በፊት ኳታር ከኤርትራ ጋር ባላት ቅጥ ያጣ ግንኙነትና ተዛማጅ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክ ግንኙነቷን ከማቋረጧም በላይ የጐሪጥ መተያየት ደረጃ ላይ ደርሰው እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትራችን ከሦስት ወር በፊት ራዕይ ስለማስቀጠል እና ራዕይ ስላለመበረዝ አበክረው ሲገልጹልን የነበረ ቢሆንም ቃላቸውን ጠብቀው ለመዝለቅ ሦስት ወር እንኳ ሳይሞላ መንታ መንገድ ላይ የቆሙ ይመስላል። የኳታሩ ጉዞ ምን ዓይነት ፖለቲካዉ ተግዳሮት አለው? እውን ጠቅላይ ሚኒስትሩ የገለአድን ተራራ መውጣት ጀምረው ይሆን? ከጉዞው በስተጀርባ ሀገራችን ምን ትጠ ብቃለች? እስኪ ትንሽ እንየው፡-

## ራዕይ በማስቀጠልና በመበረዝ መሐል

መበረዝና መደለዝ የሚሉ ቃላቶች እንደዛሬው የካድሬ መዝገበ ቃላቶች ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ከጠጅና ከፈተና ወረቀት ያለፈ ጥቅም ላይ ለመዋል ዕድል አላገኙም ነበር። ሟች ጠቅላይ ሚኒስትርን መለስ ተከትሎ ተተኪው ጠቅላይ ሚኒስትር ‹የመለስን ራዕይ ሳይበረዝና ሳይደለዝ እናስፈጽማለን› ካሉ በኋላ እስከ ታችኛው የእዝ ሰንሰለት ድረስ ዓረፍተ ነገሩን በየቦታው መናገር ፋሽን ከመሆኑም የተነሳ እነዚህን ቃላቶች ሳያስገቡ አራት ነጥብ ላይ መድረስ እንዳልተቻለ በግልፅ እየታየ ይገኛል። መለስ የኤርትራ ተቃዋሚዎችን በማደራጀት ሻእቢያን ለማጥፋት ሲሞክሩ እንጂ በኳታር ትከሻ ላይ ከሻእቢያ ጋር የመደራደር ራዕይ እንደነበራቸው ለመመስከር ምስክር ማስቆጠር አይጠበቅብኝም። እንግዲህ እዚያ ጋር አንደጥፋት ሊቆጠር ይችል የነበረው በነበረው ራእይ እቀጥላለሁ የሚል አስተሳሰብ ቢኖር ይመስለኛል። ዓለም በፈጣን የለውጥ ሂደት ውስጥ ሆና በትላንት ራዕይ ዛሬን አልፋለሁ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። በዚህ ወቅት እንኳን ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ወ/ሮ አዜብም ከራእይ በራዡች መሐል አንዷ ቢሆኑ አይገርመኝም። ዓለምአቀፋዊ ፖለቲካ ለመተንበይ የማይቻለበት ሁኔታ ላይ ተደርሰዋል። ይመስለኛል የላይኛው አመራር በቀድሞ አመራር ዝግ የነበሩትን አንዳንድ ሁኔታዎች ለማስተካከል እየሞከሩ ይገኛሉ። ከነዚህም ውስጥ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የዶሀ ጉዞ አንዱ ሊሆን ይችላል፤ የገባው መበረዝና መሰረዝ ያለበትን ሲሰርዝና ሲበርዝ በሽምደዳ ዕውቀት ላየ የታነፀው የወረዳና የቀበሌ ካድሬ ራዕይ ስላለመሰረዝና ስላለመደለዝ ይዶሰኩራል ምክንያቱም ይህ ፖለቲካ ነው።

## ዶሀ ምን ተገኘ?

ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ ኳታር የሁለትዮሽ ግንኙነቱን በንግድ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ዘርፎች ለመነጋገር ከኳታር ባለሥልጣኖች ጋር ተገናኝተው ተወያዩ የምትለው ዜና ኢቲቪ ሳጥን ውስጥ ትቀመጥልንና አንኳር ጉዳይ የሆነው የኤርትራ ጉዳይ ላይ መወያየት ይሻላል። አሁን ባለንበት ጊዜ በኢትዮጵያና በኤርትራ መሐል ማንኛውንም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለማድረግ ከኳታር የተሻለ አማራጭ ገበያው ላይ ማግኘት አይቻልም። እንደሚታወቀው ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሞት በኋላ ኢትዮጵያ የማሊያ ላውጥ በማድረግ በሯን ለድርድር የከፈተች ይመስላል። ይህን ሐሳቤን ከሚያጠናክሩልኝ አንዱ በመለስ ጊዜ በኮብራ ሀዋሳና ባሕር ዳር ሲምነሸንሹ የነበሩት ኢትዮጵየ ውስጥ የሚገኙት የኤርትራ ተቃዋሚዎች በአሁን ወቅት ችላ ከመባላቸውም በላይ ባሕር ዳር ላይ ለተቃዋሚዎቹ ፕሮፓጋንዳ ይረዳ ዘንድ ሊቋቋም ታስቦ የነበረው የሬዲዮ

ጣቢያ ግንባታ ለጊዜው ቆሟል፡፡ ይህም ኢትዮጵያ በኳታር አማላጅነት ከኤርትራ ጋር ሰላም ለማውረድ መፈለጓን ያሳብቅባታል፡፡

## ኤርትራ ምን አለ?

ከዐሥራ አምስት ዓመት በኋላ በኢትዮጵያ ጎትጓችነት ለማድረግ የታሰበው ስምምነት ሦስት ነገሮችን ታስቦ የተገባበት ይመስለኛል፡፡

**ሀ/ ዘላቂ ሰላም**

ኢትዮጵያና ኤርትራ ከሦስት ዓመት ደም አፍሳሽ ጦርነት በኋላ በኢትዮጵያ አሸናፊነት ቢጠናቀቅም በስተመጨረሻ ባደረጉት የገላጋይ ፍርድ ቤት ክርክር የጦርነቱ መንስኤ የሆኑት ውስጥ ዋነኛዋ የባድመ ቦታ ለኤርትራ በፍርድ ቤቱ መወሰኑ ይታወሳል፡፡ ሆኖም መዘዙ ብዙ ዋጋ ስለሚያስከፍል እስከ ዛሬ ድረስ በቦታው ላይ ሰላም ሳይወርድ ቆይቷል፤ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ግን ኢትዮጵያ የፍርድ ቤቱን ስምምነት ለመቀበል የተዘጋጀች የሚመስል መልእክት ከመንግስት ኮምኒኬሽን ኃላፊ ከሆኑት ከአቶ በረከት ስምኦን ሰምተናል፡፡ አቶ በረከት ስምኦን ለኤርትራ ሬድዮ የፍርድ ቤቱን ፍርድ ለመቀበል መዘጋጀታቸውን ከነገሩን አንድ ወር እንኳ አልሞላውም፡፡

መቼም ሰላም ማውረድ መልካም ሆኖ ሳለ ቁምነገሩ ግን የኤርትራን ጥያቄ አለማወቅ ላይ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በእውነቱ የኤርትራ ጥያቄ የመሬት ጥያቄ አይደለም፤ የኢኮኖሚና የበላይነት ጥያቄ እንጂ፤ የኢትዮጵያ መንግስት ባድሜን ለኤርትራ ሰጥቼ ሰላም አመጣለሁ ብሎ ካሰበ በእውነት ትክክለኛ ነጥቡን አላገኘውም ማለት ነው፡፡ አንድ እርግጠኛ የምሆነው ነገር ቢኖር ኤርትራ ወደዚህ ጨዋታ በምንም ዓይነት ሁኔታ እንደማትገባ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጨዋታ ኢትዮጵያን እንደምታሸንፍ ታውቃለች፡፡ ኢሕአዴግ መሬት በመስጠት መጥፎ ታሪክ እንደሌለው ገና ድሮ ገብቷታል፡፡ ሻእቢያ የኢትዮጵያን ጠላትነተ ለሁለት ክፍሎ ያየዋል፡፡ አንደኛውና ዋነኛው ጠላቴ የትግራይ ሹማምንት ብሎ ሲያስብ ቀሪውን የኢትዮጵያን ክፍል በሁለተኛነት ያስቀምጠዋል፡፡ ሻእቢያ ኤርትራን የአፍሪካ ሲንጋፖር አድርጋለሁ ብሎ ሲያስብ ግብአቶችንና (Input) የሰው ጉልበት (labor) በትግራይ እንደልቤ እያፈስኩኝ ያመረትኩትን እንደ ልቤ ትግራይ ላይና የተቀረው ኢትዮጵያ ላይ አየሸጥኩኝ ምናምን የሚል እቅድ ይዞ ወደ ሜደው የገባ ሲሆን ይህን ኢፍትሐዊ ንግድ ያስቀሩብኝ የትግራይ ሹማምንት ነው ብሎ ቂም ይዞ እንደነበርና የመጀመሪየውን የግፍ ዕዋ በትግራይ ውስጥ በሀይደር ትምህርት ቤት ላይ ያደረገው ግፍ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው ፡፡ ሻእቢያ መቼም ቢሆን በተረጋጋችው ኢትዮጵያ ውስጥ የሲንጋፖር ሕልሙን ማሳካት አይቻለውም፡፡ ኤርትራ ሲንጋፖርን ለመሆን ኢትዮጵያ ሩዋንዳን በማድረግ ብቻ ነው ብሎ ገና ድሮ ደምድሟል፡፡ ስለዚህ በዚህ አመለካከት መሠረት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ከዶሀ መልካም ነገርን ይዘው ተመልሰዋል ለማለት አይቻልም፡፡

**ለ/ እሾህን በእሾህ**

የጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማርያም የዶሀ ጉዞ ሁለተኛው ምክንያት እንግዲህ ከኤርትራ ጋር በመስማማት የኢትዮጵያ ተቀዋሚዎችን ከጨዋታው በዜሮ ማስወጣት ይመስለኛል፡፡ የእሾህን በእሾህ ጨዋታ በሀገራችን ከጥንት ጀምሮ ሲተገበር እንደነበር ይታወሳል፡፡ ኢሕአፓን በመኢሶን፣ ሕወሓትን በኢዲዮ እንዲሉ.... ኢሳትን በኢቢኤስ... ተስፋዬ ገብረ አብን፣ በመስፍን ነጋሽ እንዲሉ... ኢሕአዴግ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ መጠናከራቸውና አስመራ ላይ መክተማቸውን የጠረጠረ ይመስላል፡፡ በእርግጥ ላለመስማማት ተማምለው የነበሩ ከሀገር ውጭ የሚገኙ ተቃዋሚዎች ከሌላ ጊዜ በተለየ ሁኔታ የመተባበር ሁኔታ እየታየባቸው ይገኛል፡፡ በኢትዮጲያ ውስጥ በትግል ታሪካቸው አንጋፋ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ የሆነው ኦነግ እንኳን የፖሊሲ ለውጥ በማድረግ ከሴማውያን ጋር ለመስራት በሩን ክፍት ማድረጉ ለኢሕአዴግ ቁጣዩ ፈተና ምን እንደሚሆን ከወዲሁ ለመተንበይ አያስቸግርም፡፡ በዚህም ነጥብ ላይ ሻእቢያ ለድርድር በሩን አስካልከፈተ ድረስ የዶሀው ጉዞ ከወዲሁ በስኬት እንደማይጠናቀቅ ግልፅ ያደርገዋል፡፡ ይልቅስ የእሾህን በእሾህ ጨዋታን ወደ ጉን አድርጐ መንግሥት የሀገራችንን ችግር በሀገራችን እንፍታው በማለት መቀነቱን ጠበቅ አድርጐ ብሔራዊ እርቅ ቢያደርግ ይመረጣል፡፡ እሾህን በእሾህ መርሕ ይዞ የገለአድን ተራራ መውጣት ከባድ ከመሆኑም በላይ የጌዲዮን ወታደር ለመሆን ትንሽ ያስቸግራል፡፡

ሐ/ የግብፅ ጉዳይ

ሦስተኛው የዶህ ጉዞ ከዓባይ ግድብ ጋር ተያየዞ ከግብፅ ጋር የሚገናኝ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ግብፅ የዓባይ ግድብ እውን እንዳይሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ትንኮሳ ታደርጋለች ብሎ መንግስታችን የተጨነቀ ይመስለኛል፡፡ ግብፅ የውክልና ጦርነት (Proxy war) ኤርትራን ተጠቅማ ታደርጋለች የሚለው መላምት አንዱ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ግብፅ ግዙፉን አየር ኃይሏን ተጠቅማ የኤርትራ አየር ላይ እንደልቧ እየተንሳፈፈች ታጠቃናለች የሚለው ሌላው እሳቤ ይመስለኛል፡፡ ይህንንም ለመከላከል ኢትዮጵያ በኳታር አማካኝነት ከኤርትራ ጋር ሰላም ለማውረድ አስባለች ማለት ነው፡፡ ይህ መቼም መልካም እሳቤ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያይዞ ቅድመ ዝግጅት በመከላከያ በኩል ማድረግና የቀጥታ ውይይት ከግብፅ ጋር ማድረግ እንደአማራጭ ቢያዝ አይከፋም ባይ ነኝ፡፡ ሚቹ ጠቅላይ ሚኒስትር በአንድ ወቅት የዓባይን ግድብ አስመልክቶ ከግብፅ ስለሚሰነዘረው ሁኔታ ጥያቄ ቀርቦላቸው ሲመልሱ ‹ግብፅ እኛን አትደፍረንም፣ ታውቀናለች› የሚል መልስ መስጠታቸው ትዝ ይለኛል፡፡ በወቅቱ ይህ መልስ ብዙም አልተመቸኝም ነበር፡፡ ከወቅቱ ጋር የተያያዘ መልስ ነው የሚል ግምትም የለኝም፡፡ ድሮ ጦርነት በወኔ ማሸነፍ ይቻል ነበር፡፡ ዛሬ ነገሮች ተለውጠዋል፤ ጦርነት ቴክኖሎጂ ሆኗል፡፡ የላቁ ቴክኖሎጂዎችና ብዙ ገንዘብ ለጦርነት ያፈሰሰ አካል ነው፡፡ የድል ፅዋ ሊጨብጥ የሚችለው፡፡ የቹን ዙ መጽሐፍ ለዛሬ ጦርነት ዋጋ አይኖረውም፡፡ ግብፅ በየዓመቱ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ለመከላከያዋ አሜሪካ እንደምተደጉማት መረሳት የለበትም፡፡ ቴዲ አፍሮ ‹ጋሻው፣ ጉራዴው ቀላ› ሲል በግብፅኛ ‹አሞራ በሰማይ ሲያይሽ ዋለ› የሚል ትርጉም እንዳለው መረሳት የለበትም፡፡ በእርግጥም የግብፅ አየር ኃይል ግዙፍ ነው፡፡ ስለዚህም ጠቅላይ ሚኒስተራችን አብዝተው ወደካይሮ መንዝና ዳፕሎማሲውን ከግብፅ ጋር ማጠንከር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ያኔ ነው ገለአድን መውጣት የሚቻለው፡፡

## የአፍ ወለምታ

ጠቅላይ ሚኒስትራችን በዶሀ ካደረጉት ውስጥ አንዱ ከቀድሞው ደርቢያችን አልጄዚራ ቴሌቪዥን ጋር ያደረጉት ቃለ ምልልስ ይጠቀሳል፡፡ በቃለ ምልልሱ ላይ ወደ አስመራ ለመሄድና ኢሳያስን በአካል ማግኘት እንደሚፈልጉ ተናግረው ሐሳባቸውን ማጠናከሪያ መለስ 50 ጊዜ ኢሳያስን ለማናገር እንደሞከሩ ነግረውናል፡፡ የሳቸውን ፍላጎት በመልካም ባየውም የመለስ ግን የአፍ ወለምታ ትመስለኛለች፡፡ የሀገሬ ሰዎች 10፣ 50 ወይም 100 የሚሉ ቁጥሮችን አብዝቶ ይወዷቸዋል፡፡ ለምን እንደሆነ ባላውቅም አንድም ቀን ትንታኔዎች 49 ወይም 51 ላይ ሆነው አያውቁም፡፡ አ!... ለካ ኢኮኖሚያችን 11% ነው፡፡... በ1992ዓ.ም. የጦርነቱ ማብቂያ አካባቢ ዳሬ ሰላም ላይ መለስና ኢሳያስ ተገናኝተው ነበር፡፡ ኢሳያስም መለስን ለብቻቸው ካላነገርኳቸው ሀገር ይያዝልኝ ቢሉም መለስ ግን ፈቀደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን በዚያ ወቅት የመንግስት ልሳን ከሆነችው እፎይታ መጽሔት ላይ ማንበቤ ትዝ ይለኛል፡፡ ያኔ መለስ ኢሳያስን ቢያናግሩ ኖሮ አዲስ አበባ ላይ ማርክሲስቱ ተወልደ እና ስዬ አብርሃ በወቅቱ በሕወሓት ውስጥ ተከስቶ ለነበረው ክፍፍል ይጠቀሙብታል ብለው መለስ አስበውት ይሆናል፡፡ ከዚያ በኋላ ግን በተለያየ ወቅት መለስ ኢሳያስን ከመንበረ ስልጣኑ እንደሚያስወግዱ ሲዝቱ እንጂ ለድርድር ሲጠይቁ ተሰምተው አይታወቅም፡፡ ስለዚህም የአቶ ኃይለማርየምን ንግግር ለማመን ያስቸግረኛል፡፡

## እንደ ማጠናናቀቂያ

የጠቅላይ ሚኒስትሩን የዶሀ ጉዞ ለሀገራችን መልካም ነገር ይዞ እንዲመጣ ሙሉ ምኞቴ ነው፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ጅማሮ መልካም ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ነገር ግን ዲፕሎሲያዊ ጥረቱ ሀገር ውስጥም መቀጠል አለበት ብዬ አስባሁ፡፡ በተለያዩ ወቅቶች ከመንግስት ጋር ተጣልተው ትጥቅ ያነሱትንም ሆነ በስደት ያሉትን የሀገሪቱ ልጆችን ማወያየትና ወደ ሰላማዊ ፖለቲካዉ ውድድር እንዲገቡ ማሳመን ቀጣይ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ዕቅድ እንዲሆን እመኛለሁ፤ መንግሥት ሲተችበት የነበረበትን ቢያስተካክል እና የኢትዮጵያ ልጆች በአንድ የሚቆሙበትን መንገድ መንግሥታችን ቢያመቻች እመኛለሁ፡፡

# “መክሸፍ” እንደተቃዋሚ ፓርቲዎች

በዘንድሮው የሚሚያ ምርጫ 29 ያህል ፓርቲዎች አንወዳደርም የሚል የጋራ አቋም ይዘዋል፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎቹ ከምርጫ ቦርድ ጋር ለመደራደር ያወጧቸው ዝርዝር ጥያቄዎች ተቀባይነት ባለማግኘታቸው ነው ላለመወዳደር የወሰነው ሲሉም አሳውቀዋል፤ እንደነርሱ አባባል ሚዛናዊ ምርጫ በማይካሔድበት እና እራሱ ምርጫ ቦርድም ሚዛናዊ ባልሆነበት መድረክ ተወዳድሮ ማሸነፍ ስለማይቻል፤ ተወዳድሮ ምርጫ አድማቂ ከመሆን አለመወዳደር ይሻላል፡፡ ኢሕአዴግም የእነዚህ ተቃዋሚዎች በምርጫ አለመሳተፍና መሳተፍ ለኢህአዴግ ትርፍም ኪሳራም እንደሌለው በግልጽ ተናግሯል፡፡ ነገር ግን ተቃዋሚዎቹን አንድ ጥያቄ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል፡፡

## የፓርቲዎች አባላት ጉዳይ

አንድነት ፓርቲ (በተለይ አንዱአለም ከመታሰሩ በፊት በቋሚነት) ምሁራንን እየጋበዙ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሕዝባዊ ውይይቶችን ለማካሔድ ሞክረዋል፡፡ ሰማያዊ ፓርቲም ይህንኑ ፈለግ በመከተል ጥቂት ውይይቶችን አካሄዷል፡፡ በነዚህ ስብሰባዎች ላይ ግን የሚገኙት ሰዎች ቁጥር በዛ ከተባለ አንድ መቶ ቢደርስ ነው የተለየ የሰዎች ቁጥር መጨመር ይታይበት የነበረው የአንድነት ፓርቲ የየሁለት ሳምንቱ ውይይትም በአጭሩ ቀርቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንድነት ፓርቲ ለፖለቲካ እና ሕሊና እስረኞች በወር አንድ ጊዜ የሚያደርገው የሻማ ማብራት ፕሮግራም ላይ የሚገኙት ሰዎች ቁጥር 20 የማይሞላበት ጊዜ አለ፡፡ ይህ ቁጥርም የታሳሪዎችን ቤተሰብ ጨምሮ መሆኑንም ማስታወስ ያሻል፡፡ የሻማ ማብራት ፕሮግራም ማዘጋጀታቸው እና በወር አንድ ጊዜ እስረኞች እንዲታወሱ ማድረጋቸው የሚያስመሰግናቸው ሆኖ በፕሮግራሙ ላይ የሚገኘውን ታዳሚ ቁጥር ማነስ እና ከዕለት ወደ ዕለት እየተመናመነ መሄድ የተሳታፊዎችንም የአዘጋጆችንም ተነሳሽነት እንደሚፈታተነው እሙን ነው፡፡

እነዚህ ፕሮግራሞች ላይ ሕዝቡ የማይገኝባቸውን ሁለት ዐበይት ምክንያቶች ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አንደኛ፤ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ ያዘጋጀው ስብሰባ ላይ መገኘት ስለሚያስፈራ፣ ሁለተኛ፤ ስብሰባዎቹ በበቂ ሁኔታ ስለማይተዋወቁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እና ሕዝቡ መካከል ያለው ርቀት ሰፊ ስለሆነ እንዲሁም ማስታወቂያ ስለማይሰራላቸው እና ስለማይሰሙ ነው፡፡ ሁለቱንም ችግሮች መቅረፍ ግን የተቃዋሚዎቹ ኃላፊነት መሆን ይኖርበታል፡፡

ፓርቲዎቹ ከሕዝብ ጋር ያላቸውን ርቀት ለማጥበብ፣ የሕዝቡን የፍርሐት ስሜት በአርኣያነት የመግፈፍ እና ማስታወቂያ በአግባቡ የመሥራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሚያዘጋጁዋቸው ስብሰባዎች ላይ ቢያንስ መሐል ከተማ ያሉ አባላቶቻው እንዲገኙ የሚያስገድድ መመሪያ በማኖር፤ የሻማ ማብራት ሥርዐቶቹ ላይ በየክልሉ ባሉት ቢሮዎቻቸውም በተመሳሳይ ሰዐት ሥርዐቱን በማካሔድ አገር አቀፍ ጉዳዩን የማሳሰብ እና ተጽዕኖ መፍጠር የሚችል ሥራ መሥራት ይቻላል፡፡

በነዚህ ፕሮግራሞች ላይ የሚሳተፈው ሰው ማነስ በሕዝብ እና በፓርቲዎቹ መካከል ያለው ርቀት ማሳያ ነው፡፡ ሕዝቡን መቅረብ ዓላማቸው ከሆነ (መሆንም አለበት…) ችግሩን በማመን ለመቅረፍ ስትራቴጂ መቅረጽ አለባቸው፡፡ አባላቶቻቸውም ከወር መዋጮ የበለጠ፣ የፋና ወጊነት ሚና ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በእንደነዚህ ዓይነቶቹ ፕሮግራሞች እና ሌሎች ለውጥ ሊያመጡ በሚችሉ ችግሮች ዙሪያ ሞዴል ሁነው ፍርሐት ከመጋፈጥ ተግባራዊ እርምጃ እስከመውሰድ ድረስ መራመድ አለባቸው፡፡

ይህንን ማድረግ ባለመቻላቸው ብቻ የፕሮግራሞቹ ፋይዳም ሆነ ውጤት ጎልቶ አይታይም፤ የታዳሚዎቹ ቁጥርም ከጊዜ ወደጊዜ እያሽቆለቆለ ነው፡፡ እንዲያውም አንዳንዶች ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት አሏቸው እንዴ ብለው እስከመጠየቅ እየደረሱ ነው፡፡

## የአባሎቻቸው ስብጥር

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስለአባሎቻቸው ብዛት እና ስብጥር የሚያወጡት መረጃ በጣም የተገደበ ነው፡፡ እርግጥ ይህ ምስጢራዊነት በአባሎቻቸው ብቻ ሳይሆን በፖሊሲዎቻቸው እና የትግል ስልቶቻቸውም ለሕዝብ ቶሎ ቶሎ ባለማስተዋወቅም ጭምር ነው የሚንጸባረቀው፡፡ የአባላቶቻቸውን ዝርዝር መረጃ ማውጣት ባለው የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ለአባላቱ የደኅንነት አደጋ አለው ቢባል እንኳን በቁጥር ደረጃ ለምን አያሳውቁም? ግልጽነት የተሞላው አሠራር የሚጀምሩት የመንግሥት ሥልጣን ሲይዙ ብቻ ነው? የአባሎቻቸውን ቁጥር፣ የዕድሜ ሁኔታ፣ በየክልሉ

ያላቸውን የአባል ብዛት፣ የሴት አባላቶቻቸውን ብዛት፣ በየወሩ ከአባላት መዋጮ እና በልገሳ የሚሰበስቡትን ገንዘብ እና ሌሎችም ለሕዝብ ይፋ በማድረግ እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ማስመስከር እና በሕዝብ ለመገምገም እና ለመመረጥ መዘጋጀት አለባቸው። አለበለዚያ ግን ኢሕአዴግ ሕዝብ ላይ በሚያደርሰው በደል ብቻ ተማርሮ ‹‹ተበድሏልና ይምረጠን›› ማለት አሁን ያለው የፖለቲካ ምኅዳር ጥበት ተጨምሮበት የመመረጥን ነገር ‹‹ላም አለኝ በሰማይ›› ያደርገዋል።

ለምሳሌ ‹ተቃዋሚዎቹ ለወጣቱ ምን ዓይነት ቦታ ሰጥተዋል?› የሚለውን ጥያቄ ብናነሳ (ወጣት በኢትዮጵያ ስታትስቲክ ኤጀንሲ መስፈርት መሰረት ከ14 እስከ 29 ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ዜጋ ነው።) በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ ስንት አባላት አሏቸው? ከፓለቲካ የራቀውን ወጣት አባል እንዲሆን የሚያደርጉት ምን ማበረታቻ አለ? የወጣት ክንፍ አላቸው ወይ? ወጣቱን በፓርቲዎቻቸው የተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ በማስቀመጥ የሥልጣን ሽግግር አድርገዋል ወይ/የሚያደርጉበት አሠራርስ አላቸው ወይ? የሚሉትን ጉዳዮች የሚመልስ አሠራር አይተናል ለማለት ያስቸግራል።

## አናሳውን ማሳደግ

የምርጫ 2002 ውጤት ብዙ ችግር ነበረበት። ከችግሮቹ መካከል ብዙኃኑ ተቃዋሚ ካርድ አለመውሰዱ፣ ከወሰዱት ውስጥም ገሚሱ አለመምረጡ ትክክለኛውን ውጤት አያንፀባርቅም ያስብላል። ሆኖም የመጨረሻውን ውጤት ብቻ ይዘን ለዚህ ጽሑፍ እንዲመቸን እንነሳ። በወቅቱ በአዲስ አበባ ብቻ 564,813 (54.2%) ያህሉ መራጮች ለኢሕአዴግ ድምፃቸውን ሲቸሩ 380,355 (36.5%) ደግሞ መድረክን መርጠዋል ይለናል የምርጫ ቦርዱ ውጤት። እዚህ ጋር ከ380 ሺህ በላይ መራጮች መድረክን ለመምረጥ ከቻሉ ለመድረክ በራቸውን ክፍት አድርገው ነበር ማለት ነው። መድረክ እነዚህን መራጮቹን ይዞ ከምርጫው ወዲህ ምን ሠራ? እነዚህ ሰዎች መድረክን በመምረጣቸው ምክንያት ፓርላማ ውስጥ ወኪል አላገኙም፤ ይህንን ለማካካስ ፓርቲው የነርሱን ድምጽ ለመሰብሰብ ብሎም ለማስተጋባት ያደረገውስ ጥረት ምንድነው? የሚለውን ስንመለከት በትንንሽ ስኬቶች ላይ መሠረት አድርጎ የማሳደግ ስራን እንደስትራቴጂ መጠቀም የተቃዋሚው ሰፈር ችግር ሆኖ እናገኘዋለን።

## ዘመኑን መዋጀት

የተቃዋሚ ፓርቲዎች አብዛኛዎቹ አባላት እና አመራሮች የ‹ያ ትውልድ› አባላት ናቸው። አተኩሮ ለሚመለከታቸው ብዙዎቹ የዘመኑን ችግር እና መፍትሔ የሚያውቁት አይመስሉም። በዚህ ዘመን ነገሮች የሚቀያየሩት በፍጥነት ነው። መረጃ በየደቂቃው ከዚያኛው ዓለም ጫፍ ወደዚህኛው ዓለም ጫፍ ይፈሳል። አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች ግን መረጃ በየወቅቱ እና ከዓለም የመረጃ ፍሰት እኩል በሆነ ፍጥነት ሊያቀብሉ ቀርቶ የማቀበያው መንገድም የላቸውም። ብዙዎቹ ድረገጽ የላቸውም፣ የሚታተሙ ጋዜጦች የሏቸውም፣ (ችግሮቹ እንዳሉ ሆነው) ሰዎች ወደነርሱ ሒደው መረጃ እንዲጠይቁ እንጂ እነርሱ መረጃዎቹን ለዜጎች ለመስጠት የሚያስችላቸውን አሠራር አይከተሉም እንጂ ብዙዎቻቸው ቢያንስ የፌስቡክ እና የትዊተር ገጽ ሊኖራቸው ይገባ ነበር። የፌስቡክ እና የትዊተር ገጽ ያላቸው ጥቂቶቹም ቢሆኑ የወጣቱን ልብ ለማግኘት እና ዘመኑን ለመዋጀት ሲጠቀሙበት እና የተለያዩ መረጃዎችን በፍጥነት እና በተገቢው ሁኔታ ሲያስተላልፉም አይታይም። የአባላቶቻቸውን መንገላታት መታሰር የተለያዩ የሰብኣዊ መብት ጥሰቶች የፓርቲያቸውን ፓሊሲ እና ዕቅድ የአባላቶቻቸውና የአመራሮቻቸውን ሥራዎች የሚያሳይ ምንም ነገር አይታይም። ቴክኖሎጂው የሰጣቸውን አማራጭ ሐሳብን የማስተላለፊያ መንገድ ከመጠቀም ይልቅ የተለመደው መንገድ ላይ የሚደርስባቸውን ችግር ያለምንም አማራጭ እርምጃ ሲያስተጋቡ ይስተዋላል።

## ‹‹ነጻነት የማያውቁ ነጻ አውጪዎች››

ድረገጽ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ድረገጻቸው በኢትዮጵያ እንዳይታይ ታግዶባቸዋል። አንድነትን (andinet.org) ጥሩ ምሳሌ አድርጎ መጥቀስ ይቻላል። አንድነት የታገደበት ድረገጹ ብቻ አይደለም፤ በየሣምንቱ ያሳትመው የነበረውም ጋዜጣ ጭምር ነው። ፓርቲው እንዲህ ዓይነቶቹን ሕጋዊ መብቶቹን ለማስከበር የወሰዳቸው እርምጃዎች ካሉ እነርሱን አላሳወቀም ወይም ምንም እርምጃ አልወሰደም።(በፓርላማ የጋዜጣውን ጉዳይበተደጋጋሚ ከማንሳት በስተቀር) ይህ ያሉትን የሕግ አግባቦች እስከመጨረሻው እንኳን ሳይጠቀሙ ተስፋ አናገኝም በሚል የተስፋ መቁረጥ አዝማሚያ ማሳየት እንዲህ ዓይነት ችግሮችን መፍታት ያቃተው ፓርቲ እንዴት የተወሳሰበውን የኢትዮጵያ ችግር እና ኢ-ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ይፈታል ብሎ ማሰብ እንደገና ‹‹ላም አለኝ

በሰማይ›› ይመስላል፡፡ ይህ እንግዲህ በሁለት እትም ሙከራ የቀረውን የሰማያዊ ፓርቲ መጽሔት በግል ችግሮቻቸው የሚወዛገቡ እና ፓርቲ ለማፍረስ የሚሮጡ ነጻ አውጪዎችን ሳናጠቅስ ከቀረን ነው፡፡

## ተቃውሞን በመግለጫ

*ተቃዋሚዎች መንግሥት ስህተት ሰርቷል ወይም ደግሞ የተለየ ነገር አድርጓል ብለው ሲያምኑ ለግል ጋዜጦች ከሚበትኗቸው አጭር፣ ብዙ ጊዜ የታሰበባቸው የማይመስሉ የተቃውሞ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ከመበተን በላይ መታገል ያለ አይመስላቸውም፡፡ ብዙ ጊዜ ለተግባራዊ የሚቀሰቅሱት የኢኮኖሚ አቅማቸውን ነው፡፡ ለኢኮኖሚ አቅማቸውም ቢሆን ጠንክረው መሥራት ያለባቸው እነርሱ ቢሆኑም ኢኮኖሚያዊ ፍጆታ የሌላቸውን እንቅስቃዎችን በማካሔድ የሕዝቡን ንቃተ ሕሊና ለመጨመር እና ትኩረትን ለማግኘት ይረዳቸዋል፡፡ ይህ ታስቦበት ቢሠራ ተቃውሞውን መንገድ ማበርታት ይችላል፡፡*

*መግለጫ በሚያወጡባቸው ነገር ግን ኢሕአዴግ መልስ እንኳን ሊጽፍባቸው በማይዳዳቸው ጉዳዮች ላይ ተሰሚነትን ለማዳበር ፓርቲዎች እና አባሎቻቸውን ያሳተፉ ሰላማዊ ትኩረት ሳቢ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ከተለመዱት (ብዙ ጊዜ ተሞክረው ካልሠሩት) የፓርቲ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ውጪ ሕዝቡን የማግኘት ዕድሎች ይፈጥሩ ነበር፡፡ እነዚህ ለመንግሥትም፣ ለክስ የማይመቹ ነገር ግን የሕዝቡን ሐሳቦች የሚስቡ ተግባራትን ለማከናወን አለመሞከራቸው መኖራቸወን የምርጫ ሰሞን ሆይ ሆይ ብቻ ያስመስለዋል፡፡ ጥረታቸውም ከዕይታ ውጪ እና ውጤት አልባ ይሆናል፡፡ (መሪዎቻቸው አርኣያ የሚሆኑ የቡድን ተግባራትን ማከናወን - እስረኞችን መጠየቅ፣ ደም መስጠት /ማኅበራዊ ፋይዳ ያላቸውን ተግባራት በምሳሌ ማሳየት/ የብዛት እግር ጉዞ ማድረግ፣ ሕዝብ በብዛት ሊያያቸው የሚችላቸው የአድቮኬሲ እና አራማጅነት ሥራዎች ላይ መሳተፍ…ወዘተ፡፡)*

## ዴሞክራሲያዊነታቸውስ?

*የስንቶቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሌላኛው አጀንዳ ዴሞክራሲያዊነት ነው፡፡ ይህ የውስጠ ፓርቲ ዴምክራሲያዊነት ጥያቄ በፓርቲ ደረጃ በግልጽ ለመፈታቱ ማስረጃ ማግኘት ካልቻልን ዴሞክራሲያዊነታቸው በጣም አጠራጣሪ ነው፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ምክርቤቶቻቸው ስንት አባሎች እንዳሏቸው፣ የምክርቤቶቻቸው አባላት ምርጫ መቼ እንደሚካሔድ፣ በኃላፊነት የሚሾሙዋቸው ሰዎች የሥልጣን ዕድሜ ገደብ ቁልጭ ባለ መመሪያ መሠረት ይከናወናል? እድሜ ልካችንን የምናያቸውን በጣት የሚቆጠሩ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ማስታወስ በቂ ነው፡፡ ብዙዎቹ አመራሮቻቸው ለዓመታት ሳይቀየሩ አሁንም ይቀየራሉ የሚል ተስፋ ሳይሰጡ ነው የሚኖሩት፡፡ በግልጽ የሚታይ ዴሞክራሲያዊነት ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ወሳኝ ጉዳይ የሚሆነው ለሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንድ - ዴሞክራሲያዊነትን የመንግሥት ሥልጣን ከመያዛቸው በፊት ማዳበር ስላለባቸው፡፡ ሁለት - እንደሕዝብ ከመንግሥት ጋር ያላቸውን ልዩነት ማየት ስለሚኖርብን፡፡*

## በምን ምክንያት እንመርጣቸዋለን?

*በአሁኑ ሰዓት በአብዛኛው እንደሚስተዋለው ተቃዋሚዎች ዋነኛ ሥራቸው እና አትኩሮታቸው በገዢው ፓርቲ የሚፈፀሙ የሰብኣዊ መብት ጥሰቶችን እና ሌሎች ስህተቶችን መተቸት እና አግባብ አለመሆናቸውን በመግለጽ የተቃውሞ መግለጫ ማውጣት ብቻ ነው፡፡ ይህ ተገቢ አይደለም ማለት ባይቻልም እንደ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ግን ከዚህ ያለፈ ሚና የመጫወት ኃላፊነታቸውን መርሳታቸው አግባብ አለመሆኑ ሊሰመርበት የሚገባው ነው፡፡ ኢሕአዴግ የጣሳቸውን ወይም ያጠፋቸውን ጉዳዮች እነሱ እንደማይደግሙት በምን እርግጠኛ ለመሆን እንችላለን - መቃወማቸው ብቻ ማስተማመኛ እንደማይሆን ግልጽ ነው፡፡ እነርሱ የሚከተሉትን ርዕዮተ ዓለም፣ ፖሊሲ እና ስትራቴጂያቸውን እንድናውቅ እና ከኢሕአዴግ ጋር የሚወዳደሩበት ነጥብ እንዳላቸው ለማሳየት ሲጥሩ አይታይም፡፡ ብዙ ገንዘብ የማይፈጁትን ነገር ግን ርዕዮተ ዓለም፣ ፖሊሲ እና ስትራቴጂያቸውን እንዲሁም ሌሎች እንቅስሴዎቻቸውን ለኅብረተሰቡ ለማዳረስ ዘመኑ ያመጣቸውን ማኅበራዊ አውታሮች እና ድረገጾች እስካሁን በአግባቡ መጠቀም ለምን አላሰቡም? ይህን እና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን መልስ በሌለበት መልኩ የምንመርጣቸው በምን ምክንያት ሊሆን ነው? ምርጫ ወቅትን ጠብቆ የሚመጡ ክርክሮች እና ፓርቲን የማስተዋወቅ ሥራ የመንግስትን ኃላፊነት ለመረከብ በቂ ነውን?*

በርግጥ እነዚህን ጥያቄዎች ይዞ ፓርቲዎቹ ጽ/ቤት ድረስ የሚሄድ ሰው ምላሾችን አያጣ ይሆናል፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው እነዚህን ጉዳዮች ለማወቅ ፓርቲዎቹ ጽ/ቤት ድረስ መሄድ አለበት ወይ? ማነው የተሻለ ኃላፊነት የወሰደው ፓርቲዎች ወይስ ህዝቡ? ይህንንም ለማስወገድ ፓርቲዎች የተለያየ መንገድ ተጠቅመው እንቅስቃሴዎቻቸውን እና አካሄዳቸውን ማኅበረሰቡ በተለይም ወጣቱ ክፍል እንዲውቅ እና እንዲሳተፍ እንዲነሳሳ የማድረግ ሥራ መጀመር ይኖርባቸዋል፡፡

ኢሕአዴግ አገራችንን በምንፈልገው መልኩ እያስተዳደረ ስላልሆነ ብቻ ተቃዋሚን መደገፍ እና ተቃዋሚዎች እንዲያሸንፉ የመፈለግ ነገር በብዛት ይስተዋላል፡፡ ይህ ግን አግባብ እንዳልሆነ፤ ስለተቃወሙ ብቻ ተቃዋሚዎችን መደገፍም አዋጭና ጠቃሚ ስላልሆነ ጠንክረው የተለያዩ ሥራዎችን መሥራትም የታሰበባቸው መንገዶችን መቀየስም ይጠበቅባቸዋል፡፡

## ‹‹ኧረ እኔም ይቺን ዘዴ ከዛሬ በፊት አላየኋት!››

አንድ ተረት አለች፡፡ አንድ መነኩሴ በጾም ወቅት እንቁላል በሻማ እየጠበሱ ሲበሉ አበምኔቱ (የገዳሙ አስተዳዳሪ) ያገኟቸውና ‹‹እንዴ አባ ምን ነካዎ?›› ቢሏቸው ‹‹ሰይጣን አሳስቶኝ ነው›› ብለው ሲሉ፣ ተደብቆ እያየ የነበረው ሰይጣን ‹‹ኧረ እኔም ይቺን ዘዴ ከዛሬ በፊት አላየኋት!›› ብሏል ይባላል፡፡ ለሆነው ሁሉ ሰይጣንን ከማሳበብ የሰይጣን ሥራን ማቆም ይበጃል ነው አተራረቱ፡፡

ተቃዋሚዎችም ለሁሉም ድክመታቸው ኢሕአዴግን እንደምክንያት ከሚጠቅሱ ቀላል ኃላፊነት አይደለምና ድክመት እንዳለባቸው በማመን የራሳቸውን ስህተት ለማረም መረባረብ፣ ያልተሞከሩ አዳዲስ መንገዶችን ለመሞከር ማሰብ መጀመር የአቅም እጥረት ካለባቸው ኃላፊነቱን ለሚችሉ መልቀቅ እና ማንኛውንም ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር የሚያመጣ መንገድ መሞከር ይኖርባቸዋል፡፡ አለበለዚያ በዚህ አያያዛቸው ኢሕአዴግን ይቀይራሉ ብሎ ማለት ዘበት!!!

---

**ይህ ጽሑፍ ‹‹መክሸፍ*›› በሚል ርዕስ ከዚህ ጀምሮ በተከታታይ የሚወጡ ጽሑፎች አካል ነው፡፡**
(*መክሸፍ የሚለው ቃል ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የመጨረሻ መጽሐፍ ላይ ሲጠቀሙበት በተፈጠረ መነሳሳት የተጠቀምንበት ነው፡፡)

# የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችና የመደራደር አቅማቸው (ክፍል 1)

**በዳዊት ተ. ዓለሙ**

የፖለቲካ ፓርቲዎች የመደራደር አቅም (Bargaining power) ለዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ ስርአት ግንባታም ሆነ በዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ ላይ ተመስርቶ ለሚደረጉ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ስኬታማነት ወሳኝ ነው:: ሁሉን የፖለቲካ ቡድኖች ያማከለ የዴሞክራሲያዊ ተቋማት ምስረታም ሆነ የተቋማቱ ዘላቂነት በዋናነት የሚወሰነው የፖለቲካ ፓርቲዎች በሚኖራቸው የመደራደር አቅም ልክ ነው:: ሚዛናዊ ያልሆነ የመደራደር አቅም ባላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች መሀካል በሚደረግ ስምምነት የሚፈጠሩ ተቋማትና ስርዓቶች በአመዛኙ ሊያስጠብቁ የሚችሉት ይበልጥ ጠንካራ የመደራደር አቅም ያለውን የፖለቲካ ኃይል ፍላጎቶች ነው:: ይበልጥ የዴሞክራሲ ስርአት ሰፍኖባቸዋል በሚባሉ ሀገራት ውስጥ በትንሹ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑና የተቀራረበ የመገዳደር አቅም ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚገኙባቸው ናቸው:: የተቀራረበ የመገዳደር አቅም ባላቸው ፓርቲዎች (መሪዎች) ድርድር የሚመሰረቱ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት በአብዛኛው የሁሉንም ፖለቲካ ኃይሎች ፍላጎቶች የማንጸባረቅ እዳላቸው የሰፋ ነው:: ለምሳሌ ያህልም ሮበርት ፑትናም Making Democracy Work ብሎ በሰየመው የምርምር ስራው ለ20 አመታት የኢጣሊያንን ፖለቲካ በቅርብ ከተከታተለ በኋላ ይህንን እውነታ በሰፊው አመልክቷል:: ስለዚህም የፖለቲካ ፓርቲዎች የተቀራረበ የመደራደር አቅም ለሰላማዊ ፖለቲካና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ወሳኝ ነው::

በሀገራችን የፖለቲካ ቡድኖች (ፓርቲዎች) የመደራደር አቅማቸው የማይመጣጠን በመሆኑ የመገዳደር ፖለቲካ ባህላችን በአፈሙዝ የበላይነት የሚደመደምበት እንዲሆን አድረጎታል:: በዚህም የተነሳ በየወቅቱ ሲገነቡ የነበሩት ተቋማት በስልጣን ላይ ያለውን ቡድን ጥቅምና ህልውና የሚያስጠብቅ ባህሪና ቁመና የተላበሱ ሆነዋል:: የፖለቲካ ፓርቲ እሳቤና ተሞክሮ የሀገራችን የፖለቲካ ባህል ከተዋወቀበት ጊዜ አንስቶ የተመሰረቱ ፓለቲካ ፓርቲዎች ሁሉም ሊያስብል በሚችል መልኩ የመደራደር አቅማቸው በጉልበት ላይ ወይም በተወሰ ጉዳዮች ላይ ብቻ የተነጠለጠለ ነው:: ይህም በመሆኑ በሀገራችን ደካማ ወይም ኢ-ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል የራቀው ፖለቲካዊ ባህል እንዲሰራፋ ሆኗል::

## የመደራደር አቅም ሲባል

የመደራደር አቅም (Bargaining power) በተለያዩ ጸሃፊዎች በተለያዩ የአረዳድና እውቀት ዘርፎች የተለያየ ትርጓሜ ተሰጥቶታል:: በግርድፉ የመደራደር አቅም ሲባል በአንድ በተወሰነ ሁኔታ ላይ አንድ ተቋም/ግለሰብ በሌሎች ተቋማት/ግለሰቦች ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የሚያስችለው አንጻርዊ የተቋማት/ግለሰቦች አቅም ማለት ነው:: ጊዲዮን ዳሮንና እቲኢ ሰንድ በጋራ ባዘጋጁት መጸሃፍ (Poltical Bargaining: Theory, Practice and Process) ፖለቲካል የመደራደር (Political Bargaining) አቅምን ትርጓሜ ሲሰጡት:- „a tangible effort made by two or more agents with some conflict of interests to reach an agreement over an authoritative allocation of scarce resources" በማለት ነው:: በዚህ አረዳድ ውስጥ ፖለቲካ የታየበት አግባብ ወሳኝ ሃብቶችን ስርጭት መሰረት ያደረገ ነው:: ይህም ከክላሲካል „ፖለቲካ" ትርጓሚ ማለትም „ፖለቲካ ማለት ከስልጣን ጋር የተያያዘ ጉዳይ ሲሆን ስልጣንም የሀብት ክፍፍልን የሚመለከት ነው" ከሚለው ዕሳቤ የመነጨ ነው:: ስለዚህም የመደራደር ሂደት የተለያዩ ማህበረሰባዊ ወይም ቡድናዊ ፍላጎቶችን ለማስታረቅና ስምምነት ላይ የተደረሰበት የወሳኝ ሃብቶች ስርጭት ስርዓት መዘርጋት ማለት ነው:: በዚህም የተነሳ የመደራደር አቅም በፖለቲካ ሳይንስ ውስጥ የምንረዳበት አግባብ አንጻራዊነትን የሚላበስና ብዙ አላባውያንን (elements) የሚያቅፍ መሆኑን ነው:: የመደራደር አቅም ከሚታይበት አላባውያን መካከል ወሣኞቹ ድርጅታዊ ጥንካሬ፣ ፍላጎቶችን የማስታረቅና ተጽእኖ የመፍጠር አቅም፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለቸው የቅቡልነት ደረጃ፣ፖለቲካል ታክቲክ እንዲሁም ፖለቲካል ውሳኔያቸው ተተንባይነት ነው:: እያንዳንዱን ጉዳይ ብቻ በመያዝ ብዙ ሊያጽፍ ቢችልም፣ በዚህ ጽሁፍ ተከታታይ ጽሁፍ ለሁለት ከፍለን በተወሰነ መልኩ እንደሚከተለው እንዳስሳቸዋለን::

## ድርጅታዊ ጥንካሬና የመደራደር አቅም ውስኑነት

ድርጅታዊ አቅም የተለያዩ ፍቺዎች ቢኖሩትም በሶስት ቁምነገሮች ላይ ያተኩራሉ:: እነርሱም የሰው ኃይል፣ አደረጃጀት እና አሰራር ናቸው:: ኢትዮጵያ በፖለቲካ ፓርቲ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ ባህል ውስጥ የገባችው የ1960ዎቹንፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ተከትሎ ነው:: ይህም ሁናቴ በኢትዮጵያ ውስጥ የተመሰረቱት ፖለቲካ

ፓርቲዎች በግራ ዘመም ባህል በተለይ ደግሞ ጆሴፍ ስታሊን „የሌኒን ፓርቲ“ ብሎ በሰየመው አረዳድ ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: ይህ ግራ ዘመም የፓርቲ ፖለቲካ ባህል በፓርቲዎች ርዕዮተ-ዓለማዊ አቋም ብቻ የሚንጸባረቅ ሳይሆን እንደብረት በጠነከረ የፓርቲ ስነ-ስርዓት፣ በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት፣ ጥብቅ ከላይ ወደታች የዕዝ ሰንሰለት ጭምር የሚታይ ነው:: በዚህ ፓርቲ ፖለቲካ ባህል መሰረት <ጠንካራና በዲሲፒሊን የታነጸ ድርጅት በማኅበረሰብ ውስጥ ፖለቲካዊ ተቀባይነትን ለማግኘትና በፖለቲካዊ ትግል አሸናፊ ለመሆን ወሳኝ ነው::> ብሎ ያምናል:: ምንም እንኳን የሃገራችን ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩ ርዕዮተ አለምን የሚከተሉ ቢሆንም ይህ አስተሳሰብ በከፍተኛ ሁኔታ የተጫናቸው ናቸው:: በዚህ የአስተሳሰብ ማዕቀፍ ውስጥ ነው እንግዲህ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ድርጅታዊ ጥንካሬና የመደራደር አቅም የሚታየው::

እንደማንኛውም ታዳጊ ሀገር ፖለቲካ በአብዛኛው የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች የተመሰረቱት ዘመናዊ ትምህርት በቀሰሙ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው:: አብዛኛዎቹ ከፍተኛ አመራሮች በኢትዮጵያ የተማሪዎች ንቅናቄ የተሳተፉና በተለያዩ የአመራር ደረጃ የነበሩ ናቸው:: ይህም የተቀዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ከፍተኛ አመራሮች በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ከፍተኛ ልምድና ዕውቀት እንዲኖሯቸው አስችሏቸዋል:: በሌላ መልኩ ደግሞ አብዛኞቹ አመራሮች በተለያዩ ቡድኖች ውስጥ ተሳታፊ ስለነበሩና እርስ በራሳቸው በአይነ ቁራኛ የሚጠባበቁና በከፍተኛ ጥላቻና ቂም በቀል ስሜት የተዋጡ እንዲሆኑ ስላረጋቸው ከጊዜያዊ ትብብር የዘለለ በመርህ ላይ የተመሰረተ አንድነትን መፍጠር እንዳይችሉ አድርጓቸዋል:: በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እግጅ በጣም ትናንሽ በሆኑ ፖለቲካ ፓርቲዎች መሞላቱ የሚያመለክተው ቁምነገር የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ከፍተኛ አመራሮች በራሳቸው ዙሪያ የተገነቡ ፓርቲዎችን እንጂ በመርህ ላይ የተመሰረተና የጋራ ፖለቲካዊ አጀንዳ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ፓርቲዎችን መመስረት አለመቻላቸውን ነው:: ይህም ወደአንድ ላይ መሰባሰብ ቢችሉ ሊያመጡ ከሚችሉት ውጤት አንጻር እጅግ ዝቅተኛ ውጤት እንዲያመጡ ሲያደርጋቸው፤ ልምድ ያላቸው ከፍተኛ አመራሮችም እንዲበታተኑ ሆነዋል::

መሃከለኛ አመራር ደረጃ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸው የሰው ኃይል አቅም በጣም ትንሽ ነው:: አንደኛ ተምሯል ከሚባለው አጠቃላይ ኢትዮጵያዊ አንጻር ሲታይ በተቃውሞ ፖለቲካ ውስጥ ያለው ሰው እጅግ በጣም አናሳ ነው:: ሁለተኛ ከፍተኛ አመራሮች መሀከል በሚፈጠሩ አለመግባባቶች ፓርቲዎች ሲሰነጠቁ ከፖለቲካ ትግሉ የሚርቀው ከሁለቱም ወገን ከቀረው የሰው ኃይል አንጻር በጣም ከፍተኛው ነው:: ይህም የሚታየው ፓርቲዎች ከተሰነጠቁ በኋላ እንደቀድሞአቸው ለመሆን አለመቻላቸው ላይ ነው:: ሶስተኛ ፖለቲካ ፓርቲዎቹ በአብዛኛው አቅምና እውቀት ላይ ሳይሆን በጥቅመኝነት (Patronage) ላይ የተመሰረቱ ስለሆነ መካከለኛ አመራሮቹ ደካማ አቅም ያላቸው ይሆናሉ:: በአባላት ደረጃም ቢሆን የሚታየው እውነታ የሰው ኃይል ልማት ላይ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ያላቸው አነስተኛ አቅም ነው::

በተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀትና አሰራር በጣም ደካማ ነው:: አደረጃጀት በመሰረቱ የመጨረሻ ውጤትን ለማሳካት፣ ተጠያቂነትንና ግልጽነትን ለማስፈን እንደግብአት የሚታይ ነው:: በአብዛኛው የተቃማዊ ፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀት ግልጽነት የጉደለውና የፖለቲካ ፕሮግራሞቻቸውን ከማሳካት ይልቅ ቁጥጥርና የከፍተኛ አመራሮችን ተክለ-ስብዕና በሚያጎላ መልኩ የሚቀረጽ ነው:: እንደምሳሌ ሊታይ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል የተለያዩ ጥናቶች እንዳመለከቱት አብዛኛዎቹ ፖለቲካ ፓርቲዎች ስምና ፖለቲካዊ ፕሮግራም ሳይሆን የመሪዎች ስም ነው በስፋት የሚታወቀው:: አሰራር (internal working system) ፖለቲካ ፓርቲዎች እንዴት የፖለቲካ ስራዎቻቸውን እንቅስቃሴዎቻቸውን እንደሚያከናውኑ የሚመለከት ነው:: በአብዛኛው የዴሞክራሲ ማዕከላዊነት (democratic centralism) የሚለው የአደረጃጀትና አሰራር እሳቤ ጎልቶ የሚታይ ነው:: ይህም በመሆኑ አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጣም ምስጢረኛነት የበዛው አሰራር፣ የገነነ ማዕከላዊነትና ጥብቅ ከላይ ወደታች አደረጃጀት እንዲሁም ግልጽነት የሚጎላቸው የውስጥ አሰራር ድንጋጌዎች ያሏቸው በመሆናቸው ውስጣዊ ዴሞክራሲያዊ ባህል የጎደላቸው ናቸው:: በዚህም የተነሳ ተራ አባሎቻቸውንና ዜጎችን በተለምዷዊ የፖለቲካ ፓርቲ ስራዎች በሚባሉት ውስጥ የማያሳትፉና በማህበራዊ መሰረቶቻቸው ከሞላ ጎደል አየር ላይ የተንሳፈፉ ናቸው::

ይኸም በመሆኑ ፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸው የመደራደር አቅም እጅግ አናሳ ነው:: አንደኛ፣ እርስ በራሳቸው ያላቸው ድርጅታዊ ግንኙነት ሻካራና ጥርጣሬ ላይ የተተመሰረተ ስለሆነ በአብዛኛው „አንድ-ለብዙ“ በሚደረጉ ከገዢው ፓርቲ ጋር የመገዳደር ሂደቶች እስካሁን ውጤታማ ሊሆን አልቻሉም:: ለምሳሌ „28ቱ ዋነኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች“ ብለው እራሳቸውን የሰየሙት ከገዢው ፓርቲ ጋር በምርጫ ስነ-ስርአቱና በሌሎች አጀንዳዎች መወያየት ቢፈልጉም እስካሁን ያሰቡት ፖለቲካዊ አጀንዳዎች ማስፈጸም ይቅርና ከኢህአዴግ ጋር በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ መወያየት አልቻሉም:: ይህም የሚያመላክተው ተቃዋሚ ፓርቲዎች የጋራ አጀንዳ ቀርጸው ህዝቡና በማስተባበር ገዢውን ፓርቲ የማስገደድ አቅማቸውን መገንባት አለመቻላቸውን ነው::

„አንድ-ለአንድ" በሚደረጉ የመደራደርና የመገዳደር ሂደቶች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያላቸው አቅም እዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: ከ1997 ምርጫ በፊትም ሆነ በኃላ ከገዢው ፓርቲ ጋር የተደረጉ የተለያዩ ድርድሮች ውጤት አልባ ከመሆናቸውም በላይ ለገዢው ፓርቲ ፖለቲካዊ ጥቅም ለተቃዋሚዎች ደግሞ ፖለቲካዊ ክስረትን ያስከተሉ ናቸው:: ለምሳሌ መድረክ ከምስረታው ጀምሮ ከኢህአዴግ ጋር መደራደር እፈልጋለው እያለ በተለያዩ ወቅቶች ፍላጎቱን ቢገልጽም እስካሁን ከኢህዴግ ጋር መደራደር አልቻለም:: እዚጋ ሊነሳ የሚችለው ጉዳይ ገዢው ፓርቲ የመንግስትን፣ የመከላከያን፣ የደህንነትንና ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን በበላይነት ስለተቆጣጠር በተቃዋሚ ፓርቲዎችና በአጀንዳዎቻቸው ላይ ከፍተኛ ጫና ይፈጥራል የሚል ይሆናል:: ነገር ግን ላለፉት ሁለት አስርተ-አመታት የተቃውሞ ጎራው የገዢውን ፓርቲ አካሄድ ተረድቶ ይህንኑ የሚመጥንና አሸናፊ ወይም ተገዳዳሪ የሚያደርጋቸውን አቅም አለመገንባታቸው ሙሉ በሙሉ በገዢው ፓርቲ ሁሉን-አቀፍ አቅም (overwhelming power) የሚገለጽ አይደለም:: ወሳኝ በሆነ መልኩ ውስጣዊ ድክመታቸውን የሚያሳይ እንጂ:: ፈረንጆቹ እንደሚሉት ወረራ በራሱ የድክመት ማሳያ ሲሆን በወረራ ተሸናፊነት ምንጩ ደግሞ ውስጣዊ ድክመት ነው:: የገዢው ፓርቲ ተጽእኖ ውጤታማነት ምንጩ የተቃማዊ ኃይሎች ውስጣዊ ድክመት ነውና::

በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚዎች እርስ በራሳቸው ያላቸው ድርጅታዊ ግንኙነት ሸካራና ጥርጣሬ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በረጅም ጊዜ በሚደረጉ ግንኙነቶችና መስተጋብሮች (Isomorphic process) ሊፈጠሩ የሚችሉ የጋራ አጀንዳዎችና ሊደረስበት ይችል የነበረው በጋራ አብሮ የመስራት ተቋማዊ ዝግጅት አናሳና ዘገምተኛ እንዲሆን ሆኗል:: በተቃዋሚ ፖለቲካ ውስጥ የሚሳተፉ አመራሮች ምንም እንኳን በአካዳሚክ ዕውቀታቸው አንቱ የተባሉ ቢሆኑም የመሰረቷቸው ፖለቲካ ፓርቲዎች በአብዛዎቹ ውስጣዊ መረጋጋትና አንድነት የጎደላቸው ናቸው:: ይህም በመሆኑ በሚደረጉ ድርድሮች አብዛኞቹ አንድም ያነሷቸውን ፖለቲካዊ ፍላጎችውን ከገዢው ፓርቲ ጋር በሚደረጉ ውይይቶች ለማሳካት በሙሉ አቅማቸው በመሳተፍ፤ ሁለትም የገዢውን ፓርቲ ሌሎችን ፓርቲዎች በማዳከም የሚያረገውን እንቅስቃሴ ከመግታት አንጻር „ታማኝ ተቃዋሚ" በመሆን መካከል አጣብቂኝ ውስጥ የገቡና የሚዋዥቁ ናቸው:: በዚህም የተነሳ የተቃዋሚዎች የመደራደር አቅም ባላቸው ውስጣዊ ድርጅታዊ አቅም እየተሸረሸረ የማስገደድ አቅማቸው እየተመናመነ ከገዢው ፓርቲና እርስ በራሳቸው በሚያደርጓቸው ድርድሮች ተቀባይ አሊያም ከድርድሩ የሚርቁ ሆነዋል::

ከላይ እንደጠቀስኩት የድርጅታዊ አቅም ውስንነት ከመደራደር አቅም አላባውያን አንዱና ዋነኛው ሲሆን በተከታዩ ክፍል ቀሪዎቹን ሁለቱን አላባውያን ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታና ማጠቃለያ ጋር እንመለስበታለን፡፡

# የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የመደራደር አቅም (ሁለት)

**በዳዊት ተ. ዓለሙ***

ባለፈው ሳምንት በወጣው የዚህ ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል የተቃዋሚ ፓርቲዎች የድርድር አቅም ዋና ዋና አላባዎች የተነሱ ሲሆን ተከታዩ እና የመጨረሻው ክፍል ተከትሎ ይቀርባል።

## በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸው የቅቡልነት ደረጃ

የተቀዋሚ ፓርቲዎች በማህበሰቡ ውስጥ የሚኖራቸው የቅቡልነት (legetimacy) ደረጃ ፋላጎቶችን የማስታረቅና የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመንቀስ፣ የፖለቲካ አጀንዳ በመቅረጽና ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችል ተጽእኖ የመፍጠር አቅም ላይ የተመሰረተ ነው:: በተለምዶ ፓለቲካ ፓርቲዎች በሚያራምዱት ርዕዮተ አለም ላይ ተመስርተው በሚነድፉት የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ የሚወክሉትን የማህበረሰብ ክፍል ፍላጎቶች ያንጸባርቃሉ:: በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ግን በብሔር ብሔርተኛነት ላይ የተመሰረቱ ፖለቲካ ፓርቲዎች እንደመብዛታቸው፣ በፖለቲካ ፕሮግራማቸው የሚያንጸባርቁት ፍላጎቶች በአንድ የተወሰነ ብሔር ፍላጎት የተገደበና ማህበራዊ መሰረታቸውም እንወክለዋለን የሚሉት ብሔር አባላት ብቻ ናቸው:: ህብረ-ብሄራዊ የሆኑት የፖለቲካ ፓርቲዎች በግልጽ ማህበራዊ መሰረታቸውን ያለዩና በፖለቲካ ፕሮግራሞቻቸው ያስቀመጡት ፍላጎቶች ሃሳባዊነት(utopia) የተላበሰና በሃገሪቱ ካሉ ከማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የመነጨ አይደሉም::

ከላይ እንደተመለከተው በሰው ኃይል አመዳደባቸው፣ አደረጃጀትና አሰራራቸው የጥቅመኝነት ግንኙነት የሰፈነበት በመሆኑ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መሃከል ያሉ ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ሁሉም ፓርቲዎች የሚያንጸባርቁት ማህበራዊ መሰረቶቻቸው እየጠበበ ሂዶ በፓርቲዎች ውስጥ የሚሳተፉትን ሙሁራን*'party-based elites'* ሆኗል:: ስለዚህም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ማህበራዊ መሰረቶቻቸው የጠበበ በመሆኑ ህልውናቸውን የማስጠበቅ ከፍተኛ ፈተና ተጋፍጠዋል፤ ተቋማዊ አቅማቸውን የሚያዳብሩበትን እድል አነስተኛ እንዲሆን አድርጎታል፤ የተቃውሞው ፖለቲካ ካለበት  የችግር አዙሪኝ መላቀቅ አቅቶታል:: ይህም ያላቸውን የመደራደር አቅማቸውን እጅግ በጣም የወረደ እንዲሆን አድርጎታል::

ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸው ጠባብ የህበረተሰብ መሰረት በመሆኑ የየራሳቸውን ህልውናና ፍግላጎቶች ለማስጠበቅ ሲሉ ሃገራዊውንና ህዝባዊውን ትልቁን ምስል እንዲያጡ አድርጎቸዋል:: ማህበረሰባዊ ፍላጎቶችን ማስታረቅና ልዩነቶችን ማቻቻል ተለምዷዊ ከሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተግባራት አንዱ ቢሆንም፣ ይህን ተግባር የመከወን ልምድ ሊዳብር ይቅርና እጅግ በጣም ጠባብ የሆኑ ፖለቲካዊ ልዩነቶችን የማግዘፉ ልምድ ዛሬም በኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በተደጋጋሚ የሚታይ ድርጊት ነው:: የዚህ ችግር ባህሪያዊ መነሻ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ  ሁናቴ ነው:: በአንድ በኩል የተቃዋሚ ፓርቲዎች ማህበረሰቡን ለማነሳሳትና ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ያላቸውን ልዩነት ፖለቲካዊ ትርጓሚ ለመስጠት የብሔር ብሔርተኝነትን ሲያጎሉ በሌላ በኩል ደግሞ ርዕዮተ አለማዊና መደባዊ ፍላጎቶችን በመጠቀም ከተለያዩ ፓርዎች ጋር አብሮ ለመስራትና ማህበራዊ መሰረታቸውን ለመሳፋት ይጠቀማሉ:: ይህ ሁለትዮሽ አካሄድ ፍላጎቶችን በግልጽ አንጥሮ ለማውጣትና ከሌሎች ፓለቲካ ፓርቲዎች ፍላጎቶች ጋር ለማስታረቅ፣ ልዩነትን ለማጥበብ ግልጽነትንና መተማመን በመሃከላቸው እንዳይኖር አድርጓል::

በሌላ በኩል ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ቅቡልነት በማህበራዊ ምሕዳር  (Social space) ባላቸው ሚናና አቅም የሚታይ ነው:: ማህበራዊ ምሕዳር የሚገለጽባቸው ቁም ነገሮች አራት ሲሆኑ እነርሱም በማህበራዊ አቅም (Social capital)፣ ኢኮኖሚያዊ አቅም (Economic capital)፣ ባህላዊ አቅም (Cultural capital) እና ምልክታዊ አቅም (Symbolic capital) ናቸው::

ማህበራዊ አቅም ሲባል በተቃዋሚዎች መካከል ባለ ሰላማዊና ትብብራዊ ግንኙነት ሊፈጠር የሚችለው የቅቡልነት ሂደት የሚመለከት ነው::  እንደአለመታደል ሆኖ ዶ/ር መራራ ጉዲና Party Politics, Political Polarization and the Future of Ethiopian Democracy ብለው በሰየሙት የጥናት ስራቸው እንዳመለከቱት የፖለቲካ ፓርቲ ባህል የኢትዮጵያን ፖለቲካን ከተዋወቀው ጊዜ ጀምሮ ማለትም ከ1960ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ ያለው የፓለቲካ ፓርቲዎች ታሪክ የሴራና የጠልፎ መጣል የውድቀት ታሪክ ነው:: እንደ ዶ/ር መራራ አገላለጽ:-

*[…] conspiracy and political intrigues have become the hallmark of the Ethiopian political parties and their leaders with the resultant effect of frustration, disillusionment and demobilization of the common folks across the country.*

ይህ አገላለጽ በመሰረቱ ከእውነታው ብዙ የራቀ አይደለም:: ይህ የሴራና የጠልፎ መጣል ታሪክ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ደካማ ከማድረጉም በላይ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን የቅቡልነት ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ እየጎዳው ነው ያለው:: በፖለቲካ ፓርቲዎችና መሪዎች መካከል ያለውን የጊዜያዊ የመተባበር ፍላጎት እንኳን በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታየው በከፍተኛ ጥርጣሬ ነው:: ይህ ዝቅተኛ የመደራደር አቅም ገዢው ፓርቲ በቀላሉ ፓለቲካዊ ፍላጎቶቹን እዚህ ግባ በማይባል መገዳደር በቀላሉ ሊያስፈጽም የሚችልበትን እድል ከመፍጠሩም በላይ የተቃውሞ ካምፑን በተለያዩ ዘዴዎች በመከፋፈል ውስጣዊ መረጋጋት እንዳይኖራቸውና ህዝቡም በከፍተኛ ጥርጣሬ እንዲመለከታቸው በቀላሉ ፖለቲካዊ ስራዎችን እንዲሰራ አስችሎታል:: እናም ይህ ደካማ ማህበራዊ አቅም በህዝቡ ውስጥ ዝቅተኛ ቅቡልነት እንዲኖራው ብቻ ሳይሆን ያደረገው የመደራደርና የመገዳደር አቅማቸውን ውስን እንዲሆን ጭምር ነው::

የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርዎች ኢኮኖሚያዊ አቅምም ከማህበራዊ አቅማቸው የተለየ አይደለም:: የፓርቲዎች ኢኮኖሚያዊ አቅም ምንጩ በዋናነት መደበኛን ጨምሮ በተለያዩ ዘዴዎች ከአባላትና ደጋፊዎቻቸው የሚያገኙት የፋይናንስ፣ የቁሳቁስና የአገልግሎት ገቢና ድጋፍ ነው:: አንደኛ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ያሏቸው አባላት በጣም ጥቂት ስለሆነ ሊያሰባስቡት የሚችሉት መደበኛ ገቢ እጅግ በጣም ውሱን ነው:: ሁለተኛ ከመንግስት የሚያገኙት አመታዊና የምርጫ ድጎማ በጣም አናሳ ከመሆኑም በላይ በአስገዳጅ ሁኔታ ለምሳሌ በታወቀ ድርጅት የኦዲት ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ጋር የተያያዘ ነው:: ይህም ማለት አንድ የታወቀ ኦዲት የሚሰራ ድርጅት የሚያስከፍለውን የአገልግሎት ክፍያ ታሳቢ ስናደርግ፤ ፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት የሚያገኙትን ድጎማ ሙሉ በሙሉ ለፖለቲካዊ ስራቸው ማዋል አይችሉም ማለት ነው:: እንደ ባህል ፖለቲካ ፓርቲዎችን የመደገፍ ልማድ አነስተኛ በሆነባት ሀገርና ተቃዋሚ ፓርቲዎችን መደገፍ መንግስትን እንደመቃወም በሚቆጠርበት ሁኔታ ሊገኝ የሚችለው ድጋፍ አናሳ ነው::

በሀገር ውስጥ የሚገኙ አብዛኞቹ ባለሃብቶችም አንድም ማህበራዊ ግዴታቸውን ጠንቅቀው የማይረዱ መሆናቸው፣ ሁለትም „ጎመን በጤና“ ብለው ከፖለቲካዊ ንኪኪ ራሳቸውን የሚያገሉ፣ ሶስትም ከመንግስት ባለስልጣናትና ከገዢው ፓርቲ ጋር የጥቅም ግንኙነት የሚፈጥሩ እንደመሆናቸው መጠን ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን በፋይናንስና በዕውቀት የሚደግፉ አይደሉም:: በሌላ በኩል ዲያስፖራው የሚያደርገው ድጋፍ ከፖለቲካ ግለት ጋር የተያያዘ እንጂ ዘላቂነት ያለውና በመርህ ላይ የተመሰረተ አይደለም:: ከንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ከላይ እንደተመለከተው ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ባላቸው ደካማ ተቋማዊ አቅም የተነሳ ያገኙትን ገቢና ድጋፍ በተሳለጠና ውጤታማ በሆነ መንገድ የመጠቀማቸው አቅም እጅግ ደካማ ነው:: ይህም በመሆኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በምርምር ላይ የተመሰረቱ፣ የማህበረሰቡን ችግሮች ሊፈቱ የሚያስችሉ የጋራ አጀንዳ የመንደፍ ብሎም ማህበረሰቡ ውስጥ ዘልቆ በመግባት ማህበረሰቡን በነሱ ዙሪያ በማሰባሰብና የቅቡልነታቸውን ደረጃ ከፍ በማድረግ የመደራደርና የመገዳደር አቅማቸውን ገንብተው ገዢውን ፓርቲ ሰላማዊ በሆነ መንገድ በማስገደድ የፖለቲካ ፍላጎታቸውንና አጀንዳቸውን ማስፈጸም የሚችሉበት እድል እጅግ ጠባብ ሆኗል::

ባህላዊ አቅም (Cultural capital) የሚለው ዕሳቤ እ.አ.አ በ1973 ቦርዲዎ እና ጃን ክላወዴ "Cultural Reproduction and Social Reproduction" ከተዋወቀ ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ትርጓሜዎችን ቢሰጠውም በዚህ ጹሁፍ ግን የገባበት አግባብ ግን ተቋማዊ ፖለቲካል ሶሾሎጂስትስ (Institutional Political Sociologists) በሚጠቀሙት አረዳድ ነው:: ይኸውም <እንዴት አንድ ፖለቲካል ፓርቲ እንደተቋም የማህበረሰቡን ባህልና ወግ ተረድቶ በሚያደርገው ትንታኔ በማህበረሰቡ ውስጥ የጋራ ጠቀሜታ (Common Good) ማስፈን ይችላል?> የሚለውን ነው:: በዚህ አረዳድ መሰረት ምን ያህል የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች የማህበረሰቡችን ችግሮች የመረዳት ባህል አዳብረዋል? ምን ያህልስ እርስ በራሳቸው በሚያደርጓቸው ግንኙነቶችና መስተጋብሮች የአጠቃላዩን ማህበረሰብ ማህበራዊ ዕሴቶች ተከትለዋል? ምን ያህልስ ህዝቡ የማህበራዊና ባህላዊ ንቃተ ህሊናው እንዲያድግ እረድተዋል? የሚሉት ጥያቄዎችን ማየት ተገቢ ነው:: በፖለቲካ ፓርዎች መካከል ያለው ቅራኔ በተወሰነ መልኩ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ቅራኔ የሚያንጸባርቅ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ በፖለቲካ ልሂቃኖች መካከል ያለው የስልጣንና የጥቅም ሽኩቻ በምንም መልኩ ቢሆን በህዝቡ ውስጥ ያለውን አብሮ-የመኖር ዕሴቶች የሚያንጸባርቅ አይደለም:: በብሔር ብሔርተኛነት ላይ የተመሰረቱ ፖለቲካ ፓርቲዎች በተወሰነ መልኩም ቢሆን እንወክለዋለን የሚሉትን ብሔር የማህበራዊና ባህላዊ ንቃተ-ህሊናው እንዲያድግ አድርገዋል:: ሆኖም ግን

እንደመጨረሻ ውጤት የሚታየውን የጋራ ተጠቃሚነት ባህልን ከማዳበርና የጋራ በጎ (Common Good) አጀንዳ ከመንደፍና የህዝቡን ችግሮች በመቅረፍ ቅብሉነታቸውን በማሳደግ የመደራደርና የመገዳደር አቅማቸውን የመገንባት ሂደት ግን ገና ብዙ የሚቀረው ነው::

ከላይ ከተጠቀሱት ሶስት አቅሞች አንጻር ሲታይ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች የተሻለ ደረጃ ያላቸው በምልክታዊ አቅም (Symbolic capital) ነው:: ምንም እንኳን ምልክታዊ አቅም በተለያዩ ሁኔታዎች ሊገለጽ ቢችልም፤የኢትዮጵያ ተቃዋሚ መሪዎች እንደግለሰብ ያላቸው አካዳሚክ ደረጃ እንደ ትልቅ አቅም የሚታይ ነው:: እንደ ተቋም ተቃዋሚ ፓርቲዎች እዚህ ግባ የሚባል ታሪካዊም ሆነ ማህበራዊ ዳራ የላቸውም:: ለምስሌ እንደነጻነት ተምሳሌት ተደርገው ይታዩ የነበሩት በዋናነት ብሔር ተኮሮቹ ሕወሓትና ኦነግ እንዲሁም ህብረ-ብሔሮቹ ኢህአፓና ቅንጅት ነበሩ:: ከነዚህ ውስጥ አሁን ከሕወሓት ውጪ ሁሉም ከመኖር ወደአለመኖር ደረጃ ደርሰዋል:: <የተማረ ይግደለኝ!> በሚል ማህበረሰብ ውስጥ የተቃዋሚ መሪዎች እንደግለሰብ ያላቸው አካዳሚክ ደረጃ በሌሎች አቅሞች ቢታገዝ ኖሮ ሊያስገኝላቸው የሚችለው የቅቡልነትና ሊፍጥርላቸው የሚችለው የመደራደር አቅም እጅግ ከፍተኛ በሆነ ነበር:: ይህ ባለመሆኑ ያላቸውን ምልክታዊ አቅም ከገዢው ፓርቲ አመራሮች ትችት እንኳን ሊያድኑት አልቻሉም:: ለምሳሌ በ2002 የምርጫ ውድርር በኢቲቪ በሚተላፈው ፕሮግራም ላይ አቶ ሬዲዋን ሁሴን ይህን አቅማቸውን ሲተች <አቧራ እያራገፉ ብዙ መጽሃፍ ብቻ ማንበቡ ዋጋ የለውም:: የኢትዮጵያን ሁኔቴ መረዳት ጭምር እንጂ!> በማለት ነበር:: ይህ ንግግር አንድም ያላችሁ አካዳሚክ ዕውቀት ከዘመኑ የዕውቀት ደረጃ (state of the art) ጋር አይሄድም፣ ሁለትም ዕውቀታችሁ ጥራዝ ነጠቅ እንጂ የሃገራችንን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል አይደለም ማለት ነው:: ምልክታዊ አቅም በባህሪው ከተጨባጭ ባህላዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች ጋር ስለሚያያዝና ምንም አይነት ገደብ ስለሌለው ቀጣይነት ያለው ማህበራዊ ግዴታዎችን የመወጣትና እራስን የማስተዋወቅ ስራ ይጠይቃል:: በዚህም ምክንያት ተቃዋሚ መሪዎች ያላቸውን አቅም የማስጠበቅና በዚህም ማህበረሰባዊ ቅቡልነታቸውን የማሳደግና የመደራደር አቅማቸውን የመገንባት ከፍተኛ የሆነ ውስኑነት ይታይባቸዋል::

## ፖለቲካል ስትራተጂ፣ ታክቲክና ፖለቲካል ውሳኔ ተተንባይነት

ፖለቲካል ስትራተጂ ማለት ፖለቲካ ፓርቲዎች የነደፉትን ፖለቲካል ፕሮግራም እንዴት አድረገው ሊያስፈጽም እንደሚችሉ ከሀገራዊና አለማቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ተነስተው የሚነድፉት አካሄድ ነው:: ፖለቲካል ታክቲክ ደግሞ በተነደፈውን ፖለቲካል ስትራተጂ እንዴት እንደሚፈጸም የሚያመለክት ዝርዝር የአፈጻጸም ሂደትን የሚያመለክት ነው:: አንድ ፖለቲካ ፓርቲ የመደራደርና የመገዳደር አቅሙን ለመገንባት በዋናነት ፖለቲካል ስትራተጂውንና ታክቲኩን ከማህበረሰባዊው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ያገናዘበና በማህበረሰቡ ውስጥ ዘልቆ በመግባት ማህበረሰቡን ማደራጀትና ማሰባሰብ አለበት:: በዚህ ሂደት ውስጥ አንደኛ ፖለቲካ ፓርቲው በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነትን ያተርፋል:: እንዲሁም ደግሞ በሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋርም የመደራደር አቅሙን ከፍ ያደርገዋል:: በተያየዘ መልኩም ከሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመደራደር የጋራ ፖለቲካ አጀንዳ ነድፈው የጋራ ተጠቃሚነትን ያረጋግጣሉ::

በኢትዮጵያት ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አንጻር ይህ አካሄድ በመሰረቱ ብዙ የተለመደ አይደለም:: በአብዛኛው ፖለቲካ ፓርቲዎች ከነመኖራቸው ራሳቸውን ለማህበረሰቡ የሚያስተዋውቁት ምርጫ የተወሰነ ጊዜ ሲቀረው ብቻ ነው:: ከምርጫ በኋላ እንቅስቃሴ ቢኖር እንኳን መሪዎቹ ጎልተው የሚወጡበትና እንደድርጅት ፖለቲካ ፓርቲዎች የማይታዩበት ነው:: „የምርጫ ፖለቲካ ፓርቲ“ የሚለው አሰያየም በተለያዩ ሙሁራን እየተንጸባረቀ ያለው ለዚህ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ከማህበረሰባዊው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ፖለቲካል ስትራተጂና ታክቲክ ያላቸው ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በቁጥር እጅግ አናሳ ናቸው:: ፖለቲካል ስትራተጂና ታክቲክ ያላቸው እንኳን በማህበረሰቡ ውስጥ ዘልቀው ስላልገቡ አይደለም በአጠቃላይ ህዝቡ ይቅርና የፖለቲካ ንቃተ-ህሊናቸው ከፍ ብሏል በሚባለው የህብረተሰብ ክፍል እንኳን በተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ያለው ዋና ዋና ልዩነቶች እንኳን አይታወቅም:: ለዚህም ነው የልደቱ ፓርቲ፣ የበየነ ፓርቲ፣ የመራራ ፓርቲ፣ የሃይሉ ሻወል ፓርቲ፣ የቡልቻ ፓርቲ ወዘተ እየተባለ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በጋዜጦች ጭምር የሚዘገበው::

የተቃዋሚ ፖለቲካል ፓርቲዎች ያላቸው ድርጅታዊ መዋቅራዊ ሁኔታ በራሱ የነደፉትን ፖለቲካል ስትራተጂና ታክቲክ ሊያስፈጽማቸው የሚችል አይደለም:: ምን ይህሉ በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች የተደራጀና በሰው ኃይል

የተዋቀረ ቢሮ አላቸው? አብዛኞቹ አዲስ አባባ ከሚገኘው ጽ/ቤታቸው ውጭ ሌላ በተለያዩ ክልሎች ጽ/ቤት የላቸውም:: በሌላ በኩል በድርጅታዊ መዋቅራቸው ውስጥ ግልጽ የሆነ ከላይ ወደታች (vertical) የተዋረደ የስልጣን ክፍፍል እንዲሁም በተለያዩ ክፍሎች መካከል የጎንዮሽ (horizontal) የስራ ግንኙነት የላቸውም:: ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው እስከዛሬ ድረስ ፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጣዊ መከፋፈል ሲያጋጥማቸው የሚነሱት ሶስት ምክንያቶች ናቸው:: እነርሱም ግለሰባዊ አገዛዝ መስፈን፣ የመተዳደሪያ ደንብ መጣስና የተለመደውን ውስጣዊ አሰራር አለመከተል ናቸው:: የነዚህ ሶስት መሰረታዊ ችግሮች መነሻ ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ያለሆነ ከላይ ወደታችና የጎንዮሽ የስልጣንና የስራ ክፍፍሎሽ አለመኖር ነው:: ይህም መዋቅር በራሱ የሚቆም ሳይሆን ፖለቲካል ስትራተጂንና ታክቲክን የሚከተል እንደመሆኑ መጠን በተደጋጋሚ የሚከሰቱት ውስጣዊ መሰነጣጠቆች የሚያመለክቱት ነገር ቢኖር ግልጽ የሆነና ሁሉም የፓርቲው አመራሮችና አባላት የሚያስተገብሩት ፖለቲካል ስትራተጂና ታክቲክ አለመኖርን ነው::

ይህም በመሆኑ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ግልጽ የሆነና ማህበረሰባዊ መሰረት ያለው የፖለቲካ አጀንዳ መንደፍና በየወቅቱ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚደረጉ ክርክሮችንና ውይይቶችን በበላይነት መምራት አልቻሉም:: ይህም የሆነው አንድም ደካማ ድርጅታዊ አቅም በመኖር ፖለቲካል ስትራተጂን፣ ታክቲክንና የውስጥ ደንብን ተቋማዊ ማድረግ አለመቻሉ፣ ሁለትም ብቃት ባለው የሰው ኃይል አለመደረጃታቸው፣ ሶስትም ድርጅታዊ መዋቅራቸው ወደህዝቡ የቀረበ አለመሆኑና በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው የቅቡልነት ደረጃ እዚህ ግባ የማይባል መሆኑ ነው:: በዚህም የተነሳ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ከገዢው ፓርቲ ጋር የመደራደር አቅማቸው ውስን ነው:: ገዢው ፓርቲ ከሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታና ከብዙዎቹ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ችግሮች ውጭ ባይሆንም መንግስታዊ፣ ወታደራዊ፣ የደህንነት መዋቅር እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ስልጣን በመያዙ ምክንያት ያሉበትን ውስጣዊ ችግሮች ለመሸፈን ችሏል (ሕወሓት የ1993ቱን ውስጣዊ ክፍፍል የፈታበት መንገድ ልብ ይሏል):: የተቃዋሚ ፓርቲዎች ፖለቲካል ስትራተጂና ታክቲክ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ተቀባይነት ከፍ ከማድረግ አንጻርም ሆነ የጋራ አጀንዳ በመንደፍ „አንድ-ለአንድ“ እና „አንድ-ለብዙ“ ከገዢው ፓርቲ ጋር እስካሁን ድረስ በተደረጉ የመደራደር ሂደቶች አቅማቸውን ለመገንባት ያስቻላቸው ሆኖ አይታይም::

ከላይ በተመለከቱት ነባራዊ ሁኔታዎች ምክንያት ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች የሚወሰዱቸው ፖለቲካዊ አቋሞችና ውሳኔዎች ተተንባይ (predictable) አይደሉም:: ተተንባይ ያልሆኑ የፖለቲካ አቋሞችና ውሳኔዎች መብዛታቸው መንስኤዎቹ በአንድም ሆነ በሌላ አግባብ ከላይ የተጠቀሱት ድክመቶች ናቸው:: የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አንዱ መለያ ባህሪ እየሆነ የመጣው የሚወስዷቸውን ፖለቲካዊ አቋሞችና ውሳኔዎች ተተንባይ አለመሆን ነው:: እስካሁን ውስጣዊ መሰነጣጠቅ የታየባቸው ፓርቲዎች ውስጥ እንደልዩነት ከተነሱት ውስጥ ውስጠ-ፓርቲ ስርአትን የተከተለ ውሳኔ አሰጣጥ መኖሩን ነው:: ነገር ግን ይህ ችግር ገኖ የሚወጣው በፓርቲው ውስጥ በሚኖሩ ቡድኖች መካከል ስምምነት ላይ ሳይደረሰ በሚወሰኑ ፖለቲካ ውሳኔዎች ምክንያት ነው:: ለምሳሌ የአንድነት ፓርቲ መሰንጠቅ ከነ አቶ እስዬና ዶ/ር ነጋሶ ወደ ፓርቲው ለማስገባት በሚደረግ ጥረትና አንድነት መድረክን ለመቀላቀል በመወሰኑ ምክንያት ነው:: ተተንባይ ያልሆኑ የፖለቲካ አቋሞችና ውሳኔዎች ሲበዙ በአባላትና በደጋፊዎች መካከል አደናባሪ ሁኔታን የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ በማኅበረሰቡ ውስጥ የቅቡልነትንና የታአማኒነትን ጥያቄዎች ያስነሳል:: ከዚህም በተጨማሪ ይህ ሁኔታ በመርህ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ አጀንዳዎችን ነድፎ ከሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር እና ከመንግስት ጋር የሚደረጉ ድርድሮች ላይ ተጽእኖ ይፈጥራል:: ይህም የመደራደር አቅምን መልሶ የሚጎዳ ነው:: በመሆኑም የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች የመደራደር አቅማቸው ውስኑነት በተቃዋሚ ፓርቲዎቹ የውድቀት አዙሪት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየወረደ መጥቷል (ውጫዊ ተጽዕኖዎች እንደተጠበቁ ሁነው)::

## እንደማጠቃለያ

የተቃዋሚ ፓርቲዎች የመደራደር አቅም በተለያዩ አላባውያን ሲታይ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: ይህም የዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማስፈን የሚደረገውን እንቅስቃሴ በጣም እየጎዳው ይገኛል:: የተቀራረበ የመደራደር አቅም ሲኖር ፖለቲካል ፓርቲዎች በሚገነቡት ዴሞክራሲያዊም ሆነ አስተዳደራዊ ተቋሞች ዙሪያ መግባባት ስለሚደርሱን እኩል ተጠቃሚነት በሚያሰፈን ሁኔታ ተቋሞቹ ስለሚገነቡ ዘላቂነትንና በማኅበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያደርጋል:: ይህም በመሆኑ በሀሳብ ልዩነቶች ለይ በሚደረጉ ክርክሮች (arguments) እና ዕውቅና በመስጣጣት ላይ የሚመሰረት እንጂ የግለሰቦችን ማንነት በማንቋሸሽ (character assassination) ላይ ስለማይመሰረት በመሰረታዊነት ደረጃ የፖለቲካል ባህሉን ሰላማዊ እንዲኖን ያስችላል:: ነገር ግን የኢትዮጵያ

ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንደተቋም ሆነ መሪዎቹ እንደግለሰብ የመደራደር አቅማቸው ውሱን ከመሆኑም በላይ የሚደራደሩባቸው አጀንዳዎችና ያላቸው አቋም የሚመጣጠን ባለመሆኑ ሰላማዊ ፖለቲካል የትግል ባህል እንዳይሰፍን ሆኗል::

ይህን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል ቀጥተኛና ቀላል የሆነ ፎርሙላ የለም:: ይህ ችግር በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በታዳጊ አገሮች የሚታይ ከፓርቲ ፖለቲካና በተነጻጻሪ ሁኔታ ሁሉን እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ ስርአት ከመፍጠር አንጻር የልምድ እጥረቶች በሚስተዋልባቸው ሃገሮች ጭምር የሚታይ ነው:: ይህም በባህሪው ችግሩ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሽግግር ሂደት ውስጥ ሊታይ የሚችል ነው:: በመሆኑም፣ የፖለቲካ መሪዎችና ወጣቱ ትውልድ ከ1960ዎቹ እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የተጓዙበትን ሂደት በመገምገም ጠንካራ ጎኖቹን ይዞ በመቀጠል፤ ደካማዎቹን ደግሞ በማረም ወደፊት መጓዝን ይጠይቃል:: የችግሩን ምንጭ በንደፈ-ሃሳባዊ እይታዎች ማድረቅ አይቻልም:: በዋናነት ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስፈልገው የተግባር ምላሽ ነው:: ተግባሮቹን ግን እንደየችግሮቹ ጥልቀትና አንገብጋቢነት እየለዩና ቅደም ተከተል እየሰጡ፣ የማስፈጸሚ ስልቶችን እየቀየሱ፣ ልዩነቶችን ተገቢውን ክብር ሰጥቶ ነገር ግን በጋር በሚያስማሙ ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ በጋር ወደ ተግባር መግባትን የሚጠይቁ ናቸው:: ይህም የድሮው የፖለቲካ ልሂቃን ያሌላቸውን አዲስ ባህልን የመገንባት ሂደትን ይጠይቃል::

# ተቃዋሚን በአንድ የመፈረጅ ጣጣ

መቼም ተቃዋሚ ስል የትኛው ዓይነቱን ተቃውሞ ለማለት እንደፈለኩ ሳይገባችሁ የቀረ አይመስለኝም፡፡ በሃገራችን በአሁኑ ሰዓት የኢሕአዴግን አገዛዝ ወይም መንግሥትን የሚቃወሙትን ማለቴ ነው፡፡ በግለሰብ ደረጃ እና በተቋም መልክ ያልተደራጁትን ተቃዋሚዎች ትተን (እነርሱ ቢበዙም) ከምርጫ ቦርድ ዕውቅና ያገኙ ፓርቲዎችን ብቻ ብንቆጥር 79 ናቸው፡፡ (ምንጭ፤ [የምርጫ ቦርድ ድረገጽ])

በተቃዋሚ ፓርቲዎች ብዛት ደረጃ የሚሰጥ ዓለም አቀፍ ተቋም ቢኖር ኖሮ በዚህ እንኳን ከመጨረሻ ሳይሆን ከመጀመሪያ አንደኛ እንደምንሆን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን በወቅቱ ያላቸውን የሥራ ብቃት እና ቆራጥነት ማነስ ትተን፤ በቁጥር መብዛታቸው ብቻ በራሱ የፖለቲካ አካሄዳችን ብዙ እንደሚቀረው እና የአመለካከት ችግር እንዳለ በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡ እንጂ በሰላም ሃገር ለአንዲቷ ሃገር ይሄ ሁሉ ፓርቲ እኔ ነኝ ብቸኛው አማራጭ በሚል የተለየዩ አካሄዶችን እያሳየ ልባችን ባልከፋፈለው ነበር፡፡

የተቃዋሚዎቹ ብዛት ከላይ እንደገለፅኩት ሆኖ ሳለ፤ በኢህአዴግም በተቃዋሚዎችም ዘንድ ተቃዋሚዎችን እንደ አንድ የመቁጠር/የመፈረጅ ችግር በስፋት የሚስተዋል ነገር ነው፡፡

## ከኢሕአዴግ ጎራ

የኢሕአዴግ ፓርቲ፣ በፓርቲው ስር የሚገኙ ተቋማት፣ የፓርቲው አድናቂ፣ አፍቃሪ እና ተቆርቋሪ የሆኑ ከዚህ ምድብ ይካተታሉ፡፡ በዚህ ምድብ ያሉ ስለተቃዋሚዎች ሲናገሩ ስትሰሙ ወይም የጻፉትን ስታነቡ በአብዛኛው አስተያየታቸውን የሚሰጡት ሁሉንም እንደ አንድ በመቁጠር መሆኑን መታዘባችሁ ግድ ነው፡፡ እንግዲህ ያሳያችሁ 80 የሚጠጉ ተቃዋሚ ፓርቲ መኖራቸው እየታወቀ፤ ሁሉም ደግሞ የየራሳቸው ልዩነት እና አቋም እንዳላቸው እየታወቀ፤ ለምን ሁሉንም ጨፍልቀው በአንድነት፣ አንድ ዓይነት ስድብ እንደሚሳደቡ (መቼም ‹‹ምስጋና›› አንጠብቅባቸውም) ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ነው፡፡ ተቃዋሚዎቹ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር ኢህአዴግን መቃወማቸው እና ተቃዋሚነታቸው ብቻ ነው እንጂ የሚቃወሙበት መስመር፣ ምክንያት፣ የያዙት አጀንዳ፣ ዓላማቸውና እና የሚከተሉት አሰራር ፍፁም የተለያየ ነው፡፡

እውነቱ ይሄ ሆኖ ሳለ በዚህ ምድብ ያሉት ግን አንደኛው ተቃዋሚ ያለውን ሐሳብ ‹‹ተቃዋሚዎች እንዲህ አሉ፣ ሊያደርጉ ነው፣ ናቸው›› በሚል የሁሉም እንደሆነ በማስመሰል ተቃውሞን በሙሉ በአንድ በመፈረጅ አስቸጋሪ መልክ አስይዘውታል፡፡

እንግዲህ አስቡት፤ ለምሳሌ እኔ በግሌ /እንደ አንዲት ነጠላ ግለሰብ/ ኢሕአዴግን ተቃውሜ ያነሳሁትን ሐሳብ፤ ‹ተቃዋሚዎች እንዲህ አሉ› ወይም ‹ይላሉ› ተብሎ የኔ የግሌ ብቻ የሆነው ሐሳብ የሁሉም ነው ሲባል፤ ወይንም ደግሞ አንድ ተቃዋሚ ፓርቲ ተቃውሞ ያነሳውን ሐሳብ፤ የተቀሩት ተቃዋሚዎች እንዳሉት ተደርጎ ሲወሰድ እና የተቃዋሚዎች የጋራ ሐሳብ እንደሆነ ሲቀቆጠር፡፡

በተጨማሪም እነዚህ ምድቦች  የሚቃወምን ግለሰብ ከተቃዋሚ ፓርቲ ጋር የማስተሳሰር ክኅሎትም አላቸው፡፡ አንድ ግለሰብ ከተቃወም በቅድሚያ በአእምሯቸው የሚመጣው ከጀርባው የትኛው ፓርቲ እንዳለ ነው እንጂ፤ ግለሰብ እራሱን ችሎ መቃወም እንደሚችል አያስቡም ወይም ማሰብ የሚፈልጉም አይመስለኝም፡፡

## ከተቃዋሚ ጎራ

በዚህ ምድብ ኢሕአዴግን በተለያየ ደረጃ የሚቃወሙ ግለሰቦች፣ ሚዲያዎች እና የፖለቲካ ፓርቲ መስርተው የሚቃወሙትን ይመለከታል፡፡ በዚህ ምድብ የሚገኙት ከላይ እንደተነጋገርነው ብዛታቸውም የትዬለሌ ነው ልዩነትም አላቸው፡፡ ሆኖም ብዙዎቹ ‹የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው› በሚለው ብሒል መሠረት የተቃኘ የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ሲብራራ፦ እከሌ የተባለ ግለሰብ ወይም ሚዲያ ወይም ፓርቲ የተቃወመበትን ሐሳብ ሌሎችም በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ተቃዋሚ ግለሰቦች፣ ሚዲያዎች ወይም ፓርቲዎች እንዲቀበሉት/እንዲደግፉት ይጠበቃል ማለት ነው፡፡ ካልሆነ የደጋፊ ብዛት ባለው ተቃዋሚ፤ ከተቃዋሚ ሰፈር የማግለል እና ስም የማጥፋት/ስም የመስጠት ዘመቻ ይካሄዳል፡፡ ገና ለገና በተቃዋሚ ጎራ ስላሉ በሁሉም ጉዳይ መስማማት እና ስምምነትንም መግለፅ ግዴታ መሆን የለበትም፡፡ አንደኛው ተቃዋሚ የሌላውን ሐሳብ ሁሉ

(ኢሕአዴግን ስለተቃወመ ብቻ) መቀበል ከቻለማ መከፋፈልን እና ተለያይቶ መሥራትን ምን አመጣው? ለምንስ ያ ሁሉ ፓርቲ ተመሠረተ?

በሁለቱም ጎራ በተደጋጋሚ ተቃዋሚን በአንድ በመፈረጅ የሚሠሩትን ስህተቶች ለማስወገድ፤ በኢሕአዴግ ጎራ ያሉት፣ በተቃወሚው በኩል ያለውን ልዩነት ከግምት ውስጥ ያስገባ እንቅስቃሴ ማድረግ እንደሚገባ እንዲሁም ተቃዋሚዎች ኢህአዴግን መቃወም ብቻ አንድ እንደማያደርግ በመገንዘብ ለልዩነቶቻቸው ዋጋ በመስጠት እና በመከባበር ላይ የተመሠረተ አካሄድ በመከተል፤ በሁለቱም ምድብ የሚገኙት የአመለካከት ለውጥ ማምጣት አለባቸው የሚል እምነት አለኝ።

# 'ተቃዋሚ' ስንል

ሕይወት በአንድ ቦይ አትፈስም፡፡ ሕይወት ፍኖተ ብዙ ናት፡፡ ዓለምም በተቃርኖ የተሞላች ናት፡፡ ለእያንዳንዱ ጫላ፣ ጫላቱ አለችው፤ ለእያንዳንዱ በለጠ፣ በለጡ አለችው፡፡ ማሕበራዊ ሕይወታችን፣ የፖለቲካው መንገድ፣ ኢኮኖሚያዊ ሀሳቡ ሁሉ በአማራጭ የተሞላ ነው፡፡ ስለ አይዲዎሎጂ ስታነሱ ካፒታሊዝም ወይስ ኮሚኒዝም ትባላላችሁ፣ ስለ ዕምነት ስታነሱ አንድ አምላክ ወይስ ብዙ ወይስ ምንም የሚል ሐሳብ ይነሳል፣ ስለ መብት ስታነሱ የግለሰብ መብት ወይስ የቡድን መብት ሲባል ትሰማላችሁ፡፡ ማለቂያ የለውም ተቃርኖው፡፡

ሕይወት ማለትም እነዚህን ተቃርኖዎች ስንመርጥ፣ ስንጥል፣ ስናሻሽል መኖር ነው፡፡

## የፖለቲካ ተቃርኖ

ፖለቲካም ከዚህ የሕይወት ሕግ የተለየ መንገድ የለውም፡፡ ለምሳሌ አንድ ትንሽ ከተማ ውስጥ፤ ሁለት ፖለቲከኞች አሉ እንበል ሁለቱም ሕዝቡ እንዲወዳቸው ጥረት ያደርጋሉ፡፡ አንዱ ለሕዝቡ ‹‹የህብረተሰቡ ዋነኛ ችግር የእንቅልፍ ማጣት ስለሆነ እኔን ከመረጣችሁ የምን መጨናነቅ፣ ከውጭ ሀገር ለእያንዳንዱ ቤተሰብ አንድ የስነ-ልቦና ባለሙያ አስመጥቼ በመቅጠር የዕንቅልፍ ችግርን በ7 ቀናት ውስጥ አስወግዳለሁ›› እያለ ሊቀሰቅስ ይችላል፡፡ ሌላው በበኩሉ ‹‹የከተማዋ ህብረተሰብ እንቅልፍ አጥቶ መሰቃየቱ የኔ የእናንተ መልካም አገልጋይም ስቃይ ነው፡፡ እኔን የመረጣችሁ ጊዜ ግን መለኮታዊ ኃይል ከእንቅልፍ እጦት እንደሚገላግላችሁ አትጠራጠሩ›› እያለ ለምርጫው ሊተጋ ይችላል፡፡ ለእንቅልፍ እጦቱ የቀረቡት መፍትሄዎች የተለያዩ መሆናቸው ህዝቡ አማራጭ እንዲያገኝ እና ያመነበትን እንዲመርጥ ያስችሉታል፡፡

በነገራችን ላይ በከተማዋ ውስጥ ያለው የእንቅልፍ እጦት ችግር ዋነኛ መነሻ ከተማዋ ውስጥ የተተከለ ትልቅ የቆዳ ፋብሪካ የሚያወጣው ድምፅ ሊሆንም ይችላል፡፡ ፖለቲከኞቹም ይሄን ችግር ሊስቱት ይችላሉ፡፡ ዋነኛው የሕዝቡ ስቃይም ችግሩን የሚረዳለት ሰው ሲያጣ ነው፡፡

## ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ

ኢትዮጵያ ውስጥ የፓርቲ ፖለቲካ ከተጀመረ ገና 50 ዓመት እንኳን አልሞላውም፡፡ በዚህ ሁሉ ጊዜ ምን አበርክተዋል የሚለው እጅግ ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ነገር ነው፡፡

የንጉሣዊ ስርዓቱ በመውደቂያው ዋዜማ ብቅ፣ ብቅ ያሉት ፖለቲካ ፓርቲዎች ንጉሱ እንደ ወደቁ ወደ ስልጣን መንበሩ ቀረብ ቀረብ ማለት ጀመሩ፡፡ ያሳዝናል! በመጀመሪያ ሁሉም ግራ ዘመም ፓርቲዎች ብቻ ነበሩ፡፡ ሲከተልም ለህዝቡ ያቀረቡለት ሀሳብም ‹‹እኔ ከእርሱ የበለጠ ግራ ዘመም ነኝ›› እያሉ ለህዝቡ እንግዳ የሆኑትን እነ ማርክስን ካላመለክ፣ እነ ሌኒንን ካላወደስ አንተማ ኢምፔሪያሊስት ነህ እየተባባሉ አንድ ሁለት ያሉት ፓርቲዎች ፍፃሜያቸው አሳዛኝ ሆኖ አለፈ፡፡ አሸናፊው ቡድንም ሀገሪቱን በመሳሪያ አስተዳድራለሁ ብሎ ታገለ፡፡ ብሎ፣ ብሎ ግን እሱም ወደቀ፡፡

ኢህአዴግ ስልጣን ከመያዙ ጋር ተያይዞ የፖለቲካ ፓርቲዎች ነፃ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ መፍቀዱ ከስኬቶቹ የመጀመሪያው እና ዋነኛው ነው፡፡ ይሄንም ተከትሎ በዛ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ መድረኩ ብቅ፣ ብቅ አሉ፡፡

## ተቃዋሚው ከየት ወደየት?

ዲሞክራሲና ዲሞክራሲያዊነት በምስራቅ/ምእራብ ክፍፍል ማግስት ሦስተኛው ማዕበል (The Third Wave) ተብሎ ብቅ ካለ በኋላ የፓርቲ ፖለቲካ የዲሞክራሲው ማሳያ ተደርጎ ለህዝቡ እንዲቀርብ አስችሏል፡፡ ኢህአዴግም የዚህ የታሪክ አካል በመሆን የተቃውሞ ፖለቲካን የዲሞክራሲው መገለጫ እንዲሆን ከፈቀደ በኋላ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በየሰፈሩ ብቅ፣ ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡ ገና ከመጀመሪያው ኢህአዴግን ሊቀናቀን ይችላል የተባለው ኦነግ አልቻልኩም ብሎ፡

‹‹እልም ያለው ጫካ፣ እልም ያለው ዱር፣

ሲነጋገር ያድራል ከመውዜሩ ጋር፡፡›› እያለ ጫካ ገባ፡፡

ከዛ በመቀጠል አንዳንድ በተለይም ዘውግ ተኮር ፓርቲዎች ብቅ፣ ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡ የዘውግ ተኮር ፓርቲዎች ወደ ፖለቲካው መምጣታቸው ያስደነገጣቸው ግለሰቦች ‹‹የቅይጥ ብሄር ብሄረሰቦች ፓርቲ›› ብለው ፓርቲ እስከ መመስረት ደርሰዋል፡፡ ሀገር አቀፍ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም የስልጣን ሽኩቻው አልለቃቸው ብሎ ግንባር ሲፈጥሩ እና በግንባራቸው ሲደፉ ሁለት ሀገር አቀፍ ምርጫዎች አለፉ፡፡

ሦስተኛው ሀገረ አቀፍ ምርጫ ግን የተቃማዊውን ጎራ በተለየ መሰረት ላይ አስቀመጠው፡፡ የህዝቡን አመኔታም አስገኙ፣ በምርጫውም አስገራሚ ድል አገኙ፡፡ ምርጫውን እንዳሸነፉ ተናገሩ፣ ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ግን ‹‹ከበፊቱ የተሻለ ድል አምጥታችኋል፣ ነገር ግን ያሸነፍኩት እኔ ነኝ›› ብሎ ድል አወጀ ዓለማቀፍ ታዛቢዎችም ምርጫው ዓለምአቀፍ መለኪያዎችን ያላሟላ ነው አሉ፡፡

ከዛም ለትንሽ ጊዜ ብልጭ ያለው ጠንካራ የተቃውሞ ኃይል እያነሰ፣እያነሰ መጥቶ አሁን ሞተ ሲባል ጫፍ ላይ ደርሷል፡፡

ለመሆኑ የተቃውሞ ኃይሉ አሁን ላይ ሆኖ ምን አላማ ይዟል? ቁርጠኝነቱስ? መጨረሻውስ ምን ይሆን? አንዳንድ አመላካቾችን አንመልከት እስኪ፡፡

## የተቃውሞው ዓላማ

አንዳንዱ የተቃዋሚ ኃይል ተቃውሞውን የሚጀምረው ‘ተቃዋሚ’ ልንባል አይገባም በማለት ‘ተቀናቃኝ’ በሉን በሚል ጥያቄ ነው፡፡ ‹‹ተቃዋሚ ማለት ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲን ፖሊሲዎች በመቃወም ለመተካት እራሱን የሚያዘጋጅ ማለት ነው በሌላ ሀገርም በተመሳሳይ ነው Opposition Party ነው የሚባለው›› ሲባል የለም ስሜን ቀይሩ አጀንዳ አንድ ሆኖ ይመዘገባል፡፡

ሲቀጥል አብዛኛው ፖለቲካ ፓርቲ አላማ አንድን የተወሰነ ሕዝብ ብቻ በመወከል መነሳቱ እይታውን ከመንደር ውስጥ የስልጣን ፍላጎት በላይ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ጥርስ ፍንጭት* ሰዎች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ኢጥፍሰዲድ) ተቋቋመ እንበል፡፡ እንግዲህ ዋነኛ አላማው ጥርስ ፍንጭት ሰዎችን በጥርሳቸው እንደ ፈለጉ እንዲስቁበት ለማድረግ ሊሆን ነው፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ በመጀመሪያ ጥርስ ፍጭት ሰዎች እንደፈለጉ እንዳይስቁ የመብት ክልከላ አለ ወይ? የሚል ሲሆን በማስከተልም የመብት ጥሰቱስ ካለ የጥርስ ፍንጭት ሰዎችን መብት ብቻ ለማስከበር መነሳት እና ተሳክቶለት በጥርሳቸው እንደ ፈለጉ እንዲሆኑ ቢያደርግ መብቸው ሙሉ ሊሆን ይችላል ወይ? የሚል ጥያቄንም መመለስ የሚችል አይመስልም ይህ ‘የአንድ ወንዝ ፓርቲ’፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ በይፋ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱት ፓርቲዎች 76 እንደሆኑ የቦርዱ ዌብሳይት ያመለክታል ከነዚህ ውስጥ ከ53 የሚሆኑት ለአንድ ዘውግ (በተለምዶ ብሔር) መብት መከበር የሚታገሉ ሲሆኑ፣ ይሄም ከላይ ያነሳናቸው ጥያቄዎች በወሳኝነት መላሽ እንደሚስፈልጋቸው ያስገነዝበናል፡፡

ሌላው ከአላማቸው ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ግልፅ አላማ ያለው ፓርቲ ስንት ነው? ብለን ስንጠይቅ ነው፡፡ በምርጫ 2002 በአስገራሚ ሁኔታ ‹‹ፖሊሲ የለንም፣ ፖሊሲ የምንቀርፀው የኢትዮጵያ ህዝብ ከመረጠን በኋላ ከህዝቡ ጋር አብረን መክረን ነው፡፡›› የሚል ‘ፓርቲ’ ህዝቡን ‘ነፃ’ ለማውጣት እንደተሰለፈ አይተናል፡፡ ለመሆኑ ስንቱ ፓርቲ ነው አላማ ቀርፆ ህዝቡን አላማየን አይታችሁ ምረጡኝ የሚለው? ቢሮውን መኖሪያ ቤቱ ውስጥ አድርጎ አባላትን በዘመድ አዝማድ እየመለመለ ህዝብን እመራለሁ፣ እኔ ነኝ ትክክለኛ አማራጭ ቢል ህዝቡስ ምን አይቶ ይቅረበው? ለነገሩ ይሄስ ቢሆን የምርጫ ሰሞን ግርግር አይደል?
ለመሆኑ 31,869 ለሚሆነው የሐረሪ ሕዝብ 3 የተለያዩ ፓርቲዎች እኔ እሻልኻለው ብለው ሲቀርቡለት ምን ዓይነት የአላማ ልዩነት ይዘው ነው ወይስ ዙፋን ነው ጉዳዩ? እንድንል ያደርገናል፡፡

## ቁርጠኝነት

ከላይ እንደ አየነው የአላማ አለመኖር፣ መደብዘዝ ወይም መጥበብ የተቃዋሚው ጎራ የመጀመሪያው ፈተና ነው፡፡ እሽ አላማው እንዳለ ሆኖ ፓርቲዎች ያስቀመጡትን አላማ ለማስፈፀም ምን ያክል መሰጠቱ (Submission)

አላቸው? የሚለው ደግሞ ሌላው ጥያቄ ነው፡፡ ከላይ ያነሳነውን ምሳሌ እዚህም እናምጣው፡፡ የኢትዮጵያ ጥርሰ ፍንጭት ሰዎች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ኢጥፍሰዲድ) የተቋቋመለት አላማ ጥርሰ ፍንጭቱ ህዝብ በጥርሱ እንደፈለ እንዲሆን ማድረግ ነው እንበል፡፡ ፓርቲው ምን ያክል ከጥርሰ ፍንጭቱ የህብረተሰብ ክፍል ጋር አብሮ እየሰራ ነው? ለአላማውስ እስከ ምን ድረስ ነው የሚታገለው? ‹‹እኔ ድራፍት እየጠጣሁ ነው መታገል የምፈልገው›› እያለ ለሚታገልልት አላማ ሲል ከብርሌ አንገት እንኳን መራቅ የማይፈልግ ነው ወይስ እስከ ከርቸሌ ለመሄድ የወሰነ ነው? በምንዳ ተታሎ የጥርሰ ፍጭቱን ሕዝብ መብት ይሸጣል ወይስ በአቋሙ ይፀናል? እነዚህ ጥያቄዎች ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ካሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በየጊዜው የምንሰማቸው ዋነኛ ርዕሰ ጉዳዮች ናቸው፡፡

## ዲሞክራሲ ሲሉ

የኢትየጵያ ምርጫ ቦርድ በአሁኑ ወቅት በመዝገቡ ውስጥ ካካተታቸው 76 ፓርቲዎች ውስጥ 55ቱ 'ዲሞክራሲያዊ' ወይም 'ዲሞክራቲክ' የሚል ቅፅል በስያሜያቸው ውስጥ አካተዋል፡፡ ለምሳሌ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ፣ የጠምባሮ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ሕብረት፣ የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ፣ የደንጣ፣ ዱባሞ ክንችችላ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት፣ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ የሲዳማ ሀዲቾ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት እያለ ዝርዝሩ ይቀጥላል፡፡ ለመሆኑ ስንቶቹ ፓርቲዎች ናቸው እንደ ስማቸው ዲሞክራሲያዊ የሆኑት? ውስጠ ዲሞክራሲ (Democratic Centralism) በስንቶቹ ፓርቲዎች ውስጥ አለ? ከተመሰረተ አስራ ምናምን አመት የሆነው 'ዲሞክራሲያዊ' ፓርቲ እንዴት አንዴ እንኳን የድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ አይጠራም?

እንዴት አንድ የፓርቲ መሪ ራሱ ገንዘብ ሰብሳቢ፣ ራሱ ገንዘብ ያዥ፣ ራሱ ኦዲተር፣ ራሱ የፓርቲው ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅ እና አፅዳቂ ይሆናል? ምን አይነትስ 'ዲሞክራሲ' ለማምጣት ነው የሚታገለው?

የፓርቲ አባላት ‹‹ይሄ ነገር መልካም አይደለም ስለዚህ እንዲህ ይደረግ ሲሉ›› ከመንግስት ጋር ወግናችኋል፣ የስልጣን ጥመኞች ናችሁ፣ አድማ በፓርተው ውስጥ ለመምታት አቅዳችኋል እያሉ ማውገዝ እና ከፓርቲው ማባረር የተቃውሞው ጎራ ልማዳዊ ተግባር ሆኗል፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች ከነ መሪ ግለሰቦቻቸው ነገ ስልጣን ቢይዝ የሚያመጡት ዲሞክራሲያዊ ለውጥስ ምን ዓይነት ይሆን? አዎ፤ ፈተናው ብዙ ነው፡፡

ለመሆኑ የተቃውሞውን ሀይል እንዲህ በሞት አፋፍ ላይ ያስቀመጠው ማን ነው? ወደፊትስ ምንድን ነው መደረግ ያለበት? የሚለውን ለማየት በቀጣይ ጽሑፍ እንመለስበታለን፡፡

------

* ፍንጭት ማለት የፊት ጥርሱ ክፍት የኾነ ማለት ነው፡፡

# ተቃዋሚውን ማን ገደለው?

ባለፈው ሳምንት ማነው ተቃዋሚው በሚል ርዕስ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲ መንደር የቆበትን አፋፍ፣ እንዲሁም ለሞት የበቃበትን ጉዞ ለማየት ሞክረናል፡፡ ዛሬ ካለፈው ፅሁፍ የቀጠለውን እና የተቃዋሚው ጎራ አሁን ላለበት የመቃብር ህይወት ያበቁትን ጉዳዮች በወፍ በረር እናያለን፡፡

ተቃዋሚው ሞቷል ወይስ አለሞተም? ተብሎ ክርክር ቢነሳ አልሞተም ብሎ ለማረጋገጥ እና የህያዉን ተቃዋሚ ቋሚ አካል ማሳየት እጅግ ፈታኝ ነው፡፡ በተለይም አሁን ባለንበት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር አንፃር፡፡ ስለዚህም አዎ ነብሱን ይማረውና ተቃዋሚውማ ሞቷል ማለትን መርጫለው፡፡ አልአዛርን ይሆናል አይሆንም በቀጣዮቹ ጊዜያት በሚከሰቱት ክስተቶች እና በድኑ በሚሰጠው ምላሽ ይወሰናል፡፡ እናም ለዛሬ ተቃዋሚውን ማን ገደለው; በማለት እንጠይቃለን፡፡ ዋነኛ ተጠርጣሪዎችንም እንመረምራለን:: የግድያው ተካፋዮችን አንድ ባንድ ለማየት እንሞክር፡፡

## ራስን ማጥፋት (Suicide)

የሰው ልጅ ራሳቸውን ከሚያጠፉ እንስሳት አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ የሰው ልጅ ራሱን ማጥፋቱ ያልተፈታ ከባድ እንቆቅልሽ ነው፡፡ ለምን ሰው ራሱን ይጠላል? ራሱንስ እንዴት ይገድላል? የሚለው ጥያቄ ዘመናትን ተሻግሮ እስከ አሁን ድረስ ቁርጥ ያለ ምላሽ ባያገኝም መነሻው ይሄ ነው እየተባለ መገመቱ ግን አልቀረም፡፡ በዋነኛነትም በዘር የሚወረስ ራስን ማጥፋት (Biological Factors)፣ በስነልቦና ችግር የሚመጣ ራስን ማጥፋት ( Psychological Factors) እንዲሁም በማኅበረሰባዊ ችግሮች ምክንያት የሚከሰት ራስን ማጥፋት (Sociological Factors) ይጠቀሳሉ፡፡

ታዲያ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የሞተው ራሱን አጥፍቶ ይሆን? ካጠፋስ በየትኛው ምክንያት ይሆን ራሱን ያጠፋው? በሦስቱ መነሻዎች እንመልከተው እስኪ፡፡

በዘር የወረሰው ራስን የማጥፋት አባዜ ((Biological Reasons)፣) በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ከተጀመረ ግማሽ ምዕተ ዓመት እንኳን ያልሞላው ሲሆን ፓርቲ በመመስረት ወደ ፖለቲካው የገቡት ፖለቲከኞች በቀይ ሽብር- ነጭ ሽብር ተጠምደው አንዱ አንዱን ሲያሳድድ የተሸነፍው ራሱን ደብቆ መኖር ሲከብደው ራሱን ከሀገር በማሰደድ ፖለቲካዊ ራስን ማጥፋት ፈፅሟል፡፡ ይሄ ራስን የማጥፋት አባዜ ዛሬ ላለው ተቃዋሚ ከቀዳሚዎቹ በዘር ውርስ ተላልፎ እራሱን አጥፍቶ ይሆን?

በስነ ልቦና ችግር የሚመጣ ራስን የማጥፋት አባዜ (Psychological Reasons)፡ ሳይኮአናሊስቱ ሲግመንድ ፍሮይድ ራስን ማጥፋት ዋነኛው መነሻው የበዛ ራስን መጥላት (Self Hate)ነው ይለናል፡፡ ከፍሮይድ ተከትለው የመጡ ሳይኮሎጂስቶችም የፍሮይድን ሀሳብ በማጠናከር ሰው ከራሱ ጋር የሚፈጥረው ፀብ በሞት አሸናፊነት ይጠናቀቃል ይሉናል፡፡ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ምናልባትም ራሱን አጥፍቶ ከሆነ ራስን መጥላት ምክንያት ሊሆን ይችላልን? ‹‹ለዚህ ሁሉ ዓመታት ታግየ ምንም ውጤት ማምጣት ካልቻልኩ መኖሬ ምን ሊረባ? እኔስ ለምን ቆሜ እሄዳለው?›› በማለት ራስን ማጥፋት እንደ ግል ሂስ ቆጥሮት ይሆን?

በማኅበረሰባዊ ችግሮች ምክንያት የሚከሰት ራስን ማጥፋት (Sociological Factors)፡ ፈረንሳዊው የስነ-ህብረተሰብ ሊቅ ኤሚል ዱርክሄም በህብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ማጣት እንደሁም የግንኙነት መላለት ሰዎችን ወደ ራስን ማጥፋት ይመራቸዋል በማለት ራስን ማጥፋት ማህበረሰባዊ ምክንያት አለው ይላል፡፡ ታዲያ የኢትዮጵያ ተቃዋሚስ ህብረተሰቡ አልተቀበለኝም ብሎ ራሱን አጥፍቶ ይሆን? ወይስ የአባላት እና የደጋፊዎች ቁጥር ማነስ ህብረተሰቡ ለኔ ያለውን ጥላቻ ያሳያል ብሎ ራሱን አጠፋ ይሆን?

## የቤተ መንግሥቱ ገዳይ (Cold Blooded Murderer from the Palace)

ራሱን አጥፍቶ ሊሆን ይችላል ከሚለው ጥርጣሬያችን በማስከተል የሚቀርበው ሌላው ተጠርጣሪ ደግሞ መኖሪያውን ከወደ ቤተመንግስት ያደረገ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ተጠርጣሪ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ በስልጣን ላይ የቆየ ሲሆን በህግም የብዝሃ-ፓርቲ አስተዳደርን (Multi Party System) የፈቀደ ተጠርጣሪ ነው፡፡ ነገር ግን ሁለት ሀገር ዓቀፍ ምርጫዎችን ያለምንም ችግር ከ98 በመቶ በላይ ድምፆችን በማምጣት ለማሸነፍ የቻለ

ሲሆን ሶስተኛው ላይ ግን ችግር ገጥሞት ነበር፡፡ ‹‹እባካችሁ ተጠናክራችው ግጠሙኝ፣ የሚፎካከረኝ አጣሁ እኮ›› ሲል የነበረው ተጠርጣሪ ሳያስበው ህዝቡ ለተቃዋሚዎች የሰጠው ድምፅ አስበርግጎት አለማቀፍ ተቋማት ሳይቀሩ ‹‹አፍረሀል›› ቢሉትም ‹‹እንደተለመደው በሰፊ ድምፅ ማሸነፍ ባልችልም አሁንም ድሉ የኔ ነው›› በማለት ስልጣኑን አልለቅም አለ፡፡

አይ እኛ ነን አሸናፊዎቹ ያሉትን ተቃዋሚዎችም ክፉኛ አቁስሎ ለአልጋ ቁራኛ፣ ለደዌ ዳኛ አብቅቷቸዋል፡፡ ይባስ ብሎም በቁስል ላይ እንጨት እየሰደደ አንዳንዴም በርበሬ እየነሰነሰ ስቃያቸውን በማባባስ ስልጣኑን ለማራዘም ሞክሯል፡፡ በመጨረሻም አዳዲስ ህጎችን በማውጣት የተቃዋሚውን ግብዓተ መሬት እየሳቀ ከፈፀመ በኋላ አራተኛውን ሀገራዊ ምርጫ 99.6 % ድምጽ በማምጣት ‹‹አሸንፌአለሁ›› በማለት ‹‹ቧልት›› አሰምቷል፡፡

ለዚህም ማሰረጃ የሚሆኑት ሰነዶች ተጠርጣሪው ሟችን የሚያጥላሉ ፅሁፎችን በተደጋጋሚ በልሳኑ እንዲሁም በመንግስት ሚዲያዎች ሲያሰማ የነበረ መሆኑ፣ ምንጮቻቸው ከሰለጠኑት ሀገራት ነው በማለት የተለያዩ አፋኝ ህጎችን ማውጣቱ፣ በተደደጋጋሚ ሲያደርጋቸው የነበሩት ተግባራት በጥቅሉ ሲታዩ ተቃዋሚውን የገደለው የአራት ኪሎው ተጠርጣሪ ይሆን እንዴ? ያስብለናል፡፡

## ቅጥር ነብሰ ገዳይ (Mercenary)

ይሄ ተጠርጣሪ ቅጥረኛ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ከአራት ኪሎ ተጠርጣሪ ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚጠረጠር ነው፡፡ ለመጠርጠሩ ዋነኛ ምክንያት የሆነው ደግሞ ከሟች (ተቃዋሚው) ጋር አብሮ አደግ ከመሆኑም በተጨማሪ አብረው የሚበሉና አብረው የሚጠጡ ጓዶች የነበሩ ሲሆን፡፡ ከጥቂት ጊዜያት ወዲህ ግን ከቤተመንግስቱ ተጠርጣሪ ጋር በፍቅር ክንፍ ብሏል፡፡ ይሄም በዋነኛነት ሟች ከሞተ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ መሆኑ ጥርጣሬያችን ከፍ እንዲል ያደረገዋል፡፡

ለመሆኑ ይህ ተጠርጣሪ ምን ቢያገኝ ነው ወንድሙን የገደለው? ያልን እንደሆን በዋነኛነት የሚቀመጠው ሆድ አደርነት (Opportunism) ነው፡፡ ይሄን እንድንል ያስቻለን ደግሞ ተጠርጣሪው ሟች ከሞተ በኋላ የተለያዩ ንብረቶችን በግሉ ማፍራት የጀመረ ሲሆን በተለያዩ ጊዜያትም ሟችን የሀገሪቱ ዋነኛ ችግር መነሻ አድርጎ ለማቅረብ ሲሞክር ታይቷል፣ በተጨማሪም ሟች የነበረባቸውን ፓርቲዎች ለማፍረስ ከውስጥ ሌላ ‹‹አንጃ›› በመምራት ሟችን በቀን መርዞ እንደገደለው ይጠረጠራል፡፡

ሌላው እና ቅጥረኛ ገዳዩ የሟች አብሮ አደግ እንደሆነ እድንጠረጥር የሚያደርገን ጉዳይ ሟች ከሞተ በኋላ በሞቱ ደስተኛ የነበረ ሲሆን ከገዳይ ቀጣሪም ጋር አብረው መዋል እና ማደር ጀምረው ነበር፡፡ ይባስ ብሎም ‹‹ሟች መሞቱ ትክክለኛ ነገር ነው›› እያለ መግልጫ ሲሰጥ ነበር፡፡ ለህዝቡም እኔ እውነተኛ መሪህ አለሁልህ እያለ ህዝቡ ሟችን በቅጡ እንዳይቀብረው አድርጓል የሚል ጥርጣሬ አለ፡፡ እውን ተቃዋሚው የተገደለው በአብሮ አደግ ጓዱ ይሆን?

## ባሕል እንደ ተጠርጣሪ

ተቃዋሚውን ገድለውታል ተብለው ከሚጠረጠሩ አካላት አንዱ የህዝቡ ባህል በአጠቃላይ እንዲሁም የህዝቡ የፖለቲካ ባህል በተለይ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ይሄን እንድንል ያስቻለን ህዝቡ ተቃዋሚዎች ስልጣን ቶሎ ይዘው መብቱን እንዲያስከብሩለት ከመመኘት ውጭ አብሮ በመርዳት፣ አይዟችሁ በማለት፣ በአባልነት በመሳተፍ ወ.ዘ.ተ ሲደግፋቸው ብዙም አለመታየቱ ነው፡፡ ይሄም ድርጊት የህዝቡ ባህል ተቃዋሚውን በቸልተኝነት ገድሎታል እንድንል ያደርገናል፡፡

ሌላው የህዝቡ ባህል ለሟች መሞት ዋነኛውን ድርሻ አበርክቷል እንድንል የሚያደርገን ጉዳይ ተጠርጣሪው በተረቶቹ እንዲሁም በወጎቹ ለሟች መሞት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችን ሲናገር መኖሩ ነው ለምሳሌ ‹‹ሁሉንም ወይም ምንም›› በማለት የብቸኝነት መንገድን እንደ ብቸኛ አማራጭ በማየት ተቃዋሚውግማሽ እንዳይመኝ እና በጋራ እንዳይሰራ አድርጎታል የሚል ጥርጣሬ አለ፡፡

በተጨማሪም የህዝቡ ባህል ‹‹ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ›› በማለት አንድ አይነት አቋም የሌላቸውን ተቃዋሚዎች አንድ ላይ ለማድረግ ሞክሮ እንደገደላቸው ይጠረጠራል ይሄም ተግባር አንዳንዴ እንጨትን ከብረት ጋር ለማቅለጥ እንደ መሞከር ነው፡፡ ስለዚህም እውን ተቃዋሚውን የገደለው ባህሉ ይሆን?

## ሌሎች ተጠርጣሪዎች

ከላይ ከተጠቀሱት ተጠርጣሪ ገዳዮች በተጨማሪ ሌሎቻ ተጠርጣሪዎችንም ማንሳት ይቻላል ለምሳሌ ሚዲትራኒያንን አቋርጦ የመጣው ባለ ሰማያዊ አይን ተጠርጣሪ አንዱ ነው ይህ ተጠርጣሪ ቤተመንግስት ካለው ተጠርጣሪ ገዳይ ጋር ‹‹ሽብርተኝነትን መዋጋት›› የሚል ውል ተዋውሎ ለሌሎች ነገሮች ትኩረት ባለመስተጠት እና የቤተመንግስቱን ተጠርጣሪ በገንዘብ በመደገፍ ለተቃዋሚው ሞት ተጠያቂ ሊሆን ይችላል፡፡ እውን ይሄ ባለ ሰማያዊ አይን ተጠርጣሪ ተቃዋሚውን ገድሎታልን?

ሌላው ገዳይ ሊሆን የሚችችለው ተጠርጣሪይ በቀዳሚ ነገስታት ሀገሪቱ ‹‹ጥቁር ውሻ ውለጅ›› የሚል ርግማን መረገሟ ሊሆን ይችላል የሚል ኢ-ሳይሳዊ መላ ምትም ይመታል፡፡ እውን እርማኑ ተቃዋሚውን ገድሎት ይሆን?

በአጠቃላይ ተቃዋሚውን ከላይ ከተዘረዘሩት ሀይላት አንዱ ገድሎታል ወይም ራሱን አጥፍቷል ማለት እንችላለን፡፡ የገዳዩን ማንነት የሚገልፀውን ውሳኔ ለማየት ደግሞ በጉጉት እንናፍቃለን፡፡

## የካምፓስ ተማሪዎች የጎሳ ግጭት፤ ከመነሻው እስከ መድረሻው

ይህ ጽሑፍ ባለፈው ወር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ በብሔር ሰበብ በተነሳ ፀብ ላይ ተመስርተው በተከታታይ ድረገጾች ላይ የተጻፉ ጽሑፎች መነሻነት የተጻፈ ማጠናከሪያ ሐተታ ነው። ስለሆነም እዚህ ውስጥ የተበታተኑት የሰዎቹ ውይይት አጽርኖት (summary) እና ተጨማሪ ሐሳቦች ይንፀባረቃሉ።

ጃዋር መሐመድ (የፖለቲካ ተንታኝ) ነበር ውይይቱን የጀመረው፤ በጽሑፉ ‹‹ዩኒቨርሲቲዎች ነጻ መንፈስ ተኮትኩቶ የሚያድግባቸው፣ እልፍ ገጽታ ያላቸውን ችግሮቻችን ለመፍታት የሚያስችሉ አዳዲስ ሐሳቦች የሚፈልቁበት የላቀ እና ገንቢ ውይይቶች የሚካሔዱባቸው ቦታዎች መሆን ይገባቸዋል። በተቃራኒው ግን፣ የኢትዮጵያ ኮሌጆች የዘረኝነት፣ ጠባብነት እና አመጽ መፈልፈያ እየሆኑ ነው።›› ይላል።

እኔም በዚህ ጽሑፍ ይህንኑ ጉዳይ ከታሪክ እና ከወቅታዊ ጉዳዮች አንጻር እመላለስበታለሁ።

### ለመሆኑ መቼ እና በማን ተጀመረ?

የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ዕድሜ አጭር በመሆኑ ብሔር-ነክ ግጭቶች መቼ እንደተጀመሩ የሚዘረዝር መረጃ ማግኘት ቢቸግርም እንኳን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ (የአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ) እንደሆነ መገመት አይቸግርም። ሆኖም በቅርቡ በጆን ያንግ የተጻፈ፣ Peasants Revolution of Ethiopia የሚል ርዕስ ያለውን መጽሐፍ ሳገላብጥ ያገኘሁት አንቀጽ አጀማመሩን የሚገልጽ መስሎኝ ወስጄዋለሁ።

*"…ዊንጌት ውስጥ … በአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሚመሩ የትግራይ ተወላጅ ተማሪዎች በቅርጫት ኳስ ጨዋታ ላይ በተነሳ አለመግባባት ከኦሮሞ ተወላጆች ጋር ተጋጩ። ከዚያ ቀጥሎ መለስ በጣም አወዛጋቢ የነበረውን እና በአድዋ ጦርነት ወቅት የትግራይ ተወላጆች ከየትኛውም ብሔረሰብ የበለጠ የሕይወት እና የሰው ኃይል ከፍለዋል፣ ምኒልክንም ለድል አብቅተዋል የሚል የታሪክ ጽሑፍ አቀረቡ…"* (ገጽ 82) እያለ ይቀጥላል።

ይሁን እንጂ የካምፓስ ውስጥ የዩንቨርስቲ ግጭት ድምፅ አግኝቶ የቀጠለው በኢሕአዴግ ዘመን ነው። ለዚህ እንደ መንስኤ ሊቆጠር የሚችለው (1). የብሔር ፌዴራሊዝሙ፣ እና (2). ከደርግ አፈና በኋላ የተመለሰው አንጻራዊ የመነጋገር ነጻነት ነው። በደርግ ዘመን የብሔር (በጥቅሉ የፖለቲካ) ውይይት በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የመነሳት ዕድሉ ጠባብ ስለነበር ግጭቱም አይነሳም ነበር። የወቅቱን ዝምታ ራንዲ ሮኒንግ ባልስቪክ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ ባተመላቸው የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፋቸው (The Quest for Expression: State and The University in Ethiopia Under Three Regimes. 1952-2005) ላይ እንዲህ ገልጸውታል።

*‹‹…ከአብዮቱ ፍንዳታ 10 ዓመት በኋላ (የኢ.አ.) ዩኒቨርሲቲን እና በጥቅሉ ማኅበረሰቡን ከጠበቅኩት እና በንጉሡም ሆነ በክፍለዘመኑ መጨረሻ - በመለስ ዜናዊ መንግሥታዊ-ስርዓት ካየሁት በላይ በፍርሐት ተሸብቦ ነበር። ሕይወት ተስፋ በሚያስቆርጥ መልኩ የማይጠበቅ እና ደኅንነት የጎደለበት ሆኖ ነበር። ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ተማሪዎች ማንኛውንም አስተያየት በአገሪቱ ውስጥ እየተከናወነ ስላለ ጉዳይ ከመስጠት ይቆጠቡ ነበር። ምክንያቱም ንግግራቸው ሁሉ ፖለቲካዊ ትርጉም ይሰጠዋል።…››*

ጸሐፊው ወደኢሕአዴግ ዘመን ሲመልሱን፣ ‹የዩኒቨርሲቲው ዶርሚተሪዎች በጎሳ ተከፋፍለዋል፤ አማራዎቹ የጎሣ ጽንፈኝነትን ሲቃወሙ ኦሮሞዎቹ ተማሪዎች ደግሞ ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸውን እንደተነጠቁ ይሰማቸዋል። በትግሬዎቹ እና ቀሪዎቹ መካከል ደግሞ ቀዝቃዛ ጦርነት ተከፍቷል› ይላሉ። በ1993 የኦሮሞ ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲው ቤተ መጽሐፍት ውስጥ ተለቅመው እንዲጠፉላቸው የሚፈልጉትን ቃላት ዝርዝር በፊርማ ለወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አስገብተው ነበር። ይሄ ጥያቄ ምላሽ ባለማግኘቱ ተማሪዎቹ የማይፈልጓቸው ቃላቶች ያሉባቸውን መጽሐፍት ገጾች እየቀደዱ መውጣት ጀመሩ።

ከዚያ በኋላ ብሔር ነክ ጥያቄዎችን በውስጥ ለውስጥ ሽኩቻ መመለስ፣ በየብሔሩ እየተቧደኑ ማኅበራዊ ግንኙነት መመስረት እና ከማኅበራዊ ግንኙነቱ መስመር ውጪ ያለውን ሁሉ በጠላትነት መፈረጅ፣ አለምግባባቶች ሲኖሩ መደባደብ ‹‹ብዝኃነት (plurality)›ን ዒላማ ያደረገው የዩንቨርስቲ ሕይወት ክሽፈት መለያ ሆነ።

## የካምፓስ ተማሪዎች ለምን በብሔር ይጋጫሉ?

### ሀ. የመንግሥት ሴራ?

ጃዋር መሐመድ ‹የኢትዮጵያ ካምፓሶች ዓይናውጣ ጦርነት፤ መነሾ ግብ እና ተጽዕኖ› በዳሰሰበት ጽሑፉ መንግሥት ከመነሻ እስከመድረሻው ድረስ ተጠያቂ መሆን እንዳለበት ያትታል። ለጃዋር ዋና የካምፓስ ተማሪዎች ብሔር ነክ ግጨቶች መንስኤ የሚባሉት ሁለት ናቸው፤ (1). የአካዳሚያዊ ነጻነት አለመኖር (ነጻ ማኅበራት አለመፈቀዳቸው፣ የመወያያ የተማሪዎች ሕትመቶች አለመኖራቸው እና መታገዳቸውን ይጨምራል)፣ (2). የገዢው ፓርቲ የስለላ አባላት ተማሪዎቹ ውስጥ መሰግሰጋቸው እና የመከፋፈል ሚና መጫወታቸው።

ጃዋር በትንታኔው ‹‹ማኅበራት እንዲኖሩ አለመፈቀዱ የባሕል እና ማንነት ልውውጥ እና ትውውቅ ዕድል ስለማይሰጥ፣ የካምፓስ ማኅበራዊ ክበቡ በግምት፣ በተሳሳተ መረጃ፣ እና በጥርጣሬ ስለሚሞላ ለጠባብነት እና አግላይነት መንገዱን ይጠርጋል። እንዲህ ዓይነቱ ካምፓስ ደግሞ ለቡድን አመጽ የተጠመደ የጊዜ ቦምብ ነው።›› በማለት በዩንቨርስቲዎቻችን የሚነሱት ግጭቶች በማኅበራት እና መሰል ውይይቶች ሊፈቱ የሚችሉ ጥያቄዎች በፍራቻ እና አካዳሚያዊ ነጻነት ባለማግኘት ምክንያት የሚፈጠሩ መሆናቸውን ያስረዳል። እንደጃዋር ገዢው ፓርቲ ይህንን የሚያደርገው ዘመነ ሥልጣኑን ለማስረዘም ‹ከፋፍለህ ግዛ› የተሰኘ ስልት ስለሚጠቀም እንጂ የችግሩ መንስኤ ጠፍቶት አይደለም።

በተመሳሳይ መንገድ በ1990 አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ (ስድስት ኪሎ) በጎሳ ጉዳይ በተነሳ ግጭት ፖሊስ እርምጃ ሲወስድ *"ማንኛውም ኦሮሞ ስም ያለው ሰው ወደእስር ይገባል፤ የትግራይ እና አማራ ስም ያላቸው ተማሪዎችን ግን ከሌሎቹ ለይተው ‹እነዚህ የኛ ሰዎች ናቸው›፤ ወይም ‹እነዚህ የኛ ናቸው ተዉኣቸው› ይላሉ፤"* በማለት ራንዲ ጽፈዋል። ይህ ሁለት የፖሊስ ዓይን የሚያንፀባርቀው መንግሥት ጉዳዩን ከላይ የሚመለከትበትን ሁኔታ ነው።

ይህ ዓይነቱ የመንግሥት/የፖሊስ ችግሩን አፈታት የኦሮሞዎቹን ተማሪዎች የመጠቃት ስሜት እንደሚያጋግለው እና ጎሳዊ ጽንፈኝነት ውስጥ ሊከታቸው እንደሚችል መገመት ከባድ አይደለም፤ ጃዋርም በዚህ ይስማማል። የኦሮሞ ተማሪዎች ተለይተው መለቀማቸው ሌላውን በጥርጣሬ እና በአጥቂነት እንዲመለከቱት እና ጥላቻ ውስጥ እንዲወድቅ ያደርገዋል ይላል።

እዚህ ጽሑፍ ላይ ተመስርተው የተሰጡ ምላሾች የዚህን መንስኤ እውነታነት አስረግጠው፣ ነገር ግን ጃዋር ዘነጋቸው የሚሏቸውን ተጨማሪ የግጭት መንስኤዎች ይጠቁማሉ።

### ለ. የኦሮሞ ተማሪዎች የመቻቻል ባሕል ማነስ?

ዐብይ ተክለማርያም (የቀድሞዋ አዲስ ነገር ጋዜጠኛ) ለጃዋር ትንታኔ በሰጠው አጭር የምላሽ ማብራሪያ ላይ በጽሑፉ ይዘት እውነተነት ቢስማማም የጥፋተኝነቱን ድርሻ ለመንግሥት ብቻ መስጠቱ ተገቢ አይደለም ይላል። ዐብይ የምናወራውን ነገር እርግጠኝነቱን ለማወቅ ጥልቅ ጥናት ያስፈልጋል ቢልም፤ ጉዳዩ ግን አሁን እንደምንለው ‹ጥቁር እና ነጭ› ብቻ እንዳልሆነ ተናግሯል። መንግሥት ብቻ መወቀስ የለበትም የተማሪዎቹ የመቻቻል ባሕል ማነስ ለእሳቱ ነዳጅ አቀብሏል ነው አባባሉ። እሱ እንደሚለው የኦሮሞ *አክቲቪስቶች የፀረ-ነፍጠኛ* ትርክት ለዚህ ተጠያቂ ነው።

እውነት ነው፤ የኦነግ ትግል የተጧጧፈው በ‹‹*ኦሮሞ ኮሎናይዜሽን*›› ትርክት ነው፤ ኦነግ እና ብዙዎቹ የኦሮሞ ፖለቲካ *አራማጆች* የሚያምኑት የኦሮሞ ሕዝብ በብሔሩ ብቻ ሲጨቆን (‹‹ቅኝ ሲገዛ››?) ኖሯል እና አሁን ነጻ መውጣት አለበት ብለው ነው። እርግጥ ነው፤ ነጻነትን ከመገንጠል አጀንዳ ጋር ማራመዳቸውን አሁን ብዙዎቹ ቀይረውታል። ያለመገንጠል ‹‹እኩል ነጻ ሆኖ መኖር ይቻላል›› በሚል - ሆኖም ግን አሁንም ድረስ ጭቆናው አለ ብለው ማሰባቸው ለመቧደን እና ከሌላው ጋር እንዲጋጩ፣ ሌላውን በጥርጣሬም እንዲመለከቱ አድርጓቸዋል። አሁንም በዙሪያቸው ያለው ሁሉ የ‹‹ነፍጠኛ›› የበላይነቱን ሊያራምድብን ነው በሚል የመፈረጅ ሁኔታ አለ። ይህም ለተደጋጋሚ ግጭቶች መቀስቀስ መንስኤ ይሆናል፤ ከላይ እንደተጠቀሰውም መንግሥትም ሊጠቀምበት ይችላል።

በዚህ መሐል ግን የሚነሳ አንድ ጥያቄ ይኖራል፡፡

## ለምን ኦሮሞ ብቻ?

ዘላለም ክብረት (የሕግ መምህር) የጃዋርን እና ዐብይን ምልልስ አስከትሎ ባሰፈረው አስተያየት አዘል ጽሑፉ እሱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበረበት ወቅት የግጭቱ ሰለባ መሆኑን ጠቅሶ፣ ነገር ግን ባያቸው ግጭቶች ውስጥ ሁሉ የኦሮሞ ተማሪዎች መኖራቸውን ጠቅሷል፡፡ ተደጋጋሚ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ግጭቶችን የተመለከትን እንደሆነ ግጭቶቹ ሁሉ የኦሮሞ ተማሪዎችን ይነካል፡፡

ራንዲም ከላይ በጠቀስነው ጽሑፍ ላይ ሦስት የካምፓስ የጎሳ ቡድኖች መኖራቸውን ይናገራሉ፡፡ ኦሮሞዎች፣ የገዢው ፓርቲ ደጋፊ ናቸው በሚል የሚፈረጁት ትግሬዎች እና አማራዎች፡፡ ራንዲ ከደቡብ የመጡት አማራዎቹ ቡድን ውስጥ እንደሚመደቡ ተናግረዋል፡፡ በእርሳቸው መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ግጭቶች ሁሉ ሰለባ የሆኑት፣ የተከሰሱት እና የታሰሩት ኦሮሞዎች መሆናቸው ግጭቱ በአብዛኛው ኦሮሞዎችን በማዕከላዊነት የሚያካትት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

እንግዲህ በዚህ እውነታ ላይ ተመርኩዘን ስንሄድ የኦሮመ ተማሪዎችን አንድም ሆነ ብሎ የሚተነኩሳቸው አለ (የመንግሥት ሴራ እንደተባለው) አለ አሊያም እነርሱ (የመቻቻል ባሕል) ችግር አለባቸው የሚል አጣብቂኝ ጥርጣሬ ውስጥ ይጥለናል፡፡

## የኦሮሞ ሕዝብ ከሌላው ጋር…?

የኦሮሞ ተማሪዎችን የመቻቻል ባሕል ለመፈተሽ በተቻለን አቅም ወደኋላ መለስ ብለን የኦሮሞ ሕዝብ ከሌላው ማኅበረሰብ ጋር እንዴት ተቻችሎ ይኖር እንደነበር መጠየቅ ይኖርብናል፡፡ በዚህም የምናገኘው ተማሪዎቹን ከከሰስንበት ተቃራኒውን ነው፡፡ ዶ/ር ዶናልድ ሌቪን ስለኦሮሞ ሦስት ዓይነት ትርክቶች በሚያውሩበት ጽሑፋቸው የኦሮሞ ሕዝብን የመቻቻል፣ እና ከሌላው ጋር በፍጥነት የመዋሀድ ችሎታ እንዲህ በአድናቆት አስፍረውታል፡፡

*‹‹ለመላመድ፣ ለመመሳሰል፣ እና ለእርስበርስ ጋብቻ ያላቸው ፈቃደኝነት ምስጋና ይግባውና፣ የኦሮሞ ሰፋሪዎች በሄዱበት ሁሉ ካለው ሕዝብ ጋር ተዋህደዋል፡፡ የግልጽነት እና ወዳጅነት ባሕሪያቸው አዲስ መጤዎች ማኅበረሰባቸውን እንዲቀላቀል የሚጋብዝ ነው፡፡ በየሰፈሩበት አጎራባች ቦታዎች ካሉ ሰዎች ጋር ጦርነቱ ለጊዜውም ይሁን በዘላቂነት ከመቆሙ የሚዛመዱበት ነገር አያጡም፡፡ ይህ ከሌሎች ጋር የመወዳጀት ችሎታቸው እነርሱ የሌሎችን፣ ሌሎችም የነርሱን ባሕል እንዲወራረሱ አድርጓል፡፡ ኦሮሞዎች በሰሜን ክርስትናን፣ በምስራቅ ደግሞ እስልምናን ተቀብለዋል፤ በደቡብ ምዕራብ ግዛተነገሥት ሲያቋቁሙ በሸዋ ደግሞ እርሻ ጀምረዋል፡፡ ከአማርኛ ተናጋሪዎች ጋር በቀላሉ መቀላቀል መቻላቸው ምስጋና ይግባውና ቀድሞ ሴማዊ የነበረው እና ከግዕዝ፣ ትግርኛ፣ አረቢኛ፣ እና እብራይስጥ የመጣው አማርኛ ቋንቋ አሁን የምስራቃዊ ኩሽ ሰዋሰው፣ ግስ እና ዘዬ ከኦሮምኛ ቋንቋ ወርሶ ወስዷል፡፡*

*‹‹በደቡብ፣ እነዚህ ቅልቅሎች ሁሉንም ቡድን ያሳትፋሉ፡፡ ስለዚህ፣ በጉራጌ ዞን አካባቢ የሰፈሩ ኦሮሞዎች የእንሰት ባሕልን በመውረሳቸው በኦሮሞዎች ሳይቀር ‹‹ግማሽ ጉራጌ›› በመባል ይቀለድባቸዋል፡፡ የጉጂ ኦሮሞ ኦቱዎች ከሲዳማ ባሕል ጋር በጣም ከመቀላቀላቸው የተነሳ አንዳንዶቹ ሲዳምኛ ብቻ ነው የሚናገሩት፡፡ በሌላ በኩል፣ የጉጂ ኦሮሞዎች የሲዳማ እና ወላይታ ሰዎችን ወደራሳቸው ባሕል ወስደው ቀላቅለዋቸዋል፡፡››*

ይህን ስናነብ፤ ይህን ዓይነት የመቻቻል እና የመላመድ ባሕርይ ካለው የኦሮሞ ሕዝብ አብራክ ውስጥ የወጡት ተማሪዎችን የመቻቻል ባሕል ያንሳቸዋል ለማለት ስር የሰደደ መሰረት እናጣለን፡፡ እናም ‹‹የአሁኑ ተማሪዎች ግጭት የኦሮሞ ተማሪዎች የመቻቻል ባሕል ማነስ ከየት መጣ?›› ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን፡፡ እንግዲህ ለዚህ ጥየቂ የሚቀረን መልስ ጃዋር በጽሑፉ ጠቅሶት እንደነበረው ‹‹የመንግሥት ካድሬዎች ትንኮሳ›› አሊያም ዐብይ እንዳለው ‹‹የፀረ-ነፍጠኛ ትርክት የዘለቃቸው ተማሪዎቹ የመቻቻል ባሕል ማነስ›› ለችግሩ ተጠያቂዎች ሆነው ይቀራሉ፡፡

## የግጭቶቹ መነሾዎች

ዘላለም በጽሑፉ ‹‹የሐጎስ እና ገመቹ የግል ፀብ ወደ ትግሬ እና ኦሮሞ ተማሪዎች ያድጋል›› በማለት ግለሰባዊ አስተሳሰብ በቡድን እየተተካ እንደሆነ ያለውን ስጋት ጠቁሟል፡፡

የካምፓስ ውስጥ ፀቦች በግለሰቦች ግጭት ብቻ አይደለም የሚነሱት፤ በቃላት አጠቃቀምም ጭምር ነው፡፡ አንዱ ሌላኛውን ለማብሸቅ፣ ወይም ባለማወቅ በሚጠቀመው የተነወረ ቃል (the "G…" word) ሳቢያ የተነሳ ፀብ… ምናልባትም በውቀቱ ስዩም (ማኅበራዊ ሐያሲ) አስተያየት ሲሰጥ *‹‹ይህን ያለው የምን አገር ተወላጅ ነው ከማለት በፊት ማነው ያለው?››* ለማለት ባለመቻላቸው የሚመጣ ችግር ነው፡፡

ዐብይ የ‹‹ነፍጠኛ›› መጽሐፍትን በማጣቀሳቸው ክፍል ውስጥ በካምፓስ ተማሪ ኦሮሞዎች የተደበደቡ መምህራን ስለመኖራቸው ብዙ ታሪክ መስማቱን ጽፏል፡፡ ዘላለምም የተነወሩ ቃላትን የሚጠቅሱ መጽሐፍት ገጾች በየካምፓሱ ላይብረሪ ተቀድደው አልቀዋል ብሏል፡፡ የሁለቱንም አስተያየት ያደመጠ ሰው መጀመሪያ ሊጠይቅ የሚችለው ጥያቄ ቢኖር ‹‹መጽሐፍቱን በማጥፋት [ያልተወደደውን] ታሪክ ማጥፋት ይቻላል ወይ?›› የሚል ነው፡፡

‹‹ሰዎች በቋንቋቸው መማር ይገባቸዋል›› ብሎ እንደሚያምን የጠቀሰው ዐብይ ‹‹የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የተለያዩ ዓይነት አመለካከቶችን ማወቅ እንዳለባቸውም›› አክሎ ተናግሯል፡፡ ይህንኑ ሐሳብ የሚያጠናክረው ደግሞ ዘላለም ክብረት ነው፤ በሁለቱ ተንታኞች ምልልስ ላይ ተመርኩዞ በጻፈው ጽሑፍ ላይ እንዳሰፈረው ጉዳዩን ትቶ በመጽሐፍቱ መኖር/አለመኖር፣ ለመማሪያነት መጠቀስ/አለመጠቀስ ማዕከላዊ ጉዳይ ሆኖ መወሳቱ እና *"መጽሐፍቶቹ ከቤተ መጽሐፍቱ እንዲወጡ መጠየቅ መሳቂያነት/ዕብደት ነው"* ብሏል፡፡

ከላይ እንዳየናቸው ግጭቶቹ መነሾዎቻቸው አንድ ወይም ሁለት ግለሰቦች ወይም ደግሞ ቃል ቢሆንም ቅሉ ግን ተጠቂ የሚሆኑት በተለያየ ቡድን/ብሔር ውስጥ የታጠሩ ሰዎች ሁሉ ናቸው፡፡ ይህ እንግዲህ ዩኒቨርሲቲዎች ከተለያዩ ክልል የመጡ ተማሪዎችን ቀይጠው በማስተናገድ ከነልዩነት አብሮ መኖር እንዲችሉ የማድረጉ ሙከራ ምን ያህል ከስኬት እንደራቀ የሚያሳይ ውጤት መሆኑ ነው፡፡

## ለመሆኑ መፍትሔ አለው?

መፍትሔ የሌለው ችግር የለም፤ ምንም እንኳን ካምፓሶች በየብሔሩ ሽምቅ የሚዋጉ ማኅበረሰቦችን ቢያፈሩም ተማሪዎቹ ከዩንቨርስቲ ሲወጡ የሚኖሩበት ማኅበረሰብ ከተማሪዎቹ እጅግ የላቀ የመቻቻል ባሕል ስላለው እንደዚያ ዓይነቱ ነገር ማኅበረሰቡን የመበጥበጥ ዕድሉ ጠባብ ሆኖ ከርሟል - ቢያንስ እስካሁን ድረስ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ ተመርቀው ሲወጡ የሚኖሩበት ብዝኃ-ብሔሮችን አቅፎ የተቀመጠ ከተማ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ነገሮች እየተባባሱ ከሄዱ እና ካሁኑ ፈር ካልተበጀላቸው ነገሩ የተገላቢጦሽ ሊሄድ ይችላል፡፡ ተማሪዎቹ የካምፓስ ውስጥ አግላይ-አቋማቸውን በማኅበረሰቡ ውስጥ ሊያስተጋቡ እና ማኅበረሰቡም ሊቀበላቸው ይችላል የሚል ስጋት አለኝ፡፡

ለዚህ ነው ችግሩን ‹‹የካምፓስ ተማሪዎች ዛሬም እንደለመዱት በብሔር ተጋጩ›› ብቻ ብለን እንደዋዛ ማለፍ የማይኖርብን፡፡ ችግሩን እንዳያዳግም አድርጎ ለማባረር የመጀመሪያው መፍትሔ የሚሆኑትን ካሁኑ ማፈላለግ ያሻል፡-

### *ሀ. ማውራት፣ ማውራት፣ ማውራት*

[በውቀቱ ስዩም] የመጨረሻው የካምፓስ ተማሪዎች ግጭት የተከሰተ ዕለት (በታኅሳስ ወር/2005) በጻፈው አንጀት አርስ ጽሑፉ መደምደሚያ ላይ *‹‹መፍትሄው ምሁራዊ አይናፋርነትን ትቶ መወያየት ነው፤››* ብሎ መክሯል፡፡ *‹‹በተደጋጋሚ እንደምናየው፣ ባንዱ ኃጢያት ሌላው ይሙት የሚል ብሉያዊ አስተሳሰብ የካምፓስ ልማድ የሆነ ይመስላል፡፡ ብዙ የተማሩ፣ የተመራመሩ ሰዎችን እንዴት አንድ ተንኳሽ ሊያተራምሳቸው ይችላል?››* ብሎ አንድ በቃላት በሚነሳ ጦርነት እንዴት እንደሚከፋፍለን እና የመወያየት ባሕላችን ማነስ ‹‹ቃላት›› እንኳን መቋቋም እንዳነሰን ታዝቧል፡፡

*ጎሣዊ ነውረኛ ቃላት ከመጽሐፍት ውስጥ እና ከመጽሐፍት ገጾች እንዲወገዱ ከመጣር ይልቅ አማራጭ ትርክት ፈጥሮ፣ የትኛው የተሻለ እንደሆነ ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ባለማውራት፣ እና አፍን በመለጎም ከዕውቀት*

*መታቀብ እንኳ ለውጥ አይመጣም፡፡ በዝምታ እና በመፈረጅ ፍርሐት ከማለቅ በጫፍ አልባ ሙግት ውስጥ እያለፉ እያደጉ መኖር ይሻላል፡፡*

### ለ. አራማጆችና ምሁራን በትርክቶቻቸው መቻቻልን አይርሱ

**በቀለ ገርባ በ‹‹አሸባሪነት›› ፍርዱ ብያኔ ላይ ማቅለያ ሲጠየቅ ከተናገረው ውስጥ ትግሉን** *‹‹…በኦሮሞ ሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ግፍና መከራ እንደሚገባ ሳልገልጽ ቀርቼ ከሆነና ይህንንም ያደረኩት ለሕዝቦች አብሮ መኖር ከማሰብና ከወንድማማችነት ላነሰ ተግባር ከሆነ የኦሮሞን ሕዝብ… [በደሉን] ከሚገባው በላይ አጋንኘው ከሆነና ይህንንም ያደረኩት ለግል ጥቅምና ዝና ከሆነ እግዚአብሔርን ይቅርታ እጠይቃለሁ…›› ብሎ ነበር፡፡ ያ የበቀለ ንግግር የብሔር ነጻነት ትግል አጀንዳን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡*

*አሁንም የብሔር ነጻነት አራማጆች የሚታገሉለትን የብሔሮች እኩልነት እና ነጻነት ዒላማ ካልዘነጉ በቀር ሁልጊዜም በግጭት እና ከሌላው ጋር በመቆራቆስ የሚመጣ ለውጥ እንደሌለ በቅጡ መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡ ስለዚህ የተለያዩ ትርክቶች ይህንን ሐቅ ዘንግተው አንዱ ከሌላኛው ጋር ጠላትነት በማፍራት የሚመጣ ነጻነት እንደሌለ በማመን መቻቻልን ያገናዘበ ትርክት ይዞ ከአጉል ጽንፍ እና ‹‹ጽንፍ ነው አይደለም›› ሙግት መውጣት እና ለኅብረተሰቡ አብሮ፣ በነጻነት እና እኩልነት መኖር የሚበጅ የመፍትሔ ሐሳብ መቀየስ እና መታገል ያስፈልጋል፡፡ አለበለዚያ ጉዳዩን ለግል አጀንዳ በማራገብ ችግሩን ማክፋት እንጂ ማቅለል ይከብዳል፡፡*

### ሐ. መንግሥት የሚበጀውን ይወቅ

*ጃዋር ሕዝቦች በምንም ይሁን በምን (በተለይ በብሔር) ከተከፋፈሉ መንግሥት ላይ የማመጽ አቅምም አንድነቱም ስለማይኖራቸው፣ ዕድሜው እንዲረዝምለት ይፈልገዋል ይላል፡፡ ሆኖም፣ ይህ ዓይነቱ የከፋፍለህ ግዛ ጫወታ፣ በእሳት የመጫወት ያክል ነው ይላል የገዛ ሐሳቡን ሲያጠናክር፡፡*

*መንግሥት የብሔር ፌዴራሊዝም ከ‹‹መለያ-አጀንዳነት›› ይልቅ የአተገባበር እና ሌሎቹም ችግሮች እንከኖቹን ነቅሶ እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል ተጨንቆ መሥራት ይኖርበታል፡፡ ‹‹የብሔር ጥያቄ ተመልሷል›› ብሎ በደረቅ ዓረፍተነገር ለማሳመን ከመሞከር ይልቅ በየአቅጣጫው የሚነሱ ጥያቄዎችን ማዳመጥ ይበጃል፡፡ የተለዩ የብሔር አባላት የሚመረጡበት፣ የተለዩ የብሔር አባላት የሚገለሉበትን ያልተጻፈ አሠራር የምር መታገል እና የምር የብሔረሰቦችን እኩልነት ለማስፈን ቁርጠኝነቱን ማሳየት አለበት፡፡*

*ስለዚህ መንግሥት ከጊዜያዊ የሥልጣን ማስቀጠያነት ተሻግሮ የረዥም ዓመት ሕልም ማፍራት አለበት፡፡ የጎሳ ግጭት ለማንም አይበጅም፤ እርስ በእርሱ የሚበጣበጥ ሕዝብ ይዞ መምራት ብሎም ብጥብጡን ሥልጣን ለማስረዘሚያነት እስከመጠቀም ማለም ደግሞ የጅል ብልሐት መሆኑን አውቆ መንግሥታችን መጠንቀቅ እና ወደቀልቡ መመለስ ይኖርበታል፡፡*

### መ. ከመንደረተኛነትን አስተሳሰብ መላቀቅ

*‹‹ጠባብነት›› የሚለው ሐሳብ የሚመጣው ሰዎች ከራሳቸው ዙሪያ ውጪ ሌላ ዓለም እንደሌለ በማሰብ ልዩነትን መረዳት እና ከነልዩነት አብሮ መኖር ሲያቅታቸው ነው፡፡ ይህንን ነው ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ‹‹መክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ›› በሚለው መጽሐፋቸው ‹‹መንደረተኝነት›› ሲሉ የገለጹት፣ እኔ ልንገላገለው/ልንጠነቀቅለት ይገባል የምለውን አስተሳሰብ ከእርሳቸው በምዋሰው አንቀጽ አብራራዋለሁ፡-*

*‹‹…መንደረተኛነት ማለት ከመንደር በማይወጣ አስተሳሰብና ከመንደር በማይወጣ ስሜት መመራት ነው፤ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለሚኖሩ ሰዎች ዓለማቸው መንደራቸው ነች፤ ከዚያች መንደር ውጪ ሌላ ዓለም የለም፤ ቢኖርም የሚንቁትና የሚጠሉት ነው፤ መንደረተኛነት በግድ ብዙ የአስተሳሰብ ግድፈቶችን ያስከትላል፤ የራስን መንደር የዓለም እምብርት የሆነችና ዓለምንም ኢምንት አስመስሎ በመገመት፣ መንደርዋን ወሰን-የለሽ በማድረግ አስተያየትን ያጠናግራል፤ በአስተሳሰብም ደረጃ መንደረተኛነት ቁሞ-ቀር ያደርጋል፤ የአካል፣ የአእምሮንና የመንፈስን ዕድገትና እርምጃ ያፍናል፤ መንደረተኛነት የታሪክን መሠረትና የታሪክን ትክክኛ አካሄድ ለመረዳትና የታሪክ ባለቤት ለመሆን የሰው ልጅ የአለውን ችሎታ በመቀነስ ትልቅ እንቅፋት ይሆናል፡፡…››*

## *መደምደሚያ*

ጃዋር መሐመድ እና ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ በኦነግ ርዕዮተ-ዓለም ላይ በተከራከሩበት የጽሑፍ ምልልስ ላይ ጃዋር የተጠቀመውን ሐረግ ብጠቀም ጥሩ መደምደሚያ ይሆነኛል፡-

*‹‹…ኢትዮጵያ ያላለቀች ፕሮጀክት ነች፡፡ በመጨረሻዋ ቅርጹዋ ላይ ሁላችንም የየራሳችን ሚና አለን፡፡ ነገር ግን ይህ እንዲሆን የሚያስፈልገን ትንሹ የባሕሪ ለውጥ አርስበርስ መደማመጥ፣ አንዱ የሌላውን ሕመም መረዳት እና እውነታውን ሳያዛቡ እንዳለ ማቅረብ ነው፡፡ …››*

# ትግራይ እና ሕወሓት ምንና ምን ናቸው?

"An event has happened, upon which it is difficult to speak, and impossible to be silent.' ~ Edmund Burke.

## ሴቶች!

ሴቶች ፀጉራቸውን ያሳድጋሉ። ይህ ዓረፍተ ነገር በስህተት የተደነቀረ አይደለም፤ በምሳሌነት የቀረበ ነው። 1ኛ. ፀጉራቸውን የማያሳድጉ ሴቶች አሉ፤ 2ኛ. ፀጉራቸውን የሚያሳድጉ ወንዶችም አሉ። ቢሆንም ግን ዓረፍተ ነገሩ ውሸት/ስህተት ነው ሊባል አይችልም፤ ምክንያቱም የተለዩት (exceptionals) አጠቃላዩን አይገልፁም። በዚህ ርዕስ ስር የምናወራው ፍፁም እውነት ስለሆነ ነገር አይደለም፤ በአብዛኛው እውነት ስለሆነ ነገር ነው።

## ሕወሓት!

የትግራይ ተወላጆች ሕወሓት ይደግፋሉ። የዚህ ዓረፍተ ነገር እውነትነት ልክ ‹‹ሴቶች ፀጉራቸውን ያሳድጋሉ።›› እንደሚለው ዓረፍተ ነገር ነው።

በቁጥር ውዥንብር (illusion) ውስጥ ካልገባን በቀር (ኢሕአዴግ የደጋፊዎቹ ቁጥር እያለ የሚናገረው የ‹‹እውነተኛ›› ደጋፊዎቹ ቁጥር ነው ብለን ነባራዊውን እውነታ ማገናዘብ ካልተሳነን በቀር) የሕወሓት/ኢሕአዴግ ደጋፊዎች ቁጥር ከትግራይ ተወላጆች ቁጥር ጋር እኩል ነው። ነገር ግን ይኼ ትክክልም/ስህተትም አይደለም/ነውም። ምክንያቱም የትግራይ ሕዝብም ሆነ ማንኛውም ሰው የፈለገውን በሙሉ ወይም በጎዶሎ ድምፅ መደገፍ ይችላል። ስህተቱ ግን ምክንያቱ ላይ ነው - ወደእዚህ እንመለስበታለን።

ሌላ እውነት፤ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ደጋፊዎች ቁጥር ከትግራይ ተወላጆች ቁጥርጋ እኩል ከሆነ ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕወሓትን ወይ ይቃወማል አሊያም አይደግፍም ማለት ነው። ይኼም ትክክልም ስህተትም አይደለም/ነውም።

በመጀመሪያ የትግራይ ተወላጅ ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን ለምን ሕወሓትን አይደግፉም ወይም ይቃወማሉ? (ለምን ‹ሕወሓት› አልኩኝ? በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የምናወራው ወረቀት ላይ የሰፈረውን ማደናገሪያ ሳይሆን በተግባር ላይ ያለውን እውነታ ነው፤ ስለዚህ የመንግሥት ስልጣን ያለው በኢሕአዴግ እጅ ሳይሆን በሕወሓት እጅ መሆኑን ማስታወስ ይበልጥ ያግባባናል።) ለጥያቄው መልስ ስንሰጥ፦

1ኛ. ሕወሓት በትጥቅ ትግል ከመጣ በኋላ በምርጫ እና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሥልጣኑን የመልቀቅ አዝማሚያ አላሳየም፣

2ኛ. አብዛኛው እና ወሳኙ የመንግሥት ሥራ ኃላፊነት ቦታ በሕወሓት ሰዎች ተይዟል፤

እነዚህ ሁለት ነጥቦች ሌላውን/ቀሪውን ሰው በማስከፋቱ በይፋ በማይወጣ ቃል (ሕወሓትን እና የትግራይ ተወላጆችን እንደ አንድ በማየት) ብዙኃኑ የውስጥ ለውስጥ ቅሬታውን የትግራይ ተወላጆች በሌሉበት እርስ በእርሱ እንዲቀባበል አድርጎታል ማለት ይቻላል። እንዲህ ዓይነቶቹ የትግራይ ተወላጆችን በጥርጣሬ፣ በፍርሐትና አልፎ አልፎም በጥላቻ የመመልከቱ እና የማግለሉ አባዜ ደግሞ የትግራይ ተወላጆችን ወደሕወሓት ይበልጥ አየገፋ እና ታማኝ እንዲሆኑለት እያደረጋቸው መጣ። ብዙዎቹ ለሕወሓት በታመኑ ቁጥር ደግሞ በሌላው ወገን ያሉት ብዙዎቹ በትግራይ ተወላጆች ላይ ሁሉ (ያለልዩነት) ጥርጣሬ እና አልፎ፣ አልፎም ጥላቻ ጭምር እያዳበሩ መጡ። በዚህ መሐል ሁለት ዓይነት ማኅበረሰብ ተፈጠረ፦

1ኛ. የትግራይ ተወላጆችን ሁሉ በጥርጣሬ የሚመለከት፣

2ኛ. ሕወሓትን የሚደግፍ/የተደገፈ የትግራይ ተወላጅ፣

ቀሪው - አሁንም ፀጉራቸውን እንደማያሳድጉት ሴቶች ወይም እንደሚያሳድጉት ወንዶች ቁጥሩ እዚህ ግባ የማይባል ነው፡፡

## አረና!

አረና ከሕወሓት ተገንጥለው የወጡ የትግራይ ተወላጆች ፓርቲ ነው፡፡ የአረና ተቀባይነትን ከሁለት ወገን ማየት ይቻላል፡፡ 1ኛ. ከትግራይ ተወላጆች ወገን እና 2ኛ. የትግራይ ተወላጅ ካልሆኑ ቀሪ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ወገን፡፡

አረና ከሁለቱም ወገን ልባዊ፣ ሰፊ ተቀባይነትን ማግኘት አልቻለም ብዬ አምናለሁ፡፡ ከትግራይ ተወላጆች ወገን በሕወሓት ቅሬታም ቢኖራቸው ‹ከሌላውጋ ባለመስማማትም ቢሆን ጥቅማችንን የሚያስጠብቀው ሕወሓት ነው› የሚል እምነት አላቸው፡፡ አረና ያንን አያደርግም የሚለውን ተፅዕኖ ደግሞ የፈጠረባቸው በመድረክ ጥላ ከተሰባሰቡ ሌሎች ተቃዋሚዎችጋ መተባበሩ ነው፡፡ ይህ ከእርሱ በቀር ለትግራይ አሳቢ እንደሌለ በውጤታማ መንገድ መስበክ በተቻለው የሕወሓት አስተምህሮ መሠረት ሀጢያት ነው፡፡ ስለዚህ የትግራይ ተወላጆች አረናን የሕወሓትን ያክል ለመቀበል ሲቸግራቸው ይታያል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አረናን ቀሪዎቹም በጥርጣሬ እንዲመለከቱት ሆኗል፤ ይህንን ያደረገው ደግሞ ቀድሞ የጠቀስኩት የትግራይ ተወላጆችን ሁሉ ሕወሓትን አይቃወሙም/ይደግፋሉ የሚል ጥርጣሬ/እምነት አባዜ ነው፡፡ (ምናልባት አባባሌ ግልጽ የመሆን አቅም ካጠረው - አረና በትግራ ተወላጆች (ያውም ከሕወሓት የወጡ ሰዎች ስብስብ በመሆኑ) የምር ሕወሓትን ይቃወማል፣ የምር አማራጭ ሐሳብ ያመጣል የሚል እምነት በብዙዎች ውስጥ አጣለሁ፡፡ እንዲያውም፣ ሕወሓት በቀሪው ሕዝብ ውስጥ ያጣውን ተቀባይነት ለማግኘት የፈጠረው የሴራ ቡድን ነው የሚል ፍሬ አልባ ክርክር አድምጨ አውቃለሁ፡፡)

እነዚህን ነጥቦች የዚህኛውን ወይም የዚያኛውን ቡድን (አለመሆን ከታሪካችን አንፃር እንደሚከብደን ቢታወቅም፣) አይደለንም ብለን እናስብ እና መፍትሔ እንፈልግላቸው፡፡ እኔ የአረናን ዝርዝር ማኒፌስቶ ማወቅም መዘርዘርም ሳያስፈልገኝ በፖለቲካ ጦስ ትግሬ እና ትግሬ ያልሆነ በሚል በጥርጣሬ መስመር የተከፈለውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአረና መንገድ መልሶ ማስታረቅ ይቻላል ባይ ነኝ፡፡ ምክንያቱም መሠረታዊው ‹እኔ የእኛ ስብስብ አባል መሆኑን› (“I” is a subset of “We”) አምኖ መጀመር አለበት በሚል መርሕ አረና የሚወክለው የትግራይን ሕዝብ ቢሆንም ትግራይን የሚወክለው ግን ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን አምኖ መቀበል አለበት ነው፤ (ተቀብሏል የሚልም እምነት አለኝ) - አባባሌ ከሕወሓት የመከፋፈል አገዛዝ በተቃራኒ የአረና አካሄድ አብሮ መኖር ላይ የተመሠረተ ነው… ነው፡፡ ለዚህ እንደምስክር የምጠራው አረና በመድረክ ስም (መድረክ ጠንካራም ይሁን ደካማ) የተሰባሰቡ ፓርቲዎች አባል ለመሆን መድፈሩን ነው፡፡ መድረክ ውስጥ ሕብረብሔራውያን እና ብሔር ተኮር የሆኑ ፓርቲዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህን ፓርቲዎች በአንድ ያሰባሰባቸው የማኒፌስቷቸው አንድነት አይደለም፤ ተቃዋሚነታቸው ብቻም አይደለም፡፡ የራሳቸውን ሕልውና (መኖር) ከሌሎቹ ሕልውና ለይተው ማየት ባለመቻላቸው ነው፡፡ ሕወሓት ከመድረክጋ ኅብረት ሊፈጥር ቀርቶ በጠረጴዛ ዙሪያ ለመደራደር እንኳን እንደማይፈቅድ እናውቃለን፤ ምክንያቱን ብንጠይቅ የመድረክን ሕልውና እና የሕልውናውን አስፈላጊነት አምኖ መቀበል ስለማይፈልግ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ አረና በመድረክ አባልነቱ ብቻ በአንድ መዳፍ ላይ እንዳሉ ጣቶች የትግራይ እና ቀሪ ኢትዮጵያን አብሮነትን እንደሚቀበል እንቸገራለን ቢባል እንኳን የጽሑፉ ቁምነገር ስላልሆነ በፓርቲው (የአረና መንገድ በማለት) የመሰልነውን **‹‹ሌላውን በማጥፋት መኖር ሳይሆን ሌላውን በማኖር አብሮ መኖር››** የተባለ መርሕ መዝዘን ውይይታችንን እንቀጥል፡፡

ሕወሓት ‹‹እውነትም መንገድም›› እራሱ እና እራሱ ብቻ እንደሆነ ያምናል፡፡ ከእርሱ (እና የራሱ ርዕዮተ ዓለም) ውጪ ትግራይም/ኢትዮጵያም እንደማይኖሩ ያምናል፡፡ ይህ እምነት በአብዛኛው የትግራይ ተወላጆች አዕምሮ ሰርፁዋል ለማለት እደፍራለሁ፡፡ የብዙዎቹ የትግራይ ተወላጆች ሕወሓት ደጋፊነት እና የሙጢኝ ባይነትም የሚፈጠረው ከዚሁ የተሳሳተ ግንዛቤ እና ድምዳሜ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሕወሓት እና የትግራይ ተወላጆች (ሴት ወንድ፣ ወጣት አዋቂ፣ ምሁር መሐይም ሳይል) አንድነት ትግራይን ከቀሪው ሕዝብጋ በቀጭን የጥርጣሬ መስመር ለኹለት እየከፈላቸው ነው፡፡ ለነዚህ አንድ ነገር ግን በጥርጣሬ ድንበር ለኹለት የተከፈሉ ሕዝቦች መልሶ አንድ መሆን የሁላችንም ሚና ወሳኝ ነው፡፡ በሁለቱም ምናባዊ መስመሮች ክፍያ ውስጥ ያሉ ዜጎች የኹለቱም ሕልውና (የአንዱ በሌላው ላይ የተመረኮዘ) መሆኑን ለማስታወስ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ስሜትን አቁሞ እውነቱን መጋፈጥ ያስፈልጋል፡፡

ምንም እንኳን ዘመናዊ ፖለቲካ በጂኦግራፊያዊ ካርታ ቢከፍላቸውም ሕዝቦቹ ግን እነዚህን የፖለቲካ መስመሮች አቋርጠው አብረው ሲኖሩ፣ የነበሩበትን ታሪክ ለማስቀጠል አንዱ የሌላውን ሕልውና ማክበር አለባቸው። የመብት ክብር፣ የሥልጣንም ሆነ የሀብት ክፍፍል ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ችሎታ እና አግባብ ያገናዘበ መሆን አለበት። ኢትዮጵያ የኹለት ብሔሮች (ትግሬ እና ሌሎች /ያውም ክህሎት እና ዕውቀትን መሠረት ባላደረገ የአንዱ መሪነት እና የሌላኛው ተመሪነት/) ሳይሆን የሁሉም እኩል አገር የምትሆንበት ሥርዓት መዘርጋት ወይም በጊዜ ሒደት የሚዘረጋበት መንገድ መመቻቸት አለበት። ይህንን ልዩነት እየተንከባከብን ወደማይፈለግ አቅጣጫ ገፍተን አገሪቱን ገደል ከመስደዳችን በፊት በግልጽ እናውራበት፣ የትግራይም ይሁን ሌሎች ምሁራን በጉዳዩ ላይ አንደበታቸውን ይፍቱ፣ተቃዋሚ ፓርቲዎች ችግሩን እንደሌለ በዝምታ ከሚያልፉት እንዴት እንደሚቀርፉት ይንገሩን። ይኼው ነው የጽሑፉ ዓላማ!

# የዘር ፖለቲካ አዳላጭነት

በዳዊት ተሾመ

ኢትዮጵያ፣ ትግራይ እና ህውሓት ምንና ምን ናቸው? በሚል ርዕስ በበፍቃዱ ኃይሉ የቀረበው ጹሑፍ በአሁኑ ወቅት በዋናነት የኢትዮጵያ የውስጥ ፖለቲካ  የሚያጠነጥነበትን ነገር ግን በአብዛኛው ለግልጽ ውይይትና ክርክር፣ ለመድረክ ያልበቃ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ነው:: ለመድረክ ያለመብቃቱ ምክንያት በአብዛኛው ግልጽ ውይይት ያላደበርን በመሆናችንና ከብሔር ፖለቲካ ስስነት ጋር የተያያዘ ይመስለኛል:: በተጨማሪም ብዙዎቹ የሀገራችን ምሁራን በጉዳዩ ላይ የተለያዩ መጽሐፍቶችና ጹሑፎችን ቢጽፉም፤ የጻፉበት ቋንቋ በአብዛኛው በእንግሊዘኛ ስለሆነና የጻፉትም ለውጭ ታዳሚዎቻቸው ስለሆነ የጉዳዩ ባለቤት ባዳ እንዲሆን አድርጎታል:: ይህንን ዝግ ጉዳይ ጸሐፊው ለመስበር መሞከሩ በርታ የሚያስብል ነው:: ጽሑፉ ብዙ የምስማማባቸውን ሐሳቦች ያዘለ ነው:: ሆኖም ግን፣ በዚህ ጽሑፌ ሊታዩ ይገባቸዋል ብዬ ያሰብኳቸውን፣ ጸሐፊው በግልጽ ያላስቀመጣቸውንና በተወሰነ መልኩም አመክኖያዊ ግድፈቶችን ለመጠቆም ያህል ነው::

(1).
በሳይንሳዊ ምርምር ምልዕ-እውነት (100% truth) የሚባል ነገር የለም:: ምርምር በራሱ ማስረጃዎች ላይ የተደገፈና በተወሰነ ንድፈ-ሐሳባዊ መሠረት ተመስርቶ  በመከራከር፣ በመቃወም፣ እንዲሁም አዳዲስ ዕሳቤዎችንና ዕይታዎችን በማፍለቅ ወደ እውነት በተቻለ መጠን የመጠጋት ሒደት ነው:: ስለዚህም እውነት አንጻራዊነትን (relativity) የሚላበስ እንጂ ሁለንተናዊ (absolute) አይደለም:: ስለሆነም፣ ለአንድ ሰው ውይም ቡድን በአብዛኛው እውነት የሆነው ነገር ለሌላው ሰው ውይም ግሩፕ  እውነት ሊሆን እንደማይችል ታሳቢ መደረግ ያለበት ጉዳይ ነው:: በአንድ የተወሰነ ሐሳብ ውይም ጉዳይ ላይ የተለያዩ ዕይታዎችን (school of thoughts) የምናገኘው ለዚህ ነው::

(2).
ሁሉም የትግራይ ተወላጆች ሕወሓትን ይደግፋሉ የሚለው ስነ-አመክኖ (logic) ሲገለበጥ ሁሉም የትግራይ ተወላጆች ተጠቃሚ ናቸው ወደሚለው ጭብጥ ያደርሰናል:: በዚህ ሐሳባዊ ዕይታ ተመስርቶ በጸሐፊው *"የሕወሓት/ኢሕአዴግ ደጋፊዎች ቁጥር ከትግራይ ተወላጆች ቁጥር ጋር እኩል ነው"* ወደሚል ክርክር ይሸጋገራል:: በቅርቡ በታተመውና በኢሕአዴግ ዌብ-ሳይት ላይ የተለቀቀው ሰነድ (EPRDF: In Brief) እንደሚያመለክተው ከሆነ የኢሕአዴግ የአባላት ቁጥር እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2005 የነበረው 700,000 ሲሆን በ2013 ደግሞ 6.5 ሚሊዮን ነው (ገጽ 3 ይመልከቱ):: ይህንን ቁጥር ከትግራይ ሕዝብ ቁጥር ጋር ማመሳሰል በመሰረቱ ሁለት ስህተቶች አሉት:: አንደኛው የትግራይ ሕዝብ ብዛት በ2005ዓ.ም 700,000 ብቻ አልነበረም:: ስለዚህም ሁሉም የትግራይ ሕዝብ ሕውሓትን ይደግፋል የሚለው ተጨባጭ እውነታ ሊሆን አይችልም:: ሁለተኛ ይህ ማመሳሰል የተቀሩትን የግንባሩ አባል ድርጅቶችን ዕውቅና የመንሳት አካሔድ ውጤት ነው:: በመሠረታዊነት ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ ለድርጅቶቹ ተገቢውን እውቅና ሰጥቶ በማዕከላዊ የስልጣን ድልድሎሽ ላይ ያላቸውን ዝቅተኛ ድርሻ፣ ደካማ ውስጣዊ አቅም እና አነስተኛ ሕዝባዊ ተቀባይነታቸው ላይ ተንተርሶ መገምገም ይቻላል::

(3).
የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ ማኅበረሰብ ‹‹ትግራይ የሆነና ትግራይ ያልሆነ›› ብሎ መለየቱ በኔ አስተሳሰብ የድሮውን አካሄድ መድገም ነው:: ይህም ንደፈ-ሐሳባዊ መሠረቱ በዋነናነት በ1970ዎቹ የኢትዮጵያን የፖለቲካ አስተሳሰብ የተጫነው የታሪካዊ ማቴሪያሊዝም ማኅበረሰባዊ አረዳድ ነው:: ከኔ ጋር ያልሆነ ከነሱ ጋር ነው ማለት መሐከል ላይ ያለውን የማኅበረሰብ ክፍል ማጣጣል ነው:: እንደሚባለውም፣ እውነት ያለቺው መሐከል ላይ ነው እንጂ በግራም ሆነ በቀኝ ጫፎች ላይ አይደለም:: ጆህን ማረካኪስ የተባለው ጸሐፊም እንዲሁ Ethiopia: The Late Two Frontiers ብሎ በሰየመው መጽሐፉ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ ማኅበረሰብ በሁለት ከፍሎ ለማሳየት ሞክሯል:: ልዩነቱ ጸሐፊው ሐሳቡን የመሠረተው በብሔርተኝነት ላይ ሲሆን ማረካኪስ ደግሞ ጂኦግራፊክ አሰፋፈር፣ ሃይማኖትንና ብሔርተኝነት ላይ መመሥረቱ ነው:: ይህ አካሄድ ግን በዋነኛነት የኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ብሔረሰቦች መካከል ያለውን ፖለቲካዊ፣ ማኅበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች አቅልሎ የሚመለከት ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ በተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል ያለውን የመተባበር ላይ የተመሠረት ግንኙነት እና በተማሩ በሚባሉት መካከል ያለውን የስልጣን ፉክክርና ትግል ጨፍልቆ የማየትና የኂለኛውን የማጉላት አካሄድ እየተስፋፋ መምጣቱን የሚያመለክት ነው::

(4).

አረናን በተመለከተ የቀረበው በኔ አስተሳሰብ ቁንጽል ሐሳብ ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ ሦስትም ሰው ሆነ 50 ሰው ከሕውሓት ተገንጥለው ከወጡት ውስጥ አረናን ያቋቋሙት፣ መነሳት የነበረት ሐሳብ እነዚህ ሰዎች ‹ሕውሓትን ለቀው ("ተባረው") የወጡት በአካሄድ ደረጃ ባለመስማማታቸው ነው ወይስ በመርሕ፣ ስትራተጂና ግብ ላይ ባለመስማማታቸው?› ነበር:: አረናን የመሠረቱት ሰዎች (ከሕውሓት ተገንጥለው የወጡትም ሆነ ሌሎች) የትግራይን የበላይነት ለማስቀጠል በሚያስችሉ የአካሄድ ጉዳዮች ላይ ብቻ ከሆነ ከሕውሓት ጋር የሚለያዩት፣ አረና የመድረክ አባልም ሆነ አልሆነ በመሠረታዊነት አሁን ጸሐፊው ያነሳውን ችግር ሊቀርፍ የሚያስችል ሳይሆን ይበልጡንም ችግሩን የሚያስፋፋና ቅርቃር (deadlock) ውስጥ የሚከት ነው:: በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በፖለቲካ ታክቲክና ጊዜያዊ ፖለቲካዊ ትርፍ ሲባል ብዙ የተቋቋሙ ኅብረቶችን፣ ቅንጅቶችንና አንድነቶችን ማየታችንን ታሳቢ በማድረግ የአረና መድረክን መቀላቀል ይህን ያህል ሊያስገርመን የሚችል ጉዳይ አይደለም:: ይህ ከሆነ በመሠረቱ አረና መድረክን የተቀላቀለው ለፖለቲካዊ ታክቲክ እና የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚለው መርሕ ላይ በመመሥረት ይሆናል:: ነገር ግን አረና ከሕውሓት የሚለይበት ጉዳይ በመርሕ፣ ስትራተጂና ፖለቲካዊ ግቦች ዙሪያ ከሆነ እውነትም አረና መድክን መቀላቀሉ ጸሐፊው እንደሚለው „**<u>ሌላውን በማጥፋት መኖር ሳይሆን ሌላውን በማኖር አብሮ መኖር</u>**" ላይ የተመሠረተ አዲስ ፖለቲካዊ ባሕል የሚያስተዋውቅና አሁን የተከሰተውን ችግር ሊፈታ የሚያስችል አካሄድ ነው:: ስለዚህም የአረናን ዝርዝር ማኔፌስቶና ፖለቲካዊ ግቦች ሳያውቁና በትንታኔ ሳይደግፉ እንዲሁ ‹በዘር ፖለቲካ የተለያየውን የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ማኅበረተስብ መልሶ ማስታረቅ ይቻላል› ማለት አይቻልም:: የአረናን ዝርዝር ማኔፌስቶና ፖለቲካዊ ግቦች ማወቅና በትንታኔ መደገፍ መሠረታዊ ጉዳይ ነው፤ የጸሐፊውን ዕሳቤ ለመደገፍም ሆነ ለመቃወም::

የዘር ፖለቲካን በተመለከተ:- የዘር ፖለቲካ መሠረታዊ ባሕሪው አዳላጭ መሆኑ ነው:: ብዙ የብሔር ቡድኖች በአንድ አገር ውስጥ መኖራቸው በመሠረታዊ ደረጃ እንደ ችግር የሚታይ አይደለም:: ችግሩ የሚመነጨው በብሔር ቡድኖች መካከል ያለው ግንኙነት ከትብብርና ከዕኩል ተጠቃሚነት ወደ የበላይነትና አድሎአዊነት ሲሸጋገር ነው:: የሕውሓትንና የትግራይ ብሔርተኛነትን የፖለቲካ ታሪክ ከዚህ እውነታ የሚወጣ አይደለም:: የዘር ፖለቲካ አዳላጭነቱ የሚመነጨው አመክንዮአዊነትንና ምክንያታዊነትን ሽሮ ‹‹እኛ እና እነርሱ›› ወደሚለው አስተሳሰብ ሲወርድ ነው:: ይህ እኛ እና እነርሱ አስተሳሰብ በጥርጣሬና ምናባዊ ዕሳቤ አሉ የሚባሉ ልዩነቶችን አስፍቶ የሚያሳይ በተቃራኒው የአንድነትን ጉዳዮችን ፖለቲካዊ ትርጓሚ በመስጠት የሚያቀጭጭ ነው:: ስለዚህም አንድ ብሔር በጥርጣሬ መታየት ሲጀምር ለኔ ይቀርባል ወደሚለው የፖለቲካ ቡድን ይበልጥ የሚገፋው ሲሆን በሌሎች የብሔር ቡድኖች ደግሞ ይበልጥ ባይተዋርነትን የሚፈጥር ይሆናል:: ይህ ሁኔታ በደንብ ከተለጠጠ ደግሞ የደም ዘርን ወደመቁጠር ይወርዳል:: ለምሳሌ ጃዋር መሃመድ በ2010 ባወጣው ጹሑፍ (Tigrean Nationalism: From Revolutionary Force to Weapon of Repression) ላይ እንዳመለከተው አሁን ያለው ሕውሓት የትግራይን ብሔርተኝነት የሚወክል አይደለም ምክንያቱም ንፁሕ የትግሬ ተወላጆችን በማባረር ግማሽ ትግሬ ግማሽ ሌላ ዘር (በአመዛኙ ኤርትራውያን) የሆኑ የተቆጣጠሩት ድርጅት ነው:: በቅርቡም ፕ/ር ተስፋፅዮን መድኃኔ ተመሳሳይ የሆነ ሐሳብ ኤርትራን በሚመለከት ባወጡት ጽሑፍ ላይ አንፀባርቀዋል:: ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ የፖለቲካ ልሂቃኖች ደግሞ የዘር ፖለቲካን ድጋፍ ለማሰባሰቢያና አገዛዛቸውን ቅቡል ለማድረግ ሲሉ አንዱን ያቀረቡና የጠቀሙ በመምስል እና ሌላውን የመግፋት አካሄድ በመጠቀማቸው፤ የዘር ፖለቲካ የግጭትና የጦርነት ምክንያት እንዲመስል አድርጎታል:: አሁንም ሁሉም የትግራይ ተወላጆች ሕውሓትን ይደግፋሉ፤ ተጠቃሚም ሆነዋል የሚለው አስተሳሰብ የዘር ፖለቲካ አዳላጭነትን የሚያመላክት ነው::

## ፎንቱ ፎኒፍ ሪፌታ ጄናን ኢቲሌን ጂቢቻ ቲ ካቴ
## ("ስጋ ለስጋ ይደነግጣል ቢባል ጥጃ እንኳ በቁርበት ደነገጠች")

*"አገሬ፣ አገራችን ኢትዮጵያ ነች። እንደ ኢትዮጵያዊ እንከራከራለን። ኢትዮጵያ መኖር አለባት። ሁላችንም የኢትዮጵያ አባል መኾን አለብን ብዬ ነው የማስበው።"*
- ቡልቻ ደመቅሳ ይናገራሉ! ልዩ ቃለ ምልልስ

*"የኢትዮጵያ አንድነት እና ነፃነት፣ እኩልነት ከተጠበቀ፣ በተፈጥሮ ሃብት የተደላደለች፣ በታሪኳ የገነነች፣ ኢትዮጵያ ሳትከፋፈል እና ሳትቆራረስ ለዘላለም እንድትኖር፣ የጎሳ ልዩነት ሳይደረግ በኢትዮጵያ ውስጥ የተወለደ ኢትዮጵያዊ ሁሉ **ኢትዮጵያዊነት** ግዴታው እና መብቱም ነው ብዬ አምናለሁ።"*
- ጃገማ ኬሎ (የበጋው መብረቅ ይናገራል)

*"I am so humbled and am forever grateful to our ancestors; no matter what mistakes they committed, they resisted all the colonizing powers in a way that made them create a history and logo that branded Ethiopia as the very idea of the decolonizing imagination."*
- Dr. Mammo Muchie

የዞን ዘጠኝ ጦማሪዎች [ኢ-መደበኛ] ቡድን አባል መሆኤ በዚህ ዓመት ከተከሰቱልኝ ምርጥ እውነታዎች ውስጥ በጣም ጠቃሚው ነው። ቡድናችን ‹‹የንባብ ፕሮግራም›› የተሰኘ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ፣ አንድ ጽሑፍ ላይ ተመስርቶ በተወሰነ የጊዜ ዝላይ (Time Interval) መወያየት ጀምሯል።

ይህ ጽሑፍ የዚህ ‹‹የንባብ ፕሮግራም›› ትሩፋት ነው። በእንዳልክ መራጭነት ‹‹Oromo Narratives›› የዶ/ር ዶናልድ ሌቪን ጥናት ላይ ለመወያየት ተጠራርተን ተገናኘን። ርዕሰ ጉዳዩ የኦሮሞ ብሔረሰብ የፖለቲካ ጥያቄዎችና አማራጭ መልሶች ላይ በጥቅሉ የሚያጠነጥን ነበር። በጉዳዩ ላይ የጠለቀ እውቀት ለሌለው ለእንደኔ ዓይነቱ ልብን በብርሃን የሚያጥለቀልቅ (enlights) የንባብና የውይይት ፕሮግራም ነበር። ይህንን ሳያካፍሉ መቅረት ስስት ነውና፣ ባይሆን እየቆነጠርኩ ላካፍላችሁ።

የብሔረሰቦች ጥያቄ ቢያዳፍኑት የማይጠፋ፣ ቢያቀጣጥሉት የሚፋጅ፣ አይነኬ ጉዳይ ይመስለኝ ነበር። እርግጥ አላዋቂ አራጋቢ ሲያራግበው - ሰደድ እሳትም ቢሆን ማስነሳቱ አይቀርም። ነገር ግን የማይነካ ጉዳይ አድርጎ ማሰብ የተሳሳተ ነው።

የኦሮሞ ብሔረሰብ ጥያቄዎች ከማንነት እና እሴት እስከ ኤኮኖሚ፣ እስከ አስተዳደራዊ እና አመራር ሚናዎች ድረስ ሁሉንም ያካልላሉ። እኛም ጨረፍ፣ ጨረፍ እያደረግን እንመለከታቸዋለን። መጀመሪያ ወደመጀመሪያው!

### ከታሪክ በማንኪያ

የገዳ ስርዓት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በዘመናዊነት ተቃኝቶ ሊተገበር የሚችል ብቸኛው አገርበቀል ትውፊታዊ የፖለቲካ ስርዓት ነው። ስርዓቱ ለአምባገነናዊነት በማይመች መልኩ የገዢዎችን መደብ የስልጣን እና ዘመነ ስልጣን የሚገድብበት ደንብ ያለው፣ የወላጆችና ልጆች ትውልድ ክፍተትን የሚያስታርቅበት እና ትውልዶች በየዕድሜያቸው እርከን የአስተዳደር/አመራር ልምድ የሚያዳብሩበት አካሄድ ያለው፣ ከአምልኮ ግንኙነት የሌለውና (it indeed has a religious element, the good thing is that the Geddaa system explicitly differentiates the two and the leadership of ritual and the political spheres) ሲያጠፉ የሚከሰሱበት እኩልነትን ማስፍን የሚችል የሕዝባዊ አስተዳደር ስርዓት ነው። የገዳ ስርዓት በዘር የሚሾሙ (የዕድሜ ልክ ) እና በምርጫ የሚሾሙ (ቢበዛ የ8 ዓመት) መሪዎች ይኖሩታል። በቀላሉ ሊሻሻሉ ከሚችሉት ድክመቶቹ (ለምሳሌ፤ ሴቶችን አሳታፊ አለመሆኑና ከዘውዳዊነት ጋ የሚመሳሰልበት አካሄድ መኖሩ) በስተቀር ራሱን የቻለ ወጥ የዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ ስርዓት ፍልስፍና ነው። ለዝርዝሩ ይህንን (አውርዳችሁ) ወይም ይህንን (ባለበት) እንድታነቡት እየጋበዝኩ የኦሮሞን ብሔረሰብ ወደመላው ኢትዮጵያ አካባቢዎች የመሰራጨት ታሪክ በአንድ አንቀጽ እወጣዋለሁ።

ከ16ኛው ክፍለዘመን ወዲህ የኦሮሞ ሕዝቦች ወደሰሜን፣ ምስራቅ እና ምዕራብ በመስራጨት እንደአሁኑ በመላው የአገሪቱ ክልሎች ውስጥ ለመገኘት በቅተዋል። የኦሮሞ ብሔረሰብ አባላት ባላቸው በቀላሉ የመዋሃድ እና የመወዳጀት ችሎታ ምክንያት በመላው ኢትዮጵያ በሚስፋፉበት ወቅት በሰሜን ኢትዮጵያ ክርስትናን፣ በምዕራብ ኢትዮጵያ እስልምናን ተቀብለዋል፤ በደቡብ ምዕራብ መንግስት ሲያቋቁሙ፣ በሸዋ ደግሞ አርሶአደር ማኅበረሰብ መስርተዋል።

እዮኣስ (የንጉሥ የበካፋ የልጅ ልጅ) ግማሽ የኦሮሞ ብሔረሰብ አባል የሆነ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነው። ሦስት ሺህ የኦሮሞ ተወላጅ ወታደሮችም ነበሩት። ከዚያ በኋላም በኢትዮጵያ የነገሥታት ታሪኮች ውስጥ የኦሮሞ ደም ያላቸው የጎጃም ንጉሥ ተክለሃይማኖት፣ ዳግማዊ ምኒልክ፣ እቴጌ ጣይቱ ብጡል፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እና እቴጌ መነንን ጨምሮ በርካታ የንጉሣዊ ቤተሰብ አባላት ነበሩ።

## የኦሮሞ ብሔረሰብ ጥያቄዎች

የኦሮሞ ሕዝብ ከሁሉም ብሔረሰቦች ቁጥር በላይ ቢበዛም ‹‹የሁለተኛ ደረጃ ዜጋ›› ሁኗል ብለው የሚከራከሩት ብዙሐን ናቸው። በአመራር ደርሻ ከፍተኛ ሚና የነበራቸው አማሮች እና ትግሬዎች (‹‹አቢሲኒያዎች››) ‹‹የመጀመሪያውን ደረጃ›› ይወስዳሉ ነው ምሬቱ።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የምታገኝበት ቡና እና አሁን ገቢው እያደገ የመጣው የወርቅ ማዕድንም የኦሮሚያ ምድር ፍሬዎች ናቸው። ሆኖም ኦሮሚያ በኢኮኖሚ የሚገባትን ያህል አልተጠቀመችም የሚል ሌላው የኦሮሞ ብሔረሰብ ተወላጆች ዐብይ ጥያቄ ነው።

## መፍትሔዎቹስ?

ብዙሐኑ ነጭ በሆነበት አሜሪካ ጥቁር ፕሬዚደንት ሲመረጥ ‹‹ለውጥ መጣ›› ልንል እንችላለን፤ ሌላውን ስርዓቱ ይሰራዋልና። የኦሮሞ ብሐየረሰብ ተወላጅ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ቢመረጥ ግን እንዲህ በቀላሉ የኦሮሞ ተወላጆች (ወይም በጥቅሉ የብሔረሰቡ) ጥያቄ መልስ አገኘ ብለን መደምደም አንችልም።

ዶ/ር ሌቪን በጠቀስነው ጥናታቸው ውስጥ ሦስት ትርክታዊ አማራጭ መፍትሔዎችን ጠቁመው ነው ጥናታቸውን የሚደመድሙት።

**1ኛ. ትውፊታዊው ትርክት**
*‹‹… sustaining and strengthening whatever can be preserved of the traditional institutions of the Oromo Gadaa system. Toward that end they should maintain a certain distance from the political center of the Ethiopian nation. …›› (…በትውፊታዊው የገዳ ስርዓት ውስጥ አጠናክሮ ማቆየት የሚቻለውን ማስቀጠል፤ በዚያውም ከኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ማዕከል ጋር ያለውን ርቀት ባለበት ማስጓዝ።…)*

**2ኛ. የቅኝ ተገዢነት ትርክት**
*‹‹… a "national liberation struggle [that] will continue between Oromia and Ethiopia until the Oromo nation freely decides its political future by uprooting Ethiopian settler colonialism …›› (…የኦሮሞ ብሔረሰብ ተወላጆች ኢትዮጵያዊ ሰፋሪ ቅኝ ገዢዎችን ነቅለው በማስወገድ ስለራሳቸው ዕጣ ፈንታ መወሰን እንዲችሉ/እስኪችሉ ድረስ/ የብሐየራዊ ነፃነት ትግል ማድረግ …)*

**3ኛ. የኢትዮጵያዊነት ትርክት**
*‹‹… struggling to institutionalize pluralistic democracy and multicultural diversity, Oromo rhetoric and self-understanding should be revised to include appreciation of the many Oromo contributions to building the modern Ethiopian nation, and Oromo customs could be deliberately invoked and adopted to civilize the conduct of members of the national parliament and other deliberative bodies …›› (ብዝሐ ዴሞክራሲያዊነት እና ብዝሐ ባሕላዊነት በኢትዮጵያ እንዲሰፍን መታገል፣ የኦሮሞ ብሔረሰብ ለዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ግንባታ ያለውን እና የነበረውን ሚና ዋጋ ማሰጠት፣ እና የኢትዮጵያ ፓርላማ የኦሮሞን ትውፊታዊ ስርዓትና ወግ ዘመናዊነት በማላበስ ለተግባራዊነት ማብቃት።…)*

በግሌ ሦስተኛው የመፍትሔ አማራጭ ውስጥ ራዕይ ይታየኛል፡፡ በመግቢያዬ ላይ ያስቀመጥኳቸው የተቀነጨቡ አባባሎችም የሚያጠናክሩት ‹የኢትዮጵያዊነት ትርክት› መፍትሔዎችን ነው፡፡ ትውፊታዊው የገዳ ስርዓት እጅግ የሚያስደንቁ፣ መቻቻልን የሚያበረታቱ፣ የሕግ የበላይነትን የሚያሰፍኑ፣ እና ሌሎችም በርካታ ጠንካራ ጎኖች አሉት፡፡ በዶናልድ ጽሑፍ ላይ ተወያይተን ስናበቃ እንዲህ አለምኩ፤

*‹‹የኦሮሞ ክልላዊ መንግስት የገዳን ስርዓት ዘመነኝነት አላብሶ በክልላዊ አስተዳደሩ ሲተገብረው፣ የፌዴራል መንግስቱ በስኬቱ ቀንቶ (ከስኬቱ ተምሮ) ስርዓቱን ለብሔራዊ ስርዓትነት ሲያውለው - ለገዛ አገራችን ችግር አገራዊ መፍትሄ... ምኑ ቅጡ!››*

ሕልሜ እውን እስኪሆን ድረስ ማለሜን አላቆምም!!!

# እንሄዳለን - አትሄዱም

ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ በየዓመቱ በህዳር ወር የመጨረሻ ቀናት ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ ተመሳሳይ ማንነት ያላቸው የኢፌድሪ ሕገ መንግስት ‹ብሔር፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች› በማለት የሚጠራቸው ዜጎች በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች እየተዘዋወሩ ይጨፍራሉ፣ ይዘፍናሉ ይደሰታሉ፤ ቀኑም ከምንኛ የሕዝብ በዓላት እንደ አንዱ ተቆጥሮ በከፍተኛ ትኩረት ሲከበር ይውላል። ነገር ግን ከዘፈኑ እና ከጭፈራው በተቃራኒ ከነዚህ ሕዝቦች ጉያ የወጡትና ‹ሚካ ቤቴ› ያሉት የእነሱ ልጆች ‹‹ቤተሰቦቻችን አብረውት ከሚጨፍሩት ሕዝብ ጋር አብረን መኖር አንፈልግም፤ መገንጠልን እንሻለን!›› በማለት ነፍጥ አንግተው ትግል እያደረጉ ነው። ይህ ነው The Ethiopian Paradox - የኢትዮጵያ አያዎ።

## ሀገር ከወዴት?

የሀገር አፈጣጠር (State Formation) ምሁራን አን ወጥ ስምምነት ላይ ካልደረሱባቸው የህብረተሰብ ግንዛቤዎች አንዱና ዋነኛው ነው። ሀገር በመልካም ፈቃድ እንጅ በጉልበት ሊፈጠር አይችልም፤ ከተፈጠረም እደገና ፈርሶ በአዲስ ልክ መገንባት አለበት የመለው ሀሳብ በአንድ በኩል ሲቀርብ፤ በሌላ በኩል ደግሞ አይ ዛሬ ላይ ሆነን ትናንትን ልንወቅሰው አንችልም ሀገር በተለያዩ መንገዶች (by Hook or Crook) ልትፈጠር ትችላለች። ታሪክ እንዳሳየንም ሀገሮች በሰላማዊ መንገድ ብቻ እንደማይገነቡ ነው። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆኑት የGiuseppe Garibaldiዋ ጣሊያን፣ ‹ሀገራችን መገንባት ያለበት በBlood and Iron ነው› ብሎ የገነባት የOtto von Bismarck ጀርመን፣ የአንድነት ማህበሩን ለቆ መውጣት አይቻልም በማለት በጉልበት አንድነቷ የፀደቀላት የAbrham Lincolnዋ አሜሪካንን መጥቀስ ይቻላል ሲሉ ሀሳባቸው ይሰነዝራሉ። እንግዲህ እነዚህን ሁለት የተራራቁ ሀሳቦችን ማቻቻል ነው የሀገር ግንባታ ዋነኛ አላማ።

## መገንጠል እንደ መብት

የሀገሮች መኖር መሬት ላይ እውነታ ቢሆንም የተለያዩ ምሁራን መገንጠልን እንደ መብት በማየት ነገር ግን ለመገንጠል መሟላት በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ልዩነት ይፈጥራሉ። ይሄንም ተንተርሶም ሁለት መሰረታዊ የመገንጠል መብት ህልዮቶች (Theories) ይቀርባሉ። የመጀመሪያው መገንጠልን እንደ መፍትሄ (Remedial Secession) የሚመለከተው ህልዮት ሲሆን፤ የዚህ ሀሳብ ደጋፊ ምሁራን እንደሚሉትም የአንድ ሕዝብ መገንጠል በሀገሪቱ ላለው ችግር እንደ መፍትሄ ሊሆን የሚችል ከሆነ እና ይህ ተገንጣይ ክፍል ተነጥሎ ጉዳት እየደረሰበት ያለ (A continuing injustice and gross Human Right violation) ከሆነ መገንጠል አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው ይላሉ። የሁለተኛው ህልዮት አቅራቢ ምሁራን ግን የመገንጠል መብት ራሱን ችሎ የቆመ መብት (Primary Right) ሲሆን ፤ አንድ ሕዝብ መገንጠል ከፈለገ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይህ ቀዳሚ መብቱ ሊከበርለት ይገባል የሚሉ ናቸው።

## ሕገ መንግሥቱስ

Cass Sunstein የተባሉ የሕገ መንግስት ምሁር "Constitutionalism and Secession" ባሉት ፅሁፋቸው የመገንጠል መብትን በሕገ መንግስት ደረጃ መቀበል ከሕገ መንግስታዊነት (Constitutionalism) ጋር የሚጋጭ ሀሳብ እንደሆነ ሲያስቀምጡ ‹‹በታላቅ መርህ የሚመራ ዲሞክራሲያዊ ህብረተሰብ ለመመስረት በብዙሃኑ (Majorities) የሚወሰንን ውሳኔን መቀበል ይኖርብናል፣ ነገር ግን ውህዳኑ (Minorities) የመገንጠል መብት ካላቸው የብዙሃኑን ውሳኔዎች አንቀበልም በማለት የእንገነጠላለን ጥያቄ አቅርበው ውሳኔውን ሊያኮላሹት ይችላሉ፤ እንዲሁም የመገንጠል መብታቸውን እንደ ጥቅም መጠየቂያ (Bargaining tool) ሊጠቀሙበት ይችላሉ›› ይላሉ።
በሌላ በኩል ደግሞ እንደ Allen Buchanan ያሉ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ጥናት ያደረጉ ምሁራን የመገንጠል መብትን በሕገ መንግስት ገደብ በማበጀት መብቱ ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ ጥቅሙ ላቅ ያለ ነው የሚል ሀሳብ ይቀርባሉ። የዚህ ሀሳብ ደጋፊዎች ማጠናከሪያቸውን ሲሰነዝሩ፤ መብቱ በሕገ መንግስት ደረጃ ተቀባይነት ማግኘቱ ዜጎች የራስን በራስ የማስተዳደር መብታቸው እንዲከበርላቸው ያደርጋል ብሎም ወደ ሀገሪቱ መቀላቀል የሚፈልግ ሌላ ግዛት ይሄን ሕገ መንግስታዊ መብት እንደ ዋስትና ተጠቅሞ ሀገሪቱን መቀላቀል እንዲችል ያደርገዋል በማለት ነው።

## ኢትዮጵያዊ የመገንጠል ሐሳብ

ባለፉት ሀያ ዓመታት በኢትዮጵያ ግሎ እና ገኖ ሲያነታርክ የከረመ ሀሳብ ዝርዝር ብታዘጋጁ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠልን የሚያክል ግዝፈት የነሳ ሀሳብ በቀዳሚነት ሊኖራችሁ ይከብዳል፡፡ የሀሳቡ አቀንቃኞች ጉዳዩን ወደ ፖለቲካዊው ተወስኦ (Political Discourse) ያስገቡት በ ‹ያ ትውልድ› አቢዮታዊ እንቅስቃሴ ወቅት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በዋናነት በኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባር (ጀብሃ) ኤርትራን ነፃ የማውጣት እንቅስቃሴ የተጀመረው የእንገነጠላለን ጥያቄ፤ በኤርትራ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባር (ሻዕቢያ) ተጠናክሮ በመቀጠል፤ ከሰሜኑ የሀገራችን ጫፍ ተነስቶ ቀስ በቀስ የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባር (ሕወሃት) በመጀመሪያ ማንፌስቶው ‹ትግራይን ከኢትዮጵያ ነፃ አወጣለሁ› ብሎ እንዲያውጅ አደረገው፡፡ በዚህ ያላቆመው ጥያቄ በአስገራሚ ሁኔታ ወደ መሀከላዊ የሀገሪቱ ክፍል ዘልቆ ከሀገሪቱ ሕዝቦች ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘውን የኦሮሞ ሕዝብን ገንጥለን ነፃ እናወጣዋለን የሚለውን የኦሮሞ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባር ብቅ አለ፤ ጥያቄው በዚህ አላበቃም ይልቁንም ወደ ምስራቁ የሀገሪቱ ክፍል በመሄድ ኦጋዴንን ነፃ አወጣለሁ የሚሉ ሀይሎች እንደ እንጉዳይ ፈሉ፤ አፋርም ‹እኔም አይቅርብኝ› በሚል ‹እገነጥልሃለሁ› የሚሉ ልጆቹን ወደ ጫካ አሰማራ፡፡

ለብዙሃኑ ተገንጣይ ሀይሎች እንደ ምክንያት የሚቀርበው ጉዳይም የታሪክ መዛባት ነው፤ በተለይም በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ጊዜ የተከናወኑ ሰሜናዊ እና ደቡባዊ እንቅስቃሴዎች ያስከተሏቸው ክስተቶች፡፡ ብዙሃኑ ተገንጣይ ሀይሎች ‹በማዕከላዊው የአቢሲኒያ መንግስት የቅኝ ግዛት ተፈፅሞብናል፤ ይሄም ቅኝ አገዛዝ በዋነኛነት ስር የሰደደው በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ነው› ሲሉ እንደ ኤርትራ ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባር ያሉት ሀይሎች ደግሞ ‹አፄ ምኒልክ ለአውሮፓ ሃይል አሳልፈው ሰጥተውናል› በማለት ጉዳዩን ‹ከሽያጭ› ጋር ያያይዙታል፡፡

እንዲህ እንዲህ እያለ በህወሃት የተመሰረተው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) ዙፋን ላይ ሲወጣ ኤርትራ ‹ተገንጥያለሁ› ብላ ስንበት አቀረበች፤ ሄደችም፡፡ በኤርትራ መገንጠል ማግስት የፀደቀው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስትም የመገንጠል መብት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ (As a primary Right) በሕገ መንግስት መፈቀድ አለበት የሚለውን ህልዮት በመቀበል በዝነኛዋ አንቀጽ 39 ንዑስ ቁጥር 1 ላይ፡

*‹‹ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ እና ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው፡፡››*

በማለት ማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝብ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ (Unconditionally) ተገንጥሎ የራሱን ሀገር መመስረት እንደሚችል 'አበሰረ/ አረዳ'፡፡ ይሄም የኢፌድሪን ሕገ መንግስት የመገንጠል መብትን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚፈቅድ ብቸኛው የጊዜያችን የዓለም ሕገ መንግስት አደረገው፡፡

የፌደራሉን ሕገ መንግስት ተከትለው የወጡት የዘጠኙም ክልሎች ሕገ መንግስቶች በተመሳሳይ ቃላት በአንቀፅ 39 የመጀመሪያ ንዑስ አንቀፅ ላይ ከፌደራሉ ሕገ መንግስት በበለጠ እና ከረር ባለ መልኩ፡

*‹‹የ ... ብሄር/ ብሔረሰብ/ሕዝብ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግስት የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው፡፡››*
በማለት እጅግ የሰፋ መብትን 'unconditionally' እና 'with no restriction' የሚሉ መረን ዘለል ቃላትን ተጠቅመው በመስጠት የጉዳዩን አነታራኪነት ጫፍ አስነኩት፡፡

## The Nuclear Option

ብዙ ኢትዮጵያዊያን በተለይም አንድነትን በማንኛውም መንገድ የሚያፈላልጉ (Ultranationalists) ኢትዮጵያዊያን የኢፌድሪ ሕገ መንግስት ይሄን የተለጠጠ መብት መስጠቱ ኢህአዴግ የኢትዮጵያን አንድነት ባለመፈለጉ ነው፤ መጀመሪያ በትግል አጀማመራቸው ወቅት መገንጠልን እንደ ዓላማ ይዞ የተነሳ ፓርቲ የሀገሪቱን አንድነት ማስጠበቅ እንደማይፈልግ ግልጽ ነው፤ የኤርትራን መገንጠልም ያለምንም ዝግጅት እና ቅድመ ሁኔታ መፍቀዱ

የዚህ ፀረ-ኢትዮጵያ አቋሙ መገለጫ ነው፡፡›› በማለት በሕገ መንግስቱ የተሰጠው የመገንጠል መብት ኢትዮጵያን የሚበታትን የጥፋት አማራጭ (The Nuclear Option) እንደሆነ፤ ‹‹የመብት ጉዳይ ቢሆን እዚህ መብት ላይ ርቆ ከመሄድ ይልቅ አንድ የሚያደርገንን ፖለቲካል ኢኮኖሚ ለመገንባት መስራት ይቻል ነበር፡፡›› እያሉ የመገንጠል መብትን በእጅጉ ይፀየፉታል፡፡

## እፀ በለስ፡ የሚታይ እንጅ የማይበላ ፍሬ

ሌሎች ደግሞ መብቱ መኖሩ መልካም ነው፤ ነገር ግን መብቱ የሚታይ እንጅ የማይበላ ነው በማለት ሕገ መንግስቱን ተቀብለው ኢህአዴግን ይጠላሉ፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት የመገንጠል መብትን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደ መብት ማስቀመጡ የሚታይ ነገር ቢሆንም፤ ይሄን መብት እናራምዳለን ብለው የተነሱ ሀይሎች ‹በሀገሪቱ ጠላትነት ተፈርጀን ከፖለቲካ ሜዳው ተባረናል፤ እኛ የምንታገልለት ሕዝብም አፈናው በርትቶበታል›፤ ብለው ሮሮቸውን ያሰማሉ፡፡ እነዚህ ሀይሎች ድምጻሜያቸውን ሲሰጡም ‹በሕገ መንግስቱ የተቀመጠው የመገንጠል መብት ጥቅም ላይ የማይውል ከሆነ፤ ከዛሬ ነገ ይህ መብት ይከበርልኛል ብሎ ለመብቱ የሚታገለውን ሕዝብ ማሳዘን ስለሚሆን፤ ከመብትነቱ ቢፋቅ ይሻላል› በማለት ተስ ቢስነትን የሚያመላከት ሀሳብ ይሰነዝራሉ፡፡ እውነት መብቱ እንዲህ ሩቅ ነው? ብለን ስንጠይቅ፤ አብዛኞቹ ይሄን መብት ለማስከበር ‹ዱር ቤቴ› ያሉ ፓርቲዎች በህገወጥነት መፈረጃቸው ማስተዋላችን መልሳችን አዎንታዊ እንዲሆን ሊያስገድደው ይችላል፡፡

## ኢሕአዴግ ሲመልስ - ‹አይ ይሄ መለስ አይሆንም› ሲባል

የቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ‹ለምን መገንጠል መብትን በሕገ መንግስት ደረጃ ተቀባይነት እንዲኖረው ተደረገ› ተብለው በተደጋጋሚ ሲጠየቁ የሚጡት አንድ ምላሽ ነበር፡፡ ‹‹ደርግ በወደቀ ማግስት ከሶማሌ ክልል የመጡ ተወካዮች በሉ አስከፊውን ስርዓት ስላስወገዳችሁልን እናመሰግናለን፣ አሁን እኛንም እንደ ኤርትራ አሰናብቱን አሉን፡፡ እኛም ትንሽ ሰከን በሉ እስኪ፤ በግዴታ እኛ ጋር ቆዩ አንላችሁም፡፡ ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ስትኖሩ በደል የሚደርስባችሁ ከሆነ የመገንጠል መብታችሁን የሚቀበል ሕገ መንግስት እናዘጋጃለን ብለን ተመሳሳይ ጥያቄ የነበራቸውን ሕዝቦች  በዚህች አንቀፅ መለስን›› ይላሉ፡፡

ኢህአዴግ በተደጋጋሚ በተለያዩ ሰነዶቹ ስለ ጉዳዩ ማብራሪያ ሲሰጥ የኢፌድሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 39 ኢትዮጵያን እንደ ዮጎዝላቪያ ከመበታተን ያዳነ መልዓክ አድርጎ ያስቀምጣል፡፡ ለዚህም ምክንያቱን ሲያቀርብ ‹‹በአንቀፅ 39 ላይ ሁለት መሰረታዊ መብቶች አሉ እነዚህም የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት (Internal Self Determination) እና የመገንጠል መብት (External Self Determination) ናቸው፡፡ አንድ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ብሔር ወይም ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ (ምንም እንኳን የሶስቱን ቃላቶች ልዩነቶች ፓርቲው ባያመለክትም) የመጀመሪያው መብቱ ካልተከበረለት ሁለተኛውን መብት እንዲጠቀምበት መፍቀድ ዋነኛ የመፍትሄው አካል ነው፤ ይሄም ሕዝበች በፍቃዳቸውና በፍላጎታቸው የፌደሬሽኑ አካል እንዲሆኑ አስችሏቸዋል›› በማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር ንግግር ተችዎች ሲተቹ፤ ለሶማሌ ሕዝብ ተወካዮች የተሰጠው ‹እስኪ ቆይታችሁ በስርዓቱ ችግር ከደረሰባችሁ መገንጠል ትችላላችሁ› የሚል መልስ ለምን ለኤርትራስ አልቀረበላትም? እንዲሁም ዛሬ እንደ ሶማሌ ባሉ ክልሎች ብዙ የመገንጠልን ዓላማ ያነገቡ ፓርቲዎች ‹እባካችሁ መብታችን እንጠቀምበት› ብለው ሲጠይቁ ለምን ያኔ ቃል እንደተገባላቸው መብቱን ወደ መሬት አልወረደላቸውም? በማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል ኢህአዴግ ‹‹አንቀፅ 39 ላይ ሁለት መሰረታዊ መብቶች አሉ እነዚህም የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት (Internal Self Determination) እና የመገንጠል መብት (External Self Determination) ናቸው፡፡ አንድ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ‹ብሔር› ወይም ‹ብሔረሰብ› ወይም ‹ሕዝብ› የመጀመሪያው መብቱ ካልተከበረለት ሁለተኛውን መብት እንዲጠቀምበት መፍቀድ ዋነኛ የመፍትሄው አካል ነው፡፡›› ብሎ መከራከሪያውን ቢያቀርብም፤ ተችዎች በበኩላቸው በዚህ ሀሳብ ላይ ሁለት መሰረታዊ ህፀፆችን እንዳሉ ያስቀምጣሉ፡፡

አንደኛው ሕገ መንግስቱ መገንጠል መብት ምንም ቅድመ ሁኔታ የሌለው (Unconditional) ሕገ መንግስታዊ መብት እንደሆነ ያስቀምጣል እንጅ የውስጥ መብት ረገጣን (Injustice) እንደ ቅድመ ሀኔታ አያስቀምጥም፤ ይሄም

ኢህአዴግ እንደሚያስቀምጠው እንደ ዋስትና የተቀመጠ መብት ብቻ ሳይሆን፤ መረን የለቀቀ የመብት እደላ ነው ይላሉ፡፡

ሁለተኛው ፓርቲው በሚያስቀምጠው የጉዳዩ ትክክኛነት ማረጋገጫ (Justification) ላይ የሚቀርበው ትችት ደግሞ፤ ‹የፌደራላዊ ስርዓት ተገንጣይ ሀይሎችን ከአንድነት ሀይሎች ጋር አስተሳስሮ ህልውናን ማስጠበቅ ሆኖ እያለ የመገንጠል መብትን መፍቀዱ ፌደራላዊ ስርዓቱን ቅልጥሙን መስበር (A Shoot in the Foot) ነው› የሚል ነው፡፡

## ታዲያ መፈትሄውስ?


ግማሹ ሀይል የመገንጠል መብት በሕገ መንግስት መፈቀዱን ‹እነዚህ ገንጣይ-አስገንጣዮች ጉድ ሊያደርጉን እኮ ነው› እያለ፤ ይህች ‹መዘዘኛ› አንቀፅ እያለ ጉዳዩን ይፀየፈዋል፡፡ ሌላው ደግሞ ‹ዋ! በኋላ እዚሁ ጎልተናችሁ እንዳንሄድ› እያለ የመገንጠል መብትን እንደ ‹ማስፈራሪያ› በየቦታው ይመዛል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ለረጅም አመታት የመገንጠል ጥያቄን አንግበው የነበሩ ኃይላት ሳይቀር (በከፊልም ቢሆን) ‹እንነጋገር፣ እንወያይ፤ ተፈራርቶ እና ተፎካክሮ ሀገር አይገነባም› እያሉ ነው፡፡

እናም ጉዳዩን ከመፀየፍ እና እንደ ማስፈራሪያ እየመዘዙ ከመነታረክ ባለፈ፤ እነዚህ የተለያዩ ሀይላት ወደ መሀል መጥተው በጉዳዩ ላይ መነጋገራቸው መልካም ነው፡፡ መንግስትም ሕገ መንግስቱን እንደ አይነኬ ቅርስ በመቁጠር ስለ ጉዳዩ መጥፎነት ሲነሳበት ‹ያለፈውን ስርዓት ናፋቂ› እያለ፤ መብቱን የሚጠይቁ ሀይላት ሲነሱ ደግሞ ‹ጠባቦች፣ አንዴ በሕገ መንግስት የተፈታን ችግር እያነሱ የፖለቲካ ትርፍ ማጋበስ የሚፈልጉ የትርምስ ሀይላት› ብሎ መፈረጁን ትቶ፤ ‹እሽ እንነጋገር› ማለት መቻል ይኖርበታል፡፡ ያኔ የህዳር ወሩ ፌሽታ እና ደስታም እውነት ይሆናል፤ ነገር ግን እኛ የማንግባባ ከሆነና እርስ በራሳችን የምንጠቋቆም ከሆነ፣ የኛን ችግር ከእኛ ውጭ ማን ይፈታልናል? ፌሽታውስ ታህሳስ ወርን እንኳን በቅጡ ሊሻገር ይችላልን?

# GTP የት አደረሰን?

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሁለተኛው የ5 ዓመት የልማት ስልታዊ እቅድ (Plan for Accelerated Development to End Poverty, PASDEP) ጊዜ ገደብ መገባደዱን ተከትሎ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በኖቬንበር ወር 2010 ዓም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ይሁንታ ካገኘ በኋላ ነበር የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክሪያሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ሦስተኛ የ5 ዓመት ስልታዊ ዕቅድ ሆኖ መተግበር የጀመረው:: የትግበራው ዋነኛ ግብ የተጀመረው በሁለተኛው የ5 ዓመት የልማት ስልታዊ ዕቅድ አተገባበር ላይ ለተከታታይ ዓመታት ኢኮኖሚው ያስመዘገበውን ፈጣን ባለሁለት አሃዝ እድገት በማስቀጠል የኢንደስትሪው ዘርፍ የኢኮኖሚውን መሪነት ሚና ከግብርና የሚረከብበትን ቅድመ ሁኔታ ማመቻቸት ነበር::

ይህ ዕቅድ ይፋ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ ከየአቅጣጫው የተቃውሞ ትችቶችን ለማስተናገድ ተገዷል:: ዕቅዱ ላይ የሚቀርቡት ትችቶች በዋነኛነት የሚያጠነጥኑት በሁለት አንኳር ጉዳዮች ላይ የነበረ ሲሆን የመጀመሪያው የትችቶች ማጠንጠኛ የመንግስትን ቅጥ ያጣ ጉጉነት የተመለከተ ሲሆን መደገፊያ መከራከሪያውም ዕቅዱ ውስጥ እንደሚተገበሩ የታቀዱትን ተግባራትን ለመከወን የሚያስፈልገውን ያህል ገንዘብ ለማግኘት እንደሚያስቸግርና ዕቅዱ የመንግስትን የመፈፀም አቅም በእጅጉ አጋኖ ያቀረበ ነው የሚል ነበር፡፡ ሁለተኛው ትችት ሆኖ የቀረበው ደግሞ የዕቅዱ አተገባበር ከፍተኛ የሆነ የመንግስት ወጪ ስለሚፈልግ ቀድሞውንም ቢሆን ለቁጥጥር ላስቸገረው ምጥቀ ግሽበት (Hyper Inflation) በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ይሆናል ከሚለው ፍራቻ ነበር፡፡




የአንድ አመት አፈፃፀም ሪፖርቱ ይፋ ሲሆን ሁለቱም ትችቶች ተገቢ እንደነበሩ አስተጋብቷል፡፡ መጀመሪያውንም ቢሆን ለመተግበር የገንዘብ እጥረት ያጋጥመዋል የተባለለት ዕቅድ በአውሮፓ ሀገራት የተፈጠረው የምጣኔ-ሃብት ቀውስ ባስከተለው የፍላጎት መቀዛቀዝ ምክንያት ከውጭ ንግድ የምናገኘው ገቢ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተፅዕኖ ያሳደረ ሲሆን በተያያዥነትም መንግስት ከአውሮፓ አጋሮቹ አገኛለሁ ብሎ ያሰበውን ብድር በቀላሉ እንዳያገኝ እንቅፋት ሆኗል፡፡ ሌላው የገንዘብ ምንጭ የሆነው የአገር ውስጥ ተቀማጭም ቢሆን እ.አ.አ በ2010 አገሪቷ ውስጥ ባሉት የንግድ ባንኮች ከተሰበሰበው አጠቃላይ ተቀማጭ የ42.5 በመቶ አመርቂ የሚባል እድገት ቢያሳይም የዓለም ባንክ የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ጉያንግ ዚሄ ቼን እንደሚሉት ከሆነ ከአጠቃላይ ያገሪቷ ዓመታዊ ምርት (GDP) ጋር ሲነፃፀር ግን ከ5 በመቶ አካባቢ ከፍ አላደረገውም (መንግስት ይህንን ቁጥር 8.8 በመቶ ደርሷል ይላል)፡፡

ይህንንም የገንዘብ እጥረት ለመሙላት መንግስት ሊወስዳቸው ካሰባቸው እርምጃዎች አንዱ የሆነው የፕሮጀክቶችን ጥራት በመቀነስ የሚፈጁትን ወጪ የመቀነስ ስልት ሌላ ትችት ለመጋበዝ ቅርብ ነው፡፡ሌላኛው አማራጭ ቀጥተኛ የሆነ የውጭ መዋዕለ ነዋይ ፍሰት (FDI) ሲሆን ይህኛውም አማራጭ ከትችቶች የፀዳ አይደለም፡፡ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ መንግስት በስፋት እየሰራበት ያለው ሰፋፊ የእርሻ መሬት ከኢሲያ ለሚመጡ ባለሃብቶች የማከፋፈል ሂደት ዘላቂ እና የአካባቢው ነዋሪዎችን ማዕከል ያደረገ ልማት የማምጣት አቅሙ እና የባለሃብቶቹ ፍላጎት በጥርጣሬ ነው የሚታዩት፡፡ ከዚህም አልፎ እርምጃው የመሬት ወረራ (Land Grab) ነው እና ነዋሪዎችን አላግባብና ያለበቂ ካሳ ያፈናቅላል የሚሉት ክሶች ከየቦታው እየበረቱ ነው፡፡

የዋጋ ግሽበትንም በተመለከተ ለመንግስት የሚያኮራ ውጤት አልተገኘም፡፡ የዋጋ ግሽበቱ ማሻቀብ ከጀመረበት ከ6 ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ ተብለው ከተመዘገቡት የዋጋ ግሽበት መጠኖች አንዱ (40.6 በመቶ) የተመዘገበው ዕቅዱ መተግበር ከተጀመረ በኋላ ባለው ነሐሴ ወር ነበር፡፡ የዋጋ ግሽበቱን በዋነኛነት የሚመራው የእህል (ምግብ ነክ) ዋጋ መሆኑ ደግሞ ትልቁ በትር ያረፈው ከእጅ ወደ አፍ የሚኖረው ደሃ ላይ መሆኑን ይነግረናል፡፡

ያለፉት ዘጠኝ ወራት የዋጋ ግሽበት *ምንጭ፤ የኢኮኖሚስት ኢንተለጀንስ ዩኒት የ2012ሀገራዊ ሪፖርት
እንደ ዓለም አቀፍ ተቋማት ትንበያ ከሆነ በሂደት የመቀነስ አዝማሚያ እያሳየ ያለው የዋጋ ግሽበት ወደ አንድ አሃዝ የሚወርድበት ጊዜ ከ2005 የኢትዮጵያ በጀት ዓመት ሦስተኛ ሩብ አመት ቀድሞ እንደማይሆን እየገለፁ ሲሆን መንግስት በበኩሉ በመጀመሪያው እና በሁለተኛው ሩብ ዓመት የሽግግር ወቅት የዋጋ ግሽበቱ ባለ አንድ አሃዝ እንደሚሆን እየሞገተ ነው፡፡


## ትራንስፎርሜሽኑስ ምን ደረሰ?

የሀገሪቷን ኢኮኖሚ ኋላ ቀር ከሆነው ግብርና ላይ ያለውን ጥገኝነት ወደ ኢንደስትሪው ዘርፍ ለማሸጋገር የሚደረገው ጥረት ከታቀደለት ፍጥነት በላይ (በ15 በመቶ) እያደገ ቢሆንም ኢኮኖሚውን ከግብርናው ተቀብሎ ለመምራት ግን ገና ብዙ ርቀት ይቀረዋል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ሀገራችን በዕቅዱ የመጀመሪያ ዓመት አስመዘገበችው እያለ ያለውን የ11.4 በመቶ እድገት በፊት አውራሪነት የሚመራው የኢንደስትሪው የኢኮኖሚ ዘርፍ ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ዓመታዊ ምርት ጋር ሲነፃፀር ያለው ድርሻ ግን እጅግ አነስተኛ ነው (13.4 በመቶ)፡፡

## ማኅበራዊ ዘርፎችስ?

ዕቅዱ መተግበር ከተጀመረ ወዲህ የከተማ ሥራ አጥነት ከነበረበት 18.9 በመቶ ወደ 18 በመቶ የወረደ ሲሆን ይህም በከተሞች አካባቢ እየተካሄደ የሚገኘው ሰፊ የግንባታ ሥራ ውጤት ነው፡፡ መንግስት እንደሚለው ከሆነ ደግሞ የሥራ አጥ ቁጥር መቀነሱ በየከተሞቹ ለወጣቶች እያደረገው ያለው ልዩ ልዩ የማደራጀት እና የገንዘብ ድጋፎችን ተከትሎ የመጣ ውጤት ነው፡፡

የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ ወደ 392 የአሜሪካን ዶላር ማደግን ተከትሎ የፍፁም ድህነት መለኪያም እ.አ.አ 2004/5 ከነበረበት 38.7 በመቶ ወደ 29.6 በመቶ ወርዷል፡፡ ይህም ማለት ከአጠቃላይ የሀገሪቷ ዜጎች ውስጥ 29.6 በመቶ የሚሆኑት አሁንም በፍፁም ድህነት አረንቋ ውስጥ ይገኛሉ ማለት ነው፤ ለዛውም ቁጥሩን ያለጥያቄ ለማመን ከመረጥን፡፡





ሶስቱ ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች GDP ላይ ያላቸው ድርሻ *(a) — Actual *ምንጭ፤ የGTP አመታዊ ሪፖርት
ዕቅዱ መተግበር በተጀመረበት ዓመት በአጠቃላይ 20 ሚሊየን የሚጠጉ ዜጎች ትምህርት ቤት ገብተው መማር የቻሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል 43.5 በመቶው ሴቶች ናቸው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያልተጣራ ሽፋን 96.4 በመቶ የደረሰ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ዑደት ሽፋን (9-10) 41.6 በመቶ ያደገ ሲሆን በሁለተኛ ዑደት (11-12) የሴቶች ተሳትፎ ወደ 42.2 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ የመንግስት ዩንቨርሲቲዎችንም ቁጥር 32 ለማድረስ ጥረት የተደረገ ሲሆን የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎችን የመቀበል አቅም ወደ 75,348 የሁለተኛ ዲግሪና

ከዛ በላይ የሚማሩ ተማሪዎችን የመቀበል አቅም ደግሞ ወደ 6,300 አድጓል። ሪፖርቱ ስለ ትምህርት ጥራት ያለው ነገር የለም።

በጤና ረገድ የገጠር ኤክስቴንሽን ጤና ባለሙያዎች ቁጥር 34,382 የደረሰ ሲሆን ከወሊድ ጋር በተያያዘ ህመም ምክንያት ህይወታቸውን የሚያጡ እናቶች ቁጥር (Maternal Mortality Rate) ከአንድ መቶ ሺህ (እርጉዝ/የወለዱ) እናቶች መካከል 470 ደርሷል። እንደተወለዱ የሚሞቱ ህፃናት (Infant Mortality Rate) ቁጥርንም ከአንድ ሺህ አዲስ የተወለዱ ህፃናት መካከል 59 ሞት ማድረስ ተችሏል።
በጤና እና በተለይ ደግሞ በትምህርት ማዳረስ ላይ የተገኙት ውጤቶች እ.አ.አ ለ2015 በዘርፉ የታቀዱትን የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦችን (MDG) ኢትዮጵያ ልታሳካ እንደምትችል አመላካች ናቸው።

## የቁጥር ጨዋታ?

የኢትዮጵያ መንግስት ፈፀምኩ ብሎ የሚዘግባቸውን ክንውኖች በጥርጣሬ የሚመለከቱት ወገኖች ጥቂት አይደሉም። ለኢትዮጵያ መንግስት የብድርና የእርዳታ እጃቸውን የሚዘረጉትን ትልልቅ ድርጅቶች ጨምሮ አማራጭ የመረጃ ምንጭ ያላቸው ዜጎች መንግስት ሆን ብሎ በቁጥር ጨዋታ ያስመዘገባቸውን ክንውኖች የማጋነን አባዜ እንዳለበት በመጥቀስ የመንግስትን ሪፖርት የጎሪጥ ነው የሚያዩት።




የኢትዮጵያ መንግሥት እና የኢኮኖሚስት ኢንተለጀንስ ዩኒት የሚቀጥሉት ስድስት ዓመታት የኢኮኖሚ ዕድገት ትንበያ መካከል ያለው ልዩነት

# ነጻነት እና ዳቦ

በሚሰሩበት ቦታ፣ በሚኖሩበት ሰፈር ወይም አንድ ካፌ ውስጥ ቁጭ ብለው አጠገብዎ የተቀመጡ ወጣቶች ስለ እንድ ፖለቲካ ነክ ጉዳይ አንስተው ሲወያዩ ይሰማሉ እንበል፡፡ የሚወያዩበት ጉዳይ አሁን በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት የሚያስከፋ እንደሚሆን ከገመቱ፤ ወጣቶቹን ‹የቀበጡ ለት› በሚል ዕይታ ገርመም ያደርጓቸዋል ወይም እራስዎትን ከቦታው ‹አልሰማሁም› በሚል እንድምታ ያሸሻሉ አልያም የሚራራ ልብ ካልዎት ለልጆቹ ይፈሩላቸዋል — እርስዎ እንደሰሟቸው የመንግስት ሰው (‹‹ጆሮ ጠቢ››) ቢሰማቸው ሊደርስባቸው የሚችለውን እያሰቡ፡፡ ፖለቲካ ነክ አይነት ውይይቶች ላይ የሚሳተፍ የቅርብ የሆነ ሰው ካልዎት ይመክራሉ፣ ይገስፃሉ፡፡ ምክርዎትን ለማጠናከር ምሳሌ አያጡም፡፡ በሀገሪቱ ጉዳይ ያገባናል ብለው የመንግስትን ውሳኔ ተቃውመው፣ የልዩነት ሃሳባቸውን በማሰማታቸው ብቻ ለእንግልት፣ ከኢኮኖሚ ዕድሎች የመገለል እና ግፋም ሲል ለእስራት የተዳረጉ ዜጎች ብዙ ናቸው፡፡ ‹ምን አጥተሽ ነው?› ሲሉ ይጠይቋታል በሀገሪቱ ፖለቲካ ንቁ ተሳታፊ (informed active participant) የሆነች ወዳጅዎትን፡፡ ‹ስራ አለሽ፤ በልተሽ ካደርሽ እና ከእኛ ጋር ማሕበራዊ ግንኙነት እንዳታደርጊ ማንም ካልከለከለሽ፤ ምን ይሁን ብለሽ ነው ከማትችይው ጋር የምትጋፊው? ደሞ ብቻሽን ለውጥ ላታመጪ! ለኛ ጭንቀት ነው ትርፉ› በማለት አርፋ ብትቀመጥ የተሻለ መሆኑን ይነግሯታል፡፡

በነፃነት ሃሳብን የመግለፅ (ወይም የሌላ አይነት ነፃነት) እጦት እራሱን ከሚያሳይባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው ዜጎች በሀገራቸው ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆን የሚያስከፍላቸው ዋጋ ከፍተኛ እንደሆነ ተገንዝበው፥ ግላዊ የሆነ ጭቆና እስካላጋጠማቸው ድረስ የተፈቀደላቸውን ብቻ እየተናገሩ/እየፃፉ/እያደረጉ ተቆጥበው መኖርን መምረጣቸው ነው፡፡

አከራካሪውን የቅደም ተከተል ጉዳይ ወደ ጎን ትተን ነፃነትንና ብልፅግና ሁለቱም እንደሚያስፈልጉን ግልፅ ነው፡፡ የነፃነት ጫፍ የተረጋገጥባት ነገር ግን ሰዎች ከዕለት ጉርሻ እጦት በየዕለቱ የሚረግፉባት ሀገር እንዲኖረን የማንመኘውን ያክል ዜጎች ችጋር የሚባል ነገር ሲነገር ብቻ የሚሰሙባት ነገር ግን መንግስት የሚናገሩትን፣ መስራት የሚችሉትን ወይንም ለአጠቃላይ እንቅስቃሴያቸው ልኬት አበጅቶ ጥሩ ከሚቀለብ የቤት እንስሳ የማይለዩበት ሀገር እንዲኖረን ፈፅሞ አንፈልግም፡፡

## መጀመሪያ ራሴን ልቻል ወይስ መጀመሪያ ራሴን ልሁን?

ከነፃነት ይልቅ ቁሳዊ ብልፅግናን የሚያስቀድሙ ሰዎች በመከራከሪያቸው የሰው ልጆች ነፃነትን ማክበር የሚቻልበት ደረጃ ላይ ለመድረስና ዘላቂነቱንም ለማረጋገጥ ከድህነት ለመውጣት ቁልፍ የሆነውን ኢኮኖሚያዊ እድገትን ማረጋገጥ እንደ ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ፍፁም አምባ ገነናዊ ወይም ለዘብተኛ አገዛዞች (Authoritorian regimes) ዲሞክሪያሲያዊ ከሆኑና መሰረታዊ ነፃነቶችን ከሚያከብሩ ስርአቶች ይልቅ የኢኮኖሚ እድገትን ለማረጋገጥ የተሻለ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥሩ ለማሳመን ይሞክራሉ፡፡ ስለዚህም የኢኮኖሚ እድገት እስኪመጣ ድረስ የሚታጣው በሀገሪቷ የፖለቲካ ጉዳይ ላይ የመሳተፍ ነፃነት፣ የመደራጀት ነፃነት፣ የነፃና ፍትሃዊ ምርጫዎች አለመካሄድ፣ ወዘተ… ለብልፅግና የሚከፈል መስዕዋትነት ተደርጎ እንዲቆጠር ይፈልጋሉ፡፡

## አምባ ገነናዊ ስርዓት ኢኮኖሚያዊ ብልፅግናን ለማምጣት የተሻለ ምቹ ሁኔታ እንዴት ይፈጥራል?

የዚህ መከራከሪያ ፅንሰ ሐሳብ የሰው ልጆችን የሚስለው በተፈጥሮ ሰነፍ እነደሆኑ አድርጎ ነው፡፡ ሰዎች የተሻለ ውጤት ያለው ስራ የሚሰሩት በጠንካራ ቁጥጥር ስር ሆነው ሲሰሩ ብቻ ስለሆነ ይህንን ከግንዛቤ በመክተት መንግስት በዜጎቹ ላይ ክብረት የጠነከረ የስራ ሥነ-ምግባርን ለማስረፅ መስራት አለበት፡፡ የዜጎችን ነፃነት ማክበር/ማስከበር ለእድገት ‹አስፈላጊ› የሆነውን የስራ ሥነ-ምግባር ለማስረፅ መንግስት ለሚወስዳቸው እርምጃዎች እንቅፋቶች ይሆናሉ፡፡ ስለዚህም መንግሥት አስፈላጊ ብሎ ባመነበት ወቅት ሁሉ ከኪሱ እያወጣ የሚጠቀምበት ልክ የለሽ ሀይል ያስፈልገዋል፡፡

ዲሞክራሲያዊ የሆኑ ስርአቶች በአንፃሩ ልፍስፍሶች ናቸው፤ እንደብልፅግናን የሚያስቀድሙ ሰዎች መከራከሪያ ከሆነ፡፡ በዲሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ ስልጣንን ለመቆጣጠር የብዙሃኑን ድምፅ ማግኘት ግድ ስለሚል ስልጣን ላይ መውጣት/መቆየት የሚፈልግ ሃይል የብዙሃኑን ድጋፍ ለማግኘት ሲል ተወዳጅ (popular) የሆኑ ፖሊሲዎችን ይመርጣል፡፡ ለአጭር ጊዜ ህዝቡን ማስደሰት የሚችሉት እነዚህ ፖሊሲዎች የረጅም ጊዜ ውጤት ግን እድገትን

የሚያበረታታ አይደለም። ለምሳሌ አብዛኞቹ ተወዳጅ የሚባሉት ፖሊሲዎች ለዕድገት አስፈላጊ የሆነውን ሃብትን ከማከማቸት ይልቅ ፍጆታን የሚያበረታቱ ናቸው።

## ‹‹ነጻ አስተሳሰብ ለተሻለ ሕይወት!›› (ሬዲዮ ፋና)

በሌላ በኩል ነፃነት አስቀድሞ ያስፈልገናል የሚለው መከራከሪያ ማዕከል የሚያደርገው የሰው ልጆች የበለጠ ውጤታማ ስራ መስራት የሚችሉት በነፃነት ማሰብ እና መስራት ሲችሉ መሆኑን ነው። የሰው ልጆች የህልውናቸው መገለጫ የሆነውን ነፃነታቸውን ተገፍፈው ውጤታማ የሆነ ስራ ሊሰሩ አይችሉም፤ ነፃነት ከሌላቸው የተሻለ የፈጠራ ስራ ሰርተው የተሻለ ነገን ለመኖር ማበረታቻ አይኖራቸውም። ያላቸውንም ሃብትንም በአጭር ጊዜ ጥቅም በሚያስገኝላቸው ትርፋማ ስራ ላይ ብቻ ያውሉታል። ከሁሉም በላይ ግን በሚያስተዳድራቸው መንግስት ላይ አመኔታን ያጣሉ። የተሻለ ምርታማ እና የአዳዲስ ግኝቶች ፈጣሪ የሆኑ የኢኮኖሚው እድገት አቀላጣፊ ዜጎችን ለማበረታታት መሰረታዊ እና ፖለቲካዊ የሰው ልጆችን ነፃነት የሚያከብር ዲሞክራሲያዊ ስርአት ያስፈልጋል።

ፍፁም አምባ ገነናዊ ወይንም ለዘብተኛ አገዛዞች ዜጎች ለራሳቸው ከሚያውቁት ይልቅ መንግስት አስበልጦ እንደሚያቅላቸው ያምናሉ። ስለዚህም የዜጎቻቸውን ነፃነት ‹ለዜጎች ጥቅም› ሲሉ ይገድባሉ። በመጀመሪያ ዲሞክራያሲያዊ ያልሆኑ ስርአቶች በተፈጥሯቸው ለዜጎቻቸው ‹የሚሻለውን› የመምረጥ ውክልና የላቸውም/ይጎላቸዋል። ‹ለራሳቸው የማያውቁት› ዜጎች ለነፃነታቸው መነፈግ በእርግጠኝነት አጸፋዊ መልስ ይሰጣሉ — የአጸፋው ዓይነት ይለያይ እንጂ። እነዚህ አጸፋዎች ከመንግስት ጋር በምንም ጉዳይ ከአለመተባበር/ከመለገም እስከ ትጥቅ ትግል ሊደርሱ ይችላሉ። ዜጎች የሚሰጡት የአጸፋ መልስ በሀገሪቷ ባሕል፣ ታሪክ፣ ወዘተ… ይወሰናል። የትኛውም አጸፋዊ እርምጃ ታዲያ የኢኮኖሚ እድገትን በተቃራኒው አቅጣጫ ነው የሚጎትተው።

## ጥናቶችስ ምን ይላሉ?

የኢኮኖሚ እድገትን ለማረጋገጥ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን አምባ ገነናዊ አገዛዝ ያስፈልጋል እና የኢኮኖሚ እድገትን ለማረጋገጥ የሰው ልጆች ተፈጥሮ አንድ አካል የሆነው ነፃነታቸው ወሳኝ ሚና አለው በሚለው ክርክር የመጨረሻ አቋም መያዝ ለተቸገረ ሰው ፊቱን ወደ ጥናቶች ማዞር አማራጭ ነው።

አገዛዞችን በአንድ ወገን፣ ዲሞክራያሲያዊ ስርአቶችን በአንድ ወገን አስቀምጠው ሀገራትን ከድህነት ለማውጣት የትኛው ስርአት የተሻለ መዝገብ እንዳለው ለመለየት የተየ ለሌ የሆኑ በቁጥር የታጀቡ ጥናቶች ተደርገዋል። ጥናቶቹ አበክረው የሚያነሱት ጉዳይ ሁሉም አምባ ገነኖች አንድ ወጥ የሆነ ጭቆና (የነፃነት ገደብ) እንደማይፈጽሙ፡ በዛም ልክ ሁሉም ዴሞክራሲያዊ ስርአቶች ሁሉንም ዓይነት (ፖለቲካዊ፣ ግለሰባዊ፣ ወዘተ) ነፃነቶችን በእኩል ደረጃ እንደማይጠብቁ ነው። ይህንን ከግምት በመክተት ከጥናቶቹ የሚገኘው መረጃ በአጠቃላይ ሲገመገም የሚያሳየው — ሁለቱም ዓይነት የመንግስት ስርአቶች ድህነትን በማጥፋት ረገድ ያላቸው መዝገብ ቅይጥ መሆኑን ነው — ዴሞክራያሲያዊም ሆነ አምባ ገነን መንግስት ድህነትን ለማሸነፍ እርግጠኛ እና ብቸኛ መንገድ አይደለም።

## የመንግሥት ስርዓት እንደ ውጪ መጥ (exogenous)?

የአንድ ደሃ ሀገር የመንግስት ስርአት ዴሞክራያሲያዊ ወይንም አምባ ገነናዊ መሆኑ በራሱ ሀገሪቱን ከድህነት ለማላቀቅ ቀጥተኛ ተፅዕኖ የማይፈጥር ከሆነ የሚሰጠው እንድምታ ምንድን ነው? እውን የስርአቱ ዓይነት ለኢኮኖሚ እድገት ቀመር ውጪ መጥ ነው? ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ይከብዳል። በትንሹ ማለት የምንችለው ግን የዕድገት ምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች የዕድገት ቀመር ውስጥ የሚከቷቸውን ተለዋዋጮች (variables) በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የመንግስት ስርአት ተፅዕኖ ያደርግባቸዋል — መጠራጠሩ የሚመጣው የተፅዕኖው አቅጣጫ ላይ ነው።

*የአዲስ ነገሩ አብይ ተክለማሪያም ይህንኑ ጉዳይ አንስቶ ሲፅፍ የጠየቀውን ጥያቄ ደግሜ ፅሁፌን ልቋጭ፤*
*"…The question then is this: Do we still find pro-Df [Dabo First] arguments compelling even if we know that we are unable to predict the outcome of giving away our basic liberties with a reasonable degree of certainty?"*

*‹‹ጥያቄው ታዲያ ይህ ነው፤ ነጻነታችንን አሳልፈን መስጠት ስለሚያመጣው ውጤት በበቂ ደረጃ እርግጠኛ ሳንሆን ‹ዳቦ መጀመርያ› የሚለው መከራከሪያ ውሃ የሚቋጥር ሆኖ እናገኘዋለን?›› (ትርጉም የራሴ)*

ቸር እንገናኝ!

# ሳንሱር ዋጋ ያስከፍላል

ለምዕራባዊያኑ የመጨረሻ ወር በሆነው ዲሴምበር ወር መጀመርያ በሀገረ አሜሪካ ኢትዮጵያዊውን ጦማሪ እና እስክንድርነጋን ለማሰብ የተዘጋጀ መድረክ ነበር። በመድረኩ ላይ ስለ እስክንድር ነጋ የተናገሩት ተዋናይ ሊዬቭ ሽሬ የይበር እና ጸሐፊ ካርል በርንስቴይን ነበሩ። በርንስቴይን ከ40 ዓመታት በፊት የዋሽንግተን ፖስት ዘጋቢ ሆኖ በሚሠራት ወቅት ከባልደረባው ቦብ ዉድወርድ ጋር በመሆ ን በአሜሪካ መንግስት ታሪክ ትልቅ የተባለውን እና የዋተርገቱ ቅሌት በመባል ሚታወቀውን የመንግሥት ባለሥልጣናት ያሳተፈ የሙስና ቅሌት አጋልጠዋል። በነዚህ ሁለት ዘጋቢዎች ታሪካዊ ማጋለጥ ምክንያት በወቅቱ አሜሪካን በፕሬዝዳንትነት ይመሩ የነበሩት ሪቻርድ ኒክሰን ስልጣናቸውን በገዛ ፈቃዳቸው እንዲለቁ ሆኗል።

የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሳሌ ተደርጋ የምተጠቀሰው አሜሪካ በወቅቱ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ አቅም የሚያንሳት ሀገር አልነበረችም። የፖለቲካ ባህሏም (በጥቅሉ) ተጠያቂነትን የሚያበረታታ እና ሙስናን የመሰሉ ተግባራትን አፀያፊ አድርጎ የሚቆጥር ነበር/ነው ማለት ይቻላል። በዚህም ሥርዓት መሐከል ግን እንክርዳድ አይጠፋውም። እናም መደበኛው የተጠያቂነት ሥርዓት ያልደረሰበትን ማማ አራተኛው የመንግሥት ክንፍ (fourth organ of government) በመባል የሚታወቀው ሚዲያ አጋለጠው።

ነጻ የሆኑ መገናኛ ብዙኃን መኖር እና ዜጎች ሐሳባቸውን መግለጽ እና መወያየት መቻላቸው የመንግሥትን እና የባለሥልጣናቱን ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም ሕዝብን ከአደጋ ለመጠበቅ ቁልፍ መሣሪያዎች ናቸው።
እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ደሃ ሀገራት እያንዳንዱ የመንግሥት መዋለ ነዋይ ለሚፈለግለት ዓላማ መዋል አጥብቆ የሚፈለግ ነገር ነው። እውነታው ግን ይሄ አይደለም። በደሃ ሀገራት ስልጣን የሚይዙት ሰዎች/የፖለቲካ ፓርቲዎች ግን አንድም የራሳቸውን ግለሰባዊ ችግር ከሀገሪቱ ችግር በማስቀደም ወይንም በስግብግብነት አልፎ አልፎም ደግሞ ከብቃት ማነስ ሀገራቸው እጅግ አድርጋ የምትፈልገውን መዋለ ነዋይ ያባክናሉ። ይባስ ብሎም አብዛኞቹ ደሃ ሀገራት የሚመሩት ሁሉንም ነገር መቆጣጠር በሚፈልጉ እና ለምንም አይነት ነጻነት እና መብት ደንታ በማይሰጣቸው መሪዎች (totalitarian) ነው። በዚህም ምክንያት የሀገር ሃብት ሲመዘበር እና አለአግባብ ጥቅም ላይ ሲውል ለምን ብሎ የሚጠይቅ አካል አይኖርም። ካለምፍዳው እጅግ ብዙ ይሆናል።

የሕዝብ ውክልና የሌላቸው/የሚጎላቸው የድሃ ሀገራት መሪዎች ስልጣን ላይ በሕይወት እስካሉ ድረስ ለመቆየት ሀገራቸው ላለባት ምጣኔ-ሃብታዊ እና ሌሎችም ችግሮች እራሳቸውን ብቸኛ አማራጭ አድርገው ያቀርባሉ። ይህንን ለማድረግ አብዛኛዎቹ መሪዎች ሕዝብ በከፈለው ግብር የሚተዳደሩ መገናኛ ብዙኃንን የራሳቸውን ተረክ ለመፍጠር ይጠቀሙበታል። እነሱ ከሌሉ ሀገሪቷ የምትገባበትን ‹ሲኦል› ይሰብኩበታል። ይህ ብቻ አይበቃቸውም። ምንም ዓይነት የተለየ ተረክ ለሕዝብ እንዲደርስ አይፈቅዱም። የሐሳብ አህዳዊነትን በሕዝብ ላይ ለመጫን ይመቻቸው ዘንድ የበይነ-መረብ ማጥለል፣ የተለየ ሐሳብ ያላቸውን ጋዜጦች፣ መጽሔቶች ይዘጋሉ፤ ጋዜጠኞችን ያዋክባሉ፣ ያስራሉ። በዚህም የተነሳ ስልጣን ላይ ያሉት ሰዎች ሀገርን የሚጠቅም ነው ብለው የሚያወጧቸው ምጣኔ-ሀብታዊ (ሌሎችም) ፖሊሲዎችን የተለየ ምልከታ ሰጥቶ ጥቅሞቹን እና ጉድለቶቹን ተንትኖ እና ከሕዝብ ፍላጎት ጋር ያላቸውን መጣጣም አመዛዝኖ ለሕዝብ የሚያቀርብ አማራጭ እንዳይኖር ያደርጋሉ። እናም ፖሊሲዎች መታረም ከሚችሉት ህፀፆቻቸው ጋር በሰሠሯቸው ሰዎች ተደጋግመው ከተወደሱ በኋላ ወደሥራ ይገባሉ።

እነዚህ መሪዎች አንድ መሠረታዊ የሆነ የሰው ልጆች ተፈጥሮን ዘንግተዋል። ማንኛውም ጤነኛ ሰው የሚቀበለውን መረጃ እንደተሰጠው አይውጠውም። ሁልግዜም ባይሆን ባመዛኙ፣ የሰው ልጆች የሚሰጣቸውን መረጃ ማመዛዘን ይፈልጋሉ - በተለይም ድጋፍ መስጠት/አቋም ሊይዙበት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሲሆን። አማራጭ ትንተና ያጡ ዜጎ ችአንድ አንዳንዶቹ (ጥቂቶቹ) የራሳቸውን ትንተና በመስጠት አቋም ሲወስዱ አብዛኞቹ ለድጋፍም ሆነ ለተቃውሞ የሚበቃ አቋም ለመውሰድ በቂ ትንተና ለማግኘት ይቸገራሉ።በመጨረሻም ፖሊሲውን ተፈፃሚ ለማድረግ የሕዝብ ተሳትፎ/ድጋፍ አጥሮናል ብለው የሚያማርሩ የመንግሥት ድምፆችን መስማት እንጀምራለን።

## ምጣኔ ሀብት እና ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት

እ.አ.አ 1989 ድሬዝ እና ሴን የተባሉ የምጣኔ ሀብት ተመራማሪዎች ባያደረጉት ጥናት ነጻ መገናኛ ብዙኃን ባለበት ሀገር አንድም ግዜ ረሀብ ተከስቶ እንደማያውቅ ጠቁመዋል። ይህንንም ሲደግፉ ነጻ የሆነ የመረጃ ፍሰት ባለባቸው ሀገራት መንግሥታትን (ዴሞክራሲያዊ ባይሆኑም እንኳን) ከሕዝብ የሚመጣ ጫና ውስጥ ስለሚከታቸው እና

ይህንንም ለማስወገድ ሲሉ ቀድመው የሕዝብን ጥያቄ የሚመልስ እርምጃ ስለሚወስዱ እንደሆነ ይተነትናሉ። ኢሻም፣ ካፍ ማን እና ፕሪቼት የተባሉ ምሁራን እ.አ.አ 1997 ባደረጉት ጥናት መሠረት ደግሞ ግለሰባዊ ነጻነቶች (ሐሳብን የመግለፅን ጨምሮ) ማክበር በመንግስት ቁጥጥር ስር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን ምጣኔ-ሃብታዊ ውጤት (Project's Rate of return) እስከ 20 በመቶ ያክል ድረስ ይጨምረዋል። እንደነዚሁ አጥኚዎች ትንተና መሠረት ግለሰባዊ መብቶችን (ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ/የመሰብሰብ ነፃነት፣ ሐሳብን በነፃነት የመያዝ እና የመግለጽ፣ ሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ በነፃነት የመሳተፍ እና ነፃ ማኅበር ማቋቋም) አለማክበር በአኩል መጠን ከሚከሰት የዓመታዊ ምርት መቀነስ፣ የበጀት እጥረት ወይንም የወጪ እና ገቢ ንግድ ላይ ከሚያጋጥም ንዝረት ባልተናነሰ ሁኔታ በመንግስት የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ውጤታነት ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል።

እንደ በመንግሥት የሚተዳደሩ ፕሮጀክቶች ባይሆንም በግል ባለሀብቶች እና ተቋማት የሚካሄዱ ንግዶች ሐሳብን በነጻነት መግለጽ በሚቻልበት ሀገር ለገበያ የሚያቀርቧቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች የኅብረተሰቡን ደኅንነት ወይንም ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል እንዳይሆኑ ከፍ አድርገው ይጠነቀቃሉ። በግድየለሽነት ወይንም በአጭር ጊዜ ለመክበር በሚያደርጉት ሙከራ የህብረተሰቡን ደህንነት ወይንም ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል ዕቃ ወይንም አገልግሎት ቢያቀርቡ ነፃ መገናኛ ብዙሃን ሁኔታውን በማጋለጥ ህብረተሰቡን ከጉዳት ይጠብቃሉ።

## የሳንሱርዋጋ

የሐሳብ ብዝኃነትን በመቆጣጠር ሕዝብ እነሱ የሚሉትን ብቻ እየሰማ እንዲኖዳ የሚፈልጉ መንግሥታት ሐሳብን ለማፈን ብዙ ርቀት ይጓዛሉ። ሐሳብ ለማፈን ከከሚጠቀሙባቸው መንገዶች በይነ መረብን ማጥለል እና ጦማሮች እዳይከፈቱ ማገድ፣ በይነመረብን በመጠቀም ዜጎች ላይ መሰለል እና በሳተላይት የሚተላለፉ የሬድዮ እና የቴሌቪዥን ስርጭቶች ሞገዶችን መከልከል ይጠቀሳል።

የአውስትራሊያ መንግስት በ2009 ዓ.ም ሊተገብረው ያሰበው የበይነ መረብ ማጥለልን በተመለከተ ዴቪድ በርድ የተባለ ጦማሪ እንደጻፈው በበይነ መረብ የሚተላለፉ መረጃዎችን ለማጥለል ጥቅም ላይ የሚውሉት ቴክኖሎጂዎች የበይነ መረብ አገልግሎት ፍጥነትን ከ2 በመቶ እስከ 70 በመቶ ይቀንሳሉ። የማጥለል ሥራውን ‹በውጤታማነት የሚያከናውኑት› ቴክኖሎጂዎች ደግሞ ፍጥነቱን በደንብ የሚቀንሱት ናቸው።

ባሳለፍነው ነሐሴ ወር ደግሞ ኒውዮርክ ታይምስ አንድዜና ለኢትዮጵያዊያን ይዞልን ወጥቶ ነበር። ፊንፊሸር የተባለ በይነ መረብን በመጠቀም ዜጎች ላይ ስለላ ለማድረግ የሚያስችል የረቀቀ ቴክኖሎጂን እንደሚጠቀሙ ከታወቁት 10 ሀገራት አንዷ ሀገራችን መሆኗን። እንደዘገባው ቴክኖሎጂውን ለመግዛት ከ350ሺህ በላይ የአሜሪካን ዶላር ወጪ ማድረግ ይጠይቃል። ቁጥር አንድ ጠላቷ ድህነት ለሆነ ሀገር ሕገ-መንግሥቱን ጥሶ ዜጎች ላይ ለመሰለል ይህን ያህል ወጪ ማውጣት እውነትም አሀዳዊ ተረክ ለመፍጠር ምን ያህል ርቀት እንደሚኬድ ማሳያ ነው።

በሳተላይት የሚተላለፉትን ሬዲዮ እና የቴልቪዥን ስርጭትን ለመደገፍ ምን ያህል የተወሳሰበ ቴክኖሎጂ እንደሚያስፈልግ እና እሱም ምን ያህል ወጪ እንደሚያስወጣ መገመትም ቀላል ነው።

ምንም እንኳን አከራካሪ ቢሆንም ዜጎች በነጻነት ሲያስቡ እና ሐሳባቸውን በነጻነት መግለጽ ሲችሉ አዳዲስ እና ውጤታማ የንግድ ሐሳቦች ማፍለቅ ቀላል ይሆንላቸዋል። ይህም ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት መንፈግ ከሚያስከፍሉት ቀጥተኛ ያልሆኑት ዋጋዎች ውስጥ ሊካተት ይችላል።

# ትምህርት... ወዴት ዘመም ዘመም?

በመስከረም አበራ

## ዐፄው ስለትምህርት

በሀገራችን ዘመናዊ ትምርት የተጀመረው በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ቢሆንም ከመስፋፋቱ ጋር ስማቸው በታሪክ መዛግብት በጉልህ የሚነሳው ዐፄ ኃይለሥላሴ ናቸው፡፡ ከሸዋ ፖለቲካ የስልጣን ሽኩቻ በአሸናፊነት ብቅ ያሉት መልከ ቀናው ዐፄ ኃይለሥላሴ በኋላ ላይ ራሳቸው ከሸለሙዋቸው ተማሪዎች ጋር ስልጣናቸውን ያሳጣቸው ግጭት ውስጥ ቢገቡም እስከዛው ድረስ በየጠቅላይ ግዛቱ ያሉትን ልበ ብርሀን ተማሪዎች ሰብስቦ ከማስተማር ቤተመንግሥታቸውን እስከመልቀቅ ደርሰዋል፡፡ ከዚህም ባለፈ ለራሳቸውን የትምህርት ሚኒስትርነት ኃላፊነት በመስጠት ለትምህርት ሟች መሆናቸውን አስመስክረዋል፡፡ ጥሩ ውጤት አስመዝጋቢ ተማሪዎችን ከሀገር ዳርቻ ሰብስቦ ማስተማር፤ በአካል ተገኝቶ መሸለምና በቀለም የዘለቁትን ደግሞ ባሕር ማዶ ሄደው እንዲማሩ ማድረጋቸው ለትምህርት ጥራት የሰጡትን ትኩረት ያሳያል፡፡

በልላ በኩል ዐፄው ለመምህርነት የሚታጩ ተማሪዎች ላቅ ያለ ውጤት እንዲኖራቸው ስለሚጠበቅ "በዕደ ማርያም ትምህርት ቤት" በተለየ ጥንቃቄ ይሰለጥኑ እንደነበር ጉዳዩን የሚያውቁ የሞያ ባልደረቦቼ አጫውተውኛል፡፡ የእነዚህ የዚያ የትምህርት ስርዓት ውጤት የሆኑት ሰዎች ልዩነት በቀን ተቀን የሥራ እንቅስቃሴያቸው ይታያል፡፡ በዕውቀታቸው ምጡቅ፤ በሥነ ምግባራቸው የተከበሩ እና ለሥራቸው ጠንቃቃ ባለሞያዎች ናቸው፡፡ አሁንስ አስተማሪ ለመሆን የሚሰለጥኑ ዕጩዎች ምን ይመስላሉ? በሌላ ጽሑፍ የምመለስበት ይሆናል፡፡

## የፋኖዎቹ ጥንቃቄ

"ያረጀውን ዐፄያዊ ጨቋኝ አገዛዝ በአፍጢሙ ደፍቼ አዲሲቷን ኢትዮጵያ በሶሻሊዝም መዓዛ ይገፍላችሁ መጣሁ" ያለው ደርግ አገር አንድ የተማረ ሰው ለማፍራት ስንት አመት እንደሚፈጅባት ብዙም ስላልገባቸው "አንድ ጥርስ ቢኖራት በዘነዘና ተነቀሰች" እንዲሉ የነበሩትን በጣም ጥቂት ምሁራን በ72 ሰዓት የጥፋት አዋጅ እንደ ገብስ እያጨደ ሬሳውን ቢከምርም የትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ጣልቃ ልግባ ግን አላለም፡፡ የኢሠፓ ካድሬዎችም ቢሆኑ የካቲት 66 ወይም ሩሲያ ሄደው ማርክሲዝምና ሌኒንዝም እንዲጠጡና የገባቸውንም ያልገባቸውንም እንዲያነበንቡ አደረገ እንጂ የሁለተኛ ደረጃ ትምርታቸውን በቅጥ ዳር ያላደረሱ የመንደር አቢዮት ጠባቂዎችን ባለተደራራቢ ዲግሪ አላደረገም፡፡ እንግዲህ የደርግ መንግሥት ጥፋቶቹ የትዬለሌ ቢሆኑም በአፈሙዝ ወኔ የትምህርቱን ነገርም ከሆለታ ጦር ትምህርት ቤት ላስኪደው አላለምና ይህ ያስመሰግነዋል፡፡

## "ትምህርት ለሁሉም" - በገፍ

ደርጎች ከካምፕ በድንገት ካገኙት ስልጣን ሲባረሩ "በአንድ ጠመንጃ፣ በአራት ሽጉጥ እና በአንድ ቢላዋ የጀመርነው ትግል እልፍ አድርጎን እልፎችን ነፃ ልናወጣ መጣን" ያሉት የበረሀ ኮብራዎች ግን ልክ እንደ ቤተ መንግሥቱ እና መገናኛ ብዙኃኑ ሁሉ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲንም በፍጥነት መቆጣጠር እንደነበረባቸው ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ በአንድ ወቅት በቁጭት እንዲህ ብለው ነበር፡፡

*"አዲስ አበባ እንደገባን ቤተመንግሥቱን እና መገናኛ ብዙኃኑን ስንቆጣጠር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ረስተነው ነበር፡፡ ይህ ማለት ግን ዩኒቨርሲቲው የማይዳሰስ ገዳም ነው ማለት አይደለም፡፡"*

እኔ ግን አንድ ከጫካ የመጣ ቡድን እንዴት አንድ ትልቅ ዩኒቨርሲቲን ወዲያው መቆጣጠሩ አግባብ ሆኖ እንደተነገረ እስካሁን አልገባኝም፡፡

በዚህ ቁጭት ይመስላል "መሪዎቻችን" በ1987 ዓ.ም አዲሱ የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲን አውጥተው ለይስሙላ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ባለሞያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት የግማሽ ቀን ስብሰባ ያዘጋጁት፡፡ ፖሊሲው ከሚያነሳቸው ጉዳዮች አንዱ የትምህርትን ተደራሽነት ማረጋገጥ ወይም ቀለል ባለ ቋንቋ የትምህርት መስፋፋት ነው፡፡ ውጤቱም የግል የትምህርት ተቋማትን በጥቂት ዓመት ውስጥ እንደ እንጉዳይ

እንዲፈሉ አድርጓል፡፡ ሁለት ክፍል ቤት እና አንድ መጽሐፍ መደርደሪያ ያለው ሁሉ በኮሌጅ እየተሰየመ ማስታወቂያ ማስነገር ጀመረ፡፡ ለድፍን 15 ዓመት እና ከዚያ በላይ ሦስቱን የመ ሕጎች (መመዝገብ፣ መክፈል እና መውሰድ) መሟላታቸውን ብቻ እያረጋገጡ ማስመረቁን ተያያዙት፡፡ እንግዲህ የትምህርት ዘመም፣ ዘመም የጀመረው ይሄኔ ነው፡፡

ለዲፕሎማ መርሐ ግብር የተመዘገቡ ሰልጣኞች ዕድሜያቸውንና ገንዘቡን ሰጥተዋቸው መመረቂያ ዓመት ከደረሱ እዛው ኮሌጅ ዲግሪያቸውን ይቀጥላሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የተመረቁ ብዙኃኑ ተመራቂዎች የተመረቁበት መስክ የሚጠይቀውን ዕውቀት በተገቢ ሁኔታ ቀስሞ መውጣት ይቅርና ብዙ ዓመትና ገንዘብ አባክነው "ተምረው" የተመረቁበትን ትምህርት ክፍል (Department) ስም በቅጡ መጥራት የማይችሉ ሆነው አጋጥመውኛል፡፡ ከላይ የጠቀስኳቸውን የ"መ ሕጎች" እያሟሉ ተመርቀው በአገር ዕድገትና መሻሻል ላይ አሉታዊ ጥላቸውን የሚጥሉ "ባለሞያዎች" ቁጥራቸው የሚናቅ አይደለም፡፡

በቅርቡ በጣም ዘግይቶም ቢሆን የግል ትምህርት ተቋማት ከተያያዙት የትምህርት ማስረጃ ንግድ እንዲታቀቡ መለኛው ኢሕአዴግ በቀጥታም ሳይሆን በተዘዋዋሪ እነሱ ያስመረቋቸውን ምሩቃን በተለይ መምህራንን በመንግሥት መሥሪያ ቤት እንደማይቀጥር ግልጽ አደረገ፡፡ ምን ዋጋ አለው ጅብ ከሄደ የሆነው እርምጃ ለረዥም ዘመናት ዘመም ዘመም ሲል የቆየውን የትምህርት ጥራት ከውድቀት አላዳነውም፡፡ ችግሩን ጠቅለል አድርገን ስናየው አቶ መለስ ራሳቸው እንደመሰከሩት ማየትና መስማት የተሳነው የሀገራችን ሲቪል ሰርቪስና የተንቀራፈፈው ሥራ አፈፃፀም የውጤቱ ሕያው ምስክር ነው፡፡

## የረፈደበት ወደ ትምህርት ጥራት ጉዞ

ኢሕአዴግ በግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ ኃያል ክንዱን ለማሳረፍ ዳርዳር ሲል "ባለብሩህ አእምሮው" የቀድሞው ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ "ለሳቂታው" ፓርላማችን እንዲህ ብለው ነበር፡፡

*"...የግል የትምህርት ተቋማት ዲግሪና ዲፕሎማ መቸብቸቡን ተያይዘውታል፡፡ ...ዲፕሎማ ደግሞ የዲግሪ መሰላል አይደለም፡፡ ...ዲፕሎማ ያለው ሁሉ ዲግሪ መያዝ አለበት የሚል ሕግ የለም፡፡..."*

ንግግሩ ስህተት ባይኖረውም የትምህርት ጥራት ጉዳይ ከረፈደ መነሳቱና ያውም ለአቶ መለስ ይህን ያህል ዓመት ነገሩ ሳይከሰትላቸው ቆይቷል ብሎ ለማለት ይከብደኛል፡

ይህ የረፈደበት የመንግሥት እርምጃ በትምህርት ጥራት ላይ የተቃጣውን ግዙፍ ጥፋት በምንም መለኪያ የሚመልስ አይደለም፡፡ በድንገት "ነቃሁባችሁ" ብሎ ተቋማቱን በአንድ ጀንበር ከማዳከም ወይም ከማጥፋት መጀመሪያውኑ በቂ ክትትል ማድረግ እና ለጥራት ከፍተኛ ትኩረት ማድረግ ተገቢ ነበር፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደሚባለው ለትምህርት ጥራት ተገቢው ትኩረት እየተሰጠ ነው ወይ የሚለውንም ጥያቄ ለመመለስ ጥቂት ትዝብቶቼን ላካፍል፡፡

## ሽፋን የሸፈነው የጥራት ጉዳይ

ከትምህርት ጥራት ይልቅ ሽፋን ላይ እንደሚያተኩር በተደጋጋሚ የሚደመጠው ኢሕአዴግ ከአምስት ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ከ15 በላይ ዩኒቨርሲቲወችን መገንባቱንና በርካታ "ምሁራንን" ማፍራቱን ሲገልጽ በኩራት ነው፡፡ በርግጥ ኢሕአዴግ ትምህርትን ለማዳረስ ያደረገውን ጥረትና ስኬት ሳይናገሩ ማለፍ ምስጋና ቢስ ያደርጋል፡፡ በርግጥ ጥራትና ሽፋንን አብሮ ማስኬድ ትልቅ ቁርጠኝነትን የሚጠይቅና በመጠኑም ፈታኝ ቢሆንም አይቻልም ማለት ግን አይደለም፡፡

ምርጫ 97 ያስከተለውን ድንጋጤ ተከትሎ አቶ መለስ ባደረጓቸው ጉዞዎች የተለያዩ ክልልና ዞን ነዋሪዎች *"ለእከሌ ጎሳ ዩኒቨርስቲ ተሠርቶ ለኛስ?"* የሚለውን ጥያቄ ከባሕል ልብስ ስጦታ ጋር አብረው ያቀርቡ ነበር፡፡ ከማስፋፋቱ ዕቅድም ጋር ተያይዞ ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች ተከፈቱ፡፡ ዩኒቨርሲቲዎቹም ቁጥረው የተረከቧቸውን ተማሪዎች ብዙም ቁጥራቸው ሳይጎድል ማስመረቁን ተያያዙት፡፡

ዋናው ጥያቄ ግን ተማሪዎቹ በተገቢው መግቢያ መስፈርት ተለክተዋል ወይ? በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ምሩቃኑ ተገቢውን ቀለምና ስነምግባር ቀስመው ይወጣሉ ወይ? በቆይታቸውስ እውን ለቀለም ትምርታቸው ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጡ ይደረጋል ወይ? የሴት ተማሪዎች ሁኔታስ እንዴት ነዉ? የሚለው ነው፡፡ ለሁለት ዓመታት በመሰናዶ የቆዩ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት ሰባት የትምህርት ዓይነቶችን መፈተን አለባቸው ይህ ማለት ደግሞ ከ700 የሚሰላ ዉጤት የኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ እንደዉ አማካይ የማለፊያ መስፈርቱን ብንጠቀምና (ከተፈተኑት ጥያቄ ዉሰጥ 50 እንደመልሱ ቢጠበቅ እንኳ) አንድ መካከለኛ ተማሪ (ጎበዝ አልተባለም) 350 ከ 700 የሆነ ዉጤት ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ደግሞ በበፊቱ ምዘና ከ4 ነጥብ 2 ነጥብ ያመጣ ተማሪ ማለት ይሆናል፡፡ በአሁኑ ቅበላ በየዓመቱ ትንሽ ከፍ ወይም ዝቅ የማለት ነገር ቢኖርም 175 ካስመዘገቡት ጀምሮ ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት ይቻላል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ በጣም ልል የሆነ የመግቢያ መስፈርት በትምህርት ጥራት ላይ የሚያጠላውን መጥፎ ጥላ ማብራራት የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡ በርካታ የትምህርት ባለሙያዎች እንደሚስማሙበት በማንኛውም የትምህርት ደረጃ የተማሪዎች የቅበላ መስፈርት ለትምህርት ጥራት ያለው ፋይዳ የማይተካ ነው፡፡ እንግዲህ የባለሙያዎችን ምክርና የትልልቅ ዩኒቨርሲቲዎችን ተሞክሮ ቸል ማለታችን የሚታየውን የትምህርት ጥራት ወደ ውድቀት ዘመም ማለት አብዝቶ ያፋጥናል ማለት ነው፡፡

## ዋናው ካርዱ ነው

ከመጀመርያ በሰፊ ወንፊት ተጣርተው የገቡ የዘመናችን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በቆይታቸዉ በጥናት “መጨናነቅ” አይመቻቸዉም፡፡ ከዛ ይልቅ በአንድ የኢሕአዴግ አባል ወይም አጋር ድርጅት በአባልነት ተመዝግበው በየዩኒቨርሲቲዎቹ ቅጥር ጊቢ በሚደረጉ የድርጅት ጉባኤዎች ሳያሰልሱ በመገኘት አንዳንድ “ልማታዊ” ቃላትን በመሸምደድ ከቀለም ይልቅ ፖለቲካዊ “ንቃታቸዉን” ያስመሰክራሉ፡፡ የወደፊት እንጀራቸውን ወፍራም አድርጎ የሚጋግርላቸው በቀለም ትምህርት ችሎታቸዉ የሚያገኙት “A” ወይም “B” ሳይሆን በኪሳቸዉ የያዟት ቀይ ካርድ ነች፡፡ ከቅርብ ዓመት ወዲህ በተለይ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች ከዐሥራ አንደኛና ዐሥራ ሁለትኛ ክፍል ጀምሮ (ቢቻል ደግሞ ቀድሞ) የአባልነት ካርዷን በጃቸው ካላደረጉ በቀር የታማኝነታቸው መጠን ጥርጣሬ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ተማሪዎች አጫውተውኛል፡፡

## ማወቅና አለማወቅ ተደባለቁ

ይህ የተማሪዎች የወደፊት ዕጣ ፈንታ ሳይንሳዊ ግንኙነት ከሌለው የፓርቲ አባልነት ጋር ተመሳሳይ ማድረግ በማወቅና ባለማወቅ መካከል ያለውን ትልቅ ልዩነት አጥፍቶ ተማሪዎቹ የሚያስለቅስ ውጤት እያመጡ እንዲስቁ ሲያደርግ ተመልክቻለሁ፡፡ የዛሬ አለማወቃቸው የነገ ማንነታቸውን ካልወሰነው ምን ችግር አለው? ያለነው እኮ አላዋቂነት በላዩ ላይ ካድሬነት ከተደረበበት አዋቂዎችን ሳይቀር የሚያሸማቅቅ የክብር ካባ ተደርጎ በሚታሰብበት ግራ የገባው ከባቢ ውስጥ ነው፡፡

የነገሩ ግራነት የሚጎላው ኪሎ ሜትሮችን አቋርጦ ከቤተሰብ ርቆ በዋናነት ለመማርና የተሻለ ዜጋ ለመሆን የመጣ ተማሪ በውጤቱ ዝቅተኛነት ቅንጣት ሐሳብ እንዳያድርበትና ካድሬነቱን ብቻ እንዳያንድል በግልጽም በስውርም ማበረታታትና እንደ ትክክለኛ ነገር በአደባባይ የሥራና የትምህርት ዕድል የምንሰጠው ቅድሚያ ለአባሎቻችን ነው ተብሎ ሲነገር ስንሰማ ነው፡፡ መንግሥት ያልፋል ሀገርና ትውልድ ግን ቀጣይነት ያላቸው ነገሮች ስለሆኑ ቀጣዩ ትውልድ ለውጤት ቸልተኛ ከሆነ የተለየ ፍላጎትና ዓላማ ያለው መንግሥት ቢመጣ እንኳን የተጣመመውን የትውልድ አስተሳሰብ ማቃናት እንዲህ እንደ ማበላሸቱ የሚቀል አይሆንም፡፡

## የዘራነውን ስናጭድ

እንግዲህ አውቆ መገኘት ለወደፊት ስኬታማነት የተሰጠውን ቦታ ከተነጋገርን የዘመኑ ተማሪዎች የማወቅ ጉጉት ባናይባቸውና ከተማረ ሰው የሚገኙትን ትሩፋቶች (ችግር ፈቺነት፣ ሐሳብ አፍላቅነት እና አንባቢነት…) ብናጣባቸው ሊገርመን አይገባም፡፡ እንደውም የሚታየው ተቃራኒው ነው፡፡ በፊት በፊት እክሌ ስቃይ ናት/ነው እየተባለ በአድናቆት የሚነገርለት የትምህርት ብልጫ በዲጂነትና ሲዲ በማቀያየር ጥበብ አድናቆት ተተክቷል፡፡ በሀገራችን ውስጥ በዩኒቨርሲቲዎች አቅራቢያ ወይም በር ላይ miss it not የሚሉ በቀለም ያሸበረቁ የምሽት ጭፈራ ፕሮግራም መኖሩን የሚያበስሩ ማስታወቂያዎችን መለጠፍ ምንም ችግር የሌለው ነገር ነው፡፡

በዚህ ፓርቲ የሚታደሙ ሴት ተማሪዎች የሴተኛ አዳሪ እህቶቻችንን "የሥራ ልብስ" ዓይነት እራፊ ጨርቅ ጣል አድርገው ታክሲ (ባጃጅ) ሲጠብቁ ማየት ሕሊና ላለው ልብ ይነካል፡፡ ይህ ሁሉ ለምን ሆነ ስንል ዞሮ ዞሮ የሚወስደን ምንም ባይማሩም እንኳን "ያችን ነገር" ከያዙ መመረቅ ብሎም መቀጠር ካልሆነም መደራጀት ይቻላልና፡፡

ስለ ትምህርት ጥራት መዛመም ተነስቶ ሲቪል ሰርቪስን ዩኒቨርሲቲን አለማንሳት "ግንጥል ጌጥ" ይሆንብኛል፡፡ የትምህርት ጥራቱን ዘመም ዘመም በፈረስ ጉልበት ወደ ውድቀት እየገፋ ያለው የኮተቤው ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በዚህ ዝነኝነቱ "የእንትን ማምረቻ" በሚል ቅጽል ስሙም ይታወሳል፡፡ የመግቢያ መስፈርቱ፣ የስልጠና ጊዜው በቅጥ የማይታወቀው ይህ ኮሌጅ ወደ ዩኒቨርሲቲነት ከማደግ አልፎ የመጨረሻውን የትምህርት ደረጃ (ዶክትሬት ዲግሪ) እያሰለጠነ ይገኛል፡፡ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ትክክለኛ ሥራው መሆን የነበረበት ሥራ ላይ ያሉ የመንግሥት ሠራተኞችን ጉድለታቸውን ለመሙላት አጫጭር ስልጠና መስጠት ነበር፡፡ በሲቪል ሰርቪስ ዲግሪ ለመያዝ የቸኮሉ ካድሬዎች ብዙ ሳይጨነቁ ከአዋቂዎች ተርታ ይሰለፋሉ፡፡

## ኧረ!... መላ... መላ...

አብዛኞቹ የሥነ-ትምህርት ጠበብት እንደሚስማሙበት የትምህርት ሽፋንንና ጥራትን ያለ እንከን አብሮ ማስኬድ ያስቸግራል፡፡ በመሆኑም የትምህርት ጥራትን ለመታደግ ተደራሽነቱን ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ መከወንን እንደ አማራጭ ይመክራሉ፡፡ እንደሚታወቀው የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ማግኘት የሁሉም ሰብአዊ ፍጡር መብት በመሆኑ በዚህ የትምህርት ደረጃ ላይ ለትምህርት ሽፋን /ተደራሽነት/ ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው፡፡

ከሁሉ አስቀድሞ ፖሊሲ የመቅረጽ ሥራ ለባለ ሞያዎቹ መተው ያለበት ሥራ መሆኑን መንግሥት ሊገነዘበው ይገባል፡፡ ፖለቲከኞች ፖሊሲውን ቀርጸው ባለሞያዎች ሁሉ ነገር ካለቀ በኂላ ለይስሙላ አይተውት ነበር እንዲባል ብቻ የሚደረግ መሆን የለበትም፡፡

የሀገራችን ትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ብዙ ትችቶችን ያስተናገደ ቢሆንም መንግሥት ትችቶችን እንደ መልካም ግብኣት ተቀበቀሎ ከማስተካከል ይልቅ ትክክለኛነቱን በእሰጣ-ገባ መልክ ማስረዳት ይቀናዋል፡፡ የጥራት ችግርን ለመፍታትም ከፖሊሲ ክለሳ ብንነሳ ጥሩ ውጤት ማምጣት ይቻላል፡፡

ከፖሊሲ እርማት በመቀጠል መደረግ ይገባል የምለው ጉዳይ የትምህርት ተቋማት ከፖለቲካ ተፅኖ ማላቀቅ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶች (ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ጨምሮ) በግልፅም ሆነ በስውር የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ገዥ አካል ፖለቲካዊ አጀንዳ ማስፈፀሚያ መሆን የለባቸውም፡፡

የትምህርት አመራሮችን የመሾምና የመሻር ሥልጣኑም መሰጠት ያለበት አብረዋቸው ለሚሠሩ መምህራን መሆን ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም ከላይ ካለው መንግሥታዊ አካል ይልቅ መምህራኑ ማን ከማን የተሻለ የአመራር ሰጭነት ክኅሎት እንዳለው ስለሚያውቁ ትክክለኛውን ሰው በትክክለኛ ቦታ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ በትክክለኛ ሰው የሚመሩ ተቋማት ደግሞ የተሻለ ውጤት እንደሚያመጡ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡

በተጨማሪም የተሻለ እውቀትና ልምድ ያላቸውን ሰዎች ከነሱ ያነሰ ቸሎታ ባላቸው ሰዎች እንዲመሩ ማድረግ የሥራ ፍላጎታቸውን የሚቀንስ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ጥሩ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ የዩኒቨርሲቲ መምህራን መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ለመቀጠር ሲያማትሩ ይታያሉ፡፡ ይሄ የባለብዙ ዕውቀትና ልምድ መምህራን ፍልሰት በራሱ የዩኒቨርሲቲዎችን የትምህርት ጥራት የሚጎዳ ሆኖ ሳለ በነሱ ምትክ የሚገቡ ሰዎች የነሱን ጫማ ይሞላሉ ወይ የሚለው ሌላ ራስ ምታት ነው፡፡

ከዚህ የትምህርት አመራር ሰጭነት ጋር በተያያዘ ሌላ ዐበይት ጉዳይ የዩኒቨርሲቲዎች በቦርድ የመተዳደር ነገር ነው፡፡ በ1994 ዓ.ም አከባቢ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንት ዶ/ር እሸቱ ወንጨቆ ካቢኔ እና በኢሕአዴግ መካከል "አካዳሚክ ፍሪደም" ዙርያ የተነሳውን አለመግባባት ተከትሎ ኢሕአዴግ እንደ እርምት በወሰደው እርምጃ ዩኒቨርሲቲዎችን ገዥው ፓርቲ በዓይነቁራኛ መቆጣጠር ብሎም መምራት ነበር፡፡ ለዚህም ተግባራዊነት ዩኒቨርሲቲዎች በቦርድ እንዲተዳደሩና የቦርድ ሰብሳቢዎች ደግሞ በዩኒቨርሲቲዎቹ ላይ አድራጊ ፈጣሪ እንዲሆኑ ተደርገው ተሰየሙ፡፡ የቦርድ ሰብሳቢዎች ዩኒቨርሲቲው የተከፈተበት አካባቢ ተወላጅና የኢሕአዴግ ቱባ ባለሥልጣን

መሆናቸው እንደ በቂ ነገር ተደርጎ መወሰድ ደግሞ ሌላው አስቸጋሪ ጉዳይ ነው፡፡ ርዕስ መስተዳድሮች በክልል ዋና ከተማ ላሉ ዩኒቨርሲቲዎች የቦርድ ሰብሳቢዎች ናቸው፡፡ በሌሎች አነስተኛ የክልል ከተሞች ላሉ ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ሌሎች የክልሉ ተወላጆች ባለሥልጣኖች ተፈልገው የፊት አውራሪነቱ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡ የመምህራንን ደረጃን ጨምሮ ሌሎችን አንገብጋቢ ነገሮች የሚወስኑት እነዚህ ባለሥልጣናት ናቸው፡፡ የቦርድ ሰብሳቢ ባለሥልጣናቱ ትምህርት ዝግጅትና ከዩኒቨርሲቲዎች አሠራር ጋር ያላቸው ትውውቅ እና በዩኒቨርሲቲዎች ላይ የተሰጣቸው ሥልጣን ትልቅ ልዩነት ተስፋ ያስቀርጣል፡፡

ለማወቅና ለአዋቂነት እየተሰጠ ያለውን ቦታ ማስተካከል ሌላው የትምህርት ጥራትን ከውድቀት ለመታደግ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ማንኛውም ለመማርም ሆነ ተምሮ ወደ ሥራ ለመግባት የተዘጋጀ ሰው ተገቢውን ዕውቀት ቀስሞ ከወጣ በኋላ ወደ ተገቢው ሥራ ሲገባ ምሁራን በተስማሙበት መስፈርት ተለክቶ የመግባት ጉዳይ ድርድር የሌለው ብቸኛ መርህ መሆን አለበት፡፡

ሀገራችን ደሀ እንደ መሆኗ እና የትምህርት መስኩ ደግሞ በተፈጥሮ ገንዘብን የሚወስድ እንጅ እንደ ሌሎች ተቋማት አትራፊ ሆኖ ገንዘብ የሚያመጣ ባለመሆኑ ለትምህርት ሥራው ግብአት ማሟያና ተያያዥ ወጪዎች የውጭ እርዳታ ማማተሩ የሚጠበቅ ነው፡፡ እርዳታ የሚሰጡ ሀገራት ደግም ገንዘባቸውን ሲያወጡ የትምህርት ፖሊሲውን አፈፃፀሙን በራሳቸው ፍላጎት እንቃኝ መፈለጋቸው አይቀሬ ነው (ሰባ ሰላሳ ኮታን ያስታውሷል)፡፡ በሀገር ተጨባጭ ሁኔታና በለጋሽ አገራት ፍላጎት መሐል ያለውን ሰፊ ልዩነት የማጣጣምን ትልቅ ዲፕሎማሲያዊ ጥበብ የሚጠይቅ አጣብቂኝም ነው፡፡ ስለዚህም በትምህርት ሚኒስተርና ሚኒስተር ዴኤታነት የሚቀመጡ ሰዎችን ከምን ብሔረሰብ ናቸው ከማለት ይልቅ ምን የተመዘገበ አጥጋቢ የዲፕሎማሲ ሥራ ሰርተዋል፣ ወደፊትስ ምን ለመሥራት የሚያበቃ የተፈተሸ አቅም አላቸው መባል ያለበት ይመስለኛል፡፡ ከነባራዊው ሁኔታ የምንረዳው ግን የትምህርት ሚኒስተርነት በአንድ ብሔረሰብ ተወላጆች ላይ የወረደ ዛር ይመስል ለአንድ ብሔር የሚሰጥ ሹመት ነው፡፡ የትምህርት ተደራሽነትን ከማረጋገጥ ተግባር ጋር በሁሉም ደረጃ ያሉ የትምህርት ተቋማት ምን ዓይነት ስብእና ያለው ዜጋ እያፈሩ ነውየሚለው ነገር ላይም ትኩረት አድርጎ መሥራት ተገቢ ነው፡፡

# የትምህርት ጥራት ነገር (ክፍል አንድ)

በመልማት ላይ ያሉ ሀገራት ካላቸው የመዋለ-ነዋይ ውስንነት አንፃር መንግስቶቻቸው የትኛው መስክ እና የትኛው ስራ ቀድሞ መከናወን እንዳለበት ለመወሰን አስቸጋሪ የሆነ አጣብቂኝ ያጋጥማቸዋል፡፡ ድህነትን ለማሸነፍ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ከፍተኛ እና ፈጣን ውጤት የሚያስመዘገቡት መስኮች እና ተግባራት ወይንም ደግሞ ከሌሎች መስኮችና ተግባራት ይልቅ አንገብጋቢ ለሆኑት ችግሮች መፍትሄ መስጠት  የሚችሉት የመዋለ-ነዋይ ፍሰት ከሚደረግባቸው ተግባራት የመጀመርያውን ረድፍ ያገኛሉ፡፡ ብዙዎቹ ተግባራት ግን አይጠቅሙም ወይንም አያስፈልጉም ከሚል መነሻ ሳይሆን ድሀ ሀገራት በሚለዩባቸው የአቅም ውስንነት ብቻ ሳይተገበሩ ይቀራሉ፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ደሀ ናት፡፡ ከፍተኛ የሆነ የመዋለ-ነዋይ ውስንነት፣ ቢሰራ ህዝቡን ይጠቅማል ብሎ መንግስት የሚያስባቸውን ተግባራትን እውን እንዳያደርግ ማፈናፈኛ ያሳጡታል፡፡ (በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ከዚህም በላይ በብልሹ አሰራር እና በሙስና ምክንያት ሀገሪቱ እጅግ አድርጋ የምትፈልገው ነዋይ ያለ አግባብ ይባክናል፡፡) የኢትዮጵያ መንግስትን የአቅም እጦት አጣብቂኝ ውስጥ ከሚከተው ተግባራት መካከል የትምህርት ጥራት ከተደራሽነት ጋር እኩል ማራመድ አለመቻሉ ይጠቀሳል፡፡ በርግጥ ለትምህርት ጥራት መጓደል ሌሎች አያሌ ምክንያቶችን መደርደር ይቻላል፡፡ ነገር ግን የአቅም ውስንነት ትልቅ ሚና እንዳለው የማይካድ ነው፡፡

ዜጎች ለሀገራቸው ዕድገት ጉልበታቸውን፣ ገንዘባቸውን እና ዕውቀታቸውን በመጠቀም የየራሳቸውን አስተዋፅዎ ያደርጋሉ፡፡ የላቀ ዕውቀት ባለቤት የሆኑ ዜጎች የበዙባት ሀገር ከድህነት ለመላቀቅ መንገዱ እጅግ የቀለለ ይሆንላታል፡፡ ዜጎቿ ዕውቀታቸውን በመጠቀም ከድህነት የምትወጣበትን ውጤታማ መንገድ ይቀይሳሉ፣ ሀገር ተረካቢውን ትውልድ በሚገባ ይቀርፃሉ፡፡ የተማሩ ዜጎች የተመሰረተ ቤተሰብን መጥኖ መውለድ ስለሚሰጠው ጥቅም ለማገንዘብ ብዙ ወጪ አያስፈልገውም፡፡ በቤተሰቡ ውስጥ የሚወለዱ ህፃናትም እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ ትምህርት ቤት የመግባታቸው እድል ያልተማሩ ዜጎች በመሰረቱት ቤተሰብ ውስጥ ከተወለዱት ህፃናት አንፃር ሲገመገም የጎላ ልዩነት አለው፡፡

በአሁኑ ወቅት እድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ ከሆኑት ኢትዮጵያዊያን መካከል 30 በመቶ የሆኑት መሰረታዊ የሆነውን ዕውቀት ማንበብና መፃፍ ይችላሉ፡፡ ቀሪዎቹ ግን ጣቶቻቸውን ፊደላትን ለመከተብ እና አይኖቻቸውን ከወረቀት ላይ ተክለው ፊደል ቆጥረው መረጃ ለማግኘት አይቻላቸውም፡፡ ላቅ ያለ ዕውቀት ኖሯቸው ሀገራችን ከድህነት አረንቋ ለመውጣት በምታደርገው ሩጫ ንቁ ተሳታፊ ሆነው የጎላ አስተዋፅዎ ማድረግ የሚችሉት ዜጎች ደግሞ እጅግ በጣም ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ኢሕአዴግ መራሹ መንግስት ፈፀምኩ ብሎ ከሚኩራራባቸው ተግባራት መካከል የትምህርት ተደራሽነት ከግንባር ቀደምቶቹ መካከል ይመደባል፡፡ የተባበሩት መንግስታት የልማት መርሃ-ግብር (UNDP) እንዳወጣው ዘገባ እ.ኤ.አ በ2011 እድሜያቸው ለትምህርት ከደረሱ ኢትዮጵያውያን ህፃናት መካከል 82 በመቶ የሚሆኑት የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ዕድል አግኝተዋል (እ.ኤ.አ በ1990 ይህ ሽፋን ከ30 በመቶ አይበልጥም ነበር)፡፡ ለዚህም የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ሽፋን እምርታ ትልቁን አስተዋፅዖ ያደረገው እ.ኤ.አ በ2011 በሀገሪቷ የሚገኙት አጠቃላይ የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከአስር አመት በፊት ከነበሩበት ቁጥር ከእጥፍ በላይ በልጠው ማደጋቸው ነው፡፡

ምንም እንኳን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቁጥር እና ይህንንም ተከትሎ በየዓመቱ ወደ ትምህርት ቤት የሚገቡት ህፃናት ቁጥር በእጅጉ ቢጨምርም፤ ሁሉም ህፃናት የጀመሩትን ትምህርት አይጨርሱም፡፡ ደግነት እና አሰፋ የተባሉ የምጣኔ-ሃብት ባለሙያዎች በሀገር ውስጥ ፍልሰት እና የህፃናት ትምህርትን ግንኙነት ባጠኑበት ምርምራቸው፣ በገጠር የሀገሪቱ ክፍሎች ትምህርት ከጀመሩ አምስት ህፃናት መካከል አንዱ የትምህርት አመቱ ሳይጠናቀቅ ትምህርቱን እንደሚያቋርጥ ጠቁመዋል፡፡ የመጀመርያ ደረጃ ሁለቱን ዑደት አጠናቀው ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገቡት ተማሪዎች ቁጥርም ከዕድሜ እኩዮቻቸው ጋር ሲነፃፀር 34 በመቶ ብቻ ናቸው፡፡ ይኸው ቁጥር ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚገቡት ተማሪዎች ከተሰላ ወደ 4 በመቶ ብቻ ዝቅ ይላል፡፡

ኢትዮጵያ፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት ከ 2000/01- 2010/11 (እ.ኤ.አ)

| ክልሎች | 2000/01 | 2001/02 | 2002/03 | 2003/04 | 2004/05 | 2005/06 | 2006/07 | 2007/08 | 2008/09 | 2009/10 | 2010/11 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | 888 | 926 | 967 | 1050 | 1232 | 1479 | 1654 | 1776 | 1906 | 1,955 | 1978 |
| አፋር | 131 | 142 | 156 | 187 | 205 | 266 | 278 | 287 | 347 | 366 | 408 |
| አማራ | 2,928 | 2,975 | 3011 | 3157 | 4059 | 4969 | 5175 | 5682 | 6233 | 6610 | 7184 |
| ኦሮሚያ | 4,468 | 4,592 | 4758 | 5043 | 6466 | 7488 | 7952 | 9325 | 10083 | 10,742 | 11381 |
| ሶማልያ | 250 | 272 | 301 | 301 | 715 | 713 | 713 | 713 | 713 | 855 | 751 |
| ቤኒሻንጉል | 285 | 275 | 275 | 299 | 312 | 315 | 324 | 336 | 345 | 365 | 389 |
| ደ/ህዝቦች | 2,305 | 2,352 | 2426 | 2539 | 2866 | 3422 | 3715 | 4241 | 4560 | 4,956 | 5143 |
| ጋምቤላ | 136 | 143 | 149 | 155 | 162 | 163 | 182 | 180 | 180 | 205 | 215 |
| ሐረሪ | 46 | 48 | 48 | 49 | 50 | 52 | 56 | 59 | 52 | 58 | 61 |
| አዲስ አበባ | 287 | 303 | 313 | 329 | 367 | 465 | 519 | 655 | 688 | 723 | 728 |
| ድሬ ደዋ | 56 | 61 | 67 | 72 | 79 | 80 | 92 | 100 | 105 | 116 | 111 |
| Total | 11,780 | 12,089 | 12,471 | 13,181 | 16,513 | 19,412 | 20,660 | 23,354 | 25,212 | 26,951 | 28,349 |

*ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ዓመታዊ የመረጃ ቋት*

የኢትዮጵያ የትምህርት ችግር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ሁለተኛ እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚገቡት ተማሪዎች ቁጥር አናሳ መሆን ብቻ አይደለም፡፡ በተደጋጋሚ የሚነሳው እና መንግስትም የሚያምንበት የጥራት ችግር ሌላኛው ዋነኛው ለዜጎች እውቀት ማግኘት እንቅፋት ነው፡፡

ሌጋተም የተሰኘ ተቋም የ110 ሀገራት አጠቃላይ ሀብት ገምግሞ ባወዳደረበት ዘገባው በትምህርት ጥራት እና ሽፋን ኢትዮጵያን ከ110ሩ ሀገራት 107ኛ አድርጓታል፡፡ እንደ ዋቢነትም፤ 48 በመቶ ኢትዮጵያዊያን ብቻ ልጆቻቸው እያገኙ ባሉት ትምህርት እንደሚረኩ ጠቅሷል - ዘገባው፡፡ የአለም ባንክ የኢትዮጵያ እና የሱዳን ዳይሬክተር ሆነው ለ4 ዓመታት ያገለገሉት ጃፓናዊው ኬን ኦሃሺ የአገልግሎት ዘመናቸው መጠናቀቅን ተከትሎ በእንግሊዘኛ ቋንቋ በሚታተመው ፎርቹን ጋዜጣ ላይ ካሳተሙዋቸው ተከታታይ ፅሑፎች በአንዱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥራትን በሚመለከት አስደንጋጭ ሊባል የሚችል የጥናት ውጤት ጠቅሰው ነበር፡፡ የአለም ባንክ፣ የኢፌዴሪ ትምህርት ሚንስቴር እና ሌሎች ትምህርት ላይ የሚሰሩ ተቋማት በ9 ክልሎች በሚገኙ 338 የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ 13ሺ ህፃናት ላይ ባካሄዱት ጥናት ከተካተቱት የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በአንድ ደቂቃ ውስጥ 60 ቃላት ያሉበት አረፍተ ነገር ማንበብ የቻሉት ተማሪዎች መጠን (አለም አቀፍ መለኪያ ነው) ከ10 በመቶ አይበልጥም (በ8ቱ ክልሎች ከአዲስ አበባ 14.5 በመቶ በስተቀር)፡፡ ይበልጥ የሚያሸማቅቀው የጥናቱ ውጤት ከ60 ቃላት ውስጥ አንዱንም በትክክል ማንበብ ያልቻሉት ህፃናት መጠን 34 በመቶ መሆኑን ይናገራል፡፡

የንባብ ክህሎት ለተማሪዎች ያለው ፋይዳ አሌ አይባልም፡፡ ተማሪዎች መምህር የሚሰጠውን ማስታወሻ እና የመማሪያ መፃህፍትን አንብበው መረዳት ካልቻሉ ማግኘት የሚገባቸውን ዕውቀት አግኝተዋል ማለት ያዳግታል፡፡ ትምህርት አህዱ ባሉበት የመጀመርያ አመታት መደናበር የጀመሩት ተማሪዎች ከፍ ሲሉ የትምህርት ፍላጎት ኖሯቸው ንቁ እና ትምህርትን የሚወዱ ይሆናሉ ማለት ከመልካም ምኞት ማለፍ አይችልም፡፡

ኬን በፅሁፋቸው ከጠቀሷቸው ሌሎች አንገብጋቢ ጉዳዮች መካከል የተማሪዎች ‹‹አልገባኝም›› ብሎ ለመጠየቅ አለድፈርን ነው፡፡ አስቡት፤ ህፃናቱ በማንበብ ክህሎት ማጣት ምክንያት ግልፅ ያልሆነላቸውን ፍሬ ሃሳብ እንኳን ለመጠየቅ አይደፍሩም፣ አይበረታቱም፡፡ ይህ በርግጥ የህብረተሰቡ ልጆችን የሚያሳድግበት መንገድ ግልጽ ውጤት ነው፡፡ ይህም የትምህርት ሥርዓቱ ማነቆዎች በተወሰነ ደረጃ ከመንግስት ደጃፍ ውጭም እንዳሉ ይነግረናል፡፡

ዜጎች የተሻለ የትምህርት ዕድል ማግኘታቸው ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ ብዛት ያላቸው በመስኩ የተደረጉ የምርምር ውጤቶች እንደሚጠቁሙት ልጆች ትምህርት ቤት በሚቆዩበት ዓመታት እና በህይወት ዘመናቸው በሚያገኙት ገቢ ተያይዞም ለሀገራቸው ምጣኔ ሃብት በሚያደርጉት አስተዋፅዎ መካከል ቀጥተኛ ግኑኑነት አለ፡፡ ነገር ግን በዚያው ልክ ትምህርት ቤት የሚውሉት ህፃናት ዕውቀት እና ክህሎት እያዳበሩ ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ያስፈልገዋል፡፡ ይህንን ለመፈተሽ እንደ ‹‹Program for International Students Achievement›› እና ‹‹Trends in International Mathematics and Science Study››ን የመሳሰሉ አለም-ዓቀፍ መለኪያዎች ቢኖሩም ለኢትዮጵያ ምዘና ማግኘት አይቻልም፡፡

በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት ላይ ላሉት ችግሮች፤ የተማሪ አስተማሪ እና የመማሪያ መጽሐፍ ጥምርታ እጥረት እና ኢትዮጵያዊ መምህራን በስራ ሁኔታ እና በሚከፈላቸው ደሞዝ ደስተኛ አለመሆን እና የብቃት ማነስ በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

በኢትዮጵያ የቀን ቀመር 2003 ዓ.ም የተማሪ አሰተማሪ ጥምርታ ለሃምሳ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች አንድ አስተማሪ ደርሷል፡፡ አንድ አስተማሪ ሃምሳ አንድ ተማሪዎች የሚሰጠውን ትምህርት እየተከታተሉት እንደሆነ ብሎም እንደገባቸው መከታተል ይጠበቅበታል ማለት ነው፡፡ እንኳን ነብስ ያላወቁ ሃምሳ አንድ ልጆችን ይቅርና ነብስ ያወቁትን አዋቂዎች እንኳን በአግባቡ መከታተል ምን ያህል እንደሚከብድ ለማናችንም ግልፅ ነው፡፡ ክትትሉን የሚሰጡት አስተማሪዎች ደግሞ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ላይ እና ብሎም የሚሰጡት ትምህርት ይዘት ላይ የዕውቀት እጥረት ሲኖርባቸው ችግሩን ያባብሰዋል፡፡

የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ለ2003 ዓ.ም ባወጣው ዘገባ በመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ ዑደት ከሚያስተምሩት መምህራን መካከል የብቃት ማረጋገጫ ያገኙት 20.1 በመቶ ብቻ ናቸው፡፡ ይህ ቁጥር ለሁለተኛው ዑደት ሲሰላ 83.33 በመቶ ይደርሳል፡፡

**ኢትዮጵያ፡ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ አስተማሪ ጥምርታ 2003 ዓ.ም (በአማካኝ ለአንድ አስተማሪ የሚመደቡ ተማሪዎች ብዛት)**

| | ትግራይ | አፋር | አማራ | ኦሮሚያ | ሶማሌ | ቤንሻንጉል | ደቡብ | ጋምቤላ | ሐረሪ | አዲስ አበባ | ድሬ ደዋ | ሀገራዊ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የመጀመሪያ ዑደት (1-4) | 44 | 48 | 48 | 68 | 63 | 44 | 64 | 43 | 27 | 23 | 28 | **57** |
| ሁለተኛ ዑደት (5-8) | 39 | 34 | 40 | 45 | 74 | 37 | 51 | 32 | 25 | 23 | 27 | **45** |

*ምንጭ፡- የኢፌደሪ ትምህርት ሚኒስቴር አመታዊ ስታትስቲክስ*

የመምራን በስራ ሁኔታ እና በሚከፈላቸው ደሞዝ ደስተኛ አለመሆን አኻዝ ተጠቅሶ ምስክር የሚቀርብለት ጉዳይ አይደለም፡፡ እነዚህን ህይወታቸውን ማሸነፍ የሚከብዳቸው መምህራን ማስተማርን ከዕለት ጉርሻቸው ማግኛ በላይ የትውልድ መቅረጭያ መሆኑን ተገንዝበው አስፈላጊውን መስዕዋትነት እንዲከፍሉ መጠበቅ ከባድ ነው፡፡

የሁለተኛ ደረጃ እና የከፍተኛ ትምህት ችግሮችንና ላነሳኋቸው ችግሮች መፍትሄ የምላቸውን ጨምሬ በሌላ ጽሑፍ እመለሳለሁ፡፡

# የትምህርት ጥራት ነገር (ክፍል ኹለት)

በክፍል አንድ ጽሑፌ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጋር በተያያዘ ለትምህርት ጥራት ችግር መንስኤ ይሆናሉ ያልኳቸውን መዳሰሴ ይታወሳል። ያኔ ቃል በገባሁት መሠረት ሁለተኛው ክፍል በሁለተኛ ደረጃና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የትምህርት ጥራቱን የሚገዳደሩትን ችግሮች በወፍ በረር አስቃኛችኋለሁ።

የኢትዮጵያ መንግስት ለትምህርት መስክ እየሰጠ ያለውን ትኩረት ማሳያ የሚሆነው ሌላው መረጃ መስኩ በየዓመቱ ከአጠቃላይ የመንግስት በጀት የሚወስደው ድርሻ እያደገ መምጣት ነው። እ.አ.አ በ2003 ዓ.ም 14.5 በመቶ የነበረው ድርሻ በ2010 ዓ.ም 18.8 በመቶ መድረስ ችሏል። ከመንግስት በጀት ላይ የአንበሳውን ድርሻ ለመውሰድ ከትምህርት ጋር እየተገዳደረ የሚገኘው የጤና ዘርፍ ብቻ ነው። በአጠቃላይ ለትምህርት ዘርፍ ከሚውለው በጀት 23.1 በመቶ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚውል ነው።

ኢትዮጵያ፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት ከ 2000/01-2010/11 (እ.ኤ.አ)

| ክልሎች | 2000/ 2001 | 2001/ 2002 | 2002/ 2003 | 2003/ 2004 | 2004/ 2005 | 2005/ 2006 | 2006/ 2007 | 2007/ 2008 | 2008/ 2009 | 2009/ 2010 | 2010/ 2011 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | 37 | 41 | 47 | 42 | 54 | 59 | 78 | 86 | 97 | 109 | 123 |
| አፋር | 6 | 7 | 7 | 7 | 8 | 10 | 10 | 12 | 9 | 13 | 14 |
| አማራ | 81 | 85 | 88 | 102 | 127 | 159 | 188 | 204 | 235 | 262 | 288 |
| ኦሮሚያ | 133 | 139 | 156 | 198 | 263 | 313 | 334 | 385 | 418 | 461 | 528 |
| ሶማልያ | 10 | 14 | 14 | 14 | 23 | 26 | 26 | 26 | 26 | 34 | 53 |
| ቤኒሻንጉል | 10 | 12 | 13 | 18 | 23 | 25 | 27 | 34 | 34 | 37 | 43 |
| ደ/ሕዝቦች | 84 | 84 | 91 | 93 | 109 | 126 | 145 | 165 | 194 | 228 | 251 |
| ጋምቤላ | 6 | 7 | 7 | 6 | 7 | 7 | 7 | 8 | 11 | 21 | 22 |
| ሐረሪ | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 7 | 5 | 8 | 9 |
| አዲስ አበባ | 49 | 58 | 57 | 21 | 78 | 96 | 123 | 145 | 153 | 166 | 168 |
| ድሬ ደዋ | 4 | 4 | 7 | 2 | 10 | 10 | 10 | 15 | 15 | 16 | 18 |
| **ድምር** | **424** | **455** | **491** | **506** | **706** | **835** | **952** | **1087** | **1197** | **1351** | **1517** |

ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ዓመታዊ የመረጃ ቋት

የዘመናችን ትምህርት ትልቁ ችግር ዓይኑን አፍጥጦ መታየት የሚጀምረው በሁለተኛ ደረጃና እና በተለይም ደግሞ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ነው። በነዚህ የትምህርት ደረጃዎች ችግሮች በቀጥታ ከትምህርት ጋር የተያያዙ መሆናቸው እየቀረ ፖለቲካዊ ይዘት እየተጎናፀፉ ይመጣሉ። የኢሕአዴግ የካድሬ እንቁላል መጣል እና የረጅም ጊዜ አሕዳዊ አገዛዝ ፍላጎት የራስ መከላከል ሥራዎች በይፋ ይጀመራሉ።

በኢትዮጵያ ባሉት 32 የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ተማሪዎች በነጻነት እንዲያስቡ አይፈለግም፣ አይፈቀድም። እንኳን ተማሪዎቹ ይቅርና መምህራኑ ጭምር በነጻነት የሚያስተምሩትን ለመምረጥ አይደፍሩም። በንድፈ-ሐሳብ ደረጃ ለተማሪዎቻቸው የሚያስተላልፉትን ዕውቀት ሀገሪቷ ላይ ካለ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ተንትኖ ለማስረዳት የሚደፍሩት ጥቂቶች ብቻ ናቸው። ክፍል ውስጥ የተናገሩት ነገር ገዥው ፓርቲን የሚነቅፍ (የማይደግፍ) ከሆነ የእንጀራ ገመዳቸው ላይ እየተራመዱ ያሉ የሚመስላቸው መምህራን አሉ። ከክፍል ውጪም በተቋማቱ አመራሮች ለሚፈፀሙ የአሰራር ስህተቶች እና በደሎች (ለምሳሌ በዘር እየተመራረጡ መሿሿምን የመሰለ) ለመተቸት እምብዛም ፈቃደኛ አይደሉም። በዚህም ድርጊታቸው ለተማሪዎቻቸው ‹‹ቀጥ ለጥ ብሎ›› የመገዛት ጥሩ ምሳሌ ይሆናሉ።

ተማሪዎች ‹‹የውጤታማነት›› መንገድ አቅጣጫ ይሰመርላቸዋል። ለትምህርታቸው የሚሰጡት ትኩረት እና ውጤታቸው እምብዛም ቢሆንም የወጣቶች ሊግ እና ማንኛውንም የመሪው ፓርቲ ተደራሽነት የሚያሳድጉ/የሚያጠናክሩ ሥራዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆን መሞገስን፣ በጓደኞቻቸው ላይ የበላይነትን እንዲያገኙ የሚያደርግ ተሰሚነት (በትምህርት ቤት ኃላፊዎች) እና ከበድ ሲልም የንግድ እና የፖለቲካ ሥራ እንዲያገኙ ይመቻችላቸዋል። ይህ ስርዓት ለተማሪዎች የሚያስተላልፈው መልዕክት ግልፅ ነው። በትምህርት ተግቶ ዕውቀት ሸምቶ ሀገሪቷን ለመጥቀም ከመታተር ይልቅ ርካሽ የፖለቲካ ተወዳጅነት ማግኘት የስኬት መንገድ አቋራጭ ሆኖ

ይቀርብላቸዋል፡፡ የመጀመርያውን ምርጫ ለመምረጥ በቂ ማነቃቂያ ስለሌለ ለትምህርት ትኩረት መስጠት ያለውን ጥቅም ተረድተው ይሻለኛል ብለው የሕይወት መስመራቸውን የሚያስተካክሉት ተማሪዎች ቁጥር ጥቂት ነው፡፡

ትንሽ ለየት ያለ እክል የሚስተዋለው (ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ) የቴክኒክ እና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት ላይ ነው፡፡ ቅርብ ሊባሉ በሚችሉ የጊዜ ልዩነቶች ተደጋጋሚ የሥልጠና ካሪኩለም እና ምዘና ዘዴ ለውጦች ተደርጎበታል - የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት መስክ፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም ይህ የትምህርት መስክ የትኩረት እጥረት ይስተዋልበት ነበር፡፡

ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው ለሚወጡት ወጣቶች ሥራ አግኝቶ እራስን መቻል ቀላል ፈተና አይደለም፡፡ በከተሞች አካባቢ ከሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ሥራ መሥራት ከሚችሉት ሰዎች 19 በመቶዎቹ የሥራ-አጥ ናቸው፡፡ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ደግሞ እ.አ.አ በ2010ዓ.ም 71,872 ተመራቂዎችን ከግቢዎቻቸው ሸኝተዋል፡፡

ያሉትን ሁሉ ችግሮች አልፈው በቂ ዕውቀት ይዘው ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጡትን ተማሪዎች ፍሬ ለመቅመስም ተጨማሪ ፈተና አለባት - ሀገራችን፡፡ ደረሱልኝ፣ ውለታዬን መለሱ ብላ ጓግታ ስትጠብቃቸው፤ ሥራ በጀመሩ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ወይንም እንደተመረቁ ወዲያውኑ ልጆቿን በስደት ትቀማለች፡፡ እ.ኤ.አ በ2006 ዓ.ም ኢትዮጵያ አሰልጥናቸው ችካጎ ውስጥ የሚኖሩ ሐኪም ኢትዮጵያውያን ቁጥር በመላው ሀገሪቷ ካሉ ሐኪሞች ቁጥር ይበልጥ ነበር፡፡

## መፍትሄውስ?

ዩኒቨርስቲዎቻችን በሁሉም መስኮች የመጠቀ ዕውቀት ይዘው የሚወጡ ተማሪዎች እንዲያመርቱ መጠበቅ ቀና አስተሳሰብ ነው፡፡ ነገር ግን ተመርቀው በተማሩበት የሥራ መስክ እንዲሰማሩ ዕድሉን የሚያገኙት ወጣቶች ጥቂት መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም፡፡ ከዩኒቨርስቲዎቻችን የሚወጡት ወጣቶች በየተማሩበት መስክ መሠረታዊ የሆነ ዕውቀት የያዙ ነገር ግን በማንኛውም ዓይነት ሥራ ለመሰማራት ዝግጁ ሆነው እንዲወጡ ነው መጠበቅ ያለብን - ከገሀዱ አንፃር፡፡ ሀገራችን አሁን ያለችበት የልማት ደረጃ የሚፈልገውም ይህንኑ ነው፡፡ ከዩኒቨርስቲዎቻችን የሚወጡት ወጣቶችን ምጡቅ ዕውቀት እንዲይዙ አስበን ለትምህርት የሚወጣውን መዋዕለ ነዋይ በሙሉ ጥራት ላይ ያተኩር የምንልበት ደረጃ ላይ አልደረስንም - ግን በእርግጠኛነት እንደርሳለን፡፡ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የትምህርት ሚኒስትር የሆኑት አቶ ደመቀ መኮንን የሀገሪቱን ትምህርት ፖሊሲ በመጥቀስ ይህንን ሐሳብ ያስረዳሉ - *‹‹... ወጣቶች በብቃት ሠልጥነው እና በቅተው በግልም ይሁን በመንግስት በየትኛውም ዘርፍ ተወዳዳሪ እና ስኬታማ የሚሆኑበትን ዕድል መፍጠር ነው - የትምህርትና ሥልጠናው ዓላማ፡፡ ስለዚህ ለተፈለገው ሥራ ብቁ መሆንንና ማድረግን (Fit for the purpose) ማዕከል ያደርጋል ማለት ነው፡፡››*

የአዲስ አበባን ዩኒቨርሲቲ በፕሬዚዳንትነት ለ7 ዓመታት የመሩት ፕሮፌሰር አንድርያስ እሸቴ *‹‹ዩኒቨርሲቲዎችን በመገንባት እና የተመራቂዎችን ቁጥር በማብዛት ላይ ብቻ ተጠምዶ የጥራትን ጉዳይ ችላ ብሏል››* ብለው መንግሥትን ለሚተቹ እንዲህ ሲሉ ይሞግታሉ፤ *‹‹የትምህርት መስፋፋት እና የትምህርት ጥራት ተሻሚ ነገሮች እንደሆኑ ማንም ያውቃል ይህን፡፡ አንዱ ሲሳካ ሌላው ሊጎተት እንደሚችል፣ ሊዳከም እንደሚችል ሁሉም ያውቃል፡፡ ያም ሆኖ ግን ... አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንግዲህ ከ50 ዓመት በላይ ነበር፡፡ ... የትምህርት ጥራቱ እንዲህ የሚደነቅ እና የሚሞገስ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ... ስለዚህ ጥራት እና መስፋፋት ኩታ ገጠም ሆኖ ይሂዱ ከተባለ ስንት ዓመት ሊፈጅብን ነው ማለት ነው የትምህርት ተቋማትን ለማስፋፋት?››* በ1997 የትምህርት ዘመን ስምንት የነበረው የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር አሁን ላይ ወደ ሠላሳ ሁለት ከፍ ብሏል (በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት የግል እና የመንግስት ተቋማት ቁጥር 148 ይደርሳል)፡፡ እነዚህ 32 ዩኒቨርሲቲዎች በየዓመቱ 420,387 የመጀመሪያ ዲግሪ እና 14,272 የድኅረ-ምረቃ ተማሪዎችን የመቀበል አቅም አላቸው፡፡ እ.አ.አ በ2010 የዩኒቨርሲቲ ትምህርት የመከታተያ ዕድሜ ላይ (20-24) የደረሱት ኢትዮጵያዊያን ቁጥር ከ8.7 ሚሊዮን በላይ ነበር፡፡ የታዳጊዎች ቁጥር መብዛት በራሱ እና የሕዝብ ብዛት ላይ በሚያሳድረው ግፊት (Demographic Inertia) የተነሳ ዩኒቨርስቲዎችን ማስፋፋት እና በአጠቃላይም ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ማዳረስ የማያቋርጥ ጥረት ያስፈልገዋል፡፡ ነገር ግን እስከ አሁን የነበረው ሙሉ በሙሉ ማለት በሚቻል ትኩረት ተሰጥቶት የነበረው ትምህርት ቤቶችን የማስፋፋት እና ቁጥራቸውን ማብዛት የተሰጠውን ትኩረት ተቋማቱን ለማጠናከር እና ተማሪዎች ማግኘት የሚገባቸውን ዕውቀት መስጠት ማስቻል ላይ ለሚሰራው ሥራ ማካፈል መጀመር አለበት፡፡

በትምህርት መስክ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ተሳትፎን ማበረታታት እንደ አማራጭ መፍትሄ መታየት ይኖርበታል፡፡ መንግስት ያለበትን የትምህርት ተደራሽነት እና ጥራትን ኩታ ገጠም አድርጎ ለመሄድ ያለበትን የአቅም ችግር ከግሉ ዘርፍ በሚመጣ የመዋዕለ-ነዋይ ፍሰት መሙላት ይቻላል፡፡ ለዚህም መንግሥት ወጥ በሆኑና የግሉ ዘርፍ ችግሩን ለመፍታት የሚያስችለው ሁኔታ የሚያመቻቹ ደንቦችን ማበጀት እና ከዘርፉ ጋርም የጎሪጥ መተያየቱን ትቶ ተቀራርቦ መሥራት አለበት፡፡ ይህንንም በማድረጉ መንግስት ሦስቱንም የትምህርት ደረጃዎች ተደራሽነትን ለማስፋፋት የሚያውለውን ወጪ ቀስ በቀስ ወደ ተቋማትን በደንብ ማደራጀት (በመጻሕፍት፣ በቤተ-ሙከራ እና በመሳሰሉት) እና የመምህራንን ቁጥር (በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ) እና ብቃት ወደማሳደግ እንዲሁም የግል ተቋማትን ወደማገዝ እና ውጤታማ ቁጥጥር ወደማድረግ ለማዞር ዕድል ይሰጠዋል፡፡

ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው የሚወጡት ወጣቶች ሥራ አጥ መሆናቸው ስለ ትምህርት ስርዓቱ ከሚናገረው ይልቅ ስለ አጠቃላይ የሀገሪቷ ምጣኔ-ሀብት የሚናገረው ይልቃል፡፡ ሀገሪቷ ውስጥ ያሉት ባለትኩስ ኃይል ወጣቶች ከየትኛውም የዕድሜ ክልል በእጅጉ በሚበልጥበት ሀገር 85 በመቶ የሚሆነውን የሥራ ኃይል መቅጠር የሚችለው የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚው ነው፡፡ ስለዚህም ኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብተው ከሰለጠኑት ልጆችዋ ማግኘት የሚገባትን ታገኝ ዘንድ የምጣኔ-ሀብት መዋቅራዊ ለውጥ ያስፈልጋታል፡፡

ለብዙ የዕድገታችን ማነቆ ለሆኑት ችግሮቻችን እንደመፍትሄ የሚነሳው የባሕል አብዮት በትምህርትም መስክ ያስፈልገናል፡፡ ማኅበረሰባችን ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጡት ወጣቶች በተለምዶ ዝቅ ተደርገው የሚታሰቡ ነገር ግን ገቢ የሚያስገኙ እና ሀብት እንዲፈጠር አስተዋፅዎ የሚያደርጉ ሥራዎችን ሲሠሩ ሲያይ ከማንቋሸሽ ይልቅ ማድነቅ እና ማበረታታት ሊቀለው ይገባል፡፡ ትንንሽ ልጆችንም ሐሳባቸውን እና ጥያቄዎቻቸውን በጨዋነት እንዲያቀርቡ ማስተማርና ማበረታታት ይገባል፡፡

ፖለቲካዊ መልክ ላላቸው የሀገራችን ትምህርት ችግሮች ለመሪዎቻችን ቅን ልቦናን ከመመኘት ውጭ ምንም ማለት አልችልም፡፡

# ስለምንስ ከምሁራን መካከል ትፈልጉኛላችሁ?!

የትምህርት ጉዞው የተጠናቀቀ ይመስላል፡፡ ተማሪዎች በምረቃ ቀን የሚለብሱት ጋወን ፣ አስመራቂ ቤተሰቦቻቸው ወደ ምረቃው ቦታ የሚገቡበት የመግቢያ ትኬት ከየትምህርት ክፍላቸው እየወሰዱ ነው፡፡ አንድ ከዚህ በፊት ያልተለመደ ተግባር ግን ይቀራል፡፡ የአንድ ሙሉ ቀን ስልጠና፡፡ ከጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት በመጡ ባለሙያዎች ከምረቃ በኋላ ሊሰማሩባቸው ስለሚችሉባቸው የስራ አይነቶች፡፡

ገነትም ከነዚህ ሰልጣኞች መካከል አንዷ ስትሆን በ3 አመት የዩንቨርስቲ ቆይታዋ Applied Biology ያጠናች ስትሆን ከተቻለ አንድ ፋርማሲ ሰራተኛ ውስጥ አለዚም መምህር እሆናለው የሚል ህልም ነበራት፡፡ በስልጠናው የሰማችው የስራ መስክ ግን አልተዋጠላትም፡፡ ተደራጅቶ የባልትና ውጤቶችን መሸጥ፣ የከተማ ግብርና ላይ መሰማራት፣ የኮብል ስቶን ማንጠፍ ስራ፣ፓርኪንግ ወ.ዘ.ተ፡፡

ይህ በ2004 ዓ.ም ተማሪዎቻቸውን ያስመረቁ የሁሉም የመንግስት ዩንቨርስቲዎች እና ተማሪዎች ሰሞነኛ ቆይታ ነው፡፡

## ትምህርት

የሰው ልጅ ሁሉን ያውቅ ዘንድ አይቻለውም ስለዚህም ስለ ክዋክብቱ መረዳቱ የበዛለት ላላወቀው እሱም ስለ ስነ ተዋልዶ እውቀቱ ከሌለው ከአዋቂው የሚቀስምበት ስርዓት ነው ትምህርት፡፡ አንድ ሰው አቃቂ ምሁር ይባል ዘንድ በሁሉም የትምህርት ዘርፎች የዕውቀት ላቂያ ይኑረው ያኔም አዋቂ ይባላል ይለናል የRenaissance ManTheory፡፡ ለዛም ይመስላል በአብርሆት ዘመን (15-18 Century) የነበሩ ምሁራን ሁሉን አቀፍ እውቀት ነበራቸው ልንል የምንችለው፡፡ የፍልስፍና፣ የሂሳብ፣ የስነ-ክዋክብት፣ የስነ-ሰብ ወ.ዘ.ተ እውቀቶችን አንድ ምሁር አቅፎ ሊይዝ ይችል ነበር፡፡

ይሄ ትክክል አይደለም ይልቅስ በህብረተሰቡ ውስጥ እምርታ ይመጣ ዘንድ የስራ ክፍፍል (Division of Labor) ወሳኝ ነው ብሎ ስኮትላንዳዊው የስነ-ምጣኔ ምሁር አዳም ስሚዝ የሀሳብ ሽግግር ካደረገ ወዲህ፡፡ እያንዳንዱ ህብረተሰቡ አካል አንድ የስራ መስክ ላይ በተለየ(Specialize) አድርጎ ጥናት ካደረገ እና ከተማረ በዘርፉ ትልቅ አስተዋፅኦ ያመጣል በሚል የትምህርት ስርዓቶቹም በዚህ ሀሳብ መቀረፅ ጀመሩ፡፡ ባጫ ምህንድስና ፣ አበበ ህግ ፣ አይዳ እርሻ ወ.ዘ.ተ እየተማሩ በያዙት ሙያ ላቂያን ማሳት ይችላሉ የሚለው የ Specialization Theory አሁን ድረስ በትምህርቱ ዘርፍ ተግባራዊ እየሆነ ነው፡፡

## ሱፍ ለባሽ ምሁር

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ትምህርት ታሪክ መቶ አመት እንኳን አልደፈነም ፡፡ የመጀመሪያው ዘመናዊ የመንግስት ትምህርት ቤት በ1908 ነው የተቋቋመው እስከ ጣልያን ወረራም ብዙ ተማሪዎችን ማስተማር አልተቻለም በአብዛኛውም ከውጭ ተምረው የመጡ ኢትዮጵያዊያን ነበሩ እንደ ምሁር የሚቆጠሩት፡፡ ከነዚህ በውጭ ተምረው የመጡ 120 ተማሪዎች ውስጥ ጣልያን በተለምዶ የሚያዚያ 28ቱ ጭፍጨፋ ተብሎ በሚጠራው ድርጊት 75 በመቶዎቹን እንደ ገደላቸው የመንግስትን ሪፖርት ጠቅሰው Mrgery Perham, *The Government of Ethiopia* ባሉት መፅ ሃፋቸው ያስረዳሉ፡፡

እንግዲህ በጣሊያን ወረራ 75 በመቶ የተማረ ሀይሏን (በነገራችን ላይ የተማረው ሀይል 75 በመቶ ማለት 90 ምሁራን ብቻ ማለት ነው) ካጣች በኋላ እስከ ንጉሱ የስልጣን ዘመን ማክተሚያ ድረስ የተማሪዎች ቁጥር (በውጭም በሀገር ውስጥም ተምረው የመጡት) በብዙ እጥፍ ጨምሯል፡፡

** አለ ከተባለ የፈረንሳይ ህግ ትምህርት ቤት ህግ ተምሮ የሀረርጌ አውራጃ አስተዳዳሪ የእልፍኝ አሽከር፣*

** Literature 4 ዓመት ሙሉ እነ ሸክስፒርን፣ እነ ሞንታኝን፣ እነ ዳንቴን እንዲያም ሲል እነ ቶልስቶይን ሲያጠና ከርሞ በንግድ ሚኒስቴር የወርሃዊ የዋጋ ጥናት ባለሙያ መሆን፣*

** የምጣኔ ሀብት ትምህርትን እንደ ውሃ ጨልጦ በበጌምድር አውራጃ የደምቢያ ወረዳ የመንግስት ሹም ወ.ዘ.ተ እየሆኑ ነበር እነዚህ እውቀትን እና አለባበስን ከአውሮፓ የቀዱ ምሁራን ወደ ስራ አለም የሚሰማሩት ፡፡*

በርግጥ አቢዮተኛ ው *ያ ትውልድምየዚህ ሱፍ ለባሽ ምሁር* አካል ነበር፡፡

## የተማረ ሁሉ ያስተምር

*ደርጉ መጣ ሁሉንም ነገር ወደ ጦር ግንባር ከማለቱ በፊት የትምህርት ዘመቻ ጀመረ ’ማሃይምነት አይነስውርነት’* ነው በሚል የሚያሽማቅቅ መፈክር የገጠሩን ህዝብ ስሙን ይፅፍ ዘንድ ፊርማ በእርሳስ ይፈርም ዘንድ አስቻለው፡፡ ነገር ግን ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወጡ ተማሪወች የተማሩትን ትምህርት የት አደረሱት ከተባለ፡ ግማሾቹ አቢዮት ጠባቂ፣ ግማሾቹ የቀበሌ ሹም ፣ ወታደር ቤትም የገቡ አሉ፡፡

ይልቁንም ደርጉ ተማሪዎችን ከነ *ኢሀአፓ ጋ*ር ’ንክኪ’ አላቸው በሚል በጥርጣሬ ነበር የሚመለከታቸው፡፡ ይባስ ብሎም ከሀገር በፊት የምን ትምህርት ብሎ በተለምዶ *‘ምሁሩ ጦር’*የሚባለውን ወታደር ከዩንቨርስቲ አፍሶ ብላቴ ጦር ማሰልጠኛ ከተተ፡፡ የተማሩት ትምህርትም አላማው ጠፋባቸው ለነዚህ ምሁር ወታደሮች፡፡

## ስለምንስ ከምሁራን መካከል ትፈልጉኛላችሁ?!

*ኢሕአዴግ* በሥልጣን ዘመኑ ከሰራቸው አመርቂ ስራዎች አንዱ ትምህርትን በነፃ ተደራሽ ለማድረግ ያደረገው ጥረት እና ያም ያመጣው ውጤት ነው፡፡ አጠቃለይ *የትምህርት ፖሊሲ* በ1986 ዓ. ም ከወጣ በኋላ ብዙ አዳዲስ ትምህርት ቤቶች ተሰርተዋል፣ የትምህርት ቤቶች የቅበላ አቅም በብዙ እጥፍ ጨምሯል፣ ከ30 በላይ የመንግስት ዩንቨርስቲዎች ተገንብተዋል፡፡

ነገር ግን የትምህርት ፖሊሲውን ሁለት ዋነኛ ተግዳሮቶች አንቀው ይዘውታል፡፡

1. የትምህርት ጥራት ጉዳይ፡

መንግሥትም እንደሚለው ዋነኛው የትምህርት ፖሊሲያችን ፈተና የጥራት መጓደል ነው፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ:

- *የዩንቨርስቲ የChemistry ምሩቅ ተማሪዎች Chemistryን Khemistry እያሉ እንደሚጽፉ ይነገራል፡፡*
- *አራቱን የሂሳብ ስሌቶች የመለየት ችግርም የምሩቃኑ ሌላው ጣጣ ነው፡፡*
- *በሶሲዮሎጅ ተመርቀው ካርል ማርክስ ሲባል እሱ ደግሞ ማነው?*ማለትም ያስደነግጣል፡፡
- *ሕግ ተምረው የCivil Right እና የCivil Code ልዩነትን አለማወቅም ይወራል*፡፡

አዎ ጥራቱ ችግር ውስጥ ነው፡፡

2. ሁለተኛው እና አዲሱ የትምህርት ፖሊሲው ችግር ሰዎች ተምረው በተማሩበት ትምህርት መስክ ሊሰሩ አለመቻላቸው ነው፡፡

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን የ2011 ዓ.ም የከተማ ስራ አጥነት 18 በመቶ እንደሆነ መረጃው ያስረዳል፡፡ ሌሎች አለማቀፍ ተቋማት ደግሞ መጠኑ ከዚህ እንደሚልቅ ይገልፃሉ፡፡

እንግዲህ ከዩንቨርስቲ የሚወጡት ምሩቃን ከነዚህ ስራ አጦች ቁጥር ላይ የሚደመሩ ናቸው፡፡ ይሄን ቁጥር ለመቀነስ ይመስላል መንግስት ሰሞኑን እንደምንሰማው ወጣቶችን በተለያዩ የጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት ተግባራት ላይ እንዲሰማሩ እያደረገ የሚገኘው፡፡

- *ችግሩ ግን አንድ ሰው Computer Science ተምሮ የኮብል ስቶን ጠረባ ላይ የመሰማራቱን ጥቅም ስናሰላስለው ነው፡፡*
- *ችግሩ ግን አንድ ወጣት በPhysics ተመርቆ በከተማ ግብርና ተግባር ላይ ሲሰማራ የተማረውን ትምህርት ተግባር ላይ እንዴት ሊያውለው ይችላል? ያልን እንደሆነ ነው፡፡*
- *ችግር የሚሆነው Afan Oromo & Literature የተማረች ወጣት በባልትና ውጤት ስራ ላይ ተሰማርታ ስናይ ነው፡፡*

ይሄ ስኬት ነው እንዴ ለመሆኑ?

*Nelson Mandela* በግለ-ታሪካቸው ላይ ስለ ትምህርት ሲናገሩ:-

*"Education is the great engine of personal development. It is through education that the daughter of a peasant can become a doctor, that a son of a mineworker can become the head of the mine, that a child of farm workers can become the president of a nation."*

አሁን ወዳለው ሀገራችን የትምህርት ውጤት ስንሄድ ማንዴላ እንደሚሉት ትምህርት የገበሬውን ልጅ ዶክተር ፣ የማዕድን ቆፋሪውን ልጅ የሀገር መሪ የሚያደርግ መሳሪያ ነው ያሉትን የትምህርት Upgrade የማድረግ ሚና Downgrade በማድረግ የተተካ ያስመስለዋል። አለዚያማ ስለ ፓለቲካል ህልዮት ሲማር የከረመ ወጣት እንዴት የብየዳ ስራ ላይ ይሰማራል?።

ገነት *‹‹ስለ ስራ አስበሽ ታውቂያለሽ?››* ተብላ ስትጠየቅ *‹‹እኔ የምማረው እናቴ ተመርቂ ስታየኝ ደስ እንዲላት ነው እንጅ ስራ መስራት አልፈልግም››* ትላለች። እንግዲያውስ ገነቶችን ከምሁራን መካከል መፈለግ ምን ሊረባ?

# የዩንቨርስቲው ምኅዳር

ከሀገራችን ዩንቨርስቲዎች በአንዱ ነው፤ ወቅቱም 1998 ዓ.ም የታህሳስ ወር መጀመሪያ ፡፡ የፈተና ወቅት እየተቃረበ በመሆኑ ተማሪዎች በየቦታው ይቻኮላሉ፡፡ አንድ አመሻሽ ላይ ግን ያልተጠበቀ ድምፅ ተሰማ፤ የጥይት ጩኸት፡፡ ከአሁን አሁን ይቆማል ብለው ቢያስቡም ተማሪዎች ጩኸቱ እየተበራከተ ሄደ፡፡ የተማሪዎች ጩኸትም ታክሎበት ጊቢው ተረበሸ፡፡ ተማሪዎች ከጊቢ ለመውጣት በየቦታው ይሯሯጣሉ፡፡ 'እድለኛ የሆኑት' ከጊቢ ለመውጣት ቻሉ፡፡ 'እድለኛ ያልሆኑት' ደግሞ በር ተዘግቶባቸው በየዶርማቸው ታግተዋል፡፡ የጩኸቱን መነሻ በተባራሪ ሲሰሙ የበለጠ ደንግጠዋል ታጋቾቹ፡፡ የጎሳ ፀብ ነበር፡፡ የአንድ ጎሳ ተማሪዎች ከሌላ ጎሳ ተማሪዎች ጋር ተጋጭተው ነው ሽብሩ የተነሳው የሚል ነበር ምክንያቱ፡፡ ለተከታታይ 3 ቀናት ከአንድ ጎሳ የመጡ ተማሪዎች ጊቢውን ተቆጣጥረው ተማሪዋች መታወቂያ እያሳዩ እንዲያልፉ በማድረግ 'ተጣላተነዋል' የሚሉትን ጎሳ ተማሪ ሲያገኙ እየደበደቡ ሰነበቱ፡፡ በመጨረሻም በፖሊስ ጣልቃ ገብነት ጉዳ ዘግይቶም ቢሆን ተረጋጋ፡፡

ይህ ከሆነ ከ6 ዓመታት በኂላ ሚያዚያ 2004 ዓ.ም በአንድ ሌላ የሀገራችን ዩንቨርሲቲ ተማሪዎች ይጮኻሉ/ይጨፍራሉ፡፡ መዝሙር የሚዘምሩም ይመስላሉ፡፡ ‹‹አሸዋ ለግንባታ፣ ጠጠር ለአርማታ›› እያሉ ያስተጋባሉ፡፡ የጩኸታቸው መነሻም በዩንቨርስቲው የሚቀርብላቸው ምግብ ጥራት የለውም፣ እንጀራው አሸዋ አለበት፣ ወጡም ጠጠር ብቻ ነው የሚል ነው፡፡ በመጨረሻም በልመና እና በፌደራል መንግስት ሃላፊዎች ጣልቃ ገብነት ጩኸታቸው ጋብ አለ፡፡

## ትምህርት ስንል

ዶክተር እጓላ ገብረ ዩሃንስ ‹‹የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ›› ባሉት መፅሃፋቸው የትምህርትን ዓለማ ሲገልፁ፡
*‹‹ትምህርት መጀመሪያ ሰብዓዊ ነው፡፡ ማለት ሰው ከሙሉ የሰውነት ማዕረግ የሚደርሰው በትምህርት ነው፡፡ ሁለተኛ ትምህርት መክሊታዊ ነው፤ ማለት ሰው በተፈጥሮው ዝንባሌ መሰረት አንድ ሀብት፤ ጥሪ፤ ወይም መክሊት አለው፤ በዚህ መክሊት መሪነት በማህበራዊ ኑሮ ውስት ተከፋፍለው ከሚገኙት ሥራዎች ሳንዱ መሠልጠን መዘጋጀት አለበት፡፡ ሦስተኛው ትምህርት አዲስ ነገር ከማወቅ ከመመራመር የእስከ አሁኑን የዕውቀት ድንበር አልፎ ለመሄድ ከመጣጣር ጋር የተያየዘ ነው፡፡››*

በማለት ነው፡፡ በአጭሩ ትምህርት ሙሉ ሰው የመሆኛ ትልቅ መሳሪያ እንደሆነ ይነግሩናል ዶክተሩ፡፡

> **‹‹ሰማኒያ በሞላ በሶስተኛ ዓመት፣**
> **ተማሪ አፈረሰው የተፈሪን ቤት፡፡››**

መደበኛ የከፍተኛ ትምህርት በሀገራችን ከተጀመረ ረጅም ጊዜ አስቆጥሯል ማለት አይቻልም፡፡ ቀዳሚዎቹ ምሩቃን አውሮፓ እና አሜሪካ በመሄድ ትምህርታቸውን ተከታትለው ይመለሱ ነበር፡፡ በሚመለሱበት ወቅት ግን ሀገራቸው ትሰለጥን ዘንድ ቅናት አብሯቸው ይገባ ነበር፡፡ ይሄን ቅናታቸውንም ለማስታገስ በሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ይጀመር ዘንድ የንጉሱን ስርዓት መወትወታቸው አልቀረም፡፡ በመጨረሻም በኢትዮጵያ የሚኖሩ ወንጌላዊ ካናዳዊያን ከቀዳማዊ ኃይለስላሴ ፈቃድ በመቀበል አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ኮሌጅን መሰረቱ፤ ከጥቂት አመታት በኂላም የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩንቨርስቲ ተከፈተ፡፡ የዩንቨርስቲው መከፈት ለብዙ ኢትዮጵያዊያን መልካም ነገር የነበረ ሲሆን፤ ለንጉሱ ስርዓት ግን አበሳንም ይዞ እንደመጣ ይታመናል፡፡

የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩንቨርስቲ የተከፈተበት ወቅት በ1953 ዓ.ም ስኢረ መንግስት ማግስት መሆኑ ተማሪዎች ንጉሱ እና ስርዓታቸው ሊደፈሩ የሚችሉ እንደሆነ የተረዱበት ጊዜም ሆነ፡፡ ይባስ ብሎም በውጭ ሀገር ትምህርታቸውን ተከታትለው የመጡ ኢትዮጵያዊያን በኮሚኒስታዊ ፀበል እየተጠመቁ ይገቡ ነበር፤ ኮሚኒዝምንም ይሰብኩ ጀመር፡፡ በነዚህ ተደራራቢ አጋጣሚዎች ያገኙት የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩንቨርስቲ ተማሪዎችም ንጉሱ ስርዓታቸውን እንዲያስተካክሉ መገፋፋት አልፎ አልፎም መተንኮስ ጀመሩ፤ እንደነ ዩሃንስ አድማሱ ያሉት ተማሪዎች ንጉሱ በተገኙበት ሳይቀር፤ ባደባባይ ስርዓቱ ይቀየር ዘንድ ያውጁ ነበር፡፡ የስርዓቱ ባለስልጣናትም ‹‹እኛው አስተምረን በገዛ እጃችን ተማሪ ያንጓጥጠን ጀመር›› እያሉ በማስተማራቸው ቁጭት ውስጥ ገብተው ይብሰለሰሉ ነበር፡፡ የሆነ ሆኖ በ1960ዎቹ ይህ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ተቃውሚ እየተጠናከረ ሄዶ የንጉሱ ስርዓት ግብዓተ መሬት ተፈፀመ፡፡

## ትግል እንደገና

‹‹መሬት ላራሹ፣ ለላብ አፍሳሹ!›› ብለው የተነሱት ተማሪዎች የንጉሱን ስርዓት ተቃውመው የተነሱባቸውን አላማዎች በቀላሉ ማሳካት አልቻሉም፡፡ ይልቅስ ተማሪው የተሰለፈትን አላማ በወታደሩ ተቀማ ቢጨንቀውም፡

*‹‹ጉድ ፈላ ዘንድሮ፣ ጉድ ፈላ ዘንድሮ፣*
*ምሁር ወደ ጫካ፣ ወቴ ወደ ቢሮ፡፡››*እያለ ሸፈተ፡፡

የወታደራዊው መንግስት ወደስልጣን መምጣት የተማሪዎቹን ህልውና በራሱ አደጋ ላይ ሊጥለው ቻለ፡፡ ከወታደራዊው መንግስት የተገኘው ትልቅ 'ስጦታ' ሊባል የሚችለው የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩንቨርስቲን ስም አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ብሎ መቀየሩ ነው፡፡ ከዛ ባለፈ ግን ግፍ እና ጭቆናው ተባብሶ ቀጥሎ ነበር ማለት እንችላለን፡፡ ግፉ የበረታባቸው ተማሪዎችም ደብተር ጥለው ጫካ ገቡ፤ ጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስትም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችም አልፎ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን በአደባባይ ያስር፤ ይረሽን ጀመር፡፡

*‹‹የተማሪ ደብተር፣ አልጠፋም ተገኝ፣*
*በየመሃል መንገድ፣ በደም እየዋኝ፡፡››*

ተብሎ እስኪተከዝ ድረስ ‹‹ዘመቻ ተማሪ ማጥፋቱን›› ወታደራዊው መንግስት ቀጥሎበት፤ በመጨረሻም ሙሉ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎቸን አፍሶ ብላቴ ማሰልጠኛ ከተታቸው፤ ወታደራዊ ስልጠና ወስደው ይዋጉ ዘንድ፡፡ ነገር ግን ይህ የብላቴ 'ምሁር ጦር' አንድ ጥይት ሳይተኩስ ወታደራዊው መንግስት ከመንበሩ ተነሳ፡፡

## 'አዲስ ስርዓት'፤ 'አዲስ ዩንቨርስቲ'

ኢሕአዴግ ስልጣን መያዙ የዩንቨርስቲዎቻችን እና ተማሪዎቻቸውን ሁናቴ መቀየሩን መታዘብ ይቻላል፡፡ ባንድ በኩል ተማሪው ከእታፈሳለሁ ስጋት ነፃ ሆነ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግ በሃሳብ ያልተስማሙትን አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ መምህራን በአንድ አዳር አባሮ ከምሁራን ጋር ኩርፊያ ጀመረ፡፡ ይህ ሁለት መልክ ያለው ግንኙነት እንዳለ ሆኖ መንግስት ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ ሰፊ እና የማስፋፊያ ስራ መስራቱ እንደ ብርቅ ይቆጠር የነበረውን የዩንቨርስቲ ትምህርት ለብዙሃን ተደራሽ ሊያደርገው ቻለ፡፡

የትምህርት ዓላማ ሰብዓዊነት፣ መክሊታዊነት እና አዲስነት ነው እንዳልነው በኢህአዴግ የስልጣን ዘመን የመጀመሪያ አስር ዓመታት ተማሪዎችም ያገባናል በሚል መንፈስ በሀገሪቱ ባሉ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ የፊት መስመር ተሰላፊዎች ነበሩ፡፡ ከሰብዓዊ መብት ጉዳዩች እስከ የበጎ ፈቃድ አስተዋፅኦ ድረስ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች እና መምህራን ያልገቡበት ጉዳይ አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ንቁ ተሳትፎ መሃል ግን ከመንግስት ጋር በመብት ጉዳዮች ላይ መጋጨታቸው አልቀረም፡፡ ይባስ ብሎም ደም እስከመፋሰስ ድረስ ፀና፡፡ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በጎሳ ጎራ ለይቶ ዩንቨርስቲን ‹‹የጦር አውድማ›› ማድረግ አዲስ እውነታ ሆነ፡፡

የ1997 ዓ.ም ምርጫ ግን ለኢህአዴግ ትልቅ መልእክት አስተላለፈለት፡፡ ምርጫ በደረገባቸው ዩንቨርስቲዎች ውስጥ በሰፊ የድምፅ ልዩነት ተሸነፈ፤ እናም ተማሪ ጋር መተባበር (Cooperation) እንጅ መፋጠጥ (Confrontation) ዋጋ እንደሌለው ተረዳ ዩንቨርስቲዎችንም በስርዓቱ ፖሊሲዋች ማጥመቅ ያዘ፡፡ ይሄም ለዛሬዎቹ የዩንቨርስቲዎቻችን መልክ ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳደረገ ይታመናል፡፡

## ተማሪነት ዛሬ፣ አስተማሪነት ዛሬ፣ ዩንቨርስቲ ዛሬ

የትምህርት ጥራት መጓደል መንግስት የአጠቃላይ የሀገሪቱ የትምህርት ስርዓት ፈተና ነው ብሎ አውጇል፡፡ ይህ ፈተና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ደግሞ የገዘፈ እና ለነገ ሊባል የማይችል ችግር እንደሆነ በተለያየ ወቅት የቀረቡ ሪፖርቶች አመላካች ናቸው፡፡ እንግዲህ ከጥራት መጓደል ጋር ተያይዞ አላማቸወውን ማስተማር፣ መመራመር እና ህብረተሰቡን ማገልገል (Teaching, Research and Community Service) ለሆኑት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ መፈተናቸው አልቀረም፡፡ እስኪ የአሁኖቹ ዩንቨርስቲዎች መልክ እና ቁመናን እንመልከት፡፡

## 1. ዋዘኛ እና ፌዛዛ

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ከ30 በላይ ዩንቨርስቲዎች አሉ፤ ይሄም ለከፍተኛ ትምህርት እድገት ታላቅ አስተዋፅኦ ማድረጉ አያጠያይቅም። ነገር ግን የነዚህ ዩንቨርስቲዎች ማህበረሰብ ዋዛ እና ፌዛዝነት በእጅጉ ያጠቃው እንደሆነ መረዳት አስቸጋሪ አይደለም። ከአንጋፋዎቹ እስ አዳዲሶቹ ዩንቨርስቲዎች ዛሬ በጉጉት የሚጠበቁት ጉዳዩች እንደ Crazy Day, Color Day ወይም Valentines Day ያሉት ዋዘኛ ቀኖች እንጅ ትምህርት እና እውቀት አዘል ጉባኤዎች ወይም ውይይቶች አይደሉም። ትምህርት የትርፍ ጊዜ ሥራ እንደሆነ በብዙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች እንዲሁም አስተማሪዎች ዘንድ ግንዛቤ የተያዘ ይመስላል።

አብዛኞቹ ተማሪዎች ከሚያነቡት Handout፤ መምህራንንም ከሚያዘጋጁት Handout ባለፈ ስለ ሀገራቸው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የማወቅ ፍላጎት አይታይባቸውም። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማህበረሰብ በሀገራዊ ጉዳይ ላይ ፌዛዛ ነው ምንም መስማት አይፈልግም ማለት እንችላለን። በዩንቨርስቲዎች ውስጥ የመብት ጥያቄ ተነሳ ካልንም፤ መነሻዎቹ ወይ የምግብ ጉዳይ ነው አለዚያም እንደ የDSTV ካርድ የመጠቀሚያ ጊዜ ማለቅ ያሉ እዚህ ግባ ሊባሉ የማይችሉ ጉዳዩች ናቸው ።

በአንድ ወቅት የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች የንጉሱ ስርዓት በግዴታ ወደ ተላየዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እንድንዘምት እያደረገን ነው ይሄ ደግሞ ከመብቶቻችን ጋር ይጋጫል በማለት የንጉሱን ስርዓት በፍርድ ቤት ከሰው አሸንፈውት ነበር። ዛሬ ይሄን ለመብት መታገል በዩንቨርስቲዎቻችን ውስጥ የሚፈልጉ ከሆነ፤ አዎ እርስዎ የትናንት ሰው ነዎት።

## 2. ካድሬው 'ምሁር'

ከ1997 ዓ.ም ምርጫ ኢህአዴግ ትልቅ ትምህርት ቀሰመ ካልን፤ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ስርዓቱን ማጠንከርን ከቀዳሚዎቹ ትምህርቶች ማሰለፍ እንችላለን። በ1997 የክረምት ወራት የተጀመረው የመስመር ዝርጋታ ተጠናክሮ ፓርቲው በአዲስ ራእይ መፅሄቱ በ2003 ዓ.ም በመላ ሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ከ150,000 በላይ አባላት እንዳሉት እና በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍሎች ውስጥ ህዋስ እንደዘረጋ ገልጿል። እንግዲህ ይህ ቁጥር እንደሚጠቁመን አብዛኞቹ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የስርዓቱ አካል እና አስፈጻሚ እንደሆኑ ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በዩንቨርስቲዎች ውስጥ እየታየ ያለው አዲስ ገፅታ፤ የተማሪዎች ጊዜያቸውን በህዋስ ውይይት እና ግምገማ ማዋላቸው፣ ከአባላት ሁሉ ረዝሞ ለመታየት የሚደረግ ጥረት፣ ከትምህርት ውጤታቸው ይልቅ፤ በአባልነታቸው ወደሚሰጣቸውን ነጥብ አብዝቶ ማተኮር፣ ሲብስም የትምህርት ጊዜያቸውን ለፓርቲ ተግባራት በማዎል የመጡበትን ዋነኛ አላማ መሸሽ ወ.ዘ.ተ የዛሬ የዩንቨርስቲ ተማሪነት መገለጫዎች ናቸው።

## 3. የጎሳ 'ጠበቃ'

በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይእንደቀረበው ምሳሌ ያሉ ጎሳ ተኮር (Ethnocentric) ግጭቶች ሌላው የዩንቨርስቲዎቻችን መገለጫዎች ናቸው። ነገሮችን በውይይት እና በሰከነ መንገድ ከመፍታት ይልቅ ጦር መስበቅ አዲሱ እውነታ ነው። ጉዳዩን አሳሳቢ የሚያደርገው ደግሞ ከዩንቨርስቲ ፤ ዩንቨርስቲ ተሻጋሪ መሆኑ ነው። በአንድ ዩንቨርስቲ የተፈጠረ ግጭት አፍታም ሳይቆይ በሌላ ዩንቨርስቲ የሚገኙ 'የጉዳዩ ባለቤቶች' ጋር በመዳረስ እስከሞት የሚደርሱ ግጭቶችን ማየት ዛሬ ዛሬ ብዙም አስገራሚ ጉዳይ አይደለም።

ይህ የጎሳ ጥብቅና ባስ ሲልበትም የመማሪያ መፅሃፍትን እስከ መምረጥ ይዘልቃል። ‹‹ይህ መፅሃፍ ለኔ ጎሳ አይስማማምና ከቤተ መፅሃፍት ይውጣልን!›› ብለው መፅሃፍ ላይ ፍርድ ሰጥተው፤ ውሳኔውን የሚያስፈፅሙ ተማሪዎች በየንቨርስቲዎቻችን እንዳሉ ማወቅ መራር እውነታ ነው።

መምህራን እና የዩንቨርስቲዎች አስተዳደር አካላት 'ለድቀቱ' አስተዋፅኦ የላቸውም ማለት አይቻልም። ከዝግጅት ጀምሮ እስከ ስነምግባር ድረስ ከተማሪዎቻቸው የማይሻሉ መምህራን እንዳሉ ማወቅ የአደባባይ ሀቅ ነው።

የዩንቨርስቲዎች አስተዳደሮችም ሁሉም ጉዳዮች ‘ፖለቲካዊ ትርፍ’ ይገኝባቸው ዘንድ ሁሌም መትጋታቸው ከትምህርቱ ዋነኛ ዓላማ እንዲሸሹ አድርጓቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ከነዚህ እውነታዎች የምንረዳው ነገር፤ ተማሪዎች በዩንቨርስቲ የሚኖራቸው ቆይታ እንዲሁም አጠቃላይ የዩንቨርስተዎቻችን ምህዳር አሳሳቢ እንደሆነ ነው፡፡ አዎ የተማሪውን ደብተር በደም እየዋኝ ያየንበት ዘመን በማለፉ ደስ ይለናል፡፡ ነገር ግን ደስታችንን የሚገድብ አዲስ እውነታ ደግሞ ከፊታችን ይታያል፤ ደብተር የሌለው ‘ተማሪ’፡፡ ተማሪዎች የሚሟገቱለት ዓላማ (Cause) ምግብ እና ጎሳ ብቻ መሆኑ የት ያደርሰናል? ምንስ እናድርግ?

\- - -

ማስታወሻ፡ በዚህ ጽሑፍ ‘የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት’ ወይም ‘ዩንቨርስቲ’ እያልን የገለጽናቸው ተቋማት በመንግሥት የተቋቋሙትን የትምህርት ተቋማት ብቻ ያመለክታሉ፡፡

# ምሁርነት እና ምሁር

በተለያዩ የሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ አንድ የተለመደ አባባልን ማስተዋል የተለመደ ነው፤ ‹በምሑራን*› ተሳትፎ የኢትዮጵያን ሕዳሴ እናረጋግጣለን› የሚል ፅሁፍ በሕዳሴው ግድብ ፎቶ ታጅቦ፡፡ ቃላቶቹ ከተሰቀለበት ቦታ አንፃር ስንመለከተው ምሁሩ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ መሽጓል፤ ሕዳሴውንም ‹በምሑሩ› ፊት አውራሪት ይረጋገጣል የሚል አንድምታ እንዳለው መረዳትም ብዙም አይከብድም፡፡

በርግጥ ምሁሩ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ አለን? ኧረ እንዲያውም ምሁር በአጠቃላይ በሀገራችን አሉ ወይ? እያልን እንጠይቅ ዘንድ ፈቀድን፡፡

## ምሁር ስንል

በተለያዩ ወቅቶች እና ቦታዎች መታዘብ እንደምንችለው ‹ምሁር› የሚለው ስያሜ በሀገራችን ተለጥጦ ፊደል የቆረን ሁሉ አካትቶ ይዟል፡፡ ኮሌጅ የበጠሰ ሰውማ የሊቀ-ሊቃውንትነት ካባን ይደርባል፡፡ እዚህ ላይ በመጀመሪያ የምናገኘው ችግር ምሁርን (Intellectual) ከባለሙያ (Professional) መደባለቅን ነው፡፡ ባለሙያ የሚለውን ማዕረግ ከሳቴ ብርሃን የአማረኛ መዝገበ ቃላት ‹‹ሥራን ዐዋቂ መኾን ልዩ ልዩ የትምህርት ሥራን የእጅ ሥራ ጥበብን ማወቅ ወይንም ያንድ ቀን ሥራን ሠርቶ ደመወዝን ማግኘት፡፡›› በማለት የተወሰነ ስራን መስራት እና ምንዳን እንደ ምላሽ ማግኘት (Quid Pro Quo) በማለት ሲያቀርብ፡፡ ምሁር የሚለውን ስያሜ ደግሞ ‹ከፍተኛ የሆነ የማሰብና የመመራመር ችሎታ ያለው፤ ሊቅ የተማረ በኹሉ ምሉ ትምህርት ያለው ሰው› ብሎ ሰፊ ደርዝ በማስያዝ ምሁርነት ከፍ ያለ ጉዳይ እንደሆነ ያሰረዳል፡፡

Robert Roberts እና Jay Wood ‹Intellectual Virtues› ባሉት መፅሃፋቸው አንድ ምሁር ሊኖረው ስለሚገባው መሰጠቶች (Virtues) አብዝተው ይተነትናሉ እንደ ፀሃፊያኑ ገለፃም ምሁር፤ ምሁር ለመባልም እውቀትን የመሻት (Love of Knowledge) ፀናኢነት (Firmness)፣ ልበ ሙሉነት( Courage)፣ ቀናኢነት (Humility)፣ ነፃነት (Autonomy)፣ ደግነት (Generosity)፣ እና በሳት የፈተነ ጥበብን (Practical Wisdom) መታደል ይኖርበታል በማለት፤ የምሁርነት ተራራ ብዙ ነገሮችን ያቀፈ መሆን እንዳለበት ይናገራሉ፡፡

እንግዲህ የአፍላጦኗ (Plato) ሀገረ-መንግስት (State) በእነዚህ ላቅ ያሉ ስብዕናዎች የምትመራ ነች ማለት ነው፡፡

## የእኛዎቹ ወዴት ናቸው?

ምሁር መባል እንዲሁ ቀላል ነገር እንዳልሆነ ከትርጎሞቹ ለማየት ችለናል፡፡ ምሁርነትም መለያ ባህሪውን በራሱ አሳቢ መሆን በማድረግ፤ ምጡቅነትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው ማለት ነው፡፡

እናም በሀገራችን በኢትዮጵያ እነዚህን አሳቢያን ከወዴት አሉ? ብለን እንጠይቃለን፡፡ በመጀመሪያ የተማረ ሰው ሁሉ ምሁር እንዳልሆነ ለማሳየት ሞክረናል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚስመርቋቸውም ተማሪዎች ባለሙያዎች እንጅ ምሁራን እንዳልሆኑ ከትርጉሙ እና ማሟላት ካለባቸው መሰጠቶች አንፃር አይተናል፡፡

ከዚህ በመለስስ ኢትዮጵያዊ ምሁርን ወዴት እናገኘዋለን? ቀጣዩ መመለስ ያለበት ጥያቄ ነው፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት የምሁር መሰጠቶች ጋር በተያያዘ አሜሪካዊው ሊቅ Noam Chomsky የምሁራን ድርሻ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ምንድነው? ብለው ይጠይቁና ‹It is the responsibility of intellectuals to speak the truth and to expose lies-የምሁር ዋነኛ ግዴታው ለእውነት መኖር እና እውነትን መናገር ነው› ብለው ይመልሳሉ፤ የትኛውን እውነት? ሲባሉም የMartin Heideggerን የእውነት ትርጉም በመዋስ ‹ህብረተሰቡን እርግጠኛ፣ ግልፅ፣ ጠንካራ እና አዋቂ የሚያደርገውን እውነት› ብለው ይመልሳሉ፡፡

እናም ይሄ ኢትዮጵያዊ ምሁር ወዴት አለ? ፍትህ ተጓደለ የሚለው ሊቅ፣ መብት ይከበር ማለት የሚገደው ልበ ብርሃን፣ ደፋሩና ፅኑው ምሁር ኢትዮጵያ ውስጥ ወዴት ነው?

## የምሁር ካባ ለባሹ

የነጠረውን ምሁር ፈልጌ ባጣ ጊዜ፤ እስኪ ከተለመደው ‹የምሑር› ሰፈር ይፈለግ ብየ አሰሳ ገባሁ። ጂቡቲያዊው የዩኒስኮ ሰራተኛ Ali Moussa Iye በአፍሪካ ቀንድ ያለው የምሁራን ጉዳይ እጅግ አሳስቧቸው ‹The Betrayal of the Intellectuals› በሚል ርእስ፤ ስለ ቀንዱ ሀገራት የምሁራን ክህደት እና መፍትሄው አጭር ፅሁፍ ፅፈዋል። ፅሁፋቸውን ሲጀምሩም ‹የቀንዱ ሀገራት ምሁራን አደግዳጊ፣ አቤት ወዴት ባዩችና ሎሌዎች ናቸው› በማለት ነው። ሲቀጥሉ ‹They have rallied to every flag of convenience raised by powerholders and powerseekers… Intellectuals in the Horn of Africa have failed to fulfill their mission and have betrayed their people.› በማለት ‹ምሑራን› በቀንዱ ሀገራት ከዳተኛ እና ሽክም እንደሆኑ ያስረዳሉ። ጋናዊው ፕሮፌሰር ጆርጅ አይቴ እነዚህን ‹ምሑራን› 'Intellectual Prostitutes' ይሏቸዋል። የሀገራችን ‹ምሑራንስ› ከዚህ ይልቃሉን?

## ‹ግማሽ ወንበዴ፣ ግማሽ መደዴ›

ፊደል የቆጠሩ፣ በዲግሪ ላይ ዲግሪ የደራረቡ ብዙ ኢትዮጵያዊያን እንዳሉ አይካድም። ከእነዚህ ውስጥ አንባቢ-ማሀይማን (Functionally Illiterates) በዝተው ይታያሉ ማለትም ለኔ ስህተት አይደለም። ሀብት በምን መንገድ ማጋበስ እንደሚቻል ሲያሰላስል የሚውል ዶክተር እና ፕሮፌሰርን ማየት ብርቅ አይደልም። ሀብትን መፈለግ ሳይሆን ችግሩ የሕዝቡን ሀብት ዘርፎ ካልሄድኩ ብሎ መኳተኑ ነው ትዝብቱ። ይህ ነው እንግዲህ ወንበዴው የምሁር ካባ ለባሽ። በምሁርነት ካባ ለባሹ ሌላኛ ተርታ የሚሰለፈው ደግሞ ‹ሀገሪቱን ወዴት እናስኪድ?› ማለቱን ትቶ፤ ‹እኔ ወዴት ልሂድ?› ማለትን የሚያዘወትረው ነው መደዴው።

የPrinceton ዩንቨርስቲ ፕሮፌሰር የሆኑት Forrest Colburn በወታደራዊው ዘመነ መንግስት ጊዜ በፃፉትና ‹The Tragedy of Ethiopia's Intellectuals› ባሉት ፅሁፋቸው ላይ አንድ ተማሪ እንዲህ አለኝ ይላሉ "Ignorants are more concerned about Ethiopia than are intellectuals." ይህ ነው ኪሳራው፣ ይህ ነው ድቀቱ።

## አሽርጋጁ

በሌላ በኩል ደግሞ መንግስታዊ መናን በማሰላሰል መንግስትን አይዞህ በርታ የሚሉ ‹ምሑራን› አሉ። መንግስትን የሚቃወም ሀሳብም ሲቀርብ ጅራፍ እያነሱ ጀርባ ገራፊዎች ይሆናሉ። ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ መንግስትን መቃወም እንደ አንጀራ የያዙ ‹ምሑራን› ተሰልፈዋል። በመንግስት ተቀጥሮ፤ ለመንግስት ስራ መስራት ስህተት ነው እያልኩ አይደለም፤ መንግስትንም ማማከር ሀጢያት የለውም። ስህተቱ የሚጀምረው ‹ምሁራን ዋነኛ አላማቸው ለእውነት መኖር ነው› የሚለውን ጥልቅ ሀሳብ ትቢያ ላይ ወርውረው ጥለው. የምሁርነት ካባውን ግን ሲደርቡት ነው። ወይ ካባውን ማውለቅ ያለዛም ለሀሳበ መኖር ነው ምርጫው መሆን ያለበት። ግን በምን ወኔ። ‹ምሑር› ካልተባሉ መናው ይቀራላ።

## ‹ምሁር› የለሽ፣ ‹የአደባባይ ምሁር› ትፈልጊያለሽ

እንደ Edward Saïd ያሉ ፀሃፍት ‹[The] ... real or 'true' intellectual is, therefore, always an outsider, living in self-imposed exile, and on the margins of society.› ይላሉ። ‹ምሁር ከባዕቱ መውጣት የለበትም፤ ራሱን ያሳሰረ የህብረተሰብ ግንባይ ነው› ይላሉ። ይህ ‹የጋን መብራት› የሚባለው ነው።
ገጣሚው ከበደ ሚካኤል በበኩላቸው፡

››የተማረ ሆኖ፣ እውነቱን የማይገልጽ ፣
ባለ ጸጋ ሆኖ፣ ገንዘቡን የማይሰጥ፣
ደሃ ሆኖ፣ መስራት የማይሻ ልቡ፣
ሶስቱም ፍሬ ቢሶች፣
ለምንም አይረቡ።››› ይላሉ።

ዘመናዊ እሳቤው ምሁራን ለህብረተሰቡ ግልጋሎት ይሰጡ ዘንድ ይሰብካል፡፡ ምሁራን ወደ ሕብረተሰቡ ሲወጡም የአደባባይ ምሁራን (Public Intellectuals) ይባላሉ፡፡ እናም በሀገራችን እነዚህ የአደባባይ ምሁራን ያስፈልጉናል ማለታችን ያስማማን እና ግን የታሉ? ከወዴትስ ይመጣሉ? አሁንም ጥያቄ ነው፡፡ በርግጥ የጓዳውን ምሁር ሳናገኝ የአደባባዩን ምሁር መፈለጋችን ቧልት ይሆን?
ምሁሩ ወይ ወዴት ነህ? ምሁሩን ያገኛችሁ ወይም የት እንደገባ የምታውቁ እስኪ ሀሳባችሁን ወዲህ በሉ፡፡

* በዚህ ጽሑፍ በሀገራችን በተለምዶ ‹ምሑር› የሚባሉትን ለመግልጹ ሐመሩ ‹ሐ›ን መጠቀምን መርጫለሁ፡፡ ለቀሪዎቹ ግን የተለመደውን ‹ምሁርን› ተጠቅሜያለሁ፡፡

# አንባቢውን ኢትዮጵያዊ ፍለጋ

ዓለምን እንዲሁ ልናውቃት አንችልም፡፡ ዓለሚቱን ለመገንዘብ ብዙ ግብዓቶች ያስፈልጉናል፡፡ እንደዛም ሆኖ ግን ዓለምን ሙሉ ለሙሉ አናውቃትም፡፡ ስለ ዓለም ጥሩ የሆነ ግንዛቤ ያለው ሰው፤ ስለምድሪቱ ከሌሎች የተሻለ መረጃ አለው ማለት ነው፡፡ መረጃን ማግኛ መንገዶች ደግሞ ከሰው ሰው፣ ከቦታ ቦታ፣ ከጊዜ ገዜ ይለያያሉ፡፡ ፅሁፍ ከሰው ልጅ ቀደምት የመረጃ ማግኛ ዘዴዎች አንዱና ዋነኛው ነበር/ነው፡፡ ፅሁፍ በአንድ ላይ ተጠርዞ ለአንባቢው ሲቀርብ ደግሞ መፅኃፍ የሚል ስያሜን ያገኛል፡፡

እንግሊዛዊው ባለቅኔ ጆን ሚልተን (1608 - 1674) እንዲህ ይላል ‹‹*Who kills a man kills a reasonable creature, God's image; but he who destroys a […] book, kills reason itself, kills the image of God, as it were in the eye.*›› መፅኃፍ ማለት ምክንያት ማለት ነው እንደ ማለት፡፡ ያለምክንያት ህይወት እንዴት ይሆናል?

መፅኃፍ መረጃን መስጠት አንዱ አላማው ቢሆንም ከዚህ ጋር ተያይዞ ማዝናናት እና ማበልፀግን እንደ ግብ አድርጎ መመልከትም ይቻላል፡፡

## ዓለማቀፉ የመጽሐፍት እና የአንባቢ ግንኙነት

አል አረቢያ ቴሌቪዥን ባለፈው ሃምሌ ወር ሮይተርስን በመጥቀስ ያምጣው ዜና የአረቡ አለም በንባብ ባህል በኩል በጣም ደካማ እንደሆነና ከምዕራብ ሀገሮች ጋርም ሲነፃር በጣም ያነሰ መሆኑን የገለፀ ሲሆን፤ ይሄም በአረቡ አለም ዘንድ አስገራሚ ተብሎ ነበር፡፡ በተጠቀሰው የምርምር ስራ መሰረት አንድ አረብ በዓመት ስድስት ገፅ ብቻ የሚያነብ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ አንድ አሜሪካዊ በዓመት አስራ አንድ መፅኃፍት እንዲሁም አንድ እንግሊዛዊ በዓመት ሰባት መፅሃፍት ያነባል በማለት ፡፡ ‹‹እኛ የአረቡ አለም ነዋሪዎች ልጆቻችን በዓመት ስድስት ደቂቃ ብቻ ለልጆቻችን የንባብ ጊዜ ስናበረክት፤ በአንፃሩ ምዕራባዊያን ቤተሰቦች ደግሞ በዓመት አስራ ሁለት ሽህ ደቂቃዎችን ለልጆቻቸው የንባብ ጊዜነት ያውሉታል›› ይላል፡፡

ይህ የሚያሳየው የንባብ ባህል መኖር በእድገት እና በብልፅግና ላይ የሚያደርሱት ተፅእኖ ትልቅ መሆኑን ነው፡፡ አዎ Readers are Leaders.

## ኢትዮጵያዊው መጽሐፍ

ወደ ሃገራችን ኢትዮጵያ ስንመለስ፤ ያለውን የንባብ ባህል በምርምር ስራ አስደግፎ ያቀረበ ምርምር ስራ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ሊያገኝ አልቻለም ወይም ያሉትም የአንድ በጣም የተወሰነ ሁኔታን ብቻ የሚገልፁ ናቸው፡፡ ነገር ግን ተያያዥ ሁኔታዎችን አብረን በማየት ያለውን የንባብ ባህል እና የመፅኃፍ ስርጭት የሚያመለክት ስዕል ማስቀመጥ እንችላለን፡፡

ጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ ስልጣን በያዘ ማግስት አላማው ማርክሲስት-ሌኒኒስት ሕብረተሰብን ለመገንባት በማሰብ የመሰረተ ትምህርት ዘመቻ ካወጀ በኋላ፤ ማህይምነትን ለማጥፋት በሚል ግብ በተደረገው ጥረት በኢትዮጵያ የሚገኙ መሀይማንን ቁጥር ወደ ሀያ አራት በመቶ ዝቅ ለማድረግ ተችሎ ነበር፡፡ ለዚህም ስኬት በመላ ሀገሪቱ ከሰባት ሽህ በላይ ቤተ መፅኃፍት ተገንብተው እንደነበር በጊዜው የወጡ ሪፖርቶች ይገልፃሉ፡፡ ይሄም የማንበብ ባህልን ከማሳደግ አኳያ ታላቅ እምርታ እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡

ነገር ግን በወታደራዊ ዘመን የመፅኃፍት ሳንሱር በእጅጉ የበረታ ከመሆኑ የተነሳ መንግስታዊ ርዕዮተ ዓለም ከሆነው ማርክሲዝም- ሌኒኒዝም ውጭ ሌሎች ሀሳቦችን የሚያንፀባርቁ መፅሃፍት 'የአድሃሪያን' ናቸው፣ 'የኢምፔሪያሊዝም ጭምቅ መርዞች'፣ 'የአቢዮት ቀልባሾች ማንፌስቶ ናቸው' ወ.ዘ.ተ በሚሉ አልባሌ ምክንያቶች የሚታተሙት መፅኃፍት በእጅጉ በተወሰኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ብቻ የሚያጠነጥኑ ነበሩ፤ ይሄም የንባብ ባህሉን እና የሀሳብ እንሸርሸሪቱን (Discourse) እድገት አንቆ ይዞት ነበር፡፡

ኢሕአዴግ ስልጣን እንደያዘ የኢትዮጵያ ሰላማዊ እና ዲሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ፤ የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተርን አፀደቀ። ቻርተሩ ከያዛቸው ዋነኛ ነጥቦች መካከል ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት ያፀደቀውን እና ኢትዮጵያም ፈራሚ የነበረችበትን ‹‹ዓለማቀፉን የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ(UDHR) ሙሉ ለሙሉ ተቀብላለች›› የሚለው ሃሳብ ይገኝበታል። ከነዚህ መብቶች አንዱ ሀሳብን በፈለጉት መንገድ የመግለፅ ነፃነት ነው። ይሄም በንባብ ባህሉ ላይ በአጠቃላይ፣ በመፅኃፍ ገበያውን ላይ ደግሞ በተለይ በአዎንታዊ መልኩ ተፅዕኖ እንደሚሳርፍበት በወቅቱ ተገጿል። ለዛም ይመስላል በኢህአዴግ መጀመሪያ የስልጣን አመታት በደርግ ጊዜ ታፍነው የነበሩ ድምፆች መተንፈስ የጀመሩት። ነገር ግን ከመፅኃፍት ገበያው ጎን ለጎን የግል ጋዜጦች ወደ ገበያው መግባታቸው አንባቢዎችን ከጠጣር (Hard) ወደ ስስ እና ለብ ለብ (Soft) የንባብ ባህል እንዲነዱ ተፅእኖ ፈጥሮባቸዋል። ይሄም መጽሐፍ ከጋዜጣ የደረሰበት የመጀመሪያው ጠንካራ ቡጢ ነበር።

እንደዛም ሆኖ በነዚህ ዓመታት የመፅኃፍት ገበያው መልካም በሚባል ሁኔታ ላይ ነበር ማለት ይቻላል። በሂደት ግን የመፅኃፍት ገበያው እየተቀዛቀዘ መጣ። በ2001 ዓ.ም አካባቢ በሚዩዚክ ሜይ ዴይ የወጣ አንድ ሪፖርት እንደሚያመለክተው ኢትዮጵያ ውስጥ የመማሪያ መፅኃፍትን ጨምሮ በቀን በአማካኝ አምስት መፅኃፍት ለህትመት ይበቃሉ። ይህ የሚያመለክተው በዓመት በመላ ሀገሪቱ በሁሉም ቋንቋዎች፤ በሁሉም ርእሰ ጉዳዮች ላይ የትርጉም ስራዎችን ጨምሮ ወደ 1800 አካባቢ መፅኃፍት ይታተማሉ ማለት ነው። ይሄን ቁጥር ለምሳሌ በአሜሪካ እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2010 ዓ.ም በአሜሪካ ከታተሙት ሶስት መቶ ሃያ ስምንት ሽህ ሁለት መቶ ሀምሳ ዘጠኝ (328,259) መጽሐፍት ጋር ስናነፃፀረው በሀገራችን የሚታተሙትን መጽሐፍት ቁጥር አናሳነት እንረዳለን።

እንግዲህ ከ80 ሚሊዮን በላ ህዝብ ለሚኖርባት ሀገር ይህ ቁጥር እጅግ ትንሽ ቁጥር ከመሆኑም በላይ። የአንባቢውን ውስንነት እና የንባብ ባህሉን ውድቀት ያሳያል። ለመሆኑ መፅኃፍ ለምን ተዘነጋ?

## መሀይምነት

ከ84 በመቶ በላይ ህዝብ በገጠር በሚኖርባት ኢትዮጵያ የመሃይሙ መጠንም በዚያው ልክ ብዙ እነደሚሆን መገም አያዳግትም። እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ2005 ዓ.ም፤ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (UNESCO) በወጣው ሪፖርት መሰረት 45 በመቶ ኢትዮጵያዊያን ብቻ የተማሩ (Literate) እንደሆኑ ሲገልጽ፤ ቀሪዎቹ 55 በመቶዎቹ ደግሞ ያልተማሩ (Illiterate) ናቸው ይላል። ይሄም የሚያሳየው ከግምሽ በላይ የሚሆኑት ኢትዮጵያዊያን አያነቡም አይፅፉምም ማለት ነው። በጣም የሚያስገርመው በመሰረተ ትምህርት ዘመቻ አመካኝነት ማንበብ እና መፃፍ ይችሉ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ዝንጋኤ ውስጥ (Memory loss) ሆነው የተማሩትን መዘንጋታቸው ነው። እናም የመሃይሙን ቁጥር ከፍ አድርጎታል።

እንግዲህ በሀገሪቱ የመሃይማኑ ቁጥር ከተማሪው ይልቅ ማየሉ በንባብ ባህሉ እና በመፅኃፍ ገበያው ላይ የሚያስከትለው ተፅእኖ ከፍተኛ መሆኑ አያጠያይቅም። ይሄን ስንል ግን ተምሪው - ያልተማሩትን (Functionally Illiterate) ማለትም ፊደል የቆጠሩ ነገር ግን ስለመፅኃፍ ምንም ሀሳብ የሌላቸውን ዜጎች ሳንጨምር ነው።

## ዕውቀት ተኮር ኅብረተሰብ ወዴት ነው?

የመሃይማኑ ቁጥር ከላይ እንደተቀስነው ከተማሪው ዜጋ ቁጥር በላይ ቢሆንም፤ በተማሪው ህብረተሰብ ዘንድ ያለው የመፅኃፍ ግንዛቤም ሌላው ከንባብ ባህሉ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ጉዳይ ነው። የንባብ ምሽቶች፣ የማንበቢያ ቦታዎች (Reading Buzz) መኖር፣ ህፃናት ለማንበብ ያላቸው ተነሳሽነት እንዲጨምር እየተሰሩ ያሉት ተግባራት ወ.ዘ.ተ ስንመለከት የችግሩ ስር ወዴት ሊሄድ እንደሚችል መገመት ያስችለናል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለንባብ ባሕሉ ዕድገት የሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው? በዩንቨርስቲዎች ውስጥ ያሉት ንባብ ተኮር ዝግጅቶች ምን ያክል ናቸው? ተማሪዎች 'የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግን' እንዲመለከቱ ትኩረት ተሰጥቶ በሚሰራበት መጠን፤ ለመፅኃፍ ያላቸው ፍቅር እንዲያድግስ ይደረጋል ሆይ? እያልን ስንጠይቅ፤ መልሱን ለጥያቄዎቹ ከምንሰጠው መልስ ጀርባ እናገኘዋለን።

ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ በሞቱ ወቅት የአሁኑ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስተር እና የትምህርት ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ለዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል በሰጡት ቃለ ምልልስ ‹‹ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ በእውቀት የተመሰረተ ህብረተሰብን ገንብተዋል›› ብለዋል፡፡ ይሄ እንዴት ይለካል? ነው ጥያቄው፡፡ ምን ማለትስ ነው?

## 'የስክሪን ትውልድ'

ሌላው መጽሐፍን ያስረሳው ጉዳይ አዳዲስ 'አማራጮች' መስፋታቸው ነው፡፡ ከነዚህ አዳዲስ ክስተቶች አንዱ እና ዋነኛው የሲኒማው ዓለም ዘመነኝነት እና ተደራሽነት ናቸው፡፡ በአጭር ጊዜ፣ በግሩም ቴክኖሎጂ እና በተለያየ መልኩ የሚቀርቡት ሲኒማዎች ትውልዱ ለመፅኃፍ ጀርባውን እንዲሰጥ አድርጎታል፤ የሚለው መከራከሪያ ደግሞ በአንድ በኩል ይቀርባል፡፡ ግን ሲኒማ መፅኃፍን የማስረሳት አቅም አለው ማለት ይቻላል? አንዳንዶች ዘመነኞቹ መረጃን በቀላልና ክሽን ባለ መልኩ (Cooked) መፈለጋቸው ወደሲኒማው ዓለም እንዲያዘነብሉ አድርጓቸዋል ይላሉ፡፡

ነገር ግን እስኪ ስንቱ ሲኒማ ተመልካች ነው "Twilight" መጀመሪያ መፅኃፍ እንደነበር የሚያውቀው? ማነው"Avatar" አይቶ ከመፅኃፍ ላይ የተወሰደ ታሪክ እንደሆነ የሚያስተውለው? "Harry Potter" ተከታታይ ሰኒማን ተመልክቶ መፅኃፍ፤ በምእራቡ ዓለም እንደ ቅዱስ መፅኃፍ የሚመለክ መሆኑን ልብ ያለ ስንቱ ይሆን?

እንግዲህ 'የስክሪን ትውልድ' ተብሎ የተፈረጀው ዘመነኛ አይኑ ቴሌቪዥን ላይ እንደተተከለ መፅኃፍ አንብበው ሲኒማውን የሰሩትን ሰዎች እንዳደነቀ እዛው ሶፋ ላይ ይተኛል፡፡ እንዴት ነው?

## የቀበሌው 'ድራፍት ቤት'

መንግሥትም እንደዋነኛ ባለድርሻ የመጽሐፉን ዋጋ ከፍ የሚያደርጉ ስራዎችን ይሰራ ዘንድ ከሚጠበቁ አካላት አንዱ ነው፡፡ በየምንኖርበት አካባቢ ያለውን 'የድራፍት ቤት'፣ ካለው የቤተ መፅኃፍት ቁጥር ጋር አነፃፅረነው እናውቅ ይሆን? በመንግስት ድጋፍ የሚቋቋሙ 'የድራፍት ቤቶች' እንዳሉ ሁሉ፤ ምን ያክል ቤተ መፅሃፍተስ እንዲሁ ይቋቋማሉ? ብለን መጠየቅ መንግስት ለዘርፍ ምን ያህል ትኩረት ሰጥቷል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ያስችለናል፡፡

'ድራፍት ቤቶች' መኖራቸውን ልቃወም አይደለም፡፡ ነገር ግን በነሱ ትይዩስ ምን እየቀረበ ነው? ነው ጥያቄው፡፡ መንግስት በተለያዩ ፖሊሲዎቹ ትኩረት የሚሰጠው ልማት የአእምሮ ልማትን በቅጡ ያካተተ ነው ወይስ አይደለም?

ይሄን ጽሑፍ ስንጀምር ከእንግሊዊው ባለቅኔ ጆን ሚልተን ‹‹መጽሐፍ ምክንያት ነው፤ መጽሐፍ ከሌለ ምክንያት የለም ››የሚለውን ሐሳብ ተንተርሰን ነበር፡፡ እናም የእኛ ምክንያታዊነትስ እያደገ ነው ወይስ በተቃራኒው? ብለን በመጠየቅ ሳባችን እንቋጭ፡፡ እርስዎ ምን ይላሉ?

# ስደትና ፍቅር

*በሰለሞን አብርሃም (ከአውሮጳ)*

*የአንድ አገር መንግሥት ለዜጎቹ እረኛ እንደማለት ነው። እረኛ መንጋውን ይጠብቃል መንግስትም ዜጎቹን ይጠብቃል። ነገር ግን እኛ መንግስት ቢኖረንም ጠባቂ የሌለን ሕዝቦች ከሆንን ዓመታት ተቆጠሩ። እረኛ የሌለን መንጋ ከሆንን በርካታ አሥርት ዓመታት አለፉ። መንግስቶቻችን እረኛነታቸው ባሕሪያቸው አልነበረምና አውሬነቱ እያሸነፋቸው ከመንጋው ያማራቸውን እየመረጡ ሲያርዱ፣ ሲበሉ ኖሩ። አውሬዎቹን የተመለከቱና የሰሙ ኢትዮጵያውያንም ከመንጋቸው እየተለዩ ወደምድር ተበተኑ። ከመንጋው የተለየ ደግሞ መጨረሻው ጥፋት ስለሆነ በርካታ ኢትዮጵያውያን በየዱሩ አለቁ፣ በየመንገዱ ባከኑ፣ በባእድ አውሬዎች ተበሉ። የእረኛ ያለህ እያሉ የሌሎችን ባዕዳን ጠባቂዎችን አድኑን እያሉ ለመኑ። የስደት ኑሮን እንደስኬት ቆጥረው መኖር ጀመሩ።*

*መንግስታቶቻችንን ሲሸሹ ለዘላለም ያለፉትን አምላክ ነፍሳቸውን በሰላም ያሳርፍልን። በተለያዩ የዓለም አገራት ተበትነን በዘር፣ በጎሳ፣ በመንደር፣ በከተማ፣ በአመለካከት፣ በአስተሳሰብ፣ በትምህርት ደረጃ ተቧድነን ለምንኖረውም አምላክ በቸርነቱ ይጠብቀንና በሰላም ወደመንጋችን እንድንቀላቀል ይርዳን። ለአሁኑ እስቲ ከስደተኛው አበሻ የፍቅር ሕይወት ሒደት በጎ በጎውን እንታዘብ፤ ደግ ደጉን በጨረፍታ እንዳስ።*

*በስደት ኑሮ አበሻው ቡድን ቡድን መስርቶ ተሰባስቦና ተነጣጥሎ፣ ተዋዶና ተጠማምዶ በሰፊው የስደት ምድር ይኖራል። ኢትዮጵያዊው በሚኖርበት አገር ላይ ብዙ አነስተኛ ድርጅቶችን ይመሰርታል። አነስተኞቹም ድርጅቶች ለመሰነጣጠቅ ምክንያት አያጡም። ምክንያታቸው መኮራረፍን መሠረት ያደረገው የአበሻዊ የአስተሳሰብ ባሕል ሲሆን ከነዚህ ድርጅቶች አኩርፈው የሚወጡት ግለሰቦች ደግሞ ሌላ ጥቃቅን ማሕበራትን መስርተው ይኖራሉ። ኢሕአዴግ የአነስተኛና ጥቃቅን ማኅበራት ማደራጀትን ልምድ የወሰደው በስደት ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ይመስላል። ያገር ቤቶቹና በስደት ላይ ያሉት ማኅበራት ልዩነታቸው ብዛታቸው አይደለም። ልዩነታቸው አስገባሪያቸው ነው። ጥቃቅንና አነስተኛ ማኅበራቱ በአገር ቤት ሲሆን ለኢሕአዴግ ይገብራሉ። በስደት ያሉት ደግሞ ግብራቸውን የሚያስገቡት ለራሳቸው ነው። እነዚህ ቡድኖች በስደት በሚገኙ አበሾች በየስርቻው ተመሥርተው በብዛት ይገኛሉ።*

*የሚመሠረቱበት ዓላማ ምንም ቢሆን በወረቀት ያሰፈሩት መርሓቸው እና በግብር የሚያራምዱት ተግባራቸው የአብዛኞቹ ተመሳሳይ ነው። በወረቀቶቻቸው ላይ እኩልነት ፍቅርና አንድነት ሲሰበክ በአንድነት ተሰባስቦ መታገል ደግሞ ይሞገሳል። በተግባር ግን በተቃራኒው ተፈራርተው፣ ተጠማምደውና ተነጣጥለው ይጓዛሉ። በሰው ምድር ላይ በየቦታው ተመሥርተው እርስ በርሳቸው "እባብ ለእባብ ይተያያል ካብ ለካብ" ዓይነት ኑሯቸውን ሲገፉ ይኖራሉ።*

*ካገርህ ስትሰደድ የአገሬ ጉዳይ ያገባኛል ብለህ ሊሆን ይችላል። የሚያገባህ ከሆነ ከነዚህ ማኅበራት ቀረብ ወደሚልህ ሄደህ እንድትመዘገብ ትመከራለህ። ከዚያም ትሄድና አባል ትሆናለህ። ያኔ ታዲያ የምታሞግሰውና የሚያሞግስህ ታገኛለህ ማለት ነው። የማኅበራቱ ሥራ ከዚህ ስለማያልፍ ያንተም ሥራ በማኅበሩ ልክ ይሆናል። እርስ በርስ ለመሸነጋገያ በተመሠረተ አነስተኛ ማኅበር ውስጥ ከተካተትክ ከማኅበሩ አባላት መወደድን ታተርፋለህ። በዚያችው በማኅበሩ ጉድጓድ ውስጥ ትገባና በጉድጓዷ ስፋት ልክ ማሰብ ትጀምራለህ። የምታዋጣት ሳንቲምና ለስብሰባ የምትመድበው ጊዜ እኔ ላገሬ እንዲህ ነኝ እያልክ እንድትሸልል ያደርግሃል። ይህ አንዱ የስደት ጊዜህን የምታሳልፍበት ኑሮህ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ሌላው ኑሮህ ከአበሻው ማኅበረሰብ ጋር ባንድነት መኖር ይሆናል። ዝም ብሎ መኖር። ልደት፣ ዓውደ ዓመት፣ ማኅበር እያልክ መገናኘትና አንድ ላይ እንጀራ መብላት፣ አንድ ላይ ማውራት፣ ከቦታ ቦታ እየተንሸራሸሩ ከሥራና ከትምህርት የተረፈ ጊዜህን ማሳለፍ፣ ከአገር ልጅ ጋር ፍቅርን መቅጨት። ይህን ስታደርግ የስደት ጊዜን ሳይታወቅ ሽው እንዲል ያደርገዋል ማለት ነው።*

*ከነዚህ ክንውኖች ውጭ ከሆንክ ደግሞ ከአበሻው የኑሮ ጉድጓድ ተገልለሃል ማለት ነው። ከዚያም ወይ የራስህን ጉድጓድ ትቆፍራለህ ወይ ወደተለያዩ ጉርጓዶች ጎራ እያልክ ለመላመድ ትጥራለህ። እንደምንም ብለህ ወደ አንዱ ከተጠጋህ የምታየው የአበሻው ኑሮና ፍቅር ሊመስጥህና ጭንቀትህን ሊያጠፋልህ ይችል ይሆናል። ግን የስደት ነገር ምኑም እውነት እንደሌለው የተገነዘብክ ዕለት ችግር ይመጣብሃል። ላይችል አይሰጥ ይሆንና አትቀውስ ይሆናል እንጂ የአበሻው የስደት ምሽግ የሚጠይቅ አዕምሮ ላለው ሰው ለመሸከም ይከብዳል።*

## ስደተኛው ፍቅር

በስደት ዓለም አብሮ መኖርና አብሮ መብላት የአበሻዊነት ባሕሪ ነው። አበሻ ይዋደዳል ብንልም ስደቱ የአበሻዊነት ፍቅርን ሲፈታተነው ይታያል። መፈታተን ብቻም አይደለም፤ እንዲያውም እንዲህ ማለትም ይቻላል፤ ስደተኛው ፍቅር ወደሆድ አይወርድም፣ ወደ አንጀት አይዘልቅም፣ ልብን አይዳስስም፤ እንዲያው ከአፍ አያልፍም። ስደተኛው ፍቅር ባንደበት ይተረካል፣ በምላስ ይቀመሳል፣ በከንፈር ይሳማል፣ በአዞ እንባ ይታጀባል። በቃ እንዲህ እንዲህ ሲኮን ይኖራል።

ለጥገኝነት መሳካት የተፈጠረ ታሪክን መሠረት አድርጎ መኖር የተለመደበት የስደት ዓለም ለፍቅር አይመችም። አንዷ ተመችታህ ፍቅር ልመስርት ብለህ ብትጠጋ ስለመፈጠርህ ዕውቅና ሊሰጡህ የማይፈልጉ የፍቅር ጎሰኞች ይገጥሙህና የፍቅር ቋንቋህ አይደለም ለፍቅር ሰው ለመሆንህ ማረጋገጫ እንዳልሆነ አፋዊ ባልሆነ ድርጊት ሲገልፁልህ የገባህበት ጉድጓድህ ይደብርሃል፣ ኢትዮጵያዊነትህ ያስጠላሃል። አንዳንዴ ከሌላ አገር ዜግነት ካለው ሰው የሚመሠረት ፍቅር ከኢትዮጵያዊ በላይ ሲደላ ይታያል።

ተሰደህ በፍቅር የምትኖር ከመሰለህ የዋህ ነህ ማለት ሊሆን ይችላል። ይህ ማለት ፍቅር ሊይዝህ አይችልም ማለት አይደለም። ፍቅርን ልትቀበል ግን ትቸገራለህ ወይም ደግሞ ፍቅር ልትሰጥ ትቸገራለህ ማለት ይሆናል። ፍቅርን ለብቻህ ትጫወተዋለህ ስለሆነም ተጋጣሚ የሌለው አታካች ጫወታ ይሆንብሃል። እያባበልክ ወይም እየተባበልክ የምትሰጠው ወይም የምትቀበለው ፍቅር ይሆንብሃል።

ማፍቀርህ ከማንነትህና ከምንነትህ ጋር ይያያዛል። እራስህ የማታስታውሰው ማንነትህ በኩራዝ ብርሃን ይበረበራል፣ ምንነትህ ባለህ የመኖርና የማኖር አቅም ይወሰናል። አንተም የአፍቃሪህን በዋዛ አትለቃትም። ማንነቷንና ምንነቷን ለማወቅ ትተጋለህ። የዘር ማንዘር ብርበራውን አልፈህ ብትገኝ ደግሞ ሌላ የማይታለፍ ፈተና ይጠብቅሃል።

ይህ ማለት ምን ማለት መሰለህ? አንተ ባጋጣሚ ከተዋወቅካት ሴት ጋር ፍቅር ሊይዝህ ይችላል። የመጀመሪያውን ፈተና ማለፍህ ለፍቅርህ ዋስትና አይሆንም። ፍቅርህ ተቀባይነት እንዲያገኝ የምታሟላውን ማሟላት ይጠበቅብሃል። የስደትን ፍቅር ለመኮምኮም አሁንም ሁለተኛውን ማሟላት ያለብህን አሟልተህ ተገኝህ እንበል፤ የወደድካት ልጅ አንተን ሳይሆን ያሟላኸውን ነገር ስለወደደች ፍቅርህ ተጋጣሚ የሌለው ልፋት ይሆንብሃል ማለት ነው።

አንተ ዛሬ ፍቅር ለመመስረት ያሟላኸውን መስፈርት አስበልጦ የመጣ ሌላ ሰው ፍቅረኛህን የማይወስድበት ምክንያት አይኖርም። አንተም ገዛሃት፣ እርሱም ሻል ያለ ዋጋ መድቦ ይገዛታል። ይህ ውድድር ከአገርቤቱ የሚለየው የዚህኛው ምድር እሽቅድድም የገንዘብ ብቻ ሳይሆን የወረቀትም በመሆኑ ነው። የወረቀትም ብቻ አይደለም አንዳንዴም የዜግነትም ሲሆን ይታያል።

እሷ የምትሸጥ ሆና እንዳይመስልህ በመኖሪያ ፍቃድና በዜግነት የምትቀባበሏት። እሷንና ቤተሰቦቿን የተጫናቸውን የኑሮ ሸክም ለማቃለል ምርጫ ስለማይኖራት ነው። ስለዚህ ነው አታካች ጫወታውን እንኳን በትዕግስት ችለህ ብትዘልቅ ማባበሉን የማትዘልቀው። እየለመንክ እያባበልክ አፍቅሪኝ እያልክ መኖር? ከባድ ሥራ ይሆንብሃል።

ከምዕራቡ ዓለም ከሚገኝ አንድ ትልቅ ከተማ ትኖራለህ እንበል። በዚህ ትልቅ ከተማ ላይ እንደምትኖር ማኅበራዊ ግንኙነት ለመፍጠር በከፈትከው አንድ የኢንተርኔት መረብ ላይ ትጠቅስና የመረቡ የምታገኘውን በረከት መቋደስህን ትቀጥላለህ። ነገር ግን የምትኖርበት ከተማ በሰዎች ላይ ልዩነት ማምጣት የሚጀምረው ሳትውል ሳታድር ይሆናል። በውጭ አገር በመኖርህ አገር ቤት በሚኖሩት ሴት ወገኖችህ ላይ ለውጥ ማምጣት ይጀምራል። ሴት ከሆንሽም እንደዚሁ።

በቀላል ሰላምታ የሚጀመረውን ግንኙነት ለማስጨረስ ከቀረጥክ መጨረሻው ፍቅር እንዲሆን ትጋበዛለህ። የምትጠቀምበት የማኅበራዊ ግንኙነት ገጽ ላይ ፎቶህ እንኳን አለመኖሩን ስትረዳ ፍቅሩ ካንተ ሳይሆን ከምትኖርበት አገር ወይም ከተማ የመነጨ መሆኑን ስትገነዘብ በሐዘን ትወጋለህ።

ይህ ከሩቅ የምትፈጥረው ግንኙነት የአገር ቤቶቹ ወገኖቻችን ውጭ አገርን አክብዶ ከማየት ከሚመጣ የማኅበረሰባችን ሁለንተናዊ ችግር የመነጨ ይሆናል ትልና የችግሩ ምንጭ ‹‹ወያኔ›› ነው ብለህ በደፈናው ለማለፍ ትደፍርና ታልፈዋለህ፡፡ ነገር ግን እዛው አጠገብህ በምትኖርበት አገር ላይ ካሉት ወይም እንዳንተው ተሰደው ከሚኖሩት ወገኖችህ ተመሳሳዩ የፍቅር ግብዣ ሲደረግልህ ስትመለከት ነገሩ ስር መስደዱን ትገነዘባለህ፡፡

ማለቂያ የሌለው ችግራችን የት ድረስ እንደደረሰና ኢትዮጵያዊነት በየፈርጁ ወደማጡ እየገባ እንደሆነ ትረዳለህ፡፡ ድህነት ምን ያህል ማንነትን እንደሚቀይር፣ ክብርን እንደሚያስረሳ፣ ፀጋን እንደሚገፍ ታያለህ፡፡

አብሮህ ተሰዶ የስደቱ ገፈት ቀማሽ ከሆነ ሰው ነዋያዊ የፍቅር ግብዣ በአብዛኛው በሁለት መልኩ ሊቀርብልህ ይችላል፡፡ አንዱ አንተን ሳይሆን የመኖሪያ ፍቃድህን ለፍቅር የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሚያልፈው ጊዜ፣ የሚነጉደው ዕድሜ አማራጭ ሲያሳጣ በስተርጅና ሙሽርናን ለመሸሽ የሚፈጠር ፍቅር ይሆናል፡፡ ስለዚህና ለመጥቀስ ስለሚያታክቱ ብዙ ጥቃቅን ምክንያቶች የስደት ፍቅር ፍቅርነቱ ተነክቷል፣ ኃይሉን አጥቷል፣ ፀጋውን ወይም መንፈሳዊ ስጦታውን ተገፏል፡፡

የስደት ፍቅር ከጀርባው ያዘለው አታካች ዝባዝንኬ ስላለ ነገሩ ቢሰምርም እንኳን መንገዳገዱ አይቀርም፡፡ ፍቅሩ ሰርቶ፣ ልጅ አፍርቶ ቢቀጥልም እንኳ መቃሰቱ አይቀርም፡፡ ፍቅሩ ደርጅቶ በልጆች ቢደምቅም እንኳን ጥያቄ በአዕምሮ መጫሩ አይቀርም፡፡

ብቸኝነቱን፣ ብርዱንና ጨለማውን ለመቋቋም ከዚህ የተሻለ አማራጭ ስለማይኖር የስደት ሕይወት በቅርብ ካገናኘችህ ከአንዷ ጋር ትጣመራለህ፡፡ ወይ በስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውስጥ ወይ ደግሞ በሥራ ቦታ፡፡ ስደት ሲጀመር አብዝቶ ስለሚከፋ ክፉ ዘመንን በጋራ ለማለፍ ፍቅር ጥሩ ምሽግ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ጊዜውን ለመግፋት ብቻ ፍቅርን ተገን ታደርግና ካገኘሃት ጋር ትዋደዳለህ፡፡ አብራችሁ ሰርታችሁ ማደር ትጀምራላችሁ፡፡ ወልዳችሁ ትከብዳላችሁ፡፡

እንደአገር ቤት ቢሆን በዚህ መሐል በአንተ ወይም በእሷ ላይ ለሚፈጠር ችግር እርስ በርስ እየተጋገዛችሁና እየተሳሰባችሁ ማለፍ የግድ ነው፡፡ በስደት ሲሆን ግን እንደዛ አይሆንም፡፡ በመሃል ከደኸየህ? ሥራ አጥ ሆነህ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ተከልክለህ የተቸገርክ ከሆነ ‹አይዞህ፤ እኔ አለሁልህ› የምትል ሴት ከስንት አንድ ነች - በስደት ዓለም፡፡

ስለሆነም የነገር ኃይል ይበረታብሃል፡፡ ለልጆችህ ብለህ የምትችለው ነገር ቢሆንም ብዙ አሰልቺ የትዳር ሕይወት እንድታሳልፍ ስደቱ ያስገድድሃል፡፡ ያጣኸውን ሥራ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ እያማረርክ እንደባል ሳይሆን እንደተላላኪ እየተሸቀጠቀጥክ እንድትኖር ይፈረድብሃል፡፡

ይህ የሚሆነው በስደት ውስጥ ሴቶቹ ከፍተው አይደለም፤ ተመሳሳዩንና የባሰውን ድርጊት ወንዶቹም በሴቶቹ ላይ ሲያደርጉት ነው የኖሩት፡፡ ነገር ግን ሴቶቻችን ቻዮች ስለሆኑ ችግሩን በመቻል እንዳልተፈጠረ ያደርጉታል፡፡ ስለሆነም የስደት ፍቅር በየትኛውም መስፈርት ለማንም አይመከርም፡፡

የመኖርያ ፍቃድ ሲኖርህ የሚያገባህ አታጣም፡፡ የሚያፈቅርህ አታጣም የውሸት ቢሆንም፡፡ የመኖሪያ ፈቃድ ሲኖርህ ምንም ያህል ክፉተኛ ብትሆን፣ ምንም ያህል ሱሰኛና ለኑሮ የማትስማማ ብትሆን "ልጅን መውደድ ከነንፍጡ ነው" ብላ እንደ ልጅ ቆጥራህ የምትሸከምህ ሴት አታጣም፡፡

ለመከራ የተፈጠሩ የሚመስሉት ሴት እህቶችህ የሚሸከሙት የአረብን ክፋት ብቻ አይደለም፡፡ የሚሰቃዩት በአረብና በባዕድ ወንድ ብቻ አይደለም፡፡ የነዓለም ደቻሳን በደል አይተን በቁጭት የምንብሰለሰል እኛም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሴቶቻችን ሸክም ነን፡፡ የተቸገረ ቤተሰብ ከጀርባዋ የተሸከመች ሴት ለቤተሰቧ ትጨነቃለች፡፡ ስደት አልሰምርላት ያለች ሴት ስለራሷ ትጨነቃለች፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ የስደቱ የውሸት ሕይወት ሲታከልባት ሕይወቷን የከፋ ያደርገዋል፡፡ ከክፋት ደግነት እንደሚቀል የምናውቅ እኛ ስንጨመርበት ደግሞ ይታይህ፡፡

እንደምታውቀው መሪ፣ ነፃ አውጭ፣ ሽፋች ወንድ የሆነባት አገር ናት ኢትዮጵያ፡፡ የሚያሳዝነው ታዲያ ወንዶች ይህን መሆናቸው አይደለም፤ ኢትዮጵያችን የወንድ አገር በመሆኗ ምክንያት ያልተበላሸ ነገር አለመኖሩ እንጂ፡፡ እዚህም በስደት ሁሉን አዋቂ ወንድ ነው፡፡ ፖለቲከኛና ለአገሬ ሕዝቦች ነፃነትና እኩልነት እታገላለሁ የሚል አንድ ወንድ በአደባባይ የሚሰብካቸው ስብከቶች እቤቱ ውስጥ የሉም፡፡ በየሚዲያው፣ በየስብሰባው፣ በየቡና ቤቱ

የሚደሰኩራቸው የእኩልነት ዲስኩሮች እቤቱ አልዘለቁም። የሰብዓዊ መብት ተሚጋች የሆነው ወንድ ሁሉ የሰዎችን መብት ማክበር ከጓዳው እንደሚጀምር የረሳ ነው።

በየፓልቶኩና በየሚዲያው ሰለ አገር እንጨነቃለን የሚሉት ወንዶቻችን ስለጓዳቸው ነፃነትና ዴሞክራሲ አስበው አያውቁም። ይህም ስለሆነ በየስብሰባውና በየውይይት መድረኩ የምናገናቸው እነሱኑ ብቻ ነው። ይህ የአገር ቤት የወንዶች ተፅዕኖ በስደቱም ውስጥ ሳይቀየር እንደ እንጀራችን ተከትሎን ስለመጣ ፍቅርን ጨምሮ ያልተበላሸ ነገር ጥቂት ነው።

## ያልጠረጠረ ተመነጠረ

ሌላው አበሻዊ የስደት ፍቅርን አታካች የሚያደርገው ጥርጣሬ ነው። እንደ አበሻዊነትህ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ወገንህን መግባባት መብትህ ነው። ልትወዳትም ትችላለህ። ከዚህ አልፎ ለመሄድ ከፈለግህ እንደፖሊስ መታወቂያዋን ማየት ፍርድ ቤት ከመቆም ያድንሃል። ፍቅር ለመጠየቅ ባካል ባይነ ስጋህ የምታየው ዕድሜዋ በቂ ከመሰለህ ወደማትከፍለው ችግር ለመዝለቅ ቆርጠሃል ማለት ነው። አለበለዚያ በትህትና መታወቂያ መጠየቅ ይኖርብሃል። ከሃያ ምናምን ዓመት ወጣት ቆንጆ ጋር ፍቅር ጀመርኩ ብለህ ወደቤቷ ሸኝተሃት የልብህን ደስታ ወደ አካላትህ እያሰራጨህ ወደቤትህ ስትራመድ ዕድሜዋ ለምንም ያልደረሰች ሕፃን በማታለል ሕግ ጥሰሃል የሚል ክስ ይዞልህ ፖሊስ በርህ ላይ ሊጠብቅህ ይችላል። ስደት የሴቶቹን ዕድሜ በሁለት ይከፍለዋል። አንተ ባይነ ስጋ ስታይ የምታውቀውንና መንግስት የሚያውቀውን።

ልደታቸው ሁለት ነው። እትብታቸው የተቀበረበት አገር ላይ የሚከበረው ልደታቸውና በሰው አገር ሲኖሩ ያስመዘገቡት ስደት ነክ የሆነው የልደት ቀን።
የስደት ዕድሜዬን እርሳው ብላህ ፍቅርህን ብትቀጥል እንኩዋን እንደ ግንቦት ሰባትና ኦነግ ፖለቲካ ምድር ለምድር ፍቅርህን እንድትዘረጋ ግድ ይልሃል። ስለፍቅራችሁ ማንም ማየትም ሆነ መስማት አይኖርበትም። ምን ይታወቃል አንተን የወደደች አንዲት ቆንጆ ወይም እሷን የጠላት አንድ ስደተኛ “ወንጀል ሲሰራ እያየ ዝም ያለ” የሚለውን ሕግ ፈርቶ ቢጠቁምብህስ። ስለዚህ የወደደ ሰው ፍቅር ለመጀመር የአፍቃሪውን መታወቂያ በገሃድ ጠይቆ ማየት ወይም በድብቅ በጨረፍታ የትውልድ ዘመኗን ማየት ሕግ ጥሰሃል ከመባል ያድናል።
አብሮ መኖርና ትዳር ለመመስረት ካሰብክ ደግሞ ማወቅ ያለብህ እድሜዋን ብቻ አይደለም። አንድ አይነት ቋንቋ እያወራችሁ፣ አንድ ዓይነት ምግብ እየበላችሁ፣ አንድ ዓይነት ዓውደ-ዓመት እያከበራችሁ ፍቅራችሁን መቅጨታችሁ አገራችሁን አንድ አያደርገውም። አገራችሁ አንድ ባይሆንም ችግር አይኖረውም ነገር ግን ከመገረም ለመዳን ቀድሞ ማወቁ አይከፋም። ስለዚህ ዜግነቷም አንተ ካልጠበቅከው አገር ሊሆን ስለሚችል መታወቂያዋን ማየት ወሳኝ ነገር ነው። ልትፈራረም ማዘጋጃ ቤት ሄደህ ዜግነቷ ኤርትራዊ ወይ ሶማሊያዊ ነው ሲሉህ ዓይንህ እንዳይፈጥ ቀድመህ ማወቁ አይከፋም።

ለዕድሜዋና ለዜግነቷ ብቻ እንዳይመስልህ መታወቂያ ማየት ያለብህ። አንተ እያቆላመጥክ የምትጠራው ስሟም ሌላ ሊሆን ይችላል። የተዋወቀችህ እናትና አባቷ ያወጡላትን የምትወደውን ስሟን ነግራህ ሊሆን ይችላል። አንተ ከስሟ ምንም የለህ ከፍቅሯ እንጂ። ግን አንድ መጠይቅ ቀርቦልህ ልትሞላ ብትፈልግ የሚስትህ ሙሉ ስም ከሚለው መጠይቅ ስር ምን ልትሞላ ነው? ያንን ከመሙላትህ በፊት መታወቂያዋን መጠየቅ ያስፈልግሃል። ያኔ ታዲያ ከዚህ በፊት ጠርተኸው፣ ሰምተኸውና ለማቆላመጥ የማያመች አዲስ ስም ታገኝ ይሆናል። እንዲያም ሲገጥምህ ምን ይደረጋል ብለህ አዲሱን ስሟን እንደዳቦ ስም ቆጥረህ ማለፍ ነው።
ይህን ሁሉ ነገር ስታይ ሌላም ጥርጣሬ በሆድህ ሊፈጠር ይችላል። ብዙ ብዙ ጥርጣሬ።

## ‹‹ሕዝብ›› ምንድን ነው?

በክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳን ውስጥ የሙሴ ታሪክ ትልቅ ሥፍራ ይሰጠዋል፡፡ ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፆች ቅኝ ተገዢነት ነፃ ያወጣ መሲህ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሕዝቡ በሙሴ ላይ ያፈነገጥ እንደነበር ዘጸአት፣ ምዕራፍ 32 (ቁጥር 1 - 4) ይተርክልናል፡-

*"ሕዝቡም ሙሴ ከተራራው ሳይወርድ እንደ ዘገየ ባዩ ጊዜ፥ ወደ አሮን ተሰብስበው ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ ምን እንደ ሆነ አናውቅምና ተነሥተህ በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሥራልን አሉት፡፡ አሮንም፣ በሚስቶቻችሁ በወንዶችና በሴቶች ልጆቻችሁም ጆሮ ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች ሰብራችሁ አምጡልኝ አላቸው፡፡ ሕዝቡም ሁሉ በጆሮቻቸው ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች ሰብረው ወደ አሮን አመጡለት፡፡ ከእጃቸውም ተቀብሎ በመቅረጫ ቀረጸው፥ ቀልጦ የተሠራ ጥጃም አደረገው፤ እርሱም፡፡ እስራኤል ሆይ፥ እነዚህ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው አላቸው፡፡"*

በ1997 ተቃዋሚዎችን የመረጠ ሕዝብ በ2002 ገዢውን ፓርቲ ይመርጣል፣ በ2008 ለኦባማ ራሱን የሳተ ሕዝብ በ2012 ለራምኒ ይዘምራል፡፡ ይህ ሕዝብ ምን ዓይነት ፍቺ ይገኝለታል? በዚያው በምርጫ 97 ሚያዝያ 29 ኢሕአዴግን በመደገፍ ‹‹ማዕበል›› ለመሰኘት የበቃ ሕዝብ መስቀል አደባባይ ወጣ፤ በማግስቱ ሚያዝያ 30 ከዋዜማው እጥፍ የበዛ (‹‹ሱናሚ›› የተሰኘ) ሕዝብ ወጣ፤ የቱ ነው ሕዝብን በትክክል የሚገልፀው?

ዘርጋው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ‹‹ሕዝብ›› የሚለውን ቃል ሲፈታው ‹‹በአንድ አገር፣ ከተማ፣ ክልል፣ ገጠር ውስጥ የሚኖር ጠቅላላ የሰዎች ቁጥር፣ ብዛት›› ይለዋል፡፡ በርግጥ ይህ መዝገበ ቃላት እንደሚለው ‹‹ሕዝብ›› ቁጥር ብቻ ነው ወይስ ሌላ ትርጉም ይኖረው ይሆን? በየፈርጁ እንመለከተዋለን፡፡

### ሕዝብ ሕገመንግሥቱ ውስጥ

የኢፌዲሪ ሕገመንግስት (1987) በመግቢያው ላይ ‹‹እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች፡-›› ብሎ ይጀምራል፡፡ አካሔዱ ከላይ - ሁሉንም ብሐሮች ካቀፈው ስብስብ (set) ወደታች - ነጠላ ብሔር/ብሔረሰብ (subset) ስለሚወርድ ‹‹ሕዝቦች›› የሚለውን ‹‹የተለያየ የዘር ሐረግ ያላቸው ሰዎች ስብስብ›› ብለን ልንፈታው እንድንዳዳ ያደርገናል፡፡ ግን ደግሞ የአገር ውስጥ ፖለቲካ ዕውቀታችንን ስናስታውስ ሕዝቦች የሚባሉት የብሔር ዕውቅና ያላገኙ፣ የአንድ ቋንቋ እና ባሕል ባለቤቶች ናቸው፡፡ ይሄ ትርጉም የትም ስለማያደርሰን ሌላ የ‹‹ሕዝብ›› ትርጓሜ ፍለጋ እንጓዛለን፡፡

የሕገመንግስቱ ፈጣሪ ኢሕአዴግ ነውና፣ በግንባሩ ስያሜ ውስጥ ያለው ሕዝቦች ማንን እንደሚወክል እንጠይቅ፡፡ ግንባሩ የብሔር ፓርቲዎች ስብስብ ስለሆነ ብዙ ብሔሮችን በአንድነት ‹‹ሕዝቦች›› ብሏል ስንል ደግሞ እላይ ከደረስንበት ድምዳሜ የተለየ ትርጉም እናገኛለን፡፡

### ሕዝብ በቁጥር

ነገሩን በምሳሌ እንጀምረው፤ ‹‹የአዲስ አበባ ሕዝብ ኢሕአዴግን መረጠ›› ሲባል ምን ማለት ነው? በ2000ው የሕዝብ ቆጠራ መሰረት ከ1.88 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ፖለቲካዊ ምርጫ ለመምረጥ ዕድሜያቸው ይፈቅድላቸዋል፡፡ ነገር ግን ድምጻቸውን የሰጡት 1.04 ሚሊዮን ያክሉ ብቻ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ደግሞ 0.56 ሚሊዮኖቹ ብቻ ናቸው ለኢሕአዴግ ድምጻቸውን የሰጡት (ማለትም ዕድሜያቸው ከደረሱ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች አንፃር 30% ያክሉ ብቻ)፡፡ ነገር ግን የአዲስ አበባ ሕዝብ ኢሕአዴግን መረጠ ይባላል፡፡

‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞት መሪር ሐዘን አዘነ፣ መተኪያ እንደሌላቸውም ተናገረ›› ሲባልስ የትኛውን ሕዝብ ነው? ስንት ያክሉን ሕዝብ ነው?

### ሕዝብ በአስተያየት እና ፍርድ አሰጣጥ

‹‹ሕዝብ ይፈርዳል፤›› እርግጥ ነው ሕዝብ ብዙ ነገሮችን አንድ ላይ አመሳክሮ ይፈርዳል፣ የፍርድ ባለቤትም ስለሆነ ፍርዱ ቢወደድም ቢጠላም ይፀድቃል፡፡ ሕዝቦች ሶቅራጠስን፣ እየሱስን እና ሌሎችንም ያለዘመናቸው የተፈጠሩ

ነብዮችን እንደተሳሳቱ ፈርዶ አይቀጡ ቅጣት አስቀጥቷቸዋል፡፡ ስለዚህ የሕዝብ ፍርድ ሁሌም ፍትሐዊ ነው ማለት ይቻል ይሆን?

**ሀ). ሕዝብ for dummies**

ሕዝብን እና ፍርድ አሰጣጡን፣ ወይም ውሳኔ አስተላለፉን በገደምዳሜው ከተቋረ ውሃ ጋር ማመሳሰል ይቻላል፡፡ አንድ የውሃ ኩሬ ቦይ ከተቀደደለት፣ መጨረሻው ገደልም ይሁን ግድብ፣ በየትም በኩል ይቀደድለት በየትም ዝም ብሎ ይፈሳል፡፡ አንድ ኩሬ ውስጥ የተቋረ ውሃ የኬሚካል ጠብታ ብናፈስበት፣ ኬሚካሉ መርዝም ይሁን መድሃኒት ወዲያው ይቀላቀላል፡፡ ቅልቅሉም እንደኬሚካሉ ብዛት በውሃው ውስጥ ሰርፆ ይቀራል፡፡

ሕዝብም እንዲሁ ነው፡፡ የመገቡትን ሐሳብ አዳኝም ይሁን አጥፊ ይቀበላል፡፡ የከፈቱለትን መንገድ መጨረሻው ይመርም አይመር ይከተላል፡፡

ግለሰቦች የተሰጣቸውን ሐሳብ መመርመር ሲጀምሩ፣ ወይም ‹‹ለምን?›› ብለው መጠየቅ ሲጀምሩ ከ‹‹ሕዝብ›› ተራ ይወጣሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ ጠያቂ ግለሰቦች በተቀደደላቸው በመፍሰስ ፈንታ ቦይ ቀዳጅ፣ ፈር ቀዳጅ ወይም መሪ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ከሕዝብ የጋርዮሽ ሐሳብ አራማጅነት ያፈነገጡትን ግለሰቦች እንበላቸው እና ስለሕዝብ ምንነት እናስረዳቸው፡፡

**ለ) ሕዝብ ለግለሰቦች**

ሕዝብ ባገኘው ሁሉ መንገድ የሚማር ከዘመን ዘመን እያደገ፣ እየተሻሻለ የሚሄድ በአንድ አካባቢ ወይም አገር ለረዥም ዘመናት አብረው የሚኖሩ ትውልዶች ስብስብ ነው፡፡ ሕዝብ ካገኘው ነገር ሁሉ ትምህርት እየቀሰመ፣ በቀሰመው ነገር ላይ ተመስርቶ ባሕሉን እና እሴቱን የሚገነባ፣ በገነባው እሴት ላይ ተመስርቶ ፍርድ የሚሰጥ፣ ግለሰቦችንም ሆነ ሁነቶችን ገገር/ከሳች አካል ነው፡፡

በዘመናችን ሕዝባዊ አስተሳሰብን ከሚፈጥሩ ነገሮች ውስጥ
(1) ትምህርት፣
(2) መገናኛ ብዙሐን እና
(3) ስርዓተ አምልኮ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

እነዚህን ሦስት የሕዝባዊ አስተሳሰብ ምንጮች የሚገብሩት ዕውቀት የሕዝቡን ትውፊት፣ ባሕል፣ እሴት ይቀርጻሉ፡፡ ስርዓተ አምልኮን በተመለከተ ወደፊት አዳዲስ ሃይማኖቶች እና አማልክቶች የመፈጠር ዕድላቸው ጠባብ ነው፤ ቢፈጠሩም አማኝ/አምላኪ የማግኘት ዕድል የላቸውም፡፡ መገናኛ ብዙሐን እና ትምህርት ግን መቆሚያ የላቸውም፡፡

መንግስታት ስርዓተ ትምህርትን እና መገናኛ ብዙሐንን የሚቀርፁበት መንገድ ምን ዓይነት ሕዝብ ማፍራት እንደሚፈልጉ ያሳብቃል፡፡ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ለትምህርት በጣም ጉጉ ከመሆናቸው የተነሳ አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ጥረት ትምህርትን ለማስፋፋት አድርገዋል፡፡ ሚኒስትሮቻቸውም ጥሩ የትምህርት ደረጃ የነበራቸው እንጂ እንደአሁኑ ዘመን በፓርቲ ታማኝነት ብቻ የሚሾሙ አልነበሩም፡፡ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ሕዝብ እንዲያውቅ እና እንዲነቃ ያደረጉት ሙከራ በራሳቸው/በአስተዳደራቸው ላይ የሚያምፅ ትውልድ እንዲያፈራ ሆኗል፡፡

አሁን የእርሳቸውን ተቃራኒ እየተከተሉ ያሉት መሪዎች የፈጠሩት የትምህርት እና መገናኛ ብዙሐን ስርዓት ግን በአሁኑ ሰዓት ለሚስተዋሉት አምባገነን ገዢን የመቀበል (እና ‹‹መተኪያ አይገኝላቸውም›› ብሎ የመስጋት) እውነታዎች መንስኤ ነው፡፡

ሕዝብ የስርዓት ውጤት ነው፤ ጠያቂን ሕዝብ መፍጠር የመንግስት ግዴታ እንጂ መብት አይደለም፤ ጠያቂ መሆን ደግሞ የሕዝብ መብት ነው፡፡

# የሴቶች ወጪ <=> የወንዶች ገቢ

ሴቶች በዝግመተ ለውጥ ካለመቆጠር ወደ መቆጠር ከመቆጠርም አልፈን ‹ከስኬታማ ወንድ ጀርባ አንዲት ጠንካራ ሴት አለች› የሚባልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ተፈጥሮና ባህላችን ተደማምረው አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር የሴትና የወንድ የሆኑ ነገሮች እንዲለዩ ሆነዋል። የሥራ ዘርፍ፣ የትምህርት ዘርፍ፣ አለባበስ፣ አነጋገር፣ አካሄድ፣ አጻጻፍ፣ ባሕሪ፣ አመለካከት… ሁሉም የሴት እና የወንድ የሚባሉ አሏቸው። ጥልቅ የመመራመር ክህሎትን በሚጠይቁ ዘርፎች ተሰማርተው የሚገኙ አንዳንድ ሴቶች የተቀረነውን ወክለው የተቀመጡ እንጂ እንደወንዶቹ እራሳቸውን ብቻ ወክለው አይደለም። ለምሳሌ ‹የመጀመሪያው የወንድ ጄኔራል› የሚባል ነገር ሰምተን አናውቅም። ‹በመጀመሪያ ወደጠፈር የተጓዘው ወንድ› ሲባል ልንሰማም አንችልም። ምክንያቱም መጀመሪያውኑ ወደ ጠፈር የመጓዝ ተግባር እና የጦር አዛዥነት ሥራ የወንድ ብቻ ተደርጎ ስለሚቆጠር እና በዘርፉም የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶቹ ጋር ሊነፃፀር የሚችል ስላልሆነ ነው።

በአገራችን ከተለመዱና የወንዱ ተግባር ተደርገው ከሚቆጠሩ ነገሮች አንዱ ወጪዎችን የመሸፈን ኃላፊነት ነው። እስካሁን ድረስ ‹ሴትማ አትከፍልም› እየተባለ የከፋይነት ሥራ የወንድ እንደሆነ ቀጥሏል። ማኅበረሰባችን ለወንድ የወጪ ሸፋኝነት ኃላፊነት ሲሰጥ በውስጥ ታዋቂነት ጥሮ ግሮ በሚያፈራው ኃብት የሚመሰርተውን ቤተሰብ የማስተዳደር ሥራ ከሱ እንደሚጠበቅ ይረዳዋል። ስለዚህም በተሰማራበት ዘርፍ ጠንክሮ በመሥራት ገቢውን ማሻሻል የሕይወት ዘመኑ መመሪያው ይሆናል። ከሴት የሚጠበቀው ጥሩ ሚስት እና እናት እንድትሆን ነው። የራሷ ገቢ የምታገኝበት መተዳደሪያ ወይም ሥራ ያላት ብትሆንም እሰየው ነው፤ ባይኖራትም ግን ችግር የለውም። እንዲኖራት አትገደድም።

ወንድየው ወደፊት ለሚያገባት ሚስቱና በጋራ ለሚያፈሯቸው ልጆች ማስተዳደር እንዲችል ገቢውን ለማሳደግ እና ኃብት ለማፍራት ተግቶ ይሠራል። ‹ቤት ሳይኖረኝ› ‹ቋሚ ሥራ ሳልይዝ› ‹ጥሩ ደሞዝ ሳይኖረኝ› የሚሉ ወንዶች እንጂ ሴቶች እምብዛም አይደሉም። ባጭሩ ማኅበረሰባችን ለሴቶችና ለወንዶች ብሎ ሁለት የተለያየ የተግባር መንገድ አስቀምጦልናል። በሴቷ መንገድ የሚገኙ ወንዶች እንዲሁም በወንዱ መንገድ የሚገኙ ሴቶች ቢኖሩም በአብዛኛው ሴቱም ወንዱም በተመደበለት መንገድ ነው የሚንቀሳቀሰው። ይህ አመዳደብ ወንዶችን የሴቶች የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሆነው በበላይነት እንዲመሩን ያደርጋቸዋል። እኛ ሴቶችም በአብላጫ ድምፅ ያፀደቅንላቸው ይመስላል።

የዩንቨርስቲ ተማሪ በነበርኩበት ወቅት ከሴት ጓደኞቼ ጋር እራት እንበላ ብለን የካፌ ምግብ ትተን በከተማው ወደሚገኝ ሬስቶራንት ከሄድንባቸው ጊዜያቶች በአብዛኛው ለማለት ባልደፍርም ሒሳባችን በማናውቀው ሰው ተከፍሏል እንባል እንደነበር አስታውሳለሁ። ግብዣው ሲደጋገምብን ነገሩ ጣመንና እራሳችን ስንከፍል መበሳጨት ደረጃ ደረሰን ነበር። የሚከፍልልን እንደማናጣ በመተማመን ምንም ሳይኖረንም ወጥተን እራት እስከማዘዝ የደረስንበት አጋጣሚም እንዲሁ ትንሽ አልነበረም።

በሥራ ዓለም ያለች አንድ ወዳጄ ስታጫውተኝ ከጓደኞቿ ጋር በእረፍት ቀናቸው የሚጋብዛቸው ወንድ ለማግኘት ፕሮግራም እንዳለበት ሰው ዘንጠው፣ ረፈድፈድ ሲል ተያይዘው ይወጡና መጋበዝ የሚፈልጉበት ሬስቶራንት ወይም ሆቴል አካባቢ ያለ ካፍቴሪያ ይቀመጣሉ። መቼም ከሦስት ወይም ከአራት ሴት ቢያንስ አንዷ በእረፍት ቀን ደውሎ ‹ምሳ ልጋብዝሽ› የሚል አድናቂ አታጣምና የተደወለላት ሴት ያለችበትን ቦታና ከጓደኞቿ ጋር እንደሆነች በማሳወቅ መምጣት እንደሚችል ትነግረዋለች። ይመጣና እዛው ሻይ ቤት ቆይተው ምሳ ሰዓት ሲደርስ ‹የት እንብላ?› ሲባል ያው በቅርብ የሚገኘው ሬስቶራንት ወይም ሆቴል ይመረጥና ያሻቸውን ይበላሉ ያማራቸውን ይጠጣሉ። ከፋዩ የታወቀ ነው። ጋባዡን ያመጣችው ሴት ከጎኑ ከሌሎቹ በተለየ ቀረብ ብላ የመቀመጥ የውዴታ ግዴታ አለባት። ሊጋብዝም አይደል! ይህ ሰው በድጋሜ ላግኝሽ ብሎ ላይደውልላት ቢችልም ግድ አይሰጣትም። ወላድ በድባብ ትሂድ አይደል የሚባለው ለሚቀጥለው ሳምንት ደግሞ የሌላ ጓደኛቸው አድናቂ ወይም አዲስ የሚገኝ ስፖ (ስፖንሰር ተቆላምጦ ሲጠራ) አይጠፋም። ይህ ሁኔታ በጠንካራ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ የፍቅር ሕይወት ስትጀምር ወይም ትዳር እስክትይዝ ድረስ ሊቀጥል ይችላል።

ከወዳጄ የሰማሁትን በምሳሌነት ጠቀስኩ እንጂ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ሌሎች በቁጥርና በዓይነት የበዙ ታሪኮች ያደባባይ ሚስጥር መሆናቸው የማይካድ ሐቅ ነው። እንዲያውም አንባቢ ቢያንስ አንድ ከዚህ ጋር የተያያዘ እውነተኛ ገጠመኝ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ። በአስተያየት ቢያሰፍረውም ደስ ይለኛል።

ሴቶች ፍቅረኛ ከመያዛቸው በፊት ‹በስፖንሰር የመዝናናት እና ወጪን መሸፈን› መርሕ ላይ የተመሰረተ ኑሮ ለምደው፥ ፍቅረኛቸውን ወይም የትዳር አጋራቸውን በሚመርጡበት ወቅት ምርጫ ውስጥ የሚያስገቡት ወንድ ከስፖዎች ያልተናነሰ ወጪያቸውን ሊሸፍን የሚችለውን ነው፡፡ ከጓደኛቸው ያልተናነሰ ኑሮ ለመኖር ከመሻት ወይም የተሻለ ከመመኘት እና ቤተሰብን ለማስደሰት ያላቸውን ፍላጎት ለሟሟላት በዕድሜ በጣም ከሚበልጧቸው፣ ከውጭ አገር ዜጎች እና ባለትዳር ከሆኑ ጋር የፍቅር ግንኙነት ይጀምራሉ፡፡ ‹ሴቶች ፍቅረኛቸውን የሚመርጡበት ዋነኛው መስፈርት የኃብት መጠን ነው› የሚል ትችት ከወንዶች በተደጋጋሚ የሚሰነዘረውም ለዚህ ይመስላል፡፡ በዚህ መልኩ የሚመሰርቱት የፍቅር ጓደኝነት ወይም ትዳር ሴቶችን በቀጥታ የወንዶች የኢኮኖሚ ጥገኛ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ሴቶቹ ወጪያቸውን በራሳቸው ችለው ለመኖር ስለማይችሉ ባያምኑበትም ለወንዱ ትእዛዝ እና ፍላጎት ተገዝተው እንዲኖሩ ይገደዳሉ፡፡

በርግጥ ለሴቶች እንዲህ ዓይነት ባሕሪ ማሳየት ማኅበረሰባችን ከፍተኛውን ሚና ቢጫወትም በተለይ በጉዳዩ ላይ ተዋናይ የሆኑት ወንዶችና ሴቶች ተጠያቂ ከመሆን አይድኑም፡፡ በዋነኝነት ግን ከወንዱና ከሴቱ ተጠያቂው ማነው ለሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት ጉዳዩን እንደማውራት ቀላል አይደለም፡፡ ከዶሮና ከእንቁላል ማን ቀድሞ ተፈጠረ ዓይነት ነገር ነው፡፡ ወንዶች ጊዜያቸውን፣ ዕውቀታቸውን እና ጉልበታቸውን ተጠቅመው በሚያገኙት ገቢና ኃብት በመጠቀም አብራቸው የፍቅር ጊዜ ለማሳለፍ የምትፈቅድ ሴት እስክትገኝ ድረስ ያለመሰልቸት ሴቶችን ለማዝናናት ሲያውሉት ምንም አይመስላቸውም፡፡ ገቢያቸው እራሳቸውን ለማዝናናት የማይፈቅድላቸው ሴቶችም ወጪያቸውን ሸፍነው ሊያዝናኗቸው ፈቃደኛ በሆኑ ወንዶች ይደለሉና በስፖንሰር የመዝናናት መስመር ውስጥ ይገባሉ፡፡ ገንዘቡን ለዚህ ተግባር የሚያውል ወንድ ባይኖር ሴቷ በዚህ መስመር አትገኝም፤ እንዲሁም ገንዘብ የማያማልላት ሴት ብትኖር ኖሮ ወንዱ የፈለጋትን ሴት ለማግኘት ገንዘቡንና ሃብቱን ባልተማመነ ነበር፡፡ ለዚህም ነው የችግሩ መንስኤ ‹ሴት ናት›፣ ‹ወንድ ነው› ብሎ ለመፍረድ የሚከብድ የሚሆነው፡፡ እንዲያውም በመሀል ቤት የሴትና የወንድ የፍቅር ግንኙነት ወደ ‹ነፃ ገበያ›ነት እንዳይጠጋ ስጋት አለኝ፡፡

ስለዚህም ወንዶች ገንዘባቸውንና ኃብታቸውን ተማምነው ሴቶችን ለማጥመድ የሚያደርጉትን ጥረት እና ወጪዎችን መሸፈናቸውን በመተው እኛ ሴቶች የራሳችንን ወጪ መቻል እንዳለብን እንድናስብ ቢያደርጉ፤ ሴቶች ደግሞ ‹እቤት ከመዋል› ብለን ብቻ መሥራታችንን ትተን ገቢያችን ወጪያችንን እንዲችልልን የተቻለንን ሁሉ ጥረት ብናደርግ፣ ፍላጎታችንን ከገቢያችን ጋር ብናመጣጥነው እና ዓላማ ኖሮን ለምንመሠርተው/ለመሠረትነው ኑሮ በኢኮኖሚ ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ ማድረግ ብንጀምር እንዲሁም የራሳችን የሆነ አቋም ቢኖረን ወደፊት ብዙ ለውጦችን እናያለን ብዬ አምናለሁ፡፡ የአሁን ዘመን ወጣት ሴትና ወንዶች የመጪው ትውልድ ወሳኝ የማኅበረሰብ ክፍሎች ነንና፡፡

በመጨረሻም፣ ይህ ጽሑፍ የማይወክላቸው ጥቂቶች እንዳሉ ሳላስታውስ አላልፍም፡፡

# የትችት ባሕላችንን ብንተቸውስ?

ከግሪክ፣ የኤሶጵ ተረቶች አንዱ እንዲህ ይተረካል። አንድ ሰውዬ እና ልጁ፣ አህያቸውን አስከትለው ወደገበያ ሲሄዱ የተመለከታቸው የአገሩ ሰው፣ ‹‹እናንት ሞኞች፣ አህያው እኮ የተፈጠረው ሊጋለብ ነው›› ይላቸዋል። አባት ልጁን አህያው ላይ ጭኖ ትንሽ እንደተጓዙ የሆኑ ሰዎች ይመለከቱ እና ‹‹ምን ዓይነት የተረገመ ልጅ ቢሆን ነው አባቱን በእግሩ እያስኬደ እሱ የሚጋልበው?›› አሉ። አባት ልጁን አስወርዶ ራሱ መጋለብ ቀጠለ፤ ጥቂትም ሳይጓዙ ግን ‹‹ምን ዓይነት ክፉ አባት ነው ልጁን በእግሩ እያስኳተነ እሱ አህያ የሚጋልብ?›› ብለው የሚተቹ ሰዎች አለፉ። ግራ የተጋባው አባት ልጁን ከኋላው ጭኖ አህያውን ለሁለት ይጋልቡት ጀመር። ይህንን የተመለከቱ ሰዎች ‹‹ምን ዓይነት ጭካኔ ነው፣ አንድ አህያ ለሁለት የሚያስጋልባችሁ?›› አሏቸው። ግራ የተጋቡት አባትና ልጅ በመጨረሻ አህያውን ለሁለት ተሸክመውት ገበያ በመግባት የገበያተኛው መሳለቂያ ለመሆን በቅተዋል።

የተረቱ ሞራል፣ ሁሉንም ማስደሰት እንደማይቻል ነው። ይሁን እንጂ ሁሉንም የሚያስማማ መፍትሄ ባይገኝም ቅሉ ለትችቱ መፍትሄ ለመስጠት ባደረጉት መፍጨርጨር አባት እና ልጅም በፈረቃ ጋልበዋል፣ አህያውም አርፏል። የሚቀበሉትን ትችት ማወቅ እና አለማወቅ፣ ብሎም ለትችቱ ሁነኛውን መፍትሄ መፍጠር የተተቺው ድርሻ ቢሆንም ‹ትችት› ግን የማይቀር እና ሊቀር የማይገባው ነው።

አሁን የራሳችንን ትችት ባሕል ወደመተቸት እናልፋለን፤ የትችት ባሕላችንን ከመተቸታችን በፊት ግን ለቃሉ ትርጉም በማበጀት ብንጀምር መልካም ነው። ‹ትችት› የሚለው ቃል ከመነሻው አሉታዊነት እንዳለበት የሚከራከሩ አሉ። እነዚህ ተከራካሪዎች ‹ሂስ› የሚለው ቃል የተሻለ አስማሚ እንደሆነ ይናገራሉ። በሁለቱ ቃላት መካከል ያለውን ልዩነት ማስታረቅ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ስላልሆነ - ሳይስማሙ እንዲኖሩ እንተዋቸውና ‹ትችት› በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እንዲኖረው ስለሚፈለገው ትርጉም እንነጋገር።

‹ትችት› በዚህ ጽሑፍ ውስጥ *‹‹በሆነ ርዕሰ ጉዳይ፣ ሐሳብ፣ ፍልስፍና፣ ድርጊት ወይም የሥራ ውጤት ላይ የሚሰነዘር፣ በምክንያት ላይ የተመሰረተ የተቃርኖ ወይም የነቀፌታ አስተያየት ነው።››*

በአገራችን ለትችት የተነወሩ (አይነኬ) በርካታ ጉዳዮች አሉ። ከነዚህ ጉዳዮች መካከል ለጠቅላላ የትችት ባሕላችን ጉብጠት ምሳሌ ይሆናሉ በሚል በጥንቃቄ የመረጥኳቸውን ጉዳዮች እያነሳሁ ለማቅናት እደረድራለሁ። ትችቱ ያልተስማማው የመልስ ምት ቢጽፍ በዞን ዘጠኝ ጦማር ላይ ለማስፈር ከወዲሁ ቃል እገባለሁ።

## እምነትን መተቸት

የብዙዎቹ ሃይማኖቶች መሠረት እምነት መሆኑ ይታወቃል፤ እምነት ደግሞ ብዙውን ጊዜ የሚቆመው በማስረጃ ሳይሆን በእምነት በራሱ ነው። የእምነት እና የሃይማኖት ዋጋ ባልሰለጠኑ አገራት ከፍተኛ ነው፤ ይህንን የሚያሳዩ በተለያዩ ጥናቶች ሲኖሩ፥ እንደምሳሌም፣ ኢ-አማኒዎች በአውሮፓ አገራት እስከ 60 በመቶ ቢደርሱም ከሰሃራ በታች በሆኑ የአፍሪካ አገራት ግን ከ1 በመቶ በታች ናቸው፤ በኢትዮጵያም ያለው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። ይህ የእምነት ዋጋ፣ በትችት ባሕላችን ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተጽዕኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ቅዱስ መጽሐፍቶችን እና አምልኮተ ስርዓቶችን የማይመረመሩ፣ የማይገመገሙ እና የማይሻሩ ሆነው እንዲቀሩ በማድረጉ ዛሬም ድረስ በድሮ ጋሪ እየተጎተቱ ለመኖር የሚያስገድድ ሁኔታ እንዲፈጠር መንስኤ ሆኗል። ይህ ከትችት ባሕላችንጋ ምን ያገናኘዋል የሚሉ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን እምነት አጥባቂ የሆኑ አገራት ሕገመንግስታቸው ላይ የሚኖራቸው አመለካከት እና ቅዱስ መጽሐፍታቸው ላይ የሚኖራቸው አቋም እምብዛም እንደማይራራቅ ይሰማኛል።

በኢትዮጵያ ከፍተኛ ድርሻ የያዙት ክርስትና (በተለይም ኦርቶዶክስ ተዋህዶ) እና እስልምናን ብንመለከታቸው ከሌላው ዓለም ትንሽ ለየት ያለ ገጽታ አላቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎችም ከባሕሉ ጋር ተቀላቅለው፣ አንዳንድ ባሕላዊ ወጎች እንደሀይማኖቱ ቀኖና፣ አንዳንድ የሀይማኖት ስርዓቶችም እንደባሕሉ መሰረት ሆነው ቆመዋል። በውጤቱም ሁለቱንም መንካት የማይቻልበት ድባብ ፈጥሯል።

እንደምሳሌ አንድ ጠቅሰን እንለፍ። ሕዝብ በሚበዛባቸው የመኖሪያ ስፍራዎች ቤተክርስትያኖች እና መስኪዶች ተመስርተዋል። ሁለቱም ተቋማት ከፍተኛ የሆነ ድምጽ በሌሊት ያወጣሉ፣የአምልኮ መዝሙር/መንዙማቸውን ካሴት ለማስተዋወቅ ሕዝብ በተሰበሰበበት ስፍራ በከፍተኛ ድምጽ እያስጮሁ ያስተዋውቃሉ… ይህ እውነት በሁሉም ሰው የሚታወቅ ገሀድ ቢሆንም እልባት ይደረግለት በሚል፣ ለመንግስት አቤቱታ የሚቀርብበት ፈርማ

የሚያሰባስቡ ወገኖች ቢፈጠሩ ውጤቱ ምን የሚሆን ይመስላችኋል? ተቆርቋሪ ነን የሚሉትና የሚቃወሙት ወገኖች በምክንያት ማስረጃ ለመበላለጥ እና ለማሸነፍ የሚደራደሩ ወይስ ቤተ ሃይማኖቴ ተደፈረብኝ በሚል ጦርነት የሚካፈቱ?

## ብሔር ነክ ትችቶች

ብሔር ነክ አስተያየቶችን መሰንዘር በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከነውርም የከፋ ነውርም እየሆነ መጥቷል። አንዱ በሌላው ላይ በአነጋገር ዘዬው (ሌላው ቀርቶ በአንድ ቋንቋ አሜሪካዊው በእንግሊዛዊው ወይም በተቃራኒው) መቀለድ የተለመደ ነው። ወደእኛ አገር ሲመጣ ግን ዘረኝነት፣ ጥላቻ እና ጭቆና የሚል ባጅ ይለጠፍበታል። ቀልድ እንዲህ የሚያስፈርጅ ከሆነ መሠረታዊ የሆነ ትችት ምን ሊያስከትል እንደሚችል ማሰብ አስፈላጊ ይሆናል።

‹‹የሃማሴን እና አጎራባች ነዋሪዎች/ተወላጆች አንበጣ (‹‹ክረምት አግቢ››) ይመገባሉ፤›› ብሎ የሆነውን ሆነ ቢል በማሕበራዊ የስነምግባር ሕግ የሚያስቀስፍ ወንጀል ነው። ከወዲያኛውም ሆነ ከተናጋሪው ወገን እነዚህን እንስሳት መብላት ምንድን ነው ጥፋቱ? ወይም እነዚህን መብላቱ እንዲህ ዓይነት ችግር ያስከስታል እያሉ ለትችቱ መመከቻም ሆነ ትችቱን ለማቅረቢያ ምክንያት መደርደርን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ማግኘት ዘበት ነው። ለሚበሉት አለመብላቱ እንደሚያስገርም ሁሉ ለማይበሉት ደግሞ ያስፀይፋል፤ በመጨረሻም የማይበለት በቁጥር ስለሚበዙ ነገሩንም ንግግሩንም የማነወር አቅም ያካብታሉ።በተመሳሳይ የዚህ አይነት የብሔር ነክ ትችቶች እና ተያያዥ ጉዳዬች ማንሳት ጉዳዬን ከሚፈጽሙት በላይ ዘረኛ እና ሃጥያተኛ ያደርጋል።

## ቤተ ፖለቲካን መተቸት

ከተቃዋሚ እስከ ገዢው ፓርቲ ድረስ ቤተ ፖለቲካን መተቸት ከመፈረጅ አንስቶ እስከ መፈጀት ድረስ የሚያደርስ ቅጣት ያስከትላል። የገዢው ፓርቲ በአንድ በኩል ሥራዬ፣ ፖሊሲዬ፣ አመራሮቼ፣ አስተዳደሬ፣አመራሬ ፍፁም ነው የሚመስል ክርክር ሲከራከር፣ ተቃዋሚዎች በእኩል ድምፅ ሥራህ፣ ፖሊሲህ፣ አመራሮችህ፣ አስተዳደርህ፣ አመራርህ ፍፁም የተሳሳተ ነው የሚመስል ምላሽ ያሰማሉ። የገዢው ፓርቲ ባሕርይ ከጥንት ነገሥታቶቻችን ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ነው፤ ንጉሥ አይሳሳትም። እንዲያው ገዢው ይሳሳታል ያሉት አምላክን ከተቃወሙት አይተናነሱም እና ቅጣት ይገባቸዋል። ይህንን የሚያውቅ ገዢውን አይተችም።

ተቃዋሚዎችን ያየን እንደሆነም ተመሳሳይ ድራማ በግልባጭ እናያለን። ተቃዋሚዎች ለመቃወም ብቻ የተፈጠሩ እስከሚመስል ድረስ(ያሉበት የፖለቲካ ምህዳር ጥያቄ እንዳለ ሆኖ) አንድም የራሳቸውን ፖሊሲ ወይም የረባ የፖሊሲ ትንታኔ ሰርተው ሲያሳን አያስተዋልም። ነገር ግን በተቃራኒው ‹‹እሺ ገዢው ፓርቲ ከተሳሳተ ምንድን ነበር ማድረግ የነበረበት?›› ተብለው ቢጠየቁ ጠያቂያቸውን ጨዋ ከሆኑ‹‹ተቃዋሚዎችን መተቸት ትግሉን ይጎዳዋል›› በሚል በአብዛኛው ደሞ ‹‹አንተማ ወያኔ ነህ›› የሚል ፍረጃ ሊያከናንቡት ይችላሉ።

## ታሪክን መተቸት

ነገሥታቱ ዜጎቻቸውን የኔ የሆኑ እና የኔ ያልሆኑ በማለት ተከፋፍለዋቸው እንደሆነ መረጃ የለኝም። የዛሬ ኢትዮጵያውያን ግን ነገሥታቱን የኔ የሆኑ እና የኔ ያልሆኑ በማለት ሊከፋፈሏቸው ይሞክራሉ። በተከፋፈሉት መሠረትም ‹‹አፄ ዮሓንስማ ትክክል ነበሩ፣ ምኒልክ አበላሹት እንጂ… የለም አፄ ቴዎድሮስ ናቸው ያበላሹት፤›› እየተባባሉ የኔ ያሉትን ይቀበላሉ፣ የኔ ያላሉትን ደግሞ ያራክሳሉ። የአገራችን ታሪክ ከነገሥታቱ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ የአገሪቱን ታሪክም እንዲሁ በማጥላላትና በማወደስ አጣብቂኝ ውስጥ እንዲወድቅ ያደርጉታል።

ችግሩ ያለው ትችቱ መሠረት ላይ ነው። የትችቱ መሰረት (አመክንዮ) ሥራ ወይም የሥራ ውጤት ሳይሆን የግል ዝንባሌ (ምርጫ)፣ ወይም የግል ጎሣ ሆኖ ተደጋግሞ ይስተዋላል። በሌላ በኩል የዘመኑን ሁኔታ እና የዘመኑን ልሂቃን ዕውቀት ከግንዛቤ ውስጥ ባላስገባ (ወይም በዚህ ዘመን መለኪያ) ታሪክን መገምገም የራሱ የሆነ ድክመት ያለበት ሲሆን፣ አንንዶቻችን ታሪካችንን እና ባለታሪኮቻችንን የምንተቸው በተሳሳተ መለኪያ እንዲሆን አድርጎታል። በታሪክ ረገድ በዚህ ወቅት ያለው ትልቁ ችግር ባብዛኛው በተሳሳተ መንገድ መተቸት ሲሆን። ለሚዛናዊው አተቻቸትም ቢሆን በምላሹ ለጦርነት የማይዘጋጁ ኢትዮጵያውያን ቁጥር አነስተኛ ነው።

የታሪክ አባቶችን ስንዘክር/ስንወቅስ ግዴታ በፍፅምና መሆን አለበት የሚል መመሪያ የለም። የታሪክ ፋይዳው ለመማሪያ እንጂ ለመፈራረጂያ አይደለም በሚለው ከተስማማን፣ ለምሳሌ በአንድነት ጉዳይ ሊዘከሩ/ሊወቀሱ

የሚገባቸው ካሉን በጉዳዩ ብቻ መዘከር/መውቀስ ብቻ ሲቻል፣ የዛሬ ሰው ለአንድነት በሚሰጠው ዋጋ መዝኖ ‹ያ ንጉሥ› ለአንድነት ስለሠራ/ስላልሠራ በሚል ንጉሡ በሕይወት ዘመኑ ተሳስቶ የማያውቅ/ትክክል ሆኖ የማያውቅ አድርጎ ታሪክን በተሳሳተ መንገድ በመጻፍ ሌላ የታሪክ ተጠያቂ ከመሆን አያድንም፡፡

## ግለሰቦችን እና ክስተቶችን መተቸት

በግለሰቦች ጉዳይ የትችት ባሕላችን መጀመሪያ የውዳሴ ብቻ ነው፡፡ ቀጥሎ ደግሞ የርግማን ብቻ የማይሆንበት ዕድል የለም፡፡ ‹‹ቀድሞ ማመስገን ቆይቶ ለማማት አይመችም›› የሚለው አባባልም ያመሰገኑትን ሲያጠፉ መውቀስን ለማነወር የተፈጠረ ቃል ይመስላል፡፡ ፍፁም ሰው በሌለበት ዓለም ወይ ፈፅሞ ማመስገን ወይም ፈፅሞ መውቀስ ብቻ ናቸው አማራጮቹ፡፡

ፍፁም ቅዱስ የማድረግ እና የማርከስ ሥራ ባሕላችን ላይ በሰፊው እንደሚታይ ከላይ የተጠቀሰው አባባል አንዱ ማሳያ ነው፡፡ በባሕላችን አንድን ግለሰብ በመልካም እና ተወዳጅነት ዘመኑ ስህተቱን የመንገር ልምድ የለም፤ ማወደስ ብቻ የበዛበት ቆይታ ይኖረውና አንድ ትልቅ ስህተት ሲሰራ የተወደደበት እና የተወደሰበት መልካም ሥራ ሁሉ ቀርቶ ርግማኑ ብቻ ይወራል፤ በዚህ ወቅት የሱን መልካም የሚጠቅስ ሰው ቢኖር ከማስረገም በተጨማሪ የእኩይ ስራው ተባባሪ የሆነ ያክል ሁሉ ሊቆጠር ይችላል፡፡

አቶ ልደቱ አያሌውንና ምርጫ 97ትን እንደ ምሳሌ መውሰድ እንችላለን፡፡ በተለይ በምርጫ 97 ተከስቶ የነበረውን የተቃዋሚ ጎራ በመክፈል ትልቁን ሚና እንደተጫወቱ የተነገረላቸው አቶ ልደቱ (በርግጥ በቅስቀሳው ወቅትም ትልቁን ሚና ተጫውተው ነበር፤) ከምርጫው በፊት ከአምልኮ ባልተናነሰ ተወድሰው፣ ከምርጫው በኋላ ደግሞ ከስይጣን ባልተናነሰ ተወግዘዋል፡፡ አትሌቶቻችን ብዙ ጊዜ ይህንን ተጋፍጠውታል፡፡ በአሁኑ ሰአት ቴዲ አፍሮን መተቸትም ቤተ ክርስትያን የማቃጠል ያህል እነደሚሆን አይተናል፡፡ሚች ጠ/ሚር መለስ ዜናዊን በአሁኑ ሰዓት መተቸት የሚያስቀስፍ ሃጥያት ሆኖ የተቆጠረ ሲሆን፣ በተቃዋሚዎች ሰፈር ደግሞ ማወደስ ሊያስነቅፍ ይችላል፡፡

## የአመክኗዊ ትችት ዋጋችን (የAppeal to Popularity ጥገኝነት)

በክርክር ባሕላችን ውስጥ የተከራካሪው ብዛት፣ እና የደጋፊው ብዛት እንጂ የመከራከሪያ ነጥቡ ዋጋ አነስተኛ ነው፡፡ ምንም እንኳን ይህ ዓይነቱ ነገር በሌላውም ዓለምም ሊኖር የሚችል ቢሆንም በአገራችን የጎላ ነው ብሎ መሟገት ይቻላል፤ ለዚህ እንደምክንያት የማስቀምጠው የዘመናዊ ትምህርት ተዳራሽነት እና የክርክር ባሕላችን አለመዳበሩን ነው፡፡ የሆነ ሆኖ በአገራችን ትችት አሰጣጥ ልምድ መሰረት መከራከሪያ ነጥቡ (አመክንዮው ወይም the logical reasoning) ቢያመዝንም ብዙ የሐሳቡ ደጋፊ ከሌለ ተከራካሪው ተሸናፊ ነው፡፡ ተሸናፊነት ደግሞ በሐሳቡ ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን (ምናልባትም እስከመገለል) የሚያደርስ ማሕበራዊ ቅጣት አለው፡፡

እንደውም አብዛኛውን ጊዜ ‹‹ድፍን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያምንበትን ነገር ትክዳለህ/ጃለሽ እንዴ?›› የሚል ሙግት ሊገጥማችሁ ይችላል፡፡ ይህንን ዓይነቱን ፓርሰትየፈላስፋ ምሁራን Appeal to Popularity ይሉታል፡፡ ብዙሐኑ በነፈሰበት መንፈስ፡፡
በአገራችን፣ ሰዎች የሐሳብ ልዩነታቸውን እንደጥንካሬ በሚቆጥሩበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን የሆነ እምነት መከተል፣ ወይም የሆነ ሐሳብ መደገፍ ከሕይወት የመቀጠፍ አደጋ ይጋርጣል፡፡ ብዙሐኑ የሚደግፉትን መደገፍ ወይም መቃወም ትቶ የራስን አቋም መያዝ ቢያንስ በጥርጣሬ ዓይን ውስጥ ይጥላል፣ ሲከፋም ‹‹መሃል ሰፋሪ በሁለት ጥይት ይሞታል››… እንዲሉ ያደርጋል፡፡ አንድን ግለሰብ፣ ወይም ክስተት መተቸት የግለሰቡ ጠላት ወይም የክስተቱ ተቃዋሚ እንደሆነ እንጂ ለግለሰቡ መሻሻል ወይም ለክስተቱ ማጠናከሪያ የሚሆን ሐሳብ አዋጪ አድርጎ አያጽፍም፡፡

በጥቅሉ በባሕላችን ተቃራኒ ሐሳቦችን አቻችሎ የማየት እና የመረዳት ቅን ልቦና ይጎድላል፤የሥልጣኔ ዋና መንገዱም ይሄው ብቻ ስለሆነ ግን ትችት ለዘላለም ይኑር!!!

# አፋዊነት… (Sweet Talk)

**በብርሃን ፋንታ**

*"ሁላችን ከሆንን የቋንቋ ፈላስፋ*
*በተግባር መስካሪ አንድም እንዳይጠፋ"*

ይህ የእዮብ መኮንን ዘፈን ግጥም የዚህን ጽሑፍ ገገር ሐሳብ ይገልፃል፡፡ ሲነገር ከንፈር የማያደናቅፍ፣ ሲደመጥ ጆሮ የማይኮረኩር፣ በአዕምሮ ሲሰላሰል የማይጎረብጥ በተግባር መሬት ላይ የማይተገበሩት የአፍ ፈሊጥ /leap service/ በከተማችን በርክቷል፡፡ በጊዜ ብዙ ሰዎችን ታዝበናል፡፡ "ድሮም ትልቅ ነበርክ" የሚል የግጥም ፉካሬ በጌትነት እንየው ከመስማት በላይ፣ በፍትህ ጋዜጣ "መንግስት መዶሻ ነው፤ ሕዝብ ደግሞ ምስማር" ሲለን ከነበረ አምደኛ "ግድቡ በአቶ መለስ ይሰይም"፣ "ምስላቸው በብር ይታተም" የሚል ጭብጥ የያዘን ተውኔት ድርሰት ከማየት በላይ፤ ወደ መልካምም ወደ ክፉም አገራችንን በሚመራው በዛች ቀውጢ ሰዐት ፍፁም ከሚያምኑት "Meles Zenawi is back in town" የሚል ዘገባ ከማንበብ በላይ፤ "አገር ማለት የኔ ልጅ" የሚል ውብና ጥልቅ መልዕክት ያለው ግጥም ገጣሚ ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ በፍትህ ጋዜጣ አምደኛ በሆኑ ማግስት ለጠ/ሚሩ መታሰብያ ግጥም መድረክ ላይ ሲያነበንቡ ከማየት በላይ ሌላ የመከዳት ስሜት የሚፈጥር ምን ነገር አለ?! ምንም የለም!

ይህ ጽሑፍ የአቶ መለስ ዜናዊን መልካም ያልሆነ አስተዳደር ለመተቸት የተነሳ አይደለም፡፡ ወትሮም አቶ መለስ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ የሚበጀንን ነው የሚያደርጉት ብለው ሲሞግቱ ለነበሩትም አይደለም፡፡ ክፉ ናቸው፤ በደለኛ ናቸው የሚል ወንጀል ሲያቀርቡ የነበሩት ሲሞቱ ደግሞ በተቃራኒው መላዕክትነታቸውን ሲሰብኩ ለከረሙት ታዝበናል፣ አይተናል ለማለት ነው፡፡ የቀድሞ ጠ/ሚ ተፈጥሯዊ ሞት የአንዳንድ ግለሰቦች ጭንብል አስወለቀ እንጂ ይህ ችግር በአደባባይ መታየት ከጀመረ ሰንበቷል፡፡ አቶ መለስ ዜናዊ ራሳቸው የተሳተፉበት "እንደገና" የተሰኘ ዘጋቢ ፊልም ላይ እንዲህም የሚል የአፍ ፈሊጦችን አድምጠን ነበረ፡፡

*"ዋናው ሕሊና ነው… ሕሊና ደግሞ ከሁሉም በላይ ነው መሆን ያለበት! ፍትሕ፣ ስርዓት ሁል ጊዜ ፐርፌክት አካሄድ ከሄደ በዚች ምድር፣ በዚች አገር ምንም አይከሰትም፡፡"*
(አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴ)

ይህን የተናገረው በ1997 ምርጫ ምክንያት በታሰሩ የፓለቲካ እስረኞች እና መንግስት መሐል በሽምግልና የተሰየመው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ ነው፡፡ ወዳጄ እንደሚለው ኃይሌ እግረ ብርሃን እንጂ ልበ ብርሃን እንዳልሆነ አልዘነጋሁም፡፡ ሆኖም ግን በአፈጠጠ እውነት ላይ ተደራድሮ እስረኞቹን የ12 ዓመት ሕፃን ባንክ እንዲዘርፍ ልከን አሳስተን ነው ያስገደልነው የሚል የይቅርታ ሰነድ ሕሊናው እየተመለከተ ፈርመዋል፡፡ ያን ጊዜ ሕሊናውን ከወዴት ሰውሮት እንደነበረ አላውቅም፡፡ በየትኛው የሞራል እርከን ላይ ቆሞ ሰለሕሊና እንደሚሰብክም አይገባኝም፡፡ ዛሬ የስፖርት ጋዜጠኛ ፍስሐ ተገኝና የመሳሰሉት ሕሊና እያለን ያልተፈፀመውን የ11 ዓመት ታዳጊ ባንክ ሊዘርፍ ነበር የሚል ዜና አላነብም ሲሉ ከአገር ተሰደው እየኖሩ ነው፤ እነኃይሌ በአንፃሩ ዋናው ነገር ሕሊና ነው እያሉን ነው፡፡ ታዲይ ይህ ምንድን ነው… ይህ የአፍ ፈሊጥ ነው፡፡

*"ዋናው ነገር አባይን እገድባለሁ ብሎ ማሰቡ ነው ትልቅ የሚያደርገን … ለእኔ አባይን እንገድባለን ብለን 'ማሰባች' ነው ዋናው ቁም ነገሩ!…አገራዊ ጉዳዮችን መለየት አለብን፤ ያለንበት 21ኛው መቶ ክፈለ ዘመን የተለያዩ ፓርቲዎች፤ የተለያዩ ርዕዮት ዓለሞች፣ የተለያዩ የአሠራር መንገዶች የተለያዩ ነገሮች ያለበት ነው፡፡ እብርነት ውበትነት የሆነበት ዘመን ላይ ነው ያለነው፤ ከዚህ ውጭ መሆንም አንችልም፡፡ ግን እንደገና ደግሞ እነዚህን ሁሉ የሚያስተባብር አንድ ነገረ አለ፤ እርሱም ኢትዮጵያ የሚባል ነገር አለ …የፖለቲካ ፓርቲዎች ልንመሠርት የምንችለው፣ ልንከራከር የምንችለው፣ አሸንፈን ፓርላማ ልንገባ የምንችለው፣ ተሸነፈን ልንወርድ የምንችለው፣ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ስትኖር ነው፡፡"*
(ዳንኤል ክብረት)

ጤናማ ሞራል እንዲኖረን በጽሑፉ የሚተጋው፣ታሪኩን የዘነጋ ትውልድ እንደተፈጠረ በበሰለ ጽሑፍ ሸንቆጥ የሚያደርገው፣ ወጋችንን ተረታችንን መዘንጋት እንደሌለብን የሚያስታውሰው፣ ከድንጋዩ ይልቅ ሰዉ ክቡር እንደሆነ የሚመክረው ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በቀረበው ዘጋቢ ፊልም ከተናገረው የተቀነጨበ ነው፡፡ ከአፄ ልብነድንግል ጀምሮ አባይን ለመገደብ ሐሳብ የነበራቸውን ነገሥታት ታሪክ ዋጋ በማሳጣት ዛሬ እንገድባለን ብለን

'ማሰባችን' ብቻ "ትልቅ" እንደሚያደረገን ሰብኮናል፡፡ ኢትዮጵያ የምትባል ነገር ያለ ሕዝብ ነጻነት በፍትሕ ላይ ባልተመሰረተ የፖለቲካ አስተዳደር ልትፀና እንደምትችል ከታሪክ አስታዋሻችን ምክር እየተለገሰን ነው፡፡ ይህ የዳንኤል ንግግር ከአፍ ፈሊጥነት እና ገዢው ፓርቲ ሳዘጋጀው ፕሮፓጋንዳ ማጣፈጫነት የዘለለ ምን ውሃ የሚያነሳ ነገር አለው? …ምንም! ይሄም የአፍ ፈሊጥ ነው!

እነዚህ ለአስረጅነት ቀረቡ እንጂ በፖለቲከኛው፣ በኪነ ጥበበኛው፣ በጋዜጠኛው፣ በነጋዴው፣ በሐኪሙ እና በሌሎችም በቀላሉ ማንም ሊያስተውለው የሚችል አገራችንን ወግቶ የያዘ ችግር ነው፡፡ ይህ አፋዊነት በዚሁ ከቀጠለ በአገራዊ ደረጃ የሚያመጣው ልክ ያልሆነ የትውልድ አስተሳሳብ ብዙ ዋጋ ያስከፍላል፡፡

## ከ"አሲምባ ተራራ" ላይ ውረዱ!

በእውቀቱ ስዩም "ኗሪ አልባ ጎጆዎች" ባሰኘው ግጥሙ ውስጥ አያቶች የወጠኑትን፣ አባቶች የገነቡትን ቤት ልጆች ምን እንደሚሉት በቅኔ ወርዶት ሲያበቃ እንዲህ ዘግቶታል፡-
*"የአያቶቻችን ቤት፥ ይሁን ባዶ፣ ይሁን ኦና*
*በኛ ቁመት፣ በኛ መጠን አልተቀለሰምና፡፡"* (ግጥሙን በቃሌ ስለወጣሁት ቃላት ልገድፍ እችላለሁ!)

ከአሁን በፊት የነበረው ትውልድ "አሲምባ ተራራ" ላይ ያስወጣው ድንጋይና ሳሩ አይመስለኝም፡፡ ወጣት ግምባር ላይ ጥይት የሚያሰድድ፣ የሴት ልጅን ጡት የሚያስቆርጥ፣ ከአንድ ማሕፀን የወጡ ሁለት ወንድማማቾችን ጎራ አስለይቶ የሚያታኩስ አስተሳሰባቸው ነው ወደ አሲምባ ተራራ ላይ ያስወጣቸው፡፡ ‹ያ ትውልድ› ዘመኑ ያፈራውን አስተሳሰብ አላምጦ ለአገሬ የሚበጃት ይህኛው ሕሳቤ ነው የሚል ስሌት ላይ ጽኑ እምነት ጨምሮ ውድ የሆነውን ሕይወቱን ያለምንም ፍርሐት ከፍሏል፡፡ ከፋም ለማም ‹ያ ትውልድ› ይበጃል ያለውን አድርጓል፡፡ አሁን የ‹ያ ትውልድ› ክሽፈት ታሪክ መዝገብ ወይም ትውልዱ አብሰልስሎ አገሪቱ ያስመለሳተን ሐሳብ የምንወቅጥበት ጊዜ ላይ አይደለንም፡፡ ኢሕአፓ፣መኢሶን፣ ሰደድን እያጣቀሱ፤ ፋኖ ተሰማራን እየፎከሩ ሕዝቡ ከተጨበጠበት የፍርሐት ቆፈን ለማላቀቅ መሞከር ዘመንን ያለማገናዘብ በጥልቅ ያለማሰብ ችግር ነው፡፡ ገዢው ፓርቲን የሚሞግት የሚያሳጣ ፓሊሲ፣ ተቋም፣ መዋቅር እና የፖለቲካ ርዕዮት ዓለሙ ላይ ከመመራመር ይልቅ እገሌ ደርግ ነበር፣ ኢሕአዴግ ጣኦት ነው፣ ሰውዬው ኤርትራዊ ነው፣ አራማጅ ነኝ፣ ሕዝብ ፈሪ ነው፣ መብራት ተቆረጠ፣ መብራት ተቀጠለ ሐሳቦች እኛን አያነቁም፡፡ ሕዝቡ ከተከናነበው የፍርሐት ጃኖም አያላቅቅም፡፡ ዛሬ እንደ በፊቱ ኸረ ጎራውን ብቻ ፎክሮ፣ ቀረርቶ አቅራርቶ፣ እንደው በደፈናው በሽላላ የምትነቃ ኢትዮጵያ አይደለም ያለችው፡፡ ይህን መሳይ ችግር በብዛት በጋዜጣ ጸሐፊዎቻችን የሚስተዋል ነው፡፡ ይሄን ዘመን ያገናዘበ የዚህን ትውልድ ጥያቄ መመለስ የሚችል አስተሳሰብ ያነገበ አገርን ወደፊት ሊያራምድ የሚችል ጽሑፍ ብናገኝ ነው የራሳችንን አሲምባ መፍጠር የምንችለው፡፡ እንደው በደፈናው ኢሕአዴግ ክፉ ነውና ደረታችሁን አቀብሉ ሐሳብ አሁን ያለውን አምባገነናዊ ስርዓት ያጸና እንደሆነ እንጂ ለአገር አይበጅም፡፡ በ1997 ዓ.ም. ባልተመረመረ ፖለቲካ ደረታችንን አቀብለን የከፈልነው ዋጋ የሚዘነጋም አይደለም፡፡

*መድኀኒቱን ስጡን*
*"ቃልን መርጠን ከየቤቱ*
*ለመናገር መጎምዠቱ*
*ለእኛስ ነው ወይ መዳኃኒቱ?"*

ችግራችንን በተለያዩ ተረቶችና ምሳሌዎች መዘርዘር የአዋቂነት ልኬት የመሆን አዝማሚያ ይስተዋላል፡፡ ፔዳል፣ ብስክሌት፣መዶሻ፣ ምስማር፣ድስትና ክዳን፣ የግሪክ አፈ ታሪኮች፣ የአበው ተረቶችን እያጣቀሱ በሽታችንን ማብራራት አሳቢነት (Thinker) አይደለም፡፡ ሲታከክልን ዝም ብለን እንጂ ቁስሉን አዝለን ከምንዞረው ከኛ በላይ በሽታውን የሚያውቅ የለም፡፡ አሁን ያለው ስርዓት ለአገራችን ፈፅሞ እንደማይበጃ ከኑሮ በላይ የሚያስረዳ ነገር የለም፡፡

ደራሲዎች፣ ገጣሚዎች፣ ጋዜጠኞች እና ሌሎች ጸሐፊዎች በመንደር ከሚወራው በተሻለ ለአደባባይ የሚበቃ ሐሳብ አለኝ እና ወደ ጋዜጣ መጥቻለሁ ስትሉ የበሽታውን መድኀኒት ጠቁሙን፤ አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚለው መርሕ አይበጀንም ስትሉ የሚበጀንን ርዕዮተ ዓለም አሳዩን፡፡ ይሄ መንግስት መውረድ አለበት ስትሉ፣ እንዴት መውረድ እንዳለበት መንገዱን ስጡን፡፡ በደፈናው ስለተበደልን ብቻ ሕይወታችሁን ማግዱ አትበሉን፡፡ እንደው ብድግ ብሎ

ሕዝብ ቁጤማ ነው የሚል ፈሊጥ አንስቶ የቁጤማን ልፍስፍስነት እየተነተኑ ሕዝቡ ፈሪ እንደሆነ መተንተን ተራማጅነት አይደለም፡፡ ይሄ ፈፅሞ ለአገርም አይረዳም፡፡

ማቅ ልበስ፤ ውደቅ በንስሐ
*"እንደ ቶን ፍም እሳት ይፋጃል ይልሳል*
*መንገዱ ከሲኦል ያደርሳል፤*
*የደበቅከው እውነት ሳይጮህ በበረሃ*
*ማቅ ልበስ ውደቅ በንስሐ"*
(አቤል ሙሉጌታ)

ዛሬ ይርጋለም ዱባለንና ሰለሞን ተካለኝን እየኮነኑ በደላቸውን ሊያጥቡ እየሞከሩ ነው፤ ዛሬ የራሳቸውን ጉድፍ ሳይነቅሉ ሌላው ንስሐ እንዲገባ እየሞገቱ ነው፡፡ በሁለት በኩል ተስላችሁ፣ እምነት አጉድላችሁ፣ ለስጋችሁ አድልታችሁ፣ ንዋይ አሳውሯችሁ፣ ዝና ባርቀባችሁ፣ እውቀት ስንክሎባችሁ፣ ሌላም ሌላም ምክንያት ኖሯችሁ በደል ስለፈፀማችሁ ወግዱ ሂዱ ለማለት ተፈልጎ አይደለም፡፡ የአፍ ፈሊጣችሁ በእምነት ከሆነ እንሞግታችሁለን፤ በስህተት ከሆነም ይቅር እንላችኋለን፡፡ ሁለት አሥርት ዓመታት በስቃይ ለመሩን መሪ ለአንድ ቀንም ቢሆን ከልብ አዝነናል፤ ለይቅርታ ፍፁም ቅርብ መሆናችንን ያመላክታል፡፡ እኔ ስለአቶ መለስ ዜናዊ አንባቢነት ነው የጻፍኩት፣ የኔ ተቋም ይቅርታ ጠይቋል፣ የሰው እንጂ የራሴን ግጥም አላነበብኩም ዓይነት ሰንካላ ሰበብ ክደቱን አያክምም፡፡ ሁሉም ለፈፀመው በደል የራሱ የሆነ ምክንያት አለው፡፡ በቀጣይነት አምነናችሁ ብርሃናችሁን እንድንቀበል፣ ያለጥርጣሬ ፍሬያችሁን እንድናጣጥም አጥጋቢ የሆነ ማብራሪያ አሊያም ከልብ የሆነ ይቅርታ ይገባናል፡፡ ይሄ በደላችሁን ያጥባል፤ "ነጥቆ እንዳልነጠቀ ማባበል" ሕሊናችሁን አይበጀውም፡፡

ከአፍ ፈሊጥ በዘለለ ጥረት አድርጋ በነበረችው ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ በአሜሪካ ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ባደረገችው ንግግር ሐሳቤን እቋጫለሁ፡፡

*"…የዚህ ፕሮግራም ዋና ዓላማ እንደሚመስለኝ ኢትዮጵያን ማወደስ ነው፡፡ እያሰብኩት ነበረ… እውን ኢትዮጵያ የምትወደስ ናት ወይ እያልኩኝ… ይሄን በሐቀኝነት ስንመልስ ብዙ ቅር የሚያሰኙ ነገሮች አሉ፡፡ ከቅሬታም በላይ የሆኑ፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያ የነጻነት አገር አይደለችም፡፡ ኢትዮጵያ የፍትሕ አገር አይደለችም፡፡ ኢትዮጵያ ዛሬም ዜጎቿ በድህነት የሚኖሩባት በሐፈረት የሚያቀረቅሩባት፣ ብዙ ዜጎቸ የሚሰደዱባት ነች፡፡ ስለዚህ እናወድሳት ውይ ብለን እንጠይቅ፡፡… አይ መወደስማ አለባት የሚል አቅም ነው ያለኝ፡፡ ስናወድሳት ግን ምን አስበን ነው? ኢትዮጵያ ታላቅ አገር ነበረች፤ ይህን እኔ አይደለሁም የምናገረው ታሪክ ነው የሚመሰክረው መልዕክቱ ይሄው ነው:: ኢትዮጵያ ልትወደስ የሚገባት ታላቅ አገር ነች! ታለቅነትን ለማየት ግን ሁሌም በአንድነት እንቁም… አንድነታችን ሁላችንንም የሚያቅፍ… ሁላችንንም የሚያሰባስብና የኢትዮጵያ የጋራ መኖሪያነት በሚያውቁት ይሁን፡፡"*
(ብርቱካን ሚደቅሳ)

አሜን ይሁን! … "*አንድነታችን ሁላችንንም የሚያቅፍ፤ሁላችንንም የሚያሰባስብና የኢትዮጵያ የጋራ መኖሪያነት* በሚያውቁት ይሁን"… ይሁን!

# ባርነት በዘመን ሲዋጅ?

በፍቃዱ አንዳርጌ

በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ጓላ ቀሩ የአፍሪካ የባርነት ስርዓት በሁለት አፍሪካዊ ባልሆኑ ነገዶች እንደተጀመረ በጉዳዩ ዙሪያ የተፃፉ ፅሁፎች ያስረዳሉ። እነዚህ ሁለት የአረብ ሙስሊም እና የአውሮፓ ባሪያ አቅኝዎች በአፍሪካ ዙሪያ አሰፍስፈው በአፍሪካውያን ሰብዓዊነት ላይ ትልቅ ኪሳራ ሲያሳድሩ ከቆዩ በኋላም የአረብ ሙስሊም የባሪያ አቅኝዎች ከመመካከለኛው፣ከምዕራብና ከምስራቅ አፍሪካ የቃረሚቸውን ሰብዓዊ ፍጡሮች እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ሰሜን አሜሪካና ኤዥያ በመላክ የሰው ላብ የገቢ ምንጫቸውን በማሳደግ ሃያልነታቸውን ለማስጠበቅ ሲታትሩ ቆይተዋል። አውሮፓውያኑም ቢሆኑ ከ15ኛው እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ከምዕራብ፣መካከለኛውና ምስራቅ አፍሪካ በርካሽ የገዟቸውን አፍሪካዊ በትርፍ ወደ አውሮፓ፣ ሰሜን አሜሪካ፣መካከለኛውና ደቡብ አሜሪካ በመሸጥ የሰብዓዊነትን ልዕልና ተጋፍተዋል።እነዚህ በባርነት ስም ከተለያዩ የአፍሪካ ሃገሮች የሚጋዙት ምስኪኖች ትንሽ ከሚባል ስራ ጀምሮ እስከ ከባድ የጉልበት ስራ፣ ለጦርነት ፍጆታ ሲያገለግሉ ዘመናትን አሳልፈዋል።

“የምክንያት ዘመን” እየተባለ የሚጠራው ሰብዓዊነትንና ምክንያትን ያማከለው ዘመን እያቆጠቆጠ በመጣበትና ከጨለማ ወደ ብርሃን ጉዞ በሚደረግበት ዘመን (age of enlightenment) እንዲሁም የኢኮኖሚው ስርዓት ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪው መሸጋገር ተከትሎ በምእራብ አውሮፓ የባሪያ ንግድ አብሮ እያከተመ ታሪክ ወደ መሆን ተቃረበ። በዚህን ጊዜ የምዕራቡ ዓለም የባሪያ ስርዓት ገበያው እንደ ጦፈ ነበር። የማታ ማታ ግን ብሪቴን በ1833 በሁሉም ግዛቶቿ የባርያ ስርዓትን ቀሪ ስታደርግ፣ ፈረሳይ በ1848 ቅኝ ለመግዛት በሰለጠነችባው ሃገሮች የስርዓቱን ቀሪነት በህግ ደንግጋለች፤ የተባበሩት አሜሪካም ብትሆን በ13ኛው የህገ መንግስት ማሻሻያ አውግዛ ሰብዓዊነት እንዲልቅ አድርጋለች። ይህንን ተከትሎም በ1888 የአትላንቲክ የባሪያ ንግድ ላይመለስ ጦሱን ይዞ ቀርቷል። ቢሆንም ግን ይህ ባርነት ሕገ ወጥ በሆነ መልኩ እስከ 1930 ድረስ ሙሉ በሙሉ ሳይጠፋ ሰብዓዊነትን ሲጋፋ እንደቆዬ እሙን ነው።

ይህ የባርነት ዘመን በአፍሪካውያን ላይ ታላቅ የሆነ የስነ ልቦና ኪሳራ ያሳደረ ከማሰብ መብት ጀምሮ እስከ መዘዋወር መብትን የነፈገ፣ የማንነት ቀውስጥ ውስጥ የጣለ፣ የበታችነት ስሜት እንዲዳብር ያደረገ፣ በተፈጥሮ የተሰጠውን ሰብዓዊ መብት የነፈገ “ዘመነ ንፋግ” ሆኖ አልፏል።

## የሃገሩን ሰርዶ በሃገሩ በሬ!

*“ራሳችንን ለማስተዳደር ዕድሉ ቢሰጠን በፍጥነት ምድራዊ ገነት እንደምንፈጥር አስመስለን አወራን፤ በተቃራኒው ያሰፈነው ግን የፍትህ መጓደልና ብሎም ፈላጭ ቆራጭነት ነው”*
(ፕሬዘዳንት ጁሊየስ ኔሬሬ(ታንዛኒያ))

አሁንም አፍሪካውያን የታደልን አይመስልም እንደሚታወቀው በዘመነ ባርነት የነበሩ አፍሪካውያኖች ጉልበታቸውን ገብረዋል፣ማንነታቸውን አጥተው ከባህላቸው፣ ከቋንቋቸው፣ከሃይማኖታቸው ጋር ተፋተው ማቀዋል። በዘመኑም የነበሩ ባሪያ አሳዳሪዎች የሚፈልጉት ገና ያልተነካውን ትኩስ ጉልበታቸውን ለኢኮኖሚያዊ እድገት ማካበቻ እና ለሃያልነት ማስጠበቂያ ጦርነት ፍጆታ አውለውታል። ዘመነኞች የሆኑ ገዥዎቻችንም ያገሩን ሰርዶ በሃገሩ በሬ ያሉ ይመስል በሃገሬው ላይ ክንዳቸውን አበረትተው በባርነት በትር መውቃታቸውን ቀጥለዋል። የማይወቀሱ፣ የማይገሰሱ የሃገሪቱ አርማና ፈላስፋ አድርገው ራሳቸውን የነፃነት ተምሳሌት አድርገው ለገበያ ያቀርባሉ። በህዝባቸው ላይ ግፍ ይፈፅሙና ትዕዛዛቸውና ማስፈራሪያቸው ሲደርሰው በየአደባባዩና ስታዲዬሙ ነቅሎ በመውጣት “ሙሁሩ፣ፈላስፋው ፣ደፋሪው መሪያችን አንተ ለዘላለም ኑርልን አንተን እና መንበርህን የደፈረ ለዘላለም የአሸባሪነት ካባ ከላዩ ላይ አይውለቅ” የመሳሰሉ መፈክሮችና መዝሙሮች ያስፈክራሉ፣ ያዘምራሉ፣ያስደግማሉ።

ዛሬም በእኛ ዘመን በጥቁር ምድር “ባርነት” በዘመን ተዋጅቶ ከዘመኑ ጋር እንዲሄድ በማር የተለወሰ መርዝ ሆኖ ቀርቧል። የባርነት ስርዓት ማንነትን፣ ትውልድን እንደሚገድል ሁሉ ዛሬ ማንነት እየሞተ ብኩርና በምስር ወጥ እንዲሸጥ አድርጓል። ይህ ሁኔታም በእኛ ቅኝ ባልተገዛነው ኢትዮጲያውያን ላይ ቀረልን አይስልም። በእኛ በኢትዮጵያውያን ላይ የተዘረጋው “ዘመናዊ ባሪያ አሳደሪ” ስርዓት በውዴታ ግዴታ ሰንሰለት አንገታችን ተጠፍሮ ወደ ጎን እንዳንመለከትና ከባርነት ሰልፋ እንዳናመልጥ ተደርጓል። የድሮ አሳዳሪዎች የባሪያውን ጉልበት ለኢኮኖሚና ፖለቲካ ሃያልነታቸው ማስጠበቂያ እንደተጠቀሙበት ሁሉ ዛሬም በሃበሻ ምድር በዘመኑ ዋጅተውት

ትውልድን በማድከም ድክመቱን ተጠቅመው የራሳቸውን የፖለቲካ ሃያልነታቸውን እሩቅ ከፍ አድርገው ሰቅለውታል። ሰንሰለቱን እረዘም አድርገው ዘርግተው ወደ ውጼታ ግጼታ መስመር በማስገባት አንድ ሰው ስራ ለማግኘትም ሆነ ማህበራዊ አገልግሎት ሆነ ሌላ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን አንድ በውጼታ የሚፈፀም ግጼታ ይቀመጥለታል። የተሰጠውን ኢ-ምክንያታዊ ግጼታ ሲፈጽም የጠየቀው ይሰጠዋልም ይደረግለታልም። ወጥነት ያለው ሃሳብ እንዲኖርህ ብቻ የስርዓቱን ሰልፍ ልትከተል ግድ ይላል፤ ከሰልፉ ካፈነገጥክ አሁንም በዜግነትህ ብቻ ማግኘት ያለብህን ነገር ልታጣ ትችላለህ። ስለዚህ በውጼታ ግጼታ ሰልፉ ውስጥ ገብተህ ትሰለፋለህ። ሰልፉ ውስጥ ከገባህ በኋላ ግጼታ እንጅ መብት የለህም፣ አወ ማለት እንጅ ለምን ማለት የለም፣ መጎንበስ እንጅ መቃናት አይቻልም፣ እያዩ ማለፍ እንጅ ማስተካከል የለም፣ ሲርብህ መራብ እንጅ ማዛጋት አይቻልም፣ መቀበል እንጅ መጠየቅ አይኖርም። የባርነትን ጥልቅ ትርጉም በተረዳነው ይህ ራሱ ጉልበትን ያላካተተ ከባርነት አገዛዝ የማይተናነስ መሆኑን ለማወቅ ነጋሪ አያስልገውም።

አንድ ሰው በሃገሩ እየኖረ በታሪኩ ካልኮራ፣ታሪኩን ጭክ ብሎ ሲያወራ ድምፅ ቀንስ እንዲያውስ ማን አባክ አውራ አለህ፣ ሲርበው እራብኝ ብሎ መጠየቁ አሸባሪ የሚያሰኘው ከሆነ፣ ሃሳቡን በነፃነት ሲገልፅ ለምን ተብሎ ወህኒ የሚጋዝ ከሆነ፣ ተበደልኩ ሲል ፀረ ዲሞክራሲ፣ ለምን ሲል ፀረ ልማት የሚባል ከሆነ፣መሪዎቹን በሚደግፍ ሰልፍ ሳይወጣ ሲቀር የሚወገዝ ከሆነ፣ በዲግሪ ማስትሬት ተመርቆ ስራ ብሎ ሲጠይቅ ከግልምጫ ጋር ስራ አትፈጥርም ተብሎ የሚሳለቅበት ከሆነ፣ እድገት የለም ሲል ፀረ- ልማት ፣ የሃይማኖት መብቴ ሲል አክራሪ እየተባለ በሃገሩ እንደሌላ ዜጋ ተቆጥሮ ምን አገባህ እኔ አውቅልሃለው ከተባለ....... እስኪ ተጠየቁ ከዚህ በላይ ባርነት ከወዴት አለ?

## በባርነት መኖር ወይስ ወደ ነጻነት እየሄዱ መመሞት?

እስካሁን ከተለያዩ ሰዎች ጋር በግል ካደረኳቸው ውይይቶች ሆነ ሰዎች ሲወያዩ ከታዘብኳቸው አብዛኛዎቹ በዘመናዊ መልኩ የባሪያ አሳዳሪ ስርዓት ሃገሪቱ ውስጥ ሰፍኖ እንዳለና መልኩን ቀይሮ እንደመጣ የሚስማሙ ናቸው።

ባርነቱ ላይ የተስሙት ብዙዎች ተመችቷቸው እንደሆነ፣ አሁን በሃገሪቱ ተዘርግቶ ስላለው ስርአት ሲጠየቁ ግን ሲጠየቁ እረ "የደላው ሙቅ ያኝካል" አሉ የሚል መልስ ሲሰጡ ይሰማል።ታዲያ ስርዓቱ ላይ ቅሬተ ያለው ሰው ካለ ለምን ጥያቄስ አያቀርብም ያልን እንደሆነ አብዛኛው የሚሰጠው መልስ "እናውቃለን ብንናገር እናልቃለን አይነት ነው።

ይህ የነጻነትን ጣእም በቅጡ ያለመረዳት ችግር የሚቀረፍበትን መንገድ በቀላሉ አግኝተን የምንለውጠውም አይመስልም።የነጻነትን ጣእም ያለመረዳት ችግር ባይሆንም ኖሮ ለዘመናት የባርነትን እና ገገሮዎችን እያፈራረቅን አንኖርም ነበር። ይህ አዙሪት መቼ ይሆን የሚያበቃው?

# ዳያስፖራው ጽንፈኛ ወይስ ተስፈኛ?

ከነበረበት ባሕል፣ ተመሳሳይ ቋንቋ ተናጋሪ ማኅበረሰብ፣ የኑሮ ዘዬ ወይም ባጭሩ ከነበረበት አገር (በማንኛውም መልኩ) ለቆ ወደ ሌላ አገር ለተወሰነም ሆነ ላልተወሰነ ጊዜ እየኖረ ያለ ሰው/ማኅበረሰብ ቀድሞ ለነበረበት አገር ሰዎች ‹ዳያስፖራ› ይባላል (dispersed; disaspora /የፈለሰ፤ ፈላሻ እንደማለት)፡፡ አገርኛ ስናደርገው ደግሞ ከኢትዮጵያ ወጥቶ ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ የዓለም ክፍል ተበትነው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ዳያስፖራ እንላቸዋለን፡፡ ‹‹የዳያስፖራ ፖለቲካ›› ስንል ደግሞ ዳያስፖራ በሆነው ማኅበረሰባችን የሚንፀባረቀውን ፖለቲካዊ አቋም፣ አመለካከት እና እንቅስቃሴን ማለታችን ነው፡፡ በተለይ አሁን አሁን ስለአገራችን ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ‹ዳያስፖራው ምን አለ?› የሚለው ጥያቄ የማይሻር ጉዳይ እየሆነ ነው፡፡ ሆኖም ደግሞ በጉዳዮች ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን አይቶ ከኢትዮጵያ ውጪ በሚኖር ሰው የተሰጠ መሆኑን እና አለመሆኑን ለማወቅ ቀላል እየሆነ እንደመጣ የሚከራከሩም አሉ፡፡ እነዚህም፡-

- በተለምዶም የአስተያየቱን ጽንፋን ተመልክቶ ‹የዲያስፖራ ፖለቲካ›› የሚባል ስያሜ እየተሰጠው ይገኛል፡፡ የ‹የዳያስፖራ ፖለቲካ› ውስጥ በብዛት ጽንፉ ወዲህ ወይም ወዲያ ይሆን ይሆናል እንጂ ፅንፍ መያዙ አይቀርም የሚለው እምነት የብዙዎች እየሆነ ነው፤ እንዲያውም አንዳንዶቹ ሁለቱንም ጽንፎች አዳርሰዋል በሚል ሰለሞን ተካልኝ በማስረጃነት ያነሳሉ፡፡
- ዳያስፖራው እኛ (በአገር ውስጥ ነዋሪዎች) የማናውቀውን የዴሞክራሲ ጣዕም የሚያውቅ፣ እኛ የሌለን የፖለቲካ ምኅዳር ያለው፣ ገሚሱ ኑሮው ሞልቶለት የወገኑ ጉዳይ ከሩቅ የሚቆረቁረው የለውጥ ተስፈኛ እንጂ ጽንፈኛ ሊባል አይገባውም የሚሉት ደግሞ በሌላ ወገን ይገኛሉ፡፡

በርግጥም ጽንፍ የያዙ እና ማንኛውንም ዓይነት በአገራችን ውስጥ የሚታዩ እንቅስቃዎችን ጥቃቅን ጉድለቶችን እየነቀሱ በማውጣት፣ በማጉላት እና ጠንካራ ትችት ማቅረብ የዳያስፖራ ፖለቲከኞች መለያ እየሆነ ነው እንዲያውም ዋነኛ ዓላማቸው መቃወም እንጂ ለለውጥ መትጋት አይደለም ቢባልም፣ የእውነተኛ ለውጥ መንገድን ለማምጣት ገንዘባቸውን፣ ዕውቀታቸውን እና ጊዜያቸውን እየፈሰሱ ያሉትም ‹‹ከኑግ የተገኘሽ መጭ አብረሽ ተወቀጭ›› በሚል ሰበብ አብረው እየተጨፈለቁ ነው፡፡ ጉዳዩን በኮንትሮባንድ ውስጥ ለውስጥ ከማስኬድ ይልቅ በመወያየት የሚበጀውን አካሔድ በጽንፍ/ተስፋ ቅጥያ ሳንከፋፈል እንድንሄድበት ማድረግ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ነው፡፡

ምንም እንኳን እነርሱ ከሌሉበት (አስተያየታቸውን ካልሰጡበት) የኢትዮጵያ ፖለቲካ ነፍስ የሌለው በድን ይሆናል የምንላቸው ዳያስፖራዎች ቢኖሩም፣ ይህ ጽሑፍ ግን ባመዛኙ ‹‹ስንዴውን ከገለባ ለመለየት›› ሲባል ሊወቀሱ የሚገባቸውን መውቀስ ላይ ያተኩራል፡፡ ሊወቀሱ የሚገባቸው የምንላቸው እነዚህን ያካትታል፡-

- ኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተውን የፖለቲካ ምኅዳር መጥበብ የግል መጠቀሚያ (መተዳደሪያ) ከማድረግ ውጪ ፖለቲካ ያለ ለማይመስላቸው፣
- በተለያዩ አደጋዎች የደረሰባቸውን አደጋ መንግስት እንዳደረሰባቸው በማስመሰል የሐሰት ትዝብት በመፍጠር ላይ ላሉ፣
- ለምክንያት (causes) ሳይሆን ለጥገኝነት መጠየቂያ ሲባል ብቻ የመሪዎችን መምጣት ተከትሎ የሚደረጉ ሰልፎች መብዛት፣
- ይህንና ይህን መሰሎች ችግሮች እያሉባቸው ጉዳዩን እንዳይወራ ለማነወር እየጣሩ ያሉ ቀጥተኛ ተጠያቂ ዳያስፖራዎችን ነውሩን ለመጠየቅ ነው፡፡

የአንድ "ተራ" ዳያስፖራ አመለካከት እዚህ አገር ካለ ፖለቲከኛ ይልቅ (ዕድሜ ለቴክኖሎጂ እና ሐሳብን ለመግለጽ ነጻነት) ሕዝቡ ጓዳ የመግባት ዕድል ያለው እየሆነ ነው፤ ስለሆነም የኀበጠ የሚመስለንን ለማቅናት እና የተቃናውን ደግሞ ለመጠናከር መወያያ ጊዜው አሁን ነው፡፡ ለውይይት እንዲያመቸንም አንድ በሚያደርጓቸው ባሕርያት እየከፋፈልን እንመለከታቸዋለን፡-

## ጫና ያሳደዳቸው

የአገራችን ፖለቲካና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የሚጽፉ እና የተበደሉ ሕዝቦችን ድምፅ ባገኙት አጋጣሚ ሲያሰሙ የነበሩ ጋዜጠኞች፣ ጸሐፊዎች እና የሰብዐዊ መብት ተሟጋቾች እዚህ ምድብ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ አገር ውስጥ እያሉ በሠሯቸው ሥራዎች ዕውቅናን ያተረፉና የሕዝብን ጆሮ አግኝተው የነበሩ ብዙ ናቸው፡፡ እነዚህ

ሰዎች የሕዝቦቻቸው ልሳን በመሆናቸው ብቻ በስልክ ከሚደርሳቸው ማስፈራሪያ እና ዛቻ አንስቶ ለአካላዊ ጉዳት የመዳረግ፣ የመንገላታት እና የመታሰር ዕጣ ሊደርስባቸው እንደሚችሉ ጥቆምታዎች ወይም ምልክቶች በሚያገኙበት ጊዜ በተለያየ ምክንያት አገራቸውን ለቀው ለመሰደድ ይወስናሉ፡፡

እነዚህኞቹን በተመለከተ አገር ውስጥም ባሉ ሆነ ቀድሞውንም በተሰደዱ ሰዎች ‹‹መሰደዳቸው አግባብ አይደለም፤ እዚሁ ሆነው እስከ መጨረሻው ድረስ የሚደርስባቸውን ሁሉ ማለትም እስሩንም፣ እንግልቱንም፣ፍትሕ ማጣቱንም ከሕዝባቸው ጋር እንደጀመሩት መጨረስ ነበረባቸው›› የሚል አመለካከት ያላቸው ሰዎች ያሉትን ያክል ‹‹የለም፤ እነዚህ ሰዎች እስር ቤት ገብተው ለራሳቸውም ከሚንገላቱ፣ ወጥተው የቻሉትን ያህል ሕዝባቸውን በአቋራጭ ቢታገሉለት፤ በዚያውም ለዓለም አገር ውስጥ ያለውን ችግር ቢያስረዱ ይሻላል›› የሚሉትም ብዙ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ ከሩቅ ሆነው በላፕቶፕ የሚታገሉት ሰዎች የመጀመሪያውን ሲናገሩ አገር ውስጥ ካሉት ይልቅ የበለጠ ያስከፋል፡፡ ለዚያም ነው ‹‹እነርሱ ሊኖሩት ያልፈቀዱትን ሌሎች እንዲኖሩ ግፊት ያደርጋሉ›› በሚል በጽንፈኝነት የሚከሰሱት፡፡

በተረፈ ግን ብዙዎቹ በዚህ መንገድ ተሰደው የወጡ ጋዜጠኞችን እንደምሳሌ ብንወስዳቸው ባመዛኙ ከጽንፈኝነ የፀዱ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ የአዲስ ነገር ጋዜጠኞች፣ የአውራምባ ታይምሱ ዳዊት ከበደ፣ የፍትሑ አበበ ቶላ፣ እና እንደ አርጋው አሸኔ ያሉ ነጠላ ስደተኞች፣ ከተሰደዱ ወዲህ በተለያዩ አምባዎች እና ማኅበራዊ አውታሮች ከሚያሰፍሯቸው ጽሑፎች ውስጥ መረዳት እንደምንችለው፣ አንደኛ በስደት ሆነውም ብዙዎቹ አገር ውስጥ ሆነው የነበራቸውን አቋም ቀጥለውበታል፤ ሁለተኛ ከተሰደዱ ወዲህ ያሉ ወቅታዊ ጉዳዮችን በመከታተል ራሳቸውን ከአገር ውስጥ መረጃዎች አላራቁም፣ ሦስተኛ የአገር ውስጥ እውነታዎችን በተዛባ ሁኔታ አይረዱም፣ ወይም ለግል ጥቅማቸው መጠቀሚያነት ሲረባረቡበት አልታዩም፣ አራተኛ እነዚሁ ሰዎች የስርዓት ለውጥ ከመጣ ተመልሰው መጥተው እኛኑ ነውና ‹‹ጽንፈኛ›› በሚለው አብረን ልንፈርጃቸው አይገባም፡፡

## የዳያስፖራ ተቃዋሚ ፓርቲ/ቡድን አመራሮችና እና አባላት

በርካታ የቀድሞ ተቃዋሚ ፓርቲ አመራር አባላት ተሰድደዋል፡፡ በተለይም የፈረሰው የቅንጅት አባላት ከነበሩት ውስጥ ጥቂት የማይባሉት በስደት የየራሳቸውን ቡድን እና ፓርቲ መስርተዋል፤ ከነዚህ ውስጥ እንደምሳሌ የዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ግንቦት ሰባት አንዱ ነው፡፡ በሌላ በኩል የኦባንግ ሜቶ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ፣ የዶ/ር ፍስሐ እሸቴ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሽግግር ምክር ቤትም ሳይጠቀሱ የማይታለፉ ናቸው፡፡ እዚያው ለረዥም ዓመታት ነዋሪ የነበሩ፣ በተለይም በደርግ ዘመን የተሰደዱ በርካታ የኢሕአፓ ሰዎችም ፖለቲካው ውስጥ በግልም በቡድንም አይጠፉም፡፡

እነዚህንም በተመለከተ ሁለት አመለካከቶች አሉ፤ ምንም አልሠሩም/አይሠሩም እና ያቅማቸውን እየሠሩ ነው የሚሉ፡፡ ነገሮችን በምሳሌ መመልከቱ እየሠሩ ያሉትን እና ያላግባብ ስም እየፈሱ ያሉትን ለመለየት እና ወደፊትም እየጠየቅን ምስጋናችንን/ድጋፋችንን እንድንችር ያደርገናል፡፡ እነሆ ምሳሌዎቹ፡-

- በገዢው ፓርቲ በአሸባሪነት የተፈረጀው እና ግዝፈቱ እና አስፈሪነቱ በቴሌቪዥን የሚደሰኮርለት ግንቦት ሰባት እስከአሁን ድረስ የሠራው ሥራም ሆነ ያሸበረው ሽብር ምን እንደሆነ ቢጠየቅ፣ ተቃውሟቸውን በይፋ ለሚገልፁ ሰዎች ‹‹ባጅ›› በመሆን ለመንግስት ከማገልገል ውጪ ይሄ ነው የሚል መልስ ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሽግግር ምክር ቤት መነሻዬ ያለውን ለኢትዮጵያ የስርዓት ለውጥ የተዘጋጀ የሽግግር መንግስት የማዋቀር ሥራውን ትቶ በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር የሞት ቀን ላይ (እንደ መረጃ ሰጪ ሚዲያ) የጦፈ ክርክር በማድረግ የትኩረት አቅጣጫውን ስቶ ታይቷል፡፡ ሲመሠረት በሁለት ወራት ውስጥ፣ የአቶ መለስ ኅልፈት ከተሰማ ወዲህ ደግሞ በሁለት ሳምንት ውስጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ነጻ አወጣለሁ ብሎ ቃል የገባው ይሄው የሽግግር መንግስት ቃሉ ከተግባሩ የፈጠነ መሆኑ ሌሎች የዳያስፖራ ቡድኖችንም ሆነ እራሱን ከተኣማኒነት ዝርዝር ውስጥ በዚህ መንገድ እንዲያወጣ ያሰጋል፡፡
- EAC (Ethiopian Americans Council) በመባል የሚታወቀው ቡድን በተቃራኒው፣ በተቃራኒው ለኦባማ ደብዳቤ ከመጻፍ አንስቶ፣ በልማት ሰበብ የሚገኙ የእርዳታ ገንዘቦች ነጻነትን ማፈኛ እንዳይወሉ የማንቂያ ደውል ለአሜሪካ መንግስት በመደወል እየሰሩ ያሉት የሚበረታታ ነው፡፡ የጋራ ንቅናቄ የተባለውም ቡድን በተለይ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የአቋም መግለጫ ጽሑፎችን በማውጣት ይታወቃል፤ አሁንም እንኳን

> በቅርቡ ለጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ለውጥን የሚጠይቅ ግልጽ ደብዳቤ አሰራጭቷል። የHR2003 (የሰብአዊ መብት ጉዳይን ያስቀደመ መመሪያ) የአሜሪካ መንግስት የኢትዮጵያ መንግስት ላይ እንዲጥል አሊያም እርዳታ እንዲያግድ የሚያደርገውን ዶሴ በማርቀቅ እና እንዲፀድቅ እና አገር ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ ጫፍ ደርሶ የነበረ ትግል የታገሉትም የዳያስፖራ ቡድኖች ናቸው። ይህንን በምክንያት ከመሟገት እና ለውጥን ከመወትወት ወይም የ‹‹አራማጅነት›› ሚና የተሻለ የሚሠሩ እና ሊበረታቱ የሚገባቸው አሉ።

በተለያየ የፓለቲካ ግብ ውስጥ የሚንቀቀሱ የፓለቲካ ቡድኖች ምንም እንኳን የፓለቲካ አቋማቸውን በሚደግፍ መልኩ መረጃዎችን መተንተናቸው የሚያስቀወቅሳቸው ባይሆንም፣ ቡድኖቹ ግልጽ ባልሆነ የፖለቲካ ዓላማ እና የሕዝቡን ነባራዊ ፍላጎት እና ሁኔታ ከግምት ውስጥ ባላስገባ እንቅስቃሴ የሚሰጡት ትንታኔ አቅጣጫ ወይም መረጃ አምታች እና አወናባጅ መሆን የለበትም። ይህ ዓይነቱ ችግር አገር ውስጥ ያሉትም የፖለቲካ ቡድኖች ቢሆንም በዳያስፖራዎቹ ይጋነናል የሚል እምነት አለን። ውሸት ይነግሩናል ባንልም ከነርሱ ጋር የሚያሟግተንን እውነት ሊደብቁን፣ ወይም ለነሱ ፍላጎት የሚያመዝነውን ብቻ ሊያስተጋቡልን ይችላሉ የሚለው ስጋት አገር ውስጥ ባለው ወገን ዘንድ የሚፈጠረውም ይሄን ጊዜ ነው።

## ለመኖሪያ ፈቃድ ሲባል…?

ለትምህርት፣ ለስልጠና፣ ለወርክሾፕ፣ ለስብሰባ፣ ለጉብኝት እና በመሳሰሉ ምክንያቶች ከአገር ወጥተው በዚያው ቀልጠው የሚቀሩ ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም። እነዚህ ሰዎች አሁን አሁን እንደፋሽን የሚጠቀሙበት የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቅን ነው። የፖለቲካ ጥገኝነት ጠያቂዎቹን በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን። የመጀመሪያዎቹ፤ በሚሄዱበት አገር የፖለቲካ ጥገኝነት ሊያሰጣቸው የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት አገር ውስጥ በነበሩበት ወቅት የሚያደርጉ ናቸው። የተቃዋሚ ፓርቲ መታወቂያ ለማግኘት መጣር፣ መንግስትን በመተቸት ከሚታወቁ ሰዎች ጋር ፎቶ መነሳት እና መንግስትን የሚቃወሙ ጽሑፎችን በግል የሕትመት ሚዲያዎች በስማቸው ማውጣትን በምሳሌ ማንሳት እንችላለን። አጋጣሚውን አግኝተው ከዚህ አገር በሚወጡበት ወቅት ቀድመው ያዘጋጇቸውን ምክንያቶች እንደማስረጃ በማቅረብ የፖለቲካ ጥገኝነት ጥያቄ ያቀርባሉ። በሁለተኛው ክፍል የምናገኛቸው ደግሞ ከላይ በጠቀስናቸው ባንዱ ምክንያት ከአገር የመውጣቱን አጋጣሚ ድንገት ያገኙና ምንም ዓይነት ቅድመ ዝግጅት ሳያደርጉ የሚወጡ ናቸው። ካገር ሲወጡ እዛው የመቅረትን ጉዳይ በአዕምሮአቸው የነበራቸው ቢኖሩም የመመለስ ዕቅድ የነበራቸው እና እዛው ባሉበት ሐሳባቸውን ቀይረው ለመቅረት የወሰኑም ይገኙበታል።

ሁለቱንም ቡድኖች የሚያመሳስላቸው በሄዱበት ለመቅረት ያላቸው ፍላጎት፣ መኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸውና የሐሰት መረጃዎችን ለሚመለከተው ክፍል ማቅረባቸው ነው። በመጀመሪያው ቡድን ያሉት ቀደም ብለው በጉዳዩ ላይ ተዘጋጅተውበት በመውጣታቸው እንደሄዱ ማመልከቻቸውን በማስገባት ባጭር ጊዜ ውስጥም ሊሳካላቸው የሚችል ሲሆን በሁለተኛው ቡድን ያሉት ግን የሐሰት መረጃዎችን ማሰባሰብ የሚጀምሩትና የሚያገኙት ከጥቂት ቆይታ በኋላ አንዳንድ ጊዜም የቪዛቸው ጊዜ ወደማለቁ አካባቢ ወይም ካለቀ በኋላ ስለሚሆን ለብዙ መጨናነቅ፣ ወጪና እንግልት ይዳረጋሉ። እንዲህም ሆኖ መኖሪያ ፈቃድ የማግኘታቸውና ያለማግኘታቸው ጉዳይ እኩል፣ እኩል ነው።

እንደነዚህ ዓይነት "ዳያስፖራዎች" (በትዕምርተ ጥቅስ) ብዙዎቹ ስለአገራቸው የፖለቲካ ታሪክ እና ወቅታዊ ፖለቲካና ማኅበራዊ ጉዳዮች ጠለቅ ያለ መረጃ ባይኖራቸውም፣ መንግስትን የሚቃወም የማንኛውንም ግለሰብም ሆነ ድርጅት ሐሳብ ያስተጋባሉ። ለዚህም በዋነኝነት ፌስቡክ እና ትዊተርን ጨምሮ የተለያዩ ማኅበራዊ አውታሮች፣ ጦማሮችን እና ድረገጾችን እንደመሳሪያነት ይጠቀሙበታል። ባለስልጣናት ለሥራም ሆነ ለስብሰባ እነሱ ወዳሉበት ቦታ በሚመጡበት ጊዜም - ነባር፣ በእውነተኛ ተቃውሞ ጦስ ተሰድደው የወጡ የዳያስፖራ አራማጆች በሚያስባብሯቸው - ተቃውሞዎች ላይ መታደም እና በቦታው መገኘታቸውን የሚያሳይ መረጃ መያዝ ተቀዳሚ ሥራቸው ነው።

በተጨማሪም በአገራችን የሚካሄዱ ኢ-ፍትሐዊ ድርጊቶችን በመቃወም የሚደረጉ ሰልፎችና አላግባብ የታሰሩ ዜጎችን ለማስታወስ የሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ላይም ቁጥር አንድ ተሳታፊ ናቸው። ምናልባትም ከፕሮግራሙ ርዕስ በዘለለ የተዘጋጀበትን ምክንያት እና ዓላማ ላያውቁ ይችላሉ። ባጭሩ በዚህ ምድብ የሚገኙ "ዳያስፖራዎች" አብዛኛዎቹ ማለት ይቻላል የኔ የሚሉት ፖለቲካዊ አቋምም ሆነ አመለካከት የሌላቸው ሲሆን ዋነኛ ሥራቸው በመንግስት ላይ የሚሰነዘርን ማንኛውም ዓይነት ተቃውሞ ባገኙት አጋጣሚ ሲያስተጋቡ መታየት ወይም መሰማት

ነው። እነዚህ ጠቅላላውን የ‹ዳያስፖራ ፖለቲካ› ውጤታማነት እንዴት እንደሚያውኩት በሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል፦

- የተቃውሞ ሰልፎች እና ስብሰባዎች ላይ የሚሳተፉ እነዚህ ለፖለቲካው ጤንኝነት ደንታ የማይሰጣቸው ሰዎች ‹‹ጥገኝነት›› ፈላጊዎች ግንባር ቀደም እና አርማ ተሸካሚ ሆነው በፎቶ እና ቪዲዮ ማኅበራዊ አውታሮች ላይ በአጋጣሚ የሚመለከቱ እና ግለሰቦቹን የሚያውቋቸው የአገር ቤት ሰዎች ጠቅላላ የዳያስፖራውን እንቅስቃሴ በግለሰቦቹ ዓይን የመዳኘት እና በኢቴቪ ፕሮፓጋንዳ ‹‹ጥገኝነት ለመጠየቅ ሲሉ›› የሚለውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስለሚሆን፣
- ግለሰቦቹ የጥገኝነት ወረቀታቸውን ካገኙ በኋላ ተመልሰው ትግሉን ስለማይቀጥሉበት፣ መጣ ቅርት የሚሉ አራማጆችን መመልከቱ/መከታተሉ ተስፋ ስለሚያስቆርጥ፣
- ግለሰቦቹ ወረቀቱን እስከሚያገኙ ድረስ ፖለቲካዊ ተሳትፏቸውን ለማጉላት እና ተቃዋሚነታቸውን ለማሳመን ጽንፍ ድረስ ስለሚጓዙ የጠቅላላውን ዳያስፖራ መልክ በአንድ ላይ የማጉደፍ ኃይል አላቸው።

እነዚህን ግለሰቦች በጥንቃቄ መጠቀም ያልቻለ የዳያስፖራ ማኅበረሰብ ወይም ዝግጅት አስተባባሪ፣ ወይም በጥንቃቄ መከታተል ያልቻለ የአገር ውስጥ ነዋሪ መስመሩን የሳተ ግንዛቤ ስለዳያስፖራዎቻችንም ሆነ ስለአጠቃላይ እንቅስቃሴያቸው ያኖራል።

## የዳያስፖራ ሚዲያዎች

በተለይም በፖለቲካው ዙሪያ መረጃ እና ትንታኔዎችን የሚያቀርቡ በርካታ፣ ባብዛኛው ኢንተርኔት ላይ ጥገኛ የሆኑ መገናኛ ብዙሐን አሉ። ከነዚህ ውስጥ በድረገጽ የሚሰሩት እነኢትዮሚዲያ፣ ዘሐበሻ፣ ኢትዮጵያንሪቪው፣… እና አሁን እየጎሉ ከመጡት ውስጥ ደግሞ ጎልጉል ሳይጠቀሱ አይታለፉም። እነዚህ መገናኛ ብዙሐን በተለይ ገዢው ፓርቲን በሚቃወሙ መጣጥፎች ላይ ምንም መመዘኛ የሌላቸው እስኪመስል ድረስ፣በአገራዊ ስነምግባራዊ እሴቶች የሚያስገምቱ ስድቦችን በማስተናገድ ጭምር ይታወቃሉ። ከነርሱ በተቃራኒው የቆሙት እና የገዢው ፓርቲን በማንቆለጳጰስ ሥራ ተጠምደው፣ ዓላማቸው ‹‹አማራጭ ሚዲያ›› መሆን ይሁን ወይም ካድሬነት የማይለዩት እነአይጋፎረም፣ ኢትዮጵያፈርስት እና ትግራይኦንላይን የመሳሰሉት ድረገጾች ደግሞ ተቃዋሚውን እስካዋረደላቸው ድረስ የሚያሰራጩት መረጃ እውነት ይሁን ሐሰት እንኳን ለማጣራት አይጨነቁም።

በዚህ መሐል የሚዲያዎቹን ማንነት እና እሴት የማያውቀው አንባቢ በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳል። አሁን በተቃዋሚ ወገን የምንመድባቸው በሙሉ በኢትዮጵያ እንዳይነበቡ በመታገዳቸው በፊት በኢትዮጵያ ከፍተኛ ጎብኚ የነበራቸው እነናዝሬት እና ኢትዮጵያንሪቪው ከዝርዝሩ ወጥተው፣ ከፍተኛ ተነባቢነት ያላቸው እነትግራይኦንላይን መሆናቸውን የአሌክሳ ዌብ ትራፊኪንግ መረጃ ያመለክታል። ይሁን እንጂ የታገዱትን ገጾች ዜናዎች በዚህም ሆነ በዚያ እያሉ (በተለይ በማኅበራዊ አውታሮች) በኩል የሚያገኙት ብዙሐን ናቸው።

ከዚህ በፊት የአገር ውስጥ ጋዜጦች መለስ በመልካም ጤንነት ላይ ናቸው ብለው በማለታቸው ይቅርታ እንዲጠይቁን ወትውተን እንደነበር ይታወሳል። ከዳያስፖራ መገናኛ ብዙሐን መካከልም፣ በተለይ ኢትዮጵያንሪቪው ብዙ ባለስልጣናትን እና ባለሀብቶች ሳይቀር ሞተዋል፣ ተሰደዋል የሚሉ ዜናዎችን ጽፎ አንብበን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ስህተት መሆኑን ሰምተናል። በተመሳሳይ እነርሱም ይቅርታቸው ይገባን ነበር። ምንም እንኳን ይህ ጽሑፍ ይህንን ርእስ ለማንሳት ባያስብም የተአማኒታቸውን ነገር ግን ችላ ማለት አይገባም።።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንም እዚህ ምድብ ውስጥ ይካተታል። የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የዳያስፖራ እኩያው ነው መባል ከጀመረ ሰንብቷል። በፅንፈኛነት ስሙ መነሳት ከጀመረ ሰነባብቷል። ለዚህ እንደምክንያት የሚጠቀሱት፣ ሙያዊ ስነምግባር (professional ethics) ላይ እምብዛም አለመጠንቀቃቸው፣ ከዜና እና ዜና ነክ ትንታኔዎች በላይ አንጀት አርስ ፕሮግራሞችን አለመሥራታቸው፣ ከአገር ቤት ጋር የሚገናኙ ጥቃቅን የሁከት ዜናዎችን ማጋነናቸው ሳይጠቀሱ የማይታለፉ ድክመቶች ናቸው። አማራጭ መገናኛ ብዙሐን በሌለበት ኢሳትን አለማመን ቢከብድም፣ ኢሳት ይህንን ግዳጁን በሙሉ ኃላፊነት እንዲወጣ እና በሙሉ ልብ እንዲታመን ገና ብዙ ይጠበቅበታል።

እርግጥ ነው፣ እነዚህ መገናኛ ብዙሐን እዚህ አገር የታፈኑ (የተነወሩ) በርካታ እውነታዎችን ለሕዝቡ በቻሉት መንገድ ሁሉ ለማድረስ በስደት ሕይወታቸው መፍጨርጨራቸው ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ቢሆንም ጥረታቸው

ዋጋ እንዲኖረው ተአማኒነት ያላቸውን መረጃዎች ለማቅረብ መድከም አለባቸው፡፡ አለበለዚያ ስናነባቸው በጥርጣሬ እንዲሆን ልንገደድ እንችላለን፡፡

## የዳያስፖራ ምሁራን እና አራማጆች

በኢትዮጵያ ያሉ ምሁራን ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚያስደፍር ሁኔታ ዝምታን በመረጡበት በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ ወቅታዊ ፖለቲካ ምሁራዊ እይታ እንዳያጣ ትንሽ የረዱት የዳያስፖራ ምሁራን እና ሌሎችም ለነፃነት ተቆርቋሪ ስደተኛ አራማጆች ናቸው፡፡ እነአለማየሁ ኃይለማርያም፣ እነመሳይ ከበደ፣ ጃዋር መሐመድ እና ሌሎችም ሳይጠቀሱ አይታለፉም፡፡

የዳያስፖራ ምሁራን በተለያዩ ከላይ በጠቀስናቸው እና ሌሎችም መገናኛ ብዙሐን የሚያቀርቧቸው ትንታኔዎች ምንም እንኳን በአብዛኛው ወደሚደግፉት ቡድን ርዕዮት ያመዝናሉ የሚል ሐሜት ቢያጋጥማቸውም በዳያስፖራው ማኅበረሰብ ተአማኒነት ያለው መረጃ በመስጠት የተሻሉ ናቸው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት፣ ብዙ ጊዜ መከራከሪያ ነጥቦቻቸው እውነታዎች እና ሳይንሳዊ ርዕዮተ ዓለሞች መሆናቸው ነው፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ምሁራን የሚያቀርቧቸው ጽሑፎች እንደሌሎቹ አጫጭር መጣጥፎች ከስድብ ይልቅ አመክንዮ ይበዛባቸዋል፡፡ ስለዚህ የምሁራኑን ትንታኔ እያነበቡ የራስን ውሳኔ መውሰዱ ጠቃሚ እንደሚሆን መደምደም ይቻላል፡፡

በጥቅሉ፣ ፖለቲካ ቀመስ የሆኑ ጽሑፎችን የምናነበው ወይም የምንጽፈው መረጃ ለመለዋወጥ ያክል ብቻ ሳይሆን ለብሔራዊ ለውጥ ጉጉት ስላለን ነው፡፡ ቢሆንም ግን በአገር ውስጥም ሆነ በዳያስፖራው ውስጥ ብሔራዊ ብቻ ሳይሆን ግለሰባዊ አጀንዳ ያላቸውም ሰዎች አሉ፡፡ ይህ በተለይ በኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች ላይ ያተኮረው ጽሑፋችን ዓላማም፣ የዳያስፖራ ፖለቲካ ውስጥ ‹‹ማን፣ ምን እና ለምን›› የሚለውን በማገናዘብ ሁሉንም በጽንፈኝነት ወይም በተቃራኒው የዋሕነት ብቻ ሳይቀበል እንዲመረምር በማድረግ ማኅበራዊ ተዋስኦን ማበረታት ነው፡፡

በተለይ በጉዳዩ ላይ ከዚህ በፊት በተነሱ አስተያየቶች ዳያስፖራው ለሚታማበት ጽንፈኝነት የራሳቸውን ምክንያት የሚዘረዝሩ አሉ፡፡ ከነዚህ ምክንያቶች ውስጥ እኛ (በአገር ውስጥ ነዋሪዎች) በባሕላዊ አስተሳሰቦች እና በዴሞክራሲ መብት እጦት የታፈነ ማኅበረሰብ ውስጥ የነጻነትን ትክክለኛ ትርጉም እና ጣዕም በአግባቡ ማጣጣም ባለመቻላችን የመጣ ክፍተት እንደሆነ የሚናገሩ አሉ፡፡ በተጨማሪም፣ አንዳንዴ የነጻነትን ትክክለኛ ጣዕም ያጣጣሙ ስደተኞች ያን ዓይነቱ ለውጥ ወደአገር ቤት በተቻለ ፍጥነት እንዲመጣ ማሰባቸውም ለአንዳንድ ስህተቶች እንደሚዳርጋቸው ይታመናል፡፡ ዞሮ፣ ዞሮ እዚህም ያለነው ወይም እዚያ ያሉት የምንታገለው ለጋራ ለውጥ ስለሆነ እነርሱም እኛን፣ እኛም እነርሱን የምናደምጥበት መድረክ እና ቋንቋ ያስፈልገናል፡፡

# የእነርሱ እና የእኛ ሕዳሴ

የሐዲስ ዓለማየሁን "ጉዱ ካሣ"፣ የበዓሉ ግርማን "አበራ"፣ የዳኛቸው ወርቁን "አደፍርስ" ማን ይዘነጋቸዋል? እንኳን 'ፍቅር እስከመቃብር'ን፣ 'ከአድማስ ባሻገር'ን እና 'አደፍርስ'ን ያነበቡ ቀርቶ ያላነበቡም ያውቋቸዋል። እነዚህ ገጸ ባሕርያት የሚታወሱት ከዘመናቸው ባፈነገጠ ማኅበራዊ ሃያሲነታቸው ነው።

እነዚህን ገጸ ባሕርያት ወደኋላ ዞር ብለን የፈጠሯቸውን ደራሲያን ስናስብ ደራሲያኑ በየገጸ ባሕሪዎቻቸው አንደበት ማኅበረሰቡን በነገር አለንጋ ይገርፉታል፣ በምክንያት ይሞግቱታል። ያኔ እነዚህ እና ሌሎቹም ጸሐፍት ይህንን አሉ፤ ዛሬ እና የዛሬዎቹስ?

እዚህች'ጋ ሌላው የዞን ዘጠኝ ጦማሪ [ባለፈው ሣምንት]() የጠየቃትን ጥያቄ መልኳን ቀይሬ ላንሳትና፣ እንደው ለመሆኑ (ከዚሁ ከልቦለድ ዘርፍ ሳንወጣ) በአለፉት አምስት፣ አሥር ወይም ሀያ ዓመታት ውስጥ እጅግ ተወደደ አነጋገረ፣ ልቤ ውስጥ ቀረ የምንለው መጽሐፍ አለ? ከላይ የጠቀስናቸውን ገጸ ባሕርያት ያክል ያመራመረን፣ ያነጋገረን፣ የሚታወሰን ገጸ ባሕሪ አለ? - ለኔ የለም።

ጥያቄውን በልቦለድ ብቻ አነሳሁት እንጂ፣ ከአንድ ወዳጄ'ጋ ከዚህ ቀደም በመሰል ሐሳቦች ዙሪያ ስናወራ፤ እስኪ የ60ዎቹን ዘመን ወጣቶች እና የአሁኖቹን እናወዳድር ብለን በሁሉም ዘርፍ ሞክረን ነበር። ያኔ የነበሩ ወጣት ደራሲያኖችን እና ገጣሚዎቻችንን ጠቃቅሰን እና አሁን ላይ መጣን… ከበውቀቱ ስዩም እና ምናልባትም እንዳለ ጌታ ከበደ በላይ መሻገር አልቻልንም። እነአፈወርቅ ተክሌ፣ እነእስክንድር ቦጎሲያን እና ወዘተን… ጠቃቅሰን እና የነርሱ እኩያ ይሆናሉ ብለን ተስፋ የምንጥልባቸውን ሰዓሊዎች ማፈላለግ ጀመርን፣ ይሄ ነው ልንነው የምንችለው ሰው አልመጣልንም፤ ሌላው ቀርቶ የሙዚቃ ባንድ እና ዘፈን ዘርፍ ውስጥ መጣን፣ የበፊቶቹን ኦርኬስትራ ቡድኖች የሚተካ፣ ወይም ሁሌም ልብ የሚያሸብሩትን ዘፈኖች እና ዘፋኞች ይተካል ብለን የምንጠራው ዘፋኝ አልነበረንም… ምናልባት እጅጋየሁ ሽባባው… ተባባልን። ከጋዜጠኞችም ለማወዳደር ሞካክረን ነበር፣ እነ ጳውሎስ ኞኞን፣ እነ ታደሰ ሙሉነህን የሚተካ ቀርቶ ተስፋ የሚጣልበት ጋዜጠኛ አለ?

በየጊዜው በናፍቆት የምንጠብቀው የጋዜጣ ወይም የመጽሔት አምድ/አምደኛ፣ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ትዕይንት፣ ልባችን እስኪጠፋ በጋራ የምናደንቀው ወጣት ባለሙያ ወይም ጀግና… ብቻ በጥቅሉ ምንም የለንም።

ችግሩ የኛ አለማወቅ ነው፣ ወይስ አማተሮቹን ከአንጋፋዎቹ ጋር ማወዳደራችን የሚል ጥያቄም ተከስቶብኝ ነበር፤ ይሁን እንጂ እነዚህን የምናደንቃቸውን አንጋፋ ባለሙያዎች የምናደንቅላቸው የወጣትነት ሥራዎቻቸውን እንጂ አሁን በስተርጅና የሠሯቸውን (ያውም ካሉ) አለመሆኑን ሳስብ ችግሩ የእውነት የወቅቱ የፈጠጠ ችግር መሆኑ ታሰበኝ እና እንድንነጋገርበት ይገፔው መጣሁ።

## ኢትዮጵያ እንዴት ሰለጠነች?

ለውይይታችን ማጠናከሪያ፣ ኢትዮጵያን የማዘመን ሙከራዎች በየመንግሥታቱ መሞካከራቸውን እያስታወስን ከነዚህ ውስጥ ዐብይ ለውጥ ያስከተሉትን ጥንታውያን የዘመናዊነት እንቅስቃሴዎች እና የሀያኛውን ክፈለዘመን እርምጃዎች እያየን ዘንድሮ ላይ እንደርሳለን።

1. **የአክሱም ስልጣኔ**
   ከክርስቶስ ልደት በፊት 400 ዓመት አስቀድሞ የተጧጧፈው የአክሱም ስልጣኔ እስከ 10ኛው ክፍለ ዘመን ለመዝለቅ ችሎ ነበር። ይሁን እንጂ የአክሱም ስልጣኔ ስር መሠረት እና ውርሱ በቅጡ አይታወቅም። እስካሁንም ድረስ ቆመው ከሚገኙት እና አምልኮተ-መሬባትን ያመለክታሉ ከሚባሉት ሀውልቶች በቀር ለትምህርትነት የሚበቃ፣ ወይም ከዚያ ዘመን ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ትውፊታዊ ቁምነገር አለ ለማለት የሚያስደፍር ግኝት የለም፣

2. **የዛግዌ ስልጣኔ**
   የአክሱም ስልጣኔ መውደቅን ተከትሎ የኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን ለ200 ዓመታት ነገሠ። ከዚያም በመራ ተክለሃይማኖት አማካይነት የዛግዌ ስልጣኔ ተጀመረ። የዛግዌ ስልጣኔ ክርስትናን በማስፋፋት ላይ

የተመሠረተ ሲሆን ትሩፋቱም የላሊበላ ውቅር ዐብያተ ክርስትያናት እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ትውፊታዊ ትምህርት ናቸው። የዛግዌ ዘመነ መንግስት ከአክሱም ስልጣኔ በተሻለ ሃይማኖት ቀመስ ቢሆኑም ጽሑፎች ተጽፈው ለቀጣዩ ትውልድ የተላለፉበት የመጀመሪያው ዘመን ነው ማለት ይቻላል፣

3. **ሰሎሞናዊ ስልጣኔ**

ይሄንኛው የስልጣኔ ዘመን የአክሱም ዘመን ቀጣይ እና ሰሎሞናዊ ቤተሰብ ነን በሚሉ ነገሥታቶች የተመራ የስልጣኔ ዘመን ነው። የዚህ ዘመን መጨረሻ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው። ይህ ዘመን ለቅርስነት ያስመዘገባቸው ነገሮች የሉም ማለት ይቻላል (የዘመነ መሳፍንት ቤተመንግሥታትም ቢሆኑ በዚህ ዘመን መሐል የተፈጠሩ የመከፋፈል ታሪኮች ናቸው፤) ሆኖም የአሁኒቷ ኢትዮጵያ የአሁኑን ቅርጿን የያዘችው በዚህ የስልጣኔ ዘመን ነው። በዚህ ዘመን አውሮጳውያን አፍሪካን ሲቀራመቱ ኢትዮጵያውያን ግን በእምቢተኝነት ራስ ገዝ አስተዳደር የፈጠሩበት ይህ ዘመን ነው። በዚህ ዘመን በተለይም ከአድዋ ድል በኂላ የተሠሩት ሥራዎች ኢትዮጵያን ከዘመናዊነት ጋር በማስተዋወቁ ረገድ መንገድ ጠራጊዎች ናቸው ማለት ይቻላል፤ በዚህ ዘመን ባቡር፣ ዘመናዊ ትምህርት፣ የጤና ብሎም የባንክ አገልግሎቶች እና ወዘተ ለመጀመሪያ ጊዜ በአገራችን ተዋውቀዋል፣

4. **የድኅረ ጣሊያን ኃይለሥላሴ ስልጣኔ**

በዘመናዊት ኢትዮጵያ ውስጥ ጉልህ ስፍራ የሚኖራቸው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አብዛኛውን ኢትዮጵያን የማዘመን ሥራ የሠሩት ከጣልያን የአምስት ዓመት ወረራ በኂላ ነበር ማለት ይቻላል። ሚያዝያ 27/1933 ንጉሡ ከስደት ሲመለሱ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት የ'አዲስ ዘመን' እንቅስቃሴያቸውን ጀመሩ። በወቅቱ ኢትዮጵያን ከሙሉ ፊውዳላዊ አስተዳደር በከፊል አላቀዋታል፣ በብሔር እና ሃይማኖት "መቻቻል" ላይ መጠነኛ ሚዛን እንዲሰጥ በሚል ሕገ መንግሥታቸውንም አሻሽለዋል፣ ፓርላማው ለሕዝቦች በመጠኑ የተከፈተውም በዚሁ ዘመን ነው፣ በተለይም ደግሞ ዘመናዊ ትምህርት ተስፋፋ። ከዚያም በላይ እስከአሁኑ የአባይ ግድብ፣ የቁጠባ ቤቶች (ኮንዶስ)፣ የአዲስ አበባ ቀለበት መንገድ እና ወዘተ መሠረታቸው የተጣለው በዚህ የስልጣኔ ዘመን ነበር። በተለይ በዚህ ዘመን የተፈጠረው የትምህርት እና የአንባቢነት ፋሽን በመግቢያችን ላይ የጠቀስናቸውን ዘመን አይሽሬ ጠበብት ለመፍጠር በቅቷል፣

5. **የማርክሲስት ስልጣኔ**

የዚህ ዘመን ስልጣኔ ባለቤቶች የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን ወጣቶች ሲሆኑ፣ ወደማርክሲዝም የመራቸውም በዘመኑ ለነበረው ፊውዳላዊ አስተዳደር የነበራቸው የመረረ ጥላቻ ነው። በዚህ ዘመን ለተመሳሳይ ርዕዮተ ዓለም (ማርክሲዝም/ማኅበረሰባዊነት) ነገር ግን በተለያየ ቡድን ተቧድነው ሲቆራቆዙ የነበረበት ዘመን ሲሆን፣ ለሁለት አሥርት ዓመታት በዘለቀው መቆራቆዛቸው ሳቢያ 'ሰብኣዊ-ዘመናዊነት' የጎደለው ዘመነ ስልጣኔ፣ ነገር ግን በተለይ መንግሥታት ከሃይማኖታዊ ጥገኝነት የተላቀቁበት ዘመን ነበር ማለት ይቻላል። በዚህ ዘመን መጀመሪያ ላይ ተስፋ ፈንጥቆ የነበረው መሃይምነትን የመቅረፍ ‹የመሠረተ ትምህርት› ዘመቻም፣ በዘመኑ መጨረሻ ላይ ጠውልጎ ነበር፤ ሕዝቦች ለፖለቲካዊ ተሳትፎ የነበራቸው ጉጉት በፍራቻ መቀመቅ የወረደውም በዚህ ዘመን ነው፣

6. **የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስልጣኔ**

የማርክሲስትን የስልጣኔ ዘመን (በአገራችን) ተክቶ የመጣው የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ስልጣኔ አጀማመሩ ላይ ለካፒታሊዝም የቀረበ ቅይጥ ኢኮኖሚ መር ስልጣኔ ለመሆን ቢሞክርም፣ የኂላ ኂላ *ሶሻሊስታዊ ዴሞክራቲክ* ኢኮኖሚ መር የሚመስል የስልጣኔ ዘመን ሆኗል። ዘመኑን በይፋ 'የሕዳሴ ዘመን' ብሎ ለመጥራት በመንግሥት የታወጀ ሲሆን፣ በተለይ ለአንደኛ ደረጃ (አውራ) መንገዶች እና ሕንጻ ግንባታ ትኩረት የሰጠ የስልጣኔ ዘመን ነው። በዚህ ዘመንም፣ ልክ እንደ ማርክሲስታዊው የስልጣኔ ዘመናችንም ሁሉ የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊው የስልጣኔ ዘመን ለሰብኣዊ ልማት ምንም ትኩረት ያልሰጠ፣ ትምህርት ከጥራት ይልቅ በቁጥር የተመዘነበት እና በአስተዳደሩ ርዕዮተ ዓለም አስፈጻሚነት የተከረከመ ትውልድ ከማፍራት በላይ ያልተጋ ዘመን ነው ለማለት የሚያስደፍር ትውልድ ተፈጥሯል።

በየዘመናቱ የከፋፈልናቸውን የስልጣኔ መስመሮችን ተከትለን ስንመለከት፥ ለሰብኣዊ ሀብት ልማት (ዕድገት) ትኩረት የሰጠው የድኅረ ጣልያን ኃይለሥላሴ ዘመን ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን። በተቃራኒው ደግሞ አሁን ያለንበት ዘመን "የሕዳሴው ዘመን" እየተባለ በአስተዳደሩ እየተጠራ ነው። እውነት ሕዳሴ ማለት የግንብ ብቻ ነው?

## የእነርሱ ሕዳሴ

የኢትዮጵያ መንግሥት "ሕዳሴ" የሚለውን ቃል የኮረጀው ከአውሮፓጻውያን "Renaissance" ይመስላል። ሬኔሳንስ በፍሎረንስ፣ ጣልያን ተጀምሮ በመላው አውሮጳ መስፋፋት የቻለ እና ከ14ኛው እስከ 17ኛው ክፍለዘመን የዘለቀ "የባሕል እንቅስቃሴ" ወይም የባሕል አብዮት ነው።

የእነርሱ ሬኔሳንስ በመካከለኛው ዘመን እና በአሁኑ ዘመን መካከል የስልጣኔ ሽግግር ድልድይ በመሆን አገልግሏል። የዚህ ሬኔሳንስ ዋነኛው መሠረቱ ሥነ ጽሑፍ፣ ሥነ ፍልስፍና፣ ሥነ ስዕል፣ ሥነ ፖለቲካ እና ሌሎችም ላይ የዘመናዊነት መልክ ለማላበስ የተካሔዱት ክርክሮች የአስተሳሰብ አብዮቶች በማፍለቅ አውሮጳውያንን ግንባር ቀደም የስልጣኔ ቀዳጅ አድርጓቸዋል።

የእኛ "ሕዳሴ" ግን በቀለበት መንገዶች እና በ"ሰማይ ጠቀስ" ሕንጻዎች ላይ የተንጠለጠለ በመሆኑ የቀለበት መንገዱን አጠቃቀም እና የሕንጻዎቹን አጠቃቀም እንኳን በአግባቡ የማያውቅ እና ቢያውቅም የማያከብር ብዙሐን አፍርቷል። የትምህርት ፖሊሲውም በበኩሉ ብዙሐኑን ተከራክሮ የሚያሳምን የሐሳብ ሊቅ ሊፈጥር ቀርቶ የሥራ ማመልከቻ በተስተካከለ ሰዋሰው መጻፍ የማይችል የዲግሪ ምሩቅ እያፈራ ነው፣ ሚዲያው እንኳን ሊያስተምር እና አርኣያ ሊያኖር ወይም ሊያቀርብ ቀርቶ "ወሮ በሎች" ልላቸው የምፈቅደው ሰዎች መናኸሪያ ሆኗል።

አሁን ያለንበትን ዘመን ስንታዘበው፥ አንድም አያቶቻችን ባኖሩልን የኩሩነት፣ የጨዋነት እና የሥነ ምግባር መመሪያ ሳንታነፅ አሊያም ሉላዊነት (globalization) ዘልቆን ከሰለጠኑት ዓለማት እኩል በሐሳብ ሳንራመድ - እንዲሁ የባከንን ትውልድ ሆነን መቅረታችን ያሳስበኛል። የዚህ ብክነት መፍትሔው - መማር እና ማንበብ ነው ማለት ይቻላል። ነገር ግን እንደ ትውልድ የትምህርት ዕድሉንም ሆነ እውነተኛ ለውጥ አጎናፂፊ ትምህርት ወይም የሚለውጥ ንባብም ሆነ ማንበቢያ በማጣት እየተሰቃየን እንደሆነ ሳስብ ደግሞ ስለራሳችን አዝናለሁ።

# "ጠንቅቆ" የመጻፍና አለመጻፍ ጉዳይ

በእንግሊዝኛው spelling ወይንም orthography የሚባለውን ፕሮፌሰር አምሳሉ አክሊሉ "ጠንቅቆ መጻፍ" ሲሉ ሠይመውታል። ጠንቅቆ መጻፍ በአማርኛ ቋንቋ ትክክለኛውን ሆሄ በትክክለኛው ቃል ላይ መጠቀምን ይመለከታል።

ስንጽፍ 'መጽሀፍ፣መጽሃፍ፣ መጽሐፍ፣ መጽሓፍ፣ መጽኅፍ፣ መጽኃፍ፣ መጽኻፍ፣ መፅሀፍ፣ መፅሃፍ፣ መፅሐፍ፣ መፅሓፍ፣ መፅኅፍ፣ መፅኃፍ፣ መፅኻፍ' ከሚለው ውስጥ የትኛው ነው ትክክል ከሚለው ጥያቄ አንስቶ፥ ትክክለኛው ቃል ከታወቀ በኋላ ያንን ቃል በተጠቀሙ ቁጥር ለማስታወስ መቸገሩ፣ ያንኑ የሆሄ አጠቃቀም በርቢዎቹ ላይ (መጽሐፍ፣ ጸሐፊ፣ ጽሕፈት...) ላይ ለመተግበር እስከማስታወስ ድረስ በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ማለፍ የግድ ነው።

ሰሞኑን ከኢቴቪ እስከ ፍትሕ/አዲስ ታይምስ... ከፍትሕ/አዲስ ታይምስ እስከ ፌስቡክ ቃላትን በትክክለኛ ሆሄያቸው የመጠቀም እና ያለመጠቀም፣ ተደጋጋሚ ደምፅ ያላቸውን ሆሄያት የማስወገድ እና ያለማስወገድ ጉዳይ በጣም እያወያየ ነው።

ችግሩን መፍትሔ የሌለው ወይም ክርክሩ ማቧሪያ የሌለው የሚያስመስለው ደግሞ በተለይ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የሆሄያቱ መቀያየር የድምፅ እና የትርጉም ልዩነት የማያመጣ መሆኑ ነው። (ይህ ዓይነቱ ልዩነት ግን በግዕዙ ውስጥ የተለመደ ነው) ሌላኛው የአይቀነስ ባዮች መከራከሪያ ነጥብ ደግሞ "መቀነስ ምን ይጠቅማል?" የሚል እና "ከዚህ በፊት የተዘጋጁ እና የተከማቹ መዝገቦች እና ድርሳናት ማንበብ ይቸግራል" የሚል ነው።

ለነዚህ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ መስጠት በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። በርግጥ የሆሄያቱ መብዛት ለቋንቋው ቴክኖሎጂካል አገባብ (በተለይ ከኮምፒዩተር የቁልፍ ሰሌዳ አቀማመጥ አንጻር አስቸጋሪ እየሆነ ስለሆነ) ቢቀነስ ይጠቅማል ማለትም ይቻላል። የሆነ ሆኖ የዚህ ዓይነቱ ክርክር ሰሞኑን የተፈጠረ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ መጽሐፍ እጃችን የገባው፥ ለዞን ዘጠኝ የቋንቋ ዘዬ እያዘጋጀን ሳለን ነበር።

መጽሐፉ የፕሮፌሰር አምሳሉ አክሊሉ "የአማርኛ ሞክሼ ሆሄያትን ጠንቅቆ ያለመጻፍ ችግርና መፍትሔ" ይሠኛል። በመጽሐፉ መግቢያ ላይ በተለያዩ የሕትመት ውጤቶች ላይ የሆሄያት አጠቃቀም ግድፈቶች ለመጽሐፉ መዘጋጀት ምክንያት እንደሆናቸው ጠቅሰዋል። ሆኖም የአማርኛ ቋንቋዎች መርሐ ልሳን (አካዴሚ) በ1973 ባወጣው የአጻጻፍ ሥርዓት ላይ "ለአንድ ድምፅ አንድ ምልክት" በሚል መርሕ 'ሐ'፣ 'ኀ'፣ 'ሠ'፣ 'ዐ' እና 'ጸ' እንዲወገዱ 'ሀ' እና 'አ' እንደ 'ኸ' እና 'ኧ' እንዲተኩ ቢወሰንም የተጠቀመበት ባለመኖሩ መክሸፉን ይነግሩናል። ስለዚህ ሆሄያቱ እንዲጻፉ በማለት እነዚህን ሞክሼ ቃላት የያዘ፣ ጠንቅቆ መጻፍን የሚያግዝ ነው - መጽሐፋቸው።

በዚህ እና በነዚህ ጠንቅቆ የመጻፍ ጉዳዮች ዙሪያ በግሌ በተደጋጋሚ በማሰብ እና በመሞከር በርካታ መሠረታዊ ቃላትን ከነሆሄያቱ እንዲለምዱብኝ በማድረጌ ባልተለመደው ሀሄ ተጽፈው ሳይ ቅሬታ ይሰማኝ ጀምሯል። ችግሩ ይህ ልምድ አጻጻፋቸውን በትክክለኛው በለመድኳቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በተሳሳተ ልምድ የምጽፋቸው ቃላት ላይም እውነት ነው። ሌላው ችግር፣ በሞክሼ ሆሄያት ሊጻፉ የሚችሉ እጅግ በርካታ ቃላት አሉ። አንዳንዶቹን እጃችን በመራን ሆሄ መጻፍ ከመልመዳችን የተነሳ በየትኛውም ሆሄ ተጽፈው ብናይ ምቾትም ቅሬታም አይሰማንም። እንደ እንግሊዝኛው "የጠንቅቆ አጻጻፍ ማረሚያ (spelling correction)" ያስፈልገዋል ሆኖ እናገኘዋለን።

## ሶፍትዌር እንደ መፍትሔ

የማይክሮሶፍት ኦፊስ ወርድ የተለመደ የእንግሊዝኛ ቃለት spelling ስህተት ሲሠራ በራሱ እንዲያርም ተደርጎ ተሠርቷል። ተመሳሳይ ነገር በአማርኛው ቋንቋ ላይ ለመተግበር ቢታሰብም በተለይ በቋንቋው ላይ ጠንቅቆ የመጻፍ ጉዳይ ትክለኛውን የሞክሼ ሆሄ የመምረጥ ችግር ከእንግሊዝኛው የspelling ችግር የቀለለ ሆኖ እናገኘዋለን። ስለዚህ በዚህ በሶፍትዌር ሥራ ላይ የተሠማሩ ሰዎች "ጠንቅቆ አጻጻፍ" አጋዥ የሆነ ሶፍትዌር ቢያዘጋጁ እና... ለምሳሌ 'መጽሀፍ፣መጽሃፍ፣...' ብለን ስንጽፍ በትክክለኛው ሆሄ 'መጽሐፍ' ብሎ ቢያርመን ትልቅ እፎይታ ነው።

# የፍርሐት ዘመን

በሕይወታችን የምናደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ከመከወን እንድንቆጠብ ለራሳችን ስንነግር ወይም ውስጣችን ሲሰማው የፍርሐት ስሜት ተሰማን ልንል እንችላለን። የፍርሐትን ምንጭ በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ የመጀመሪያው ፍርሐታችንን የምናምንበት፣ ምክንያቱም ከራሳችን የመነጨ ድክመት በሚሆንበት ጊዜ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ድርጊቱን በመፈፀማችን ሊደርስብን ይችላል ብለን የምናስላው አግባብ ያልሆነ ጉዳት/በደል በማሰብ ድርጊቱን ከመፈፀም ስንቆጠብ ነው፡፡

ከላይ እንዳልኩት የለት ተለት እንቅስቃሴዎቻችን ውስጥ ምንጫቸው ከሁለት አንዱ ወይም ከሁለቱም የሆነ ፍርሐት ሊያሳድሩብን የሚችሉ ጉዳዮች ብዙ ናቸው፡፡ ይህ ጽሑፍ የሚያጠነጥነው በአሁን ሰዓት በሀገራችን የሚታየውን የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ሐሳብን የመሰንዘር፣ የመወያየት፣ የመሳተፍ እና የመተቸት ፍርሐትን ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በተጠቀሰው የፍርሐት ምንጭ የሚከሰተውን ነው፡፡

## ተማሪዎች

ተማሪዎች ስለ ዕድሜያቸው ለአቅመ ማገናዘብ ከደረሱት ጀምሮ ማለቴ ነው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት ዕድሉ ያላቸው ወይም ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና የሚገቡ ወይም በግል ኮሌጅ ገብተው የሚቀጥሉና ውጤታቸው ትምህርታቸውን የማያስቀጥላቸው ሲሆኑ ሁሉንም የሚያመሳስላቸው አንድ ነገር አለ፡፡ ትምህርታቸውን የቀጠሉትም ያልቀጠሉትም በደረጃቸው ሥራ የመያዝ እና ራሳቸውን ለማኖር የመጣር ግዴታ አለባቸው፡፡ ሥራ ለማግኘት ደግሞ ያልተጻፈው ሕጋችን በኢሕአዴግ መጠመቅን ይጠይቃል፡፡ ሥራ አጥ ሆኖ ኢሕአዴግን መቃወም ወይም ስህተቶቹን እየነቀሱ መተቸት የማይታሰብ ነው፡፡ ይህን ጠንቅቀው ስለሚያቁ ተማሪዎች ቀደም ብለው አባል ወይም በደጋፊነት መዝገብ መስፈርትን እና የሚፈለገውን ሟሟላት ሌላው ተግባራቸው ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ዋናው ነገር እንጀራ ነው፡፡ ምናልባትም ከተደላደሉና የትም ተቀጥረው የመሥራት ዕድላቸው የሰፋ ሲሆን ወደራሳቸው ሊመለሱ የሚችሉ ቢሆንም በጣም ኢሕአዴግ በሆኑ ቁጥር ጥቅማ ጥቅሞቹም በዛው ልክ ስለሚጨምሩ እዛው ሰምጠው የሚቀሩ ይበዛሉ፡፡ ለዚህም ነው በብዙ መጽሐፍት ያነበብነውን የሀገራቸውን ፖለቲካ የሚተነትኑ እና የራሳቸው የሆነ አቋም ያላቸው ተማሪዎች ማየት ሕልም የሆነብን፡፡

## ሠራተኞች

ደረጃው ይለያይ እንጂ የመንግሥት የሆኑም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆነ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በግልፅ ሐሳባቸውን ለመሰንዘር አይደፍሩም፡፡ በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ውስጥ የኢሕአዴግ አባል ወይም ደጋፊ የሆኑ ሰራተኞች የሚያገኙትን እድገትና የተለያዩ ዕድሎች በማየት ሌሎች ገለልተኛ ሆነው የነበሩ ሠራተኞች አባል እንዲሆኑ ይገደዳሉ፡፡ ሁሉም ሰው የሚሠራው ለለውጥ እና ለዕድገት መሆኑ የማይካድ ሐቅ ነው፡፡ ለዚህም ለውጥ እና ዕድገት የሚያስገኘውን መንገድ አልቀበልም ብለው በራሳቸው ሐሳብ የፀኑ ብዙዎች በነሱ መያዝ ያለበት የኃላፊነት ቦታ ለቦታው በማይመጥን ሰው እንደሚያዝ በተደጋጋሚ የምንሰማው ስሞታ ነው፡፡

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከተመሰረቱበት ዋና ዓላማ ጎን ለጎን መንግሥቱን የሚመራው ፓርቲን ዓላማ የማስፈፀም ኃላፊነትም ያለባቸው ይመስላል፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የኢሕአዴግ ፓርቲ ጽ/ቤት የሚመስሉበት አጋጣሚ አለ፡፡ በፓርቲው ያለው መዋቅር እና አሠራር አባል በሆኑ (ያው አብዛኞቹ አባል ናቸው) ሠራተኞች በመሥሪያ ቤቱም ተፈፃሚ ነው፡፡ የ1 ለ 5 የውይይት አደረጃጀትን ጨምሮ ሌሎች ፓርቲውን የሚመለከቱ ስብሰባዎች በሥራ ሰዓት ቢካሄዱም ችግር የለውም፡፡

መንግሥታዊ ያልሆኑ መሥሪያ ቤት የሚሠሩ ሠራተኞችም አባል መሆን ላይጠበቅባቸው ይችል ይሆና እንጂ መንግሥትን መቃወም እና መተቸታቸው በአሠሪዎቻቸው አይወደድላቸውም፡፡ ምክንያቱም አሠሪዎች ከመንግሥት ጋር መነካካት አይፈልጉም፡፡

## አሠሪዎች

ከላይ አሠሪዎች ከመንግሥት ጋር መነካካት አይፈልጉም ብያለሁ፡፡ አባል ወይም ደጋፊ መሆን ሥራዎችን እንደሚያፋጥን እና ከመንግሥት ጋር በሚያገናኛቸው ጉዳይ ሁሉ እንግልት እንደማይኖርባቸው ስለሚያውቁ ብዙ አሠሪዎች አባል ወይም ደጋፊ ይሆናሉ፡፡ ወይም ከዳር ሆነው የሚመለከቱ ይሆናሉ፤ ግን አይቃወሙም ወይም አይተቹም፡፡ ስለሆነም ሠራተኞቻቸው አባል ቢሆኑላቸው እሰየው ነው፤ ተቃዋሚ ወይም የሚተቹ ባይሆኑ ግን ምርጫቸው ነው፡፡ ባጠቃላይ ከመንግሥት ጋር እሰጣ ገባ ውስጥ መግባት ስለማይፈልጉ መንግሥት የሚያስደስተውን ነገር ቢያደርጉ ይመርጣሉ፡፡

## ባለሀብቶች

በድህነት ወይም በአቅም ማነስ ምክንያት ብቻ መንግሥትን ለመደገፍ የምንገደድ ቢመስለንም በሚገርም ሁኔታ ይህን ፍርሐት ገቢያቸው ከፍተኛ የሆኑ ባለሀብቶችም ይጋሩታል፡፡ ዓላማቸው ባላቸው ሀብት ላይ ሌላ ሀብት መጨመር ስለሆነ ምንም ቢሆን ከመንግሥት ጋር ተስማምቶ መስራት ይፈልጋሉ፡፡ ከመንግሥት ትዕዛዝ ባይቀበሉም (የተቀበሉም ሊኖሩ ይችላሉ)፤ ለተቃዋሚ ድርጅች እና ፓርቲዎች ንብረታቸውን ባለማከራየት፣ መንግሥትን የሚተቹ ማንኛቸውም ዓይነት ሥራዎችን ስፖንሰር ለማድረግ ፈቃደኛ ባለመሆን፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ባለመርዳት እና በመሳሰሉት ድርጊታቸው ፍርሐታቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንግዲህ ማን ቀረ? ዋና ዋናዎቹን ጠቀስኩ እንጂ ይህ ዓይነቱ ፍርሐት ያልገባበት ቦታ የለም፡፡ አብዛኛው ዜጋ በሀገራችን የፖለቲካ ጉዳይ መወያየት፣ መሳተፍ እና መተቸትን እርግፍ አድርጎ ትቶታል፡፡ ሐሳቡን በአደባባይ ቢናገርም ቢወያይም መንግሥትን የማያስከፋውን እየመረጠ ነው፡፡ የመንግሥት መ/ቤት ደጅ ሳንረግጥ መኖር አለመቻላችን ባልከፋ ነገር ግን ጉዳያችን በአግባቡ እንዲፈፀም ደግሞ የመንግሥት ወዳጅ መሆን እንደመስፈርት መጠየቁ፤ ካልሆንን የሚደርስብን እንግልት እና በደል ተደማምረው የፍርሐታችን ልክ መድረሻ በማሳጣት የመንግሥት አጎብዳጅ እንድንሆን አድርጎናል፡፡ ሲጠሩን አቤት ሲልኩን ወዴት ሆኗል ነገሩ፡፡ የመንግሥትን ስህተት በግልፅ የሚናገር፣ የሚወያይ፣ የሚተች፣ የሚቃወም፣ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል የሆነና በነዚህ ሰዎች ዙሪያ ያለ ሰው ደግሞ መንግሥት ወዳጅ አይደለም፡፡ ወዳጅ ካልሆነ ደግሞ መንገዱ ቀና አይሆንም፡፡ ይህ እንግዲህ በሕገመንግሥቱም ሆነ በማናቸውም የኢሕአዴግ ሕጎች ያልተጻፈ ነገር ግን ዜጎችን አግባብ ወዳልሆነ የፍርሐት ቀጠና እየወሰደ ያለ አስተሳሰብ ነው፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲዎችም የአባላት ቁጥር ያለመጨመር እና እንቅስሴዎች መቀዛቀዝ ምክንያት አንዱ ይሄ ነው፡፡ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ሲያካሂዱ የሚገኘው ሰው በጣም ጥቂት ነው፡፡ አብዛኛዎቹን ኢሕአዴግ በሰበብ አስባቡ አባል ያደረጋቸው ሲሆን፤ የቀሩት ደግሞ ስብሰባው ላይ ቢገኙ የሚደርስባቸውን ነገር በማሰብ እና በመፍራት ብቻ አይገኙም፡፡

ይህን ስጋት እና ፍርሐት አስወግደው በራሳቸው ሐሳብ ብቻ በመመራት መንግሥትን እየተቃወሙ እና እየተቹ የሚደርስባቸውን ጫና ተቋቁመው እስካሁን ያሉ ጥቂቶች ቢኖሩም ብዙዎቹ እስር ቤት እና በስደት ናቸው፡፡ የተለያዩ ማኅበራዊ አውታሮች ላይ የምናያቸውን መንግሥትን በግልፅ የሚተቹ ጽሑፎች እና አስተያየቶችን አይተን ጸሐፊው ወይም አስተያየት ሰጪው ከኢትዮጵያ ውጪ እንደሆነ መታሰቡም ሀገር ውስጥ ያለውን ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ ፍርሐት በግልጽ ያሳያል፡፡ አንዳንዴም ከሀገር መውጣት እንደፈለገ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል፡፡ ከአሠሪ ወይም ከመንግሥት ሰው ከሚደርስ ማስጠንቀቂያ ወይም ማስፈራሪያ በተጨማሪ የጸሐፊው ቤተሰብ፣ ጓደኛ ወይም የቅርብ ሰው ነኝ ባይ ምክር፣ ማስፈራሪያ እና ተግሳፅ ሊያስተናግድ ግድ ይለዋል፡፡ ከኛ ሐሳብ ጋር የሚመሳሰል ሐሳብ ያለው ሰው አጋጥሞን እንኳን በግልጽ ሊያወራን ቢሞክር ‹ተልኮብኝ ይሆን› በሚል ጥርጣሬ እንጂ በሙሉ ልባችን ለማውራት ፍርሐት አለብን፡፡ በፌስቡክና ሌሎች ማኅበራዊ አውታሮች ራሳችንን ገልጸን የተሰማንን እና የምናቀውን ሐቅ ለማውራት እንፈራለን፡፡ ሌላም ሌላም ብዙ ፍርሐቶች አሉብን፡፡

ምክንያቱም እንፈራለን፡፡

ግራ የሚያጋባ የወቅቱ ሐቅ! ማብቂያውን እናፍቃለሁ፡፡

# ወጣት ሴት የመሆን ጣጣ

እኛ ሴቶች በተወሰነ ጊዜ በቋሚነት የምንገናኝ ሴት ጓደኞች አይጠፉንም፡፡ የከተማዋ ካፌዎች ውስጥ የሚሆነው ይህ ቆይታችን በተለይ ወደ ሥራው ዓለም ከገባን ወዲህ ስለወንዶቻችን (በተለመደው አጠራር ባሎቻችን) እና በዚያው ዙሪያ ስላሉ ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ሲሽከረከር ይቆያል፡፡ ፓለቲካ ያልተቀላቀለበት፣ ጠንካራ ማኅበራዊ ችግሮች የማይወሩበት እና ቀላል ጨዋታ የሚመስለው ይህ ቆይታ ከባድ የማይመስሉ ነገር ግን የወጣት ሴቶችን ሕይወት እና አኗኗር የሚያመሳቅሉ ጉዳዮችም ይነሱበታል፡፡ የሚለያዩ የማይመስሉ ጥንዶች ሕይወት "ውይ we break up እኮ" በሚል ቀላል የትካዜ ቃል የሚጠናቀቅበት፣ "surprise…………… guys am engaged………." የሚል ጩኸት የሚደመጥበት፣ አልፎ አልፎም አስቸኳይ ስብሰባ ተጠርቶ "I think am pragenat ምን ይሻለኛል" ተብሎ የሚተከዝባቸው ናቸው፡፡ ወደ "በሰለ ወጣትነት" ከገባንበት ጊዜ አንስቶ የወጣት ሴቶች ችግሮች በውበታቸው እየተሸፈኑ ወይም እየተለመዱ ሳይሆን አይቀርም መነጋገሪያ ሲሆኑ ሰምተንም ተወያይተንባቸውም አናውቅም፡፡ በዛ ቢባል የቁሳቁስ ፍቅርና የቸልተኝነት ነገር እያነሳን ሴቶቻችንን ማማረር ነው፡፡

ወጣት ሴት መሆን ጣጣ ነው፡፡ አመቱ ከመፍጠኑ አንስቶ የሚጠበቅብን አበዛዙ አብዛኛውን ዓመታት ባልሰከነ ውዥንብር ውስጥ እንድንከርም ያደርገናል፡፡ በዚህ ላይ የማኅበረሰቡ ግልጽነት ያጣ ጫና እና ማስፈራሪያ ለአንዲት ወጣት ሴት የመረጃ ምንጯ ጓደኞቸዋ ብቻ፣ ትክክል የሚሆነውም ብዙዎቹ ጓደኞቸዋ ያደረጉት ነገር ይሆናል፡፡ በትምህርት ቤት እና ከቤተሰብ ጥብቅ ቁጥጥር በአንጻራዊነት ነጻ በሚኮንባቸው በነዚህ ዓመታት የቦይ ፍሬንድ ምርጫ እና ውዝግቡ፣ የማግባት አለማግባት እና የዕድሜ ነገር ሐሳቡ ሁሉ ቀላል ቢመስሉም መስመር ካለው (focused) የሐሳብ መስመር በተደጋጋሚ ሲያናጥቡ እና ለብዙ የሚጠበቅ አቅም ያላቸውን ሴቶች ከተለመደው መንገድ ሲያስቀሩ ይስተዋላል፡፡

**የመምሰል ጣጣ**

ወጣት ሴት ሆኖ ወጣት ሴቶችን አለመምሰል ችግር ነው፡፡ ሁላችንም ከአለባበስ ጀምሮ እስከ አስተሳሰብ ድረስ እንድንመሳሰል ይጠበቅብናል፡፡ ወንዶች እንዲጋብዙን ዝግጁ ሆኖ መገኘት፣ የተመጠኑ የሴት ልጅ ዕውቀቶች ላይ ብቻ ማተኮር እና መመሳሰላችንን የሚያፈጥኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ እንድናተኩር መደረጋችን ግድ ነው፡፡ የሴት ጓደኛው በአለባበስ፣ በአወራር፣ በመግባባት ዘዬ ዘመናዊ ሴቶቸን እንድትመስል የማይፈልግ እና የማይገፋፋት ወንድ የለም፡፡ በመሠረቱ በዚህ ዕድሜ ብዙ ሚና የሚኖራቸው የወንድ ጓደኞች ራሳቸው ልዩነትን በፍጹም አይቋቋሙም፡፡ ከለመዱት የሴቶች ዓይነት ወጣ ያለች ሴት ስትገኝ የግንኙነት መስመሩ ብዙም ሳይቆይ የሚቋረጥበት ጊዜ የሚበዛውም ለዚያ ነው፡፡ "አረ ሴት ልጅ ምሰይ? የምን ጎረምሳ መምሰል ነው?" የሚሉ ወላጆችም ቀላል አይደሉም፡፡ የጓደኛ እና የጎረቤት ልጆች እንደምሳሌ እየተጠሩ የመመሳሰልን አስፈላጊነት ከወላጆቻችን ጀምሮ እስከ ወንድ ጓደኞቻችን ድረስ እንመከራለን፡፡ በዚህም ምክንያት መሆን የምንፈልገውን እና የምናስበውን ሳይሆን ወንዶቻችን እንደነሆን የሚፈልጉትን ነው እየሆንን ያለነው፡፡ ለምሳሌ ብንጠቅስ፡- ወንዶች ወፍራም የሆነች ሴት ስለማትመቻቸው ወይም ምርጫቸው አይደለችም ብለን ስለምናስብ እኛ ሴቶች ክብደት ለመቀነስ፣ ለመክሳት እና ቦርጭ ለማጥፋት ከረሃብ አድማ ያልተናነሰ የአመጋገብ ዘየ ስንከተል ይስተዋላል፡፡ ከልክ በላይ መወፈር አግባብ ነው እያልን ሳይሆን ‹ወንዶች ስለማይመቻቸው› ግን መሆን አልነበረበትም፡፡

## የዕድሜ ጣጣ እና ፍርሐቱ

ታዲያ በዚህ ጊዜ ወጣት ሴት የመሆን ጣጣው አንዱ የትኛው ነው ትክክለኛው ወንድ የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ግንኙነት መጨነቅ፣ የትኛው ይሆነኛል ብሎ ማሰብ እንዲሁም ገፋ ሲል ይሄኛው የመጨረሻው ይሁን ብሎ መመኘት ያጋጥማል፡፡ በዚህ የፍቅር ግንኙነት መልኩን ቀይሮ ቅልጥ ያለ ስሌት ወደመሆን በተጠጋበት ዘመን የመጨረሻውን ሰው ፍለጋ ሐሳቡ ቀላል አይደለም፡፡ የማኅበረሰብ አወቃቀራችን ከተወዳዳሪነት ይልቅ ዕድሜ ላይ ያተኮረ ከመሆን አለመላቀቁ እና ከወላጆቻችንም አልፎ እኛ ላይ መጋባቱ ደግሞ ሐሳቡን የከፋ ያደርገዋል፡፡ ሴት ልጅ አይደለሽ በዕድሜሽ አትቀልጂ፣ በሴት እድሜ እንዲህ ይቀለዳል እንዴ የሚሉ አባባሎች ከእናቶቻችን ጀምሮ እስከ ጓደኞቻችን ድረስ ይዘወተራሉ፡፡ ምንም እንኳን የሴት ልጅ ዕድሜ በተፈጥሮው የሚያስቀምጣቸው ገደቦች ቢኖሩም ከልክ ላለፈ ፍርሐት ተዳርገው ብዙ ሲጠበቅባቸው በፍጥነት የዕድሜ ውድድር ውስጥ ገብተው ሰጥመው የቀሩ ሴቶች ቀላል አይደሉም፡፡ በዚህ ላይ ማኅበረሰባዊ ግዴታ ሲጨመርበት ከዕድሜ ጋር ያለው ሩጫ ቶሎ ተጀምሮ ቶሎ ይጠናቀቅና ለረዥም ጊዜ የሚቆየው ውጤቱ ብቻ ይሆናል፡፡ ይህንን

ማኅበረሰባዊ ግጼታ ያልተወጡ ወይም የተለየ አቅጣጫ የያዙ የሚመስሉ (ቢያንስ ለጊዜው ያልተሳካላቸውም ቢሆኑ) ወጣት ሴቶች የግል ፍርሐታቸውን ማኅበረሰቡን እና አቻ ግፊትን የመቋቋም ጣጣ ይጠብቃቸዋል፡፡

## የግል እሴት እና ማኅበረሰባዊ ጥበቃን (social expectation) የማስታረቅ ጣጣ

ብዙ የከተማ ወጣት ሴቶች በልጅነት ጊዜ የነበሩን የመረጃ ዕድሎች ሰፊ እንደመሆናቸው መጠን በተቻለ መጠን የተለያዩ መረጃዎቻችን ላይ ተመስርተን ሕልሞቻችን እናስቀምጣለን፡፡ ከዚያም ከፍ ሲል ጠንካራ እሴቶችን ልናዳብር እንችላለን፡፡ እነዚህ እሴቶች መሪ ለመሆን ማለም፣ የተለያዩ የአመራር ቦታዎች ላይ ለመገኘት ማሰብ፣ የትምህርት እና የሌሎች ደረጃ ከፍተኛ ደረጃ መድረስ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ጠንካራ እሴቶች በመካከለኛ የወጣትነት ዘመን ላይ ሲደረስ በከፍተኛ ተግዳሮቶች እና በተለመዱ ትዳርን የመጨረሻ የሴት ልጅ ስኬት አድርጎ በሚያይ ማኅበረሰባዊ እሴቶች ውስጥ ይዋጣሉ፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ በሀገራችን ሴት ልጅ በተማረች እና በበቃች ቁጥር ስኬታማ የቤተሰብ እና የትዳር ሕይወት የመመስረት እድሏ ይቀንሳል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የትዳር አጋርዋን የምትፍካከርበት ገቢ ማምጣት ከቻለች እና ቤተሰብዋን እስከደገፈች ድረስ በተለያዩ መስኮች የምታርገው እንቅስቃሴ ላይ ጎልታ መታየት ከትዳር በፊት ከሆነ ለሰከነ ኑሮ የማትሆን እና ለቤት አመራር የማትሆን ከትዳር በኋላ ከሆነ ደሞ ቤተሰባዊ ኑሮዋ ላይ ጠንካራ ትርጉም ያለው ሥራ ያለው እንቅስቃሴ የማታደርግ ተደርጋ ትወሰዳለች፡፡ ይህ የግል እሴት የመኖር ሙከራን ከሌሎች ማኅበራዊ ኃላፊነቶች ጋር አጣምሮ የማየት ማኅበረሰባዊ አባዜ ለብዙ ታላላቅ ቁም ነገሮች ሕልም የነበራቸው ሴቶችን <u>የትዳር ስኬታማ</u> ብቻ አድርጎ አስቀርቶዋቸዋል፡፡ ይህንን ለማስታረቅ በሚደረግ ትግል የሚያልፊው ጊዜ ደግሞ ሌሎች ፍርሐቶች እየወለደ መጨረሻ ላይ ከምንም ሳልሆን ቀረሁ የሚል ቁጭት ውስጥ ወድቀው የሚቀሩ ሴቶች ቀላል አይደለም፡፡

## የወንዶቻችን ነገርስ ቢሆን?

ወንዶቻችን በቃል ሲነገር ጠንካራ ሴት፣ ራዕይ ያላት በጠንካራ ገቢ የተደገፈች ምኞታቸው እንደሆነች ቢወራም በተግባር ግን ወደ ጠንካራ ጉዳዮች የምትሳብ ሴትን ለመቅረብ የመድፈር ሙከራቸው በጣም አናሳ መሆኑን የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊያን ሴቶችን ጨምሮ የብዙ ተመሳሳይ ሴቶች ይመሰክራሉ፡፡ ራስዋን በሚገባ መግለጽ የምትችልን ሴትን በተግባር የሚፈሩ ምናልባትም ከቀረቧት በኋላ ደግሞ ተመሳሳይ እንድትሆን ተጽእኖ የሚያሳድሩ ወንዶች በአብላጫው ይገኛሉ ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በተለይ የሐሳብ ልዩነት የምታበዛ ምክንያት የምትደረድር የምትጠይቅ ከተለመዱ ጉዳዮች ወጣ ባሉ ሐሳቦች የምታስብ ከሆነ ደግሞ የወንወዶቻችን የንግግር ፉከራ ከንግግር የማያልፍ እንደሆነ ለማስመስከር ቀላል ይሆናል፡፡ (የፍልስፍና እና የፖለቲካ መጽሐፍትን የምታነብ፣ ስለሜክ አፕ የማታወራ ሴት ሲያዩ የሚፈረጥጡም አይጠፉም) ታዲያ አንዳንድ ወንዶቻችንን የሴቶችን አበሳ ከሚያበዙ ጉዳዮች ጎራ ቢመደቡ መጨከን ይሆናል?

## የተፈጥሮና የባሕል ተፅዕኖ

ተፈጥሮና ባሕል ለሴትም ለወንድም የተለያየ ኃላፊነቶችን ሰጥቷል፡፡ በዚህም መሰረት ሴት ልጅ በተፈጥሮ ልጅ በሆዷ ተሸክማ መውለድ እና የማጥባት ስራ የሷ ብቻ ነው፡፡ ይህን ምንም ልናደርገው የማንችለው የተፈጥሮ ኃላፊነት ነው፡፡ ባሕላችን ደግሞ ሴት ልጅ ከጋብቻ በፊት የወሲብ ግንኙነት መጀመር እንደሌለባት ይሰብካል፡፡ ከነድንግልናዋ ብታገባ ተመራጭነት አለው፡፡ ድንግልና በአብዛኛው ሴት ልጅ ከዚያ ቀደም ከወንድ ጋር ግንኙነት አለመፈፀሟን ማረጋገጫ ተደርጎም ይወሰዳል፡፡ ለወንድ ግን ተመሳሳይ ማረጋገጫ ማግኘትን ተፈጥሮ አትፈቅድም ወይም አልሰማንም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ፈገግ የሚያሰኙ ገለጻዎችንም እናስታውሳለን፡፡ ‹ድንግልናዋን አስወሰደች/ወሰደ›፣ ‹ድንግልናዋን አስረከበች/ተረከበ› እና የመሳሰሉ ገለጻዎች ሴቷን እንደሰጪ ወንዱን እንደተቀባይ ስለሆነም የተቀበለው አካል ብቻ እንደሚጠቀም ሰጪ ደግሞ ተጎጂ ተደርጎ የመቁጠር ባሕል በተለምዶው ይታያል፡፡ ይህ ባሕል ከድንግልናው በኋላ በሚኖሩ ግንኙነቶች በቆመ ጥሩ ነበር፡፡ እኛ ሴቶች ከወንዶች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ወቅት የወሲብ ግንኙነት ማድረጋችን ወንዶች እንደተጠቀሙብን የሚታሰብበት በተለይም ግንኙነቱ በሚቆምበት ወቅት ሴቷ እንደተበደለች የመቁጠር አስተሳሰብ ሌላው አስቸጋሪ ማኅበረሰባዊ ጣጣችን ነው፡፡ ይህ ግን ፍፁም ስህተት እና መቅረት ያለበት አስተሳሰብ እንደሆነ ከጋብቻ በፊት ወይም ያለጋብቻ የሚመጣ ልጅ መኖር እንደሌለበትም በማኅበረሰባችን የተደነገገ ሕግ ነው፡፡ ከዚህ ሕግ ውጪ የሆነች ሴት ደግሞ ከማኅበረሰቡ የሚጣልባትን ቅጣት ትቀበላለች፡፡ ይህን ቅጣት ሽሽትም ብዙ መሆን የማይገባቸው ነገሮች ይሆናሉ፡፡ ከዛ ውስጥ አንደኛውና ዋነኛው ያለዕቅድ የተረገዘን ፅንስን ለማስወረድ የሚደረግ ጥረት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ

እርግዝና በመከሰቱ ምክንያት ብቻ ያለፅቅድና አብራ ለመኖር ከማትፈልገው ጋር ወደ ትዳር ሕይወት መግባት ነው። ይህ ቀላል ሊባል የማይችል እና በማኅበረሰብ ለሴት ልጆች ብቻ እንዲጋፈጡት የተሰጠ ጣጣ ነው።
ሴት ልጅ የወሲብ ፍላጎት እና ተነሳሽነት እንደሌላት ተደርጎ የሚቆጠረውም የዚሁ ተፅዕኖ ውጤት ነው። ሴት ልጅ ወሲብን ስትፈጽም የተሰጣትን ተያያዥ ማኅበረሰባዊ ኃላፊነቶች አብራ ስለምታስታውስ የማርገዝ ያለማርገዝ የማኅበረሰቡ ውስጥ የወሲብ ባሕሏን ተከትሎ የሚመጡ ኃላፊነቶችን ማሰብ ከወንዱ እኩል ወሲብን እንዳታጣጥም እና እንዳትናፍቅ (ከወንዱ እኩል ነው ያልነው) መንስኤ ሆኗል።

## ስርአተ ጾታዊው ውዝግብ... በሌለ ነገር? (In the middle of nowhere?)

በዚህ ጊዜ ወጣት (ከተሜ) ሴት መሆን ከእናቶቻችን እና ከተለመደው በተለየ የማኅረሰባዊ ልምድ በተለይ ለተለያዩ የአኗኗር ስልቶች እና መረጃዎች ቅርብ እንድንሆን አድርጎናል። ነገር ግን ከተለመደው የማኅበረሰባዊ የሴት ልጅ ኃላፊነቶችን መቀበል እና የማንቀበላቸው ላይ በተግባር የመቃወም አጣብቂኝ የዚሁ ዕድሜ ጣጣ ነው። በዚህ ዘመን ዘመናዊነትን እና ባሕላዊ ኃላፊነትን አጣምረው የሚይዙ ሴቶችን ማግኘት የወደፊቱ ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ተግዳሮት ነው። በዚህ አጣብቂኝ ውስጥ የምንገኝ ወጣት ሴቶች እንደፊልም እኩዮቻችን በተግባር ዘመናዊ መሆንን በመፈለግ እና የሚጠበቅብንን ጠንካራ ማኅበረሰባዊ ኃላፊነት አለመረዳት ውስጥ ወድቀን እንገኛለን። ካፌዎች ውስጥ ሲዝናኑ መዋል እና የቤት ጓዳን በአግባቡ ማስተዳደር አብረው ማስኬድ የቸገራቸው ብዙ እህቶችን ማየት በተዛባ መልኩ ለዓመታት ሲሰጥ የነበረውን የስርአተ ጾታ ጽንሰ ሐሳብ በተግባር ለማየት ሁነኛ ማሳያ ሊሆን ይችላል። ታዲያ በዚህ የተዛባ እና በንባብ ባልተደገፈ የስርአተ ጾታ ዕውቀት ያለፉ ወጣት ሴቶች የሴቶችን ማኅበረሰባዊ ሚና ባለመረዳት ባሕላዊውንም ቤተሰባዊ ኃላፊነትም ሆነ ዘመናዊውን ከቤት ውጪ ያሉ ጠንካራ የሥራ እና የኢኮኖሚያዊ የበላይነት ሳይዙ መሐል ሜዳ ላይ የመቅረት ዕጣ ፈንታ ያጋጥማቸዋል።

እነዚህ የተለያዩ ጣጣዎች መሐል የሚያልፉ ወጣት ሴቶች ግን በቁሳዊ እና ብልጭልጭ ፍላጎቶቻቸው ሲታሙ ሲተቹ እንጂ እየተባባሰ የመጣውን የውስጣቸውን ውዝግብ ያስተናገዱ ችግሮችን በሚዳስሱ ውይይቶች ሲካተቱ ሰምተን አናውቅም። ብዙ ጊዜ ስለኛ ስለሴቶች የሚናገሩት ወይም የሚጽፉት ወንዶች በመሆናቸው የዘረዘርናቸው የኛ ብቻ ጣጣዎች ትኩረት ተሰጥቶአቸው ስለጉዳዩ ግንዛቤው እንዳይኖር አድርጓልም።

እስቲ ምንያህሎቻችን ነን ቡቲክ በር ላይ፣ ካፍቴሪያዎች ውስጥ እና ባጠቃላይ በዙሪያችን የምናያቸውን እና የምናቃቸውን ወጣት ዘመናዊ ቆነጃጅት በዚህ መልኩ ለመረዳት ሞክረን የምናውቀው?

# ወጣት ወንድ የመሆን ጣጣ

በወጣትነት ወንድ ዕድሜ ክልል ከሆንክ አሁን የምናወራው ነገር ቢያንስ አንድ ቀን እንደገጠመህ አንጠራጠርም፡፡ መንገድ ላይ እየሄድክ ነው እንበል፣ ሰፈሩን አታውቀውም፡፡ ወደየሆነ ቦታ አቅጣጫ የሚያመለክትህ ሰው እየፈለግክ ነው፤ አንዲት በአንተ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለች ሴት ከወዲያ ማዶ ስትመጣ አይተህ በመደሰት ‹‹ይቅርታ የኔ እህት፤›› ትላታለህ - አቅጣጫ ለመጠየቅ፡፡ ሴቲቱ ገልመጥ ብላ ታይህና (ወይም ቀድማ ካየችህ) እንዳልሰማ ሰው ፊት ነስታህ ታልፍሃለች፡፡ አቅጣጫውም አልተገኘ፣ ክብርህም አልተጠበቀ ይሉሀል ይህን ጊዜ ነው - በለካፊ ወንድነት የመፈረጅ ጣጣ፣ ወጣት ወንድ የመሆን ጣጣ! ነገር ግን ይሄ ‹‹እዳው ገብስ›› የሆነ ጣጣ ነው፡፡

የዞን ዘጠኝ ብቸኛ የሴት ጦማርያን የሆኑት ማሕሌት እና ሶልያና ባለፈው ሳምንት ማገባደጃ ላይ ያስነበቡን ‹‹ወጣት ሴት የመሆን ጣጣ›› ለዚህ ጽሑፍ መወለድ መንስኤ ሆኗል፡፡ እነርሱ የወጣት ሴትነትን ጣጣ በዘረዘሩ ቁጥር ወንድ ሆኖ እያነበበ ያለ ወንድ የመሆን ጣጣን ማሰብ የሚቸግረው ይኖራል ብሎ ማለት ዘበት ነው፡፡ ነገርዬው ‹‹የሴቶች ጉዳይ›› ብቻ የሚጮህበት ዘመን መሆኑ፣ ወንዶች ወንድ በመሆናቸው ብቻ የሚጋረጡባቸውን ፈተናዎች (ወይም በዚህ ጽሑፍ ቋንቋ ‹ጣጣዎች›) የሚያወራ መገናኛ ብዙኃን የለም፡፡ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የሴቶቹን ጣጣ ማጣጣል፣ ወይም ዕውቅና ማሳጣት ሳይሆን ወጣት ወንድ በተለይ እና ወንድ በጥቅሉ መሆንም በራሱ የራሱ ጣጣዎች እንዳሉት ማመላከት እና ለጣጣዎቹ ዘላቂ መፍትሄ ወደሚያመጡ የውይይት አጀንዳዎች የዞን ዘጠኝን ነዋሪዎች በዚህ መድረክ እና ከዚህም ውጪ እንዲያበረክቱ ማነሳሳት ነው፡፡

## በልጦ የመገኘት ጣጣ

በሀገራችንም ሆነ በዓለማችን በተገነቡ ባሕሎች እና እሴቶች መሠረት ወንድ ልጅ የአውራነት፣ ወይም በልጦ የመገኘት ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ለምሳሌ የፍቅር ወይም የትዳር አጋር ለማግኘት በትምህርት ደረጃ፣ በደመወዝ ሌላው ቀርቶ ተፈጥሮ በሚያስገድዳቸው ቁመት እና ዕድሜ ሳይቀር በልጦ መገኘት አለበት፡፡ ይህንን ባሕል አመጣሽ በልጦ የመገኘት ኃላፊነት በዘመነኝነት ለመስበር ቢሞከርም የተሳካ አይመስልም፡፡ ሴቲቱን ከፍሎ የሚያስተምር፣ ሸምቶ የሚያስውብ፣ አግብቶ ቤቱ የሚያመጣ እንጂ በተቃራኒው የሚንቀሳቀስ ወንድ የለም፤ ሴቶቹም (ብዙኃኑ) አይፈልጉትም፡፡

ወንድ ልጅ ለሴት ልጅ ከለላ እንዲሆን በወንዶቹም በሴቶቹም ይጠበቅበታል፡፡ ሚስቱን ከለካፊ ጎረምሳ ማስጣል (መጠበቅ)፣ መሠረታዊ ፍላጎቷን ማሟላት፣ በየካፌው መጋበዝ፣ የዕድሜ፣ የትምህርት እና የደሞዝ (አቻው የሆነችውን ሳይቀር) ሙሉ የኢኮኖሚ ጥብቅና ማድረግ ያልተጻፈ ግዴታው ነው፣ ወዘተ… ወዘተ… ከዚህም በላይ ደግሞ በዚህ ክፉ ዘመን ኑሮን ታግሎ አሸንፎ፣ ጎጆ መሥርቶ፣ የቤት ዕቃ ሞልቶ፣ ሠርጎ ማግባት አለበት፡፡ ይህንን ሁሉ ማድረግ ስለሚከብደው ቆሞ የቀረ አለሴ የመሆን ጣጣ ፊቱ ላይ ተደቅኖበታል፡፡

ይህንን ዓይነቱን ጣጣ የወጣት ወንዶች ጣጣ ብቻ ብለን የጠራነው ያለምክንያት አይደለም፡፡ በዚህ ዘመን እና ባሕል ውስጥ ሴቶች የቤተሰብ ራስ የመሆን ኃላፊነት የለባቸውም ማለት ይቻላል፡፡ እርግጥ ነው፣ ጎጆ ከወጡ በኋላ የቤቱን ምሰሶ መሸከሙ የሁለቱም ድርሻ የሚሆን ቢሆንም በተለይ የጎጆው መሠረት የሚጣልበት ንዋይ በወንዱ ጋጋሪነት እንዲሟላ መሆኑ ከባድ ጣጣ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሴቶች እንዲያውም ቤቱን ሞልቶ እና አደራጅቶ የተገኘው ወንድ ቤት ዘው የማለት የተሰናዳ ዕጣ ፈንታ ባለቤቶች ናቸው፡፡ ምስኪኑ ወጣት ወንድ ግን የ‹ገርልፍሬንዱ›ን ወቅታዊ ፍላጎት በሚሟላት እና ስለወደፊቱ በማቀድ መሐል ብኩን ‹ችስታ› የመሆን ዕጣ ሲገጥመው ‹ገርልፍሬንዱ› ይህ ሰው ለቁም ነገር አይሆንም በሚል ንቃው፣ ራሱን በሀብት ሲያደራጅ ያረጀ ወንድ ጠቅልሏት - ወጣቱ ከሁለት ያጣ ሆኖ የመቅረት ዕድሉ የዘወትር ድራማ ሆኗል፡፡

## የአደገኛ ቦዘኔነት ጣጣ

ወጣት ወንድ፣ በተለይም እኩዮቹን ለመምሰል ፀጉሩን ካፍተለተለ፣ ሱሪውን ዝቅ አርጎ ከታጠቀ - ምንም እንኳን አለባበስ ከማንነት ጋር ቀጥተኛ/የማይነጠል ግንኙነት ባይኖረውም በቃ አለቀ - አደገኛ ቦዘኔ ነው፡፡ በአደገኛ ቦዘኔነት የሚፈረጀው በመንግስት (ብቻ) ከመሰላችሁ ተሳስታችኋል፤ በሕዝቡ ነው፡፡ ታክሲ ውስጥ ለመግባት ከሌላው ሰው ጋር ሲጋፋ ገልመጥ፣ ገልመጥ እያለ ኪሱን የሚያሸሽበት፣ እጁን በጥርጣሬ የሚመለከትበት ብዙ ሰው ነው፡፡

ሥራ አጥነት የአገሪቱ ቁጥር አንድ ችግር መሆኑ ቢታወቅም፣ ከተሞች በቂ (ያውም ካለ) የወጣቶች መዝናኛ እንደሌላቸው ቢታወቅም፣ ወጣት ወንዶች መንገድ ዳር ሰብሰብ ብለው ቆመው ከእኩዮቻቸው ጋር ሲጨዋወቱ ሲታዩ፣ ሴት ሲለክፉ፣ ማጅራት ሲመቱ፣ ወይም ደግሞ ሌላ የውንብድና ተግባር ሲፈፅሙ ፈልገው እንጂ አገራዊ-ማኅበራዊ ቀውስ አባክኗቸው ነው ብሎ የሚያዝንላቸው የለም፡፡

በርካታ ወጣት ወንዶች ከሚታሙበት የሱስ አዘውታሪነት ችግር ጀርባ ይህ ‹በአደገኛ ቦዘኔነት› (ዱርዬነት) የመፈረጅ ጣጣ አለ፡፡ ብዙዎች መንገድ ዳር ላለመቆም የሚያገኙት አማራጭ ካፍቴርያ ወይም ጫት መቃሚያ ቤቶችን ነው፡፡ ለትንሽ አገልግሎት ብዙ ዋጋ የሚጠይቁት ካፍቴሪያዎች ወጣት ደንበኞቻቸው ‹ብዙ ሳይገለገሉ፣ ብዙ መቀመጣቸው›ን ስለማይፈልጉት እንዲወጡላቸው ብዙ ምልክቶችን ያሳያሉ፡፡ ይህ የግል ኩራታቸውን የሚፈታተናቸው ወጣት ወንዶች፣ ከዚህ ይልቅ ከግማሽ ቀን በላይ ቁጭ የሚባልበትን ጫት መቃሚያ እንደተሻለ ጊዜ ማሳለፊያነት በመቁጠር ላይ ናቸው፡፡

## በሴት ጠላትነት የመፈረጅ ጣጣ

አንዲት ሴት ልጅ ጾታዊ ጥቃት በደረሰባት ወይም ተመሳሳይ ነገር በተከሰተ ቁጥር ሴቶቹ ሁሉ፣ ወንዶችን ሁሉ በጥርጣሬ እና በመኮነን ዓይን ይመለከታሉ፡፡ ወንጀሎች የሚፈጸሙት ሰብኣዊነት በሚጎላቸው ሰዎች መሆኑ ቢታወቅም፣ ልጃቸውን የገደሉ እናቶች ያሉ መሆኑ ቢታወቅም… ሴት ልጅ በወንድ ጓደኛዋ አንድ ጥቃት በደረሰባት ቁጥር ሁሉም ወንዶች ላይ ጣት ይቀሰርባቸዋል፡፡ በጥርጣሬ ዓይነት ይታያሉ… ‹‹ውይ ወንዶች!›› ይባልላቸዋል፡፡

በአዲስ አበባ፣ ወረዳ ምንትስ፣ ቀበሌ ምንትስ ውስጥ ‹‹አንድ ባል ሚስቱን በጭካኔ ገደለ›› የሚል ዜና በተነበበ ቁጥር፣ ‹‹አንድ ሰው፣ ሌላ ሰውን መግደሉ›› ወንዱንም ሴቷንም እኩል የሚያሳዝን ዜና መሆን ሲገባው፣ ሴቶቻችን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ወንዳቸውን በጥርጣሬና በፍራቻ ዓይን (በማያውቀው ጉዳይ) ሲመለከቱት እና የአጥቂነት ውርስ ሲያከናንቡት ማየት የተለመደ እና የዘመናችን ወንድ በቀላሉ ሊወጣው የማይችለው ጣጣ እየሆነ መጥቷል፡፡ ወንዱም ቢሆን እንዲህ ዓይነት ዜና በሌላኛው የከተማዋ ጫፍ በተከሰተች ቁጥር ‹የጥፋተኝነት ስሜት› እያዳበረ እንዲመጣ ተገዷል፡፡

## የቅድሚያ መነፈግ ጣጣ

በጥቅሉ ሴቶች ዕድል ተነፍገዋል የሚባል ሚት (myth) አለ፡፡ ይህ ሚት ምንም እንኳን በከተማው ውስጥ፣ ዛሬ ዛሬ እውነት ይሁን አይሁን ባይረጋገጥም፤ በከተማ ውስጥ ወንዱም ሴቷም ዓይነቱ ይለያይ እንጂ ፈተና የሚገጥማቸው መሆኑ ቢታመንም ሴት ዕድል የተነፈጋት ወንዱ ግን እንደነጻ እየተቆጠሩ ዕድሉን ከወንዱ የማስነጠቅ ጣጣውም ቀላል የሚባል አልሆነም፡፡ ‹‹ቅድሚያ ለሴቶች›› የሚለው አባባል የት እና ለምን እንደሆነ የተዘነጋ ይመስላል፡፡ ለፖለቲካ ፍጆታ በተሰናዳ የስርዓተ ጾታ ፕሮግራም ሰለባነት፥ ቁስሉን ያልነካ ይልቁንም ወንዶችን ከሴቶች በሚያለያዩ/በሚያራርቁ አጀንዳዎች በተጠመዱ ‹ፌሚኒስቶች› ሳቢያ የሚመጣ ሌላም ጣጣ አለ፡፡በአውሮጳ የኮርፖሬት አመራር ላይ የደረሱ ሴቶች ቁጥር ሦስት በመቶ አይሞላም፡፡ እውን ሴቶች ዕድሉን ተነፍገው ነው፣ እውን ቅድሚያ ተነፍገው ነው እዚያ መድረስ ያልቻሉት ለሚለው ጥያቄ ጥልቅ ምርምር እንደሚያስፈልገው የአውሮጳውያኑ እውነታ ሞጋች ነው፡፡ ቢሆንም ግን በአገራችን፣ አንዴ መዘመር በተጀመረው የዕድል መነፈግ ሰበብ ብዙ ወጣት ወንዶች እኩል ዕድል ይዘው ቀርበው ‹‹በቅድሚያ ለሴት›› በዝረራ የመሸነፍ ጣጣን የመሸከም ዕጣ ፈንታ ተጋርጦባቸዋል፡፡

የወጣት ወንዶች ጣጣ እነኚህ ብቻ አይደሉም፤ የአቻ ግፊት ጣጣ፣ ሴቶቹ እንደጠቀሱት ዓይነት የመምሰል ጣጣ፣ ሌሎቹም ሌሎቹም እየተገዳደሩት ይገኛል፡፡ ጥያቄው ታዲያ ለመሆኑ ይሄ ሁሉ ጣጣ መፍትሄ አለው፣ ሊኖረውስ ይችል ይሆን የሚለው ነው፡፡

## መነጋገር እንደመፍትሔ

መነጋገር የነገር ሁሉ መፍትሔ ነው፡፡ በተለይ ሴቶች በወንዶች ላይ፣ ወንዶች በሴቶች ላይ የሚያመጧቸው እያልን የዘረዘርናቸው ጉዳዮች ሁሉ ባብዛኛው ባለመነጋገራችን፣ እንደነውር በጣፍናቸው ችግሮች ሳቢያ የተከሰቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ወንዱ ገንዘብ ሳይኖረው ‹‹የለኝም›› ላለማለት ተበድሮ ‹ገርልፍሬንዱን› ከጋበዘ፣ ሴቲቱም

‹‹የወንድ ልጅ ደሞዝ… የሴት ልጅ ዕድሜ አይጠየቅም›› እንደሚባለው ስላለው ነው የሚጋብዘኝ በማለት ሊፕስቲክ፣ ቻፕስቲኳን ብቻ እየገዛች በሱ ላይ ጥገኝነቷን ካዳበረች… ወዳጅነት ሳይሆን ባይተዋርነት ብቻ በሁለቱ ውስጥ እንደነገሠ ይከርማል፡፡ ብዙዎቹ በግልጽነት ላይ ያልተመሠረቱ የፍቅር ግንኙነቶችም በመሰላቸት የሚፈርሱት በዚሁ ምክንያት ነው፡፡

ስለዚህ በሁሉም ጉዳዮች ዙሪያ መነጋገር፣ መነጋገር፣ መነጋገር!

# ስለ ወንድና ሴት የመጻፍ ጣጣ

በ[ውብሸት ታደለ]

*ይህ አጭር ጽሑፍ በዞን ዘጠኝ ጦማር ላይ "ወጣት ሴት የመሆን ጣጣ" በሚል ጽሑፍና ለዚህ ጽሑፍ ምላሽ በተሰጠ "ወጣት ወንድ የመሆን ጣጣ" በሚል ጽሑፍ አነሳሽነት የቀረበ ነው።*

ስለስርዓተ ጾታ የሚደረጉ ውይይቶችና ክርክሮች በተለያዩ የልማድ ማነቆዎች የታሰሩ ናቸው። ከመጀመሪያው ዙር የፌሚኒስቶች ንቅናቄ በኋላ የተፋፋመው የስርዓተ ጾታ ጉዳይ የአብርሆት ዘመን ፍልስፍናን ኋላ ቀር ሊያስብለን በሚያስችል ደረጃ ግሩም ሐሳቦች የቀረቡበት ነው። ከግሪክ ፈላስፋዎች ጀምሮ አብዛኞቹ የቅድመ ፌሚኒዝም ፈላስፋዎች ስርዓተ ጾታን በተመለከተ የጻፉት ሐሳብ ከሰው ልጅ ልማድ መላቀቅ ያልቻለ ነው። ይህን አስተሳሰብ በአግባቡ ለመቃኘትና ክርክሮቻችንን አዲስ መልክ ለመስጠት የፌሚኒስቶችን ሐሳብ መዳሰስና የቅርብ ጊዜ ፀረ-ፌሚኒዝም አስተሳሰቦችን መፈተሽ ያስፈልጋል። በበኩሌ በዞን ዘጠኝ አባላት የተነሱት ነጥቦች የአገራችን የከተማ ወጣቶች ከስርዓተ-ጾታ አንፃር ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ በመግለጽ በኩል በቂ ናቸው ብዬ ባምንም ሁኔታውን በመተርጎምና በመተንተን በኩል ግን ውስንነቶቻቸውን ታዝቤያለሁ። ስለዚህም ጽሑፎቹ ትኩረት የነፈጓቸውን ወይም የዘነጓቸውን ጉዳዮች በአጭሩ በማቅረብ የክርክሩ ሂደት ቅርፅ እንዲይዝ ለማገዝ ጥቂት ነጥቦችን ማንሳት ፈለግሁ። በጉዳዩ ላይ በቀጣይ ሰፋ ያለ ሐሳብ ለማቅረብ ስላሰብኩ ለጊዜው የማነሳቸው ነጥቦች ውሱንና በቀረቡት ጽሑፎች ዙሪያ ያጠነጠኑ ናቸው።

## ጾታዊ ማንነት (Essentialism)

ማንኛውንም ነገር በሁለት ተቃራኒ ጎራ የመክፈል ልማድ (Dichotomy) በስርዓተ ፆታ ጉዳይም የተጠናወተን አባዜ ነው። በራሳችን አዕምሮ ውስጥ የፈጠርናቸው የማንነት ተቃራኒ ምድቦች የራሳቸው ሕልውና እንዳላቸው የመውሰድ አስተሳሰብ ለምድቦቹ ሥነ-ሕይወታዊ ዳራ እንድንሰጣቸው አድርጎናል። ስለዚህም በክርክሮቻችን ውስጥ ሴትና ወንድ እንደ ቋሚ ማንነቶች (Essences) የሚቆጠሩበትና ማንኛውንም ግለሰብ ከሁለት ተቃራኒ የማንነት ቅርጫቶች ውስጥ በአንዱ ለመጨመር የምናደርገው ጥረት ሊፈተሽ ይገባዋል። ይህ አስተሳሰብ በግለሰቦች መካከል ያለውን ልዩነት የዘነጋና የግለሰብ ባህርይ የሚቀዳው ከሁለቱ ተቃራኒ "የተፈጥሮ" ቡድኖች መሃል ካንዱ እንደሆነ ታሳቢ የሚያደርግ ነው። የፌሚኒስቶች ንቅናቄ በጥልቀት የፈተሸው አንዱ እውነታ ይህ ነው። ይህም የፌሚኒስቶች ሙግት "ማንነት" የምንለውን ጉዳይ በእጅጉ የፈተነና "የተቃራኒ ጾታ" የፍቅር ግንኙነትን ታሪካዊ መሠረት ያናወጠ ነው። ይህን ጉዳይ በአግባቡ ለማጤን እንዲቀየሩ የፈለግናቸውን የወንድና የሴት ባህርያት ማሰብ በቂ ነው። እነዚህ ባህርያት ከተቀየሩ ወንድና ሴት የሚባሉ ማንነቶች ከየት ይመጣሉ? ይህን ጥያቄ በስነ-ህይወታዊ ትንታኔ ለመመለስ መሞከር ስርዓተ-ፆታችን ካለበት እንዳይንቀሳቀስ መፍቀድ ነው። ዋናው ነጥብ ግን በሁለቱም ጽሑፎች ላይ ይህ ጉዳይ በልማድ ዕይታ ሙሉ ለሙሉ እንደተሸፈነ መታዘቤ ነው። ይህን ስል አሮጌው የጾታ ስርዓት በቋንቋችን ላይ የፈጠረውን ውሱንነት ዘንግቼ አይደለም።

## የእኛ ወጣቶች

በጽሑፎቹ ላይ የተነሱት ነጥቦች የአገራችንን የከተማ ወጣቶች ለይተው የሚመለከቱ ናቸው። ዕይታው ስርዓተ ጾታን የባሕል ውጤት እንደሆነ ከመቁጠር የሚመነጭ ነው። ይህ ሐሳብ በራሱ ችግር አለበት ብዬ አላምንም። Simone de Beauvoir የተባለችው ዕውቅ ፌሚኒስት የስርዓተ ጾታን ባሕላዊ መሠረት በተመለከተ ሰፊና አሳማኝ ሐሳቦች አቅርባለች። ጥያቄው የሚመነጨው ግን የወጣቶቹ መለያ ባሕርያትን በተመለከተ በዞን ዘጠኝ ጸሐፊዎች የቀረቡት ነጥቦች በእኛ ባሕል ውስጥ ብቻ የሚገኙ አለመሆናቸውን ስናስተውል ነው። ለምሳሌ ሴቶች በሬስቶራንቶች መጋበዝን ፋሽን እንዳደረጉት የሚኮንን ሐሳብ አለ። በሌላ መልኩ ወንዶች ሐሳቦቿን የምትገልጽላቸው ሴትን እንደሚርቁ ተቀምጧል። እነዚህ እውነታዎች በሌላው ዓለምም የሚታዩና ዓለም አቀፋዊ መሠረት ያላቸው ናቸው።

ጆን ግሬይ "Men are from Mars, Women are from Venus" በሚለው መጽሐፉ ሴቶች ለግንኙነት ትኩረት ስለሚሰጡና ሌሎችን ማገዝ ዋና እሴታቸው ስለሆነ ከወንድ  ገንዘብም ሆነ ሐሳብ መቀበላቸውን እንደመረዳዳት እንጅ እንደጥገኝነት እንደማይቆጥሩት፣ በተቃራኒው ግን ወንዶች ሌሎችን ስለማገዝም ሆነ ስለግንኙነት ግድ ስለሌላቸው ከሌላ ሰው (ከሴቶች) የሚመጣን ሐሳብም ሆነ ገንዘብ መቀበል የዝቅተኝነት (የጥገኝነት) ስሜት

እንደሚፈጥርባቸው ይገልፃል። የሴቶችን የሞራል ዕድገት በተለዬ መልኩ ያጠናችው ካሮል ጊሊጋንም ከግሬይ ሐሳብ ጋር በሚስማማ መልኩ የሴቶች የሞራል ዕይታ ስለሌሎች መኖርን ቅድሚያ እንደሚሰጥ ታብራራለች። በሌላ በኩል Chris Haywood እና Mairtin Mac an Ghaill የተባሉ ጸሐፊዎች "Men and Masculinities" በሚለው መጽሐፋቸው ወንድ ልጅ በአምራችነትና በቁስ አቅርቦት የተወጠረ መሆኑን እያስተዛዘኑ ጽፈዋል። ስለዚህም በዞን ዘጠኝ ጸሐፊያን እንደተሞከረው የወጣቶቹን ባሕርያት ከባሕላችን አንፃር መመልከት ከእናቶቻችን ንግግርና ፍላጎት ጀርባ ያለውን ትልቅ ኃይል ካለማስተዋል ይመነጫል። ባሕሉ የትልቁ ኃይል እጅ እንጅ ራሱ ትልቁ ኃይል አለመሆኑን ልንዘነጋ አይገባም። ይህን ሐሳብ ባንቀበለው እንኳን ቢያንስ የዚህን ኃይል መኖር ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል።

## የተዘነጋ ልጅነት

የስርዓተ ጾታ መሠረት የሚጣለው በአብዛኛው በልጅነት የዕድሜ ዘመን ወቅት እንደሆነ ሳይኮአናሊስቶችና ሶሲዮሎጅስቶች ያብራራሉ። እናቶች የልጅ አሳዳጊነትን ሚና በብቸኝነት እየተጫወቱ መሆናቸው ሴት ልጆች የእናታቸውን ሚናና ባሕርይ በቀላሉ እንዲወርሱና ወንድ ልጆች ግን ማንነትን ፍለጋ ወደ ውጭ ለማማተር ክፍት እንደሚሆንላቸው ያስረዳሉ። ይህ ሂደት የትውልድ መተካት (Reproduction) ሚና ለሴቶች ብቻ የቁስ ማምረት (Production) ሚና ደግሞ ለወንዶች ብቻ እንዲሰጥ አድርጓል። ስለዚህም የወጣቶቹ ባሕርይ በአጭር የወጣትነት ጊዜ የመጣ ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት አይታየኝም። ማኅበረሰቡ ከወጣቶቹ የሚጠብቃቸውም ነገሮች ሆኑ መመሳሰልን የሚሰብከው ስርዓት በድንገት የመጣ አይደለም። ወላጆች ከልጆቻቸው የሴትነትን ወይም የወንድነትን መለያዎች የሚጠብቁት እንደዛ እንዲሆኑ አድርገው ስላሳደጓቸው ነው። መቼም ያልዘሩትን ለማጨድ አይመኙም። ለዚህ ነው ትኩረታችን ልጅነትን ዘንግቶ ከወጣትነት መጣበቅ የለበትም የምለው።

## ብሶት ወለድ ዕይታ

ሌላው ከጽሑፎቹ የታዘብኩት ነገር ወደ መፍትሄ የማያደርሱ ብሶት ወለድ ትንታኔዎች መሆናቸውን ነው። ውስብስቡን ኋላ ቀር የጾታ ስርዓት ለመቀየር በአመዛኙ ኃላፊነቱን ለራሳቸው ለወጣቶቹ የሚተው ይመስላሉ። ከዚያም ሲያልፉ ወደ ባሕላችን ክንዳቸውን ያዞራሉ። ይህ አካሄድ ሩቅ የሚያስኬድ አይደለም። ወንድ አምላክ በሚመለክበትና ቋንቋዎች በፆታ ስልት በተቃኙበት (ለሕይወት አልባ ነገሮች እንኳን የጾታ መለያ በተሰጠበት) ዓለም በትናንሽ የድርጊት ለውጥ የሚመጣ ነገር ቢኖር የመልክ ለውጥ ነው። በዚህ መሐል ስርዓቱ ይበልጥ እየጠነከረና ምክንያታዊ እየመሰለ ይሄዳል። ምክንያታዊ የሚመስልን ስርዓት ለመቀየር ደግሞ አሁን ያለንን የመቀየር ዕድል ያክል ቀላል አይደለም። ስለዚህም ወደ ጠንካራ የፖለቲካ ስትራቴጂ የሚወስዱን ትንታኔዎች ላይ ማተኮር የተሻለ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

## በመጨረሻም

በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት ሰጥተው በመጻፍ ጥሩ ጅምር ላሳዩን የዞን ዘጠኝ ጸሐፊዎች ለማሕሌት ፋንታሁን፣ ለሶሊያና ሽመልስ፣ ለበፍቃዱ ኃይሉና ለእንዳልካቸው ኃ/ሚካኤል ያለኝን ክብር ገልጨ ሌሎቻችሁ የምትጽፉትን ለማንበብ በመመኘት ባበቃስ?!

## ልፈራ የሚገባኝ "ሕይወቴን ያለክብር እንዳልመራ" ነዉ እንጂ "ክብር የተነፈገዉ ሕይወቴን እንዳላጣ አይደለም።"

ፍቃዱ አንዳርጌ

ዞን 9 በተባለዉ የመወያያ መድረክ ላይ ብዙ ጠቃሚ ሃሳቦች በተለያዩ ፅሃፊዎች እየተነሱ ሲብራሩና ለዉይይት ሲቀርቡ እከታተላለዉ ይበል የሚያሰኝም ነዉ ። እንደ አስተያየት ግን በየጊዜዉ የሚነሱ ሃሳቦች እንደ ቆዳ እየለፉ ማለፍ እንዳለበት ይሰማኛል።

ዛሬ እኔም የማህሌት ፋንታሁን "የፍርሐት ዘመን" የሚለዉን መጣጥፍ አንብቤ ከሃሳቧ ላይ ሃሳቤን መጨመር ፈለኩ ፡- ማህሌት በፅሁፏ የዘረዘረቻቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለትም "ተማሪዎች፣ሰራተኞች ፣አሰሪዎችና ባለሃብቶች ፍርሃት መር ኑሮ ለመኖራቸዉ ተማሪዉ ተመርቆ ስራ አጥ እንዳይሆን፣ ሰራተኞች የስራ ዋስትናቸዉን፣ እድገት እና የትምህርት እድል የሚያገኙት በመፍራት ስለሆነ፣ አሰሪዎች ከቀዳሚ አለቆቻቸዉ ሞገስን እና ጥቅማጥቅምን ያገኙ ዘንድ እነሱዉ እራሳቸዉ ፈርተዉ ሰራተኞችን የፍርሃት ሀሁ ማስቆጠር ስላለባቸዉ እና በቁስ ቀዳሚነትም ያመኑት ባለሃብቶችም ቢሆኑ ጣሪያ የሌለዉ ፍላጎታቸዉ ይሞላ ዘንድ የፍርሃት መንፈስ ይጠናወታቸዋል።" ብላለች።

እኔም ሁሉም ሳይፈልግ ወደ ፍርሃት ዓለም የሚያደረገዉ ጎዞ መነሻዉ የእዉቀት፣የምክንያት እና ፍላጎት ያለመመጣጠን እንደ ሆነ እና መጨረሻዉም "የፍርሃት ማህበረሰብ"(fear society) መፈጠር ሊሆን እንደሚችል አምናለሁ ። በፍርሃት እሳቤ የተከበበ ማህበረሰብ ደግሞ የተቃወሰ ማህበራዊ ስሪት ስለሚኖረዉ ለመጪዉ ትዉልድ ሊያስተላልፈዉ የሚችል ባዶ የፍርሃት መንፈስን ብቻ ነዉ። እዉቁ ፈላስፋ "ፕላቶ" የሰዉ ልጅ የተስተካከለ፣ ጤናማ እና ከፍርሃት የፀዳ ምክንያታዊ ስብዕና ይኖረዉ ዘንድ ሊሟሉ ይገባል ያላቸዉን ነገሮችን ዘርዝሯል። እኛም "ፍርሃት" ከስነ ልቦና ስሪታችን ጋር የተያያዘ ስለሆነ የሊቁን ስራ በከፊል እንመልከተዉ እንዲህም ይላል "የሰዉ ልጅ አካለዊና ስነ ልቦናዊ ስሪቱ የተስተካከለ ሊሆን ግድ ይለዋል። የሰዉን ልጅ የነፍስ ሁነት ከሶስት ከፍሎ ማዬት ይቻላል። የመጀመሪያዉ "ምክንያታዊ" ክፍል ሲሆን አንድ ሰዉ እንዲጠይቅ፣ እንዲያዉቅ ፣እንዲከራከር እና ሃሳቡን እንዲገልፅ የሚያደርግ ክፍል ሲሆን፤ ሁለተኛዉ "መንፈሳዊ ክፍል" የሚለዉ ሲሆን ደግሞ አንድ ሰዉ መልካም ፈቃዱን የሚሰጥበት እና የፍርሃት እና የድፍረት ስሜቱ የሚብላሉበት ክፍል ነዉ። ሶስተኛዉ ፍላጎትን መሰረት ያደረገዉ ፍላጎታችን የሚርመሰመስበት ክፍል ሲሆን የምግብ፣የመጠጥ፣የወሲብ፣ የሃብትና መሳሰሉ ፍላጎታችን ማንፀባረቂያ ክፍል ነዉ።" ይቀጥልናም "የአንድ ሰዉ የተስተካከለ ስብዕና ይኖረዉ ዘንድ የእነዚህ ክፍሎች የተመጣጠናና የተስማማ አካሄድ ሊኖራቸዉ ግድ ነዉ" ይለናል።

እዚህ ላይ ዋናዉ ነጥቡ የሰዉ ልጅ ለማይገደቡ ፍላጎቶቹ ብቻ አዳሪ እንዳይሆን፣ በአጉል ፍርሃት ተሸብቦ ድንጉጥ እንዳይሆን ምክንያትን የማቅረብ አቅሙ ሊጎለበት ግድ ይለዋል። ምክንያታዊነት ወደ መድረክ ሊመጣ የሚችለዉ ደግሞ ጥልቅ ወደ ሆነዉ የእዉቀት ዉቅያኖስ በመማር፣በማንበብ ፣በመጠየቅ እና በመከራከር ስንገባ ብቻ ነዉ። አንድ ሰዉ ጥቅሙንና ፍላጎቱን ብቻ በማስቀደም ምክንያትን ገሸሽ በማድረግ መንገዱን የጀመረ እንደሆነ አሁንም መዘበራረቅ ሊከሰት ይችላል። ዋናዉን ጉዳያችን "ፍርሃትን" ነጥለን ያየነዉ እንደሆነ እንድንፈራ ያደረገን ነገር ፅኑ የመኖር ምኞት፣የቁስ ሰቀቀን፣ በስራ እጦት ያለመስቃየት፣የሰዉ ፊት ላለማየት፣የደረጃ እድገት፣ብቸኝነትን መፍራት እና መሰል ስሜት ነዉ። እነዚህን ዝርዝር እና ግልፅ የፍርሃታችን ምንጮች ግን በፍርሃታችን የተነሳ ከምናጠዉ ነገር ማለትም የማወቅ፣ያወቅነዉን ነገር የመጠየቅ፣በሰዉነታችን ያገኘናቸዉን ሰብዓዊ መብት ከማጣት አንፃር በምክንያታዊ እይታ ሲመዘኑ ዉሃ አይቋጥሩም። ለዚህም ነዉ የፍርሃታችን መነሾ የፍላጎታችንና የምክንያታዊ መሆን አለመመጣጠን የሚሆኑት። ለዚህም እንደ ማሳያ የተማሪዎችን፣መምህራንና ሰራተኞችን ፍርሃታቸዉን እንደ ገቢ ምንጫቸዉ እና የፍላጎታቸዉ ማሚያ እንዲመስከቱ ያደረገበትን ሁኔታ አንስተን መመልከት እንችላላን።

### ተማሪዎችና መምህሮች

አዎ ተማሪዎቻችን የፍርሃት ቆፈን ይዟቸዋል። በድህነት ተምረዉ ፣ተመርቀዉ ስራ እንዳያጡና የቤተሰብ ሸክም እንዳይሆኑ ይሰጋሉ። ለስጋታቸዉ ማሳለጫ ይሆናቸዉ ዘንድም ሳይፈልጉ የፍርሃት መንገድን ይዘዉ

ይሽመጥጣሉ። ይህ ለምን ሆነ? ያልን እንደሆነ መልሱን ሩቅ ሳንሄድ ከነባራዊ ሁነቶች መረዳት እንችላለን። አብዛኛዉን የተማሪ ክፍል ያየን እንደሆነ ከሚማርበት የትምህርት ዘርፍ የዘለለ ወደ ሞራላዊ ልዕልና የሚያደርስ የማወቅ፣የመጠየቅ እና የማንበብ ልምዱ ከዜሮ በታች ሆኖ እናገኘዋለን። ታዲያ የዕለት ዉሎዉን በአዉሮፓ እግር ኳስ ፣ የሆሊዉድን ፊልም ሰንጠረዥ መዉጣት መወረድ ሲነታረክ የሚዉልን ተማሪ ምክንያት አንስተህ ከፍራትህ ተፋታ ማለት ትንሽ ምፀት ይሆናል።ይሄ ደካማነቱም ፍርሃትን ወልዶ በራስ አለመተማመንን ገንብቶ ለአምባገነኖች በቀላሉ እንዲበረከክና በወጥመዳቸዉ እንዲወድቅ ያደርገዋል። ይሄ ጉዳይ የዓለም ዉራነታችን የሚያሳየን ደግሞ አዉሮፓዎችና ምዕራባዊያኖች እዚህ አለማቀፋዊነት ደረጃ የደረሱት በእዉቀት ተጠምቀዉ፣በምክንያት ዓለም እየኖሩ ፍርሃትን ገፊዉ የሚገባቸዉን በመጠየቅ መሆኑን ስንገነዘብ ነው።

መመህሮቻችንም የዚህ ፍርሃት ሰለባ ናቸዉ።አንድ ሁለት የትምህርት ዓይነት ይይዙና ከዚያ ባለፈ ያላቻዉን ጊዜ ወገባቸዉ ላይ ሽርጥ አሸርጥዉ የፑል ዲንጋይ ሲደልቁ የሚዉሉ፣ከተማሩት ትምህርት የዘለለ ወንዝ የሚያሻግር እዉቀት ማነስ የተጠናወተዉ ፣ እንግዲህ መሸ ወደ ምሽት ቤት ልዉጣ እያሉ የቢራ ጠርሙስ ጨብጠዉ ሌቱን በንባብ ሳይሆን በዳንኪራና በቧልት የሚያነጉ መምህሮች አያሌ መሆናቸዉን ስንመለከት በምክንያት የሚሞግት መመህር ሆይ ወዴት ነህ? እንድንል ያደርገናል። እንደ ገቢ ምንጭ ብቻ የሚጠቀምበትን መመህርነት ላለማጣት ተማሪዎችን ከነባራዊ ሁኔታ ጋር እያገናዘቡ ማስተማር ህልም ይሆንበታል። እንደ ማሳያ ዩኒቨርሲቲ እያለሁ ያጋጠመኝን ጉዳይ ላንሳ መመህሩ ክፍል ዉስጥ በሚያስተምርበት ሰዓት ከተማሪዎች ጥያቄ ይቀርብለታል። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ጥያቄዉ ፖለቲካዊ ይዘት ነበረዉ፤በራሱ የሚተማመን ትዉልድ የመፍጠር ሃላፊነት የነበረበት መምህር መልስ ግን ሁላችንም ቅር ያሰኘና እኛም እንደ እርሱ ማሰብ እንዳለብን በሚያመላክት አነጋጋር “ይሄ ፖለቲካ ነዉ እንለፈዉ” ነበር ያለዉ። ተማሪዉ ከፍርሃት ይላቀቅ ዘንድ የመምህሩ ደፋርነትና ምክንያታዊነት ወሳኝነት ነበረዉ። ያ ግን ሳይሆን ቀረ እኛም ፍርሃት ፍርሃት ሲለን “ይሄ ፖለቲካ ነዉ” እንለፈዉ ማለት ጀመርን።

### የመንግሥት ሰራተኛው መደብ

በቤተሰብ፣በሰፈር፣በቀሌ፣በጎጥና በሃገር ደረጃ የቁስ አካል ቀዳሚነት በነጋሪት እየተነገረ ከሰራተኛዉ መደብ ሰብዓዊነትን ያማከለ እንቅስቃሴ ላይታሰብ ይችላል። ይህ በቁስ ሰቀቀን የሚባትልን የማህበረሰብ ክፍል የአምባገነኖችን ወጥ የሆነ አስተሳሰብ እንዲይዝ በሚደረግበት ጊዜ ፍርሃት የራሱ ሆነ ሚና ይኖረዋል። አብዛኛዉ የሰራተኛዉ ክፍልም ከዩኒቨርሲቲ፣ከኮሌጅና መሰል የትምህርት ተቋሞች እንደተመረቀ በተማረበት ትምህርት መስክ የመቀጠር እድሉ የጠበበ ስለሆነና የትምህርትን፣የንባብን ምዕራፍ እንደተዘጋ አድርጎ ስለሚያስብ ስራ እንደጀመረ በማግስቱ ምን እንደተማረ ወዴት እንደሚያመራ ግራ ይገባዉና ዘልማዳዊ ኑሮን ይገፋል ። ቢሮ ዉስጥና በመስክ በተዘረጉ ቢሮክራሲዎች ይታሰርና እርምጃዉን ባለበት ይረግጣል። የእድሜ መጨመርና እራስን በኢንፎርሜሽን፣በንባብ አለማሳደጉ ዛሬ ላይ ተቀምጦ ከሁለትና ከሶስት ዓመት በኋላ ስለሚያደርገዉ የመቶ እና ሁለት መቶ ብር ጭማሪ ተስፈኝነት፣ ይቺንም እድገት ላለማጣት የማይሆነዉን ሆኖ መታዬትና ፍርሃት ብቅ ማለት ይጀምራሉ። እድገቱም ቢቀር የያዙትን ላለማጣት የሚደረግ የመፍጨርጨር ጉዞ።

በአጠቃላይ የፍርሃታችን መነሻ ያየነዉ እንደሆነ በክብር መኖርን፣ በሰብዓዊነታችን ያገኘናቸዉን መሰረታዊ መብቶች እንዳናጣዉ ከምንሳሳለት ሕይወት፣ቁስ፣ከስራ ተራ መገፋትን ፣ግዞት መዉረድ ጋር ስናነፃፅረዉ ስለሚያንስብን ነዉ። ይህ ሊሆን የቻለዉ ደግሞ ፍላጎታችን በምክንያት ባለመመራቱ ነዉ። አንድ ሰዉ በሕይወት መኖርን ሲመኝ አብሮ በክብር፣ሰብዓዊነቱ ተክብሮ ሊኖር ግድ እንደሆነ ማመን ስንችል ነዉ ከፍርሃት ነፃ የምንሆነዉ ። አንድ ሰዉ በስራዉ ላይ እንዲቆይ ከፈለገ መብቱ እስከተከበረ ድረስ እንጂ መብቱ ሳይከበር ስራ ላይ መቆየቱ አግባብ እንዳልሆነ ስንረዳ ነዉ ፍርሃትን የምናስወግደዉ። እኔ ልፈራ የሚገባኝ “ሕይወቴን ያለክብር እንዳልመራ” ነዉ እንጂ “ክብር የተነፈገዉ ሕይወቴን እንዳላጣ አይደለም።” እንዲህ ነዉ ደግሞ የመኖር ፍላጎት በምክንያት ሲሟሽ።

# ሕፃናትና ኢትዮጵያችን

በኢዮብ ብርሃነ

ልጆች የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች ናቸው። የነገይትዋ ኢትዮጵያ ተተኪ ብላቴናዎች ከአበባነት ወደ ፍሬነት እንዴት ይቀየራሉ? ምን ዓይነት ፍሬዎች እንድናገኝ እየተሰራ ነው? የሚለውን ጥያቄ በዚህ ጽሑፍ ወፍ በረር ለመዳሰስ እሞክራለሁ።

ልጆችን ከአስተዳደጋቸው መሠረት አስይዞ አርሞ ማሳደግ ጥቅሙ ለቤተሰብ ብቻ ሳይሆን ትሩፋቱ ለአገርና ለወገን የሚጠቅሙ የነገይትዋን ኢትዮጵያ የሚረከቡ ብቁ ትውልድ እንዲኖረን ያስችላል። ይህ ግን ዝም ብሎ አይመጣም ከቤተሰብ እስከ ማህበረሰቡ እንዲሁም ልጆች ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ብዙ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበት ትምህርት ቤት ትልቁን ኃላፊነት ይወስዳሉ። ሰንሰለታማው የኃላፊነት ድርሻ አንድ ቦታ ላይ ከተስተጓጎለ ወይም ሰንሰለቱ ከተበጠሰ "አሜከላ ዜጋ" የማፍራታችን ዕድል ይጨምራል።

ሕፃናት ወረቀቶች ናቸው ንፁህ ሕሊናቸውን በመልካም ነገሮች እየተገነቡ እንዲያድጉ ከላይ የተጠቀሱት አካላት ምን ምን መደረግ አለባቸውብሎ መወያየት ለነገ የምንፈልገው አይነት ትውልድ ምን አይነት ይሁን የሚለውን ለማወቅ ይረዳናል።

## ፩፡ቤተሰብ

በቤተሰብ ውስጥ ስለልጆች ያለው አመለካከት ላይ ለውጥ ቢኖርም አሁንም በቤተሰብ ደረጃ ብዙ ችግሮች አሉብን። ለአብነት ያህል ብናነሳ ልጆችን የማበረታታት ባህላችንንም ብዙ የሚቀረው ነው። እሰየው፣ ጎበዝ፣ በርታ፣ በጣም ተለውጠሃል ወዘተ… የሚሉ ሞራል የሚገነቡ ማበረታቻዎችን ቢኖሩንም እነዚህን ማበረታቻዎች በተከታታይ ለሕፃናት ማሰማት በራሳቸው የሚተማመኑ ልጆችን ለመፍጠር አዎንታዊ አስተዋፆ አለው። በአንፃሩ

- ልጅ ያቦካው ለእራት አይበቃም
- ልጅና ጫማ አልጋ ስር
- ነገር ሁለት ፍሬ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ ወዘተ…

ከላይ የተጠቀሱ ሞራል ገዳይ አባባሎችን በማዝነብ ብላቴናዎችን ማሸማቀቅ ልንተወው የሚገባን ማኅበራዊ እንከኖቻችን ናቸው። ወላጆች ልጆቻቸው ፊት ለፊት መጨቃጨቅ፣ መደባደብና መዘላለፍ የልጆችን ሕሊና ክፉኛ ከመጉዳቱም በላይ ቤት ውስጥ ሰላም ከሌለ ሕፃናት በጭንቀት ውስጣቸው ክፉኛ ስለሚጎዳ ትምህርታቸውን በአግባቡ መከታተል ይሳናቸዋል። ወላጆች አቅማቸው በፈቀደ መጠን የልጆቻቸውን ስሜት ማጥናት አለባቸው።ወደ ቀለም ትምህርታቸውም ሆነ በልዩ ተስእጦአቸው አሊያም በሙያ ምርጫቸው በየትኛው መስክ ዝንባሌ እንዳላቸው በፅሞና መከታተል ያሻል ። ስሜታቸውን በመጫን ወላጆች የሚመኙትን ወይም ሞክረው ያቃታቸውን ነገር በልጆቻቸው ላይ ለማየት መሞከርና ካለፍላጎታቸውና ዝንባሌዎቻቸው ማሳተፍ ደስተኛ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋልና ወላጆች ጥንቃቄ ሊወስዱ ይገባቸዋል። በተጨማሪም ከትምህርት ውጪ ያሉትን ሰዓታት ልጆችን ቤት ውስጥ ብቻ እንዲታጎሩ በማድረግ፣ በፊልምና የግዴታ ሥራ ማጥመድ ልጆች ልጅነታቸውን በአግባቡ ተጫውተው እንዳያልፉ ያደርጋቸዋል። በዕቅድ ይመሩ ዘንድ ወላጆች የጫወታና የጥናት ጊዜያቸውን በመመደብ የጊዜ ክቡርነትን በልጅነታቸው በማስተማር የጊዜ አጠቃቀምና ኢትዮጵያዊነት(ቀጠሮ ላይ ያለንን አገራዊ ደካማነት) የሚታረቁበትን መሠረት መጀመር አለብን።

ወላጆች በአቅማቸው መጠን በምጣኔ መውለዳቸው አስፈላጊውን አሟልተው የሚያስድጓቸው ልጆች እንዲኖሩዋቸው ያደርጋል።ልጆችን በባዶ ሆዳቸው ትምህርት ቤት መላክ ወንጀል ነው። ባዶ ሆድ ጆሮ የለውምና! አዋዋላቸውን መከታተልና ባልጀሮቻቸውን ማወቅም ለተሻለ አስተዳግ ግድ ይላል ፤ ይህም ልጆች በጓደኞቻቸው ተፅዕኖ የሚበላሹበትን አጋጣሚዎች ይቀንሰዋል። በተጨማሪም ልጆች በሰውነት ማጎልመሻ በሚወዱት ዝንባሌያቸው ይሳተፉ ዘንድ ማበረታታት ጤናማ ብላቴናዎችን ለማግኘት ያግዛል።

ልጆችን አጉል ቅጣት በመቅጣት አካላዊና ሞራላዊ ተፅዕና መፍጠር፣ አባትን ወይም እናትን በተናጠል እንዲፈሩ ማድረግ ተሸማቃቂ ስለሚያደርጋቸው ጥፋትን መደበቅን፣ መሰሪነትንና ፍርሃትን ይማራሉና ሊሰመሩባቸው ይገባል።

## ፪፡ማኅበረሰቡ

ከወላጆች በመቀጠል ቤተዘመድ፣ ጎረቤት፣ የወላጆች የሥራ ባልደረባዎች ልጆችን በመልካም ዓርያነት የመምራት ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል። ልጆችን የሚያሳድገው ማኅበረሰቡ ነው፤ ልጆች ከትምህርት ቤት ጥፋት ፈፅመው ሲመጡ ወላጆች እንዳያውቁባቸው በመፍራት ለጎረቤት ወይም ለወላጆቻቸው ጓደኞች፣ ቤተዘመድ አሊያም ለማያውቁት አልፎ ሂያጅ ወላጅ ሆኖ ትምህርት ቤት እንዲሄድላቸው በመማፀንና ጥፋታቸውን ይሸሽጉላቸው ዘንድ ሲማፀኑ ልጆቹን መተባበር ከጥፋታቸው እንዳይማሩ ያደርጋቸዋል። በአንፃሩም ሐሰትን ይማራሉና ማኅበረሰባችን ይህን የወንጀል ተባባሪነት ምንጭ ማድረቅ አለብን። ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱትን እንስት ታዳጊዎችን ፆታዊ ትንኮሳ ማድረግና፣ ሲፈፀምባቸው እያዩ በምን አገባኝ በዝምታ ማለፍ ለትውልድ መምከን አሉታዊ ጎን አለውና ሁላችንም በሕግ የበላይነት የሚያምኑ ታዳጊዎችን ለማፍራት የሕፃናትን ጥቃቶች መከላከል አለብን።

## ፫፡ትምህርት ቤት

ትምህርት ቤት ትውልድ ለማነፅ ዋናውንና ወሳኙን ሚና ይጫወታሉ። መምህራን ልጆችን በትምህርት ብቻ ሳይሆን በማኅበራዊ ህይወታቸው የተሻሉ ዜጋ ይሆኑ ዘንድ ክትትልና ማበረታቻ በመስጠት የታረሙ ይሆኑ ዘንድ ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው። የልጆችን ሞራል የሚሰብሩ ንግ ግሮችን፣ አካላዊና ሞራላዊ ቅጣቶችን መቅጣት፣ በሕፃናት ፊት ፀያፍ ምግባራትን መፈፀም ለልጆች በዕኩይ ምግባር ማደግ ድርሻ አላቸው።

መምህራን የተማሪዎቻቸውን ወቅታዊ አቋም አካላዊና ሞራላዊ ብቃታቸውን መከታተል አለባቸው፣ልጆችን በመቅረብ ያለባቸውን ቤተሰባዊ ችግሮች መረዳትና መፍትሔ መስጠት አለባቸው። (በአገራችን በተጨናነቁ ክፍሎች ውስጥ የሚማሩትን ሁሉንም ልጆች መከታተል ለመምህራን አዳጋች መሆኑ ይሰመርበት)

## ፬፡መንግሥት

መንግስት በታዳጊ ሕፃናት ላይ የሚደርሱትን አስፈላጊ ያልሆኑ የመብት ጥሰቶች ከምንም በላይ ቅድሚያ በመስጠት ሕግ አስፈፃሚው አካላትን ልዩ ስልጠናና የአቅም ግንባታ በማድረግ ልጆች የተሻለ ዜጋ ይሆኑ ዘንድ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፣ ከትምህርት ቤት የሚያስቀሩ ወላጆች፣ አካላዊና ወሲባዊ ጥቃት የሚያደርሱ ወንጀለኞች ላይ ሕጉን በማስፈፀም ላይ ጠንካራ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት። በተጨማሪም የልጆች መዝናኛ ማዕከላትን፣መናፈሻዎች፣የሰውነት ማጎልመሻ አገልግሎት መስጫ ተቋማትንና የልጆች የጽሕፈት መሳሪያዎች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ከቀረጥ ነፃ ቢቻል ካልሆነም ተመጣጣኝ ዋጋ ይኖራቸው ዘንድ ድጋፍ ማድረግ አለበት።

ሕፃናት በትምህርት ቤት ውስጥ የሕግ ከለላ ትምህርቶችን ማስተማርያ ስልቶችን ማሳወቅ መብትና ግዴታቸውን በለጋ ዕድሜያቸው ይረዱ ዘንድ ያስችላቸዋል። መንግስት ልጆች የመብት ጥሰት ሲገጥማቸው ከሕግ አካላት ጋር የሚገናኙበትን የቀጥታ መስመር የስልክ ቁጥር ያውቁ ዘንድ የማስተማርያ መጻሕፍቶችን ማሳተምና ማስተማር ግድ ይላል።

የመዋዕለ ህፃናት ደረጃዎችን መዳቢ የልጆች ጉዳይን የሚከታተል አካል ሊኖረን ይገባል። የታዳጊ አጥፊዎችን ማረሚያ ማዕከላት በመሥራት በወጉ ታርመው የተሻለ ዜጋ የሚሆኑበት ያሉትንም ብቃት ባላቸው ባለሙያና ቁሳቁስ ማጠናከር፣ ያልተሰራባቸው ክልሎች ላይ መስራት ያስፈልጋል።

ሁላችንም የምንመኛት የተሻለች ኢትዮጵያ የምትገነባው ኃላፊነት የሚሰማቸው በግብረገብ፣ በትምህርት የታነፁ ተተኪዎች ሲኖሩን ነውና ሁላችንም ያሉብንን ግዴታዎች መወጣት ይጠበቅብናል። ያኔ ሕልማችን እውን ይሆናልና!

ቸር ያቆየን!

# የቀለም ልዩነት(መድልኦ) በአገራችን ኢትዮጵያ

በእዮብ ብርሃነ

ይህን ጽሑፍ ከላይ ርዕሱን አይታችሁ ምን ለማለት ፈልጎ ነው? አሊያም ሁሌም ጠንካራ ጎናችን የሆኑትን መስማትና ማንበብ ስለለመድን ይህ ሐሳብ ግርታ የሆነ ስሜት ሊፈጥርባችሁ ይችላል። ሐቅ ቢመርም መዋጥን መልመድ አለብና የተሰማኝን ጻፍኩት የሚሰማችሁን በጨዋ ደንብ አክሉበት። (ፀያፍ ካልተሳደቡ አስተያየት ያልሰጡ የሚመስላቸውን ታታሪ ተሳዳቢዎችን ነው ማሳሰቢያው የሚመለከተው!)

በኢትዮጵያችን ውስጥ ጥቁሩ ማኅበረሰብ (ከጠይም በላይ የጠቆሩትን ማለቴ ነው) በቆዳው ቀለሙ ብቻ መድልዖ ይደርስበታል የማግለልና በቀለም ብቻ የሚፈፀሙት በደሎችና መንስኤዎችን ለመዳሰስ እሞክራለሁ።

## ፩፡-የሥራ ዕድል

ሥራ ለማግኘት ከትምህርትና ከችሎታ መመዘኛዎች በተጨማሪ የምትጠየቀው ወይ የሚፈለግብህ/ሽ ነገር አለ። የት አገር እንዳትሉኝ በእኛዋ ኢትዮጵያችን ውስጥ መልከ መልካም መሆን አሊያም ጠይም የቆዳ ቀለም ሚዛኑን ትደፉ ዘንድ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ። የስራ አመራር፣ አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ሹመቶች ወዘተ... ግርማ ሞገስና ውበት ከብቃት ይልቅ ሚዛን ይደፋሉ። የቤት ሠራተኝነት የምትቀጠር አንዲት ሴት ጠቆር ካለች የመጥፎ ገድ ምልክት ተደርጋ፣ ልጆቻችን ሊፈሩ ይችላሉ ተብሎ፣ ያቺ ምስኪን የሥራ ዋስትና ታጣለች። በተፈጠሩበት አገር ላይ መገለል ጉዳቱ ምን ያህል መሆኑን ከቀመሱት በላይ ማን ሊሰማው ይችላል?

(አካላዊ ውበትና ቅርፅ የሚሹ የሥራ መስኮች የሉም እያልኩኝ ግን አይደለም!)

## ፪፡-የፍቅርና የትዳር አጣማጅ ማግኘት ጫናዎች

አንዲት የአገራችን ልጅ ከናይጀሪያዊ ጓደኛዋ ጋር በፍቅር ከነፈች ሲበዛ በጣም ትወደዋለች እሱም በጣም ይሳሳላታል፣ የተማረ ስልጡን ባለሙያ ነው። በፍቅር የወደቀችለት ልጅን አግብቶ ቤተሰብ መመሥረት ይፈልጋል፤ እሷም ትፈልጋለች ግን ያደገችበት ማኅበረሰባዊና ቤተሰባዊ ጫና በትምህርት ያገኘችውን ዕውቀት በልጦ በጭንቀት ማዕበል ውስጥ በሰመመን እየተብከነከነች መኖርን አስመረጣት። ለምን እየወደደችው፣ እያፈቀረችው የትዳር አጣማጁ መሆንን አትሻም? መልሱ ቀላል ነው የቀለም ልዩነት ብቻ ነው። የቆዳው መጥቆር፣ የከንፈሩ መተለቅ አካላዊ ገፅታውን እሷ ብትወድለትም ቤተሰቦችዋ ግን እንደማይቀበሉት ታውቃለች። ያንንም በቀጥታም በተዘዋዋሪም ነግረዋታል የመካነ አዕምሮ (ዩንቨርሲቲ) መምህሩ ወንድሟ በፌስቡክ ላይ ምስሉን አይቶ ዘራችንን ልታበላሺ ላልጠፋ ወንድ ባርያ ትይዣለሽ? በማለት አሸማቋታል (ይህ ሰው ለተማሪዎቹ ምን ይሆን የሚያስተምራቸው? የዘር፣ የቀለም ልዩነት ወንጀል በሆነበት ዘመን ያልተለወጠ ሰው በተለይ መምህር መሆኑ ጥፋቱን ያሰፋዋል!)

ሁለት አማራጮች ብቻ ነው ያላት የሥራና የፍቅር አጣምጅዋን የሕይወት አጋርዋ አድርጋ መቀጠልና ከቤተሰብ ጋር ያላትን ቁርኝት ማቆም፣ሁለተኛው ውስጧ እያነባ ውድዋን ትታ በቤተሰቦችዋ ሚዛን ውስጥ የሚገባ ባል ማግባት ሁለቱም ውሳኔዎች እጅጉን አስቸጋሪ ከባድ ውሳኔዎች ናቸው ለውቧ የአገሬ ጉብል አጣብቂኝ ውስጥ ሆና በእኽኽኽ ኑሮዋን ትገፋዋለች።

ስንቶቹ ዜጎቻችን ይሆኑ ይህን ፍራቻ ሽሽት ከሚወዱት ጋር መጣመር ፈርተው በብቸኝነት የሚማቅቁት? ቤት ይቁጠራቸው!

በተለይ ጫናው በሴት እህቶቻች ላይ ሲሆን ይበረታል።

## ፫፡-በቱሪዝም ገቢ ላይ

ጭስ አልባው ኢንዱስትሪ የሚባለው ቱሪዝም ላይ የቀለም ልዩነት (መድልኦ) እንከኖቻችን አሉታዊ ጫናችዎን ያሳርፋሉ። አንድ ጥቁር አሜሪካዊና ሌላው የአገሩን ልጅ ባለነጭ ቆዳውን በእኩል ዐይን የማየት ችግሮች አሉብን።

በካፍቴሪያዎች፣መዝናኛ ቦታዎች ውስጥ ለነጭ ሲሆን ፈገግታውና መስተንግዶው ሽርጉዱን ላስተዋለ ያስደምማል። ነጮች የተሻለ ክፍያና ጉርሻ ስለሚሰጡ ነው ብላችሁ ካሰባችሁ ተሳሳታችኋል፤ እጃቻቸው ባይፈቱም የቆዳቸው ቀለም ግን ደራጃቸውን ከፍ ያደርግላቸዋል። ያ የእነሱ ሕፀፅ አይደለም የኛ ደካማ የአስተሳሰብ ደረጃ ነው። በአንድ ወቅት በመዲናችን አዲስ አበባ ውስጥ ያደረ ኬክ በልቶ ሆዱ የታመመ ፈረንጅ ኬክ ቤቱን ከሰሰ ፍርድ ቤቱም የኬክ ቤቱን ባለቤት አስጠርቶ

*"ለምን ያደረ ኬክ ለደንበኞችህ በመሸጥ ጤናቸውን ታሳጣለህ?"* ሲባል።

*"ክቡር ዳኛ የእኔ አይደለም ጥፋቱ የአስተናጋጆቹ ነው። ያደረ ኬክ ለፈረንጅ ሲሆን አትሽጡ ብያቸው ነበር ረስተው ነው የሰጡት ትዛዜን ባለማክበር.."* በማለት ነበር ምላሹን የሰጠው። ከዚህ ምፀታዊ መልስ ጀርባ ግን መንስኤውን የምናገኝበት ፍንጭ ይሰጠናል ለነጭ ያለን የተዛባ ግንዛቤን።

ሌላም ላክልላችሁ የአሜሪካ የዐውደ-ሰብ መድረክ አዘጋጅ (ቶክሾው) ኦፕራ ዊንፍሬይ አዲስ አበባ ስትደርስ እስዋን ቸል በማለት የስዋን ጠባቂዎች ሲንከባከቡ በማየትዋ የተሰማትን ቅሬታ በገሃድ ገልፃለች። ሌላም ሌላም ብዙ ማለት ይቻላል ሁሉን ቢናገሩት ሆድ ባዶ ይቀራል!

በቆዳው ቀለም መንኳሰስ የደረሰበት ቱሪስት ተመልሶ አገራችን የመምጣት ዕድሉ ከመቀነሱም በላይ ለሌሎችም ስለ አገራችን ያለውን ተመክሮ ሲያካፍል መጥፎ ተመክሮውን ስለሆነ በቱሪዝም ላይና በመልካም ገፅታችን ላይ ጠባሳውን ያሳርፋልና ሳይውል ሳያድር መታረም አለበት። እንግዳ የማክበር ባሕላችን ለሁሉም የሰው ዘር በእኩል ያለማዳላት ሊሆን ይገባል። ማንም እራሱን የፈጠረ የለምና!

## የቀለም መድልኦው ምንጮች

### ፩፦ቤተሰብ

ብላቴናዎችን ከቤት ውስጥ ጀምሮ ወላጆች ሲያሳድጉዋቸው ከራሳቸው ልጆች ውስጥ ጠቆር ያለውን "ባሪያ"፣ ነጣ ያለውን "ቀዮ" በሚሉ ተቀፅላዎች በመጥራት የቀለም ልዩነቱን ከቤት ያስጀምሩዋቸዋል። በዚህ አስተሳሰብ ያደገን ልጅ ጥቁር ማኅበረሰብ ውስጥ ገብቶ ሲኖር የመቀላቀል ችግሮች ይኖሩበታል ራሱን የተለየ ፍጡር አድርጎ ያስባልና!

### ፪፦፡የአምልኮ ተቋማት

በአገራችን አንጋፋዎቹ የክርስትናና የእስልምና እምነቶች ውስጥ ቀደም ብሎ ለሃይማኖት ትምህርት ለቆሎ ተማሪነት፣ ለደረሳነት ቤተሰብ የመማር ዕድሉን ሲሰጥ መልከ መልካም የሆኑትን በመምረጥ ሰው ፊት ሲቆሙ ግርማቸው ይማርካል ከሚል የተሳሳተ ግንዛቤ በፈጠረው እሳቤ በመነሳት ፈጣሪ በእኩል የፈጠራቸውን ልጆች ወላጆች ሲያበላልጡ የአምልኮ ማዕከላቱም ያንን የሚያርም አሠራር ስለሌላቸው እኩልነት በመድልኦ ሲቀየር ዝምታን መርጠዋል።

### ፫፦ባሕላዊ እሴቶቻችን

የዐውድ ዓመት ክብረ በዐል ቀናት የሚገዙ የእርድ እንስሳት ሳይቀሩ በአገራችን ከስጋቸው ይልቅ የቆዳ ቀለማቸው ውበት የምርጫ መስፈርት በመሆኑ በዋጋ ላይም ከፍተኛ ልዩነት አለው። ጥቁር ወይ ዐይን ውስጥ የማይገባ ቀለም ያለው በግ ሆኖ ክብደቱ ከነጬ ወይ ከቀዩ በግ ቢበልጥም በገዢዎቹ ምርጫ ላይ የስጋው ጥራት ሳይሆን የቆዳው ቀለም ጎብር ዋጋውን ያወርደውና ተፈላጊነቱ ይቀንሳል፣ በዶሮ ሽመታው ላይ ገብስማ፣ ቀይና ነጭ ዶሮ ከሌላው በተሻለ ተፈላጊ በመሆናቸው ዋጋቸው የናረ ነው። ብዙ ብዙ ማለት ይቻላል። የቀለም ልዩነቱ በሰው ላይ ብቻ አይቆምማ ላባና ቆዳ የምንበላ ሕዝቦች እንመስላለን። በእህልና ጥራጥሬ ሰፈርም መድልዖው አለ በብረት ማዕድን የበለፀገው ጥቁር ጤፍ ከነጩ ጤፍ ዋጋው ያንሳል። ለምን ይመስላችኋል? ጣዕሙ ወይም የያዘው ንጥረ ነገር ከነጩ አንሶ አይደለም ጥቁር በመሆኑ ብቻ የልዩነቱ ሰይፍ ጥቁሩ ላይ አረፈ። ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል! እያለ የአገሬ ሰው በተሰመረ መም ላይ መጓዙን አልተወም። ትናንት ዛሬ አይደለምና ካለፉት ስህተቶች ተምረን የሚታረመውን ባሕላዊ እሴቶቻችንን አርመን የራሳችንን በማከል የተሻለ የአዲስ ትውልድ ጉዞ ማድረግ አለብን።

ወደኋላ ሄዶ በሃሳብ ከማለም፣ ቀኑ እንዳይመሽብሽ ትናንት ዛሬ አይደለም፣ (ብሏልና ሙዚቀኛው)

## ፩-ማኅበረሰባችን

ማኅበረሰባችን በነጭ ቅኝ ያልተገዛችው ኢትዮጵያ ውስጥ ቢኖሩም በሐሳብ ግን በገሃድ ሲታይ በቅኝ ከተገዙት አገሮች በላይ ጭንቅላታችን ተሰርቋል።

አንድ ጠይም ኳስ ተጫዋች ሲታይ "ኢትዮጵያዊ አይመስልም?" ስንል በአንፃሩ ጠቆር ያለ የአገራችን ተጫዋችን ግን "ከጋና ነው የመጣው?" የምንል ኢትዮጵያ የጠይም አሊያም የቀይ ዳማ አገር ብቻ እናስመስላታለን። ኢትዮጵያችን የጥቁር፣ የነጭ፣ የጠይሙ፣ የቀይዳማው የሁሉም አገር ናት። ማንኛችንም ለኢትዮጵያችን እኩል ልጆቿ ነን ይህንን መቀበል አለብን ሁላችንም ዜጎቿ። ጥቁርና ነጭ ገፅታን ሳይሆን የተዋበ አዕምሮን የማክበር ባሕል ብናዳብር ለራሳችንም ለአገራችንም ይበጃልና!

ሰላምና ፍቅሩን በብዛት ይስጣችሁ!!!

# የደሞዝ Vs. የጠብሽ* ሰሞን

አነጋገራችንን፣ አካሄዳችንን፣ አበላላችንን፣ አስተያየታችንን ባጠቃላይ የምናደርገውን ማንኛውም እንቅስቃሴ ላይ ቀጥጠኛ አስተዋፅኦ ካላቸው ነገሮች አንዱና ዋነኛው በኪሳችን ያለው ገንዘብ ዋነኛው ነው፡፡ ገንዘብ ከምናገኝባቸው አንዱ መንገድ ደግሞ ተቀጥሮ መሥራትና ወር ሲያልቅ የሠራንበትን ክፍያ/ደሞዝ ማግኘት ይገኝበታል፡፡ አብዛኛው በከተማ አካባቢ የምንኖር በዚህ መስመር ውስጥ እንገኛለን፡፡

ደሞዝ ተቀብሎ ቀጣዩን የደሞዝ ቀን እንደ ምፅአት ቀን በጉጉት የማይጠብቅ ካለ ይህ ሰው ከደሞዙ ውጪ ሌላ ተጨማሪ ገቢ አለው ወይም አንድ ቀልድ ላይ እንደሰማሁት በአስማት ነው የሚኖረው ማለት ነው፡፡ ደሞዛችን እዛው እንዳለ ወይም በተወሰነ ጭማሪ… ብቻ ኑሮ ግን በብዙ እጥፍ ጨምሮ መኖር መቻላችን እውነትም አስማተኛ ያስብላል፡፡ እንደየደረጃው ይለያይ ይሆናል እንጂ አብዛኛው ደሞዝተኛ ደሞዝ ከተቀበለ በኋላ ካሉት የተወሰኑ ቀናት ውጪ ለመጪው የደሞዝ ቀን ስንት ቀን እንደቀረው በመቁጠር፤ ቀሪውን ጊዜ በብድር እንዴት እንደሚያሳልፍ በማውጠንጠን፤ የሰቀቀን ኑሮ መኖሩን የተለማመድነው ይመስላል፡፡

የደሞዝ ሰሞንና የጠብሽ ሰሞን እንደየሰው ይለያያል፡፡ በአብዛኛው ደሞዝ ከተቀበሉ ከ10-15ኛው ቀን በኋላ ሰሞነ ጠብሽ ይገባል፡፡ ደሞዝ የተቀበሉ እለትም ደሞዟ ብድር ብቻ ከፍላ የዕለቱለት ጠብሽ የሚጀምርበት አጋጣሚም አለ፡፡ የበዓል ወቅቶች እና ጳጉሜ ወር "የጠብሽ" ወቅትን ከሚፋጥኑ/ከሚያረዝሙ ምክንያቶች ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ የጳጉሜ ወር ግን ለምን ደሞዝ እንደሌላት ሁሌም ይገርመኛል፡፡ በዛ ላይ የአዲስ ዓመት ወጪ ተጨምሮበት አስቡት፡፡

## የደሞዝ ሰሞን 1

የደሞዝ ሰሞንን አስታከው የሚመጡ ወጪዎች ብዛታቸው አይጣል ነው፡፡ በመሥሪያ ቤት ለተለያዩ ጉዳዮች የሚሰበሰቡ መዋጮዎች፣ በየመሥሪያ ቤቱ እና ካፌው እየዞሩ እርዳታ የሚጠይቁ እና የመንገድ ላይ ለማኞች የሚበዙት በዚህ በደሞዝ ወቅት ነው፡፡ መንገድ ላይ የተለያዩ ዕቃዎችን ለሽያጭ ይዘው የሚወጡ ነጋዴዎችም ከሌላው ቀን በተለየ መንገዱን ሞልተው የምናያቸውን ደሞዝተኛን የሚያባብል እና የሚያግባባ ቃላት በመጠቀም ሸቀጦቻቸውን እንድንገዛ ሲታትሩ የሚታዩት በዚሁ በደሞዝ ወቅት ነው፡፡ እኛም አዎንታዊ ምላሻችንን አንነፍጋቸውም፡፡

## የደሞዝ ሰሞን 2

ከቤተሰብ፣ ጓደኛ እና በአካባቢያችን ከምናገኛቸው ሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ይጠብቃል፡፡ ሰላምተኞች፣ ደውሎ ጠያቂ፣ አስታዋሽ እና እንገናኝ ባዮች እና አሰባሳቢዎች እኛ ነን፡፡ ከፋይ ወይም ከፋይ ለመሆን ልባዊ የሆነ ተነሳሽነት እናሳያለን፡፡ ሲያወሩን በጥሞና እናዳምጣለን (የተሰበሰበ ቀልብ ይኖረናል)፡፡ ድንገት የሚያውቁት ሰው ካለ በማለት አካባቢን እያስተዋሉ መሄድ፡፡ (ምክንያቱም ገንዘብ በኪስ አለ፤ ሻይ ቡና እንበል ቢባሉ ቢያንስ ወጪን ተጋርቶ ለመክፈል ቢበዛ ደግሞ ለመጋበዝ ይችላሉ፡፡)

## የደሞዝ ሰሞን 3

የሌለን ነገር ግን ሊኖረን ይገባል የምንለው ነገር ይበዛል፡፡ በተለይ ልብስ፣ ጫማ፣ መጽሐፍ፣ የቤት ቁሳቁስ…እና የመሳሰሉት ከዝርዝራችን ውስጥ የመካተት እድላቸው ሰፊ ነው፡፡ በመንገዳችን ያገኘነው መገበያያ ቦታ ወይም ሥራዬ ብለን እገበያው ቦታ በመሄድ የምንፈልገው ነገር እንዳለ እናያለን፡፡ እናማርጣለን፡፡ ልንገዛም ላንገዛም እንችላለን ነገር ግን ለማየትም እንኳን ቢሆን የምንሄደው የደሞዝ ሰሞን ነው፡፡ ይህ አምሮታችን የበዛ ከሆነና ያማረንን ሁሉ የምንገዛ ከሆነ የጠብሽ ሰሞንን ያለጊዜው እንዲመጣ ያፋጥናል፡፡

## የደሞዝ ሰሞን 4

ለቀን ወጪያችን መጠንቀቅ አይታይብንም፡፡ የእግር መንገድ እንጠላለን፡፡ አውቶብስ፣ ሃይገር ባስና ሌሎች ታሪፋቸው ዝቅተኛ የሆኑ ትራንስፖርቶችን አንጠቀምም፡፡ የምንመገብበት ምግብ ቤት ከሌላው ቀን ደረጃው ከፍ ያለ ይሆናል፤ ምሳ ከቤት ቋጥሮ መምጣት ይረሳና የምግብ ቤቶች ተጠቃሚ እንሆናለን፡፡

## የደሞዝ ሰሞን --ሌሎች

በየሳምንቱ የሚወጡ ትኩረታችን የሚስቡ ጋዜጦችን እና መፅሄቶችን ገዝቶ ማንበብ፡፡ የሚያዝናንን ነገር ለምሳሌ እንደ ፊልም እና ቲያትር ማዘውተር፡፡ መጠጥ፣ ሲጋራ፣ ጫት እና የመሳሰሉ ሱሶችን በምርጫችን ማስተናገድ፡፡ እራስን ማዝናናት፡፡ ‹‹ቺክ›› ለመጥበስ ወይም ፍቅረኛን ለማግኘት ማቀድ እና ተግባራዊ ማድረግ፡፡ በዚሁ ወደጠብሽ ሰሞን እንሽጋገር…

## የጠብሽ ሰሞን 1

ደሞዝተኛ ደሞዙን ጨርሶ ቀጣዩ ደሞዙ እስከሚደርስ ያለውን ጊዜ ለማሳለፍ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይጠበቅበታል፡፡ ከዛ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ተበድሮ ያን የጠብሽ ጊዜ በቁጠባና በማብቃቃት ጥበብ ማሳለፍ ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ደሞዝተኛ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አበዳሪዎች እንዲኖሩት ከሚሠራው ሥራ ባልተናነሰ ተግቶ መሥራት አለበት፡፡ አበዳሪዎች ቋሚ ወይም የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ መ/ቤቱ የገንዘብ ሰብሳቢ ካለውና ገንዘብ ሰብሳቢ የሆነው ሰው ወይም ጓደኛ ከሆኑ  ብዙም ሳይጨናነቁ ብድር በቀላል የማግኘት እድላቸው ሰፊ ነው፡፡ ‹አበዳሪ ሲያበድር የሰጠ ይመስለዋል› የምትለዋ አባባልም በተበዳሪ የተፈጠረችና በጠብሽ ወቅት በአበዳሪና ተበዳሪ ግንኙነት ተደጋግማ የምትጠቀስ ናት፡፡

## የጠብሽ ሰሞን 2

ከጓደኛ ጋር ያለንን ግንኙነት እንቀንሳለን፣ ለወሳኝ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ስልክ አለመደወልን እንመርጣለን ወይም ሚስድ ኮል እናደርጋለን፣ ጓደኞችን ለማግኘት ብዙም ደስተኞች አንሆንም፣ ከማንኛውም ሰው ጋር ባንገናኝ እንመርጣለን፣ ብዙ ጊዜ ስልካችንን ልናጠፋ እንችላለን፣ ሰዎች ሲያወሩን ቀልባችንን ሰብስበን አናዳምጥም፣ በራስ የመተማመን መንፈሳችን ይቀንሳል፡፡

## የጠብሽ ሰሞን 3

በጣም አስቸኳይ እና በእለቱ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር የምንገዛው አዲስ ነገር አይኖርም፡፡ አዲስ የሚገዙ ነገሮችን አይናችን እንዳያይ መከልከል ባንችልም ለአእምሮአችን ግን ያየነው አዲስ ነገር እንዴት እንደማያስፈልገን፤ ባለን ነገር መቆየት እንደምንችል፣ ከለው ሰው ተውሰን መጠቀም እንደምንችል እና የመሳሰሉ ምክንያቶችን እንነግረዋለን፡፡

## የጠብሽ ሰሞን 4

ወጪያችንን ለመቀነስ ከፍተኛ ጥረት እናደርጋለን፡፡ ዋጋው ረከስ ያለ ቤት ተመርጦ መመገብ ይጀመራል፡፡ አውቶብስ፣ ሃይገር ባስና የመሳሰሉትን ዝቅተኛ ታሪፍ ያላቸውን የትራንስፖርት መንገዶችን እንጠቀማለን፡፡ የተወሰነ መንገድ በእግር ልንጓዝ እንችላለን፡፡ ምሳ ቋጥረን መምጣታችንን እንጀምራለን፡፡ እነዚህን ስናደርግ ግን ጠብሽ ሰሞን ላይ በመሆናችን እንዳልሆነ ለማሳወቅ የተለያዩ ምክንያቶችን ስንሰጥ ይሰማል፡፡ ለምሳሌ የምግብ ቤቱን፡- ‹ምግቡ እኮ ያው ነው ዋጋው ብቻ ነው፡፡ የዚ የዚ….›፡፡ የትራንስፖርቱን፡- ‹ከታክሲ እኮ ቀድሞ የሚደርሰው ባስ ነው፡፡ በዛ ላይ ቀጥታ ሰፈሬ ያደርሰኛል…›፡፡ በእግር መጓዛችንን ደግሞ ለጤንነት ወይም ክብደት ለመቀነስ ጥሩ ነው ብለን እንደሆነ እንናገራለን፡፡ ምሳ ቋጥረን ስንመጣ ‹የሆቴል ቤት ምግብ እኮ ጥሩ አይደለም፡፡ በምን እንደሚሠሩት አይታወቅም፡፡ ምንም ቢሆን እቤት የተሠራ ይሻላል፡፡….› እና የመሳሰሉትን ምክንያቶች እንሰጣለን እንጂ የተበደርናትን ብር አብቃቅተን እስከ ደሞዝ ለመድረስ የምናደርገው እንደሆነ አንናገርም፡፡

## የጠብሽ ሰሞን--ሌሎች

ጋዜጣ እና መጽሔት ገዝተን እናነብ የነበርን ወደ ኪራይ እንገባለን፡፡  የገዛ ወይም የተከራየ ሰው ተውሰን ልናነብም እንችላለን፡፡ ፊልም እና ቲያትር ማየት አያምረንም፡፡ መዝናናት አይታሰብም፡፡ የሱስ ነገር ስለማይሆንልን ተጋባዥ የምንሆንበትን አጋጣሚ እናመቻቻለን፡፡ በተወሰነም ፍላጎታችንን እንገድባለን፡፡ ፍቅረኛን ለማግኘትና ‹‹ቺክ›› ለመጥበስ ይህን ወቅት አንመርጠውም፡፡

እነዚህን ብቻ ሳይሆን ብዙ ነገሮችን እየሆንን እና እያደረግን፤ ሁለቱ ወቅቶች እየተፈራረቁ ሲገዙን ወሩ ያልቃል፡፡ በዚህ ተመሳሳይ ዑደትም ቀናት ወራትን፤ ወራት ዓመታትን እየሆኑ ጊዜዎች ያልፋሉ፡፡

በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በሁለቱ ወቅቶች የሚኖረን አስተሳሰብ የተለያየ ነው፡፡ በተለይ የገንዘብ አወጣጥ መርሓችን በሁለቱ ወቅቶች ፍፁም አይገናኝም፡፡ የጠብሽ ሰሞን በምንከተለው የገንዘብ አወጣጥ ቀመር እየተመራን ሙሉ ወሩን ማሳለፍ ብንችል የት በደረስን ብዬ አስብና እሱን ለማሰብ ግን የጠብሽ ሰሞን ጭንቅላት እንደሚጠይቅ ትዝ ሲለኝ እተወዋለሁ፡፡ ልክ ይህን ጽሑፍ ለጻፈፍ የጠብሽ ሰሞን ጭንቅላት እንደጠየቀኝ ሁሉ ማለት ነው፡፡

ረጅም እድሜ ለአበዳሪዎቻችን!

-----

* ጠብሽ - በኢ-መደበኛ (‹‹የአራዳ››) አነጋገር ዘይቤ ባዶ ኪስ ወይም የችግር ሁኔታን ይገልጻል፡፡

# ከተሜውን ናፍቆት

መንገድ ላይ ነዎት፤ አንድ ከተማን ለቀው ወደ ሌላ ከተማ እየተጓዙ ነው፤ ቢጓዙ ቢጓዙ ቀጥለው የሚጠባበቁት ከተማ አልደረሱም፤ ገጠሩ ረዝሞብዎታል፤ ‹እንዴ ይህ ሀገር ገጠር ብቻ ነው እንዴ?› ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ። እባኮትን ዝም ብለው ይጓዙ ገና ብዙ የገጠር መንገድ ይቀርዎታል። ትንሽ ከተማ ነገር ያገኙ መስሎዎ ፈገግ ሊሉ ይችላሉ፤ አይሞኙ ፈገግታዎት ከከንፈርዎት ዘሎ፤ ፊትዎትን ከማዳረሱ በፊት ያች እያለፉትት ያለችው ከተማ ከመቅፅበት ከእይታዎት ተሰውራ በድጋሚ ከማያልቀው ገጠር ተቀላቅለዋል፡ እንግዲህ መበርታት ነው።

ፍጡራን በዓለም ሲኖሩ መሰላቸውን ፈልገው እና ተፈቃቅደው አንድ ላይ መኖራቸው ሀቅ ነው። ሰው ልጅ ባህሪም ብቻ አይደለም። ነገር ግን የሰው ልጆች ይሄን ቁርኝት እና አብሮ መኖር አጠናክረው እና የበለጠ አጥብቀው በአንድ አብረው ይኖሩበታል። ከተሞችም የዚህ ግንኙነት ቀጥተኛ ውጤቶች ናቸው። በግንኙነቱ የሚፈጠሩት ከተሞች ሲመሰረቱ እና ሲወድሙ እንደገና ሲመሰረቱ፤ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ2008 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለመጀመሪያ ጊዜ ከዓለም ሕዝብ ከግማሽ የሚበልጠው በከተማ እንደሚኖር አወጀ። ከተሜው ዓለምን ከገጠሬው ተረከበ።

## ከተሜ (Urbanism)

የዓለም እድገት እየጨመረ በመጣ ቁጥር በከተሞች የሚኖረው ሕዝብ ቁጥርም እየጨመረ እንደሚመጣ፤ መረጃዎቹን ተመልክቶ መገንዘብ ይቻላል። ይሄም ከተሜነትን ከእድገት ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ ማስረጃ ነው። ብዙ የከተማ ነዋሪ በተፈጠረ ቁጥር የዛች ሀገር እድገት በተሻለ መስመር ላይ ነው እንደማለት። Bert Hoselitz, የተባሉ ምሁር 'The Role of Cities in the Economic Growth of Underdeveloped Countries' ባሉት መፅሃፋቸው:

*"Cities are sources of innovation, loci of and providers of motivation for change, and centers where a peasant may go to remove himself from the constricting political organization and static economy of the countryside."*

ይላሉ። ከተሞች የሀሳብ መፍለቂያ፣ የፈጠራ መመንጫ እንደሆኑ እና ለገጠሬውም ገጠር ከተሰኘው ‹እስር ቤ›ት ወጥቶ ወደ ‹ነፃነት ምድር› የሚገባበት በር እንደሆነ ይገልፃሉ። ይሄም ስልጣኔ ከከተማ እንጅ ከገጠር አትቀዳም የሚለውን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው። ከተሜ ሰፊውን ዓለም በማወቁ ተጠቃሚነቱ ይጎላል፤ ዓለምንም ለመከተል ያተጋዋል።

## ገጠሬ

በሌላ በኩል ዓለምን ለረጅም ዘመናት ነግሶባት የኖረው የገጠሬነት ይትበሃል ነበር። በገጠሬ ባህል ውስጥ ጎልቶ የሚታየው የተበተነ አኗኗር፣ ለለውጥ ድንጉጥ መሆን (Change Resistant)፣ የንፅረተ አለም (World Outlook) መጥበብ ዋነኛዎቹ እንደሆኑ ባለሙያዎች ያስረዳሉ። የኑው መበተንም ሀሳብ በጋራ እንዳይብላላ እና የሀሳብ ፍጭቶች (Thesis Vs. Antithesis) አዲስ ሀሳብ (Synthesis) እንዳይፈጥሩ ያግዳቸዋል። ለውጥን መፍራቱ ደግሞ በትናንት በሬ ለማረስ መሻትን፣ ዛሬን መርሳትን እንዲሁም ለነገ ባዕድ መሆንን ይፈጥርበታል ለገጠሬው። በሌላ በኩል ደግሞ የገጠሬው ዓለም ከአራቱ ጋራዎች አለመዝለሉ የታፈነ እና ሌላውን ዓለም የማያውቅ፤ ራሱንም ከሌላው ዓለም ነባራዊ ሁኔታ ጋር የማያዋህድ ‹ደሴት› ያደርገዋል። አዎ ሕይወት በገጠር በባህር ተከበበች ደሴት ላይ ያለች ሚጢጢ ነገር ነች። ይህ ማለት ግን ገጠሬ ሁሉ-ጭፍን እና በግምት የሚኖር ነው ለማለት አይደለም።

## ገጠሬው ከተማን ሲሻ

በተለያዩ መንገዶች ገጠሬው ወደ ከተማ መግባቱ አይቀርም። የስበት ሀይሉ (Center of Gravity) ከተማ ነውና ገጠሬው በከተማ ሀሳብ ይሳባል፤ ከተማም ይገባል፤ ራሱንም በከተሜ ሀሳብ ለመቅረፅ ይጥራል ከተሜም ይሆናል። ገጠሬው ከተሜ ሲሆን ምን ይፈጠራል? ስንል May Diaz and Jack Potter የተባሉ ፀሃፍት 'Introduction: The Social Life of Peasants', in Peasant Society ባሉት መፅሃፋቸው ላይ ‹‹የመንግስት ቁጥጥር ይበጣጠስል፤ መንደሩ ግን ይኖራል›› - *"The state apparatus could disappear overnight and an*

*individual village could still manage to survive"* ይሉናል፡፡ ይህም ማለት ገጠሬው በከተማ መሻቱ ‹ግለሰቡን ሰው› ከትቢያ ፈልጎ የማውጣትን መላ ይማራል፤ ዓለምን ያውቃል፤ እንደገናም ዓለምን ያሰፋል፡፡

## ገጠር እና ከተማ በኢትዮጵያ

የከተማ አመሰራረት እና እድገት በቀዳሚዎቹ ዘመናት በኢትዮጵያም የተለየ ታሪክ አልነበረውም፡፡ ከአክሱም ስልጣኔ መክሰም በኋላ በሀገሪቱ ከተማ የሚባለው ፅንሰ ሀሳብ ጨርሶ ጠፍቶ ነበር፤ የነገስታቱ ግዛትም እጅግ የጠበበ እና ከመንደር ያልዘለለ እንደሆነ ታሪክ ያስረዳል፡፡ በጦርነትም የነገስታቱ መቀመጫ የሆኑትን ‹ዓምባዎች› ሰብሮ የገባ ሀይል ስልጣኑን ለመያዝ ይቀልለት ነበር፤ ድሉንም ዓምባዎቹን ሙሉ ለሙሉ በማውደም ይገልፅ ነበር፡፡ ይሄም ዓምባዎቹ ጎልብተው ወደከተማነት የሚሸጋገሩበትን እድል በእጅጉ አቀጭጮታል፡፡ በነገስታቱ ወንዝን እና ተራራን መሰረት በማድረግ የሚመሰረቱት የመናገሻ ‹ከተማዎችም› ለአጭር ጊዜ የሚቆዩ እና እዚህ ግባ ሊባሉ የሚችሉ አልነበሩም፡፡ በዚህም ምክንያት ከተማና ከተሜነት ያልነበረ፤ ብቅ ሲልም በነገስታቱ ግብግብ ‹‹ጨርሶ አጠፋ› በሚባል ሁኔታ አመድ ሲሆኑ ነበር፡፡ ለዚህም ነው *"During the past millennium in Ethiopia, the state and not the city has been 'the decisive criterion of civilization"* ሲሉ Eric Wolf የሚናገሩት፡፡

ይሄም ማለት ኢትዮጵያዊያን በገጠር መኖራቸው፤ በከተማ የሚገኘውን ጥቅም ከማጣታቸውም በተጨማሪ የመንግስት ‹ሎሌ› ሁነው ኖረዋል እንደማለት ነው፡፡ መንግስት ‹ነጭ-ነግ፤ጥቁር ወተት; ውለድ እያለ ‹እርፍ አሽክሞ-ጅራፍ አንግቶ› ኢትዮጵያን ሲሰራና ሲያፈርስ ነበር እንደማለት፡፡

## ከፊውዳሉ ወደ ላብ አደሩ ወደ አርሶ አደሩ

በፊውዳላዊ ስርዓቱ ወቅት ገጠሬው እንደ ገባር ለመኳንንቱ ተደልድሎ በጉልበቱ እና በላቡ የመሳፍንቱ ሎሌ ሆኖ ኖረ፡፡ ለምን እረገጣለሁ? ከማለት ይልቅ ‹ግብር በዛብኝ› የሚሉ ትንሽ አመፆችን በየቦታው አስነስቶ ከሸፈ፡፡ ሙሉ የመብት ጥበቃ ይደረግልኝ ሊል አልቻለም፤ ገጠሬ ነውና፡፡ ይልቁንስ ተማሪዎች ‹መሬት ለአራሹ፣ ለላብ አፍሳሹ› ብለው የገጠሬው መብት ይጠበቅ ዘንድ ተነሱ እናም ፊውዳላዊውን ስርዓት ገረሰሱት፤ በላባደሩ የሚመራ ከተማ-ተኮል አብዮትም ታወጀ፤ ወታደሩ በመሃል ገብቶ ነገሩን ሁሉ አፈረሰው፤ ህልሙን አደፈረሰው፤ ለስሙ ግን እኔም ለላባደሩ ነኝ ብሎ ገጠሬውን ገሸሽ ያደረገ ስርዓትም ዘረጋ፡፡ገጠሬውን ለማዘመን ወታደራዊው መንግስት በሰፈራ ፕሮግራሙ፣ አማካኝነት ትናንሽ አዳጊ መንደሮችን ለመፍጠር ሙከራ አደረገ - አልተሳካም፡፡ ነገር ግን የገጠሬው ቁጥር በፊውዳሉ ስርዓት ጊዜ ከነበረው በትንሹ ሊቀነስ ችሎ ነበር፡፡

በወታደራዊው መንግስት የተተካው በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኢሕአዴግ) አርሶ/አርብቶ-አደሩን በሌላ ቋንቋ ገጠሬውን መሰረት ያደረገ ዲሞክራሲያዊት እና የበለፀገች ኢትዮጵያን እፈጥራለሁ በማለት ግብርና መር የኢንደስትሪ ስትራቴጂን ነደፈ፤ ስንቶች የከተማ ትግል ብለው እንደወጡ ሲቀሩ እኔ አርሶ አደሩ ዛፍ ፍሬ አፈራሁ አለ፡፡ ገጠሬውም ሀገሪቱን በአጠቃላይ ፖለቲካል ኢኮኖሚውን በተለይ ለመምራት በትረ - ሙሴውን ጨበጠ፡፡

## ገጠሬው ይመራልን?

ከዛሬ 50 ዓመት በፊት ገደማ (በ1959 ዓ.ም) በማእከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን በወጣው መረጃ መሰረት የዛሬዋን ኤርትራ ጨምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ 248 ከተሞች የነበሩ ሲሆን የከተማው ሕዝብ ብዛትም ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ሕዝብ 8 በመቶውን ብቻ ይይዝ ነበር፡፡ በ2004 ዓ.ም በወጣው የማእከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን መረጃ መሰረት ደግሞ ደግሞ በመላ ሀገሪቱ 973 ከተሞች ያሉ ሲሆን ከአጠቃላይ ሕዝቡም 17 በመቶ የሚሆነው በነዚህ ከተሞች ውስጥ ይኖራል፡፡ ይህም ማለት ቀሪው 83 በመቶው የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁንም ገጠሬ ነው ማለት ነው፡፡

ኢሕአዴግ ስልጣን በያዘበት ወቅት ከነበረው 86 በመቶ የገጠር ነዋሪ በሁለት አስርት ዓመታት ውስጥ በ3 በመቶ ብቻ ነው የተቀነሰው፡፡ በአብዛኛው የዓለማችን ክፍሎች የሚኖሩ ገጠሬዎች በአሁኑ ወቅት ድህረ-ገጠሬ (Post-Peasant)፤ ማለትም ከከተማ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት የሚፈጥሩ ነዋሪዎች ደረጃ ላይ እንደ ደረሱ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይሄም ማለት በቀጣይ ወደ ከተሜነት ራሳቸውን ለመቀየር አንድ እርምጃ ወደፊት ሂደዋል ማለት

ነው፡፡ መንግስት የኢትዮጵያ ገጠሬ ይሄን ደረጃ መውጣት ጀምሯል ቢልም፤ በ20 ዓመታት ከታየው የከተሜነት ጉዞ አንፃር ተመልክተው ‹አይ አይመስለንም› የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡
Frederick Gamst ስለ ኢትዮጵያ የከተማ-ገጠር ተወስኦ ሲያወሱ:

*"Lack of urbanism is found to be hindering the rate of modernization in Ethiopia where nonliterate [sic] people are still gradually making the transition into peasants."* በማለት ነው፡፡ የከተሜነት አለማደግ ኢትዮጵያን ከዘመናዊነት ጉዞዋ አቅቧታል፤ ያልተማረው ሕብረተሰብም ገጠሬ እየሆነ ነው እያሉ ነው፡፡

መንግስት በበኩሉ በተደጋጋሚ እንደሚገልፀው ‹መሰረቴ፤ ሰፊው አርሶ አደር ነው› ይላል፡፡ ‹የዲሞክራሲ ተቋማትን እና የልማት አውታሮችን የምዘረጋው ይሄን አርሶአደር መሰረት አድርጌ ነውም› ይላል፡፡ በአወዛጋቢ የምርጫ ወቅት እንኳን ‹አመኔታ በገጠሬው ላይ ነው› ይላል፡፡ ነገር ግን ገጠሬነት ለሀገር እድገት ‹እዳ› ነው ይሉታል ምሁራን በበኩላቸው፡፡ ‹‹የተበተነ፣ ለውጥ-ጠል እና ዓለመ-ጠባቡን ገጠሬ እንደ መከታ መያዝ አይገባም፤ ይልቁንም ገጠሬውን አዘምኖ ከተሜ ማድረግ ነው ድሉ›› ይላሉ እነዚህ አካላት፡፡

ከላይ የጠቀስናቸው Frederick Gamst 'Peasantries and Elites without Urbanism: The Civilization of Ethiopia' ባሉት ፅሁፋቸው ላይ የከተሜነት አለማደግን ጠቅሰው የሚያቀርቡትን ሂስ እንደገና እንጥቀስ፡

*"Lack of urbanism prevents in Ethiopia the beginnings of a concentration of a pool of laborers who are without bonds to the land. Such a labor pool is necessary for industrialization, and thus for the ensuing general modernization of all of the ways of life in Ethiopia. Lack of urbanism will […] insulate Ethiopia and its peasants from fundamental changes in traditional ways of life."*
መንግስት እንደሚለው ጉዟችን ወደ ኢንደስትሪ ከሆነ መግስት በፍቅር የወደቀለት ገጠሬው ትልቅ መሰናክል ነው ማለት ነው፡፡ መንግስት በአንድ በኩል የኢንደስትሪ ልማትን (Industrialization) አመጣለሁ ብሎ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ‹ገጠሬውን አትንኩብኝ› እያለ መንታ መንገድ ላይ ቆሞል፤ አንድ እግሩን በግራ፣ አንድ እግሩን በቀኝ በኩልም እየለጠጠ ይገኛል፡፡ መጨረሻውስ? የለውጥ ፊር ቀዳጁን ከተሜስ መች ይቀርበዋል? መቸስ ገጠሬውን ከተሜ ያደርገዋል? ነው ጥያቄው፡፡

# አንድ እሁድን በማረሚያ ቤት…

ትላንት እሁድ (ጥር 12/2005) የርዕዮት ዓለሙ ወዳጆች ልደቷን አስመልክተው እንድንጠይቃት በፌስቡክ ሁሉንም ሰው ጋብዘው ነበር፡፡ እኛም ሰብሰብ ብለን ለመሄድ ተቀጣጠርን፤ ሆኖም የእሷ ልደት ላይ ከመገኘታችን በፊት ውብሸት ታዬን ለመጠየቅ ወስነን ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ ሳረስ ተሰባሰብን፡፡ ውብሸት የታሰረው ቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ነው፡፡ ቂሊንጦ የሚገኘው አቃቂ ድልድይ አካባቢ ከሚገኘው የጥሩነሽ ሆስፒታል፣ በፒስታ አጭር የታክሲ/ባጃጅ/ጋሪ መንገድ ከተጓዙ በኋላ ነው፡፡

ቂሊንጦ ከቃሊቲ ማረሚያ ቀለል ያለ መንፈስ አለው፡፡ እርግጥ ነው ቀለል የማለቱ ነገር የሚጀምረው መግቢያው ላይ ካለው የማረሚያ ቤቱ ፖሊሶች አቀባበል ነው፡፡ ከዚህ በፊት ቃሊቲ ስንመላለስ ባላየነው መልኩ የታራሚዎቹን ጠያቂዎች በአገልግሎቶቻቸው ላይ አወያይተዋል፡፡ አወያዩ ከዚህ በፊት ይደረግ የነበረው ውይይት ለአጭር ጊዜ ተቋርጦ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን በወር አንዴም ቢሆን እንደሚቀጥል በመናገር ጀምሮ ጎብኚዎች እየገጠሟቸው ያሉ ችግሮች ካሉ ጠየቀ፡፡ ሆኖም አንዳንድ ሰዎች እጃቸውን እያወጡ ከማመስገናቸው በቀር የጎላ ይሄ ነው የሚባል ችግር እንዳልገጠማቸው ተናገሩ፤ ይህንንም ከገባን በኋላ ውብሸት ሁሉም ነገር ጥሩ እንደሆነ አረጋግጦልናል፡፡ ይህ የቂሊንጦ ማረሚያ ቤት አሠራር ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ርዕዮትስ ስንጠይቅ ከሚገጥመን የፖሊሶች ማመነጫጨቅ፣ ላለማስገባት ሰበብ መፈለግ እና ከመሳሰሉት የሚያበሳጩ እና ተስፋ የሚያቀርጡ ተግባራት ጋር ሲተያይ ፍፁም ተቃራኒ ነው፡፡ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት የቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ልምድን ቢወስድ መልካም ነው፡፡

ከውብሸት ጋር የነበረን ቆይታ በሰዓት የተገደበ አልነበረም፤ (ይህ ቃሊቲ ቅዳሜ እና እሁድ ርዕዮትን ለመጠየቅ ስንገባ ከተሰጠን 30 ደቂቃ አንጻር ሲታይ ዓለም ነበር፡፡) ውብሸት በመልካም ጥንካሬ ውስጥ ነው፡፡ ንግግሩ ትህትና የተሞላበት ነበር፡፡ ከገባ ጀምሮ እስካሁን ስላለው ብዙ ጉዳዮች አጫወተን፡፡ ማረሚያ ቤቱ ውስጥ ካሉት ሰዎች ውስጥ በግምት 30 በመቶ የሚሆኑት በፖለቲካ ሰበብ እንደታሰሩ እና ከነዚህም ውስጥ አብዛኛዎቹ ከኦነግጋ ንክኪ አላችሁ በሚል እንደተፈረደባቸው አጫውቶናል፡፡ አንዳንዶቹ እስረኞች በጣም አፍላ ወጣቶች ከመሆናቸው የተነሳ ቢያጠፉ እንኳን መክሮ ከመልቀቅ በላይ እርምጃ እንደማይገባቸው አጫወተን፡፡ ውብሸት በአሁኑ ጊዜ ጠዋት ጠዋት በማረሚያ ቤት ውስጥ በሚገኘው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያስተምር ሲሆን በተጨማሪም የአረብኛ ቋንቋ ስልጠናም ለታራሚዎቹ በመስጠት ጊዜውን በአግባቡ እንደሚያሳልፍም ነግሮናል፡፡

ውብሸትን በአገር አሸባሪነት በሕግ ከመፈረጁ በተቃራኒው የዋህ እና ቅን ልብ ያለው መሆኑን ሲሰጠን ከነበሩ ማብራሪያዎቹ ለመረዳት አልከበደንም፡፡ በግቢው ውስጥ ሳይብረሪ እንዳለ ስንጠይቀው የሰጠን ምላሽ ያልጠበቅነው ስለነበረ አስገርሞናል፡፡ ላይብረሪ እንዳለ ነገር ግን በቂ መጽሐፍት እንደሌሉት እና ይህን ችግር ለመቅረፍ ከዓለም አቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ድርጅት (CPJ) ጋር ተጻጽፌ የተወሰነ መጻሕፍት በእርዳታ ሳስመጣ የሚል ሐሳብ አቅርቦላቸው እንደነበረ ነገረን፡፡

ሌላው ከጓደኞቹ ወይም ከቤተሰቦቹ የሚገቡለትን መጽሐፍት በተመለከተ የሚመጣለት መጽሐፍ ሁሉ እንደማይገባለት፤ የተመረጡ መጽሐፍቶች ብቻ እንደሚደርሰው ነግሮናል፡፡ ሌላው ቀርቶ ‹‹የሎጥ ሽሽት›› የሚል ልብወለድ መጥቶለት እሱጋ ሳይደርስ መመለሱን አጨዋውቶናል፡፡ ይህ ችግር ርዕዮት ጋርም ያለ ችግር ነው፡፡ መጽሐፍ ለሷ እንዲሰጥ የሚመለከተው ክፍል ገብቶ ይዘቱ ተመርምሮ ነው እንዲገባላት የሚደረገው፡፡ ይህም በጣም ረጅም ጊዜ እንደሚፈጅ እና በአብዛኛውም መጽሐፍቹ እንደማይደርሷት በአንድ ወቅት ነግራናለች፡፡

ውብሸት ከፍርድ ሒደቱ ጋር በተያያዘ የቀረበበትን ውንጀላ ሲያወራልን በምስክርነት የቀረቡትን የስልክ ንግግሮቹን ሁሉ እራሱ ያደረጋቸው ቢሆንም አተረጓጎማቸው ግን እንዳስወነጀለው ነግሮናል፡፡ ለምሳሌ እርሱ ሚዜ ለመሆን በስልክ ስለሱፍ እና ሸሚዝ ያወራቸው ንግግሮች ተቀርፀው የኮድ ንግግር ናቸው ተብለው ለምስክርነት እንደቀረቡበትም ፊቱ ላይ በግልጽ በሚነበብ ይቅርታ አጫውቶናል፡፡ በሌላ በኩል በእሱ መዝገብ ከገቡ አንዳንድ ታራሚዎች ጋር ሆነው ያስገቡት የይቅርታ ደብዳቤ ስዊዲኖቹ ጋዜጠኞች ከማስገባታቸው አንድ ወር ቀደም ብለው ያስገቡ ቢሆንም፣ ስዊዲኖቹ ከተፈቱ ከአምስት ወር በኋላም እነውብሸት አለመፈታታቸው ‹‹ሁለት ዓይነት አሠራር አለ እንዴ?›› የሚያስብል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከውብሸት መልስ ወደቃሊቲ አመራን፣ አንድ ታክሲ ስላላገኘን ተከፋፍለን ነበር የተጓዝነው፡፡ ከፊሎቻችን አብዛኛዎቹ የታራሚ ጎብኚዎች ከሚመጡበት በተቃራኒው መንገድ (ነገር ግን ወደተመሳሳይ በር) በመምጣታችን

በሩ ጋር ከደረስን በኋላ በሌላ በኩል ዞረን እንድንመጣ ከጠባቂዎቹ አንዱ ነገረን፡፡ እንደተነገረን ለማድረግ ቢያንስ ከ15 ደቂቃ በላይ ዙሪያ ጥምጥም ለመጓዝ ተገደድን፡፡ ዞረን ስንመጣ ገና ወደዋናው በር ለመድረስ በግምት ከመቶ ሜትር በላይ ሲቀረን መታወቂያ እያሳያን ወደበሩ እንቀርባለን፣ በሩ.ጋርም መታወቂያ እናሳይ እና እንገባለን፣ ከገባንም በኋላ ሌሎቹ ጎብኚዎች እስኪወጡ ጠብቀን በፖለቲካ ነክ ጉዳይ የታሰሩ ሰዎች በሚጠየቁበት ሰዓት ወደውስጥ ለመዝለቅ ጓዛችንን (ስልክ፣ ቁልፍ፣ ፍላሽዲስክ.. የመሳሰሉትን) መታወቂያ አሳይተን ወደውስጥ እንዘልቃለን፤ (ይህ የዘወትር የጉብኝቱ ቅደም ተከተል ነው፡፡)

ቃሊቲ ጊቢ ውስጥ ስንገባ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምን፣ ዶ/ር ያዕቆብን ጨምሮ የርዕዮት እናት፣ አባት፣ እህት፣ ወንድም እና ጓደኞቿን ጨምሮ ሌሎችም በርካቶች ቀድመውን ደርሰው ነበር፡፡ ገና ሰዓቱ እስከሚደርስ ቁጭ ባልንበት ስሜታችን መጋጋል ጀመረ፡፡ ሰዓቱ ደርሶ መግባት ስንጀምር ወደእነርዕዮት ዞን ከመድረሳችን በፊት የሙስሊሞች ጉዳይ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ በመባል የሚታወቁት እስረኞች ወጥተው በዘመዶቻቸው ሲጎበኙ አየን፡፡ (በነገራችን ላይ እነዚህን መጎብኘት የሚችለው በቤተሰብ ሊስት ውስጥ ያሉ ውስን ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡) ከዚያም ‹‹እንዴት ናችሁ፣ በርቱ፣ አይዟችሁ›› እያልን ስናልፍ ሲያከላክሉ ከነበሩት የጥበቃ ኃላፊዎች አንዱ አብሮን ርዕዮትን ሊጠይቅ የመጣውን ወዳጃችንን ነጥሎ ያዘው፡፡

ከጥቂት ሳምንታት በፊትም ሌላው ወዳጃችን እንዲሁ እነርሱን በማበረታቱ ርዕዮትን የመጠየቅ መብቱን ተገፍፎ ግብግብ ውስጥ ገብቶ ስለነበር፡፡ ታሪክ ራሱን እየደገመ እንደሆነ ገብቶን አንዳንዶቻችን ዝም አልን፡፡ ሙስሊሞቹን እስረኞች ከሚጠይቃቸው ውጪ ሌሎችን ለመጠየቅ መጥቶ ‹‹ማበረታቻ›› አስተያየት ማስተላለፍ ጠባቂዎቹን ያናድዳቸዋል፣ ሆኖም ምክንያታቸው ምን እንደሆነ መረዳት አልቻልንም፡፡ ከብዙ ልምምጥ በኋላ ወዳጃችን ተለቆ ተቀላቀለን፡፡

ወደእነ ርዕዮት መጠየቂያ ቦታ ቀርበን ስናስጠራት ርዕዮት ቀይ በቀይ ለብሳ ከተመለመደው እና ብርታቷን ከሚመሰክረው ፈገግታዋ ጋር ብቅ አለች፡፡ ከመሃከላችን ዶ/ር ያዕቆብ ‹‹ሃፒ በርዝዴይ ቱ..ዩ…›› በሚል ሞቅ ያለ (ከዚህ በፊት ቃሊቲ ውስጥ መደመጡን እንጠራጠራለን) ዜማ የጀመሩትን እኛም ተቀብለነው በሞቀ ዜማ ተቀበልናት፡፡ የዚያን ሰዓት ርዕዮትን ሆኖ ለሚያስበው ሰው ስሜት የሚያሞቅ ከባቤ እንደተፈጠረ አይጠራጠርም፡፡

ቃሊቲ ያለአመሏ ዘና አለች፡፡ ርዕዮት ኬክ እንድትቆርስ ስትጋበዝ ‹‹ፕሮ በኔ ስም ይቁረስልኝ›› ብትልም ሁለት ኬክ በመዘጋጀቱ ፕሮፌሰሩ አንዱን ሌላኛውን ራሷ ቆርሰው ሁላችንም ተቃመስን፡፡ በመስተንግዶው ለወትሮው ታራሚዎቹ እና ጎብኚዎቹ የሚያወሩትን በንቃት የሚከታተሉት ሴት ፖሊሶችም ሳይቀሩ መሳተፋቸው አስደናቂ ነበር፡፡

ርዕዮት ከታጠረው ሽቦ ወዲያ ሆና ወዲያ ወዲህ እያለች የተሰጠችንን አጭር ደቂቃ ለሁላችንም ለማብቃቃት የራሷን ጥረት አደረገች፡፡ ሆኖም ከአበዛዛችን የተነሳ ሁላችንንም ማዳረስ ከባድ ነበር፡፡ ሆኖም ልደቷ፣ ምናልባትም ቤቷ ብትሆን ኖሮ ሊደምቅ ከሚችለው በላይ ደምቆ ታየ፡፡ እርሷም ‹‹ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ፣ አከብራችኋለሁ፡፡ በነበረኝ አቋም እንደምፀናም አረጋግጥላችኋለሁ፡፡ ጋሽ መስፍንም አንተ በመከርከኝና በአስተማርከኝ መንገድ ተጉዤ እዚህ ደርሻለሁ፡፡ አመሰግንሃለሁ፡፡›› የሚል አጭር ንግግር አድርጋለች፡፡

ከርዕዮት ጋር (በዚህኛው የሴቶች ዞን) ከታሰሩት መካከል የአቶ ጁነዲን ሳዶ ባለቤትም ይገኙበታል፡፡ ከርሳቸው በተጨማሪ ከግንቦት ሰባት ጋር በተያያዘ የታሰሩት ወ/ሮ እማዋይሽና ከርዕዮት ጋር በተያያዘ ክስ የታሰረችው ሒሩትም አብረው ልደቷን አክብረዋል፡፡

ልደቱ በጣም ደማቅ ቢሆንም ከዚያ መውጣት የማችሉ ሰዎች፣ መውጣት የማይችሉት ደግሞ ጥፋት መሆኑን ባላወቁት ሥራ (ባላመኑት ወንጀል መሆኑ) ግን አጥንት የሚሰብር እውነታ ነው፡፡ ሰዓታችን ገደቡ አልቆ ስንወጣ ሙስሊሞቹ ታራሚዎች ዘመዶቻቸውን ተሰናብተው እስኪገቡ ድረስ ለጥቂት ደቂቃዎች ባለንበት እንድንቆም ታገድን፡፡ ብናልፍ የምናደርገው ነገር እነርሱን በእጅ ውልብልቢያ መሰነባበት እና ‹‹አይዟችሁ›› የሚል ማበረታቻ ቃል መጠቀም ቢሆንም የማረሚያ ቤቱን ጠባቂዎች ይህ አላስደሰታቸውም፡፡

ከእገታችን ተለቀን ስንወጣ ከግቢ ውጭ ብቻ የሚፈቀደውን ፎቶ መነሳት ጀመርን፡፡ አንዳንዶቹ ሲሄዱ ጥቂቶቻችን ወደኋላ በመቅረታችን ግን ያልጠበቅነው መዘዝ ተከተለን፡፡ ማረሚያ ቤቱ ጋር ፎቶ መነሳት እንደማይቻል ተነገረን፡፡ ምንም እንኳን እንደዚያ ዓይነት ነገር የሚከለክል ማስታወቂያ ባይኖርም እነርሱ ካሉ/አሉ በመሆኑ ብንለማመጥም አልሆነም፡፡ እንዲያውም የካሜራዋን ባለቤት ከነካሜራው ይዟት ከኛ ነጥሎ ወሰዳት፡፡ ጓደኞችን

‹‹ከቀረሁ ለቤተሰቦቼ ንገሩልኝ›› ብላ በቀልድ ሄደች፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተመልሳ ስትመጣ ካሜራዋ ውስጥ የነበሩትን ፎቶዎች አስጠፍታ (‹ዲሊት› አስደርጋ) ነበር፡፡

በዚህ መልኩ የዕለቱ በሥራዎቻቸው የምንወዳቸውን ጋዜጠኛ/ታራሚዎች በመጎብኘታችን እራሳችንን በመሸለም ከስዓቱን በመዝናናት አሳለፈን፡፡ እነር ርዕዮትም ቀሪውን ጊዜ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን በመመልከትና ከሌሎች ታራሚዎች ጋር በማውራት ያሳልፉታል፡፡ በዚሁ ይህንን ጽሑፍ ከመደምደማችን በፊት ቀጣዩን የነርዕዮትን ልደት ከአጥር ውጪ የምናከብርበት ቀን እንዲቀርብ መልካም ምኞታችንን እናስተላልፋለን፡፡

# ኢትዮጵያውያን ፍቅር ያውቃሉ?

‹‹ፍቅር ማወቅ እና አለማወቅ›› የሚባል ነገር አለ? ‹‹ፍቅር ማወቅ›› የሚባል ነገር ካለስ - ኢትዮጵያውያን ፍቅር ያውቃሉ? - የዛሬ የፍቅር (የቫለንታይን) ቀን ጽሑፋችን በዚህ ዙሪያ ያጠነጥናል፡፡

## መቃጠር (Dating)

"Dating" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በአገርኛ አማርኛ እኩያ አንድ ቃል ፍቺ ይገኝለት ከተባለ - መቃጠር - የሚለው ተቀራራቢ ይሆናል፡፡ ሆኖም ‹‹አቃጣሪ›› የሚለው የቆየ ቃል የሚሰጠው አሉታዊ ትርጉም ነው፤ ሁለት ሰዎች መሐል ነገር የሚያመላልስ ማለት ሲሆን በፍቅርም ቢሆን አቃጣሪ የሚለው (በተለይም ከጥንታዊ አመጣጡ አንጻር) ቤተሰቦቻቸው ለመገናኘት ዕድሉን የነፈጓቸውን ተፋቃሪዎች በመሐል እየተመላለሰ የፍቅር መልዕክታቸውን የሚያደርስ የሚል ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ትርጉሙን ቦርቀቅ ስናደርገው ደግሞ ሁለት ሰዎች እንዲፋቀሩ ለማድረግ በመሐላቸው የድለላ ሥራ የሚሠራ - የሚያቃጥር (dating agent) - እስከሚል ትርጉም ሊደርስ ይችላል፡፡

የፈረንጅኛውን ትርጉም ስንወስደው ደግሞ የተለየ እና አዎንታዊ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ዊኪፔዲያ ለምሳሌ ለDating የሚሰጠው ትርጉም እንዲህ ይተረጎማል ‹‹Dating is a form of courtship consisting of social activities done by two people with the aim of each assessing the other's suitability as a partner in an intimate relationship or as a spouse. While the term has several meanings, it usually refers to the act of meeting and engaging in some mutually agreed upon social activity in public, together, as a couple….››

ኢትዮጵያ ውስጥ አንዳንድ ዘመነኛ ከተሜዎች ካልሆኑ በስተቀር፣ መግጠም አለመግጠማችንን እናጥና ብለው ተከታታይ ቀጠሮዎች አመቻችተው፣ አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ ቀጠሮ በ‹መቃጠር› የሚጠናኑበት እና የሚወያዩበት መንገድ አለ ለማለት ይከብዳል፡፡ አጋጣሚዎች ፈቅደው ከንፈር ለከንፈር ሲገናኙ በሚጀመር የከንፈር ወዳጅነት ድንገት ወደ‹‹ግንኙነት›› ወይም ዕውቅና ያልተሰጠው ፍቅር (affair) ይገባሉ፡፡

ይህንን የመቃጠር ልምድ ማዳበር የግንኙነት ወቅት ለሚኖሩ ክፍተቶችን ለመቀነስ ይረዳል የሚሉ ልምዱ መዳበሩን የሚያበረታቱ ሲኖሩ በሌላ በኩል ደሞ ከባሕላችን ውጪ የሆነና በእኛ ማኅበረሰባዊ ባህሪ ሊለመድምና ውጤታማ ሊሆን አይችልም በሚል ያጣጥሉታል፡፡

## ፍቅረኝነት፣ ፍቅር አገላለገጽ እና "Romance"

ልክ እንደ‹dating› ሁሉ ‹romance› ለሚለው ቃልም ሁነኛ የአገርኛ አማርኛ ትርጉም ማግኘት አይቻልም፡፡ ‹romance› ማለት ፍቅርን መግለጫ መንገድ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ጥንዶች ፍቅረኞቻቸውን ለማስደሰት ቢፈልጉም እንኳን ፍቅረኛቸውን ለማስደሰት አቅደው የሚያደርጉበት ልምድ/ባሕል የለም ብሎ መከራከር ይቻላል፡፡ እንዲያውም ብዙዎች የፍቅር አጋራቸውን ‹‹ፍቅረኛዬ›› ነች ብሎ ማለት እያሳፈራቸው፤ በእንግሊዝኛ ‹‹ቦይፍሬንዴ/ገርልፍሬንዴ›› ማለት እየቀናቸው ነው፡፡ ያውም ይህ በከተማ ውስጥ ነው፡፡ በገጠሩ ክፍል በምስጢር ከሚጠበቅ የከንፈር ወዳጅነት ተሻግረው ለትዳር ከበቁ በኋላ ፍቅር የሚገለጸው በቁፍጥንና ነው፡፡ በሁሉም የኢትዮጵያውያን ብሔሮች እና ባሕሎች ብዙም በማይራራቅ ሁኔታ ባሎች ሚስቶቻቸውን በመቆጣጠር እና በመቆጣት የበላይነታቸውን ከማሳየት በላይ ሌላ ፍቅር የሚገልጹበት መንገድ የለም ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ግን ፍቅር የላቸውም ተብሎ ሊተረጎም አይገባም፤ ፍቅር አላቸው ነገር ግን ፍቅራቸውን የመግለጫ መንገድ/ባሕል/ልምድ ግን የላቸውም፡፡ በተደጋጋሚ ሲገለጽ እንደሚስተዋለው ዱላ የፍቅርና ቅናት መገለጫ እየተባለ ቢነሳ አሁን አሁን ግን ጉዳዩ ወንጀል በመሆኑም ጭምር በጊዜ ሂደት ቢያንስ እንደፍቅር መገለጫነት መቆጠሩ ቀርቶአል፡፡

### ማቆላመጥ

አንዱ የኢትዮጵያውያን ፍቅርን የመግለጽ ችግርን የሚያንፀባርቀው ፍቅረኞችን ለማቆላመጥ የምንጠቀምበት ቃላት ማጠር ነው፡፡ ፈረንጆቹ ‹‹honey, sweetie, baby…›› እያሉ የፍቅረኛቸው ስም እስኪረሳቸው ሲያቆለማምጡ

የኛዎቹ ግን የፍቅረኛቸውን ስም እንኳ በቁልምጫ መጥራት የሚከብዳቸው ጊዜ ይስተዋላል፡፡ ስንቶች ፍቅረኞቻቸውን ‹‹ማሬ፣ ጣፋጯ፣ ፍቅሬ…›› ብለው በአደባባይ ይጠራሉ? ከጓደኞቻቸው ጋርስ በግልጽ ያስተዋውቃሉ? ብዙ ጊዜ ከወጣቶቹ አንደበት የማትጠፋው ‹‹የኔ ቆንጆ›› የምትል ቃል ራሷ፣ የወል ስም እየሆነች አጠቃቀሟ የምር ይሁን የልምድ ለመለየት ያስቸግራል፡፡

## ኩራተኝነት

ኩራተኝነት በኢትዮጵያ ወንዶች ውስጥ የተለየ ለፍቅር የመመረጫ መንገድ ነው፡፡ ሴቶቹም ‹‹ኩራቱ…›› ብለው ያደንቁታል፣ ‹‹ጅንኑ…›› ብለው ይዘፍኑለታል፤ ወንዱም ያንኑ ያጠናክራል፡፡ አለዚያ ወንድ ልጅ ፍቅሩን ብሎ ጠብ እርግፍ ቢል፣ ሌላው ቀርቶ እርሷን ለመርዳት ማጀት ቢገባ ‹‹ኤጭ… እሱ ደግሞ ወንድ ነው እንዴ!? ሴታ፣ ሴት ነገር…›› ተብሎ የወንድነት ማረጋገጫውን ሊነጠቅም ይችላል፤ እሱም አይሞክረውም፡፡ ሴቶቹም ‹‹ኮስታራ ወንድ ይስበኛል›› እያሉ ያበረታታሉ ወንዶቹም ‹‹እንኳን ዘንቦብሽ…›› ዓይነት ብለው ነገሩ እንደነበረ ይቀጥላል፡፡

አበሻ ያልሆኑ ወንዶች፣ ፍቅራቸውን መግለጫ ፅጌረዳ አበባ ይሰጣሉ፣ በየሬስቶራንቱ ወንበር ይስባሉ፣ የወይን ጠጅ ብርጭቆ ይሞላሉ፣ የመኪና በር ይከፍታሉ… ወዘተ፣ ወዘተ… እስኪ ኢትዮጵያዊውን ከተሜ እንመልከተው እና ከፈረንጆቹ ኮርጆም ሆነ በራሱ በኢትዮጵያዊ መንገድ ፍቅሩን የሚገልጽበት የተለየ ልምድ የሚባለው ነገር አለ? ምንድን ነው?

## በጨዋ ደንብ መለያየት (Silent breakup)

‹መለያየት› በየትኛውም ዓለም ላሉ ጥንዶች ከባድ ነው፡፡ ለምሳሌ ጥቃት አድራሾች በርካቶች ናቸው፡፡ በምዕራቡ ዓለም ዝነኞች ሲያገቡ ‹‹ብንለያይ የፍቅር ሕይወታችንን እንዳትጽፍበት/ፊበት›› ተባብለው ይፈራረማሉ፡፡ ወጣቷ ዘፋኝ ቴይለር ስዊፍት ለኒውስ ዊክ በሰጠችው ቃለምልልስ ‹‹ፍቅረኞቼ ስንለያይ እባክሽ አትዝፈኚብኝ›› ይሉኛል ብላለች፤ በርግጥ ከጆናስ ብራዘርስ ባንድ ታላቅየው ጋር በነበራት የፍቅር ግንኙነት እና መለያየት ዙሪያ እሷም፣ እነርሱም ዘፍነውባታል፡፡

ለኢትዮጵያውያን ግን መለያየት ከሁሉም የባሰ በጣም ከባድ የቤት ሥራ ነው የሚመስለው፡፡ ምዕራብ አገራት ውስጥ ሳይቀር ሚስቶቻቸውን የገደሉ ኢትዮጵያውያን እና ፍቅረኞቻቸውን የቀጡ ሰዎች ቁጥር ተመሳሳይ በደል ከፈፀሙ የአገራቱ ነዋሪዎች ቁጥር የሚበልጥ ይመስላል - በዜና እንደምንሰማው፡፡ በአገራችንም ከማስፈራራት፣ ማሳደድ እና ጥፊ በተረፈ እስከ ጩቤ መማዘዝና አሲድ መረጫጨት መለያየትን እየተከሉ የሚመጡ ነገሮች ሆነዋል፡፡ እርግጥ ነው እነዚህኞቹ ከቁጥራቸው አንፃር ብዙውን ሊገልፁ ባይችሉም፣ በከፊልም ቢሆን መከሰታቸው አሳፋሪ ነው፡፡

ከዚህ በተረፈ እኛም አገር በመለያየት ዙሪያ ከጓዳ ለሕዝብ የበቁ ብዙ ታሪኮች አሉ፡፡ የዘፋኟ የሃይማኖት ግርማ ባል መጽሐፍ ጽፏል፤ ገጣሚው ኤፍሬም ስዩምም እንዲሁ ‹‹ፍቅር እዚህ ቦታ ፈገግ ብሎ ነበር›› በማለት በቀድሞ መድብሉ ያሞገሳትን ‹‹ሶሊያና›› የተባለች ሴት፣ መልሶ ረግሟታል፡፡

ትዕግስት እና መቻቻል የሚባል ነገር - በተራ ጥንዶች መለያየትም ላይ አይስተዋልም፡፡ ጫጫታ ይበዛበታል፤ ወዳጅ ጓደኛ ይነካካበታል፣ ሮሮ እና ብሶት ይስተጋባበታል - እስከድብድብም ሊደርስ ይችላል፡፡ ሴቷም በራስዋ ወንዱም በራሱ ከባቢ የግንኙነቱን ጉድፎች የአጋራቸውን ችግሮች ይናገራሉ፡፡ በጣም የተለየ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር አብዛኛው ግንኙነት ሲጠናቀቅ ለወደፊት ሰላምታ ያህል እንኳን የሚሆን ትእግስት አይቀራቸውም፡፡ ተለያይተው ጓደኛ የሚሆኑ ጥንዶች ከስንት አንድ ናቸው፡፡

## የፍቅር ቀንና ፍቅርን ማወቅ

እነዚህን እና የመሳሉትን ተያያዥ ጉዳዮች ስንመለከት ኢትዮጵያውያን የቫላንታይን ቀንን ዓይነት በዓላትን የምናከብርበት የባሕል መቆሚያ ሊያጥረን ይችላል፡፡ በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን (በተለይ ለዚህ የተፈጠሩ የሚመስሉ ኤፍኤሞች) ስለበዓሉ አከባበር ሲያነሱ መጤ ባሕል ነው፣ የእኛ አይደለም፣ የምዕራባውያን ተጽእኖ ነው የሚሉ ቀላል መከራከሪያዎችን ከማንሳት ውጪ የባሕላችን መሠረታዊያንን እና ልምዳችንን እንዲሁም የፍቅር መግለጫ መንገዶቻችንን ለውይይት አንስተው ግን አይስተዋሉም፡፡

ቀኑን ሳለማበላሸት ግንኙነቶች ችግሮቻቸውን ዋጥ የሚያደርጉበት፣ በአቻ ሴቶች መካከል ቀኑን አክባበር አስመልክቶ ውድድር ቢጤ ውስጥ የሚገቡበት፣ አልፎ አልፎም ለቀኑ ሲባል ብቻ ለሰዓታት የሚቆዩ ግንኙነቶች የሚፈጠሩበት የመኝታዎች (የኪራይ) ዋጋ በጣም የሚወደድበት ቀን እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ደግሞ የፍቅረኞች ቀን አከባበር ከሚገባው በላይ አትኩሮትን እየሳበ ነው፡፡ በተለይ ጉዳዩ ‹‹በኤፍኤሞች አየር ሰዓት ማሟያ›› እና ‹‹የኢንተርኔት ትርጉም ማንበቢያ›› ከሆነ ወዲህ ቀላል የማይባል የወጣቱ ክፍል ባይፈልግ እንኳን  ጉዳዩን ከትኩረቱ ማስወገድ እንዳይችል አድርጎታል፡፡ ይህ የባሕላችን የፍቅርን መግለጫ እጥረት መገለጫ እንዲሁም ሁሉም የሚያከብረው ኢ-ሃይማኖታዊ በዓላት/ፌስቲቫሎች እጥረት ሆኖ ሊቆጠርም ይችላል፡፡

ይህ ቀናት የማክበር ሰበብ ፍለጋ ምናልባትም ከፍቅር ባሕላችን አንጻር ፍቅራችንን የምናከብበት ሌላ ቀን ስለሌለን (ዓመቱን ሙሉ ተኮሳትረን ከርመን) ዕድሉንም የመጠቀም አዝማሚያም ይሆናል፡፡ ፍቅረኞች የፍቅረኞች ቀንን ያክብሩ፡፡ ፍቅርን የመግለጽ ባህልም ያዳብሩ፡፡ አትኩሮቱን ገደብ መስጠት ግን ከሚዲያዎቻችንም ሆነ ከእኛ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡ ለማይገባቸው ጉዳዮች ከአቅም በላይ አትኩሮት መስጠት በቀኑ ማግስት የምንጋፈጠውን ግላዊም ሆነ ማኅበራዊ እውነታ ካለመቀየሩም በተጨማሪ አትኩሮት የሚገባው ጉዳይ ላይ አትኩሮታችንን በሚገባ እንዳንሰጥ እንዳያግደን ያሰጋል፡፡ ቢያንስ፣ ቢያንስ በዕለቱ ስለፍቅር እና የፍቅር ግንኙነትን ተከትሎ ስለምንተገብራቸው ባሕላዊ ድርጊቶቻችን በጎነት እና መሻሻል ስለሚያስፈልጋቸው ልማዶች እያወጋን ብናሳልፈው፣ ዕለቱ ዋጋ-ቢስ ከመሆን ይተርፋል፡፡

---

ማሳሰቢያ፡- ይህ ጽሑፍ የተጻፈው ስለብዙኃኑ እንጂ ስለአንዳንድ የተለዩ /ወጣ ያሉ/ ኢትዮጵያውያን አይደለም፡፡ አስተያየት ሰጪዎችም ራሳቸውን ሳይሆን ብዙኃኑን እና ባሕሉን እያሰቡ ቢሆን ይመረጣል፡፡

# ሴት የመሆን ጥቅሞችና መታደሎች

ሴት መሆን መታደል ነው ብዬ ብጀምር የሚስቅብኝ አይጠፋም! ሴት የመሆን ጉዳቶች ላይ ተደጋጋሚ ነገር ሲነገር ሰምተናል፡፡ የቤት ውስጥ የሥራ ጫናው፣ ማኅበራዊ ኃላፊነቱ፣ የዘመን አመጣሽ ተግዳሮቶቹ፣ ከወንድ ይልቅ ለባሕል እና ለማኅበረሰብ የመገዛት ኃላፊነት ሳያችን ላይ መጫኑ፣ የሚታየው አካላዊ ጉዳት (አሲዱ፣ አስገድዶ መድፈሩ፣ ድብደባው…) የማይታየው ሥነ ልቦናዊ ጉዳት (እኔ፣ አንቺ፣ እናቶቻችን ሁላችንም የምናልፍበት የአእምሮአዊ ጭንቀት ሐሳብ እና ትግል) ሁሉም በተደጋጋሚ ተወርቶላቸዋል፡፡ የሴቶች ቀን ላይ ቆመን ሴት የመሆን ጥቅሞች እና ደስታዎች ላይ ለመጻፍ ብንነሳ ማን ይከለክለናል?

የሴቶች ቀን ሲነሳ ‹‹ሌላው የወንዶች ቀን ነው፤›› የሚል ተራ ክርክርን በዚሁ ነካ አድርጌ ልለፍ፡፡ ማርች 8 የሴቶች ቀን ሲሆን ሌሎቹ የሰዎች ቀናት ናቸው፡፡ የወንድም፣ የሴትም፣ የሕፃንም፣ የሽማግሌም፣ የነጋዴም፣ የወጣትም… - የሁሉም ሰዎች ነው፡፡ የአባቶች ቀን፣ የእናቶች ቀን፣ የበዓላት ቀን ነገር ሲነሳ ይህ ክርክር ትዝ የማይላቸው ሰዎች ለምን ‹‹የሴቶች ቀን›› ላይ ብቻ እንደሚበረቱ አላውቅም?!

**ሴት የመሆን መታደሎች**

ሴት የመሆን መታደሎቹ አንዱ ኃላፊነትን በሚገባ የመወጣትን ክኅሎት አብሮ ይዞ መምጣቱ ነው፡፡ አናስተውለው ይሆናል እንጂ ሴት ልጅ ይዛው የማይስተካከል፣ ሴት እንደኃላፊነት ተሰጥቷት የማይፈፀም ነገር የለም፡፡ እንደውም ከወንዶች በተለየ የኃላፊነት ስሜት የሚሰማቸው ሴቶች መሆናቸውን ለማረጋገጥ በተለያዩ የቤት እና ከቤት ውጪ ባሉ ኃላፊነቶች ውስጥ ያሉ ሴቶችን ማየቱ ይበቃል፡፡ የተረሳ ነገርን ማስታወስ፣ ጉዳይን በቁም ነገር መያዝ፣ ነገሮች የሚያመጡትን ውጤት አለማጣጣል እና ችላ አለማለት ሲታይ ኃላፊነትን ለመወጣትማ ሴት ልጅን የመሰለ ነገር የለም ያስብላል፡፡

ለኃላፊነት መብቃት ብቻ አይደለም፤ ውሳኔ መስጠት ሌላው ከሴትነት ጋር አብሮ የተሰጠ ቁርጥ ባህሪይ ነው፡፡ ሴቶች ውሳኔ መስጠት ረገድ ማቅማማት እና እጅ መስጠት አይታይባቸውም፡፡ እስካመኑበት ድረስም ፈራ ተባ አይሉም፡፡ ቆራጥ ውሳኔ የአለቃ ሴቶች፣ የእናቶቻችንም ጭምር ባሕርይ ነው፡፡ ይህ ታዲያ ውሳኔ የመስጠትን ብልሐትና ኃላፊነት አብሮ ይጨምራል፡፡

ውበት ሲነሳ ሴትነትን አለማንሳት የማይቻል ነው፡፡ ውበት በብዙ መልኩ ሊገለጽ ይችላል፤ ሴት ልጅ ላይ የተገለፀውን ያህል ግን የትም የለም፡፡ **የውበት መገለጫው የሴት ልጅ ሰውነት ነው፡፡** የማታምር ሴት ልታጋጥም ትችል ይሆናል የውበት አንዱን ክፍል ያልያዘች ግን አትገኝም፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ‹እንትንዋ ያምራል፤› የሚል አድናቆትን የምናስከትለው ለሴት ነው፡፡ ውበት ከተነሳ አይቀር ከነምሳሌው፣ ከነመገለጫው እና ከነለዛው ተሟልቶ የሚገኘው ሴት ልጅ ላይ ብቻ ነው ብል ማጋነን አይሆንም፡፡ ሴት መሆን በራሱ ውበት ነው! እንደው እንደምሳሌ እንኳ ብናነሳው ባለቅኔዎች ስለወንድ ልጅ ፍቅር ይጽፉ ይሆናል እንጂ ስለውበቱ ስንኝ አያባክኑም፡፡ ስለሴት ልጅ ውበት ያልገጠመ ባለቅኔ ግን ባለቅኔ የሆነም አይመስለው፡፡ በውቀቱ ስዩም በኗሪ አልባ ጎጆዎች ውስጥ ‹‹ብታውቂ›› ብሎ የጻፋትን እናስታውስ፡-

*ስትሥቂ!*
*ጠፈርን እንደምታደምቂ*
*መንፈስን ካዚም እስራት*
*እንደምታላቅቂ*

*ብታውቂ!*

*ስትስሚ!*
*አጥንት እንደምታለመልሚ*
*ታማሚ ልብ እንደምታክሚ*

*ብታውቂ!*

*ስታወሪ!*
*ዱዳ እንደምታናግሪ*
*መነኩሴውን ከሱባኤ፣*
*ፈላስፋውን ከጉባኤ*
*እንደምትጠሪ*

*ብታውቂ!*

*እንኳንስ በ'ኔ ልትሥቂ*
*ከራስሽ ጋር ፍቅር ይዞሽ*
*አይሽ ነበር ስትማቅቂ!!!*

ማኅበራዊ ኑሮ እና የሥርዓተ ጾታ አሰላለፍ ቢሸፍነውም ተፈጥሮ ለሴት ልጅ አድልታለች፤ ለዚህ ክርክር አያስፈልገውም። **የሰው ዘርን ወደ ምድር የማምጣት ኃላፊነት እና መንገድ የታደለው ለሴት ነው።** ይህንን ታላቅ ሥራ እና ኃላፊነት ከሴት በቀር መቀበል እና መተግበር የሚችል ሌላ ፍጡር አልተሠራም። አይሠራምም! ሴት መሆን ይህንን የመውለድ ብቻ ሳይሆን የማሳደግ፣ የተፈጥሮ ምግብ የመመገብ የመሳሰሉትን መታደል አብሮ ይዟል። ይህ መታደል ማኅበረሰባዊ ጫናና ማጣጣል ቢጨመርበትም ከዚህ በላይ መታደል ምን አለ? ‹‹እናትነት እውነት፤ አባትነት እምነት›› ነው የሚለው አባባልስ የዚህን መታደል ጥቂቷን ያሳይ የለ!?

የሴት ልጅ መታደል ዘጠኝ ወር አርግዞ በመውለድ ፀጋ ብቻ አይወሰንም፤ ሌላው ቀርቶ በሥርዓተ ጾታ የሴት ልጅ በቤት ውስጥ መወሰን በራሱ የራሱ መታደል አለው። ሴት ልጅ (እናት) በቤት ውስጥ መዋል በመቻሏ ብቻ የታደለችው ምስጢር አለ። እናት ልጆቿን አቅርባ በምትፈልገው አቅጣጫ ማሳደግ ትችላለች። መቼም ‹‹ሴትን ማስተማር ማኅበረሰቡን ማስተማር ነው፤›› ሲባል ያልሰማ ሰው አይኖርም። ይህን ማለት ያስፈለገው ሴት/እናት ለልጆችዋ ያላትን ቅርበት ለማመልከት ነው። እናት ያፈራችው ዕውቀት ለልጇ መድረሱ አይቀርም የሚል መደምደሚያ ላይ ዓለም በመድረሱ ነው። ለመሆኑ ‹‹የእናት ፍቅር›› የሚለው ቃል ‹‹የአባት ፍቅር›› ከሚለው የጎላ ጣዕም እና ጉልበት እንዳለውስ አስባችሁት ታውቃላችሁ። እርግጥ ነው፤ ልጆቻቸውን እጅግ አድርገው የሚወዱ አባቶች ሳይቀሩ ‹‹እናት ናቸው›› የሚል ቁልምጫ ነው የሚሰጣቸው - መታደል ነው። ሌላው ቀርቶ አገር እንኳን የምትመሰለው በሴት/እናት ነው።

አገር በሴት የምትመሰለው መውደድን ለመግለጽም ጭምር። ካመጣነው አይቀር ሴት ልጅ ተወዳጅ ብቻ ሳትሆን ተወዳጅ መሆኗንም መጥቀስ አለብን። ሴት ልጅ አፍቃሪ ናት። ምናልባት ከልቧ እስክታስገባ የሚፈጅባት ጊዜ ሊኖር ይችላል እንጂ ሴት ለጅ ስታፈቅር እንከን አልባ ፍቅር ነው የምታፈቅረው። ምንም ለራሷ ሳታስቀር ሁለ ነገሯን ሰጥታ ነው የምታፈቅረው። ለዚያም ይመስለኛል ‹‹ሴት ልጅ ስታፈቅር ሙሉ ለሙሉ አይኗን ጨፍና ነው፤ ወንድ ግን አጮልቆም ቢሆን ያያል›› የሚባለው። ኃይለጊዮርጊስ ማሞ ‹‹ሴት እና ፈጣሪ›› ባሰኘው መድብሉ ላይ ‹‹ተፈጥሮ›› በሚል ርዕስ የጻፈው ግጥም ይህን ባሕሪዋን ከነቆራጥነቷ ደምሮ ያሳያል፦

*ሴት ካፈቀረችሁ፥ ከተያዘ ነፍሷ፣*
*የቤተሰብ ክብር፥ ጨዋታ ነው ለእሷ፣*
*ከጠላችሁ ደግሞ፥ ለዓይኗ ተፀይፋ፣*
*ፈጣሪንም ብትልክ፥ ትሄዳለች አልፋ።*

መሪነትስ ቢሆን?! አመራር የእኛ ነው። በአደባባይ ወንዶች ወንበሩ ላይ ይቀመጡ እንጂ የወንዶችን የውጪ የታይታ ዓለም፣ ከውስጥ ሴቶች ይቃኙታል። ቢበዛ መንገዱን ማወቅ ይጠይቅ ይሆናል እንጂ የሚፈለገውን አቅጣጫ የማስያዝ የተደበቀ ሥልጣን የሴቶች ነው። አልጋ ላይ ፓሊሲ ከማስቀየር ጀምሮ፣ የአልጋ ጨዋታን የመምራት ኃላፊነት የሴቶች ነው። ጠይቆ እምቢ አለመባል የውበት እና የኃላፊነት እመቤት መሆን ማኅበረሰብን መገንባት እና ሕይወትን ማጣፈጥ የሴቶች መታደሎች ናቸው። በነገራችን ላይ ይህንን የተደበቀ የሴቶች በወንዶች ላይ የማዘዝ (ወይም በወንዶች ወኪልነት) የመምራት ሥልጣን ማንነቱን የማላስታውሰው ገጣሚ ጠቃቅሶታል። በቃሌ እንደማስታውሰው ልውጣላችሁ፦

*አንተ አዳም ራስ ነህ፥ ይላል ቅዱስ ቃሉ፣*
*አንች ሔዋን አንገት ነሽ፥ ብለው ያወራሉ፣*

*አንተ ራስ፣ እሷ አንገት*
*ብታሽከረክርህ ታዲያስ ምን አለበት?*

ሌላው እና በብዙ ሰዎች እምብዛም ያልተስተዋለው ነገር ግን አሁንም የሥርዓተ ጾታው የፈጠረው ሌላ ዕድል አለ፤ የፍቅር ግንኙነት የመጀመር ኃላፊነት - ይኼ ኃላፊነት ሴት ላይ አልተጣለም። ሴት ልጅ እንደ ወንድ የወደደችውን ወንድ ለፍቅር የመጠየቅ እና ነገሮችን የመጀመር ኃላፊነት የለባትም። ይህንን የማድረግ ባሕላዊ ኃላፊነት ለሴት ልጅ አለመሰጠቱ ጉዳቱ የሚያመዝን የሚመስላቸው ይኖራሉ፤ እውነታው ግን ሴት ለጅ የወደደችውን ወንድ መጥቶ እንዲያነጋግራት የምትጋብዝበት ብዙ መንገድ ሁልጊዜም አላት። ዞሮ፣ ዞሮ እሷ ለምትፈልገው ግንኙነት ቀድሞ የሚያናግራት፣ ለማስቀጠል የሚጠበቅበትን ሀሉ የሚያደርገው እሱው ነው። እየፈለገች ተፈላጊ የመሆን ዕድሏ በጇ ነው።

በየጊዜው ከሚነሱት ምሬት ብቻ የተሞላባቸው ጉዳዮች አንፃር ስናየው፥ ዛሬን እንኳዋን ሴትነትን እንዲህ ብናከብር ምናለ?!

# የቅድመ ምርመራ ቅድመ ምርመራ

ስለ ቅድመ ምርመራ ስናወራ ሃሳቡን በጠንካራ ሁኔታ ተግባራዊ ያደረገው የደርግ መንግስት ሳይጠቀስ አያልፍም፡፡ ከዚያ በፊት በነበረው ጊዜ ‹ንጉሥ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ› የሚለው አስተሳሰብ በስፋት ስለሚታመንበት ንጉሡን ከሚያወድስ እና የንጉሡን ፈቃድ ከሚያሟላ የህትመት እና የብሮድካስት ስራዎች ውጪ ለመስራት ሃሳብ አልነበረም፡፡ የደርግ መንግስት የንጉሡን ስርዓት ካስወገደ በኋላ ደግሞ የቅድመ ሳንሱር ጉዳይን ጠበቅ ባለ በሕግ ደንግጎ ቀረበ፡፡ ሳንሱር ሳይደረጉ መፅሃፍት አይታተሙም፡፡ ሌሎች የህትመት ውጤቶችም የሚያስተላልፉት መልዕክት ስርዓቱ የሚደግፈውን ርዕዮተ ዓለም ፅንሰ ሃሳብና አስተሳሰብ ብቻ ነበር፡፡ በሃገራችን ባይታተምም ውጭ ሃገር የታተመ ከስርዓቱ ጋር የሚፃረር ወይም የሚተች መልእክት ያለውን መፅሃፍ/የህትመት ውጤት ለማንበብ እንኳን አይቻልም፤ ወይም እንደ ሰረቀ ሰው ተደብቀው ነበር የሚያነቡት፡፡

ከደርግ ቀጥሎ የመጣው የኢህአዴግ መንግስት ደግሞ የህትመት ነፃነት ያስፈልጋል በሚል ቅድመ ምርመራም ክልክል እንደሆነ አወጀ፡፡

***አንቀፅ 29.3 ሀ/ ‹‹የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን››***

ይህን ህግ መሰረት በማድረግም በሬድዬና ቴሌቭዥን ደረጃ የታየ ለውጥ ባይኖርም ብዙ የግል ሃሳብ የሚንፀባረቅባቸው ጋዜጦችና መፅሄቶች ተፈለፈሉ፡፡ ለ97 ሃገራዊ ምርጫም እነዚህ የግል የህትመት ውጤቶች ህብረተሰቡን በማንቃት እና የሃራቸው ፖለቲካ ጉዳይ ያገባኛል ብለው እንዲያስቡ በማድረግ ረገድ አሉታዊ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ኢህአዴግም በምርጫው ውጤት እና በህዝቡን ስሜት ተደናግጦ ይመስላል ከ97 ምርጫ በኋላ በሰበብ አስባቡ ጋዜጠኖችንና አዘጋጆችን ማሰር እንዲሁም ለራሱ የሚመች ለትርጉም የማይመች እና ከፕሬስ ጋር የተያያዙ ህጎችን ማውጣት እና ተግባራዊ ማድረግ የጀመረው፡፡

ኢህአዴግ ስለዲሞክራሲያዊ መብቶች ህግ ላይ የማስፈርና የመናገር ችግር የለበትም፡፡ በግልፅ እንደሚታየው በህገመንግስታችን አንቀፅ 29 ላይ ***‹የአመለካከት እና ሐሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት›*** በሚል ርእስ በሰባት ንኡስ አንቀፆች ተከፋፍሎ በቂ የሚባል ሽፋን ተደርጎለታል፡፡ ባለስልጣኖቹም ይቺን አንቀፅ ደጋግመው ያነበንቡልናል፡፡ የታሰሩ ጋዜጠኞችን በተመለከተም የሚመለከታቸው የመንግስት ሰዎች ሲጠየቁ ‹የታሰረ ጋዜጠኛ እና ፖለቲከኛ የለም› ይሉናል፡፡ እውነቱን እና በተግባር የምናውቀው ግን በተቃራኒው ነው፡፡

ህገመንግስቱ የሰጣቸውን መብት ተጠቅመው ሃሳባቸውን በነፃ ለመግለፅ የሞከሩት የተለያየ የወንጀል ስያሜ እየተፈጠረላቸው እስር ቤት እንዲገቡ እየተደረገ ነው ተብሎ መንግስትም በተደጋጋሚ ሲታማ ይሰማል፡፡ ከእስሩ ጋር ተያያዥ የሆኑት እንግልት፣ ድብደባ እና ስቃይን የመሳሰሉ ውንጀላዎችን ሳንዘነጋቸው ማለት ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ያሉት ደግሞ ወይም ተሰደዋል ወይም መስራት አቁመዋል፡፡ የተቀሩት ከነገ ዛሬ የጓደኞቻቸው እጣ እንደሚደርሳቸው የስጋት እና የሰቀቀን ኑሮ ውስጥ ሆነው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ይህ እንግዲ ለሃገራችን ምን ያክል ኪሳራ እንደሚያስከትል ለመገመት ፊደል መቁጠርም አያስፈልግም፡፡

የቅድሚያ ምርመራ በማኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን የምትገልፀዋ አንቀፅ የምታገለግለው ልክ አይጥ ወጥመድ ላይ እንደሚቀመጥ ምግብ ነው፡፡ አይጧ ምግቡን ብላ ስትመጣ ወጥመዱ እንደሚይዛት ሁሉ በአንቀፅ 29 ላይ የተደነገገውን መብት ተጠቅሞ ሃሳቡን ለመግለፅ የሚሞክርም እንዲሁ በወጥመዱ የመያዝ አደጋ ይገጥመዋል፡፡ ስለዚህ ህጉ ኖረም አልኖረም ልዩነት የለውም ማለት ነው፡፡ እንዲያውም ኪሳራው ይበዛል፡፡ የፍትሕ ጋዜጣን እንደ ምሳሌ መውሰድ እንችላለን፡፡ ህትመት በሚገባበት ወቅት ከመታተሙ በፊት ጋዜጣው ላይ ሊወጣ የነበረ ዜና እንዲያስወጡት ለአዘጋጆቹ ከማተሚያ ቤት ተነገራቸው፡፡ አዘጋጆቹ ደግም ይህ የቅድመ ምርመራ እገዳውን እንደሚፃረር ሲነግሯቸው ጋዜጣውን አተሙትና ከታተመ በኋላ (ከስርጭት በፊት) እንዲታገድ ተደረገ፡፡ እንግዲህ በአታሚውም በአሳታሚውም ወገን የሚያስከትለውን ኪሳራ አስቡት፡፡ ከቅርብ ጊዜ ትዝታችን እንኳን ብንጀምር፤ ባሳለፍነው ሰባት ወር ጌዜ ውስጥ ሦስት ጋዜጦችና አንድ መፅሔት ታግደዋል፡፡ በነዚህ የህትመት ውጤቶች ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩት ፀሃፊያንና ጋዜጠኖችም የስራ አጥነት አደጋ ያጋጥማቸዋል፡፡ ይህን የሚያዩ የጋዜጠኝነት እና ስነፅሁፍ ተማሪዎች እንዲሁም የመፃፍ አቅሙና ዝንባሌ ያላቸው ወጣቶችም ተስፋቸው የመነመነ ይሆናል፡፡ ኪሳራው ብዙ ነው፡፡ ተዘርዝሮ የሚያልቅም አይደለም፡፡

በሕገመንግስቱ የተደነገገልንን ***‹የአመለካከት እና ሐሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት› እና ‹‹የቅድሚያ ምርመራ በማኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን››*** መብት ከመንግሥት ባልተናነሰ መልኩ የሚጥሱ አካላት መበራከት ደግሞ ሌላው በቅርቡ እየተስተዋለ ያለ ቀላል የማንለው ችግር ነው፡፡ዋናዎቹ ማተሚያ ቤቶች እና የሆቴል ወይም የአዳራሽ ባለቤቶች ሲሆኑ በአሁን ሰዓት እነዚህ አካላት ህትመቶች ወይም ነፃ ሳቦች ለህዝብ እንዳይደርሱ በማድረግ ረገድ ከፍተኛውን ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡ ብዙዎቹ ማተሚያ ቤቶች በራሳቸው ስልጣን ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ወይም መንግስትን የሚተቹ መፅሃፎችን ለማተም ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ የስብሰባ አዳራሽ ያላቸው ሆቴሎች ባለቤቶች እና መሰብሰቢያ አዳራሽ ብቻ ያላቸው ቦታ ባለቤቶች የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ወይም ሌሎች ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ስብሰባዎችን ለማስተናገድ እንዲሁ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ ዋና ዋናዎቹን ጠቀስኩ እንጂ የመንግስት አካል ጋር ሳይደርሱ የሚከሰቱ እገዳዎች ብዙ ናቸው፡፡ ይህን ነው የቅድመ ሳንሱር ቅድመ ሳንሱር የምለው፡፡ እራሳችን በራሳችን ወይም በቅርብ ጓደኞቻችንም ሳንሱር እንደረጋለን፡፡ ከምናወራው ሰው ጋር ሃሳባችንን ሙሉ በሙሉ ለመናገር የማንደፍር ወይም አይምሯችን ውስጥ እየቆረጥን የምናስቀረው ከሆነ እራሳችንን ሳንሱር አደረግን ማለት ነው፡፡ ፅሁፍም ፅፈን ከሆነ በቅርብ የሚያይልን ሰውም ከመንግስት ሊመጣ የሚችለውን ቅጣት ስጋት ‹ይቺን አስወጣት› የሚል ከሆነ እሱም ሳንሱር እያረገን ነው፡፡ በርግጥ የቅድመ ሳንሱር ቅድመ ሳንሱር መበራከት ከመንግስት ጋር ላለመሳፈጥ፤ ከመንግስት አይን ራቅ ብሎ ሰላማዊ ኑሮ ለመምራት የሚደረግ ጥረት እና የመንግስትን ዱላ ከመፍራት የመጣ ነው፡፡ መንግስትም እንዲህ አይነት አካላት መኖራቸውን አጥብቆ ይፈልጋል፡፡ ባለፈው ፓርላማ ላይ ጠ/ሚ ኃይለማርያም ሲናገር እንደሰማነው የማተሚያ ቤትን እና የመሰብሰቢያ አዳራሽን አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ ችግሩን የማተሚያ ቤቱ እና የአዳራሽ ባላቤት እንደሆነ እና ጠያቂውም ከነሱ ጋር እንዲጨርስ እንጂ የመንግስት ጥፋት እንዳይደለ ተነግሯል፡፡

አሁን በሃገራችን እንደምናስተውለው ጥቂት ደፋሮች ወይም ፍርሃታቸውን ያሸነፉ ብቻ ናቸው ሲፅፉ ወይም ሲያወሩ የምንሰማው፡፡ የአብዛኛዎቻችን ስራ ደግሞ ስራዎቻቸውን አይተን/አዳምጠን የገቡበት ገብተን ጎበዝ! ጀግና! በርታ! ማለት፤ ሲታሰሩ ካለንበት ፈቅ ሳንል ዘላቂነት የሌለው አይዞህ! አይዟችሁ! እንላለን-ሄድን ልንጠይቃቸው እንኳን አንፈቅድም ወይም ድፍረቱ የለንም፤ ሲሰደዱ ደግሞ እንሳደባለን፡፡ በቃ ይሄ ነው የአብዛኞቻችን የስራ ድርሻ - ተመልካችና ፈራጅ፡፡ መመልከትና መተወን በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡

ሃሳቤን ለመጠቅለል ያክል ጥቂት ፍርሃታቸውን ያስወገዱትን ብቻ እንዲናገሩ ወይም እንዲፅፉልን ብቻ ከምንጠብቅ እራሳችንም የድርሻችንን በመወጣት፤ እራሳችንን ወይም በቅርብ ያሉትን ጓደኞቻችን ማስፈራራት፣ ተስፋ ማስቆረጥና ሳንሱር ማድረጋችንን ብንተውና ሁላችንም ፍርሃታችንን በተወሰነ መጠን አሰወግደን ሃሳባችንን ያለፍርሃት መግለፅ ብንጀምር እንዲሁም በመጠኑ ህገመንግስቱ ላይ የተፃፈውን መብታችንን እንኳን ለማስከበር ቆርጠን ብንነሳ ለውጥ ማየት የምንችል ይመስለኛል፡፡

# የስደተኛው ማስታወሻ ከአውሮፓ

**(ይህ ከአንድ ስደተኛ የተላከልን ተከታታይ ጽሑፍ ኹለተኛው ክፍል ነው፡፡)**

## ናፍቆት

እስክትመጪ ያልኩሽ ስትመጪ ከምትደናገሪ ቀድመሽ እንድትዘጋጂ ብዬ ነው፡፡አንቺ ብቻ ሳትሆኚ ማንም ለመሰደድ የሚቋምጥ ሁሉ እስኪሰደድ የስደትን እውነተኛ ገፅታ ይወቅ ለማለት ነው! እስኪመጣ ይወቅ! እስክትመጣ ትወቅ! እስኪመጡ ይወቁ! ስለ አውሮፓ አእምሯችሁ የሚነግራችሁ ወሬ ውሸት ነው፡፡ስለአውሮፓ ሰዎች የሚነግሯችሁ ሃሰት ነው፡፡ አትመኗቸው፤ እወቁና ራሳችሁ  ፍረዱ፤ እወቁና ተዘጋጅታችሁ ወደ አውሮፓ ኑ ለማለትም ጭምር ነው፡፡

ከአገርሽ እንደወጣሽ ብዙ ፈተና ይጠብቅሻል፡፡ አንዱ ፈተና ናፍቆት ነው፡፡ የማይናፍቅሽ ነገር የለም፤ አንተ ብቻ ነህ የምትናፍቀኝ አንተን ካገኘሁ ምንም አይናፍቀኝም የምትይውን አነጋገርሽን የምታፍሪበት እዚህ መጥተሽ ያቺ ለማየት የምተፀየፊያት ሽሮ ከሁሉ በላይ ስታሳሳሽ ነው፡፡ አምርረሽ የጠላሽው ወይም እጅግ የሰለቸሽ ሁሉ እየፀፀተሽ ይናፍቅሽ ይጀምራል፡፡ የምትወጃቸውንማ ማናገር እስኪያቅትሽ ድረስ ሲቃውን አትችይውም፡፡ ቤተሰብሽን፣ ጓደኞችሽን ስታናግሪ ያኔ እኔን ከተለያየን ከሶስት ሳምንት በኋላ ስደውልልሽ እንደሆንሽው ትሆኛለሽ፡፡ ናፍቆት አንደበትሽን ይሸብበዋል፣ ናፍቆት ቃልሽን ያጠፋዋል፣ ናፍቆት አልቃሻ ያደርግሻል፡፡ ስለዚህ መለስ ቀለስ የምትይበትን የስደት መንገድ መምረጥ ይኖርብሻል፡፡

እኔን ናፍቆት እንዴት እንዴት እንዳረገኝ ልንገርሽ፦ እንደገባሁ ትውልደ ፓኪስታን ከሆነ አንድ ጎልማሳ ላይ የተከራየኋት ጠበብ ያለች ቤት ነበረችኝ፡፡ ረከስ ያለችውን መርጬ ነበር የተከራየሁት፡፡ ሳሎን እና ኩሽና የጋራ ሲሆን መኝታ ቤት እና ሽንት ቤት የግል ነበር፡፡ ከዚህች ቤቴ በተቃራኒው የከተማው ክፍል የሚገኘውን ዩኒቨርሲቲ ለመድረስ ከአንድ ሰአት በላይ እጓዝ ነበር፡፡

ጉዞው ረጅም ቢሆንም ለውጪው ዓለም አዲስ በመሆኔ ምክንያት በየመንገዱ የማየው ትዕይንት የጉዞውን ርዝመት እንዳይታወቀኝ አድርጎኝ ነበር፡፡ ሁሉም ነገር ይገርመኝ ስለነበር አንዱን አይቼ ሳልጨርስ ሌላው እየተተካ እንዲችው እየተቁለጨለጭኩ ነበር የምመላለሰው፡፡ ጠዋት ጠዋት በምድር ውስጥ ባቡር ላይ ተጠቅጥቀውና ተኮራርፈው ከሚጓዙት ፈረንጆች ውስጥ ጋዜጣ የማያነብ ሰው ማግኘት ይከብዳል፡፡ ይህን ሳይ ባቡሩንም፣ አንባቢውንም፣ ጋዜጣውንም እመኛለሁ፡፡ አገሬ ላይ እንዲህ አይነት ትዕይንት መቼ ይሆን የማየው እያልኩ፡፡ ከፈረንሳይ ለጋሲዮን ወደ ልደታ በምድር ውስጥ ባቡር እየሄድኩ እለታዊዋን አዲስ ነገር ጋዜጣን እያነበብኩ ብጓዝ፤ ማይጨው አደባባይ ወርጄ መስመር ስቀይር ከባቡሩ ጉርጓድ መውጫ በር ላይ እንደ ስሙ የዘመነውን አዲስ ዘመንን ገዝቼ ወደ ልደታ ለመሄድ ስሽጋገር እያልኩ እመኝ ነበር፡፡ (ይህን እየተመኘሁ ትምህርት ቤት ደርሼ ኢሜሌን ስከፍት አንዱ ወዳጄ አንድ መልዕክት አስቀምጦልኝ አገኘሁ፡፡ የሰላም ያርገው ብዬ ብከፍተው 'ዘንት' ይላል፤ የምድር ውስጥ ባቡሩን ብንሰራው እንኳ ጋዜጣውን ርሳው ማለቱ ነበር፡፡)

ምኞት ብቻ ሆኜ ሁሌ ስለአገሬ ሳስብ ስለምውል የባሰ የአገሬ ሰው እየናፈቀኝ ሄደ፣ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራቶች ውስጥ አማርኛ ያወራሁት በስልክ ብቻ ነበር፡፡ ስጓዝ ከምመኛቸው ክስተቶች ባሻገር የአገሬን ሰው ለማግኘት አይኔ ይቅበዘበዛል፡፡ አንድ ሁለቴ አበሻ የመሰሉኝን ሰዎች ሰላምታ አቅርቤ ተሸውጃለሁ፡፡ ነብር ዝንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን አይለቅም የሚለውን ነገረ መጽሃፍ ቅዱስ አውቃለሁ ብዬ ሰላምታ ሳቀርብ ሰምቼ በማላውቀው ቋንቋ መልስ አገኘሁና አረፍኩት፡፡ ይጥቆርም ይቅላም፣ ይርዘምም ይጠርም፣ ይወፍርም ይክሳም፣ ሴት ብትሆንም ወንድ፤ ሳይናገር ሳይጋገር የማየው ሰው ከሃበሻ ምድር እንደፈለሰ ለማወቅ አልቸገርም የሚል ትዕቢት ነበረብኝ፡፡ ከሁለቱ ሙከራዎቼ ቡሃላ ግን ትዕቢቴም ተነፈሰና ሙከራዬን አቆምኩ፡፡ ስለሆነም ወደዘወትር ምኞቴ ተመልሼ ያየሁትን ጥሩ ነገር ሁሉ፤ ይህ ኢትዮጵያ በኖረ፣ ይህን አገሬ ስመለስ እሰራዋለሁ እያልኩ መጓዜን ቀጠልኩ፡፡

በነዚያ የትኩስነት ወራት ባንዳቸው ቀን ሁሉን ነገር እየተመኘሁ አንድ ፌርማታ ላይ ቆሜ በብቸኝነት እየተከዝኩ አውቶቡስ እጠብቃለሁ፡፡ ከክፍል እንደወጣን ከባድ ዝናብ ይጥል ነበር፡፡ ዝናቡ እስኪያባራ ስጠብቅ ዘወትር የምጓዝበት ባቡር ጥሎኝ ሄደ፡፡ የሚቀጥለው እስኪመጣ ላለመጠበቅ በአውቶቡስ ልሄድ ወስኜ እየጠበቅኩ ስላንቺ

አስባለሁ። ባትመጪና እኔ ብመለስ እያልኩ እመኛለሁ። አንቺን አስጥሎ ያሰደደኝ እውነት አሁን አሁን አልጥምህ እያለኝ ተቸግሬያለሁ። የትምህርቱ ቀላል መሆን አሁንን እንዳላስብ አድርጎ ስላለፈውና ስለወደፊቱ እንድጨነቅ አድርጎኛል።

እኔና አንቺ የተፈጠርነው ለመፈቃቀር ነበር፤ በሚገባ ተፈቃቀርን። እነዚያ የማታውቂያቸው አለቆቼ ለምን ይሆን የተፈጠሩት? እነሱን ሳስባቸው ይገርመኛል። ልጆች ወልደዋል፤ ሚስት አላቸው። ታዲያ ከአጋራቸው ጋር ይፈቃቀራሉ ማለት ነው? እኔ እንደሚመስለኝ መፈቃቀር ሲያቅተን ነው የሰዎችን ፍቅር ለመበጠስ የምንነሳው። መፈቃቀር ሳንችል ስንቀር ነው ለምድር አሜኬላ የምንሆነው። እኔ አንቺን ያፈቀረው ልቤ ሌላ ሰው ላይ ክፋትን ይፈፅማል ብዬ አላምንም። አንቺን ያፈቀርኩ ዕለት ጥሩ ሰው መሆኔን አውጅኩ። አንቺን ያፈቀርኩ ዕለት ለማንም ይማልጎረብጥ ጥሩ ዜጋ መሆኔን አረጋገጥኩ። አንችን ከማፍቀሬ በፊት ግን በልምዱና በዕውቀቴ መጠን የምመራ ከንቱ ሰው ነበርኩ።

የማፍቀርን ጥቅም የረሱትን እነዛን አለቆቼን እያሰብኩና ልቦና እንዲሰጣቸው እየተመኘሁ አውቶቡስ ጥበቃዬን ቀጥያለሁ። እንደድንገት አይኔን ወደጎኔ ላክ ሳደርግ የብርጭቆ ቂጥ የሚመስል መነፅሩን ገርግዶ አንድ አይነ ውሃው ከአበሻ ወገን የሚመስል ሰው ከጎኔ ቆሞ እሱም እንደኔ አውቶቡስ ይጠብቃል። ልብ ብዬ ሳየው የማውቀው የማውቀው ሲመስለኝ በድፍረት ወደ ልጁ ሄድኩና ሰላምታ ሰጠሁት።
ለሰላምታዬ ምላሽ በአማርኛ ሲመልስልኝ ልጨብጠው የዘረጋሁትን እጄን አስረዝሜ ተቃቀፍን። ሳሚ እባላለሁ አለኝ ስሜን ነገርኩት። ከዚያም ብርቅ ሆነብኝ መሰል ብዙ ጥያቄዎች ጠየቅኩት። ከሶስት ጓደኞቹ ጋር እንደሚኖር ሲነግረኝ ወደሚሄድበት ይዞኝ እንዲሄድ ለመንኩት። ትንሽ አቅማማና እሺ አለኝ። እያወራን ተያይዘን ወደመኖሪያቸው ሄድን።

አውሮፓ ላይ የአገርሽን ሰው ለማግኘት ያለሽ እድል እንደ አመጣጥሽ ይወሰናል። ጥገኝነት ልትጠይቂ ከመጣሽ በቀላሉ ከወገኖችሽ ጋር ትገናኛለሽ። እንዲያ ሲሆን አንቺን የሚናፍቅሽ ናፍቆት እኔን ገጥሞኝ ከነበረው የአማርኛ ናፍቆት ይለያል። ያን ቀን ያገኘሁት ልጅ ሌላ ቦታ ጓደኛ ለመጠየቅ ሄዶ እየተመለሰ ነበር። አብሬው ስጓዝ እጅግ ደስ ብሎኝ ነበር። ለምን ደስ እንዳለኝ የማውቀው እኔ ብቻ ነኝ። አገርሽ ላይ ተቀምጠሽ ይህን እያነበብሽ 'ናፍቆት ነው' ብልሽ እንደምፀት እንደምትቆጥሪው ይገባኛል።

ከሳሚ ጋር በተስማማነው መሰረት ሰፈሬ መውረዱን ተውኩትና አብሬው ሄድኩ። መኖሪያቸው ከከተማው ጥቂት ወጣ ይላል። እንደደረስን እንደ ተማሪ ዶርም ከተደረደሩ ክፍሎች ውስጥ አንዱን ከፍቶ ገባን። በክፍሉ ውስጥ ሁለት አልጋዎች አሉ። ማንም ሰው ክፍሉ ውስጥ አልነበረም። ማንም አለመኖሩን ሲያይ ስልኩን አወጣና ደወለ። 'የት ነው ያላችሁት?'በስልኩ ውስጥ ትንሽ አወራና ስልኩን ዘጋ። 'ቦርሳህን እዚሁ አስቀምጠውና እንሂድ ከጓደኞቼ ጋር ላስተዋውቅህ' አለኝና ለብሶት የነበረውን የብርድ ጃኬት አውልቆ ወደ በሩ አመራ። ሕንፃው ባለ አንድ ፎቅ ነበር። የነበርንበት ክፍል አንደኛው ፎቅ ላይ ስለነበር ወደ ምድር ወረድንና የጓደኞቹን ቤት አንኳኳ። ከውስጥ ደራ ያለ ወሬ ይሰማል፤ ብዙ ኢትዮጵያውያን እንዳሉ በማወቁ የበለጠ ደስ አለኝ።

የሚገርመው ይህን ያህል ሰው እንደምወድ ያወቅኩት ከአገሬ ስወጣ መሆኑ ነው። አንቺም ዛሬ አገርሽ ላይ ሁሉንም ባይሆንም የፈለግሺውን መውደድና ማድረግ ትችያለሽ፤ ግን በእጅ የያዙት ወርቅ ስለሆነ ምንም አታደርጊም። እዚህ ስትመጪ ግን እንዲህ በሆንኩ ኖሮ፣ ያን ባደርግ ኖሮ፣ ይህን በጎበኘሁ ኖሮ እያልሽ መቆጨት ብቻ። በዚህች አጭር የህይወት ጉዞ እንደ ኢትዮጵያዊ ተፈጥረሽ እሱን ንቀሽ ያልሆንሽውን ለመሆን እየጣርሽ የሰውን ስታባርሪ እንዲሁ ማለፍ የሚያስቆጭ አይመስልሽም?

ሳሚ ከሶስቱም ልጆች ጋር አስተዋወቀኝ። ስናወራ አመሸንና መሽትሽት ሲል ስልካቸውን ተቀብዬ እየፈነደቅኩ ወደ ቤቴ አመራሁ።

## የምቾት ውስጥ ፍዳዎች

መንግስቱ ሃይለማርያም በዘመናቸው የነበረውን ወጣትና ማህበረሰቡን ሲተቹ 'ወደ ማሰልጠኛ ሲወሰድ ገና ጦር ሜዳ ሄጄ ጥይት ይገለኛል ብሎ በማሰብ ከሚበር መኪና ላይ እየዘለለ እየወረደ የሚሞት ወጣት ነው የሚላክልን' ብለው ነበር። ብሄራዊ ውትድርና በደፈናው እንደመቅሰፍት ተቆጥሮ ስለነበር ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ዘመቻው እንዳይሄዱ ለማድረግ በምድር ውስጥ፣ በጎተራ፣ በድብኝትና በቋት ውስጥ ይሸሽጓቸው እንደነበር ይነገራል።

ውትድርናን አንዴ ማህበረሰቡ አውግዞታልና በዘመኑ የነበረውም ወጣት ተልዕኮውን ለመጥላት ምክንያት አላስፈለገውም። ለዚህም ነበር ተልዕኮውን ለማምለጥ ሲባል በያንዳንዱ ሰው ይደረግ የነበረው መስዋዕትነት ከተልዕኮው በላይ ሲያስከፍል የነበረው።

ውዴ- የአሁኑ ዘመን እርስ በርስ ጦርነት የለም፣ ብሄራዊ ውትድርናም የለም። ማህበረሰቡ በደፈናው የሚጠላውም ልጆቹንም የሚያስደብቅ ነገር ዘንድሮ የለም። ግን ልጆቹን እንደወጡ እያስቀረ ያለ ክፉ መቅሰፍት መልኩን ቀይሮ መጥቷል። ይህም መቅሰፍት ስደት ነው። ዛሬ ወደ ደቡብ አፍሪካ ጫካዎች፣ ወደ ሰሜን አፍሪካ በረሃዎች እና ወደ ምስራቅ አፍሪካ በባሕር ላይ በጅምላ ማለቅ ለኢትዮጵያውያን ስደተኞች የተለመደ ክስተት መሆኑን በየሚዲያው ላይ ትሰሚያለሽ፡ወጣቱም ቢሆን በስደቱ ውስጥ ስላለው አደጋና እልቂት ማሰብም ሆነ ላለመሰደድ የሚጠቅሰው ምክንያት አያስፈልገውም። በቃ ሁሉም በጭፍን መሰደድን ይመርጣል። ባገኘው ቀዳዳ ተጠቅሞ ነቅሎ አገር ጥሎ ይኮበልላል።

ለምሳሌ ባለፈው የተፈጠረውን ክስተት ላስታውስሽ። በ2004 አጋማሽ ላይ የተፈጸመ አሳዛኝ ስደት ነው። በተሳቢ መኪና ላይ በተጫነ ኮንቴይነር ውስጥ ታጭቀው ከናዝሬት የተነሱት 70 የሚሆኑ ወገኖቻችን ወደጅቡቲ ያመራሉ። ጅቡቲ ደርሰው ከዚያም ወደ አረብ አገር ለመሻገር አልመው። ስለሁኔታው ጥቆማ የደረሰው ፖሊስ ተሳቢውን መከታተል ይጀምርና በአንድ የአፋር በረሃ ውስጥ ደርሶበት መኪናውን ያስቆመዋል። የፖሊስን መምጣት ቀድሞ ያስተዋለው ሹፌር መኪናውን አቁሞ ይሸሻል። የክልሉ ፖሊስ በአፋር በረሃ ውስጥ ተሳቢውን ሲደርስበት ከኮንቴይነር ውስጥ ካሉት ሰዎች ውስጥ 11 የሚሆኑት ጅቡቲን ለዘላለም ሳያዩዋት አልፈዋል። ፖሊሶቹ የኮንቴይነሩን በር ለመክፈት ጥቂት ደቂቃዎችን ቢዘገዩ ኖሮ ደግሞ ሁሉም መንገደኞች በመታፈን ያልቁ ነበር።

አሁንም በተመሳሳይ ወቅት ሌላ አሳዛኝ ክስተት ሰምተናል። የጉዞአቸው አላማ ከአገራቸው ተነስተው ደቡብ አፍሪካ መድረስ የነበረው ኢትዮጵያውያኑ ስደተኞች በታንዛንያ በኩል ህገ-ወጥ በሆነ ሁኔታ ወደ ማላዊ ያቋረጡት በጀልባ ነበር ። ይሁንና 28 ሰዎች ብቻ የመጫን አቅም ነበራት የተባለችው ጀልባ ላይ ወደ 60 የሚጠጉ ስደተኞች በመጫናቸው ጀልባዋ መገልበጧ ነበር በወቅቱ የተዘገበው። ይህች ኢትዮጵያውያንን የጫነች ጀልባ በማላዊ ሃይቅ ላይ በመገልበጧ 47 ኢትዮጵያን ወንዶች፣ ሴቶችና ህጻናት ሞቱ። የአካባቢው ነዋሪዎችም የኢትዮጵያውያኑን አስከሬን ከሃይቁ ዳርቻ ጥቂት ሜትሮች ርቀት ላይ በተቆፈረ ጉድጓድ ውስጥ በጥድፊያ ቀበሩት። ኢትዮጵያዊ ክብር አያስፈልገውም ብለው ማስ ማስ አድርገው የቀበሩትን አስከሬን ለኢትዮጵያውያኑ ክብር የነፈገ ድርጊት ነው ያለው ቀይ መስቀል እንደ አዲስ ስራዓትን የጠበቀ ቀብር እንዲፈጸምላቸው ቢያደርግም ኢትዮጵያውያኑ ግን እንደወጡ ቀርተዋል።

አለም ዓቀፍ የስደተኞች ማሕበር (IOM) እንደሚለው በኤደን ባህረ ሰላጤ ላይ በአመት ከሁለት ሺ በላይ ኢትዮጵያውያን ያልቃሉ። በጥቅምት ወር 2005 መጨረሻ አካባቢም ከሶማሊያ ቦሳሶ ወደብ ሁለት ስደተኞችን የጫኑ ጀልባዎች ይነሱና ጉዟቸውን ወደ የመን ሸጉዋ ያደርጋሉ። ሁለቱም ጀልባዎች ሸቡዋ ወደተባለው የየመን ጠረፍ እየተቃረቡ ሳለ አንዱ በመስጠሙ ምክንያት የ72 ኢትዮጵያውያን አስከሬን በባሕሩ ላይ ተንሳፎ እንደተገኘ ታውቋል። በዚህ የመስመጥ አደጋ የሞቱት ኢትዮጵያውያን ቁጥር በትክክል የማይታወቅ ሲሆን 72 የተባለው ባህሩ ላይ ሬሳቸው ተንሳፎ እና ባህሩ ወደዳር ተፍቷቸው የተገኙት ብቻ ናቸው።

በደርግ ዘመን እንደ ሃጢአት ተቆጥሮ የነበረው ብሄራዊ ውትድርና በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጊዜ እንደ ጀብድ ሲቆጠር አይተናል። የትኛው ጦርነት ምክንያታዊ እንደሆነ መጠየቅ የማያስፈልገው የእኛ ሰው ጥሩን ከመጥፎ የሚለየው እንዴት እንደሆነ ግራ ያጋባል። በመንግስት በኩል የሚነገረውን በማመን ነው እንዳይባል 'ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር' የሚለው የደርግ ድምፅ አይሰማም ነበር። ስለዚህ የእኛ ሰው ጦርነትን እንደመጥፎ ይቆጥራል ማለት ይከብዳል።

ውዴ- በየጦር ግንባሩ ይሞት ከነበረው ያልተናነሰ ወጣት በስደት መንገድ ላይ እንደወጣ በሚቀርበት ጊዜ ላይ እንደደረስን ይሰማኛል። ታዲያ ይህ እየታወቀ ልጆቹን ወደ ጦርነት ሲልክ እንዲያ ሲያለቅስ የነበረ ማህበረሰብ ወደ ስደት ሲልክ እንዲህ የሚስቀው ለምን ይሆን? በጦርነቱ ውስጥ መሞት፣ መማረክ አሊያም ማሸነፍ ይኖራል፤ በስደቱም ውስጥ መሞት አለ፣ በአካል ሳይሞቱ በመንፈስ መሞት አለ፣ ታስሮ መሰቃየት፣ መጠረዝ፣ በምቾት እየኖሩ ራስን ማጣት የመሳሰሉት እንግልቶች አሉ። ጦርነት ገዳይ እንደሆነ እሙን ነው ነገር ግን ስደቱም የዕድል ጉዳይ ካልሆነ በቀር ገዳይ ነው። ከብዙሃኑ ስደተኛ ጥቂት የታደሉ ይሳካላቸው ይሆናል እንጂ በዘፈቀደ ተሰደው

ሰው የሚሆኑ በጣም ጥቂቶች ናቸው። ታዲያ ይህ ፀሃይ የሞቀው ዕውነት እያለ ስደትን እንደበጎ ቆጥሮ ሁሉም ሰው ለምን አልሰደድ እንዲል ያደረገው ማን ይሆን?

ውይ የጀመርኩልሽን ታሪክ ረስቼ በገዛ ራሴ ብሶት ውስጥ ይዤሽ ጠፋሁ አይደል? ኢትዮጵያውያን እንደኑሯቸው የተለያየ የስደት መንገድ አላቸው። ከፍተኛ ገቢ ያላቸው የሚሄዱት የስደት መንገድ፣ መካከለኛ ገቢ ያላቸው የሚጓዙበት የስደት መንገድ እና በድህነት አረንቋ ውስጥ የተዘፈቁ የሚሄዱበት የመሰደጃ መንገድ ለየቅል ነው። የመንገድ ፈተናው እንደገቢያቸው ቢለያይም የስደት መዳረሻቸውን ከረገጡ ቡሃላ ግን ፈተናው ለሁሉም እኩል ይሆናል። በቦይንግ ተንፈላሶ የተሰደደውም በባሕር ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ እያለ የተሰደደውም እኩል የሚዳኙበት የስደት ህይወት ላይ እኩል ይቀመጣሉ። አብዛኞቹ ከአገራቸው የተሰደዱበት ምክንያት ምን እንደሆነ ቢገምቱትም በውል የሚያውቁት ግን ጥቂቶች ናቸው። የስደት ምክንያታቸው በአገራቸው ተስፋ መቁረጣቸው ቢሆንም የብዙዎቹ ተስፋ መቁረጥ ግልፅ አይደለም። ምን ተስፋ እንዳስቆረጣቸው ሳያውቁት እንዲሁ ተስፋ ይቆርጡና አንዳንዶቹ የተደላደለውን ኑሯቸውን በትነው ለስደት ይነሳሉ፣ አንዳንዶቹ ጅምር ልፋታቸውን አጨናግፈው ለስደት ይዳረጋሉ የተቀሩት ደግሞ የበይ ተመልካች መሆን ያቅታቸውና አገር ጥለው ይፈረጥጣሉ። ግን ከነዚህ አንዱም ለመሰደድ እንደምክንያት ስለማይቆጠር ሁሉም የስደት ህይወትን ተደላድሎ ለመጀመር ፈተና ይሆንባቸዋል።

ኢትዮጵያውያን በአምባገነናዊ ስርዓት ስር እየማቀቁ፣ እጅግ ባልተስተካከል አስተዳደር ውስጥ እየተጎሳቆሉ፣ በሙስና የተበከለ ስርዓት ውስጥ እየዳከሩ፣ በከፋ ድህነትና ርሃብ ውስጥ እየኖሩ እንደሆነ ቢታወቅም እነዚህ ምክንያቶች ግን አንድን ዜጋ ለስደት ሊዳርጉት እንደማይችሉ ይነገራል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በሰኔ 1943 ስለጥገኝነት ያስተላለፈው ድንጋጌ ማን ጥገኝነት እንደሚገባው በግልፅ አሳውቋል። በዚህ ድንጋጌ መሰረት ሰዎች የጥገኝነት መብታቸው ይከበርላቸዋል። በዚህ አንቀፅ መሰረት የኢትዮጵያውያን የጥገኝነት ማመልከቻ ሲዳኝ ስደታችን ከድንጋጌው ጋር ተያያዥነት የለውም ተብሎ በተለያዩ አገሮች መንግስታት ይታመናል። የምንሰደደው አገራችን ላይ ለመኖር ፈርተን ሳይሆን የተሻለ ሕይወት ሽተን እንደሆነ እና መንግስታችንም አንፃራዊ ሰላምና ዲሞክራሲን እንደመሰረተ ይነግሩናል።ከዚህ በሁዋላ የምነግርሽ ያጋጠሙኝ ታሪኮችም እነዚህን ህግጋትና አስተሳሰቦች የመሸወድና እንደማንኛውም ሰው ተቆጥሮ የመኖር ትግሎች ናቸው። ጥገኝነት የማግኘት ጥበቦች የሚል መጽሃፍ የሚያጽፉ ብዙ ገጠመኞች እዚህ አሉ። ሁሉም ግን ኢትዮጲያዊነት የት ደረስ እንደረከሰ የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው። እነሳሚ አብረው የሚኖሩበትን ቦታ እና ጓደኞቹን እየለመድኩኝ ስመጣ ብዙ ታሪኮቻውን ለመስማት እድሉን አግኝቻለው። ይህንን አይነቱን ውስጥን የሚነካ ታሪክ ለአንቺ ካልነገርኩ ለማን እነግራለሁ?

# ኹለት ዓይን፣ ኹለት ዕይታ

በኢዙና አሕመድ

ጊዜው ለውጡ ከተካሄደ አምስት ዓመት በኋላ ነበር፡፡ በወቅቱ የነበረው መንግስት ባጎናፀፈው የመወዳጀትና የመተባባር ባህል መሠረት ሃይማኖቶች ሕብረ ዝማሬ ያስተጋባሉ፡፡ የዱቤዎች ፈጣን ምቶችና የከበሮዎች ቀስስተኛ ድለቃዎች ተደማምረው የራሳቸው የሆነ ሜሎዲ ፈጥረዋል፡፡ ዘማርያን በአንድ በኩል በሚያስረቀርቀው ድምፃቸው ዓለማቸውን ይቀጫሉ፡፡ መንዙማዎች በሌላ በኩል ያስተጋባሉ፡፡ ትላልቅ እንጨቶች የተጣለባቸው እሳቶች ይርመሰመሳሉ፡፡ ግቢው ጭስ በጭስ ሆኗል፡፡ ቄስና ሼህ አራጆች ሰንጋዎቻቸው ጥለው በትልቁ ጎራዴ ይበርካሉ፡፡ ደሞች በየአቅጣጫው ቦይ ፈጥረው ግቢውን ደም በደም አድርገውታል፡፡ የስጋ ዘለላዎች በተዘረጉት ቀጫጭን አጠናዎች ላይ ተዘርግተዋል፡፡ በሌላ አቅጣጫ ደግሞ የሀገሬውን የባህል ጭፈራና ዝማሬ በጋራ ሆነው ያቀልጡታል፡፡ ከግቢው ውጪ የፈረስ ውድድር እየተካሄደ ነው፡፡ ጎረምሶች የገና ዱላቸውን ይዘው የገና ኳሳን ይጠልዛሉ፡፡ ሰዎች በእያንዳንዱ ነገር የመሳተፍ ውዴታ ውስጥ ተጠምደዋል፡፡ ይህ ሁሉ ግርግር በአካባቢው ማኅበረሰብ ትብብር ተሰርቶ የተጠናቀቀው በደቡብ ሸዋ በሐይቆችና ቡታጀራ አውራጃ የሚገኘው መስጊድ ለማስመረቅ ነበር፡፡

አባቴ በዛን ወቅት በብሔራዊ ስሜት ነህሉሎ ነበር፡፡ ከፍተኛ የብሔራዊ ስሜት ጡዘት ውስጥ ገብቶ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ‹የአሞራ አገር ዋርካ፣ የእስላም አገር መካ› እንዳልተባለ አሁን ደግሞ ሙስሊሞች እንደክርስቲያን ወንድሞቻቸው እንደአንድ ዜጋ ተቆጥረዋል፡፡ እንደሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታ የመታየቱ፣ የማሸሚጠጡና በጎሪጥ የመመልከቱ ብሎም የመፀየፉ ስርዓት ካከተመ አምስት ዓመት ደፍኗል፡፡ አባቴ ለውጡ ባስከተለው የማኅበረሰብ ግንኙነት ምክንያት ተደስቶ ሴት ልጁን ‹ኢትዮጵያ› አላት፡፡ ባያውቀው ነው እንጂ ለልጁ ትልቅ የዕድሜ ልክ የቤት ሥራ ነበር የሰጣት - ነፍሱን ይማረውና፡፡ የሙስሊሞች እንደኢትዮጵያዊ በእኩል ዓይን የመታየት የቤት ሥራ፡፡ ይሄው የቤት ሥራው ሳይሠራ ፈተና ሆኖብን ምንም ለውጥ ሳይካሄድ እንዳለን አለን፡፡ በሁለት አቅጣጫ የተወጠረ ስስ ገመድ ይዘን አንዳች የአንዳችንን ከኢትዮጵያዊነት መዝገብ ለመፋቅ ጥረት አያደረግን፡፡ ይገርማል አባቴ በአዬዎቹ ጊዜ የነበረው ስርዓት ዳግመኛ ይከሰታል ብሎ ቢያምን ኖሮ ይህንን የዕድሜ ልክ የቤት ሥራ ከልጁ ዘንድ ባላስቀመጠ ነበር፡፡

ሙስሊሞች በኢትዮጵያውነታቸው ላይ የመለየት ሥራ የሚሰሩት መንግስታት ብቻ አይደሉም፡፡ የባለፉት መንግስታት ሰበካ ያጀሉ አንዳንድ የአዬው ዘመን አመለካከት ያላቸው በማኅበረሰቡ ውስጥ ተሰግስገው የጥላቻ አመለካከታቸውን በማኅበረሰቡ ላይ ያሰራጫሉ፡፡ እስቲ አንድ ታሪክ ላጫውታችሁ፡፡ ለታሪክ ሁሉ ነገር ታሪክ ነው፤ እዚህ አገር ከመወለዳችን በፊት ታሪክ፣ ከተወለድን በኋላ ታሪክ፣ አፈርም ስንለብስም ታሪክ፣ ሌላ የለንም ታሪክ፣ ታሪክ…፡፡ እዚህ ላይ ግን ኢትዮጵያ በድሮ ማንነቷ አንቱ ከሚባሉት ሀገራት ውስጥ አንዷ መሆኗን አልክድም ችግሩ ግን የድሮ ማንነት አሁን ባለንበት ሁኔታ ላይ ለመመንዘር ስንሞክር ነው፡፡

ወደ ታሪኬ ልግባ… በአንድ ወቅት እህቴ ‹ኢትዮጵያ› ትምህርቷን ለመማር አንድ ስሙን በማልጠቅሰው የትምህርት ተቋም ውስጥ የመመዝገብ ሂደት እያከናወነች ነበር፡፡ መዝጋቢው ዕድሜያቸው ጠና ያሉ ባጠቃላይ እምቢ አላረጅም ብለው እዛ ተቋም ውስጥ የቀሩ አዛውንት ናቸው፡፡ ለምዝገባ ስሟን ጠየቋት፡፡ መለሰችላቸው ‹‹ኢትዮጵያ አህመድ…›› ያደፈውን መነፅራቸውን ወደ ግንባራቸው ከፍ አድርገው የጥላቻ ንግግራቸውን አወረዱት ‹‹… ቆይ ቆይ አባትሽ ምን እየሰራ ነው?! ሁለት የማይቀላቀል ነገር ያቀላቅላሉ፡፡ ኢትዮጵያ ብሎ አሕመድ የማይሆን ነገር! ሰው እንዴት ዘይትና ውሃን ለማቀላቀል ይሞክራል?! ኤዲያ! ዛሬ ደግሞ ምንድነው የምታሰማኝ…›› ይህን ሁሉ ተብትበው ኢትዮጵያ ከአሕመድ ጋር ደብለው መመዝገቡን ግን አልተዉትም፡፡ ሥራቸው ነውና፡፡ ቆይ እስቲ ሰዎች ኢትዮጵያ ከአሕመድ ጋር ወዳጅነት መፍጠር አይችሉም እንዴ? መቼም ይህ ስያሜ የሚያስገርመው ክርስቲያኑን ብቻ አይደለም ሙስሊሙንም ጭምር እንጂ! አንዳንዱ አገሩን ከዚህ ውጪ አድርጎ የሚስል ‹‹ይቺ በምኗም ተምሳሌት የማትሆን አገር¡… እንዴት አባትሽ ይህንን ማንንም የማይወክል ገዳይ ስያሜ ያወጣልሻል?›› የሚለውን ጨረር ይለቃል፡፡ አንዳንዱ ደግሞ አፉን እያጣመመ ‹‹ተሃድሶ ተካሂዷል ማለት ነው!›› ይላል፡፡ አንድ ሰው ተወልዶ እትብቱ የተቀበረበት ያደገበትና ስንት ውጣ ወረድ ያሳለፈበት አካባቢ ብሎም አገር የመውደድ ተፈጥሮአዊ ግዴታ ያለበት ይመስለኛል፡፡ ሰው መቼም የተወለደበት አካባቢ ነውና የሚመስለው፡፡

## የኢትዮጵያዊነት ስፌት

ሙስሊሞች በኢትዮጵያ ውስጥ በሌላ ዓይን መታየት ከጀመሩ ሰነባብተዋል፡፡ በትንሹ አበበና አሕመድ ትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸውን ቦታ ብንመለከት ለየቅል ነው፡፡ ያው አበበ በየመጽሐፍቱ ‹‹በሶ በላ!›› እንደተባለ ይዘከራል፡፡ አሕመድ ደግሞ በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ምሳሌያዊ ቦታም የለውም፡፡ ስለዚህ አበበና አሕመድ ኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸው እንድምታ የተለያየ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊና አረባዊ፡ በአንድ አገር ውስጥ ሁለት የተለያዩ ዜጎች አንዱ የእናት ልጅ ሌላው የእንጀራ እናት ልጅ ሆነው የሚታዩ መምሰል ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡

በዚች እኛን ዜጎችዋን በምታስደምም አገር ሙስሊሞችን እንደመጤ የማየቱ እንድምታ ታውቆም ይሆን ሳይታወቅም በቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ሲገለፅ ይስተዋላል፡፡ ቴዎድሮስ እንደአገር ገንቢ፣ አሕመድ ግራኝ እንደአገር አፍራሽ፡፡ ቴዎድሮስ ከቱባው የኢትዮጵያ አንድነት ጋር ሲገኛኝ በአንፃሩ ደግሞ አህመድ ግራኝ ወራሪና በታኝ የሚለውን የታሪክ ስያሜ ይለጠፍበታል፡፡ እነዚህንና የመሳሰሉትን እንድምታዎች ከቅርብ ክርስቲያን ዘመዶቻችን ሳይቀር ሲገለፅ ይታያል፡፡ እስቲ በአንድ ወቅት ከአንድ ወዳጄጋ ስለኢትዮጵያዊነት ስንጨዋወት የነገረኝን ላውሳላችሁ፡፡ በክርክራችን መሃል ወዳጄ ምርር ብሎ ማውራቱን ቀጠለ፡፡ ‹‹እኛ (ክርስቲያኖች) ከሳውዲ ስትሰደዱ ተቀብለን ስላስጠለልን ነው እንዲህ የምትሆኑት፤ የዛን ጊዜ በእንግድነት ባንቀበላችሁ እና ባናስተናግዳችሁ ኖሮ ኢትዮጵያዊ አትሆኑም ነበር›› አለኝ፤ በጣም ተናደድኩ ኢትዮጵያዊ ደም እያለኝ እንደ መጤ በመቁጠሬ በጣም ስሜታዊ ሆንኩ፡፡ ‹‹ቆይ ቆይ ወዳጄ! አንተ እያልከኝ ያለኸው መጤ ነህ ነው፡፡ በዛን ጊዜ ከአሁኗ ሳውዲ የመጡትን እንግዶች ተቀብለው በእንግድነት ያስተናገዱትኮ ያንተውም የእኔም አያቶች ነበሩ፡፡ ክርስትናም እስልምናም የመጡት ከውጭ ነው፤ ያንተም የእኔም አያቶች እዚህ ነው እትብታቸውን የቀበሩት! ማንም አረባዊ ማንም እስራኤላዊ አይደለም፡፡ እምነቱ ይለያይ እንጂ…›› አልኩት፡፡ ዕድሜ ለETV! በእኛ የኢድ በዓል እቺን የማትቀየር ኢትዮጵያዊና እስላማዊ ግኑኙነት ሁሌ እንደደሰኮረ ነው፡፡ ከዓመት ዓመት እንደዲሪቶ እየቀጣጠሉ አንዲት ሃባ የማይለወጥ የጃጀ ድስኮራ!! ይህ ድስኮራ በደንብ ስርዓት ባለው መልኩ በትክክለኛ መልዕክት ተላልፎ ሁሉንም ባኮራ ነበር፡፡ ነገር ግን የእያንዳንዱ ነገር ላይ ላዩ የሚያውቁት የETV ጋዜጠኞች በግልብ እያሉት እንደተለመደው ያልሆነ እንድምታ በማኅበረሰቡ ላይ ይፈጥራሉ፡፡

ኢትዮጵያዊነት በአፄዎቹ ጊዜ ሲሰፉ ሁሉን የኢትዮጵያ ቀለማት እንዳያካትት ተደርጎ ነው፡፡ ሕብረ-ቀለማዊነትን በማያስተናግድ በአንዲት ትንሽ ማንገቻ የታሰረ ትንሽዬ የሕፃን ቁምጣ፡፡ በአሁን ጊዜ ሁሉም ዜጎች እዛ ቁምጣ ውስጥ እራሳቸውን ሲከቱ ማንነታቸው በዜሮ የሚባዛበት የተንሸዋረረ ዜግነት ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ይህን ትንሽዬ ኢትዮጵያዊነት እንደማያካትታቸው ሲያውቁ ሌላ ተቃራኒ ፅንፍ በመፍጠር ማንነታቸውን ያስከብራሉ፡፡ የተለያዩ የማንነት ፅንፎች መፈጠራቸው ለሀገሪቷ ዕድገት ማነቆ ነው የሚሆነው፡፡ “የተከበሩ ሚች አባታችን” ‹‹የአክሱም ሃውልት ለወላይታ ምኑ ነው?!›› ነበር ያሉት፡፡ ይገርማል! ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከሰሜን እስከ ደቡብ ባለው የማንነት መገለጫ እንዲኮራ አባታዊ ምክር መስጠት ነበር ከመሪ የሚጠበቀው ፡፡ የአክሱም ሃውልት ለወላይታው የማንነት መገለጫ ካልሆነ፣ የላሊበላ አብያተ ክርስታኒያት ለሙስሊሞች እንደራስ ቅርስነት ካልታየ፣ የገዳ ስርዓት ለአማራው መኩሪያ ካልሆነ፣ የሐረር ግንቦችና የነጃሺ መስጊዶች ለክርስቲያኑ እንደራሱ ቅርስ ካልተቆጠረ ኢትዮጵያ ምኗን አገር ሆነች፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያዊነት ሁሉኑም የሚያካትትና ኢትዮጵያውያን ደግሞ ሆደ ሰፊ ሊሆኑ ይገባል ባይ ነኝ፡፡

ወቅቱ በጃንሆይ ገዜ ነበር፡፡ ከጉራጌ ቀቤና የተገኙት የቃጥባሬ ሼህ ጥልቅ የሆነ ኢትዮጵያዊ ስሜት ነበራቸው፡፡ ይህንን ብሔራዊ ስሜት እምነቱ ውስጥ የተለያዩ እስላማዊ እንዲሁም ኢትዮጵያዊ የሆነ ማንነትና ባህል እንዲፈጥሩ አድርጓቸዋል፡፡ የቃጥባሬ ሼህ ኮፍያ ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ? ኮፍያው ላይ ከሦስት የተለያዩ ቀለሞች ማለትም አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ የተዋቀሩ ሲሆን አምስት ክቦች ይታያሉ፡፡ አምስቱ ክቦች አምስቱን የእስምልና ማዕዘናት ሲያመለክቱ ሶስቱ ቀለማት ደግሞ ኢትዮጵያነት ያመለክታሉ፡፡ ይሄ ነው ኢትዮጵያዊነት በእምነት ውስጥ! ሁሉንም የሚያካትት! አሁንማ ሁሉም ጥግጥጉን ይዞ ሌላውን የማያካትትና ሌላውን ከአገራዊ አንድነት የሚፍቅ ተግባራት እያከናወነ በቃ የሚለው ጠፍቷል፡፡ አርቆ አሳቢ ድሮ ቀረ፡፡ ሁሉን ነገር ማጦዝ ነው በተንሸዋረረና ሁሉን በማያካትት እይታ….

ጊዜው ቴዎድሮስ ‹‹እምቢ ለአገሬ!›› ብሎ ራሱን የሰዋበትና አጤ ዮሐንስ በተገኘው አጋጣሚ ስልጣኑን ተረክቦ ሙስሊሞች ሃይማኖታቸውን በሀይል እንዲቀይሩ ከፍ ሲልም ያለ ርህራሄ የሚቀላበት ወቅት ነበር፡፡ በዛን ወቅት በጎጃም ሀገረ ገዢ የነበረው ይህንን አስገድዶ ክርስቲያን የማድረግ ዘመቻ በሚገርም ጥበብ ተወጣው፡፡ የሃይማኖት ቅየራው ሂደት የሚካሄደው በዋነኝነት ስጋ በማብላት ነበር፡፡ ሕዝበ ሙስሊም በተሰበሰበበት ቄሱ ከመጋረጃ ፊት ሼኩ ከመጋረጃ በስተኋላ ሆነው ሰንጋውን አጋደሙት፡፡ ከዛማ ከመጋረጃ በስተጀርባ የሚገኙት የሃይማኖት አባት በሬውን ሸልተው ከበጋረጃው ፊትለፊት ለሚገኙት የሃይማኖት አባት ማረጃውን አቀበሉት፡፡ ቄሱ ማረጃውን ወደ ላይ ከፍ አደርገውት ‹‹ይሄው በስመ አብ ብለን ባርከነዋል›› አሉ፡፡ ይህንን ሚስጥር የሚያውቁት ጥቂት

የሃይማኖት አባቶችና ባለስለጣናት እንዲሁም የዛ አካባቢ የሙስሊም ማኅበረሰብ ነበር፡፡ ይሄ ነው ጥበብ፣ መተባበሩ በአካባቢው ማኅበረሰብ ለዘላለም ሲወሳ ይኖራል፡፡ ምንም እንኳን ከዛሬ 100 ዓመት በፊት ሙስሊሞችን ሃይማኖት የማስቀየር ስርዓት በቀጥተኛ መንገድ ቢገባደድም አሁንም ሙስሊሙን ሸባ የማድረግ፣ ሸባ አድርጎም ከሃይማኖቱም የማራቅ ሂደት እንደቀጠለ ነው፡፡ ቀጥሎ እንመልከተው፡-

## ጭንቅላቱን በለው

እንደሚታወቀው እንደኢትዮጵያ ባሉ አገራት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ አባት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ለቤተሰቡ የመሪነት ሚና ይጫወታል፣ የገቢ ምንጭም ነው፣ ቤተሰቡን ከአደጋ ይከላከላል፣ ባጠቃላይ የቤተሰቡ ራስና ምሰሶ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በአሁን ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ሙስሊሙ የራሴ የሚለውን መሪ እንዳይኖረው ተደርጓል፡፡ መሪ ለመሆን ከፍ ከፍ የሚሉት ታዳጊ መሪዎች ጭንቅላቻቸው እየተመቱ ቤታቸው ይቀመጣሉ፡፡ ሌላው ደግሞ እንኳን አንድ ማኅበረሰብ ለመምራት ይቅርና አህያዎችን በሰልፍ መምራት የሚያቅተው ሰው የሸሆና ሐጂ ካባ ይከናነብና የዚህ ከአፍሪካ በብዛቱ ሦስተኛ የሆነ ሕዝብ ባልፈለገው መልኩ ‹‹መሪ›› ተብሎ ይቀመጣል፡፡ በሌላ ወገን ከሃይማኖቱ አልፎ በሀገሪቱ ጉዳዮች ላይ የሁሉም አገር የሆነችን ኢትዮጵያ ወክሎ አገራዊ ሚና ይጫወታል፡፡ ይሄ ነው ሁለት የተለያየ ዕይታ… በሙስሊሞች በኩል የመሪነት ሚና እንዳይጫወቱ ተቋማቸው ሸባ ሆኗል፡፡ ይህ ተቋም ሕጋዊ ዕይታው ከአንድ ኩባንያ የማይተናነስ በየዓመቱ ፍቃዱን የሚያድስ ተቋም ነው፡፡ ከግዴታዎቹ ውስጥ በዋነኝነት በዓመት ሦስቴ ለበዓላት ራሱን ማሳየትና የማያውቁትን ፖለቲካ መዶስከር ነው፡፡ በሙስሊሞች ዘንድ አንድ ነገር ጠብ ማድረግ የተሳነው ተቋም፡፡ ከባለሙያዎች ይልቅ ባህላውያን የሚበዙበት ተቋም፡፡ ካለመሪ አንድን የአገሪቷ እኩሌታ የሚሆን ማኅበረሰብ ለመምራት ይቅርና አንድን ቤተሰብ መምራት አይቻልም፡፡ በአሁኑ ጊዜ የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ሙስሊሙ አውራው እንደተመታበት የንብ ቀፎ ተበታትኖ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ሙስሊሞች ያለመሪ እንዳይቀሳቀሱ ተብትቦ የያዛቸው ገመድ ሊፈታ ይገባል፡፡

## ወደ አንድ ጎን ያዘመሙ የሲቪል ሰርቪስ ተቋማት

እንደሚታወቀው አገራችን ኢትዮጵያ ሃይማኖትና መንግስትን መለያየት እንደመፍትሄ ተመለክታ ትግበራውን ከጀመረች እነሆ ግማሽ ምዕተ አመት ሊሞላን ጥቂት ነው የሚቀረን ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት አንድ የመንግስት ተቋም ተሂዶ ስለአንድ ሃይማኖት የሚያመለክቱ ጥቅሶችንና ፎቶዎችን መመልከት የተለመደ ነው፡፡ አንዳንዴ የሰቀላ ፉክክር በግልፅ የሚካሄድ ከፍ ሲልም የሰቀሉት የሃይማኖት ጎራ ለማገልገል የተቆረጠ ነው የሚመስለው፡፡ አገሪቷ የምትመራው በዓለማዊ ሕግ ሆኖ ተቋማቱ ግን ሲወርድ ሲዋረግ የመጣውን ሃይማኖታዊ ማንነቱ እንደተጠበቀ ነው፡፡ ባጠቃላይ መለስተኛ የሃይማኖት ተወካዮች ይመስላሉ፡፡ ይህ ነው እንግዲ መገለጫው ወደ አንድ ጎን ያዘመሙ ነገር ግን ሁሉንም እናስተናግዳለን የሚሉ የመንግስት ዓለማዊ ተቋሞች፡፡ አንዳንዴ እንዲሁም የራሳቸውን የሚያቀነቅን ሲመጣ ነገሮች በሚያስገርም ፍጥነት ይጠናቀቃሉ፡፡ አመለካከታቸውን የማይደግፍ ሲመጣ ግን ጉዳዩን መጎተት፣ ማመናጨቅ ሲበዛም መሳደብ የራሳቸው ነው፡፡ ምንም እንኳን ባብዛኛው ኢትዮጵያዊ ፈሪሃ አምላክ መሆኑን ባልክድም አለማዊነት ሁላችንም የሚያግባባ መስሎ ይታየኛል፡፡

## ተቋም የለሽ ማድረግ

ሙስሊሞች ተቋም የለሽ ማድረግ ከትልቁ መጅሊስ እስከ ትናንሽ መድረሳዎች ድረስ የዘለቀ ነው፡፡ እስላማዊ የሆኑ ተቋማት ሲቋቋሙ በጥርጣሬ ዓይን ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ ለሙስሊሙ ስለየማይገሰሰው ሕገመንግስት ይሰበካል በሌላው ወገን ደግሞ የራሱን የሃይማኖት አጀንዳ እንዲያከናውን ባለሙሉ መብት ይሆናል፡፡ በቅርቡ በመቋቋም ሂደት ላይ እያለ ባልታወቀ ምክንያት የተቋረጠው የዘምዘም ባንክ በዐብይነት የሚጠቀስ ነው፡፡

## መሠረተ ልማት ማሳጣት

ይህ ጉዳይ ለአንዳንዶቹ ላይዋጥ ይችላል ነገር ግን ሕዝበ ሙስሊሙን ከአፄዎቹ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ከመሠረተ ልማት ማራቅ አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡ ዓለም አቀፍ እስላማዊ ግብረሰናይ ድርጅቶች እንዳይገቡ በሩን መከርቸም የሌላው ዓለምአቀፍ የሚሽነሪዎች ተቋም እንዲገቡ የጥሪ ደውሉን በተደጋጋሚ መምታት የተለመደ ሆኗል፡፡ ባጠቃላይ ሙስሊሞች በመሠረተ ልማት አመካኝቶ የሚሽነሪዎች ሰለባ ማድረግ በግልፅ የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ ታዲያ ምን ይደረግ በንፁህ መጠጥ ውሃ እየተመጣ!

## በሩን መከርቸም

እንደሚታወቀው እስልምና ዓለም አቀፋዊ ሃይማኖት ነው፡፡ በየትኛው የዓለም ቦታዎች እስልምና አይገኝም ማለት ይከብዳል፡፡ ሙስሊሞች ደግሞ የጋራ የሆነውን ችግሮቻቸውን በዓለም አቀፍ ስብሰባዎችና አጀንዳዎች ላይ ይፈታሉ፡፡ ይህ ዓለም አቀፋ እስላማዊ ግኑኙነት ከትንሽዋ ጅቡቲ እስከ ብዙ ሙስሊም ሕዝብ የሚገኝባት ኢንዶኔዥያ ያካትታል፡፡ ኢትዮጵያ ግን በብዛቱ ከአፍሪካ ሦስተኛ የሆነ የሙስሊም ሕዝብ እያላት በዓለም አቀፋዊ መገናኛ ብዙሐን ‹‹የክርስቲያን ደሴት ነኝ!›› ብላ በሩን ከዘጋች ሰነባብታለች፡፡ ሌላው ደግሞ ከግኑኙነቱ አልፎ የዓለም አቀፍ የግኑኙነቱ ኃላፊ ሲሆኑ ሙስሊሙ ግን ምንም ዓይነት ምልክታ እንዳያሳይ በማፅቀብ ታጭቋል፡፡ ማፅቀቡ መቼ ያበቃል? ዋናው ነገር ሠላም፣ ዋናው ነገር ጤና፣ ዕድሜ መስታወት ነው እናያለን ገና! ተብሎ የለ…

## በመጨረሻም

እምነቶች ጌታቸውን የሚጠሩበት ስያሜ ወይም ቋንቋ ቢለያይም መሠረታቸው ግን አንድ ነው፤ እሱም በመልካም ፀባይ ያዛሉ፣ ከክፉ ምግባር ይከለክላሉ እንዲሁም ለራስህ የምትወደን ለወንድምህ እንድትወድ ያዛሉ፡፡ ኢትዮጵያ ደግሞ የሦስቱ አብርሃማዊ ሃይማኖች ቤት ናት ብዬ ብገልፀው ማጋነን አይሆንም፡፡ ሦስቱም በሰላማዊ መንገድ የራሳቸውን አሻራ የጣሉባት አገር ናት ኢትዮጵያ፡፡

የኢትዮጵያና የኢስላም ግንኙነት ከሌላው ሀገር በተለየ መልኩ የቆየ ነው፡፡ ኢስላም ለዓለም ከመሰበኩ በፊት ኢትዮጵያ ነው የከተመው፡፡ የሰላት ጥሪ አዛን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስረቀረቀው የሐበሻ ልጅ የሆነው ቢላል ነው፡፡ እናትና አባታቸውን ያጡት ነቢዩ መሀመድ በኢትዮጵያዊው እናት እንደ እናት ክብካቤ ተደርጎላቸው አድገዋል፡፡ ነቢዩ መሐመድ መካና መዲና አልመች ሲላቸው ሙሉ እምነታቸው ኢትዮጵያ ላይ ጥለው ባልደረቦቻቸውንና ልጆቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ ሰደዋል፡፡ እንግዳ ተቀባይ የሆነው የሀገራችን ሕዝብ ብቸኝነት እንዳይሰማቸው መልካም እንክብካቤና እምነታቸውን በነፃነት እንዲያከናውኑ ፈቅደዋል፡፡

እንደሚታወቀው ውጭ ያሉ አካላት የራሳቸውን ኢ-ኢትዮጵያዊ አመለካከት ለማስረፅ እስከ አሁን ያልተቀረፈው ድህነትና ድንቁርና መፍትሄ ዘየድን በማለት እየሰረጉ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም አንድነት ከሀይልም በላይ መሆኑንና ድህነትና ድንቁርናን ደግሞ በራሳችን ቀናኢ መፍትሄ አሻሽለን ልናሳያቸው ይገባል፡፡ ምክንያቱም ከውጭ የሚመጣ ‹‹መፍትሄ›› የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አለውና፡፡ በአንድነት ስንሠራ ነው ለውጥና ልማት የሚያመጣው ነገርግን ሁሉንም ያላማከለ ወደ አንድ ጎን የተንጋደደ ተግባር እንደ ግመሏ ጆርባ በአንድ ጎን ያበጠ ይሆናል፡፡ አንዱ አድጎ ሌላው ቢተኮስ ምንም ለውጥ ባያስከትልም እንኳን ያደገው ዕድገት ይገታል፡፡

በጽሑፌ ማገባደጃ ላይ በወሎ ክፍለ ጠቅላይ ግዛት ጎጃም በሚባለው አካባቢ በ1897 እ.ኤ.አ የተወለዱተ የታላቁን አሊም ሸህ ሰዒድ መሐመድ ሳዲቅ ድንቅ ንግግር ልጥቀስና ልሰናበት፡፡
*‹‹ … እኛም የአንድ አገር ሕዝብ የሆነው ኢትዮጵያኖች፣ ያንድ ቤት ሰው ስለሆነ ደካሞች በኃይለኞች እንዳይደመሰሱ፡፡ ….የሰው ልጆች በአዕምሮ ተመስርተው እንዲኖሩ የተመሰረተውን ሀይማኖት ለመለያየ መሳሪያ ማድረጋችን ቀርቶ እንዲሁ እንደተጀመረው መተሳሰራችን እየበረታ እንዲሄድና ለራስህ የምትወደውን ለወንድምህ አድርግ በተባለው መሠረት እርስ በርሳችን ተፋቅረን ያለው ለሌለው አካፍሎ… ያልተማረው ተምሮ ሕግን አክባሪ እንድንሆን እንመኛለን…››* ~ (ደሴ ከኢድ አልፈጥር ሰላት በኋላ በ3/6/1954)

# የዓለም ሃይማኖቶች እና ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት

*መግቢያ*

*አንቀጽ ፲፰*

*እያንዳንዱ ሰው የሐሳብ የህሊናና የሃይማኖት ነጻነት መብት አለው፤ ይህም መብት ሃይማኖቱን ወይም እምነቱን የመለወጥ ነጻነትንና ብቻውን ወይንም ከሌሎች ጋር በኅብረት በይፋ ወይም በግል ሁኖ ሃይማኖቱን ወይም እምነቱን የማስተማተር በተግባር የመግለጽ የማምለክና የማክበር ነጻነትን ይጨምራል።*

*አንቀጽ ፲፱*

*እያንዳንዱ ሰው የሐሳብና ሐሳቡን የመግለጽ መብት አለው፤ ይህም መብት ያለጣልቃ ገብነት በሐሳብ የመጽናትንና ዜናን ወይም ሐሳቦችን ያላንዳች የድንበር ገደብ የማግኘትን፣ የመቀበልን ወይም የማካፈልን ነጻነትን ይጨምራል።*

*እንዲህ ጎን ለጎን አጠጋግቶ ያስፈራቸው ዓለም አቀፉ የሰብኣዊ መብቶች ድንጋጌ* (UDHR) *ነው። ይሁንና በድንጋጌው በቅደም ተከተል እንደመስፈራቸው ሲስማሙ አይስተዋልም። በአንድ ያለማችን ክፍል ያለ የማመን መብቴ ተደፈረ የሚል ግለሰብም ሆነ ቡድን በሌላው የዓለማችን ክፍል የሚገኙ ሰዎችን የመናገር ነጻነት ሲደፈጥጥ ይስተዋላል። ሌላው የመናገር መብቴ ገደብ የለውም የሚል ደግሞ የሌላውን ሰው የማመን መብት ሲጥስ እና በአማኒው እሴቶች ሲያፌዝ ተመልክተናል። ይህ እሰጥ አገባ በተለያዩ እምነቶች፣ በአማኞች እና እምነት የለሾች፣ ባስ ሲል ደግሞ አንድ እምነት አለን ብለው በሚናገሩ ቡድኖች መካከልም ይስተዋላል። በቅርቡ በሀገረ አሜሪካ በ‹ዩቲዩብ› የተለቀቀ አንድ ቪድዮን ተከትሎ በተነሳው ብጥብጥ ምክንያት ይህ ርዕሰ ጉዳይ በዓለም ዙርያ መነጋገሪያ ሆኗል። ዐሳብን በነጻነት መግለጽ እስከምን ድረስ ነው? እስከመቼ እምነቶች የነውጥ እና ሁከት መነሾ ምክንያት ሆነው ይቀጥላሉ? የሚሉ ጥያቄዎች በብዙዎች በሕሊናቸው እንዲያመላልሱ አድርጓል።*

*በሀገራችን ዓለም አቀፉን ወጀብ የተከተለ ትርምስ ባይፈጠርም አንዳንድ ብልጭታዎች መታየታቸው አልቀረም። በተለይ ሁለቱ የየሀገራችን ሰፊ ተከታይ ያላቸው እምነቶች (እስልምናና ክርስትና) ‹‹ያለመሪ›› የሃይማኖት አባት በተቀመጡበት በዚህ ወቅት ጉዳዩ እጅግ አሳሳቢና የሰከነ ውይይትን የሚጠይቅ ነው። የኢሕአዴግ መንግስት በተለመደ ስልቱ እኔ ብቻ ላውራ ስለሚል ቁሱም ሼኩም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ካህናት እንዲሆኑ ይፈልጋል።በዚህም ምክንያት እንኳን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጉልህ ተጽዕኖ ያላቸው እምነቶች ይቅርና ሌላው ግለሰብም ይናገር፣ የተለየ አስተሳሰብ ይኑረው፣ ያን ይገልጽ፣ ያንፀባርቅ ዘንድ አልተፈቀደለትም። ለዚህ ማሳያ እሩቅ ሳንሄድ ይህች ጦማር በኢትዮጵያ እንዳትነበብ የደረሰባት ተደጋጋሚ እገዳ ማሳያ ነው። ይህ ጽሑፍ ከሰው ልጅ መሠረታዊ እሱነቱ ጋር የተያያዙት እምነት እንዲሁም ዐሳብ መግለጽን እንዴት ማየት አለብን የሚለውን በመዳሰስ ለውይይት መነሻ የሚሆን ዐሳብን ለማቅረብ ይሞክራል፣ ለማብራራት የሚሞክረው ‘ይህ እምነት ልክ ነው፣ ያኛው ጸብ አጫሪ ነው ወይም እምነቶች ሁሉ ልክ ናቸው የሚለውን ሳይሆን የተለያየ እምነቶች ያሉበት ሀገር (በተለይ ኢትዮጵያ) እንዴት ትኑር የሚለውን ይሆናል።የውይይታችን ማጠንጠኛም ከዚህ ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንደሚያተኩርም ተስፋ አደርጋለሁ።*

## *መቻቻል እና የተዛባ ትርጉሙ*

*አብዮታዊ ዴሞክራሲ ካመጣብን ቃላትና የተዛቡ ዐሳቦች አንዱ ‘መቻቻል’ ነው። ብዙ ጊዜ የእምነት ጉዳዮች ሲነሱ የመንግስት ሚዲያዎች ይህንን ቃል ደጋግመው በመጥራት ግጭቱን የሚያበርዱ ይመስላቸዋል። መቻቻል መቻቻል፣ መቻቻል፣. . . . ይህ ግን ከእምነቶቹ ዶግማ አንጻር ከተመለከትነው እጅጉን የተንሸዋረረ ሆኖ እናገኘዋለን። በመሠረቱ ሁለት የተለያዩ የእምነት አስተምህሮዎች ሊቻቻሉ አይችሉም፤ ተቻቻሉ ከተባለም አንዱ አንዱን ካልጨቆነ በስተቀር ሌላ ሁለቱንም ያልሆነ ሦስተኛ አዲስ እምነት ነው የሚሆኑት። ይህ ለሌሎች ጉዳዮች ሊሠራ እንደሚችል የተለያዩ ንደፈ-ሐሳቦች ሰፊ ማብራሪያን ይሰጣሉ። ነገር ግን ብዙ አዝማናትን ለተሻገሩት በብዙ ክርክር ላለፉት እንደ ክርስትና እና እስልምና ካሉ እምነቶች ጋር ግን አይገጥምም። አንድ በህልዎተ እግዚአብሔር በሚያምን እና ይህች ዓለም አስገኝ፣ ፈጣሪ የላትም ብሎ በሚያምን መካከል የተቀመጠ ዐሳብ ካለ ሌላ አዲስ አስተሳሰብ ነው። ለምሳሌ ፈጣሪ ሊኖርም ላይኖርም ይችላል ብሎ እንደ መጠርጠር ያለ። በክርስትና “እግዚአብሔር*

አንድ ልጁን ለሁሉ ቤዛ አድርጎ እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶታል" ሲል በእስልምና ደግሞ በግልጥ "አላህ አይወልድም፣ አይወለድም" ይላል። ታዲያ የመንግስት ባለስልጣናት እንዴት ነው መውለድ እና አለመወለድን ለማቻቻል ጥረት የሚያደርጉት???

ይህንን እንደ ጥቁር ከሰልና እንደ ነጭ ወተት ያለ ልዩነት በማድበስበስ፣ ለእምነት ተቋማት ተቋማዊ ነጻነታቸውን በመስጠት በቡድን አሊያም በግል የፈለጉት እምነት እንዲከተሉ ከመፍቀድ ይልቅ የቄሳራዊ ጳጳስነት (Caesario papal) መንገድን መከተል ይዟል። ይህም እምነት ተቋማቱን በቀሚስ ለባሽ ካድሬዎች በእጅ አዙር ለመምራት የሚደረግ ጥረት ነው። በአደባባይ ለሚዲያ ቀለብ ይሆን ዘንድ የካህናትቱን መስቀል ሲሳለሙ እና በየመስኪዱ ሲሰግዱ በማሳየት እኛም በእምነት ጥላ ስር ነን (ምእመን ነን) ለማለት ይሞከራል። ይህም በየእምነቱ፣ በአማንያን አለመመራት፣ ተቋማቱን በተገቢው መንገድ ለማስተዳደር ባለመቻላቸው ምክንያት ብሶት፣ ቁጭትና ጥያቄዎች እንደፈጠሩ አድርጓል። ለዚህ እንደምሳሌ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን ጥያቄዎች ማንሳት ይቻላል።

መንግስት አብዮታዊ ዴሞክራሲ ነው የምከተለው (አብዮታዊ ዴሞክራሲ በራሱ ከእምነቶች ጋር ብዙ የሚያላትም ገጾች ቢኖሩትም ዛሬ ከተነሳንበት ዐሳብ ጋር የሚሄደውን ብቻ ይዘን እንሄዳለን።) ቢልም እምነቶችን በተመለከተ በሕገ መንግስቱ ላይ እንደሰፈረው "መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፤ ሃይማኖት በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም" ማለቱ በእምነቶች ላይ ያለው አመለካከት ኢ-ሃይማኖታዊ ሴኩላሪዝም (irreligion or secularism) መሆኑን በግልጽ ያሳያል። በዚህም ምክንያት ሃይማኖቶች ከብዙ መንግስታዊ አካላት (መንግስት ከሕዝብ ተነጥሎ እንደተለየ አካል ተቆጥሮ) ከአገልግሎት ሰጪ፣ ከትምህርት ተቋማት፣ ከመንግስት ሚዲያ ከመሳሰሉት. . . ሲገለሉ በተግባር አይተናል። ብዙዎቻችንም የሁከት፣ የብጥብጥ ስጋት ስላለብን ጉዳዩን በዝምታ ይሁንታን አጎናጽፈነዋል። ይህም ለችግሮች መፍትሔ የመሆን አቅም ያላቸው የእምነት በጎ እሴቶች እንደአማራጭነት እንኳን እንዳይታዩ አስገድዷቸዋል።

በመሠረቱ ሴኩላሪዝም እንደመድህን መቀበል ተገቢ አይደለም። በየትኛውም መስፈርት የኢ-ሃይማኖታዊነት (ሴኩላሪዝም) ሕይወት መርህ ሳይንሳዊ አይደለም፤ ሃይማኖታዊ የሕይወት ዘዬም እንዲሁ ሳይንሳዊ አይደለም። ሳይንስ;- ሴኩላሪዝም ከአማኒነት እንደሚሻል ማሳየት አይችልም ምክንያቱም ጉዳዩ ከሳይንስ በላይ (beyond science ) ነውና። የሃይማኖት ኅልዮት በአመክንዮ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል የታመነ ነው። ይህንንም ማድረግ፣ መጠየቅ የቅኖች መንገድ ነው። በሴኩላሪዝም እውነት እና በሃይማኖት እውነት መካከል ያለው ውዝግብ ግን በመደበኛ ሎጂክ ሊፈታ አይችልም። ይህ እውነታ በሁለት እምነቶች መካከልም ለሚካሄድ ክርክርም አይሰራም። የእስልምናን ስህተት ለማሳየት መጽሐፍ ቅዱስ (Christian scriptures) መጥቀስ እንደማለት ነው።ለክርስቲያን መጽሐፍት ከቅዱስ ቁራን እና ሌሎች የበለጠ ስልጣን መስጠት ኢ-ምክንያታዊነት ነው፤ ከመጽሐፈ ሞርሞንም ቢሆንም የበለጠ የስልጣን የበላይነት የለውም።

ይህ ሴኩላሪዝምን እንደገለልተኛ የማየት አካሄድ የተዛባ ነው። ምክንያም ሴኩላሪዝም ይህ ዓለም ከየት እንደመጣ እና ወዴት እንደሚሄድ የራሱ ትንታኔ አለው። ይህንን ካደረገ ከሌሎች ሃይማኖቶች ምን ለየው? ከጸበኞች መሀል አንዱን መርጦ ዳኛ አደርጎ መሾም ሲከፋ ደግሞ "እነዚህን አመጸኞች ግረፋቸው" ብሎ ልምጭ እንደመስጠት ያለ ነው። ሴኩላሪዝም የተውኔቱ አካል (entity) ነው እንጂ አዘጋጅ፣ አጋፋሪ ወይም ጸሐፌ ተውኔት ሊሆን አይገባውም። መንግስት ሴኩላሪዝምን እንደ ኅልዮት የማበረታታት መብት የለውም፤ በጉልበት ታንክ ተደግፎ ግን ተችሏል። ይህ ግን አላዋጣንም። ታሪካችንም ይህንን አያስተምረንም። ሀገሪቷ ጠንካራ ማኅበራዊ ጅማት ስላላት እንደሀገር መቀጠል ችላለች፤ ነገን ግን መተንበይ አንችልም።

## ከሴኩላሪዝም ባሻገር

ታዲያ ሴኩላሪዝም መፍትሔ ካልሆነ መፍትሔው ምንድን ነው የሚለውን ማጥናት ይገባል። በመሰረቱ ወደድንም ጠላንም አምልኮ ከሰው ልጅ ጋር የተሳሰረ፣ ከስሜት በላይ የሆነ አቅም ያለው ኃያል እንደሆነም ተረድተናል።ብዙዎች ፍልስፍናን እና ሐሰሳን ለሕሊና ሰጥተው ለሃይማኖት ደግሞ ተረትን ይሰጣሉ፤ ከቀደሙት እጅግ የበዙት ደግሞ ሃይማኖት ፀረ-ሕሊና ወይም ህየንተ ሕሊና ሆኖ የሚቆም ነገር አይደለም፤ መልዕልተ ሕሊና ነው እንጂ ነው ይላሉ። ከሕሊና በላይ ነው እንደማለት። በዚህም ምክንያት ሃይማኖት እንደ ተበላ ዕቁብ የምንዘነጋው እንደ አረጀ አፈጀ ልማድ አሽቀንጥረን የምንጥለው ነገር አይደለም። ከዚህ ይልቅ የእምነትን መሠረታዊ ባሕርያት በማጥናት መፍትሔ መፈለግ ይበጃል።

የትኛውም እምነት ሁለት መልኮች አሉት፤ የመጀመሪያው ይህች ዓለም ከየት እንደመጣች፣ ሰዎች በምድር ላይ እንዴት መኖር እንዳለባውቸውና ከሞት በኋላ ደግሞ ተስፋቸው ምን እንሆነ የሚያትት ነው፡፡ ይህም በየእምነቱ ሊቃውንት የሚተነተን ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተለየ መብት (privilege) የሚሰጥ ሌሎችን የሚያገልል (exclusivist) የተንኳሸነት ባህርይ ያለው ነው፡፡ ይህም ሕዝብ አሕዛብ፣ አማኒ ኢ-አማኒ፣ የተጠመቀ ያልተጠመቀ ብሎ የአዳምን ዘር የሚከፋፍል ነው፡፡ ይህ ልዩነት በመቀጠሉ በማኅበረሰቡ ውስጥ ከፍ ያለ ቦታ የሚያገኙ እና የገንዘብ ጥቅም የሚያገኙ የእንጀራ ገመዳቸው ከእነዚህ የእምነት ተቋማት ጋር የተሳሰረ ሰዎች ደግሞ ልዩነቱን የበለጠ እንዲሰፋ ተግተው ይሰራሉ፡፡እውቁ ጸሐፊ ሰልማን ሩሽዲ የቁጣ መፈልፈያ (outrage industry) የሚላቸው ዓይነት ነገር ናቸው፡፡ እነዚህ ኃይላት እምነትን የወግ አጥባቂዎች ማጎሪያ፣ የቁጡዎች መነሐሪያ፣ ኋላቀር፣ ማኅበረሰባዊነትን የሚንድ፣ ከሕሊና ውጪ ያለ (anti-rationale) ያደርጉታል፡፡

ሁለተኛው የእምነት ገጽ ደግሞ በተቃራኒው ሁሉን ሰብስቦ የሚያቅፍ፣ ስለሰብዓዊነት የሚሰብክ፣ የሰው ልጆችን የሚያስተሳስር ነው፡፡ ለበጎ ምግባር ሰውን የሚቆሰቁስ፣ ያጣው እንዲያገኝ፣ ያለው የበለጠ እንዲኖረው፣ የወደቀ እንዲነሳ፣ የታመመ እንዲድን፣ ለፍጹምነት ናፍቆት ያለው (nostalgic) ነው፡፡ በአጠቃላይ በነገረ መለኮት ዕውቀት ከመራቀቅ ይልቅ ስለፍቅር አብዝቶ የሚጨነቅ ነው፡፡ በእኛ ማኅበረሰብ ይህ መልክ የመጉላት አዝማማሚያ አለው፡፡ አቡነ ዘበሰማያት አንዴ መዝለቅ የማይችሉ ወይም "ያላህ ያረቢ አትበለን እምቢ" ብለው በእምነት ከማይመስላቸው ጋር ሳይቀር በፍቅር የሚኖሩ፤ ከአሕዛብ ጋር አትብላ! ከካፊር ጋር አትወዳጅ! የሚለውን ስብከት አልፈው (transcendence) ተካፍለው የሚበሉ ኢትዮጵያውያን ተቆጥረው አያልቁም፡፡ ሐዘኔታን የተላበሰ፣ ለድሆች የሚራራ፣ በደልን የሚጠየፍ ድሀ ሲበድል፣ ፍርድ ሲጓደል የሚቆጠቁጠው ነው፡፡ እንደማሕተመ ጋንዲ እና እማሆይ ትሬዛ ያሉ ታላላቆች ካልሆነ ብዙዎቹ የሃይማኖት መሪዎች ያልኖሩበት ነው፡፡

የእምነት ሰው ሁለቱንም መልኮቹን ይዞ የሚዞር ነው፡፡ አንደኛ ሲጎላ አንደኛው ደግሞ ሲደበዝዝ የሚኖር፡፡ በዚህም ምክንያት ዓለማችን ታንክና መድፍ በመስቀል የሚባርኩ ጳጳሳት፣ የጀሐድ ጦርነት የሚያውጁ ዑላማዎችን አስተናግዳለች፤ ብዙ ደም ፈሷል ብዙ ንብረትም ጠፍቷል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ሙሉ ሕይወታቸውን ለድሆች የሰጡ፣ ለፍትሕ እና ለእኩልነት የቆሙ፣ ድምፅ ለሌላቸው ምፃቸውን የሰጡ ደጋጎችንም አይተናል፡፡

ይህ መልክ እንዲለዋወጥ ምክንያት የሆኑ ብዙ የእምነቶቹ የውስጥ ጉዳዮችና ከሌላው ጋር (በሌላ የእምነት ጥላ ስር ካለው፣ ከኢ-አማኒው እንዲሁም ግራ ከገባው) የሚጋሯቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ዐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ነው፡፡

ዐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ግንባር ቀደሙ እና የእምነቶቹን ሰላማዊነትን የሚቃኝ መልክ የሚያሲዝ ነው፡፡የመጀመሪያው እምነቶቹ በሕዝቡ ዘንድ በግልጽ እንዲነገሩ ዕድል ስለሚሰጥ የስማ በለው ደጋፊ አይኖራቸውም፡፡ሁሉም አውቆ እና ጠይቆ ስለሚረዳ እንደከብት የሚነዳውን ቁጥር ባያጠፋውም ይቀንሰዋል፡፡ ሁለተኛው ተገፋን እንዳናስተምር፣ እምነታችንን እንዳንመሰክር ተለከለን የሚል የእምነት ክፍል አይኖርም፡፡ ሐሳቡን በነጻነት የሚገልጽ እምነት፣ ነጻ የሆነ ህዝባዊ ምህዳሩን(public space) አቅሙ እንደፈቀደ ያለ አድሎ የሚጠቀም እምነት፣ ተቋማዊ ነጻነቱ የተጠበቀለት እምነት ለእኩይ ምግባራት ቦታ አይኖረውም፡፡ በዚህ ሂደት የእምነቶች መልካም ገጽ እያበበ ጸብ አጫሪነት እየከሰመ ይሄዳል፤ ፉክክር ካለም ለጽድቅ(ለእውነት) ይሆንና ማኅበረሰቡን የከበበው የቁስም ሆነ የመንፈስ ድህነት ይወገዳል፡፡

ከሴኩላሪዝም ጋር ያለው ትልቁ ግጭት እዚህ ጋር ያለ ይመስለኛል፡፡ ሴኩላሪዝምን የአውሮጳ ስልጣኔ ምንጭ እምነትን ደግሞ የኋላቀርነት ምልክት የማደረግ አባዜ በመኖሩ ከላይ እንዳየነው ካለምንም ፍልስፍናዊ ዳራ (philosophical background) ሴኩላሪዝም ተቀባይነትን አግኝቷል፡፡ የአውሮጳ ስልጣኔ በመሠረቱ ከሴኩላሪዝም ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡ የአውሮጳ የስልጣኔ መንፈስ ምን እንደ ሆነ ለማስረዳት ዶ/ር እጓለ ገብረዮሐንስ በፍልስፍና ካነሆለላቸው ሀይድልበርግ (Martin Heidegger) የኒቨርሲቲ እንደተመለሱ የጻፉትን መግለጹ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

"በስነ ምግባር ረገድ የሰውን ጠባይና ችሎታ በመመርመር ከከፍተኛ የሞራል ሐሳብ ጽርየት ደርሰዋል፡፡ በማኅበራዊ ኑሮ ረገድ የእያንዳንዱ መብት እና ተግባር ተጠብቆ ሰው በንጹሕ ተምኔቱ መሠረት በሰላም ተደስቶ የሚኖርበትን የሕግ ውሳኔ አስገኝተዋል፡፡ በሀብት በንብረት በኩል ባነሰ ድካም ብዙ የሥራ ፍሬ በማስገኘታቸው ከራሳቸው አልፈው ለመላው ዓለም የሚተርፉ ሆነዋል፡፡ በሥነ ፍጥረት ዕውቀትና የእርሱ ዘርፍ በሆነው በቴክኖሎጂ ረገድ ከላይ እንደጠቀስነው የሰውን ሕሊና በጣም በማበልጸጋቸው ሰው ከሰውነት ድንበር ለማለፍ ምንም አልቀረው፡፡

በውበት ጥበባት ረገድ እነ ራፋኤልን ዳቢንቺን ሞዛርትን ቤቶሆቨንን ስመ ስማቸው ብቻ ብዙ ይናገራል፡፡ የአውሮጳ ስልጣኔ በአጭሩ ይሄ ነው፡፡ ባጭር ለመናገር ስንል ሳንበድለው አልቀረንም፡፡ ግን በሌላ ዕድል እንክሰዋለን፡፡

. . . .እሊህን የሕሊና ሕግጋት ወይም የስልጣኔ ፍሬዎች ያስገኙት አውሮጳውያን ናቸው፡፡ ግን እስያውያንም አፍሪካውያንም የራሳቸው ለማድረግ ይችላሉ፡፡ ዕውቀት ሲባል በጠቅላላ በማናቸውም ሰው ዘንድ በአምሳለ ዘርዕ ያለ ነገር ነው፡፡ ያንተም የኔም አይደለም፡፡ የሁላችንም ነው፡፡"

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ የምዕራብ ክርስትና መምህራን ሴኩላሪዝም የእነርሱን ብዙ እሴቶች ገንዘብ በማድረጉ በቀጥታ እምነታችንን ተቀበል ከማለት ይልቅ ወደ ሴኩላሪዝም በማስጠጋት ቀስ በቀስ ወደራሳቸው የእምነት ጎራ ለማስገባት (በሰፈሩት ቁና መስፈር አይቀርም እንዲሉ ወዳጅ ያደረጉት ሴኩላሪዝም እነርሱ ካበጁለት መስመር በማፈንገጥ ብዙ የምግባር እሴቶቻቸውን እንዲያጡ ሆኗል) ሙከራ ሲያደርጉ ተስተውሏል፡፡ይህም ሌሎች እምነቶች የከሸፈውን ሚሺነሪ በዘዴ ቀይረው መጡ እንዴ ብለው እንዲጠይቁም አስገድዷቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የመጠቃት ስሜት ሳለለ ከምዕራብ የመጣን ነገር ሁሉ እንደ ርኩስ የማየት ዘይቤ አለ፡፡ ይህ በልማት እና በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ላይ አሻራው ጥሏል፡፡ ይህንን የመጠቃት ስሜት በመላው ዓለም በሚገኙ ሙስሊሞች እና ምስራቃውያን ክርስቲያኖች (ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስያናትም ከዚህ ይመደባሉ) ይጋሩታል፡፡ ይህም እምነቶቹን ለመጠቀሚያነት ለሚያውሉ ሰዎች ምእመናንን ለእኩይ ዓላማ ለማሰለፍ እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡ በመላው ዓለም የሚገኝ የትኛውም ሙስሊም አሜሪካ እና ምራባውያንን እንዲጠላ ተቀርጿል፡፡ ይህ አል ቃይዳን እና መሰል አሸባሪ (ይቅርታ አሸባሪ በኢትዮጵያ ሳይሆን በምዕራባውን ትርጉሙ ነው የተጠቀምኩበት) አባላትን ለም መሬት እንዲያገኝ ረድቶታል፡፡

የመላው ዓለምን ችግር የመፍታት አቅም ላይኖረን ይችላል፡፡ ሀገሪቱን ሴኩላር ማድረግ በእምነቶች መካከል ያለን ችግርንም ሆነ እምነቶች አመጡት የሚባለው ችግር ማስቀረት አይቻልም፡፡ ነገር ግን ሀገር በቀል የሆኑ መልካም እሴቶችን በመንከባከብ የብዙሐን ሀገር (pluralistic state) መገንባት እችላለን፡፡ በብዙሐን ሀገር የትኛውም እምነት ሆነ እምነት የለሽ በእኩል የሚታይበት ለጋራ እሴት ሰብኣዊነት በማስቀደም በኅብረት የሚሠራበት ነው፡፡ የተገፋ የእምነት ክፍል ስሌለ (ሁሉንም እምነት ከሚገፋው ሴኩላሪዝም በተቃርኖ) ለአክራሪነት ቦታ አይኖርም፡፡

የኢሕአዴግ መንግስት ግን በጀመረው የጥፋት ጎዳና መቀጠል መምረጡን የምንረዳው እምነቶችን ከህዝባዊው ምህዳር ማግለሉ አንሶት ተቋማዊ ነጻነታቸውንም ለመስጠት ፍቃደኛ ባለመሆኑ ነው፡፡ Jo¨ rg Hausteina* and Terje Østebø "EPRDF's revolutionary democracy and religious plurality: Islam and Christianity in post-Derg Ethiopia" የሚል ርዕስ በሰጡት ጥናታቸው ኢሕአዴግ በሃይማኖት ጉዳዮች ጣልቃ በመግባት ሕዝባዊውን ምሕዳር በማወኩ ምክንያት፣ በእምነቶች መካከል ሀገራዊ መግባባት በማራቁ ምክንያት እምነቶቹ የየራሳቸው የተለያየ የታሪክ ትርክት እንዲኖራቸው ማድረጉን ይገልጻሉ፡፡ ይህ ለሃይማኖት ጽንፈኝነት መምህራን ለመጽሐፋቸው ርዕስ ለሁከታው መቀስቀሻ እንደ የተቀበረ ድማሚት ያገለግላቸዋል፡፡

ሌላው ሕሊችንን ከፍ ከፍ ማድረግ የሚጠበቅብን ጉዳይ የእምነቶችን እሴቶች በተለመለከተ ነው፡፡ ሃይማኖቶች በጊዜ ሒደት ያበለጸጓቸው የራሳቸው እሴቶች አሏቸው፡፡ እነዚህ እሴቶች በዚያ በእነርሱ ወረዳ ለሌለ ሰው ትርጉም ባይሰጡም ለምእመናን ግን ትልቅ ዋጋ አላቸው፡፡ ብዙ ጊዜ ግን እምነትን የሚያሄሱ ሰዎች ይህንን ግምት ውስጥ አያስገቡም፡፡ ለሌሎች ተነጻጻሪ እሴቶች የሚያደርጉትን ጥንቃቄ ለእምነቶች እሴት ሲያደርጉ አይታይም፡፡ ለምሳሌ የአንድ ሕዝብ በዳሌ መጨፈር፣ ትከሻን ማውረግረግ፣ የአንዳንድ ድምጾች መደጋገም፣ ከትናጋ ጋር የሚጋጩ ድምጾች መብዛት የመሳሰሉ ነገሮች ያን ጎጥ ያስከፋሉ ተብሎ ስለሚታሰብ በእርሱ ላይ ላለመቀለድ ይሞከራል፡፡ ይህ ግን እምነቶች ላይ ሲደረግ አይስተዋልም፡፡ የሀገሪቱ መንግስትም ሴኩላር በመሆኑ ለእነዚህ የሰላም እሴቶች ድጋፍ እና ጥበቃን አያደርግም ይህም ለምንጓጓለት ሐሳብን በመግለጽ የሚያምንም ማኅበረሰብ ግንባታ እንቅፋት ሆኗል፡፡

ይህን ስናደርግ በእኔ እምነት "የክርስቲያን ደሴት" ወይም "ኢስላማዊት በሸሪአ የምትመራ ኢትየጵያን" ከመስበክ ይልቅ የጋራ ቅኝቶችን የሚደግፉና ለአዳዲስ አስተሳሰቦች በር የሚከፍቱ ቤተ እምነቶች ይኖሩናል፡፡ ነገር ግን እኛን የሚወክል ሀገራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ስርዓትን ተባብረን በሰላማዊ መንገድ ካልጠየቅን ምን አልባት በፈጣሪ ለማመን ፍቃድ መጠየቅ ሊኖርብንም ይችላል፡፡ በፈጣሪ መኖር አላምንም ብንል ደግሞ በፓርቲችን ማመን ግዴታህ ነው የሚባልበት ዘመን ሩቅ አይሆንም፡፡ጽሑፌን ሁሉን በሚያስማማው እና ‹‹በአንተ ላይ ሊደረግ የማትፈልገውን በሌላው አታድርግ›› በሚለው ድንቅ ዓረፍተ ነገር ስዚጋ ልቤን ደስ እያለው ነው፡፡

# መጅሊሱን ከውስጥ ስንመለከተው

በመሐመድ ካሊድ

በአንድ የግል ጋዜጣ የዘንድውን አወዛጋቢ የመጅሊስ ምርጫ አስመልክቶ የተመረጡትን ሰዎች ፕሮፋይል እየተመለከትኩ ነበር፡፡ ከጎኔ የነበረ ሰው የሙስሊም ኮፍያዬን ቀና ብሎ ተመልክቶ ከበፊቱ መጅሊስ የተሻለ ዓለማዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ዕውቀት እንዳላቸው ነገረኝ፡፡ በጋዜጣ መሸጫ ዙሪያ "ሲቪሎች" ስለሚበዙ እሱም መረጃ እየሰራ ይሆናል በሚል ግምት በአጭሩ ያለውን መስማማቴን በንቅናቄ ገልጬ ገጹን በመገልበጥ አባረርኩት (አባረረኝ)- ብቻ ያው ነው፡፡ ከዚህ ሰውዬ አስተያየት ጀምሮ እስከ ዛሬ ያማጥኩትን ለአንባቢያን ላበቃ ዘንድ እነሆ ብእሬን አነሳሁ፡፡

ስለ ሰላማዊ ትግል በሚወራበትና ሙስሊሙ ማኀበረሰብ ለ 1 ዓመት ሙሉ ሕገ ወጡ መጅሊስ ይወገድ ከማለት ጀምሮ እስከ መሪዎቼ ይፈቱ ከዚያም ምርጫው ውድቅ ይደረግ ጥያቄ በአወሊያ ተጀምሮ እስከ ታላቁ አንዋር መስጂድ በዘለቀው የሰላማዊ ተቃውሞ የአንድ ዓመት ክብረ በዓል እየተከበረ ባለበት ወርሐ ታኅሳስ የመጨረሻ ሳምንት ስለ በግዱ መጅሊስ ማውራት ባይመስጥም ቢያንስ ውስጣዊ አሰራሩን ታነቡት ዘንድ ከትቤዋለሁ፡፡

## አዲሱ መጅሊስ

በመጅሊሱ "የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ" በሚለው ይሁን የእውነት አምነውበትና በአላማው ተመስጠው አሊያም ካድሬነት በሀይማኖት ተቋም ብዙ ተሰላፊ ስለሌለውና ሕወሓቶች ስለማይበዙበት በቀላሉ ትልቅ ካድሬ ሆኖ ለመገኘት ሲሉ አለያም የሀጅ ቢዝነስ አሪፍ ነው ሲባል ሰምተው አላውቅም ብቻ ወንድሞቻቸው አደባባይ እየጮሁ አልፈው ጥቂቶች የተወዳደሩበት በግዴታ ምርጫ ተካሂዶ እነሆ  እንደገና ተዋቅሯል፡፡ (አህመዲን አብዱላሂንም እንደስም ይጠራበት የነበረውንና ጨርቅ ከመሆኑ በቀር የአጼ ምኒሊክን ዘውድ የሚመስለውን ጥምጣሙን ተገላግሎ በኮፍያና በሸሚዝ መሀል ቦሌ ፈታ ብሎ ሲሄድ ልናየው ችለናል፡፡)

አዲሱ መጅሊስ የመጣበትን የምርጫ ሂደት ከቀበሌ መጀመሩ በታሪክ የመጀመሪያ ነው፡፡ ይህን ምርጫ ለማስተባበርም የተሰጠውም የመንግስት ሚዲያ ሽፋን ከመቼውም የተሻለ ነው፡፡ ተቃውሞውም እንዲሁ ታላቅ ነበር፡፡ ለዚህም ይመስላል በመጅሊሱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በድግሪና በማስተርስ ድግሪ ደረጃ የተማሩ ሰዎች ለስራ አስፈጻሚነት ደረጃ መድረሳቸው፡፡ ስለነዚህ ጉዶችም ብናወራ የመጅሊሱን ሁኔታ ለመረዳት የሚረዳ ይመስለኛል፡፡

አዲሱ መጅሊስ በሸህ ኪያር ሙሀመድ ፕሬዝዳንትነት ይመራል፡፡ በዋናው የመጅሊስ ስልጣን ላይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት እና ለስላሳው ለውሳኔ የሚቸገሩት ሙሀመድ አሊ እንደ ዋና ጸኀፊ ተወዝተዋል፡፡ በምክትል ፕሬዝዳንትነት የህዋሃት አባል የሆኑትና የቀድሞ የትግራይ ክልል የሸሪዓ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፣የክልሉ እስልምና ጉዳይ ፕሬዝዳንትነትና ሁሉንም ስራ አስፈጻሚ አባረው የሁሉም ዞኖች ተወካይ በመሆን ሁሉን ነገር የራሳቸው ጠቅለው በመያዝ ያላቸውን የአንባገነንነት አቅም ያስመሰከሩት ሼህ ከድር ማህሙድ ተሰይመዋል፡፡ ከዚህ ውጭ ሌሎቹን ስራ አስፈጻሚዎች በሌላ ጊዜ አስተዋውቃለሁ፡፡

ይህ መጅሊስ በጎኑ እንዳይተኛ የሚያደርጉ ሀሳቦችን በመዳሰስ ትንሽ ልበል፡፡ መጅሊስ ማለት ሙስሊሙን ማህበረሰብ በሀይማኖታዊ ጉዳዩ የሚዎክል ተቋም እንደመሆኑ በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል እንዲሉ ብዙ ነገር አርፎ እንዳይተኛ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ጽሁፍ የመጅሊሱን ፈተናዎች እና የፈተናውን ተዋናኞች ከዚህ በታች ባጭሩ እንዳስስ፡፡

## 1. የመጅሊሱ ቅቡልነት

መጅሊሱ ከድሮውም ለቅቡልነት አልታደለም፡፡ ይሁንና ያሁኑ ይባስ እንዲሉ ህዝበ ሙስሊሙ መጅሊሱን አንቅሮ ተፍቶታል፡፡በሙስሊሙ ማህበረሰብ አኳያ መጅሊሱ እመራዋለሁ የሚለው ህዝብ እየከሰሰውና እየገረመመው መኖሩ ጤናማ አይደለም፡፡  ይሁንና ያለፈው አልፏል እስኪ አንድ እድል እንስጣቸው ብሎ የሚነሳ ሙስሊም እንኳ ቢኖር በጥንቃቄ ካልተያዘ ያጡታል፡፡ ለዚህ ነው መጅሊሱ ለቅቡልነቱ የሚሰራውን ስራ ፈታኝ ነው የምለው፡፡ መጅሊሱ መልኩ ከፍቷል፡፡ ከሁሉ በፊት ፊቱ መዋብ አለበት፡፡ የመጅሊስን ክፉ ፊት ለማስዋብ ብዙ

የመዋቢያ መሳሪያዎች (ኮስሜቲክሶች) የሚያስፈልጉት ሲሆን ምን ቢኳኳል ግን ፊቱ ላይ ያሉት ሁለት ቡጉንጆች ካልተወገዱ ሊዋብ አይችልም፡፡

እነዚህ ቡጉንጆች ኮማንደር ሙራድና ጀማል ሙሀመድ ሳሊህ ሲሆኑ እነዚህ እያሉ ገጽታን ማስተካከል የሚታሰብ አይደለም፡፡ እነዚህ ሁለት ሰዎች የባለፈው ስራ አስፈጻሚ ይወገድልን ብሎ ህዝብ ሲጠይቅ አብሮ ፎቷቸው ተለጥፏል፡፡ ውሎ ማደሪያቸው ሳይቀር በተለያዩ ሶሻል ሚዲያዎች ተለቋል፡፡ ቀድሞም የመጅሊሱ ማንኛውም ውሳኔ የሚወሰነው በሰላም መምሪያ ጣልቃገብነት ነው፡፡ ትምህርት፣ቁርአን፣ልማት፣ሀጅ ወዘተ.. ብቻ ሁሉም ነገር ላይ የሰላም መምሪያ ጣልቃ ገብነት ያስፈልገዋል፡፡ ይህ ኃላፊነት የስራ አስፈጻሚ ሲልም በየክፍሉ ያሉ የስራ ሓላፊዎች መሆን ሲገባው እንዴት ጠቅሎ ወሰደው? ብዬ ስጠይቅ ያገኘሁት መልስ ቢኖር መንግስት ነው የሚል ነው፡፡ ብዙዎች እነደውም የሰላም መምሪያው ፕሬዘዳንቱን ማዘዙ የአደባባይ ሚስጥር እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

አዲሱ መጅሊስ በክብነት የሚመሩት ሙስሊሙን ሲያተረማምሱ የኖሩት እነ ጀማል ሙሀመድ ሳልህ ( የእውነት ስሙ ገብሬና ለትግል ሲባል ስሙ ከነአያቱ የተቀየረ ተብሎ የሚታማ) በዲሲፒሊን ከጉለሌ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ የተሰናበተው ኮማንደር ሙራድ ፎቷቸው ከሌሎች ጋር በመሆን ለህግ እንዲቀርቡ በዚህ ሳምንት ዓመቱን በሚያከብረው ድምጻችን ይሰማ የፊስ ቡክ ገጽ የለጠፋቸው ናቸው፡፡

ይታያችሁ ኮማንደር ሙራድ የመጅሊስ ጽ/ቤት ኃላፊ ሆኖ ሲሾም ያለ ሀፍረት በሴትነታቸው የጠየቃቸው ሁለት ሴት ጓደኛሞች የመጅሊሱ ሰራተኞች ምን ይሰማቸዋል? ገብሬ እንደዱሮው ሁሉ ስራ አስፈጻሚውን አመራርና አመራር ያልሆነ ብሎ ከፍሎ ሀሳብ በማቅረብ የፈለገውን ስራ አስፈጻሚ ከስራ ሲያሳግድ ማየት እንዴት.....እንዴት..... እንዴት...ቅቡልነትን ያመጣል?

የፌደራል መጅሊስ 400 የሚሆን ሰራተኛ አለው፡፡ ይሄ ሰራተኛ ጉዳዬ ካማረው ለአደባባይ አሳልፎ ይሰጥሃል፡፡ በተለያዩ ጋዜጦች ላይ ካየናቸው የሂሳብ ሰነዶች ጀምሮ ለየመንግስት መስሪያ ቤቱ እስከገቡት ሰነዶች ድረስ ያለው ሚስጥር የወጣው በተለያዩ ሰራተኞች ነው፡፡ ባጭሩ የመጅሊሱ ሰራተኛ ማለት ወሳኝ ምስክር ማለት ነው፡፡ ምክር ቤቱ የስራ ባህሉ ክፉኛ የተጎዳ ከመሆኑ የተነሳ እድሜ ለነ እንቶኔ አብዛሀኛው ሰራተኛ ከስራ ይልቅ ወሬ ማቀበል እንደሚያሳድግ ገብቶት የነገር ማቀበል ሚና መጫወት ህሊናው የፈቀደ እያቀበለ ህሊናው ያልፈቀደው ደግሞ በስራ የሚመጣ ነገር እንደሌለ በመገንዘብ ቀኑ ሲመሽና ሲነጋ እየታዘበ ልጆቼን ላሳድግ የሚል ሆኗል፡፡

ከዚህ ባሻገር የአህሉሱና ወለወጀማአ እና ሱፊ ሰለፊ ጉዳይ ገና አነጋጋሪ ነው፡፡ የየእስልምና ምክር ቤቶቹ ምርጦች የመጡት በሱፊ መስፈርት ነው፡፡ ህዝቡ ደግሞ አንድነት እያለ ነው፡፡ የመጅሊሱ አመራሮች ቃለ መሃላ የፈፀሙትም በዚሁ መልኩ ነው፡፡ ሙስሊሙን ማህበረሰብ በአህሉሱና ወለወጀማዓ አስተምህሮ ለመምራት! ታዲያ የተመረጡበት መስፈርት ተቀይሮ አንድነትን ከግምት ውስጥ ያስገባ አካሄድ ቢሞከር ቅቡልነትን ለማግኘት ያግዝ ይሆናል፡፡

ሶስተኛው ጉዳይ የህዝብ ግንኙነት ስራ በአብዛሀኛው ቅቡልነትን ከመገንባት አኳያ ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡ ይሁንና መጅሊስ ገብታችሁ የህዝብ ግንኙነት ክፍሉን ብትመለከቱ በሰው ሃይል ረገድ በእጅጉ ተጎድቷል፡፡ ለዚህ ይመስላል አዳዲሶቹ ስራ አመራሮች ውሉ ጠፍቶባቸው ቢሮዎችን በመቀላቀል ትላልቅ ቢሮዎችን በመፍጠርና ቀለም በመቀባት ስራ ላይ የተጠመዱት፡፡ አዲሶቹ መጅሊሶች ከገቡ ሶስት ቢሮዎች ፈርሰው አንድ ትልቅ ቢሮ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ሁለት የትውውቅ መድረኮች ተከፍተዋል፡፡ ......ወዘተ፡፡

## 2. የመጅሊሱ የውስጥ መዋቅር

መጅሊስ በውስጡ የተለያዩ የልማት ተቋማት ያሉት ሲሆን የአወሊያ ተቋማት እና የልማት ኤጀንሲ እንዲሁም በመጅሊሱ የተለያዩ ዘርፎች ስር ያሉ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ በነዚህ ተቋማት ስር ከ 400 በላይ ሰራተኞች ያሉ ሲሆን ከትምህርት ዝግጅትና ልምድ አኳያ ጥሩ ሊባል የሚችል አቅም ያላቸው ሰዎች አሉ፡፡ በዚህ ተቋም ያለፈ የስራ ሂደት ታዲያ ይህን የሰው ሀይል በአግባቡ ስራ ሊያሰራ የሚችል አደረጃጀትም ሆነ ህግና ደንብ የሌለው በመሆኑ ሰራተኛው በማያውቀው ምክንያት በዙሪያው ሲከናወን ቆይቷል፡፡ ይህ በዚህ ሂደት የተዳከመና የተሰላቸ ሰራተኛ ስለመጅሊሱ ከስራ አስፈጻሚዎች በላይ ያውቃል፡፡ መጅሊሱ ሲቋቋም ጀምሮ አዲሱን በመቀበል እና ነባሩን በመሸኘት ከ 15 ዓመታት በላይ ከመጅሊሱ ጋር የቆዩ ሰራተኞች ከ1987 ጀምሮ የነበሩ መጅሊሶችን ተመልክተዋል፡፡ በንግግር የተካኑ የነበሩት መጅሊስ ስራ አስፈጻሚዎች በባዶ ተስፋ ሲደልሉት ቆይተዋል፡፡

በመሆኑም የመጅሊሱ ሰራተኞች ተጨባጭ ለውጥ በተግባር ካላዩ ለመጅሊሱ የኔነት ስሜት ፈጽሞ ሊሰጡት አይችሉም፡፡

የመጅሊሱ ነባር ስራ መረጃ አያያዝም ደካማ በመሆኑ የመጅሊሱ ስራ አስፈጻሚዎች በቀጥታ ወደ ስራ ለመግባት የሚችሉበት ሁኔታም አይኖርም፡፡ መጅሊሱ ያለው የስራ መመሪያም ሆነ መዋቅር በሰኔ 1993 ዓ.ም የተዘጋጀ ሲሆን አሁን ካለው መዋቅር ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው እስከሚመስል ድረስ በሂደት ተቀያይሯል፡፡ የመዋቅሩን ማርጀት ተከትሎም በርካት መደቦች በተፈለገው ጊዜ ሊቀጠር በተፈለገው ሰው ልክ ሲፈጠሩ ቆይተዋል፡፡በዚህ ሂደት የተጠራቀሙ ሰራተኞች ቀን አሳላፊ ሆነው ተቀምጠዋል፡፡ የስራ አስፈጻሚ ሚስት፣ልጅ፣እህት ባጠቃላይ ዘመድ አዝማድ ሆነው ግቢውን የረገጡና በዛው የቀሩትን ብዛት መጅሊሱ ይቁጠረው፡፡ ከእንግዲህ ይህን ሰራተኛ ነው ሁሉንም የሚመጥን የትምህት ዝግጅትና ልምድ ላይ ተመስርቶ ስራ ሰጥቶ ወደጤናማ ተቋም አካል መቀየር የሚቻለው፡፡

## 3. የውጭ እጆች

ሌላኛው የመጅሊስ ጣጣ ሆኖ የሚገኘው የውጭ እጆች ልብ በሉልኝ ፡፡ ይህ ምክር ቤት በሀጅና ኡምራ ስራ ከብዙ ድርጅቶች ጋር ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በዚህ አወዛጋቢ የሀጅና ኡምራ ስራ የመስራት አበሳ ከተቋሙ ጋር ያነካካቸው ሰዎች ሁሉ ምንጊዜም ስራ አይፈቱም፡፡ ከመጪው ስራ አስፈጻሚ ጋር ሲስማሙ አብረው በመስራት ሳይስማሙ ይሄኛውን ጥለው ለነሱ የሚመቸውን ለማስመጣት ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ይሄ እጅ ምንጊዜም ስራ አይፈታም፡፡ ታዲያ ይህ እጅ አንዴ በጋዜጣ ሌላ ጊዜ በመጽሄት፤ ካልሆነም በተለያዩ የመንግስጥ የደህንነት መዋቅሮች ውስጥ አልፎ መምጣቱ ነው መከራው፡፡ አላሰርቅ ያለ ስራ አስፈጻሚ በሆነ ምክንያት አሸባሪ እንደማይባልና ከስራ እንደማይታገድ ምን ዋስትና አለን??

## 4. የመጅሊሱ የሰላም መምሪያ

ሌላኛው የመጅሊሱ ጣጣ የመጅሊሱ የሰላምና መረጃ መምሪያ ነው፡፡ የቀድሞ መጅሊስ አመራሮች መጅሊሱ በተለያየ ጊዜ ስልጣኑን ማቆየት ሲሳነው የዙፋኑ ጠባቂዎች እንዲሆኑ ለማድረግ ያመጣቸው የሚታወቅ ሙያም ሆነ ትምህርት የሌላቸው ሰዎችን ያቀፈ ክፍል ነው፡፡(ይህ ክፍል ከላይ የጠቀስኳቸውን ኮማንደር ሙራድን አቶ ገብሬ (ጀማል ሙሀመድ ሷሊህን) ጨምሮ 30 ሰራተኞችን የያዘ ነው፡፡ ይህ ቡድን በሀጅ ጉዞ 43434 ብር ተሸፍኖለትና ተጨማሪ 30000 ብር አበል ተሰጥቶት ሀጅን ሊቆጣጠር ሳይቀር ሳውዲ ይሄዳል፡፡ በመጅሊሱ ምርጫ ሂደትም በተለይም ዋና ጸሃፊ የነበረውን አቶ አልሙሀመድ ሲራጅን ለማስመረጥ እልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ እንደነበረ በሰፊው ተወርቷል፡፡ ይህ ክፍል የመጅሊሱ ግል ማህደሩ ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ መረጃ እንኳ የሌለው መሆኑን የሚያመለክተውን የመጅሊሱን ሰራተኛ በግጭት አፈታት ከአምስተርዳም ዩኒቨርስቲ ማስትሬት ድግሪ አለው ብሎ በኢትዮ ሙስሊም ጋዜጣ ሲያስነበበን ነው ተብሎም ይታማል፡፡

በአዲሱ የመጅሊስ ምርጫ የተመረጡት የመጅሊስ ፕሬዝዳንት የትምህርት ደረጃ ቀድሞ ተነግሮን ነበር፡፡ይህ በኋላ ላይ ሲጣራ ሃሰት ሆኖ የተገኘው ይህ የተመራጮች መረጃ የተቀነባበረው እና የሚነዛው በዚሁ ክፍል ስር ለዚህ ስራ በተሰማሩ ሰራተኞች መሆንም የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡

የፕሬዝዳንቱ ቤተሰቦች የጉዞ ወኪል ቢዝነስ ያላቸው ሲሆን ከድፍን ኦሮሚያ ይህን አይነቱን ሰው ማምጣቱ በአንድ በኩል ለሀጅ ሙስና የተመቻቸና በልቶ የሚያበላ ነው የሚል ሃሜት በአዲሱ አመራር ላይ በሰፊው እየተወራ ቢሆንም የሰላም መምሪያው የግልና ተቋማዊ ድጋፍ አዲሱም መጅሊስ ከቀድሞው የተለየ እንዳልሆነ ያመለክታል፡፡ አዲሱ ፕሬዝዳንት ግቢ ከገባ ጀምሮም ከሰላም መምሪያ ጋር ጠንካራ ግንኙት እንዳለው መገንዘብ ተችሏል፡፡

## እንደመውጫ

የሕዝብ ተሳትፎ ለልማት ወሳኝ እንደሆነ ሁሉ ለሀይማኖትም ወሳኝ ነው፡፡ እና እስኪ ትንሽ ቢያንስ የተማረውን ሙስሊም አሳትፉ፡፡ አቅጣጭ ቀይሱ፡፡ ለሀገር ልማት አጋዥ የሁኑ አያሌ ነገሮች መስራት ይቻላል፡፡ ***<u>አዲሱ ስራ አስፈጻሚ ላይ ተስፋ መጣል የመጡበትን መንገድ መርሳት ቢሆንም</u>*** ከድሮው አሰራር እቅፍ ለመውጣት መሞከር

ከቻሉ አሁንም የሙስሊሙ እውነተኛ ተወካይ ለመሆን መሞከር ይቻላል፡፡ ብዙ የሀይማኖት እውቀት ባይኖረኝም በሰማይ ቤት አካውንት እንዳለን አምናለሁ፡፡ ተስፋ አልቆርጥም፡፡ ታሪክና ፈጣሪ መዝግበው እንደሚይዙንም አለመርሳት ነው፡፡

ውድ አንባቢያን የመጅሊሱ የቅርብ ሰዎች ብዙ ሳይዘጋጁና ሳይጨነቁ ይህን ሁሉ መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ ለግል ደህንነታቸው ሲሉም የተወሰነውንም ዝርዝር ነገር እንደማይነግሩኝ ገልጸውልኛል፡፡ ይሁንና በሂደቱ ያወቅኩት ነገር ቢኖር በመጅሊሱ የተማሩ ሰዎች በዙሪያው እንዳሉትና ያሉትን ሰራተኞች በአግባቡ ቢጠቀም ውጤታማ የመሆን እድል እንዳለው ነው፡፡

ይሁንና ሰራተኞቹ  የሰላም መምሪያ ግን ለሰራተኛውና ለስራ አስፈጻሚ አለመገናኘት ብዙ ሚናዎችን ከመጫወት አይቦዝንም ብለው ያሙታል፡፡ አዲሱ ስራ አስፈጻሚ ይህን ሰላም መምሪያ ካለው ሚና ለማቀብ ደፍሮ ሊያፈርሰው ይችላል የሚል ተስፋም እንደሌላቸው ነግረውኛል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ይህን ጽሁፍ ለሚያነብ ሙስሊምም ሆነ ሌላ ወገን የመጅሊስ ጉዳይ የሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን የሁላችንም በመሆኑ ለመስተካከሉ የቻልነውን ሁሉ ጥረት እንድናደርግ እላለሁ፡፡

# የጉዞ ማስታወሻ፤ መቐለን በአንድ ቀን

ከአዲስ አበባ ብዙም ርቆ የማያውቅ ሰው ሃያ ኪሎ ሜትር ሲራመድም ቢሆን የጉዞ ማስታወሻ ይጽፋል፡፡ እኔም የዛሬ ሁለት ዓመት እጄን ይዛ ጎንደር የወሰደችኝ ወዳጄ፣ ዛሬ (ኅዳር 12፤ 2005) ደግሞ መቐለ ወሰደችኝ፡፡ ጉዞዬ ረዥምም ነው፤ ገና አክሱም ላሊበላና ሌሎች ጥቃቅንና አነስተኛ ቦታዎችን እጎበኛለሁ፡፡ ይህንን ያህል ካስቀናኋችሁ ይበቃል፣ አሁን በጥቅሉ ላስነብባችሁ አቅጄ የነበረውን የጉዞ ማስታወሻ አላስችል ስላለኝ አመሻሹን የማደሪያዬን መስኮት ሰብሮ የዘለቀ፣ ምንጩ ግን ያልታወቀ ዋይፋይ ተጠቅሜ ጻፍኩት፡፡

ለመናዘዝ ያክል፤ መቐለን ሳስብ መጀመሪያ የሚመጣብኝ ነገር ሕወሓት ነው፡፡ እንዴያው እንዲሁ… ትንሽ ስጋ እንደመርሬ ትወጋ… የሚለው አባባል በራሱ ኢሕአዴግ ለመቐሌ ሳያዳላ አይቀርም የሚል ጥርጣሬ ሽው እንዲልብኝ አድርጎ ነበር… ነበር ያልኩት ያለነገር አይደለም፡፡ የመሐመድ ሰልማን ተወዳጅ መጽሐፍ ፒያሳ ‹አደይ መቐለ› ባለው ትረካው ነገሩን ሁሉ ድባቅ መትቶታል፡፡ መቐሌ የምስኪኖች እና አቧራ የዋጣት ከተማ ናት ብሎ ነበር ልበል?!

መቐለ ስገባ ግን ያልጠበቅኩት ነው የገጠመኝ፡፡ ሲጀመር ስፋቷ እንደዚህ አልመሰለኝም ነበር፤ ከሌሎች የክልል ከተሞች አንጻር መቐለ ሰፊ ነች፡፡ ሲቀጥል፣ አቧራ የለባትም - መሐመድ መቼ እንዳያት እኔ እንጃ እንጂ እኔ በተንቀሳቀስኩባቸው ቦታዎች ሁሉ ውስጥ ለውስጡ ሳይቀር ለዓይን በአማረ የኮብል ስቶን ድንጋይ የተነጠፈች ከተማ ነች - አደይ መቐለ፡፡ እኔ እኮ አቧራ ሲባል የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ ጅማ ሄጄ ያየሁትን ዓይነት መስሎኛል፡፡

ወደ መቐለ የተጓዝነው በሰላም ባስ ነበር፡፡ ሰላም ባስ ዕድሜ ለፉክክር - የስካይ ባስን የመሳሰሉ አዳዲስ ባሶችን በአገልግሎት ላይ ያዋለው በቅርቡ ነበር፤ እናም ምቾቱ እምብዛም አልተጓደለብንም፡፡ የመቐለ መንገድ በተለይም ወደትግራይ ክልል እየተቃረብን በመጣን ቁጥር የተራራው ነገር እያስገረመኝ ነበር፤ እያስገረመኝ ብቻ ሳይሆን እያሳሰበኝም ጭምር፡፡ ኢትዮጵያ ይሄን ሁሉ ተራራ ተሸክማ ምን ታደርገዋለች? ወይ አርሳው ቀለብ አታመርት፣ ወይ አፍርሳው ከተማ አትቆረቁርበት - ይሄ ‹‹ጋራ ሸንተረርሽ›› እያልን የምንዘፍንላት ዘፈን ልክ ‹‹ድንግልናሽ›› እያልን ምንም ያልተሠራባት፣ ያልተበላባት መሆኑን በተዘዋዋሪ እንምንናገረው ይሆን?

መቐለ የገባነው በማግስቱ ጠዋት ሁለት ሰዓት ነበር፡፡ (የመጀመሪያውን ቀን አላማጣ ላይ ማደር ነበረብን፤) እንደገባን መዝናኛ ቁርስ ቤት የተባለ የከተማዋ ዝነኛ ቤት ውስጥ የከተማዋን ዝነኛ ቁርስ በላን - ፋታ፡፡ ከዚያ ጉዞ ወደ አፄ ዮሐንስ 4ተኛ ቤተ መንግሥት፡፡

በነገራችን ላይ የመለስ ፎቶ መቐለን እንደአዲስ አበባ አላጥለቀለቃትም፡፡ ይህንን ቀድሞ መቐለ ደርሶ የተመለሰ አንድ ወዳጃችንም አጫውቶን ነበር፡፡ ምክንያቱ ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄዬ መልስ ያገኘሁ የመሰለኝ የቴክኖ ሞባይል ማስታወቂያ አንድ ሕንፃ ግድግዳ ላይ በትልቁ በእጅ ተስሎ ስመለከት ነው - ይመስለኛል መቐለ ውስጥ የቢልቦርድ ማተሚያ የለም - ቢኖርም ውድ ነው፡፡

የአፄ ዮሓንስ ቤተመንግሥት በእድሳት ላይ በመሆኑ በርቀት ከማየታችን በቀር፣ የተመለከትነው በፎቶ ነበር፡፡ ፎቶው ላይ ድንጋዩ እንደጎንደር ቤተመንግስቶች ተክቦ ስናይ ‹‹ታዲያ የሚታደሰው ለምን በሲሚንቶ ይለሰናል?›› ብለን ጠየቅን፡፡ ‹‹ቤተ መንግሥቱ በፊት የተለሰነ ነበር፣ ደርግ ነው ልስኑን ያፈረሰው›› አሉን፤ ‹‹ደርግ ቤተ መንግሥቱን በካምፕነት ተጠቅሞበት›› እንደነበርም ነገሩን፡፡ ሙዚየሙ ውስጥ ከአፄው ዙፋን፣ ባለወርቅ ‹ምላጭ› መሳሪያዎች እና የፈረስና በቅሎ ኮርቻዎች በቀር ሌሎቹ የራስ ጉግሣ እና ሌሎችም መሣፍንቶች ቁሳቁሶች ናቸው፡፡ ስለዚህ የእዚህኛው ሙዚየም ጉብኝታችን ረዥም ሰዓት ሊፈጅ አልቻለም - ጉዞ ወደ ‹ሓውልቲ› - የሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት እና ሙዚየም፡፡

## የሰማዕታቱ መታሰቢያ

የሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት አጠገብ ስንደርስ የሕወሓትን ዋና ጽ/ቤት ተመለከትን፡፡ መጀመሪያ ላይ አናደደኝ፤ ምክንያቱም የሰማዕታቱ መታሰቢያ ሐውልት እና የሕወሓት ዋና ጽ/ቤት አንድ ጊቢ ናቸው፡፡ ያናደደኝ ደግሞ እንዴት በመንግስት በጀት የተሠራ አንድ ሙዚዬም የፓርቲ ግቢ ውስጥ (ወይም እንዴት የሕዝብ ሙዚየም ውስጥ የፓርቲ ጽ/ቤት) ይገነባል በሚል ነበር፡፡ ኋላ ላይ ግን ስመለከት የሚያስደንቀኝ ነገር ተፈጠረ፡፡ ሙዚየሙ

የተገነባው በሕወሓት አሠሪነት ነው ይላል ደጃፉ ላይ ያለ ጽሑፍ። ወደ ውስጥ የምንገባበትም ትኬት የሚያመለክተው ከአፄ ዮሓንስ ቤተመንግስት ሙዚዬም በተለየ የክልሉ መንግሥት የቱሪዝም ጽ/ቤት ትኬት አይደለም። ያስደነቀህ ታዲያ ምንድን ነው ካላችሁ - የሕወሓት አቅም፤ ያንን የሚያክል ሐውልት እና ጊቢው ውስጥ ያሉ ግሩም ሕንፃዎችን የማስገንባት አቅም። እዚያው ቆም ብዬ የተቃዋሚዎችን አቅም አሰብኩት - አሳዘኑኝ።

የሰማዕታቱ ሐውልት ያለበት ጊቢ ውስጥ አርብ እና ቅዳሜ ብቻ ፊልም የሚያሳይ የማቲ መልቲፕሌክስ ሲኒማ ቤት እና የሰማዕታቱ መታሰቢያ ሙዚየም አለ። ወደሙዚየሙ ገባን ሙዚዬሙ በአቅርቦቱ በአራት ቢከፋፈልም በይዘቱ ግን ፎቶ እና መገልገያ ቁሳቁሶች የሚታዩበት ነው። የሚገርሙ ጥንታዊ መሳሪያዎች (ጦርነቱ የተካሄደው በምንሊክ ጊዜ ነው እንዴ - የሚያስብሏችሁ)፣ የሬዲዮ ማሰራጪያዎች፣ ሌሎች ቁሳቁሶች እና በርካታ ተራኪ ፎቶዎች ሙዚየሙ ውስጥ ይገኛሉ።

ፎቶዎቹን ስመለከት ሆነ ብዬ እፈልግ የነበረው የአቶ ስዬን እና የአቶ መለስን ፎቶ ነበር። ብዙዎቹ ታጋዮች ተሰብስበው፣ አፈር ለብሰውና እና ተጎሳቁለው (እየተሳሳቁም፣ በሥራ ላይ ተሰማርተውም ቢሆን) በጋራ የተነሷቸው ፎቶዎች ውስጥ መለስ የሉም። መለስ ፌስቡክ ላይ ከምናውቃቸው አንዳንድ የብቻዎቻቸው ፎቶዎች እና ከሁለት ስብሰባዎች ውስጥ በቀር ሌላ ቦታ የለም። አቶ ስዬ ግን ከናካቴው የሉም። ሌላው የገረመኝ ግን የ1977 የምሁራን ስብሰባ የተባለ ፎቶ ላይ የአቶ በረከት ስምኦንን ፎቶ ማየቴ ነው። እዚያ ውስጥ ከአቶ በረከት ያቺ ፎቶ በቀር ሁሉም ሰዎች የሕወሓት እና የሕወሓት ብቻ ናቸው።

‹የትሮይ ፈረስ› የሚል መጽሐፍ ላይ አንድ ኤርትራዊ ምሑር ‹ለኤርትራ ሕዝብ የሚበጀው ሰላምና ዕርቅ ነው› በሚል የጻፉትን መጽሐፍ ሽፋን መሳሪያ ባፍጢሙ ተደፍቶ አበባ በቅሎበት ነበር፤ የዚህን መጽሐፍ ምላሽ መለስ ‹የኤርትራ ሕዝብ ትግል ባፍጢሙ አይደፋም› በሚል ሲጽፉ ጠብመንጃውን በሽፋን ገጻቸው አቃንተውታል ሲል አስነብቦናል። ያቺን የመለስ ምላሽ የተባለችውንም መጽሐፍ ስመለከታት ሰውነቴን ብስጭት ውርር ሲያረገኝ ታወቀኝ። ዘራፍ አይባል ነገር።


በወዳጆቻችን እዩ የተባልነውን ሁሉ ጊዜ በሚፈቅድልን መሠረት አዳረስነው፤ ከሁሉም ደስ የሚለው ግን የከተማዋ ሕዝብ መስተንግዶ ነው። ፈገግታውን የማይሰስት ሰው ያለበት ከተማ የሚኀበኝ ባይኖረውም ሳያውቁት ይናፈቃል:: እኔ ግን በማለዳ ወደአክሱም መጓዜ ነው - ስለአክሱም ቆይታዬ የምጽፈው ነገር እንደሚኖረኝም አትጠራጠሩ::

# የጉዞ ማስታወሻ፤ ሥልጣኔ ወደላይ እና ወደታች

አክሱም ከአዲስ አበባ አንድ ሺሕ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ አንድ ሺሕ ኪሎ ሜትር ያውም በመኪና፣ ያውም ያንን ጠመዝማዛ መንገድ ለተጓዘ ሰው አንድ ሺሕ ነገር መጠበቅ አያስገምተውም፡፡ ጥያቄው ‹በምስል እና በተንቀሳቃሽ ምስል ያየነውን፣ ተጽፎ ያነበብነውን በአካል ሲያዩት እንዳሰቡት ይሆናል ወይ?› ነው፡፡

ከመቐለ ወደ አክሱም ስንጓዝ ውቕሮ (ከጠበቅናት በላይ የደመቀች ከተማ)፣ አዲግራት፣ አድዋ (ከጠበቅናት የደበዘዘች) ከተማን አቆራርጠናል፡፡ አድዋ ከተማ ጦርነቱ የተደረገበት ተራራ ሥር የባንዲራ መስቀያ እና የመታሰቢያ ጽሑፍ የተጻፈበት እምነበረድ ነገር መኖሩን በመኪናው ፍጥነት አስተውያለሁ፡፡ ነገር ግን አንድ ሰሞን ብዙ ተወርቶለትና ገንዘብ ተሰብስቦለትም የነበረው የአድዋ ተራራ ላንድማርክን ፍለጋ ዓይኔን ወደላይ ባንከራተትም ማየት አልቻልኩም፤ አብረውኝ የነበሩትን የአገሬው ሰዎችም ብጠይቃቸው የሚያውቁት ጉዳይ የለም፡፡

አክሱም ከተማ የዕድሜዋን ያክል አይደለችም፡፡ ጎስቋላነቷ ገና ከደጃፏ ያሳብቃል፡፡ እንዲያውም አካባቢውን የምታውቀው ወዳጃችን እንዳጫወተችን ከሆነ ከፎቅ አቅም እንኳን አብዛኛዎቹ የተገነቡት ከ2000 ወዲህ ነው፡፡ ማረፊያችንን ካመቻቸን በኋላ ወደአክሱም ሐውልቶች መጓዝ ጀመርን… አዲሱ የአክሱም ከተማ እና አሮጌው የተያያዙ ናቸው ከአዲሱ ወደአሮጌው የጥቂት ደቂቆች የእግር ጉዞ በማድረግ ይደረሳል፡፡ ያቺው ወዳጃችን ‹‹የአሁኗ አክሱም የበፊቱ አክሱም ላይ ነው የተገነባችው›› የሚባል አባባል እንዳለ ነገረችን፤ ቢቆፈር ከስር የሚወጣ ጥንታዊ ከተማ አይጠፋም በሚል ዓይነት፡፡ ጥቂት እንደተጓዝን ፊት ለፊታችን አየነው - አክሱምን ቆሞ አየነው፣ የአክሱም ሐውልቶችን ቆመው አየናቸው፡፡



አድዋ ተራራ አክሱም

ከተተከለ ጀምሮ እንደቆመ ያለው የአክሱም ሐውልት ትንሽ በመዝመሙ መወጠሪያ በአንድ ጎን ተደርጎለታል፡፡ ሌላኛው ደግሞ ከሮም በፊታውራሪ አመዴ እና ሌሎችም ትግል የመጣው፣ እንደታጠበ ዓይነት አዲስ መልክ ይዞ በግርማ ሞገስ አጠገቡ በጥቂት ሜትሮች ርቀት ላይ ቆሟል፡፡ ሌላኛው እና ትልቁ የሚባልለት ደግሞ ከአዲሱ ጥቂት ሜትሮች ፈቀቅ ብሎ ተሰባብሮ ተኝቷል፡፡ ተሰባብሮ የተኛው ውፍረቱ ሲያዩት ከሁለቱም እጅግ የገዘፈ እንደሆነ ያሳብቃል፡፡ የቆሙት ሐውልቶች በጥቂት ስኩዌር ሜትሮች ስለታጠሩ መጠጋት አይቻልም፡፡ ከወደቀው አክሱም ስር ዋሻ ነገር አለ፡፡ የዋሻው ኮርኒስ ላይ ያሉት ግዙፍ አለቶች እንዴት እንደተቀመጡ የአክሱም ሥልጣኔ ዘመን ሰዎች ብቻ ናቸው የሚያውቁት፡፡

ቀጠልን፤ እዚያው ጊቢ ውስጥ ያለውን ሙዚየም ጎበኘነው፡፡ ጥንታዊ የአክሱም ዘመን ቅሪቶች (ሳንቲሞችን ጨምሮ) እዚያው ይገኛሉ፡፡ በስተመጨረሻም በትግራይ ክልል የሚገኙ ቅርሶችን የሚያስተዋውቅ ቪዲዮ መመልከት ይቻላል እና በጉጉት ቁጭ አልን፡፡ ቪዲዮው የተዘጋጀው ለውጭ አገር ቱሪስቶች በመሆኑ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው የሚተረከው፡፡ ገና ሲጀምር የትግራይን ካርታ ለይቶ ቀይ አቀለመውና… ትግራይ The Open Air Museum ነች አለ፤ እውነት ነው፡፡ ተራራዋ፣ ታሪካዊ ቦታዎቿ ብዙ ናቸው፡፡ ትግራይ ከኤርትራ፣ አማራ፣ አፋር እንደምትጎራበትም ተናገረ፡፡ በመቀጠልም… ትግራይ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ አልፋና ኦሜጋ መሆኗን ነገረን፡፡

## በቪዲዮ አስቀየሙኝ

በትረካው ላይ አድዋ ይጠቀሳል - የአድዋ ጦርነትን የመሩት ምኒልክ እና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ቦታ የላቸውም፤ 120 ከድንጋይ የተፈለፈሉ ቤተ ክርስቲያኖች መኖራቸውን ጠቅሶ ትግራይ የኢትዮጵያ የክርስትና ዋና ከተማ ናት ይላል - ላሊበላስ?... ከዘመናዊ ከተሞች መቐለ በዕድሜ ትልቋ ናት ይላል - የምር? አጤ ዮሓንስ ከነገሥታት ሁሉ ጀግናው መሆናቸውንም ነገረን።.... አንደኛ እና ትልቅ የሚሉትን የመሳሰሉ ቃላት የተጠቀሱበትን አገባብ መቁጠር ያታክታል። እንኳን ትልልቅ እና አንደኛ ነገሮች በዙ - ደስ ይላል ችግሩ ግን በጥቅሉ ይሄ አይደለም፤ እኛ ሁሉንም ቅርሶች እንደኢትዮጵያዊነታችን የኛ ብለን ልንነበኛቸው ኪሎሜትሮች አቋርጠን ስንሄድ የትረካው ሙሉ መንፈስ ግን ታስቦበት በሚመስል መንገድ እየነበኘነው ያለነው የትግራይ ሀብትን እንጂ የኢትዮጵያን እንዳልሆነ ነገረን። እኔ በበኩሌ ሙዴ ወዲያው ነው የተጨረበው! በእንግሊዝኛ Belongingness አሳጡኝ ብለው ይገልጽልኝ ይሆን? እንዲያም ሆኖ ግን የባለግርማ ሞገሱን ተራኪ ድምጽ የት ነበር የማውቀው እያልኩ እያሰላሰልኩ ነበር - በመጨረሻ ተከሰተልኝ። ለካስ የድኅረ ምርጫ 97ን ብጥብጥ ተከትሎ ኢሕአዴግ ለኤምባሲዎች እና ዲፕሎማቶች የላከው የቪዲዮ ሲዲ ላይ ይተርክልን የነበረው ድምፅ ነው። መቐለ - የሰማዕታት መታሰቢያ ሙዚየም ውስጥ ካየናቸው የትግሉ ወቅት ጽሑፎች መካከል በትግርኛ የተጻፈ ‹የኢትዮጵያ ታሪክ ማስተካከያ› አይቻለሁ፤ ሁሉንም ብስጭቴን ትቼ ጉብኝቴን በመቀጠሉ ላይ ያተኮርኩት፣ የአገሬውን ሕዝብ መስተንግዶ እና እነዚህ ዓይነቶቹ የመከፋፈል ዘመቻዎች የአንድ ቡድን ዒላማዎች መሆናቸውን ለራሴ በማስታወስ ነው።

ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስትያን ከሐውልቱ ፊት ለፊት ትገኛለች። ከቤተ ክርስትያኑ ፊት ለፊት ለቲዎሎጂ ኮሌጅነት እየተገነባ ያለ ሕንፃ ቀድሞ የነበረውን ውበት እንደጋረደው ያስታውቃል። ሁሉም ሰው መጎብኘት የሚችለው አፄ ኃይለሥላሴ ያሠሩትን ቤተ መቅደስ ነው። የቃል ኪዳኑ ታቦት አለበት የሚባለው ቤት እና ጥንታዊው ቤተ ክርስትያን ግቢ ውስጥ ሴቶች መግባት ስለማይፈቀድላቸው እኔም የጾታዬን አበርክቶ አንጼ ግቢውን በመዞር እና ፎቶዎች በማንሳት ተጠቀምኩበት።


እጼ ካሌብ (ምድር ስር) ንግሥት ሳባ ቤት መንግሥት

ግማሽ ቀኗ እንዲህ ስላለቀች ወደመቐለ በማግስቱ ጠዋት ልናደርገው ያቀድነውን ጉዞ ወደ ከሰዓት በኋላ አራዘምነው። በማግስቱ የአጤ ካሌብን ቤተ መንግሥት ለመጎብኘት ስንፈልግ ባጃጆች በሙሉ ‹‹ሩቅ ነው፣ ኮረኮንች ነው›› እያሉ 200 ብር እያሉ ካስቸገሩ በኋላ በመጨረሻም ለደርሶመልስ በ150 ብር ተስማምተን ጥቂት ኮረኮንቹን እንዳሻቀብን አጤ ካሌብ ቤተ መንግሥት ስር እንደደረስን ተነገረን፤ በእግርም ብንመጣ15 ደቂቃ እንደማይፈጅብን እያሰብን በመቆጨት፣ 60 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ መረብ ወንዝን ያቀፈውን ተራራ (የኤርትራ ድንበር) አሻግረን እያየን ወደ ቤተ መንግሥቱ ዘለቅን። ቤተ መንግስቱ እስከ ሦስት ፎቅ የሚረዝም ቢሆንም አሁን ግን ከመሬት በላይ ያለው ጥቂት ፍርስራሽ ብቻ ነው፤ ሆኖም ከመሬት በታች ያለው ክፍል አሁንም ድረስ በሕይወት አለ።

ለማንቀሳቀስ ቀርቶ ለማሰብ የሚከብዱ ትልልቅ ድንጋዮች የምድር ስሩ ቤት ኮርኒስ እና ግድግዳ ሆነው ተጋድመዋል፤ ቆመዋል፡፡

## ጥንታዊ ቤተ መንግሥቶቹ

አጤ ካሌብ ጦረኛ ንጉሥ እንደመሆናቸው ከመሬት ወለል ስር መኖሪያ መገንባታቸው አያስገርምም፡፡ ነገር ግን የዛሬ 1400 ዓመት ወደኋላ እንዲያ ዓይነት ቤተ መንግሥት ማነጽ መቻላቸው የሚያስገርም ነው፡፡ በዚያ ላይ ማብራሪያ እንደሰጡን ሽማግሌ ከሆነ ሌላም ተቆፍሮ ያልወጣ የምድር ቤት ምድር ሊኖር እንደሚችል ግምታቸውን ነገሩን፡፡ ግድግዳው ላይ ወደታች የተሳሉ ቀስቶች እያሳዩ፡፡ ይገርማል፤ የሳቸው ንግግር ቤተ መንግሥቱ እንዴት እንደተገኘ የሰማሁትን ታሪክ አስታወሰኝ፡፡ አንድ ገበሬ ሲያርስ ድንጋይ ይገጥመዋል፡፡ ድንጋዩን ሊፈነቅለው ሲሞክር የተገነባ እንደሆነ ይረዳል፡፡ ለከተማው መስተዳድር ያመለክትና መስተዳድሩ በባለሙያዎች ሲያስቆፍሩት ያንን የሚያክል ቤተ መንግሥት ተገኘ፡፡ ታዲያ የሚያስገርመኝ ነገር፤ ያ ቤተ መንግስት በ14 መቶ ዓመቶች ውስጥ አፈር ሲለብስ፣ በዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎች እና ባለ ሦስት ፎቁ ቤተ መንግሥት እንዴት ፈረሰ? እንዴት ስለአጤ ካሌብስ ስለሌሎቹ ነገሥታቶቻችን ያሉንን ያክል (የተጻፈው ቢቸግር) አፈታሪኮች አይኖሩንም?

ከዚያ መልስ ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደተገነባ የሚታመነው የንግሥተ ሳባ ቤተ መንግሥት ነበር ወደሚባለው ፍርስራሽ አመራን፡፡ ወደዚያ የሚወስደውም መንገድ ኮረኮንች ነበር፡፡ የክልሉ መንግሥት እና የከተማው መስተዳድር ለነዚህ የቱሪስት መዳረሻዎች መንገድ በመዘርጋት ገቢውን ማሳደግ እንዳለበት ለምን እንደዘነጋ በማሰብ ተገረምኩ፡፡ ቤተ መንግሥቱ ከካሌብ በጣም የሚሰፋ እና ብዙ ክፍሎች ያሉት ነው፡፡ ሆኖም ከወገቡ በታች ፈርሷል፡፡ ይሄንኛው ከካሌብ ቤተመንግሥት የሚለየው ምድር ውስጥ ክፍሎች ስለሌሉት ነው፡፡ የሚመሳሰለው ደግሞ ከምድር በላይ ያሉት ካቦች አደራደር ነው፡፡ ካቦቹ የተደረደሩት ወደላይ ከፍ ባለ ቁጥር በእርከን በእርከን በመሆኑ በመሬት ስበት የመናድ ዕድሉን ያጠብባል፡፡ እናም አሰብኩት፤ አገነባባቸው የመሬት ስበት የሚያመጣውን የመናድ ዕድል በሚቋቋም መንገድ በመሆኑ እነዚህ ሕንፃዎች የፈረሱት በሰው ሰራሽ መንገድ እንጂ በተፈጥሮ አይሆንም፡፡

ከሰዓት በኋላ ወደመቐለ የሚመለስ መኪና ብንፈልግም ማግኘት አልቻልንም፡፡ ወደመቐሌ የሚሄደው 'ቅጥቅጥ' ስላመለጠን ማግኘት የምንችለው ከአክሱም የአድዋ፣ ከአድዋ የአዲግራት፣ ከአዲግራት የመቐለ እንደሆነ ተነገረን - ያውም ከቀናን፡፡ ተጨማሪ ቀን የማደር ዕቅድ ስላልነበረን ተስፋ ቆረጥን፡፡ ዐሥር ሰዓት ላይ እወስዳችኋለሁ ያለ ለሥራ የመጣ የመንግሥት መኪና ሾፌርን መጠበቅ ጀመርን፤ ለቀጭን ጉዳይ በሄደበት የውሃ ሽታ ሁኖ በመቅረቱ ግን ለሁለተኛ ቀን አክሱም አደርን…ደግነቱ በማግስቱ ሌሊት ዐሥር ሰዓት ላይ ሁለት ባልደረቦቹን ጨምሮ መጣ፡፡

ከአክሱም ወደ መቐለ የተመለስንበት መኪና ውስጥ ያሉ የትግራይ ክልል መንግሥት ሠራተኞች ወሬያቸው በሙሉ በፖለቲካ የተቃኘ ነው፡፡ ቋንቋው ትግርኛ በመሆኑ በቅጡ አልሰማሁትም እንጂ ብዙ ቁም ነገር ሳያመልጠኝ አይቀርም፡፡ እየሾለኩ ጆሮዬ ከገቡ ቃላት ውስጥ HR2003 በተደጋጋሚ ሲነሳ ነበር፤ አድዋ ላይ ስንደርስ አንዱ ‹‹አባባ ተስፋዬ አድዋ መጥተው ‹የዛሬ አበባዎች፣ የነገ ካድሬዎች››› አሉ ብሎ አሳቀን፡፡ በየመሐሉ የመለስ ስም ተደጋግሞ ይነሳ ነበር፤ አጠገቤ የተቀመጠው እንዲያውም ‹‹የአዲስ አበባ ሕዝብ በመለስ ሞት ከማንም በላይ ማዘኑን›› ነገረኝ፡፡ በትግርኛ ሲያወራ ደግሞ ቡልቻ ‹‹ለመከላከያ ለምን 4 ቢሊዮን ብር ተመደበ?›› ብለው ሲጠይቁ መለስ ‹‹አገር እኮ በጾምና በጸሎት አትጠበቅም›› ብሏል ብሎ በሳቅ አዝናናቸው፡፡

## ቴዲ አፍሮ በትግራይ

በጉዞዋችን ላይ የምንሰማው የኤርትራ ሙዚቃ የነበረ ቢሆንም የቴዲ አፍሮን የመጨረሻ አልበምም ሹፌሩ ከፍቶልን ነበር፡፡ ወዲያው የጨዋታው አቅጣጫ ወደቴዲ አፍሮ ተሸጋገረ፡፡ ቴዲ አፍሮ ቀብር ላይ ተገኝቷል እንዴ ብለው ጠየቁኝ፡፡ ‹‹አይ ቀብር ላይ አልተገኘም፤ የተገኘው ቤተ መንግሥት ነው፡፡›› አልኩኝ፡፡ ‹‹እዚያማ ሰድበውታል አልተባለም እንዴ?›› አለኝ አልፎ አልፎ ብቻ በውይይቱ የሚሳተፈው ሹፌር፡፡ ሰምቼ ነበር፤ ግን ለምን እንደሆነ ሳላውቅ ካድኩኝ፡፡

ቴዲ አፍሮ አንዴ ትግራይ ማዘጋጃ ውስጥ ኮንሰርት አዘጋጅቶ እሱም ከተገኙት 16 ሰዎች ውስጥ አንዱ እንደነበር ጋቢና የተቀመጠው ልጅ ነገረን ‹‹እኔም ራሱ በሰው ተጋብዤ ነው የሄድኩት›› በማለት፡፡ ከኔ ጎን የተቀመጠው

ደግሞ ‹‹ገዛ ገረሥላሴ (የመቐሌ ባሕላዊ ጭፈራ ቤት ነው) መጥቶ ያቃል ግን ማን ይገባለታል?›› ሲል የአዲስ አበባውን ጣኦት አጣጣለው፡፡

ጨዋታው ቀጠለ፤ ‹‹እሱ ግን ምንድነው አስመራ፣ አስመራ የሚለው… ለምን አክሱም አይልም? ለምን ጎንደር አይልም?…›› ከጎኔ ያለው ጠየቀ፡፡ ከጋቢና ያለው ‹‹የቴዲ እናት አባት ኤርትራዊ ናቸው፤ አዲ ቋላ ነው የተወለዱት›› ብሎ ማብራሪያ ሰጠ፡፡ በጥቅሉ ግን ከወሬያቸው መንፈስ እንደተረዳሁት ከሚወዱት ኤርትራ ዘፈን ወዲህ የሚያደምጡት እሱኑ ነው፤ እንዲያው ብቻ ግራ የገባቸው አቋሙ ከማን ጋር እንደሆነ ነው፡፡ ምክያቱም ‹‹እሱ ቆይ ለምንድን ነው ከሌሎቹ አርቲስቶች ጋር አንድ ላይ የማይሆነው… ሌሎቹ ለመለስ ቀብር እንትትን ሲሉ ነበር…›› ብለዋል፡፡ ‹እንትትን› ያሉት ምን እንደሆነ አላወቅኩም፡፡

በመንገዳችን መሐል የኢትዮጵያ የመጀመሪያው የሚባለው የነጃሺ መስጊድ ጋር ከፍተኛ አከባበር አየን፡፡ ምንድን ነው ስንል ለካስ ኅዳር 15 ቀን በያመቱ መስጊዱ የቆመበት ሰደቃ አለ፡፡ ወይ ትግራይ - እውነትም ክፍት ሙዚየም፡፡

እንዲህ እንዲህ እያልን ያንን ፈታኝና ጠመዝማዛ መንገድ በኤርትራ ጉዳይ (በነገራችን ላይ ከአፋቸው የማይነጠለው የኤርትራ ወሬ ትግራዋዮች ዛሬም እንደሚናፍቋት ያሳብቅባቸዋል)፣ በወያኔና ደርግ ጦርነት እና በመለስ ሙገሳ ወሬዎች ያንን አስፈሪ አቀበት እና ጠመዝማዛ መንገድ ፉት ብለነው መቐለ ተገኘን፡፡ በተመከርነው መሠረት ወደላሊበላ ጉዟችን መቀጠል ነበረበትና የላሊበላ መኪና ነገ ጠዋት ለመያዝ ዛሬውን ወልዲያ መግባት አለብን፤ መኪና ከየት ይምጣ ለሚለው ጥያቄ ጀብደኛ መልስ አገኘንለት፡፡ 90 ኩንታል ከኂላው የጫነ አይሱዙ ውስጥ ተሳፈርን፡፡

የአይሱዙው ሾፌር ዮሐና የምትባል ከተማ ላይ በፌዴራል ፖሊሶች የተዘጋ መገንጠያ መንገድ 100 ብር ጉቦ በመክፈል አስከፈተ፡፡ ለምንድን ነው ስንለው፤ ‹‹መንገዱ እስከአላማጣ ያለውን ዳገት የሚያቀል አቋራጭ ነው ግን ገና ግንባታው እስኪያልቅ ማቋረጥ ስለተከለከለ ነው በጉቦ የምንጓዘው አለ፡፡ ከሁለት ሰዓት በላይ እንደተጓዝን ትራፊክ አዲሱ መንገድ ላይ ቆሞ ጠበቀን፤ ሾፌሩን ሦስት መቶ ብር ቀጥቶ አበሳጨው፡፡ እንደምንም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት መብራት ጠፍቶባት ‹ከፊል ጨለማማ› የሆነችው ወልዲያ ደረስን፡፡

ከወልዲያ ወደላሊበላ የተሳፈርነው በሚኒባስ ነው፡፡ ሚኒባሱ ወደ ባሕርዳር የሚወስደውን መንገድ ጥሎ ወደላሊበላ የሚገነጠለው ጋሸና የተባለች ከተማ ላይ ሲሆን ከዚያ በኂላ ያለው 64 ኪሎሜትር ውስጥ 60 ያክሉ ፒስታ በመሆኑ ከመንገጫገጩ ባሻገር ከመኪናው ስንወርድ አቧራ ላይ ኳስ የተጫወተ ሰው መስዬ ነበር፡፡ የዓይኖቼ ሽፋሽፍት ላይ ሳይቀር አቧራ ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው ግን የላሊበላ ከተማ ነገር ነው፡፡ ከላይ ለአክሱም ከተማ ጎስቋላ የሚለውን ቃል በመጠቀሜ ከጎስቋላ የከፋ ቃል ላገኝ ባለመቻሌ ሳልገልጸው አልፋለሁ፡፡

## ዕድገተ አክሱም ወ ላሊበላ

የዚህን ጽሑፍ ዋና ርዕስ የሰጠሁት የአክሱም ስልጣኔ ከመሬት በላይ የላሊበላ ደግሞ ወደ መሬት ስር የሚለውን ተንተርሼ ነበር፡፡ ሳስበው ግን የሚከተሉት ሁለት አንቀጾችም ቢጨመሩ ተገቢ ነው፡፡ በነገራችን ላይ የትግራይ ከተሞች ማማር የጀመሩት ከሦስት ዓመት ወዲህ መሆኑን አብሮኝ ተሳፈረ ያልኳችሁ የነገረኝ ሲሆን ኢሕአዴግ በ97 አዲስ አበባ ላይ ቅንጅት እንዳስደነገጠው፣ በ2002 ደግሞ አረና ትግራይ ላይ ሳያስደነግጠው አልቀረም፡፡ ዞሮ ዞሮ የትግራይ ከተሞች አድገዋል ልላችሁ ነው፤ ይህን ስል የተጋነነ ምስል እንዳትይዙ ከሌሎች ከተሞቻችን አንፃር መሆኑን እወቁልኝ፡፡ ለመንደርደሪያ ያክል ወደአክሱም ስንሄድ ያገኘነው አንድ ሰው ስለአክሱም ‹‹እያደገች ነው›› ያለንን እና ወደላሊበላ ስንሄድ ከጎኔ የተቀመጠው ደግሞ በራስ ተነሳሽነት ‹‹ዘላለም የማያልፍላት ከተማ›› ብሎ የተማረረውን ንፅፅር አስቀምጩላችሁ ልጀምር፡፡

ከአዲስ አበባ ስወጣ አክሱምን እና ላሊበላን የመጎብኘት ዕቅድ ነው የነበረኝ፡፡ አክሱም ለመድረስ እና ወደ ላሊበላ ለመድረስ በብዙ የገጠር ከተሞች ውስጥ ማረፍም ማለፍም የግድ ነውና በዚያ ሒደት ውስጥ ሳልፍ የተመለከትኩትን ሳልናገር ማለፍ ይከብደኛል፡፡ መቐሌ እንደደረስኩ በመቐሌ መደነቁን ቀድሜ ተናግሬያለሁ፡፡ ከመቐሌ ወደ አክሱም ስሄድ እና ስመለስ ያረፍኩባቸው እና ያለፍኩባቸው ከተሞች ሁሉ ተስፋሰጪ የዕድገት አዝማሚያ የሚያሳዩ፣ በተለይም ደግሞ በየመሃሉ የምናያቸውን መንገደኞች ጨምሮ (እጃቸውን በተማጽኖ

ከሚያውለበልቡት የተጎሳቆሉ አሮጊቶች በቀር) ሁሉም ነቃ ያሉ እና ከተሜነት የሚነበብባቸው ናቸው። ካየሁት መገመት እንደምችለው ትግራይ ወደ ከተሜነት እያመራች ነው።

በተቃራኒው ግን ወደ ላሊበላ ለመጓዝ ደምቢያ ስንደርስ ከተማዋ ዓይን የሚገባ ነገር የሌላት መሆንዋ ብቻ ሳይሆን መኪና እንዲፈልጉልን የምንነግራቸው ደላሎች ሁሉ ‹ሞባይል› የላቸውም፤ መቐሌ ግን ሁሉም ባለሞባይል ናቸው። አብረውን የተሳፈሩት ሁሉ ባላገርነታቸው የሚጎላ ከተሜዎች ናቸው፤ ጋሸና የተባለችው ከተማ ስንደርስ ደግሞ ከቤቶቹ ቁጥር የጫት ቤቶቹ ቁጥር የሚበዛ ይመስላል። ብቻ ልዩነቱ የሕንፃ ብቻ ሳይሆን የሰውም ነው። ከመቐሌ ወዲያ ያሉት ተስፋ ሰጪ ስልጣኔ ላይ ሲሆኑ ከዛ ወዲህ ያሉት ሁሉ ደግሞ እስካሁን ከባላገርነታቸው መላቀቅ አልቻሉም። የከተሞች እና ከተሜነት መስፋፋት ለአንድ አገር ዕድገት አመላካች አይደለም ብሎ የሚከራከረኝ ይኖር ይሆን? (ይህ እንግዴህ የድህነቱን ልዩነት ሳናነሳው ካለፍን ነው።)

ለዚህ ልዩነት ምክንያቱ ምን ይሆን ተባባልን - ከጓደኛዬ ጋ። ምናልባት የትግራይ ክልል አስተዳደሮች በጀታቸውን ባግባቡ ስለሚጠቀሙ? ከሆነስ ሌሎቹ ለምን እንደነሱ አልተጠቀሙም? ምናልባት እነሱ በመንግሥት እምነት ስላላቸውና መንግሥትም በነርሱ እምነት ስላለው ጠንክረው ስለሚሠሩ እና መንግሥትም የሚሠሩ ሰዎችን በፖለቲካዊ አመለካከት ሳይሆን በሥራ ችሎታ ስለሚሾም? ወይስ… የእነርሱ ሹመኞች እና የንግድ ሰዎች አቅም ስለናረ የከተሞቻቸውን ሕዝባዊ እና ንግዳዊ እንቅስቃሴ አሳድጎት ነው? መልስ አልነበረንም።

## ላልይበላን በጨረፍታ

ስለላልይበላ ጉብኝቱ ትረካ ሳስብ የጨነቀኝ እንደፖርቼጋላዊው ጎብኚ መታመን ያቅተኛል ብዬ አይደለም፤ ያየሁትን በትክክል መግለጽ ይቸግረኛል ብዬ ነው። የአክሱም ታሪክ ያስጎመዣል ቅሪቱ (በአካል የሚጎበኘው) ግን አንጀት አያርስም። የላሊበላ ደግሞ ተቃራኒ ነው። የሚወራው ነገር ሲታይ ከሚፈጥረው ስሜት እና አግራሞት አንጻር የሚገለጽ አይደለም። አንድ ግዙፍ ድንጋይ ወደታች ተፈልፍሎ ሕንፃ ሲወጣው፣ ሕንፃው ፎቅ እና ውስብስብ ዲዛይን ሲኖረው፣ አንዱ ክፍል ገብተው ሌላኛው ውስጥ ሲገቡ እንደገና አዲስ ሲሆን፣ ሕንፃው የተሰራው ደግሞ ከ839 እስከ 813 ዓመታት በፊት መሆኑን ሲያስቡት፣ ‹‹ወቸ ጉድ›› ያስብላል።

አንዳንዶቹ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያናት (ሕንፃዎች፤ በተለይ በቡድን አንድ እና ሁለት ውስጥ ያሉት) በፀሐይና ዝናብ መፈራረቅ ምክንያት መሰነጣጠቅ ስለጀመሩ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ ማኅበራዊ እና ባሕላዊ ድርጅት (UNESCO) ጣሪያ ተገንብቶላቸዋል። አንዳንዶቹ ምሰሦዎቻቸው በመፍረሱ በተጠረቡ ድንጋዮች ካብ ተተክተዋል - ሆኖም ግን አብዛኛው ሕንፃ እንዳለ አለ። የላሊበላ ኤርፖርት በቀን ሦስቴ (አንዳንዴም አራቴ) በረራ እንደሚያስተናግድ እና አብዛኞቹም ቱሪስቶች መሆናቸውን አስጎብኛችን ነግሮናል። እኛም እንዳየነው አክሱምን ሊጎበኙ ከሚመጡ እጅግ የበዙ የውጭ ዜጎች ጉብኝቱ ላይ አግኝተናል። እነዚህ ሰዎች ግን የሚያርፉበት ደህና ደረጃ ያለው ሆቴል ያላት ጥሩ ከተማ ነች ለማለት አይቻልም - ላሊበላ። የእውነት ቢታሰብበት የቱሪዝም ገቢዋ ብቻ ከተማዋን ማሳደግ ያቅተዋል ብሎ ማሰብ ይከብዳል።

እኛ በጣም የለመድነውና ሁሌም ስለላሊበላ ስናስብ የሚመጣልን የቤተ ጊዮርጊስ ምስል ነው። እሱ እንግዲህ የመጨረሻው የንጉሥ ላሊበላ ሥራ ነው። ከዚያ በፊት የተሠራውም ቤተ አማኑኤልም የሚያስገርም ጥበብ ግድግዳው ላይ ተሠርቷል። በስፋት ትልቁ የሆነው የቤተ መድኃኔዓለም እና የመጀመሪያ ሥራው የሆነው ቤተ ማርያም ውስጣዊ ዲዛይኖች ጥበብ ዓይን አያስከድንም። የሚገርመው የሁሉም ቤቶች ውጪያዊና ውስጣዊ ዲዛይኖች አይመሳሰሉም። ምናልባት አብዛኞዎቹን የሚያመሳስላቸው ነገር ካለ የውስጥ ምሰሦዎቻቸው እርስ በርሳቸው ሲጣመሩ የሚመሠርቱት የአክሱም ሐውልት አናትን የመሰለ ዲዛይን ነው።

ጀብዱ ለሚወድ ሰው መተላለፊያ ዋሻዎቹ ከሆኑት ውስጥ ረዥሙንና በድቅድቅ ጨለማ የተሞላውን መተላለፊያ ያለመብራት ማቋረጥ ግሩም አማራጭ ነው። አንዴ መብራት አብርቼ ካየሁት በኋላ… ጣሪያው ከአናቴ እንደሚርቅ፣ መሬቱም ድፍን እንደሆነ አይቼ… በዚያ ድቅድቅ ጨለማ ለመራመድ አንዴ ጣሪያውን ዳበስ፣ አንዴ ቀኜን፣ አንዴ ግራዬን ዳበስ ከዚያ በቀኝ እግሬ መሬቱን መታ፣ መታ አድርጌ አንድ እርምጃ፣ አሁንም ድጋሚ እንደዚያ እያልኩኝ አቋረጥኩት። በዓይናችን ላይ ያለን እምነት እንደዚህም አጋጣሚ ታስቦኝ/ተገልጦልኝ አያውቅ!

ውቅር አብያተ ክርስትያናቱን በጥድፊያ ባለችን ግማሽ ቀን ጎብኝተን/ሳንጠግበው ስንጨርስ ወደ ሙዚየሙ ወሰዱን። ሙዚየሙ ሕንፃዎቹ ሲጠረቡ አገልግለዋል ተብላ ከምትታሰብ አንዲት መጥረቢያ እስከ የመስቀል፣

የአልባሳት፣ አትሮኖሶች እና በርካታ የብራና ጥንታዊ መጽሐፎች ድረስ ይገኙበታል። በተጨማሪም ንጉሥ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያናቱን ከመጥረቡ በፊት እንጨት ፈልፍሎ የሠራቸው አምሳያዎች/ሞዴሎችም ይገኛሉ።

በመጨረሻም ነገሬን ከዚህ በላይ ሳላስረዝመው የምላችሁ ቢኖር አንድ ነው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሁለት ይከፈላል፦ ላሊበላን የጎበኘ እና ያልጎበኘ ተብሎ። ቶሎ ጎብኙት እና ከቆጫችሁ እከሰሳለሁ።



# የጉዞ ማስታወሻ የቀሰቀሰው የጉዞ ማስታወሻ ከታሪካችን ታሪክ ምጾቶችና ቁጭቶች ጋር!

በፍቅር ለይኩን

የበፍቄ የጉዞማስታወሻ ከ4 ዓመታት በፊት ከአንድ አማርኛን አቀላጥፎ መናገርና መፃፍ ከሚችል በእጅጉ ካስደነቀኝ ሰው ጋር ወደ ሰሜኑ የአገራችን ክፍል ተጉዤ ነበር፡፡ ይህ ሰው ለሁለተኛው ድግሪ ማሟያ የሚሆነውን የምርምር ጽሑፍ የመጀመሪያዎቹ የሙስሊም እምነት ተከታዮች በነቢዩ መሀመድ ትዕዛዝ ወደ አክሱም ግዛት ያደረጉትን ስደት ዋቢ በማድረግ፡-

አክሱማውያን በወቅቱ ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር የነበራቸውን ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ግንኙነቶችን በተመለከተ ለመመረቂያ የሚሆነውን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ከአሜሪካዋ የሜኔሶታ ግዛት ከመጣ አንድ አሜሪካዊ ነጭ ጎልማሳ ጋር የኢትዮጵያችንን የጥንታዊ፣ የማእከላዊና የቅድመ ዘመናዊ ታሪክና ሥልጣኔ እምብርት የሆኑትን ሰሜናዊ ከተሞቻችንን አብረን ተጉዘን ለማየት ዕድሉን አግኝቼ ነበር፡፡

ምንም እንኳን በአንጋፋው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ *Department of History and Heritage Management*/በታሪክና በቅርስ አስተዳደር የትምህርር ክፍል፡- ታሪክ፣ አርኪዮሎጂና ቅርስን ባጠናም ስለ ታሪካችንም ሆነ ስለ ቅርሶቻችን በዓይን አይተን፣ በእጆቻችን ዳሰን ምስክርነት ለመስጠት ትምህርቱ ተግባራዊ ድጋፍ የታገዘ ባለመሆኑ ከቃል የዘለለ እውቀት ለማግኘት አልታደልንም ነበር፡፡ አሁንም ድረስ በአብዛኛው በቃል ትምህርት ላይ የተደገፈው የዩኒቨርስቲው የትምህርት ሥርዓት ለዚህ ዕድል እንድንበቃ ሁኔታዎችን የሚያመቻች አይደለም እናም እውቀታችን ፊደል ዘመምነት ሚያጠቃው ነበር ብል ብዙም ያጋነንኩ አይመስለኝም፡፡

ይህ አሜሪካዊ የጉዞ ወጪዬን በሙሉ ሸፍኖልኝ በመጽሐፍ ብቻ ማውቃቸውን የትናንት ታሪኮቻችን፣ ዓለምን ጉድ ያሰኘውን ሥልጣኔያችንና ቅርሶቻችንን ሕያዋን ምስክሮችን በዓይኔ ለማየት በመቻሌ ራሴን እንደ ትልቅ ዕድለኛ ነበር የቆጠርኩት በወቅቱ፡፡ አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው እንኳን አክሱምን፣ ላሊበላንና ጎንደርን ቀርቶ በዚህ በቅርባችን የሚገኙትን ታሪካዊ ቦታዎችና ቅርሶቻችንን ስለ መጎብኘት ማውራት የቅንጦት ያህል እንዳይቆጠርብኝ በሚል አንዳች አሉታዊ ስሜት ውስጤን ተጫነው፡፡

ትዝ ይለኛል ከጉዞዬ መለስ በኋላ ከመቀሌ ከተማ የመጣችውን የክፍል ጓደኛዬን ስለ አክሱም ቆይታዬ ስነግራት፡- ‹‹አ ታድለህ!›› አለችኝ ለካ እሷም ከምትኖርበት ከመቀሌ ከተማ በሁለት መቶ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ብቻ የምትገኘውን አክሱምን ጎብኝታው አታውቅም ኖሯል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በአብዛኛው የአቅም ጉዳይ ሲሆን ሲብስ ደግሞ አንዳንዶቻችን ዋንኛ ምክንያት የሆነው ስንፍና ይመስለኛል፡፡

በአንፃሩ ደግሞ የተመቻቸ አጋጣሚና አቅምም እያላቸው ማንነታቸውን፣ የትናንት ታሪካቸውንና ቅርሶቻቸውን ከመጎብኘት ይልቅ ለአንድ ምሽት መዝናኛ በሺህ የሚቆጠር ገንዘብ የሚመነዝሩትን፣ የአገራቸው ታሪክና ቅርስ ለማወቅ ካላቸው ጉጉት ይልቅ ስለ አውሮፓ ከተሞች፣ የእግር ኳስ ክለቦችና ተጨዋቾቻቸው የጫማ ቁጥራቸውና ስለሚበሉት ምግባቸው ሳይቀር ሰፋ ያለ መረጃ ያላቸውን የሸገርን ዘመናዊዎችን ሳስብ ወይ ጉድ ለማለት እገደዳለሁ፡፡ ለማንኛውም የበፍቄ የጉዞ ማታወሻ የሰሜን የአገራችንን ክፍል ቆይታ ትዝታዬን ቢቀሰቅስብኝ እኔም የሰሜኑ ጉዞዬ ያጫረብኝን ስሜቴንና ገጠመኜን ለዞን ፱ኝ አንባቢዎች ለማጋራት ስል ብዕሬን አነሳሁ፡፡

የሰሜን ኢትዮጵያ ጉብኝታችን ላሊበላን፣ ባህር ዳርን፣ ጎንደርንና የትግራይን ዋና ዋና ታሪካዊ ከተሞችንና የቱሪስት መስህቦቻችንና ቅርሶቻችንን ያካተተ ነበር፡፡ በዚህ ጉብኝቴ አስደናቂ ገጠመኞቼ መካከልም ለዛሬ አንዱን ላካፍላችሁ ወደድሁ፡፡ ምናልባት ወደፊት የጉዞ ማስታወሻዬን መለስ ብዬ በመመልከት ስለ ጉዞዬ ገጠመኝና ስለሳደረብኝ ስሜት በሰፊው እተርከው ይሆናል፡፡

በትግራይ ቆይታችን የአክሱምን ሀውልቶች፣ የታሪካዊውን፣ ለአፍሪካውያንንና ለመላው ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ቀንዲል የለኮሰውን የአድዋን ሰንሰለታማ ተራሮችንና በዛ ትንግርተኛ ተራራ ላይ አባቶቻችን ጎሳ፣ ሃይማኖት፣ ዘር፣ ወገን ሳይለዩ… ወንድ ሴት፣ ቄስ፣ መነኩሴ፣ ሼኽ አንድ ሆነው ለጋራ ቤታቸው፣ ለጋራ እናታቸው ነፃነት፣ አንድነትና ህልውና በደማቸውና በአጥንታቸው ስለ እማማ ኢትዮጵያ ፍቅር የከፈሉት መስዋእትነት በደም ደምቆና

አሸብርቆ ሕያው ሆኖ ከሚታይበት የአድዋ ተራራ ላይ ዓይኖቼ ተሰክተው የትላንትናዋንና የዛሬዋን ኢትዮጵያን እያነጻጸርኩ ከታሪክ ጋር ሙግት የገጠምኩበት ትውስታዬ ዛሬም በኅሊናዬ ነፍስና ሥጋ ነስቶ ሕያው ሆኖ አለ።

የአድዋ የአፍታ ቆይታችንን በኋላ በመንገዳችን ላይ የጎበኘናቸው ሽሬ፣ ሀውዜን፣ የሃ፣ አዲግራትና ደብረ ዳሞ በውስጤ የተዉት ትዝታና ናፍቆት አሁንም ድረስ ሕያው ነው። በአዲግራት ያገኘናቸው ስለ አክሱማዊው አልነጃሺ ከአባቶቻቸው የተቀበሉትን አፌ ታሪክ የተረኩልን የአዲግራት አልነጃሺ መስጊድ ኢማሞች፣ ሼኽዎችና የዕድሜ ባለጸጋዎች ፍቅራቸውና ልዩ የሆነ ኢትዮጵያዊው መስተንግዶአቸው በልቤ  በማይደበዝዝ ቀለም ታትሞ በውስጤ አለ። አሁን በጉዞአችን ወቅት በሽሬ ከተማ የተከራየነውን መኪና አቁመን ለጥቂት ደቂቃዎች ባደረግነው ቆይታ ያጋጠመኝን ላውጋችኹ።

ድህነት ክፉኛ ያጎበጣት በምትመስለው በሽሬ ከተማ ላይ ባደረግነው ቆይታችን በጭቃና በድንጋዮች በተሠሩት አብዛኛው ቤቶቿ መካከል እንደ ነገሩ በቆመ የጸጉር ማስተካከያ ቤት አናት ላይ ‹‹ቴዲ ካፍሮ ጽጉር ቤት›› የሚል ስያሜ አየሁና ዓይኔም ቀልቤም ወደዚሁ የጸጉር ቤት ስያሜ ተሳበ። እናም ለአፍታ ቴዲን፣ የቴዲ አፍሮን የ1997ቱ እና የሚሊንየሙ ዋዜማ ዜማዎቹን፣ የትግራይን ሕዝብ እንወክለዋለን የሚሉትን ፖለቲከኞቻችንና የትግራይ ሕዝብን እያፈራረቅኹ በዓይነ ኅሊናዬ ለመቃኘት ሞከርኩ።

*‹‹በአስራ ሰባት መርፌ በጠቀመው ቁንጣ፣*
*ለለውጥ ያጎፈረው ወንበር ላይ ሲወጣ፣*
*… አዲስ ንጉሥ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ።*

ሁላችንም ለእርቅ፣ ለእማማ ኢትዮጵያችን ሰላምና ብልጽግና እጅ ለእጅ እንያያዝ፣ ቂም በቀል ይቅር፣  ለሕዝብ ፍቅር ራሱን አሳልፎ የሰጠ ኢትዮጵያዊው ማንዴላ ማን ይሆን… በሚሉና በመሳሰሉ የቴዲ የዜማዎቹ ግጥሞች ኃይለ ቃል ውስጣቸው በበገነ በአንዳድ አፍቃሪ ኢህአዴግ ጥርስ ውስጥ የገባው ቴዲ አፍሮ በትግራይዋ ድህነትና ጉስቁልና በተጫናት ሽሬ ከተማ ያለ ምንም ተቃውሞና ከልካይ ስሙ በትግሪኛ ቋንቋ እንደነገሩ ተወላግደው በተፃፉ የአማርኛ ፊደላት ከፍ ብሎ ተሰቅሎ ማየቴ የጥላቻ፣ የመራርነትና የጽንፈኝነት አባዜ ወዲህና ወዲያ የሚያላጋውን አገሬን ፖለቲካና ፖለቲከኞች እንደታዘባቸው አስገደደኝ።

በአምቻና በጋብቻ የተሳሰረውን፣ የሃይማኖት ልዩነት ድንበር ያልገታው በሐዘንና በደስታ የማይለያየውን፣ የእማማ ኢትዮጵያ የሀገሩ ፍቅር ስሜት በማይበጠስ የፍቅር ሰንሰለት ያስተሳሰረውን የወገኔን የአንድነት ስሜትና መስዋእትንት ከጉራ እስከ ጉንደት፣ ከዶጋሊ እስከ አድዋ፣ ከመቀሌ እስከ ማይጨው፣ ከምጽዋ እስከ ቀይ ባህር በታሪክ መነጽር ወለል ብሎ ታየኝ።

ለእማማ ኢትዮጵያ ነፃነትና አንድነት በጀግኖቻችን ደም የቀላው ቀይ ባሕር አዲስ በተፃፈ ተረት ተረት የአብሲኒያዋ ቅኝ ግዛት ስር ወድቆ ነበር የሚለው የታሪክ ምጸት በኅሊናዬ ገዝፎ ሲታየኝ በደርግ ዘመነ መንግሥት ኢትዮጵያንና ኤርትራን ለማሸማገል ተልከው የነበሩት ነፍሰ ኄር አቡነ ፊሊጶስ በእንባ በተቀላቀለበት ድምፅ በሲቃ ሆነው የተናገሩት ቃላቶቻቸው በአዕምሮዬ አቃጨለብኝ፡-

*‹‹…እውን አንተ ቀይ ባሕር የአገራችን ጠረፍ እንዳልነበርክና ስለ አንተም የአገራቸው አንድነትና ነፃነት እያንገበገባቸው የሺህዎች ጀግኖች ደም በአንተ ካልፈሰሰማ ታሪክ ይፍረደና…››* በማለት ዕንባቸውን ወደ ባህሩ የረጩበት ጎምዛዛው የታሪካችን ሙሾና እንጉርጉሮ በጆሮዬ ተሰማኝ።

ይህ የአቡኑ ደምፅ በዳሞ ተራራ ከእኔ ጋር ነበር። በስደት ወደ አክሱም በመጡት ከዘጠኙ ቅዱሳን መካከል አንዱ የሆኑት ሶርያዊው አባ ሚካኤል/በአክሱማውያን አጠራር አባ አረጋዊ በደብረ ዳሞ ተራራ ጫፍ ላይ በገደሙት ድንቅና ታሪካዊ በሆነው በደብረ ዳሞ ገዳም ባደረግነው ቆይታ ስለ ገዳሙ ታሪክና ስለ አባ አረጋዊ ያጫወቱን አባት በገለፃቸው መካከል ከተቀመጡበት ድንጋይ በሩቅ ያለውን ተራራ አሻግረው እያዩ ልጆቼ ያ የሚታያችሁ የኢትዮጵያና የኤርትራ ድንበር ነው አሉን የተቆራረጠ በሚመስልና ሽምግልና በተጫነው ድምፁት።

በእኚህ አረጋዊ መነኩሴ በንግግራቸው ውስጥ አድማሱን ታኮ በርቀት ድብዝዝ ብሎ በሚታየው ተራራ ላይ የተተከለው ዓይናቸው ለኤርትራና ለኤርትራውያን ያላቸውን ናፍቆትና ስስት በሚገባ የሚያጋልጥ ነበር። ዘመናት ያላስረጁት በፍቅር የጸና፣ በደም የደመቀ የአንድነታችን አሻራ፣ የእነዚህ ሁለት ሕዝቦች የጋራ ታሪክ ከግዙፉ የታሪካችን ማህደር ደምቆና ጎልቶ ቢታየኝ ዓይኖቼ ዕንባ አቆረዘዙ፣ እኔም ከደብረ ዳሞ ባሻገር በእኚህ መነኩሴ

ልብ ያልተረሳችው፣ በታሪክና በአባቴ ትዝታና ትርክት ውስጥ በውስጤ የገዘፈችው ኤርትራ/አስመራ በዓይነ ኅሊናዬ ታየችኝ።

የሸሬው የቴዲ ካፍሮ ጸጉር ቤት ማስታወቂያ፣ ዳህላክ ከሚለው ዜማው፣ ከሁለቱ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በታሪክና በባህል በተሳሰሩ የዛሬዎቹ ሁለት ሕዝቦች ተራ በተራ በአዕምሮዬን ጓዳ መፈራረቅ ያዙ። ኅሊናዬ ከግዙፉ ታሪካችን መካከል በደም የተመረቀውን በጎሳና በዘር መለያየት የጠየመውን የታሪካችንን ታሪክ ጉድ፣ ጉዳንዳንጉድ ማመላለስ ጀመርኩ። እናም የተሳፈርንበት የመለያየት፣ የጎሰኝነት ባቡር ማብቂያው የት ሊሆን እንደሚችል ሳስብ ውስጤን የሐዘን ደመና ሸፈነው።

በአንድ ወቅት ፕ/ር መስፍን በአንድ ጽሑፋቸው እንዳሉት፡- ‹‹ባቡሩ በዘረኝነት፣ በጎሳ፣ የጥፋት፣ በመለያየትና በጥላቻ እንዲህ ባለ አስፈሪ ፍጥነት መምዘግዘግና ሊያደርሰው ያለው ጥፋት ሲታሰበኝ እኔም እ-ግ-ዚ-አ እ…ማ…ማ…ዬ…፣ እ-ግ-ዚ-አ…አ…አ…አ ኢ-ት-ዮ-ጵ-ያ…ያ…ያ…ያ፣ እናት አገሬ… ለማለት ወደድኹ በለሆሳስ።

የበፍቄ የሰሜን ኢትዮጵያ ቆይታው ከአራት ዓመታት በፊት የሰሜኑ የአገራችን ክፍል ቆይታዬን ቢያስታውሰኝ ትውስታዬን ከታሪካችን ታሪክ በመነሳት እንዲህ ልተርከውና ዛሬያችንን በትናንት የታሪካችን መስታወት እጅግ በጣም በጥቂቱ እንዲህ ልፈታትሸው ሞከርኩ። እናም በዛች በትንሽዋ የሸሬ ከተማ ከፍ ብሎ የተሰቀለው የቴዲ ካፍሮ ጸጉር ቤት በርካታ የአሳብ ግትልትሎችን በውስጤ አመጣብኝ።

ከያኒው እንደዘፈነውና እንደተመኘልን በቅን ኅሊና፣ በበጎነት፣ በሕዝብ ስለ ሕዝብ ፍቅር የተጋ ንጉሥና መሪ ማየት ሳንታደል በጥላቻና በመረጋጋም አባዜ ተጠላልፎ የወደቀውን ትውልዴን፣ የዘመኑን መሪዎቻችንና ፖለቲከኞቻችንን ሳስብ መጨረሻችን ምን ይሆን አልኩ በልቤ፣ ከልቤ!?

ይቅር እንባባል፣ ቂም በቀል ይቅር በሚል መንፈስ እርቅን፣ ፍቅርን ለአገሩና ለሕዝቡ የሰበከው የወጣቱ ከያኒ ዜማ ዛሬም ተግባራዊ የሆነ ምላሽን ያገኘ አልመሰለም። ዛሬም እርስ በርሳቸው የሚካሰሱ፣ የአንዱ ውድቀት ጮቤ የሚያስረግጠው፣ ለበቀልና ለጥፋት የተሳሉ ሠይፎች ቁጥራቸው እየተበራከተ ነው።

ዛሬ ዛሬ የእርቅ፣ የፍቅርና የሰላም መዝገብ ናቸው ተብለው በሚታሰቡት የሃይማኖት ተቋማት እንኳን የምናየውና የምንሰማው ጉድ ጆሮን ጭው የሚያደረግ እየሆነ ነው። ለአብነትም ያህል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እያየነውና እየሰማነው ያለው ነገር ከመስገረም አልፎ ምን ዓይነት ጉድ ነው በሚል እጃችንን አፋችን ላይ እንድንጭን እያደረገን ነው።

የኢትዮጵያው ሲኖዶስ፣ ሕጋዊውና ስደተኛው ሲኖዶስ፣ ገለልተኛ… በሚል መለያየትና እንዲያም ሲል የትግሬ፣ የአማራ፣ የጎንደሬ… አብያተ ክርስቲያናት በሚል በአገር ቤትና በውጭው ዓለም እንደ አሜባ ተከፋፍለው በዓይነ ቁራኛ የሚተያዩትን ቤተ አምልኮቻችንንና አገልጋዮቻቸውን ማሰብ ነፍስን በጣሙን የሚያደክምና የሚፈትን ነው።

እርስ በርሳቸው ተከፋፍለው ያሉ የሃይማኖት አባቶች ለራሳቸውም ሆነ ለሕዝባቸው የሰላም ሰባኪና ፍቅር መስዋእት ሊሆኑ ቀርቶ በእኔ ልሾም፣ አሁን ተራው የወሎ፣ የጎጃሜ፣ የኦሮሞ …ወዘተ በሚል በጎሳ ፖለቲካ ውስጥ ተዘፍቀው አደባባዮቻቸው የብዙዎች ድኾችና ፍቅርን እውነተኛ ፍርድንና ፍትህን ያጡ የበርካታ ራሄሎችና መጻጉዎች እንባዎች የሚፈሱባቸው የግፍና የወዮታ አደባባይ ወደ መሆን ተለውጠዋል።

እርቅን፣ ፍቅርን፣ አንድነትን፣ ሰላምን የሚሰብኩ ማንዴላዎች ገና በአገራችን የፖለቲካ ሰማይ ላይ ከፍ ብለው ደምቀው ለመታየት አልቻሉም፣ እናም መለያየቱ ጎሰኝነቱ ዘርኝነቱ ከቤተ መንግሥት እስከ ቤተ ክህነቱና መስጊዱ ተባብሶ ቀጥሏል። የሕዝብ ብሶትና ጩኸት ማሰማት ያለባቸው ስለ እውነት፣ ፍቅርና ፍትህ መቆም ያለባቸው ከያኒዎቻችንም ያልበላንን ሲያኩልን የሚውሉ ላም ባልዋለብ ኩበት ለቃሚዎች ሆነው የጥበብን ንጹህ ነፍስያ ክፉኛ እያጎደፏትና እያሳደፏት ነው።

ለአብነትም ያህል በቅርቡ የጠቅላይ ሚ/ሩን ሞት ተከትሎ እንደ ንዋይ ደበበ ያሉ አቀንቃኞች አቶ መለስን ከሙሴ ጋር ሲያነፃፅሩና ከፈጣሪ ዘንድ ልክ እንደ ሙሴ ሕዝቤን ግዛ ተብሎ የሙሴ በትር የተሰጠው ነቢይ አድርገው በመቁጠር ሲያቀነቅኑላቸው ኅሊናቸውን ትንሽ ስቅቅ አላላቸውም። ለመሆኑ ንዋይና መሰሎቹ የሊቀ ነቢያትን የሙሴን ታሪክና የአመራር ጥበብ *(Exraordinary Leadership Wisdom and Skill)* በሚገባ ያውቁት ይሆን ወይስ… ብለን እንድንጠይቅ እንገደዳለን።

በፈጣሪው ዘንድ እጅግ ትሑት የሚል ምስክርነትን ያገኘውና የእስራኤልን አምላክ ያሕዌን ፊት ለፊት የማነጋገር ልዩ ክብርንና ዕድልን የተጎናጸፈው ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን ከ*430* ዓመታት የግብፅ ባርነት ያወጣ ብቻ ሳይሆን ሕዝቡን እንደ ነፍሱ የሚወድ፣ ለሕዝብ ተፈጥሮ፣ ለሕዝቡ ኖሮ፣ ለሕዝቡ መስዋእት ሆኖ ያለፈ ከሰውም ከአምላክም ዘንድ ምስክርነት የተሰጠው መሪ ነበር፡፡

ይህ የዓለማችን ታላላቅና ጥበበኛ መሪዎች ተምሳሌት ተደርጎ የሚወሰደው ሙሴ በአንድ ወቅት ፈጣሪውን ይህን ሕዝብ በምድረ በዳ ከምታስቀረው እኔን ለዘላለም ከሕይወት መጽሐፍ ደምስሰኝ በማለት ለሚመራው ሕዝብ ያለውን ፍፁም ፍቅርና ክብር በተግባር የሳየ ታላቅ መሪ ነበር፡፡ ሙሴ በሕዝቡ ፍቅርና ክብር ራሱን የዘነጋ በመንፈሳዊው ሆነ በዓለማዊው የመሪነት ሞዴል ሆኖ የሚጠቀስ መሪ ነው፡፡

እንዲህ ዓይነት ልዩ የሆነ የአመራር ጥበብና የሕዝብ ፍቅረ የነበረውን ሙሴን ልናወዳድር ብንፈቅድ አቶ መለስና የትግል ጓዶቻቸው ውድና ብርቅ የሆነውን የወጣትነት ወርቃማ ዘመናቸውን በጊዜው ከነበራቸው ምቾትና ወደፊትም ከትምህርታቸው በኂላ ሊገጥማቸው የሚችለውን ከፍተኛ ቦታ እንደምንም በመቁጠር ዱር ቤቴ ብለው ወደ በረሃ የከተሙበት ቆራጥ የትግል መንፈሳቸው ከሙሴ ጋር ሊያመሳስላቸው ይችል ይሆናል ብለን እናስብ እንችል ይሆናል፡፡

በተረፈ ግን ሕዝቡን ከራሱ በላይ በመውደድ ነፍሱን እንኳን ለመስጠት ወደኂላ ያላላውን ሙሴን ‹‹ሥልጣን ወይም ሞት!›› በማለት ማን ወንድ ነው ከወንበሬ የሚነቀንቀኝ የሚል ኃይልን ከሙሴ አመራር ጥበብ ጋር ማወዳደር እብደት ነው የሚሆነው፡፡ ለዚህ ምርጫ *1997*ትን ተከትሎ የሆነውን የንጹሐን ኢትዮጵያውያንን እልቂት፣ ስደትና መከራ ብቻ ማስታወስ ከበቂ በላይ ነው፡፡

በሰሜኑ ጉዞዬ ትዝታ ተነስቶ ውሉ የጠፋ ወደ ሚመስለው ፖለቲካችን የተንደረደረው ጽሑፌ ለዛሬ በዚህ ልቋጨው ወደድሁ፡፡ ወደ ፊት ብንኖርና እግዚአብሔሩ ቢፈቅድ በቀጣይ የጉዞ ማስታወሻዬን ቀኘት በማድረግ በታሪክ፣ በቱባ ባህል፣ ሺህ ዘመናት በሚቆጠርላቸው ቅርሶች ስለ ተዋቡት፣ ትንግርታዊው ሰሜኑ የኢትዮጵያችን የጉዞ ማስታወሻዬ ሌሎች ገጠመኞቼን አንስቼ ጥቂት ለማለት እወዳለሁ፡፡

# አክሱምን ወላይታ አገኘሁት!!! (የአርባ ምንጭ ጉዞ ማስታወሻዬ)

ኅዳር 12 ቀን 2005 ዓ.ም በሥራ ጉዳይ ወደ ጋሞ ጎፋ ዞን ዋና ከተማ አርባ ምንጭ መሄድ ነበረብኝ፡፡ ለሁለት ቀን ተኩል የሚበቃኝን ሸክፌ ከመሥሪያ ቤቴ በተመደበልኝ መኪና ከቀኑ 8:00 ሰዓት ላይ ለሚነሳው በረራ ለመድረስ ወደቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ጉዞ ጀመርኩ፡፡ በቅዱስ ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን በኩል ወደ ቦሌ የሚወስደውን መንገድ ይዘን ስንጓዝ ከመንገዱ ግራ እና ቀኝ ላይ የተደረደሩት የፌደራል ፖሊስ አባላት አቀባበል ወይንም ሽኝት የሚደረግለት ባለሥልጣን/እንግዳ እንዳለ ስለጠቆመኝ መንገዱ ሳይዘጋ ቦሌ ለመድረስ ጥረት እንዲያደርግ ለሹፌሩ ጠቆምኩት፡፡ ብዙም ሳንጓዝ አትላስ ሆቴል የትራፊክ መብራት ላይ ስንደርስ በስፍራው የነበሩት የትራፊክ ፖሊሶች ወደ ቺቺንያ ወይንም ወደ ቦሌ ሩዋንዳ የሚወስደውን መንገድ እንድንጠቀም አስገደዱን፡፡ ወዲያውኑ ሰዓቴን ተመለከትኩ፤ ለሰባት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ይላል፤ ብዙም አልተረበሽኩም፡፡ በስተቀኝ በኩል ታጥፈን በውስጥ ለውስጥ አቋራጭ መንገድ ጥቂት ከሄድን በኋላ መልሶ ዋናውን መንገድ ስላገናኘን መኪናውን አቁመን እንግዳውን እስኪያልፍ መጠባበቅ ጀመርን፡፡

በዚያው ሰሞን ወደ ሩዋንዳ ዋና ከተማ ኪጋሊ ሄዶ የነበረ አንድ የሥራ ባልደረባችን በአምስት ቀን ቆይታው ሁለት ጊዜ በመንገድ ያለፋቸው ፕሬዝዳንት ፖል ካጋሜ በከተማው መንገድ ላይ ሲጓዙ እሳቸው ከሚጓዙበት አቅጣጫ በተቃራኒው የሚወስደው የመንገዱ ጎን ክፍት እንደሚሆን የነገረኝን ለሹፌሩ እያጫወትኩት ሳይረን እያሰማ የሚከንፈውን ሞተረኛ ተከትለው ካልተሳሳትኩ አምስት መኪኖች በፍጥነት ወደ ቦሌ የሚወስደውን መንገድ ይዘው ሲያልፉ አየን፡፡ ካለፉት መኪናዎች ሦስቱ ባለግርማ ሞገሶቹ ጥቋቁር ሼቭሮሌቶች ነበሩ፡፡ ያለፉት ባለሥልጣን ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ መሆን አለባቸው (በእርግጥም ነበሩ፤ ለሥራ ጉብኝት ወደ ጎረቤት ሀገር ኬንያ እያቀኑ)፡፡ እንደ ሥራ ባልደረባችን ከሆነ ፕሬዝዳንት ካጋሜን የሚያጅቡት አንድ ሞተረኛ ፖሊስ ከፊት እና አንድ መኪና ከኋላ ሆነው ነው፡፡ ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ይህን ሁሉ ጥበቃ የሚደረግላቸው ከፕሬዝዳንት ካጋሜ ይልቅ ለደኅንነታቸው የሚሰጉ መሪ ስለሆኑ ነው? ወይስ ኢትዮጵያዊያን ከሩዋንዳዊያን ይልቅ አስፈሪ ሕዝብ ስለሆንን? ይህንን እቆቅልሽ እያሰላሰልኩ መንገዱ ተከፍቶ ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ የአገር ውስጥ በረራ የሚደረግበት ጣቢያ ቁጥር 1 ደረስኩኝ፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድን ቀልቤ አይወደውም፡፡ ምናልባት የመጀመርያ በረራ ባደረኩበት ወቅት በድርጅቱ እንዝላልነት ምክንያት ያጋጠመኝ በሕይወቴ ከዛ በፊትም ሆነ በኋላ አጋጥሞኝ የማያውቅ እንግልት ተፅዕኖ አድርጎብኝ ይሆናል፡፡ ጥሎብኝ ደግሞ በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ቦታ የምሰጣቸው የቤተሰብ አባላት እና የቅርብ ጓደኞቹ ለአየር መንገዱ ተቀጥረው ሠርተዋል/እየሠሩ ነው፡፡ አየር መንገዱ ላይ ያለኝ አቋም ከነዚህ ወዳጆቹ ጋር አልፎ አልፎ ቅራኔ ውስጥ ይከተኛል፡፡

ተርሚናሉ ውስጥ ገብቼ በመፈተሻ መሳሪያው ካለፍኩ በኋል የያዝኩት ሻንጣ ማሽኑን አልፎ እስኪመጣ ቀበቶዬን እያጠለኩ ስጠባበቅ ‹‹ወደ አርባ ምንጭ ስለሆነ እንጂ ሌላ ቦታ ቢሆን አይፈቀድም›› የሚለው ከማሽኑ ጀርባ ተቀምጣ ሻንጣዎች ውስጥ ያለውን እቃ በምስል የምትከታተለው የጥበቃ ባለሙያ ንግግር ቀና አደረገኝ፡፡ ‹‹አቤት›› አልኳት በተገረመ ድምፅ፡፡ ‹‹አይ አንተን አይደለም›› አለችን በአገጯ ከአጠገቤ የቆመውን ሰው እየጠቆመችኝ፡፡ ሰውየው ስሙ ያልተጠራው እሱ ሻንጣ ውስጥ ያለው እቃ ምን እንደሆነ ገብቶታል፡፡ ተረጋጋሁ፡፡ ወዲያው ደግሞ ሌላ ሐሳብ ገባኝ፤ ሌላ በረራ ላይ የማይፈቀድ ነገር ግን አርባምንጭ ስለሆነ የሚፈቀድ እቃ ምንድን ነው?

የአየር መንገዱ ሠራተኞች የ‹ቼክ-ኢን› ሰዓታቸው የደረሱትን በረራ ተሳፋሪዎችን በሁለት መስኮቶች እያስተናገዱ ነበር፡፡ ከሚያስተናግዱት የአየር መንገዱ ሠራተኞች መካከል አንደኛዋ ፀጉሯን መሸፈኛ (በእስልምና እምነት ሥርዓት) ‹ሂጃብ› አድርጋለች፡፡ ‹ሂጃቡ› ከለበሰችው የአየር መንገዱ ሰራተኞች የደንብ ልብስ ጋር አብሮ እንዲሄድ መደቡ ነጭ ሆኖ አረንጓዴ መስመሮች ያሉበት ሲሆን በቀጭኑ ‹የኢትዮጵያ/Ethiopian› የሚል ጽሑፍ አርፎበታል፡፡ ብዙ ድርጅቶች እንኳን ለሠራተኞቻቸው ይቅርና ለሚያገለግሏቸው የእስልምና እምነት ተከታዮች ምቾት እምብዛም እንደማይጨነቁ ስለማውቅ በአየር መንገዱ እርምጃ ተደሰትኩኝ፡፡ ወድያውኑ ስልኬን አውጥቼ ብዙ ግዜ በአየር መንገዱ ላይ የማማርርባት ጓደኛዬን ቁጥር መታሁ፡፡ ስልኩ ሲነሳም በአየር መንገዱ ውስጥ እንዳለሁ ጠቅሼ የደወልኩት እንደበፊቱ ለማማረር ሳይሆን ባየሁት ነገር ደስ ስላለኝ እንደሆነ፤ ጥፋት ሲሆን እንደማማርረው ሁሉ በቀጣሪዋ ሥራ ስደሰትም ማመስገን እንዳለብኝ ጉራ ቢጤ ቸበቸብኩ፡፡

ከፊቴ ከነበሩት ሰዎች ቁጥር አንፃር ሰልፍ ላይ ረጅም ሰዓት ያሳለፍኩ ስለመሰለኝ ‹ቼክ-ኢን› አገልግሎት የሚሰጡት ሠራተኞችን መከታተል ጀመርኩ፡፡ ጥርጣሬዬ ልክ ነበር፡፡ እኔ ስደርስ ቀድመውኝ ከፊቴ ከነበሩት

መንገደኞች መካከል ከሦስት በላይ ተሳፋሪዎች ‹ቼክ-ኢን› ጨርሰው ወደ እንግዳ መቆያ ስፍራ አልተመሩም፡፡ ችግሩን ለማጣራት ሞክሬ ጥፋቱ የደንበኞች አገልግሎት የሚሰጡት ሠራተኞች እንዳልሆነ ተረዳሁኝ፡፡ ችግሩ ሠራተኞቹን የሚረዳቸው ‹ሲስተም› እክል ስለገጠመው ነበር፡፡ የመንገድ መዘጋቱን ተከትሎ አብዛኛው ተሳፋሪ ዘግየት ብሎ በመድረሱ ምክንያት ሰልፉ በርከት ብሏል፡፡ የደንበኞች አገልግሎት ሰራተኞቹ ደንበኞቻቸውን በቶሎ ማስተናገድ ስላልቻሉ ኮምፒውተር እየቀያየሩ ይሞክራሉ፣ ስልኮቻቸውን እያነሱ ችግሩን ለበላይ ሰዎች ለማስረዳት ይሞክራሉ፣ ፊታቸው ላይ መጨነቃቸው ያስታውቃል፡፡ እዛው ሰልፍ ላይ ሆኜ ለስምንት ሰዓት አስራ አምስት ደቂቃዎች ብቻ ቀሩት፡፡ አርባ ምንጭ ስራዬን የምጀምረው በማግስቱ ስለነበር ማርፈድ አላስጨነቀኝም፡፡ ነገር ግን ከአየር መንገዱ የተሰጣቸውን ሰዓት ተንተርሰው የሥራ ወይንም ሌላ ቀጠሮ የያዙ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ገመትኩኝ፡፡ ‹‹ቀድሞ ማመስገን ኋላ ለሐሜት ይቸግራል›› የሚለውን የሀገሬን አባባል አስታወስኩኝ፡፡

ስምንት ሰዓት ሊሆን ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩት አንድ በአካባቢው ከዛ ቀደም ያላየሁት በእጁ መገናኛ ሬድዮ (ዎኪ-ቶኪ) የያዘ የአየር መንገዱ ሠራተኛ (የቅርብ አለቃ ይመስለኛል) ወደ ጅማ እና አርባ ምንጭ የምንሄድ ተሳፋሪዎችን ጠይቆ ከሰልፉ ውስጥ ለይቶ ‹ቼክ-ኢን› በ‹ማንዋል› እንዲሰራልን አዝዞ ወደ አውሮፕላኑ በቀጥታ እንድንሳፈር አደረገ፡፡

## የወሰደኝ ጢያራ

አውሮፕላኑ ውስጥ ተሳፍረን ቦታ ቦታ ከያዝን በኋላ የበረራ አስተናጋጆቹ የሻንጣ ማስቀመጫ ሳጥኖቹን መዝጋት ጀመሩ፡፡ ከተቀመጥኩበት ወንበር ቀጥሎ የነበረው ወንበር አናት ላይ የነበረው ሻንጣ ማስቀመጫ እንደሌሎቹ በቀላሉ ሊዘጋ አልቻለም፡፡ የበረራ አስተናጋጅዋ መዝጊያው ላይ ኃይል ጨምራ ወረወረችው፡፡ ለጆሮዬ የሚረብሽ ድምፅ ነበር፡፡ በመጀመርያ ሙከራዋ መዝጋት ስላልተሳካላት የበለጠ ኃይል ተጠቅማ ሞከረችው፡፡ ቁጣ የሞላው ፊት ይዤ ዞርኩኝ፡፡ አስተናጋጇ አልዘጋ ካለው ሻንጣ ማስቀመጫ ስር ትይዩ የተቀመጡትን መንገደኞች (በእርግጠኝነት ድምፁ ከኔ በላይ ይረብሻቸዋል) ፈገግታ የተሞላበት ይቅርታ ጠይቃ ወደ መውጫው በር አመራች፡፡ ስትመለስ በግሪስ የተበላሸ ነጭ ቱታ የለበሰ መካኒክ አስከትላ መጣች፡፡ የሻንጣ ማስቀመጫውን ለመዝጋት የመጀመርያ አማራጭ አድርጎ የወሰደው አስተናጋጇ ስታደርግ የነበረውን መድገም ነበር፡፡ ለሱ ተሳካለትና እየተንጎማለለ ወረደ፡፡

ጉዞ ለመጀመር አውሮፕላኑ ወደ መንደርደሪያው ሲያመራ ከበረራ አስተናጋጆች ውስጥ አንዷ በድምፅ ማጉያው ሰላምታ አስቀድማ ‹‹ይህ በረራ ከአዲስ አበባ በጅማ አድርጎ ወደ አርባምንጭ የሚሄድ ነው…›› አለችን፡፡ ‹ወቸ ጉድ› አልኩኝ በሆዴ ትኬቱን ለማግኘት ሻንጣዬን እየከፈትኩኝ፡፡ ትኬቱ ላይ እንዲህ የሚል ተጽፏል፤

| | | |
|---|---|---|
| DATE | BRDOFF | TIME |
| 21NOV | ADDAMH | 1400 |

ከዚህ ውጭ አርባ ምንጭ ከመድረሳችን በፊት ጅማ እንደምናርፍ የተጻፈ ነገር የለውም፡፡ በረራዬን ሳስመዘግብም ሆነ (በኋላ ጠይቄ እንደተረዳሁት) የመሥሪያ ቤቴ ጉዳይ አስፈፃሚ ትኬቱን ሲገዛ ይህ መረጃ አልተሰጠኝ/ንም፡፡ ምናልባት ከመሳፈሬ በፊት የበረራ መነሻ እና መድረሻ ሰዓት የሚያሳዩት የቴሌቪዥን መስኮቶች ላይ በረራው በጅማ በኩል አድርጎ ይጓዛል የሚል መረጃ ከነበረ አላስተዋልኩም፡፡ ኖሮ ከነበረም ከአዲስ አበባ አርባ ምንጭ ለመድረስ የሚፈጅብን 65 ደቂቃ መሆኑ ቀርቶ ከሁለት ሰዓት በላይ መሆኑን በመጨረሻ ሰዓት ማወቅ ለውሳኔ የሚረዳ መረጃ አይደለም (It's Irrelevant)፡፡

አውሮፕላኑ ምድርን ለቆ የአየር ጉዞ ጀምረን የወንበር ቀበቶችንን መፍታት እንደምንችል ከተነገረን ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንድ ተሳፋሪ ከመቀመጫው ተነስቶ ሻንጣውን ከፈተና በላስቲክ የታሸገ ነገር አውጥቶ ወደወንበሩ ተመለሰ፡፡ ከተቀመጠ በኋላ የወንበር ማስደገፊያውን (ጠረጴዛ) አወረደና ላስቲኩን ፈትቶ አስቀመጠው፡፡ ዓይኔን ማመን አቃተኝ፡፡ ሰውየውን አስታወስኩት፡፡ በር ላይ የጥበቃ ባለሙያዋ በረራው ወደ አርባ ምንጭ ስለሆነ እንዲያሳልፍ የፈቀደችለት ጫት ነበር፡፡ ከበረራ አስተናጋጆቹ አንዷ ጫቱን ባየች ጊዜ ወደ ተሳፋሪው ጠጋ ብላ ሹክ አለችው፡፡ ወድያውኑ ላስቲኩን ጠቀለለና ወደ ሻንጣው መለሰው፡፡ አየር መንገዱ ተሳፋሪዎች በረራ ላይ ትንባሆ ማጨስ የሚከለክል መሆኑን አውቃለሁ፤ ጫት እንዳይቅሙ የሚከለክል መመርያ እንዳለው ግን አላውቅም፡፡ የጥበቃ ባለሙያዋ ለምን እንደፈቀደች እና የበረራ አስተናጋጅዋ ለምን እንደከለከለችው (በግምት ነው) ግልፅ አልሆነልኝም፡፡

ጅማ አርፈን የጅማ ተሳፋሪዎችን አወረድንና አዳዲስ ሰዎች ወደ አውሮፕላኑ ገብተው በወረዱት ሰዎች ምትክ ሞሉት፡፡ ከጅማ ወደ አርባ ምንጭ ለዛውም በአውሮፕላን የሚሄዱ ይህን ያክል ሰዎች መኖራቸው አልዋጥልህ አለኝ፡፡ እንደተለመደው የበረራ አስተናጋጅዋ ‹‹…ይህ በረራ ከጅማ ተነስቶ በአርባ ምንጭ ወደ አዲስ አበባ የሚሄድ ነው …››፡፡ አሁን ‹ይህቺ ነገር የተለመደች ናት ማለት ነው› አልኩኝ ለራሴ፡፡

የማይደረስ የለም እና አርባ ምንጭ ደረስኩኝ፡፡ ከአውሮፕላኑ ወርደን ወደ ጣብያው እንግዳ ማረፍያ ስንገባ ሁለት የሰማይ ስባሪ የሚያካክሉ ነጮች የመገናኛ ሬድዮናቸውን ወገባቸው ላይ አንጠልጥለው ከአውሮፕላኑ የወረደውን ሰው በዓይኖቻቸው ይመረምራሉ፡፡ የወታደር ስሪያቸው የዘነጋሁትን ነገር አስታወሰኝ፡፡ የዩናይትድ ስቴትስ መከላከያ ሚኒስትር መሥሪያ ቤት ‹በወዳጅ› ሀገራት ካቋቋማቸው ሚሳኤል ተሸካሚ ሰው አልባ በራሪዎች (ድሮን) ከሚያስነሳበት ጣብያ አንዱ አርባ ምንጭ አየር ማረፊያ ላይ ይገኛል፡፡

## ለምለም ካሉስ - አርባምንጭ

ከአርባ ምንጭ አየር ማረፊያ አንስቶ ከተማ ድረስ የሚወስደው መንገድ ‹ኢትዮጵያ ሀገሬ ልምላሜሽ ማማሩ› የሚለውን ዘፈን ያስታውሳል፡፡ ናሽናል ጂዮግራፊ ላይ ድሮ የታንዛንያ ፓርኮችን አይቼ በተፈጥሮ ውበታቸው የቀናሁት አርባ ምንጭን ስላላየኂት ብቻ እንደሆነ ገባኝ፡፡ ግራ ቀኙ አረንጓዴ ነው፡፡

አርባ ምንጭን በአካል ሄጄ ሳያት የመጀመርያዬ ነበር፤ ሆኖም ዞር ዞር ብዬ ከተማዋን ለማየት ከሄድኩበት ሥራዬ የሚተርፍ በቂ ጊዜ አላገኘሁም፡፡ ከተማዋ የሁለት ‹ክፍለ ከተሞች› ውጤት ናት - ሲየቻ እና ሲቀላ፡፡ ሲየቻ የአርባ ምንጭ ከተማ ንግድ እንቅስቃሴን የሚመራው ክፍል ሲሆን ሲቀላ ደግሞ የዞኑን ጽሕፈት ቤት እና የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ጊቢን ጨምሮ የመንግስት ተቋማትን አቅፎ የያዘው የከተማው ክፍል ነው፡፡

## አርባ ምንጭ

*‹‹ኑድሬ ጋሞ ጎፋ አይቻ አርባ ምንጭ፤*
*ምዝሪ ካልሲሪ የዴስ አባያ ጫሞ ሙሌ››*

(ትርጉሙ፡- ‹‹ሀገሬ ጋሞ ጎፋን ጎብኙ አርባ ምንጭን ኑ እዩ፣ አባያ እና ጫሞ ሙሉ ናቸው ጠግባችሁ ጠጥታችሁ ትመለሳላችሁ› እንደማለት ነው) ሲል አዚሞ ከተማዋን እና ነዋሪውን ላሞገሰበት እና ላስተዋወቀበት ውለታው ለአርቲስት አቡሌ ጫቦ ሲየቻ መሐል አደባባይ ላይ የመታሰቢያ ሀውልት አቁማለታለች - ይህ ሀውልት ለከተማው ብቸኛው ነው፡፡

አርባ ምንጭ በርካታ ውኃ ሀብት ባለቤት ናት፡፡ ከአርባ ምንጭ የአየር ማረፊያ ወደ ከተማው ሲሄዱ የሚያገኙት የኩልፎ ወንዝ ከገፀ-ምድር የውኃ ሀብቶቿ የመጀመርያው ነው፡፡ አባያ እና ጫሞ ደግሞ በዓሳ ምርታቸው በመላው ኢትዮጵያ ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው ሀይቆች ናቸው፡፡ ከዚህ ላይ ደግሞ የከተማዋ ስም መነሻ የሆኑት አርባዎቹ ምንጮች አሉ፡፡ ሁለቱ ሀይቆች ብዛት ላላቸው አዞዎችም መኖርያ ናቸው፡፡ በሲየቻ በኩል ለማግኘት የሚቀለውን ጫሞን ጠጋ ብዬ አይቻለሁ፡፡ ሀይቁ የከተማው ሰው በተለምዶ የእግዜር ድልድይ ብሎ የሚጠራው ጉብታ ጋር ትግል ላይ ይመስላል - ከመንትያው የአባያ ሀይቅ ጋር ለመቀላቀል፡፡ የጫሞ ሀይቅ አዞዎች የዋሆች ናቸው ይላቸዋል ሀገሬው፤ ከአባያ ሀይቅ አዞዎች አይምሬነት ጋር እያነፃፀረ፡፡

ከተማዋ ውስጥ ያለው የፈረንጆች ብዛት ያስገርማል፡፡ እንደዚህ ብዛት ያላቸው የውጭ ሀገር ተወላጆች በብዛት የሚገኙበት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ሌላ ከተማ ማየቴን እጠራጠራለሁ፡፡ የድሮን ማዘዣ ጣብያውን ተከትሎ የመጡት አሜሪካውያን ናቸው ከተማዋን ያጥለቀለቋት ብዬ አስቤ ነበር፡፡ ነገር ግን ብዛታቸው እና የሚያወሩት ቋንቋ ቅይጥ መሆን ግምቴን አፈረሰው፡፡ እንደውም በኋላ ጠይቄ እንደተረዳሁት የአሜሪካን ወታደሮች ከከተማው ሰው ጋር የሚገናኙት ለገበያ እና ለመዝናናት ከሚኖሩበት ካንፕ ሲወጡ ነው፡፡ የሚኖሩበት ካምፕ ፓራዳይዝ ሎጅ ይባላል፡፡ እጅጉን የሚጠበቀው ይህ ሎጅ ከአሜሪካኖቹ ውጭ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችን ነው በአንድ ጊዜ ለማስተናገድ የሚችለው፡፡ ባለቤቶቹ ከአሜሪካ መንግስት ምን ያህል ገቢ ሊያገኙ እንደሚችሉ አስቤ ተደመምኩ፡፡ ባለቤቶቹ የሚታወቁ እነደሆን ጠየቅኩኝ፡፡ ሎጁን ያሠራው በአካባቢው ለብዙ ዐሥርት ዓመታት ነዋሪ የነበረ እያሱ የሚባል ሰው እንደሆነ ነገር ግን ከአሜሪካን ወታደሮች መምጣት ጋር ተያይዞ አንድ ሕዝብ በደንብ የሚያውቃቸው ‹እመቤት› ባለቤትነቱን እንደተጋሩ ጥርጣሬ እንዳለ ተነገረኝ፡፡

## *አክሱምን ላገኘው ነው...*

*ከቀኑ ዐሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ የመሥሪያ ቤቴ አርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ደርሼ በማግስቱ ለምጀምረው ሥራ የሚያስፈልጉኝን ወረቀቶች ወስጄ ወደ ማረፊያዬ አቀናሁኝ፡፡ በማግስቱ ለሥራዬ የማገኛቸውን ሰዎች ሥም ዝርዝር ሳገላብጥ አንድ ሥም ቀልቤን ሳበው - አክሱም ኦናሞ (የአባቱ ስም ለዚህ ጽሑፍ ሲባል የተቀየረ)፡፡ እስካገኘው ድረስ ጓጓሁ፡፡*

*በማግስቱ በጥዋት ወደ ሥራ አመራሁኝ፡፡ ከአርባ ምንጭ ሙቀት ጋር አድካሚ የሥራ ቀን ነበር፡፡ የሥራ ባልደረባዎቼ ግን ‹እንደውም በደህና ወቅት መጥተህ ነው፤ ትንሽ ገፋ አድርገህ ብትመጣ ኑሮ ምን ልትሆን ነበር? እያሉ ማበረታቻ መሰል ማስፈራሪያ በፈረቃ ሲለግሱኝ ዋሉ፡፡ ወደ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል አካባቢ ተራው ከአክሱም ጋር የምገናኝበት ሆነ፡፡*

*አክሱም ተወልዶ ያደገው ኮንሶ በምትገኘው ልዩ ስሟ ኮልሜ ተብላ በምትጠራ ስፍራ ነው፡፡ በጊዜው ግዳጅ ላይ የነበሩት አባቱ ከትግራይ ክፍለ ሀገር አክሱም አካባቢ ግዳጃቸውን ጨርሰው ሲመለሱ ተወልዶ የጠበቃቸውን ሦስተኛ ልጃቸውን አክሱም ብለው ስም እንዳወጡለት አጫወተኝ፡፡ ሐሳብ ገባኝ፡፡ ኮንሶ ተወልደው፣ አድገው፣ ወልደው ለብሔራዊ (የኢትዮጵያ) ግዳጅ ትግራይ ለሄዱት አቶ ኦናሞ አክሱም ልጃቸው ነው! ይህን ሳይሰሙ የሞቱት አንድ ሰው ትዝ አሉኝ፡፡ ስለ **አክሱም ሃውልት እና ስለ ወላይታ ሕዝብ** ምንድን ነበር አሉ የተባለው? ...*

*ዕለቱ በውጥረት ተጠናቀቀ፡፡ በማግስቱ ጠዋት በከተማው ወደሚገኝ አንድ ጥሩ ሆቴል ቁርስ ለመመገብ ጎራ አልኩኝ፡፡ ቁርስ አብራኝ ለመመገብ የቀረበችው እንስሳ ቀልቤን ገፈፈችው፡፡ ከዚያ ቀን በፊት እንደዚች ዓይነት እንስሳ አጋጥሞኝ አያውቅም ነበር፡፡ ስጋ በል ትሁን ዕፅዋት ተመጋቢ ግራ ገብቶኝ ነበር፡፡ በአቅራቢያዬ የነበሩት ሰዎች መረጋጋት ነበር ብዙም እንዳልደነገጥ የረዳኝ፡፡ እንስሳዋ ከሚዳቆ ጋር የምትቀራረብ ሲሆን ስስ ትባላለች፡፡*



*በአርባ ምንጭ የነበረኝ ቆይታ ሰዓታት ብቻ ቀርተውታል፡፡ የመጣሁበትን ሥራ በጊዜ አጠናቅቄ ዞር ዞር ማለት ፈለኩኝ፡፡ ወደ ቢሮ አቅንቼ ሥራዬን አጣድፌ ለመጨረስ ሞከርኩኝ፡፡ የመጨረሻዋን ፊርማ አኑሬ ሰዓቴን ተመለከትኩኝ፡፡ ምሳ በልቼ፣ አርባዎቹን ምንጮች አይቼ፣ አዞ እርባታ ደርሼ ትኬቱ ላይ በተመለከተው ጊዜ ለመልስ ጉዞዬ በረራ ለመድረስ ያለኝ ጊዜ አንድ ሰዓት ተኩል ነበር፡፡ የምሄድባቸውን ቦታዎች መቀነስ እንዳለብኝ ወስኜ ባልደረባዎቼን አማከርኩ፡፡ የአዞ እርባታው ከአየር ማረፊያው ብዙም ስለማይርቅ እሱን አይቼ ማለፍ እንደሚሻል የሰጡኝን ሀሳብ ተቀብዬ ከምሳ በኋላ ወደዛው አመራሁ፡፡*

*አዞ እርባታ በደቡብ ክልል መንግሥት የሚተዳደር ተቋም ሲሆን ዕድሜያቸው አምስት ዓመት የሞላቸው አዞዎችን ቆዳ ገፍፎ ከሀገር ውጪ እየላከ በመሸጥ አዞዎች ለሀገሪቷ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ እንዲሆኑ መስዕዋት ያደርጋቸዋል፡፡*



የአዞ እርባታ ጉብኝቴን ጨርሼ ወደ አርባ ምንጭ አየር ማረፊያ ሄድኩኝ። አየር ማረፊያው ስደርስ እንድደርስ ከተነገረኝ ሰዓት አንድ ሰዓት አርፍጄ ለረበራው አርባ አምስት ደቂቃ ሲቀረው ነበር። ወደ አውሮፕላኑ መሳፈር የሚያስችለኝን ወረቀት (boarding pass) ከተቀበልኩ በኋላ አንዱን ጥግ ይዤ የጀመርኩትን ተከታታይ ፊልም መኮምኮም ጀመርኩ። አውሮፕላኑ መጥቶ ለመሳፈር ስንነሳ የተከታታይ ፊልሙን ሁለት ክፍሎች (እያንዳንዳቸው አርባ ደቂቃ ይፈጃሉ) ጨርሼ ሦስተኛውን አጋምሼ ነበር። እንደአካሄዱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ ቁጥር 134/5 ከአዲስ አበባ ተነስቶ ጅማ ላይ ተሳፋሪዎች አውርዶ እና ከጅማ ወደ አዲስ አበባ የሚሄዱ ሰዎችን አሳፍሮ ነበር አርባ ምንጭ ከተፍ ያለው።

## የመለሰኝ ጢያራ

ወደ አውሮፕላኑ ስንገባ የሚገርም ሙቀት ተቀበለን። ‹‹ቤታችሁን ሞቅ ሞቅ አድርጋችሁ ነው የጠበቃችሁን›› ስትል አፌዘች ከጀርባዬ በመሳፈር ላይ የነበረች ተሳፋሪ በር ላይ ቆማ እንኳን ደህና መጣችሁ እያለች ለምትቀበለን የበረራ አስተናጋጅ። በመጀመርያ ያገኘሁትን ክፍት ወንበር ሰው እንደሌለበት አረጋግጬ ተቀመጥኩኝ።
መንቀሳቀስ ከመጀመራችን በፊት ከፊቴ የነበረው ወንበር ላይ የተቀመጠችው ፈረንጅ ሴት ወደኋላዋ ዞራ አጠገቤ የተቀመጠውን ፈረንጅ አንድ ያልተሰማኝን ጥያቄ ጠየቀችው። ሰውየው እጁን ወደወንበሩ ስር ከሰደደ በኋላ ‹‹No, but we are gone be fine, don't worry›› አላት። ደግማ ዞራ ‹‹But, we should complain to the company, or something…›› አለችው በአስቂኝ የጣልያንኛ ቅላፄ። ሰውየው ወደ ፊቱ አዘንብሎ ድንገት ያስቆጣኝን ንግግር ተናገረ ‹‹This is Ethiopia!›› ይህችን ይወዳልና! ምን ብላ ይሆን የጠየቀችው መጀመርያ? ምን ለማለት ፈልጎ ነው እሱስ? ኧረ ቆይ ልክህን ባልነግርህ ብዬ ወሬ ለመጀመር አጋጣሚ መፈለግ ጀመርኩኝ።
ሙቀቱ ከአቅሜ በላይ ስለሆነብኝ ማቀዝቀዣ ንፋስ ማስገቢያውን እስከመጨረሻው ከፈትኩት ምንም ተጨማሪ ቅዝቃዜ ሊሰማኝ አልቻለም።


ዞር አልኩና ጅማ ይሆን አርባ ምንጭ የተሳፈረው ጠየኩት።
‹‹አርባ ምንጭ›› አለኝ።

‹‹ማቀዝቀዣው ይሥራ አይሥራ እርግጠኛ አይደለህማ፣ ምናልባት የአውሮፕላኑ በሙሉ ኃይሉ መብረር ሲጀምር ይሰራ ይሆናል›› አልኩት።

‹‹ምናልባት›› ሲል መለሰ። ‹አለቅህም!› አልኩኝ በሆዴ።

‹‹ይቅርታ ይህንን በመጠየቄ፣ ምንድን ነበር ቅድም ሴትየዋ የጠየቀችህ?›› ከፊታችን ወዳለችው ሴትዮ እየጠቆምኩኝ።

‹‹አ፣ የጠየቀችኝ ወንበሩ ስር ውሀ ላይ ለመንሳፈፍ የሚረዳ ልብስ እንዳለ ነበር››፡፡ (እያንዳንዱ ወንበር ጀርባ የሕይወት አድን ልብስ ከወንበሩ ስር እንደሚገኝ የሚገልጽ ጽሑፍ አለ)




‹‹አንተ ደግሞ ‹ይሄ ኢትዮጵያ ነው› አልካት፤ ምን ለማመልከት ፈልገህ ነበር?›› ጥያቄዬን ቀጠልኩ ከለስላሳ ፈገግታ ጋር፡፡

‹‹ለማለት የፈለኩት እዚህ ሀገር ነገሮች የሚከሰቱት በዝግታ ነው፡፡ በጣም በዝግታ! አርባ ምንጭ የመጣሁት የቆላ ዝንብን ለማጥፋት የሚረዳ መድኃኒት ለመርጨት ነበር፡፡ አውሮፕላን ማረፊያው ላይ ቆመው ያየሀቸው አራት ትንንሽ አውሮፕላኖች ለዚሁ ሥራ የመጡ ናቸው፡፡ (አውሮፕላኖቹ ለአሜሪካን ወታደሮች የአደጋ ጊዜ ማምለጫ ነበር የመሰሉኝ) የጉምሩክ መሥሪያ ቤት የሚረጨውን መድኃኒት ወደ ሃገር ውስጥ ለማስገባት ከሁለት ሳምንት በላይ ስለፈጀበት አብረውኝ የመጡት 10 ባለሙያዎች ሆቴል ቁጭ ብለው እየተቀለቡ ነው፡፡ ከጤና ሚኒስትር መሥሪያ ቤት ወደ ኢትዮጵያ እንድንመጣ የሚጋብዝ ደብዳቤ ለመጻፍ 10 ቀን እንደፈጀባቸው ታምናለህ?... እዚህ ሀገር የሚማርክ የመሬት አቀማመጥ፣ እጅግ በጣም እንግዳ አክባሪ እና ተቀባይ ሕዝብ እንዲሁም በሕይወቴ ከቀመስኳቸው ቢራዎች በጣም ምርጥ ከሆኑት የምመድበው ቢራ (ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ) አለ፡፡ ነገር ግን ነገሮች የሚከናወኑበት ፍጥነት እልህ አስጨራሽ ነው፡፡››

የቅድሙ ወኔ የት እንደገባ ጠፋ፡፡ ‹‹በሕዝባችን እና በተፈጥሮ ውበታችን ያስደሰትንህን ያክል በሚቀጥለው ስትመጣ ምናልባት በቢሮክራሲያችን ፍጥነትም ተሻሽለን እናስደስትህ ይሆናል›› አልኩት፡፡

‹‹ያ እንደሚሆን በጣም እጠራጠራለሁ›› አለኝ፡፡ ተስፋ እንኳን እንዲኖረው ለማድረግ ለማግባባት የሚበቃ ወኔ ውስጤ አጣሁ፡፡

ጨዋታ ቀየርን፡፡ ስማችንን ተቀያየርን፡፡ ኤድዊን ይባላል፤ ደቡብ አፍሪካዊ ነው፡፡ ጥሩ ይቀልዳል፡፡ በተለምዶ የሀገር ውስጥ በረራዎች ላይ ሁለት የበረራ አስተናጋጆች እንደሚኖሩ ዛሬ በተለየ ሁኔታ አራት እንደሆኑ እና እርስ በእርስ በተደጋጋሚ እየተገጫጩ እንደሆነ ትዝብቴን አጫወትኩት፡፡ ‹‹አራቱም ቆንጆዎች ስለሆኑ ረብሻቸው ችግር የለውም (we don’t mind their stumbling in to each other)›› ሲል አሾፈ፡፡ በሚገርም ሁኔታ በዛ ሙቀት እንቅልፍ ወሰደው፡፡ በሙቀቱ መንገላታቱን ያስተዋለች አንዷ የበረራ አስተናጋጅ ‹‹የሚጨመር ነገር አለ?›› አለችኝ፡፡ ‹‹ውሃ›› አልኳት - እግዜር ይስጥሽ፡፡

ከሙቀቱ የተገላገልነው አዲስ አበባ አርፈን በሩ ሲከፈት ነበር፡፡ ‹‹Thank God›› አለ እድዊን - የአዲስ አበባን አየር ሲተነፍስ፡፡

በመውረድ ላይ ሳለን ከፊታችን ተቀምጣ የነበረችው ጣልያናዊ ሴት በሩ ላይ ቆማ የምታሰናብተው የበረራ አስተናጋጅን ‹ወንበሩ ላይ ከወንበሩ ስር የሕይወት አድን ልብስ እንዳለ ተጽፏል፤ ልብሱ ግን የለም› ስትል ጠየቀቻት፡፡ አስተናጋጇ ‹በረራው በውሀ ላይ ስላላለፈ...› ጠያቂዋ ሴት መልሷን አላስጨረሰቻትም፤ ጥላት ሄደች፡፡ ከአርባ ምንጭ አየር ማረፊያ ተነስተቶ አንድ ደቂቃ እንኳን ሳይበር ነው አውሮፕላኑ የአባያ ሀይቅን ሰንጥቆ የሚያልፈው፡፡

# ፎቶግራፍ የሌለው የጉዞ ማስታወሻ

የገና ማግስት በቅጡ ሳልዘጋጅ ከቤቴ በመውጣቴ ካሜራ እንደሚያስፈልገኝ የተረዳሁት 200 መቶ ኪሎ ሜትር ከተጓዝኩ በኋላ ነበር - አዋሽን ስንሻገር፡፡ ስለዚህ በዚህ የጉዞ ማስታወሻ ላይ ምስል ከሳች ትረካ እንጂ ምስል የለም፡፡ እየተጓዝኩ ያለሁት ወደአፋር ነው፤ ሰመራ፡፡ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ገደማ ከአዲስ አበባ ተነስተን፣ የመኪና ጉዞ ምቾትን ትርጉም በሚያሰጠው ላንድክሩዘር ጉዞ ጀመርን፡፡ አዳማ ላይ ቁርጥ እና ጥብስ ለመብላት ሲቆሙ እኔም በሳቅ እና በፈገግታ አጀብኳቸው፡፡

ከአዲስ አበባ በወጣሁ ቁጥር የሚገጥመኝ ችግር ምርጫዬ የሆነ ምግብ ነው፡፡ ሁሉም ሰው ጥብስ ወይም ቁርጥ መብላት እንደሚያምረው ቁርጤን ስላወቅኩ… እኔም ሽሮ፣ ፓስታ፣ አትክልት የመሳሰሉትን ለብቻዬ እፈልጋለሁ፡፡ አብረውኝ ከሚጓዙት አንዱ ‹‹ቬጅቴርያን ነህ ወይ?›› አለኝ፤ ‹‹አይደለሁም›› አልኩት እንጂ ምንም የምለይበት የለኝም፡፡ እርግጥ ነው ዱለት፣ ክትፎ፣ አሩስቶ ምናምን ከተገኘ አልምርም፡፡ የዛን ዕለት ጠዋት ግን ለነርሱ ከቀረበው ጥብስ ላይ ጥቂት ዛላዎች እያነሳሁ ነካከስኩ፡፡

አዋሽ አርባ የተባለችው ከተማ ከመግባታችን በፊት የአዋሽ ወንዝን ማቋረጥ ነበረብን፡፡ የአዋሽ ወንዝ ሞልቶ ድልድዩ አግድርም የተዘረጋ ታንኳ መስሏል፡፡ ስንመለስ ታንኳው (ድልድዩ) በከፊል ሰምጧል፡፡ ስንሄድ ከአዋሽ አርባ ከተማ ወደግራ ታጥፈን ወደሰመራ ከማምራታችን በፊት የድንገቴ ዕቅድ ለውጥ አደረግን፤ ሐረርን አይቻት የማላውቀው እኔ በመሆኔ ለምን በጨረፍታ አናሳየውም ተባባሉ፤ እርግጥ ነው እኔን ሰበብ አርገውኝ ነው እንጂ እነርሱም መሄድ የፈለጉበት ምክንያት አላቸው፡፡

## ሐረር - የታጠረች ከተማ?

በካፊያ ታጅበን ወደ12 ሰዓት ገደማ ሐረር ገባን፡፡ የ1000 ዓመቷን እመቤት ሐረር አንድ ቀን ለጉብኝት እንደምሄድባት አውቅ ነበር፤ ግን እንዲህ በድንገቴ ይሆናል ብዬ ስላላሰብኩ ድጋሚ መምጣት እንዳለብኝ እያሰላሰልኩ በወፍ በረር ጎበኘኋት፡፡ መቼም ጉብኝት ያውም በማታ፣ ያውም (በእግር መንሸራሸሩ ባይቀና እንኳ) የሕዝብ ትራንስፖርት ሳይጠቀሙ የጉብኝትን ጣዕም ያሳጣል - ስለዚህ አየኋት ለማለት በማያስችል ሁኔታ ቃኘኋት፡፡ ምናልባት በዚያ ፍጥነት ካየሁት የማስታውሰው የአዲስ አበባውን አጤ ምኒልክ ሐውልት መንትያ የሚመስለውን የራስ መኮንን ሐውልት እና ጀጎልን ነው፡፡ ያቺ ጨረፍታ ግን ሐረር - የታጠረች ከተማ ሲባል የነበረኝን ግንዛቤ ለመቀየር በቂ ነበረች፡፡ በዘመኗ ከተማ የነበረችው አሁን ከአንድ የሀብታም ግቢ የምትሰፋ አይደለችም፡፡

ዞሮ፣ ዞሮ በሩ (የሸዋ በር) ውበት እና ሞገሱ እንደጠበቅኩት ነው፡፡ ጊቢው ውስጥ የመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን እና የከተማዋ ሙዚዬም አጥር ላጥር ተዋደው ይታያሉ፡፡ ጅብ የመመገብ ትርኢት የሚታይበትን ቦታም በጣት ጥቆማ አመላክተው በጊዜ አሳብበው አስጎብኚዎቼ ሳያሳዩኝ መልሰውኛል፤ ለነገሩ ከጅብ ጋር ቁራጭ ስጋ ከመናጠቅ ተረፍኩ፡፡

ተመልሰን እራት ቁርጣቸውን ልንበላ ወደአንድ ሆቴል ሄድን፡፡ ሆቴሉ ሰፊ ጊቢ ሲሆን አንድ ትልቅ ክፍል ውስጥ በማይክሮፎን የተደራጀ ቢንጎ ጫወታ ያካሂዳል፡፡ ቢንጎ አጨዋወቱ እንዴት እንደሆነ የማውቀው ጉዳይ የለም፤ ነገር ግን ያ ሁሉ ሰው በዚያ ዓይነት ተመስጦ ሲጫወት ለማየት ጥቂት ተመሰጥኩ፡፡ ራት ተበላ፣ ታደረ፤ ከንጋቱ 11 ሰዓት ላይ የመልስ ጉዞ መገንጠያውን 300 ኪሎ ሜት አልፈነው ወደመጣነው ሰመራ ከተማ፡፡

## ጉዞ ወደ ሰመራ

የአፋር ክልል ሙሉ ለሙሉ በረሃ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም ለጥ እና ቀጥ ባለው መንገዱ ዳር እና ዳር አንዳንዴም ሰማይ እስከሚደፋበት ባለው ርቀት ሙሉ አገሩ ከሰው ቁመት በማይበልጥ፣ ባብዛኛው አረንጓዴ በሆነ ችፍርግ ቁጥቋጦ እና ጫማ ሊውጥ በሚችል ደርቆ (ይመስላል) ቢጫ በሆነ ሳር የተሸፈነ ነው፡፡ አረንጓዴው ቁጥቀጦ እስከገዋኔ ይቀጥላል፡፡ ከገዋኔ በኋላ ግን ቁጥቋጦው ቢኖርም አረንጓዴ ሳይሆን ቅጠሉ የረገፈ እና ግንዱ/ጭራሮውም የደረቀ ይመስላል፡፡

መንገዱ እጅግ በሚያሰለች ሁኔታ ቀጥ ያለ እና ረዥም በመሆኑ አያልቅም፡፡ መደመጨረሻ አካባቢ ላይ እንኳን እኛ ተጓዦቹ መንገዱ ራሱ የሰለቸው ይመስለኛል፡፡ የመቀሌ ጉዞ ማስታወሻዬ ላይ አገሪቱ በተራራ ከመዋጧ የተነሳ ወይ አትታረስ፣ ወይ ከተማ አትሆን ብዬ መማረሬ ትዝ አለኝ፡፡ እዚህ ደግሞ ያልታረሰ እና ምናልባትም ቢታረስበትም በሙቀቱ ምክንያት ፍሬ የማይሰጥ፣ ለከተማ ኑሮም የማይመች ለጥ ያለ ወፍ ዘራሽ የቁጥቋጦዎች ማሳ ይመስላል፡፡ እዚያም ሆነ እዚህ ጥቅም ላይ ያልዋሉ (ሊውሉ የሚችሉ የማይመስሉ) ምድሮችን ነው ያየሁት፤ ባገሬ ገረመኝ፡፡

የመኪናችን ማቀዝቀዣ ፀሐይ መውጣቷን እንጂ ከነልጆቿ መውጣቷን አስረስቶኝ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሾፌራችን ለሽንት ብሎ መኪናዋን ሲያቆማት በሩን ብርግድ አድርጌ ብቅ ስል እሳት ውስጥ ዘልዬ ብዬ የገባሁ ነው የመሰለኝ፡፡ ነፋስ ቢጤ አለ፤ ነፋሱ ግን የእሳት (የፀሐይ አይመስለኝም) ወላፈን አዝሏል፡፡ መሬቱ ክው ብሎ ደርቆ ውኃ የሚባል አይቶ እንደማያውቅ ያሳብቃል፡፡ ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም በሚል ተፈጥሮ የፈቀደችልኝን ያህል ከጓደኞቼ ጎን ተሰልፌ መሬቱን አጠጣሁት፤ ትንሽ እፎይ ያለ ይመስለኛል፡፡ ተንደርድሬ ወደመኪናው ውስጥ በመግባት ያንን የሚፋጅ ሙቀት መልሼ አመለጥኩት፡፡

በነገራችን ላይ በርቀት እና አልፎ፣ አልፎም በቅርብ ርቀት የሚታዩ ቀጫጭን *ቶርኔዶዎች* (የሚሾር ነፋስ) አሉ፡፡ እነዚህ ቶርኔዶዎች የመሬቱን አቧራ እየጠቀለሉ ወደላይ ሲያጎኑት በርቀት ተመልክቼ መጀመሪያ ላይ ደንግጬ ነበር፡፡ ይሄ እሳት የሆነ አገር እሳት መትፋት ቢጀምርስ - ‹‹እሳተ ገሞራ ነው እንዴ?›› አልኳቸው፤ ‹‹አይ አቧራ ነው›› ብለው ገላገሉኝ፡፡ ስንመለስ ደግሞ ስንሄድ ያላየናቸውን ዝንጀሮዎች፣ ሚዳቆዎች እና ሰስ አየን፡፡ ለካስ እነርሱም ያንን በርሃ ይዳፈሩታል ያሰኛል፡፡

ሌላው አስገራሚ ገጠመኝ ሰመራ እስከምንደርስ ድረስ የተንቀሳቃሽ ስልካችን ከኔትወርክ ያለመውጣቱ ምስጢር ነው፡፡ ምንም የቴሌ ሞገድ መቀበያ በሌለበት ጭው ባለ በረሃ ውስጥ የአካባቢው ለጥታ ይሁን ሌላ አልገባኝም፤ ኔትዎርክ ግን በሽ ነው፡፡

## የውኃ ምጽዋት

በጉዟችን መሐል አንዳንድ የአገሬው ነዋሪዎች ባዶ የውኃ ላስቲክ ከረጢት እየወዘወዙ ያሳዩናል (በነገራችን ላይ እነዚህ ነዋሪዎች ጠቅልለው የሚይዟትን የኬሻ ክብ ጎጇቸውን ተክለው እና በፍየሎቻቸው/ግመሎቻቸው ተከበው አልፎ አልፎ ከመታየታቸው በቀር በአራት መቶ ኪሎ ሜትር ውስጥ የረባ የገጠርም ሆነ የከተማ መንደር የለም ማለት ይቻላል፡፡) እናም እነዚህ የውኃ ላስቲክ የሚወዘውዙት ለምን እንደሆነ ስጠይቅ ውኃ እየለመኑ እንደሆነ ተነገረኝ፡፡ አንዳንዶቹ በጎናቸው በጨርቅ የተጠቀለለች ኮዳ ይዘዋል፤ በኮዳዋ የግመል ወተት እንደሚይዙባት ገመትኩ፡፡ አካባቢው ምንም ውኃ ስለሌለው ወተታቸውን ሲጨርሱ በየመንገዱ ዳር ውኃ እየለመኑ ከመጠጣት በቀር ምንም አማራጭ የላቸውም፡፡ የሚያሳዝነው ግን አብዛኛው መኪና (በመንገዱ የሚበዙት ወደወደብ የሚሄዱና የሚመጡ የጭነት መኪኖች ናቸው) ምንም ሳይሰጣቸው ያልፋል፡፡ የሚያልፈውን መኪና ሁሉ ይለምናሉ፤ እንደእኛ ዓይነቱን (የጭነት ያልሆነ) መኪና ደግሞ አብልጠው ይለምኑታል፡፡ ያለንን ውኃ ከሰጠን በኋላ ግን ቀሪዎቹን ከንፈር በመምጠት በዓይናችን ከመሸኘት በላይ አማራጭ አልነበረንም፡፡ ይህንን ቢመለከቱ ኖሮ፣ ፀጋዬ ገብረመድኅን ‹‹ረሃብ ስንት ቀን ይፈጃል?›› የሚለውን ግጥማቸውን ‹‹ውኃ ጥም ስንት ቀን ይፈጃል?›› ብለው እንደገና ይጽፉት ነበር፡፡

በየመንገዱ ዳር እና ዳር ላይ ብዙ የተበጣጠሱ የመኪና ጎማዎች አየሁ፡፡ ግራ ገብቶ ብጠይቅ የፈነዱ የመኪና ጎማዎች እንደሆኑ ተነገረኝ፡፡ ጎማዎቹ የአስፋልቱ እሳት ስለሚለበልባቸው እና ከላይም ጭነቱ ስለሚከብዳቸው ድንገት ይፈነዳሉ፡፡ ለዛም ይመስላል፤ አንዳንድ የአፋር ጊቢ አጥሮች ግማሽ ጎናቸው በተቀበረ ጎማዎች የታጠሩት፡፡ እኔ የመኪናዎች ጎማ መፈንዳት ታሪክን ከሰማሁ በኋላ መረጋጋት አቃተኝ፡፡ ምናልባት የኛ መኪና ጎማ ቢፈነዳስ? (መኪናችን እየበረረች የነበረው በ120 ኪሜ. በሰዓት ፍጥነት ነበር፡፡) ምናልባት አንዱ ኮንቴነር የጫነ ተሳቢ መኪና ጎማ ፈንድቶ ላያችን ላይ ቢወጣስ?... ሁለቱም አልተከሰተም፡፡

ገዋኔ ከተማን ካለፍን በኋላ አሰልቺው ቀጥ ያለ ጉዞ በመጠነኛ አቀበት ላይ የዚግዛግ ጉዞ ጀመረ፡፡ አካባቢው ሆነ ተብሎ የተኮለኮሉ በሚመስሉ ትላልቅ ተፈረካካሽ ዓለቶች (sedimentary rocks) አስገራሚ ውበት የተሰደረ ነው፡፡ ከወዲያ ማዶ የተንጣለለ ውኃ (ሐይቅ መሳይ ታይቶኝ) ተገርሜ ጠየቅኩ፡፡ ለካስ አሸዋ ውስጥ ሰምጦ የሚቀረው አዋሽ ወንዝ ተቀልቦ ግድብ እየተሰራበት ኖሯል?! ግድቡ የሚሰራው ለተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ እንደሆነም ተነገረኝ፡፡

ያ ግድብ ያቋተው ውኃ ሊዋኙበት ቢሞክሩ እንደፍልውኃ እንደሚፋጅ መገመቴ አልቀረም፡፡ በነገራችን ላይ የአዋሽ ወንዝም ቢሆን አሸዋ ውስጥ ገብቶ ከስሞ የሚቀረው እዚያ ውኃ የጠማው መሬት ውስጥ መሆኑን ስረዳ ከባድ ሳይንስ እንዳልሆነም ጭምር ነው የተረዳሁት፡፡ በዚያ ዓይነት ሙቀት እንኳን መሬቱ እኔም ራሴ አዋሽን ጠጥቶ ለመጨረስ የሚያስችል አቅም የሚያጥረኝ አልመሰለኝም፡፡

## ሎጊያ እና ሰመራ

ሎጊያ ከሰመራ 7 ኪሎሜትር ወዲህ የምትገኝ ትንሽዬ ነገር ግን ከሰመራ የተሻለ ሰው፣ ሰው የምትሸት ከተማ ነች፡፡ ከተማዋ ከአንዲት ባለአንዲት ፎቅ ትንሽዬ ቤት በቀር ጎልቶ የሚታይ እንኳን ቤት የላትም ነገር ግን ሰመራ የመንግሥት ሥራ የሚሠሩት ሳይቀሩ የሚኖሩት ሎጊያ ውስጥ ነው፡፡ በሎጊያ መንገድ ዳርና ዳር ላይ የተደረደሩት መኪናዎች ብዛት ከከተማዋ መኖሪያዎች ብዛት ይበልጣል፡፡ በሰመራ ግን ጥቂት መኪኖች በየመንግሥት መሥሪያ ቤቶቹ ውስጥ ከመኖራቸው በቀር ጭርታ ያጠቃታል፡፡ በሰመራ ብዙ የመንግሥት ሕንፃዎች እና ጥቂት የቁጠባ መኖሪያ ቤቶች ከመኖራቸው በቀር የሥራ ብቻ ከተማ በመሆን ተወስናለች፡፡

እኛም ሎጊያ የደረስነው በስምንት ሰዓት በመሆኑ ለምሳ አረፍን፡፡ ምግብ ልንበላበት የገባንበት ቤት ግድግዳው ወደጣሪያ አካባቢ ክፍተት አለው፤ በዚያ ላይ ከቆርቆሮው ጣሪያ ስር ሳጣራ ተነጥፏል፡፡ ይሄ ሁሉ ሆኖም ግን ሙቀቱን መቀነስ ስለማይቻለው በግምት 7ሜትር በ10 ሜትር በሚሆነው በዚያ ክፍል ውስጥ ብቻ አምስት ‹ቬንትሌተሮች› ተሰቅለዋል፡፡ ቀና ብዬ ሳየው ቤቷ ድንገት ተነስታ እንደሄሊኮፕተር የምትበር፣ የምትበር መሰለኝ፡፡

የደረስንበት ወቅት አካባቢው ቀዝቀዝ የሚልበት እንደሆነ ቢነግሩንም የውጪውም ሆነ የቤቱ ውስጥ የእሳት ወላፈን ያህል የሚፋጅ ነው፡፡ አንድ የአገሬው ሰው ‹‹የአፋርን ሙቀት ቤት ውስጥ በመግባት ማምለጥ አይቻልም›› ብሎ እንቅጩን ነገረን፡፡ ለአዳር የተከራየነው አልቤርጎ ውስጥ በአጎበር ቦታ ቬንትሌተር ተገጥሞለታል፡፡ ቬንትሌተሩ ሰው ውስጥ ባለበት ሰዓት ሁሉ መሾር አለበት… እንዲያው ለብ ለማድረግ ያህል፡፡ የተከራየነው ክፍል ጣሪያ (ሰገነት) ላይ የክፍት አየር አልጋዎች ተደርደረዋል፡፡ ከጥቂት ወራት በኋላ (በተለይ ግንቦት፣ ሰኔ እና ሐምሌ ላይ) ቤት ውስጥ ማደር እንደማይቻል እና አልቤርጎ የሚከራይ ሰው ሰገነት ላይ የተነጠፉ አልጋዎች ላይ ከላይ እንደሚጋደም ተነገረን፡፡

ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ ቀዝቀዛ ሻወሬን ወስጄ ሳበቃ ያለወትሮዬ በቲሸርት ዘንጬ ለእራት ወጣሁ፡፡ የምሽቱ ሙቀት የኔን የቀጭኑን ብላቴና ወዝ ለማፍለቅለቅ ሰከንድ አልፈጀበትም፡፡

## ‹‹ብር ያለው በርሃ ነው››

ለአገሩ የሚስማማ ሸበጥ ቢጤ መግዛት ፈልጌ ነበርና ሳጠያይቅ ዋጋቸው ውድ እንደሆነ ተረዳሁ፡፡ ‹‹እንዴ ምንድን ነው ነገሩ? ይሄንን ጫማ እኮ ሐረር 200 ብር ተብዬ እምቢ ብያለሁ›› አልኳቸው፡፡ ‹‹ታዲያ ሐረር እዚህ የለ!›› አለኝ አንዱ፤ አብራው የነበረችው ቆንጆዬ ኮረዳ ደግሞ ‹‹ሐረር ምን ገንዘብ አለ፤ ገንዘብ እኮ ያለው በርሃ ነው›› ብላ ውድ መሆኑ ብር ያለበት አገር ከመሆኑ እንደሚያያዝ አረዳችኝ፡፡ ልጅቷ እውነቷን ነበር፤ ኑሮ በአፋር ውድ ነው፡፡ እዚህ ግባ የማይባል ቤት ውስጥ ጥብስ ከ50 ብር በታች፣ ሽሮ ደግሞ ከ30 ብር በታች አታገኙም፡፡ ሰመራ ውስጥ ጥሩ የሚባለው ነገር ግን በአዲስ አበባ ዞር ተብሎ ላይታይ የሚችለው የኤርታሌ ሆቴል አልጋ ድፍን አንድ ሺሕ ብር ያስከፍላችኋል፡፡

የሄድንበትን ጉዳይ ጨርሰን ስንመለስ ያንን አሰልቺ ጉዞ የምናለዝብበት ቴክኒክ እያሰብን ነበር፡፡ ጉዟችንን የጀመርነው ዘጠኝ ሰዓት በመሆኑ በርከት ያለ እሸግ ውኃ ገዝተን መንገድ ላይ ለሚጠይቁን ሰዎችም ለማቀበል ይዘናል፡፡ ለነገሮችም፣ ለእርስ በእርሳችንም ስለተለማመድን ጨዋታችን ደመቅ ብሎ ነበር፡፡ በመንገዳችን መሐል የፌዴራል ፖሊሶች በግምት በየሁለት መቶ ሜትር ርቀት ላይ ጥንድ፣ ጥንድ እየሆኑ ቆመው አየን፡፡ በነገራችን ላይ እዚህ አካባቢ የሾፌራችንን የትውልድ ሐረግ መጥቀስ አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡ ሾፌራችን (ስሙ ለዚህ ጽሑፍ ሲባል የተሸሸገ ቢሆንም) የቅድም አያቱ ስም ግን ይገለጻል - አቶ አስረስ ይባላሉ፡፡ አቶ አስረስ የመለስ ዜናዊ አስረስ አያት ናቸው፡፡ ሾፌራችን የ25 ዓመት የሹፍርና ልምድ አለው፤ ከመለስ ጋርም ከዝምድናው በተጨማሪ ጥቂት አብረው ተምረዋል፡፡ ሹፌሩ ለመለስ ያለው አድናቆት ከዝምድና ብቻ የመነጨ አይመስልም፡፡ በንግግሩ ቁጥብ ቢሆንም መለስ የአገሪቱን የ40 ዓመት ዕቅድ እንዳቀደላት እና ከዚህ በኋላ መሥራት እንጂ ምንልሥራ ብሎ መጨነቅ እንደማያስፈልግም ነግሮኛል፡፡

በመንገዳችን ላይ የገጠሙንን ፌዴራል ፖሊሶቹን እያየን ሳለን ሁለት ፌዴራል ፖለሲሶች እንድናሳፍራቸው ለመኑን፡፡ ከዚያ በፊት ለአሳፍሩኝ ልመና ብዙም የማይግደረደረው ሾፌራችን በፍጥነት መኪናውን አቆመ እና ተጫኑ:: ዕድሜያቸው ከ25 የማይበልጥ ወንድና ሴት ወታደሮች ናቸው፡፡ እሱ የመጣው ከተንቤን እሷ ደግሞ ከማይጨው እንደመጡ ነገሩን፡፡ ደሞዛቸው ከአንድ ሺሕ ብር እንደማይበልጥ ነገር ግን ምግብ ካምፕ ውስጥ እንደሚዘጋጅላቸው ነገሩን፡፡ እዚያ የመጡት ኢሳዎች እና አፋሮች ከመንገድ ወዲህ ያለው ጎሳ ፍየል፣ ከመንገድ ወዲያ ያለውን ጎሳ ሳር በመንጣ (ወይም ከዚያ ባልበለጠ ምክንያት) ለሊት ሲታኮሱ ስለሚያድሩ እነርሱን ለመጠበቅ ነው አሉ፡፡ ነገር ግን የዛን ዕለት ወታደሮቹ የበዙት በሌላ ምክንያት መሆኑን ነገሩን፡፡

አንድ ሾፌር ከሌሊቱ አምስት ሰዓት ላይ ሲነዳ በማይታወቁ ሰዎች ታግቶ ነበር፡፡ (ለወትሮው መንገዱ የ24 ሰዓት አገልግሎት ይሰጣል፡፡) ወታደሮቹ እንደነገሩን አጋቾቹ ለሚስቱ ደውለው እንዲያናግራት አድርገዋል፡፡ እዚህ ነን እያሉ… ያሉበት ቦታ ሲኬድ አይገኙም፡፡

‹‹ገንዘብ ፈልገው ነው?›› አልናቸው፤

‹‹ኧረ የምን ገንዘብ፤ ነገር ፍለጋ ነው እንጂ›› አለ፡፡ ‹

‹‹ማንን ነው ነገር የሚፈልጉት?›› አልናቸው፡፡

‹‹እኛን ነዋ…!›› አለ፡፡

‹‹ለምን?››

‹‹አሸባሪዎች ናቸው›› አለ፡፡ ሁላችንም ደነገጥን፡፡

እኔ በበኩሌ መንገድ ላይ መታገት አለ የሚባለው ሐሳብ ሲከሰትብኝ ፌዴራል ፖሊሶች አጠገቤ ሲኖሩ ተሰምቶኝ የማያውቅ የደኅንነት ስሜት ተሰማኝ፡፡ ምነው ባልወረዱ የሚል ስሜትም አደረብኝ፡፡ ሹፌራችን ጥያቄውን ቀጠለ

‹‹ባለሥልጣን ነው

‹‹አይደለም፤››

‹‹ትግሬ ነው?››

‹‹አይደለም፡፡››

‹‹ታዲያ ምን አድርገን ብለው ነው?›› አለን፡፡ ሹፌራችን ትግሬ ነው ወይ ያለበትን ምክንያት አብራራልን፤ አሸባሪዎቹ ትግሬ ሲባል ኢሕአዴግ ይመስላቸዋል በማለት፡፡ ሹፌሩ ቀልድ አዋቂ ነው፤ አሁን ‹‹መለስ ስለሞተ›› ማገት ያለባቸው ‹‹የደቡብ ሰው ነው›› በማለት ሁላችንንም ፈገግ አሰኘን፡፡

እንዲህ እንዲህ እያልን፣ አዋሽ አርባ ከመሸ ደረስን፣ እዚያው አደርን፣ በማግስቱ እኩለ ቀን ላይ አዲስአበባ ደርሰን ተበተንን፡፡ በመጨረሻ ግን ያየሁት ነገር የሰጠኝ ግንዛቤ አፋር ክልል፣ በታዳጊ አገር ውስጥ ያለች ታዳጊ ክልል መሆኗን ነው - ለነገሩ መንግሥትም ታዳጊ ካላቸው ሦስት ክልሎች አንዷ አድርጓት የለ!?

## መጽሐፍ፤ ከወዴት አለህ?

ባለፈው ሳምንት ፅሁፋችን አንባቢ ኢትዮጵያዊን ፍለጋ በሚል ርዕስ፤ ያለውን የንባብ ባህል ከመጽሃፍ ገበያው ጋር እንዲሁም ለምን ይህ ሆነ ብለን ጠይቀናል፡፡ በዛሬው ፅሁፋችን ደግሞ ምን ይፃፋል? እንዴትስ ይፃፋል? ለማን ይፃፋል? ብለን እንጠይቃለን፡፡

አንድ ፀሃፊ መፅሃፍ ሲፅፍ ብዙ አይነት አላማዎችን ይዞ ሊነሳ ይችላል፡፡ ሀሳብን ከማስተላለፍ እራስን እስከማሻሻል ድረስ፡፡ ከዓላማ ሁሉ ገዝፎ የሚታየውና የመፅሃፉን ዋጋ ከፍ የሚያደርገው ደግሞ መፅሃፉ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሳደረው ተፅዕኖ እና የሃሳብ አመንጭነቱ ነው፡፡ አንባቢውም መፅሃፉን ገዝቶ ሲያነብ አንድ ነገር መጠበቁ አይቀርም፡፡  እናም የደራሲው ዋና ሚና የሚጠበቀውን ተፅእኖ በተደራጀ እና በሚዋጥ መልኩ ለሚጠብቀው አንባቢ ማድረስ ነው፡፡

በሀገራችን አሁኑ ወቅት በተለይም በአማርኛ ቋንቋ ለአንባቢው እየቀረቡ ያሉ ፅሁፎች ከዚህ አንፃር እንዴት ይገመገማሉ ነው የፅሁፋችን ዋነኛ አላማ፡፡ ምንስ ችግሮች አሉም እንላለን፡፡ በዚህ ፅሁፍ ለማየት የሞከርኩት ሁሉም አይነት መፅሃፍት ውስጥ ለኔ ገዝፈው የታዩኝን ጉዳዮች ነው፡፡

### The Zeitgeist is 'Self-help'

በሀገራችን ዋና ዋና ከተሞች እግረኛ መንገድ እንዲሁም ብርቅ የሆኑትን የመፅሃፍት መደብሮች ተዘዋውሮ የተመለከተ ሰው፤ በአንድ ነገር ቀልቡ መሳቡ አያጠራጥርም፤ 'የራስ አገዝ' (Self-help) ወይም በተለምዶ 'የስነ ልቦና' መፅሃፍት የሚባሉት መፅሃፍት በገበያው ውስጥ ባላቸው ድርሻ፡፡ አዎ ገበያው 'ምክር፣ ምክር' ይሸታል፡፡

'ሀብታም የመሆኛ ሚስጥሮችን' ከSecrets Stock Market እስከ Save, Run & Invest ፣ 'ስኬታማነትን በአጭር ጊዜ ለመቀዳጀት' ይረዱ ዘንድ ከleadership እስከ Entrepreneurship፣ 'የወሲብ የፀደይ ወራትን' ይኖሩበት ዘንድ ከHow to Kiss a Breast እስከ Kamasutra ወ.ዘ.ተ በምክር መልኩ ተዘጋጅተው የመፅሃፉን ዓለም በአምባገነንነት ይዘውታል፡፡ ጥያቄው ግን እነዚህ አብዛኞቹ የትርጉም ስራዎች የሆኑ ራስ አገዝ መፅሃፍት አንደሚታሰበው የዜጎችን ንቃተ ህሊና ከፍ በማድረግ የግራ መጋባቱ መፍትሄ ይሆናሉ? እነዚህ ሲያሻቸው ከምዕራብ አለያም ከምስራቅ ፍልስፍና በትንሹ እየጨለፉ ስለማንኖርበት ህይወት የሚያስጎበኙን መፅሃፍት እውነተኛ ዋጋቸው ስንት ነው?

ይህ ከ1980ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ እያደገ የመጣው የራስ አገዝ መፅሃፍት የገበያ አምባገነንነት ጫፍ (Apex) ላይ ደርሷል ማለት የሚያስችለን አሁን ያለንበት ወቅት ነው፡፡ 'የራስ አገዝ' መፅሃፍትን በሽሚያ ተሽጠው ማለቅ ስንመለከት፣ ጊዜው የነሱ ነው እንድንል ያደርገናል እናም የአምባገነንነታቸው መጨረሻ በቅርብ አልመስለን ይላል፡፡

### የነጭ ሳሩ አንበሳ መሃል ፒያሳ ኬክ ቤት ውስጥ ምን ያደርጋል?

ደራሲ እና ሀያሲ መስፍን ኃ/ማርያም የአንዳንድ ድርሰቶች አኳኋን አላምር ሲለው ‹‹አንዳንዱ ደራሲ በጣም ያስገርማል፤ ድርሰቱን አስከተወሰነ ቦታ ይወስደው እና መቋጫ ታሪክ ሲጠፋበት ዋናው ገፀ ባህሪ 'መሃል ፒያሳ ኬክ እየበላ እያለ፤ ከነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ አምልጦ የመጣ አንበሳ ገደለው' በማለት ታሪኩን ይቋጨዋል፡፡›› ይለናል፡፡ እንግዲህ የስነፅሁፋችን ሌላው አዝማሚ አይረቤ ታሪክን በደረቀ ቋንቋ አጅሎ ‹‹ይህ እንደ ልቤ የማየውና ለ12 ዓመታት አምጬ የወለድኩት የበኩር ልጄ ነው፡፡ እነሆ ተቋደሱልኝ›› መባላችን ነው፡፡

በሀገራችን የተደራጀ የስነፅሁፍ ገምጋሚ አካል ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ 'የደራሲያን' መበራከት ለግልብ መፅሃፍት መንስኤ ተደርጎ መወሰድ ይችላል፡፡

ከሳቴ ብርሃን የአማርኛ መዝገበ ቃላት 'ድርሰት' የሚለውን ሀሳብ፡ ሐዲስ ጥበብን ፤ፍልስፍናን [...] በጽሕፈት መግለጥ በማለት ድርሰት የጥበብ ሽግግር እንደሆነ ይገልፃል፡፡ አያይዞም  'ደራሲ' የሚባለው ማነው; ለሚለው ጥያቄ መልስ ሲሰጥ ደራሲ ማለት፡ ጥበብን፣ ትምህርትን[ና] የዕውቀት መጻሕፍትን የሚደርስ ነው ይለናል፡፡ እንግዲህ አሁን ገበያውን 'ከራስ አገዝ' መፅሃፍት ጎን ለጎን እየገነኑበት ያሉት 'ድርሰቶችስ' የዕውቀት ሽግግር ላይ እንዴት ናቸው? ቋንቋን ለማሳደግስ ምን አስተዋፅኦ እያደረጉ ነው? ተነበው በልብ ይቀራሉ ወይስ ያቅራሉ?

የነዚህ መፅሃፍት 'ደራሲዎችስ' እንደ ማእረግ ስያሜያቸው ጥበብን ያውጃሉ? ትምህርት እና ዕውቀትንስ ይሰብካሉን? አንባቢያቸውን ያዝናናሉ ወይስ ያሳዝናሉ? የዚህን ሁሉ ጥያቄ መልስ የአብዛኛውን መፅሃፍት ግማሽ ገፅ እንኳን ሳናገባድድ የምናገኘው ነው፡፡ ታዲያ ዘመኑን ማን እየደረሰው ነው? ብለን ስንጠይቅ ግን ድንጋጤ ሽው ይልብናል፡፡ ታዲያ ይሄን ሁሉ ዘመን ሽዋን የማያውቅ አንበሳ በጠራራ ፀሃይ ማሃል ፒያሳ ሲንጎማለል ሳንደነግጥ ኑሯል?

## Blurb እንደ ውዳሴ ከንቱ

መፅሃፍት ወደ ገበያው ከመውጣታቸው በፊት ለቅድሚያ ግምገማ ለአንዳንድ ሰዎች ሰጥቶ እርማት ማግኘት ትልቅ ብልህነት ነው፡፡ ነገር ግን የግምገማው አላማ ገበያ ተኮር ሲሆን ነገሩ ወደሌላ አቅጣጫ ይመራናል፡፡ ይህ እንግዲህ በብዙ መፅሃፍት ላይ የሚታይ 'አዲስ' ሂደት ነው፡፡ ለብ ለብ የሆነች፣ መናኛ የግጥም መድብል ያሳተመ አንድ ጎረምሳ ከመፅሃፉ ጀርባ አንድ ታዋቂ 'የስነ ፅሁፍ' ሰው ‹‹ሓይን ያውጣህ አንተ ልጅ፡፡ የቃላት አመራረጥህ የFrost ተፅእኖ እንዳለብህ ያሳያል፣ ከፑሽኪንም ጋር መንትያነትክን መመስከር ሳይኖርብኝ አይቀርም፡፡ ምን አለፋችሁ አሁን የማስተዋውቃችሁ የሸክስፒርን እኩያ ነው፡፡›› ብለው አስተያየት ሰጥተው አንባቢው ተሸምቶ ይገዛና፤ እንዴት ነው ነገሩ? ብሎ ይጠይቃል፡፡

ስለቁንጅና ውድድር ማሰልጠኛ ይሆን ዘንድ አንዲት 30 ገፅ የማትሞላ ፅሁፍ ከጀርባዋ ‹‹እንደ ሀሳቡ ጥልቅ ቋንቋ፣ እንደ ውበት ሰባኪነቷ ባህልን አክባሪነቷ ያስደምማል፡፡ በሌላ ዳጎስ ያለ ስራሽ ለማየት ቸኩያለሁ›› የሚል የአንድ ጉምቱ 'ምሁር' አስተያየት አይታችሁ መፅሃፉን ስታዩት በሆሊውድ ተዋንያን ምስል የተሞላ አልበም ሲሆንባችሁ፤ ምንድነው ከማለት ሌላ ምን ትላላችሁ?

እናም እጠይቃለሁ በመፅሃፍ ላይ የሚሰጥ አስተያየት (Blurb) ለማን ነው? ምንድን ነው? ውዳሴ ከንቱውስ የት ያደርሰን ይሆን?

## ‹‹ዘመን አይሽሬ (Classic) መጽሐፍ ቁጠር ብለው፣ ዴርቶጋዳ አንድ አለ››

በሃገራችን የስነፅሁፍ ታሪክ አጭር ነው ማለት ሁላችንም የሚያስማማ ሀሳብ ነው፡፡ ስነ ፅሁፉ አድጓል ወይስ አላደገም የሚለው ጥያቄ ግን እንደ ቀዳሚው ቀላል ካለመሆኑም በተጨማሪ አከራካሪም ነው፡፡ ከ1950ዎቹ መገባደጃ እስከ 1970ዎቹ መጀመሪያ ያሉትን 15 ዓመታት የኢትዮጵያ የአማርኛ ስነ ፅሁፍ የፍካት ጊዜ ነበር የሚለው በብዙሃኑ ተሰሚነት አለው፡፡ በዚህ ወቅት ነበር እነፍቅር እስከ መቃብር፣ ሌቱም አይነጋልኝ፣ አደፍርስ፣ ከአድማስ ባሻገር፣ አልወለድም የመሳሰሉት ብሉይ (Classic) የአማርኛ ድርሰቶች የታተሙት፡፡ እስከ አሁንም የአማርኛ ድርሰት መለኪያ ሆነው ይቀርባሉ፡፡

እንግዲህ ከዚህ የፍካት ዘመን ወደፊት 40 ዓመታትን ስንቆጥር አሁን ያለንበት ወቅት ላይ እንደርሳለን፡፡ እናም ዛሬስ ምን ይፃፋል? ብለን ለመተየቅ እንወዳለን? አዎ 'ዴርቶጋዳ' ተፅፏል፡፡ ግን ግን ልካችን ዴርቶጋዳ ነውን? ዴርቶጋዳን ለማጠልሸት ሳይሆን፤ በእውነት ስነፅሁፋችን ለመታዘብ ያክል ነው ይሄን ያልኩት፡፡ ዴርቶጋዳ የዘመኑ ብሉይ (Classic ) ስራ ነው ካልን የነ 'አደፍርስ' ምትኮች ከወዴት አሉ? ስለ ምንኖረው ህይወት የሚፅፍልን ደራሲስ ከወዴት ነው?

# “የቃሊቲው መንግሥት” እኔ እንዳነበብኩት

ባህር ማዶ ካለች አንዲት ወዳጄ ጋር ስለአንዳንድ ጉዳዮች (ስለሀገር ፣ ስለቤተክርስቲያን ፣ ስለወገን ወዘተ…) በምናወራበት የአዘቦት ወጋችን መሐል የፓስታ ሳጥን ቁጥሬን እንድነገራት ጠየቀችኝ፡፡ በሆዴ ‘ለዲያስፖራዎች የወገብ እና የጫማ ቁጥርን መስጠት ፋሽን ካለፈበት ሰንብቷል፤ ለምን ጠየቀችኝ? ያውም ጾስጣዬን ሆሆ!!’ እያልኩኝ አቀበልኳት፡፡ ከቀናት በኃላ ሳጥኔን ከፍቼ አዲስ የመጣ ነገር እንዳለ እንዳረጋግጥ ነገረችኝ፡፡ በፖስታዬ ምንም ነገር አለማግኘቴን ነግሬያት ጉዳዩን በዚሁ ልቋጨው ስንደረደር የኖረችበት የዲያስፖራ ዴሞክራሲያዊ ባህል ፣ መብትን የመጠየቅ ልማድ ግድ ብሏት በዚያው ካለው ከአገልግሎት ሰጪ ተቋም የመልዕክቱን ልዩ ቁጥር (tracking number) ጠይቃ ሰጠችኝና በአንድ የፖስታ ቤቱ ሰራተኛ ርዳታ ዳጎስ ያለው መጽሐፍ በእጄ ገባ፡፡ እኔም በከፊል ለኪሴ ሳስቼ በከፊል ደግሞ ለሙስናው መስፋፋት የግሌን አስተዋጽኦ ላለማበርከት ብዬ እርዳታ የለገሱኝን ሰው በእግዚአብሔር ይስጥልኝ ተሰናብቼ ከታላቅ የንባብ ዐራራ ጋር ወደጎጆዬ አመራሁ፡፡

**ርዕስ - የቃሊቲው መንግስት**

**ዝግጅት ፣ጥንቅር ፣ ጸሐፊ - ሲሳይ አጌና**

**የገጽ ብዛት** - 443

**አሳታሚ** - Netsanet publishing and distributing agency

**ዋጋውና እና የት እንደታተመ አይገልጽም**

ከምርጫ 97 በኃላ የቅንጅት መሪዎች ፣ ጋዜጠኞች ፣ የማኅበረሰባዊ እና ሙያዊ ማኅበራት ሰራተኞች እንዲሁም ከአርባ ሺህ በላይ ዜጎች በጅምላ መታሰራቸው ይታወቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያን የሚጎበኙ የውጭ መንግስታት እና አለምአቀፍ ተቋማት ተወካዮች አራት ኪሎ ከደረሱ በኃላ ወደቃሊቲ መውረድን አስለመዱ፡፡ በዚህም ምክንያት በሸገር ሁለት መንግስታት እንዳሉ ይተረት ጀመር፤ የአቶ መለስ ዜናዊው ‘የአራት ኪሎው መንግስት’ እና በቅንጅት መሪዎች በቡድን የሚመራው ‘የቃሊቲው መንግስት’፡፡ወደኃላ እንደምናነሳው የመጽሐፉ ይዘት ስለዚህ ቃሊቲ ስለወረደው መንግስት ስለሚያትት ጸሐፊው ጥሩ ርዕስን መርጧል፡፡የሽፋን ስዕሉ ደግሞ የቤተ መንግስቱን የቃሊቲ ወህኒ ቤት አጥርና ሚያዝያ 30 1997 ዓ.ም. መስቀል አዳባባይን ያጥለቀለቀው ፣ ከሰው መሀል መርጦ ያነገሳቸውን ህዝብ ማስፈሩ ደግሞ እጅግ ገላጭ ሆኖ አግኝቼዋለው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት መንግስት እሰረኞቹን መያዝ ከተጀመረበት ከጥቅምት 22 1998 ዓ.ም. ጀምሮ የመሰረተ ዐሳቡ ክቡድነት ያህል ለሀገሪቱ መጻዒ ጊዜ አንዳች ነገር ባላበረከተ ይቅርታ ከእስር እስከተፈቱበት ሐምሌ 13 1999 ዓ.ም. ድረስ ጥቃቅን ነገሮች ሳይቀር እየዘረዘረ ያስቃኘናል፡፡ጥቅምት 22 ከምሽቱ ሶስት ሰዓት አከባቢ ይጀምርና ራሱ በተባራሪ የሚያገኛቸውን መረጃዎች ሲጠቃቅስ ይቆይና በቁጥጥር ስር ሲውል ደግሞ ወደ ወህኒ ቤት ይዞን ወርዶ በትዝታዎቹ ተመስጦ ውስጥ ይከተናል፡፡ በተደደጋጋሚ በመታሰሩ፣ ብዙ ጊዜ ቃሉን ስለሰጠና በሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች በሸገር ያሉ ወህኒ ቤቶችን ከነመንገዶቻቸውን ፣ ከነመርማሪዎቻቸው እና ዘቦቻቸው ጥንቅቆ ያውቃቸዋል፡፡ከቃሊቲ በተጨማሪ እንደ ዓለም በቃኝ እና ማዕከላዊ ያሉ ዝነኛ እስር ቤቶችን በነዋሪነት ስለሚያውቃቸው እያንዳንዷን ኮሽታ በጥንቃቄ እንዲያስተውል ረድተውታል፡፡ስለወንጀል ምርመራ ቆይታው ካሰፈረውና ፈገግ ያሰኘኝን ተረክ ላቀብላችኹ፡፡

…አዲስ እስረኛ በገባ የመጀመሪያው ቅዳሜ ምሽት 2 ሠዓት ከእራት በኂላ አንድ ዘፈን ፣ አንድ ገጠመኝ ፣ አንድ ቀልድ ማቅረብ አለበት ፡፡ ቀልድ እና ገጠመኝ መናገር ግዴታ አይደለም፡፡ሆኖም መዝፈን ግን ለማንም የማይቀር ነው ፡፡እንኳን ሕዝብ በተሰበሰበበት ሊዘፍን ለብቻው እንኳን ሆኖ አንጎራጉሮ የማያውቅ የእኔ አይነቱ ጋግርታም ግን ሌላ አማራጭ ይሰጠዋል፡፡ይህም ኦሪጅናል ካሴት ገዝቶ ለቤቱ ማጫወት ነው፡፡ኦርጂናል ካሴት ግዛ የሚባለው እና ግዴታ የሚጥልበት እስረኛ ቴፕ በሌለበት ክፍል ወስጥ ኦሪጅናል ካሴቱ ተገዝቶ ምን ላይ እንደሚጫወት ግራ እየተጋባ 13ቱን ብር ሲከፍል ፣ ኦሪጅናሉ ካሴትም ቴፑም በአንድነት ከዚያው ከእስረኛው መሐል ብቅ ይላል፤ ኦሪጅናል ካሴት የሚባለው ከእሰረኛው መሐል ጥሩ ድምጽ ያለው ስለአዲሱ እስረኛ ሆኖ (በእርሱ ተገብቶ) የሚያንቆረቁረው ዜማ ነው ፤ ከ13ቱ ብር ካልተሳሳትኩ ሦስቱ ብር ለዘፋኙ ይሰጠውና ቀሪው 10 ብር ለቤቱ ገቢ ይሆናል፡፡…

ወንጀል ምርመራ ፣ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ ፣ ማዕከላዊ እያለ ወደዋናው መዲና ቃሊቲ ይወስደናል፡፡በዚያ ደግሞ ያስገረሙት ሁነቶችና ተዋንያንን ምስል ከሳች በሆነ መልክ ያስቃኘናል፡፡ "መነኩሴው" ፣ ሽማግሌዎቹና ወፈፌዎቹ ፣ደቦቃና አስመራ ድርደር (በወህኒ ቤቶች የቦታ ጥበት ምክንያት የተፈጠሩ የመኝታ ዘይቤዎች)... ይነግረንና ወደጠነከረው ርዕሰ ጉዳይ የክስ ቻርጅ ያመራል፡፡ ስለ ዳኞች እና ዓቃቤ ሕግ የኋላ ታሪክ በማስቀደም እያንዳንዷን የፍርድ ቤት ውሎ በዝርዝር ይተነትናል፡፡

የየዕለቱ ፍርድ ቤት ውሎችን ሲጀምር ከፍርድ ሂደቱ ተዋንያን ንግግር መካከል የሚመዛት እምቅ ኃይለ ቃል ለመጽሐፉ ውበት ለአንባቢያን ደግሞ ወደችሎቱ የምትወስድ ምትሀት ናት፡፡ "ምን እምነት ክህደት ትጠይቁናላችኹ ጠ/ሚ/ሩ ሞት ፈርደውብን የለ! የጠ/ሚ/ሩን ውሳኔ በፖስታ አድርጋችኹ ቃሊቲ ላኩልን ፣ አታመላልሱን" የሚለውን የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ንግግር ስናነብ ፍርድ ቤቱ ምን ያህል ከደረጃ በታች ይጫወት እንደ ነበር እንረዳለን፡፡የሲቪክ ደርጅት አባላት የሆኑት ዳንኤል በቀለ /ከአክሽን ኤይድ/ ፣ ነጻነት ደምሴ /ከ ኦርጋናይዜሽን ፎር ሶሻል ጀስቲስ ኢን ኢትዮጵያ/ እና ካሣሁን ከበደ / የአዲስ አበባ መምህራን ማኅበር ሊቀመንበር / በቀር ሌሎቹ ተከሳሾች በዚህ ፍርድ ቤት እምነት ስለሌለን አንከራከርም የሚል አቋም በመያዛቸው መድረኩን ዓቃቤ ህግ ብቻ የሚናገርበት አድርጎታል፡፡

ዓቃቤ ህግ መጀመሪያ ካቀረበው 25 ገጽ የክስ ቻርጅ በተጨማሪ 24 የቪዲዮ ካሴቶች ፣ በጣት የሚቆጠሩ የድምጽ ማስረጃዎችና ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎች በአይነት 94 በገጽ ብዛት 900 ሲሆን ይህም ጸሐፊው ጠ/ሚ/ሩ በቶን የሚመዝኑ መረጃዎች እንዳላቸው የተናገሩት ውሸት መሆኑንና ግራም እንኳን የሚሞላ እንዳልሆነ በመግለጽ አንባቢን እስኪደክመው በመዘረዝር እንዲያስረዳ ረድቶታል፡፡ (ዓቃቤ ከዚህ ሁሉ እንቶ ፈንቶ ማስረጃ በኃላ 382 ምስክር መጥራቱ ደግሞ የጠ/ሚ/ሩ በቶን የሚመዘን ማስረጃ አለን ዲስኩር በአየር ላይ እንዳይቀር መጨነቁን ያሳብቅበታል፡፡) የፀሐፊው ጥቂት ማብራሪያዎች ጠንካራ አለመሆን እርሱንም እንደዐቃቤ ህጉ አሰስ ገሠሡን የሚጎትት አስመስሎታል፡፡ እዚህ ጋር የህግ ባለሙያን ዕውቀት የሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ የወሰደው ጥንቃቄን ሳላደንቅ አላለፍም፡፡ነገር ግን ከአቀረባቸው ተደጋጋሚ ማስረጃዎች ይልቅ ለማሳያ አንድ አንድ እየጠቀሰ ቢያልፍ ትዕግስት የለሽ አንባቢን መጽሐፉን ሳይጨርስ እንዳያስቀምጠው ይረዳው ነበር፡፡ከዚህ በተጨማሪም ሰነዶቹን በሙሉ ወጥ በሆነ መንገድ አባሪ ላይ ቢያካትታቸው ኖሮ የፈለገ እያመሳከረ ፣ ያልወደደ ደግሞ ሳይጎረብጠው ባልተቆራረጠ የንባብ ጡዘት እንዲያነብ እድል ይሰጥ ነበር፡፡

ከፍርድ ሂደቱ በተጨማሪ ጋዜጠኛው የዳሠሳቸው የመጽሐፉን ዋጋ ከፍ የሚያደርጉት የአጣሪ ኮሚሽኑ እንቅስቃሴና ስለተቀለደበት ይቅርታ በማስረጃ ያቀረባቸው ትንታኔዎች ናቸው፡፡በተለይ አጣሪ ኮሚሽኑ አባላት በምርመራው ያገኙትን ውጤት ለማዳን ሀገርን ጥሎ እስከመሰደድ መድረሳቸው አንጀትን ያኝካል፡፡ለኮሚሽኑ የተሰጠው ሀላፊነት ቀጭን ነበር 'መንግስት በሰኔ 1 1997 እና በጥቅምት 22 1998 ዓ.ም. የወሰደው እርምጃ ተመጣጣኝ ነበር / አይደለም' የሚል ፡፡ መንግስት ውጤት ለመቀየር የአጣሪ ኮሚሽኑ አባላት ላይ ጫና በማሳደሩ ምክንያት በቪዲዮ የተደገፈ ማስረጃ ይዘው መሰደዳቸውን የምናገኘው ከሲሳይ አጌና መጽሐፍ ነው፡፡ ኢትዮጵያ "ሁላችንም የጠበቅነው ከ10 እስከ 16ሺ ነበር የሞተው ግን 1 ሺህ አይሞላም ስለዚህ ተመጣጣኝ ነው ፡፡" ያሉት የእነ ሼህ ኤልያስ ሬድማን ብቻ ሳይሆን ለእውነት መስዋዕትነት የከፈሉት የነአቶ ፍሬህይወት ሳሙኤል ፣ የአቶ ወ/ሚካኤል መሸሻ ሀገር መሆኗን ለትውልድ ጽፎ ማስቀመረትን የመሰለ ታላቅ ገድል የለም፡፡በተለመደው ድፈረት በረከት ስምኦን ስለተሰደዱት የአጣሪ ኮሚሽኑ አባላት ሲጠየቅ "ለጥገኝነት ማግኛ የሚደረግ ሙከራ ነው" ማለቱን ተከትሎ አቶ ወ/ሚካኤል መሸሻ የሰጡት መልስ የእውነት ወዳጆችን ያጽናናል፡፡ "እኛ የየትኛውም ፓርቲ አባል አይደለንም እንዲያውም የመንግስት ሹመኞች ነን... አሁን እድሜዬ 55 ደርሷል ፤ በምክትል ሚኒስቴር ደረጃ ደሞዝ አገኛለው ፤ መንግስት መኪና መድቦልኛል ፤ በዚህ እድሜዬ ከዚህ በላይ ምን እፈልጋለው?"

በቅርቡ አዲስ አበባ ላይ በተደረገው ዎርልድ ኢኮኖሚክ ፎረም ኦን አፈሪካ ላይ የደሞክራሲ መርሆች በራሳቸው የሚቆሙ መሆናቸውን የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የምር ግን ለነዚህ መርሆች ታማኝ አለመሆናቸውን እንዲያውም በደረሱበት ላይደርሱ መሐላ ከፈጸሙ እንደሰነበቱ የምነረዳው የፍትሕ ስርዓቱ ላይ የፈጸሙትን ማፈራረስ ይህ መጽሀፍ አጋልጦ ሲያሳየን ነው፡፡

በመጨረሻም በመጽሐፉ የኋላ ሽፋን አርቲስት ታማኝ በየነ ፣ጋዜጠኛ ደረጀ ደስታ እና ጋዜጠኛ አበበ ገላው አጭር አስተያታቸውን አስፍረዋል፡፡ በአንድ አይነት የቦለቲካ ሜዳ የሚጫወቱ ሰዎችን አስተያየት ከመደርደር ይልቅ እንደኔ እንደኔ ጉዳያዊ እውቀት(subject authority) ያላቸውን ቢያካትት መልካም ነበር፡፡ የታሪክ ምሁራን ፣

የህግ ባለሙያዎች ወይም ከሂደቱ ተሳታፊ የፓሊተካ መሪዎች አንዳቸውን እንደምስክርነት ቢያቀርብ የተሻለ ይሆን ነበር እላለው፡፡

በቅርቡ ታትሞ ካነበብናቸውና በዚህ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ዙሪያ የተጻፉ ሽያጭን ብቻ ማዕከል ካደረጉት አንስቶ ጲላጦሳዊ ከደሙ ንጹህ ነኝ የምትል የእጅ እድፍ ድረስ ያሉትን መጽሐፍት ስንናጤን የሲሳይ አጌና ይበል የሚያሰኝና ትውልድ ለታሪክ እና ለምርምር ሲያጣቅሰው የሚኖር ነው፡፡ በወቅቱ ዋና ተዋናይ የነበሩ የፓለቲካ መሪዎች አቶ በረከት ስምኦንን ጨምሮ ከያሉበት የአስተሳሰብ ምህዳር የተቃኘ መጽሐፍ አስቃኝተውናል፡፡አንድ የታሪክ ተማሪ የሆነ ወዳጄ “ወቅቱን ለታሪክ መዝግቦ ለማስቀረት የተሻለ ሚዛናዊ ትርክት ያካፍሉናል ብዬ የምጠብቀው ያን የህሊና(የዐሳብ) እስረኛ እስክንድር ነጋና ሲሳይ አጌና ነው” ሲል የነገረኝ ትክክል መሆኑን የተገነዘብኩት የዚህን መጽሐፍ የመጨረሻ ገጾች በስስት እየቆጠርኩኝ ሳነብ ነው፡፡

## የ"ኢሕአዴግ ቀይ እስክሪብቶ"ን እኔ እንደወደድኩት…

የ14 ዓመት እስር ፍርዷ ወደአምስት ዓመት በይግባኝ ዝቅ የተደረገላት ርዕዮ አለሙ፣ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ ሌላም ድርብ ድል አስመዝግባለች - የመጀመሪያ መጽሐፏን በማስመረቅ!

ርዕስ፡- የኢህአዴግ ቀይ እስክሪብቶ የገጽ ብዛት፡- 204 የጽሑፍ ብዛት፡- 19 ዋጋ፡- 40 ብር የመጀመሪያ እትም፡- ሐምሌ 2004 አርትኦት፡- ስለሺ ሐጎስ የሽፋን ገጽ ዲዛይን፡- አርኣያ ጌታቸው
የመጽሐፉ ርዕስ ‹የኢህአዴግ ቀይ እስክሪብቶ› ይሰኛል፡፡ ከሰኔ 2002 እስከ ሰኔ 2003 በአዲስ ፕሬስ ጋዜጣ፣ በቼንጅ መጽሔትና በፍትህ ጋዜጣ ላይ የታተሙ ጽሑፎቿ ስብስብ ነው - መጽሐፉ፡፡

‹የኢህአዴግ ቀይ እስክሪብቶ› የሚጀምረው በርዕዮት ምስጋና ነው፡፡ እግዚአብሔር፣ እጮኛዋ፣ ቤተሰቦቿ፣ ወዳጆቿን እና የታሰረችበት (ዞን ስምንት መሆኑ ይታወቃል) ድረስ በመሄድ የጠየቋትን የfacebook ‹‹አሸባሪዎች›› ሳይቀር ያልተመሰገነ የለም፡፡

በመግቢያዋ ላይ ‹‹…[ኢሕአዴግ] ራሱ ላጸደቀው ሕገ መንግስት ታማኝ ቢሆን ኖሮ፤… እኔም ራሴ አርፌ ልማታዊ ጋዜጠኛ እሆን ነበር›› ያለችው ርዕዮት፣ በመጽሐፏ ውስጥ ‹ልማታዊ ጋዜጠኝነትና ልማታዊ ጋዜጠኞቻችን› ባለችው ጽሑፏ (በነገራችን ላይ ይህንን ከሁሉም አስበልጬ ወድጄላታለሁ) - ስለልማታዊ ጋዜጠኝነት ባስቀመጠችው ብያኔ መሰረት በአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ላይ በሰነዘረቻቸው ገንቢ አስተያየቶች ‹‹ልማታዊ ጋዜጠኛ›› መባል ነበረባት፤ ትርጉሙ ባይዛባ ኖሮ!

ርዕዮት በጽሑፎቿ ከድህነት አንስቶ እስከ ድህነትን መጠቀሚያ ስላደረገው የኢሕአዴግ ፖለቲካ፣ ከሃይማኖት አባቶች ‹‹ለሁለት ጌታ ተገዢነት›› እስከ ያለ ፍትሐዊ ውድድር ስለተገኘው አውራ ፓርቲነት፣ ከኢትዮጵያዊነት እስከ እንስታዊነት የሚቀራት ርዕሰ ጉዳይ የለም፡፡

አጻጻፏ ለዛ ያለው ከመሆኑም ባሻገር ትረካዋ ጨዋታ አዋቂ አበው ‹‹ነገር በምሳሌ፣ ጠጅ በብርሌ›› እንዲሉ በአገርኛ ተረቶች የተከሸኑ በመሆናቸው ለማንኛውም አንባቢ ያለችግር የጉዳዩን ዝርዝር ዘልቀው ያስረዱታል፡፡ ከብዙ ተቺ ጸሐፊዎች በተለየ ጽሑፏን በግል አስተያየቶቿ ከመሙላት ይልቅ ማስረጃ ጥናቶችን ማጣቀሷ ደግሞ ለክርክሯ ጭብጥ ጥንካሬን አላብሶታል፡፡ በተጨማሪም ትችቶቹን ብቻ ሰንዝሮ እና የሚኮነነውን ኮንኖ እጅን ከማጣጠፍ ይልቅ መፍትሔ የምትላቸውን በጽሑፎቿ መደምደሚያ ላይ ጠቆም እያደረገች ማለፍን መምረጧ ተጨማሪ እሴት ሆኖላታል፡፡

ከመከራከሪያ ማስረጃዎቿ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የተለያዩ ቦታዎች ላይ መጠቀሟ፣ ጥቅሶቹን ለማይቀበሉ አሳማኝ አለመሆናቸውን እንደችግር አይቼዋለሁ፡፡ ይሁን እንጂ እሷ ግን የምታምንበትን ቤተ ሐይማኖት እና መጽሐፍ ቅዱስም ቢሆን ‹‹የማይነኩ›› በማለት ሳትሞግት አላለፈቻቸውም፡፡

‹‹የሐይማኖት አባቶቻችን ማንን እያገለገሉ ነው?›› ባለችው ጽሑፏ ‹ፍቅር እስከ መቃብር› ላይ የፊታውራሪ መሸሻን ፊት እያዩ ሲያዝኑ የሚያዝኑ፣ ሲደሰቱ የሚደሰቱ፣ ሲቆጡ የሚቆጡትን ቄስ ሞገሴን እያጣቀሰች የዘመኑ ታጻሳትን ብፅዕና ትተቻለች፣ ለሁለት ጌታ መገዛት እንደማይቻል መጽሐፍ ገልጣ ታስረዳለች፡፡ ‹እንስታዊነት እና እኛ› ባለችው ጽሑፏም ጥናት እያጣቀሰች ሴቶችን የወንዶች ረዳት ብቻ አድርገው የሚያቀርቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እና የሸርዐ ሕግጋትን ተችታለች፡፡

ትችቶቿ (ገንቢ አስተያየቶቿ ቢባሉም ያንሳቸዋል፤) በበቂ መረጃ እና መከራከሪያ ሐሳቦች ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው፣ እንደአንዳንድ ንዴት የመራቸው ጸሐፊዎች መዘባረቅ ወይም ስድብ አይስተዋልባቸውም፤ ከሐሜት የማያመልጡትን ተቃዋሚዎችንም ቢሆን ያለባቸውን ተፅዕኖ ያገናዘበ ተገቢ ትችት አድርሳቸዋለች፡፡ እንደምሳሌም ስለሰለማዊ ትግል ስታወራ ‹‹ጄን ሻርፕ… ከዘረዘሯቸው 198 የሚደርሱ የአመፅ አልባ ትግል ዓይነቶች ውስጥ በሀገራችን ያሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች አምስቱን እንኳን በትክክል ስለመጠቀማቸው እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡…›› (ገጽ 166) ብላለች፡፡

ርዕዮት በ‹የኢህአዴግ ቀይ እስክሪብቶ› ውስጥ፣ በአራት ክፍሎች ከተካተቱ 19 ጽሑፎች መካከል ከ6ቱ በቀር በሌሎቹ ውስጥ ምርጫ 1997ን አስታውሳናለች፡፡ ይህም ርዕዮትን እንደብዙዎቻችን ሁሉ ያኔ የተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ ፍሬ ናት ብዬ እንዳስብ አድርጎኛል፡፡

ለማንኛውም መጽሐፉ ከሽፋን ገጹ ጀምሮ እስከ ውስጥ ይዘቱ የሚጠገብ ዓይነት ሁኖ አላገኘሁትም፤ እግረመንገዳችንንም በአገራችን የፍትሕ ስርዓት የመንግስት ክፉ መዝገብ ውስጥ የሚያስገባው ምን ዓይነት ጽሑፍ እንደሆነ ለመታዘብ ስለሚረዳን፣ ሁላችሁም እንድታነቡት ጋብዤያችኋለሁ።

# ዋኤል ጎኒም ኢትዮጵያዊ ቢሆን ኖሮ…?

ጎኔም የግብጽ ደኅንነት ሰዎች ደብድበው የገደሉትን ካሊድ ሰኢድ ለማሰብ ‹‹እኔም ካሌድ ሰኢድ ነኝ›› የተሰኘ የፌስቡክ ገጽ ከፍቶ ለግብጽ አብዮት ያበቃ ሰው ነው፡፡ የመጀመሪያውን የአደባባይ እንውጣ ጥሪ ያቀረበው ይኸው የፌስቡክ ገጽ ነው፡፡ ዋኤል አደባባይ የወጡበትን የመጀመሪያ ቀን (ጃንዋሪ 25) አንድ ዓመት ለማክበር (Revolution 2.0 የተባለ) መጽሐፍ አሳትሟል፡፡ የመጽሐፉ ገቢ በሙሉ በአብዮቱ ለተጎዱ ሰዎች መደጎሚያ እንደሚውልም ተነግሯል፡፡ አሁን እዚህ ልጽፍላችሁ ያሰብኩት ግን ዋኤል ገጹን እና የግል ማንነቱን አስመልክቶ ለሚቀርብለት ጥያቄ ይሰጥ የነበረውን መልስ ነው (መጽሐፉ ላይ እንዳሰፈረው)፤ ዋኤል ኢትዮጵያዊ ቢሆንና የከፈተው ገጽም ኢትዮጵያዊ ቢሆን ኖሮ… በሚል ምናባዊ ምሳሌ፡፡ ስለዚህ ጽሑፉ በዋኤል የተጻፈው በኢትዮጵያኛ ተተርጉሞ ነው ልትሉት ትችላላችሁ፡፡

## ስምህ ማነው?

[1]ስሜ ሽብሬ ደሳለኝ ነው፤
[2]ስሜ ዩሱፍ አብደላ ነው፤
[3]ስሜ እስክንድር ነጋ ነው፤
[4]ስሜ ርዕዮት አለሙ ነው፤
[5]ስሜ አሕመዲን ጀበል ነው፤
[6]ስሜ አንዱአለም አራጌ ነው፤
[7]ስሜ በቀለ ገርባ ነው፤
[8]ስሜ ኦልባና ሌሊሳ ነው፤
[9]ስሜ መስፍን ነጋሽ ነው፤
[10]ስሜ አርጋው አሽኔ ነው፤

ስሜ…. ብዙ ነው፡፡

እኔ በጎዳና ላይ የተገደልኩ፣ ያለወንጀሌ የታሰርኩ፣ ያለሀጢያቴ የተገረፍኩ፣ መብቴን በፍርሐት የተነጠቅኩ፣ ከገዛ አገሬ የተሰደድኩ ኢትዮጵያዊ ነኝ፡፡

## ዕድሜህ ስንት ነው?

ዕድሜዬ ይህን ያህል ነው አልልም፤ ነገር ግን ከተወለድኩ ጀምሮ ያለው ያው አምባገነን መሪ ነው፤… ሙስናውም ያው ነው፤…. ጭቆናው ያው ነው፤… እናም በአገሬ የገነነው የፖለቲካ ፓርቲ ‹‹ተስፋ የለም›› ይባላል፡፡

## ከጠቀስካቸው ሰዎች ጋር ዝምድና አለህ?

እነዚህ ሰዎች የተኛውን ውስጤን ቀስቅሰውታል… ዕድሜ ለነርሱ አሁን ለውጥ ማምጣት እንደምችል ይሰማኛል፤… ታዲያ በራዕይ አልተዛመድንም ማለት ይቻላል?... አንድም ቀን አግኝቻቸው የማላውቃቸው እነዚህ ሰዎች ወንድሞቼ/እህቶቼ ናቸው፡፡

## ይህንን የምታደርገው ለምንድን ነው?

ወገኖቼ ላይ የሚደርሰውን በደል ተመልክቼ ወደጥናት ክፍሌ ስገባ እምባዬን መግታት አልችልም፤… ፍርሐት የተጫናቸው ኢትዮጵያውያን ምን ያህል ውርደትን እንደሚታገሱ አየሁ… ከራሴ በመጀመር በፍርሐት የምሠራውን ስህተት ሁሉ ማረም ጀመርኩ፤ እናም ለዛ ነው ይህንን ገጽ የፈጠርኩት፡፡ ለተበደሉ ወገኖቼ ያለቀስኩት ለሞቱ ዘመዶቼ ካለቀስኩት በላይ ነው… በየዕለቱ ፎቷቸውን ስመለከት ድብታ ውስጥ እገባለሁ፤ ኢ-ፍትሐዊነትን እስከመጨረሻው ለመዋጋትም ለራሴ ቃል እገባለሁ፡፡

## ማነው በገንዘብ የሚረዳህ?

ፈጣሪ ይመስገን፣ የገንዘብ ምንጮቼ ብዙ ናቸው። የመጀመሪያው ንቃተ ሕሊናዬ ነው… ይህ ምንጩ በቀን አራት ሰዓት ብቻ እንድተኛ እና ጠዋትም ፊቴን ከመታጠቤ በፊት የፌስቡክ ገጼን እንድከፍት ያስገድደኛል።

ሁለተኛው ምንጩ መማሬ ነው። በመማሬ ደስተኛ ነኝ፤ ዕውቀቴን አገሬን ለማገልገል አውለዋለሁ።

ሦስተኛው ምንጩ የልጆች አባት መሆኔ ነው። ሁሌም የሚጨንቀኝ ልጆቼ አንድ ቀን ‹‹አባዬ፤ ዜጎች ሲጨቆኑ እያየህ አቅምህ የሚፈቅደውን ለምን አላደረግክም?›› ብለው ይጠይቁኛል ብዬ ነው።

የመጨረሻው ምንጩ የሕዝብ ፍቅር ነው። አይቶኝ የማያውቅ፤ አይቼው የማላውቀው እና በስም የማንተዋወቀው ሕዝብ ፍቅር… በየዕለቱ የአመሰግናለሁ ማስታወሻ ይደርሰኛል…. የተለያዩ ዲዛይኖች፣ ሎጎዎች፣ ቪዲዮዎች ይልኩልኛል… ገጹ ብዙ ሰዎች ጋር እንዲደርስ ያስተዋውቁልኛል።

## ስለዚህ ምንድን ነው የምትፈልገው?

ይህንን ገጽ የፈጠርኩት ራሴን ከአደጋ ለመጠበቅ ብቻ አይደለም.. ነገር ግን አገራችን መልሳ የኛው የሕዝቦቿ እንድትሆን ከመፈለግ በላይ ሌላ ዓላማ የለኝም… አንድ ቀን እንዲህ ይሆናል ብዬ አልማለሁ፡- እርስ በእርስ ዳግም እንዋደዳለን፤ ሁላችንም ኢ-ፍትሐዊነትን እንቃወማለን፤ ከመሐከላችን ማንኛውም ሰው ክፉ ነገር ቢያይ ራሱ ይፈታዋል… እናም የመንግሥት ቅጥረኛ አንድን ዜጋ በጥፊ ከመምታቱ በፊት አንድ ሺሕ ጊዜ ያስብበታል።

## አትፈራም?

በጣም እፈራለሁ እንጂ፤… ፍርሐት እኮ የሰው ልጅ ተፈጥሮ ነው… ለተጨቆኑ ዜጎች የሚቆረቆር እንደእኔ እና እናንተ ያለ ሰው ግን ካለ ፍርሐቱ ይከስማል… ዕጣፈንታችንንም የምንወስነው እኛው ራሳችን እንሆናለን… እንዲህ እያልን፡- ‹‹ማንም ያለዕድሜው አይሞትም፣ ማንም ያለወንጀሉ አይታሰርም፣ ማንም አገሩን ለቅቆ አይሰደድም…›› አንድ ዘመዴ በ25 ዓመቱ ሞተ… ቁም ነገር ካልሠራሁበት የኔ ዕድሜ መርዘሙስ ምን ዋጋ አለው?

ብዙ ሰዎች ይህንን ለማመን ይቸገራሉ፤ እውነቱን ለመናገር ቃሉ የወጣው ከልቤ ነው… አገሬን ከልቤ እወዳታለሁ እናም በተሻለ ሁኔታ የምንኖርባት አገር እንድትሆን እፈልጋለሁ። መፈንቅለ መንግሥት ወይም አብዮት የማቀጣጠል ዓላማ የለኝም… እራሴን እንደፖለቲካዊ መሪም አልቆጥርም… ዋሊያዎችን እና ሉሲዎችን የሚደግፍ፣ ካፌ ደጃፍ ላይ ቁጭ ብሎ ተቆራጭ እየበላ፣ ማኪያቶ እየጠጣ ጋዜጣ የሚያነብ ተራ ዜጋ ነኝ።… የሚከፋኝ ብሔራዊ ቡድናችን በሰው አገር ሲሸነፍ ነው። … ቁምነገሩ በኢትዮጵያዊነቴ መኩራት እፈልጋለሁ።… ማንም ሰው የዜግነት ክብሩን ተገፍፎ እንዲጨቆን አልፈልግም። ይኸው ነው ምኞቴ።

----

[1] - ሸብሬ ደሳለኝ፤ ምርጫ 97ን ተከትሎ በተነሳው ብጥብጥ የመንግሥት ጥይት ሰለባ የሆነች ወጣት ተማሪ፤ [1] - ዩሱፍ አብደላ፤ በተመሳሳይ ወቅት የተገደለ የኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ተማሪ፤

[3] - እስክንድር ነጋ፤ በሽብርተኝነት ተከሶ የተፈረደበት ጋዜጠኛ፤

[4] - ርዕዮ ዓለሙ፤ መረጃ ለሽብርተኞች አቀብለሻል በሚል የተፈረደባት ጋዜጠኛ፤

[5] - አሕመዲን ጀበል፤ በሙስሊሞች የመጅሊስ ይቀየር ጉዳይ የታሰረ፣ ጋዜጠኛ እና ደራሲ፤

[6] - አንዱአለም አራጌ፤ ሽብር አሲረሃል በሚል የተፈረደበት የአንድነት ፓርቲ አባል፤

[7] - በቀለ ገርባ፤ ከኦነግ ጋር ግንኙነት አለህ በሚል የተፈረደበት የኦፌዴን ም/ሊቀመንበር፤

[8] - ኦልባና ሌሊሳ፤ ከኦነግ ጋር ግንኙነት አለህ በሚል 8 ዓመት የተፈረደበት የኦብኮ አባል፤

[9] - መስፍን ነጋሽ፤ በሽብርተኝነት አዋጅ/ክስ ምክንያት ከተሰደዱ የቀድሞዋ አዲስ ነገር ጋዜጠኞች አንዱ፤

[10] - አርጋው አሸኔ፤ የመረጃ ምንጩን እንዲሰጥ በመንግሥት ኃይሎች በግዴታ በመጠየቁ የተሰደደ ጋዜጠኛ፤

# እኛና ሶማሊያ

ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት አሁን ሶማሊያ ተብላ የምትጠራውን ሀገር አብዛኛውን ግዛት ያስተዳድር የነበረው አሕመድ ግራኝ በሰሜን የሚያዋስኑት ባብዛኛው ክርስትያንያዊ ከሆኑ አስተዳደር ግዛቶች ላይ ያካሄደው አስከፊ ወረራ አሁን ኢትዮጵያ ተብላ በምትጠራው አገራችንና በጎረቤት አገር ሶማሊያ መካከል ጊዜ እየጠበቀ ለሚያገረሸው ጦር መማዘዝ እና ቁርሾ የመጀመርያው አድርገው ይወስዱታል አንዳንድ ተንታኞች፡፡

ሁለቱ አገሮች ዘመናዊ በሆነ ማዕከላዊ መንግስት መተዳደር ከጀመሩበትና ሶማሊያ ከቀኝ አገዛዝ ነፃ ከወጣችበት ጊዜ አንስቶ ቢያንስ ሁለት ጊዜ በይፋ ጦር ተማዘዋል፡፡ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት ጋር አብሮ ሶማሊያ ማዕከላዊ መንግስት ካጣች በኋላ ደግሞ የኢትዮጵያ መንግስት ለደህንነቴ ስጋት እየፈጠሩ ነው ያላቸው ታጣቂዎች ላይ በተለያየ ወቅት ጥቃት ሲፈጽም ቆይቷል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የኢትዮጵያ ጦር ጥቃቱን የሚፈፅመው ድንበር አካባቢዎች ላይ ወይንም ድንበር አልፎ ከገባም ጥቃቱን ፈፅሞ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ነበር ለቆ የሚወጣው፡፡ ጥቅሙን የሚያስጠብቁ የጎሳ ሪዎችንም ያስታጥቃል በሚል የኢትዮጵያ መንግስትን ክስ የሚያቀርቡበትም ጥቂት አልነበሩም፡፡

እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር በሰኔ ወር 1998 ዓ.ም የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ሕብረት በሚል እራሱን የሚጠራ ቡድን የሶማሊያን ዋና ከተማ ሞቃዲሹንና አብዛኛውን የአገሪቱን ደቡባዊ ግዛቶች ተቆጣጠረ፡፡ እንደ ብዙዎች ዕይታ በዚያድ ባሬ የሚመራው መንግስት ወድቆ አገሪቷ መንግስት አልባ ከሆነች በኋላ ሶማሊያ ለመጀመሪያ ጊዜ አንፃራዊ ሰላም እና ሰፊ ግዛት የሚያስተዳድር መንግስት ያገኘችው ሕብረቱ ሞቃዲሹን በቁጥጥር ስር ሲያውል ነበር፡፡

ሕብረቱ በማዕከላዊ እና ደቡባዊ የሶማሊያ ግዛቶች ያገኘውን የበላይነት በሰሜን የሀገሪቱ ግዛቶች መድገም አልቻለም፡፡ ለዚህም ተጠያቂ ያደረገው በአካባቢው ታጣቂዎችን ትረዳለች ያላትን የኢትዮጵያን መንግስት ነበር፡፡ ይህንንም ተከትሎ ቅዱሳዊ ጦርነት (ጂሃድ) ኢትዮጵያ ላይ ማወጁን ሕብረቱ በይፋ አስታወቀ፡፡

ጦርነት የታወጀባት የኢትዮጵያ መንግስትም ይህ አደጋ ግልጽ እና በጊዜ መፍትሔ ሊሰጠው የሚገባ ነው ሲል ፓርላማውን ሞግቶ ‹‹ማንኛውን አስፈላጊ እርምጃ›› እንዲወስድ የአብላጫ ድምፅ ይሁኝታ አገኘ፡፡ በታህሳስ ወር 1999 ዓ.ም ከሕብረቱ ኃይሎች ጋር በሶማሊያ ግዛት ውስጥ ውጊያ እንደጀመረ የኢትዮጵያ መንግስት ይፋ አደረገ፡፡

ኢትዮጵያ ረዥም ድንበር የምትጋራው ከሶማሊያ ጋር ነው:: 1,600 ኪ.ሜ.!

ዓመት ከፈጀ ውጊያ በኋላ በኢትዮጵያ ወታደሮች የሚደገፈው የሶማሊያ ሽግግር መንግስት ሞቃዲሹን ተቆጣጠረ፡፡ በወቅቱ የኢፌደሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ ውጊያው በጦርነት በተሞላው ሕይወታቸው ካዩት ውጊያዎች ሁሉ ከፍተኛ የሆነ አለመመጣጠን የጎላበት እንደነበር ተናግረው ነበር፡፡ ምን ያህል ኢትዮጵያውያን ሕይወታቸውን እንዳጡ ግን ለመናገር ኃላፊነት (ግዴታ) እንደሌለባቸው ለማስረዳትም ሞክረው ነበር፡፡

ጊዜ በገፋ ቁጥር እና የኢትዮጵያ ጦር ወደሶማሊያ ዘልቆ እንዲገባ ምክንያት የነበረው የሕብረቱ ኃይሎች የመጨረሻ ጠንካራ ይዞታ ከነበረው ከኪስማዩ ግዛት ተሸንፈው ከተባረሩ በኋላ ‹የኢትዮጵያ ጦር ሶማሊያን ለቆ የሚወጣው መቼ ነው?› የሚለው ጥያቄ በተደጋጋሚ መሰማት ጀምሮ የነበረ ቢሆንም ከኢትዮጵያ መንግስት በኩል ግን ዓላማዬን ጨርሻለሁና ለቅቄ ልውጣ የሚል አዝማሚያ አልታየበትም ነበር፡፡

የሶማሊያ የሽግግር መንግስት ለሀገሪቱ ሰላም እና መረጋጋት ብቸኛ አማራጭ አድርገው ለሚያዩት ሶማሊያዊያንና ጉዳዩ ያገባናል ለሚሉ የውጭ ኃይሎች የኢትዮጵያ ጦር በሸሪፍ ሼክ አሕመድ የሚመራው የሽግግር መንግስት ሞቃዲሹን እንዲቆጣጠር በማገዙ ደስተኛ እንደነበሩ አያጠራጥርም፡፡ ነገር ግን ጦሩ በሶማሊያ የነበረውን ቆይታ ባራዘመ ቁጥር አብዛኛው ሶማሊያዊያን ቅሬታቸው እየበረታ ሄደ፡፡ እንደውም አንዳንድ አክራሪ (አክራሪ ያሰኛቸው ምን ይሆን? የኢትዮጵያ መንግስት…??) የሚባሉ ታጣቂ ቡድኖች ከሽግግር መንግስቱ ጋር ለመደራደር የኢትዮጵያ ጦር አገሪቱን ለቆ መውጣቱን እንደቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ ጀመሩ፡፡

በዚህ መሀል ነበር ተሸንፎ የተበታተነው ሕብረቱ ኃይል ከመካከለኛው ምስራቅ ጠንከር ያለ ‹የእንርዳህ› ጥሪ የቀረበለት፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ1990ዎቹ መጀመሪያ የአገሪቷን አለመረጋጋት እና መንግስት አልባነት እንደሽፋን ተጠቅሞ እግሩን ወደ ሶማሊያ ማስገባት የሞከረው አል-ቃይዳ ሶማሊያዊያን ከመካከለኛው

ምስራቅ መጤ አክራሪ የእስልምና አስተምህሮት ይልቅ ከባህላቸው ጋር የተዋሀደውን እስልምና በመምረጣቸው ሳይሳካለት ቀርቶ ነበር፡፡ ዓለም አቀፋዊ ጅሃድ ሶማሊያውያን ሕይወታቸውን ለመስጠት የሚፈቅዱለት ጉዳይ ሆኖ አላገኙትም ነበር፡፡ ከዓሥር ዓመት በኂላ ግን አል-ቃይዳ ጥሩ እድል ተፈጠረለት፡፡ ‹ከክርስቲያን አገር› የመጡ ወታደሮች ላይ ለመተባበር ለሶማሊያውያን ጥያቄ ሲያቀርብ እንደቀድሞ ላለመቀበል ምንም ምክንያት አልነበራቸውም - ሶማሊያዊያኑ፡፡

ታድያ የ1999ኙ የሶማሊያ ወረራ ከሁለት ዓመት ተልዕኮ ቆይታ በኂላ ተጠናቆ የኢትዮጵያ ጦር በጥር ወር 2001 ዓ.ም ወደ አገሩ ሲመለስ ሶማሊያ ውስጥ አል-ሸባብ ለሚባል ከአል-ቃይዳ ጋር ግንኙነት ላለው እስላማዊ አክራሪ ቡድን ማንሰራራት ምክንያት ሰጥቶ ነበር፡፡

ሶማሊያውያን ወጣቶችን (ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑ አባላቱ ዕድሜ ከ20 ዓመት በታች ነው፡፡ ‹አገራችንን ከክርስቲያኖች ወረራ እንከላከል› በሚል ስሱ (sensitive) መመልመያ መቀስቀስ የቻለው አል-ሸባብ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሶማሊያን መልቀቃቸውን ተከትሎ ድሮም ቢሆን በቅጡ ያልተደራጀውን የሽግግር መንግስት ጦር በቀላሉ በማባረር በዛ ያሉ የአገሪቱን ግዛቶች በጁ አስገብቷል፡፡

የኢትዮጵያ ጦር ከመውጣቱ በፊት በመንግስታቱ ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት ወደ ሶማሊያ የተሰማራው የአፍሪካ ሕብረት ሰላም አስከባሪ ኃይል የሰላም ስምምነት አካል ያልሆነውን አል-ሸባብን ለመቆጣጠር አልቻለም ነበር፡፡
የአል-ሸባብን ማንሰራራት እና እያደር መጠናከር ተከትሎ፣ መጀመሪያ የኬንያ ጦር በስተደቡብ በኩል ‹ድንበር ጥሰው ዜጎቼን እያፈኑ› ያስቸገሩ ታጣቂዎችን ፍለጋ በሚል ምክንያት ከዚያም የኢትዮጵያ ጦር ‹የአፍሪካ ሰላም አስከባሪ ኃይልን እንዲረዳ› ከኢጋድ አባል ሀገራት የቀረበለት ጥያቄን ተቀብሎ በሕዳር ወር 2004 ዓ.ም በይፋ ወደ ሲማሊያ ድጋሚ አመራ፡፡ ይህ ጦር አሁንም እዛው ያለ ሲሆን መቼ እንደሚመለስም በይፋ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡

## የሶማሊያ መፍትሔ - ችግሩን በሚገባ መረዳት

ሶማሊያውያን 275 አባላት ያሉት ብሔራዊ ምክር ቤት መርጠዋል፡፡ ምክር ቤቱም ከማዕከላዊ መንግስቱ መውደቅ በኂላ ለመጀመርያ ጊዜ በሶማሊያ ምድር በተደረገ ምርጫ ሀሰን ሼክ መሐሙድን የአገሪቷ ፕሬዝዳንት አድርጎ መርጧል፡፡
ተመራጩ ፕሬዝዳንት ትልቅ ወጣ ውረድ ያለው ኃላፊነት ነው የተሰጣቸው፡፡ ከሃያ ዓመታት በላይ የተረጋጋ ሰላም አግኝታ የማታውቀው ሶማያን ሰላም መስጠት ከኃላፊነታቸው ሁሉ የላቀው ነው፡፡ ይህንን ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ሁሉንም ሶማሊያውያን የሚያግባባ ሐሳብ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሁሉንም ሶማሊያውያን ማለት አል-ሸባብንም ይጨምራል፡፡ ሶማሊያ ውስጥ የተረጋጋ ሰላምን ለማምጣት የአል-ሸባብን መውደቅ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚያዩ ሁሉ ስህተት እየፈፀሙ ነው፡፡ ምን አልባት አል-ሸባብን ወግቶ ማሸነፍ እና ወታደራዊ ድርጅቱን ቅርፅ ማሳጣት ይቻል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ሁለት አደጋዎች ተከትለው የመምጣታቸው ዕድል ሰፊ ነው፡፡

አንደኛ፤ ተደራጅቶ በመዋጋት የተሸነፈው አል-ሸባብ የትግል ቅርፁን ቀይሮ ወደ ሰርጎ ገብ ጥቃት መጣልና ወደ ሰፊ አጥፍቶ ጠፊ ጥቃቶች ፊቱን ሊያዞር ይችላል፡፡ የሶማሊያ የመከላከያና ፖሊስ ኃይል ደግሞ እየተሸሎከሎከ ጥቃት የሚፈፅም ኃይልን ተከታትሎ ሊያድን የሚያስችል በቂ አቅም ስለሌላቸው የሰላም መፍትሔውን በዕጅጉ ሊያርቀው ይችላል፡፡

ሁለተኛ፤ ሶማሊያ ውስጥ እስካሁን እንዳየነው የአንድ ታጣቂ ኃይል መውደቅ በሌላ ታጣቂ ኃይል ይተካል፡፡

ስለዚህም ሶማሊያውያንን ወደ ብሔራዊ መግባባት ለማምጣት በሚደረገው ጥረት አል-ሸባብን ማካተት ምርጫ የሚኖረው ጉዳይ አይመስልም፡፡ ምን አልባት አል-ሸባብ እራሱ ወደ ድርድር አልመጣም ብሎ አሻፈረኝ ሊል እንደሚችል መገመት ከባድ አይሆንም፡፡ ይህንንም ለማሸነፍ ግን አማራጮች አሉ፤

በመጀመርያ የአል-ሸባብ ጠንካራ መመልመያ የሆኑትን የውጭ ኃይሎች በተለይም የኢትዮጵያ ወታደሮችን ወደ አገራቸው በመመለስ (በአፍሪካ ሕብረት ጥላ ስር ያለው ኃይል ሲቀር) አል-ሸባብን የመመልመያ ምክንያት

ማሳጣት ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት እንደድሮ የመመልመል አቅም የማይኖረው አል-ሸባብ የተለሳለሰ አቋም ሊይዝ ይችላል፡፡

ሁለተኛውና ተያይዞ መሰራት ያለበት ለሶማሊያዊያን ወጣቶች ጠብ-መንጃ አንግቶ ከመዋጋት የተሻለ ምርጫ መስጠት ነው - የሶማሊያን መልሶ ግንባታ ቢያንስ ቢያንስ አንፃራዊ ሰላም ባሉባቸው ቦታዎች በማፋጠን፡፡ ይህ ደግሞ አሁን አደራጅቶ የያዘውን ወጣት ልብ ወደ ቀድሞ ለአል-ቃይዳ አስቸጋሪ ወደነበረው ሶማሊያዊ አስተሳሰብ በመመለስ አል-ሸባብን የኃይል መሰረት በማናጋት ያዳክመዋል፡፡

## የኢትዮጵያ ሚና

አሁን ሶማሊያ ለደረሰችበት ተስፋ ሰጪ ደረጃ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ማንም ሊከፍለው ያልደፈረውን መስዕዋትነት ከፍለዋል፡፡ አሁን ተራው እግራችንን ወደ ሶማሊያ እንድንሰድ ከዳር ሆነው ያበረታቱን ምዕራባዊያን ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን መፍትሔዎች ለማስፈፀም ፍላጎቱ እንጂ አቅሙ የለንም (በተለይም መልሶ ግንባታውን በተመለከተ)፡፡

‹‹እስከ አሁን መስዕዋትነት የከፈልንበት የሶማሊያ ሰላም እና መረጋጋት ዋጋ እንዳያጣ እና አሁን የተገኘው ተስፋ በጥዋቱ እናዳይጨልም አጥብቀን እንፈልጋለን፤ ስለዚህም ለመሳርያ መግዣ ለማዋል የማትሰስትን የፈረጠመ የገንዘብ አቅማችሁን ተጠቅማችሁ ለሶማሊያ መልሶ ግንባታ ማዋል የሚገባችሁ ጊዜ አሁን ነው›› የሚል ኮስተር ያለ የውለታ ምላሽ ጥያቄ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን እንጠብቃለን፡፡

# አንድ ለመንገድ፡- ከካምፖሎጀው ፍጥጫ ማግስት

*በታምራት ተሰፋዬ*

እኛ ኢትዮጵያውያን ጥሎብን በብዕር ለመግለጽ ከምንችለውም በላይ በእግር ኳስ አቅላችንን እስከምንስት ድረስ ልክፍት ውስጥ ገብተን በራሳችን የሚያረካን ጠፍቶ የሌሎችን ማድነቅ ከጀመርን ይኸው ሦስት አሥርት ዓመታቶች ተቆጠሩ። ይበል ነው፤ ይኸው ጊዜ ተለውጦ ለረዥም ጊዜ አልጎመራ ያለው ፍሬ ሊበስል ከጫፍ ላይ ደርሷል። ኢትዮጵያ ሱዳንን አሸንፋ ለአፍሪካ ዋንጫ አልፋለች። ታዲያ ለምን እግረመንገዳችንን የኢትዮ-ሱዳን ጂኦ ፖለቲካዊ ግንኙነት ላለፉት 20 ዓመታቶች ምን ዓይነት ገጽታ እነደነበረው በትንሹ ለመዳሰስ አንሞክርም።

## ደርግና ሱዳን

የደርግ መንግስት ከሱዳን ጋር ኦፊሻላዊ ግጭት ባይኖርበትም እባብ ለእባብ እንደሚባለው የሁለቱም መንግስታዊ አስተዳደሮች እርስ በእርስ ሲጠባበቁ እነደነበር የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ። ሱዳን ሕወሓትንና ሻዕቢያን በክልሏ ላይ እንደልብ እንዲፈነጩና የራሳቸውን ቢሮ እንዲከፍቱ ስታደራጅ ደርግ የመልስ ምት በሚመስል መልኩ የደቡብ ሱዳን ነጻ አውጪዎችን በማስታጠቅና በፋይናንስ በመደጎም የበቀል ዱላውን ይሰነዝር ነበር። በዚህ ወቅት የሱዳን ሕዝብ በሁለት ጎን ተጠቃሚ ነበር። ሕወሓት በእርሻና በትራንስፖርት ዘርፍ ተሰማርቶ ሀገራቸውን ሲረዳ በሌላ አቅጣጫ ደርግ ነጻነት ለሚፈልጉ ሕዝቦች ያለውን በመስጠት ሕዝቡ በሁለቱም ወገን ተጠቃሚ እንዲሆን አድርጎ ነበር።

## የገደለው ባልሽ…

ኢሕአዴግ ስልጣን በያዘ በአንደኛ ዓመቱ ወርሃ ሰኔ ላይ ዱብ ዕዳ ወረደ። ሀገራችንን ለመጎብኘት ወደ አዲስ አበባ የመጡት የግብጹ ፕሬዝዳንት ቦሌ አየር ማረፊያ ሲደርሱ አቀባበሉ በፖሊስ ኦኬስትራ ይሆናል ተብሎ ሲጠበቅ ነገሮች ተገላብጠው በክላሽ እና በቦንብ ሆነ። ስድስት የሚሆኑ የአረብ ሀገር ተወላጆች ሙባረክን በክላሽ እንኳን ደህና መጣህ ቢሉትም የግድያው ዕቅድ ሳይሳካ ቀርቶ አራቱ አዲስ አበባ ላይ ሲሙቱ አንዱ ሸሽቶ ሱዳን ገባ። ግጭቱ ኢትዮጵያና ሱዳን ላይ በመሆን ክርክሩ አሳልፈሽ ስጪኝ አልሰጥም ሆነ በመሰረቱ በወቅቱ ሙባረክ ከኢትዮጵያ ይልቅ ለሱዳን ቅርብ ነበሩ። እንደውም በአንድ ወቅት በአንድ እንትን የሚባለው ደረጃ ላይ ደርሰው ነበር። መኖር መልካም ነው ብዙ ያሳያል፤ ይኸው በክላሽና በቦንብ ያልተፈቱት ሙባረክ በHeዝብ ጩኸት ተረቱ። እኛም በርእስነት የተጠቀምኩትን ተረት ሳንተርት ኢትዮጵያና ሱዳን ሰላም አወረዱ።

## የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት

ሱዳን በዚህ ወቅት የጆከርነት ሚናዋን ስትጫወት ሰነበተች፤ ከወደብ አከራይነት እስከ መሳሪያ አስተላላፊነት በመሳተፍ በአንድ ድንጋይ እንደሚባለው ከሁለቱም ሀገር ጋር በመሰለፍ ኢኮኖሚዋን አፈረጠመች። ጦርነቱ የሁለቱንም ሀገሮች ኢኮኖሚ ያሽመደመደ ሲሆን በተቃራኒው የሱዳን ሕዝብ በጦርነቱ ተጠቃሚ ለመሆን በቃ።

## የሚሊኒየም ዋዜማ

በበርበሬ ገበያ ላይ በታየው ቅጥ ያጣ የዋጋ ጭማሪ ‹‹አልጫው ሚሊኒየም›› የተባለው ሀገራዊ በዓል የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የሱዳንም በዓል እስከሚመስል ድረስ መዲናችን በሱዳን ዘፈን ‹‹እልል በቅምጤ›› ስትል አመሸች። በዕለቱ ነፍሳቸውን ይማረውና የቀድሞው ጠ/ሚኒስትራችን ከአልበሽር እና ከባለቤታቸው ጋር በሱዳን ሙዚቃ ሲደንሱ አመሹ። በወቅቱም ጥላሁን ገሠሠ እያለ እንዴት በሱዳንኛ የሚሉ ድምጾች ከየአካባቢው መሰማት ጀመሩ። መቼም ይህቺ ነገር ለተራ ፖለቲከኛም አትጠፋም፤ ይህ ጸሐፊ ሆን ተብሎ የተደረገ ነው ብሎ ያምናል። በወቅቱ መለስ ግንኙነታችን በሙዚቃችሁ ከመጨፈርም በላይ ጥርጣሬ የሌለበት መልካም ጉርብትና እንዲኖረን እንፈልጋለን የሚል መልዕክት ለአልበሽር ለማስተላለፍ አስበው ይመስለኛል። አልበሽርም መልዕክቱን በመረዳት በሚመስል መልኩ ግንኙነቱን ማጠንከር ላይ መሥራት ጀመሩ።

## ጥላሁን ገሠሠና አልበሽር

ሄግ የሚገኘው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ዳርፉር ላይ በደረሰው ቀውስና በተያያዥ ጉዳዮች አልበሽር ላይ የበረራ እገዳና በማንኛውም ጊዜ ተይዘው ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ዋራንት ቆረጠባቸው፤ ምድር ቀውጢ ሆነች፡፡ ሰውየው በነጻነትና በመታሰር መሀል ላይ ወደቁ፡፡ እንቅስቃሴያቸው ሁላ ድጋፍ ለማገኘት ደፋ ቀና ሆነ፡፡ በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ ታላቁን የሙዚቃ ሰው አጣች፡፡ እንደተለመደውም አጀንዳው በኢትዮጵያ ወደ አንድ አቅጣጫ ዞረ፤ ጨዋታው ሁላ ጥላሁን ጥላሁን ሆነ፤ በዚህ ወቅት አልበሽር ወደ አዲስ አበባ ድምጻቸውን አጥፍተው ከተፍ አሉ፡፡ የዋሆች ለቀብር ይሆን ብለው ያስባሉ፤ አልበሽር ግን ዋራንቱ ምንም ተጽእኖ እንዳላሳደረባቸው እና ፋርሽ እንደሆነ በኢትዮጵያ ጉብኝት አስመሰከሩ፡፡ በወቅቱ ሚዲያው ሁላ ከአልበሽር ይልቅ ጆሮዋቸውን ለሙዚቃ ተንታኙ ሠርጸ ፍሬስብሓት አዋሱት፡፡ ጨዋታው ሁላ ሞናሊዛዬ ነሽ ሆነ፤ አልበሽርም ድምፃቸውን እንዳጠፉ በአረብኛ ሞናሊዛዬ ነሽን እያንጎራጎሩ ጉብኝታቸውን ጨርሰው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ፡፡ ዓለም አቀፉ ሚድያም የሄግ ሕግ አልተከበረም በማለት ለአንድ ሰሞን ተንጫጫ፤ ኢትዮጵያም (አልበሽርን ያለምንም ኮሽታ በማስተናገድ) ግንኙነቷ ለችግር ጊዜም እንደሆነ ለፕሬዚደንቱ ስታሳይ ጥላሁን በበኩሉ በሕይወት እያለ ሚሊኒየም አዳራሽ ባለመገኘት ለሱዳን ያደረገውን ውለታ በመሞቱ ደግሞ ሚዲያውን ይዞ አጀንዳውን በማዞር ውለታውን ዳግም አረጋገጠላቸው፡፡ ነፍስ ይማር ሌላ ምን ይባላል፡፡

## ኢትዮጵያ እነደ ጆከር

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ለሁለት ለተከፈሉት ሱዳኖች እንደ ጆከር በመሆን በሁለቱም መሀል ላይ ድልደይ በመሆን እያገለገለች ትገኛለች፡፡ በዚህ ወቅት ለሁለቱም ሱዳኖች ከኢትዮጵያ ውጭ የጋራ ፍላጎታቸውን የሚስከብር እንደሌለ የተረዱ ይመስላል፡፡ እናም ኢትዮጵያ በዚህ ቀውጢ ሰዓት ከሱዳን ሕዝብ ጋር በመቆም አለኝታነቷን አረጋግጣለች፡፡

## ያልተነካው አጀንዳ

ነፍሳቸውን ይማርና የደቡብ ሱዳን የመጀመሪያው ፕሬዝዳንት የነበሩት ጆን ጋራንግ የደቡብ ሱዳንን ወሰን (border) እስከ ባሮ መነሻ ድረስ መሆኑን በለሆሳስ ይናገሩ ነበር፡፡ ይህ መቼም ለኢትዮጵያ አስደንጋጭ ነው፤ በእርግጥም ደቡብ ሱዳን በዚህ ወቅት ድክ ድክ እያለች ስለሆነ ይህን ጥያቄ ማንሳት ባትችልም አጀንዳው ግን ጠረጴዛ ላይ እንዳለና ከጊዜዎች በኋላ መነሳቱ እነደማይቀር ግልጽ ነው፡፡ በእውነቱ የጋምቤላ ኢትዮጵያዊነት ላይ ምንም ድርድር አያስፈልግም፤ ነገር ግን ነገሮች ጥሩ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ በአንድ ወቅት ለሥራ ጋምቤላ በሄድኩበት ወቅት ብዙውን ቁጥር የሚወክለው የኑዌር ኽዝብ ከስልጣኑ እራሱን አግሎ ባሮን ይዞ እየተመመ መሆኑን ለመገንዘብ ችያለሁ፡፡ የቤት ስራውን በጊዜ መጀመር መልካም ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በኅብረ-ትርኢት ሙዚቃን ከመልቀቅና የቁንጅናን አክሊል ለክልሉ ከመስጠትም በላይ ጋምቤላ ላይ ትልቅ ሥራ መሰራት ያለበት ይመስለኛል፡፡ ሕዝቡን የስልጣን ተጋሪ ማድረግና መሠረተ ልማቶችን ማስፋፋት ችግሩን በዘላቂነት ይቀርፈዋል ተብሎ ታሰባል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ነገሮች ከሆኑ በኋላ መቱ እና ቴፒ ላይ ቆሞ ዘራፍ ከማለት ውጪ አማራጮች ላይኖሩ ይችላሉ፡፡

ለትዝታ እና ለማንቂያ ያክል ይህንን ካልኳችሁ አሁን ደግሞ ወዳቋረጥኳችሁ የድል ማግስት ጭፈራ ልመልሳችሁ ‹‹…የእርግብ አሞራ……የእርግብ……የእርግብ አሞራ…›› (የእርግብ አሞራ ማለት ግን ምን ማለት ይሆን?)

# ከነጻነት እስከ ነጻ ምርጫ

በናትናኤል ፈለቀ እና ኤዶም ካሣዬ

ጎረቤት ሀገር ኬንያ እ.አ.አ በ1963 ዓ.ም ነበር ከእንግሊዝ ቀኝ አገዛዝ ነፃ የሆነችው፡፡ በቀጣዩ ዓመት ኬንያ ራስዋን የቻለች ሪፐብሊክ ሆና ስትቋቋም የነፃነት ትግሉን እና የኬንያ አፍሪካ ብሔራዊ ኅብረትን (ካኑ) ይመሩ የነበሩት ጆሞ ኬንያታ* (የአሁኑ ተመራጭ ፕሬዝዳንት ኡሁሩ ኬንያታ አባት) የኬንያ የመጀመርያ ፕሬዚዳንት ሆኑ፡፡ ምክትላቸው ደግሞ የአሁኑ ተሰናባች ጠቅላይ ሚኒስትር ራይላ ኦዲንጋ አባት ኦጊንጋ ኦዲንጋ** ነበሩ፡፡
ኦዲንጋ የኬንያ የመጀመርያ ምክትል ፕሬዝዳንት በመሆን ለሁለት ዓመት ብቻ ነበር ያገለገሉት፡፡ ከፕሬዝዳንት ኬንያታ ጋር በፈጠሩት አለመግባባት ምክንያት ሥልጣናቸውን በገዛ ፈቃዳቸው ለቀው የኬንያ ሕዝቦች ሕብረት የተሰኘ የፖለቲካ ፓርቲ በማቋቋም የኬንያታን ሥልጣን መገዳደር ጀመሩ፡፡ ጆሞ ኬንያታ ለነፃነት ትግል አጋራቸው ብዙም ክፍተት መስጠት አልፈለጉም፡፡ በሁለቱ አባቶች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት እያደገ ሂዶ እ.አ.አ በ1969 ዓ.ም. በኪሲሙ ግዛት ሕዝብ በተሰበሰበበት የተከሰተ የሁለቱ መሪዎች ‹እንኪያ ሰላምታ›ን ታክኮ በተፈጠረ ሁከት ሰዎች ከሞቱና ከቆሰሉ በኂላ ኦጊንጋ ኦዲንጋ ቀጣዮቹን ሁለት ዓመታት በእስር እንዲያሳልፉ ተገደዱ፡፡

እ.አ.አ በ1978 እስኪሞቱ ድረስ ኬንያን ለመምራት የምዕራባውያኑን ድጋፍ ያገኙት ኬንያታ ፊታቸውን ወደ ምስራቅ ያዞሩት ኦዲንጋ ላይ ሙሉ የፖለቲካ እና የሥልጣን የበላይነት ወስደው ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ከኩኩዩ ቤተሰብ የሆኑት ኬንያታ የ14 ዓመት ሥልጣናቸውን በሞት ሲነጠቁ የተኳቸው ከካለንጂን ጎሳ የሆኑት ዳንኤል አራፍ ሞይ ይሁኑ እንጂ በሕይወት ሥልጣን ላይ በቆዩባቸው ዓመታት ግን ቤተሰባቸውን በሀብት አንበሻብሸዋል እንዲሁም የኩኩዩ ጎሳን የቁጥር የበላይነት ወደ መንግሥት ተቋማት ሥልጣን የበላይነትም አምጥተዋል ተብለው ይከሰሳሉ፡፡

ሥልጣን በእጃቸው የወደቀላቸው ሞይ ቀስ በቀስ ኬንያታ ሲገነቡ የቆዩትን ሥልጣንን በብቸኝነት መቆጣጠርን እና ተቃዎሚዎቻቸውን የማፈን ልምድ እያዳበሩ ሄደው እ.አ.አ 1982 ኬንያ በአሀዳዊ ፓርቲ (ካኑ) የምትተዳደር ሀገር እንደሆነች በይፋ አሳወጁ፡፡

የሞይ የሥልጣን ዘመን ለኬንያውያን ከቀኝ ግዛት በኂላ የነበረ አስከፊ ወቅት ነበር፡፡ ዜጎች ስለራሳቸው ሀገር መረጃ ለማግኘት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በነበሩትን መገናኛ ብዙኃን ላይ እምነት ስላልነበራቸው ዜናዎችን የሚያገኙት ከቢቢሲ ዓለም አቀፍ አገልግሎት እና የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮን ከመሰሉ ምንጮች ነበር፡፡ እ.አ.አ 1978 በተደረገ ምርጫ ሥልጣን የያዙት ሞይ እ.አ.አ በ1983 እና 1988 ሁለት ምርጫዎችን የራሳቸው ፓርቲ ካኑ ካቀረባቸው እጩዎች ጋር ተወዳድረው አሸንፈዋል፡፡ የ1988ቱ ምርጫ መራጮች ድምፅ የሰጡት በሚስጥር ሳይሆን ለእያንዳንዱ ተወዳዳሪ የተለየ ኮሮጆ ተዘጋጅቶ መራጮች ድምፃቸውን መስጠት ለሚፈልጉት ተወዳዳሪ የተለየ የተራ ሰልፍ ተሰልፈው ነበር፡፡ ይህም ማለት እያንዳንዱ ዜጋ ለማን ድምፁን መስጠት እንደሚፈልግ ገና ሰልፉን ሲመርጥ ይታወቃል ማለት ነበር፡፡

የ1988ቱን ዓይን ያወጣ ነፃነት እና ፍትሐዊነት የጎደለው ‹‹ምርጫ›› ተከትሎ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከወዳጅ ሀገራት በደረሰባቸው ጫና ሞይ ሕገ መንግስቱን ለማሻሻል ተስማሙ፡፡ የተሻሻለው ሕገ መንግስት የመድብለ ፓርቲ መኖርን የፈቀደ እና የፕሬዝዳንቱን የሥልጣን ዘመን በሁለት ብቻ የገደበ ሆነ፡፡ በዚህም ምክንያት እ.አ.አ በ1992 እና በ1997 ዓ.ም የተካሄዱትን ሁለት ፕሬዝዳንታዊ ምርጫዎች በማሸነፍ የሞይ የ24 ዓመት የሥልጣን ቆይታ አበቃ፡፡

የ1997ቱን ምርጫ በማሸነፍ የመጨረሻ የሥልጣን ዘመናቸውን ሲጀምሩ ሞይ ወዲያው ነበር ተተኪያቸውን ማዘጋጀት የጀመሩት፡፡ በወቅቱ ወጣትነቱን በሚገባ ያላጠናቀቀውን የ36 ዓመቱ የመጀመርያው የኬንያ ፕሬዚዳንት እና የካኑ መሥራች ጆሞ ኬንያታ የበኩር ልጅ ኡሁሩን (ነፃነት ማለት ነው ትርጉሙ) ተተኪያቸው እንዲሆን አስበው የተለያዩ የፓርቲ እና የመንግሥት ኃላፊነቶች ላይ እንዲሠራ ሲያደርጉ ቆይተው በመጨረሻም በይፋ ተተኪ ፕሬዚዳንት እንዲሆን የካኑ ፓርቲን ወክሎ እንዲወዳደር ድጋፋቸውን ሰጡት፡፡ ይህ ክስተት ካኑን ወክለው ለፕሬዚዳንትነት ለመወዳደር ይሹ የነበሩ እና ኡሁሩ ልምድ እንደሚጎለው በሚያምኑ አንጋፋ የፓርቲው አባላት መካከል ቁጣን ቀስቅሶ ነበር፡፡

እ.አ.አ በ1982 ዓ.ም ሞይ ላይ በተካሄደ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተሳትፈሃል በሚል (በኋላ ሕይወታቸውን በተባባሪነት በተረኩበት “Raila Odinga: an enigma in Kenyan Politics” ብለው በሰየሙት መጽሐፋቸው የመፈንቅለ መንግሥቱ ሐሳብ ነዳፊ እንደነበሩ አምነዋል፡፡) ለ10 ዓመታት በእስር የቆዩት የኦጊንጋ ኦዲንጋ ልጅ ራይላ ኦዲንጋ በ1997ቱ ምርጫ ለፕሬዝዳንትነት ተወዳድረው 4ኛ ሆነው ካጠናቀቁ በኋላ ብዙዎች ባልጠበቁት ሁኔታ ፓርቲያቸውን ከካኑ ጋር ቀላቅለው ነበር፡፡ ኋላ ላይ ሞይ ለ2002ቱ ምርጫ ኡሁሩን ከደገፉ በኋላ እንደገና ከካኑ በመነጠል የለዘብተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲን አቋቁመው በኋላም ከሞዋይ ኪባኪ ፓርቲ ብሔራዊ ጥምረት ጋር በመሆን ብሔራዊ የቀስተደመና ቅንጅት (ናርክ) የሚባል ኅብረት ፈጥረው ምርጫውን በማሸነፍ ኪባኪ የፕሬዝዳንትነት ስልጣን ጨብጡ፡፡

የኪባኪ እና የራይላ ኅብረት ሲመሠረት በተስማሙት መሠረት ለራይላ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታ እና ግማሽ የካቢኔ መቀመጫ ለፓርቲያቸው አባላት እንዲሰጥ የተጠበቀ ቢሆንም እውነታው ግን እንደዛ አልሆነም፡፡ ይባስ ብሎም እ.አ.አ 2005 ዓ.ም የሥልጣን ኃይል ከክልል መስተዳድሮች ላይ ቀንሶ ወደ ፕሬዝዳንቱ እንዲያዘምም ያደርጋል የተባለለትን ሕገ-መንግሥት ኪባኪ ለሕዝበ ውሳኔ ሲያቀርቡት ራይላ አጥብቀው ተቃወሙ፡፡ በሕዝበ ውሳኔው ውጤት መሠረት ሕገ-መንግስቱ በ57 በመቶ የድምፅ ብልጫ ውድቅ ከሆነ በኋላ ኪባኪ ራይላን ጨምሮ ከለዘብተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ የነበሩትን የካቢኔ አባላት ጠራርገው አባረሩ፡፡ በዚህም ምክንያት ከሁለት ዓመት በኋላ በተካሄደው ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ሁለቱ ሰዎች ፊት ለፊት ተፋጠጡ፡፡

## የ2007 ምርጫ

በ2007 በተካሄደው ምርጫ የወቅቱ ፕሬዝዳንት ኪባኪ ለሁለተኛና ለመጨረሻ ጊዜ ሲወዳደሩ ከኬኒያ የነፃነት እወጃ አንስቶ ለ44 ዓመታት የተቃውሞውን ሜዳ በመሪነተ የዘለቁት ራይላ ኦዲንጋ ለሁለተኛ ጊዜ የፕሬዝዳንትነት ማዕረግ ለማግኘት ወደ ውድድር ገብተዋል፡፡ በ2002ቱ ምርጫ እና በ2005 የሕገ መንግሥት ሕዝበ ውሳኔ የኬኒያ ምርጫ ቦርድ በውጤታማ ሥራ የተወደሰ ቢሆንም የ2007 ምርጫ ሊካሄድ ጥቂት ቀናት ሲቀሩት የጊዜው ፕሬዝዳንት ሞዋይ ኪባኪ በምርጫ ቦርድ ውስጥ ከነበሩ ሃያ ሁለት ባለስልጣናት ዐሥራ ሰባቱን ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ሳያማክሩ መቀየራቸው ገና ከጅማሮው የቦርዱን ተዓማኒነት ጥያቄ ውስጥ ጥሎ ነበር፡፡

ምርጫው በታህሳስ 27 ቀን 2007 ተካሂዶ በማግስቱ ከምርጫ ጣቢያ የሚመጡ ሪፖርቶች የራይላን አሸናፊነት የሚያበስሩ መሆናቸውን ተከትሎ የራይላ ፓርቲ በታኅሳስ 29 አሸናፊነታቸውን በይፋ አበሰረ፡፡ ይሁን እንጂ በዛው ቀን የሚመጡ የምርጫ ውጤቶች የተገላቢጦሽ ሆነው የኪባኪን የበላይነት የሚያሳዩ ሆኑ፡፡ ዘጠና ከመቶ ከተቆጠሩ የምርጫ ጣቢያዎች ከ120ዎቹ 180ዎቹን ኪባኪ እንደሚመሩ ይገልፅ ነበር፡፡

በታኅሳስ 30 ራይላ በጋዜጣዊ መግለጫ ውጤቱን እንደማይቀበሉና እንደተጭበረበሩ እንዲሁም ኪባኪ ሽንፈትን አምነው መንበራቸውን እንዲለቁ ቢጠይቁም ምርጫ ቦርዱ ግን የኪባኪ አሸናፊነትን አወጀ፡፡ ኪባኪም የሕዝብን ድምፅ እናከብራለን ሲሉ በዛው ቀን የፕሬዝዳንትነት ቃለ መሃላ ፈፀሙ፡፡ መንግሥት በሚያስተዳድረው የቴሌቭዥን ጣቢያ ማሸነፋቸው ተነግሮላቸው ቃለ መሃላ የፈፅሙትን ሞዋይ ኪባኪን በመቃወም በርካታ የብርቱካናማ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ደጋፊዎች የተቃውሞ ሰልፍ ወጡ፡፡ ተቃውሞው በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ኀሳ ግጭት ተቀየረ፡፡

የንያንዛ ክልል፣ ናሮክ፣ ናይቫሻ እና ናይሮቢ ግጭቱ የተባባሰባቸው ቦታዎች ነበሩ፡፡ በኤልዶሬት ከተማ በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ በተነሳ ግጭት ብቻ 30 ሰዎች ሲሞቱ በአጠቃለይ ቁጥራቸው አንድ ሺሕ ሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ ንፁኃን ዜጎች ምርጫውን ተከትሎ በተነሳው ግጭት ሕይወታቸውን አጥተዋል፣ 350 ሺህ ዜጎች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል፣ 80 በመቶ የሃገሪቱ የቱሪዝም ገቢ ሲቀንስ መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ዋጋም በእጥፍ ንሮ ነበር፡፡

እንደብዙ የአፋሪካ አገሮች የኬኒያ መራጮች ድምፃቸውን የሚሰጡት በጎሳ፣ በዘር ሃረግ እንዲሁም በዝምድና ከመሆኑም ባሻገር የፖለቲካ ፓርቲዎችም አመሠራረታቸው ጎሳን ተንተርሰው ነው፡፡ ኩኩዩ የተባለውን ጎሳ በመወከል የመጀመሪያው የኬኒያ ፕሬዝዳንት ጆሞ ኬኒያታ እና ሦስተኛው ፕሬዝደንት ሞዋይ ኪባኪ በድምሩ ለ25 ዓመታት ኬኒያን መርተዋል፡፡ ሚች ፕሬዝዳንት ጆሞ ኬኒያታን በመተካት ፕሬዝዳንት የሆኑት በአምባገነንነት የሚታሙት ዳንኤል አራፍ ሞይ ካለንጂን ጎሳ በመወከል ለ24 ዓመታት ኬኒያን መርተዋል፡፡

የ2007 ምርጫ ውጤት በኬኒያ የነፃነት ታሪክ ለ44 ዓመታት መንበረ ሥልጣኑን ያልተጋሩት የሃገሪቱን 13 በመቶ የሕዝብ ቁጥር የሚወክሉት ሉዎ ጎሳ አባላት ከእጃቸው ተመንተፎ እንዳመለጣቸው ነበር የተሰማቸው። በቀድሞው የተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ ኮፊ አናን አደራዳሪነት የ2007 ምርጫ ከተካሄደ ከሁለት ወር በኋላ ሥልጣን ለመጋራት ኪባኪና ራይላ ተስማሙ። የመንግሥትን ሥራዎች ማስተባበርና መቆጣጠር ኃላፊነት ያለው አዲስ የጠቅላይ ሚኒስተርነት ማዕረግ ለተቃዋሚው ራይላ ተሰጣቸው። ከሥራቸው ሁለት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስተርነት ማዕረግ ያላቸው ከሁለቱ ተፎካካሪ ፓርቲዎች እንዲሆኑ ሲደረግ የኪባኪን ፓርቲ በመወከል ኡሁሩ ሲመረጡ የራይላን ፓርቲ በመወከል ሙዳቫዲ ተመርጠው ወደ ሥራ ገብተዋል።

## ዓለም አቀፍ የወንጀል ችሎት (አይ.ሲ.ሲ.)

በንፅፅር በወጣትነታቸው የፕሬዝዳንትነት ማዕረግ በማግኘት ወደ ቤተመንግስት የሚገቡት ኡሁሩ ኬኒያታ፣ በኬኒያ ከሚገኙ ቱጃሮች መካከል ቁጥር አንድ ስለመሆናቸው ፎርብስ መጽሔት ያትታል። ገና ከ29 ዓመት ዕድሜያቸው ጀምሮ  የጡት አባታቸው የቀድሞው ፕሬዝዳንት ዳንኤል አራፕ ሞይ ወደ ሥልጣን እንዲመጡ ያለማምዷቸው የነበረ ቢሆንም  በ2002 ምርጫ "የቤተመንግሥት ፕሮጀክት" የሚል ቅፅል ስም ያተርፉ እንጂ በምርጫው አሸናፊ የሆኑት ኪባኪ ነበሩ።

በ2007 ምርጫ ኡሁሩ ኬኒያታ ከኪባኪ ጎን የቆሙ ሲሆን ምርጫውን ተከትሎ የመጣው ግጭት ግን ዘላቂ እርግማን እና ምርቃትን በአንድ ላይ ይዞላቸው መጥቷል። በግጭቱ ወቅት አንድን ጎሳ ከሌላው ጋር በማጋጨት፣ ግጭቱን በማሴር እና በማባባስ ወንጀል ተከስው ፍርዳቸውን እየተጠባበቁ የሚገኙት ኡሁሩ በዘንድሮው ምርጫ ወቅት ዓለማቀፉ የወንጀል ችሎት ጥቁር አፍሪካውያን ላይ ብቻ የተነጣጠረ ሴራ ነው በማለት ሕዝባቸው ለሃገር ሉዓላዊነት እንዲነሱ እና ከእጅ አዙር ቀኝ ግዛት እንዲላቀቁ፣ ኬኒያ ነፃ አገር ናት በማለት በምርጫው የተከሰሱበትን ወንጀል ወደጎን በመተው ይባስ ብለው ለራሳቸው ጥቅም ለምርጫ ቅስቀሳ ፍጆታ አውለው የፖለቲካ ትርፍ አግኝተውበታል።

የውጪ ኃይሎች ለሚያሳርፉብን ጫና አንበረከከም ብለው በተደጋጋሚ በምርጫ ቅስቀሳ ውቅት ይናገሩ የነበሩት ኡሁሩ ሃገራዊ አንድነት ስሜትን በመፍጠር በተቃራኒው ራይላን ለውጪ ኃይሎች ሃገሪቷን አሳልፎ የሰጠ የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርሰ ቅስቀሳቸው ውጤት አስገኝቶላቸዋል።

የዓለማቀፉ የጦር ወንጀል ችሎት ተከሳሽ ኡሁሩ ወደ ምርጫ ሲገቡ ለምክትል ፕሬዝዳንትነት እጩ ያደረጓቸው ዊሊያም ሩቶ እንደእርሳቸው በችሎቱ ተከሳሽ ናቸው። የግብርና ሚኒስቴር በነበሩበት ወቅት የግለሰቦችን መሬት በመዝረፍ፣ በሙስና የተከሰሱት ሩቶ ሥልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት ተደጋጋሚ ችግሮች በዙሪያቸው ቢያንዣብብም በዚህ ዓመት በተደረገው ምርጫ ግን የኬኒያ ሕዝብ ዳግም ድምፅ አልነፈጋቸውም።

በኬኒያ ምርጫ ለማሸነፍ የኩኩዩ ጎሳ አባል መሆን ወይም የኩኩዩዎችን ድምፅ በዋንኛነት መበተን አሊያም የኩኩዩ ጎሳን ተንተርሰው ከተመሠረቱ ፓርቲዎች ጋር ኅብረት መፍጠር እንደሚያስፈልግ የሚነገር ቢሆንም ራይላ ይህንን ማድረግ ባለመቻላቸው አሳዛኝ ተሸናፊ በመሆን የኬንያ ፕሬዝዳንት የመሆን ተስፋቸው ለመጨረሻ ጊዜ ከሽፏል።

## የተሻሻለው ሕገ መንግሥት

ሁለተኛው የኬኒያ ሕገ መንግሥት እ.ኤ.አ በነሐሴ ወር 2010 ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን የመጀመሪያው ሕገ መንግሥት በ1969 ከነጻነት በኋላ ነበር የወጣው። በአዲሱ ሕገ መንግሥት በዋንኛነት ሕግ አስፈፃሚው፣ አውጪውና አስተርጓሚው አካላት እንዲለያዩ ወስኗል። መንግሥት በክልልና በብሔራዊ ደረጃ እንዲዋቀር ሆኖ፣ የብሔራዊ መንግሥት የክልሎች ኃብት ስብጥር ዕኩል በኩል እንዲያደርግ ደንግጓል። በሁሉም የመንግሥት ክፍሎች የሚሳተፉ አካላት በሹመት ሳይሆን በብቃት መሆን እንዳለበት ያስቀመጠው አዲሱ ሕገ መንግሥት የጾታ መድሎን ከማስቀረቱም ባሻገር የኬኒያ ዜጎች የሌላ ሃገር ዜግነት ደርበው መያዝ እንደሚችሉ አስቀምጧል።

የ1969ኙ ሕገ መንግሥት ለፕሬዝዳንቱ የሰጠውን መጠነ ሰፊ ሥልጣን በመገደብ፤ በመንግሥት አስፈፃሚ አካልና ሕግ ተርጓሚ አካል መካከል ልዩነት እንዲኖር ያደረገው አዲሱ ሕገ መንግሥት፣ መንግሥት ለሚፈፅማቸው ማናቸውም ጥፋቶች ተጠያቂነት እንዲኖር ሕጋዊ መሠረትን አስቀምጧል። ክልሎች እራሳቸውን በራሳቸው

የማስተዳደር መብት እንዲኖራቸው የሚያዘው አዲሱ ሕገ መንግሥት፣ አዲስ በተቋቋመ የመሬት ኮምሽን በኩል የመሬት የይገባኛል ጥያቄ ያለቸው ዜጎች ምላሽ እንዲያገኙ ፈቅዶ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰብኣዊ መብቶች የማይደፈሩ እና የማይገረሰሱ መሆናቸውን ደንግጓል፡፡

## የ2013 ምርጫ አሰላለፍ (ኬንያታ-ሩቶ/ ሙዳቪዲ/ ራይላ)

በ2007 ምርጫ የብርቱካናማ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ በመወከል ወደ ፕሬዝዳንትነት መንበር ለመምጣት ያለሙት የያኔው የፓርቲው ጸሐፊ የዛሬው ተመራጭ ምክትል ፕሬዝዳንት ዊሊያም ሩቶ፣ በወቅቱ ከፓርቲው ምርጫ በራይላ እና በሙሳሊያ ሙዳቫዲ የተሸነፉ ቢሆንም የፓርላማ አባል ከመሆን ግን ማንም አላስቀራቸውም፡፡
በኦሬንጅ ፓርቲ ትኬት የፓርላማ አባልነትን ያገኙት ሩቶ በ2007 ራይላ ፕሬዝዳንት እንዲሆኑ ድጋፍ የቸሩ ሲሆን ብዙም ሳይቆይ የምርጫውን ውጤት ተከትሎ በተነሳው የርስ በርስ ግጭት፣ የኪባኪ ደጋፊዎች ላይ ጥቃት በማድረስ፣ግጭቱን በማቀናበርና በማባባስ በዓለም አቀፉ ወንጀል ችሎት ተከሰዋል፡፡

የአሁኑ ተመራጭ ምክትል ፕሬዝዳንት  ከኡሁሩ  ኬኒያታ ጋር በጋራ አብረው ወደ ቤተመንግሥት ለመግባት ተስማምተው መሥራት የጀመሩት በ2012 ሁለቱም በዓለም አቀፉ የወንጀል ችሎት ክስ ከተመሰረተባቸው በኋላ ሲሆን በ2007 ምርጫ ሁለቱም በተቃራኒ አቅጣጫ የነበሩ ቢሆንም ክሱ "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ"  እንዲሉ፣ አብረው እዲሠሩ መንገድ ከፍቶላቸዋል፡፡

በሌላ በኩል በዘንድሮው ምርጫ ለራይላ መሸነፍ አስተዋፅኦ እንዳደረጉ ከሚጠቀሱት መካከል ሙሳይላ ሙዳቫዲ ናቸው፡፡ በኦሬንጅ ዲሞክራቲክ ሙቭመንት ፓርቲ ውስጥ አምባገነንነት ሰፍኗል፣ ከራይላ በቀር ፓርቲውን በመወከል ፕሬዝዳንት ለመሆን ማንም እንዳይሳተፍ ሆን ተብሎ ሴራ ይፈፀማል፣ ለዚህም ተጠያቂው ራይላ ራሳቸው ናቸው በማለት ገና የፓርቲው የውስጥ ምርጫ ሳይካሄድ ፓርቲውን ለቀው የወጡት ሙዳቫዲ፣ ራይላ በምዕራብ ኬኒያ ያላቸው ድጋፍ እንዲሸነሸን አስተዋፅኦ  እንደዳደረጉ ይነገራል፡፡

በተቃራኒው የኪኒያ ምርጫ ከጎሳ ምርጫ  እንደማይለይ የተረዱት ሙዳቫዲ ዩናይትድ ዲሞክራቲክ ፍሮንት ፓርቲን ወክለው  በዘንድሮው ምርጫ ለፕሬዝዳንትነት ሲወዳደሩ በምክትል ፕሬዝዳንትነት የኩኩዩ ጎሳ አባል የሆነውን ጀርሚያ ኮኒን የመረጡ ሲሆን  በምርጫው ግን ስኬት ከእርሳቸው ጋር አልነበረችም፡፡ እንዳውም በብዙ የማኅበረሰብ አውታሮች ኮኒ እንኳን በምርጫው መዳቫዲን ሳይሆን ኬኒያታን ነው የመረጡት ሲሉ መቀለጃ አድርገዋቸዋል፡፡

## ሦስቱ አሸናፊዎች

ኡሁሩ - እ.ኤ.አ ማርች 4 ቀን 2013 የተካሄደውን ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ በማሸነፍ ቀጣዩ የኬንያ ፕሬዝዳንት እንደሚሆኑ የምርጫ እና የድንበር ማካለል ኮሚሽኑ እና የኬንያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መስክረውላቸዋል፡፡ ለሚቀጥሉት 5 ዓመታትም ኬንያን በፕሬዝዳንትነት ለማገልገል መሃላ ይፈፅማሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡
ራይላ- ተሰናባቹ ጠቅላይ ሚኒስትር ከአርቃቂዎቹ አንዱ ሆነው ያስፀደቁት አዲሱ የኬንያ ሕገ መንግሥት ለሀገሪቱ ፕሬዝዳንትነት ለመወዳደር ባስቀመጠው የዕድሜ ገደብ መሠረት ከአሁን በኋላ ለፕሬዝዳንትነት መወዳደር አይችሉም፡፡ እ.አ.አ በ2007 (በኪባኪ) እና በ2013 (በኬንያታ) በተደረጉት ሁለት ተከታታይ ምርጫዎች ተሸንፈዋል፡፡ የማርች 4ቱን ምርጫ እና ያቀረቡትን ቅሬታ ተከትሎ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ እደሚያከብሩ እንዲሁም ለተመራጩ ፕሬዝዳንት መልካም ምኞታቸውን በይፋ ማሳወቃቸው ግን የዲሞክራሲ አሸናፊ ያደርጋቸዋል፡፡

ሞዋይ ኪባኪ -  በኬኒያ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የኢኮኖሚ እምርታ እንዳስገኙ የሚነገርላቸው ተሰናባቹ ፕሬዝዳንት፣ ሕገ መንግሥቱ ለፕሬዝዳንትነት ያስቀመጠውን የሁለት 5 ዓመት አገልግሎት ዘመን ገደብ አክብረው፣ ሕገ መንግሥቱን ላሻሽል የሚል የተለመደ የአፍሪካ መሪዎች ሁካታ ሳይፈጥሩ እሳቸው ያልተወዳደሩበት ምርጫ እንዲካሄድ በማድረግ ለብዙ አፍሪካዊያን መሪዎች ምሳሌ አስቀምጠዋል፡፡ በተጨማሪም በጎሳ ፖለቲካ የተተበተቡትን የመንግሥት ተቋማት ታማኝነት እንዲያንሰራራ ቢያንስ የመጀመሪያውን እርምጃ የተራመዱ መሪ ሆነው አልፈዋል፡፡

ከሁሉም በላይ የነጻ ምርጫው ባለቤት - የኬንያ ሕዝብ ነው ትልቁ አሸናፊ፡፡ ኬንያም እንደሀገር ለዲሞክራሲ መዳበር እና ለዲሞክራሲያዊ ተቋማት መጠናከር በአጠቃላይ ለአፍሪቃ በተለይም ደግሞ ለአፍሪቃ ቀንድ ሀገራት መማርያ መሆን የምትችልበት ደረጃ ላይ መድረሷን አስመስክራለች፡፡

## የኬኒያ እና የኢትዮጵያ ምርጫ ምንና ምን?

ኬኒያ ነጻነቷን ከተቀናጀች በተያዘው ዓመት 2013 ኃምሳ ዓመት የሚሞላት ሲሆን በኃምሳ ዓመት ጊዜ ውስጥ አራት ፕሬዝዳንቶችን ቀያይራለች፡፡ ጆሞ ኬኒያታ በሞት ከስልጣን ሲሰናበቱ፣ ሞይና ኪባኪ የስልጣን ጊዜ ገደባቸውን ጨርሰው ለተተኪ ያስረከቡ ናቸው፡፡ በአንፃሩ ኢትዮጵያ ባለፉት ኃምሳ ዓመታት ውስጥ አራት መሪዎችን ስታፈራርቅ ፣ አፄ ኃይለ ሥላሴ እና መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በግድ ከስልጣናቸው ሲሰናበቱ፣ የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር መለስም ሞት ከስልጣን ለይቷቸዋል፡፡ የአሁኑ ጠ/ሚ ኃይለማሪያምንም የሚተካቸው ከራሳቸው ፓርቲ ይሁንታ አግኝቶ ይመጣ እንደሆን እንጂ በነጻና ፍትሐዊ ምርጫ አሸንፎ እንደሚመጣ ማሳያ ምንም ተስፋ የለም፡፡

የኬኒያ ዲሞክራሲ ባለፉት ኃምሳ ዓመታት በበርካታ ፈተናዎች ተፈትኖ፣ እየነጠረ ችግሮችን እየቀረፈ ስለመሄዱ የዘንድሮው ምርጫ ማረጋገጫ ሲሆን ለዚህ ደግሞ መገናኛ ብዙኃን የማይተካ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ከምርጫ በፊት፣ በምርጫው ወቅትና ከምርጫው በኋላ የኬኒያ መገናኛ ብዙኃን የተለያዩ መረጃዎችን ለዜጎች በማድረስ ለዲሞክራሲያዊ ሒደቱ ኃላፊነታቸውን በሚገባ በመወጣታቸው ተወድሰዋል፡፡ በተቃራኒው የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ዕድገታቸው ቁልቁል እንደ ካሮት ሆኖ ዛሬ ላይ ጠፍተው አማራጭ ሐሳቦች የማይስተናገዱበት ደረጃ ላይ እየደረስን ነው፡፡

ገለልተኛው የኬኒያ ምርጫ ቦርድ በተለይ በዘንድሮው ምርጫ ከምንግዜውም በላይ ዜጎች በምርጫው አመኔታ እንዲያድርባቸው አስችሏል፡፡ በተገላቢጦሽ ታላቅ አቅም እንዳለው በታዛቢዎች የተነገረለት የኢትዮጵያው ምርጫ ቦርድ፣ አቅሙን በመጠቀም በዘረጋቸው የምርጫ መዋቅሮች ይበልጥ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ምርጫን እንዲሸሹ አደረገ እንጂ ነጻ እና ፍትሐዊ ምርጫን ማከናወን አልቻለም፡፡ በሕዝብም ዘንድ ያለው ታማኝነትም ኢትዮጵያ ውስጥ ሳለው በተቋማት አለመተማመን በምሳሌነት ሊቀርብ የሚችል ነው፡፡

በኬኒያ ምርጫ የሕዝብ ተሳትፎ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጨምሮ ፉክክሩ አንገት ለአንገት ደርሶ የዓለምን ሕዝብ በአንድ ላይ ልብ ሲሰቅል፣ ብዙዎች በአገሪቱ የእርስ በእርስ ብጥብጥ ይነሳል ብለው ቢገምቱም የሆነው ግን እንደዛ አልነበረም፡፡ በተለይ ራይላ ኦዲንጋ መሸነፋቸውን በፍርድ ቤት እንደሚሞግቱ ሲናገሩ አገሪቷ በጎሳ ግጭት ትናጣለች ብሎ ያልገመተ አልነበረም፡፡ ራይላ ግን የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተቀብለው ኬኒያ ከሁሉም እንደምትበልጥ ለዓለም ሲያበስሩ የኬኒያ ፍርድ ቤት ገለልተኛ አቋም እንዳለው ጭምር ዓለም እንዲያውቅ አድርገዋል፡፡ ይህንን መሰል ክስተት በኢትዮጵያ ለማየት የ1997 ምርጫን ተከትሎ ወደእስር ቤት የገቡ መሪዎችን እና የፍርድ ውሳኔን ያስታውሷል፡፡

------

*በዚህ ጽሑፍ ሙሉ ስማቸው ካልተጠቀሰ በስተቀር ኬንያታ ማለት ጆሞ ኬንያታ ለማለት ነው፡፡ ልጅየውን መጥቀስ ስንፈልግ ኡሁሩን ተጠቅመናል፡፡

**በተመሳሳይ ኦዲንጋ ማለት ኦጊንጋ ኦዲንጋ ማለት ሲሆን ልጃቸው ራይላ በሚል ተጠቅሰዋል፡፡

# የውኃ-ፖለቲካ እና የአባይ ጉዳዮች፡ ወፍ በረር ቅኝት

በዘሪሁን አበበ ይግዛው

## እንደ መነሻ

ባለቅኔ እና ጸሐፌ-ተውኔት ጸጋዮ ገብረመድህን ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ ባሳተመው የግጥም ካሴት አዋሽ ለሚለው ግጥሙ መግቢያ ማብራሪያ ሲሰጥ… "በማናቸውም የዓለም ህዝብ ባህል ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የየአገሩ ወንዝ ጉዞ በተለይ የታላላቅ ወንዞች ጉዞ፤ የየአገሩ የሰፊው ህዝብ ጉዞ፤ የየትውልዱ ጉዞ ተምሳሌት ሆኖ ይቀረባል።" ይለናል። በርግጥ የእያንዳንዱ ሀገር ወንዝ የእያንዳንዱን ህዝብ ጉዞ ታሪክ ይናገራል። እውነት ነው ከዶን በራይን እና በቴምስ እስከ ዳኑብ በአውሮጳ፣ ከዮርዳስ እስከ ኤፍራጠስ እና ጢግሮስ በመካከለኛው ምስራቅ፣ ከኮሎራዶ እስከ ሚሲሲፒ በሰሜን አሜሪካ፣ አማዞን በደቡብ አሜሪካ፣ ኢንደስ-ጋንጅስ በህንድ፣ ፓኪስታንና ባንግላዴሽ፣ ያንገቲዝ በቻይና፣ እንዲሁም ጉዳያችን የሆነው አባይ በአፍሪካ ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ ወንዞች የሚያልፉባቸውን የሚያገናኟቸውን ህዝቦች እና ሀገሮች ስናይ ከወንዙ ጋር የሚያቆራኛቸው እጅግ በጣም አያሌ ምክንያቶች አሉ። ምክንያቱም እነዚህ ወንዞች ህይወትን፣ ስልጣኔን እና ማንነትን ገንብተዋልና። እርግጥ ነው ኤፍራጠስ የሚባል ከገነት የሚፈስ ወንዝ ባይኖር የአሲሪያም ሆነ ሞሶፖታሚያ ወይም የባቢሎን ስልጣኔ ባልኖረ፤ እርግጥ ነው አባይ የሚባል ህይውትን ያዘለ ከኤደን የሚመነጭ ወንዝ ባይኖር ግብጽ የሚባል ሀገርም ሆነ ህዝብ ባልኖረ። ወንዞች የሀገራት ስልጣኔ መሰረቶች እና ማማዎች ናቸው። ምንም እንኳን በአካባቢ ጥናት-ጅኦግራፊ እይታ ወንዞች አንድ ወጥ የሆኑ ስነ-ምድራዊ ክስተቶች ቢሆኑም በዘመናት በሰው ልጆች በተፈጠሩት ወሰኖች እና ድንበሮች መሰረት ወንዞች ከተፈጥሯቸው በተለየ ፖለቲካዊ ሆነው እናገኛቸዋለን። እነዚህንም ወንዞች ወሰን ተሻጋሪ ብለን እንጠራቸዋልን።

## ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች ለግጭት ወይስ ለትብብር?

ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች በተፍጥሯቸው የሀገራትን ወሰን አያውቁም። ነገር ግን ባያውቁም ለአገራት እና ህዝቦች ካላቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማኀበራዊ እና ባህላዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ጥቅም አኳያ በአገራት የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና ውጭ ጉዳይ ፖሊስ ዋና አካል ይሆናሉ። በዚህም ምክንያት የአስኳላው ዓለም በእንደዚህ አይነት ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች ባህሪ ላይ ጫፍ እና ጫፍ የቆመ አቋም አላቸው። አንዳንዶቹ ለግጭት እና ለጦርነት መሰረቶች፣ መሳሪያዎች እና ምክንያቶች ናቸው ሲሉ (ለምሳሌ ግሌክ፣ ክሌር) ሌሎቹ እንደ አሮን ወለፍ እና መሰሎቹ ደግሞ ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች በአገራት መካከል ግጭት መቀነሻ እና የትብብር እና አንድነት ማቀጣጠያ መሰረቶች ናቸው ይላሉ። ዋናው ነገር ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች የግጭት ምንጭ/ምክንያት እንዲሁም የትብብር መሰረት ሊሆኑ ይችላሉ። ዋናው እና ትልቁ ነገር በአገራት መካከል ያለ ታሪካዊ ግንኙነት፣ የአቅም ሚዛን፣ የኢኮኖሚ እድገት፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ/ሃይማኖታዊ መስተጋብሮች  እንዲሁም የአገዛዝ ዓይነቶች እና የመንግስታት ባህሪ ዋና ዋና ጉዳዮች እና ተጽእኖ አሳዳሪ ነገሮች ናቸው። ከዚህ አንጻር ወሰን ተሻጋሪ ወንዞችን ስንመረምር ኤፍራጠስ-ጢግሮስ፣ ዮርዳኖስ እንዲሁም አባይ/ናይል ከትብብር ይልቅ ለግጭት ቅርቦች ናቸው።

## አባይ-ናይል

እንደ አባይ-ናይል ተፋሰስ እጅግ በጣም መራራ ጦርነቶችን ያስተናገደ አለ ለማለት እቸገራለሁ። ጦርነቶች ይካሂያዳሉ። ባህርያቸውም አይቀየርም ምክንያታቸው እና አድራጊያቸው ይለያይ እንጅ። የአባይ ተፋሰስ የጦርነት ማስተናገድ ልዩ የሚሆነው ምክንያት ግን እራሱ አባይ የጦርነቱ ምክንያት መሆኑ ነው። ከታሪክ ማህደር እንደምንረዳው ከ1832 እስከ 1876 ድረስ ብቻ እንኳን በኢትዮጵያ እና በግብጽ መካከል 16 ታላላቅ ጦርነቶች ተካሂደዋል። በሁሉም ጦርነቶች አሸናፊዋ ግን ተወራሪዋ ኢትዮጵያ ነበረች። ግብጽ ሱዳንንም ወርራ ነበር። በኬዲቭ እስማኤል ጊዜም የነጭ ናይል ተፋሰስ አገራትን ለመውረር እጅግ በጣም ጉገቱ ነበራት። አንድም በኢትዮጵያ መሸነፏ ሁለትም የቅኝ ግዛት በአፍሪካ መስፋፋት ይህ እንዳይሆን ምክንያት ሆነ።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን ያለው የተፋሰሱ አገራት ግንኙነትም በውጥረት የተሞላ እና በግጭት የታጀበ ነበር። በግብጽ እና በሱዳን የተከወነው እና በኢትዮጵያና በሌሎች የላይኛው ተፋሰስ አገራት ዘንድ ተቀባይነት የሌለው የ1959 ስምምነት ከመፈረሙ በፊት ሁለቱ ተፈራራሚ የግርጌ አገራት ወደ ጦርነት ሊያመሩ ነበር። ሆኖም ግን ለግብጽ ኀደኛ የሆነ መንግስት በመፈንቅለ መንግስት አማካኝነት ወደ ስልጣን በመምጣቱ ፊርማዉ ሊከናወን ችሏል።

በግብጽና በሌሎቹ የላይኛው ተፋሰስ አገራትም ግንኙነቱ ሸካራ ነበር። በተለይ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነቱ ሙሉ በሙሉ የግጭት ነበር። የመልክዓ-ምድራዊ ርቀት ገድቦን ተነፈስን እንጂ ሁሉቱ አገራት ጎረቤቶች ቢሆኑ ኖሮ ማለቂያ የሌለው የቀጥታ ጦርነትን በተመለከትን ነበር። ምስጋና ለርቀት። ይህ ርቀት ግን ኢ-ቀጥተኛ ጦርነትን በተለይም የውክልና ጦርነትን ሊያስቀር አልቻለም (ይህን በሰፊው ከስር እናየዋለን)።

ከነጭ አባይ አገራት ጋር በመጠኑ የትብብር ግንኙነት ለመጀመር የሞከረችው ግብጽ ሙከራዋ የራሷን ፍላጎት ለመጫን እንጅ ለተፋሰስ አቀፍ ልማት ባለመሆኑ ሙከራዎቹ በሙሉ ከሽፈዋል። ሀይድሮሜት፣ ኡንድጉ እና መሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። ሆኖም ግን እኤአ ከ1990ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ኢትዮጵያ በውሃ መጋራት/ክፍፍል ዙሪያ ካልሆነ በቀር በሌላ በምንም የትብብር መድረኮች አልሳተፍም በማለቷ እና ግብጽ በውሃ ለመደራዳር ፈቃደኝነት በማሳየቷ እንዲሁም በዓለምአቀፍ የለጋሽ አገራት ቡድን ግፊት አዲስ ምዕራፍ በናይል ተፋሰስ ተከፈተ። ይህም ሁሉን የተፋሰሱን አገራት ኤርትራን አይጨምርም የያዘ የውሃ መጋራት/ክፍፍል ድርድር እና የናይል ተፋሰስ ኢኒሼቲቭ /Nile Basin Initiative/NBI በ1999 እኤአ ተቋቋመ። ኢኒሼቲቩ በዋናነት የቴክኒክ ስራዎችን እየሰራ እንዲሁም የየአገራቱ ተደራዳሪዎች ውሃ መጋራትን/ክፍፍልን እየተደራደሩ እስከ 2007 ቀጠሉ። በመሐል ግን የላይኛው እና የታችኛው ተፋሰስ አገራትን ጫፍ ለጫፍ ያቆመ ክስተት ተፈጠረ።

## የናይል ወንዝ የትብብር ስምምነት ማዕቀፍ / Nile Basin Cooperative Framework Agreement/

የናይል ተፋሰስ አገራት በዚህ የስምምነት ማዕቀፍ ድርድር ወቅት በአንዱም በሌላውም ሲስማሙ ሲነታረኩም ለ10 ዓመታት ዘልቀዋል። በዋናነት የስምምነት ማዕቀፉ ይዘት የተፋሰሱ አገራት በናይል ወንዝ ላይ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና የሁሉም አገራት የውሃ ዋስትና በእኩል እንዲጠበቅ ነው። ይህም ሲሆን በአንድ አገር ላይ የሚከናወን የውሃ ልማት ስራ የሌላውን አገር የውሃ ዋስትና በጣም የሚጎዳ መሆን የለበትም ይላል የስምምነት ማዕቀፉ። በጥቅሉ ፍትሐዊ እና ምክኒያታዊ የውሃ መጋራት/ክፍፍል የዚህ ስምምነት አንኳር እና የማእዘን ድንጋይ ነው። ይህንም ለማሳካት የናይል ወንዝ ተፋሰስ ኮሚሽንን ማቋቋም የስምምነቱ ዋና ተግባር ነው። በርግጥ በሁሉም ማለት በሚቻል መልኩ የተፋሰሱ አገራት ከተስማሙ በኃላ በመሐል አንቀጽ 14ን በተመለከተ ግን ስምምነት አልነበረም። በመጀመሪያ ይህ አንቀጽ ያወራ የነበረው ስለ "ቀደምት ስምምነቶች" (previous agreements) ጉዳይ ነበር። እዚህ ላይ ልብ ልንል ይገባል። የናይል/አባይ ተፋሰስ በታሪኩ ሁሉንም የተፋሰሱን አገራት ያቀፍ ስምምነት አይቶ አያውቅም። አሉ ከተባሉ ያሉት በአንድ ወቅት አዲስ ነገር ጋዜጣ ላይ እንዳተትኩት የቅኝ ግዛት ውጤት የሆነው የ1929 ግብጽ-እንግሊዝ (እንግሊዝ ሱዳን በመወከል እንደ ቅኝ ገዥ) እና የ1959 ግብጽ-ሱዳን ስምምነቶች ናቸው። እነዚህ ደግሞ አይደለም የወንዙ የራስጌ አገራት በተለይ ኢትዮጵያ እየተቃወመቻቸው አይደለም ከዓለምአቀፍ ህግ አፈጣጠር እና አተገባበር አንጻር ስናያቸው ምንም አይነት የሞራልም ሆነ የህግ ገዥነት የላቸውም። ደግሞስ 86 በመቶ በላይ ውሃ የምታበረክተው አገር ያልተገኘችበት ስምምነት እንዴት በውሃ ተቀባይ አገራት ብቻ ተከውኖ ሁሉን ገዥ ስምምነት ይሆናል?

ወደ ጉዳያችን ስንመለስ አንቀጽ 14 ይህን ነባር ስምምነቶች የሚዳስስ የነበረ ቢሆንም በውል እንኳን በሳይንሱ ዓለም ያልዳበረ የውሃ ዋስትና(water security) በተሰኘ ጭንጋፍ ሃሳብ ተተካ። በመሆኑም የራስጌ እና የግርጌ አገራት በዚህ አንቀጽ 14 ንዑስ-አንቀጽ (ለ) መስማማት አቃታቸው። ኢትዮጵያ እና የነጭ አባይ አገራት(ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ቡሩንዲ፣ ሩዋንዳ፣ የኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣ ኡጋንዳ) አንቀጽ 14 ንዑስ-አንቀጽ (ለ) እንደሚከተለው ይነበብ በማለት ተስማሙ።

*"የማንኛውንም የናይል ተፋሰስ አገር የውሃ ዋስትና በጎላ መልኩ እንዳይጎዳ"*
በተቃራኒው ግብጽ ደግሞ እንደሚከተለው ይሁንልኝ አለች
*"የማንኛውንም የናይል ተፋሰስ አገር የውሃ ዋስትና እና የአሁን አጠቃቀም እና መብት በጎላ መልኩ እንዳይጎዳ"*

ግብጽ አሁን አለኝ የምትለው ውሃ እና መብት ለአስርት ዓመታት አገራቱ እንዲቀየር ሲደራደሩበት የነበረውን ስርዓት ሌሎቹን የተፋሰሱን አገራት ያገለለ እና ፍላጎታቸውን እንዲሁም ጥቅማቸውን ያላገናዘበ የ1959 ስምምነት ነው። ይህን ሃሳብም የ1959 ስምምነት ባለ እዳ ናትና ባትፈልገውም ሱዳን እንደ በቀቀን አስተጋባችው። ከዚህ እንደምንረዳው ግብጽ እና ሱዳን ይህን ጭንጋፍ ሃሳብ የውሃ ዋስትና ስምምነት ላይ በመሸንቆር የነበረው የዜሮ-ድምር ውጤት ባለመለዮ የናይል ተፋሰስን ስርዓት በጀርባ በር በኩል ለማስገባት ጣሩ። ስለዚህ ትግሉ እና ፍጭቱ ያለው አምባገነናዊ እና ኢፍትሐዊ የሆነ እንዲሁም ጥቂት አገራትን ብቻ በተለይም ግብጽን በሚጠቅም ስርዓት

እና ሁሉንም የተፋሰሱን አገራት እኩል የሚያከብር እንዲሁም እንደየድርሻቸው በእኩልነት ተጠቃሚ በሚያደርግ ስርዓት መካከል ነው፡፡ በዚህም ልዩነት ምክንያት ግብጽ እና ሱዳን በአንድ በኩል ኢትዮጵያ እና የነጭ አባይ አገራት ደግሞ በሌላ በኩል ተሰለፉ፡፡ ይህ የሆነው በ2007 ኡጋንዳ ላይ በተካሄደው የናይል ውሃ ሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ ነበር፡፡ ከዚህም በኋላ በተለያዩ የተፋሰሱ አገራት ከተሞች ስብሰባዎች ተካሄዱ፡፡ ግብጽ እና ሱዳን ግን የአባ ቢላዋ ልጅ ብለው ወይ ፍንክች አሉ፡፡ እንዲህ ከሆነማ ምን እንጠብቃለን በማለት የላይኛው ተፋሰስ አገራት (ኢትዮጵያ፣ ኡጋንዳ፣ ሩዋንዳ እና ታንዛኒያ) በግንቦት 4 ቀን 2010 እኤአ በኢንቴቤ ኡጋንዳ ተፈራረሙ፡፡ በኋላም በቀናት ልዩነት ኬንያ እንዲሁም ጥቂት ወራት በኋላ ቡሩንዲ ተቀላቀሉ፡፡ እንደ ስምምነት ማዕቀፉ ከሆነ 6 አገራት ስለፈረሙት ህግ ሊሆን የሚቀረው በየአገራቱ ህግ አውጭ አካላት/ፓርላማ ቀርቦ መጽደቅ ብቻ ነው፡፡ የኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክም ስምምነቱን እንደምትቀላቀል ይጠበቃል፡፡

## ግብጽ-ጉራ እና ጉራ

ግብጽ ከመሀመድ አሊ ጀምሮ እስከ ኬዲቭ እስማኤል ድረስ ባለው ጊዜ ብቻ ኢትዮጵያን ወርሮ በመያዝ ቅኝ ለማድረግ ብዙ ጥራለች፡፡ ቅጥረኛ ወታደሮችን ከአሜሪካ እና ከአውሮፓ ቀጥራ ተዋግታለች፡፡ በገዳሪፍም ገባች በአፋር፤ በጉንደትም መጣች በጉራ ግራ የሚያጋባ ሽንፈትን እየተጎነጩ ከመመለስ በቀር አማራጭ አልነበራትም፡፡ በ1875 እና 1876 የተደረገውን ዘመቻ ልዩ የሚያደርገው "ሁሉንም የአባይ ሸለቆ በአረንጓዴው የግብጽ ባንዴራ ስር ማዋል" በሚል መፈክር ታጅቦ በሙሉ አቅም የተደረገ መሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ጉራ (ይህ ጉራ ይጥበቅ) ጉራ ላይ ጉራ ሆኖ ቀርቷል፡፡ በአፄ ዮሐንስ መሪነት በራስ አሉላ አባ ነጋ  አዝማችነት ግብጽ የኢትዮጵውያን ሰይፍ የቀዳላትን ተጎንጭታ ተመልሳለች፡፡

አባይን በተመለከተ የግብጽ ኢትዮጵያ ፖሊስ የተቀረጸው በ1860ዎቹ መጨረሻ በ1870ዎቹ መጀመሪያ ነበር፡፡ ዋርነር ሙዚነገር በተሰኘ የስዊዝ ቅጥረኛ፡፡ ዋና የፖሊሲ ምክሩ ይህን ይመስላል፡፡ "ግብጽ የአባይ ውሃ ሳይጓደል እንዲደርሳት ከፈለገች አንድም ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ካልሆነም በሃይማኖትና በብሔር ክፍፍል የምትታመስ እንድትሆን ማድረግ አለባት፡፡" የዚህ ፖሊስ ቀራጺ ይሙት እንጅ ይህ ፖሊስ በጥሬ ነገሩ ሳይቀየር ስልቱን ብቻ እየቀያየረ አለ፡፡ ጉራ ላይ ያልተሳካላት ግብጽ ዛቻውን/ጉራውን እና የእጅ አዙር ውጊያውን/ የውክልና ጦርነትን ስራዬ ብላ ከያዘችው አምስት አስርት ዓመታ አለፉ፡፡

## የዊኪሊክሱ ጦማር ጉራ ወይስ . . .

ባፈው ሰሞን ወሬና "ሚስጢር" አሹላኪው ዊኪሊክስ ከአሜሪካው የደህንነት ድርጅት ስትራትፎር ሾልኮ እጄ የገባው የበየነ መረብ መልዕክት መሰረት ግብጽ በዲፕሎማሲያዊ መንገዶች የምፈልገውን በእነ ኢትዮጵያ ላይ ካልጫንኩ በሚሳኤልም፣ በኮማንዶም፣ በጀትም በመጠቀም በሰዓታት ልታጠቃን አንዳሰበች በሊባኖስ የሚኖሩ ዲፕሎማቷን ጠቅሶ ገልጾልናል፡፡ የግብፃውያን ከአባይ ጋር በተያያዘ ዋናው ችግራቸው በማስፈራራት እና ኃይል በመጠቀም የራሳቸው የሚያደርጉት ይመስላቸዋል፡፡ ይህም የሆነው በዋናነት የአባይ ወንዝ መነሻና ብዙውን ውሃ አበርካች የሆነችው ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ በጦርነት በመኖሯ እና አቅሟን የማጠናከር ጉዞዋ ያልተስተካከለ በመሆኑ ለውስጥ የደህንነት ጉዳዮች ትኩረት መስጠቷ ውሃውን እንዳትጠቀም እንቅፋት መሆኑ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ግብጽ ሱዳንን በመዛት ማስበርገግ መቻሏ እና ከካምፕ ዴቪድ ስምምነት በኋላ ከአሜሪካ የሚጎርፍላት ረብጣ ዶላር እና ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ልቧ እንዲያብጥ ስላደረገው ነው፡፡ ከላይ እንዳየነው የጦርነት ክዋኔ በዘመናት ይለያያል እንጅ ባህሪው ባለመለወጡ ምንም መሳሪያ ብታከማች ግብጽ በታሪኳ አትዮጵያን አንድም ጦርነት አሸነፍ አታውቅም፡፡  ከዚህ አንጻር ስንመለከተው በዊኪሊክስ በኩል የሾለከው ጦማር ተራ ወሬ ሊባል የሚችል ነው፡፡ ሆኖም ግን ስንገጣጥማቸው ሙሉ ትርጉም የሚሰጡን ክስተቶችን ስላየን ይህን ጦማር ማቅለል ዋጋ ሊያስከፍል ስለሚችል በአንክሮ መመልከት ተገቢ ነው፡፡ ምንአልባት ምንአልባት አንዳች ክፉ ነገር የህዳሴ ግድቡ ላይ ብታደርስ የማያቋርጥ የውሃ ጥማትን ለሚመጣው የግብጽ ትውልድ ትተዋለች፡፡ እጅግ በጣም ውስብስብ በሆነው መካከለኛው ምስራቅ ውስጥ እየኖረች የእስራኤል እና የአረቦች ጉዳይ ባልለየለት ሁኔታ እንዲህ አይነት እስጣ ገባ ውስጥ መግባት የሚበላው ራሷን ግብጽን ነውና፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዊኪሊክስ ይፋ ያደረገው መረጃ እንደሚያሳየው ግብጽ ኢትዮጵያን በሽርክ ለማጥቃት ኩርሲ በተባለች ዳርፉር ሱዳን ውስጥ በምትገኝ ቦታ የሚስጢራዊ ወታደራዊ ማዘዣ እያቋቋመች እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይህ ምን ያክል እውነት ነው? ወደፊት የምናየው ጉዳይ ይሆናል፡፡

## የዳርፉሯ ኩርሲ እና የእስራኤል ዱላ በያርሙክ-ሱዳን ለአባይ ምኑ ነው?

ባሳለፍነው ሳምንት ጆሯችንን ከነልቡ የሚይዙ ሁለት ዋናዋና ጉዳዮችን ሰምተናል፡፡ አንደኛው የእስራኤል በያርሙክ ካርቱም አቅራቢያ "የሱዳንን" የጦር መሳሪያ ፋብሪካ መምታቷ ነው፡፡ ይህ የጦር መሳሪያ ፋብሪካ በተገኘው መረጃ መሰረት ግብጽም ኢራንም በጋራ የሚሰሩበት ነው፡፡ የእስራኤል ይህን እርምጃ መውሰድ ወስዳ ከሆነ ሀማስ የሚያገኛቸውን የሮኬቶች ምንጭ ለማድረቅ ነው፡፡ በጎሪጥ የሚተያዩት ኢራን እና ግብጽን (በተለይ በአሁን ሰዓት) አንድ የሚያደርጋቸው አንድ ነገር ቢኖር የፍልስጤም-እስራኤል ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ሱዳን ጋር አብረው መስራታቸው አይደንቅም፡፡ ወደ ሐማስ የሚጎርፉ መሣሪያዎችን አመጣጥ ስንመለከት ኢራንን፣ ሱዳንን እና ግብጽን እናገኛለን፡፡ ከዚህ አንጻር የእስራኤል እርምጃ እንዲሁ አይደንቅም፡፡ የእኛ ጉዳይ የሚሆነው ግን ይህ የጦር መሣሪያ አብሮ ማምረት ነገን መሰረት ያደረገ ሊሆን ስለሚችል የማንቂያ ደወል ነው፡፡ እስራኤል ሆይ ስላነቃሽን እናመሰግናለን፡፡

ሁለተኛው ጄኔራል ኒኮላይ ማካሮቭ የተባሉ የሩሲያ ጦር ኃይሎች አዛዥ ለፕሬዝዳንታቸው ለቭላድሚር ፑቲን ባቀረቡት ሪፖርት መሰረት የግብጽ አየር ኃይል ተዋጊ ጄቶችን ኩርሲ ወደተሰኘችው ሚስጢራዊ ቦታ እያጓጓዘች እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ የአገራችን ሰው ሲተርት ያልተፈሳ አይሸትም ይላል፡፡ ከኩርሲ ጅኦግራፊያዊ አቀማመጥ አንጻር ግብጽ ይህን አላደረገችም ለማለት ይከብዳል፡፡ ሱዳንም ይህን ወታደራዊ አገልግሎት ሰጠች ለማለትም እንዲሁ፡፡ ምክንያቱም ለሱዳን እጅግ የሚበጃት ከግርጌ አገር ግብጽ ጋር ማበር ሳይሆን ከራስጌ አገር ኢትዮጵያ እና የነጭ አባይ ተፋሰስ አገራት ጋር መተባበር እና ለፍትሐዊ የውሃ መጋራት መስራት ነውና፡፡ ለግብጽም በእርግጥ የሚበጀው ይሄው ትብብር ነው፡፡ የሆነ ሆኖ አንዳንድ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን ባገኘ ብዬ በመካነድር የታገዘ የሳተላይት ምስሎችን ለማግኘት ያደረግሁት ጥረት አልተሳካም፡፡ በዚህ አጋጣሚ አጅግ ለረቀቀ ሳተላይት መሣሪያዎች ቅርበቱ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች ይህንን ነገር ቢያካፍሉን አይከፋም፡፡ (የቦታ ስም ኩርሲ ዳርፉር)

## የውክልና ጦርነት

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት በቀጥታ ውጊያ ላይ ሽንፈትን እንደጋቢ የተከናነበችው ግብጽ ኢትዮጵያን ለማንበርከክ የተከተለችው ሙዚንገር የነገራትን ስልት ነው፡፡ ኢትዮጵያን በእርስበርስ ውጊያ እና ፍጅት ደካማ ማድረግ፡፡ ሁሌም ኢትዮጵያን ለመውጋት ለተነሳ ቡድን ይሁን አገር የግብጽ ድጋፍ አለው፡፡ ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጋር ባደረገቻቸው ውጊያዎች በሙሉ ጦርነቱ በእጅ አዙር ከግብጽ ጋር ነበር፡፡ ሻዕቢያ፣ ጀብሃ እና መሰሎቻቸው እርዳታ ይቸራቸው የነበረው ከካይሮ ነበር፡፡ በርግጥ ሻዕቢያ የአረብ አሸከርነቱን አሁንም አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ የተባበሩት መንግስታት ጸጥታው ምክር ቤት በውሳኔ ቁጥር 1724/2006 እንዳሳሰበው የድሮው አል ኢትሀድ አል ኢስላሚያ የኋላው የኢስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት የአሁኑ አል ሸባብ በግብጽ ይረዱ እንደነበር ይፋ አድርጓል፡፡ ይህ የሚያሳየን ግብጽ ኢትዮጵያን ለሚያተራምስ ማንኛውም አካል ቀዳሽ እና አጉራሽ መሆኗን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ወደ ልማት ስራዎች ከመዞር ይልቅ እንዲህ አይነት ቁስሎችን ታሰታምማለች፣ አባይም ያለከልካይ ሲፈስ ይኖራል፡፡ የዚህ መንገድ አዋጭነት ያከተመ ይመስላል፡፡ የሆነ ሆኖ እንዲህ አይነት ከፍተቶችን ኢትዮጵያ የምትሞላው በመሳሪያ ሳይሆን የውስጥን ጉድፍ በማንሳት፣ የውስጥን ቀዳዳ በመሙላት ነው፡፡ በርግጥ በመሳሪያ መቀጣት ያለበት የውጭ ቅጥረኛ ካለ መቀጣት አለበት፡፡ ነገር ግን ዜጋ አኩርፎ የውጭ ቅጥረኛ ከመሆኑ በፊት የሚያስኮርፉትን ነገሮች ለይቶ እንዳያኮርፍ ማድረግ ብልህነት ነው፡፡

ከዚሁ የውክልና ጦርነት ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ በሶስት አቅጣጫዎች ፈተና ይበዛባታል፡፡ አንድም የግብጽ አሽከርነቱን ባስመሰከረው በኢሳያስ አፈወርቂ መንግስት በኩል ሲሆን ይህም እጅግ በጣም አደገኛው ነው፡፡ ሁለተኛው ሶማሊያ ነው፡፡ ሶማሊያ ሰላም እንዳያገኝ ከሚሰሩት አገራት መካከል ግብጽ አንዷ ናት፡፡ በ1990ዎቹ አጋማሽ ኢትዮጵያ የሶማሊያ አንጃዎችን ሶደሬ ላይ በመሰብሰብ ተስማምተው የራሳቸው መንግስት ቢያቋቁሙም ካይሮ ላይ በተደረገ ሌላ ስምምነት አዲሱ መንግስት ሊፈርስ ችሏል፡፡ አሁን ያለው ሁኔታ ከመጥፎ ይሻላል፣ ነቅቶ መጠበቅ ግን ሸጋ ነው፡፡ ሶስተኛው በደቡብ ሱዳን በኩል ሊመጣ የሚችል ነው፡፡ ይህ የሆነው በደቡብ ሱዳን ፍላጎት ሳይሆን ሀገሪቱ ካላት አቅም ማነስ አንፃር ድንበሯን መቆጣጠር የማትችል ደካማ መንግስት በመሆኗ ነው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ እነዚህን ሁነቶች መሰረት ያደረገ ፖሊሲ መቅረጽ ግድ ይላታል፡፡

### ሱዳን በሁለት ቢላ መብላት . . .ግራ መጋባት

ሱዳን እና ኢትዮጵያ ግንኙነታቸው በውጣ ውረድ የታጀበ ነው፡፡ አንዳንዴ ሰላም እና ፍቅር ሌላ ጊዜ ደግሞ በቁርሾ እና በግጭት የተሞላ ነው፡፡ ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በፊት ኢትዮጵያ እና ሱዳን ሸካራ የሚባል ግንኙነት ነበራቸው፡፡ ከጦርነቱ በኋላ ግን ሁለቱ አገራት በፍቅር ከንፈው አይተናል፡፡ ለዛ ይመስላል ኢትዮጵያ የሱዳኑ መሪ አል በሽር ላይ በዓለምአቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት የወጣባቸውን የእስር እዝ ያላከበረችው፡፡ ሱዳን በበኩሏ የህዳሴው ግድብ መጀመር ይፋ ከሆነበት ጊዜ እስከ አሁን ድረስ ጊዜ ምንም ዓይነት ተቃውሞ አላሰማችም፡፡ ከዚህ አልፎም ለግንባታ የሚውሉ የተለያዩ ማሽኖችን ለኢትዮጵያ አበርክታለች፡፡ ከዚሁ ባሻገር ደግሞ ግብጽና ሱዳን እጅግ በጣም በፍቅር የተሞላ ባይሆንም ወዳጅ የሚያስብል ግንኙነት አላቸው፡፡ በ1959 ስምምነትም ሱዳንን የግብጽ እስረኛ አድርጓታል፡፡ ከሙባረክ መንግስት ጋር የነበራቸው ግንኙነት ለዘብተኛ የሚባል ነበር፡፡ ሆኖም ግን አዲሱ የሞሐመድ ሙርሲ መንግስት ለሱዳን ያለውን ወገንተኝነት ለመግለጽ የተቻለውን ሁሉ እያደረገ ነው፡፡ በዚህ ዓመት በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ንግግር ያደረጉት የግብጹ መሪ ሱዳን ብዙ መሰዋዕትነትን ከፍላ ዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ችላ ብሏታል በማለት አጋርነታቸውን ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር ቢኖር የሱዳን እና አሁን ስልጣን ላይ ያለውን የግብጽ መንግስት አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ሁለቱም "አክራሪ" ኢስላማዊ መሆናቸው ነው፡፡ ሁሉም ሙስሊም ወንድማማቾች አሏቸው፡፡ ልዩነቱ የሱዳኑ በስውር መስራቱ ነው፡፡ የቀድሞው የሱዳን ጠቅላይ ሚኒስቴር ሀሰን አል ቱራቢ ዋናው የሱዳን ሙስሊም ወንድማማቾች መሪ መሆናቸው እና የለየላቸው ጸረ-ኢትዮጵያ መሆናቸው ነው፡፡ ከዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሌላው ጉዳይ የአል በሽር መንግስት ግብጽን ማንኛቸውንም ጥያቄ ተጠይቆ እምቢ ቢል የግብጽ መፈንቅለ መንግስት ሰለባ ሊሆን ስለሚችል መፍራቱ አይቀሬ ነው፡፡ ከዚሁ ባሻገርም የአረብ ነን ባይነት ስሜት ልባቸውን ወደ ግብጽ ይወስዳቸዋል፡፡ ሱዳኖች ከአባይ ውሃ ተጠቃሚነት አንጻር ግን ከላይኛው ተፋሰስ አገራት ጋር መተባበርንም ይፈልጋሉ፡፡ ግን እስረኞች ናቸው፡፡ እናም ሱዳን በሁለት ቢላ እየበላች ግራ ተጋብታ ትታያለች፡፡ የትኛውን ትመርጥ ይሆን? ጊዜ ይፈታዋል፡፡

### ደቡብ ሱዳን እንኳን ደህና መጣሽ!

በአጠቃለይ ለአምስት አስርት ዓመታት በሁለት ዙር በተካሄደ ጦርነት ደቡብ ሱዳን ራሷን ከካርቱም ካፋታች አንድ ዓመት ሆናት፡፡ የዚች ሀገር መፈጠር የአንዲት ሀገር መፈጠር ብቻ አይደለም ውጤቱ፡፡ እጅግ እየቆዩ የሚወጡ ብዙ ጉዳዮች አሉ አንድምታቸው ለምስራቅ እና ሰሜን አፍሪካ ጎላ ብሎ የሚታይ፡፡ የእለሚ ትሪያንግልን ጨምሮ አንዳንድ የደንበር ጉዳዮች ከጎረቤት አገራት ጋር ዋና ጉዳይ ነው፡፡ ትልቁ እና ከዚህ የበለጠው ጉዳይ ግን አባይ ላይ ሊመጣ የሚችለው አንደምታ ነው፡፡ የእስር ቤቱን ድባብ ያቅልልላቸውና የግብጽ የቀድሞ መሪ ሆስኒ ሙባረክ የራስጌ አገራት አዲሱን የአባይ ስምምነት ማፅቀፍ ሊፈራረሙት እንደሆነ ግልጽ ሲሆንላቸው ወደ አሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ ሁሴን ኦባማ 'የደቡብ ሱዳን የሪፈረንደም ሂደት ከተያዘለት ጊዜ ይዘገይ የሚል' የድረሱልኝ ጥሪ አስተላለፈው ነበር; አሜሪካም እንደማይሆን አሳሰበች እንጂ፡፡ ግብጽ ይህን ያደረገችው ደቡብ ሱዳን የራስጌ አገራትን እንደምትቀላቀል እርግጠኛ በመሆኗ ነው፡፡ ለደቡብ ሱዳን መጨቆን እና ፍትህ ማጣት የግብጽ አጅ ከፍተኛ ነበርና ቢለምኑም እሺ እንደማይባሉ ያውቁታል፡፡ የመጀመሪየው ጉዳይ የ1959 ስምምነት ጉዳይ ሲሆን ደቡብ ሱዳን ይህን ስምምነት ከሱዳን ጋር የምትጋራበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ ምክንያቱም ይህ ስምምነት በሚፈረምበት ጊዜ 'እኛ አኛ ንቅናቂ' ከካርቱም ጋር ለነፃነት እየተዋጋ ነበር፡፡ ሌላው ምክንያት ደግሞ የስምምነቱ ወራሽ ሀገር ሱዳን እንጅ ደቡብ ሱዳን አለመሆኗ ነው፡፡ ከዚህ ላይ ግብጾች ሁሌም እንደሚሉት የውሃ ስምምነቶች እንደ ድንበር ስምምነቶች ናቸው አዲስ አገራት የሚወርሷቸው ሊሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ደቡብ ሱዳን ይህን ስምምነት ልትቀበል የምትችልበት ምንም ዓይነት አስገዳጅ ምክንያት የለም፡፡ ለዚህም ይመስላል ወደ ነፃነት የወሰዳቸው እና ለ6 ዓመታት ስልጣን እና ሐብት አጋርቷቸው የነበረው የሰላም ስምምነት የውሃን ጉዳይ ሳይነካ ያለፈው፡፡ ያም ሆነ ይህ ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል የመወሰን ስልጣኑ የራሱ የደቡብ ሱዳን ነው፡፡ ዋናው ነገር ከአባይ ድርሻ የሚጠይቅ አዲስ አገር ተፈጥሯል፡፡ ይህም በላይኛው ተፋሰስ አገራት ዘንድ ደቡብ ሱዳን መጣሽ... እንኳን ደህና መጣሽ አስብሏል፡፡ ለታችኞቹ ተፋሰስ አገራት ግብጽ እና ሱዳን ግን ሌላ ፈተና እና መጥፎ ዜና ነው፡፡

## ኢትዮጵያ

የገነት ማስረሻን "ጭስ አልባው ነዳጅ-አባይ" የሚል ሙዚቃ ልብ ብሎ ላደመጠ ሰው የሚገራርሙ መልዕክቶችን ይዟል፡፡ ቁጭት፣ እልህ፣ የሀገር ፍቅርን እንዲሁም በተፋሰሱ አገራት መካከል የሚኖርን ትብብር እና ግጭት

ይተርካል፡፡ የውሃ ፖለቲካ ሀልዮትን በአጭሩ የሚተነትን ታላቅ ሙዚቃ ነው፡፡ (ይህን እና ሌሎች የአባይ ሙዚቃዎችን በተመለከተ አንድ ቀን እንመለስበት ይሆናል፡፡) ሆኖም ግን ይህን ሙዚቃ በመስማት አንድ ሰው የኢትዮጵያን አባይ ላይ ያላትን አቋም፤ ፖሊሲ እና ስልት/ስትራተጂ መገንዘብ ይችላል፡፡ የኢትዮጵያ አቋም ውሃውን በጋር በመጠበቅ በጋር እየተጠቀምን በጋራ እንበልጽግበት ነው፡፡ ለዚህም የትብብር ፖሊስ ስኬት መፍትሄ ስልቱ ራሱ ትብብር ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ትብብር አልቀበልም የሚል ካለ ኢትዮጵያ የአባይን ውሃ በማልማት የህዝቧን ኑሮ የማሻሻል ሙሉ መብት እና ግዴታ ስላለባት ከመጠቀም ወደ ኋላ አትልም፡፡ ያንንም እያደረገች ነው፤ ከጣና-በለስ እስከ ተከዜ፣ ከዲዴሳ እስከ ፊንጫ፣ እንዲሁም ህዳሴ ግድብ በመቀጠልም ከካራ ዶቢ በመንዳያ ቤኮ-አቦ እያለማች ነው፤ ልታለማም ነው፡፡ ይህንም ስታደርግ አገሪቱ በዋናነት መከላከልን መሰረት አድርጋ ነው፡፡ ግብጽ በየሌጋሽ አገራቱ ብድር እና እርዳታ ስታስከለክል በራስ ወጪን በመሸፈን (ጣና-በለስና ህዳሴን እንዲሁም ተከዜን ልብ ይሏል) ትልልቅ ፕሮጀክቶችን እየሰራች ነው፡፡ ሌላው አገሪቱ ተጠንቅቃ ደጋግማ አስባ የገባችበት ነገር ቢኖር ግብጽ ደጋግማ እንደምትለው ጦርነት ካማራት ምን ያክል ተዘጋጅተናል የሚለው ነው፡፡ ዋናው ነገር አጥርን ሳያጠብቁ እንዲህ አይነት ፕሮጄክት አይጀመርምና ወደ ዝርዝሩ አልገባም፡፡ ሆኖም ግን ሁለት ነገሮችን ማለት ያሻል፡፡ አንድ የኢትዮጵያን መንግስት በመሳሪያ ለመጣል እየታገሉ ያሉ ታጣቂዎችን መፍትሔ መፈለግ ጥሩ ነው፡፡ ሳያውቁትም ይሁን አውቀው የጠላት አሽከር መሆናቸው አይቀርምና፡፡ ከዚህ አንፃር ሰሜን እና ምዕራብ ኢትዮጵያ ላይ የሀገሪቱ ኃይል በተጠንቀቅ ሊቆም ይገባዋል፡፡ ሁለተኛ ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት ነዳጅ የምታስገባው በዋናነት ከሱዳን ነው፡፡ ይህ ነገር ምንን ይነግረናል ብለን ስንጠይቅ አሁንም የማንቂያው ደወል እያቃጨለ ነው፡፡ የጦርነትን ከበሮ ወዲያ ይጣልልን እና አሁንም ጦርነት ውስጥ ብንገባ እንዴት ነው የኃይል ፍላጎትን የምንሸፍነው? መመለስ ያለበት ጥያቄ ነው፡፡ አሁንም ባህሩን ባህሩን እንድንል ያደርገናል፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ሰዓት ከዚያ ባህር ላይ ውሃ እየጠጡ ያሉት ግመሎች ባለ አራት እግሮቹ ሳይሆኑ ባለ ሁለት እግሮቹ በዋናነት ግብጽ እና ኢራን ናቸውና፡፡ ፡፡

## ማጠቃለያ

የአባይን ጉዳይ እንዲህ ጀምሮ እንዲህ ማጠቃለል መመኮሩ ራሱን አባይን በጭልፋ እንደማለት ነው፡፡ ባይሆን ለዛሬው ወጋችን ገደብ እናበጅለት እንጂ፡፡ የአባይ ውሃ ለአገራቱ የትብብር መሰረት መሆን የሚችል ታላቅ የስልጣኔ መሰረት ነው፡፡ ሆኖም ግን በግርጌ አገራት ግትርነት በተለይ በግብጽ ግትርነት ምክንያት የፍትሐዊ የውሃ ክፍፍልና ትብብር ስርዓት ለጊዜው ቆሟል ማለት ይቻላል፡፡ ይህም አንዳንድ ምስሎችን ስንገጣጥም ትርጉም በሚሰጥ መልኩ በተፋሰሱ አገራት መካከል ግጭት ሊኖር እንደሚችል ይነግረናል፡፡ ያ ግጭት ቀጥተኛ ባይሆንም የእጅ አዙር/የውክልና ጦርነት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ በጊዜውም ሆነ ያለ ጊዜው የሚዘንበውን ዝናብ ለመከላከል ኢትዮጵያ ጠንካራ ዳስ መስራት አለባት ብዬ አምናለሁ፡፡ ምንጊዜም ቢሆን ጠንካራ ኢኮኖሚ እና ጦር ኃይል ሲኖር ጥቅሙ የትየለሌ ነው፡፡ እናም ዘገር ለሚነቀንቅ በሰዓቱ ዘገርን ማሳየት መብትም ግዴታም ነው፡፡ በተቻለ መጠን ግጭትን ለማስወገድ መጣር ደግ ነው፤ትብበርን ማስቀደም ለብዙሀኑ ጥቅም ነው፡፡ ትብብር አያሻንም የሚሉ ካሉ ግን ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርምና እኔም እንደ ገነት ማስረሻ እንዲህ አልኩ

***ፍሰስበት እና በሀገርህ ሜዳ***
***የሚቆጣን ካለ ያበጠው ይፈንዳ!!***

# የኢትዮጵያ የእግር ኳስ ቡድን የአዲስ ጉዞ ጅማሬ

**በኤርሚያስ አማረ**

ከዓለም የእግር ኳስ ካርታ ላይ ከጠፋን ሰነበትን፤ ከአጠቃላይ ሕዝቧ ከግማሽ የሚልቀው ወጣት በሆነባት ሀገርም ሰላሳ አንድ ዓመት ሩቅ ነው፡፡ አሁን ያለው ትውልድ የሀገሪቱ እግር ኳስ ትልቁ ማሰሪያ በሆነው ብሔራዊ ቡድን ላይ የሚያውቀው የአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎን ማሳካት እንደማይችል፤ ከሜዳው ውጪ ማሸነፍ ቀርቶበት በአነስተኛ ጎል ተሸንፎ መምጣት እንደሚሳነው እና አባላቱ ከሌሎች ሀገራት አቻዎቻቸው በሥነ ልቦና፣ በአካል ብቃት እና በቴክኒኩ ሰፊ ልዩነት እንዳላቸው ነበር፡፡

በአሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው እየተመራ በሃያ ዘጠነኛው የአፍሪካ ዋንጫ የተሳተፈው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በአዲሱ ትውልድ ጭንቅላት ውስጥ ያሉትን አስተሳሰቦች ሙሉ በሙሉ ባይቀለብስም የመቀልበስ አቅም እንዳለው ግን በትልቁ መድረክ ላይ አሳይቷል፡፡ ይህ ቡድን ለዚህ ደረጃ መብቃቱ በራሱ እንደ አሸናፊነት የወሰዱት ዜጎች ቁጥርም ቀላል አይደለም፡፡ አሁንም መከራከሪያቸው ብሔራዊ ቡድኑ ለሶስት አስርታ ከዓለምአቀፍ መድረኮች ርቋል ነው፡፡

## በዕድል፤ የተሰጣቸውን ዕድል...

አንድ የማይካድ ነጥብ ቢኖር ለሃያ ዘጠነኛው የአፍሪካ ዋንጫ ያበቁን ጀግኖች ኢትዮጵያ በእግር ኳስ ታሪኳ ለአቅመ ሜዳ ካደረሰቻቸው ምርጥ ተጫዋቾቿ ጋር ሲነፃፀሩ ቀዳሚውን ቦታ ሊወስዱ እንደማይችሉ ነው፡፡ ይህን መደምደሚያ ለመስጠት ቢያንስ በባለፉት ሰላሳ ዓመታት በሀገሪቱ እግር ኳስ ውስጥ ማለፍ ግድ ይላል፡፡ ዞረን ወደ ዋናው ሕልማችን ወይም ግባችን ስንመለስ ሙሉጌታዎች ያላሳኩትን ሳልሃዲን እና አዳነ መፈፀም ችለዋል፡፡ የእነ አዳነን ታሪክ ከዕድል ጋር የሚያይዙ ዜጎች ጥቂት አይደሉም፡፡ ዕውነት ነው፤ ለረጅም ዘመናት በአፍሪካ ዋንጫ ጉዞ በማጣሪያዎች ከሰሜን እና ምዕራብ አፍሪካ ሀገራት ጋር እየተደለደልን የቀደመው ትውልድ ኢትዮጵያን ወደ ትልቁ የእግር ኳስ ካርታ ሊመልሳት አልቻለም፡፡ ወደፊት ታሪክ ሲዘክራቸው እንዴት አላለፉም ወይም እንዴት ማሳካት አቃታቸው ከሚለው ይልቅ በግርድፉ አላለፉም ወይም ለአፍሪካ ዋንጫ አልበቁም የሚለው ነጥብ ትልቁን ቦታ ይወስዳል፡፡ አዲሱም የእግር ኳስ ትውልድ ተሳትፎውን ያሳካበት መንገድ ሳይሆን የደረሰበት ቦታ በታሪክ መዝገብ ላይ ደምቆ ይፃፋል፡፡

በ1990ዎቹ በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን እና በኢንጂኒየር ግዛው ተክለማርያም በሚመራው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን መካከል ጥሩ መቀራረብ ተፈጥሮ ነበር፡፡ በተለይ በእግር ኳሱ የበላይ ፊፋ ፕሬዚዳንታዊ የምረጡኝ ዘመቻ እነ ሌናርት ዮሐንሰን በካፍ በኩል የኢትዮጵያን ድምፅ አጥብቀው የሚፈልጉበት ዘመን ነበር፡፡ ተቀራርቦ የመነጋገሩን ዕድል ያገኙት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አመራሮች የእነ ሙሉጌታ ትውልድ ከአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎ የሚሰናከልበትን "ዓብይ" ምክንያት ፊት ለፊት ማንሳታቸው አልቀረም፡፡ "ሁልጊዜ የምንደለደለው ከሰሜን እና ምዕራብ አፍሪካ ሀገራት ጋር" ... የፌዴሬሽኑ ሰዎች ጥያቄ ወይም አቤቱታ ነበር፡፡ በእንዲህ ዓይነት መንገድ የተጀመረው ማግባባት ከዓመታት በኋላ የሰሜን እና ምዕራብ አፍሪካ ብሔራዊ ቡድኖች የሌሉበት ምድብ ውስጥ ያስገባን ጀመር፡፡ የሚፈሩት ሀገሮች ቢኖሩ እንኳን በቅርብ የእግር ኳስ ታሪካቸው ያን ያህል የምንርበተበትላቸው አልነበሩም፡፡ በሶስት የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያዎች እነ ግብፅ ከሌሉበት ምድብ ብንደለደልም የማለፍ ሕልማችን ግን ሊሰምር አልቻለም፡፡

ይልቅስ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን መልካም አጋጣሚ ይዞ የመጣው ካፍ የአፍሪካ ዋንጫን ውድድር መርኃ ግብር ወደ ጎዶሎ ቁጥር ዓመታት ለመቀየር ያደረገው ውሳኔ ነው፡፡ በዚህም በአንድ ዓመት ልዩነት ሁለት ጊዜ አህጉራዊው ዋንጫ ሊካሄድ በቃ፤ በ2012 እና በ2013፡፡ የጨዋታ ካላንደር መጨናነቅ አፍጥጦ የመጣበት የካይሮው ጽ/ቤት በአራት የደርሶ መልስ ግጥሚያዎች አላፊ ቡድኖችን ለመለየት ተነሳ፡፡ ይህን ዕድል በአግባቡ የተጠቀሙበት የሰውነት ቢሻው ልጆች በዕድል ሳይሆን የተሰጣቸውን ዕድል ወደ ውጤት ቀይረው ሕልማችንን አሳኩልን፡፡ የእኛ የተመልካቾች ብቻ ሳይሆን የእነርሱም ሕልም ሰመረ፡፡

## ሜዳ ሳይኖር ብሔራዊ ቡድን

በደቡብ አፍሪካው ውድድር ከወከሉን ሃያ ሶስት ተጫዋቾች በሥርዓት ከተዋቀረ የታዳጊዎች ሥልጠና (ፕሮጀክት)

ላይ የተገኙት ከአምስት አይበልጡም። አብዛኞቹ በራሳቸው እና በትውልድ መንደራቸው ለስፖርቱ ልዩ ፍቅር ባላቸው ዜጎች ጥረት እና ክትትል ለዚህ አኩሪ ታሪክ የበቁ ናቸው። የእነ ደጉ ዘመን እግር ኳሰኞች በሜዳ የታደሉ አይደሉም። ለእግር ኳስ መስፋፋት ትልቁን አስተዋፅኦ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ስፖርቱ በቀላሉ ኳስ ማንከባለያ ሜዳ ካገኘ መከናወኑ ነው። የሰፈር ሜዳዎች በአዳዲስ ሕንፃዎች እና ግንባታዎች እየተመናመኑ በመጡበት አዲስ አበባ የእግር ኳስን ሀ..ሁ የሚቆጥሩ ታዳጊዎች ቁጥር እጅግ እየቀነሰ ነው። ይህም በብሔራዊ ቡድኑ ከመዲናዋ መንደሮች የተገኙትን ተጫዋቾች ውስን አድርጎታል። በእርግጥ ተፈላጊው ነጥብ የብሔራዊ ቡድኑ ስኬት እንጂ የአካባቢ ውክልና ባይሆንም ይህ አደጋ አዲስ አበባን አዳክሞ ወደ ክልል ከተሞችም ተሻግሯል። የብሔራዊ ቡድኑ ተጫዋቾች በእንዲህ ዓይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ አልፈው ለአኩሪ ታሪክ ካበቁን፤ የእግር ኳስ መሠረተ ልማቶች ቢስፋፉላቸው በሃያ ዘጠነኛው የአፍሪካ ዋንጫ የታዩብንን ቀዳዳዎች የማንደፍንበት ምንም ምክንያት አይኖርም። የቀደመው ትውልድ በክዋክብቱ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ "ኩብለላው" እየኮረኮመው ወርቃማ ዘመኑ አልፎበታል። የዚህኛው ትውልድ እግር ኳስ ደግሞ ያለ መሠረት ልማቶች ከአቅሙ በታች እንዲያመርት ተፈርዶበታል። ሜዳ እና ተያያዥ ጉዳዮች ሳይሟሉ በስኬት የታጀበ ብሔራዊ ቡድን ማለም አሁንም የዋህነት ነው።

## ውድድሩ እና የእኛ ቡድን

ትላልቆቹ ግብፅ እና ካሜሩን በቀሩበት ውድድር እኛ መሳተፋችን ከሰላሳ አንድ ዓመታት ጥማታችን ጋር ተዳምሮ የሚነሳ ሌላው የስኬታችን መለኪያ ሆኗል። ይህንኑ ክስተት መዘው በአፍሪካ ቡድኖች መካከል ያን ያህል የገዘፈ የብቃት ልዩነት ሜዳ ላይ የለም የሚሉ ድምፆች ይደመጣሉ። እነደእኔ እንደእኔ በዚህ ዘመን በእግር ኳስ ሜዳ በተፎካካሪ ቡድኖች መካከል የሚታየው ልዩነት የተንበራቀቀ አይደለም። እግር ኳስን በውጤት መለኪያ (በአሸነፈ/ተሸነፈ) ብቻ ካየነው በእኛ እና ወደ ቀጣዩ ዙር ባለፉት ስምንት ቡድኖች መካከል ትልቅ ወንዝ አለ። ቁምነገሩ ሜዳ ላይ በእንቅስቃሴ የታየው ነገር ነው። ከጎል ቁጥሩ ጀምሮ ኳስ ይዞ እስከመንቀሳቀስ፣ ተጋጣሚ እንደፈለገው ጨዋታውን እንዳይዘውር እስከመቆጣጠር፣ ጠንከር ሲልም በክዋክብት የታጠሩትን ትልልቅ ቡድኖች አጥቅቶ እስከመጫወት በእግር ኳስ ካርታ ሚጢጢ ከሚባሉት ቡድኖች በሃያ ዘጠነኛው የአፍሪካ ዋንጫ ታይቷል።ነገር ግን መደምደሚያውን የሚሰጠው ወደ ሩብ ፍፃሜ ማለፍ እና መውደቅ ከሚለው አንፃር እንዳልሆነ ይሰመርበት። ሃያ ዘጠነኛው የአፍሪካ ዋንጫ በቀደሙት ዓመታት ጎላ ብሎ የሚታየው እና የውድድሩን ጣዕም የሚያሳጣው የኃይል አጨዋወት እጅግ መቀነሱን የታዘብንበት ውድድር ነው።

## አንድ ለሰባት

የሩብ ፍፃሜው ጉዞ በሰባት የምዕራብ አፍሪካ ሀገሮች ተወሯል፤ አንድ ፀጉረ ልውጥ የሆነችውና ከደቡብ አቅጣጫ የገባችው አዘጋጇ ሀገር ናት። እንደ ክፍለ አህጉር ካየነው የዘንድሮው ውድድር ለምዕራብ የአፍሪካ ሃገሮች ትልቅ ስኬት ሆኗል። የአፍሪካ እግር ኳስ የኃይል ሚዛን በሰሜን እና ምዕራብ ሀገራት መካከል ይገኛል። ይህ የኃይል ሚዛን ፉክክር ከሜዳ ውጪም በእግር ኳሱ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ይንፀባረቃል። በሃያ ዘጠነኛው የአፍሪካ ዋንጫ ሰሜኖቹ በሶስት ቡድን ተወክለው ከ1992 በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የሩብ ፍፃሜ ተወካይ ሳያገኙ ተመልሰዋል። አሁን ያለው ፈተና አንድ ለሰባት ነው፤ ደቡብ አፍሪካ ከሰባቱ የምዕራብ አፍሪካ ተወካዮች ጋር የምታደርገው ፍጥጫ። በነፃነት ማግስት በተሳተፈችባቸው ሶስት የአፍሪካ ዋንጫ ውድድሮች ወርቅ፣ ብር እና ነሐስ ያከታተለችው የማንዴላ ሀገር ወቅታዊ ብቃቷ በአዘጋጅነቷ ውስጥ ራሱን ደብቋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተሳትፎም ከውጤት አንፃር ሳይሆን በቀጣይ ለእግር ኳሱ ይዞ ከሚመጣው በጎ ነገሮች አንፃር በደማቁ ሊፃፍ፣ ሊነገር እና ለውይይት ሊቀርብ ይገባዋል።

ማክሰኞ ምሽት በይፋ የተሰናበትነው መድረክ ለወጣቶቻችን እግር ኳስ ተጫዋች መሆን የት ድረስ እንደሚወስድ በተጨባጭ መልስ የሰጠ ነው። ይህ መልስ ለታዳጊዎቹ ብቻ ሳይሆን ታዳጊዎቹን ኮትኩተው ለሚያሳድጉ ወላጆችም ጭምር ነው። ሌላው የዓለምአቀፍ መድረክ ልምድ ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለን የተረዳንበትም ውድድር ሆኖ አልፏል፤ ሃያ ዘጠነኛው የአፍሪካ ዋንጫ። በአርበኝነት ስሜት ሳይሆን ውጤት ያጣንባቸውን ጨዋታዎች በእግር ኳስ ቴክኒክ መነጥር ስንፈትሻቸው የፈራነውን ያህል ከዓለም እግር ኳስ እንዳልራቅን እንረዳለን። ከፍ ሲል ልጆቻችን ነጋ ጠባ ከምንዘምርላቸው የአውሮፓ እግር ኳስ አድማቂዎች ጋር አብሮ የመቆም አቅም እንዳላቸው የመሰከርንበትም ሆኗል።

የደቡብ አፍሪካው ድግስ ከዛሬ ጀምሮ በትልቁ የሚያጣው የእኛን ትኩረት ብቻ ሳይሆን ለእግር ኳስ ስፖርት ልዩ ፍቅር ያላቸው የኢትዮጵያን ልጆች ቀለም እና ዝማሬ ነው፡፡ ሃያ ዘጠነኛው የአፍሪካ ዋንጫ የእግር ኳሳችንን ብቃት፣ አቅም እና ድክመት በደንብ ያየንበት ውድድር ነበር፡፡ ከሙገሳው ጀርባ እነዚህን ሶስት ነጥቦች ወደ መሬት አውርዶ የአጭር እና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን በመንደፍ ተገቢውን ምላሽ የሚሰጥ የእግር ኳስ ሥርዓት ኢትዮጵያ አጥብቃ ትሻለች፡፡ ትላንትና ማታ ወደ ሀገራቸው የገቡት ጀግኖቻችን የሚከተሉትን ጥያቄዎች በብሔራዊ ቡድኑ ሥም ይዘው ከደቡብ አፍሪካ ተመልሰዋል፡፡ የመንደር ሜዳዎችን ተንከባከቡልን! ዘመናዊ ስቴዲየም ገንቡልን! የአሰልጣኞቻችንን አቅም አሳድጉልን! መሠረት ያለው የታዳጊዎች ሥልጠና ዘርጉልን! አስተማማኝ የሊግ ውድድር አዋቅሩልን! በዕውቀት የሚሠራ እና የሚያሠራ የእግር ኳስ አመራር አስቀምጡልን! … ፡፡

*እንኳን ለምትወዷት ሀገራችሁ አበቃችሁ!*

# እግርኳሳችንና ተግዳሮቶቹ…

**በፍስሐ ተገኝ**

*"እግርኳስ እኛነታችንን እንድናውቅ ይረዳናል። የምንኖርባቸው ከተሞች የእለት ከ እለት ህይወቶች የሆኑት ንግዶች፣ ጨ ሻቶች፣ ኳኳታዎች፣ ውብቶችንእና አስቀያሚዎችን ያንጸባርቃል። እግርኳስ ማንነታችንን ኢጋነን እና አትርፈን የምናሳይ በት ምልክት ነው። ሰዎች የአንተን ማንነት እና ህይወትበምታሳየው እግርኳስ ውስጥ መመልከት ይችላሉ። እግርኳስ ጠን ካራ፣ ሀይል ያላቸው እና ሁላችንም በአንድነት የምንጋራቸውን ምስሎች ማንጸባራቂያውብ ነገር ነው"*በማለት የተናገረው አርጀንቲናዊው የቀድሞው የአለም ዋንጫ ባለቤት እና "የእግርኳስ ፈላስፋው" በሚለው ቅጽል ስሙ የሚታወቀው ሆርጌ ቫልዳኖ ነበር።

## የእግር ኳስ ፍቅራችን…

የእግርኳስ ጨዋታዎችን ለመመልከት በሚል ከትምህርት ቤት አምልጠን ወጥተን ስታዲዬሞች ስንሄድ የነበረው፣ ማታ ቴሌቭዥን ያላቸው ጎረቤቶች ፈልገን እግርኳስን ለማየት ወላጆችን ለማታለል አልጋችን ውስጥ ሰው የተኛ ለማስመሰል ትራስ ደብቀን በመስኮት በመውጣት የምንነጉደው፣ መኪና እያጠብን ያገኘነውን ገንዘብ በማጠራቀም እና ከቤተሰብ የተቀበልነውን የኪስ ገንዘብ ለስታዲዬም መግቢያ ትኬት መግዣ በሚል እስከሳምንቱ መጨረሻ ድረስ ስንሰበስብ የነበረው፣ ገንዘብ ከሌለን ደግሞ ስታዲዬሞች መግቢያ በሮች ወይም ከተንበሪዎች (ከሀረር አካባባቢ ከሆኑ) አጠገብ በመቆም ጨዋታው ሊጠናቀቅ 15 ደቂቃዎች ያህል እስኪቀሩት ጠባቂ ፖሊሶችን አይን አፍጠን እያየን በልጅ ፊት ቋንቋ የምንልማመጠው እግርኳስ ጨዋታን ለማየት እና ልንገልጸው የማንችለውን መንፈሳዊ እርካታን ለማግኘት ነበር።

እነዚህን ነገሮች ስናደርግ ታዲያ ተቺዎች፣ እንቅፋቶች እና አላጋጮች አላጋጠሙንም ማለት አይደለም። ግን "ደግሞ ለሞተ እግርኳስ እና ለቅሪላ" እያሉ ሲያሾፉብን የነበሩ ሰዎች ታዲያ ድንገት ያ አስተያየታቸው በሀገራዊ ፍቅር እና ስሜት ተቀይሮ እግርኳስን ከእኛ ጋር እያጣጣሙ ሲያዩ እና የራሳቸውን አስተያየቶች ሲሰጡ ማንበብ፣ መስማት እና መመልከት በእውነትም የዚህ የ29ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ትልቁ ክስተት ነበር ማለት ይቻላል። በደቡብ አፍሪካ አስተናጋጅነት በተካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ ተካፋይ የነበረው እና ከዛምቢያ ጋር አቻ ተለያይቶ፣ በቡርኪና ፋሶ እና ናይጀሪያ ብሄራዊ ቡድኖች ተሸንፎ ከውድድር ውጪ የሆነው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ሜዳ ውስጥ ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች የሀገሪቷን እግርኳስ ለረጅም ጊዜ ሲከታተል ለነበረ ተመልካች አዲስ ባይሆንም ለበርካቶች (ኢትዮጵያዊያን ለሆኑ እና ላልሆኑ) ግን አስደናቂ እና ጭራሽም ያልጠበቁት አይነት ነበር። ያ ፈጣን አጭር ኳስ ቅብብል፣ ከአምስት ሜትሮች ባነሰ ርቀት ላይ በቆሙ ሁለት እና ሶስት ተጨዋቾች መካከል ጠባብ ቦታዎችን በመጠቀም የሚደረጉት አንድ-ሁለት ቅብብሎሽ፣ የቆሙ (የቅጣት ምት እና የማእዘን ምቶች) ኳሶችን የማጥቃት እና የመከላከል ችግሮቹ፣ አስደናቂ የግል ችሎታዎች እና ያልተገራ እና ተፈጥሯዊ የሆነው ጥበብ ለማየት ጊዜውን እና አቅሙን ሲሰዋ የነበረ ኢትዮጵያዊ የእግርኳስ አፍቃሪ በሙሉ ያለምንም ማቋረጥ ሲያያቸው የሰነበቱ ክስተቶች እና ሂደቶች እንደሆኑ ያውቃል።

ታዲያ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ሜዳ ላይ ባሳየው እንቅስቃሴ የተገረሙት እና ሀገሪቷን በስፖርቱ አለም በሩጫው ብቻ ያውቋት የነበሩ የጨዋታ አስተላላፊዎች (commentators) እና ተንታኞች (pundits) በአንድነት ማለት ይቻላል ተጨዋቾቹ ራሳቸውን ሜዳ ላይ ለመግለጽ አለመፍራታቸው፣ ለእይታ ቀላል እና ማራኪ በሆነው አጭር ኳስ አጨዋወታቸው በመገረም አድናቆታቸውን ማፍሰስ ጀመሩ። እነዚህ አድናቆቶች ታዲያ (ከገለልተኛ ወገኖች የተሰሙ በመሆናቸው) በስሜት እና በሀገር ፍቅር ወኔ ብሄራዊ ቡድኑን ለመደገፍ ለወሰነው በፊት እግርኳሱን ይከታተል ላልነበረው ኢትዮጵያዊ ልክ እንደአስቴር አወቀ ሰረቅራቃ ድምጽ ለጆሮው የሚጣፍጡ ሙዚቃዎች ነበሩ።

## የክለቦች ችግር በአህጉራዊ ሜዳ

በዘንድሮው የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ባየነው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን አጨዋወት ብንደሰትም በርካታ የዘርፉ ባለሞያዎች "ነገር ግን" ብለው የሚጀምሩት ትችት የበፊቶቹ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድኖች እና ክለቦች ላይ ይሰነዘሩ ከነበሩት ትችቶች ጋር ተመሳሳይነት ነበራቸው። በተለይ በተደጋጋሚ ከኢትዮጵያ ክለቦችም ሆነ ብሄራዊ ቡድኖች ጋር የተጫወቱ የውጪ ሀገሮች ተጋጣሚ ቡድኖች አሰልጣኞች በተደጋጋሚ የኢትዮጵያ ቡድኖች ላይ

ከሚያቀርቧቸው ትችቶች መካከል ታክቲክ ላይ ወይም የጨዋታ እንቅስቃሴ ላይ ያተኮሩት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። ኳስን ለመቀበል ወደክፍት/ባዶ ቦታ መሮጥ፣ የሜዳውን ስፋት እና ርዝመት ግምት ውስጥ አስገብቶ የሚቆምባቸውን ቦታዎች ማወቅ፣ ከቡድን አባል ጋር መቀናጀት፣ ኳሱን ለመቀበል ክፍት ቦታዎች ላይ መገኘት፣ በራስ እና በተጋጣሚ ሜዳ ላይ ኳስን በበላይነት መቆጣጠር፣ እንቅስቃሴዎችን ኳስ እግር ስር ከመግባቷ በፊት ቀድሞ ማንበብ፣ መቼ ኳስን ማቀበል እና በግል እያንከባለሉ መሄድ እንዳለባቸው ትክክለኛ እርምጃን መውሰድ፣ ኳስን ለጓደኛ ሲያቀብሉ እና ሲያንከባልሉ ከተጋጣሚ ቡድን ተጨዋች እይታ/ንባብ መሸፈን፣ የተጋጣሚ ቡድን ሊጠቀምበት የሚችለውን አደገኛ ቦታ እና ሰው መከላከል እና መሸፈን የሚሉት በዋናነት የሚጠቀሱ የታክቲክ ስርአቶች ቀድሞም ቢሆን በኢትዮጵያ እግርኳስ ቡድኖች ላይ በተደጋጋሚ የሚታዩ ታሪካዊ ችግሮች ናቸው። እነዚህን ክፍተቶቻችንን ይዘን ለአህጉራዊ እግር ኳስ መምጣታችን በ29ነኛ የአፍሪካ ዋንጫ በሚገባ ታይቷል።

## ጥንካሬያችንና ጉድለቶቻችን

ሜዳ ውስጥ ባሉት እንቅስቃሴዎች ላይ ብቻ አተኩረን የኢትዮጵያ እግርኳስ የሚደነቅባቸውን እና የሚተችባቸውን ነገሮች ነጣጥለን ብናይ የሚደነቅባቸው ነገሮች ግለሰቦች በተፈጥሮ ያገኟቸውን (ያለአሰልጣኝ ወይም አስተማሪ ሊገኙ የማይችሉ) ችሎታዎች ሲሆን፣ የሚተችባቸው ደግሞ በትምህርት እና በስልጠና ሊያገኙቸው በሚችሏቸው ነገሮች ላይ ነው። ኢትዮጵያዊያን ተጨዋቾች አብዛኞቹ አጨዋወታቸው ኳስን በመያዝ ላይ የተመሰረተ እና ለአይን የሚማርክ እንቅስቃሴ ቢሆንም ተጋጣሚ ቡድንን ለማሸነፍ ግን በቂ እንዳልሆነ በተደጋጋሚ ታይቷል። እ.አ.አ በ1907 ዓ.ም የእንግሊዙ ኖርዝሀምተን ክለብ አሰልጣኝነት የተረከቡት ኸርበርት ቻፕማን በጊዜው "እግርኳስ ጨዋታን ለማሸነፍ ኳስን በቁጥጥር ስር ማድረግ ብቻ በቂ አይደለም፤ ኳሱን የት እንደተቆጣጠርከው እና የተቆጣጠርክበት ሁኔታዎች ወሳኝነት አላቸው" በማለት የተናገሩት ለምን የሀገራችን ተጨዋቾች በዚህ በአፍሪካ ዋንጫው ላይ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ቀደምም ቢሆን ኳሱን ቢቆጣጠሩም ያንን ቁጥጥራቸውን ወደውጤት መቀየር በተደጋጋሚ እንደተቸገሩ ፍንጭ የሚሰጥ ነው።

Inverting the Pyramid የተሰኘው በእግርኳስዊ አጨዋወት ታክቲክ ላይ ያተኮረ መጽሀፍን የጻፈው ብሪታኒያዊው የስፖርት ጋዜጠኛ ጆናታን ዊልሰን "አንድ ቡድን የራሱን እግርኳሳዊ ፍልስፍና ሜዳ ላይ ለማሳየት ከሁለት ነገሮች መካከል አንዱን መምረጥ አለበት" ይላል። "ወይ ኳሱን መቆጣጠር እና ተጋጣሚው ቡድን እንዲጫወት በፈቀደለት ክፍት ቦታ ላይ መጫወት አለበት፣ አሊያም ደግሞ መከላከልን በመምረጥ የራሱ ሶስተኛው የመከላከያ ሜዳው ክፍል ከኳስ ጀርባ የሚቆሙ የሰዎችን ቁጥር በማብዛት ኳስን ለማግኘት ረጅም ጊዜ እንደሚወስድ አምኖ መጫወት።" ኳስን ይዞ የሚጫወተው "proactive" ቡድን ሲሆን፣ ኳሱን የሚከላከለው ደገም "reactive" በመባል ይታወቃል።

የቀድሞው የጣሊያኑ የኤሲ ሚላን ክለብ ታላቅ አሰልጣኝ አሪጎ ሳኪ በአንድ ወቅት ዘ ጋርዲያን (The Guardian) ጋዜጣ ላይ የጣሊያን እግርኳስ አምደኛ (columnist) ከሆነው ፓውሎ ባንዲኒ ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ በተለይ አጨዋወታቸው ኳስን በመቆጣጠር (possession football) ላይ ያተኮሩ ቡድኖች ውጤታማ ለመሆን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እሳቸው ኤሲ ሚላን ውስጥ የተገበሩትን እና በዚህ አጨዋወት ዘዴ ዝነኛ የሆኑት የሆላንዱ አያክስ አምስተርዳም እና የስፔኑ ባርሴሎና ክለቦችን ተሞክሮ መነሻ በማድረግ የተናገሩት ኳስን መቆጣጠር/አጭር ኳስ ላይ የተመሰረተ አጨዋወት ያላቸው የኢትዮጵያ ቡድኖች (ብሄራዊ እና ክለቦች) ለምን ውጤታማ ለመሆን እንደተቸገሩ በግልጽ የሚያብራራ ነበር።

"ታላላቅ ቡድኖች ኳስን እና ቦታን የመቆጣጠር አላማ ያለው ተመሳሳይ አይነት ባህሪ አላቸው። መቼ የያዛቸውን ተጨዋቾች ማምለጥ እንዳለባቸው እናመቼስ የተከፈተ ቦታን መቆጣጠር እንዳለባቸው ጠንቅቀው ያውቃሉ። ሁልጊዜ ማሰብ ያለባቸውእና እርምጃዎችን/ውሳኔዎችን መውሰድ ያለባቸው ግንከተጋጣሚያቸው ቡድን ሳይሆን ከቡድናቸው ተጨዋቾች እናእንቅስቃሴ በመነሳት መሆን አለበት።" ነበር ያሉት አሪጎ ሳኪ "እግርኳስ በጣም የተወሳሰበ ስፖርት ነው። ስታጠቃ በተጨዋቾችህ መሀል ያሉት ርቀቶች ትክክለኛ መሆን አለባቸ ው። ጊዜ አጠባበቅህ እና አጠቃቀምህልክ ሊሆን ይገባል። የያዝሀን ተጨዋች ማስለቀቂያ ትክክለኛ መንገድ ሊኖርህ ይገባል። እነዚህ ነገሮች ከሌሉህ የምትጫወተው እግርኳስ ፍሰትአይኖረውም። ብዙውን ጊዜ ቡድኖች ቡድን ከመሆ ን ይልቅ ዝም ብለው የተጨዋቾች ስብስብ ሆነው ይቀሩና በአንድነት መንቀሳቀስ ሲቸገሩ ታያለህ።" ሲሉ ማብራሪያ ሰጥተው ነበር በአፍሪካ ዋንጫው ላይ የተሳተፈው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድንም ሆነ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ቡድኖች ሜዳ ውስጥ ሲገቡ የትኛውን የአጨዋወት ዘዴ መቼ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ በግልጽ

ከማየት ይልቅ ድንገት በአጋጣሚዎች ከ proactive ወደ reactive ሲቀያየሩ እና ያንንም በአግባቡ ሳይፈጽሟቸው ሲቀሩ ነው የሚታዩት።ይህ በስልጠና የሚገኙ ክህሎቶችን ያለማግኘት በአፍሪካ ዋንጫ የታየ ችግራችን ነበር።

## አስተዳደራዊው ነገር

እነዚህ በስልጠና የሚገኙ የላቁ እግርኳሳዊ እውቀቶች በተጨዋቾቻችን እና በአሰልጣኞቻችን አእምሮ ውስጥ እንዲኖሩ እና ብሎም ሜዳ ውስጥ እንዲተገበሩ ለማስቻል ደግሞ ከፍተኛውን ሚና መጫወት ያለበት ከእግርኳስ ሜዳው ውጪ ያለው እና ነገሮችን የማመቻቸት ሀላፊነት ያለበት አስተዳደራዊ ክፍል ነው።

*"በእኔ አይን ውስጥ የእግርኳስ ሜዳ ጫካ ማለት ነው"የሚለውቫልዳኖ እዛ ጫካ ውስጥ ዛሬም ድረስ የሚካሄዱት ነገሮች ከዛሬ መቶ አመታትበፊት ይካሄዱ ከነበሩት ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው ይናገራል። "ከመቶ አመት በፊት ይጫወት የነበረ አንድ አጥቂ ኳስን ይዞ ወደተጋጣሚጎል ሲደርስ 'ምን ማድረግ አለብኝ' ብሎ የሚያስበው ልክ ዲስቴፋኖ፣ ፔሌ፣ ማራዶናና እና ሊዮ ሜሲ በተመሳሳይ አጋጣሚ ከሚያስቡት ጋርተመሳሳይነት አለው። እየተለወጠ ያለው ግን የጫካውን ዙሪያ የከበቡት ነገሮች ናቸው።"*

እነዚህ ቫልዳኖ "ከጊዜ ወደጊዜ ይለዋወጣሉ" ያላቸው ጫካውን/ሜዳውን የከበቡት ነገሮች ዘመናዊ የእቃ-አቅርቦቶች፣ ስልጣኔዎች፣ ሳይንሳዊ እና ፍልስፍናዊ አጨዋወቶች፣ ታክቲኮች፣ የገንዘብ ድጋፎች እና የስፖርት ገበያዎች እና አስተዳደሮች ናቸው።

ብዙዎቻችን ሜዳ ላይ ተጨዋቾች እና አሰልጣኞች የሚሰሯቸውን ስህተቶች በአይናችን ስለምናያቸው ብቻ ለሽንፈት እና ለእግርኳሱ ድክመት የቀጥታ ተሳታፊዎቹን እንደምክንያት እያቀረብን ረጅም ጊዜ ሰንብተናል። ታዲያ ይህ ሲሆን በተለይ በተለያዩ ጊዜያት ከተጨዋቾች እና አሰልጣኞች ጀርባ ተደብቀው የእግርኳሱን አደረጃጀት እና ሂደት ወደኋላ እየጎተቱ ድንገት ብልጭ የሚሉ ውጤቶች ሲገኙ ልክ "የአብዮቱ ዋና መሰረቶች ነን" በሚል ትቢት እራሳቸውን በዋናነት በማስቀመጥ ስለ "ጠንካራ ሰራተኛነት፣ ስፖርትን ከታች ከህጻናት ጀምሮ ማስፋፋት፣ ህብረት፣ ስታዲዬም መገንባት፣ እግርኳሱ ላይ መዋለ-ነዋይ ማፍሰስ" የመሳሰሉ የሚያብረቀርቁ ወሬዎችን በማውራት እያጭበረበሩ መኖራቸውን ከተያያዙት አመታት አልፈዋል።

ከ12 አመታት በፊት ኢትዮጵያ የአፍሪካ ወጣቶች እግርኳስ ሻምፒዮናን አስተናግዳ አራተኛ ደረጃን አግኝቶ በማጠናቀቁ አርጀንቲና ላይ በተካሄደው የአለም ወጣቶች ሻምፒዮና ላይ የተካፈለው የኢትዮጵያ ወጣት ብሄራዊ ቡድን በሻምፒዮናው ላይ በታላቁ ሆላንዳዊ አሰልጣኝ ሉዊ ቫን ሀል ይመራ ከነበረው የሆላንድ ወጣት ብሄራዊ ቡድን ጋር ያደረገውን እንቅስቃሴ ጨምሮ ያሳያቸው ድንቅ ብቃቱ በሀገሪቷ ህዝብ ላይ ልክ የአሁኑ የአፍሪካ ዋንጫው ተሳታፊ ብሄራዊ ቡድን የፈጠረውን አይነት ስሜት እና ተነሳሽነት መፍጠሩን የተገነዘቡ "እግርኳሳችንን በጋራ ለማሳደግ ቆርጠን መነሳት አለብን" የሚለው፣ ተቆርቋሪ መስሎ መታየት የሚፈልገው ፖለቲከኛ እና የስፖርቱ የበላይ ሀላፊ አጋጣሚውን በመጠቀም ሊያደርጉት የማይችሉትን የተጋነኑ ቃልኪዳን መግባቱን፣ የእግርኳስ ፌዴሬሽኑም "ኢትዮጵያ ልክ እንደሩጫው ሁሉ ስሟ በእግርኳሱም አለም ላይ ይገናል" የሚለው ንግግሩን ማስተጋባቱን ተያይዘውት ቃሎቻቸው በተግባር ሳይሆን በሌሎች ቃሎች ታጅበው ይሄው 12 አመታት አለፉ እና እንደገና በተመሳሳይ ተነሳሽነት በተጨዋቾች እና በጥቂት የቡድን አባላት ጥረት የተገኙትን ውጤቶች ተገን አድርገው እንደገና የሚያብረቀርቁ ወሬዎቻቸውን አሁንም እያወሩልን ነው።

ለኢትዮጵያ እግርኳስ አፍቃሪ ትእግስት አዲስ ነገር አይደለም። ይህ ትግስተኛ ህዝብ የሚመኘው እና ማየት የሚፈልገው ግን የሚመለከታቸው የስፖርቱ የበላይ ሀላፊዎች በአሸናፊነት ጀርባ ላይ ተንጠልጥለው ለመታየት ጥረት ለማድረግ ከሚያወጡት ጉልበት ላይ ግማሹን እንኳን ቆጥበው ቃል ሲገቡልን የነበሩትን እና አሁንም እየገቡልን ያሉትን ሩብ ያህሎቹን እንኳን ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል። ያላቸውን አቅም እና ችሎታ ተጠቅመው የአቅማቸውን ያህል በመጣር ቢያንስ የሀገሪቷ እግርኳስ "አለሁ" ብሎ በአፍሪካ እግርኳስ ውስጥ ስሙን እንዲያስተጋባ እና ህዝቡም በአንድነት በታላቅ ደስታና ስሜት ለአጭር ጊዜም ቢሆን እንዲቦርቅ ላስቻሉት ተጨዋቾች የሚገባቸውን ክብር እና አድናቆት ሊሰጣቸው ይገባል።

# ስለግብ ጠባቂዎች እስኪ እንነጋገር

**በኤፍሬም ማሞ**

ለአሁኑየዋሊያዎቹን በአፍሪካ ዋንጫ ከ31 ዓመት በኋላ ተሳትፎ እንደመጨረሻ ግብ አድርገው ወስደው፣ አይ በእግር ኳስ የሚሆነው አይታወቅም ምናልባትም ወደሚቀጥለው ዙር ሊያልፉ ይችሉ ይሆናል ከሚሉት ወገን ነገርኩ፡፡ የልምድ ማነስ ያመጣውን ችግር ያው በሜዳ ላይ እስተውለነዋል፡፡ ኢትዮጵያን በመወከል በደቡብ አፍሪካ ላደረጉት የልብ ጥረት ሁሉም የቡድን አባላት ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ ሞቅ ያለ የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ይጠብቃቸዋል ብሎ ማስብ ስህተት አይመስለኝም፡፡

ግን ጥቂት ስለበረኞቻችን እንነጋገር፡፡ አንድ በረኛ የሚፈጽመው አስደናቂ የግብ ሙከራን የማዳን እንቅስቃሴ የቡድን አባላትን የማነቃቃቱን ያህል በቀላሉ ሊድኑ የሚችሉ ኳሶች ከመረብ ማረፋቸው ደግሞ ተስፋ መቁረጥን የመዝራት እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡በአህጉራዊ ውድድሮች በሶስት ጨዋታዎች ሁለት ግብ ጠባቂዎቿ ከሜዳ በቀይ ካርድ የተወገዱባት አገር ማየት እንዲህ የተለመደ ክስተት አይመስለኝም፡፡ ጀማል ጣሰው በዛምቢያው ጨዋታ ወደ ጎል ያላነጣጠረች ኳስን ይዞ ከመጣ ዛምቢያዊ ሲላተም ከቀይ ሌላ ዳኛው የሚያሳዩት ካርድ አልነበረም፡፡ የሲሳይ ባንጫም በናይጀሪያው ጨዋታ በቀይ መወገድ ሊወገድ የሚችል ስህተት ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

**በረኞቻችን በአገር ውስጥ ክለብ**

ታዲያ በረኞቻችን ይህንን ሁሉ ስህተት እንዲህ በመሰለ ታላቅ አህጉራዊ ውድድር መፈጸም ምንጩ ከየት ነው ብሎ መጠየቅ የአባት ነው፡፡ ነገሩ ግን ወዲህ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ወክለው በደቡብ አፍሪካው የአሃጉራዊ የእግርኳስ ውድድር የቀረቡት ግብ ጠባቂዎች በአገራቸው የክለብ እግር ኳስ ያላቸው ሚና ከወንበር ማሞቅ አንጅ የግብ መጠበቅ ተግባር ላይ አይደለም፡፡

የቅዱስ ጊዮርጊሱ ዘሪሁን ታደለ ለኡጋንዳዊው ሮበርት ኦዶንከራ የአንደኛ ደረጃ ግብ ጠባቂነትን ቢያስረክብ ብዙ የማቅማማት እድል አይኖረውም፡፡ አንድ ክለብ ከፍተኛ ገንዘብ አውጥቶ ያስመጣውን ተጫዋች አስቀምጦ የአገሬውን ተጫዋች ያሰልፋል ብሎ መጠበቅ የዋህ ቢያሰኝ ነው፡፡

የቡና ገበያ እግር ኳስ ቡድንም ዘካሪያ ኦንያንጎን ከኬንያ አስመጥቶ ለአገር ልጆች የግብ ጠባቂነት ሚና ወንበር ማሞቅን አድርጓል፡፡ ጀማል ጣሰውም ከደቡብ አፍሪካዊው ሞካሲ ጃኮብ ተመርጦ በጨዋታ የመሰለፍ እድሉን ያገኛል ማለት ዘበት ነው፡፡

የደደቢት የእግር ኳስን የተጫዋቾች ዝርዝር ላየ ጃኮብ ሞካሺ የተሰኘ እንግዳ ስም ለቁጥር አንዱ ቦታ ተሰጥቶ ያያል፡፡ ይህ ከደቡብ አፍሪካ የፈለቀ ግብ ጠባቂ ለአገር ልጆች በተጠባባቂ ወንበር መቆየት ተጠያቂ መሆኑን ልብም የሚለው አይመስለኝም፡፡

የሃገራችን ስሙ-ጥር የእግር ኳስ ቡድኖች እንዲህ ከውጭ ሃገር የግብ ጠባቂዎች ጋር ፍቅር በፍቅር የሆኑት በአገር ልጆች የግብ አጠባበቅ ክህሎት ማነስ ወይስ እነሱን በሚያበቃው ስልጠና ክፍተት? ጥናት አድራጊዎች ጉዳዩን ቢዳስሱት የተሻለ ነው፡፡

## መፍትሔውስ?

ታዲያ መፍትሄው ምን ይሆን ለሚለው ጥያቄ ግን ሩቅ ሳንሄድ ወደ ግብጽ ሃገር እናገኝዋለን፡፡ ሳልሃዲን ሰዒድ ለአገር ውስጥ ብዙሃን መገናኛ በሰጠው ቃለ-ምልልስ በግብጽ ሃገር የክለቦች ውድድር ላይ የውጭ ሃገር ተጫዋቾችን ማስመጣት የተከለከለ እንደሆነ ተናግሯል፡፡ በዚህኛው የአፍሪካ ዋንጫ ቀንቷት ያልተሳተፈችው ግብጽ ስመ ጥር በረኞችን በማፍራት ከአሃጉሩ ቀደምት አገሮች መሆኗ የታወቀ ነው፡፡

ይህ መልዕክት ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ባለስልጣናት ይድረስና ከግብጽ በተገኘው ልምድ አንጻር ተቃኝቶ የአገር ውስጥ የእግር ኳስ ቡድኖች የግብ ጠባቂነቱን ስፍራ ለአገር ልጆች ቢለቀቅላቸው መልካም ይሆናል፡፡ በአፍሪካ ዋንጫው እንዳስተዋልናቸው አይነት ስህተቶችን የማስወገጃው አንዱ መንገድ በረኞቻችን አስፈላጊውን የጨዋታ

ልምድ እንዲያገኙ ማድረግ ይሆናል። ሁነኛ አሰልጣኝ ፈልጎ የግብ ጠባቂነትን ክህሎት እንዲዳብር ማድረግ ጥሩ ነው። ከዚያ ባለፈ ግን፣ የመጫዎቻ ሜዳዎችን ማመቻቸት፣ የታዳጊዎችና ወጣቶች ስልጠናን ማጠናከር፣ የአስፈላጊ ቁሳቁሶች አቅርቦት፣ የአስተዳደር ጉደፈቶችን መቅረፍ፡ ተያያዥ ግን ጠቃሚ ግብዓቶች መሆናቸው እንደማይዘነጉ አምናለሁ።

# የዓለም ዋንጫው ለኢትዮጵያ ምኗ ነው?

**በጌታቸው ሺፈራው**

በአሁኑ ወቅት የአገራችን ወጣት ትኩረት የሚሰጠው ነገር እግር ኳስ ሆኗል፡፡ ወጣቱ ለእግር ኳስ ብቻ የሚሰጠውን ትኩረትም አንዳንዶቹ የስርዓቱ ወጣቱን የማደንዘዣ ስልት ውጤታማነት ማረጋገጫ አድርገው ይወስዱታል፡፡ በአገራችን በአሁኑ ወቅት ከማይታገዱት የውጭ ጣቢያዎች መካከል የቀሩት የእግር ኳስ ማስተላለፊያ ጣቢያዎች ብቻ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም አሁን አሁን ሥርዓቱ ‹‹ያመነው ፈረስ›› አደጋ ላይ እየጣለው ይመስላል፡፡ ለይስሙላህም ሰንደቅ ዓላማ መከበር ሳይጀምርና ካድሬዎች ሰንደቅ ዓላማ ሲያዩ ይደነግጡ በነበረበት ወቅት ጀምሮ ወጣቱ ሰንደቅ ዓላማ ለብሶ የሚገኘው አዲስ አበባ ስታዲየም ብቻ ነበር፡፡ ይህን ተከትሎም ብዙዎቹ ሥርዓቱ የማይፈልገው ‹‹የአገር ፍቅር ያለው አዲስ አበባ ስታዲም ብቻ ነው›› እስከማለት ደርሰዋል፡፡

## የአፍሪካ ዋንጫውና የኢትዮጵያውያን

ኢትዮጵያውያን ለሶስት ዐሥርት ዓመታት ተለይተውት የቆዩትን የአፍሪካ ዋንጫ በተቀላቀሉበት በዚህ አመት ኳስ ወጣቱ ደነዘዘበት ከሚባለው ‹‹እግር ኳስ›› በላይ ሆኖ አልፏል፡፡ ይህ የብሔራዊ ቡድናችን ተሳትፎ ኢትዮጵያን በርሃብ ለሚያውቋት አፍሪካዊያንና የዓለም ሕዝብ አዲስ የአጨዋወት ዘይቤ፣ የደጋፊ ስሜትና ድምቀት እንዲሁም ሊረሳ ተቃርቦ የነበረውን ሰንደቃችን አሳይተዋል፡፡ ፖለቲካዊ ችግር ውስጥ ለምትገኘው ኢትዮጵያም በደቡብ አፍሪካ የተገኙት ደጋፊዎቻችን ድምፃቸውን ለማሰማት ሞክረዋል፡፡ በአዲስ አበባ ድምፃችን ታፍኗል ያሉትም ሆነ የአገራችን ፖለቲካ ምኅዳር ተጠርቅሞባቸው በጥገኝነት የሚገኙት ተቃዋሚዎች ብሔራዊ ቡድናችንን ከመደገፍ ባሻገር ለጊዜው መንግሥት ሊዘጋው ባልፈለገው ዲ ኤስ ቲቪ በኩል የኢትዮጵያውያንን ድምፃቸው ሳይታቀብ አሰምተዋል፡፡ መንግሥት ብሔራዊ ቡድናችን የአቶ መለስን ቲሸርት ለብሶ የአፍሪካን ዋንጫ ለአቶ መለስ መታሰቢያ ያደርገዋል በሚል ተስማምቶ የነበረ ቢሆንም የእነማንዴላዋ አገር ላይ ከካድሬነት ይልቅ ነጻነትን ከደጋፊዎቻቸው የተማሩት ተጫዋጮቻችን የደቡብ አፍሪካ ሜዳ በእብይተኝነታቸው አሸንፈው ተመልሰዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ኢህአዴግ ብሔራዊ ቡድናችን በመጀመሪያዋ ጨዋታ ነጥብ አስጥሎ ይዟት የወጣውን የባለፈው ዓመትን ሻምፒዎን ዛምቢያ ያልተናነሰ ሽንፈት ደርሶበታል ለማለት ይቻላል፡፡

## የዓለም ዋንጫውስ?

ጥቋቁሮቹ አናብስቶች በአፍሪካ የተሻለ የእግር ኳስ ደረጃ ያላትና የዓለም ዋንጫና የአፍሪካ ዋንጫን ያስተናገደችውን ደቡብ አፍሪካን በአገሯ ነጥብ አስጥሎ፣ ቦትስዋናንና ማዕከላዊ አፍሪካን አሸንፎ የዓለም ዋንጫ ማጣሪያውን በሁለት ነጥብ ልዩነት እየመራው ነው፡፡ በዚህ አካሄዱ ወደ ብራዚል የሚጓዝበትን አጋጣሚ እያሰፋ ነው፡፡ ይህ ከመሠረትነው፣ አንዴ ዋንጫውን አንስተን ስንሳተፍበት ከቆየነው የአፍሪካ ዋንጫ በእጅጉ የተለየ መድረክ ነው፡፡ ይህ 20ኛው የዓለም ዋንጫ 2006 ዓ/ም ከሰኔ መጨረሻ እስከ ሐምሌ መጀመሪያ በብራዚል ይካሄዳል፡፡ የዓለም ዋንጫው ኢሕአዴግ 100% (ከዚያም በላይ ሊሆን ይችላል) ለማሸነፍ ከሚፈልገው የ2007 ምርጫ የሚቀድመው ለወራት ያህል ብቻ ነው፡፡

ብዙ ሳይታሰብበትም ቢሆን በአፍሪካ ዋንጫ የተቃዋሚዎቻችን ድምፅ፣ የሕዝባችንና የእግርኳሳችን ውበት፣ የደጋፊዎቻችን ድምቀት ለሌሎች ብቻ ሳይሆን ለእኛ ለኢትዮጵያውያንም አስገራሚና የማይረሳ ትዕይንትና ትዝታ ሆኖ አልፏል፡፡ የዓለም ዋናጫ ዐሥራ አምስት ያህል ወራት ይቀሩታል፡፡ በአፍሪካው ዋንጫ ብዙም ሳያስቡበት ያን ያህል ድምፅ ማሰማት የቻሉት ተቃዋሚዎቻችንና ሙስሊም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በዓለም ዋንጫ ከዚህ የተሻለ ዝግጅት አድርገው ሊጠባበቁት እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡ ከምንም በላይ ብራዚል ድምፃቸውን ለሚያሰሙት ኢትዮጵያውያን አመች ትመስላለች፡፡ አፍሪካ ውስጥ ከሚኖረውን ወደደቡብ አፍሪካ ካቀናው ዲያስፖራ ይልቅ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ የሚገኘው የአገራችን ሕዝብ ወደ ኳሷ አገር ብራዚል ለማቅናት ይቀናዋል፡፡ ዲያስፖራው እስካሁን ገንዘብ ለማሰባሰብ ወይንም ለስብሰባ ተወካዮቹን በእየአህጉሩ ሲልክ ከነበረው በተቃራኒ ራሱ አገሩን ወክሎ ወደ ብራዚል ለመሄድ የሚያስችለውን ዕድል ብራዚል አዘጋጅታለታለች፡፡ የዓለም ዋንጫ ከአፍሪካ ዋንጫም በላይ ለማየት የሚያጓጓ መሆኑ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ከአፍሪካ ዋንጫ የተሻለ እንዲመርጡት ያደርጋል፡፡ በዚህ መድረክም ኦባንግ ሜቶ ወይንም ታማኝ በየነን ሳይጠብቁ ኢትዮጵያውያን

ከደቡብ አፍሪካዎቹ ደጋፊዎቻችን የተማሩትም እና ጊዜ ገዝተው ያጠናከሩትን ሰላማዊ የትግል ስልት ለዓለም ሕዝብ እንደሚያቀርቡ የሚያጠራጠር አይሆንም፡፡

የብራዚሉ የዓለም ዋንጫ  እስከ 500 ሺሕ ደጋፊዎች ሊሳተፉበት እንደሚችሉ ተገምቷል፡፡ ኢትዮጵያ ከሁለት ሚሊዮን በላይ የዳያስፖራ አባላት እንዳሏት ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ መካከል ደግሞ ከፍተኛ ቁጥር ያለው በሰሜን አሜሪካና ምዕራብ አውሮፓ የሚኖር ነው፡፡ ከዚህ ዲያስፖራዋ መካከል 0.5 በመቶው እንኳ ወደ ብራዚል ቢያቀና 10 ሺሕ ያህል ደጋፊዎች ይኖሩናል ማለት ነው፡፡ በእርግጥ  ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ አገር ውስጥ የሚኖሩ ዜጎችም ወደብራዚል እንደሚያቀኑ አያጠራጥርም፡፡ በአሁኑ ወቅት አንድ ሙስሊም  ለሂጅራ ወደ መካከለኛው ምስራቅ ከሚሄድ ይልቅ አንዋር መስጊድ የታፈነውን ድምፅ  ብራዚል ላይ ሆኖ ለማሰማት ከብሔራዊ ቡድናችን ጋር ማቅናትን ቅድሚያ የሚሰጠው ይመስለኛል፡፡ ሂጅራው እምነትን በነጻነት ማመን ሲቻል የሚደረግ ነውና በነጻነት ለማመን የሚያስችል ሁኔታን እንደመፍጠር ቅድሚያ የሚሰጠው አይመስልም፡፡ አብዛኛው ኦርቶዶክስም ቢሆን የእምነቱ አባቶች ቅልስ ቤቶች እየፈረሱ ሽንኮራ አገዳ ወደሚተከልባቸው ገዳማት ሄዶ ከመጸለይ ይልቅ ችግሩን ከብራዚል በቀጥታ በሚተላለፈው የዓለም ዋንጫ ሆኖ ቢያሰማ ‹‹ሰመዓት›› የመሆን ዕድል ይኖረዋል፡፡

አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎቻችንም እነ አቶ አየለ ጫሚሶ የፈረሙትን ‹‹ደንብ›› ፈርመው 2007 ምርጫን ከማጀብ ይልቅ ድምፃቸውን ከፍ አድርጎ ሊያስተላልፍላቸው የሚችለውን፣ ከኢቲቪ በእጅጉ በተሻለ ሰዓት የሚሰጣቸውንና ያልተጭበረበረ ውጤት የሚያገኙበትን የብራዚሉን የዓለም ዋንጫ ቢቀላቀሉ  የተሻለ እንደሚሆን ይታሰባል፡፡ በምርጫው ተሳታፊ የሆኑትም ኢትዮጵያ ከሚያደርጉት ይልቅ የብራዚል ሜዳዎች ትልቅ የቅስቀሳ መድረኮች መሆን የሚችሉ ናቸው፡፡ በእርግጥ ተጫዋቾቻችንም ቢሆን ደቡብ አፍሪካ ያሳዩትን እንብይተኝነት ትግል በደቡባዊው አሜሪካ ከፍ ወዳለ ደረጃ ማድረስ ከቻሉ ለቀሪው ትግል ከፍተኛ ጥቅም ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በመሆኑም በደቡብ አፍሪካዋ ሞምቤላ ስታዲየም ከነበረው ትግል ይልቅ የብራዚል ቤሌም፣ ቤሎ ሆሪዞንቴ፣ ብራዚላ፣ ካምፖ ግራንዴ፣ኩያባ፣ ኩሪቲባ፣ ማኑስ፣ናታል፣ ፖርተፐአልግሬ፣ሬሲፌ፣ ኦሊንዳ፣ ሪዮብራንኮ፣ሪዮ ዲጀነሮ፣ሳልቫዶርና ሳኦ ፖሎ ለኢትዮጵያውያን አመች ምሽጎች ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ በቅርቡ ኢሕአዴግ ባካሄደው በ9ኛው የኢሕአዴግ ጉባኤ ብራዚል በክብር እንግዳነት እንድትሳተፍ  ተጠርታ የነበረች ቢሆንም ‹‹አይመጥነኝም!›› በሚመስል መልኩ ሳትሳተፍ ቀርታለች፡፡ ምናልባት ከዚህ የኢሕአዴግ ጉባኤ በኋላ በተደረገው የ‹‹ብሪክስ (BRICS)›› ስብሰባ የዓለም ዋንጫን በተራ እያስተናገዱ ያሉት የደቡብ አፍሪካና  የብራዚል መሪዎች ስለ ዓለም ዋንጫ፣  ምድባቸውን እየመሩ በመሆናቸው ሊሳተፉ ስለሚችሉ አገራት ሊያወሩ ስለ ኢትዮጵያ ደጋፊዎችም የሚችሉበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ የደቡብ አፍሪካን ምክርና መረጃ ሳትጠብቅም ቢሆን ብራዚል ለአፍሪካ ዋንጫ ድምቀት የነበሩትን ኢትዮጵያውያንን  አስተውላቸዋለች፡፡ በመሆኑም ብራዚል እራሷ ኢትዮጵያ የዓለም ዋንጫውን ብትቀላቀል የምትቀበላት በደስታ ነው፡፡ የዓለም ዋንጫው ዓለማቀፋዊ ተደራሽነትምና የኢትዮጵያውያን በዓለም ዋንጫ የሚያደርጉት የሰላማዊ ትግል ተሳትፎ ምናልባትም ከቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት በኋላ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ጠንካራ ተቃውሞ የሚያደርጉበት ‹‹የትግል ቦታና ድጋፍ›› ያገኙ ያህል የሚታይ ነው፡፡ መቼም የ20ዎቹ ሀብታም አገራት ሰብሰባ ውስጥ በአንድ ጋዜጠኛ  ለሴኮንዶች የሚደረግን ተቃውሞ ትልቅ የሰላማዊ የትግል ስልት መሆኑን ያመነበት፣ ውጤቱንም ያየው ዲያስፖራው ማኅበረሰባችን  በመቶ ሚሊዮን ሕዝብ በቀጥታ በፍቅር የሚታየውን እና ፖሊስ ሳይከለክለው ለ90 ደቂቃዎች ኢሕአዴግን አንገት ማስደፋት የሚችልበትን የብራዚሉን መድረክ እንዲሁ ያልፈዋል ተብሎ አይጠበቅም፡፡

## ብሔራዊ ቡድናችን ባያልፍስ?

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ምድቡን እየመራ ነው፡፡ ምድቡን መርቶ ሲያጠናቅቅ ወደብራዚል ለማለፍ ከ10ሩ የምድብ አሸናፊ ውስጥ ከአንዱ ጋር በደርሶ መልስ ማሸነፍ ይጠበቅበታል፡፡ በአሁኑ ወቅት በብሔራዊ ቡድኑ እየታየ ያለው መሻሻልና በአፍሪካ ዋንጫ በዛምቢያና ናይጀሪያ ላይ ያሳየው ብቃት ብሔራዊ ቡድኑ ሊያልፍ ተስፋ ሰጭ ነው፡፡ ሆኖም ኳስ ነውና ሊሸነፍም የሚችልነት አጋጣሚ የማይታበል ነው፡፡ የብሔራዊ ቡድናችን በብራዚል መገኘቱ ደጋፊዎችም ለሚያሰሙት ድምፅ ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ ሆኖም ይህ ስሜቱን ሊያቀዘቅዘው ይችላል እንጂ ያጨናግፈዋል ማለት አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ አለፈችም አላለፈችም የብራዚሉ የዓለም ዋንጫ ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም ተጫዋቾቹ ባይኖሩም ሜዳው ግን ለኢትዮጵያውያን ክፍት ነው፡፡ ደግሞ አፍሪካ የምትልካቸው አምስት ተወካዮችን እና ሌሎችም በሕዝባችን ዘንድ ተወዳጅ ቡድኖች  ብራዚል ላይ ይቀጥላሉ፡፡ በአፍሪካ ዋንጫ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ከተሰናበተ በኋላም ቢሆን ኢትዮጵያውያን ያገኙትን አጋጣሚ ተጠቅመው

እስከመጨሻው ለማለት በሚቻል መልኩ ድምፃቸውን አሰምተዋል፡፡ ሰንደቅ ዓላማቸውን አውለብልበዋል፡፡ በመሆኑም የብራዚሉ የዓለም ዋንጫ ብሔራዊ ቡድናችን ሊያጠናክረው የሚችለው እድል እንጂ በእሱ ብቻ ሊወሰን የሚችል አይመስልም፡፡ በተለይ ጎይት ሀውስና ሌሎቹ ዲያስፖራው ቀድሞ ድምፁን ሲያሰማባቸው የነበሩ ቦታዎችና አጋጣሚዎች አሁን አሁን እየተለመዱ ወይንም እየቀነሱ በመምጣታቸው የሚያሳድሩት ጫና አነስተኛ መሆኑ ብራዚልን አዲስ ተመራጭ የትግል ቦታ ያደርጋታል፡፡ ምንም እንኳ መሞከሩ የማይቀር ቢሆንም የኢህአዴግ አፀፋም እንቅስቃሴም ቢሆን በብራዚል ቦታ አይኖረውም፡፡ ‹‹ብሪክስ››ን በቀዳሚነት ለምትመራው፣ ለዓለምና ለኢትዮጵያ ሕዝብ 11 በመቶ አደግን፣ ‹‹የመሪ ሌጋሲ››፣ የአባይ ግድብ፣ ‹‹አሸባሪነት››፣ አክራሪነት ድጋፍም ተቃውሞም ሊሆኑ አይችሉም፡፡

## ሰንደቁን እንደ መሳሪያ

ሰንደቅ ዓላማችን ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ከእኛ ለወሰዱት አብዛኛዎቹ የአፍሪካ፣ የካሪቢያና ደቡብ አሜሪካ አገራትም መለያ ምልክት ነው፡፡ እንደአለመታደል ሆኖ ግን ብዙው የዓለም ሕዝብ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለም ያሉትን የሰንደቅ ዓላማ ከኢትዮጵያ ይልቅ የጋና እና የሌሎቹም የአፍሪካ አገራት ምልክትነቱ ያውቀዋል፡፡ እንኳን ድምፅ ማሰማቱ ተጨምሮበት ኢትዮጵያውያን በብራዚል ሰንደቅ ዓላማችን ማስተዋወቁ በራሱ የሚናቅ ዓላማ አይደለም፡፡ በዓለም ዋንጫ ለዓለም የሚተዋወቁት ሰንደቅ ዓላማዋንና ሌሎች ጉዳዮችን ወደዓለም አቀፍ የማስታወቂያ ተመን ብንቀይራቸው የማይሞከሩ ናቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ብራዚል የእኛን ሰንደቅ በምልክትነት ካነገቡት አገራት ደጋፊዎች ጋር በመሆን ተቃዋሚዎች ሰንደቁን ድምፃቸውን ይበልጡን ለማሰማት ሊጠቀሙበት የሚችሉ መሆናቸው ትግሉን የሰንደቁ ቀለማት ያደመቁትና ጠንካራ ያደርገዋል፡፡ ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በምልክትነት የሚጠቀሙት ቤኒን፣ ካሜሮን፣ ማሊ፣ ቶጎ፣ ቡርኪናፋሶና ጋናን የመሳሰሉት አገራት ከእነደጋፊዎቻቸው በደቡብ አሜሪካዋ ብራዚል ባይገኙም ይህን ዕድለኛ ሰንደቅ ዓላማ የሚያውለበልበው አያጣም፡፡ ደቡብ አሜሪካ የራስ ተፈሪያን መፍለቂያና መኖሪያ አህጉር ነች፡፡ ጃማይካ፣ ትንዳንድና ቴቤጎ፣ ጉያና፣ ዶሚኒካ፣ ግራናዳ፣ ሀይቲ፣ብረዚል፣ አርጀንቲና፣ ፓናማ፣ ሜክሲኮ፣ ፔሩ፣ ኮሎምቢያ፣ ቺሊ፣ ዩራጋይ፣ ቬንዙየላና አጠቃላይ ደቡብ አሜሪካና ካሪቢያን ከ6 ሚሊዮን በላይ ከሚሆኑት የአለም ራስ ተፈሪያን ተከታዮች መካከል እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የንቅናቄው ተከታይ መኖሪያ ናቸው፡፡ ዕድሜ ለእነ ማርከስ ጋርቬይና ቦብ ማርሌይ እንጂ ከደቡብ አሜሪካና ካሪቢያን አልፈው ከኮንጎ እስከ ጃፓን ይህን ኢትዮጵያን እንደ ጽዮን የሚቆጥረው በርካታ የእንቅስቃሴው ተከታዮች ተስፋፍተውበታል፡፡ በሁሉም የደቡብ አሜሪካና የካሪቢያን አገራት የራስ ተፈሪያን ማኅበራት ተመስርተዋል፡፡ አብዛኛዎቹ የደቡብ አሜሪካ የራስ ተፈሪያን ንቅናቄዎች ከቀሪው አለም በተሻለ የተደራጁና ስማቸውም ሆነ እምነታቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለኢትዮጵያ ባለቸው ጥልቅ እምነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከኢትዮጵያውያን ባልተናነሰ አንዳንዴም በተሻለ ስለኢትዮጵያ የሚዘምሩ ሕዝቦች ናቸው፡፡

በራስ ተፈሪያዊያን ዘንድ ኢትዮጵያ የምታከብረው ልደት፣ የእትጌ መነን የልደት ቀን፣ አፄ ኃይለሥላሴ ጃማይካን የጎበኙበት ቀን፣ የአፄ ኃይለሥላሴ ልደት፣ የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት፣ ኃይለሥላሴ የነገሱበት ቀን በድምቀት ይከበራል፡፡ የራስ ተፈሪያን ንቅናቄ የነጻነት ንቅናቄ አንድ አካልና ለአፍሪካ ነጻነት ትልቅ አስተዋጽኦ የነበረው ነው፡፡ እስከአሁንም ድረስ ለአፍሪካ አንድነት፣ ዕድገትና የጥቁር ነጻነት ትኩረት ሰጥቶ ይታገላል፡፡ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ደግሞ ከራስ ኮፍያ፣ እስከ ቀለበት፣ቀበቶና የጫማ ማሰሪያ ድረስ የተቀደሰ ምልክታቸው ነውና የሚደግፉት የራሳቸው የሆነ ብሔራዊ ቡድን ቢኖራቸውም ኢትዮጵያ በቋሚነት የምትደገፍ አገር ነች፡፡ እንግዲህ ይህን ሁሉ መሳሪያ በመጠቀም ትኩረት ለመሳብ ብራዚል ትልቅ ዕድል ፈጥራለች፡፡ የብራዚሉ የዓለም ዋንጫ ምልክት ደግሞ ለኢትዮጵያውያን የተሰየመ በሚመስል ሁኔታ ‹‹inspiration›› ወይንም መነቃቃት፣ መነሳሳት የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

በዓለም ዋንጫ የሚጫወቱት አገራት ዋንጫው ትርፍና ከመዝናኛ ያላለፈ ነው፡፡ ለኢትዮጵያ ግን ከዚህም በላይ ዓላማ ይኖረዋል፡፡ በአፍሪካ ዋንጫ ኢትዮጵያውያን ዲሞክራሲ ግንባታን ከጀመሩት ጋና፣ ዛምቢያ፣ ደቡብ አፍሪካና ናይጀሪያ ብቻ ሳይሆን ከዲሞክራቲክ ሪፓብሊክ ኮንጎ ደጋፊዎችም በተለየ ከእግር ኳሱ በላይ ህልውናቸውን የሚወስነው ፖለቲካ ላይ ድምጻቸውን ማሰማታቸውም ለዚህ ማስረጃ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ወደ ብራዚል መሄድ ባይችልም ድምፅን ለማሰማት የሚያስችለው መድረክ በስፋት የተከፈተ መሆኑን አይቴናል፡፡ ቡድናችን ለዓለም ዋንጫው ማለፍ ከቻለ ደግሞ ስሜቱም ሆነ ትግሉ ደማቅና ደማቅ ውጤት የሚያመጣ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያውያን በሶማሊያና ኤርትራም ሳይቀር ወደውጭ ለመውጣት ሌት ተቀን በምንጥርበት በአሁኑ

ወቅት ራስ ተፈሪያኑ ቅድስትና የተስፋይቱ ምድር ወደሚሏት ኢትዮጵያ በመምጣት መሬቷን በጫማ ላለመርገጥ ባዶ እግራቸውን እየኖሩባት ነው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ያልቻሉትን ጨምሮ በብራዚል የሚገኙት ወይንም የሚሄዱት ራስታዎች ለአናብስቶቹንም ሆነ ለደጋፊዎቻቸው የሚሰጡት ትርጉም እኛ የዓለም ዋንጫን ከምናይበት በተመሳሳይ ከተራ ኳስ በላይ ነው፡፡ ራስታዎቹ ኢትዮጵያውያንን መቀበል ልክ እየሱስ በነበረበት ወቅት ወይንም በቅርብ እርቀት የሚያውቀውንና ከቅድስቷ ጽዮን የመጣ ሰው እንደማግኘት ያዩታል፡፡ ለዚህም እንደመንፈሳዊ ዜማ ሁሉ በሬጌ ሙዚቃቸውና በሰንደቅ ዓላማችን እንደሚቀበሏቸው የሚያጠራጥር አይሆንም፡፡

ደቡብ አሜሪካውያን ሌሎች ጭቁኖችን በመርዳት የሚታሙ አይደሉም፡፡ አርጀንቲናዊ ቼ ጉቬራ የኩባና ቮልቪያን ሕዝብ ነጻ ለማውጣት ካደረገው ተጋድሎ ላቲኖቹ ድንበር ዘለል ሰብአዊነትን ተምረውበታል፡፡ ቼ ደቡብ አሜሪካዎችን ነጻ ከአወጣ በኋላም ቢሆን ወደጭቁኗ አፍሪካ በመምጣት ለነጻነት የቻለውን ያህል ታግሏል፡፡ ይህም ላቲኖቹ የዝሆን ቀንድን በኮንትሮቫንድ ከሚያጋብሱት ተራ ዜጎቿ ጀምሮ ለእርስ በእርስ ጦርነት መሳሪያ ለመሸጥ፣ ርካሽ እቃ ለማራገፍ፣ ነዳጅና አልማዝ ለመመዝበር ወደ አፍሪካ ከምትመጣው ቻይና የተለየ ዓላማ እንዳላቸው አስረጅ ነው፡፡ በቼ ጉቬራ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ንቅናቄ አነስተኛ በመሆኑ ወደ ኢትዮጵያ ባያቀናም ነጻ ያወጣት ኩባ ግን በክፉ ቀን ደርሳልናለች፡፡ አሁን ስልጣን ላይ በሚገኙት ገዥዎቻችን መንገድ መሪነት እስከድሬዳዋ የወረረንን ተስፋፊው የሶማሊያ ጦር ያሸነፍነው በኩባዎች ረዳትነት ነው፡፡ በአጠቃላይ ደቡብ አሜሪካ ውስጥ ብሔራዊ ቡድናችን፣ ደጋፊዎች፣ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ያነገቡ አገራት፣ ራስ ተፈሪያን ተጠቅሞ ትልቅ ትኩረት መሳብ ይቻላል፡፡ ሰብአዊነትን መሠረት ያደረገ ድንበር ዘለል ትግል አዲሳቸው ያልሆነው ደቡብ አሜሪካዎች በመልክም ቢሆን ለኢትዮጵያውያን ቅርብ በመሆናቸው በዚህ የዓለም ዋንጫ የኢትዮጵያውያንን ጥምረት የሚፈራ ኃይል ጠያይምና ቀዮችን ላቲኖች አይቶ ሙሉ ሜዳውን ኢትዮጵያውያን እንደያዙት ሊረዳ ይችላል፡፡ መቼም በታሰበው መልኩ ከተሳካ ኢሕአዴግ የዓለም ዋንጫ በብራዚል እንዲዘጋጅ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች እጅ አለበት ማለቱ የማይቀር ነው፡፡ ደግነቱ ብራዚል እንደ ሶማሊያ ወታደር የሚልኩባት ወይንም እንደ ኤርትራ የሚዝቱባት አገር አይደለችም፡፡

## ተቃዋሚዎቻችን ምን ያህል ይጠቀሙበታል?

ደቡብ አሜሪካ ለኢትዮጵያውያን ምቹ ናት፡፡ ዋናው አጋጣሚውን የመጠቀምና ያለመጠቀም ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች በሥርዓቱ አፋኝነትም ይሁን በራሳቸው ድክመት አጋጣሚዎችን ሲጠቀሙ አይስተዋሉም፡፡ ለአብነት ያህል የየኔሰው ገብሬን መሰዋት እና ሌሎች አጋጣሚዎችን ተቃዋሚዎች አንድ አገር ወዳድ ዜጋ ከሚያደርገው በላይ ተጠቅመውበታል ለማለት አያስደፍርም፡፡ አንድ የሰላማዊ ትግልን እከተላለሁ የሚል አካል እንደ ምርጫ፣ የሰዎች መፈናቀል፣ እስራትና የመሳሰሉትን ትልልቅ ክስተቶች መጠበቅ ባይኖርበትን እነዚህ ክስተቶች ሲፈጠሩ ግን ለአገር በሚጠቅም መልኩ ማራገብና አጀንዳ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

ለምሳሌ ያህል በግራዚያኒ ላይ የተደረገውን ተቃውሞ ኢሕአዴግ ለጊዜው በማስቆሙ ብቻ መቆም የለበትም፡፡ ተቃዋሚዎችም ሆኖ ሌሎች አካላት በተደጋጋሚ ሰልፉ በመጥራት አጀንዳቸው ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኢሕአዴግ ራሱ እስኪወጣ አሊያም በግልጽ ምን አገባኝ እስኪል ድረስና ከዚያም በኋላ ተቃዋሚዎች አጀንዳቸው አድርገው ቢንቀሳቀሱ ትልቅ የትግል ስልት መሆን የሚችል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሕዝብና መንግሥት በየፊናቸው የሚግባቡበት ወይንም የሚጠረጥሩት ምልክት ማስረጽ አስፈላጊ ቢሆንም ኢትዮጵያውያን እየተጠቀምንበት አይደለም፡፡ ይህ ስልት በአንድ ወቅት የጀርመኑን ናዚ ይቃወሙ የነበሩ ወጣቶች ዋነኛ ስልት ነበር፡፡ ፀረ ናዚ ወጣቶች ናዚ የምዕራባዊያን ነው ብሎ የሚቃወመውን የፀጉር አቆራረጥና አሠራር፣ አለባበስ፣ ሙዚቃ ሙሉ በሙሉ ወይንም በሙቀራረብ መልኩ አዘውትረው ተቃውሟቸውን ገልጸውበታል፡፡ የጀርመን ሙዚቃዎችን በአሜሪካ የሙዚቃ ስልት ተጫውተው ሥርዓቱ በግልጽ ለመቃወም እንዳይችል ነገር ግን በጥርጣሬ እንዲሞላ አድርገውታል፡፡ የጀርመን ሕዝብ እንደ ፋሽን መከተል ሲጀምር ሥርዓቱ ሕዝቡን በጥርጣሬ መመልከትና በፍርሐት መራድ ጀምሮ ነበር፡፡ አንዳንዴ በመመሳሰል ብቻ የሚታሰሩ ጀርመናውያን ወጣቶች የሥርዓቱን አስከፊነት ሳይወዱ በግድ በማየታቸው ዋነኞቹ የስልቱ አቀንቃኞች ሆነዋል፡፡

በቅርቡ ኢትዮጵያ ውስጥ ግራዚያኒን ለመቃወም በተጠራው ሰልፍ ሰልፈኞቹ ቀይ ቲሸርት ለብሰው ስለነበር ፖሊስ አላፊ አግዳሚውን ቀይ ለባሽ አስሯል፡፡ ሰልፈኞቹ ከእስር ቤት ሲወጡ እስር ቤት የቀረው ፖሊሶቹ የፈሩት ቀይ ልብሳቸው ብቻ ነው፡፡ ቀይ ልብስ በበርካታ ሰዎች ዘንድ የሚዘወተር የአዘቦት ልብስ ነው፡፡ ‹‹ቫላንታይን›› እና ሌሎች አንዳንድ አጋጣሚዎች ሲሆኑ ደግሞ በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ ይለበሳል፡፡ ይህን

ተከትሎም ቀይ ልብሶችንም ለኢሕአዴግ አንድ የመቃወሚያ ምልክት ማድረግ ቢቻል በቤተ መንግሥት ጥግ የሚያልፉትን ጨምሮ የአገራችን ቀይ ለባሾች በሥርዓቱ ላይ ጥርጣሬን የሚፈጥሩ ይሆናሉ። በአደባባይ ብሶቱን መግለጽ የማይችለው፣ ሚዲያና ጠንካራ ተቃዋሚ ያጣው ወጣት በቀይ ፋሽን ኢሕአዴግን ማብገኑ የማይቀር ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ኢሕአዴግ ቀይ ለባሹን ሰው ብቻ ሳይሆን አብዛኛው አካሉ ቀይ የሆነውን የቢሾፍቱውን አውቶውስ ሁሉ በአሉታዊነት አለመመልከቱን እጠራጠራለሁ።

# ቀዩ መስመር

የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር አቶ መለስ ዜናዊ ከፓርላማ ንግግሮቻቸው ባንዱ ‹ቀይ መስመር› ሲሉ የገለፁት መስመር ነበር፡፡ ያ ቀይ መስመር ዛሬ ስሙ በቀጥታ ባይነሳም በአዲሱ ጠቅላይ ሚንስትርም እንደሚታወቅ ለቪኦኤ የእንግሊዝኛው አገልግሎት የሰጡት ቃለ ምልልስ ያሳብቃል፡፡ ቀዩ መስመር ለኛ የማይታየን ነገር ግን ለገዢዎቻችን ብቻ የሚታያቸው፣ እኛ ሳይገባን ፍርድ ቤቱ ገብቶት የሚፈርድበት እውነት ሆኖ አልገለጥልህ ቢለኝ ይህን ጻፍኩ፡፡

ደርግ ስሙ የገነነበትን ጭቆና ኢሕአዴግ አጠናክሮታል፡፡ በጊዜው ‹‹አስገንጣይ፣ አሸባሪ፣ ድልድይ አፍራሽና ነጭ ለባሽ›› እየተባሉ ይጠሩ የነበሩት አሁን ባለተራ ሆነው ሌሎችን እነርሱ ይጠሩበት በነበረው ስም ለመጥራት በቅተዋል፡፡ በዚህ አያያዝ ደርግ እነርሱን ከፈጠረ እነርሱም በበኩላቸው ሌላ ጨቋኝ/አምባገነን ለመፍጠር እየተጉ ነው ያስብላል፡፡

እስከዛሬ ብለነው፣ ብለነው የነበረውን ለአዲሱ አመራር (‹‹አዲስ›› ካለ) መድገም ሳይኖርብን አይቀርም፡፡እናም እንጠይቃለን?ለምን በወረቀት ላይ ያለውን ዲሞክራሲ መሬት ላይ አታወርዱትም? ለስንት ዓመታትስ አንድ ፓርቲ ለስልጣኑን ለማስጠበቅ ብቻ እንዲህ ይተጋል? ለምንስ ዜጎች ወደ ፍርሐት ጥግ ተገደው ይወሰዳሉ? ለምንስ መብቶቻቸው ይሸራረፋሉ? ለምንስ ነገሮች ከሕግ ይልቅ በባለስልጣን ይሁንታ ይከናወናሉ? (ይህ ከ80ሚሊዮን ሕዝብ ሲቀነስ 5 ሚሊዮን /የፓርቲ አባላት/ ሕዝብ ጥያቄ ነው! መቼም የፓርቲ አባላት እዛው የመጠየቅ እድል አላቸው ብዬ ነው፡፡)

‹‹ደርግ ያለ ወያኔ አይኖርም›› ይባል የነበረው አባባል ዛሬም ራሱን ደግሞ፣ ዛሬ ኢሕአዴግዎችም በተራቸው ግንቦት ሰባትን፣ አርበኞች ግንባርን፣ ኦብነግንና ሌሎችንም ፈጥረው፣ ያለነርሱ የማይኖሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡የግንቦት ሰባት እና መሰል ድርጅቶች መኖር የጋዜጠኞች ማሰሪያ ሰበብ፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ማስፈራሪያ እና የሚዲያዎች ማጥፊያ ሰበብ ሆኗል፡፡

እነዚህ መራር እውነቶች ኢትዮጵያውያንን ከአገራችን ሌላ አገር ሊያስመኙን ከጀመረ ቆየ፡፡ በአገራችን እንዳሰብነውና እንደፈቀድነው መኖር ዘበት እየሆነብን እንደሆነ የውጭም የውስጥም ቡድኖች ምስክርነት አያሻንም፤ ኑሯችን ይነግረናልና፡፡ ሕግ ሲሻል በመመሪያ ሲብስ በባለስለጣን ይጣሳል፣ ዜጎች እንደሁለተኛ ዜጋ ይገፋሉ፣ መብት ከወረቀት ላይ በቀር የለም፤ መብት ጠያቂዎች ስለምን ሌላ ታርጋ ይለጠፍባቸዋል?

ምንም እንኳን የጥላቻ ፖለቲካ ያራምዳሉ እያለ ገዢው ፓርቲ ቢከሳቸውም አገር እያስተዳደርኩ ነው ከሚለው መንግስት ይልቅ ሰላማዊ ትግል የሚያካሂዱት ተቃዋሚዎች ኃላፊነት ይሰማቸዋል፡፡ ቢያንስ እነርሱ ነፍጥ አንግተው ድልድይ እናፍርስ ከማለት ይልቅ፣ በመገፋት ውስጥም ቢሆን በሐሳብ ለመሸናነፍ እየታገሉ ነውና፡፡

ዛሬ ላይ እየለማች ነው የምትባለው አገራችን በደርግ 17 ዓመታት የአገዛዝ ዘመን (የሚከተለው ርዕዮተ ዓለም ችግር ቢኖርበትም፣ ባይኖርበትም) እንዳትለማ ጋሬጣ የሆነበት፣ ትግራይን እንገነጥላለን ያሉ ለደርግ የሥራ ጊዜ ዕድል ወይም ፋታ እንኳን መስጠት ያልቻሉ የዛሬዋ ገዢዎችም የተጠያቂዎች ድርሻ አላቸው፡፡ ለአገራችን የድህነት አረንቋ ውስጥ መውደቅ ተወቃሹ የደርግ ርዕዮተ ዓለም ብቻ ሳይሆን፣ ደርግ መሥራት የሚችለውን እንዳይሠራ፣ መነጋገርም ይቻል አይቻል እንዲያሳይ ዕድል ያልፈቀዱለት እነዚህኞቹን ተዋጊ አካላትም ጭምር ነው፡፡

በትግል ወቅት፣ በድልድይ አፍራሽነት፣ በሕዝብ ተቋማት ዝርፊያ እና የሰብዓዊ እርዳታን ለመሳሪያ ግዢ በማዋል፤ በነፃነት ትግል ስም በጦርነት አድምቶና ደምቶ በተራው ከሚጨቁነው ያለጦርነት በመግባባት ሰላማዊ ትግል የሚያካሂደው ተቃዋሚ ኃይል በብዙ መስፈርት ብሪት ካነሱት የተሻለ ኃላፊነት እንደሚሰማው ያሳያል፡፡ እነዚህ ዜጎች ምንም እንኳን የየራሳቸው ድክመት ቢኖርባቸውም፣ ያለግድያ ሊመጣ የሚችለውን ለውጥን ተመኝተዋል፡፡ ከነሱ በባሰ ለውጥን አመጣን የሚሉት ካስፈለገ ብረት ማንሳት ወይም ሕጉን ያለአግባብ መጠቀም ይቀናቸዋል፡፡

አለማየሁ ገላጋይ ፍትሕ ጋዜጣ ላይ ባሰፈረው በአንድ ጽሑፉ እንዳለው ‹‹ክብደቱን የማያውቀው ኢህአዴግ ለእስክሪብቶ ታንክ ያዝልሀል፡፡›› ሐሳብን በሐሳብ የመመከት አቅም ማጣት ሐሳብን በማፈን፣ ሌሎችን መቀጣጫ በማድረግ፣ የአሸባሪነት ወይም ሌላ ታርጋ በመለጠፍ ዜጎችን ማሳቀቅ ሕጋዊ ዕውቅና በተሰጠበት አገር መነጋገርን

ከባድ ያደርገዋል። እንደኔ እንደኔ፣ ተነጋግሮ መተማመን የማይችል፣ ወይም ዱላ የሚቀናው አንድም ሐሳብ የለውም፣ አሊያም ሐሳቡ እንደማያሳምን ራሱም ያውቀዋል።

## ዲሞክራሲ በሌለበት ለምን ስሙ ይነሳል?

መንግስታችን እርሱ ሲፈልገው ካልሆነ በስተቀር የማያከብረውን ሕገ-መንግስት መብት አላችሁ ብሎ ማሳመን ከባድ ሥራ ይመስለኛል። ከሕገመንግስቱም ባሻገር አገራችን የተፈራረመቻቸው ዓለምአቀፍ ድንጋጌዎችና ስምምነቶች መብታችንንን ደጋግመው ያስታውሱናል፤ እኛም ወግ ደረሰን ብለን ስንጠቀምባቸው ከበስተኋላችን የማናውቀው ታርጋ ተለጥፎብን እናገኛለን። በዚህ ጊዜ እና ‹‹አይደለሁም›› ብንልም (ከመንግስት ያወቀ ቡዳ ነው እንዲል መሐመድ ሰልማን ‹‹ፒያሳ፤ መሐሙድ ጋ ጠብቂኝ›› ባሰኘው መጣጥፉ) ‹‹አዋቂዎቹ›› ነህ ብለዋልና ‹‹መግባት ወይም መውጣት››፣ አልያም ‹‹ጥምር አገልጋይ›› መሆን የሚባል ቁርጥ ምርጫ ይሰጡናል።

አሁን ደግሞ አዲሱ ጠ/ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም የቀድሞ አለቃቸው ቃና በሚመስል መልኩ፣ሁለት ኮፍያ አድርገን እንደምንጫወት ይነግሩን ጀምረዋል። የአንድ ዜጋ መብቱን ተጠቅሞ መጻፍ፥ መጻፍ ሳይሆን አሸባሪነት መሆኑ አሁንም ከቀጠለ ዴሞክራሲ ከስሙ በቀር በተግባር የታለ ለሚል ጠያቂ መልሱ ምንድነው የሚሆነው?

ቀዩ መስመር በጨቋኝ በኩል ሲታይና በተጨቋኝ በኩል ሲታይ ቦታው የተለያየ ነው። ለጨቋኝ፤ ስልጣኑን፣ ገመናውን፣ ባዶነቱን፣ ሙስናውን የሚሳብቅበት፣ ይህም ሥራውን ተአማኒነት አሳጥቶ ስልጣን የሚነሳው መስሎ ከታየውና፤ ያገባኛል ባዮች ተደማጭነትን ካገኙ ያ ‹ቀይ መስመር› ማለፍ ነው።

ለተጨቋኝ፤ መብቱ - ሕገመንግስቱ ላይ የተቀመጠለት፣ ገደቡ - አገሩ እንጂ ባለስልጣን ወይም ፓርቲ አይደለም። ያገሩንም ጥቅም አሳልፎ አይሰጥም። የአገራችን ሕጎች ሆን ተብለው ለብዙ ትርጉም ተጋላጭ እንዲሆኑ ተደርጓል፣ በስህተት ያልተደረጉ ካሉም በስህተት እንዲተረጎሙ ይደረጋሉ እንጂ ተቃዋሚዎችን ከማስከሰስ አይመለሱም። ይህ ደግሞ ሆነ ተብሎ - ለስልጣን ጥበቅና ሲባል የተደረገ እንጂ፣ የቃላት ድህነት ኖሮብን የተፈጠረ እንከን አይደለም።

የሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 9፣ የሕገ መንግሥት የበላይነት በሚለው ስር ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ፡- *ሕገ መንግሥቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ነው። ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፤* ይላል (መስመር የኔ)። በሕገ መንግሥቱ ከላይ የተጠቀሰውን ይዘን አንቀጽ 10 ደግሞ ስለ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲህ ይላል፡-

1. ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው፣
2. የዜጎች እና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ።

በዚህ ሐሳባችንን ካጠናከርን ዘንዳ አንቀጽ 29 የአመለካከት እና ሐሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት ስር ደግሞ፡-

1. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል። (የእኔ አስተያየት፡- እውነታው ስንይዝ እንፈረጃለን የሚለው ነው)
2. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሐሳቡን የመግለጽ ነጻነት አለው። ይህ ነጻነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነጻነቶችን ያካትታል። (የእኔ አስተያየት፡- አለ ብለው ቢተነፍሱ እንደማስረጃ ተቆጥሮባቸው የተለጠጠ ትርጉም ባለው ‹እንዳበጃሽ› በሆነው ሕጋችን ዜጎች ለስደትና ለእስር ተዳርገዋል)

መብቴን በቴሌቪዥን ብቻ ማየት አልፈልግም ወረቀት ላይ የተጻፈው ብቻውን ምንም አያደርግልኝም የምንፈልገው መብታችን ወደመሬት ይወርድ ዘንድ ተግባራዊ እንዲሆንና ሕግ እንዲከበር ነው። እናስቀጥላለን የተባለው ‹ልማት› ይቀጥል፣ ፍረጃውና ዜጎችን ማግለሉ ግን አያግባባንምና ይቁምልን። መቼም የማንግባባበትን ቀይ መስመር ማስመሩ የተሻለ ጨቋኝ ለመሆን መጣጣር ካልሆነ በቀር የትም አያደርስንም።

# "መክሸፍ" እንደ ኢትዮጵያ ሚዲያ - መጽሔቶች

ወቅቱ መጽሔቶች እንደአሸን የፈሉበት፣ ጋዜጦች ደግሞ ቁጥራቸው የተመናመነበት ነው፡፡ ብዙዎቹ [የአማርኛ] መጽሔቶች የሚወጡት በየ15ቀኑ ቅዳሜ ቀን ነው፡፡ ጥቂቶች በወር አንዴ እና አዲስጉዳይ ብቻ በየሳምንቱ ይታተማል፡፡ በመጽሔቶቹ ታሪክ አንጻራዊ ደረጃ ሊሰጠው የሚችለው እና የራሱን ስም (ብራንድ) እየገነባ ነው ሊባል የሚችለው አዲስጉዳይ ነው፡፡ በየሳምንቱ መውጣቱ፣ የመጽሔት ቅርጽ (structure) መያዙ፣ በርካታ ጸሐፊያን እና አምደኛ ያሉት መሆኑ ለዚህ አስተዋጽኦ አድርጎለታል፡፡ ሌላው ቀርቶ አዲስ ጉዳይ በየ15 ቀኑ፣ ከዚያም በየሳምንቱ መታተም መቻሉ በራሱ ሌሎቹንም ስቧቸዋል፡፡ ባለሙሉ ቀለም ለመሆንም የመጀመሪያ አርኣያቸው ሆኗል፡፡ ይሁን እንጂ አዲስጉዳይም ቢሆን በተለይ ከይዘት ጥንካሬ ትችት ማምለጥ አይችልም፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን አዲስ ጉዳይን እና ሌሎቹን መጽሔቶች በአንድ መስፈርት መመዘኑ ተገቢ ስለማይሆን እሱን ነጥለን ትተን ሌሉቹ /አብዛኞዎቹ መጽሔቶች/ ላይ ያሉትን ችግሮች እና "ከሽፈዋል"፣ በአዲስ መንገድ ትንሳኤ ያስፈልጋቸዋል ብለን እንከራከራለን፡፡

በማስተዋል አሳታሚ ከተገዛ በኋላ የተለየ ጥንካሬ ያላቸው ፖለቲካዊ ትችቶችን በበርካታ ጸሐፍት ያስተናግድ የነበረው አዲስ ታይምስ ጋዜጣም ተስፋ ሰጪ ነበር፡፡ ነገር ግን የአዲስ ታይምስ ሕትመትም ለጊዜው በመቋረጡ በዚህ ጽሑፍ አንዳስሰውም፡፡

## ይዘት

ለዚህ ጽሑፍ ሲባል ያገላበጥናቸው መጽሔቶች ሁሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ ከአንድ፣ ሁለት በቀር ቋሚ አምድ የላቸውም፡፡ ይህም የተዘበራረቀ ሐሳብ ያላቸውን ጽሑፎች እዚህም እዚያም በመሰደር፣ የአንባቢን ሐሳብ በአንድ ማኖር እንዲሳናቸው አስገድዷል፡፡ ይህ ጉዳይ ተጽዕኖውን የሚያሳድረው በአንባቢዎቻቸው ብቻ ሳይሆን በመጽሔቶቹም በራሳቸው ላይ ነው፡፡ መጽሔቶቹ በየጊዜው የሚያወጧቸውን ርዕሰ ጉዳዮች በተመለከተ ሦስት እና አራት ነገሮችን ብቻ ማስተዋል ይችላል፡፡ እነዚህም፡- የቴዲ አፍሮ የግል እና የግል ያልሆኑ ጉዳዮች፣ የሃይማኖት ልዩነት እና መከፋፈል አጀንዳዎች፣ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ጉዳይ እና አሁን ደግሞ - ገበያው ይጠይቃልና - የአገር ውስጥ ፖለቲካ ጉዳዮች ናቸው፡፡

መጽሔቶቹ በነዚህ ጉዳዮች ላይ እንደየወቅቱ ወረት ‹‹መንደረተኛ›› ሊባል በሚችል መልኩ ጉዳዮችን ያራግባሉ፡፡ ነገር ግን በጽሑፎቻቸው አንጽሮተ-ዕይታ ለመጨመር አይሞክሩም፤ ሌላው ቀርቶ አንዱን አጀንዳ እጅግ በሚያሰለች መልኩ ለረዥም ጊዜ ይዘው ማመንዠክ ይወዳሉ፡፡ እንደምሳሌ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማርያም ስለጤፍ መወደድ መንስኤ ብለው የተናገሩትን ብዙዎቹ መጽሔቶች እንደርዕስ መዝዘው ይይዙት እና ነገር ግን ምንም ፋይዳ የሌለው ትንተና ከርዕሱ የበለጠ ዋጋ በሌለው ሐተታ ያቀርባሉ፡፡ (ይህ ዜና ማመንዠክ አባዜ የቀድሞው ጠ/ሚኒስተር ሞትን እንዲሁም ተከትለው የመጡ የፓለቲካ ወሬዎችን ይጨምራል፡፡)

## የጽሑፎቹ ወጥነት - "ኢቪዲኦን ወደ ወረቀት?"

መጽሔቶቹ ብዙ ቦታዎች ላይ የጽሑፎቹን ጸሐፊ ስም ሳይጠቅሱ ያልፋሉ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ሁለት ነው፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት ጽሑፎቹ ወጥ ሥራዎች (originals) ስላልሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ጥቂት አባላት ብቻ ስለሚኖሯቸው እና እነዚያው ጸሐፍት ሁሉንም ነገር (ፖለቲካውን፣ ፋሽኑንም፣ ኢኮኖሚውንም፣ ማኅበራዊውንም፣ መዝናኛውንም) ብቻቸውን ስለሚጽፉት እንዳይታወቅ ከመፈለግም ነው፡፡

በሰው ኃይል እጥረትም ይሁን በፈጠራ ማነስ መጽሔቶቹ ወጥ ያልሆኑ ሥራዎችን ሲያትሙ ስም እንኳን ለመጥቀስ የሚዘነጉበት፣ የዋነኛውን ጸሐፊ ፈቃድ ለማግኘት እንኳን የማይገዱበት እና ኢትዮጵያዊ ካልሆነ እንዲያውም የራሳቸው የፈጠራ ጽሑፍ እንደሆነ አስመስለው የሚያቀርቡበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡

እዚህ ላይ በምሳሌ ሳይጠቀስ የማይታለፉት የዳንኤል ክብረት እና የአቤ ቶክቻው ጽሑፎች ናቸው፡፡ የዳንኤል ክብረት ጽሑፎች አዲስጉዳይ ላይ ታትመው፣ ከዚያ የግል ድረገጹ ላይ ከወጡ በኋላ ከዚያ ተገልብጠው መልሰው ሌሎች መጽሔቶች ላይ ማንበብ የተለመደ ድራማ ነው፡፡ አቤ ቶክቻውም በግል ድረገጹ ላይ የሚያትማቸው ፖለቲካዊ ወጎች ከአንድ በላይ በሆኑ መጽሔቶች ላይ በአንድ ቀን ታትመው የሚወጡበት አጋጣሚ በርካታ ነው፡፡

በዚህ እና በሌላም መንገድ መጽሔቶቹ ግፋ ቢል ከ5 እምብዛም በማይበልጡ፣ እንዲያውም ብዙ ጊዜ የማይጽፉ ነገር ግን ለመጽሔቱ ሞገስ ሲባል ስማቸው ብቻ በሰፈሩ አምደኞች ስም ከለላ በጥቂት ጸሐፊዎች ቁንጽል ሐሳብ በሚስተናገዱ በርካታ ጽሑፎች እና በይነመረብ እና ማኅበራዊ አውታሮች ላይ በሚገለበጡ ጽሑፎች ጥገኝነት ገንዘብ ብቻ በመሥራት ላይ ናቸው፡፡ ይህንን የመጽሔቶቻንን ነገር ያየ ሰው ኢቪዲኦን ወደ ወረቀት የመቀየር ሥራ ላይ ብቻ መጠመዳቸው በሐፍረት አንገት ሊያስደፋው ይችላል፡፡

## እውነታ ማዛባት

የመጽሔቶቻችን ሌላኛው ትልቁ ችግር እውነታ ማዛባት ነው፡፡ ለምሳሌ ቆንጆ መጽሔት በቁጥር 34 እትሙ ‹‹ብርቱካን ስዩን በነጻ ለቃለች›› የሚል ነገር በጽሑፉ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ብርቱካን አቶ ስዩን በዋስትና የለቀቀች መሆኑን መረጃ ለሌለው አንባቢ የተለየ እውነት ሰጥቶ ያሰናብተዋል ማለት ነው፡፡

መጽሔቶች እውነታውን የሚያዛቡት በስህተት ብቻም አይደለም፡፡ ገንዘብ የተቀበሉለትን (በተለይ የጥበብ) ሥራ አዋድዶ በመጻፍም አሳፋሪ ተግባር ውስጥም አይታጡም፡፡ በዚህ መደድ፣ ለምሳሌ ባለፈው ቅዳሜ (ጥር 19/2005) የወጡት ሎሚ እና ማራኪ መጽሔቶች በከተማዋ ምንም ሊባል በሚችል መንገድ ያልተደመጠውን የብርሀኑ ተዘራ ‹‹ተበቺሳ›› አልበም እንዴት አሞካሽተው እንዳለፉት ማንበብ ጥርጣሬውን ለማረጋገጥ መንገድ ይሆነናል፡፡ ሎሚ (ቁጥር 40) ‹‹ተበቺሳ ከሚገባው በላይ ነው ተቀባይነቱ›› ሲል፤ ማራኪ (ቁጥር 33) ደግሞ ‹‹ብርሀኑ ተዘራ ገበያውን እየመራ ነው›› ይለናል፡፡ ጽሑፉን ሲያስነብቧችሁ ግን ማስረጃቸው የቃላት ድርደራ ብቻ ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡

## ርዕሰ አንቀጽ

የመጽሔቶቹ ድክመት ጣሪያ የሚነካው በርዕሰ አንቀጾቻቸው ነው፡፡ ብዙዎቹ መጽሔቶች ለ40 ገጽ እትማቸው ግማሽ ገጽ ርዕሰ አንቀጽ መጻፍ አይችሉም፡፡ የሚጽፏቸው አንቀጾችም ቢሆኑ ጠንካራ ጉዳዮችን ለመንካት የማይደፍሩ፣ አቋም ይዘው የማይሞግቱ ናቸው፡፡ ሎሚ መጽሔት ‹‹ማንዴላ በነጻ ወታደራዊ ስልጠና ያገኙባት አገር በመሆኗ፣ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች ወደደቡብ አፍሪካ ለመሄድ ቪዛ ፍለጋ መቸገር የለባቸውም›› የሚል መከራከሪያ ርዕሰ አንቀጹ ላይ አስፍሯል፡፡ ቆንጆ መጽሔት ርዕሰ አንቀጽ የጻፈለትን ጉዳይ (የውኃ ክፍል፣ ቴሌ እና መንገድ ትራንስፖርት ተስማምተው እንዲሰሩ የሚመክር አንቀጽ) ዋና ትንታኔ ‹ሦስቱ ባዶ ወንበሮች› በሚል ጽሑፍ አስቀምጧል፡፡ ሆኖም ጽሑፉ የተወሰደው ከኤፍሬም እሸቴ (አደባባይ) የግል ድረገጽ ላይ ነው፡፡ ኤፍሬም በመጽሔቱ ላይ በአምደኝነትም ሆነ በአዘጋጅነት ስሙ አልሰፈረም፡፡

ባለፈው ቅዳሜ (ጥር 19/2005) ከወጡት መጽሔቶች ሁሉ በአንጻሩ ጥሩ ርዕሰ አንቀጽ ይዞ ወጥቷል ሊባል የሚችለው ላይፍ መጽሔት ሲሆን ‹‹ኢቲቪ የመንግሥት ሌባ?›› የሚል ጥያቄ አቅርቦ በአንጻሩ የተሻለ ለመሞገት ሞክሯል፡፡፡፡

## የሽፋን ገጽ እና የገጽ ቅንብር

የዲዛይን ጉዳይ ሌላኛው የመጽሔቶቻችን አንባቢዎች የራስ ምታት ነው፡፡ የሽፋን ገጽ ዲዛይኖች ብዙውን ጊዜ በብዙ ምስሎች የታጨቁ ከመሆናቸው የተነሳ የትኛውን አይተን፣ የቱ ላይ ማተኮር እንዳለብን ራሱ ግራ ያጋባሉ፡፡ ሊያ መጽሔት (በቁጥር 20) በአንዲት የሽፋን ገጹ ላይ ብቻ የቴዲ አፍሮ፣ ኃ/ማርያም ደሳለኝ፣ ሰብለ ተፈራ፣ አማኑኤል በቀለ፣ መኣዛ መንሥቴ እና ‹ፎርቹን› ጋዜጣ EPRDF Generation በሚል ርዕስ ከረዥም ጊዜ በፊት ለጻፈው ጽሑፉ የተጠቀመበትን ጀርባቸው ብቻ የሚታዩ 9 ወጣቶች ምስሎች አትሞ ወጥቷል፡፡

ሎሚም (በቁጥር 40) እትሙ ሰባት የውስጥ ታሪኮቹን ርዕስ በምስል አስደግፎ ሽፋን ላይ አትሟቸዋል፤ ላይፍ መጽሔትም (በቁጥር 99) አምስት የውስጥ ታሪኮቹን ምስል ሽፋን ገጹ ላይ አውጥቷል፡፡ መጽሔቶቹ በተጨማሪም በውስጥ ገጾቻቸው ቋሚ የሚባል የጽሑፍ አቀማመጥ፣ የፎንት መጠን እና ዓይነት አመራረጥ፣ የምስል አደራደር የላቸውም፡፡ ይህ ሁሉ ተደማምሮ ሲታይ የአንባቢን የማንበብ ፍላጎት ጥርቅም አድርጎ ለመዝጋት ሲባል የተፈጠሩ ያስመስላቸዋል፡፡

## ተስፋ ሰጪዎቹ

መጽሔቶቹ በዚህ ሁሉ የመክሸፍ አደጋ ውስጥ ሆነውም እንኳ ተስፋ ሰጪዎች ከውስጣቸው አይታጡባቸውም፡፡ እንደምሳሌ ዕንቁን እና ቁምነገርን መውሰድ ይቻላል፡፡ ዕንቁ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ የሆኑ ጽሑፎችን በበርካታ ቋሚ አምደኞች እና አዘጋጆች፣ በተወሰነላቸው ርዕሰ ጉዳዮች እና ሙያዊ ዕውቀቱ ባላቸው ሰዎች እያስተናገደ በየ15 ቀኑ የሚታተም መጽሔት ነው፡፡ (የይዘታቸው ጉዳይ ገደቡ እንዳለ ሆኖ) ቁምነገርም በተለይ በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከአብዛኛዎቹ መጽሔቶች ተርታ ለመውጣት የመሻሻል እርምጃዎችን ለማድረግ እየሞከረ መሆኑ የሚደነቅ ነው

## የከሸፉትን ማን አከሸፋቸው?

ጥያቄው በጥናት የተደገፈ መልስ ያስፈልገዋል፡፡ ሆኖም ከአክሻፊዎቻቸው መካከል ፈጣሪያቸው ኢሕአዴግ እንዳለበት መናገር ቀላል ነው፡፡ ኢሕአዴግ የግል መገናኛ ብዙኃንን ከፈቀደ በኋላ ቀስበቀስ፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እየገደላቸው ነው፡፡ ስስ ወይም ፋይዳ የሌላቸውን ጽሑፎች ብቻ የሚነግሡበትን ባሕል የፈጠረውም የቁጥጥር ፍቅሩ ነው፡፡ ጠንካራ እና የተሻለ ይዘት ያላቸው የሕትመት ውጤቶች በአንባቢ እጦት ሳይሆን በኢሕአዴግ በጎ ፍቃድ እጦት ከገበያ በአጭሩ ይሰናበታሉ፡፡ አስተዳደራዊ ተግዳሮቶችን መፍጠርና ሲብስም የሕግን ከለላነት መጠቀሚያ የሚያደርገው መንግሥት መጽሔቶችን "አደጋ ወደሌለበት ማኅበረሰባዊ ለውጥ ወደማያመጣ ጨዋታ" ገፍቷቸዋል፡፡ ነገር ግን በክሽፈቱ ውስጥ የአሳታሚዎቹ ለሥራ ጥራት ቁርጠኛ አለመሆን እና ትርፍ ተኮር መሆን ትልቅ ሚና ያለው መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡

አሁን ነጻ ጋዜጣ ማሳተም በኢትዮጵያ ‹‹የማይቻል›› ደረጃ እየደረሰ ያለበት ነው፡፡ ብዙዎቹ የግል ማተሚያ ቤቶች ማተም የሚችሉት መጽሔት በመሆኑ እና ፖለቲካዊ መረጃዎችን ለማግኘት ሕዝቡ ረሀቡን በመጽሔቶች እያሳየ በመሆኑ መጽሔቶቹ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ተገደዋል፡፡ ነገር ግን አሁን ያለው የመጽሔቶች የአቅርቦት ባሕል መቀየር አለበት፡፡ ስለዚህ ትልቁ ቁምነገር ግን መጽሔቶቹን ማን አከሸፋቸው ሳይሆን እንዴት ወደትንሳኤ ይምጡ የሚለው ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ የመጀመሪያው ጉዳይ ችግር እንዳለባቸው በማመን ችግራቸውን ለይተው ለማወቅ እና ለማረም ቁርጠኝነት ላይ እንዲደርሱ መምከር ነው፤ ከዚያ ስም ያለው መጽሔት ለመገንባት መውሰድ የሚገባውን ‹ሪስክ› ሁሉ መውሰድ፡፡ ይህንን ለሚሞክር አንባቢው እንደማያሳፍር በተደጋጋሚ አሳይቷልና፡፡

# የግል ፕሬሱ ለአቅመ አማራጭነት ብቁ ነውን?

## ጠቅላላ ሁኔታ

በኢትዮጵያ አንድ ብሔራዊ ቴሌቪዥን ጣቢያ ብቻ ያለ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ የክልል ቴሌቪዥኖችም ቢሆኑ ሙሉ ለሙሉ በመንግስት ይዞታ ስር ናቸው፡፡ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በመንግስት ይዞታ ስር ያሉ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች የመንግስት ልሳን ወደመሆኑ አመዝነዋል፡፡ ለግል የተሰጡ በጣት የሚቆጠሩ የሬዲዮ ጣቢያዎች ቢኖሩም በኤፍ.ኤም. የተወሰኑ ናቸው፡፡ ከኢትዮጵያ ሬዲዮ ውጪ ያለው ብሔራዊ ሬዲዮ ጣቢያ ንብረትነቱ ጥቂት የገዢው ፓርቲ አባላት በመሆኑ ለገዢው ፓርቲ የመወገን አዝማሚያ አለው፡፡ ከዚህ እውነታ በመነሳት ለማንም በማይወግኑ የግል ይዞታዎች ውስጥ የሚገኘው ነፃ ፕሬሱ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ጽሁፍ ‹ነፃ ፕሬሱ ምን ያህል አማራጭ ሚዲያ መሆን ይችላል?› ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት የተለያዩ መስፈሪያዎችን በመጠቀም ለመመለስ ይሞክራል፡፡

ከየካቲት 2001 እስከ ህዳር 2004 ድረስ 224 ያክል የሕትመቶች ውጤቶችን ለማዘጋጀት 211 ድርጅቶች እንደተመዘገቡ የብሮድካስት ባለስልጣን መረጃ ያመለክታል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 137ቱ መጽሔት እና ቀሪዎቹ 87ቱ ጋዜጦች ናቸው፡፡ ከአንድ ክልል በላይ ከሚሰራጩት ሕትመቶች ውስጥ 75 ያህሉ ‹‹የተቋረጡ/የተሰረዙ›› መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ይሁን እንጂ በገበያ ላይ ከሚውሉት የግል ሕትመቶች መካከል ሳምንታዊዎቹ ሃያ አይሞሉም፡፡ *(በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ፡- ሪፖርተር፣ The Reporter፣ አዲስ አድማስ፣ ሰንደቅ፣ ኢትዮ ቻናል፣ ነጋድራስ፣ መሰናዘሪያ፣ ፍትሕ፣ ፍኖተ ነፃነት፣ የኛፕሬስ፣ The Sub Saharan Informer፣ Fortune፣ Capital እና ፕሬስ ዳይጀስት (ሁሉም ሳምንታዊ)፤ ከመጽሔቶች፡-ሙሐዝ (ወርሃዊ)፣ አዲስጉዳይ (ሳምንታዊ) እና አዲስ ታይምስ (ወርሃዊ) - በኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ጉዳዮች የሚያጠነጥኑ ሕትመቶች ናቸው፡፡)*

በእንግሊዝኛ የሚታተመውና ንግድና ማስታወቂያ ላይ አተኩሮ የሚሰራው፣ ብቸኛው ዕለታዊ የግል ጋዜጣ The Daily Monitor ይሁን እንጂ ዕለታዊ ስርጭቱ 2000 አይሞላም፡፡ የአገሪቱ ኦፊሴላዊ ቋንቋ በሆነው አማርኛ ቋንቋም ሆነ በሌሎች የክልል ቋንቋዎች የሚታተም አንድም ዕለታዊ፣ የግል ጋዜጣ በአገሪቱ የለም፡፡

የሕትመት ውጤቶቹን ስርጭት በተመለከተ በሚያዝያ ወር፤ 2004 በወጣው መረጃ መሰረት ከፍተኛ ስርጭት ያስመዘገበው ፍትሕ ጋዜጣ ሲሆን ሳምንታዊ አማካዩ 21,750 ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠው አዲስ አድማስ በበኩሉ 12,000 ቅጂዎች አማካይ ስርጭት ሲያስመዘግብ ፕሬስ ዳይጀስት እና መሰናዘሪያ የተባሉት ጋዜጦች 230 እና 960 ዝቅተኛ አማካኝ ቅጂዎችን አሳትመው አሰራጭተዋል፡፡ ከመጽሄቶች ደግሞ አዲስጉዳይ በ20,000 ቅጂ ከፍተኛ ስርጭት አግኝቷል፡፡ ከዚያ በመቀጠል ሎሚ መጽሔት 12,000 ቅጂ በማሰራጨት ሁለተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል፡፡ ይህንን መረጃ ያገኘነው ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ሲሆን ትክክለኝነቱን ማረጋገጥ አንችልም:: ምክንያቱም አሳታሚዎቹ የማይስማሙባቸው ቁጥሮች እንዳሉ ሁሉ፣ በመረጃው ላይ የአማርኛውን የእንግሊዝኛ መጽሔት እስከማለት የተደበላለቀ ነገር አለ፡፡ አለመታደል ሆኖ እንጂ እንደ አሜሪካ ባሉ ሀገራት ነጻ የሆኑ እንደ ኒልሰን ሬትንግያሉ ሳምንታዊ የሚዲያ ውጤቶችን ተነባቢነትን (Readership) እና ስርጭትን (Circualation) የሚለኩ ኩባንያዎች አሉ:: በርግጥ የሚዲያው ሕልውና በሚያጠራጥርበት ሁኔታ፣ አንባቢ የሚቆጥር ነፃ ኩባንያ ማቋቋም ይከብዳል፡፡

ጋዜጦች (ከሕግ አውጪው፣ ሕግ ተርጓሚው እና ሕግ አስፈጻሚው ቀጥሎ) 4ተኛው መንግስት የሚል ቅጽል የተሰጣቸው ቢሆንም ይሄ ደረጃ ግን በኢትዮጵያ የግል መገናኛ ብዙሐን ዘርፍ ገና እንዳልተደረሰበት ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ የግል ፕሬሱ (የገበያ/commercial ወይም የሐሳብ/thought) ተጽዕኖ የሌለበት፣ ዜና እና አስተያየትን የለየ፣ ሕፀፅ ሐታች (critical analysis) ጠንካራ ተቋም እንዳልወጣው ያለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ውጤቶች ይዘክራሉ፡፡ ሃሌሉያ ሉሌ የተባለ በኢትዮጵያ የግል/ነጻ ሚዲያ ላይ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ምርምሩን ያካሄደ ወጣት ተማራማሪ ይህን በማስመልከት “the private press has neither been a vital information channel for the general public nor has it had a pivotal function as a watchdog of government performance” (*‹‹የግል ፕሬሱ አንድም ለብዙሐኑ ዐቢይ የመረጃ ምንጭ አልሆነም አሊያም ደግሞ የመንግስትን ብቃት ታዛቢ ማንፀሪያ ችካል ማኖር አልቻለም፡፡››*) ብሏል፡፡ ጥያቄው ‹‹ለምን?›› የሚለው ነው፡፡

## የግል ፕሬሱ ጥንካሬ

ምንም እንኳ የግል/ነጻ ሚዲያው የተቃውሞ ፖለቲካን ይደግፋል፣ የመንግስትን ስኬታማነት የመዘገብ አንጀት የለውም የሚል ትችት ከተለያዩ ወገኖች ቢቀርብበትም እንደ ተቋም ከተቋቋመበት ግዜ አንስቶ በበርካታ ውጣ ውረዶች ሊያልፍ ተገዷል:: ለአብነት ጦሰኛውን ምርጫ 97 ተከተሎ በርካታ የፕሬስ ውጤቶች ተዘግተዋል:: ጋዜጠኞቻቸውም ለእስር እና ለስደት ተዳርገዋል:: ከዚህ ያመለጡትም ቢሆኑ በበርካታ ሀገራት እንዲቀር በተደረገው የፕሬስ የስም ማጥፋት ወንጀል (Criminal Defamation) ተጠርጥረው ክሱን ለመከላከል ወደ ፍርድ ቤት ይመላለሳሉ:: ከዚህም በላይ ከግዜ ወደ ግዜ እያደገ የመጣው የህትመት ዋጋ ተቋቁመው አማራጭ የመረጃ ምንጭ ለመሆን የሚሞክሩት መፍጨርጨር በራሱ ሊደነቅ ይገባዋል::

## የግል ፕሬሱ ድክመቶች

የግል ፕሬሱ ምርጫ 97 ተከትሎ በደረሰበት የማዋከብ እና ሕልውናን አደጋ ላይ እስከሚጥል ሁኔታ ድረስ የተወዳዳሪነቱን አቅም ለማሽመድመድ የሚዳርጉ ፈተናዎች ደርሰውበታል፡፡ የተረጋገጠ የመረጃ ምንጭ (verification) እጥረት፣ ሞቅ፣ ሞቅ የማድረግ (sensationalism) አባዜ፣ ፅንፈኝነት (extremism) እና ቀጣይነት/ዘላቂነት(sustainability) የለውም ለማለት በሚያስደፍር ይዞታ ላይ ነው፡፡

በተለይም የፕሬሶች ዘላቂነት ጉዳይ አንገብጋቢ ወደመሆኑ እየተሸጋገረ ነው፡፡ ቀደምት የተባሉት ጋዜጦች ቢዘጉም፣ ተሳካላቸው የሚባሉት እነሪፖርተር፣ አዲስአድማስ እና ፎርቹን ጋዜጦች የመጀመሪያ ዓመቶቻቸው ላይ የነበራቸውን የእድገት ፍጥነት ባለበት አቁመው፣ ወይም እያቀለቀሉ በማዝገም ላይ ናቸው፡፡ ሪፖርተር ዕለታዊ ጋዜጣውን ማሳተም ይጀምራል ተብሎ ሲጠበቅ የእንግሊዝኛ እትሙን ሳምንታዊነት እንኳን በኪሳራ ለመደጎም ተገድዷል፡፡ አዲስ አድማስ የእንግሊዝኛ ጋዜጣ አሳትማለሁ ብሎ በሰፊው ካስተዋወቀ በኋላ ትቶታል፤ የአማርኛውም ጋዜጣ ቢሆን ከበፊት የስርጭት ብዛቱ በከፍተኛ ሁኔታ ወርዷል፡፡ በተቋማዊ አደረጃጀቱ የተሻለ ተስፋ ተጥሎበት የነበረው አዲስ ነገር ጋዜጣም ከሁለት ዓመታት በላይ መጓዝ አልቻለም፡፡ አውራምባ ታይምስ ጋዜጣም ሲዘጋም 17 ሰራተኞቹን ሜዳ ላይ ጥሎ ነው፡፡

በሌላ በኩል የግል ፕሬሱን እየተፈታተነ የሚገኘው ውስጣዊ ችግር ነው፡፡ ለምሳሌ አዎንተኝነት (Confirmest) ላይ ማተኮር ቀዳሚ ተጠቃሽ ችግር ነው፡፡ ይህ ከምርጫ 97 በኋላ በይዘታቸው ለስላሳ የሆኑ ወይም የመንግስትን ቀልብ በማይስቡ ስፖርትና ፋሽን ዙሪያ፣ በተለይም ደግሞ በቴዲ አፍሮ ጉዳዮች ላይ ብቻ የሚያጠነጥኑ ወሬዎችን (የቴዲ አፍሮ አባዜ ወይም The Teddy Afro Mania ብንለው እንመርጣለን) ጉዳዮች እያሳደዱ የሚያወጡ መጽሔቶች መበራከት፡፡ ከዚህ አለፈ ሲባልም ደግሞ ከስንት አንዴ በሚከሰት ጉዳይ ላይ (ለምሳሌ አንድ ጠንቋይ በወንጀል ፍርድ ቤት ሲቀርብ የሰውዬውን ስም የሚያስነሳ ማንኛውንም ታሪክ እያግበሰበሱ ማተም፣ አንዲት ሴት ጾታዊ ጥቃት ሲደርስባት ከጉዳዩ'ጋ ግንኙነት የሌላቸውንና ከተአማኒነትም አንፃር ምንም ዓይነት ተጨባጭነት የሌላቸውን የፍቅር ግንኙነቷን የሚመለከቱ አሉባልታዎችን ሳይቀር እያሳደዱ ማተም) ለአንባቢው በማያገባው ነገር ተጠምዶ፣ በሚመለከተው አገራዊ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ መረጃ ሳያገኝ እንዲቀር ምክንያት ሆኗል፡፡

ሚዲያዎቹ በዚህ ረገድ አንድን ግለሰብ ወይም ሁኔታ ሲያወድሱም ሆነ ሲያጠለሹ በፍፁማዊ መንገድ እንደሆነ ከመታማት አልተረፉም፡፡ ሌላው ቀርቶ፤ ጋዜጦቹና መጽሔቶቹ በቋንቋ አጠቃቀም እና ገጽ መሰናዶ (layout design) እንኳን ሳይቀር የማንበብ ፍላጎትን ለመሳብ የማይሞክሩ ከመሆናቸውም ባሻገር ብቸኛ ትኩረታቸውን እና ስልታቸውን በማስታወቂያ ገንዘብ ማጋበስ አተኩረው የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው እና ስለማሕበራዊ አበርክቷቸው (social contribution) የሚጨነቁ አለመምሰላቸው፣ በተለይም መጽሔቶቹ አብዛኛው ይዘታቸው ከኢንተርኔት የተገለበጠ መሆኑ ለሕትመት ሚዲያው ወጥ አስተዋፅዖ ጉድለት ራሱን የቻለ ሚና አለው፡፡

## የግል ፕሬሱ ተግዳሮቶች

የግል ፕሬሱ ካለፈው ልምድ ያዳበረው ድባብ እና ሌሎች ውስጣዊ የኢኮኖሚ እና የአስተዳደር ብቃት ማነስ ከሚጥልበት ችግር በተጨማሪ በርካታ ተግዳሮቶች ተደቅነውበታል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያክል፦

- **የባለሙያ እጥረት፤** በጋዜጠኝነት ሙያ የተመረቁ ወይም ለሙያው ፍቅር ያላቸው ጋዜጠኞች በሙያው ከመስማራት ይልቅ ወደ ሕዝብ ግንኙነት ሥራ መሰማራታቸውና፣ ከሕትመት ሽያጩ ለሚገኘው ትርፍ (ወይም በጽሁፉ ስለሚገኘው ጊዜያዊ ክፍያ) ብቻ ሲሉ የሚሰሩ ጸሐፊዎች መበራከት፣
- **የሽብርተኝነት ክሶች፤** በጋዜጠኞች ላይ እየደረሰ ባለው የሽብረተኝነት ክስ ጋር በተያያዘ ወደ ሙያው የሚገቡ ወጣቶች የፍርሃት ቆፈን የሚጸፍ እና የማይጻፉ ጉዳዮችን እንዲለዩ ማድረጉ፤ በሌላ ቋንቋ የራስን ጽሁፍ በራስ ቅድመ ምርመራ (self-censorship) ውስጥ ማሳለፈ መበራከቱ፣
- **የሕትመት ዋጋ መናር፤** ከ5 ዓመታት በፊት አንድ ባለ 16 ገጽ ሳምንታዊ ጋዜጣ ለማተም በአማካይ 90 ሳንቲም ብቻ ያስወጣ የነበረ ሲሆን አሁን ግን ተመሳሳይ ገጽ ያለው ጋዜጣ ለማተም ከ2.90 ብር በላይ እንደሚጠይቅ ያደረገነው ምርምር ያሳያል፣
- **ሙያዊ ስነምግባር ማነስ፤** ማስታወቂያ ልስጥህና ዜና ስራልኝ ለሚሉ ማባበያዎች መንበርከክ እና ዜና መሰል ማስታወቂያዎች (advertotials) መስራት:: ለምሳሌ ‹አዲስ መኪና የሚገጣጠም ፋብሪካ መከፈቱን እና የመገጣጠሚያው መከፈት ለአገሪቱ ትልቅ ሚና እንዳለው የሚያስተዋውቅ ዜና ከሰሩ በኋላ፣ ዜናውን ተከትለው በሚወጡ ተከታታይ እትሞች ላይ የመገጣጠሚያውን ኩባንያ ማስታወቂያ ማውጣት› የሚመስሉ ተግባራት መበራከት እና
- **የፕሬስ እና የፀረ ሽብር ሕጉ፤** የፕሬስ ሕጉ እና የፀረ ሽብርተኝነት ሕግጋት በጋዜጠኞች ደሕንነት እና በስራቸውም ላይ ክፉ ጥላውን አጥልቷል። የስም ማጥፋት፣ የዜና ምንጭን የመጥቀስ አስፈላጊነት፣ አሸባሪ ተብለው የተፈረጁ የሚናገሩትን መዘገብ እና የመሳሰሉትን በሕጉ መሰረት ለመጻፍ ለሚፈልጉ፣ የመንግስትን እርምጃዎች ከማወደስ በቀር ለመተቸት ወይም ስህተቶችን ለማጋለጥ የሚያስችል ምንም መፈናፈኛ መንገድ አልቀረላቸውም።

## አማራጭ መፍትሄዎች

- **የዜጎች ጋዜጠኝነት** (Citizen Journalism)፤ የአዲሱ ዘመን ቴክኖሎጂ ካመጣለን ትሩፋቶች ውስጥ አንዱ በታሪክ ነጋሪዎች(Story Tellers፤ ጋዜጠኞችና ግለሰቦች) እና ተራ ግለሰቦች መሀከል ያለውን ሰፊ መስመር ማጥበቡ ነው:: ይህንንም በመጠቀም ዜጎች ያዩትን የሰሙትን እና አስተያየቶቻቸውን ፌስቡክን፣ ዩ ቲዩብን፣ ትዊተርን፣ ብሎጎችን እና ሌሎችንም የዜጎች ጋዜጠኝነት መደበ አለፎችን (Citizen Journalism platforms) በመጠቀም፣ ለዜጎች ከፍተኛ ተዳራሽነት ባለው የተንቀሳቃሽ ስልክ አማካይነት እንዲናገሩ መፍቀድ፣ ማበረታት እና ምቹ ስርዓት መፍጠር ችግሩን ለመቅረፍ አሌ የማይባል አስተዋፅዖ ያበረክታል፣
- **ነፃ ጋዜጠኞችን መፍጠር፤** ጋዜጠኞች ከስጋት ነፃ የሚሆኑበት ስርዓት ሊዘረጋላቸው ይገባል። ይህንን ከግብ የሚያደርሱ፣ ለጋዜጠኞች መብት የሚሟገቱ፣ ነፃ የጋዜጠኞች እና የጋዜጦች ማሕበራት መመስረት ይኖርበታል። በዚህ ረገድ ነፃ ሊባል የሚችል የጋዜጠኞች ማሕበር ተዘርግቷል ማለት ባይቻልም፣ አዲሱ የኢትዮጵያ ፕሬስ አሳታሚዎች ማሕበር (ኢፕአማ) ላይ እንደአዲስነቱ ተስፋ ሊጣልበት ይችላል፣
- **የፕሬስ አሳታሚዎች ተቋማዊ አደረጃጀትን ማጠናከር፤** ጋዜጠኞች ሲሰደዱ ወይም ሲታሰሩ የሚዘጉ ወይም የሚበተኑ በጥቂት ጋዜጠኞች ላይ ብቻ ጥገኛ/ተመርኳዥ የሆኑ ተቋማትን ወደ ራስመር ተቋምነት ማሳደግ፣ በአክስዮን የሚመሩ ተቋማትን ማቋቋም፣ ጋዜጦች ከመንግስት የማተሚያ ቤቶች እንዲወጡ የአሳታሚዎች ማተሚያ ቤት ማቋቋም እና ወዘተ. መፍትሄዎች ናቸው።

## መደምደምያ

የግል ፕሬሱን በደመስማሳው ለማየት እንደሞከርነው በብዙ መልኩ፣ በተለይም ‹‹በገገርው ፓርቲ ልሳንነት›› እያገለገሉ ያሉትን የመንግስት ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ እና ጋዜጦችን በስርጭት አድማስም ሆነ በይዘት ለመቀናቀን አሊያም ተመጣጣኝ የሆነ ሚዛን ለመድፋት የሚያስችል አቅም አላዳበረም። የአቅም እጥረቱ ከባለሙያነት (professionalism)፣ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ከፋይናንስ አንፃር ብቻ የሚመነጭ ሳይሆን ሚዲያው በማይቆጣጠራቸው አገር አቀፍ ስርዓታዊ እንከኖች እና አዋጆች ሳቢያም የተወለደ ነው።

መንግስትም በበኩሉ፣ ከሚያወጣቸው አዋጆች፣ ከአገዳቸው ጋዜጦች እና በጋዜጠኞች ላይ ከመሰረታቸው ክሶች በመነሳት የፕሬሶቹን አማራጭ ድምጽነት የፈለገው እንደማይመስል መናገር ይቻላል። ምናልባትም ይሄ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ የአውራ ፓርቲ መርሕ'ጋ የተወዳጀ አካሔድ ሊሆን ይችላል። በማንኛውም አካሔድ ግን ነፃ ፕሬሶች የአውራ ፓርቲውን መስመር በማስተካከልም ቢሆን የሚኖራቸው ሚና የማይታበል ነው።

በተቃራኒው መንግስት በ21 ዓመት ጉዞው ለነፃ ሚዲያ የሚመች ስርዓት ዘርግቻለሁ እያለ ይከራከራል፡፡ የግል ፕሬሱ ግን አራተኛ መንግስት በመሆን ደካማ ስርዓቶችን ማውገዝ፣ ዐቢይ ማሕበራዊ ጉዳዮችን ለውይይት ማብቃት (agenda setting) እና ተጠያቂነትን በቀዳሚነት መምራት አልቻለም፡፡ ለዚህ አቅም አለመዳበር እና የወደፊት ዕጣ ፈንታው መንግስትም ሆነ ሌሎች የግል ፕሬሱ ዋነኛ ተጫዋቾች/stakeholders (አሳታሚዎች፣ ጋዜጠኞች…) ተጠያቂዎች/ኃላፊዎች ናቸው፡፡

# ድምፃችን ይሰማ!

ርዕሳችንን የተዋስነው ‹‹ለሙስሊሙ ጉዳይ መፍትሔ አፈላላጊው ኮሚቴ›› ከሚጠቀምበት የፌስቡክ ገጽ ስያሜ ነው፡፡ ‹‹ድምጻችን ይሰማ›› የሚለው ሐረግ የአገራችንን ነባራዊ ሁኔታ በአግባቡ የሚገልጽ ነፍሰጡር ሐረግ ነው፤ ብዙ ፍቺዎችን ይወልዳል፡፡ ጥያቄ፣ ተማፅኖ እና ትዕዛዝም ሊሆን ይችላል፡፡

ሙስሊሙ ማኅበረሰብ በርካታ ጥያቄዎችን አንስቷል፡፡ ከጥያቄዎቹ መካከል ‹‹መጅሊሱ›› አይወክለንም እና ይቀየር የሚለው አንዱ ነው፡፡ ለዚህ የተገኘው ምላሽ መጅሊሱን የሚተኩ አባላት የመምረጥ መብት ቢሆንም አካሔዱ ሌላ ጥያቄ አጭሯል፤ አባላቱ መመረጥ ያለባቸው በቀበሌ ጽ/ቤቶች በኩል ነው በሚል፡፡ ይህንን ደግሞ አብዛኛው ሙስሊም ሃይማኖታዊ ጉዳይን ከፖለቲካ ጋ ከመቀላቀል ለይቶ አልተመለከተውም፡፡ ስለዚህ ጥያቄው መልስ እስኪያገኝ ድረስ ተቃውሞውን ለመቀጠል የወሰነ ይመስላል - በሰላማዊ ተቃውሞ፡፡

የሰላማዊውን ተቃውሞ ዑደት (cycle) ብንመለከተው - ይጠይቃሉ፣ መልስ የለም፤ ይማፀናሉ፣ መልስ የለም፤ ያዝዛሉ መልስ የለም፡፡ መጠየቅ ተፈጥሯዊ ግዴታቸው ነው እና አያቆሙም፣ መማፀን ሰብአዊ ልምዳቸው ነውና ይተገብሩታል፣ ማዘዝ ሃይማኖታዊ ነፃነታቸው ከፖለቲካ ተፅዕኖ እንዲወጣ የተሰጣቸው ሕገመንግስታዊ መብታቸው ነውና ያዝዛሉ፡፡ ይህ ደግሞ የሰው ልጅ ባሕሪ ነው፡፡ ዕውቁ ቼካዊ ጸሐፊ ፍራንዝ ካፍካ ይህንን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፤ ”Believing means liberating the indestructible element in oneself, or, more accurately, liberating oneself, or, more accurately, being indestructible, or, more accurately, being.”

በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጥያቄ እና በመንግስት ምላሽ ምሳሌ የምንረዳው ጠቅላላውን የሕዝብና መንግስትን ግንኙነት ነው፡፡

ባለፉት 21 ዓመታት ውስጥ /በተለይም ሕገመንግስቱ ከፀደቀ ወዲህ ባሉት 17 ዓመታት/ ሕዝቦች በድምጻቸው መንግስትን ከመሾምና ከመሻር ጀምሮ ያለው መብት በሙሉ ተሰጥቷቸዋል ይባላል፡፡ እውነት ተሰጥቷቸዋል? እስቲ የኢትዮጵያን የጨዋታ ሕግ እንመለከት፡፡

## የምዕራባውያን ሚና እና ድምፃችን

ምዕራባውያን አፍሪካን ወይም ኢትዮጵያን እንደመለስ ዓይነት ባሉ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የመግባባት እና የማሳመን ችሎታ ባላቸው ልሂቃን ዓይን መመልከት እና የአፍሪቃ ቀንድን ከቧታል ከሚሉት አደጋ ይጠብቅልናል ብለው በሚያስቡት መሪ ማስገዛት ይፈልጋሉ፡፡ በመሆኑ ሙስሊም ማኅበረሰብም ሆነ ሌላው በሰላማዊ መንግድ ድምጹን በማሰማት ላይ ያለ ሰው ለትግሉ ምላሽ እርሳቸውን የመሰለ ሰው በማግኘት አለማግኘቱ ላይ የተንጠለጠለ ነው::

ምዕራባውያን በአፍሪካውያን እና በአረብ ላይ ያላቸው አመለካከት በጥቅሉ ጨለምተኛ ነው ማለት ይቻላል፤ አረብን ከእስልምና ጋር በመቀላቀልም ቢሆን ከመታማት አይተርፉም፡፡ ምንም እንኳን በአገራችን ውስጣዊ ጉዳይ ላይ አያገባቸውም ብሎ መዝጋት ቢቻልም፣ በመንገዳችን ላይ የሚጥሉብንን እንቅፋት ግን ከመጋፈጥ አንተርፍም፡፡ ስለዚህ ስለድምጻችን መደመጥ ሲባል እነርሱን የማሳመንም ዕዳ አለብን፡፡

## አብዮታዊ ዴሞክራሲ እና የድምፅ ዋጋ

ምርጫ 97 እና ውጤቱ ገዢው ፓርቲ ለዴሞክራሲ እሴቶች የሚሰጠው ዋጋ ግምት ውስጥ የወደቀበት የመጀመሪያው አጋጣሚ ነው ማለት ቢቻልም፣ ይህንን ጥያቄ ለማንሳት የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ብያኔ ማወቅ እና ከአጀማመሩ ጀምሮ ያለውን ሒደት መመርመር ያስፈልጋል፡፡

አብዮታዊ ዴሞክራሲን ይህ ነው የሚል ብያኔ የሚሰጥ ምሁር እስካሁን አልተገኘም፡፡ ምናልባትም ክፍተቱ የተፈጠረው በዘፈቀደ የሚጓዙበት ርዕዮተ-ዓለማዊ መንገድ ከመሆኑ አንጻር ነው ብሎ ለመደምደም ያስችል ይሆናል፡፡ የልማታዊ ጋዜጠኝነት አካዳሚያዊ ፍቺ ተዛብቶ በነባራዊቷ ኢትዮጵያ፣ በመንግስት ይዞታዎች ስር ባሉ ሚዲያዎች ‹‹ይሁንታን ማምረት›› እየሆነ እንደሆነ ከዚህ በፊት በዞን ዘጠኝ ላይ አውርተናል፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲም፣ ኢሕአዴግ በጥቅሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ መራጌ ጥያቄ ዳቦ እንጂ ዴሞክራሲ አይደለም ከሚለው ፊሊጥ'ጋ የተያያዘ እንደሆነ መገመት ወደተሳሳተ ድምዳሜ አያደርስም፡፡ በዚህ ስሌት ዳቦን (ልማትን) ለማምጣት

ሲባል ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች የሚደፈጠጡበት የሚል አንድምታ ላይ ለመድረስ የመንገደድበት ጊዜ ይኖራል፡፡

ድምጽ በዴሞክራሲያዊ ስርዓቶች ውስጥ ያለው ዋጋ ከፍተኛ ቢሆንም፣ (መለስ እንደሙጋቤ ‹‹አፍሪካ የሚያስፈልጋት የምዕራባውያኑ ዓይነት ዴሞክራሲ አይደለም›› ማለታቸው ይታወቃል፤) ስለዚህ አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ አፍሪካውያንን የሚስማማ ዴሞክራሲ ነው ቢሉን እንኳን ለሕዝባዊ ድምጽ የሚሰጠው ዋጋ እስካሁን ተለይቶ አልታወቀም፡፡

የምርጫ 97ን ውጤት ተከትሎ ‹አሸናፊው እኔ ነኝ፣ እኔ ነኝ› በሚለው የገዢውና ተቃዋሚ ፓርቲዎች እሰጥ አገባ መካከል ‹‹ምርጫው ይደገም›› በሚል ተቃዋሚዎች የጠየቋቸውን ወረዳዎች ባብዛኛው ባለመቀበል፣ ወትሮም ነፃ የመሆኑ ነገር የሚያጠያይቀው የምርጫ ቦርድ - የሕዝቦችን ድምጽ ዋጋ አሳጣው፡፡ ትንሽ ቆይቶ ይህንን ርምጃ እየተቃወሙ አደባባይ የወጡ ተቃዋሚዎችን ድምጽ የሚሰማ ነፃ ወገን ጠፍቶ - ቢያንስ ለ193 ሰዎች ሞት መንስኤ ሆነ፡፡

ይህንን ክፉ ገጠመኝ በወቅቱ ሲዘግቡ የነበሩት አገር በቀል ጋዜጦች በጅምላ ታገዱ፡፡ ይህ ጊዜ ብዙዎች ድምጻቸው በምርጫ ዋጋ እንደሌለው ብቻ ሳይሆን ሌላ ድምጻቸውን የሚያሰሙበት መንገድ እንደሌላቸውም ተስፋ መቁረጥ ደረጃ ላይ ደረሱ፡፡ ከዚህ አጋጣሚ በኋላ በተለይም በተቃዋሚው ጎራ ያሉ ወገኖች በደርግ ዘመን አለ ይባል የነበረው የፍርሃት ማስካቸው ውስጥ ገብተው ተሸሸጉ፡፡ ለምርጫ 2002 የተመዘገቡ ሰዎች ቁጥር ከምርጫ 97ቱ በእጅጉ ማነሱም የሚናገረው ሕዝቦች ‹‹ድምጻችን ላይሰማ ነገር…›› ብለው ተስፋ መቁረጣቸውን ነው፡፡

በየጊዜው የሚያሻቅበው የኑሮ ውድነት፣ መንግስት ልማትን ከሰብአዊ መብት የማስቀደሙ ውዝግብ፣ የፓርቲ አባልነት በመንግስት ተቋማት የሁለተኛ ዲግሪ የማግኘት ዕድል ከማስጠት ጀምሮ ላሉ ጉዳዮች እንደዋስትና መታየቱ፣ እጅግ በርካታ መንግስትን የሚነቅፉ ዜጎች ባሉበት አገር በፓርላማው ውስጥ አንድ ብቻ ተቃዋሚ መኖሩ… ወዘተ፣ ወዘተ… እጅግ የሚያስጮሁ ሐቆች ሆነው ሳለ ሕዝቡ ዝምታን መምረጡ ድምጼ ሰሚ የለውም ብሎ ተስፋ ወደመቁረጡ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህንን ዓይነቱን ለመብት ተቆርቋሪነት መቀዛቀዝ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን Political apathy (‹ፖለቲካዊ ዳተኝነት› እንበለው፣) ይሉታል::

‹ፖለቲካዊ ዳተኝነት› የዜጎች በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ምንም ዓይነት ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማድረግ ፍላጎት አለመኖር ነው፡፡ እንደምሳሌም፣ ሰበቡ ምንም ይሁን ምን ‹ፖለቲካዊ ዳተኝነት› ውስጥ የገቡ ሕዝቦች አለመምረጥ፣ ሕዝባዊ አስተያየት አለመስጠት፣ ዜግነታዊ ግዴታን ለመወጣት አለመሻት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በርካታ ምሁራን እንደሚስማሙበት ደግሞ እንዲህ ዓይነቱ ‹ፖለቲካዊ ዳተኝነት› የአንድን አገር ዕድገት ባለበት ቆሞ እንዲቀር መንስኤ የመሆን ዕድሉ ሰፊ ነው፡፡

## ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ድምፃችን

ተቃዋሚ ፓርቲዎች የገዢው ፓርቲ አይወክለንም የሚሉ ድምጾችን ማስተጋባት /አሊያም ቢያንስ ድምጾቹ ወይም ጥያቄዎቹ አግባብ መሆን አለመሆናቸው ላይ አስተያየት መስጠት/ እንዳለባቸው በጥቅሉ ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በዚህ ጽሑፍ እንደምሳሌ (sample case) የያዝነውን የሙስሊሞችን ጉዳይ እንኳን በሚመለከት ያለውን ሁኔታ ብናስተውል ተቃዋሚዎች ያላቸው ድርሻ እጅግ አነስተኛ ሁኖ እናገኘዋለን፡፡ እስካሁን ድረስ ጥቂቶቹ ተቃዋሚዎች ብቻ ጊዜያዊ መግለጫቸው ላይ ‹‹ጣልቃ ገብነቱን›› እንቃወማለን ከማለት ባሻገር፣ መሬት ላይ ወርዶ ሊተገበር የሚችል የመፍትሄ ሐሳቦችን በመጠቆምና የሚመለከታቸውን አካላት በማነጋገር፣ ወይም ድምጹን በማጉላት የሠሩት ሥራ አለ ለማለት የሚያስደፍር ነገር የለም፡፡

አንዳንዶች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ራሳቸው ድምጻቸውን የተቀሙ እንደሆኑ ይከራከራሉ፡፡ የሚሰጡትን የአቋም መግለጫም ቢሆን ገዢው ፓርቲ ከቁብ ቆጥሮ ያዳምጣቸው እንደሆነ እንኳን በጥርጣሬ የሚጠይቁ እልፍ ናቸው፡፡

## ከድምፃችን ተቀማ እስከ ድምፃችን ይሰማ?

የሙስሊሞች ጉዳይ መፍትሄ አፈላላጊው ኮሚቴ አባላት በሙሉ እንደታሰሩ ተሰምቷል፣ የገዢው ፓርቲ በርካታ ሙስሊሞችን በየክፍለሃገሩ እያስተባበረ ሰልፍ እያስወጣ ይገኛል፡፡ እነዚህ ሰልፍ የሚወጡ ሰዎች ‹‹ምርጫውማ በቀበሌ ነው መካሄድ ያለበት›› እያሉ ለትዝብት የሚዳርግ ክርክር ሲከራከሩ በኢቴቪ አይተናል፡፡ ኢቴቪ እነዚህን

ሰዎች ሰፊ ሽፋን መስጠቱ ራሱ ምን እየተሰራ እንደሆነ ግልጽ ያደርገዋል፡፡ ገዢው ፓርቲ ድምጽ መስማት ስለማይችል ድምጽ መቀማት ጀምሯል ማለት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ ድምጽ የማስመለስ ጥረቱ ደግሞ የሚቀጥለው፡፡

በዚህ ዘመነ-መንግስት ድምጽ የመቀማት ወግ የነበረ፣ ያለ እና ኢሕአዴግም እስካለ የሚቀጥል ይመስላል፡፡ ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት ይቻል ነበር ቀርቷል፣ በምርጫ 97 መቶ በመቶ የተቃወመ በምርጫ 2002 መቶ በመቶ ደገፈ የሚል ስላቅ ተሰምቷል፣ በየዕለቱ ሁለት ሦስት ጋዜጦች ይወጡ እንዳልነበር አሁን ከሳምንቱ ሦስት ቀናት (ሰኞ፣ ሐሙስ እና አርብ) ምንም ፖለቲካ ነክ ጋዜጦች ማግኘት አይቻልም፡፡ ሐሳብን የመግለጽ መብት በሕግ ሰፍሯል ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ የማይጎበኙ ድረገጾች ቁጥር በየቀኑ ያድጋል:: እነዚህ ሁሉ ድምጽ የመቀማት መንግስታዊ ስልት ውጤቶች ናቸው፡፡

## ሰላማዊ ትግል እና ‹‹ድምፃችን ይሰማ››

ከቱኒዚያ እና ከግብጽ የፀደይ አብዮት መማር እንደቻልነው፣ ሰላማዊ አብዮታቸው (የነርሱ) ድኅረ ምርጫ 97 ላይ ከነበረው (ከኛ) የተለየ መልክ አለው፡፡ ምንም እንኳን በእኛ አገር፣ ለሕዝባዊ ተቃውሞዎች የመንግስት ሠራዊት የሚወስዳቸው ርምጃዎች ሕዝቡን የሚያስቆጡና ወደአመፅ የሚመሩ ቢሆኑም፣ ያኔ የነበረው ድንጋይ ውርወራ ላይ ያተኮረ አመፅ ከሰላማዊነት ያፈነገጠ ነበር፡፡ አሁን ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጥያቄውን የሚያቀርብበት መንገድ ግን አስተያየት ሰጪዎች ‹‹የገዢው ፓርቲ ቅጥሮች›› ናቸው በሚሏቸው ሰዎች ብጥብጥ ለመፍጠር የተሞከረ ቢሆንም በብዙሐኑ ለሰላማዊነት ተገዢነት በተደጋጋሚ ከሽፏል፡፡ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጥያቄውን ወይም ተቃውሞውን አመፅ አልባ በሆኑ መንገዶች ብቻ ለማድረግ መወሰኑ እና ከስድስት ወራት በላይ በትግሉ በፅናት መቆየቱ የሚያሳየን፣ በሰላማዊ መንገድ ረዥም ጉዞ መጓዝ እንደሚቻል ቢሆንም መልስ ሳያገኙ እስካሁን መቆየታቸው ግን መንግስትን በቸልተኝነት ከመወንጀል አያተርፈውም፡፡

እንዲያውም የኢትዮጵያ መንግስታዊ ተቋማት ለሰላማዊ ትግል እና ለድምጻችን ይሰማ ጥያቄ ከፍተኛ ደንቃራ ሊሆኑ እንደሚችሉ መጠርጠር ይገባል:: በብዙ ታዳጊ አገራት እንደምናስተውለው፣ የኢትዮጵያ መንግስታዊ ተቋማት፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት አንፃር ያላቸው ተወዳዳሪነት አነስተኛ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኗ ኢትዮጵያ፣ ለምሳሌ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨትም ሆነ ማሰራጨት የመንግስታዊ ተቋም ኃላፊነት ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ወሳኝ የአገሪቷ ተቋማት (ፖሊስ፣ ፍርድቤት እና ዩንቨርስቲዎች) የስርዓቱን ወይም የገዢው ፓርቲን ለማገልገል የቆሙ የመምሰላቸውን ጉዳይ ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡

ሕገመንግስቱም ቢሆን ከተመሳሳይ ችግር ሰለባ ከመሆን አላመለጠም፡፡ ዴሞክራሲያዊ መርሆችን በንቀጾቹ እንዲያካትት ቢደረግም በዕለት ተዕለት የመንግስት ባለስልጣናት ተግባር ግን ሲጣስ ይውላል፡፡ ስለዚህ የሰላማዊ ትግል ሚና ሕገመንግስቱን ማስጠበቅ ነው ማለትም እንችላለን፡፡

## የድምፃችን ይሰማ ተስፋ

የፌስቡኩ ‹ድምጻችን ይሰማ› ገጽ ላይ የሚሰፍሩ ጽሑፎችን ለተመለከተ ሁለት ነገሮችን መረዳት ይችላል፡፡ አንደኛ፤ የዜጎች ጋዜጠኝነት (citizens journalism) ምን ያህል እየተተገበረ እንደሆነ እንደሆነ እና የሌላውን ሕዝብ ስሜት ላለመጉዳት ምን ያህል ጥንቃቄዎች እየተደረጉ እንደሆነ በግልጽ ማየት ይቻላል፡፡ የገጹ አስተዳዳሪዎች ከተለያዩ ወገኖች የሚገኙ መረጃዎችን ለመላው ሕዝብ እንዲዳረስ የሚያደርጉበት ፍጥነት አስደናቂ ነው፡፡ በሌላ በኩል በተለያዩ ሚዲያዎች ላይ የተሰነዘሩ የእርምት አስተያየቶችን በሂደት እያስተካከሉ ሲመጡ በጥብቅ የተከታተላቸው የሚረዳላቸው ጥንካሬያቸው ነው፤ የሰላማዊ ትግል ባሕሪም ይኸው ነው፡፡

በዚህ ዓይነት፣ ሕዝቦች አንድነታቸውን እና ሰላማዊነታቸውን በፅናት እስከጠበቁ ድረስ ብሎም የሚጠይቁትን ነገር ሚዛናዊነት እና ምክንያታዊነት እስካወቁ ድረስ፣ መልስ ማግኘታቸው የማይቀር እውነታ ነው፡፡ እዚህጋ መልስ ለመስጠት የማይፈልጉ ሰዎች ሚና ጥያቄውን በሚያቀርቡት ሰዎች ጥንካሬ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ መብት በገዢዎች ችሮታ የሚሰጥ ነገር ሳይሆን በሕዝቦች ፍላጎትና ፈቃደኝነት ላይ የሚገነባ ጉዳይ ነው፡፡ ሕዝቦች ‹ድምጻችን ይሰማ› ካሉ፣ የግድ ነው - ድምጻቸው ይሰማል፡፡

# ልማታዊ ጋዜጠኛነት ወይስ ይሁንታን ማምረት?

በዚህ ጽሑፍ የማቀርብላችሁ ርዕሰ ነገር ልማታዊ ጋዜጠኝነትን ይመለከታል፡፡ አዲስ ጉዳይ መጽሄት በተከታታይ እትሞቿ ስለ ልማታዊ ጋዜጠኝነት የተለያዩ ሰዎችን ሙግት ይዛ ቀርባ ነበር:: መጽሄቷ አንጋፋ የጋዜጠኝነት መምህር የሆኑትን አቶ ማእረጉ በዛብህን ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና በመቀጠልም የኝህኑ መምህር ጽሑፍ ‹አንዳንድ ነጥቦች ስለ ልማታዊ ጋዜጠኝነት› በሚል ርዕስ ለአንባቢ አቅርባለች:: ከቃለ መጠይቁም ሆነ ከቀረበው ጽሁፍ በመነሳት በሀገራችን ልማታዊ ጋዜጠኝነት የሚባለው የጋዜጠኝነት ዘውግ እየተተገበረ ነው ማለት ያዳግታል የሚል ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን:: በእውነቱ ከሆነ የአቶ ማእረጉ አቋም የኔም አቋም ነው:: ከዚህም ባሻገር የፍትሐ አምደኛ ኃይለመስይቀል በሸዋምየለህ ደግሞ ‹‹በኢትዮጵያ የነጻው ፕሬስ እየተደመደመ ነውን?›› እያለ ይጠይቃል:: ነገር ግን በዚህ በሳቸው ጽሁፍ አነሳሽነት ሁለት ከጋዜጠኝነት ሙያ ጋር ዝምድና ያላቸው ወጣቶች ‹‹የለም፤ የአቶ ማእረጉ ድምዳሜ ስህተት ነው›› ይሉናል ፡፡ እንዳውም ‹‹አቶ ማእረጉ ሆነ ብለው እውነታውን ለመካድ በመሻት ልማታዊ ጋዜጠኝነት በኢትዮጵያ የለም የሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ካልደረሱ በቀር፥ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊካድ በማይቻል ሁኔታ የልማታዊ ጋዜጠኝነት ውስን ዘውጎች በመንግስት መገናኛ ብዙሐን እና በአንድ አንድ FM ራዲዮን ጣቢያዎች እየተተገበሩ ናቸው›› ሲሉ የክርክር ነጥባቸውን አቅርበዋል::

የነዚህ ሁለት ወጣቶች አቋም የነሱ ብቻ አቋም አድርጌ አልመለከተውም:: የመንግስትም አቋም እንደሆነ አምናለሁ:: አለመታደል ሆኖ እንጂ መንግስት ለዲሞክራሲ መጎልበት እንዲህ መሰረታዊ ፋይዳቸው ላቅ ያሉ ጉዳዮችን አደባባይ አውጥቶ ሕዝባዊና ምሁራዊ ክርክሮች እንዲካሄዱ ከመፍቀድም አልፎ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነበረበት ግን አልሆነለትም፤ ወደ ምክንያቶቹ አልሄድም የጽሁፌ ትኩረት አይደለምና፡፡ የግል መገናኛ ብዙሃንም ቢሆኑ ጥቂቱ በሀገር ውስጥ ግማሹ ከሀገር ውጪ በመሆን እንዲህ ያለውን ጉዳይ በተንጠባጠበ እና አልፎ አልፎ በሚነሳ የአምድ ማሟያነት ከክርክር ባለፈ ጉዳዩን በጥልቀት በመመርመር የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ለመጠቆም በሰፊው ለመስራት በሞከሩ ነበር: ምንም እንኳ የእስካሁኑ ሙከራቸው ቢያስመሰግናቸውም፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው ልማታዊ ጋዜጠኝነት ነው/አይደለም የሚለው ክርክር በልማታዊ ጋዜጠኝነት ኀልዮቶች ላይ የተንጠለጠለ መሆን የለበትም:: በእርግጥ የ"ልማታዊ" ጋዜጠኝነት ኀልዮቶችን ፋይዳ እና መገለጫዎቹን የ"ልማታዊ" ጋዜጠኞችን ስነ ምግባር እና ሌሎችንም ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ቅርበት ያላቸውን ዝርዝር ጉዳዮች በሙሉ መነጋገርም መወያየትም ተገቢ ነው:: ነገር ግን ይህን የመሰለ ሀገራዊ አብይ ጉዳይ በኀልዮት ደረጃ ብቻ ተወያይቶ ወይም "ምናምን" ብሮድካስት ኮርፖሬሽን፤ በሚባለው ራድዮ ጣቢያ አንዳንድ ፕሮግራሞች ላይ ምንትስ ስለሚባል ሰፈር ወጣቶች ድህነትትን ለመዋጋት በማህበር ስለመደራጀታቸው ሰምቻለሁ:: ምንትስ በሚባለው FM ራድዮ ዜጎች ያለ ፍርሃት በስነተዋልዶ ጤና ሲወያዩ ሰምቻለሁ፣ አይቻለሁ፤ ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተተገበረ ያለው ልማታዊ ጋዜጠኝነት ነው ብሎ አፍን ሞልቶ ማውራት ይችላል ለሚሉ ባልዳረባዎቼ እኔ ልላቸው የምችለው ነገር ቢኖር እነዚህ የክርክር ነጥቦች የየዋህነት አልያም የጅልነት ወይም ደግሞ አውቆ የተኛ ዓይነት የመከራከሪያ ነጥቦች ናቸው:: ምክኒያቱም ልማታዊ ጋዜጠኝነት በኀልዮት ደረጃ እንኳ በቅጡ ያልተደላደለ ወጥ የሆነ የጋዜጠኝነት ስነ ምግባር የሌለው ከምዕራባዊያን የጋዜጠኝነት ባህል እንኳ በምን እንደሚለይ ጥርት ባለ ሁናቴ ሳይታወቅ፥ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተተገበረ ያለው ልማታዊ ጋዜጠኝነት ነው ብሎ በችኮላ ከመደንገግ በፊት የሀገራችንን የሚዲያ መልክዐ ምድር(Media Landscape)፣ ህጋዊ ዳራቸውን እና ጋዜጠኞቻችን ሙያቸውን እየተገበሩ ያሉበትን አውድ በሚገባ ዘርዝር አድርጎ ማየቱ ይቀድማል ብዬ ስለማምን ነው:: ከዚህም ባሻገር የመገናኛ ብዙሃን የሥራ ባህል እና የጋዜጠኝነት ልምድ ትንተና ባንድ አገር ውስጥ ካላቸው ተጨባጭ ኹኔታ ነው መጀመር ያለበት፡፡ እስቲ ተጨባጩን የአገራችንን የመገናኛ ብዙሐን የሥራ ባህል እና የጋዜጠኝነትን ስራ አንኳር ነጥቦች በወፍ በረር እንቃኛቸው፦

## የኢቴቪ ልማታዊነት ሲጠየቅ

በሀገራችን የሚዲያ መልክዐ ምድር ላይ የሚገኙትን እድሜ ጠገብ እና ሰፊ ጂኦግራፊያዊ ተደራሽነት ያላቸውን የመገናኛ ብዙሃን፦ ኢቴቪ፣ የኢትዮጵያ ራዲዮ እና አዲስ ዘመንን ጨምሮ በየክልሉ የሚገኙትን የመገናኛ ብዙሐንን በባለቤትነት የሚያስተዳድረው መንግስት ነው:: ይህም በአዋጅ የተረጋገጠለት መብቱ ነው:: ነገር ግን መንግስትም ይሁን ግለሰብ በባለቤትነት የሚያስተዳድረው የትኛውም የመገናኛ ብዙሃን ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ትርፍን ከማጋበሻነት በተጨማሪ የባለንብረቱን የፖለቲካ አቋም ማራመጃ ለመሆን ምቹ ነው:: በዚህ ጉዳይ ላይ የመገናኛ ብዙሃንን የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ(Poletical Economy of the Mass Media) በመተንተን እውቅ የሆኑት ኖአም ቾምስኪን እና ኤድዋርድ ሄርማን በ 1988 "ይሁንታን ማምረት" (Manufacturing Consent: The Political Economy of

the Mass Media) በሚል ርዕስ ካሳተሙት መጽሃፍ የፕሮፓጋንዳ ሞዴል የሚለው ጽንሰ ሐሳብ የሀገራችንን የመገናኛ ብዙሃን መልክዐ ምድር እና የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ በደንብ አድምቶ ስለሚገልጽልኝ ዋቢ አድርጌ ከዚህ እንደሚከተለው እጠቀስዋለሁ (ትርጉም ራሴ)፦

"መሰረታዊ የሀብት እና የፖለቲካ ስልጣን ክፍፍል መዛነፍ በሰፊው በሚስተዋልባቸው ሀገራት መገናኛ ብዙሐን ስልታዊ በሆነ ዘዴ የሚስተዋለውን አለመመጣጠን የማድበስበስ ታላቅ ሚናን ይጫወታሉ:: በተለይም የስልጣን መዘውሩን የሚቆጣጠሩት ጥቂት ቢሮክራቶች ከሆኑ እና ሞኖፖላዊ የመገናኛ ብዙሐን ቁጥጥር የሰፈነበት ስርዐት ከሆነ በተለይ ደግሞ ሕጋዊም ሆነ ሕገ ወጥ (ጭማሪ ከራሴ) የቅድመ ምርመራ አሰራርን የሚያበረታታ ከሆነ የመገናኛ ብዙሐን ስልጣን ላይ ለሚገኙት ልሂቃን ጥቅማቸውን ማስጠበቂያ መሳሪያ መሆናቸው ሳይታለም የተፈታ ነው:: (ገጽ 1፤ 1988)

ይህ ማለት ደግሞ መንግስታት የህዝቡን አስተያየት በመገናኛ ብዙሐን በኩል በሚገባ ለመቆጣጠር እንዲያመቻቸው ዕድል ይፈጥርላቸዋል ማለት ነው:: በዚህም መሰረት መንግስታት በቁጥጥራቸው ስር የሚገኙትን መገናኛ ብዙሐን በመጠቀም ህዝቡ ወይም ጋዜጠኛው በራሱ ተነሳሽነት የመረጠውን ርዕሰ ጉዳይ ወይም በወቅቱ እየሆነ ያለውን እንገግጋቢ የመገናኛ ብዙሐንን ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ወደ ጎን በመተው የራሳቸውን እጀንዳ ማራጋቢያ እና የኢኮኖሚ ጥቅም ማስጠበቂያ ያረጉታል ማለት ነው::

ለጥቂ ይህንን በምሳሌ ላስረዳ ተከተሉኝ:: በሀገራችን የሚዲያ መልክዐ ምድር ላይ ከላይ ከጠቀስኩት የቾምስኪ እና የሄርማን ኀልዮት አንጻር በግሉም ሆነ በመንግስት የመገናኛ ብዙሐን የሚስተዋሉ የባለቤትነት ቁጥጥር ምሳሌዎችን በደምሳሳው ልጠቃቀስ:: ላካሄድ እንዲያመቸኝ ከስርጭት ሽፋን ተደራሽነት እና ስለ መንግስት መገናኛ ብዙሐን በዓይነ ህሊናችን ስናስብ ሁልዜም ድቅን ስለሚልብን የመንግስት መገናኛ ብዙሐን ፊት አውራሪ ከሆነው ኢቴቪ ልጀምር:: መንግስት ኢቴቪን ልክ እንደ ሐረር ሰንጋ ገመድ በአንገቱ ላይ አስሮ ወደ ፈለገበት እንደሚነዳው ከሚያሳብቅበት የመገናኛ ብዙሐን ቀዳሚው ነው:: በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ላይ የፍልስፍና ዲግሪ ጽሁፋቸውን የጻፉት ኖርዊያዊው ቴርዬ ስካርድል (Terje S. Skjerdal) በ2008 "Conflicting professional obligations among government journalists in Ethiopia" በሚል ርዕስ ካሳታሙት የጆርናል ጽሁፍ በመጥቀስ የክርክር ነጥቤን ላጠናክር ለነገሩ የኢቴቪን የመንግስት አፍነት ለማስረዳት ምስክር መጥቀስ አያሻውም:: ከወቀሳ ለመዳን ግን (Terje) ቴርዬ የጆርናል ጽሁፍን ሲጽፍ በማስረጃነት የተጠቀመውን ስሙ እንዲጠቀስ ያልፈለገ የኢቴቪ የእንግሊዝኛ ዴስክ ከፍተኛ ሪፖርተር በሀዳር 2000 የኢትዮጵያ የፕሬስ አዋጅ ከመጽደቁ በፊት ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞት ስለነበረው የፕሬስ አዋጅ የተቃውሚ ድምጾችን ያካተተ የዜና ዘገባ በመስራቱ በወቅቱ የማስታወቂያ ሚንስትር ከነበሩት ከአቶ በረከት ስሞኦን የደረሰበትን ጫና እንዲህ ያስረዳል (ትርጉም ከራሴ)፦

"የፕሬስ አዋጁ በጣም አፋኝ ነው የሚል አስተያየት የሚሰጡ በርካታ ሰዎች እራሱ አቶ በረከት ስሞኦን በሚመራው በፕሬስ አዋጁ ዙሪያ በተዘጋጀ የውይይት መድረክ ላይ በሰፊው ይደመጡ ነበር:: በመሆኑም በማታው የዜና እወጃ ሰዐት በዚህ ዙሪያ ባዘጋጀሁት የዜና ዘገባ ላይ የነዚህን ሰዎች እስተያየት አካትቼ አቀረብኩ::"

"በማግስቱ ግን እዛው ኢቴቪ ሕንጻ ላይ ይገኝ ከነበረው ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ስልክ ተደውሎ ተጠራሁ:: ሚንስትሩ በሰራሁት የዜና ዘገባ ተበሳጩብኝ:: ለምንስ እንዲህ ዓይነት ዜና እንደሰራሁ ጠየቁኝ:: እኔም ዜናው ባላንስ እንዲኖረው ወይም ሚዛናዊ እንዲሆን ነው ስል ያለ ምንም ፍርሐት ላስረዳቸው ሞከርኩ:: እሳቸው ግን ይህ የባላንስ ወይም የሚዛናዊነት ጉዳይ አይደለም:: ይህ የመንግስት መገናኛ ብዙሐን እንደ መሆኑ መጠን መስበክ ያለብህ ስለመንግስት ነው:: አሉኝ"::(ገጽ 6፤ 2008)

ሌላ ምሳሌ ልጨምር:: መሐመድ ሰልማን በ2011 ፒያሳ መሃሙድ ጋር ጠብቂኝ በሚል ርዕስ ካሳተመው የወጎች እና የመጣጥፎች መድብል መንግስት በመገናኛ ብዙሐን ላይ ያለውን ቁጥጥር እና የቾምስኪን እና የሄርማንን ኀልዮት ስነ ጽሁፋዊ ለዛ ባለው መንገድ ስለሚያስረዳልኝ ኢቴቪ እና ተዛማጅ ትዝታዎቼ ከሚለው መጣጥፍ የኢቴቪ የዜና ቀመር የሚለውን ቃል በቃል እንደሚከተው ገልብጬዋለሁ::

"ኢቴቪ አንድን ዜና ዘለግ ላለ ጊዜ እያቦካ የመጠቀም ባህል አለው:: ለምሳሌ ከአላማጣ ማይጨው መንገድ ሊሰራ ነው ብለን ብናስብ ከሚሰራው መንገድ ይልቅ ዜናው እንደሚረዝም በዚህ መልክ ማየት እንችላለን:: በትንሹ ከአንድ መንገድ አሥር ዜናዎች ይፈለፈላሉ::

1. ከአላማጣ ማይጨው የሚደርሰውን የጠጠር መንገድ ወደ አሥፋልት ለማሳደግ የሚያስችል ብድር ከቻይናው ማክሲም ባንክ ተገኘ።
2. ከአላማጣ ማይጨው የሚደርሰውን መንገድ ለመስራት ከቻይናው ሲራቢሲ ኩባንያ ጋር ስምምነት ተካሔደ::
3. ከአላማጣ ማይጨው የሚወስደውን መንገድ ለመጀመር የመሰረት ድንጋይ ተጣለ::
4. ከአላማጣ ማይጨው የሚወስደው መንገድ ግንባታ ተጀመረ::
5. ከአላማጣ ማይጨው የሚወስደው መንገድ ግንባታ እየተፋጠነ ነው ተባለ::
6. ከአላማጣ ማይጨው የሚወስደው መንገድ ግንባታ በመንተቱ ነዋሪዎች ተቸገርን አሉ::
7. ከአላማጣ ማይጨው የሚወስደው መንገድ ግንባታ 65 በመቶው ተጠናቀቀ::
8. ከአላማጣ ማይጨው የሚወስደው መንገድ ግንባታ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ይጠናቀቃል ተባለ:
9. ከአላማጣ ማይጨው የሚወስደው መንገድ ግንባታ ተጠናቀቀ::
10. ከአላማጣ ማይጨው የሚወስደው መንገድ ግንባታ በመጠናቀቁ የአካባቢው ነዋሪዎች ደስታቸውን ገለጹ::

ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ዜና በ10 ተመንዝሮ ሲቀርብለት 10 ጎዳናዎች የተሰሩለት ስለሚመስለው "ይህ መንግስት ምነኛ ልማታዊ ነው" ሲል ይገረማል::" (ገጽ 73/74 2004) የህዝብ ይሁንታን ማምረት ይሉሃል ይህ ነው:: ውዱ ባልደራባዬ መሐመድ ሆይ የኖአም ቾምስኪን እና ኤድዋርድ ሄርማን የፕሮፖጋንዳ ሞዴል ኢትዮጵያዊ በሆነ ትንትና ለማስረዳት ስራዬን ምነኛ አቀለልክልኝ?!

ከዚህ ባሻገር የመንግስት ጠንካራ የባለቤትነት ቁጥጥር በከፍተኛ ሁኔታ የሚስተዋልበት ከቅርብ ግዜ ወዲህ እንደ የአዲሱ ዘመን የመገናኛ ብዙሐን አውታር የሚቆጠረው የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ነው:: ከቴሌኮም አገልግሎቶች መሃከል የሞባይል ስልክ አገልግሎት እና ሌሎችም የመረጃ መረብ ወይም የኢንተርኔት አገልግሎቶችን ከ85 ሚሊዮን በላይ ለሚሆን የኢትዮጵያ ህዝብ በብቸኝነት የሚያቀርበው አትራፊው እና ብቸኛው የኢትዮጵያ ቴሌኮም ኮርፖሬሽን ነው:: ስለ ቴሌኮም የአገልግሎቶት ጥራት መጓደል ተጠቃሚው በሚገባ ስለሚያውቀው በዚህ ጽሁፍ ምንም አልልም:: በዚህ ላይ ተጠቃሚው ለቴሌኮም አገልግሎቶች የሚከፍለው ዋጋ እጅግ ውድ መሆኑን የ2011 የFreedom Houseን ሪፖርት ጠቅሶ ነብዩ እያሱ ስደት በጋዜጠኛው ዓይን በሚለው አዲስ መጽሃፉ ላይ ዘግቧል:: (ገጽ 312፤ 2004):: በአንጻሩ ግን ልማታዊ ጋዜጠኝነት በሰፊው ይተገበርባቸዋል በሚባሉት እንደ ህንድ ባሉ ሀገራት የቴሌኮም አገልግሎቶች የዜጎችን አሳታፊነት በማሳለጥ ዜጎች ለልማት ብቻም ሳይሆን ለመልካም አስተዳደር እና ለግልጽነት መጠናከር የድሮዎቹ የመገናኛ ብዙሐን ተብለው ከሚጠሩት እንደ ሬዴዮ እና ቴሌቪዥን ሁሉ ኅብረተሰብን በመቅረጽ ለሀገር እድገት የማይተካ ሚና ይጫወታሉ።

ከላይ የተቀሱት ማሳያዎች በኢትዮጵያ ሚዲያ መልክዐ ምድር ላይ አድራጊ ፈጣሪ መንግሥት መሆኑን ያረጋግጥልናል:: እላይ በጠቀስኩት የቾምስኪ እና የሄርማን ሀልዮት መሰረት ደግሞ መንግስት ከፍተኛ ቁጥጥር በሚያሳድርባቸው ሀገራት መገናኛ ብዙሐን የህዝብን ይሁንታ በማምረት ሥራ ነው የሚጠመዱት:: ይህንንም ሥራቸውን (ይሁንታ ማምረትን) የዳቦ ስም አውጥተውለት ልማታዊ ጋዜጠኝነት ይሉታል እንጂ ልማታዊ ጋዜጠኝነት የሚባል ነገር የለም፤ ለኔ ባሀገራችን የሚድያ መልክዐ ምድር ላይ ዛሬ የሚስተዋለው ከዚህ ብዙም የሚለይ አይደለም:: አቶ ማእረጉም ለማለት የፈለጉት ይህንኑ ይመስለኛል:: እስቲ አሁን ደግሞ ልማታዊ ጋዜጠኝነት ከኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሐን ሕግ አንፃር ምን ይላል::

## ልማታዊ ጋዜጠኝነት ከሕግ አንጻር ያስኬዳል?

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 29 ዜጎች ዘርፈ ብዙ ከሆኑ የመገናኛ ብዙሐን መረጃን የማግኘት እና የመሰላቸውን አስተያየት የመያዝ መብታቸው ተረጋግጦላቸዋል:: በተለይ ደግም በአንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት በመንግስት ቁጥጥር ስር የሚገኙ መገናኛ ብዙሐንም እንኳ ቢሆኑ የአስተሳሰብ እና የአስተያየት ብዙሐነትን (Diversity of Expression and Opinion) ማረጋገጥ አለባቸው:: በመንግስት ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ የተደረጉበት ምክንያት ይህንኑ ለማድረግ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የመገናኛ ብዙሐን እና የመረጃ ነጻነት አዋጅ ቁጥር 590/2000 መገናኛ ብዙሐን በነጻነት ስራቸውን ማከናወን እንዲችሉ ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን በድጋሚ አረጋግጧል:: እዚህ ላይ እንዲተኮርበት የምፈልገው ነጥብ ታዲያ በመንግሥት ቁጥጥር ስር የሚተዳደሩ የመገናኛ ብዙሀን እና የነዚሁ ድርጅቶች ምንደኛ ጋዜጠኞች የአስተሳሰብ እና የአስተያየት ብዙሐነትን በተግባር ለማረጋገጥ መትጋት አለባቸው እንጂ በልማታዊ ጋዜጠኝነት ስም ራሳቸውን እንደ ሀገር ገንቢዎችም ሆነ እንደ መንግስት አጋሮች በመቁጠር ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 5 ያረጋገጠውን ዲሞክራሲያዊ መብት እንዲጣስ

ተባባሪ መሆን የለባቸውም:: ከላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ትልልቅ መንግስታዊ አጀንዳዎችን ለሀገሪቱ ብቸኛና መለኮታዊ መፍትሄ አድርገው ያቀርባሉ መንግስትን የሚተቹ ዜጎችን ደግሞ ትችቱ ለምን እንኳ እንደተሰነዘረ ቀርበው እንዲያስረዱ ሳያደርጉ የሀገር ጠላቶች እና መርዶ ነጋሪ እንደሆኑ ተደርገው ይቀርባሉ:: ከሕጉ አንጻር ግን ይህ የመብት ጥሰት እንጂ ልማታዊ ጋዜጠኝነት አይደለም:: ለኔ አንድ ጋዜጠኛ በከፍተኛ የሞያ ልቀት እና የስነ ምግባር ብቃት ያለ መንግስትም ሆነ ያለ ቱጃር ተጽእኖ በነጻነት ስራውን ከሰራ እሱ ጋዜጠኛ ነው:: ከፈለጋችሁ ልማታዊ የሚል ቅጥያ ልትጨምሩበት ትችላላሁ::

## ነጻ የግል መገናኛ ብዙኃንስ?

በግል የመገናኛ ብዙኃንም ቢሆን የተጋነኑ "ልማታዊ" ዜናዎች ባይስተዋልባቸውም:: በማስታወቂያ አስነጋሪዎች ተጽእኖ ምክኒያት ማስታወቂያዊ ዜናዎችን፣ ማስታወቂያዊ ዶክመንተሪዎችን እና ሌሎችንም ፕሮግራሞች (Adevertorials) ማየትም መስማትም እየተለመደ መጥቷል:: በኤፍ ኤሞቻችንም ሆነ በጋዜጦቻችን አንዳንድ ዘገባዎች ላይ እነዚህን ክፉ የጋዜጠኝነት ተግዳሮቶች አልፎ አልፎ አያለሁ:: ስም ሳልጠቅስ ምሳሌ ልስጥ፤ አንድ ማንትስ የሚባል ወፍ ዘራሽ ቱጃር BIKS የሚባል ብስኩት ፋብሪካ በቅርቡ ከፍቷል ወይም አለው እንበል:: ይህ ወፍ ዘራሽ ቱጃር ብስኩቱን በገፍ መሸጥ ይፈልግ ስለነበር ማስታወቂያ ማሰራት ያስባል:: ከተማው ውስጥ ያሉት የማስታወቂያ ለፋፊ ድርጅቶች በደቂቃ ታይታ/ተሰምታ ለምታበቃ ማስታወቂያ ዋጋቸው የሚቀመስ አልሆነለትም:: በዚህ ላይ ማስታወቂያ ማስታወቂያ ነው:: በአጋጣሚ አንድ ቀን ይህ ባለሀብት ማንትስ ልማት ማህበር ባዘጋጀው ቴሌቶን ላይ አንድ ሁልግዜ በራዲዮ ድምጹን እየሰማ ባካል ግን የማያውቀውን ትንታግ ልማታዊ ጋዜጠኛ ይተዋወቃል:: አጋጣሚውንም በመጠቀም ለልማታዊ ጋዜጠኛው ማስታወቂያ ማሰራት ፈልጎ ዋጋው አልቀመስ እንዳለው ይነግረዋል መፍትሄ ካለውም እንዲያማክረውም ይጠይቀዋል:: ጋዜጠኛውም የሆነ አካባቢ ስለሚኖሩ ምንዱባን ያአኗኗር ችግር የሚመለክት የራዲዮ ዶክመንተሪ ለመስራት እያሰብኩ ነው ይህንን ፐሮግራም በአነስተኛ ዋጋ ስፖንሰር አድርግና ስለ BIKS ብስኩት ፋብሪካ ሰፋ ያለ እና ተከታታይ የዜና ዘገባ ላቅርብልህ የሚል የልማታዊ ጋዜጠኝነት ሞያዊ ምክሩን ሰጠው:: በዚህም ተስማሙ ባለጸጋውም ከፍተኛ ከሆነ የማስታወቂያ ወጪ ከመዳኑም ባሻገር በቀላል ወጪ የኩባንያውን ስም በተጋጋሚ ማህበራዊ ችግሮችን ከሚፈቱ ልማታዊ ሀገር በቀል ኩባንያዎች ተርታ ተሰለፈለት:: ህዝቡም ይህንን ልማታዊ ባለጸጋ ለሀገር አሳቢ ለደሀ አዛኝ አድርጎ ስለሚያስበው ብስኩት ሲገዛ ሁልግዜም የBIKSን ነው::

እዚህ ላይ ግን የማስታወቂያ አስነጋሪ ባለሀብቶች የዜና ሽፋን ስጠኝ እና ማስታወቂያ ልስጥህ ተጽእኖ የትም ሀገር ላይ ያለ ተጸእኖ ስለመሆኑ ዋቤ መጥቀስ አያሻውም ቢሆንም ግን እንደኛ የፋይናንስ ነጻነታቸው እጅግ ፈታኝ እና እስቸጋሪ የሚሆኑባቸው የግል መገናኛ ብዙሀን በሚገኙባቸው ሀገራት ማስታወቂያዊ ዜናዎችን በልማታዊ ጋዜጠኝነት ስም መስራት መፍትሄ የሌለው መሆኑን እገነዘባለሁ:: የሀገራችን በተለይ የህትመት የግል መገናኛ ብዙሐን እለት እለት እያሻቀበ የመጣውን የህትመት ዋጋ ለመቋቋም ሲሉ በዚህ ዓይነት ተጽእኖ ውስጥ መግባታቸው ሳይታለም የተፈታ ነው:: ነገር ግን አሁን በሀገራችን በህትመት ላይ የሚገኙትን በተለይ ከፋይናንስ ተጽእኖ ውጪ ያሉትንም ፖለቲካዊ ጫናዎች ተቋቁመው በነጻነት ያለ ፍርሀት የጋዜጠኝነት ስራቸውን ለሚሰሩ ምስጋና ቢያንሳቸው እንጂ አይበዛባቸውም:: እኔም ለስራቸው መገን እላለሁ::

## ማጠቃለያ

የሀገራችንን የሚድያ መልክዐ ምድር በአንድ ተራራ እንመስለውና ይህንን ተራራ ለሁለት የሚከፍል ትልቅ ሸለቆ አለ ብለን እናስብ:: ከተራራው ግርጌ እስከ ጫፉ ድረስ ያለውን ምቹ እና ገላጣ ስፍራ የመንግስት የመገናኛ ብዙሀን የሚባሉ መጥቀስ ቢያስፈልግ፦ ኢቴቪ፣ የኢትዮጵያ ራዲዮ፣ አዲስ ዘመን፣ ሄራልድ፣ FM97.1 አሁን ደግሞ በየክልሉ ያሉ የመንግስት አዳዲስ የክልል "ኢቴቪዎች" እና የግል ወይም ነጻ የሚል ቦሎ ለጥፈው በልማታዊ ጋዜጠኝነት ስም በመዝናኛ እና ስፖርታዊ አደንዛዥ ወሬዎች አየሩን የተቆጣጠሩ የሰፈሩበት ሲሆን ተራራውን ለሁለት በሚከፍው ትልቅ ሸለቆ ውስጥ ደግሞ በመሰናክሎች የተተበተቡ ከህዝብ ጋር ለመገናኘት ወደ ተራራው ገላጣ ስፍራ ለመውጣት ሙከራ ሲያደርጉ በሸለቆው ዳር እና ዳር የቆሙ እና ሰፊውን የተራራ ክፍል የማያስደፍሩ ሰዎች መልሰው ወደ ሸለቆው የሚከቷቸው ራሳቸውን የነጻው ፕሬስ አባላት እያሉ የሚጠሩ በተራራው ገላጣ ስፍራ የሚገኙት ደግሞ የግል ሚዲያ እያሉ የሚጠሯቸው የሚገኙበት የተራራው ክፍል ነው:: በዚህ ዓይነት የሀገራችን የሚዲያ መልክዐ ምድር ታዲያ ሊኖር የሚችለው ልማታዊ ጋዜጠኝነት ወይስ የጋዜጠኝነት ጣዕረ ሞት?

# እንዴት እንደመጥ?

በስካይፕ ካንድ ወዳጄ ጋር በማውራት ላይ እያለን እንዳጋጣሚ ሆኖ በኔ በኩል ያለው ማይክ መስራት አቆመ፡፡ የነበርኩበት ኢንተርኔት ካፌ ውስጥ፣ ስካይፕ ለማስጠቀም አገልግሎት የሚሰጡ ውስን ቦታዎች ሁሉም ስለተያዙና መቀየር ባለመቻሌ እዚያው የነበርኩበት ቦታ ሆኜ የወዳጄን ወሬ በጆሮዬ እየሰማሁ ምላሼን በጽሑፍ ለማድረግ በመወሰን ወሬያችንን ቀጠልን፡፡ እሱ በቃላት ለሚያወራልኝ ነገር እኔም በጽሑፍ እየመለስኩ ጥቂት እንደቆየን የኔ የጽሑፍ ምላሽ እሱ ለሚያወራልኝ ነገር ተመጣጣኝ ምላሽ መስጠት እንደማይችል ገባኝ፡፡ የሚያበሳጭ ነገር ሲያወራ እኔ ከዚህ በኩል ሆኜ እንዴት በብስጭት እንደማወራ አይሰማኝም፤ እንደማይሰማኝ እያወኩም የምፅፈውን ብስጭቴን ጮክ ብዬ ማለቴም አልቀረም፡፡ የሚያስደስትና የሚያስቅ ነገር ሲናገርም እንዲሁ ባለሁበት ሆኜ እደሰታለሁ እስቃለሁ፡፡ እሱ ግን አይሰማኝም፡፡ለተናገረው ነገር ምላሽ ፅፌ ሳልጨርስ ሌላ ወሬ ይጨምራል፡፡ ለሌላኛውም ምላሽ ልሰጥ ስሞክር ሌላ ንግግር፡፡ በዚህ ምክንያት ምንም ሳንግባባ እኔም ምንም ተመጣጣኝ ምላሽ መልስ ሳልሰጥ በሌላ ቀን ለመገናኘት ተቀጣጥረን ተለያየን፡፡

የነበርኩበትን ሁኔታ የተሰማኝን ስሜት እንደኔ አጋጥሟችሁ የምታቁ በጣም ትረዱታላችሁ ብዬ አስባለሁ፡፡ ከወዳጄ ጋር ከመጨረሳችን በፊት በዚህ ተስማማን-----ለካ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝቦች በእንዲህ ባለ መልኩ ለመግባባት እየሞከሩ ነው - የህዝብ ጩኸት ሊደመጥ ያልቻለው፡፡ በትርጉም ደረጃ መንግስት ማለት ህዝብ እንደሆነ ነው የምናቀው፡፡ መግባባት ባለመቻላችን ግን የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ ተለያይተናል ብዬ አምናለሁ፡፡የህዝብ ተወካይ ተብለው ምክር ቤቶችን ጨምሮ በተለያየ ቦታ የሚገኙ ሰዎች ጥረታቸው ገዢው ፓርቲው የሚለውን ሁሉ ለህዝብ ለማሳመን እንጂ የወከላቸውን ህዝብ ሃሳብ ለመንግስት ሲያቀርቡ አይደለም፡፡ በስም ብቻ የህዝብ ተወካይ ተባሉ እንጂ በስራቸው የገዢው ፓርቲ ተወካዬች ናቸው ማለት ነው፡፡

ስለዚህም መንግሥት እነዚህ ወኪሎቹን እንደልሳንነት እየተጠቀመባቸው እንደሚገኝ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ እንዲሁም 99% የሚሆነው ሚዲያ ተጨማሪ የመንግስት ልሳን በመሆን ያገለግላል፡፡ የመንግስት ልሳን ደግሞ የሚያወራው ወላጅ ለልጁ አበላ፣ አጠጣና አለበሰ ዓይነት ወሬዎችን ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ወሬዎች እንዴት ዜና ሆነው ወይም እንደ ተአምር ተቆጥረው በተደጋጋሚ እንድንሰማቸው ሲደረግ ይገርመኛል፡፡ በጣት ከሚቆጠሩ ጋዜጦች በስተቀር ሬድዮና ቴሌቭዥን ጣቢያዎች ጨምሮ ሙሉ ለሙሉ በዚህ ተግባር የተጠመዱ ናቸው፡፡ ለዚህም ይመስለኛል በጣት የሚቆጠሩት ጋዜጦች በአብዛኛው የመንግስትን አግባብ ያልሆኑ ስራዎችንና የህዝብን አቤቱታ ወይም በደል በማሰማት ብቻ የተወሰኑት፡፡ በነዚህ ውስን ጋዜጦችና ፓርላማ ባለ አንድ የህዝብ ተወካይ አማካኝነት ሃሳቦቻችንን ለመግለፅ ቢሞከርም ከመንግስት ልሳን ጋር ተወዳድሮ ተደማጭነትን ማግኘትና መፍትሄ ማስጠት መቻል የህልም እንጀራ የሆነብን ነገር ነው፡፡

## "ጉድ" አንድ ሰሞን ነው?

ጋዜጦቹ በሳምንት በሚወጡበት ጊዜ ብዙ አዳዲስ ዜናዎችን፣ ክስተቶችን እና ትችቶችን ይዘው ይወጣሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜም ቢሆን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ወቅታዊ ጉዳይን እስመልክቶ የሚሰጡትን መግለጫ ወይም ተቃውሞ ያቀርባሉ፡፡ በተደጋጋሚም መንግስት ህገመንግስቱን አክብሮ እየሰራ እንዳልሆነ፤ እራሱ እንድንመራበት ቀን ከለሊት እየተናገረ ነገር ግን ተግባር ላይ እያዋለው እንዳልሆነ ይናገራሉ፡፡ ግን መቼም ጊዜ መንግስት ጆሮ ገብተውና ምላሽ ተሰጥቷቸው አያቁም፡፡ እነዚሁ ጉዳዮች በፌስቡክና በተለያዩ ማህበራዊ ድረገፆችም ያንድ ሰሞን ጉዳይ ሆነው ለውይይት ይቀርባሉ፡፡ የማበራዊ ድረገፅ ተጠቃሚዎች ባላቸው እውቀት እና ችሎታ ተጠቅመው በጉዳዩ ላይ ገለፃቸውን እና ትንታኔያቸውን ያካሂዳሉ፡፡ ሌላ አጀንዳ ሲመጣ ደግሞ የፊተኛው ይረሳና ስለ አዲሱ ጉዳይ ብቻ ይሆናል ወሬው፡፡

ጉዳዮቻችን በተቻለ ፍጥነት ምላሽ ወይም እርምት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ሆነው ሳለ መንግስት ግን ከዝምታ የዘለለ ምላሽ ሲሰጥ አይስተዋልም፡፡ ምላሽ ተሰጠም ከተባለ ፓርላማ ውስጥ እንደምናየው የተድበሰበሰ ወይም ጥያቄውን ሳይሆን ጠያቂውን በመዝለፍ ወይም ደግሞ ኢ-ተአማኒ የሆነ ማስተባበያ በመስጠት ይሆናል፡፡ ፓርላማውማ የሹፈት መድረክ ከሆነ ቆይቷል፡፡ የጠ/ሚኒስቴሩን ኩምክና እንጂ ለተነሱት ጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሾችና ማብራሪያዎች ሰምተን አናውቅም፡፡ ሌላ አንገብጋቢ ጉዳይ ሲከሰትም እንዲሁ ይፃፋል፣ ይተቻል፣ ይተነተናል ወይም ፓርላማ ይቀርባል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ተድበስብሶ ወይም ‹ምላሽ ተሰጠ› ተብሎ ይታለፋል፡፡ አንዳንድ ጌዜ ደግሞ ትችቱ ወይም ጥያቄው አዲስ በወጡ አዋጆች ላይ ይሆንና ከተጠበቀው በላይ ጥያቄዎች ሲኖሩ የሚሰጡት ምላሾች የሚገርሙ ናቸው፡፡ አንደኛው ምላሽ ጥፋት እንደተሰራ ማመን እና አዋጁ ሲረቀቅ

ህዝብ ማሳተፍ እንደነበረበት ወደፊት እንዲህ ዓይነት አዋጅ ሲወጣ ተመሳሳይ ጥፋት እንደማይሰራ ይነገረናል። ጥፋትን ማመን ምላሽ መሆኑ ነው እንግዲህ። ልክ ‹አዎ የመንግስት ሌቦች አሉ› እንደተባልነው ዓይነት ማለት ነው። ሌላኛው አዋጁ ከወጣና ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ህዝብ እንዲወያይበት ማድረግ በሚል ውይይት ሳይሆን ተሰብሳቢወቹ አዋጁን ተምረው እንዲወጡ የሚደረግበት አካሄድ ነው።

በጋዜጦቹ ላይ የምናነባቸው ትችቶች ወይም የሚነሱ ጥያቄዎች የአንድ ሰሞን መነጋገሪያ ርዕስ ከመሆን አልፈው መፍትሄ ወይም እርምጃ ተሰጥቶባቸው አያውቁም። ይህ በሃገራችን የተለመደ ዑደት ነው። ኢሕአዴግ ከዚህ ዑደት ለመውጣት ጥረት ሲያደርግ አይታይም። በተቃራኒው በተገኘው አጋጣሚ እንዲህ ዓይነት ትችት የሚፅፉትን ማሰር፣ እንዲሰደዱ መገፋፋት እና ህትመቱ እንዲቆም ሲያደርግ ነው የምናየው። በማህበራዊ ድረገፆች የሚደረጉትን ትንታኔዎችና ውይይቶችንም ለመገደብ ድረገፆቹ በሃገር ውስጥ እንዳይታዩ ማገድ ዋነኛ ተግባሩ ነው። ከዚህ የምንረዳው ጩኸታችን መሰማት በማይቻል መጠን ሆኖ ሳይሆን መንግስታችን ካሉት የስሜት ህዋሳት ጆሮውን ሊሰጠን አለመፈለጉን ነው። እንዲያውም ዝም ብንል እንደሚመርጥ በተለያየ መልኩ እየገለፀልን ነው።

**አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም** እንደሚባለው መንግስት ሆን ብሎ እያወቀ ‹‹አልሰማም!›› ከሆነ ያለን መቼም የሚሰማን አይመስለኝም። ጆሮው ለሚሰማ ሰው ስንናገር የማይመልስልን ምን ሲሆን ነው? ምንም እንደማናመጣ ሲያስብ፣ መልስ ሲያጣ እና ለኛ ግድ ሳይሰጠው ሲቀር (ሲንቀን) ነው። መንግስትም የኛንም ጩኸት ሰምቶ ምላሽ የማይሰጥበት ምክንያት ከዚህ ውጪ አይሆንም። ስለዚህ ምንም አታመጡም እየተባልን ነው ወይም ለጥያቄዎቻችን መልስ የለውም ወይም ንቆናል ወይንም ሁሉንም። እና መፍትሄው ምን ይሁን ትላላችሁ? እስቲ እንምከርበት።

# ዳኛቸውና ገዢ ሐሳቦቹ

የአገራችንን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ስፋት እና ጥልቀት ስናስተውል ብዙዎቻችንን በቀቢጸ ተስፋ እንባክናለን፡፡ ይህን ለማሻሻል የተጀመረ ተዋስኦ አለመኖሩ ደግሞ ሀዘናችንን እጅግ ያበረታዋል፡፡ በተማሩትና በሰለጠኑበት የሙያ ዘርፍ ዙሪያ እንኳን ትንፍሽ የማይሉ ነገር ግን ማዕረጋቸው ላጠራር የከበደ ሰዎች በየመስኩ ተደርድረዋል፡፡ብዙዎቹ ልሂቃን ትውልድን በሚገራና አቅጣጫ በሚያሳይ መልኩ አርአያ አለመሆናቸው አገሪቱ በሐሳብ ክፍተት እንድትዳክር አድርጓታል፡፡ ዞን ዘጠኝም የነገዋ ኢትየጵያ መጻዒ ተስፋ የሚያሳስባቸው ወጣቶች ስብስብ እንደመሆኑ መጠን የራስንም የአቻንም መደናበርን ለመቀነስ ወይም ሐሰሳን ለመደገፍ ስናስብ አገሪቱ ካሏት ጥቂት የአደባባይ ምሁራን አንዱ የሆነው ዶ/ር ዳኛቸው አሠፋ ላይ አይናችን አረፈ፡፡ **(በዚህ ጽሑፍ ላይ እኚህን የተከበሩ ምሁር ‹አንቱ› ሳንል የቀረነው፣ ለንባቡ ቅልጥፍና እንዲመች በማሰብ መሆኑን አንባቢዎች እንድታውቁልን፡፡)**

ከዚህ በፊት ለአደባባይ የዋሉት *ሥራዎቹ* እጅግ ቢማርኩንም ወጥ የሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይህንን የሐሳብ ኦና (idea vacuum) ለመሙላት ከሚታትር መምህር የበለጠ ለመቅሰም በአንድ ወዳጃችን እርዳታ አገኘነው፡፡የዳኛቸው ሐሳቦች እጅግ የሚገዙ ለአብዛኛው ሰው ቅርብ የሆኑና በቀላሉ በሚገቡ ናቸው፡፡ ሀገራዊ ስነ ቃሎችና ስነጽሑፎችን በማጣቀስ፣ የሀገራችንን የቅርብና የሩቅ ታሪኮች ከፍልስፍና ንድፈ ሐሳብ ጋር በማጣመር የመተንተን አቅም አለው፡፡ ይህንን ታላቅ ምሁር ከአዲስ አበባ የኒቨርሲቲ ውጭ ላለው የህብረተሰብ ክፍል በማስተዋወቅ አዲስ ነገር ጋዜጣ ጉልህ ሚና ተጫውታለች፡፡ በወቅቱ በእስር ቤት የነበረችውን የአእምሮ እስረኛ ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳን እስራት ኢፍትሕዊነት አስመልክቶ በጻፋቸው ተከታታይ ጽሑፎች ወደ አደባባይ ብቅ ያለው ዶ/ር ዳኛቸው በብዙ አካዳሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ዙርያ ገዢ ሐሳቦችን እያካፈለ ይገኛል፡፡እኛም ከነዚህ ብዙ ጉዳዮች ውስጥ የተወሰኑትን በመምረጥ ትውልድ ሊያተኩርባቸው እና የምር ሊያነባቸው እና ሊያዳምጣቸው የሚገቡ መሆናቸውን ለመጠቆም እንዲህ አቅርበነዋል፡፡

## ስለ የአደባባይ ተዋስኦ /public discourse/

ዶ/ር ዳኛቸው የዲሞክራሲ ባህል እንዲዳብር ከተፈለገ ጫፍ አልባ ውይይት (endless conversation) ያስፈልጋል ይላል፡፡ በንግግር ተዋስኦ የሚመጣው ችግር በበለጠ ንግግር ማሸነፍ ይገባል ሲልም ይከራከራል፡፡ አንዳንዶች ያለገደብ ውይይትን መፍቀድ ለብዙ የምግባር ችግሮች (ዘለፋ፣ ስድብ እና ልቅ ወሲብ ቀስቃሽ ምርቶች ለመሳሰሉት..) ይዳርጋል ይላሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች መኖራቸው አይካድም፡፡ ይህ ግን እቀባ/ እግድ በመጣል ሊፈታ አይችልም፡፡ ከነጻ ንግግር የሚመጣን ችግር ለመፍታት የበለጠ ነጻ ንግግር (more free speech) መፍቀድ ይገባል፡፡ ብሔርን ከብሔርን ያጋጫል፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት ያላትማል የሚል ሰባራ ሰንጣራ ምክንያት በመስጠት ነጻ ንግግርን/ማሰብን ለማለፍ ወይም ለማገድ መሞከር ተገቢ አይደለም ይላል፡፡ የውይይት ባህል መዳበር እንዳለበት ሲያስረዳ ደግሞ አውሮጳውያን የዲሞክራሲ ባህል ጉዞን ሲጀምሩ በዘመነ አብርኖት (enlightenment) ወደ አንድ ክፍለ ዘመን ለሚጠጋ ጊዜ የነበራቸውን ወግ እና ባህል ፈትሸዋል፡፡ ሰፋ ያለ የውይይት ዘመንን በማለፍ ከዲሞክራሲ ባህል ጋር ተለማምደዋል ከዲሞክራሲ አሰራር ጋር የሚጣረሱ ተግባራትን እና ጽንሰ ሐሳቦችን ሁሉ ለማጥራት ችለዋል ይለናል፡፡

## ኢትዮጵያ እና የአደባባይ ተዋስኦ ባሕላችን

አውሮጳውያን የአደባባይ ተዋስኦ ባህላቸው እጅግ የጠነከረ እንደሆነ የሚመሰክረው ዶር ዳኛቸው ለዚህም በዘመነ አብርኖት የዲሞክራሲ ባህላቸውን እንዳያዳብሩ የሚያግዱ ጽንሰ ሐሳቦችን በይፋ በውይይት ማስወገድ በመቻላቸው እንደሆነ ያስረዳል:: ከነዚህ ጽንሰ ሐሳቦች ውስጥ ተጠቃሹ *ማኒያዊነት* ይሰኛል፡፡

የኢትዮጵያ ባህል በተወሰነ *መልኩ ማኒያነዊነት* (Manichaeism) እንደተጫነው የሚጠረጥረው ዶ/ር ዳኛቸው ለዚህ እንደማስረጃ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገድላትን ይጠቅሳል፡፡ ማኒያነዊነት አስተምህሮ መነሻው በሦስተኛ ክፍለ ዘመን በተነሳ እና ራሱን ከዞራስተር፣ ቡዳህና ክርስቶስ ቀጥሎ የመጣ የመጨረሻው ነብይ አድርጎ በሚቆጥረው በማኒ ነው፡፡ *ማኒያዊነት* የኖስቲክዝም (Gnosticism) ክፍተኛ ተጽእኖ ቢኖርበትም መሰረታዊ አስተምህሮው መላውን ጠፈር በክፉና ደግ አምላክ ትግል እንደተፈጠረች በመጥቀስ ነገሮችን ሁሉ ቅዱስና ርኩስ ብርሃንና ጨለማ በማለት ምንታዌ አድርጎ ይከፋፍላል፡፡ ይህ አስተሳሰብ በአገራችን መኖሩ የዴሞክራሲ ባህልን እንዳንገነባ እንቅፋት ሆኖብናል፡፡

ግሪኮች አንድ ፓለቲካዊ ፍልስፍናቸውን የገለጹበት ብሒል አላቸው፡፡ አንተ መንግስትን ማማት አትችልም ምክንያቱም አንተ ራስህ የመንግስት ነጸብራቅ ነህና ግዛትና ባህሉ (state and culture) ተዋህዶ የሚኖር ነው፡፡ ብዙ ጊዜ አምባገነን መሪዎችን በማየት የኛ ናቸው ለማለት ስንቸገር ይታያል:: እንደ ዶ/ር ዳኛቸው ሐሳብ ግን እነዚህን አምባገነኖች የሰራቸው የኛው ማኅበረሰብ ባህል ነው፡፡ ለዚህ እንደማስረጃ መንግስቱ ኃ/ማርያም፣ መለስ ዜናዊና ኢሳያስ አፈወርቂን እንደምሳሌ ያቀርባል፡፡ በውጭ ትምህርት መልክ ለመደበቅ ቢሞክርም የኢትዮጵያዊ ባህል ማሳያ ናቸው፡፡ ምርጫ 97ን ተከትሎ በሀገራችን የተከሰተው ውዥንብር ማንሳት ይቻላል፡፡ Politics is the art of compromising *(ፖለቲካ ማለት የማመቻመች ጥበብ ነው፡፡)* በባሕላችን ያለው ማኒያዊነትግን ይህን እንድንረዳ አልፈቀደልንም፡፡ መንግስት ፍጹማዊ ድል ለመጎናጸፍ የቅንጅት መሪዎችን በመወንጀል ሰብስቦ አሰረ፡፡ ቅንጅት ደግሞ ህዝቡ ተሰልፎ የሰጠውን መብት ሙሉ በሙሉ አልተሰጠኝም በማለት አልቀበልም የምፈልገው ፍጹማዊ ድልን ነው አለ በማለት ዶ/ር ዳኛቸው ይተነትነዋል፡፡

## የዘመን መንፈስ

እንደ ሔግሊያን አመለካከት በአንድ ሀገር መንግስትን የሚበይነው (assign) የሚያደርገው መንፈስ አለው፡፡ ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ እጓለ ገብረ ዮሐንስ "የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ" በተሰኘ መጽሐፋቸው መግቢያ ላይ አውሮጳ፣ በጀርመን ሀገር ሳሉ ላዩት ለዚያ ዘመን ወጣት መንፈስ መጽሐፋቸውን እንደመታሰቢያ ሲያቀርቡ *"ከፍተኛ መንፈስ ለተነሳው ወጣት እጅ መንሻ እንዲሆነኝ..."* ማለታቸው በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ስለነበረው ለመማር፣ ለማወቅ፣ አገርን ለመለወጥ የሚያስብ መንፈስ እንደነበረ እንረዳለን፡፡ እያንዳንዱ ስርዓት የራሱ መንፈስ አለው፡፡ ከዚህ መንፈስ ውጭ ከዚያ ስርዐት መጠየቅ አስቸጋሪ ነው፡፡

እንደ ዶ/ር ዳኛቸው ትንተና የአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስተ ሦስት የዘመን መንፈሶች ነበሩበት፡፡ የመጀመሪያው ምንሊክ እንደወለላ ትተዋት የሄዷትን አትዮጵያ ማያያዝና አሐዳዊ ስርዓትን መዘርጋት ነበር፡፡ ሁለተኛው ደግም ከቅኝ ገዢዎችና ኢምፔሪያሊስቶች ትንኮሳ ሉዓላዊት ኢትዮጵያ መጠበቅና የተከበረ የውሃ በርን በበሰለ ዲፕሎማሲ አንድ ጥይት ሳይተኮስ ማስገኘት ነበር፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ዘመናዊት ኢትዮጵያን መገንባት ሲሆን ይህም የሞሶሎኒን አማካሪዎች አስደንግጦ *"ለተፈሪ አስር አመት ከሰጠኸው ኢትዮጵያን ዘመናዊ ያደርጋታል፤ ቶሎ ብለህ ኢትዮጵያን ውረር፤ ኋላ አልሰለጠነችም ብሎ ለመውጋት አስቸጋሪ ነው"*የሚል መልእክት እንዲስተላለፉ አስገድዷቸዋል፡፡ የዘመናቸው መንፈስ ያዘዛቸው ይሄን ነው፡፡ ወታደራዊው መንግስት አገርን ለማያያዝ ካደረገው ጥረት ውጪ የረጋ የተጨበጠ መንፈስ አልነበረውም፡፡ ኢህአዴግም ለወጉ ዴሞክራሲ፣ ፌደራሊዝም፣ ሕገ መንግስት የመሳሰሉ ነገሮችን ቢያወራም መንፈስ ግን ያን አላሸከመውም፡፡ በዲሞክራሲ በኩል፣ በነጻነት በኩል፣ በመብት በኩል መመልከት ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ነው፡፡ አሁን እንደተረዳደሁት ይላል ዶ/ር ዳኛቸው ዴሞክራሲዊነት እንዲያብ፣ ሕገ መንግስታዊነት እንዲመጣ፣ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ መንፈስ እንዲነሳ ኢህአዴግ መታለፍ (supplant) አለበት፡፡ አሁን ኢሕአዴግም ይህን የተረዳ ይመስላል በሚዲያው ስለልማት፣ ስለዕድገት መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ስለማሰለፍ ብቻ ነው የሚያወራው፡፡

## ወንበር በሌለበት ኢትዮጵያዊ ፍልስፍና!?

ሁለት ዓይነት ፍልስፍናዎች አሉ የመጀመሪያው በእንግሊዘኛው small p የሚጽፉት ፍልስፍና (philosophy) ሲሆን ሁሉም ሰው ይህ ፍልስፍና አለው፡፡ ገንዘብ አወጣጥ፣ ልብስ አስተጣጠብ፣ የምግብ አበሳሰል የመሳሰሉት... ለነገሮች ያለው አዝማሚያ ማለት ነው፡፡ *'ብዙ ገንዘብ ለሰው ማበደር አልወድም፤ ይህ ፍልስፍናዬ ነው'*ማለት ይቻላል፡፡ በcapital P የሚጽፉት (Philosophy) ግን የተወሰኑ መመራመሪያ መንገዶችን አበጅተው መሰረታዊ ጥያቄዎችን በማንሳት የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው፡፡ አርስቶትል በሜታፊዚክስ እንዲህ ብሏል *"እኛ ብቻ ነን እውነት ላይ ለመድረስ መፈላሰፍ አለብን ያልን ለሌላ ነገር አይደለም፤ ግብጾችን እዩ ስልጣኔ አላቸው ግና ከኋላ ሌላ ዓላማ አላቸው፣ ፐርሺያንም ተመልከቱ እኛ ብቻ ነን ፍልስፍናን ለፍልስፍና ስንል የተከተልን"*ብሏል፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ፍልስፍና ስንመጣ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ሺህ ዓመታት የዘለቀ በሀይማኖታዊ አሻራ የቀለመ የትምህርት ዘይቤ አለ፡፡ ይህ የትምህርት ስርዓት በክፋፈላቸው ውስጥ ፍልስፍና የሚያስተምር የትምህርት ዘርፍ የለም፡፡ ከዋሽራ ጀምሮ ባሉ አድባራት እኔ መምህር እገሌ ፍልስፍና አስተምራለሁ ብሎ ወንበር የተከለ መምህር የለም፡፡ ወንበር ማለት የትምህርትና ስልጠና ተቋም (institution) ማለት ነው፡፡ በቅርቡ የተነሳ የሳይንስ ታሪክ ምሁር በመካከለኛው ዘመን የነበረ የእስልምና ሳይንስ የት ደረሰ ብሎ ይጠይቃል፡፡ በመስቀል ጦርነት ወቅት ምዕራባውያን እና ሙስሊሞች ሲዋጉ ምዕራባውያኑ በወታደሮች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ከርኩስ መንፈስ ጋር

በማያያዝ በጠበል እና በጸሎት ለመፈወስ ሲተጉ የሙስሊም ሀኪሞች ግን በተቃራኒው በሰውየው ላይ ደረሰውን የጎራዴው ጋር እና ሌሎች ሁኔታዎች ጋር በማያያዝ ሳይንሳዊ ግምት ለመስጠት ጥረት ያደርጉ ነበር። ከላይ ያነሳነው የታሪክ ምሁር እንዲያ ተስፋ ሰጭ የነበረው የእስልምና ሳይንስ ወዴት ጠፋ ብሎ ይጠይቅና የምዕራብ ክርስትና በመካከለኛው ዘመን ለነበረው እውቀት፣ ፍልስፍናና ወንበርን ስትሰጠው እስልምና ግን ወንበር ባለመስጠቷ የያ ተስፋ ሰጭ (promising) ሳይንስ ሊጠፋ ችሏል። በኢትዮጵያም እንዲሁ ወንበር ስላልነበረ ፍልስፍና አለ ለማለት አይቻልም ባይ ነው - ዶ/ር ዳኛቸው።

የዘርዓ ያዕቆብን እንደ ብልጭታ (Bleeps) ማንሳት ይቻላል። ነገር ግን ይህን ከምዕራባውያን ተማረው ለማለት አይችልም። በሌሎች የአፍሪካ ሀገር እንዳደረጉት እንዲሁ ጋልበውት (በባህል፣ በሀይማኖት) እንደሄዱት በኢትዮጵያ ተመሳሳይ ሁኔታ አልገጠማቸውም። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ሲደርሱ የራሳችን የሆነ ቅዳሴ (Liturgy)፣ ትርጓሜ (hermeneutics) የንባብ ባህልና ስነ ጽሑፍ እንዳለ ሲያዩ እንደደነበሩ (shoked እንደሆኑ፣) ይህም ድንጋጤያቸው እስከ ቅርብ ጊዜ አብሯቸው እንደቆየ እንደሚገምተው ዳኛቸው ሐሳብ በዘመኑ የነበረው ተጋላጭነት (exposure) ይህን በራሱ እንዲጠየቅ አድርጎታል። ለዚህ እንደ መነሻ የሚያገለግለው በዘርዓያዕቆብ ዘመን የመንበረ ጳውሎስ ትርጓሜን፣ የእስክንድርያንም፣ የኢትዮጵያውያን ሊቃውንትን ትርጓሜ አጠናው ማለቱን ይጠቅሳል። ይህንንም ቅዱስ ላሊበላ በኢየሩሳሌም የነበረውን ቆይታና ልዑል ተፈሪ መኮንን በአውሮጳ በፓሪስ ከተማ ለሦስት ወራት ያደረጉት ጉብኝት የፈጠረባቸውን ተጽእኖ በተወሰነ መልኩ ያስረዳል። ከዚህ ቀደም እንደ ዘርዓያዕቆብ ያለ ሰው ከኢትዮጵያ ሊወጣ አይችልም ብለው የጻፉ ምሁራን አሉ። ፕሮፌሰር ሳምነርና መምህር አለማየሁ ሞገስ ለአብነት ይጠቀሳሉ። ሚዛን የደፋ ሐሳብ እንዳላቀረቡ የሚስማማው ዳኛቸው መኖሪያውን በካናዳ ያደረገው የፍስሐ ታደሠ ክርክር ሳቢ የሆነ አዲስ ሐሳብ ይዞ እንደመጣ ይቀበላል። እንደፍስሐ ሐሳብ የዘርዓ ያዕቆብ ያነሳቸው ንባብ፣ ሐሰሳ፣ ስለመጠየቅ፣ ስለአእምሮ ሲያነሳ የኢትዮጵያውያንን ሊቃውንት አይመጥነንም። ስንት ብዙ ውስብስብ (sophisticated ) ጽሑፎች እያሉ እንዲህ ሊባል አይገባም። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ብዙ ጠይቀዋል ከዚህ በላይ ያውቃሉ ባይ ነው። እድሜ ከሰጠን ወደፊት ፍስሐ ታደሠ ያለበት ተዋስኦ እንደገና እንደሚኖር ዳኛቸው ፍንጭ ይሰጣል። እስከዚያው ግን ዘርዓያዕቆብን እንደኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ነው የምንወስደው።

## ማኅበራዊ ጅማት ወይም ውል /social fabrics or contract/

የአገር አመሰራረትን አስመልክቶ ሁለት ዓይነት እሳቤዎች (schools) አሉ። የመጀመሪያው አገርን እንደ ተክል፣ እንደሚያድግ አበባ፣ ስር፣ ቅርንጫፍ ያለው ቀስ እያለ እየተከማቸ (sedimented) የሚያድግ ሲሆን ማኅበራዊ ጅማት (social fabrics)፣ ጥቅል የጋር ትውስታ (collective memory)፣ ወግ (norm) የመሳሰሉት ገንዝብ ያደረገ ነው። ሁለተኛው ደግሞ አገር እንደጭቃ ተድቦልቡላ እንዲሁ በዘፈቀደ የተፈጠረ ነው ባይ ናቸው። ለዚህ ትልቋ ምሳሌ ዩኤስ አሜሪካ ናት። ብዙዎቹ የአፍሪካ አገሮችም በቅኝ ግዢዎች ነው እንዲህ ባለ ሁኔታ የተመሰረቱት። እንደዳኛቸው ሐሳብ ኢትዮጵያ በጠነከረ ማኅበራዊ ጅማት የተገነባች አገር ነች። ጉዳዩ በአካል ጨብጠህ የምትይዘው ዓይነት ነገር አይደለም ሜታፊዚካልም ይመስላል። ኢትዮጵያዊነት መንፈስ እጅግ ጠንካራ ነገር ይናገራል፤ ለዚህ እንደምሳሌ በቦስተን ዩንቨርሲቲ ሳለ የገጠመውን ያነሳል። በኒው ዮርክ ከተማ ለሦስት ቀናት መብራት ይጠፋል ከዚያ በሀገሪቱ ከፍተኛ የሆነ ዝርፊያና ወንጀል ይከሰታል። በዚያን ወቅት ከሶቪየት ተባሮ በአገረ አሜሪካ ያለ ሶልኒስተን የሚባል የኖቤል ሽልማት አሸናፊ ነበር። በዚያ ወቅት በሀርቫርድ የኒቨርስቲ ንግግር እንዲያደርግ የተጋበዘው ሶሊንስተን እንዲህ ሲል አሜሪካኖቹን ልካቸውን ነገራቸው። ሀገራችሁ ጨቅላ ናት፣ ሦስት ቀን መብራት ቢጠፋ እርስ በርስ አንገት ለአንገት እነዴት ትያያዛላችሁ፤ ሀገሬ ራሺያ ግን ታላቅ ሀገር ናት። ነገ ዛሬ አምባገነኖች ቢይዟትም ስርዐቱ ነገ ይወድቃል። በጠንካራ ማኅበራዊ ጅማት የተገመደች ናት።

አሁን ዛሬ ላይ ሆነን ዶ/ር ዳኛቸው ተነቦ የማያልቅ መጽሐፋችን ነው። ለብዙ ተዋስኦች ጤናማ ገዢ ሐሳቦች አሉት። የኢትዮጵያን ታሪክንም አብጠርጥሮ ያውቀዋል። ፍልስፍና ለእርሱ ክህሎት ነው። ልክ እንደ ፈረንሳያዊው ፈላስፋ ሰ በሀገሪኛ የስነጽሑፍ ውጤቶች አጅቦ ታላላቅ የፍልስፍና ቲዎሪዎቹን ለብዙዎች በሚገባና በሚማርክ መልኩ ያቀርባል። እኛ ከባህሩ በጥቂቱ እንዲህ ተመልክተናል። የበረታ እንዲዋኝበትም ሲሻው ጠጥቶ እንዲሰክር ፈቅደናል። ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም።

ከዶ/ር ዳኛቸው ስራዎች መሀከል ጥቂቶቹ፤ የቄሳር እና አብዮት መጽሐፍ ዳሰሳ፣ አንዲት ኢትዮጵያ ሬድዮ፣ ግልጽ ደብዳቤ ለአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አቶ ኩማ ደመቅሳ፣ ግልጽ ደብዳቤ ለአዲስ አበባ የኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት አዲስ ጉዳይ መጽሔት፣ ሰብል እርሻ በጅብ ማረሻ ፍትሕ ጋዜጣ፣ ዳኛቸው ስለ ብርቱካን አዲስ ነገር ጋዜጣ፣

# “አራማጅነት” በኢትዮጵያ

ኤዶም ካሣዬ የኢትዮጵያ አካባቢ ጋዜጠኞች ማሕበር አባል የሆነች ለአካባቢ ተቆርቋሪ ጋዜጠኛ (Environment Journalist) ነች፡፡ ምንም እንኳን በአጋጣሚ ያለችበት አካባቢ በቆሻሻ የተበከለ ቢሆንም እንኳን የወረቀት ቁርጥራጭ፣ የማስቲካ ልጣጭ፣ ያገለገለ ሶፍት ጨምሮ ምንም ዓይነት አገልግሎት የሰጠ ቁስ መንገድ ላይ አትጥልም፤ አብረዋት ያሉትንም እንዲጥሉ አትፈቅድም፡፡ በየቦታው የቆሻሻ ማስወገጃ ከረጢት (bin) ወይም ገንዳ በቀላሉ ስለማይገኝ በቦርሳዋ እንዲህ ዓይነቶቹን መወገድ ያለባቸው ኮተቶች ማጨቅ የተለመደ ጉዳይዋ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የፋቀችውን የተንቀሳቃሽ ስልክ ካርድ እዚያው የገዛችበት ሱቅ ትታ ነው የምትወጣው፡፡ የላስቲክ ማሸጊያ ካላቸው ቁሳቁሶች ይልቅ የወረቀት ማሸጊያ ያላቸውን መግዛት ትመርጣለች፣ በጋዜጠኝነት ሙያዋ በተገኘው አጋጣሚ ስለ አካባቢ ነክ ጉዳዮች ትጽፋለች፣ አባል በሆነችበት የተፈጥሮን አድን ኢትዮጵያ ማኅበር አማካይነት በየዓመቱ ለችግኝ ተከላ ትሳተፋለች፣ የተተከሉት ችግኞች እንዲጸድቁ ከሚንከባከቡ የአካባቢ ሰዎች ጋር ትገናኛለች፡፡

በአካባቢ ጉዳዮች ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የሕይወት መስኮች እንደ ኤዶም ጥልቅ ስሜት ያላቸው በርካታ ሰዎችን ከፍ ሲልም ማህበረሰቡንም እዚህ ደረጃ ለማድረስ ከሚያስፈልጉ ማህበረሰባዊ ጉዳዮች መሀከል አራማጅነት(Activism) በዋናነት ይጠቀሳል::

አገራችን፣ 80 በመቶ ሕዝቧ በዝናብ ውሃ ላይ ጥገኛ ከመሆኑ አንፃር የአካባቢ ጉዳይ ዋነኛ አጀንዳዋ ነው፤ ሆኖም በቁጥር የሚዘረዘሩ የአካባቢ ጉዳይ ‹አራማጆች› የሉባትም፣ ኢትዮጵያ ፈርጀ ብዙ የባሕል አብዮት እንደሚያስፈልጋት ብዙዎች አስተያየታቸውን ይሰነዝራሉ፣ ነገር ግን በተግባር እንቅስቃሴ አብዮቱን ለማራመድ የተዘጋጁ ሰዎች አይታዩም፡፡ ኢትዮጵያ እና መንግስቷ ከሰብአዊ መብት በደል ጋር በተደጋጋሚ ስማቸው ይነሳል፣ ነገር ግን ለሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ዓይን የሚገቡ አራማጆች የሉንም፡፡

## “አራማጅነት” ምንድን ነው?

Activismን አንዳንዶች አራማጅነት፣ ሌሎች አቀንቃኝነት፣ አንዳንዶችም ተሚጋች እያሉ ይተረጉሙታል፡፡ እኛም በዚህ ጽሑፍ “አራማጅነት” የሚለውን ብንመርጥም ሌሎቹንም እንደየአገባቡ አስፈላጊነት ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ ሌላው አቀንቃኝነት በተለይ advocacyን ይወክላል የሚል ነገር ቢኖርም፣ በሁለቱም (activisim and advocacy) ውስጥ ተመሳሳይ ሚናዎች ስለሚኖሩ በጥቅሉ አራማጅነት ያልነውን ተከትለን እንሄዳለን፡፡

አራማጅነት ቀጥተኛ የማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ወይም አካባቢያዊ ለውጥ ለማምጣት የሚደረግ ጥረት ነው ሲል ዊክፔድያ ይበይነዋል፡፡ የዚህ ለውጥ ‹አራማጆችን› (activistsን) ደግሞ ለአንድ ጉዳይ ድጋፉን ወይም ተቃውሞውን በተግባር የሚያሳይ ሰው ነው ይለዋል፡፡ ‹አራማጅነት› በጉዳዩ ላይ ሕዝባዊ ንቃትን (awareness) ማስጨበጥ፣ ደብዳቤዎችን ለፖለቲከኞች እና ለጋዜጦች ከመጻፍ ጀምሮ እስከ ማስተባበር እና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ እስከማድረግ (የተወሰኑ ሸቀጦችን አለመግዛት፣ ሰልፍ መውጣት፣ የጎዳና ተቃውሞ፣ አድማ እና ሌሎችም) ድረስ የሚዘልቁ የተለያዩ መገለጫ ተግባራቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

## አራማጆች ለምን?

አራማጆች የሚያስፈልጉባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፤ ዋነኛው የትኛውም ጠንካራ መንግስት ማኅበረሰቡ ውስጥ ፈጣን የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ስለማይችል ነው፡፡ በአገራችንም ቢሆን የፀረ ኤችአይቪ፣ የትራፊክ ጽ/ቤት፣ የሴቶች ጉዳይ እና ሌሎችም ቢሮዎች ቢኖሩም ችግሮቹን መቆጣጠር ቀርቶ ለመቆጣጠር የቀረበ ሙከራ የተደረገበት ጊዜ አልታየም፡፡ ይህም የሚሆነው መንግስት የአስፈፃሚዎች አቅም ማነሱ፣ የአደረጃጀቱ ዴሞክራሲያዊነት ማነሱ፣ የትምህርት ፖሊሲው በማሕበራዊ ንቃት ዘርፍ ያነሰ ትኩረት መስጠቱ እና ሌሎችም ምክንያት ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን ክፍተት የሚሸፍኑ አራማጆች እና አራማጅነት በሰፊው ይፈለጋሉ፤ በተለይም ለታዳጊ አገራት፡፡

## ምን ዓይነት አራማጅነት?

‹‹አራማጅነት›› ማለት መንግስትን/ተቃዋሚዎችን መደገፍ ወይም መቃወምም አይደለም፡፡ ይልቁንም ለማኅበረሰቡ ጤናማ የአእምሮ እና የቁስ ዕድገት እሴት የሚጨምሩ ለውጦች እንዲመጡ፣ ለውጡን ማሕበረሰቡ በእውቀት መር አካሔድ እንዲያመጣው መሥራት ነው፡፡

በአገራችን ብዙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሕዝቡ ለውጥ ለማምጣት፣ ዴሞክራሲ ለማስፈን፣ መልካም አስተዳደር ለመዘርጋት እና ወዘተ እየሰራን ነው ይላሉ፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች የራሳቸውን ግብ አስቀምጠው መንቀሳቀሳቸው ምንም ችግር ባይኖርበትም አገራዊ ለውጥ የሚመጣው ግን በፓርቲ መስራቾች እና በአባሎቻቸው ብቻ አይደለም፡፡ እውነተኛ ለውጥ የሚመጣው በፖለቲካ ፓርቲዎች መፈራረቅ ብቻ ሳይሆን (በእርግጥ ይህ ከተቻለ ተግባራዊ ትምህርቱ የሚናቅ አይደለም) ነገር ግን በሕዝባዊ አስተሳሰብ ለውጥ ነው፡፡

## አራማጅነት በሌሎች አገራት

በሌላው ዓለም፣ በተለይም ያደጉ አገራት ውስጥ አራማጆች በማሕበራዊ ለውጥ አማጪነት ሁነኛ ሚና አላቸው፡፡ አሜሪካዊው ማርቲን ሉተር የጥቁሮች መብት በሀገረ አሜሪካ እንዲከበር፣ ዴዝሙን ቱቱ በደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ ላይ፣ ኬንያዊቷ ዋንጋሪ ማታይ የአካባቢ ጥበቃ እና የፖለቲካ መብት ተቆርቋሪ በመሆን ዓለም አቀፍ እውቅናን ለማትረፍ የበቁ እና በጉዳዩ ዙሪያ ሳይጠቀሱ የማይታለፉ ናቸው፡፡

## “አራማጆች” እና “አራማጅነት” በኢትዮጵያ፤ ጥቂት ምሳሌዎች

(፩) አንድ ሰሞን፣ ጋሽ አበራ ሞላ በሚለው ስሙ ይበልጥ የሚታወቀው የክራሩ *ኤክስፐርት* ስለሺ ደምሴ በከተማ ንፅህና እና አረንጓዴነት ዙሪያ ከፍተኛ የአራማጅነት ሚና ተጫውቷል፡፡ በወቅቱ ባደረገው ቅስቀሳ መላውን የአዲስ አበባ ወጣት በማነሳሳት ለአጭር ጊዜም ቢሆን አዲስ አበባን ከቆሻሻ ገንዳነት ወደ አረንጓዴ መዝናኛነት የመለወጥ ተስፋ አሳይቷት ነበር፡፡ የጋሽ አበራ ሞላ ፕሮጀክት አሁንም የቀጠለ ቢሆንም የአራማጅነት ሚናው ግን የሞተ ይመስላል፤ ለዚህም ነው ቀድሞ እናየው የነበረውን ያህል ለውጥ አሁን ማየት ያልተቻለን፡፡

(፪) ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) መወለድ ምክንያት የሆኑት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ፕሮፌሰሩ በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ አራማጅነት ከየትኛውም ኢትዮጵያዊ የተሻለ የሰሩ ሰው ናቸው፡፡ ይህ ሚናቸው ግን በምርጫ 97 የፓርቲ አባል ሁነው ከመጡ በኋላ የቀነሰ ሲሆን፣ ከዚያን ጊዜ ወዲህ በግለሰብ ደረጃ በአገር ውስጥ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ሆኖ የሚታይ ግለሰብ እምብዛም የለም፡፡

(፫) እስከመጨረሻው ዘልቆ የሆነ ውጤት ባያመጣም፣ በ1994 በአቶ ልደቱ አያሌው (ፓርቲ ኢዴፓ አስተባባሪነት) ‹‹ኢትዮጵያን የአሰብ ወደብ ባለቤት ለማድረግ›› በየከተማው ፊርማ የማሰባሰብ እና ሕዝባዊ ስብሰባዎችን እያደራጁ ንቃት ለማስጨበጥ ያደረጉት ሙከራ ፖለቲካዊ ተራማጅነት (political activism) ሊባል ይችላል፡፡

(፬) ታማኝ በየነ በሙያው አርቲስት ቢሆንም ኢሕአዴግ በአገዛዝ አፍላ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአንድ አቋሙ ይታወቃል፡፡ የዴሞክራሲያዊ እና ሰብአዊ መብቶች አራማጅ ተብሎ ሊጠራም ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ እርሱም ስደተኛ በመሆኑ መረጃ የሚሰጣቸው፣ ወይም የሚያቀነቅንላቸው ሰዎች ባመዛኙ በዴሞክራሲያዊ እና ሰብአዊ መብቶች ዙሪያ ለተሻለ ግንዛቤ የተሻለ ተግባራዊ አማራጭ ያላቸው ብቻ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን በአገር ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ባለመሆናቸው በኢትዮጵያ የሚያመጣው ለውጥ የሚጠበቀውን ያህል የጎላ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

(፭) ዘውዱ ጌታቸው በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የፀረ ኤችአይቪ/ኤድስ እንቅስቃሴ ማሕበር (ተስፋ ጎህን) የመሰረተ ሰው ነው፡፡ ምንም እንኳን አሁን በጉዳዩ ላይ ለመስራት እንደአሸን የፈሉ በርካታ ማሕበራት ቢኖሩም፣ ዘውዱ ጌታቸው ማሕበሩን በመሰረተበት ሰዓት ማኅበረሳባችን ስለጉዳዩ የነበረው ግንዛቤ ለማውራት እስከመጠየፍ ይደርስ እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ ዘውዱ ጌታቸው እና ማሕበሩ የሰሩት ሥራ ሁሉንም ሰው ግንዛቤ ከማስጨበጥ ጀምሮ እስከ ተጠቂዎቹን ድጋፍ እና ሚቋቋም ድረስ ዘልቋል፡፡

(፫) ሳጅን አሰፋ መዝገቡ ‹‹በኢትዮጵያ አትንዱ›› የሚል ዓለም አቀፍ ባጅ ያሰጠንን የትራፊክ አደጋ አስከፊነት ግንዛቤ በማስጨበጥ ከመንግስት ተቀጣሪነታቸው ውጪ የሚሰሩት ሥራ እንደአራማጅነት የሚያስቆጥራቸው ነው፡፡

(፬) በግለሰብ ደረጃ ጎልተው የወጡ ግለሰቦች ባይኖሩም፣ በኢትዮጵያ ሴት ጠበቃዎች ማህበርም ሲሰራ የነበረው (ከጥብቅና መቆም በላይ) የማንቃት እንቅስቃሴው፣ ማሕበሩን ከአራማጅነት ተርታ ያሰልፈው ነበር፡፡

ሌሎችም ጥቂት ምሳሌዎች ልንጨምር ብንችልም ለ80 ሚሊዮን ሕዝብ ግን በስንት ጭንቅ ትውስ የሚሉ እና በጣት የሚቆጠሩ የዘርፍ አቀንቃኞች ብቻ አይበቁትም፡፡

## የሌሉን

በአገራችን በጣም አስፈላጊ ሆነው ሳሉ ጭራሹኑ የተዘነጉ የሚመስሉም አሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

- የፀረ ሙስና አራማጆች የሉም፣
- በትምህርት ጥራት ዙሪያ የሚሰሩ አራማጆች የሉም፣
- በፕሬስ፣ በመደራጀት እና በጥቅሉ በሕገመንግስታዊ መብቶች መከበር ዙሪያ የሚሰሩ አራማጆች የሉም፣
- ፀረ-እፅ (anti-drug) በተመለከተ፣
- የፍትሐዊ የንግድ ስርዓት፣
- የከተማ ንፅህናን በተመለከተ፣
- የሴቶች መብትን በተመለከተ፣
- በጎዳና ተዳዳሪነት እና ፀረ-ድህነት ላይ፣
- የኢንተርኔት ነፃነትን በተመለከተ እና
- በሌሎችም ጉዳዮች ዙሪያ በቂ አራማጆች የሉንም፤ ይሁን እንጂ ችግሮቹ ስር የሰደዱ እና በመንግስት አቅም ብቻ የሚፈቱ አይደሉም፡፡

## አራማጆች እና ውጤታቸው

በመግቢያችን ላይ የተጠቀሰችው ጋዜጠኛ የአካባቢ ተቆርቋሪነቷን በግለሰብ ደረጃ እየተገበረችው ቢሆንም በዙሪያዋ ያሉ ሰዎችን መጠነኛ ግንዛቤ ከማስጨበጥ የበለጠ ሕዝብ ጋር በመድረስ ለውጥ የምታመጣበትን ሥራ እየሰራች አይደለም፡፡ ስለዚህ እሷን አራማጅነት ደረጃ ላይ ማስቀመጥ ያስቸግራል፡፡ እየዘረዘርነው በመጣነው ማብራሪያ መሰረት እሷ የአካባቢ ጉዳይ አራማጆች ፍሬ ናት፤ በሆነ ጉዳይ አራማጅ/አቀንቃኝ/ተሟጋች የምንላቸው፣ ከራሳቸው አልፈው የማኅበረሰቡን አባላት ልክ እንደ ተጠቀሰችው ጋዜጠኛ ዓይነት በጉዳዩ ዙሪያ ተቆርቋሪነት እንዲያዳብሩ እና ተገቢውን ግንዛቤ እንዲጨብጡ ለማድረግ የሚሰሩትን ነው፡፡

እንዳለመታደል ሆኖ አገራችን እንኳን በዓለም ዙሪያ የሚጠቀሱ ቀርቶ በአገር ውስጥ እንኳን ከአንድ ጉዳይ ጋር አወዳጅተን የምናስታውሳቸው አራማጆችን አላፈራችም፡፡ ለዚህ ተጠያቂ በርካታ ምክንያቶች ይኖራሉ፤ አንደኛው የሲቪክ ማሕበራቱ አዋጅ ነው፡፡

ይህ አዋጅ በአራማጅነት ላይ ትልቅ ቡጢ ያሳርፋል፡፡ ግለሰቦች ለውጦች እንዲመጡ የአራማጅነት ሚናን እንዲወስዱ የፋይናንሻል አቅም ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን፣ የሲቪክ ማሕበራቱ በአገር ውስጥ ድጋፍ ካልተዳደሩ በቀር ይህንን ድጋፍ የማድረግ መብት የላቸውም - በተለይ በመብት ጉዳይ፡፡ ይህም፣ አገር በቀሎቹን የየሰብአዊ መብት ጉባኤን እና የሴት ጠበቃዎች ማሕበር ላይ ያደረሰው ማሽመድመድ ሳይጠቀስ አይታለፍም፡፡ መሰረታዊ ፍላጎቶቹ ያልተሟሉለትን ሕዝብ ሲቪክ ማሕበራትህን ራስህ አስተዳድር ማለት ለችግሩ ተባባሪ ከመሆን የተሻለ እርምጃ አይደለም፡፡

ሌላኛው እና ሳይጠቀስ የማይገባው ምክንያት፣ የግለሰቦች የደህንነት ስጋት ነው፡፡ ግለሰቦች በሚያራምዷቸው አስተሳሰቦች እና አመለካከቶች እየተመለመሉ የሹመኞች ጥርስ ውስጥ የሚገቡበት ስርዓት ውስጥ መሆናችን የማይካድ ነው፡፡ ይህ ድባብ ግለሰቦች ለውጥ ማምጣት በሚፈልጉበት እና በሚችሉበት መስክ ተሟግተው ከመጠመድ ይልቅ በጥላው ተሸፍነው ማለፍን ይመርጣሉ፡፡

ጠቅላላው ነባራዊ እውነታ ይህ ቢሆንም፣ ዕድሉን ለማግኘት እየታገሉ በተለያዩ ምክንያቶች ግባቸውን ያልመቱ በርካታ አራማጆች መኖራቸውን ግን መካድ አይቻልም፡፡ ይህ ጽሑፍ የዞን ዘጠኝ የ2005 የመጀመሪያው ጽሑፍ

እንደመሆኑ፣ በዚሁ አጋጣሚ ዓመቱ በርካታ ግለሰቦች እና ተቋማት ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ለውጥ ለማምጣት የሚሰሩበት ዓመት እንዲሆን መልካም ምኞታችንን እንገልፃለን።

# ነጻ ሐሳብ የማያውቁት ኤፍኤሞቻችን

**ኤፍሬም ማሞ**

1984 ዓ.ም በአገራችን የመገናኛ ብዙሃን ጨዋታ የተለወጠበት ነው፡፡ የደርግ መውደቀትን ተከትሎ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት በፕሬስ ህጉ እውን ሆነ፡፡ የግል ጋዜጦችም እንደ አሸን ፈሉ፡፡ የፕሬስ ህጉ በታወጀበት የመጀመሪያ አምስት አመታት ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ የህትመት ውጤቶች ዕውን እንደነበሩ ይታወሳል፡፡በአሁኑ ሰዐት ያሉትን መሰል የህትመት ውጤቶች መቁጠር እጅግ ቀላል ስራ መሆን አለበት፡፡

የ1987ቱ ሕገ መንግሥት ሐሳብን በነጻ የመግለጽ መብትን ቢደነግግም የማሰራጫ መገናኛ ብዙሃንን በተመለከተ ግን በፈቃጁ አካል እሽታን ለማግኘት እስከ 1991 ዓ.ም መጠበቅ ነበረብን-የብሮድካስት ህጉ እስከሚወጣ ድረስ፡፡ ይህም ሆኖ የግል ሬዲዮና ቴሌቪዥን ነገር የውሃ ሽታ እንደሆነ ስምንት አመታት አለፉ፡፡ በ 1999 ዓ.ም ከአመታት ጥበቃ በኋላ 15 አመልካቾች ለነበሩበት ዘርፍ ለሁለቱ የግል ባለቤቶች የአየሩ ሞገድ ተፈቀደላቸው-ቁጥራቸው አፍሮ ኤፍ ኤምን ጨምሮ ከሶስት ከፍ ለማለት ግን አልቻለም፡፡ የቴሌቪዥኑ ነገር አሁንም እየታሰበበት ነው፡፡

የአፍሪካን መገናኛ ብዙሃን በጥልቀት በማጥናት ታዋቂ የነበሩት ዛምቢያዊው ፍራንሲስ ካሶማ የሬዲዮ እጅግ አስፈላጊነት ጎልቶ የሚወጣው በቀውስ ወቀት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በርካታ የመፈንቀለ መንግስት ሙከራን ባስተናገደችው አፍሪካ የሬዲዮ ጣቢያዎች የጦር አውድማ እንደሚሆኑና ጣቢያውን ያልተቆጣጠረ ቡድን ጥረቱ ሁለ ከንቱ እንደቀረ ጽፈዋል፡፡

የግል የህትመት ውጤቶች ገና ከመጀመሪያው በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ማጥላላት ስራዬ ብለው ያዙ የሚለው ሐሌሉያ ሉሌ በ1999 የጻፉት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽኑፍ ነው፡፡ ጸሃፊው ከነጻ ፕሬስ አዋጅ መውጣት በኋላ የወጡ በርካታ የህትመት ውጤቶች በከፍተኛ ደረጃ የብቃት ማነስና የጋዜጠኝነት ሙያ ስነምግባር እጥረት የነበረባቸው፤ እንዲሁም የተፈቀደውን ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ካለልክ መጠቀም ያበዙ ነበሩ ይላሉ፡፡ አክለውም እነዚህ አሳታሚዎች ገለልተኛ ሆነው አለመገኘታቸውና አለማቀፋዊ ተቀባይነት ያላቸውን የጋዜጠኝነት መርሆች ለመከተል አለመፈለጋቸውን እንደ ዋና ችግር ይጠቅሳሉ፡፡

መንግስት ሬዲዮና ቴሌቪዥንን ለግል ባለቤቶች ለመፍቀድ ማመንታቱ እነዚህ የመገናኛ ብዙሃን ያላቸውን ጠቀሜታ ጠንቅቆ በመረዳቱ ነው የሚሉ ብዙ ናቸው፡፡ በግሉ የህትመት ዘርፍ ከታየው ልምድ በመነሳት በሬዲዮ/ቴሌቪዥን ፈቃድ ዙሪያ ቆጠብ ማለቱ ተመርጦም ይሆናል፡፡ ማንበብና መጻፍ የሚችለው የሃገራችን ህዝብ ብዛት ከግማሽ በታች ይገመታል፡፡ ይህ እውነታ ሬዲዮ በብዙሃን ተደራሽነቱ ልቆ እንደሚገኝ ያሳየናል፡፡

በመርህ ደረጃ የህዝብ የሆኑት በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ መገናኛ ብዙሃን በገዢው ፓርቲ ላይ ያተኮሩ ትችት አዘል ዝግጅቶችን አቀረቡ የሚባልበት ወቅት አለ ብሎ የሚከራከር ያለ አይመስለኝም፡፡ ቢኖር እንኳን በአንዳንድ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶችና ሃላፊዎቻቸው ድክመት ላይ አተኩሮ አለፍ ሲልም የአፈጻጸም ችግር በሚል ማሰሪያ ተድበስብሰው የሚያልፉ መሆናቸውን አስተውለናል፡፡ በአጠቃላይ ትችትን እንደመርዶ የመቁጠር አዝማሚያ ይስተዋላል፡፡

መንግስት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በሚያሳድረው ተጽዕኖ ምክንያት ይሁን ወይም በስንት ጥበቃ የተገኘውን የሬዲዮ ባለቤትነት መብት ላለማጣት በሚደረግ ጥረት በመንግስት/ገዥው ፓርቲ አንጻር የሚሰሙ ትችት አዘል ድምጾች በግል ሬዲዮ ጣቢያዎች መስማት የመስቀል ወፍ ዝማሬን ያህል የሚናፍቅ ነው፡፡ የኤፍ ኤም ሬዲዮ ዝግጅቶች በመዝናኛና ስፖርታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ተጨናንቀው የምናስተውለው ሊነኩ የማይፈለጉ እውነታዎች በመኖራቸው ይመስላል፡፡ የመንግስት ጠንካራ እጆች በጀርመኑ ዶቼ ቬለ እና የአሜሪካ ደምጽ የአማርኛ አገልግሎት ላይ የወሰዱት የሽበባ እርምጃ እንደ ማንቂያ ደወል ሳይወሰድ ይቀራል?

ኤፍ ኤም ጣቢያዎቻችን ጎመን በጤና፣ፖለቲካን በሩቁ ብለዋል፡፡ በመዳሰስ ላይ ያሉ ወቅታዊ ማህበራዊ ጉዳዮችም በስጋት የታጀቡና የሆነ አካልን ላለማስቀየም ትጋት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ታዲያ የግል የህትመት ውጤቶች ይዘውት የሚወጡትን ያህል የገዥውን ፓርቲ አሰራር የሚተቹ ድምጾች ሬዲዮኖቹ ይዘው ባይወጡ እንኳን መንግስትንም ሆነ ተቃዋሚውን የሚመለከቱ ዝግጅቶችን በነጻነት ማንሸራሸር ነበር ከነሱ የሚጠበቀው፡፡

ይህን ልበል አንጅ ትችት በሬዲዮ ሞገድ ላይ ጭራሽ እየተስተዋለ አይደለም ማለት ግን አይደለም፡፡ ትችቱ ያነጣጠረው መንግስት ላይ አለመሆኑን ግን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ በዛሚ ፐብሊክ ኮኔክሽን ባለቤትነት የተመዘገበው ዛሚ 90.7 በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ይገዳደራሉ ባላቸው ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች ላይ አተኩሮ የሚያቀርበው ዝግጅት አለው፡፡ አፍቃሪ-መንግስት ነው ተብሎ የሚታማው ይኸው ጣቢያ የሚያስተላለፈው *የጋዜጠኞች ክብ ጠረቤዛ*እሁድ ረፋዱ ላይ በዋናነት በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት በጎ ጎን በማጉላት ስራ ላይ የተጠመደ ነው የሚመስለው፡፡ የዚህ አይነቱ ዝግጅት በዓየር ላይ መዋል መንግስትን ግድ የሚለው አይመስለኝም የግል ህትመት ውጤቶቹ እንደሚያትሙት አይነት ይዘት የለውምና፡፡

*የጋዜጠኞች ክብ ጠረቤዛ*አዘጋጆች መድረኩ ለሁሉም ክፍት እንደሆነ ቢገልጹም በአንድ ወቅት አሁን በስደት ላይ የሚገኘውን የቀድሞው አውራምባ ታይምስ ጋዜጠኛ ዳዊት በአለም አቀፍ መድረክ መሸለምን በኮነነ ዝግጅት ላይ ሽላሚዎቹን ብሎም ጋዜጠኛውን ከፍ ዝቅ አድገው ያቀረቡበትን ማስታወስ በቂ ነው፡፡ *የጋዜጠኞች ክብ ጠረጴዛው*አዘጋጆች ጋዜጠኛው ወይም ሌሎች የተለየ አቋም ያላቸው መድረኩን ተጠቅመው ተፎካካሪ አስተያየት ማቅረብ እንደሚችሉ መጋበዛቸው "እንዳያማህ ጥራው…" የሚለወን አገርኛ አባባል የሚያስታውስ ነው፡፡ እንዲህ ያለው አሰራር ከጋዜጠኝነት ስነ-ምግባር የወጣ ድርጊት በሬዲዮ ላይ ለመታየቱ ማሳያ ነውና አዘጋጆቹ ራሳቸውን እንዲመለከቱ የሚጋብዝ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

በዝግጅቱ የቀረቡ መሰል ውይይቶችን እንደማስረጃ ማቅረብ ቢቻልም ከቅርብ ጊዜዎቹ አንዱ ጋዜጠኛ አበበ ገላው በቡድን ስምንት ስብሰባ ላይ ጠ/ሚንስትር መለስን የተጋፈጠበትን ሁኔታ የተኮነነበት ዝግጅት ሌላው ነው፡፡ መድረኩ አንዳንዴ ሃሳብ በነጻ የሚንሸራሸርበት ይምሰል እንጅ፤ በዋናነት የአንድ ወገን ደምጽ የሚሰማበት መስሎ ይሰማኛል፡፡ ያ ወገን ደግሞ የማንንም እርዳታ የማይሻና በህትመትና ማሰራጫ ዘዴዎች ተደራሽነቱ የሰፋ በመሆኑ እንደ *የጋዜጠኞች ክብ ጠረጴዛ*ያሉ ዝግጅቶች ቢቻል ድምጻቸው እንብዛም ለማይሰማው ወገኖች መሆን ይገባው ነበር፡፡

መንግሥት ተቃወሙኝ በሚላቸው የሕትመት ውጤቶች ላይ ጊዜ ጠብቆ እጁን ጠበቅ እንደሚያደርግ ከገበያ የወጡ በርካታ ጋዜጦች ማስረጃዎች ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ በሬዲዮ ተዋናዮች ላይ የሚፈጥረው የስነ ልቦና ተጽዕኖ ቀላል አይሆንም፡፡ ቢልልንና በርካታ ሃሳብ በነጻ የሚንሸራሸርባቸው የሬዲዮ ጣቢያወች ቢኖሩን መልካም ነበር፡፡ እስከዚያው ድረስ ግን ገዥው ፓርቲ ትዕግስቱን ቢሰጠውና አሁን በስራ ላይ ያሉት የግል ኤፍ ኤም ጣቢያዎች ይኸው መብት ያለገደብ የሚንጸባረቅባቸው እንዲሆኑ ቢፈቅድ የነቃ ትውልድን በመፍጠር ለሃገር እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይቆጠራል፡፡

# የበይነመረብ ደህንነት (Internet Security) እንድምታዎች!

“ኢትዮጵያውያን በይነመረብ ላይ መታየት ጀምረዋል” የሚባሉበት ደረጃ ላይ ናቸው እንጂ “በይነመረብ እየተጠቀሙ ነው” ለማለት የሚያስደፍር ነገር የለም። የሲአይዬ የአገራት ጥሬ ሐቅ ብሎ ያስቀመጠው ቁጥር እንደሚያመለክተው፣ በኢትዮጵያ ከበይነበመረብጋ የተገናኙ ኮምፒዩተሮች ቁጥር447,300 (እ.ኤ.አ. 2009) እንደሆነ ነው። ይህም አገሪቱን ከ231 አገራትና ግዛቶች አንጻር በ202ኛ ደረጃ ላይ ያስቀምጣታል። ፌስቡክ ደግሞ የኢትዮጵያ ተጠቃሚዎቹ ቁጥር 618400 ደርሷል፣ ባለፈው ስድስት ወር ብቻ ከ120ሺህ በላይ ተጠቃሚዎችን አግኝቻለሁ የሚል ሪፖርት አለው።

ቁጥሩ ከሕዝብ ብዛቱ አንፃር በጣም ትንሽ መሆኑ ግን ተፅዕኖ ፈጣሪነቱን አያስክደውም። በኢትዮጵያ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተፅዕኗቸው ከፍተኛ የሆኑ ግለሰቦች ኢትዮጵያውያን በየነበመረብ ተጠቃሚያን ናቸው፣ አብዛኛዎቹም የፌስቡክ እና ትዊተር ማሕበራዊ አውታሮች ተጠቃሚ ናቸው። በርግጥ በኢትዮጵያ የሚገኙት ቴሌቪዥኖችም ቁጥር ከዚሁ የበለጠ እንዳልሆነ ቆየት ያሉ መረጃዎች ያሳያሉ። ስለዚህ የበይነመረብ ተጠቃሚዎች ተፅዕኖ ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተጠቃሚዎች አይተናነስም ብለን በመደምደም እንጀምር።

## ለመሆኑ ኢንተርኔት የማነው?

*“የበይነመረብን መሰረተ ልማት ሸርፍራፊ በባለቤትነት የያዙ በርካታ ድርጅቶች፣ ኮርፖሬሽኖች፣ መንግስታት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ግለሰቦች እና አገልግሎት ሰጪዎች አሉ፤ ነገርግን ማንም በሙሉ ባለቤትነት አልያዘውም።”* ይላል webopodia የተሰኘ ኢንሳይክሎፒዲያ። አንድ ግለሰብ በሙሉ ባለቤትነት አልያዘውም ማለት ግን በበይነመረብ እና ተጠቃሚዎቹ መረጃ ላይ ስልጣን ያላቸው ቡድኖች የሉም ማለት አይደለም።አይፒ አድራሻ የመስጠት ስልጣን ያላቸው (እንደነ ኢትዮቴሌኮም)፣ የድረአምባ ስያሜ ሰጪዎች (ቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ እልፍ ዓለምአቀፍ ድርጅቶች)፣ እና እነ የበይነመረብ አርክቴክቸር ቦርድ ቢፈልጉ ተባብረው መግደል፣ አልያም ደግሞ በነጠላ ማቁሰል ይችላሉ።

ግን አስፈሪው ጉዳይ ይህ አይደለም። የድረአምባ (website) ባለቤቶች መረጃዎቻችንን አሳልፈው ለሌላ ወገን ቢሰጡብንስ የሚል ስጋት ይኖር ይሆን? ለምሳሌ የጉግል ኩባንያ በየ6 ወሩ ይህንን መረጃ አጥፉልን እናየግለሰቦችን መረጃ ስጠን የሚሉ ጥያቄዎችን ከየትኞቹ መንግስታት እንደተቀበለ ሪፖርት የማውጣት ባሕል እንዲፈጥር ያደረገው ይሄው ጫና ነው። እርግጥ ነው በጉግል መረጃ ላይ ኢትዮጵያ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ በማቅረብ አልተጠቀሰችም። ይህ ግን ከመንግስቱ ፍላጎት ጋር የሚገጥም አይመስልም።

የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን መረጃ አስወግድልኝ ብሎ አለመጠየቁን በጥርጣሬ ለመመልከት የሚያስችሉ በርካታ ምክንያቶች አሉ። ዋነኛው በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይነበቡ ካልታገዱት የጦማሮች ቁጥር የታገዱት የመብለጣቸው ጉዳይ ነው። ሌላው ቀርቶ የታገዱትን ድረአምባዎች እና ጦማሮች በኢትዮጵያ ለማንበብ የሚረዱ ፕሮክሲዎችን በጉግል አማካይነት ከበይነመረብ ላይ ለማውረድ ፈልግ የሚለውን ስትጫኑ “Sorry! The page cannot be displayed.” የሚል ለማግኘት ትገደዳላችሁ።

በበይነመረብ ላይ እነዚህ ዓይነቶቹ እገዳዎች መኖራቸው አገራችንን እንደነፃ ፕሬሱ ሁሉ “ነፃ ያልሆነች” አስኝተዋታል። ፍሪደም ሐውስ “ነፃ ያልሆነች” ሲላት፣ ኦፕንኔት ኢኒሼቲቭም በበኩሉ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ጽሑፎችን “በአሳሳቢ ደረጃ የሚያጠሉ (Substantial filtering)” አገራት ምድብ ውስጥ አስቀምጧታል።

ስለዚህ ብቸኛው የበይነመረብ አገልግሎት አቅራቢ ኢትዮቴሌኮም (በመንግስት ይዞታ ስር) ያለ እንደመሆኑ፣ በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በይነመረብ የመንግስት ነው ብሎ ማለት ድፍን ስህተት አይሆንም። አንድባንድ ከማገድ እስከ ሙሉ ለሙሉ የመዝጋት አቅም እና ስልጣን አላቸውና!

## ማኅበራዊ አውታሮች፤ ነጻ አውጪ መሳሪያ ወይስ መታሰሪያ?

በተለይም ከአረቡ ዓለም የፀደይ አብዮት ወዲህ ፌስቡክና ትዊተርን ጨምሮ ሌሎችም ማሕበራዊ አውታሮች እንደ ነፃ አውጪ መድረኮች መታየት ጀምረዋል። ጥቂት የማይባሉ ኢትዮጵያውያንም ቢሆን ፌስቡክን በአዲስ አብዮት

ተስፋ ይመለከቱታል። የዚሁ ውጤት ነው በመቶዎች የሚቆጠሩ አብዮት ናፋቂ የፌስቡክ ቡድኖች እንዲፈጠሩ ምክንያት የሆነው።

ይሁን እንጂ፣ ማሕበራዊ አውታሮችን ተጠቅመው ተመሳሳይ ግብ ያላቸውን ሰዎች ከመቀስቀስ እስከ መረጃ መለዋወጥ ድረስ እየተጠቀሙበት ነው። "ለመንበሩ ቀናኢ ነው፣ ከአርባ ዓመት ወዲህ አውራነቱን አሳልፎ አይሰጥም" እየተባለ የሚታማው የገዢው ፓርቲም ነገሩን በንቀት አልተመለከተውም። እንዲያውም የፌስቡክ የቡድን ገጾችን አንድ በአንድ እየተከታተለ ማገዱን ተያይዞታል። በዚህ መሃል ታዲያ ገና ለገና ‹ኢትዮጵያ› የሚል ቅጽል ብቻ ስላለው ‹ደጉ ኢትዮጵያ› በሚል ስም ለበጎ አድራጎት የተፈጠረ የፌስቡክ ቡድን ገፅ ሳይቀር ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይነበብ ተደርጓል። ይህ እያግበሰበሱ የማገድ እርምጃ ሌላ ጥያቄ ወልዷል። ገዢው ፓርቲ እየተቃወሙኝ ነው ወይም ተቃውሞ እያስተባበሩኝ ነው ያላቸውን ግለሰቦች በዚህ አማካይነት ቢከታተላቸውስ?

የማሕበራዊ አውታር ተጠቃሚዎች አውታሩን የሚቀላቀሉበት የመጀመሪያው ዓላማ ከጓደኞቻቸው ጋር ለመገናኘት በመሆኑ በርካታ የግል መረጃዎቻቸውን በግልጽ ማስቀመጣቸው የተለመደ ነው፣ ነገር ግን በፖለቲካ ቅኝቱ እየተማረኩ በሚገቡበት እና ከማያቁት ሰው ጋር በሚመሰርቱት ምናባዊ ወዳጅነት (virtual friendship) በቀላሉ ግላዊ መረጃዎቻቸውን ሊያጡ ወይም አሳልፈው ሊሰጡ ይችላሉ። በአሁኑ ግዜ የውሸት ስሞች ያሏቸው (anonymous) ሰዎች አሉ። እንደነዚህ ዓይነት የነፃ አውጪ ታጋዮች ቢኖሩም፣ በተቃራኒው ሰላዮችም ይኖራሉ።

## የቴሌኮም አዋጁስ ምን ይነግረናል?

የቴሌኮም ማጭበርበር አዋጅ በቅርቡ ፀድቋል፤ አዋጁ ‹ስካይፕ መጠቀም ይከለክላል፣ አይከለክልም› በሚሉ አጀንዳዎች ተሸፍኖ ለሌሎች አሳሳቢ ጉዳዮች ቁብ መስጠት አለመስጠቱ ሳይታወስ ታልፏል። በመረጃ እና ተግባቦት ቴክኖሎጂ (Information and Communication Technology) የበለፀጉ አገራት የቴሌኮም ማጭበርበር አዋጆቻቸው ላይ፣ የግለሰቦችን ደህንነት (privacy)፣ የንብረት ባለቤትነት (intellectual property)፣ የኮምፒዩተር ሰርጎገብነት (hacking)፣ የወሲብ ቪዲዮዎች (pornography) እና የሕፃናት ስነልቦናዊ ጥቃትን የመሳሰሉ ጉዳዮችን ለመቆጣጠር ሲወጡ፣ በእኛ አገሩ የቴሌኮም ማጭበርበር አዋጅ ግን ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ሕዝብን እና እሴትን ከአደጋ ስለሚከላከሉ ጉዳዮች አንዳችም ያነሳው ነገር የለም። ይልቁንም ‹በአገር ደህንነት› ስም የገዢውን ፓርቲ ላይ ተቃውሞ የሚያሰሙ ድምጾችን በማፈን በተዘዋዋሪ የበይነመረብ ላይ ሐሳብን በነፃ የመግለፅ መብት የሚነፍጉ አንቀጾች ተሰግስገውበታል። ይህም ማሕበራዊ አውታሮች፣ በተለይም በአገራችን ከነፃ መድረክነታቸው ይልቅ አጋላጭነታቸው እያየለ እንደመጣ ሌላ ምስክር ነው።

## የተመስገን ደሳለኝ ገጠመኝ (እና ፍቺው)

ፍትህ ጋዜጣ ላለፉት ወራቶች በስርጭት ብዛት ከፍተኛውን ድርሻ የያዘ ጋዜጣ ነበር። ጋዜጣው ሙሉ ለሙሉ በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ሲሆን፣ የገዢውን ፓርቲ በመንቀፍም ይታወቃል። ሆኖም ጋዜጠኞቹ በተደጋጋሚ እንደገለፁት እና አዲስ ዘመን ጋዜጣ ‹አጀንዳ› አምድ ላይ ብዙ ጊዜ እንደተነበበው ከፍተኛ ጫና እየደረሰባቸው ነው። አሁን ደግሞ ከናካቴው ጋዜጣው እንዳይታተም በፍትህ ሚንስትር ታግዷል።

ጋዜጣው ከመታገዱ ጥቂት ሳምንታት ቀደም ብሎ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ተመስገን ደሳለኝ ሁለት ደብዳቤዎችን በኢሜይል አድራሻው እንደተቀበለ ጽፏል። የመጀመሪያው ደብዳቤ የተጻፈው ራሱን የአልሻባብ መልዕክተኛ ብሎ ከሚጠራ ሰው ሲሆን፣ እንደተመስገን አገላለጽ አልሻባብ እና ፍትህ ጋዜጣ የኢትዮጵያ መንግስትን እያጥላሉ ለመስራት ስምምነት ያላቸው አስመስሏል። በሁለተኛው ደብዳቤ ደግሞ ሌላ የአልሻባብ ተወካይ ነኝ ባይ ተመስገን የመጀመሪያውን ደብዳቤ የተቃወመው የወሰደውን ገንዘብ ላለመመለስ ፈልጎ እንደሆነ ለማስመሰል ሞክሯል። ተመስገን፣ እነዚህ ደብዳቤዎች የተጻፉት ከመንግስት ካድሬዎች እንደሆነ እና ክስ ለመመስረቻ ሰበብ እያሴሩ እንደሆነ ያለውን እምነት አትቶ ገልጧል።

በርግጥ ይህ ዓይነቱን ደብዳቤ አስመስሎ በመጻፍ እና በማሴር የመንግስት አቃቤሕግ ክስ ሊመሰርትበት ይችላል። ነገር ግን ቴክኖሎጂው ለበጎም ለክፉም መዋል የሚችል ነውና (ወይም በሌላ አነጋገር ለማንም አይወግንምና) ኢሜይሉ፣ ከየት እንደተላከ በዝርዝር ማወቅና ክሱ የተሳሳተ እንደሆነ ሊታወቅባቸው የሚችላቸው በርካታ መንገዶች አሉ። የኢሜይል አገልግሎት ሰጪዎች የተላኩልንን ደብዳቤዎች ምንጭና ዝርዝር መረጃ የሚሰጡ መሆኑ በቂ ምሳሌ ነው። እንደምሳሌም የዋና፣ ዋና ኢሜይል አገልግሎት ሰጪዎችንየኢሜይል ላኪ መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል እዚህ መመልከት ይቻላል።

## እኛና ኬንያ

ከሀገራችን የሕዝብ ብዛት ከግማሽ በታች የምታንሰው ጎረቤታችን ኬንያ ከ11 ሺህ በላይ ጦማሪዎች እንዳሏት ይገመታል:: በኢትዮጵያ ያሉት ጦማሪዎች እና ጦማር ቁጥር በጣት የሚቆጠሩ ቢሆንም እነርሱም በአዝጋሚው የበይነመረብ አገልግሎት የተሰላቹና በአፈናው የተሳቀቁ ናቸው። የበይነመረብ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎችንም ብንመለከት በአገራችን አንድ ለናቱ የሆነው ኢትዮቴሌኮምን ብቻ ስናገኝ፣ በትንሽዋ ኬንያ ግን ከአራት ያላነሱ አንፃራዊ በሆነ መልኩ የተሻለ አገልግሎትን ረከስ ባለ ዋጋ የሚያቀርቡ፣ የበይነመረብ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎችን ይገኙባታል:: ኬንያ በICTእና ተያያዥ ግልጋሎቶች በርካታ የሚያስቀኑ ውብ የሆኑ ዕድገቶችን ከዕለት ዕለት በማስመስገብ ላይ ያለች አገር ነች:: አገራችን ውስጥ የሚገኙ የሶፍትዌር ኩባንያዎቻችን ከጎረቤታችን ኬንያ የሶፍትዌር ኩባንያዎች ጋር ስናወዳድር የኛዎቹ እዚህ ግቡ የሚባሉ አይደሉም። በይነመረብ የገቢምንጭ መሆን እስካሁን አልቻለም፣ የዜና አውታሮችም በይነመረብን በሙሉ ልባቸው አልተቀላቀሉትም።

ኬንያውያን እ.ኤ.አ. በ2008 ያካሄዱትን ምርጫ ተከተሎ የተቀሰቀሰውን ብጥብጥ እና አለመረጋጋት በጥራት ለመዘገብ በሚል ያቋቋሙትን በስዋሂሊ ቋንቋ ‹‹ኡሻሂዲ›› ብለው የሰየሙትን ኩባንያ እንመለከት:: ይህ ኩባንያ በበጎ ፍቃደኞች አገልግሎት ላይ የተመሰረተ ሲሆን በሀገሪቱ የተንሰራፋውን ሙስና እና የመልካም አስተዳደር እጦት በሚገባ በማጋለጥ እየቀነሰው ይገኛል:: የፈጠራ ሥራን ማበረታት እና ማስፋፋት ለምሳሌ የማፕ ኬብራ ፕሮጀክት ወጣቶች በጋራ በመሆን በኬንያ ካርታ ላይ ከ1 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የሚኖርበትን የድሆች መንደር እንዲተዋወቅ እና ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝ አድርገዋል:: ኬንያውያን በእንደዚህ ዓይነት ሥራዎቻቸው ለዴሞክራሲ፣ ለመልካም አስተዳደር እና ልማታዊ መቀላጠፍ አገራቸውን አብቅተዋታል። ይህ የሆነው በቂ የበይነመረብ እና ቴክኖሎጂ ነፃነት በመኖሩ ነው።

በተቃራኒው ቻይናውያን በዓለምአቀፉ ማሕበረሰብ በኢንተርኔት ጠላትነት ይታወቃሉ። የኢትዮጵያ መንግስትም ይህንኑ ሞዴል በመውሰድ የቻይና ቴክኖሎጂዎችን እየተጠቀመ ጦማሮችን እና ድረአምባዎችን በማገድ የበይነመረብ ማጥለል ሥራውን በሰፊው እና በገሃድ ተያይዞታል።

## አጭር መደመደሚያ

ግብጻዊው ዊኤል ጎሆኒም በ2010 የግብፃዊያን አመጽ ወቅት ለሲኤንኤን እንዲህ ሲል ተናግሯል *"If you want to liberate a society just give them the Internet" (አንድ ማኅበረሰብ ነፃ እንዲወጣ ከፈለጋችሁ በይነመረብ ስጡት)* እኛም ይህንኑ እንደግማለን፤ ሕዝቦች ነፃ ካልወጡ ዴሞክራሲም፣ መልካም አስተዳደርም፣ ዕድገትም የለምና!

# የያዘን አባዜ

ያለፈ ታሪክን መመርመርና ማወቅ አሁን ለምንኖርበት ነባራዊ ሁኔታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው የማይካድ ሐቅ ነው፡፡ ታሪኩ ምንም ሆነ ምን እንዳለና እንደነበረ ለትውልድ መተላለፍ አለበት የሚል እምነት አለኝ፡፡ ባለፈች አንዲት ሰከንድ ውስጥ የተፈጠረች ክስተት እንኳን ከታሪክነት ትመደባለች፡፡ ከግለሰብ ጀምሮ አገራትም ጭምር የራሳቸው የሆነ ታሪክ ይኖራቸዋል፡፡ በተለምዶ ግን ታሪክ ስንል ቶሎ ብሎ ወደ አእምሮአችን የሚመጣው የአገር ታሪክ እንደመሆኑ መጠን እኔም የማወራው ስለ አገር ታሪክ እንደሆነ ይታወቅልኝ፡፡

## ግራ ገብቶናል!

በርግጥ ሁሉም ዓይነት ታሪኮች ተያያዥነት አላቸው፡፡ ስለግለሰቦች ሳናወራ ስለአገር እናውራ ማለት አንችልም፡፡ በብዛት የአገር ታሪክን የያዙ ፅሁፎች አገሪቷን ሲያስተዳድሩ በነበሩ መሪዎች የቆይታ ዘመን ተከፋፍለው በጊዜው የነበሩ መሪዎች እና የቤተሰብ ታሪክን ጨምሮ የአገሪቷን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚካዊ ሁኔታ በዝርዝር ያካትታሉ፡፡ እስካሁን እንደተመለከትኩት ከሆነ ከሚፅፈው ሰው አኳያ ታሪክን በደጋፊ፣ በተቃዋሚ/ጠላት እና በምሁራን የሚፃፍ ብለን በሦስት ከፍለን ልናየው እንችላለን፡፡ በአሁኑ ሰዓት በደጋፊና በተቃዋሚ ተፅፈው የምናገኛቸው ታሪክ የሚተርኩ መጽሐፍቶች ቁጥራቸው ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ መሄዱ አሳስቦኛል፡፡ በዛው ልክ ግራ የተጋባንበትና የትኛውን ተቀብለን ‹ታሪካችን› አድርገን እንደምንወስድ ያላወቅንበት ሁኔታ ያለና ወደፊትም በዚሁ መቀጠሉ አይቀሬ ይመስለኛል፡፡

በጣም አስፈላጊውና ልናውቀው የሚገባን ታሪክ ምርምር ተደርጎ በዘርፉ ምሁራን የተጻፉትን መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን የዚህ ዓይነት መጽሐፍቶችን በሚፈለገው መጠን ማግኘት ተአምር ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ኃላፊነትን ወስዶና ታሪክን ለትውልድ ለማስተላለፍ የሚሰራ አካልም ያለን አይመስለኝም፡፡ ስለዚህም አሉን የምንላቸው የታሪክ ድርሳናት ዘመኑን ወይም መሪውን በመውደድ ወይም በመጥላት ተመርኩዘው እና በሁለት ጎራ ተከፍለው ፅንፍ በመያዝ የተፃፉ ናቸው ብንል ስህተት የማይሆን ነው፡፡

የንጉስ አገዛዝ በነበረት ጊዜ ብንመለከት ጸሐፍያኖቹ ራሳቸው የንጉሡ ጸሐፊ ወይም ወዳጅ ይሆኑና ስለንጉሱና አገዛዛቸው መልካምነት ከመናገር እና ከመጻፍ ውጪ ሌላ አማራጭ አይኖራቸውም፡፡ በደርግ ዘመን ሳንሱርን በመጠቀም አገዛዙን አስመልክቶ ተችቶ ወይም ተቃውሞ መፃፍ በሕግ የተከለከለ ነበር፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን ደግሞ እንደተፈለገ መጻፍ እንደሚቻል በመርህ ደረጃ ይነገርና ተግባር ላይ ግን ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ በሁሉም ጊዜያቶች የተጻፉ ታሪኮች ግን ተመሳሳይ የሚያደርጋቸው ነገር አለ፡፡ ሁሉም ማለት ይቻላል ካለፈው ወቅት ጋር ሲነፃፀር የራሳቸውን አገዛዝ የተለየና አዳዲስ ለውጦች የታየበት እንደሆነ ያለፈው ግን ትክክል እንዳልነበረ መናገር እና መፃፍ የዘወትር ተግባራቸው ነው፡፡ ይህ ተግባር ታሪክን ከማጥፋት ባሻገር አንድ ታሪክ ያለውን ሕዝብ በጎራ ከፋፍሎ ከአንድ በላይ ታሪክ በማስተማር ትክክለኛውን ታሪክ መረዳት እንዳይችል ያደርጋል፡፡

## ‹ነግ በኔ›

ያለፉት አልፈዋል ከመውቀስ በስቀተር ምንም ማድረግ አንችልም፡፡ አሁን ያለው የኢሕአዴግ መንግስት ግን አትኩሮት ሰጥቶ በተቻለ መጠን በገለልተኛ ወገን የአገራችን ታሪክ የሚፃፍበት ሁኔታ ቢጀመር መልካም እንደሆነ ተገንዝቦ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ግራ በመጋባት ያለውን ትውልድ መታደግ አለበት፡፡ እስካሁን እየሰራቸው ያሉ ነገሮች ግን ከዚህ በተቃራኒ ናቸው፡፡ የቀድሞ ታሪካችንን በራሱ እይታ በመመልከትና የራሱ ድምዳሜዎችን የኛም እንዲሆኑ ነው የሚደረገው፡፡ መቼም የቀድሞ መሪዎቻችን በጊዜያቸው ሙሉ መጥፎ ነገር ሲያደርጉ ነበር ማለት የሚያስኬድ ነገር አይደለም፡፡ እንዲያውም ያኔ ፈተናው በበዛበት ወቅት በብዙ ነገር ተፈትነው ለኢትዮጵያ አገራችን ከማንም በላይ መስዋእትነት የከፈሉ፣ ታግለውና ተከራክረው አገራችንን ያቆዩልን መሪዎች ነበሩን፡፡ ነገር ግን ይህን መልካም ሥራቸውን ማውራት አሁን ያለውን መንግስት እንደመቃወም የሚቆጠርበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡ እነዚህ ታሪኮች እና ተዋናዮቻቸው የሚዘከሩበትና የሚከበሩበት የድል በዓላት አከባበር ድምቀት ከጊዜ ወደጊዜ ቀንሷል፡፡ በዚሁ ከቀጠለ እንዲያውም ሳይረሳም አይቀርም፡፡

ይህ ታሪክን የመቅበር ወይም የመበረዝ ሥራ በዚህ ወቅት አገር ከሚመራ መንግስት የሚጠበቅ አይደለም፡፡ ‹የኋላው ከሌለ የለም የፊቱ› የሚለው የቴዲ አፍሮ ዘፈን በትክክል ይገልፀዋል፡፡ የኋላችንን የምንጥል ከሆነ እኛም ያልኖርን ጊዜ ታሪካችን እንደማይኖር መታወቅ አለበት፡፡ ትላንት ጠላት ወይም አሸባሪ ሲባል የነበረው አሁን

መሪውን እንደጨበጠው ሁሉ ዛሬ አሸባሪ ወይም ጠላት የሚባለው ነገ መሪውን እንደሚይዝ ሳይዘነጋ የህዝብ የሆነን ታሪክ ለትውልድ እንዲተላለፍ የማድረግ ሥራ ቢሠራ መልካም ነው፡፡

## ሙዚየም ወይስ የኢሕአዴግ የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ?

ከመጽሐፍት በተጨማሪም በወቅቱ የነበሩ ሰዎች ምስክርነት፣ ስዕላዊ መግለጫዎች፣ ቪዲዮና ኦዲዮዎች፣ ፎቶግራፎች እና ሌሎች መሰል ነገሮችም ታሪክን እንድናቅ የሚረዱ ነገሮች ሲሆኑ ሙዚየም መጽሐፍትን ጨምሮ ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች ሁሉንም በአንድነት ልናገኝ የምንችልበት ታሪካዊ ቦታ ነው፡፡ ይህን በማሰብ የዞን ዘጠኝ ኢ-መደበኛ የጦማሪዎች ቡድን በደርግ ዘመን በ‹‹ቀይ ሽብር›› ሕይወታቸውን ሳጡ ዜጎች የተሰራውን መታሰቢያ ሙዚየም ጉብኝት አድርገናል፡፡

ፎቶግራፎች፣ የተለያዩ ደብዳቤዎች፣ መጽሔቶችና የሕትመት ውጤቶች፣ አልባሳቶች፣ ይጠቀሙባቸው የነበሩ መሳሪያዎች እና ሌሎችም በሙዚየሙ የተካተቱ ሲሆን በያንዳንዱ ግርጌ መግለጫ ተፅፎባቸዋል፡፡ መግለጫዎቹን ስናነብ የታዘብነውና ያስገረመን ነገር በአብዛኛዎቹ መግለጫዎች የኢሕአዴግ መንግስት በደርግ ላይ ያለውን አመለካከት እና ትንታኔዎች የሚያሳዩ ጽሑፎች መሆናቸው ነበር፡፡ በኢቲቪ ከሚቀርቡት የደርግን መንግስት የሚያወግዙ ዶክመንተሪዎች ላይ ከምንሰማቸው ንባቦች ጋር ወይም በተመሳሳይ ርዕስ በኢሕአዴግ ከሚዘጋጁ የፎቶግራፍ አውደርዕይ ጋር ልዩነት የለውም፡፡ ኢቲቪን በአንድ ህንፃ ማየቱ ታዲያ ምኑን ሙዚየም ሆነው? ውሳኔውን ለተመልካች ወይም ለአንባቢ ትቶ በወቅቱ የነበረውን ነገር ብቻ መግለፅ ከባድ ነገር ሆኖ ነውን? እንግዲህ ነገ የሚመጣው ደግሞ ይህን ሙዚየም እንዴት እንደሚቀይረው እና ምን ዓይነት መግለጫዎች እንደሚጽፍበት ማሰብ ነው፡፡

ታሪካችን ግን በእንዲህ ያለ ሁኔታ ገዢዎቻችን በተለያዩ ቁጥር መቀያየር እና የነሱን ሐሳብ የሚያንፀባርቅ ሳይሆን ትክክለኛው ታሪክ ተጠንቶ ተመሳሳይ የሆነና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ እና ውኸንብር የማያስነሳ መሆን ይኖርበታል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ለማንኛውም በኛ በኩል አንድ እና ትክክለኛ ታሪክ እንዲኖረን ማድረግ የምንችለውን እናድርግ፡፡

# የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሞያዎች ማኅበር ዛሬ

የ1997ቱን አገራዊ ምርጫ ተከትሎ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር መጥበብ መገለጫ ነው ከተሰኙት እና ከትልቅ ጉሩምርምታ በኋላ ከጸደቁት ሕጎች መካከል ይመደባል - የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን እና የሙያ ማኅበራትን ለማስተዳደር የወጣው አዋጅ ቁጥር 621/2009። እንደ አብዛኞቹ ተመሳሳይ አዋጆች ሁሉ የኢትዮጵያን ፖለቲካ በቅርበት የሚከታተሉ ሰዎች ይህንንም አዋጅ የሚያዩት መንግስት በቀላሉ መቆጣጠር የማይችላቸውን ድርጅቶች ወይ ከጨዋታ ውጪ እንዲሆኑ አልያም በቁጥጥሩ መዳፍ ስር እንዲወድቁ ያስገደደበት መሣሪያ አድርገው ነው። የመንግስት ጥርስ ውስጥ ባልተፈለገ አዝማሚያ መግባት ከአዋጁ አንቀፅ እንደሚያስመዝዝ የተረዱ ብዙ ማህበራት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ‹‹ወደቀፏቸው›› ተመልሰዋል ቢባል ብዙዎች ይስማማሉ። እንቅስቃሴያቸው እና ውሳኔያቸውም ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት መንግስት እንዴት ሊረዳው ይችላል ከሚል እይታ መተንተኑ የሥራችን አንዱ አካል ሆኖ እስከመቆጠር ደርሷል ብለው የሚናገሩም ጥቂቶች አይደሉም።

በሀገራችን ካሉ ጠንካራ ከሚባሉ የሙያ ማኅበራት መካከል የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል። ማኅበሩ በገለልተኛ የሞያ ማኅበርነት ከሚጠቀሱ ማኅበራት አንዱ ነው። ማኅበሩ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የነበረው ጥንካሬ ከሌሎች ተመሳሳይ ማኅበራት ጋር በንፅፅር ሲታይ ጥንካሬውን አሁንም ይዞ መቀጠል ችሏል ለማለት ያስደፍራል። እንደ ብዙዎች ግምት ግን፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ሕጉ እንዲጠነሰስ ምክንያት ከሆኑ ጥቂት ማኅበራት እና የበጎአድራጎት ድርጅቶች ዋነኛው ነበር።

ጠንካራነቱን እንደያዘ መቀጠል ችሏል የሚባለውን የዚህን ማኅበር የዕድገት ዝግመተ ለውጥ (Evolution) በቅርብ የተከታተሉ ሰዎች ማኅበሩ የዕድገት ጡዘት ጫፍ ማየቱንና አሁን ያለበት ደረጃ እንዲደርስ መሰረቱን ያስጨበጡት የሀገሪቱ አንጋፋ የምጣኔ - ሐብት ባለሙያዎች ከማኅበሩ ጎን መሸሻቸውን ይናገራሉ። እንደማሳያ አድርገው የሚያነሱትም የማኅበሩ አንጋፋ መስራቾች እና አባላት በነበሩበት ወቅት ይካሄዱ የነበሩ ሕይወት ያላቸው ውይይቶች አለመኖር እና ማኅበሩ የሚያከናውናቸው ተግባራት በሕዝብ ዘንድ የነበራቸውን ቅቡልነት መቀነስ ነው። እንደነዚህ ሰዎች ማብራሪያ ማኅበሩ አሁን የሚመሰገንባቸው ምርምሮች፣ የህትመት ውጤቶች እና ሌሎችም ተግባራት አንጋፋዎቹ በነበሩበት ወቅት በእነሱ ጥረት የተጀመሩ ናቸው።

በአንጋፋዎቹ አመራር ወቅት ከተጀመሩት ተግባራት አንዱ የሆነው በኢትዮጵያ ምጣኔ - ሐብት ላይ በየአመቱ የሚያካሂደው አለም አቀፍ ኮንፍረንስ ከሐምሌ 12-14 ሲ.ኤም.ሲ አካባቢ በሚገኘው የማኅበሩ ባለአራት ፎቅ ህንፃ ላይ ለሦስት ቀናት ተካሂዷል። በኮንፍረንሱ ማጠቃለያ ላይ እንደቀረበው ግምገማ ከሆነ ኮንፍረንሱ ላይ እንዲቀርቡ እቅድ ተይዞላቸው ከነበሩት 89 የምርመምር ውጤቶች መካከል 84ቱ በተሳካ ሁኔታ መቅረባቸውንና (በማኅበሩ የፌስቡክ ገፅ ላይ ዘግይቶ የወጣው መረጃ የቀረቡትን የጥናት ውጤቶች 95 ያደርሳቸዋል፣) ተሳታፊዎችም ባመዛኙ የቀረቡት የጥናት ውጤቶች በዳሰሷቸው ጉዳዮች ደስተኛ መሆናችውን መስክረዋል።

የአንጋፋ መስራች አባላትን ከማኅበሩ መራቅ እና በማኅበሩ አዘጋጅነት ይካሄዱ የነበሩትን ሕይወት ያላቸው ክርክሮች መቋረጥን አስመልክቶ የአዲስ ነገሩ ዘሪሁን ተስፋዬ የማኅበሩ የምርምር ክፍልን በዳሬክተርነት የሚመሩትን ዶ/ር አሰፋ አድማሴን ከዓመታት በፊት ጠይቋቸው ሲመልሱ፤ ‹‹ብዙዎቹ ምሁራን ማኅበሩን ሸሽተዋል። በአንጻሩ ወጣቱ ትውልድ በተሳትፎ ጥሩ ለውጥ እያሳየ ነው… ብዙዎች እንደቀድሞው ሞቅ ሞቅ ያሉ (Sensetional) ጉዳዮችን እንድናነሳ ይሻሉ። እኛ ግን ከስሜት ይልቅ ምክንያትን እናስቀድማለን፤›› ብለው ነበር።

ለአሥር ተከታታይ ዓመታት የተካሄደው ዓለም አቀፍ ኮንፍረንስ ለዶ/ር አሠፋ መከራከሪያ ጥሩ ማሳያ የነበረው ይመስላል። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በኮንፍረንሱ ላይ ተገኝቶ የታደማቸው 9 መድረኮች ላይ ከቀረቡት ወደ 29 የሚጠጉ የጥናት ውጤቶች መካከከል ዕድሜያቸው በግምት ከ40 የሚዘሉት አቅራቢዎች ከ4 አይበልጡም ነበር። ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ መሳተፍን በተመለከተ ግን ዶ/ር አሰፋ የአቋም ማስተካከያ ያደረጉ ይመስላል። የ2003 ዓ.ም የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በተካኼደበት ወቅት ከአባላት ‹ለምን በሀገሪቱ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ አስተያየት ለመስጠት እስክትጠየቁ ድረስ ትጠብቃላችሁ፤ ማኅበሩ በሀገሪቷ ምጣኔ-ሃብታዊ ጉዳዮች ላይ ለምን የነቃ ተሳትፎ አያደርግም?› የሚል ጥያቄ ያስተናገዱት ዶ/ሩ ‹‹የሀገሪቷን ሁኔታ የምታውቁት ነው። ከሁሉም ነገር በፊት ህልውናችን ይቀድማል። አሁን ያለው ሁኔታ ያንን እንድናደርግ አይፈቅድልንም›› ሲሉ መልስ ሰጥተው ነበር።

‹‹የማኅበሩ መግስትን ደፍሮ መተቸት አቁሟል የሚሉ ትችቶች ከዚህም ከዚያም በርትተዋል። መተቸቱን ማቆሙን ግን ከጥፋት መቁጠር አግባብነት የለውም›› ይላሉ በኮንፍረንሱ ላይ ተሳታፊ የነበሩ አንድ ግለሰብ።

ቀጥለውም ‹‹ማኅበሩ ከመንግስት ጋር ፊት ለፊት ከመጋጨት ይልቅ በስልታዊ መንገድ ተጉዞ ቀጣይነቱን ቢያረጋግጥ የወደፊቷ ኢትዮጵያ ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ማሳረፍ የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡›› ይላሉ፡፡ አቋማቸውን በምሳሌ ለማስረዳትም ማኅበሩ ለ2012 የፈረንጆቹ አመት የሀገሪቱ ምጣኔ ሃብት ላይ ያቀረበውን አጠቃላይ ዘገባ ይጠቅሳሉ፡፡ በምጣኔ-ሃብት ዘገባው ማኅበሩ የሀገሪቷን የኢኮኖሚ ዕድገት መጠን በተመለከተ የራሱን ቁጥር ከመጠቀም ይልቅ የገንዘብ እና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትርን ቁጥር መጠቀም መርጧል፡፡ ‹‹መንግስት በእንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች ላይ ስሱ (Sensative) ነው፡፡ ማኅበሩ የራሱን ቁጥሮች ቢጠቀምና ዕድገቱ ከ11.4 በመቶ በታች ነው ብሎ ቢዘግብ ኖሮ፤ አይደለም የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ዲኤታው መጥተው የመክፈቻ ንግግር ሊያደርጉ ይቅርና የጥናት ውጤታቸውን ያቀረቡትን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሰራተኞችን ጥናታቸውን እንኳን እንዳያቀርቡ ይከለክሏቸው ነበር›› ይላሉ እኝሁ ተሳታፊ፡፡

ለዘብተኝነትን መርጧል የተባለው ማኅበር ግን በዘገባው እንዲህ ብሏል፤

*"While one can sense that there are signs of high economic growth episodes in the country, the deterministic nature of the growth shades doubt on the accuracy of measuring the GDP in the sense that labour, capital, technology and most importantly nature cannot be so perfect to give a highly predictable constant rate of growth such as this [more than 10% growth rate for consecutive 8 years]. This happens in spite of the fact that a number of the fact that a number of shocks such as draught and international financial crisis put the economy on the test." EEA Annual Report on the Ethiopian Economy 2012 pp. 4*

‹‹[በኢትዮጵያ ውስጥ] ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች እንዳሉ ግልፅ ቢሆንም ተመዘገበ የተባለው የዕድገት መጠን ወጥነት (አለመዋዠቅ)፣ የአጠቃላይ ዓመታዊ ምርት (GDP) የተለካበትን መንገድ ጥርጣሬ ውስጥ ይከተዋል ምክንያቱም ከተፈጥሮ የሚገኙትን የምርት ግብአቶች ጨምሮ ሁሉም ልክ እንደሚፈለገው ሆነው እንደዚህ ዓይነት ወጥነት ያለው ከፍተኛ የዕድገት መጠንን ሊደግፉ የሚችሉበት አጋጣሚ እጅግ ጥቂት ነው፡፡ ኢኮኖሚው ወጥነት ያለው ዕድገት እንዳስመዘገበ የተዘገበው ደግሞ በድርቅ እና በአለም አቀፉ የፋይናንስ ቀውስ በሚፈተንበትም ወቅት ነው፡፡›› የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባከሙያዎች ማኅበር - የ2012 የኢትዮጵያ ምጣኔ-ሃብት ዓመታዊ ዘገባ ገፅ 4፣ (ትርጉም የራሴ)

ምንም እንኳን አንጋፋዎቹ መስራቾች እና ማኅበሩን በአመራርነት ያገለገሉት አባላት መሸሽ በማኅበሩም ጭምር የታመነ እውነታ ቢሆንም 10ኛው ዓመታዊ ኮንፍረንስ ግን 17 የሚሆኑ መስራች እና 3 ልዩ አስተዋፅዖ ያደረጉ አባላትን የኮንፍረንሱ አንድ አካል አድርጎ አክብሯቸዋል፡፡

አሁን ማኅበሩ የያዘው የማመቻመች መንገድ የት ያደርሰው ይሆን? ዘላቂነቱን አረጋግጦ የሀገሪቷን ምጣኔ ሃብት ወደ ብርሃን የሚመሩ ምርምሮችን የሚያፈልቅ እና በመንግስት እና በህዝብ ከምር የሚወሰድ ተቋም የሚሆንበትስ ጊዜ ምን ያህል ቅርብ ይሆን? ጊዜ ብቻ መልስ አለው፡፡

# ፖካ ዮኬ፣ IDIOT PROOF - ETHIOPIA

በዚህ በምህንድስናው የትምህርት ዘርፍ ልብን የሚሰቅዝ ህሊናን የሚቆጣጠር ርዕስ ብዙውን ጊዜ አይኖርም፡፡በተለይ እንደኔ መሐል አዲስ አበባ በሚገኙ የድሆች መንደር ተወልዶ ያደገ ሰው ለራሱም ሆነ ለማኅበረሰቡ ችግሮች ከግል ጥረት እና ላቂያ በላይ መወቀራዊ መስተካከል እንደሚያስፈልግ ሰለሚያምን ካልገባው ወይም ካልተሸወደ በስተቀር በሁለንተናው አይተ.ጋም፡፡ምህንድስና ደግሞ ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም “ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ስር እናውላለን፡፡” ካሉት በተቃርኖ ተፈጥሮን ባለበት አኳኃን ከሳይንሳዊ ጥናቶች በመረዳት ለሰው ልጆች ጥቅም የሚውልበትን መንገድ ማፈላለግ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአጭር ጊዜ በስሎ የሚበላ ፣ ለብዙዎች ችጋር የወዲያው መፍትሔ የሚሰጥ አይደለም፡፡ የሚያጠግብ ቢኖር እንኳ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን የሚፈታ ሰው ሰው የሚሸት መፍትሔ አይሰጥም፡፡ብዙዎች ስሙን ከሩቅ ቢያከብሩትም ቆዳቸው ሳሳ ያለ ሰዎችን አይመስጥም፡፡አንዳንዴ ግን አልፎ አልፎ ልብን ላፍታ የሚያሸፍት ነገር አይጠፋም፡፡ዛሬ በምኞት መልክ እንድንጫወትበት ያሰብኩት ርዕስም ከነዚህ የአንድ ሰሞን የፀሳብ ግልቢያዎች በረከት የተገኘ ነው፡፡

የአንድን ማሽነሪ ንደፍ የሚሰራ ሰው ከሚያደርጋቸው ጥንቃቄዎች ውስጥ አንዱ IDIOT PROOF ይሰኛል፡፡ይህም ማሽኑን የሚያመርተውን ፣ የሚገጥመውን፣ የሚያንቀሳቅሰው እና የሚጠግነውን ሰው ክህሎት እና ንቃት በመጠርጠር የሚጀምር ነው፡፡ ምንም እንኳን ሰውየው አስፈላጊው ዕውቀት ቢኖረው ፣ ተገቢውን ስልጠና ቢያገኝ እንኳ ይሳሳታል ተብሎ ይታመናል፡፡ይህም ከሰው ስህተት ከብረት ዝገት አይጠፋም እንደሚለው ሀገርኛ ቢሒል ያለ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት እንዲህ ያለ ስህተት ይከሰታል ፤ እንዲህ አድርጎ ገልብጦ ይገጥመዋል ፤ የቀኙን ወደግራ የግራውን ወደቀኝ ይቀያይረዋል ብሎ በመገመት ስህተት ፣ ሰህተቱን በመመንጠር የስራውን ክንውን ህጸጽ አልባ ማደረግ ነው ፡፡በአቪየሽን እና ወታደራዊ ማሽኖች ላይ ስህተት ቢፈጠር ጉዳቱም የከፋ ስለሚሆን ይህ ደናቁርትን የማጥለል ጥበብ በብዛት ይስተዋላል፡፡ ማረፊያ ጎማው (landing gear) ተገልብጦ በተገጠመለት አውሮፕላን ቢሳፈሩ ምን እንደሚፈጠር አስቡት? አያድርስ! ነው ብለው ፈጣሪዎን ይጠሩታል ወይስ ለአእዋፍ እንኳ ያልተፈቀደውን ዘላለማዊ በረራን ይመኙለታል? ጉድና ጅራት ከወደኋላ መሆኑን የተረዱት ፈረንጆቹ ግን በአጋጣሚ ይህን ማረፊያ ጎማ የሚገጥም ሰው ከደናቁርት ወገን ሊሆን ስለሚችል ተስሳቶ እንኳን ገልብጦ እንዳይገጠመው አድርገው ከወዲሁ ያበጁታል፡፡ ጃፓኖች ይህንን ጥበብ ፖካ ዮኬ ይሉታል፡፡ትርጓሜውም መወድቂያህን አሳምር ወይም በጥንቃቄ ውደቅ (fail-safing) እንደማለት ነው፡፡ለነገሩ የምህንድስናውን አነሳው እንጅ በሌሎች የትምህርት ዘርፎችም ይህ ስልት እንደሚተገበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡እስኪ ቅጥ አምባሩ ለጠፋው ቦለቲካችን ለምን አንሞክረውም?

የኢትዮጵያን ያለፉ 40 ዓመታት የቦለቲካ ጨዋታ ላስተዋለ ሰው ብዙ የዕውር ድንብር ታሪኮች ያጋጥሙታል፡፡በአስራ ዘጠኝ ስልሳዎቹ አለማችን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ እንደገባች ታሪክ ያስረዳናል፡፡በመሆኑም የገበሬዎች አመጽ ወይም የተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ እንደመነሻ ምክንያት ያገልግሉ እንጂ አብዮት የማይቀር ነበር፡፡ ነገር ግን አብዮቱ ሲጀመር በመሀል መንይማን እንደሚያኮላሹት የተረዳ እና በሩን ለመዝጋት ሙከራ ያደረገ አልነበረም፡፡ካረጀው እና ካፈጀው ዘውዳዊ ስርዓት መላቀቅ ነበረባት፡፡ ነገር ግን ከዘውዳዊው ስርዓት መኳንንት እና መሳፍንት የባሱ ደናቁርት በወንበሩ ሊቀመጡ እንደሚችሉ መገንዘብ የተገባ ነበር፡፡በኃላም ማርክሲዝም አለምን ሲያጥለቀልቅ የኢትዮጵያን በር እንደሚያንኳኳ መረዳት ነብይ መሆንን አይጠየቅም፡፡ነገር ግን በወቅቱ ከነበረው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ከነበሩብን ችግሮች እና መልካም ሁኔታዎች አንጻር ሳይቃኝ እንደወረደ በመተግበሩ የአንድ ትውልድ ወጣት እንዳይሆን እንዳይሆን ሆኖ አልፏል፡፡ ነፍጥ ያነገቡ ሰዎች ከወደ ደደቢት ተነስታው በቃህ እስኪሉትም የቻለውን ያህል ጥፋት እንዳደረሰ በመንገር እንደ ኢተቪ አላደክማችኹም፡፡

በ1983 ዓ.ም. በአዲስ አበባ እናቶች ጸዓዳ ቀሚሳቸውን ገጭ አድርገው ፣ፈንድሻቸውን አፍክተው አስፋልት ላይ እየበተኑ የኢትየጵያ ትንሳኤ እበራፍ ላይ የቆመ መሆኑን ሲያበስሩ ነበር፡፡ብዙም ትሻልን ሰድጄ ትብስን አመጣው ማለት የጀመሩት ግን ልማዳዊው (sentimental) የሀገር ፍቅር የሌላቸው በብሔር ቦለቲካ የተለከፉ ደናቁርት በቴሌቪዥን መስኮት ቀርበው ኢትዮጵያን ሲያራክሱ ነበር፡፡አንዳንዶች አሁን ሀገሪቷ ያለችበትን ሁኔታ ከቀድሞ ጋር በማነጻጸር የተሻለ ሁኔታ ውስጥ እንዳለች ይናራሉ፡፡ከድንቁርና እና ደናቁርትን ማጥሊያ(Idiot proofing institutions ) ተቋማት አንጻር ስንገመግመው አላዋቂነት ለብቻው ተቀምጦ እናያለን፡፡ለአብነት ያህል የሀገሪቱን ፓርላማ ፣ምርጫ ቦርድ ፣ የፍትሕ አካላት ፣ የሀይማኖት ተቋማት ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፣ የሚዲያ ተቋማት መዘርዘር ይቻላል፡፡በቅርቡ በአንድ የህግ ባለሙያ ወዳጄ ጉትጎታ የእነ እስክንድር ነጋ የክስ መዝገብ ወደሚታይበት ወደ ልደታ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጎራ ብዬ ነበር፡፡በኔ ባልተማረ ሰው ምልከታ ‘በህግ አምላክ ሲሉት

ውሃ እንኳን ይቆማል' የሚባልበት ሀገር ውስጥ ያለ ፍትሕ ተቋም አይመስልም፡፡ድኀረ መለስ ኢትዮጵያ ከሚጠብቃት ትልልቅ የቤት ስራዎች ውስጥ አንዱ በህግ ፍትሕ ርትዕን አገኛለው የሚልን መተማመን በማኀበረሰቡ ወስጥ ዳግም ማስረጽ ነው፡፡

የዛሬ ስልሳ አመት ገደማ በሀገረ አሜሪካ 'ጥቁር ሰው ነው' ፣ 'ሴት ከወንድ እኩል ነች' ብለው ለመቀበል የሚቸገሩ ሰዎች ቁጥራቸው የትየለሌ ነበር፡፡ ችግራቸውን እያስወገዱ ድንቁርናን እየከሉ ስለመጡ ዛሬ ሰማየ ሰማያት ደርሰው በጥቁር ፕሬዚዳንት ለመመራት በቁ፡፡እኛ ግን ምንአልባት በአጸደ ስጋ ቢገኙ እንኳን ከሌላው ኡትዮጵያዊ የከፋ ጉዳት ደርሰብን የማይሉ ወገኖቻችንን እየጠቀስን የልዩነትን ግንብ እንገነባለን ፤ የጥላቻን ጉድጓድ እንቆፍራለን ፤ ልዩነትን እንሰብካለን፡፡

ከዘመኑ የቅኝት ስልት ጋር ራስን እያስታከኩ መንጎድ ቀላል ነው ፡፡ተገደን የምንገባበትም ነው፡፡ማርክሲስት መጣ ተቀበልነው ፡፡ማርክሲስት ወደቀ ተውነው፡፡ምዕራባውንን ስንከተል ነበር አሁን ደግሞ ወደቻይና አዘንብለን ያለምንም ማስተዋል እየከነፍን ነው፡፡ዋሽንግተንም ቤጅንግም መሄድ እጅግ ቀላል ነው፡፡ መለስ ዜናዊም ጥሩ ነገር በዚያ አልገጠማቸወም እንጂ በቅርቡ ዲሲ አይተናቸው ነበር፡፡በወንበሩ ተደላድለው መቀመጣቸው ያልየው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝም በታላቋ ቻይና ቴሌቪዥን ቀርበው የወዳጅ ሀገርን ለጋስነነት ሲያወድሱም ታዘበናል፡፡እንዲህ ቀላል ነው፡፡እኛን የቸገረን አዲስ ማዕበል በመጣ ቁጥር የጠነከረውን ጥፊ መቀበላችን ነው፡፡ እንደ የውሃ ላይ ኩበት እየተገላበጥን መሄዳችን ካለፈ ታሪካችን ተምረን መጻዒው ጊዜ ስህተት የለሽ ማድረግ አለመቻላችን ነው፡፡

ግብጾች እና ታህሪር እንዲህ ያለ ትስስር ያላቸው ይመስለኛል፡፡መነይምነትና ደናቁርት ስጋ ለብሰው እንዳየሰለጥኑባቸው የሚያደርጉበት መድረክ፡፡አባቶቻቸው ፒራሚድ ሲገነቡ እነርሱ ደግሞ የሰህተትና ድንቁርና ማጥለያ አደባባይ ታህሪርን አበጅተዋል፡፡ በአንዋር ሳዳት እግር ስር የተተካውን ሙባረክን ከነድንቁርናው ያጠለሉት ታህሪርን ይዘው ነው፡፡ወታደራዊውን ፍርድ ቤትንም እንከባበር ያሉት እዚያው ነው፡፡ከሰው መሐል መርጠው ወደ መድረክ ያመጡት ሞሐመድ ሙርሲስ ቢሆን ከተሰመረለት መስመር ውልፍት ቢል ይለቁታል? እድሜ ከሰጠን አብረን የምናየው ይሆናል፡፡ እንዲህ ስላችኹ በቃ መስቀል አደባባይ እንገናኝ እንዳትሉኝ፡፡ ቀስ! … ቀስ! …ገና ብዙ የቤት ስራ አለብን ግብጻውያን እኮ ታንክ ተደግፈው ነው እምቢኝ ድንቁርና! ያሉት ፡፡ ይልቅስ እንደአሁኑ ወቅት ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ እንደማያጣፍጥ በተረዳን ጊዜ ነው ፖካ ዮኬ የሚሰፈልገን የኛ የነገዋ ኢትዮጵያ ወደኃላ የምትራመድ መሆን አይገባትም፡፡ ካለፈ ስህተቷ ተምራ ማንም ደንቆሮ የማይጠመዝዛት ወደፊት የምትጓዝ… "Anything that can go wrong, will go wrong" ህልም እና ምኞታችንን ማን ይከለክለናል፡፡

# የኪራይ ሰብሳቢ ማዕበል

"Rent-seeking may, indeed, impose costs to the economy as high, if not higher, than those arising from corruption." - Anthony Ogus , Corruption and Regulatory Structures.

## ገንዘብን መግዛት (Rent seeking)

በስነ ምጣኔ ሳይንስ ከእያንዳንዱ ኢኮኖሚ ጀርባ ብዙ ጋሬጣዎች(Economic Inefficiencies) ሊኖሩ ይችላሉ ለምሳሌ እንደ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት፣ የገንዘብ እና የፊስካል ፖሊሲ ክፍተት፣ ሙስና ፣ ገንዘብን መግዛት (Rent seeking) ወ.ዘ.ተ ናቸው፡ ከነዚህ የኢኮኖሚ ማነቆዎች ውስጥ ገንዘብን መግዛት (Rent seeking) የተባለውን ስንመለከት፡፡በአጠቃለይ ኢኮኖሚስቶች ‹‹እሴት አልባ ትርፍ ወይም አሁን ያለው ገንዘብ በራሱ ያለምንም ዕሴት ማጎልበት ተጨማሪ ገንዘብ እንዲገዛ ለዛ መበርታት›› ብለው ይተረጉሙታል፡፡

John Mbaku የተባሉ ኢኮኖሚስት 'Corruption and Rent-seeking' ባሉት ፅሁፋቸው ገንዘብን መግዛትን ‹‹የመንግስት ፖሊሲዎችን ውጤት ለማስቀየር የሚደረግ እንቅስቃሴ›› ብለው ይተረጉሙታል ፡፡ የገንዘብን መግዣ ድርጊቶች ስንመለከት የተያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

Anne Kruger የተባሉ የሚኒሶታ ዩንቨርስቲ ኢኮኖሚስትThe Political Economy of Rent-Seeking Economy'ባሉት ፅሁፋቸው ‹‹ገንዘብን ለመግዛት የሚደረገው ውድድር አንዳንዴ ንፁህ እና ህጋዊ በሆነ መልኩ አንዳንዴ ደግሞ እንደ ሙስና፣ ጥቁር ገበያ እና ህገወጥ የዕቃ ማስተላለፍ ያሉትን ህገወጥ መንገዶች በመጠቀም ሊከናወን ይችላል›› ይላሉ፡፡ ይሄም ገንዘብን መግዛት ሁሌም ህገወጥ ተግባር ብቻ አይደለም ወደሚለው መደምደሚያ ያደርሰናል ማለት ነው፡፡

John Mbaku ከላይ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው በታዳጊ ሀገራት የገንዘብን መግዛት ተግባር በስፋት የሚታይ እንደሆነ ይሄም በከተሞች ጎላ ብሎ እንደሚታይ እና ከገንዘብን መግዥ ተግባራት ማነኞቹ ቢሮክራሲያዊ ሙስና እና የፖለቲካ አመፅ ማስነሳት መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ አያይዘውም ‹‹በመንግስት የተያዙ ሞኖፖሊዮች ለገንዘብን መግዣ ተግባራት ዋነኛዎቹ መፈልፈያዎች ናቸው›› ይላሉ፡፡ ‹‹ምክንያቱም እነዚህ ኖፖሊዩች ተወዳዳሪ ስለሌላቸው ገንዘብን እንደፈለጉ ያደኑታል ያለምንም ማህበራዊ አበርክቶ ደንበኞችም ያለምንም አማራጭ የቀረበላቸውን አገልግሎት ይጠቀማሉ፡፡››

## ኪራይ ሰብሳቢነት ስንል

ኢትዩጵያ ውስጥ የገንዘብን መግዣ (Rent Seeking) ፅንሰ ሃሳብ ከሶሻሊዝም ጋር አብሮ እንደጎለበተ ለማየት ይቻላል እንደ ካፒታሊዝም ውድቀት ተደርጎ በመወሰድ፡፡ በዋነኛነት ግን የህብረተሰቡ ተወስኦ(Public Discourse) አካል እየሆነ የመጣው ከ1997 ዓ.ም ሀገር አቀፍ ምርጫ በኋላ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ 'AFRICAN DEVELOPMENT: DEAD ENDS AND NEW BEGINNINGS' ባሉት እና ከ600 ገፅ በላይ እንዳለው የተነገረውን የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያቸውን ከሆነው ፅሁፍ ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ (Preliminary Draft) ላይ በ50 ገፅ ቁራጭ ታሪኮች (Excerpts) ፅሁፍ እ.አ.አ በ2006 ዓ.ም አቅርበዋል፣ ለውይይት አላማ በሚል፡፡ የዚህ ፅሁፍ ዋነኛ ማጠንጠኛም ይሄው የገንዘብን መግዛት (Rent Seeking) ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ለዛም ይመስላል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ 50 ገፅ አካባቢ ፅሁፍ ውስጥ ወደ መቶ ለሚጠጋ ጊዜ Rent Seeking የሚለውን ቃል ይደጋግሙታል፡፡ አንድ ምዕራፍም በአፍሪካ ያለውን የገንዘብን መግዛት (Rent Seeking) ፖለቲካል ኢኮኖሚን ለመተንተን አውለዋል፡፡

እንደ መደምደሚያም "Only when there is a state that has the characteristics of a developmental state can one meaningfully discuss the elimination of rent-seeking behavior. In its absence rent-seeking will be rampant no matter what the size of the state might be." በማለት የገንዘብን መግዛት ክፉ ጠንቅን የሚዋጋው ልማታዊ መንግስት (Developmental State ) እንጅ ከዳር ቆሞ የሚመለከት መንግስት (Night watch man State) አይደለም በማለት ሀሳባቸውን ያሳርፋሉ፡፡

እንግዲህ በኢትዮጵያ የገንዘብን መግዛት ፅንሰ ሀሳብ 'ኪራይ ሰብሳቢነት' በሚል ስም ዋነኛ የውይይት አርዕስት የሆነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከላይ የጠቀስነውን ፅሁፍ ይፋ ካደረጉ በኋላ ነው። የኢህአዴግ ዋነኛ ልሳኖችም ጉዳዩን ለህብረተሰቡ በሰፊው ማቀበል የጀመሩት ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው በኋላ ላይ ከፓርቲው ልሳኖች በተጨማሪ የመንግስት የሚዲያ ተቋማትም ጉዳዩ የሀገሪቱ ታላቅ ስጋት እንደሆነ አድርገው እያቀረቡት ይገኛሉ።

## ‹‹ደላሎችን በሙሉ ኪራይ ሰብሳቢ ናቸው ማለት ተገቢ አይደለም››

ይህ አንድ የደላላ ማህበር ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ የፃፈው ደብዳቤ ርዕስ ነው። አሁን ባለው አካሄድ መንግስት በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን በ2 ጎራ ከፍሏል ማለት ይቻላል። የልማታዊነት ጎራ እና የኪራይ ሰብሳቢነት ጎራ። ኪራይ ሰብሳቢው ማነው? ካላችሁ እስከ አሁን ድረስ በፓርቲው ሰነዶች ውስጥ ግልፅ ትርጉም አልተሰጠውም ይልቅስ ድርጊቶችን ብቻ በመጥቀስ ይሄ ኪራይ ሰብሳቢነት ነው ይሄ ልማታዊነት ነው በማለት እየተገለፀ ነው።

ጨዋታ ነውና ጉዳዩን እንደሚከተለው እንየው እስኪ ፡

- ኪራይ ሰብሳቢነት ምንድን ነው?
- *እስከ አሁን የተገለፀ ነገር የለም።*
- የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮች ምንድን ናቸው?

*‹‹ኪራይ ሰብሳቢው በዋነኛነት የመሸገባቸው፣ መሬት፣ ግብር፣ ንግድ፣ የመንግስት ግዥ አሰራሮች ናቸው››* *አዲስ ራዕይ* ቁጥር 2 ቅፅ 3 ቁጥር 8 ገፅ 45-46

ኪራይ ሰብሳቢነት በመንግሥት መስሪያቤቶች ውስጥ እንዴት ይገለፃል?

*‹‹የመንግስት መዋቅሩ የኪራይ ሰብሳቢነት ፍርፋሪ በመለቃቀም የተጨማለቀ ወይም ከዛሬ ነገ ፍርፋሪ ይጣልልኝ ይሆናል ብሎ የሚጠብቅ ሰው ያልተለየው መዋቅር ነው። የኪራይ ሰብሳቢነት የውስጥ አርበኛ ነው።››* አዲስ ራዕይ ቁጥር 2 ቅፅ 3 ቁጥር 8 ገፅ 28-29 እያለ የመንግስት ሰራተኛውን ይከሳል እንዲያም ሲል *'የመንግስት ሌቦች'* ይለዋል።

ኪራይ ሰብሳቢነት በጥቅሉ በሀገሪቱ እንዴት ይገለፃል?

*‹‹ከአስር አመታት በፊት የሀገራችን ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ ለኪራይ ሰብሳቢነት የተመቸ እና ኪራይ ሰብሳቢው የሚቆጣጠረው ነበር።ኪራይ ሰብሳቢነትን የመታገል እና የማዳከም ስራችን በመሰረቱ በትክክለኛ አቅጣጫ እየተጓዘ ነው ። አደጋውን ለይተናል ምንጩን እና የትግል አግባቡን አስቀምጠናል። ተግባራዊ ትንቅንቅ ጀምረናል።››* እንዲሁም *‹‹ኪራይ ሰብሳቢው መግቢያ መውጫውን ከማወቁ እና የቁማርተኛ አይነት ድፍረት ተጠናወተው በመሆኑ ከእያንዳንዱ እንቅስቃሴው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ከሚገባው በላይ ተግቶ እየሰራ ይገኛል።››* አዲስ ራዕይ ቁጥር 2 ቅፅ 3 ቁጥር 8 ገፅ 45

ኪራይ ሰብሳቢነትን በዋናነት መታገል ያለበት ማነው? ብላችሁ ስትጠይቁ ደግሞ፡

*‹‹የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር በመታገል ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የዜግነት ግዴታ ያለበት ቢሆንም መምህራን ካለባቸው ብቁ ዜጋ የመቅረፅ ኃላፊነት አኳያ ያለባቸው ኃላፊነት ድርብ ነው።››* አዲስ ራዕይ ቁጥር 2 ቅፅ 3 ቁጥር 9 ገፅ 54 ብሎ መምህሩን ሀላፊነት ይሰጠዋል።

የኪራይ ሰብሳቢነት እና የዕምነት ግንኙነት እንዴት ነው ካላችሁ?

*‹‹አክራሪነትን ከኪራይ ሰብሳቢነት ጋር አስተሳስረን እንፋለመዋለን››* አዲስ ራዕይ ቁጥር 2 ቅፅ 3 ቁጥር 9 ገፅ 38 እንዲሁም *‹‹አክራሪነትን ከኪራይ ሰብሳቢነት ነጥለን መታገል አንችልም››* አዲስ ራዕይ ቁጥር 2 ቅፅ 3 ቁጥር 9 ገፅ 40 በማለት የኪራይ ሰብሳቢነትን አድማስ ከአክራሪነት ጋር አያይዞ ያየዋል።

Where is the Rendezvous of this 'ኪራይ ሰብሳቢነት'? ካላችሁ መልሱ ፡

*‹‹የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከቶች በከተሞች ሰፋ ያለ አድማስ አላቸው፡፡››* አዲስ ራዕይ ቁጥር 2 ቅፅ 3 ቁጥር 9 ገፅ 31

ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዴት ይታያሉ?

*‹‹በሀገራችን የሚገኘው የተቃውሞ ቡድን ባነገበው አላማና በኪራይ ሰብሳቢነቱ አንድ ነው፡፡››* አዲስ ራዕይ ጋቢት ሚያዚያ 2002 ገፅ 4

ለመሆኑ ኪራይ ሰብሳቢነት በህግ ያስቀጣል?

*‹‹ዋናዎቹን ኪራይ ሰብሳቢዎች ወደመቅጣት የምንገባው ከመጥፎ ተግባር አልላቀቅ ሲሉና ማረሚያ ሌላ አማራጭ ሲጠፋ ነው፡፡››* አዲስ ራዕይ ቁጥር 2 ቅፅ 3 ቁጥር 8 ገፅ 33

በአጠቃለይ ከኢትዮጵያዊያን ምን ይጠበቃል?

*‹‹የልማት አብዮቱን ለማጎልበት ኪራይ ሰብሳቢነትን ለቀቅ ልማታዊነትን ጠበቅ››* አዲስ ራዕይ ቁጥር 6 ቅፅ 3 ቁጥር 8 ገፅ 36 እያለ ፓርቲው ምላሽ ይሰጣል ጉዳዩንም ከመሬት ወራሪዎች እስከ ፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች እንዲሁም መምህሩን እና የሀይማኖት መሪዎችን እየነካካ መጨረሻ የሌለው እስኪመስል ድረስ ይጓዛል፡፡ ይሄን ስንመለከትም ኪራይ ሰብሳቢነትን እንረዳው ዘንድ ይከብድብናል፡፡ ምን ማለት ይሆን? ያስብለናል፡፡

ለማንኛውም፡

*‹‹ጉልበተኛ ይሰይማል፡፡ መሰየም የጉልበተኛ አንዱ እና ትልቁ አቅም ነው፡፡ አንተ ሽብረተኛ ነህ ምክንያቱም ፂምህ ከደረትህ ደርሷልና፣ አንች ያለፈውን ስርዓት ናፋቂ ነሽ ምክንያቱም አባትሽ ለንጉሱ ስርዓት አፋሽ አጎንባሽ ነበርና፣ አንተ መንግስትን በሀይል ለመገልበጥ ከሚሰሩ ሀሎች አንዱ እና ዋነኛው ነህ ምክንያቱም ሀምሌ 27 የተባለ ፓርቲ ልሳን እቤትህ ተገኝቷልና ወ.ዘ.ተ እያለ ስያሜው ይቀጥላል፡፡ ምክንያቱም ጉልበተኛ ሲሰይም ማንም ተው አይለውምና፡፡››*

# አባይን መልሱልኝ!

***አባይ……. አባይ…….. አባይ…….. አባይ***
***የአገር አድባር ያገር ኩራት ……..የአገር ሲሳይ***

ቲቸር ታደሰ ከማልረሳቸው የአንደኛ ደረጃ መምህራን መካከል አንዱ ናቸው፡፡ ታዲያ የስድስተኛ ክፍልን የህብረተሰብ ትምህርት ለየት የሚያደርገው የቲቸር ታደሰ ከክፍል ሥራ እና ከንባብ በተጨማሪ ይዘዋቸው ይመጡ የነበሩት ከክፍለ ጊዜው ጋር የተገናኙ ጨዋታዎች እና የጠቅላላ እውቀት ጥያቄዎች ነበሩ፡፡ ታሪክ ቀመስ ትረካዎችን ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ሲያነቡልንም አስታውሳለሁ፡፡ (አዲስ ዘመንም የሚነበብ ታሪክ የሚጽፍበት ወቅት ነበረው ማለት ነው?) ታዲያ በአብዛኛዎቹ ክፍለ ጊዜዎች መጨረሻ ላይ ስለቀድሞ የኢትዮጵያ ስልጣኔ ታሪክ እና ስለተያያዥ ጉዳዮች ሲያወሩ የአባይ ጥቅም ላይ አለመዋልን በቁጭት ማንሳታቸው አይቀርም ነበር፡፡

ከሚሽነሪ ት/ቤቱ ጥብቅ ሃይማኖታዊ ስነ ስርዓት በመነሳት ምንም አይነት መንፈሳዊ ያልሆነ ሙዚቃ መዝፈን የሚያስቀጣ ቢሆንም ቲቸር ታደሰ ግን በኅብረተሰብ ትምህርት በሬድዮ ክፍለ ጊዜ ማጠናቀቂያ ላይ በተደጋጋሚ የሚመጣውን፤

> አባይ……. አባይ…….. አባይ…….. አባይ
> የአገር አድባር ያገር ኩራት ……..የአገር ሲሳይ

በጋራ እንድንዘምር ይፈቅዱልን ነበር፡፡ የኅብረተሰብ ትምህርት እና ልጅነት ሲነሳ አብሮኝ የሚከሰተው የአባይ ትዝታን የምጋራው እኔ ብቻ ነኝ ብዬ አላስብም፡፡ ዓይነቱ የተለየ ቢሆንም ስለአባይ ስንማር እና ሲነገረን የኖርናቸውን ነገሮች በማስታወስ የአንደኛ ደረጃ የህብረተሰብ ትምህርቱ እና የአባይ ትውስታ የሚቀላቀልበት የኔ ቢጤ ወዳጅ መቼም አላጣም፡፡

## የአሁኑ አባይ የማን ነው?

"የታላቁ የህዳሴ ግድብ" ግንባታ ከተጀመረ አንድ ዓመት ያለፈው ሲሆን የምንጨርስበትን ጊዜ የማናውቅ/የናፈቅን/የጠረጠርን ይመስል የጀመርንበትን ቀን በትልቅ ድግስ እና ግርግር አሳልፈነው ነበር፡፡ ሰሞኑን ታዲያ አራት ኪሎ መንገድ ላይ የሚገኘው "የፓርቲያችን" ጽ/ቤት አቅራቢያ ሳልፍ ያየሁት ትልቅ ቢል ቦርድ /ፖስተር መነሻ ሆኖኝ ከዚህ በፊት ይሰማኝ የነበረውን የልጅነቴን አባይ የመነጠቅ ስሜት ወደ አደባባይ ለማምጣት መረጥኩ፡፡

አባይን እንደ ኢትዮጵያዊነት መገለጫ የምንቆጥረው ሰዎች መቼም ጥቂት የምንባል አይደለንም፡፡ ታዲያ በኢህአዴግ ጽ/ቤት ህንጻ ላይ የተሰቀለው ትልቅ ቢል ቦርድ የታላቁን የህዳሴ ግድብ እና አባይን ከጀርባው ያደርግና ከላዩ ላይ ትልቅ የፓርቲውን አርማ በብሔር ብሔረሰቦች ባንዲራ አጅቦ የተለመደውን የግድቡን ግንባታ ቅስቀሳ የመሰለ መፈክር ያስቀምጣል፡፡ ይህ አባይን የፓርቲ የማድረግ አባዜ እነ ኢቴቪን እና ፋናን በመሳሰሉ የፓርቲ ልሳኖች ሲገለጽ ከርሞ አሁን ቢልቦርዱ ጠቅልሎ ስለገለጸልኝ ነው፤ ‹አባይ የማን ነው?› የሚለውን ጥያቄ ያነሳሁት፡፡ እሺ! ኢህአዴግን ያልመረጠስ? የፓርቲ አባል ያልሆነስ? አባይ የእርሱ አይደለምን? የአባይን መገንባት ሲፈልጉ የኖሩት ኢህአዴግ እና ተቀጥጽላዎቹ ብቻ ናቸው? ይህ ህዝባዊ የጋራ መገለጫን ነጥቆ የፖለቲካ ጨዋታን ማድመቂያ ማድረግ የተለመደ የፓርቲው አካሄድ ቢሆንም (የባንዲራ ቀንን ያስታውሱዋል) የህዳሴው ግድብ ነገር ግን ከፓርቲ አመራሮች ጨዋታና የኢቲቪ ፕሮፓጋንዳ ባለፈ የእያንዳንዱ ካድሬ ንግግር ማሟሻ እና መለማመጃ ሆኖ ከራቀን ቆይቶዋል፡፡

በየትኛውም የሲቪል ሰርቪስ ስራ ውስጥ የቢሮክራሲው አንዱ አካል እየሆነ የመጣው ግድብ የእኛ ያልሆነ እና ለፓርቲው ብቻ የተሰጠ ይመስል በባለቤትነት የያዙት ካድሬዎች ብዛት ሳያንስ በየግርግዳው ላይ አባይን የሚያሞግሱ ፋከራዎችን (የማይገናኙ ጉዳዮች ማገናኛም ጭምር ሆኖ) ለማግኘት አቅራቢያዎ የሚገኝ ወረዳ ጽ/ቤት ጎራ ማለት ይበቃል፡፡ ገፋ ሲልም ለግል ጉዳይዎ አገልግሎት ለማግኘት የሄዱበት የሲቪል ሰርቪስ መሥሪያ ቤት የህዝብ አገልጋይ ከአገልግሎቱ በላይ ስለግድቡ ለደቂቃ አለመቋረጥ ሲጨነቅ ሊያገኙት ይችላሉ፡፡

ከአገር ኩራትነት እና ግርማነት ቁልቁል ወርዶ የካድሬ ጉዳይ፣ የፖስተር ማድመቂያ፣ የንግግሮች መክፈቻ እና መዝጊያ ሲሆን "ኧረ ተው አባይ እኮ የእኛም ነው" የምንለው ለማን ነው?

## ለሰከንዶች እንዳይቋረጥ...

ሰሞኑን የምንሰማቸው ካድሬያዊ ንግግሮች አቅጣጫ የሳቱት አባይን የእኛ ጉዳይ እንዳልሆነ በማስመሰላቸው ብቻ አይደለም፡፡ ከጉዳዩ ጋር የማይገናኙ ፍሬ ነገሮችን በመቀላቀል የግድቡ መገንባት ጥያቄ ውስጥ እንደሆነ አድርገው ማቅረባቸውም ጭምር ነው፡፡ ለምሳሌ አንዱ የክ/ከተማ (ወረዳ) ስራ አስፈጻሚ "የግድቡ ግንባታ ለደቂቃ እንዳይቋረጥ የእኛ ድርሻ ከፍተኛ ነው" የሚል ንግግር በስበሰባው ማጠቃለያ ላይ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ጉዳዩን የሚገርም የሚያደርገው በሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት ሰጪው እና በግድቡ ግንባታ መቋረጥ እና አለመቋረጥ መካከል ጨርሶ ግንኙነት አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን የግድቡ መቋረጥ እንደ አንድ የሚያሰጋ እውነት ሆኖ መቅረቡም ጭምር ነው፡፡ "መቋረጥን ምን አመጣው?" ብለን ብንጠይቅ የግድቡን ተገንብቶ ማለቅ በውስጠ አዋቂ የመጠርጠር ስሜት እየተሰማን እና እያሳየን እንዳለን ያሳብቅብናል፡፡

ይህ በቅጡ ያልተቃኘ ካድሬያዊ ፕሮፖጋንዳ እንዲባል የሚፈለገውን(መባል ያለበትን) መልእክት መሳቱ እኛን ከማሰልቸቱ እና ወደ ዳር ከመግፋቱ ባሻገር ያለው ትልቁ ችግሩ ነው፡፡ እስቲ አሁን አባይ እንዳይቋረጥ ሥራህን በስርዓት መስራት አለብህ የሚል ኩርኩም የሚደርስበት ሲቪል ሰርቫንት (የደሞዙ ነገር ሳያንስ) አባይን ቢያኮርፈው ይፈረድበታል፡፡

## "እስቲ እንነጋገር፥ የደሞዙን ነገር..."

ታላቁ ሩጫ እንደቀድሞው ለዛው ቢሆን ኖሮ የሚዘፈንለት አንድ ነገር አባይና የደሞዛችን ነገር፣ አባይ እና የመዋጮው ነገር ይመስለኛል፡፡ የመንግስት ሠራተኛው ፍቃዱ ሳይጠየቅ ሌላው ሰው ደግሞ በሰበብ አስባቡ በተጽእና ስር ሆኖ የሚቆረጥበት ገንዘብ ሌላው አባይን ከእኛ የነጠቀ ጠላታችን ነው፡፡ አስተዋፅዖው እና መዋጮው በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ቢሆን ኖሮ አንድ ሠራተኛ በፍቃዱ ወዶ የሚያዋጣው 5 በመቶ የደሞዙ ድርሻ ተገዶ መቶ በመቶ ከሚያወጣው በተሻለ የጋራ የባለቤትነት ስሜት ይፈጥርለት ነበር፡፡ ታዲያ ምን ዋጋ አለው? በየወሩ የደሞዙ ዕለት ያለፍላጎቱ እና ያለ ነጻ ፍቃዱ የሚቀነስበትን ብር እያሰበ የሚያዋጣና ኑሮ የሚያንገዳግደው ደሞዝተኛ የአባይን ባለቤትነት በጥያቄ ማየቱ የሚገርም አይሆንም፡፡ በዚያ ላይ ደሞ የካድሬ አለቃ እና የኢቲቪ የጋራ ፕሮፖጋንዳ ሲጨመርበት የአባይን የጋራነት ለመርሳት በጣም ቅርብ ይሆናል፡፡

## "አባይን የደፈረ..."

አሁንም የፈረደበት አባይ ከፓርቲው አርማ ጀርባ ከመሆን አንስቶ እስከ ሊቀመንበሩ ፎቶ ማድመቂያነት ድረስ አባይን የደፈረ መሪ ቅጽል ይዞ አደባባይ ከከረመ ቆይቶዋል፡፡ አባይን የመገንባት ፕሮጀክት ጥሩ ሆኖ ሳለ ያላለቀውን ፕሮጄክት እውቅና በሙሉ ለአንደ ግለሰብ ሰጥቶ በየአደባባዩ ማናፈስ (እንዲናፈስ መፍቀድ እና ማበረታታት) ፓርቲ የሚታማበትን የአንድ ግለሰብ ግነት እና አምልኮ እንደተጨማሪ መገለጫ ተደርጎ ቢቆጠርበት ብዙ አያስገርምም፡፡ ይህ ሊቀመንበሩን እና የአባይ ግንባታን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ አድርጎ የማሳየት አባዜ ፓርቲውን እና ኢትዮጲያዊነቱን በሁለት ልብ ለይቶ ለሚይዝ ኢትዮጲያዊ አባይን የመራቅ እና የመነጠቅ ስሜት ቢፈጥርበት ለምን ሆነ ብሎ መፍረድ ከባድ ይሆናል፡፡ በፓርቲው ህዝባዊ ህትመቶች ላይ የሊቀመንበሩን ፎቶ ላለማስቀመጥ የሚጠነቀቀው ኢሕአዴግ አባይን በ21 ዓመት መሪው ፎቶ ጀርባ እያስቀመጠ የጋራ አባያችንን ለግሉ ሲያደርግብን አቤት የሚባለው ለማን ነው?

## "በኅብረተሰብ ክፍለጊዜ የዘመርኩለትን ኢትዮጵያዊውን አባይ መልሱልኝ!"

የእኔ አባይ ከሁሉም ሰው ጋር የምግባባበት የዘር ግንዳቸውን እና የፖለቲካ አቋማቸውን ከማላውቃቸው የልጅነት ጓደኞቼ ጋር የዘመርኩለት ነው፡፡ እባካችሁ ያንን አባይ መልሱልኝ!! የእኔ አባይ ባለመጠቀሜ የተቆጨሁበት አፈሩን ለምን አናስቀረውም? ብዬ ከጓደኞቼ ጋር በልጅነት አንደበት የተወያየሁበት ነው፡፡ እባካችሁ መልሱልኝ!! የእኔ አባይ የጋራ፣ የሁሉም የሆነው በቲቪ ሲመጣ በፏፏቴው የምደነቅበት አባይ ነው፡፡ እባካችሁ ኩራቴን መልሱልኝ!! የእኔ አባይ የማንም ፓርቲ ያልሆነ ጥቅም ላይ ለመዋል ኃላፊነት የሚሰማው፣ በፕሮፖጋንዳ ያልተለወሰ እውነተኛ ልማት ሲጠብቅ የነበረ ህዝባዊ ሃብት ነው፡፡ እባካችሁ መልሱልኝ!! አባይን የአንድ ፓርቲ

የፖለቲካ ጉዳይ፣ የአንድ ፓርቲ ልሳን መገለጫ፣ የአንድ ፓርቲ ኩራት አድርጋችሁ ለፊትለፊት ገጽታ ግንባታ ብቻ አትጠቀሙበት፡፡ የጋራ አባያችንን ወንዛችንን መልሱልን፡፡ ያኔ ሳናማርር አዋጥተን በጋራ እንገነባዋለን!! "እንደጀመርነው እንጨርሰዋለን" ነው ያለው ያ……ልማታዊ ጋዜጠኛ!!!!???

# የኛ ኃይል

“ፒያሳ፤ መሐሙድጋ ጠብቂኝ” በመሐመድ ሰልማን የተጻፈ እና ከፍተኛ ተወዳጅነትን ያተረፈ ኢ-ልቦለዳዊ መጣጥፎች ስብስብ ነው፡፡ የዛሬ ዓመት ገደማ ሚዩዚክ ሜይዴይ ኢትዮጵያ በተባለ መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት አማካይነትመጽሐፉን የመገምገሚያ ዝግጅት አምስት ኪሎ በሚገኘው ብሔራዊ ሙዚዬም ቀርቦ ነበር፡፡ በውይይቱ መሐል የመጽሐፉ ዝነኝነት ምንጮች ምን ምን ናቸው የሚል ውይይት የነበረ ሲሆን ከአስተያየት ሰጪዎቹ መካከል ‹‹ደራሲው የአዲስ ነገር ጋዜጣ ጸሐፊ የነበረ›› መሆኑን እና ‹‹ጽሑፎቹም በአዲስ ነገር ጋዜጣ እና ድረገጽ ላይ ወጥተው የነበሩ›› መሆናቸውን ጠቀሰ፡፡ ውይይቱ የአዲስ ነገር ጋዜጣ መታሰቢያ ይመስል፣ የትዝታ ጫወታው ተጧጧፈ እናም ከውይይቱ ተሳታፊዎች አንዱ የሚከተለውን ሲናገር ረዥም ጭብጨባ አዳራሹን አደመቀው ወጣቱ አስተያየት ሰጪ በንግግሩ መሃል የተጠቀመው እና ጢም ብሎ የሞላውን አዳራሽ በጭብጨባ ያናጋው ንግግር የሚከተለው ነበር፡፡

‹‹ይህ ትውልድ በአዲስ ነገር ጋዜጣ የሚደራደር ትውልድ አይደለም፡፡››

ጉዳዩን አስገራሚ የሚደርገው ወጣቱ ይህንን የተናገረው አዲስ ነገር ጋዜጣ መታተም ካቆመች ከሁለት ዓመታት በኂላ መሆኑ ሲሆን፣ አጋጣሚው የጋዜጣዋ መንፈስ በበርካቶች ልብ ውስጥ በትኩስነት መኖሩን የሚናገር ነበር፡፡

ዛሬ፣ ጥቅምት 5/2005 የዓለም የጡመራ የተግባር ቀን (Blog Action Day 2012) “የኛ ኃይል” በሚል መሪ ቃል ይከበራል፡፡ የጡመራ የተግባር ቀን በየዓመቱ የሚከበር፣ በዓለም ዙሪያ ያሉ ጦማሪዎች በሙሉ በአንድ ሐሳብ ዙሪያ የሚጽፉበት ቀን ነው፡፡ የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ2007 ሲሆን በተመሳሳይ ዓመት ‹‹አካባቢ››፣ በ2008 ‹‹ድህነት››፣ በ2009 ‹‹አየር ለውጥ››፣ በ2010 ‹‹ውሃ››፣ በ2011 ‹‹ምግብ›› በሚል ሲካሄድ ዘንድሮ ደግሞ በ2012 ‹‹የእኛ ኃይል›› በሚል እየተካሄደ ይገኛል፡፡

የዘንድሮው መሪ ቃል፣ ማኅበረሰብ፣ እኩልነት፣ ፀረ-ሙስና እና ነጻነትን በተመለከተ የኛ ኃይል ምን እንደሆነ በመስበክ እንዲከበር ታስቦ የተመረጠ ነው፡፡ አከባበሩ ቀላል ነው፤ አስተባባሪዎቹ እንዳስቀመጡት *‹profile someone or a group who inspires you by the way they made a positive influence… (ባመጡት አዎንታዊ ተጽዕኖ ያነቃቃችሁን የየሆነ ሰው ወይም ቡድን በመምረጥ ጻፉ…)›* የሚል ነው፡፡

እኛም ጮክ ብለን ስናስብበት እና በጭንቅላታችን ያቃጨለችው አዲስ ነገር ጋዜጣ ብቻ ሆነች፡፡ አዲስ ነገር ጋዜጣ ለሁለት ዓመታት (ከጥቅምት 2000 እስከ ታሕሳስ 2002) ብቻ በስርጭት የቆየች ነገር ግን መራኄ አዘጋጇ መስፍን ነጋሽ የጋዜጣዋን ሁለተኛ ዓመት አስመልክቶ እንደገለፀው ‹‹አጭር ግን ረዥም ዓመት›› የኖረች ያክል የማትረሳ ጋዜጣ ናት፡፡

አዲስ ነገር ጋዜጣ በሌጣ ግለሰብ ተፅዕኖ እና ባለቤትነት የማትመራ፣ በስድስት መሥራች አባላት የተቋቋመች እና በሕፀፅ አታች (critical analysis) ጽሁፎቿ ከፍተኛ ተወዳጅነትን እና ተነባቢነትን ለማትረፍ የበቃች፣ የአንባቢውን ቁጥር ያሳደገች፣ የጸሐፍትን ችሎታ የፈተነች (standard ያኖረች)፣ በየጊዜው በማደግ እና ተፅዕኖ በመፍጠር ላይ የነበረች ጋዜጣ ነበረች፡፡ ጋዜጣዋ በቅንጅት መፍረክረክ ሰሞን ተመስርታ በተለይም ኢሕአዴግን በሚነቅፈው ማኅበረሰብ ውስጥ የነበረው የስሜት ስብራት በመጠገን ከፍተኛ መነቃቃትን ለመፍጠር የቻለች እና በማንኛውም መለኪያ አማራጭ መገናኛ ብዙሐን የሚለውን ማዕረግ ለመቀበል የምትመጥን ናት ለማለት ያስደፍራል፡፡፡

ሃሌሉያ እና Terje S Skjerda **የተባሉ የጥናት ባለሞያዎች** በግል ጋዜጦች ብቃት ላይ እ.ኤ.አ. በ2009 ባደረጉት እና ሁሉንም የግል ጋዜጦች ሊባል በሚችል መልኩ በነቀፉበት ጥናታቸው ውስጥ አዲስ ነገር ጋዜጣን እንዲህ ሲሉ ነበር የጠቀሷት፡-

*[To be fair,...] There are newspapers which have steered away from extremist reporting and instead try to give space for different voices. Late 2007 saw the launch of Addis Neger, a private newspaper which by 2009 has grown to become one of the two largest Amharic weeklies with a weekly circulation of*

*25,000-30,000 copies. Its profile is serious,balanced and critical journalism with emphasis on commentaries and in-depth stories. Within the professional limitations that exist, Addis Neger and other publications have produced valuable reporting which has challenged the government in the public sphere.*

*([ሚዛናዊ ለመሆን...] ከፅንፈኛ ሪፖርቶች አፈንግጠው ለተለያዩ ድምፆች ቦታ የሰጡም ጋዜጦች ነበሩ፡፡ በ2002 ከአገሪቱ ሁለት ከፍተኛ ስርጭት ያላቸው (ከ25,000-30,000 ቅጂ) ጋዜጦች መካከል አንዱ ለመሆን የበቃው የአዲስ ነገር ጋዜጣ መመስረት በ2000 አጥቢያ ታየ፡፡ ይዘቱ በአስተያየቶች እና ጥልቅ ታሪኮች ላይ ያተኮረ፣ ቁምነገር አዘል፣ ሚዛናዊ እና ሂስ አዘል ጋዜጠኝነትን የተከተለ ነበር፡፡ በነባራዊው የሙያተኞች እጥረት አዲስ ነገር እና ሌሎችም መንግስትን በሕዝባዊ ክበብ ውስጥ የሚገዳደር እሴት ፈጥረዋል፡፡)*

አዲስ ነገር ጋዜጣ፣ መስራቾቿ እና ጋዜጠኞቿ በመሰደዳቸው አሁን መታተም ካቆመች ሦስት ዓመታት እየተጠጋት ነው፡፡ ሁለቱ ጋዜጠኞቿ ዐብይ ተክለማርያም እና መስፍን ነጋሽም በቅርቡ ሽብርተኝነትን በመተባበር የ8 ዓመት እስር ተፈርዶባቸው በስደት ላይ ይገኛሉ፡፡ አዲስ ነገር ጋዜጣ ላይ ይወጡ የነበሩት ጽሑፎች ግን እስካሁንም ተፅዕኗቸው አልበረደም፡፡ ዳንኤል ክብረት፣በእውቀቱ ስዩም እና መሐመድ ሰልማን የአዲስ ነገር ላይ ጽሑፋቸውን መጽሐፍ አድርገዋቸው እንደአዲስ በብዙ ሺህ ኮፒዎች ተሸጠዋል፡፡ እነሠርጸ ፍሬስብሓት በሙዚቃ ላይ፣ እነማስረሻ ማሞ በፊልም ላይ የሚጽፏቸው ሂሶች የአልበሙን እና የፊልሙን ገበያ ከመወሰንም በላይ፣ ባለሙያዎቹ ለሥራቸው እንዲጠነቀቁ፣ ለአድማጭ ተደራሹም እንዲመርጥ የሚያደርጉ ነበሩ፡፡ ዶ/ር ብርሃኔ ረዳኢ በአስቂኝ የአጻጻፍ ስልቱ የሚያቀርባቸው የሕክምና ነክ ጉዳዮች የብዙዎችን ቀልብ እንደገዙ እስከዛሬም ይታወሳሉ፡፡

የአዲስ ነገር በኢትዮጵያ ፕሬስ ላይ የፈጠረችው ተጽእኖ በቀላሉ የሚታይ አልነበረም፡፡ እንደ አማራጭ፣ ተወዳጅ እና ተመራጭ ሚዲያ ሆኖ ከመቆየትም፣ በተጨማሪ የንባብ ባሕልን ወደ ፋሽንነት ለማምጣት እንዲሁም የወጣቱን ትውልድ ድምጽ የማሰማትም ሚና ነበራት፡፡ አዲስ ነገር ወደ ንባብ እና ወደ ቁም ነገር ያመጣቻቸው አያሌ ወጣቶች ዛሬም ከአዲስ ነገር አለመኖር በኂላም ሐሳብን በነጻነት ስለ መግለጽ ሲጨነቁ እና ሲጠበቡ ይታያሉ፡፡ በአዲስ ነገር መነሳሳት የተነሳም ወደ ጡመራ እና ውይይት የመጡ፣ ተስፋ ማድረግ የጀመሩም ቀላል አይደሉም፡፡

ከሚዲያው የሚመነጭ ጤናማ የአደባባይ ተዋስኦ በጠፋበት በፕሬሱ የጨለማ ዘመን ማግስት አዲስ ነገርን ማግኘት ለጤናማ ሕዝባዊ ውይይቶች መከፈት አስተዋጽዖ የነበረው ከመሆኑም በላይ ጋዜጣዋ መንግስትን በጠንካራ መልኩ በመተቸት ብትታማም የገዥውን ፓርቲ አቋም የሚያንጸባርቁ ቋሚ አምደኞች ነበሯት፡፡ አሁን በሥራ ላይ የሚገኙ እና ታዋቂ የሆኑ የሚዲያ ተቋማትም ቢሆኑ ራሳቸውን ሲገልጹ አዲስ ነገርን ማነጻጸሪያ ሲያደርጓት ተስተውሏል፡፡

በኢትዮጵያ የፕሬስ /ሐሳብን በነጻ የመግለጽ/ ነጻነት እያሽቆለቆለ ለመምጣቱ የአዲስ ነገር ጋዜጠኞችን እንኳን የሚያሠራ ክበብ አለመፈጠሩ ዐብይ ምስክር ነው፡፡ ዛሬ በዓለም የጡመራ ተግባር ቀን ጋዜጣዋን እና ጋዜጠኞቹን ማስታወስ ያስፈለገንም ለዚሁ ነው፡፡ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፣ የሕዝብ ድምጽ /የሕዝብን ብሶት/ የሚያስተጋባ፣ የሕዝብን መንፈስ የሚያነቃቃ ጋዜጣ ያስፈልገናል፡፡ አዲስ ነገር ጋዜጣ የፈጠረችው እና ለመግደል የሚያስቸግር መንፈስ ቢኖር ይኸው መንፈስ ነው፡፡ ዓመታት አልፈውም "ዛሬም በአዲስ ነገር የማይደራደር ትውልድ" ለመፍጠር በቅታለችና!!!

# ከሞቱ ዜና ጋር በተያያዘ

የመለስን ሞት ተከትሎ ብዙ እየተባሉ ያሉ ነገሮች አሉ፡፡ ሬድዮና ቴሌቭዥኑ ሙሉ ሰዓቱን ጠ/ሩ በህይወት ዘመናቸው ያከናወኗቸውን ተግባራት እና ያደረጉትን ንግግር ሃዘን ውስጥ የመክተት ብቃት ካላቸው ክላሲካል ሙዚቃ እና ዋሽንት ጋር በማቀነባበር በማሰማት ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የጠ/ሩን ሞት በተመለከተ በተለያዩ በአገራችን ክልሎች የሚገኙ ነዋሪዎችና ታዋቂ ሰዎች የተሰማቸውን መሪር ሃዘን እና በምን አይነት ሁኔታ እያዘኑ እንዳሉ እየተከታተሉ ዘገባዎችን ያቀርባሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ስርአተ ቀብሩ እስኪፈፀም ድረስ እንደሚቆይ ቢነገርም ከዛ በኋላም ምናልባት እንዳሁኑ ሙሉ የፕሮግራማቸውን ሰዓት ባይሆንም እስከተወሰነ ጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ ሊቀጥል እንደሚችል ጥርጣሬ አለኝ፡፡ ጋዜጣና መፅሄቶችም ስለመለስ በሚያወሩ ፅሁፎች እንዲሁም ከተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የተላኩ የሃዘን መግለጫዎችን ከታዋቂ ሰዎች የተሰጠ አስተያየት ጋር ይዘው ወጥተዋል፡፡

ፌስቡክ መንደር ደግሞ ጠ/ሩ የመሞታቸው ዜና በአገር ውስጥ ሚዲያ እስከተነገረበት ሰዓት ድረስ አትሌቶቻችን በለንደን ኦሎምፒክ በተሳተፉበት ወቅት ስለተገኙት ውጤቶች ከተወራባቸው ውስን ቀናት ውጪ ለተከታታይ ስልሳ ቀናት ወሬው ሁሉ በአብዛኛው የመለስ የጤና ሁኔታ ነበር ብል ማጋነን አይሆንብኝም፡፡ የተለያዩ ምንጮችን በመጥቀስ መሞቱን ሲዘግቡ የነበሩ ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉ ኢትዮጵያዊ ሚዲያዎች ነበሩ፡፡በጠና መታመሙን እና ከዚህ በኋላ ብዙ ጊዜ እንደማይቆይ የሚያትቱ ወሬዎችን ያስነበቡን የውጪ ደህረ ገፆችም የነበሩ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ በአገር ውስጥ የሚገኙ ጋዜጦች በጣም እስክንገረም ድረስ እርስ በርሱ የሚጣረስ መረጃ ሲያቀርቡ ነበር፡፡ ከኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስቴር የሚሰጡ መግለጫዎችም እንዲሁ ግልፅነት የጎደላቸው እና ሙሉ ምላሽ የሚሰጡን አይነት አልነበሩም፡፡ በስተመጨረሻም አቶ በረከት የመለስ ጤንነት በመልካም ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ እና ለአዲስ አመት መጥተው እንኳን አደረሳችሁ እንደሚሉን ነግረውን ነበር የቆምነው፡፡

ሞቱ በአገራችን ሚዲያ እስከተነገረበትም እለት ድረስ በፌስቡክ እና በተለያዩ የሶሻል ሚዲያዎች ያሉ ተሳታፊዎች ‹አልሞተም›፣ ‹ሞቷል› እና ‹በጠና ታሟል› ብለው ማሳመኛ የሚሉትን ሃሳቦች እያነሱ በንቃት ሲወያዩ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ከዚህም አልፈው ድህረ መለስ ትንታኔ ሲሰጡ እና የተለያዩ ግምቶቻቸውን ሲያካፍሉም ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የመለስ ሞት በአገራችን ሚዲያ አብዛኛው ሰው ባልጠበቀበት ሰዓት ሲገለፅ ውይይቱ በመለስ ሞት ማዘንን እና አለማዘንን በመግለፅ ተቀየረ፡፡ ያዘኑት ያላዘኑትን ባለማዘናቸው፤ ያላዘኑቱ ደግሞ ያዘኑትን በማዘናቸው መውቀስና መተቸት ተጀመረ፡፡እስካሁንም ድረስ ይህ መወቃቀስ አላቆመም፡፡ በበኩሌ ‹ማዘን› ወይም ‹አለማዘን› ከውስጥ የሚመነጭ ስሜት እስከሆነ ድረስ ባለመስማማት መለያየት ሲቻል ‹ማዘን ነበረብህ› ወይም ‹ማዘን አልነበረብህም› ብሎ መፍረድ እና ያልተገቡ ቃላትን መወራወር ትክክል አይመስለኝም፡፡ ደግሞም ማዘንም ያለማዘንም የግለሰብ መብት እና ምርጫ ናቸው እንጂ ግዴታ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በፌስቡክ በምናያቸው ውይይቶች ላይ የሚስተዋሉት ወቀሳዎችና ትችቶች ግፋ ቢል ስድብ ቢታከልባቸው ነው፡፡ በርግጥ እኛ ሳናቅ በስውር የተፈፀሙ ወይም የሚፈፀሙ ከስድብ የዘለሉ ነገሮች ተከስተውም ሊሆን ይችላል፡፡ በማረሚያ ቤቶችና በአንዳንድ ቦታዎች ግን ነገሩ አለአግባብ ተካብዶና ትኩረት ተሰጥቶት እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆናቸውን የሚያመላክቱ ነገሮች እየሰማን ነው፡፡

ሰሞኑን ርዕዮትን ለመጠየቅ ማረሚያ ቤት በሄድኩበት ሰዓት የሰማሁት ነገር የሚያስደነግጥ ነው፡፡ የመለስ ሞት ከተነገረ በኋላ ያልተለመዱ ማስፈራሪያዎችና ዛቻዎች እየሰማች እንደሆነ በማዘን ነግራኛለች፡፡ ሌሎቹ እስረኞች ‹እነዚህን ልጆች ከመግደላችን በፊት ውሰዱልን› ብለውናል ተብለው እሷና እማዋይሽ የተባለች ሌላ ፍርደኛ ከነበሩበት ክፍል እንዲወጡ ተደርገው ሁለቱም ወደተለያየ ክፍል እንደተላኩና ከማያቋቸው በቀጠሮ ላይ ያሉ እስረኞች ከሚገኙበት ክፍል እንዲዛወሩም ተደርገዋል፡፡ ከተነገራቸው ማስፈራሪያ እና ወደ አዲሱ ክፍል ተለያይተው በመወሰዳቸው ምክንያት እንቅስቃሴያቸው ሁሉ በከፍተኛ ስጋት የተሞላ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ለወትሮው ፈገግታ በተሞላበት ፊት እና ብሩህ ተስፋዋን በሚያመላክት የራስ መተማመን መንፈስ ጠያቂዎቿን የማዋራት እና የማጫወት ልምድ የነበራት ርዕዮት ሰሞኑን ከደረሰባት ዛቻ እና ማስፈራሪያ በመነሳት ያደረባትን ስጋት ስትናገር እንባዋን መቆጣጠር አልተቻላትም፡፡ ከመለስ ሞት ዜና መነገር ጋር በተያያዘ ሆነም ሌላ ያፈፀመችው ጥፋት እንደሌለና ምናልባትም ግን የመለስ ፎቶ ያለበትን ካኔቴራ በ120 ብር ግዙ ሲባል መግዛት እንደማትፈልግ መናገሯ እንዲሁም ይህን መንግስት በመተቸት የምትታወቅ በመሆኗ ምክንያት ይህ ሁኔታ እንደተከሰተባት የምትጠረጥር ሲሆን ‹‹ይህን የምነግራችሁ የሞትና የሽረት ጉዳይ ስለሆነ እንድታውቁት ነው እንጂ ከዚህ በፊትም ምንም አልነበረም ማለት አይደለም›› ብላለች፡፡

በተያያዘ ዜናም ባለፈው አርብ ፍኖተ ጋዜጣ በልዩ እትሙ በቅሊንጦ ማረሚያ ቤት የሚገኘው የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ ፕሬዝዳንት ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔር ‹መለስ ሞተ ተብሎ ሲነገር ሌሎቹ ሲያለቅሱ አንተ ስቀሃል› ተብሎ በእሰረኞች ከፍተኛ ድብደባ እንደደረሰበት እና ባለቤቱ ከፖሊሶች ‹ካልመከርሽው እስረኞች ሊገሉት ይችላሉ› የሚል ማስጠንቀቂያ እንደደረሳቸው እንዲሁም ከጠ/ሚር መለስ ሞት ጋር በተያያዘ የአንድነት አባላት እየታሰሩ መሆኑን አስነብቦናል፡፡ ወዴት እየተኬደ ነው ትላላችሁ? እነዚህ ሰዎች መለስ ይማረን ሊያስብሉን ይሆን ይሆን?

# የታክሲ ሰልፍ መጀመሪያውና መጨረሻው

ጠዋት ሁለት ሰዓት አካባቢ ወደቦሌ ለመሄድ አራት ኪሎ የተገኘ ሰው እጅግ ረዥም ሰልፍ ለመሰለፍ ይገደዳል (የጥቅምት 6/2005 ሰልፍን በፎቶው ይመልከቱ!) የቦሌ ታክሲ ለመጠቀበቅ ከተሰለፉት ሰዎች ፊት ለፊት ስምሪታቸው በፈረንሳይ ለጋሲዮን ወደጉራራ የሆኑ ታክሲዎችም ተሰልፈው የሚቀድሟቸው ታክሲዎች እስኪሞሉ ድረስ ይጠብቃሉ፡፡ ይህ የአዲስ አበባ ታክሲ የሰሞኑ አጀንዳ ነው፤ እንኳን ደህና መጣችሁ፡፡



## የታክሲ ስምሪት ጉዳዮች

የታክሲ ስምሪቱ በ2004 መባቻ እንደወጣ የተደሰቱም የተበሳጩም ነበሩ፡፡ የስምሪቱ ጉዳይ ሁለት ዓመት ተጠንቶበታል ተብሎ የነበረ ቢሆንም፣ ስድስት ያክል መስመሮች ስምሪት ሳይመደብላቸው መቅረታቸው የሚታወስ ክስተት ነው፡፡ እንዲያም ሆኖ የታክሲ ስምሪቱ ወዲያው እንደተተገበረ የተዘበራረቁ ነገሮችን ለማስተካከል በሚል በሁለት ወር ውስጥ ማሻሻያዎች ወጥተው ተተግብረዋል፡፡

የታክሲ ስምሪቱ ክፍያን በልምድ ሳይሆን በኪሎ ሜትር እንዲሆን አድርጎ የነበረ ሲሆን፣ ማሻሻያው ደግሞ ታክሲዎች የተሰማሩበትን ቦታ ታሪፍ ፊትለፊት እንዲለጥፉ የሚያስገድድ ነበር፡፡ ሁሉም አልተተገበሩም፤ እንዲያውም አንዳንድ ተሳፋሪዎች ታሪፎቻቸውን (እስከ መደባደብ በሚደርስ ትግል) ለማስከበር ቢሞክሩም ቀስበቀስ ሁሉም ተስፋ እየቆረጠ ወደበፊቱ የልምድ አሠራር ተመልሷል፡፡ ሌላው እያቆራረጡ መጫን በስምሪቱ ወቅት የተከለከለ ቢሆንም አስፈጻሚ ባለመኖሩ እሱም በድሮው አሠራር ቀጥሏል፡፡

እነዚህ የስምሪቱ ቅጥያ አገልግሎቶች አልተተገበሩም፡፡ ለመሆኑ ስምሪቱስ ማምጣት የነበረበትን የትራንስፖርት እጥረት ቀርፏል፤ ወይም ለመቅረፍ የተወሰነ አስተዋፅዖ አድርጓል? - ጥያቄያችን ነው፡፡

ሲሳይ ፋንታዬ ለአምስት ዓመታት የታክሲ ሾፌር ሆኖ ሠርቷል፡፡ የታክሲ ስምሪት የታክሲ እጥረቱን አባብሶታል ብሎ ያምናል፡፡ ባነጋገርኩት ወቅት በምሳሌ የነገረኝ እንዲህ በሚል ነበር፤ ‹‹ታፔላ ቢኖርም ባይኖርም ለውጥ የለውም፤ እንዲያውም… ከቦሌ ተነስቼ ወደሜክሲኮ እሄዳለሁ እንበል፣ ሜክሲኮ ስደርስ ስምሪት ከሌለብኝ ወደጦር ኃይሎች ሊሄዱ የተሰበሰቡ ሰዎች ከገጠሙኝ እነርሱን እዚያ አደርሳለሁ፡፡ በዚህ መንገድ ሰው የበዛበትን ቦታ ያማከለ አሠራር መሥራት ይቻላል፡፡››

ሲሳይ የተናገረው እውነት ነበር፤ በፎቶው ላይ የሚታዩት እና ታክሲ ጥበቃ ከተሰለፉት ሰዎች ፊትለፊት የተሰለፉት ታክሲዎች በየጎደለበት አቅጣጫ ቢንቀሳቀሱ ኖሮ ይህ አይከሰትም ነበር፡፡ እነዚህ አራት ኪሎ ላይ የተሰለፉት ታክሲዎች በበፊቱ አሠራር ቢሆን አጭርም፣ ረዥምም እየጫኑ ፈረንሳይ ደርሰው እጅግ ተሰብስቦ የሚጠብቃቸውን ሰው ትንሽ መፍትሔ ይሰጡት ነበር፤ የስምሪት ጣጣ ባይኖርባቸው፡፡

የስምሪቱ ሌላው ችግር ለብልሹ አሠራር የተጋለጠ መሆኑ ነው፡፡ የስምሪቱን አቅጣጫ የሚያወጡት የታክሲ ማኅበራቱ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ የታክሲ ማኅበር የራሱ አቅጣጫ/ዞን ውስጥ ያሰማራል፡፡ ለምሳሌ ፀሐይ እና አዲስ ሕይወት ከሽሮሜዳ እስከ ሜክሲኮ፣ ከአራት ኪሎ በፈረንሳይ እስከ ጉራራ ድረስ አቅጣጫቸው ነው፡፡ ሆኖም እዚህ አቅጣጫ ላይ (እንደዕለታዊ ሁኔታዎች ሊለያይ ቢችልም) በጥቅሉ ከሽሮሜዳ እስከሜክሲኮ የሚሰማራ ታክሲ ከአራት ኪሎ ወደፈረንሳይ ከሚሰማራ ታክሲ ይልቅ ያተርፋል፤ ወይም ብዙ ገቢ ያገኛል፡፡

ስለዚህ ታክሲዎች የማኅበራቱ አስተባባሪዎችን በገንዘብ በመደለል የሚፈልጉት መስመር ላይ ብቻ ለረዥም ጊዜ ወይም ለሁል ጊዜ እንዲመደቡ ያደርጋሉ፡፡ ከላይ ባነሳነው ምሳሌ፣ ሁሌም ከሽሮሜዳ ሜክሲኮ የሚሰማራ ታክሲ የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ይህንን ታክሲ ለመጥቀም ደግሞ ሌሎቹ በፈረንሳይ መሰማራት ስለሚኖርባቸው (ወይም በሜክሲኮ ለመሰማራት ከሚፈጅባቸው ጊዜ የላቀ ርዝመት በመፍጀት) ተጎጂ ይሆናሉ፡፡

## የታክሲ ሥራ ያዋጣል?

በቅርቡ በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ በወጣ ዜና ብዙ የታክሲ ባለንብረቶች ታክሲዎቻቸውን እየሸጡ መሆኑን ያትታል፡፡ ለምን የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የመጀመሪያው ጉዳይ የሚሆነው ሥራው ‹ያዋጣል ወይስ አያዋጣም?› የሚለው ነው፡፡

ቀደም ሲል የጠቀስነው ሾፌር ‹‹አያዋጣም›› ባይ ነው፡፡ ‹‹እንዲያውም፤ የታክሲ ሥራ ከባለንብረቱ ይልቅ ለሾፌሩ ያዋጣዋል›› ይላል፡፡

የታክሲ ባለንብረት በየቀኑ ከሾፌሩ የሚቀበለው 120 (አሁን 150 ሆኗል) ብር ነው፡፡ ይሄ 120 ብር በወሩ ቀናት ሲባዛ 3,600 ብር ይሆናል፡፡ ከዚህ ውስጥ በየወሩ ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን እነ‹ቴስቲኒ› (በባለሙያው አጠራር) በ2000 ብር፣ ባትሪ በ400ብር - ስድስት ወር ያገለግላል፣ ጎማ እስከ2000 ብር አውጥቶ መቀየር እና ብልሽትም ከገጠመው ማሠራት የባለንብረቱ ኃላፊነት ነው፡፡ ይህንን ሁሉ ወጪ መሸፈኑ እንኳን ሊያተርፍ እንዲያውም የሚያከስር እየሆነ እንደሆነ ባለንብረቶችም እየተናገሩ ነው፡፡

ከ5 ዓመት በፊት ‹ቴስቲኒ› በ250 ብር ማስቀየር ይቻል ነበር፣ ባትሪ በ400 ብር እና ጎማ እስከ 500 ብር ማስቀየር ይቻል ነበር፤ አሁን ግን የታክሲ ሥራን የመለዋወጫዎቹ ዋጋ የማይቀመስ ስላደረገው፣ ከሥራው የሚወጡ እንጂ ወደሥራው የሚገቡ ባለንብረቶችን ማግኘት እያከበደ መጥቷል፡፡

የታክሲ ሾፌሮች ከ350 ብር እስከ 400 ብር የወር ደሞዝ ይኖራቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ታፔላ ከተጀመረ ወዲህ ከዕለት ገቢያቸው ላይ በአማካይ እስከ 50 ብር እየያዙ ይወርዳሉ፡፡ ይህ መጠን በፊት በአማካይ 150 ብር እንደነበረ ይናገራሉ፡፡ የቀነሰው ገቢያቸው እንጂ ቅጣቱ እንዳልሆነ እና በጣም እንዳማረራቸው ያነጋገርኳቸው የታክሲ ሾፌሮች በሙሉ ተናግረዋል፡፡ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ለሾፌር የሚከፍሉት ከ900 እስከ 1100 ብር ነው፣ ብዙ ጫና የለውም፣ አልፎ አልፎ ጥቅማ ጥቅሞችም አይጠፉትም… ይህንን አስመልክተው የመንግስት መሥሪያ ቤት ውስጥ ለመቀጠር እየተፍጨረጨሩ ያሉ ሾፌሮችም ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ ይህ የሚያሳየን የታክሲ ሥራ ለሾፌሩም፣ ለባለንብረቱም ከዕለት ዕለት መክበዱን ነው፡፡

የተሳፋሪው ቁጥር እየጨመረ በመጣ ቁጥር የታክሲዎች የማስተናገድ አቅም እጅግ እያጠረ መጥቷል፡፡ በፊት በግፊያ ታክሲ ውስጥ ለመግባት ይደረግ የነበረው ትንቅንቅ አሁን የማይሞከርበት ደረጃ እየደረሰ ስለመጣ ተጠቃሚው ሰልፍን እንደመፍትሔ ወስዶታል፡፡ ሜክሲኮ /ቡናና ሻይ አካባቢ/ የተጀመረው የታክሲ ጥበቃ ሰልፍ በየአካባቢው እየተስፋፋ ነው፡፡ ሰልፉ የተጠቃሚውን ጨዋነት ያሳያል፣ ነፍሰጡሮች እና አዛውንትን ከሌሎች እኩል እንዳመጣጣቸው እንዲስተናገዱ ያደርጋል፤ በጣም የሚበረታታ ነው፡፡ ነገር ግን ጊዜያዊ ችግርን የመቀበያ መንገድ እንጂ መፍትሔ ሊባል ፈፅሞ አይችልም፡፡

አሁን ሰልፉም ቢሆን መጀመሪያውና መጨረሻው (ጫፍ ለጫፍ) መተያየት የማይችልበት ደረጃ እየደረሰ ስለሆነ ጠዋት ሥራ ለመግባት ያሰበ ሰው ተራው እስኪደርሰው ሲጠብቅ አይውልም፡፡ ስለዚህ የሚመለከተው ክፍል /መንገዶች እና ትራንስፖርት ባለስልጣን/ ዘላቂ እርምጃ ዛሬውኑ /ሳይቃጠል በቅጠል/ መተግበር ካልጀመረ ወደማይወጣበት አዘቅት እኛንም ራሱንም መውሰዱ ነው፡፡

# የታክሲዎቻችን ነገር

ከሌላው የኑሯችን ሳንካ ባልተናነሰ የአዲስ አበባ ከተማ ታክሲዎች አሠራር ተጠቃሚዎችን ማማረር እና ማበሳጨት ሥራቸው ከሆነ ሰነባብቷል፡፡ ከረዳትና ከሹፌር ጋር አተካሮ ሳይገጥም የሚሄድ ተሳፋሪ ያለበት ታክሲ ውስጥ መገኘት መታደል ነው፡፡ ባለታክሲ ስል ሾፌርንም ረዳትንም በጅምላ ወይም በተናጠል ማለቴ ነው፡፡ የፀቡ መንስኤ ሁል ጊዜ ባለታክሲ ነው ብዬ አላስብም ተሳፋሪም ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን የዛሬ ርዕሴ ባለታክሲዎችን የሚመለከት ነው፡፡

## ባለቤት፣ ሹፌርና ረዳት

የታክሲ ሥራ ዋና ተዋናይ ሲሆኑ፤ ሁሉም አንድ የሚያረጋቸው የቀን ገቢያቸው ከፍ የሚልበትን ማንኛውንም መንገድ መጠቀማቸውና ለተሳፋሪም ርህራሄ የሌላቸው መሆኑ ነው፡፡ የታክሲ ባለቤት ሹፌር በሚሆንበት ጊዜ ረዳቱ ለከፍተኛ ቁጥጥር አደጋ የተጋለጠ ነው፡፡ ሹፌሩ ተቀጣሪ በሚሆንበት ጊዜ ግን በአብዛኛው ሹፌርና ረዳት በመመካከርና በመረዳዳት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ይኖራቸዋል፡፡ ረዳቱ የታክሲው ባለቤት የሚሆንበት ጊዜም አለ፡፡ ወይም የታክሲው ባለቤት ሹፌር ይቀጥርና የራሱ የቅርብ ሰው የሆነ ረዳት ይመድባል፡፡ (የባለቤቱ ዘመድ የሆኑትን ረዳቶች ሹፌሮች ‹‹ዕንባ›› ነው የሚሏቸው፤ ዕንባ ጠባቂ እንደማለት፡፡) ይህም ለሒሳብ ቁጥጥር ያመቸዋል፡፡ በሁለቱም መንገዶች ረዳቱ ሹፌሩን ሲመራ እና ሲያዝ ይስተዋላል፡፡ አብዛኛዎቹ ረዳቶች ሹፌር የሆነ ወቅት ያክል ከረዱ በኋላ የሹፌርነትን የሥራ መደብ ይይዛሉ፡፡

## እነሱ ብቻ ተናጋሪ

ተሳፋሪን የሚተቹ እና የሚወቅሱ ጥቅሶችን ታክሲ ውስጥ ለተሳፋሪ ዕይታ በሚያመች መልኩ የሚለጥፉትን ነገር ባየሁ ቁጥር እኛም እኮ እንደነሱ የልባችንን የሚናገር ጥቅስ ለጥፈን ታክሲ ውስጥ መግባት ብንችል ብዬ አስባለሁ፡፡ አንጀታችን እያረረም ቢሆን አንብበን ዋጥ አድርገናት እንኄዳለን እንጂ መልስ ለመስጠት ሞክረን አናውቅም፡፡ ከሚለጥፏቸው ጥቅሶች ውስጥ እስቲ እነዚህን ላስታውሳችሁ፡፡

- የታክሲ ከሌለህ ወርደህ በባስ ሂድ
- ባለጌና ዋንጫ ከወደአፉ ይሠፋል
- ሰው አካውንት ይከፍታል፤ አንዳንዱ አፉን ይከፍታል
- ማስቲካ የሚታደል መስሏችሁ አፋችሁን እንዳትከፍቱ
- ጤነኛ ካልሆኑ መውረጃዎ ደርሷል
- የቤትህን አመል እዛው!!!
- ለካፌና ለላዳ ብዙ ይከፍላሉ፤ እኛ ጋ ሲሳፈሩ ለምን ይጨቃጨቃሉ

በተጨማሪም እነሱ ያሉት ነገር ካልሆነ ተሳፋሪን በመስደብ እና በማመነጫጨቅ ሰላማቸውን ያሳጧቸዋል፡፡ ተሳፋሪዎችም ወይ እየሰሙ ዝም ይላሉ፤ ቢመልሱላቸውም ተመጣጣኝ የሆነ ምላሽ አይኖራቸውም፡፡ አለፍ ሲልም እስከመማታት ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

## የሚመሩበትን ሕግ የሚጥስ ሌላ ሕግ ማውጣት

የታክሲ ሥራን የሚቆጣጠር አካል የሚሰሩበትን መስመር እና በመንገዱ የርቀት መጠን የዋጋ ታሪፍ ባወጣው ደንብ መሠረት መሥራት እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡ እነሱ ግን እንዳሻቸው ከተቀመጠላቸው መመሪያ ጋር የሚፃረር አዳዲስ ሕግ እና ደንብ እራሳቸው እያወጡ ያለአንዳች መሳቀቅ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያክል፡-

- ከመነሻ የተሳፈረ ተሳፋሪ የሚወርደው የትም ሆነ የትም የረጅሙን ርቀት ታሪፍ መክፈል አለበት
- የሚሄድበት መስመር ታፔላው ላይ ተለጥፎ እያለ፤ ሲጭን ግን መስመር ቆራርጦ እና ተሳፋሪው የሚሄድበትን/የሚወርድበትን ቦታ ጠይቆ የተስማማውን ማሳፈር
- መሽቷል፣ በመንገድ ተጨናንቋል እና ተቆፋፍሯል ሰበብ ከታሪፉ በላይ አላግባብ ማስከፈል
- ደርቦ ማስቀመጥ ግዴታ ነው አለበለዚያ ሌላው አማራጭ ከታክሲው መውረድ

## ለደንባቸው አለመገዛት እና ሙሰኝነት

ታክሲዎች የሚነሱበት ቦታ እና ተሳፋሪዎች በብዛት የሚወርዱበት ወይም የሚጫኑበት አካባቢዎች ላይ ተራ በማስከበር ሥራ ላይ ከተሰማሩ ሰዎች ዕይታ በመሰወር ተሽሎክሉከው ለማለፍ ይጥራሉ፡፡ እንዲህ የሚያደርጉት ለተራ ሚከፈለውን ክፍያ ላለመክፈል ሲሆን ይህን ክፍያ ላለመክፈልም አንዳንዶቹ አስከባሪዎቹ ካሉበት ቦታ ጥቂት ወደፊት ወይም ወደኋላ ሄደው የተራ ሳይከፍሉ ይጭናሉ፡፡ አንድ ወቅት ተራ አስከባሪዎች ይህን ችግር ለመቆጣተር በቲኬት መሥራት ጀምረው እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ብዙም ግን አልዘለቁበትም፡፡ ያው አዲስ አሠራር ጀምሮ ወዲያውኑ መተው ለአገራችን ብርቅ አይደለም፡፡

ሙሰኞች ናቸው የምልበት ምክንያት ደግሞ፤ ሰልፍ ያለበትም ሆነ የሌለበት ቦታ ሹፌሩ ወይም ረዳቱ የሚውቀው ሰው ሳይሰለፍ እና ሳይጋፋ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ቅድሚያ የመስጠት ተግባር የሚፈፅሙት ታዲያ ለሚውቁት ተሳፋሪ ብቻ አይደለም፡፡ ቀልባቸው ለወደደው ሰውም ቅድሚያ የሚሰጡበት ሁኔታ አለ፡፡ በብዛት ይሄ ዕድል የሚገጥማቸው ሴቶች ናቸው፡፡ በተለይ ውብ እና ዓይን ገብ የሆኑቱ፡፡ ቀጠን ሰብሰብ ያሉ ተሳፋሪዎችም አብዛኛውን ጊዜ ተመራጮች ናቸው፡፡ በአንፃሩ ወፍራም የሆኑ ተሳፋሪዎች ሦስተኛ ሰው ለመጨመር ወይም ኋላ መደዳ ከሆነ ደግሞ አራተኛ ሰው ለመጨመር ስለማያመቹ ባለታክሲዎች አይመርጧቸውም፡፡ ከዚህ ቀደም በተከራካሪነት ወይም በተጨቃጫቂነት (መብታቸውን የሚያስከብሩም ሊሆኑ ይችላሉ) የሚያውቋቸውን ተሳፋሪዎች አይጭኑም፡፡

## መልስ አለመስጠት

አሁን አሁን መልስ መጠየቅ በተለይ በሳንቲም ቤት እንደ አሳፋሪ ተግባር እንደሆነ እየቆጠሩት እና እያስቆጠሩት ነው - ባለታክሲዎች፡፡ ካልተጠየቁ መልስ አይሰጡም፡፡ በተቻላቸው አቅም ያረሳሳሉ፡፡ ሲጠየቁም ሳንቲም የለም የሚል ምክንያት በመስጠት ወይም መጀመሪያውኑ ሳንቲም እንደሌላቸው በመንገር መልሱን የሚያስቀሩበትን መንገድ ይፈጥራሉ፡፡ መልስ የሚጠይቅ ተሳፋሪ እንደ ጠላታቸው፤ የማይጠይቀው ደግሞ እንደ ወዳጃቸው አድርገው ይወስዳሉ፡፡

ባጠቃላይ ግን ሒሳብ ለመሰብሰብ እንደሚቸኩሉት መልስ መስጠት ላይ ይዘገያሉ፤ ባይመልሱም ደስታቸውን አይችሉትም፡፡

## ጭካኔ እና የበዛ ራስ ወዳድነት

ተሳፋሪን የሚያቋሽሽ እና የሚያዋርድ ስድብ መሳደብ ይቀናቸዋል፡፡ ትልቅ አይሉ ትንሽ ሲሳደቡ መሳቀቅ እንኳን አይታይባቸውም፡፡ መልስ ለጠየቃቸው ተሳፋሪ እንኳን ስድብ እና ማመነጫጨቅ የሚቀናቸው ባለታክሲዎች አሉ፡፡ ተሳፋሪዎች ለያዙት ዕቃ የሚጠይቁት ክፍያ በጣም አስደንጋጭ ነው፡፡ ምንም ቦታ ለማይይዝ ዕቃ የሚጠሩት ብር ምን ያክል ለተሳፋሪዎች እንደማያስቡና ጨካኝ መሆናቸውን ያሳብቃል፡፡ አጭር መንገድ ለሚሄድ ተሳፋሪ የረጅም ርቀት ሒሳብ ሲጠይቁ ሕፍረት እንኳን አይሰማቸውም፡፡ በዚህ ምክንያት ተሳፋሪ ልከራከር ቢል "ማን ግባ አለህ"፣ "ተናግሬ ነው ያስገባሁት"፣ "እኔ መች እዚህ ቦታ ጠራሁ" (ዘልሎት አይሄድ እንግዲህ ይታያችሁ)፣ "ብር ከሌለህ የለኝም አትልም?"፣ "ከሌለህ በባስ አትሄድም" እና የመሳሰሉት ውርጅብኞች ይከተሉበታል፡፡

ኧረ ከዚህም የበለጠ በከተማችን ስላሉ ታክሲዎች ብዙ መባል ይችላል!ላሁን ግን ይበቃኛል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በታክሲዎች ተግባር ያልተማረረ ካለ እርሱ የባለታክሲው ዘመድ፤ ሳይሰልፍ፣ ሳይጋፋ እና መንገድ ሳይቆራረጥበት የሚሳፈር ወይም የመኪና ባለቤት መሆን አለበት፡፡

በተረፈ ታክሲዎቹ በማን አለብኝነት፣ በምን ታመጣላችሁ እና ከኛ ውጪ አማራጭ የላችሁም በሚል የንቀት መንፈስ እኛን ማማረራቸውን ቀጥለዋል፡ ታዲያ እነዚህ ትናንሾቹ ኢሕአዴግ መር መንግሥት መባል ያንሳቸው ይሆን?

# ‘ሰንደቁ’ ላይ ያለው ‘ዓላማ’

ወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) ስልጣን በያዘበት ማግስት ነው፡፡ በጊዜው የነበረው የሀገሪቱ ሰንደቅ ዓላማ አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለማትን ብቻ ያዘ ነበር (በርግጥ በሕግ የተደነገገ ባይሆንም በአንዳንድ የደርግ ተቋማት ውስጥ ሰማያዊ መደብ ያለው ሰንደቅ ዓላማም ይስተዋል ነበር)፡፡ የወቅቱ ባለስልጣናትም አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀዩ ሰንደቅ ዓላማ ላይ የብሄሮችን መፈቃቀድ የሚገልፅ አርማ መኖር አለበት፤ አርማውስ ምን አይነት ይሁን? የሚል ሃሳብ ይቀርባሉ፡፡ የታሪክ ፕሮፌሰር የሆኑት ላጲሶ ጌ. ዴሌቦም ሀሳባቸውን እንደሚከተለው ሰነዘሩ ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ በጣም ተጨቁኖ የኖረ ሕዝብ ነው፡፡ ስለዚህም በሰንደቅ ዓላማው ላይ የሚቀመጠው አርማ ይሄን ጭቆናውን የሚገልፅ መሆን ይኖርበታል፡፡ ለዚህም ደግሞ ‘ከአህያ ምስል’ የተሻለ አርማ የለም፡፡ ሕዝቡ እንደ አህያ ለዘመናት አምባገነንነት ተጭኖበት በጭቆና ውስጥ ነበርና፡፡››

ይህ ከሆነ 17 ዓመታት በኋላ ተሻሽሎ የወጣው የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር 654/ 2001 በአንቀፅ 4 ላይ እንዳሰፈረው ‹‹ብሄራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን በየዓመቱ መስከረም ሁለኛ ሳምንት ሰኞ በድምቀት ይከበራል፡፡›› ከአዋጁ መውጥት አስቀድሞ በሰኔ 2000 ዓ.ም በግለሰቦች አነሳሽነት መከበር የጀመረው የሰንደቅ ዓላማ ቀን ዘንድሮ ለ5ኛ ጊዜ *“ሰንደቃላማችንን ከፍ አድርገን በመለስ ቀያሽነት የተጀመረውን ህዳሴ እናረጋግጣለን!”* እንደሚከበር ተገልጿል፡፡ ነገር ግን የዘንድሮው ክብረ በዓል በአዋጁ ከተደነገገው ቀን አልፎ ጥቅምት 19/2005 ዓ.ም ነው የሚከበረው፤ ይሄን አስመልክተን በኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ዙሪያ ያሉ ሀተታዎችን ለመመልከት ተነሳን፡፡

## ሰንደቅ ዓላማ

ከሰንደቅ አላማ ቀለም እና ምልክት ጀርባ ታሪክ፣ ባህል፣ ማንነት እንዲሁም አንዳንዴ አስተሳብን የሚያመለክት መንፈስ አለ፡፡ የካውካሲያን ህዝቦችን (ለምሳሌ የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣የሩስያ፣ የአውስትራሊያ ወ.ዘ.ተ) ሰንደቅ አላማዎችን ብንመለከት በአብዛኛው ነጭ፣ ቀይ እና ሰማያዊ ቀለማትን ለሰንደቅ አላማነት ይጠቀማሉ፡፡ የቀለማቱም ምርጫ በተወሰነም መልኩ የህዝቦቹን አንድ አይነት አመለካከት ይገልፃሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአፍሪካዊያንን ሰንደቅ ዓላማ ስንመለከት አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለማት ከፍ ብለው እና በተለያየ አደራደር ተቀምጠው እናያለን፡፡ ይሄም ተመሳሳይ ምክንያት እንዲሸተን ያደርገናል፡፡

## ታሪክ ወ አፈታሪክ

የሀገራችን የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ በሀገሪቱ ውስጥ አነታራኪ ከሚባሉ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ንትርኩም የሚጀምረው ከታሪካዊ አመጣጡ ጀምሮ ነው፡፡ በዚህም ጉዳይ ታሪክን ከአፈታሪክ (History from Myth) ለመለየት አስቸጋሪ ከመሆኑ አንፃር በዋነኛነት ጎልተው የሚሰሙትን ታሪኮች እና አፈታሪኮችን አዳቅለን ለማየት እንሞክር፡፡

በአሁኑ ወቅት ያለውን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ለምን አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለማት ሊሆን ቻለ? ለሚለው መልስ የተለያ ወገኖች የተለያዩ ምክንያቶችን ያቀርባሉ፡፡ ክርስቲያናዊ ትርጉሙም ገዝፎ ይታያል፡፡ እንደ አንዳንድ ፀሃፍት ‹‹የቀድሞ አባቶቻችን እና እናቶቻችን ወደ ጦር ሜዳ ሲሄዱ የተለያዩ የዛፍ ዝንጣፊዎችን ይዘው ይዘዋወሩ ነበር፡፡ የሚይዙት ዝንጣፊም አረንጓዴ በመሆኑ በተለያዩ ነገሮች አረንጓዴ ነገርን በማዘጋጀት እንደ ቀዳሚው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሆነ፡፡›› በማለት አጀማመሩን ይገልፃሉ፡፡

አፈታሪኩ ሲያስከትልም ‹‹ኢትዮጵያ ከሕገ ልቦና ወደ ሕገ ኦሪት በንግስተ ሳባ አማካኝነት ስትሸጋገር በእግዚአብሄር ተስፋ ማድረግን ለማመላከት ኢትጵያዊያኑ ቀድመው ይጠቀሙበት የነበረው አረንጓዴ መለያ ላይ ቢጫ ቀለምን በመጨመር አንድ እርምጃ ወደፊት ተሻገ›› በማለት ክልኤቱ ይላል፡፡ ክርስቲያናዊ አፈታሪኩ ሲቀጥልም ‹‹በንጉስ ባዚን ጊዜ ወደ እየሩሳሌም አቅንቶ ወንጌልን አውቆ የተመለሰው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ክርስትናን ወደ ኢትዮጵያ ይዞ ከመግባቱ ጋር ተያይዞ፤ ኢትዮጵያዊያን እየሱስ ክርስቶስ በደሙ ቤዛ እንደሆናቸው በማመናቸው ቀድመው ይጠቀሙበት የነበረውን አረንጓዴ እና ቢጫ መለያ ላይ ቀይ ቀለም በመጨመር አሁን ያለውን ቀለም እንዲይዝ አድርገውታል›› ይላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ የሆነው እግዚአብሄር አለምን ዳግም በጥፋት ውሃ ላለመምታት ለኖህ የገባውን ቃልኪዳን የፈፀመው በቀስተዳመና ነው፤ በቀስተ ዳመናውም ውስጥ ገዝፈው የሚወጡት ቀለሞች አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ በመሆናቸው የነሱን አምሳያነት ነው የሚል አፈታሪክ

ይደመጣል። ከዚሁ ከኖህ ጋር ተያይዞ ‹‹የጥፋት ውሃው በጎደለ ጊዜ እንደ ብስራት መግለጫ የታየው የወይራ ቅጠል መጀመሪያ አረንጓዴ፣ ሲቆረጥ ወደ ቢጫ በመቀየር መጨረሻ ላይ ቀይ ቀለምን በመያዝ ይደርቃል እናም ሰንደቅ ዓላማችን የወይራው ተምሳሌት በመሆን መልካም ዜናን ገላጭ ነው›› የሚል አፈ-ታሪክም ይደመጣል።

የቅርብ ጊዜ ታሪኮች ደግሞ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የአሁኑን ቀለም የያዘው ባለፍት 150 ዓመታት በተደረገው ክለሳ ነው። ከዛ በፊት የነበረው ሰንደቅ ዓላማ ሌሎች የተለያዩ ቀለማትን የያዙ ነበሩ ይሉናል። ነገር ግን አንዳንዶች በአፄ ቴዎድሮስ ሁለተኛ ጊዜ ነው የአሁኖቹ ቀለማት ጥቅም ላይ የዋሉት ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ የለም የለም በአፄ ዩሃንስ አራተኛ ዘመነ መንግስት ነው ይላሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አይ በዳግማዊ ምኒልክ ንግስና ዘመን ነው፤ ይህ የሆነው በማለት ታሪኩን ያወሳስቡታል። እንግዲህ የቀለማቱ ታሪክ እና ትርጉም ስምምነት ላይ ሳይደረስበት ሲሰረዝ እና ሲደለዝ አሁን የምንጠቀምበትን አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለማት በሰማያዊ አርማ እና በቢጫ ኮከብ የታጀበ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ደርሰናል። ውዝግቡ ግን አሁንም እንደቀጠለ ነው። እስኪ በአሁኑ ወቅት በሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ ላይ የሚነሱትን አንዳንድ የውዝግብ ነጥቦች እያነሳን እንመልከት።

## ሰንደቅ ዓላማ ወይስ ሰንደቅ ዓላማዎች?

ከጣሊያን ወረራ በማስከተል በተፈጠረው አጋጣሚ ኢትዮጵያ የቀድሞ የግዛት አካሏን እና ለ50 ዓመታት በጣሊያን ቅኝ ግዛት ምክንያት ተነጥሎ የኖረውን የግዛት ክፍሏ ይመለስላት ዘንድ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት አመለከተች። የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም ከረጅም እና አታካች ውይይት እና ግምገማ በኋላ በአሜሪካን መንግስት አነሳሽነት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን እንድትዋሃድ ወሰነ። ኢትዮጵያም በውሳኔው ለጊዜው ግር ብትሰኝም እንደ አሜሪካን እና ህንድ አይነት ታላላቅ ሀገሮችም በዚሁ የፌደሬሽን ስርዓት እንደሚመሩ መገለፁ ብዥታውን እንዲያለዝበው ሆነ።

ነገር ግን በብዙ ኢትዩጵያውያን እና በኤርትራ የሚገኘው የአንድነት ማህበር (The Unionist Party) ፤ ኤርትራ ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ተለይታ የራሷን ሰንደቅ ዓላማ ማውለብለቧ አልተዋጠላቸውም ነበር። ይሄም ነገር ይቀለበስ ዘንድ አብዝተው በመጎትጎታቸው ለ10 ዓመታት የቆየው ፌደሬሽንም በንጉሱ ፊርማ ፈረሶ የኤርትራ ሰንደቅ ዓላማም ጉዳይ አከተመ።

የኢህአዴግን ስልጣን መያዝ ተከትሎ የኤርትራ መገንጠል ብዙ ኢትዮጵያዊያንን ያስደነገጠ ጉዳይ ነበር። በሽግግር መንግስቱ ወቅት ተረቆ የፀደቀው የኢፌደሪ ሕገ መንግስት ፌደራሊዝምን እንደ መንግስታዊ መዋቅር መቀበሉ ደግሞ አንዳንድ ወገኖች በተለይም አጥባቂ ኢትዮጵያዊንን (Ultranationalists) ‹‹ይህች ሀገር ተገነጣጥላ ልታልቅ ነው›› የሚል ሌላ ስጋት ውስጥ ከተታቸው።

ሕገ መንግስቱ የፌደራል ስርዓቱ በክልልሎች እንደሚዋቀርና እያንዳንዱ ክልሎችም የራሳቸው የሆነ ሰንደቅ ዓላማ እና አርማ እንደሚኖራቸው መደንገጉ፤ ለነዚህ ወገኖች የኢህአዴግን ፀረ-ኢትዮጵያዊነት መረጋገጫ ነበር። ኢህአዴግ በበኩሉ ‹‹ፌደራሊዝሙ እንደዚህ ካልተዋቀረ አብረን መኖራችን ያሰጋናል፤ ክልሎች የራሳቸው ሰንደቅ ዓላማ እና ዓርማ እንዲኖራቸው መፍቀዱ ደግሞ አሜሪካን በሚያክል ትልቅ ሀገር ሳይቀር ተቀባይነት ያለው የራስን በራስ የማስተዳደር አንዱ መገለጫ ነው። ኢትዮጵያም በተወሰኑ ቀለማት ብቻ አትገለፅም።›› የሚሉ ምላሾችን በመስጠት ለክልሎች የራሳቸውን ሰንደቅ ዓላማዎች እንዲመርጡ አስቻላቸው።

ከዛን ጊዜ ወዲህ የሱማሌ ክልል ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ወደ 11 ርዕሰ መስተዳደሮችን የቀያየረ ሲሆን፤ በሰንደቅ ዓላማ መቀየሩስ ለምን ይቅርብኝ? በሚመስል ምክንያት ሁለት የተለያዩ ሰንደቅ ዓላማዎችን ቀይሯል፤ ይሄም ድርጊት ብዥታን መፍጠሩ አልቀረም። በሌላ በኩል የትግራይ ክልል ሰንደቅ ዓላማ ህወሃት በትግል ወቅት ይጠቀምበት የነበረው ሰንደቅ ዓላማ ለትግራይ ክልልም ማበርከቱ ትክክል አይደለም የሚል ሀሳብ መነሳቱ አልቀረም።

እንግዲህ አንድ ሀገራዊ ሰንደቅ ዓላማ? ወይስ ሁሉም ክልሎች ከሀገራዊ ሰንደቅ ዓላማው ጎን ለጎን የሚያውለበልቡት የራሳቸው ሰንደቅ ዓላማዎች? የሚለው ሃሳብ አነታራኪነቱን ይዞ ቀጥሏል።

## ‹‹ባንዲራ ጨርቅ ነው ... አንዳንድ ሀገሮች ከወረቀትም ይሰሩታል››

ባለፉት ዓመታት ሰንደቅ ዓላማ በተነሳ ቁጥር የቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ መነሳታቸው አልቀረም፡፡ በአንድ ወቅት ‹‹ባንዲራ ጨርቅ ነው›› ማለታቸው እንደ አንድ ሀገሩን የማይወድ መሪ እንዲቆጠሩ ያደረጋቸው ሲሆን፤ ከብዙ ኣመታት በኂላ ‹‹ባንዲራ ጨርቅ ነው›› ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነ ሲጠየቁ፤ ‹‹አዎ ባንዲራ ትርጉም ከሌለው እንደወረደ ጨርቅ ነው፤ እንዲያውም አንዳንድ ሀገሮች ከወረቀት ይሰሩታል፡፡ ባንዲራ ትርጉም ይኖረው ዘንድ ዜጎች ሊወዱት እና ትርጉም ሊሰጡት ይገባል፡፡›› በማለት ምክንያታቸውን ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡

ነገር ግን ማሳመኛቸው ያልተዋጠላቸው ሰዎች ‹ምንም ቢሆን እንደ ሀገር መሪ እንደዚህ ማለት አልነበረባቸውም›› በማለት ሀሳባቸውን ያጣጥሉባቸዋል፤ አቶ መለስንም በፀረ-ኢትዮጵያዊነት ይፈርጇቸው ነበር፡፡ መለስ ግን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እንደ ሰንደቅ ዓላማ ቀን ባሉ በዓላት ላይ በመገኘት ስማቸውን ለማደስ መጣራቸው አልቀረም ነበር፡፡

## The Magic Emblem

ሌላው በአሁኑ ወቅት በሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ ላይ ጎልቶ የሚነሳው ክርክር፤ በአሁኑ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ያለው አርማ ምንነት እና ትርጉም ነው፡፡ ለዛም ይመስላል ጉራማይሌ የሆነ የሰንደቅ ዓላማ አይነት በየቦታው የምንመለከተው፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት በአንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ እንዲሁም ተሻሽሎ የወጣው የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ 654/2001 በአንቀፅ 8 ላይ እንዳስቀመጡት በሰንደቅ ዓላማው ላይ ያለው ዓርማ ሰላምን፣ እኩልነትን አንድነትን እና ተስፋን ገላጭ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ይህ ትርጉም ያልተዋጠላቸው ወገኖች ምልክቱን በብዙ መልኩ በመተርጎም በህገ መንግስቱም ሆነ በአዋጁ የተጠቀሱት የአርማው ምክንያት ውሸት ነው ይልቅስ ‹‹የአንድ ብሄርን የምግብ አይነት አመላካች ነው›› ፣ አይ ‹‹ምልክቱ የኢህአዴግ አመራሮች ከሶሻሊዝም ምንጭ እየጠጡ (From Socialism Background) የጎለመሱ በመሆናቸው የሶሻሊዝሟን ኮከብ በአቋራጭ ሰንደቅ አላማዋ ላይ ማስቀመጣቸው ነው፡፡›› ይላሉ፡፡ ይባስ ብሎም አንዳንዶች ‹‹የጥንቆላ ምልክት ነው፤ እንጅማ የኮከብ ምስል ከኢትዮጵያ ጋር ምን አገናኘው?›› ይላሉ፡፡

የሆነ ሆኖ የሰንደቅ ዓላማ አዋጁ በሕገመንግስቱ ከተቀመጠው ዓርማ ውጭ የተሰራ ሰንደቅ ዓላማን መጠቀም እስከ አንድ አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን፤ የኮከቡን አርማ ከያዘው ሰንደቅ አላማ ውጭ ያሉ ታሪካዊ ሰንደቅ ዓላማዎች በቤተ መዘክር እንደሚቀመጡ እና በአረጁ ጊዜም እንደሚቃጠሉ ይገልፃል፡፡

## ዳግማዊ ቦሊቪያን መቅደም

በንጉሱ ዘመን የነበረው የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ በአንዳንድ የትርጉም ምክንያቶች ከአረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ወደ ቀይ ቢጫ እና አረንጓዴነት ለመቀየር ኢትዮጵያ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት አመልክታ ይህ አደራደር በደቡባ አሜሪካዊዋ ሀገር ቦሊቪያ የተያዘ መሆኑን ተገልጾ ጥያቄዋ ውድቅ ተደርጎባታል፡፡

እንደ መላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰማያዊ አርማ የሌለበትን ንፁህ አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ እንደ ትክክለኛው የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ በመቁጠር፤ በፓርቲያቸው ፕሮግራም ውስጥ ያካተቱ ሲሆን ለተባበሩት መንግስታት ድርጅትም የቦሊቪያው ታሪክ እንዳይደገም ይሄን ቀለም የያዘ ሰንደቅ ዓላማ ለሌላ ሀገር እንዳይፈቅድ እስከ መጠየቅ ደርሰዋል፡፡

የሀገራችን ፖለቲካ ፓርቲዎች በሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ ላይ እንኳን ስምምነት ላይ አልደረሱም፡፡ ለየትኛው ሰንደቅ አላማም ክብር (Allegiance) እንደሚሰጡም አልተስማሙም፡፡ ይህ ልዩነት ህብረተሰባችን ውስጥም አለ፡፡ ብቸኛው መፍትሄ ወደ ውይይት ቀርቦ ሀሳብን መሸጥ እና መግዛት ነው፡፡ ያለዚያ የተለያየ ሰንደቅ ዓላማ ይዘን የኢትዮጵያን ጥቅም በጋራ ማስጠበቅ እንዴት ይቻለናል?

# በኢትዮጵያ የቡድን አመራር ተጀምሯል?

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከማንኛውም የሕዝብ ወገን (ከወጣቶች፣ ከሴቶች፣ ከነጋዴዎች…) ጋር ሲወያዩ/ሲያወሩም ሆነ ሲያገኙ ብቻቸውን ሆነው ነበር፡፡ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ግን ይህ ዕድል የተሰጣቸው አይመስልም፤ ቀደም ሲል የአገሪቱን ባለሀብቶችን ሲያነጋግሩ ከአራት ሚኒስትሮች ጋር በመሆን ነበር፡፡ የኡጋንዳን የነጻነት 50ኛ ዓመት በዓል ላይ የተገኙት ከበርካታ ባለሥልጣናት ጋር (አቶ በረከት ስምኦንን ጨምሮ) ነበር፡፡ በመጨረሻም ደግሞ ከሰሞኑ የተከሰተው የሦስት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች መሾም ኢትዮጵያ ውስጥ የቡድን አመራር ተጀምሯል? የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም፡፡ ተጀምሮስ ከሆነ የቡድን አመራር ለኢትዮጵያ ይበጃት ይሆን?

## ሦስት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር - ድንገተኛ?

ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ዞን ዘጠኝ ላይ ‹ከመለስ በኋላ› በሚል የጠቅላዩን ሞት ተከትሎ በተነበበ ጽሑፋቸው *"…ከሁለት ዓመት በፊት ከኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር መካከል አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ እንዴት የምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴርነትን ሹመት እንዳገኙ ማስታወስ ይገባናል፡፡ በዚህ ወቅት ፓርቲው በመተካካት ጥያቄ እና በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ጤና መቃወስ ምክንያት ተወጥሮ ነበር፡፡ በዚህም ጊዜ በጣም የሚያስገርመውና የሚያስደምመው የሕወሓት ልሂቃን ሁለት አማራጭ ይዘው ቀረቡ፡፡ አንደኛ በአገሪቱ ላይ ዴሞክራሲ እንዳይቀጭጭ ከተፈለገ እና እኛ የምንወክለው የሕዝብ ቁጥር አነስተኛ ስለሆነ የጠቅላይ ሚኒስቴሩን ቦታ ከብአዴን እና ኦህዴድ ብንመርጥ የግንባራችንን የኃይል ሚዛን ስለሚያዛባው በኛ በኩል ተቀባይነት የለውም የሚል ሐሳብ አቀረቡ፡፡ ሁለተኛ የጠቅላይ ሚኒስቴሩን ጽ/ቤት ለሦስት ወይንም ለሁለት በመክፈል የስልጣን ክምችቱን (premiership) ብናሰራጨው የተሻለ ይሆናል አሉ፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያው ሐሳብ በግንባሩ ተቀባይነት በማግኘቱ ከሁለቱ ብዙኃን ፓርቲ ውጪ የሆነ ሰው በምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴርነት ለመምረጥ በቅተዋል፡፡ ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ ሀገሪቱን ለሌሎች ስጋቶች ስለሚያጋልጣት ተቀባይነት አላገኘም…"* የሚል አንቀጽ አስፍረው ነበር፡፡

ዶ/ር ጌታቸው አሰፋ እንደተናገሩት ቀደም ሲል ኢሕአዴግ ተወያይቶበት የነበረው የሦስት ጠቅላይ ሚኒስትር አጀንዳ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ስም መምጣቱ መልኩን ቀይሮ የመጣ መፍትሔ እንጂ ድንገተኛ ክስተት አይደለም፡፡ ምናልባትም ደግሞ በመገናኛ ብዙኃን እንደተደሰኮረልን፣ የመለስን ምትክ በአንድ ሰው ማምጣት ስለማይቻል ለአራት እንዲሆን የተበጀ አዲስ መፍትሔ ነው ብሎ ማለት የዋህነት ይሆናል፡፡ ይልቁንም ለሕወሓት በሩን ለመክፈት ይመስላል፤ ሹመቱን እንመልከተው፡፡

## አዲሱ ሹመት

ዶ/ር ደብረጽዮን ገ/ሚካኤል (ሕወሓት) የኢንፎርሜሽንና ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና የፋይናንስና የኢኮኖሚ ዘርፍ ክላስተር አስተባባሪ፣ አቶ ሙክታር (ኦሕዴድ) የመልካም አስተዳደር ማሻሻያ ዘርፍ አስተባባሪ፣ አቶ ደመቀ መኮንን (ብአዴን) የማኅበራዊ ዘርፍ አስተባባሪ፣ አቶ ቴዎድሮስ አድሃኖም (ሕወሓት) የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እና ሌሎችም ተሹመዋል፡፡ እዚህ ግን የመረጥኳቸው በጣም ስትራቴጂያዊ ሹመቶች ናቸው ያልኳቸውን ብቻ ነው፡፡

በአዲሱ ሹመት መሠረት የጠቅላይ ሚኒስትሩን ደኢሕዴን ጨምሮ ሁሉም የኢሕአዴግ አባል ፓርቲዎች በጠቅላይ እና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ማዕረግ በመሾማቸው ሁሉም ፓርቲዎች እኩል ውክልና ኖሯቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ኢሕአዴግ ከዚህ ቀደም ያልነበረው የሁሉም ፓርቲዎች ውክልና በአዎንታዊ መልኩ ሲታይ የቡድን አመራር ሊያመጣ የሚችል ቢመስልም፤ የዘርፎቹ አፈጣጠር እና የሌሎችም የሚኒስትሮች ሹመት ቀድሞ ቦታ ያጣ የመሰለውን "የኢሕአዴግ አለቃ" ሕወሓት መልሶ ወደላይ ያፈናጠጠው ሆኖ ተጠናቋል፡፡

በዚህ አሰላለፍ የመረጃ፣ ደኅንነት፣ ኢኮኖሚ እና ጦር ሰራዊቱ ጉዳይ በሕወሓት ቁጥጥር ስር ውሏል፡፡ ከሕገ-መንግሥቱ ተጻራሪ በሚመስል መልኩ ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ኃላፊነት ለአራት ተሸንሽኖ ሦስት አራተኛው ለምክትሎቹ ተሰጥቷል፡፡ ይህንን ዓይነቱ አሰላለፍ ብዙዎችን ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያምን ሥልጣናቸውን የነጠቀ ሹመት ሲሉት፤ በሌላ በኩል የኃይል ሚዛኑ ያረፈው ደኅንነትና መረጃ፣ ኢኮኖሚውንና ጦር ሰራዊቱን የሚቆጣጠረው ሕወሓት እጅ ላይ መሆኑ አሁንም ዞሮ፣ ዞሮ

## የቡድን አመራር

የቡድን አመራር የአንድን ግለሰብ የበላይነት ለማስወገድ ወይም በነጠላ የሚሠራ አገራዊ ስህተትን ለመቀነስ የተዘየደ የአመራር መንገድ ነው። የቡድን አመራር በቭላድሚር ሌኒን የተዋወቀ USSR ሶሻሊዝምን ለመምራት የቀረበ እና በስታሊን አማካይነት የተስፋፋ የአመራር ስትራቴጂ ነው። ይሁን እንጂ በቡድን ለመምራት በመወሰን ብቻ ስርዓትን ለመለወጥ እንደማይቻል በሚያሳብቅ ሁኔታ ስታሊን የራሱን ኃያልነት በሚያጠናክር (ማዕከል ባደረገ) ቡድን ጽንሰ ሐሳቡን አክሽፎታል። ከራሺያ በተሻለ ቻይናን በአንድዬ ‹‹ኮሚኒስት›› ፓርቲ የጠቀለሏት ማኦ ሴቱንግ ኅልፈተ ሕይወት በኋላ የተከተለው የቻይና የቡድን አመራር የእርሳቸውን ፖለቲካ በማስቀጠል እና አንጻራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በተከታታይ በማስመዘገብ ስኬታማ ሆኗል ማለት ይቻላል።

አሁንም ኢትዮጵያን በአንድዬው ‹‹አብዮታዊ ዴሞክራሲ - ግንባር›› የጠቀለሉት መለስ ኅልፈትን ተከትሎ የመጣው አመራር አንዱን የጠቅላይ ሚኒስትርነት ማዕረግ ለአራት ከፋፍሎ፣ ቀድሞ ምንም አይሠራም ቢባል ማጋነን የማይሆንበትን የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታን 75 በመቶ ሥራ ሰጥቶታል። ይህ በእርግጥ የቡድን አመራር ይባላል? እውን ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም በተረፈቻቸው ሩብ ሥልጣን አገሪቷን በራስ መተማመን መምራት ይችላሉ?

አዳዲሶቹ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ሥራቸውን ተከፋፍለው ከመሠማራታቸው በፊት ብዙዎች ዶ/ር ደብረጽዮን ለብቻቸው ኢኮኖሚውን እና ከመረጃ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በበላይነት እንዲመሩ መሾማቸውን በማስታወስ ሥልጣናቸው በተዘዋዋሪ በኃይለማርያም ላይ ሳይቀር የበላይ እንደሚያደርጋቸው ከመናገርም በላይ፣ እንዲያውም ከሁለት ዓመት በኋላ የሚመጣውን ምርጫ ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስትር ሊሆኑ የሚችሉት እሳቸው መሆናቸውን አመላካች ነው እያሉ መከራከር ጀምረዋል - እግረ መንገዳቸውንም ሹመቱ የቡድን አመራር ሳይሆን አንድ ሰውን ማዕከል እንዳደረገ በመጠቆም፡፡ ስለዚህ እየመጣ ያለው የቡድን ሳይሆን የሌላ ግለሰብ አመራር ነው ቢባል ይቀላል፡፡

# የቀይ ለባሾቹ ውሎና አዳር

ወጣቷ ዓለምን የቀን አጋጣሚ ስድስት ኪሎ አካባቢ፣ በዕለተ እሁድ (መጋቢት 8/2005) አንቀዥቅዥ አመጣት፡፡ በዕለቱ የለበሰችው የአዘቦት ቀይ ቲ-ሸርት በፖሊስ ቁጥጥር ስር ለመዋል ምክንያት ይሆነኛል ብላ አልተገመተችም ነበር፡፡ በሰዓቱ የባለራዕይ ወጣቶች ማኅበር እና የሰማያዊ ፓርቲ አባላት የኢትዮጵያውያን ጠላት የነበረው የፋሺስት ጣሊያን ጄኔራል ግራዚያኒን ኃውልት (በጣሊያን አገር፣ የትውልድ መንደሩ አካባቢ) መቆም በመቃወም የሰልፍ ጉዞ ከስድስት ኪሎ (የካቲት 12 ሰማዕታት መታሰቢያ ኀውልት) እስከ ጣሊያን ኤምባሲ ድረስ ለማድረግ እየተንቀሳቀሱ ነበር፡፡ የሰልፉ ተሳታፊዎች ከጀርባው ላይ ‹‹ለግራዚያኒ ኀውልት ማሠራት አባቶቻችን የከፈሉትን መስዋዕትነት ማራከስ ነው›› የሚል ጽሑፍ የታተመበት ቀይ ቲ-ሸርት ለብሰው ነበር፡፡ የኢሕአዴግ ካድሬዎች ደግሞ ‹‹ይቺ ባቁላ…›› በሚል ምክንያት ነው መሰለኝ ‹‹የተቃውሞ ሰልፍ…›› የሚባለውን ነገር ለማስቆም ራሱ ግብግብ ፈጥሮ፣ ራሱ ቀይ ለባሾቹን ማፈስ ሲጀምር ዓለምንም አብሮ አፍሶ አጋዛት፡፡



በተመሳሳይ ሰዓት ለሥራ ጉዳይ ጓዙን ጠቅልሎ ወደአፋር ለመጓዝ እየጠበቁት ያሉ ባልደረቦቹን ለማግኘት በታክሲ ውስጥ ይጓዝ የነበረ አንድ ሰው ከስድስት ኪሎ ተነስቶ አምስት ኪሎ እስኪደርስ የተመለከተውን ሁካታ ዓይቶ ላለማለፍ ከታክሲ ይወርዳል፡፡ ፖሊሶች ከሰልፈኞቹ ውስጥ አሳደው የያዙትን እያፈሱ መኪና ውስጥ ሲያጉሩ፣ ከፖሊሶች ዕይታ እየተሰወረ በሞባይሉ ፎቶ ለማንሳት ሲሞክር፣ አንድም የረባ ፎቶ ሳያነሳ በሦስተኛው ፎቶ ላይ ከፖሊሶች ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጠመ፡፡ እሱም ተይዞ ተከተላቸው፡፡ ይህ ድንገተኛ እስረኛ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ሆነ፡፡

የታፈሱት ሰልፈኞች ሁሉ የታጎሩት በአራዳ ፖሊስ መምሪያ ጊቢ ውስጥ ነበር፡፡ ጊቢው ውስጥ እንደደረስኩ ከፊት ለፊቴ ደረጃው ላይ የተኮለኮሉትን ሰልፈኞች ተመለከትኩ፡፡ ወጣቶቹ ታፍሰው የገቡ ሳይሆን ወደው የተሰበሰቡ ይመስሉ ነበር፡፡ እንዲያውም በገባሁ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ጮክ ብለው ይዘፍኑ ጀመር፦

‹‹… ተከብረሽ የኖርሽው ባባቶቻችን ደም፣ ባባቶቻችን ደም
እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም…››

በዚህ ጊዜ ከፖሊሶቹ አንዱ አብሮ ሲዘምር ይታይ ነበር፡፡ ፖሊሶቹ የተሻለ ትሁቶች ቢሆኑም፣ ሲቪል ለባሾቹ ግን ማመናጨቅ እና ማዋከብ ዋነኛ ሥራቸው ነበር፡፡ እኔን በመኪና ይዘውኝ ከመጡት ውስጥ አንዱ ‹‹ዴሞክራሲ በዛ…›› የሚለውን ቃል እየደጋገመ በቁጭት ይናገራል፡፡ ብዙዎቹ የመምሪያው ፖሊሶች ከየት እንደመጣ የማያውቁት ኮማንደር ግን የተቆጨው በመዘግየቱ ነው፤ ‹‹ይሄን ያክል እስኪሰባሰቡ መቆየት አልነበረብንም›› አለ - እኔው ጎን ቁጭ ብለው ሲነጋገሩ፡፡ በሬዲዮናቸው ሲለዋወጡ ከነበረው ውስጥም ‹‹ሱማሌ ተራ የተጎዳውን ሰውዬ የት ወሰዳችሁት?… ተክለሃይማኖት ሆስፒታል?…›› ይባባሉ ነበር፡፡ በዚሁ ጉዳይ ይሁን አይሁን ግን ‹‹መረጃም (ማስረጃም)›› አልነበረኝም፡፡

ጊቢው ውስጥ ከሌሎቹ እንዳልቀላቀልና ብቻዬን እንድቆይ አድርገውኛል፡፡ ባንድ በኩል ስልኬ ላይ ያሉትን ፎቶዎች አጥፍተው ይፈቱኛል፣ ጉዞዬም ይቀጥላል በሚል ደስ ብሎኛል፡፡ በሌላ በኩል በዓይን የማውቃቸውን እነዚያን ልጆች ቀረብ ብዬ አለማነጋገሬ ቆጭቶኛል፡፡ በዚህ መሐል ግን ሁሉም እየሄዱ ቃል ሲሰጡ ቆዩ (ቃል ሲባል ቃል እንዳይመስላችሁ፤ ከስም አንስቶ የኔ የምትሉትን ነገር በሙሉ ይጠይቋችኋል)፤ ከዚያም የኔም ተራ ደረሰና ቃል ሰጥቼ ሳበቃ እኔም በቀላሉ እንደማልሰናበት ሲያረዱኝ የጓዝ ኮተቴን ሁሉ አስመዝግቤ እዚያው ተጠቃለልኩ፡፡

ከዚያም ቃል የመስጠቱ ሥነ ስርዓት ቀጠለ፤ የመጣው ሁሉ በራሱ መንገድ ያንኑ ጥያቄ መልሶ፣ መላልሶ እያንዳንዱን ታሳሪ (ተጠርጣሪ ልበል ይሆን?) ይጠይቃል፤ እያንዳንዱም ተጠርጣሪ ይመልሳል፡፡ ሆኖም ብዙዎቹን መርማሪዎች የብስጭት መንስኤ የሚሆን ነገር ባለራዕዮቹ ወጣቶች ሳይናገሩ አይወጡም ነበር፡፡ ብሔር ሲባሉ

‹‹ኢትዮጵያዊ›› ይላሉ። ይህንን የሚሉት ‹‹ብሔር›› የሚለው ቃል ከግዕዝ የተወሰደ ሲሆን፣ ትርጉሙም ‹‹አገር›› መሆኑን እያጣቀሱ ነው። ታዲያ ይህ አባባል ለመርማሪዎቹ የሚያበሳጭ ድፍረት ነበር።

ፖሊሶቹ የሆነችውን ሁሉ እየደወሉ፣ ለአለቆቻቸው ይናገራሉ። ከዚህ መሐል ከሰልፈኞቹ አንዱ ለብሶት የነበረው ባንዲራ ላይ በእስክርቢቶ የጻፈውን ደብዳቤ ከስልኩ ወዲያ ላለ ሰው በንባብ ሲያጽፉት ሰምቻለሁ። ጽሑፉ ባብዛኛው መንፈሳዊ ነው ቢባል ይቀላል። ‹‹ለእመቤታችን በአስራትነት የተሰጠችው አገራችን ኢትዮጵያ…›› ብሎ ነው የሚጀምረው።

ምርመራው/ጥያቄው ቀጥሏል፤ ከጠያቂዎቹ መካከል የደኅንነት እና የኢንሳ ሰዎችም ነበሩበት። ከጥያቄዎቻቸውም ውስጥ የኢሜይል አድራሻ እና የይለፍ ቃል፣ የፌስቡክ አድራሻ እና የይለፍ ቃልም ይጠይቁ ነበር። እያንዳንዱ ታሳሪ (ተጠርጣሪ አልልም) ስሙን በቪድዮ ካሜራ ፊት እንዲናገር ይገደድ ነበር። እንግዲህ ይህንኛው መጀመሪያ ላይ እያንዳንዱ ሰው ከተነሳው ፎቶ በተጨማሪ መሆኑ ነው። በዚህ የጅምላ እስር ውስጥ ካስተዋልኳቸው ጉዳዮች ውስጥ የሴቶቻችንን ጀግንነት ነበር። ለምሳሌ፣ እኔ ያለምንም ማንገራገር ምስሌን አስቀርጬ ወደቃለመጠይቁ ሳልፍ የሰማያዊ ፓርቲዋ አመራር አባል ሐና ዋለልኝ ‹‹አልቀረጽም፣ አሻፈረኝ›› ብላ ስትሟገት ድምፅዋ ይሰማኝ ነበር።

ሲመሽ ይፈቱን ይሆን? እዚሁ ያሳድሩን ይሆን? ሌላ ቦታ ይወስዱን ይሆን? ምን ብለው ይከሱን ይሆን? እየተባባልን የተሰባሰብንባት አንዲት በረንዳ መሳይ ክፍል ውስጥ፣ ኢቴቪ በቀጥታ የሚያስተላልፋቸውን የአዳማ እና የመቐለ የኦሕዴድ እና የሕወሓት ስብሰባዎች መኮምኮም ጀመርን። አሳሪዎቻችንም በስልክ አለቆቻቸውን እያነጋገሩ ሽር ጉዳቸውን አጧጡፈውታል። ኢቴቪም ብቻውን በዓሉን ማክበር አልቻለም። መብራቱ ብልጭ ድርግም አበዛ። ብልጭ ድርግም አልኩ እንጂ ያበዛውስ ድርግም ማለት ነው፤ አልፎ፣ አልፎ ግን ላፍታ ብልጭ እያለ ነበር። በጨለማው ውስጥ ራታችንን በጨለማ ተቋደስን። ሁላችንም ምሳ ያልበላን ቢሆንም አንዳንዶች ግን ቁርሳቸውንም አልበሉም።

የመታሰራችን ዜና በማኅበራዊ አውታሮች በመጠኑ ቢስተገባም የብዙዎቻችን ቤተሰቦች ግን አልሰሙም፤ ደውሎ የማሳወቅ ዕድሉም አልተሰጠንም። እዚያው ጨለማ ውስጥ ከቆየን በኋላ ወደ 3፡00 ሰዓት ገደማ ወደ ጃንሜዳ አካባቢ የሚገኝ ማረሚያ (እስር ቤት) በሁለት ዙር ተወሰድን ከ30 በላይ እስረኞች አንድ ላስቲክ ብቻ ወለሉ ላይ የተነጠፈበት ክፍል ውስጥ ብንታጎርም በእርስ በርሳችን ጫወታ ተጠምደን ነበር። (በነገራችን ላይ እኛ ወደዚህ እስር ቤት ስንዛወር ቀይ ለባሽዋ ዓለም ተለቅቃ ወደቤቷ ሄዳለች።) የሄድንበት በሰልፉ ዋዜማ ሲቀሰቅሱ ከታሰሩ ሌሎች ጋር ተቀላቅለናል። የጅምላ እስሩ ጉዳይ በዋዜማው እንደተጀመረ ያወቅኩትም ያኔ ነው። ቀድመው ከታሰሩት ውስጥ ሁለቱ ክፉኛ ቡጢ እና ካልቾ ቀምሰው እንደሆነ ለማወቅ እስኪናገሩ መጠበቅ አያስፈልገንም ነበር፤ የአንደኛው ጃኬት የደረቀ ደም ከፊትለፊት ይታይበታል።

ለአምስት ሰዓት ዐሥራ አምስት ደቂቃዎች ሲቀሩት ግን እንደገና እንድንንቀሳቀስ ተነገረን። ከኛ ቀደም ብለው ሴቶቹም ወደቀጨኔ (ችሎት መድኃኔዓለም ኮንዶሚኒዬም አጠገብ ያለ) ወረዳ 9 ማረሚያ ቤት እንደተወሰዱ እና ከኛም ውስጥ 12ቶቻችን መከተል እንዳለብን ተነገረን። እዚያ እንደደረስን ግን ምነው እዚያው በቀረን የሚያስብል ትዕይንት ገጠመን። እያንዳንዱ ክፍል እላይ በላይ ተደራርበው በተኙ እስረኞች ተጨናንቋል። ሌላው ቀርቶ ጫማ ማስቀመጫ ቦታ እንኳን በክፍሉ ውስጥ ስለሌለ ጫማዎቻችንን ውጪ እያስቀመጥን እንድንገባ ተገደድን። ሦስቱ (አራት ሜትር በአራት ሜትር የሚገመቱ) ክፍሎች ውስጥ አንዱ 37፣ አንዱ 34 እና ሌላኛው ውስጥ 30 እስረኞችን ይዟል።

እንዳጋጣሚ 30 ሰዎች የያዘው ውስጥ ነበር እኔ የደረሰኝ። የኛ ክፍል ይሻላል ተብሎ ዶ/ር ያዕቆብንም አመጧቸው። ጉዳዩ በጣም አሳዛኝ ነበር። እኛስ ባልደከመ ጉልበታችን እንችለዋለን፤ ለርሳቸው ግን በጣም ፈታኝ እንደሚሆን መገመት ቀላል ነው። ክፍሉ በጣም ጥቅጥቅ ብሎ ከመሞላቱ የተነሳ ለኛ ቦታ ለማግኘት የቤቱ ካቦ ተነስቶ እያንዳንዱን እስረኛ እየቀሰቀሰ ማጠጋጋት ነበረበት። በቦታ ጥበት ምክንያት ደረቁ ወለል ላይ በአንድ ጎናችን እንድንተኛ ከመገደዳችን የተነሳ እኔ ይህን ጽሑፍ እስከምጽፍበት ሰዓት ድረስ ቁርቋሬው የፈጠረው ሕመም ጎኔን አያስነካኝም። ካቦው አጠጋግቶልን ሲጨርስ ሁላችንንም የገቢ ገንዘብ ተቀበለን እና ተኛን። እዚያ ክፍል ውስጥ መተኛት ማለት፣ መተኛት ማለት አይደለም። የክፍሉ መታፈን እና አስቀያሚ ጠረን፣ሙቀት፣ በዚያ ላይ እየተቀባበሉ የሚያጨሱት ሲጃራ ጢስ፣ ከዚያ እና ከዚህ የሚተኮስ የፈስ ሽታ… ብቻ የአበሳ ናሙና ነበር። ሌሊቱን ሲዘንብ ማደሩ ግን በከፊልም ቢሆን የክፍሉን አየር አቀዝቅዞታል፤ ችግሩ ዝናቡ ውጪ ያስቀመጥነው ጫማ ውስጥ ውኃ መሙላቱ ብቻ ነበር።

እንደምንም ነጋልንና ወደፍርድ ቤት እንደምንሄድ ተነግሮን ጥንድ ጥንድ እየተደረግ በካቴና ተቆላለፍን፡፡ ከመሐከላችን አንዱ የማኅበሩ አባል፣ ፀጉሩን አጎፍሮ ስለነበር (ለፍርድ ቤቱ ውበት አይመጥንም ብለው ይሆናል) ይቆረጥ አሉና መቀስ አንስተው ይከመክሙት ጀመር፡፡ ፀጉሩን ቆርጠው ሲጨርሱ አሰለፉንና ካቴናችንን ፈቱት፡፡ ‹‹ፍርድ ቤት መወሰዳችሁ ቀርቷል፣ ምናልባት ፖሊስ ጉዳዩን ይፈታዋል›› ተባልንና ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወደጃንሜዳ ማረሚያ ቤት መልሰው ወሰዱን፡፡ እዚያ ስንደርስ ለፖሊስ ዋስ እያቀረብን እንድንፈታ ተፈቀደልን፡፡ ቀድሞውንም የታሰርነው ያለወንጀል በመሆኑ አስገራሚ ውለታ አልነበረም፡፡

የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ የሚያስፈልገው ቅድመ ሁኔታ ለመስተዳድሩ ማሳወቅ ሲሆን፣ መስተዳድሩ ደግሞ በ48 ሰዓት ውስጥ ‹‹አይሆንም›› የሚል ደብዳቤ ካልጻፈ እንደተፈቀደ ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ ሰልፍ ማድረጉ ሕጋዊ ስህተት የለበትም፣ ጉዳዩ ባንድ ጀምበር የተወለደ ሳይሆን ጋዜጦች ዜና የሰሩለት፣ ቁጥቦቹ ሬድዮዎች ሳይቀሩ ያወሩለት ጉዳይ ስለሆነ ወንጀል ነው ፍርድ ቤት ሊያቀርቡት አይችሉም/አይገባቸውምም፡፡ ነገር ግን ‹‹…ካፈርኩ አይመልሰኝ…›› ይመስላል በዋስትና እንድንፈታ ፈቅደው ያገቱብንን ንብረቶቻችንን እየመለሱ መጋቢት 9/2005 እኩለ ቀን ላይ አሰናበቱን፡፡

# ኹለት ማስታወሻዎች ለኢሕአዴግ

በዋሲሁን አወቀ

***አንድ፡- ኢሕአዴግ ሆይ የምትናገረውን የምትተገብር ድርጅት ያድርግህ!!!***

***የፌደራሊዝም ነገር***

እነሆ ከጥቂት ወራት በኋላ 22ኛ የልደት በዓሉን የሚያከብረው ኢሕአዴግ በአባላቱ እና በሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠውን አስተያየትና ትችት ለመቀበል አሻፈረኝ እንዳለ የአንድ ወጣት ዕድሜ ሞላው። ኢሕአዴግ በተለያዩ ጊዜያትና አጋጣሚዎች የብሔር ብሔረሰቦችን መብት እንዳስከበረ፣ በብሄራዊ ድርጅቶች መካከል ፍትሐዊ የሥልጣን ክፍፍል እንዳደረገ እና በክልሎች መካከል ተመጣጣኝ የዕድገት ደረጃ እንዳለ ሲናገር ቆይቷል። ነገር ግን በተግባር ያለውና በኢሕአዴግ እየተነገረ ያለው አልገናኝ ብሎ ያስቸገረኝ እኔን ብቻ አይመስለኝም።የብሔር ብሔረሰቦች መብት ተከበረ ሲባል ሁሉም ብሔር በሔረሰቦችና ሕዝቦች በዕኩልነትና በመፈቃቀድ በጋራ የሚኖሩበት ሁኔታ ሲመቻች እና በሀገሪቱ ባለው አስተዳደራዊ መዋቅር ውስጥ እኩል ተሳታፊ መሆን ሲችሉ ነው። ይህ ግን ከንድፈ ሐሳብ ባለፈ ሲተገበር አላየሁም።

አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት አንድን መንግሥት እንደመንግሥት ፀንቶ እንዲቆይ ከሚያስችሉት ነገሮች መካከል የመንግስት ጠንካራ መዋቅር ዋነኛው ነው። ከነዚህም ውስጥ መከላከያ፣ ደኅንነት፣ ውጭ ጉዳይ ፣የጠቅላይ ሚኒስቴር/ፕሬዚዳንት ስልጣን (እንደየሀገራቱ የመንግሥት አወቃቀር ይወሰናል) ዋና ዋናዎቹ ናቸው።በኢሕአዴግ የስልጣን ዘመን እነዚህ አራቱ ክፍሎች ከአንድ ብሔር በተገኙ ግለሰቦች እጅ ለበርካታ ጊዜ የቆዩና አሁንም የቀጠሉ ናቸው። መከላከያን ለምሳሌ ብንወስድ እንኳዋን ከጠቅላይ ኢታማዦር ሹሙ ጀምሮ እስከታችኛው መዋቅር ያሉ አመራሮች በአብዛኛው ከአንድ ብሔር የተገኙ መሆናቸው አስፍኜዋለሁ ያለውን ዕኩልነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው። የደኅንነት ቢሮው እና ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መ/ቤቶችም ቢሆን በተመሳሳይ ሁኔታ መታማታቸው አልቀረም።እንደውም ሁለቱን ቦታዎች ከእነሱ ውጭ ለመያዝ የሚያስብ ውጉዝ ከመአርዮስ የተባለ ይመስል እንደ አባት ርስት እየተፈራረቁ በውርስ መልክ ይዘዋቸዋል። ጠ/ሚኒስቴርነቱም ቢሆን በሰው እንጅ በአሠራር እና በአስተሳሰብ ነጻነቱን አላወጀም ብየ አምናለሁ።

በኢኮኖሚ ጥቅምና በአጠቃላይ የእድገት ምጣኔ በክልሎች መካከልም ልዩነቶች ጎልተው ይታያሉ። የኢንዱስትሪ ስብጥሩን እንኳ እንደምሳሌ ብንወስድ ልዩነቱን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ለዚህ ልዩነት በኢሕአዴግ በኩል የሚሰጠው የማሳመኛ ምክንያት ደግሞ በክልሎች የመሠረተ ልማት አውታሮች በዕኩል ደረጃ ባለመስፋፋታቸው የኢንዱስትሪ ስብጥሩ እንዳይመጣጠን አድርጎታል የሚል ነው። ይህንን ልዩነት ማጥበብ ደግሞ 21 ዓመት ሲመራ የቆየው ኢሕአዴግ እንጅ የማንም ኃላፊነት አልነበረም።

ኢኮኖሚውም ቢሆን በኑሮ ውድነቱ መናርና በኢኮኖሚው ቅጥ ያጣ ጡዘት ሕዝቡ እየተማረረ ቢሆንም ኢሕአዴግ ግን ተከታታይ ዕድገት እያስመዘገብኩ ነው ይላል። ይህ አባባል ጉም እንደመጨበጥ የሆነባቸው አንዳንድ ሰዎች መንግሥትን ያሙታል። አንዳንድ አካላት መንግሥት ነጋዴ፣ ደላላ እና አረጋጊ ሆኖ ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ ዓይነት ሥራ እየሠራ ኢኮኖሚውን እያጦዘብን ነው ይላሉ። ምክንያት ብለው የሚያስቀምጡት ደግሞ ትእምት (EFFORT)ን በመሳሰሉ የንግድ ድርጅቶቹ ኢሕአዴግ /በተለይም ህወሓት/ በእጅ አዙር እየተጠቀመ በመሆኑ የኢኮኖሚውን መረጋጋት እና የኑሮ ውድነቱን መለዘብ አይፈልገውም ነው። እንደውም ትልቁ ደላላ መንግሥት እንጅ ሌሎቹ አይደሉም የሚል ማማረርም መስማት አዲስ አይደለም።

መቼም አንድ 21 ዓመት የሞላው ወጣት ምን ማድረግ እንዳለበት መካሪ የሚያስፈልገው አይመስለኝም። ኢሕአዴግ ግን እንደመንግስት ዕድሜ መቁጠር እንጅ መጎልመሱን እንድጠራጠር ስላደረገኝ የሚከተሉትን ምክሮች ለመለገስ ተነሳሁ

- የፌዴራል /የሚኒስቴሮች/ የሥልጣን ክፍፍል በዕኩልነት ላይ የተመሠረተ ይሁን። በተለይም ደግሞ 4ቱ
- ዋና ዋና ብዬ የጠቀስኳቸው ክፍሎችን በተመለከተ የተያዘው ጠቅላይነት ይቁም።
- የብሔር፣ ብሔረሰቦች መብት ይረጋገጥልን። ዕኩልነታችን በፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የጋራ ተጠቃሚነት
- መርሕ በተግባር ይታይ።

- የክልሎች ዕድገት በዕኩል ደረጃ የሚሄድበት ሁኔታ ይመቻችልን፡፡ የኢንዱስትሪ ስብጥሩና የመሠረተ ልማት አውታሮች ሽፋን በእኩል ደረጃ ይዳረስልን፤
- ሁሉም ብሔር፣ በሔረሰቦችና ሕዝቦች በሀገሪቱ ጉዳይ ላይ በዕኩልነት ላይ እንድንወስንና እንድንሳተፍ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አጋጣሚዎች ይመቻቹልን፡፡

ኢትዮጵያ የሁላችንም እንጅ የጥቂት ግለሰቦች ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎች ንብረት አይደለችም፡፡ ስለዚህ አሁን ስላለችው ብቻ ሳይሆን ስለወደፊቷ ኢትዮጵያም የሚያስቡ ዜጎችን ለመፍጠር ያስችል ዘንድ ኢሕአዴግ ጥርጊያውን ማስተካከል አለበት ብዬ አምናለሁ፡፡

## ሁለት፡- ከድርጅታዊ በዓል እና ከብሔራዊ በዓል የቱ ይበልጣል?

ኢትዮጵያ ሀገራችን የአኩሪ ታሪክ ባለቤት መሆኗን ማንም የሚመሰክረው ሐቅ ነው፡፡ ራሷን ለነጭ ቅኝ ገዥዎች ሳታስገዛ፣ ዳር ድንበሯን አስጠብቃ ኖራለች፡፡ ለዚህ ደግሞ የአያቶቻችን እና የአባቶቻችን ሚና ከፍተኛ ነበር፡፡ ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ ሚናቸውን የምንዘክርባቸው የተለያዩ በዓላት ቀበሌያዊና አካባቢያዊ በሆኑ በዓላት እየተተኩ አዲሱ ትውልድ እንዳይዘክራቸው እየተደረጉ ነው፡፡ ግንቦት 20፣ ህዳር 11፣ የካቲት 11……ወዘተ የመሳሰሉ የእርስ በእርስ ጦርነቶችን ውጤት የሚዘክሩ ሕዝባዊነት የሌላቸው በዓላት ከብሔራዊውና ሕዝባዊው የአድዋ በዓል በበለጠ መልኩ ሲከበሩ ማስተዋል ከጀመርን ይሄው 22 ዓመት ሊሆነን ነው፡፡

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በመርዝ፣ በእሳት፣ በጦር መሣሪያና በአካፋ በአሰቃቂ ሁኔታ በፋሺስት ኢጣሊያ የተጨፈጨፉበት ዕለት የሚዘከርበት የካቲት 12፤ ለእናት አገራቸው ዳር ድንበር መከበር እና ሉዓላዊተቷን ይዛ እንድትቀጥል ውድ ሕይወታቸውን የሰዉት ኢትዮጵያውያን የሚዘከሩበት የካቲት 23 በየትኛውም መስፈርት ብንለካው አሁን በመንግሥት (በኢሕአዴግ) ደረጃ ከሚከበሩት ግንቦት 20 እና መሰሎቹ አንጻር ያለው ሀገራዊ ፋይዳና ብሔራዊነቱ እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ (መቼም ወንድሙን የገደለና የአገር ወራሪ ጠላትን የገደለ በእኩልነት የሚመዘን ካለ አዕምሮው በትክክል ስለመሥራቱ እጠራጠራለሁ፡፡)

**ልዩነታቸውን ለማየት ያህል**

**አድዋ**

- ሕብረ ብሔራዊ በሆነ መልኩ የውጭ ወራሪ ጠላትን ለመመከት የተደረገ ታላቅ ተጋድሎ ነበር፤
- ዳር ድንበርን ለማስከበርና የኢትዮጵያውንን ነጻነት እንደተጠበቀ እንዲኖር ለማድረግ መስዕዋትነት የተከፈለበት ነበር፤
- የተረጋጋች እና አንድነቷን የጠበቀች ኢትዮጵያን ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲሁም የነጮችንበተንኮል የተሞላ የድንበር ማካለል ሥራ ለመግታት የተደረገ ጦርነት ነበር፤
- ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ እንድትታወቅ ያደረገ፣ በርካታ አውሮፓውያን ቆንስላዎቻቸውን በአዲስ አበባእንዲከፍቱ ያደረገ ነበር፤
- ለሀገርና ለሰንደቅ ዓላማ ሲሉ መስዕዋትነትን መክፈል፣ ለሆዳቸው ሳይሆን ለነጻነታቸው እንዲታገሉ፣ ኢትዮጵያ የጥቂቶች ሳትሆን የሁሉም መሆኗን በተግባር ያሳየ ነበር፡፡

**ግንቦት 20 ና መሰሎቹ**

- ወንድም በወንድሙ ላይ ጦርነት ያወጀበት፣ የኢትዮጵያውያንን ደም ያፋሰሰ የእርስ በእርስ ጦርነት ነው፤
- ዳር ድንበርን ለማስጠበቅ ሳይሆን ስልጣን ለመቆናጠጥ የተደረገ ታሪካዊ ስህተቶችን የፈጠረ እልቂትነው፡፡ (ምጽዋና አሰብን ከእጃችን ያስወጣ በመሆኑ)፤
- አንድነትንና መረጋጋትን ሳይሆን ሕዝብ በሕዝብ ላይ እንዲነሳ መስመር የከፈተ ነው፤
- 21 ዓመት ሙሉ የኢትዮጵያን ስራዊት (በደርግ ጊዜ የነበረውን) በጠላትነት የፈረጁ ሰዎች በአል ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ባለ ግንቦት 20ዎቹ ለኢትዮጵያዊነት ሳይሆን ለጎሰኝነት ያላቸውን አድልዖ ነው፡፡
- ታሪክን ማንቋሸሽ ዋነኛው ዓላማቸው አድርገው መነሳታው ሳያንስ ሌላውን በመውቀስ ራሳቸውን ለማክበር
- የሚጥሩ የምስኪኖች ስብስብ እንደሆኑ ይሰማኛል፡፡ አሁን ካለው ጋር ከመወዳድር ይልቅ ወደኋላ ተጉዘው ራሳቸውን ከጥንት ጋር በማወዳደር ለውጥ አመጣን ሊሉን ይፈልጋሉ፡፡ (በዲሞክራሲ፣ በትምህርት፣ በቴክኖሎጂ፣ በማኅበራዊ ዕድገት ወዘተ ጎረቤት አገሮች የደረሱበትን እየተመለከቱ እንኳ አያፍሩም!?)

## እንደማጠቃለያ

የአድዋ ድል ኢትዮጵያ ዳር ድንበሯን አስጠብቃ፣ ታፍራና ተከብራ እንድትቆይ ያደረገ ታላቅ ድል ነው፡፡ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ጥቁር ሕዝቦች ራሳቸውን ቀና አድርገው በኩራት እንዲሄዱና ለነጻነታቸው እንዲታገሉ ያስቻለ ነው፡፡

አሁን እየተሄደበት ያለው ታሪክን የማንቋሸሽ ተግባር በሕዝቦች መካከል ቅራኔን የሚፈጥር አንጅ ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ የሌለው አጉል ኪሳራ ስለሆነም ኢትዮጵያዊ ነን የምንል ትውልዶች በሙሉ ይህንን ስህተት ሲፈጸም እያየን ማለፍ፣ የአባቶቻችን ውርስ አይደለም፡፡ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም የአያቶቻችን እና የአባቶቻችን ሚና የሚያንሰራራበትን መንገድ መፈለግ አንዱ መፍትሄ ይመስለኛል፡፡ የካቲት 12 ፋሺስት ኢጣሊያ የጨፈጨፋቸው ሰማዕታት መታሰቢያ፣ የካቲት 23 የአድዋ ድል በዓል መታሰቢያ፣ ሚያዚያ 27 የአርበኞች መታሰቢያ በመሳሰሉ በዓላት ላይ በመገኘት ታሪካቸውን መዘከር የኛ ኃላፊነት መሆኑን ተገንዝበን በድምቀት የምናከብበትና ከጥቃቅን እና አነስተኛ በአላት አከባበር የምንወጣበት ጊዜ ሩቅ እንዳሆን እመኛለሁ፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን ከጨለመ መንጋቱ አይቀርም!

# “የተዘነጉት እስረኞች” እና የተዘነጋው የቤተሰቦቻቸው ስቃይ

ላለፉት አራት ዓመታት ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ቅዳሜ እና እሁድ የሄደ ሰው ወጣቷን ናርዶስን ሳያገኝ አይመለስም፡፡ ናርዶስ ገና የ20 ዓመት ወጣት እና በኪያሜድ የመጀመሪያ ዓመት የነርሲንግ ተማሪ ናት፡፡ ናርዶስ ዘሪሁን በየሳምንቱ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት የምትመላለሰው በ‹‹አሸባሪነት›› ‹በእነብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ መዝገብ› ከተከሰሱት 36 ሰዎች መካከል ዕድሜ ልክ የተፈረደባትን እናቷን ልትጎበኝ ነው፡፡ እነዚህ እስረኞች ሚያዝያ 16/2001 አመሻሹ 12 ሰዓት አካባቢ ነበር ሁሉም በያሉበት በቁጥጥር ስር የዋሉት፡፡ እኛም 4ኛ ዓመታቸውን ለማሰብ ተሰባስበን ወደቃሊቲ ማረሚያ ቤት በተለይ እማዋይሽ ዓለሙን ለመጠየቅ ሄደን ነበር፡፡ እንደተለመደው ናርዶስንም አገኘናት እና ብዙ ነገሮችን አጫወተችን፡፡

ናርዶስ ትረካዋን የጀመረችው እናቷን እና ሌሎችም በተመሳሳይ መዝገብ ተከሰው የተፈረደባቸውን ሰዎች አያያዝ ነበር፡፡ ‹‹ሳስበው የተረሱ ያህል እየተሰማኝ ነው፤ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ሚዲያዎች ስለነሱ አይደለም እያነሱ ያሉት፡፡ በእናቴ ክስ የታሰሩት ከ30 ሰዎች በላይ ናቸው፡፡ አንድ ሰሞን ከይቅርታ ጋር በተያያዘ ስማቸው እየተነሳ ነበር አሁን ግን ሁሉ ነገር የተረሳ ይመስለኛል›› በማለት የእስሩ ሕመም ለታሳሪዎቹ እና ለቤተሰቦቻቸው ግን የሚረሳ ዓይነት አለመሆኑን ነገረችን፡፡

‹‹ሚያዝያ 16፣ አርብ ቀን ነበር ሁሉም የተያዙት›› በማለት ሲታሰሩ የነበረውን ጠቅላላ ሁኔታ በማስታወስ ትጀምራለች፡፡ ‹‹ለአንድ ሰው የመጡ የማይመስሉ ብዙ ሲቪል የለበሱ እና የፌዴራል ፖሊስ ልብስ የለበሱ ፖሊሶች መሳሪያቸውን አቀባብለው ነበር ወደቤት የገቡት፡፡ ስልካችሁን አጥፉ ወደማንም እንዳትደውሉ አሉን፡፡ የብርበራ ማዘዣ ይዘው ነበር፤ ‹ቤት ልንፈትሽ ነው የመጣነው እማዋይሽ ዓለሙ በቁጥጥር ስር ውለሻል› አሏት ቤት ፍተሻው እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ድረስ ቀጥሏል፡፡ ቀኑ አርብ ነበር፤ እናቴ ደግሞ እስከ 12 ሰዓት ትጾም ስለነበር ከሥራ ወደቤት እንደገባች ‹ምግብ ስጡኝ› እያለች እያለ ነበር ፖሊሶች የገቡት ስለዚህ ምግብ ሳትበላ ውላ ነው ወደ እስር ቤት የወሰዷት፡፡ ከዚያ በኋላ አራት ወራት ያክል ዓይኗን አላየነውም ነበር፤ ትሙት ትኑር የምናውቀው ነገር አልነበረም፡፡ ደግነቱ በሌላ ጉዳይ ታስራ በተፈታች ሴት አማካይነት መልዕክት ደረሰኝ፡፡ ‹አንቺ ደህና ከሆንሽ ሽሮ እና ጎመን ሰርተሽ አስገቢልኝ፤ እኔ ደግሞ ደኅንነቴን የባናና ማስቲካ ወረቀት እልክልሻለሁ፡፡ ደኅና ካልሆንኩኝ ግን ያ ነገር ይቀራል› ብላ ላከችብኝ፡፡ ከዚያ እኔም ሽሮ እና ጎመን ሠርቼ በመላክ፣ እሷም የባናና ወረቀት በመላክ ደኅንነታችንን የሚገልፅ መልዕክት እንለዋወጥ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ እየሆነ ባለበት ሰዓት እኛ በሌለንበት ጉዳያቸው ፍርድቤት ይታይ ነበር፡፡›› በማለት ጉዳያቸው በኢፍትሐዊ መንገድ በመንግሥት እንደተያዘ አጫውታናለች፡፡

‹‹እናቴ ስዕል መሳል ትወዳለች፡፡ እናም በየጊዜው የጀመረቻቸው ስዕሎች የተበላሹ ሲመስሏት ቅርጫት ውስጥ ትጥላቸዋለች፡፡ ይመስለኛል፤ የቤት ሠራተኛችን እጅ አለበት፡፡ ስትታሰር የቀረበባት መረጃ እነዚህ የተጣሉ ወረቀቶች ተሰብስበው ‹የድርጅቱን አርማ ስታዘጋጅ ነው› የሚል ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ፈቃድ የነበረው፣ ያውም የማይሠራ ሽጉጥም እንዲሁ በማስረጃነት የቀረበባት መሆኑ ነው፡፡›› በማለት ለእርሷ ፍርዱ ፍትሐዊ አለመሆኑን እና እናቷም ነጻ መሆኗን እንደምታምን ነግራናለች፡፡

‹‹የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ ሲታሰሩ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የተላለፈው ዜና ነው፤ እንኳን አገር ወዳዷ እናቴ ማንም ባገሩ ላይ የሚያደርገውን ነገር ነው አደረጉ ያለው፤›› የዜናውን ፖለቲካዊ ወገንተኝነት ወቅሳለች፡፡ እናቷ ሕዝብና አገር የማሸበር ፍላጎት ሊኖራት ለአገር ፍቅር ሕይወቷን የሰጠች መሆኗን ስታጫውተን ‹‹እናቴ ሁልጊዜ የምትነግረኝ ነገር አለ፤ ሕይወቴ ማለፍ ካለበት አገሬን በሚጠቅም ነገር መሆን አለበት ትለኝ ነበር፤›› ብላናለች፡፡ ነገር ግን መንግሥት በአንድ በኩል ‹‹ሕገ መንግሥቱን ለመናድ በመሞከር ነው ያሰርኳችሁ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ እስረኞች የሉኝም ይላል፤›› ካለች በኋላ ‹‹ተቃዋሚ መባላቸው ካልቀረ የኢሕአዴግ መንግሥት የፖለቲካ እስረኞች እንደሆኑ ቢያምን እንኳ ጥሩ ነው፤›› ብላናለች፡፡ ‹‹እናቴ ለአገሯ ከማንም በላይ ሠርታለች ብዬ አምናለሁ፡፡ ነገር ግን አገራችን ለእናቴ ውለታዋን እየከፈለቻት ነው ብዬ አላምንም፡፡ ያለሃጢያታቸው ሃጢያት ተሰጥቷቸው ነው ያሉት›› በማለት ፍርዱ አገር ወዳድ እናቷን የሚያዋርድ እንደሆነ በሐዘን ተርካልናለች፡፡

የእናቷ በአሸባሪነት መፈረጅ ለናርዶስ ማኅበራዊ እና ስነልቦናዊ ቀውስ እያደረሰባት መሆኑንም አጫውታናለች፡፡ ‹‹ለትምህርቴ መስጠት የሚገባኝ ጊዜ ያህል መስጠት አልቻልኩም፤ እናቴ የታሰረችው እኔ ስምንተኛ ክፍል እያለሁ ነበር፡፡ ዩንቨርስቲ መግባት ሲኖርብኝ አሁን ግን ‹ነርሲንግ› እየተማርኩ ያለሁት በዚሁ ተፅዕኖ ነው፡፡

ሌላው ቀርቶ የእነርሱን የእስር ዜና ኢቲቪ ከአቀረበበት መንገድ አኳያ ትምህርት ቤት ውስጥ ራሱ እኔን መቅረብ የሚፈሩ ሰዎች አሉ፤› በማለት የእናቷ እስር በእርሷ ማኅበራዊ ሕይወቷ ላይ ያጠላበትን ጥላ አጫውታናለች፡፡

‹‹እስጢፋኖስ አካባቢ የሚገኘው እና በእናቴ ስም ተይዞ የነበረው የቀበሌ ቤታችን በልማት ስም ሲፈርስ እንኳን ለጎረቤቶቻችን በምትኩ ሲሰጣቸው ለእኛ ግን አልተሰጠንም፡፡ ሌላው ቀርቶ መታወቂያ እንኳን ለኛ ለመስጠት ፈቃደኞች አይደሉም›› ቤታቸውን ካፈረሱባቸው በኋላ አክስቷ ጋር እየኖረች እንደሆነ ስትነግረን በየመሐሉ እየገታችው ታወራልን የነበረው እምባዋ ከቁጥጥር ውጪ ሆኖ ሲወርድ ማድረግ የቻልነው ነገር ቢኖር በዝምታ ማጀብ ነበር፡፡

‹‹ያለአባት ያሳደገችኝን የእናቴን ፍቅሯን አልጠገብኩትም›› የምትለን ናርዶስ ‹‹በዚህ ዕድሜዬ ለኔ የሚገባኝ ቦታ ቃሊቲ አልነበረም፡፡›› በማለት ብዙ ነገር መሥራት በነበረባት ጊዜ ቃሊቲ በመመላለስ እንዲባክን መንግሥት እንደፈረደባት እንደሚሰማት ነግራናለች፡፡ ‹‹አራት ዓመቱን በአሰቃቂ ሁኔታ ነው ያሳለፍኩት፤ ከ16 ዓመታት በኋላ ከእስር የተፈታው አባቴ የራሱን ሁሉ ነገር ትቶ ሕይወቴን ለኔ መስዋዕት ባያደርግ ኖሮ አልወጣውም ነበር›› በማለት እንደዕድል እናቷ ከመታሰሯ ሁለት ወር ያክል ቀድሞ በተፈታው አባቷ ድጋፍ ከብዙ ቀውስ እንደተረፈች እየነገረችን ከናቷ ጋር የነበራትን ፍቅር ‹‹እናቴ ሁሉ ነገሬ ነች!›› ብላለች፡፡

‹‹እናቴን ሊጎዳ የሚያስብ ሰው እኔን አንድ ነገር ሊያደርግ ይችላል በሚል ተሳቅቄ ነው የምኖረው›› በማለት በዙሪያዋ ያለውን ወዳጅ እና ጠላት እንኳን ማመን እየቸገራት እሷ ራሷም ቢሆን ከማኅበረሰብ የመነጠል እና የመስጋት ስነልቦናዊ ችግር ውስጥ እንደሆነች አስረድታናለች፡፡

‹‹የርዕዮትዓለሙ እህት እስከዳር ዓለሙ ‹የቤታችን ሰላም እና ፍቅር ከርዕዮት ዓለሙ ጋር ታስሯል› ያለችው በጣም ትክክል ነው›› በማለት በታሰሩት ሰዎች ቁጥር እኩል የሚሆኑ ቤተሰቦች በከፍተኛ ፈተና ውስጥ እያለፉ መሆኑን አበክራ ነግራናለች፡፡

የናርዶስ ታሪክ የብቻዋ ታሪክ አይደለም፡፡ የሌሎች የብዙ ቤተሰቦቻቸው የታሰሩባቸው ቤተሰቦች ታሪክ ነው፡፡ ናርዶስም ‹‹እንደኔ ሁሉ ችግር ላይ ያሉ፣ አባቶቻቸው የታሰሩባቸው ብዙ ልጆች አሉ›› ብላናለች፡፡ በዚሁ መዝገብ ተከሰው የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው አቶ መላኩ ተፈራ ቤተሰቦችም ከሰኞ እስከ እሁድ ቃሊቲ ደጃፍ ላይ ከማይጠፉት ሰዎች ውስጥ ይመደባሉ፡፡ በሥራ ጉዳይ ከአገር ውጪ ያለችው ልጃቸው ፅዮንም አባቷን ለመጎብኘት ሲባል ቶሎ፣ ቶሎ እንድትመላለስ ተገድዳለች፡፡ እነጄኔራል ተፈራ ማሞ፣ እነአሳምነው ፅጌ እና ሌሎችም ደግሞ በእስረኞች መሐል ‹‹ተነስቷል በሚል ፀብ›› ሰበብ ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት ወደዝዋይ እንዲዛወሩ ተደርገዋል፡፡ ይህ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዳይገናኙ ሌላ ተጨማሪ ጫና አሳድሮባቸዋል ብላናለች፡፡ እዚህ የቀሩት ታሳሪዎችም አጋሮቻቸውን በማጣት ለብቸኝነት ስሜት ተዳርገዋል፡፡

ከነርሱ መዝገብ ውጪ ያሉ ሌሎችም እስረኞች እና ቤተሰቦቻቸው በተመሳሳይ ፈተና ውስጥ መሆናቸውን እስረኞችን ለመጎብኘት በሄድንባቸው ጊዜያት ተረድተናል፡፡ መንግሥት ለፖለቲካ ግብአቱ የይቅርታ ደብዳቤ ካስፈረማቸው በኋላ እንኳን ለመፍታት ፍላጎት አያሳይም፡፡ ይልቁንም፤ ከቦታ ቦታ እያዘዋወረ ስቃያቸውን ያበዛል፡፡ ለዚህ እንደምሳሌ ባለፈው አርብ (ሚያዝያ 11/2005) ወደዝዋይ እንዲዘዋወር የተደረገው ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ተጠቃሽ ነው፡፡ በእርሱ የጋዜጠኝነት ደሞዝ ላይ ጥገኛ የነበሩት ባለቤቱ እና ልጁ (ፍትሕ ውብሸት) በእናትዬው መፍጨርጨር ሕይወታቸውን እንዲመሩ ከመገደዳቸውም በላይ አሁን የቤቱን አባውራ ለመጠየቅ ዝዋይ ድረስ እንዲመላለሱ ተፈርዶባቸዋል፡፡ ለዚህም ነው መንግሥት የፖለቲካ አይደሉም የሚላቸውን የፖለቲካ እስረኞችን ከነቤተሰቦቻቸው ከሚቀጣበት መንገድ ይታረም ዘንድ ሊጠየቅ ይገባዋል በማለት የምንመክረው፡፡

# Development in Silence, Democracy's unbecoming!

**By Tewodros Yalew( Special for the campaign)**

## To Embrace Rights

At the heart of Civil and Political Rights rests the liberty and freedom of individuals. As opposed to the other rights deemed as economic, welfare or development; civil and political rights bestow the individual with the power or ability to design and mold his or her society as well as his or her life in the best acceptable manner as possible. In working towards this end, individuals living under the common umbrella of their state, become citizens with shared common goals and different interests. The first guarantee that can bring forth this kind of consensus building between citizens that work for their common destiny, among these can be cited prosperity and growth of the nation and its sovereignty, and galvanize their differentiated interests is the space of freedom and liberty. Within this space citizens can freely and unencumbered by the force of a single interest group, discuss dialogue and build consensus to formulate the best ideal means of sustaining their life within a particular state. When this space is stifled undemocratic governments silence every form of independent dialogue which they have not endorsed. The means of dialogue such as the right to assembly and association, freedom of expression, right to demonstration become impossible in a government that is decided upon mainstreaming the interest of a privileged group. Such privileged groups take different forms and shapes in different countries of the world, be it business elite, military, a minority, a religious sect, etc.

Freedom and liberty which are indispensable for a society that is bent upon the will of its citizens rather than the force of the powers that be to create commonly agreed upon principles of government, are as we know them today subscribed mainly in the UDHR and other international human right instruments and in most cases national constitutions that have adopted these universal moral codes. These human rights are meant to protect the individual from the undue interference of the government upon their liberty to pursue their life as they deem fit and work with their fellow citizens in their issues of common purpose.

## Revolutionary or Armored Democracy?

The EPRDF that has been at the throne of government in Ethiopia for the past twenty one years has so much to prove for all that ask, is its hold on power supported by the people? Civil and political rights provide diverse ways of test for governments that boldly claim to be democratic. Major among these tests are freedom of expression, freedom of assembly, freedom of association, right to demonstration and petition. In all situations of patronage the free exercise of these rights can easily expose the true character of these veiled democracies. Undemocratic governments are comfortable when citizens are only concerned with their economic well being but get tempered when they want to be part of the decision making process and push for this by claiming their right to be the sole residuals of power as opposed to being mere patrons.

EPRDF's score in these tests has repeatedly been a failure. Experience has shown their impatience for rights and their actions have unveiled their true colors of armored democracy.

EPRDF has been the smoking gun of response for demonstrations on academic independence by students (thirty one people have died following student demonstrations on April 10, 2001) or even public demonstrations for free election (more than two hundred people have been shot dead by government security forces following public demonstration after the May 2005 elections). Twenty one journalists languish in prison for marching a legion of words and ideas against oppression, corruption and silence but this has unfortunately disturbed EPRDF's peaceful abode of suppressed democracy.

An Ethiopian scholar Dr. Dagnachew Assefa has once said that EPRDF measures its success by its achievements of good governance than its score on democracy. Good governance here refers to the provision of services than the restraint by the government of its undue and illegal interference upon the liberty of citizens. But, the scholar adds that when it comes to this patronage-client relationship between the government and the governed, Hitler's German was no less efficient than its counterparts in Europe at the time. The late Prime Minister Meles Zenawi has been the leading orchestrator of this approach of government where development supersedes any other task by the state wherein citizens sit at the receiving end of the system completely disempowered and at worst suppressed by their leaders. These words by the late prime minister in May 2012 at the World Economic Forum starkly represent EPRDF's stance on the issue of democracy, "I don't believe in bedtime stories, contrived arguments linking economic growth with democracy".

If such is EPRDF's stance on democracy, it finds its solace in the Chinese, Singapore and other similar countries that are convinced of the precedence of economic growth before democracy. Indeed these countries have succeeded in building huge economies but their stability is superfluous gained through suppressing the freedom of their citizens. Perhaps the 1989 Tiananmen Square massacre in China where more than two thousand people were gunned down for holding pro democracy demonstration epitomizes the economic growth- anti democracy model aversion for people power. EPRDF has for long tried to emulate the Chinese model of governance by trying to silence every dissent. But the Ethiopian polity is devoid of any such parallel as relative ethnic homogeneity, the Asian values or other cultural maxim that can be used by the power elites to come up with a national consolidation scheme which is indispensable to resolve differences either by simply writing them off or setting them aside. If the Chinese or Singaporean people have formed a consensus either through suppression or persuasion, EPRDF seems to have completely ignored the implications of striding for development without consolidating its power among Ethiopians. It seems it has depended on its sheer violence and armor to silence every voice of concern by the people except its own agenda.

Ethiopia is a diverse country home to different interests bent on their language, religion, ethnicity, political outlook, etc. Perhaps none other than EPRDF is well adept in reading the lines of difference in the Ethiopian polity and capitalizing on them. But once it took control of power, it has decided to make itself the single most supra entity in the Ethiopian politics representing every interest within the society. But nothing other than power greed leads to such erroneous calculation. For one, besides the total theoretical or practical impossibility of one group representing every other group, EPRDF's party structure is incompatible with its desire. Formed out of strict ethnic identity the EPRDF's building block party's can only claim allegiance to their

ethnic group they claim to represent. By trying to silence every other voice and locking the political space within its own agenda of sustaining power, EPRDF is pushing other legitimate groups of interest in the country towards the cliff. The HPR of Ethiopia represents EPRDF's single most mockery of plural democracy whereby it claims 99.6 percent of the sit. In practice the government is being run by a single powerful group that completely resides over the legislature, the executive, and the judiciary. But it does not stop here. The government is also in control of the media by incessantly wiping out newspapers and magazines and sending their journalists to the dungeon.

If the space of civil and political rights is not opened for all, Ethiopia finds itself in the difficult position of risking instability. The existing power in government has already gave birth to strong blocks of interest political as well as economic. Ethiopians face economic inequality and a staggering speed of inflation where the few stash the cash that has been the cause of skyrocketing prices of commodities while the majority simply looks while their hands cannot reach even their most basic needs. Millions of hectares of their land are being tilled by foreigners and the seeds of their land exported flying in the face of their poverty. These and other issues are not allowed to be discussed or, if needs be demonstrated against, simply because the government does not want to hear from the citizens. If the government is deaf to its own people perhaps their mentors have a piece of advice: Gao Xiqing of the China Investment Forum, warned Meles: "Do not necessarily do what we did". Policies of "sheer economic growth" should be avoided, he said. "We now suffer pollution and an unequal distribution of wealth and opportunities… You have a clean sheet of paper here. Try to write something beautiful." Yes try to write something beautiful and let the people author their future. Let universal rights of assembly, demonstration, expression, be our common guarantee against tyranny and oppression. Not armory bur the power of the people can defend the country from uncompromising interests that threaten our stable future.

I would like to finish by reciting what a former revolutionary against both the feudal regime and the Derg, Hiwot Teffera had wittingly reminisced in her book Tower in the Sky,

*"On April 23, 1974, a little over two months after the revolution had erupted, Endalkachew's government (Endalkachew Mekonen was the then prime minister), declared that the party was over. It prohibited demonstrations and strikes. Some ministers and high ranking officials of the previous government were thrown into jail accused of corruption and mismanagement. The government was not unified and had no full control over the military. That was its undoing".*

Yes governments impatient with people's power and dissent has pushed the people and drove them underground and some to the guerilla but the end of it all was a disaster where everyone claimed to be the sole owner of the truth and disregarded the wisdom in the people to best know their interest.

# ኢሕአዴግ ሥልጣኑን በምርጫ ይለቃል?

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በመፈንቅለ መንግሥት ወረዱ፣ ደርግ በትጥቅ ትግል ወረደ፣ ኢሕአዴግ እስካሁን አልወረደም፤ እንደአያያዙም ሆነ እንደአነጋገሩ በቅርቡ የሚወርድ አይመስልም፡፡ ኢሕአዴግም ቢሆን ግን መውረዱ አይቀርም ጥያቄው ‹‹አልወርድም›› የሚያስብለው ምክንያት አለው ወይ እና ታዲያ እንዴት ይወርዳል የሚለው ነው፡፡ እዚህጋ ‹‹መውረዱ ለምን አስፈለገ?›› የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በርካታ ሕዝባዊ ብሶቶች፣ እያሽቆለቆለ የመጣ መልካም አስተዳደር፣ ዴሞክራሲ እና ሰብአዊ መብት አያያዝ እና ሌሎችም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሲዘረዘሩ በመክረማቸው እና ማንም ለነዚህ እንግዳ ስለማይሆን ለጊዜው እሱን መዝለል ይኖርብኛል፡፡ አንድ ነገር አለ፤ ኢትዮጵያ ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር (በተለይ የምርጫ) ማየት አለባት - ነገር ግን እስካሁን አላየችም፣ ስለዚህ ከአሁን በኋላስ ታያለች ወይ ብለን መጠየቃችን የግድ ይሆናል፡፡

ኢሕአዴግ በ‹‹ዴሞክራሲያዊ›› ስርዓት እየተመራ፣ ምርጫ በየአምስት ዓመቱ እያካሄደ እንዴት ከሥልጣን አልወረደም ለሚለው ጥያቄ ቅንጥብጣቢ የመልስ መዋጮ በማድረጉ ረገድ የተቃዋሚዎች ድክመት እና የሕዝቡ በፕሮፓጋንዳ መታጠብ ሊጠቀሱ ይችላሉ፤ ነገር ግን በዋነኝነት የኢሕአዴግ ከሥልጣን ለመልቀቅ አለመፈለግ ቢጠቀስ ስህተት አይሆንም፤ ኢሕአዴግ ወይም አባላቱ ሥልጣን በዴሞክራሲያዊ መንገድ በቅርቡ ለማስረከብ ፈቃደኛ የሚሆን አይመስለኝም የምልባቸውን ማስረጃዎች ወደታች እዘረዝራቸዋለሁ፡፡

ኢሕአዴግ ብዙ ከሕገመንግሥቱ ጋር የሚፃረሩ በሚል የተወቀሱም፣ ባይፃረሩም ከስርዓት ማስከበር ይልቅ ቁጥጥርን ግብ ያደረጉ አዋጆችን አፅድቋል፡፡ ባለሥልጣናቱ እስከ 40 ዓመት ኢሕአዴግ ሊቆይ እንደሚፈልግ ተናግረዋል፡፡ እነዚህ ምልክቶች ኢሕአዴግ አገሪቱን በሥርዓት ለመምራት፣ ወይም መስመር አስይዞ ሥልጣን ለመልቀቅ ፍላጎት ስላለው የሚያደርጋቸው እንደሆኑ ደጋፊዎቹ በእርግጠኝነት ይናገራሉ፡፡ ኢሕአዴግ ጠንክረው የሚቃወሙትን ሁሉ አገር ለማፍረስ ዕቅድ እንዳላቸው በጥርጣሬ ይናገራል፤ እነዚህን ምክንያቶችም ሥልጣኑን ለመስጠት ፈቃደኛ የማይሆንባቸው ቁም ነገሮች አድርጎ ሲያቀርብም አጋጥሞናል፡፡ ነገሩ ግን በነዚህ ምክንያቶች ብቻ የማይወሰን ነው፡፡ ኢሕአዴግ ሥልጣኑን ለመልቀቅ ቢፈልግ እንኳን የሚከተሉት ጉዳዮች ይፈታተኑታል፡፡

1. **የኢኮኖሚ ኢምፓየሩን ጉዳይ ለማን ይተው?**

   ይህንን ጉዳይ ኢሕአዴግ ራሱ እንደሚያምንበት በማተት ነው የምንጀምረው፡፡ ፓርቲው አምና የመንግሥት ባለሥልጣናትን በመከረበት ዶሴው ላይ ‹‹የፖለቲካ ኢኮኖሚ ኪራይ ሰብሳቢነት›› በሚል የሰየመው የፖለቲካ ስልጣናቸውን መከታ በማድረግ በከፍተኛ ሙስና በተርመጠመጠ አሠራር የትላልቅ ንብረት እና ንግድ አስተዳዳሪ የሆኑ አባሎቹን ድርጊት ነው፡፡

   የኢሕአዴግ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ምንጩ ያልታወቀ ከፍተኛ ሀብት ባለቤቶች ናቸው፡፡ ሀብታቸውን አፍርተው ከጨረሱ በኋላ እንኳን የመጣው የሀብት ማስመዝገብ አዋጅ ተግባር ስኬታማ ሆኖ እንደተነገረን በሁለት ወራት ውስጥ የባለሥልጣናቱ ሀብት ለሕዝብ ይፋ ያልሆነው ይህንኑ ምስጢር ለመደበቅ እንደሆነ መገመት አይከብድም፡፡ ስለዚህ ይህንን የአባላቱን የኢኮኖሚ ኢምፓየር ወይም በውስጥ ቋንቋቸው ‹‹የፖለቲካ ኢኮኖሚ ኪራይ ሰብሳቢነት›› ጣጣ ላለመጋፈጥ ሲባል ተፅዕኖ ፈጣሪ አባላቱ ፓርቲው ሥልጣን ሲለቅ ዝም ብለው አያዩትም (በቀላሉ እንዲለቅ ላይፈቅዱለት ይችላሉ)፡፡
2. **ቦታውን የማይመጥኑ ሹመኞች ዕጣ ፈንታ**

   ኢሕአዴግ ሹመት ለመስጠት የፖለቲካ ታማኝነትን እንጂ አካዳሚያዊ ብቃትን እንደማያስቀድም ደጋግሞ መናገሩ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ እነዚህ ከወረዳ ሊቀመንበርነት እስከ ሚኒስትርነት ማዕረግ የተሰጣቸው ቦታውን የማይመጥኑ የፖለቲካ ታማኞች፣ የማይመጥናቸውን ማዕረግና ክብር ለማስቀጠል ኢሕአዴግን በሥልጣን ማስቀጠሉ የማይደራደሩለት ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም ደግሞ የማዕረጋቸውና ጥቅማ ጥቅሞቻቸው ቀጣይነት ዋስትና የሚኖረው በፓርቲው የገዢነት ቀጣይነት ላይ ነው፡፡ ይህም የኢሕአዴግ ፖሊሲ ፓርቲው በምርጫ ከተሸነፈ እንዲወርድ በወረቀት ላይ ቢፈቅድም እንኳን እያንዳንዱ ሹመኛ አቅሙ በሚፈቅደውና መቆጣጠር ወይም መምራት በሚችለው ልክ ኢሕአዴግ በሕጋዊም ሆነ በሕገወጥ መንገድ ሥልጣን ላይ እንዲቆይ የማይፈነቅለው ድንጋይ አይኖርም፡፡
3. **በሥልጣን ሽፋን የተሠሩ ወንጀሎች ዕዳ**

ይሄንኛው ከሁለቱ ምክንያቶች ጋር በተዘዋዋሪም ቢሆን ይገናኛል፤ ወንጀሎቹ ለሹመት እና ለኤኮኖሚ ሳይሆን እንዲሁ በትምክህተኝነት የተሠሩ እና ምናልባትም ደግሞ ሹመቱን እና ኢኮኖሚውን ለማምጣት የተሠሩም ሊሆኑ ይችላሉ። ኢሕአዴግ ለዴሞክራሲ ዋጋ ሰጥቶ፣ ፍትሐዊ ምርጫ አካሔዶ እና ተሸንፎ ከአመራሩ ቢወርድ በሥልጣን ሽፋን የተፈፀሙ በርካታ ወንጀሎች ይወጡና አመራሮቹ እና አስፈፃሚዎቹ እንደአስፈላጊነቱ ለፍርድ መቅረባቸው አይቀሬ ነው። ሌላው ቀርቶ የፓርቲ ኃይላቸውን ተጠቅመው የመንግሥት ንብረት ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ፣ ጉዳዮች አግባብ ባልሆነ አካሔድ እንዲቀላጠፉላቸው ያደረጉ ሁሉ ተጠያቂ መሆናቸው አይቀርም። ይህ ኢሕአዴግን ገና ከሩቁ የሚያስፈራው ጉዳይ ነው። ስለዚህ ከሥልጣን ከመውረዱ በፊት አስቦበት ተንጠልጥሎ አይቀርም አይባልም።

እንግዲህ ከላይ የጠቀስኳቸው ሦስቱም ምክንያቶች ኢሕአዴግ የሰዎች ስብስብ እንደመሆኑ ሰዎቹ የሠሯቸው ሀጢያቶች ሰለባ መሆኑን ነው። እነዚህ ሰዎች ለሀጢያታቸው ተገቢውን ቅጣት ማግኘት ስለሚፈሩ ወይም ስለማይፈቅዱ ፓርቲው በወረቀት ላይ ካሰፈረው ዴሞክራሲያዊነት በተፃራሪ በማንኛውም መንገድ ከሥልጣን እንዳይወርድ ይሠራሉ፤ በዚህም መግባባት አያቅታቸውም። እንዲያውም በእኔ አመለካከት የኢሕአዴግ ውስጣዊ ጥንካሬ ይህንን ገመና ለመጠበቅ ሲባል የመጣ የግል ጥቅምን በፓርቲ ከለላ የማዳን ጥንካሬ ነው ብዬ እላለሁ። ኢሕአዴግ አባላቱ በነዚህ ሦስት ፈተናዎች አጣብቂኝ ውስጥ ሆኖ ትክክኛ ዴሞክራሲያዊ የሥልጣን ሽግግር ያካሂዳል ብሎ ማለት እንደማይቻል ከተስማማን ችግሩን እንዴት ሊቀርፈው ይችላል በሚለው ላይ እንነጋገር።

1. ኢሕአዴግ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ /በተለይም ‹‹አዲሱ አመራር››/ ሙስና ላይ ቁርጠኛ ዘመቻ በመጀመር ባያስመሰክርም ለመሆን እየማለ ነው። ይህ እርምጃው ምናልባትም የላይኛዎቹን ወንበሮች ሁሉ ባዶ ሊያደርግበት ስለሚችል ቆርጦ የሚቆርጥ ግን አይመስልም፣ በዚህ ካልቆረጠ ታዲያ ማድረግ የሚችለው ትልቁ ነገር አዲስ የሚመጡት ላይ ቁጥጥሩን ማጥበቅ ነው፤ ነባሮቹም አዲስ ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ማድረግ - ዞሮ ዞሮ የእስካሁኑም ቢሆን ከተጠያቂነት ስለማያድነው የማረሳሻ ጊዜ ይፈልጋል።
2. ኢሕአዴግ በቢፒአር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶቹን አሠራር ለማሻሻል ሲሞክር የሥራ ቦታዎችም በሚመጥኗቸው ሰዎች እንዲሞሉ የሚል እንቅስቃሴ አድርጎ ነበር። ሆኖም አሠራሩ ራሱ ለሙስና የተጋለጠና የፓርቲ ሰዎች አላግባብ የተሾሙበት እንደነበርና ችግሩን በሌላ ችግር እንደተካው ፓርቲው ራሱ የኋላ ኋላ በገደምዳሜም ቢሆን አምኗል። ስለዚህ የከሸፈውን እንደከሸፈ በመተው ፓርቲው የቀረፀውን ፖሊሲ ማስፈፀም የሚችሉ፣ ነገር ግን የግዴታ የፓርቲው አባል ያልሆኑና የተማሩ /ወይም ባጭሩ ቦታዎቹን የሚመጥኑ/ ሰዎች እየቀጠረ ቀስ በቀስ ክፍት ቦታዎችን በባለሙያ መሙላት እና ለሥራ አጥ የፓርቲ አባሎቹ የራሱን ሌላ ተጠያቂነት ውስጥ የማያስገባው የሥራ ፈጠራ ዕድል ማመቻቸት ይጠበቅበታል።
3. የኢሕአዴግ አባላት በተለያዩ የሥልጣን ሽፋኖች በገቡባቸው ወንጀሎች እጃቸው ተርመጥምጦ እስከዘላለም መዝለቅ እንደማይችሉ የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት። ስለዚህ ለፓርቲያቸው ቀጣይ ሕልውና የሚያስቡ ከሆነ አመራሮቹ ከአሁኑ ስህተት የሠሩ አባላቶቻቸውን በለመዱት ግምገማ ከመማር ይልቅ ወደፍትሕ በማቅረብ ሌሎቹንም ማስተማር ፓርቲውንም ማንፃትም ከፓርቲው የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው። ያለእነዚህ እርምጃዎች በድብብቆሽ እስከመጨረሻው መዝለቅ ከባድ ስለሚሆን ፓርቲው ቁርጠኝነት ላይ መድረስ አለበት።

እንግዲህ እነዚህን ምክሮች /መፍትሔ ቢጤዎች/ ፓርቲው ልተግብራቸው ብሎ ቢነሳ እንኳን /በነገራችን ላይ ይነሳል የሚል ፍንጭ እስካሁን አላሳየም/፣ በተግባር እርምጃ እራሱን ለማንፃት ከፍተኛ ጊዜ እንደሚፈጅበት መገመት ቀላል ነው። ስለዚህ ይህንን ከፍተኛ ጊዜ ለማግኘት ሲባል ደግሞ ሌሎች ወደስልጣን ኃላፊነት እንዳይመጡ የሚተገበራቸውን መንገድ የማደናቀፍ እና የማሳት ተግባራት ይቀጥላል ማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ የቀድሞ ችግሮቹን መልሶ እየደገመ ወደማይወጣው ‹‹**የስህተት እና የማረሚያ ጊዜ ፍለጋ ዑደት**›› ውስጥ ሊያስገባው ይችላል። ማለትም ‹‹ለችግሮቹ ማስተካከያ ጊዜ ይፈልጋል፤ ያንን ጊዜ ለማግኘት ሚዲያ ያፍናል፣ የፖለቲካ ምኅዳሩን ያጠብባል፣ የምርጫ ድራማ ይሠራል፤ በዚህም ተጠያቂ ስለሚሆን ይህንን የሚያካክስ ጊዜ ይፈልጋል - ጊዜ ለማግኘት ደግሞ ቀድሞ የሚያደርገውን ማድረግ አለበት… ይሳሳታል፣ የማረሚያ ጊዜ ይፈልጋል፣ የማረሚያ ጊዜ ለማግኘት ይሳሳታል፣ የማረሚያ ጊዜ ይፈልጋል፣…›› እያለ ይቀጥላል።

ታዲያ ይህ ዑደት ኢሕአዴግ እንዴት በሠላም ሥልጣን ይለቃል የሚል ጥያቄን እንድንጠይቅ ያስገድደናል።

ይህንን ዑደት ኢሕአዴግ እንዲሰብር ከተፈለገ ከራሱም ከሌሎችም ኢሕአዴግን ከሚተቹ ቡድኖች አንድ እርምጃ አንዱ ወደሌላኛው መራመድ ይኖርባቸዋል። ኢሕአዴግ ለአገሪቷ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ሲባል በፍትሐዊ ምርጫ

የሥልጣን ሽግግር እንዲካሔድ በበላይ አመራሮቹ በኩል ቢወስንና በአስፈፃሚዎቹ ላይ ስለአተገባበሩ ጫና ቢያደርግ፤ ተቃዋሚዎችም ኢሕአዴግ ከረፈደም ቢሆን ይህንን እርምጃ በመውሰዱ ብቻ ያገራችንን ‹‹**የድሮውን የመቅጣት ዑደት**›› አባዜ ላለመድገም ሲባል በይቅርታ ቢያልፉትና ለመጪው መንግሥት ጠንካራ ሥርዓት መገንባቱ ላይ ቢያተኩሩ - ለዚህም ቅድሚያ ቃል የሚገቡበትን መንገድ ቢያመቻቹ ችግሩ በቀላሉ ሊፈታ ይችል ይሆናል፡፡ ኢሕአዴግም በምርጫ ወርዶ ተቃዋሚ የመሆን ታሪክ ሲሠራ እናየው ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያም ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር በታሪኳ ማየት ትችል ይሆናል፡፡

# አብዮት ወይስ አዝጋሚ-ለውጥ?

‹‹ለውጥ የማይለወጥ ሕግ ነው፤›› አሮጌውን በአዲስ መተካት ያስፈልጋል፡፡ ችግሩ የቡድን ሥርዓት ለውጥን ማምጣት ነጠላ ለውጥ እንደማምጣት ቀላል እና ተቆጣጥረው በተፈለገው አቅጣጫ በቀላሉ ማስኬድ የማይችሉት መሆኑ ላይ ነው፡፡ በዚያ ላይ የጊዜ ጉዳይ አለ፤ ለውጡ በቶሎ ነው የሚፈለገው ወይስ ቀስ ብሎ ይደርሳል? በአንድ ዘርፍ ነው ወይስ በብዙ ጎኖች?

በአገራችን የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ እንደሚያስፈልግ የሚስማሙ ሰዎች ቁጥር ጥቂት አይደለም፤ የሥርዓት ለውጥ የማይፈልጉት እንኳን ሥርዓቱ በስም ብቻ ሳይሆን በተግባር የሚታይበት ለውጥ እንዲመጣ ይፈልጋሉ፡፡ የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ ብቻውን ለውጡን እውነተኛ ያሰኘዋል? በሁሉም ረገድ ለውጥ ለማምጣት የትኛው መንገድ ያዋጣል? አብዮታዊ ወይስ ዘመን አመጣሽ (አዝጋሚ ለውጥ)?

‹‹ለእያንዳንዱ ትውልድ አንድ አብዮት›› ያስፈልገዋል ይባላል፡፡ በተለይ የሰሜን አፍሪካ ሕዝቦች ረዥም ዓመት የቆዩ መሪዎቻቸውን በአብዮት ከገረሰሱ ወዲህ ባሉት ሁለት ዓመታት ሌሎች ተመሳሳይ ታሪክ ያላቸው ሌሎች አገራትም በአብዮት ምጥ ተይዘዋል፡፡ ኢትዮጵያም ከ1960ዎቹ ወዲህ ልታይ የነበረው ለውጥ ምናልባትም የ1997ቱ የምርጫ ለውጥ ነበር፤ አልተሳካም እንጂ ቢሳካ ኖሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ያህ ነበር፣ ሕዝቡም የሥልጣን ባለቤት ይሆን ነበር፡፡

የምርጫው መክሸፍ የተዳፈነ የአብዮት ስሜት ቀስቅሷል ባይ ነኝ፡፡ ያ የተዳፈነ የአብዮት ስሜት በሰሜን አፍሪካውያውኑ አብዮት ተነቃቅቶ አብዮት ይመጣል በሚል ተስፋ የሚያደርጉ ብቻ ሳይሆን፣ አብዮቱን እንመራለን የሚሉም እንቅስቃሴ ጀማምረዋል - ጥቂቶቹ በማኅበራዊ አውታሮች፣ ቀሪዎቹ ደግሞ ከባሕር ማዶ፡፡ እኔ ግን አሁን ልጽፍ የምፈልገው ስለእነዚህ እንቅስቃሴዎች አይደለም፤ ‹‹ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት አብዮት ነው ወይስ አዝጋሚ-ለውጥ?›› የሚል ጥያቄ ጠይቄ መልስ አፈላልጋለሁ፤ አብረን እናፈላልግ፡፡

አብዮትም ሆነ አዝጋሚ-ለውጥ ሁለቱም የሽግግር መንገዶች ናቸው፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ከራሷም ሆነ ከሌሎች አገራት ተሞክሮ በመነሳት የሚያስፈልጋት አብዮታዊ ለውጥ ነው ወይስ አዝጋሚ /ሒደት የወለደው/ ለውጥ የሚለውን በአፅንኦት ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ የአብዮት እና የአዝጋሚ-ለውጥ ለውጦች ('Revolutionary and Evolutionary changes') ብዙ ተፈጥሯዊና የማይነጣጠሉ (አብረው የሚጓዙ) ባሕርያት አሏቸው ሆኖም ሁለቱም የየራሳቸው መለያም አያጡም፡፡ የአብዮት ለውጥ ትልቅ እርምጃ ባንዴ የሚራመዱበት፣ ከተሣካ የሚፀና ነገር ግን አስፈሪ እና በተግባር ለመተርጎም የሰው ሕይወት የመክፈል ያክል የሚከብድ፣ ብዙ ጊዜ በአንድ የፖለቲካ ወይም ሌላ ስርዓት ላይ በማመጽ የሚመጣ ነው፡፡ የአዝጋሚ-ለውጥ ለውጥ ግን በአንዴ ጥቂት /የማይስተዋል/ እርምጃ የሚሄዱበት፣ አተገባበሩ አደጋ የሌለው ነገር ግን ለውጡን ለማፅናት የሚከብድ እና ረዥም ጊዜ የሚፈጅም ነው፡፡

የቱ ነው እውነተኛ ለውጥ የሚያመጣው? የቱን ለውጥ ነው ሕዝብ የሚፈልገው? የትኛው ለውጥ ነው ለሕዝብስ የሚያስፈልገው?

## ለውጥ በፖለቲካው ላይ ብቻ?

ፖለቲካዊ ለውጥ ያለ ማኅበራዊ፣ ባሕላዊ እና ሃይማኖታዊ ስርዓቶች ለውጥ ለማምጣት መጣር ባዶ ጆንያ ያለድጋፍ ለማቆም እንደመሞከር ነው፡፡ ሴት ልጅ ከወንድ እኩል መሥራት ትችላለች ብሎ በማይቀበል ማኅበረሰብ ውስጥ የሴት መሪ በአብዮት በማምጣት ተቀባይነት ማግኘት አይቻልም፤ እረፍት የሚበዛበትን የሥራ ባሕላችንን ነፃ ኢኮኖሚ በማወጅ ብቻ ማሻሻል አይቻልም፣ ሃይማኖት ቁጥር አንድ ተቀባይነት ባለበት አገር ላይ ማርክሲዝማዊ ኢ-አማኒነትን በማወጅ ለውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡

በዓለማችን ከታዩ ትላልቅ አብዮቶች ውስጥ የአውሮጳውያን አብዮት ሳይጠቀስ አይታለፍም፡፡ በተለይ የእንግሊዝ፣ ፈረንሳይ እና ራሽያ አብዮቶች የመንግስት ስርዓታቸውን ብቻ ሳይሆን የምጣኔ ሀብት፣ ማኅበራዊና ባሕላዊ እሴቶቻቸውን እና ስርዓቶቻቸውን ለውጠዋል፡፡ ይህም ለውጡን የእውነተኛ ለውጥ አድርጎታል፤ ምክንያቱም ማኅበራዊ ስርዓቶች እና ባሕላዊ እሴቶች ከፖለቲካዊ ስርዓቱ ጋር እንዲዋሀዱ ሆነዋል፡፡ እኛም ጋ ስንመጣ መጠየቅ የሚያስፈልገን ተመሳሳይ ጥያቄ ይሄው ነው፡፡ የሚመጣው ለውጥ በአብዮት ከመጣ ማኅበራዊ ስርዓቶቻችን (እነ እድር፣ እቁብ እና ማኅበርን መጥቀስ ይቻላል) ምን ያህል ከሚመጣው ለውጥ፣ ርዕዮተ-ዓለም እና ዴሞክራሲያዊ

ስርዓት ጋር ለመስማማት ተዘጋጅተዋል? ባሕላዊ እሴቶቻችን (እነ ለቅሶና ሠርግ፣ ወዘተ) ምን ያህል ለመጪው ስርዓት ተገዢ እና ተጣጣሚ ናቸው? እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቅ የሚያስፈልገው ምንም እንኳን አንድ ሕዝብ በተወሰኑ ቡድኖች መሪነት አብዮት ማስነሳት ቢችልም፣ አብዮቱ ግን ከለውጥ ይልቅ በተደጋጋሚ እንደታየው የጥቂት ቡደኖችን ዓላማ ለማሳካት ብቻ እንዳይሆን ነው፡፡

የላይኛውን አንቀጽ በሌላ ምሳሌ ለማጠናከር ያክል፤ እንበል - የፖለቲካ ሥርዓቱ ላይ በማበይ (አብዮት በማስነሳት) አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊን በሊበራሊዝም በመተካት ብቻ - የሕዝቡን ‹‹ንጉሥ አይከሰስ፥ ሰማይ አይታረስ›› እምነት እንዴት መንቀል ይቻላል? ጭቆናን ታግለው የጣሉ ሰዎች ራሳቸው መልሰው ጨቋኝ እንዳይሆኑ እንዴት ማድረግ ይቻላል? (ምክንያቱም የስርዓቱ ለውጥ ይህንን አያደርግልንም፤ ለማድረግ ቢፈቅድም እንኳን ሕዝቡ ልብ ውስጥ እንዲዘልቅ መልሶ ዝግመታዊ የለውጥ ጊዜ ይጠይቃል፡፡)

አዝጋሚ-ለውጥ ከፖለቲካዊ ስርዓቶች ይልቅ ማኅበራዊ ስርዓቶችን እና ባሕላዊ እሴቶችን ቀስ በቀስ በማረቅ እና ከዘመኑ ጋር በማጣጣም ረገድ ከአብዮት የተሻለ ሚና ይጫወታል፡፡ በአገራችን ሴት ልጆችን ከማጀት አውጥቶ ትምህርት ቤት መላክ፣ ሙዚቀኝነት እንደአዝማሪነት (እንደባላባት አጫዋችነት) ሳይሆን እንደሙያ ማየት እና የመሳሰሉት እየተሻሻሉ የመጡት በጊዜ ሒደት በአዝጋሚ-ለውጥ ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ በየከተማው አደባባዮች ዳር ማታ፣ ማታ ለወሲብ ንግድ የሚቆሙ ሰዎችን እንደተራ/የተለመደ ነገር ማየት እና ሌሎችም አሉታዊ ማኅበረሰባዊ ሚና ያላቸውም ነገሮች ለመለመድ የበቁት በአዝሚ-ለውጥ ሒደት ነው፡፡ እንግዴህ የአዝጋሚ ለውጥ ደካማ ጎንም ይኸው ነው፡፡ አዝጋሚ ለውጥ ማኅበረሰቡ ከሁነቱ ድግግሞሽ እና ከሚያደርጉት ሰዎች መበራከት አንፃር እየተለመደ የሚመጣ የለውጥ ሒደት ነው፡፡ ነገር ግን ለውጡ (ባብዛኛው) ታቅዶና፣ መንገድ ተጠርጎለት የሚመጣ ስላልሆነ ወደአንድ ተፈላጊ የሆነ ግብ ያደርሳል ብሎ ማሰብ ይከብዳል፡፡ ነገር ግን በሲቪክ ማኅበራት የሚመራ ለውጥ ብዙ ጊዜ ማኅበራዊ ለውጦችን አቅጣጫ በማስያዝ የሚከናወን ለውጥ ነው፡፡ ስለዚህ ፖለቲካዊ ስርዓቱ ለውጥ ጎን ለጎን የሲቪክ ማኅበራቱ ስርዓትም ለውጥ ይፈልጋል ማለት ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ ስናነሳ ፖለቲካዊ ሥርዓቱ ሲቪክ ማኅበራቱን የሚያይበት ዓይን፣ የሚቆጣጠርበት መንገድ እና የሚያደራጅበት መንገድ ማምጣት በሚችሉት ለውጥ ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ስለሚኖረው፥ ዞሮ ዞሮ ማኅበራዊ ለውጦች በፖለቲካዊ ሥርዓቶቹ ለውጥ ላይ ጥገኛ ሁነው እናገኛቸዋለን፡፡

በአዝጋሚ ለውጥ የሚመጣውን ማኅበረሰባዊ እመርታ ከአብዮታዊ አመጣሽ ለውጥ ጋር ኩታ ገጠም ማስኬድ ካልተቻለ በቀር እውነተኛ ለውጥ መመኘት ከንቱ ይሆናል፡፡ ለውጡ ፈጣን እንዲሆን እና ኋላ የቀረችውን አገር ወደፊት የሚያራምድ እንዲሆን ‹አብዮት ያስፈልጋታል› ማለት ይቻላል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ማኅበራዊ እና ባሕላዊ እሴቶቿን ከፖለቲካዊ ለውጡ እኩል ለማራመድ ስር የሰደደ ለውጥ ለማምጣት ከተፈለገ ‹አዝጋሚ-ለውጡን› መታገስ አሊያም ምን ያህል አዝጋሚ የሚለውን ለማሻሻል ዘዴ መንደፍ ያስፈልጋል፡፡

## አብዮት እንደመጠቀሚያ?

የአብዮት አመጣሽ ለውጥ ዋነኛው ችግሩ፣ ድንገት ፈንድቶ በማይቆጣጠሩት እና በማያገናዝቡት ፍጥነት የሚያመጣው ለውጥ ለጥቂቶች መጠቀሚያ ሊሆን የመቻሉ ነገር ነው፡፡ ነባሩን ጨቋኝ በአዲሱ መተካት፤ የራስን ርዕዮተ-ዓለም፣ እምነት እና ፍልስፍና የሚያራምድ ቡድን በብዙሐኑ ላይ መጫን የአብዮት አመጣሽ ለውጥ ጠንቆች ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ብዙ ጊዜ አብዮቶች ሲከሽፉ የሚታዩት - ሕዝቡ አብዮቱን እውን ካደረገ በኋላ ወደየግል ኃላፊነቱ ወይም የዕለት እንጀራ ወደማሳደዱ ይመለሳል፤ መሪዎች ግን የፈለጉትን ስርዓት መዘርጋት ይቀጥላሉ፡፡ ስኬታማ ታሪክ አላቸው ከሚባሉት የፈረንሳይ አራት አብዮቶች ውስጥ በተለይ የመጀመሪያው የከሸፈ አብዮት ነበር፡፡ ሌሎቹ ሦስቱም የተደረጉበት የሚፈለገው ለውጥ ላይ፣ በተፈለገው ጊዜ እና መንገድ መድረስ ስላልተቻለ ነው፡፡ አሁን በሰሜን አፍሪካ እየተደረጉ ያሉ አብዮት አመጣሽ ለውጦችም ኪሳራቸው ከወዲሁ ከሕዝባዊ እልቂት እስከ ርዕዮተ-ዓለማዊ ጽንፈኝነት ሲጓዙ የሚስተዋሉበት አጋጣሚ አለ፡፡

ወደኢትዮጵያ መለስ ብለን ያለፉት ሁለት ተከታታይ የአገራችንን ለውጦች እውነት ለውጥ አምጥተው ነበር ወይ ብንልም ተመሳሳይ ምላሾችን እናገኛለን፡፡ የሁለቱም ለውጦች ውጤት ቢያንስ ለሁለት ዐሥርት ዓመታት ፀንቶላቸዋል፡፡ የበፊቱ ንጉሣዊ አምባገነንነትን ገርስሶ በወታደራዊ አምባገነንነት ተካው፤ ሁለተኛው ወታደራዊውን ፈንቅሎ ሕገ-መንግሥታዊ አምባገነንነት የሚሉትን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ገደብ አልባ ሥልጣን በመስጠት በሕግ ሽፋን የመግዣ (rule by law) አስከተለ፡፡ ይህ የሚያሳየን ኢትዮጵያ ሦስተኛ ለውጥ ብታካሄድም ጉልቻ ከመቀያየር በላይ ለውጥ ላያመጣ ይችላል የሚለው ጥርጣሬ ተገቢ መሆኑን ነው፡፡

ይህ ማለት ግን አብዮት ጭራሽ ፋይዳ የለውም ማለት አይደለም፡፡ የከሸፈ አብዮትም ቢሆን እንኳን ማኅበረሰቦች ያላቸውን አቅም የሚመዝኑበትን ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ አብዮት ሕዝቦች ራሳቸውን ከጨቋኝ ገዢዎች እና ሥርዓት ነጻ የሚያወጡበት አቋራጭ መንገድ እንደሆነ ይነግራቸዋል፡፡ በዕድሜው የአብዮት ጭላንጭል ያየ ትውልድ ከአብዮታዊ ትግሉ መላቀቅ ይከብደዋል የሚል እምነት አለኝ - ስለዚህ እውን እስኪሆን ደግሞም፣ ደጋግሞም ቢሆን ያስነሳዋል፡፡

አብዮትን ውጤታማ ለማድረግ ከተፈለገ በእውነተኛ የአብዮታዊ ለውጥ ሦስት ደረጃዎች ውስጥ ማለፍ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡ የቅድመ አብዮት ዝግጅት፣ የአብዮቱ ፍንዳታ እና ድኅረ አብዮት ደረጃዎች፡፡ **የቅድመ አብዮት** ዘመን እውቀት የመሸመቻ ዘመን ነው - ሊለወጥ ስለሚችሉት ነገሮች እና እንዴት ሊለወጡ እንደሚችሉ የማንሰላሰያ ጊዜ፤ የድኅረ አብዮቱ መጀመሪያ ብዙ ጊዜ በተስፈኝነት ይሞላል፣ የለውጥ አምጪዎቹ (አብዮተኞቹ) አንደበተ ርቱዕ ንግግሮችን ያደርጋሉ - ነገር ግን ተመራማሪዎች ይሄ ተስፈኝነት ብዙም እንደማይዘልቅ እና ተግባሩ ሲጀመር ተቃዋሚ ፅንፈኞች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ አስረድተዋል፡፡ እንደምሳሌም፤ የፈረንሳይ እና የራሺያ አብዮቶች እና በአያቶላህ የተመራው የኢራን አብዮት በጠቅላይ ገዥ አምባገነንነት የተተካው በዚህ ሒደት ነው በማለት፡፡

በግብጽ ለተቀሰቀሰው አብዮት ከዐሥር ዓመት በፊት በየጋዜጣው እና በይነመረብ ላይ የሚታተሙት ሕዝባዊ ተዋስኦዎች የቅድመ-አብዮቱ ምልክቶች ናቸው፣ በኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ የነዋለልኝ መኮንን የብሔር ጥያቄ እና ‹‹መሬት ላራሹ›› የአብዮቱ ቅድመ-ምልክቶች ናቸው፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ ባሳለፈቻቸው ለውጦች የለውጥ አማጪ ነን ባዮቹ ቃል-ኪዳኖች ከፖሊሲ ቀረፃው ስለሚቀድም የተጋነነ (ambitious) ነው፡፡ አሁን ግን ኢትዮጵያ በእንደነዚያ ዓይነት ለውጦች ውስጥ መግባትዋ አይመከርም፤ የተቀረፀ ፖሊሲ ይዞ ቃል ኪዳን የሚገባላትን የመምረጫ ዕድል ያስፈልጋታል ብዬ አምናለሁ፡፡

## ‹‹አብዮት ራሱ የአዝጋሚ-ለውጥ ሒደት ውጤት ነው››

አብዮት - የቅድመ አብዮት ዝግጅት ውጤት ሲሆን ነው እውነተኛ ለውጥ የሚያመጣው ብለው የሚከራከሩ ምሁራንም አሉ፡፡ ይህ አብዮቱን ራሱን አዝጋሚ ለውጥ እንዲሆን ወይም ከአዝጋሚ ለውጥ ጋር እንዲመሳሰል ያደርገዋል፡፡ አብዮት እንዲፈነዳ /እንዲመጣ/ በፖለቲካ፣ ማኅበራዊና ባሕላዊ ውጥረቶች ውስጥ የቆየ ሕዝብ ያስፈልጋል - ያ ሕዝብ በመጨረሻ የታመቀ ብስጭቱን ሲያፈነዳው እና ለውጥ ሲጠይቅ ለውጥ ይሆናል (አብዮት ይፈነዳል)፡፡ ስለዚህ አብዮትን ማንቀዥቀዥ ወይም ማጣደፍ ወደ ማይፈለግ አቅጣጫ ሊያመራ ወይም ደግሞ ከሸፎ ለውጡ ሊመጣ የሚችልበት ዕድሜ በድጋሚ የ‹‹ቢከሽፍስ?›› ፍርሐት እንዲረዝም ያስገድደዋል፡፡ ስለዚህ የቅድመ አብዮት ሥራ ከአብዮት መቅደም እና መብሰል አለበት የሚለው መደምደሚያ ላይ መድረስ ይቻላል፡፡

ዶ/ር አንድሪው ዋላስ ‘Revolution vs Evolution’ ባሠኙዋት አጭር መጣጥፋቸው ለውጥ እንዴት መምጣት አለበት ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ሲሞክሩ አዝጋሚ ለውጥ ለአብዮታዊ ለውጥ ምቹ ጥርጊያ ይፈጥራል ቢሆንም አብዮቶች አንድን ማኅበረሰብ ወደፊት ያራምዳሉ ከሚለው የጋራ ግንዛቤ በተቃራኒ ሁሉም አብዮቶች ተራማጅ ማኅበረሰብ በመፍጠሩ ረገድ ይሳካላቸዋል እንድንል ታሪክ አይፈቅድልንም በማለት በቀስታ (safely) እንድንጫወተው ይመክራሉ፡፡ እንደ ዶክተሩ ድምዳሜ *‹‹…አብዮተኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደስልጣን ሲመጡ ቀድሞ የነበረውን ጽንፈኝነት፣ ቁጥጥር፣ ፍረጃ እና በመጨረሻም ሌሎች አብዮቶች ሁሉ የሚከተሉት ዓይነት እንደሆነውና በፈረንሳይ የመጀመሪያው አብዮት እንዳየነው ዓይነት መልሶ ግንባታ ይጀምራሉ፡፡ ይህ አካሔድ ግን [እናውቅልሃለን በሚል] በአብዮቱ ከተወሰነለት በላይ የማኅበረሰቡን ዕድገት አያሳይም፤ ታሪክም የሚነግረን ማኅበረሰብ የሚለወጠው በቴክኖሎጂ ዕድገትና እሱን ተከትሎ በሚያድገው ተግባራትን የመፈፀም አቅም ነው፡፡ እርግጥ ነው፤ ፖለቲካዊ መዋቅር በማኅበራዊ ስርዓት ውስጥ አንዳንዴ ወደፊት የመራመጃ መንገድ ነው፣ ሆኖም ለማኅበራዊ ለውጥ የሚያስፈልገን ዝግመታዊ የለውጥ ሒደት ነው፡፡››*

## ለውጥ ለማን እና በማን?

ለአገራችን የሚበጀው ለውጥ በማን እጅ እንዳለ በእርግጠኝነት አይታወቅም - በኢሕአዴግ ወይስ በተቃዋሚዎች፡፡ ኢሕአዴግ ያለበት ችግር የፖሊሲ ነው ወይስ የዴሞክራሲያዊነት? ተቃዋሚዎች ያላቸው ጥንካሬስ? ሁለቱም ወገኖች ይበጅም፣ ይጉዳ የየራሳቸው ጥንካሬ እና ድክመቶች አሉባቸው፡፡ የኢሕአዴግ አባላት በአመራሮቹ የሚሰጣቸውን ከማስፈፀም እና ከማስተጋባት ባሻገር፣ ለሕዝቡ ስለሚቀርቡ እና ሕዝብም ስለሆኑ - ‹‹የለም፣ ይሄ

መታረም አለበት›› ብለው ቢታገሉ እና ፓርቲው ፖሊሲውን እንዲያስተካክል፣ የፖለቲካ ምኅዳሩን እንዲያሰፋ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰብኣዊ መብቶችን እንዲያከብር ቢያምጹ ፓርቲው ያለአባላቱ መቆም ስለማይችል ሳይወድ በግዱ ይስተካከላል - ይህም አብዮት/ለውጥ ነው። ተቃዋሚዎችም ውስጥ እንደዚያው። አብዮቶች በገዢው ፓርቲ እና ተቃዋሚዎች ውስጥ ቢጀመሩ በአገሪቱ ላይ እውነተኛ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ።

የክፍል አለቃ፣ የትምህርት ቤት ዳይሬክተር፣ የቢሮ አለቃ፣ የዕድር ሊቀመንበር፣ የማኅበር ሙሴ እና ወዘተ በማኅበረሰባችን እና ተቋሞቻችን የሚመረጡት እንዴት ነው? በቁመና፣ በሹመት፣ በግርማ ሞገስ፣ በመንፈሳዊ ዝንባሌ ወይስ በምን? እነዚህ አመራረጦች የራሳቸው ሚና ቢኖራቸውም ዴሞክራሲያዊ እሴቶችን አያለመልሙም፤ ስለዚህ እያንዳንዱ አካል መሪውን ሲመርጥ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ዕጩው በአባላት ተጠቁሞ፣ ተመርጦ ቢሾም - እታች የተለመደው እላይ ድረስ ይሄዳል። መሪው ሕዝቡን ሳይሆን፣ ሕዝቡ መሪውን መምረጥ የሚችልበት ስርዓት በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚዘልቀው፣ በእንደነዚህ ዓይነቶቹ ሹመቶች ላይ ማኅበረሰቡ በጊዜ ሒደት (በአዝጋሚ-ለውጥ) ዴሞክራሲን እንዲለማመድ ማድረግ ሲቻል ነው። ይህ እንግዲህ ማኅበረሰባዊ ለውጥ በመሆኑ ነፃ የሲቪክ ማኅበረሰብ ሲኖር የሚመጣ ነው፤ ከሌለ በአብዮትም ቢሆን ማምጣት መፍትሔ ሊሆን ይችላል።

# ለውጥን መቋቋም እና መፍራት

ለውጥን በምናብ ይወዱታል እንጂ በተግባር አይዳፈሩትም - ሰዎች፡፡ የሥርዓት ለውጥ ሲሆን ደግሞ ፍርሐቱ ያይላል፡፡ የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ ሲሆን ደግሞ ከማንኛውም ሥርዓት ለውጥ በላይ ያስፈራል፡፡ የፍርሐት ፖለቲካዊ አንድምታ ከታሪክ አንጻር እየተመለከትን ስለራሳችን ለውጥ እንድናወራ ነው ይህ ጽሑፍ የተጻፈው፡፡

## የፍርሐት ዘመን (Reign of Terror፡ 1793-1794)

የመጀመሪያው የፈረንሳይ አብዮት መባቻ ላይ ከፍተኛ ፍርሐት ሰፍኖ ነበር፡፡ አምባገነኑ ሉዊስ 16ኛን ገርስሰው ሰብኣዊ መብት እና ሕገ-መንግስታዊ አስተዳደርን ከአሜሪካ ለመኮረጅ የሞከሩት ፈረንሳውያን እርስ በእርሳቸው ተቀናቃኝነት ባፈሩት የለውጡ መሪዎች ጊሮንዲኖች እና ያቆቢኖች (Girondins and the Jacobins) አንደኛው ሌላኛውን ‹‹የአብዮቱ ጠላት›› በሚል በደም የታጠበ አብዮት በማድረጋቸው 25 ሺሕ ለሚደርሱ ሰዎች እልቂት መንስኤ ሆኗል፡፡ ያንን ጊዜ የፍርሐት ዘመን (The Reign of Terror) በሚል ታሪክ ጸሐፊያን ያስታውሱታል፡፡

እኔ የፈረንሳዩ አቻ ትርጉም ነው ልለው የምለውን ማሕሌት ፋንታሁን የፍርሐት ዘመን በሚል ርዕስ ዞን ዘጠኝ ላይ ከዚህ ቀደም ጽፋዋለች፡፡ ጽሑፏ ያለንበትን የፍርሐት ወቅት ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ ለመሆኑ ይሄ ፍርሐታችን የፈረንሳይ አብዮት የወለደው የ‹‹ፍርሐት ዘመን›› ጋር የሚያመሳስለው ነገር ይኖር ይሆን በሚል የሚከተለትን ሁለት ክስተቶች ለማስታወስ እንገደዳለን፡፡

## ሀ). ቀይ ሽብር

ምናልባትም ለአሁኑ ትውልድ አባት የሚባሉት የ‹‹ያ ትውልድ›› አባላት፣ የሚፈልጉት ለውጥ አቅጣጫውን እንዳይስት እና በየግላቸው መቆጣጠር እንዲመቻቸው ሲባል የሄዱበት መንገድ ሽብር ነበር - ቀይ እና ነጭ ብለው የሰየሙትን ሽብር፡፡

በዚህ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆነ የሽብር ድርጊት ሳቢያ አምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደሚለው እስከ ግማሽ ሚሊዮን የሚደርሱ ሰዎች አልቀዋል፡፡ ሌኒን ‹‹ያለ ቀይ ሽብር ማኅበረሰባዊነት አይገነባም›› ብሏል በሚል በአንድ ርዕዮት ዓለም እኔ እበልጥ፣ እኔ እበልጥ በሚል እና ደርግ ጊዜያዊ መንግሥት አቋቋሞ ወደካምፑ ይመለስ የሚሉና ሌሎችም አብዮቱን ያቀጣጠሉ ጥያቄዎችን መልስ በመሻት እና በመነፈግ መካከል ለመገዳደል ሳይቀር የሶቪየት ኅብረትን ቀይ ሽብር የሚል ስም የተዋሱት ኢሠፓዎች እና ነጭ ሽብር የሚባል ምላሽ የሰጡት ኢሕአፓዎች ልክ የፈረንሳይ አብዮት ልጆች እንደሆኑት ጊሮንዲኖች እና ያቆቢኖች ‹‹አብዮት ልጆቿን በላች›› ተብሎላቸዋል፡፡ ይህንን ተከትሎ የቻለው ሲሰደድ የቀረው መፍራት የሚችለውን ያክል የሚፈራበት ታሪክ ተፈጥሯል፡፡ ይህ ፍርሐት በከፊል የተቀረፈው በኢሕአዴግ አፍላ የሥልጣን ዘመን ነበር፡፡

## ለ). ድኅረ ምርጫ 97

ግንቦት 7፤ 1997 - የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት መለስ ዜናዊ በቴሌቪዥን መስኮት ቀርበው ከዛን ዕለት ጀምሮ ለ30 ቀናት ምንም ዓይነት ሕዝባዊ ስብሰባ ማድረግ እንደማይፈቀድ እና ፌዴራል ፖሊሱም ተጠሪነቱ በቀጥታ ለርሳቸው ሆኖ በተጠንቀቅ እንደሚቆም ገለፁ፡፡ ጉዳዩ አስደንጋጭ ነበር፤ ምክንያቱም የዛን ዕለት የተካሔደው ምርጫ እንጂ ሌላ ምንም ነገር አልነበረም፡፡

ሰኔ ወር ላይ ኢሕአዴግ ምርጫውን በበላይነት እንዳሸነፈ ምርጫ ቦርድ በማስታወቁ እና ተቃዋሚዎች ምርጫው ይደገም ያሉባቸውን ቦታዎች በአብዛኛው በመከልከሉ… በየከተማው ሕዝባዊ ቁጣ ተቀሰቀሰ፡፡ በወቅቱ ኢሕአዴግ ያቆሰለውን አቁስሎ፤ የገደለውን ገድሎ ለመደራደር ፈቃደኝነት በማሳየቱ መጠነኛ መረጋጋት ተከሰተ፡፡ ነገሮዬው ግን ብዙም ሳይዘልቅ በቀጣዩ ዓመት ጥቅምት 22/1998 ነገሩ ሁሉ ወደብጥብጥ ተገለባብጦ ተጠሪነታቸው በጠቅላይ ሚኒስትሩ የነበሩት የፌዴራል ፖሊሶች መንግሥት ባመነው ብቻ 193 ሰዎችን ሕይወት ቀጠፉ፡፡ ከዚያም ፍርሐት ሆነ፡፡

በቀይ ሽብር - ነጭ ሽብር ፍጅት ዶ/ር አለማየሁ ረታ እንዳሉት ‹‹እጅ እጁን በእሳት ብረት እየተገረፈ›› አብዮቱን የተነጠቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ የለውጥ ፍርሐት፣ በኢሕአዴግ የዴሞክራሲ ዝማሬ ተዘናግቶ በምርጫ ለውጥ ቢጠይቅም የኋለኛው ከፊተኛው የጎላ ለውጥ እንደሌለው በሚያረጋግጥ መልኩ ዳግም የፍርሐት ዋሻው ውስጥ እንዲሸሸግ በልማት ስም ዴሞክራሲውን መልሶ ተነጥቋል፡፡

## "ከማያቁት መላክ የሚያውቁት ሰይጣን"

ሌላኛው በፖለቲካዊ የሥርዓት ለውጥ ላይ የሚመጡ ተቃውሞዎች ምንጭ ‹‹ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል›› የሚለው አባባል ይገልጸዋል፡፡ ይሕ ሕዝብ ይህንን ተረት የፈጠረው ካለፈው ልምዱ በመነሳት ነው፡፡ የሚመጣው ለውጥ በግልጽ የማይታየው ሕዝብ የባሰ ይመጣብኛል ብሎ መፍራቱ የሚያስገርም አይደለም፤ ይህንን ተረት ለመሻር ለውጥ አምጥቶ የኋለኛው ከፊተኛው እንደሚሻል በተደጋጋሚ ማስመስከር ብቻ ነው መፍትሔው፡፡ የዚህ ተረት አምላኪዎች ኢሕአዴግ እራሱ እንዲለወጥ እንጂ፣ ፓርቲው በሌላ እንዲተካ አይፈልጉም፡፡ እርግጥ ነው፤ እነዚህ ሰዎች የዘነጉት ነገር ኢሕአዴግን መለወጥም ራሱ ለውጥ መሆኑን የምናወራበት ጊዜ ይመጣል፡፡

ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ‹‹የቀድሞ አምባገነኖች እልፍ ሀብት ማፍራት ይወዱ ነበር፤ የአሁኖቹ ግን ሕዝብ መግዛት ብቻ ነው የሚያስደስታቸው›› ይላሉ፡፡ ይሄ አባባል ግን የኛዎቹን የሚገልጻቸው አይመስለኝም፡፡ መሪዎቻችን በጣም ሀብታሞች ከመሆናቸው የተነሳ ለመናጢ ድሀ እንኳን የማይበቃ የወር ደሞዝ እየተቀበሉ አነሰኝ ሲሉ አይደመጡም፣ ልጆቻቸውን ዓለምአቀፍ ት/ቤት ያስተምራሉ፣ ሕንፃ ይገነባሉ፣ ትልልቅ አክሲዮን ይገዛሉ፡፡ በአጭሩ ልታይ፣ ልታይ አይሉም እንጂ(?) ሀብታሞች ናቸው፡፡ ቁምነገሩ ሀብታም መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን የሀብታቸውን ምስጢርም ሳይቀር ሕዝቡ ማወቁ ላይ ነው፡፡ እናም አዲስ ተረት ተፈጥሯል፤ ‹‹የጠገበው ይግዛን›› የሚባል! ይህም እንግዲህ ሌላው ለውጥን የመቃወሚያ (የሚያስፈራ) አንድ ምክንያት ሆኖ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

## ሰውኛ የለውጥ ፍርሐት

ለውጥን የሚያስፈራን ቀድመን የጠቃቀስናቸው እሳት የጎረሱ እሳት የለበሱ የለውጥ ገጠመኞች ብቻ አይደሉም፡፡ ጥልቀቱ ይለያይ እንጂ በሁሉም ሰው አእምሮ ውስጥ ተፈጥሯዊ የለውጥ ፍርሐት እና መቋቋም (resistance) አለ፡፡

የሥነ-ልቦና ምሁራን ሰዎች ማንኛውንም ዓይነት ለውጥ የሚቃወሙባቸውን የተለያዩ ምክንያቶችን ይዘረዝራሉ፡፡ ለምሳሌ ሰዎች የሚሰበክላቸው ለውጥ ጥቅሙ ላይታያቸው ይችላል ወይም የሚጎዳቸው ዓይነት ይሆናል፤ ለውጦቹ በእርግጥ ይመጣሉ ብለው ማመን ይቸገራሉ ወይም ይመጣበታል የተባለው መንገድ አያሳምናቸውም፤ ለውጡን አመጣለሁ ወይም እመራለሁ በሚለው አካል እምነት ላይኖራቸው ይችላል፤ ለውጡን ቅድሚያ ላይሰጡት ይችላሉ ወይም ደግሞ ለውጡ ለነርሱ ዋጋ የሚሰጥ (ወይም ከለውጡ በኋላ ተወዳዳሪ የመሆን አቅም ያላቸው) አይመስላቸውም፤ ለውጡ የተለየ ክህሎት ወይም ሌላ መለያ ያላቸውን የሚጠቅም ብቻ ሊታያቸው ይችላል፤ ለውጡ ተጨማሪ ኃላፊነት ወይም ሥራ ይዞባቸው የሚመጣም ሊመስላቸው ይችላል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሰዎች ከለመዱት የምቾት ዞን መውጣት ይከብዳቸዋል፡፡

ሰዎች አንድን ለውጥ የሚቋቋሙት በብዙ መንገድ ነው፤ እነዚህ መንገዶች ለውጡን በሚያመጡ እርምጃዎች ላይ ካለመተባበር እስከ ለውጡን የሚቃወሙ እንቅስቃሴዎች ማራመድ ሊደርስ ይችላል፡፡

እነዚህን ፍርሐቶች እና ለውጥን የመቋቋሚያ ምክንያቶች እንኳን መላ አገሪቱን እለውጣለሁ ብሎ ለተነሳ ፓርቲ እና አራማጅ ቀርቶ የአንድን ድርጅት አሠራር እለውጣለሁ ብሎ ለተነሳ መሪ ከባድ ፈተናዎች ናቸው፡፡

## ጥቂት መፍትሔዎች

የለውጥ ፍርሐቱን ለመስበር የመጀመሪያው ለውጡ እንደሚያስፈልግ የሚያምን፣ ለውጡ የሚመጣበትን መንገድ የሚያመላክት፣ ፍርሐቱን የሚጋፈጥ፣ ችግሩን የሚቋቋም እና ስሜቱን ማጋባት የሚችል ፈር ቀዳጅ መሪ ወይም የሚችሉ መሪዎች ያስፈልጋሉ፡፡ መሪ የሌለው የለውጥ ሒደት አለ ብሎ ማለት ይቸግራል፡፡

ለውጡ የሚመለከታቸውን ሰዎች (የኅብረተሰብ አካላት) በለውጡ ሒደት ውስጥ ዋና ተዋናይ ማድረግ፡፡ የስርዓት ለውጥን በተመለከተ ብዙ ከማውራት፣ ከመወያየት እና መረጃ ከመለዋወጥ በላይ ፋይዳ ያለው ነገር የለም፡፡ የለውጡ ባለቤቶች ስለለውጡ ማወቅ እና በቂ ግንዛቤ ማፍራት የሚችሉበትን መንገድ በአትኩሮት ማሰብ እና መተግበር ያስፈልጋል፡፡ ይህ ካልሆነ ለውጡን የተቀበሉት ቢመስሉም እንኳን ለተግባሩ ላይታዘዙ ይችላሉ፡፡

ለውጥ ሲካሔድ ለውጡ የሚጎዳቸው አካላት (የኅብረተሰብ ክፍሎች) ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በለውጡ በቀጥተኛ መንገድ የሚታወኩ ሰዎች የለውጡ ሰለባ ሳይሆን የለውጡ ተጠቃሚ የሚሆኑት እንዴት ነው በሚለው ዙሪያ ላይ ቀድሞ መዘጋጀት፤ መዘጋጀት ብቻም ሳይሆን በለውጡ ምንም ዓይነት ቁስል እና ጠባሳ እንዳይፈጠር መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ አለበለዚያ ያ የለውጥ ቁስል ሁሌም የታሪክ ማጣቀሻ ሆኖ መቅረቱ የግድ ይሆናል፡፡

ለውጥ ሁሌም የተለየ ነገር ይፈልጋል - ግን ምን ያህል?... በአንድ ግዜ ብዙ እና ትልቅ ለውጥ ለማምጣት መታገል የሰው ልጅን የልምድ ቀጠና አፈራርሶ አዲስ ልምድ እንዲገነባ ማድረግ በመሆኑ ከመክበዱም ባሻገር፣ ለግራ መጋባትና ለስህተት መንገድ ይከፍታል፡፡ ስለዚህ ለውጦችን በአንዴ ሳይሆን ቀስ በቀስ (በየእርከኑ) እና በበቂ ዝግጅት ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡

ለውጡን በአንድ ጀምበር ለማስኬድ አለመሞከር፤ ይህ በተለይ በፖለቲካዊ ስርዓቶች ላይ የሚከብድ ይመስላል - ነገር ግን የማይቻል ነገር አይደለም፡፡ ሆኖም የስርዓትን ለውጥ አንዱን በአንዱ ለመተካት ከማሰብ ይልቅ ከነባሩ ጎን ለጎን አዲሱን በማስጀመር፣ ነባሩን ስርዓት እየገዱሉ፣ አዲሱን እያጎለበቱ የሚሸጋገሩበትን ጊዜ ማመቻቸት/ማቀድ፡፡

ስጋቶችን አለማጣጣል ያስፈልጋል፤ ለውጥን መቋቋም ሰውኛ ባሕርይ ነው በሚል ብቻ በቸልተኝነት ማለፍ ተገቢ አይሆንም፡፡ ምናልባትም አንዳንዴ የሚነሱት ስጋቶች እና ፍርሐቶች እውነትም ተገቢ ስጋቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ስጋቶች፣ ፍርሐቶች እና ጥያቄዎችን ጆሮ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

## "ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም"

ለውጥ የግድ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ሁሉንም የማይጠቅም ቢሆን እንኳን ለብዙኃኑ ሲባል የግድ መምጣት አለበት፡፡ የለውጥ ፍርሐትን እና ተቃውሞን እንደችግር ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት አይቻልም፡፡ ነገር ግን በቂ ዝግጅት በማድረግ ግን በተገቢው መንገድ መቀነስ ይቻላል፡፡ የለውጥ ፍርሐትን እና ተቃውሞን ሳይቀንሱ ግን ለውጥን መጨበጥ ዘበት ነው፡፡ የፈረንሳዮቹ የፍርሐት ዘመን አንድ ዓመት ሳይዘልቅ በሞቀ አብዮት ተገፍፏል፡፡ አብዮት አብዮትን እየወለደ ከአራት አብዮት በኋላ የዛሬዋ ፈረንሳይ የበለፀገች እና ዴሞክራሲያዊ ሆናለች፤ ለእኛም ይህ የፍርሐት ዘመን ተገፍፎ ብለፅግናና ዴሞክራሲ እንዲመጣ ፍርሐታችንን ለመጋፈጥ መቁረጥ አለብን፡፡ ‹‹መፍራት ያለብን ፍርሐትን ራሱን ነው›› እንዲሉ ፍራንክሊን ሩዝቬልት፡፡

# የሥርዐት ለውጥ እና ሃይማኖቶች

ሃይማኖት ከጊዜ ወደጊዜ ፖለቲካዊ አቅሙን እያጣ የሚሄድ እና በገለልተኛ አስተሳሰብ የሚተካ እንደሆነ ፖለቲከኞች ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ ሆኖም እውነታው ተቃራኒ መሆኑን ‹ሃይማኖቶች በየጊዜው ያንሰራራሉ› (“Religious resurgence is a cyclical phenomenon”) በማለት እንደዶናልድ ስሚዝ ያሉ የፖለቲካ እና ሃይማኖትን ግንኙነት በጥልቀት ያጠኑ ምሁራን ይናገራሉ፡፡

በቅርቡ ከአየናቸው የአረብ አብዮቶች እንኳን መረዳት እንደምንችለው የቱኒዚያው ኤናህዳ (Ennahda) እና የግብፁ ሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲዎች በምርጫ ማሸነፋቸው ምናልባትም እምነት ላይ መሠረታቸውን ያደረጉ የፖለቲካ አጀንዳዎች ወደፊት ተመልሰው ይመጡ ይሆን የሚለውን ጥያቄ ጆሮ እንዲሰጠው አድርጓል፡፡ በኢትዮጵያም ቢሆን ሃይማኖታዊ በዓላት ከመቼውም ጊዜ በላይ በደማቅ ሁኔታ ከጊዜ ወደጊዜ እየተከበሩ መምጣታቸው፣ የዶግማ ጦርነቶች በቪዲዮ ካሴቶች መበራከታቸው እና ሌሎችም ምልክቶች የሃይማኖትን ቦታ መልሶ ወደፖለቲካው መድረክ እንደማይመጣ እርግጠኛ ሆኖ መናገርን እያከበደው ይመስላል፡፡

ምንም እንኳን ሴኩላሪዝም (ከሃይማኖት ነጻ የሆነ የፖለቲካ ዐውድ መፍጠር) ሙሉ ለሙሉ እውነት ሊሆን የማይችል እንደሆነ ቢታመንም ያደጉ አገራት ከታዳጊዎቹ ይልቅ የሃይማኖትን ተጽዕኖ ከመንግሥት ጫና ላይ በማላቀቁ ረገድ የተሻለ እየተሳካላቸው ነው፡፡

በድህነት ደረጃቸው ሦስተኛው ዓለም በሚባሉት እንደኢትዮጵያ ባሉ አገራት የሃይማኖቶች ሚና በፖለቲካው ዕጣ ፈንታ እስከመፍረድ ሊደርስ እንደሚችል ይታመናል፡፡ ኢኮኖሚያቸው ዝቅተኛ የሆኑ እና ነጻነታቸውም ውሱን የሆኑ ሰዎች ተስፋ የሚጥሉት ከመንግሥታዊ ሥርዐቱ ይልቅ ‹‹በፈጣሪያቸው›› ላይ መሆኑ ያፈጠጠ እውነታ ነው፡፡

Religion and Politics in Arab Transitions በሚል ርዕስ በባራሕ ሚካኤል FRIDE ለተሰኘ አንድ የአውሮፓ የማሰቢያ ቋት (Think Tank) የተሠራ ጥናት እንደሚተነትነው ‹የአንድ አገር ማኅበረሰብ ሃይማኖተኝነት በአገሪቱ የሥልጣን ሽግግር ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል፤ ሆኖም ሃይማኖት በሥልጣን ሽግግር ላይ የጎላ ሚና ከተጫወተ ሽግግሩ ዴሞክራሲያዊ ውጤት ላይኖረው ይችላል› ይለናል - ጤናማ ዴሞክራሲ በአንድ ወይም ጥቂት የሃይማኖት እሳቤዎች ብቻ የተገደበ እንደማይሆን (ወይም ብዝኃነትን እንደሚያገናዝብ) እያብራራ፡፡

የሃይማኖት ጉዳዮች ብዙውን ጊዜ የሚያያዙት ከፖለቲካዊ ሥልጣን ጋር ነው፡፡ ብዙዎች ሃይማኖትን ሥልጣን ለማግኛ (ለጥሩም ይሁን ለክፉ) ተጠቅመውበታል፡፡ ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1980ዎቹ በላቲን አሜሪካ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከአምባገነናዊ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዐት ለመሸጋገር በተደረገው ጥረት ውስጥ የጎላ ሚና ተጫውታለች፡፡ ቤተክርስቲያኗ በአርጀንቲና የNational Reorganisation Process in Argentinaን ደግፋለች፤ በቺሊ ለPinochet አገዛዝ ተቃውሞዋን ገልፃ በኤል ሳቫዶር ለሚካሄደው ሕዝባዊው የለውጥ እንቅስቃሴ ድጋፍ አሳይታለች፡፡ በቱርክ የጉለን (Gülen) እንቅስቃሴ የተመራው በሱፊ እስላም ወንድማማቾች ነው፡፡ ይህ እና መሰል እንቅስቃሴዎች የሚያስረግጡልን ፖለቲካዊ ፍላጎት ላላቸው አማኞች ሃይማኖት ጥሩ አብዮታዊ መሣሪያ መሆኑን ነው፡፡

በሌላ በኩል በዓለማችን በዝነኝነታቸው የሚታወሱት የፈረንሳይ፣ የሜክሲኮ፣ የሩሲያ፣ የቻይና፣ የኩባ አብዮቶች በሙሉ እና የ1960ዎቹ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የተነሳሱት በገለልተኛ (ሴኩላር) ርዕዮት-ዓለሞች ነው፡፡ ሆኖም ተሳክቷል (አንጻራዊ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር አምጥቷል) የሚባለው የአሜሪካ አብዮት ደግሞ በተቃራኒው በክርስትና እምነት እሴቶች የተነቃቃ ነው በማለት ሃይማኖት መር የሥርዐት ለውጥ የተሻለ አማራጭነቱን የሚሰብኩም አይታጡም፡፡ ነገር ግን መጠየቅ የሚገባን ‹ሃይማኖት ለአብዮት (ለሥርዐት ለውጥ) እንቅፋት የሚሆንበትስ ዕድል የለም ወይ!?› ብለን ነው፡፡

## ሃይማኖት ለአብዮት እንቅፋት ይሆናል?

የተለያዩ ሃይማኖቶች ስለሥልጣን እና ሹመት የተለያየ አቋም አላቸው፡፡ በጥቅሉ ስናስበው ሃይማኖት ዓለምአቀፋዊ ሲሆን ፖለቲካዊ ሥልጣን ግን ሰዎች በፈጠሩት የጂኦግራፊ ካርታ ላይ የተመሠረተ ሰው ሰራሽ

ሥልጣን ቢሆንም ቅዱስ መጽሐፎች ግን የራሳቸውን አቋም ማንፀባረቃቸው አልቀረም፡፡ ለምሳሌ የክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ወደሮሜ ሰዎች ምዕራፍ 13፥1-2 እንዲህ ይላል፡-

*ማንኛውም ሰው በሥልጣን ላሉት ሹማምንት መገዛት ይገባዋል፤ ከእግዚአብሔር ካልሆነ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለሥልጣናት በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው፡፡ ስለዚህ፣ በባለሥልጣን ላይ የሚያምፅ በእግዚአብሔር ሥርዐት ላይ ማመፁ ነው፤ ይህን የሚያደርጉትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ያመጣሉ፡፡*

በእስልምና ሃይማኖት ቅዱስ መጽሐፍ - ቁርኣን ላይም ተቀራራቢ ነገር እናገኛለን፡-

*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ፤ መልክተኛውንና ከናንተም የሥልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ፤ በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትኾኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልክተኛው መልሱት፤ ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው፡፡ (ቅዱስ ቁርኣን ምዕራፍ 4፤ አል-ኒሳእ፡፡ ክፍል 5፡፡ ቁጥር 59)*

ከላይ እንዳየነው ክርስትና መንግሥት ላይ ማመፅን በፍፁም ቃል ይቃወማል፤ በሌላ በኩል በክርስትና ኢየሱስ ‹‹የቄሳርን ለቄሳር›› ብሏል ብለው የመንግሥት እና ሃይማኖትን መነጣጠል የሚነግር ነው የሚሉም አይታጡም፡፡ ወደእስልምናም ስንመለከት ከባለሥልጣናት ጋር ካልተግባባችሁ ወደአላህና መልክተኛው መልሱት እንጂ ምድራዊ መፍትሄ ፈልጉለት አይልም፡፡ እርግጥ ነው በእስልምናውም ባለሥልጣን የሚለው ቃል የሚወክለው የቤተ ሃይማኖቱን አባቶች እንጂ የመንግሥት ሹማምንትን አይደለም ብለው የሚከራከሩ አሉ፡፡ በጥቅሉ ግን፣ እኔ በምረዳው እና ከቀደሙት አስተምህሮቶችም ማየት እንደሚቻለው… ሃይማኖተኞች ለመታዘዝ ቅድሚያ እንዲሰጥ እንደሚወተውቱ ነው፡፡ ችግሩ በጥቅሉ ‹‹መታዘዝ›› የሚለው ቃል ሕዝብን ለሚበድል ባለሥልጣናትም ቢሆን ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል የተለየ ሐሳብ አላስቀመጡልንም፡፡

እነዚህን የሃይማኖት ኃይለ ቃሎች የሚረ'ዱ መንግሥታትም ሃይማኖትን መጠቀሚያ ለማድረግ ይሞክራሉ፡፡ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሕገ መንግሥት የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ያልሆነ ብቻ ሳይሆን፣ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ያልሆነች ሚስት ያገባ ሰው መንገስ እንደማይችል ቃል በቃል ይጠቅስ ነበር፡፡ ንግሥናውም ከእግዚአብሔር የተገኘ እንደሆነ ከላይ የጠቀምነው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በሚመስል ሐረግ ያስረዳል፡፡

መንግሥታት ሃይማኖትን በተለያዩ መንገዶች ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ በርካታ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ Jeff Haynes የተባሉ ተመራማሪ Religion in Third World Politics በሚለው ጥናታቸው ሃይማኖት በሦስተኛው ዓለም መንግሥታት እንዴት መጠቀሚያ ሊሆን እንደቻለ ሲጠቁሙ ሥርዐት ለማስቀጠያነት (Regime continuity)፣ ሕዝብ ትዕዛዝ እንዲቀበል ለማሳመኛነት (Public order maintenance)፣ ሥልጣንን ተቋማዊነት ለማላበስ (Institutionalization of authority) እና ለዜግነት እንደቅድመሁኔታ በማስቀመጥም (Promotion of citizenship) ጭምር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩል በዚህ ዘመን አምባገነን መንግሥታት ሃይማኖት እንደመጠቀሚያ የሚሆነው በከፋፍለህ ግዛ ስትራቴጂ ነው፡፡ አንደኛው ሃይማኖት ሌላውን በጥርጣሬ እንዲመለከተው እና ለሁለቱም ግን እንደዋስትና መንግሥትን በማስቀመጥ እንዳይተባበሩ እና መንግሥት ላይ እንዳይነሱ ማድረግ እየተለመደ የመጣ ዘዴ ሆኗል፡፡ ቀጣዩ ጥያቄ ታዲያ፡-

## ሃይማኖተኞች በመንግሥት ላይ ያብያሉ?

ከሃይማኖቶች ዶግማ በመነሳት ሃይማኖተኞች የሚያብዩት ሃይማኖታቸው የተጠቃ ሲመስላቸው እንጂ እነርሱ እንደሕዝብ የተጨቆኑ ሲመስላቸው አይደለም የሚል መደምደሚያ ላይ መድረስ የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ሃይማኖትን ከለላ ለማድረግ የሞከሩት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን በአብዮት መውረድ እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል፡፡ በንጉሡ ሥርዐት ላይ ለተነሳው አብዮት አንዱ መነሾ የሃይማኖቶች መገለል ነው፡፡ ለምሳሌ "በኢቫንጀሊካል ክርስቲያኖች አመለካከት በንጉሡ ዘመን [ቤተክርስትየናቸው] ሲደርስባት የነበረው እንግልት ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን እጅ አለበት ብለው ማሰባቸው ጽናታቸውን እንዳበረታው እና ሥርዐቱን ለመጣል በሚደረገው ትግል ውስጥም አማራጭ ፍለጋ ተሳትፎ እንዳደረጉ" Revolution and Religion in Ethiopia በተሰኘ መጽሐፋቸው ላይ Øyvind M. Eide የተባሉ ተመራማሪ አትተዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የዶናልድ ስሚዝ Religion, Politics, and Social Change in the Third World ቅኝ ተገዢዎች ሃይማኖትን በመጠቀም አብየው (አብዮት አቀጣጥለው) ነጻ የወጡባቸውን አራት መንገዶች ይዘረዝራሉ፡-

1. ሃይማኖት በራሱ የአመራር ዕድል/ተቀባይነት ያጎናፅፋል (ማሕተመ ጋንዲ ስማቸው በሒንዱ እምነት ‹‹ታላቅ ነፍስ›› የሚልና ከቤተ እምነቱ የተገኘ በመሆኑ በአብዛኛው አማኝ ተቀባይነት አስገኝቶላቸዋል፤)
2. ሃይማኖት ለውጥ ፈላጊዎች እርስ በእርስ የሚተሳሰሩበት ምክንያት በመስጠት ለታጋዮቹ (ወይም ለውጥ ጠያቂዎቹ) የስሜት ጥንካሬን ያጎናጽፋል፣
3. ሃይማኖት ለትግሉ ወይም ተቃውሞው ጥንካሬ የሚሆን መሠረት ይጥላል፣ (በእስልምና ቃፊሮች (ያልታመኑ ገዢዎች) ላይ የሚደረግ ጅሃድ (ቅዱስ ጦርነት) ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል፡፡)
4. ሃይማኖት የመቃወሚያ መንገድ ይሰጣል (ለምሳሌ ጋንዲ ‹satyagraha› የተሰኘውን የአመጽ አልባ ሰላማዊ ትግል ፅንሰ ሐሳብ ያገኙት ከሒንዱ እምነታቸው ነበር፡፡)

ከዚህ በተጨማሪም አብዛኛዎቹ ሃይማኖቶች ነጻነት እና እኩልነትን እንደመርሕ የሚመለከቱ መሆናቸው በፖለቲካዊ ሥርዐቶች ላይ በቀጥታ ባያምፁም እንኳን የሥርዐቱን ድርጊቶች በማውገዝ ሃይማኖታዊ አብዮተኞች ከቤተ እምነታቸው ስለሚታገሉለት ለውጥ የማጠናከሪያ ሐሳብ ማግኘት ይችላሉ፡፡ በዚህ መንገድ ነው የላቲን አሜሪካ አብዮት በክርስትና እና የግብፁ (የ1952/እ.ኤ.አ.) አብዮት በሙስሊም ወንድማማቾች ድጋፍ እና ሃይማኖታዊ እሳቤ ተነሳስተው ለለውጥ የበቁት፡፡

እነዚህ የታሪክ ዳራዎች ላይ በመመርኮዝ አሁን የሚታየው የሙስሊም ኢትዮጵያውያን እና ‹‹የመጅሊሳቸው›› ውዝግብን ተከትሎ  ጥያቄ ጥያቄን እየወለደ ቤተ እምነታዊው ጥያቄ ወደፖለቲካዊ እና ሥርዐታዊ ለውጥ ጥያቄ ያድግ ይሆን፣ ካደገስ ያዋጣ ይሆን የሚሉት ጥያቄዎች ኢትዮጵያውያንን እያወያዩ ነው፡፡

## የሙስሊሞች ጥያቄ ወደአብዮት ያመራ ይሆን?

ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በታኅሳስ ወር/2004፣ በአወሊያ ትምህርት ቤት የጀመሩት ‹‹አል አሕባሽ›› የተሰኘ አስተምህሮት እየተጫነብን ነው ሮሮ - ቀጥሎም ‹መምህራኖቻችን አይባረሩ› እንቅስቃሴ… መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴዎች በመምረጥ፣ መጅሊሱ ይቀየርና ሕገ መንግሥቱ ይከበር እስከማለት ዘልቋል፡፡ ይሄው ጥያቄ የተመለሰበት መንገድ የመጅሊሱ አባላት በቀበሌ እንዲመረጡ ማድረግና ያንን የተቃወሙትን የኮሚቴ አባላት እና ሌሎችንም ማሰር እና በሽብርተኝነት መክሰስ ሲሆን… ይህ የመንግሥት እርምጃ ሙስሊሙን ማኅበረሰብ በማስቆጣት ተቃውሞዋቸውን በየሣምንቱ አርብ ከጸሎት በኋላ እየገለጹ ዓመት እንዲደፍኑ አድርጓቸዋል፡፡

በተቃራኒው በየከተማው እነዚህን ብሶተኞች የሚቃወሙ ሙስሊም ሰልፈኞችን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ደጋግሞ አሳየ፡፡ ብዙዎች ሰልፈኞቹን መንግሥት ያስተባበራቸው እንደሆኑ መገመት አልቸገራቸውም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰልፈኞች በሰልፉ ብዙም አልዘለቁበትም፤ በሌላ በኩል ከታሪክ እንደምንረዳው በደርግ ዘመን ‹‹የሃይማኖት መሪዎች የኢምፔሪያሊስቶችን አብዮት የሚያደናቅፍ ሴራ አወገዙ›› የሚል ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተው እንደነበሩ ሁሉ አሁንም ‹‹የእንትን መስኪድ ኢማሞች ‹አንዳንድ› ድብቅ ሴራ አጀንዳቸውን በሙስሊሙ ዘንድ ለማራመድ የሚፈልጉ … አወገዙ፡፡›› የሚለውን ዜና ከፕሮፓጋንዳ ለይቶ ማይት ስለማይቻል ነው፡፡

መንግሥት የሙስሊሞቹን ጥያቄ በአጭሩ መልስ የማይሰጠው እንደሚናገረው ‹‹አክራሪነትን›› ለመከላከል ብቻ ነው ማለት ያስቸግራል፡፡ ይልቁንም የመንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ ገብነት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያንም የውስጥ ለውስጥ አጀንዳ በመሆኑ (‹‹የቀድሞውን ጳጳስ የሕወሓት አባል/ደጋፊ ናቸው›› እስከማለት ድረስ) የሙስሊሞቹን ጥያቄ መመለስ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችንና ምናልባትም ሌሎችንም ፊት እንደመስጠት ይሆንብኛል ብሎ ሳይጠረጥር አይቀርም፡፡

የሆነ ሆኖ ምንም እንኳን መንግሥት የሃይማኖተኞችን ጥያቄዎች በጉልበት ቢደፈጥጥም (‹‹ምርጫውን በቀበሌ በማካሄድ››) ወይም የየሳምንቱን ጥያቄ እንዳልሰማ በማለፍ ‹‹ሰልችቷቸው እንዲተዉት›› ለማድረግ ቢሞክርም፤ እስካሁን ከተለመከትነው መገመት እንደምንችለው… እነዚህ ሰዎች ስትራቴጂያቸውን እየቀያየሩ ያላቸውን ሁሉ አማራጭ ወደመጠቀም አያመሩም ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡

በቅርቡ እንኳን ያሳዩት የቢጫ ካርድ ተቃውሞ ከእግርኳስ ጨዋታ ሕግ የተወረሰ ሲሆን እንደማስጠንቀቂያ ታይቷል፡፡ ቀጣዩ ቀይ (የማሰናበቻ) ካርድ እንደሚሆን ቢገመትም መቼ እና እንዴት ለሚለው ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም፡፡ ይሁን እንጂ ሙስሊሞቹ የቀይ ካርድ እርምጃቸውን ከጀመሩ ሕዝባዊ ተቃውሞ ከመስኪድና ከጸሎት ስብሰባ ውጪ ሊጠሩ እንደሚችል መገመት ቀላል ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ እርምጃ (ከመንግሥት ተገማች ምላሽ ጋር ተደማምሮ) አገሪቱን ወደአብዮት ሊመራት ይችላል ብሎ መጠርጠር ከባድ አይመስለኝም፡፡

ነገር ግን እንደምናስበው ይህ ዓይነቱ አብዮት በሒደቱም ሆነ በውጤቱ ቀላል አይሆንም፡፡ የሙስሊሞቹ አደባባይ መውጣት ጥያቄያቸውን ከሃይማኖታዊው ይልቅ ፖለቲካዊው ትርጉሙ ስለሚያመዝን (የመንግሥት አይቀሬ ሥልጣን ፈልገው ነው ፕሮፓጋንዳ ታክሎበት) ሙስሊም ላልሆነው የኅብረተሰብ አካል የጥርጣሬ መንፈስ ሊፈጥር እና አንዱ በሌላው ላይ የመቃወም አቋም ሊያስይዝና ለፖለቲካውም ለማኅበረሰቡም የማይበጅ ነገር ሊፈጠር ይችላል፡፡

## እንደመደምደሚያ

ሃይማኖቶች ለአብዮት የሚያበረክቱት እና ማበርከት የሚችሉት ሚና አሌ የሚባል ባይሆንም፤ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ አብዮታዊ ለውጥ ይመጣ ዘንድ ከታሰበ የአገሪቱን ብዝኃ ሃይማኖትነት ማገናዘብ የሚችል ገለልተኛ/ሴኩላር ለውጥ ቢመጣ እመርጣለሁ፡፡ የሃይማኖተኞች ወይም ሃይማኖትን ግብ ያደረጉ አብዮተኞች ሚናም ሃይማታዊ/አምልኮአዊ ጣልቃ ገብነት ከመቃወም ወይም የማምለክ/አለማምለክ ነጻነትን (ማለትም በጠቅላላው ሥርዐት ውስጥ የእምነት ነጻነት ሥርዐቱን ለይቶ /ምን ያህል ነጥሎ ማየት ይቻላል የሚለውን ለውይይት በመተው/ ለማስተካከል) ከመሻት በላይ የተሻገረ መሆን የለበትም፡፡ በጥቅሉ ግን ሃይማኖተኞች እንደዜግነታቸው የሥርዐት ለውጥን መሻት ብቻ ሳይሆን የለውጡ ዋነኛ ተዋናይ የመሆን መብቱም ግዴታውም አለባቸው፡፡

# 1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት እና የነጻ ማኅበራት ፋይዳ

በ2004 የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ‹‹መጅሊስ ይቀየር›› ጥያቄ መቀስቀሱን ተከትሎ ኦሮሚያ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ዩንቨርስቲዎች በአንዱ ውስጥ በጉዳዩ ዙሪያ ለመወያየት ስብሰባ ተጠራ። ስብሰባው ላይ የዩንቨርስቲው የተማሪዎች ኅብረት ፕሬዚደንት የነበረው የእስልምና እምነት ተከታይ እጁን አውጥቶ ‹‹ትላንትና ምንም ነገር እንዳልናገር ከዩንቨርስቲው አስተዳደር ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኝ ነበር፥ ሆኖም…›› ብሎ ሐሳቡን ተናገረ፤ ያ የዩንቨርስቲ የተማሪዎች ኅብረት ፕሬዚደንት በማግስቱ ከኃላፊነቱ ተነሳ።

ይህ በኢሕአዴግ ዘመን ያለውን ግለሰባዊም ሆነ ቡድናዊ መብት ደረጃ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ምሳሌ ሲሆን በዚሁ ተንደርድረን፣ በ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት ጉልህ ሚና የተጫወቱትን ተመሳሳይ አካላት እንመለከታለን፤ ለመሆኑ እነዚህ ሕዝባዊ አካላት እነማን ነበሩ?

የ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት የኂላ ኂላ ገጠሬው ቢቀላቀለውም፣ በአብዛኛው የተመራው በከተማ ነዋሪዎች ነው ማለት ይቻላል። አንዳርጋቸው ጥሩነህ Ethiopian Revolution 1974-1987፡ A transformation from an aristocratic to a totalitarian autocracy (1993) በተሰኘው ጥናታቸው ላይ በአብዮቱ ዋና ተዋናይ የነበሩትን አካላት ከነ[ተቀራራቢ] ቁጥራቸው ዘርዝረዋቸዋል።

*“የኢትዮጵያ ንግድ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን 80,000 አባላት፤ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር (አባላቱ የመንግሥት ሠራተኞች ነበሩ፤) ብዛታቸውም 18,000 ነበር። ከመንግሥት ሠራተኞቹ በተጨማሪ 10,000 የምድር ጦር እና 30,000 የፖሊስ አባላትን ጨምሮ 55,000 የሠራዊት አባላትን የሠራተኛ ማኅበሩ ያካትታል።*

*በወቅቱ የተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር 70,000 ነበር፤ ከነርሱ ውስጥ 6,000ዎቹ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ናቸው፤ (በተጨማሪም በውጭ ሃገራት የዩንቨርስቲ ጥናት ላይ የነበሩ ሌሎች 2,000 ተማሪዎች ነበሩ)።*

*“ስለዚህ ከጠቅላላው 3 ሚሊዮን የከተማና ከተማ ቀመስ በታዎች ነዋሪ ሕዝብ ውስጥ ፖለቲካዊ ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ የነበሩት የመንግሥት ሠራተኞች፣ ወታደሮች እና ተማሪዎች ከ300,000 የማይበልጡ የከተማ ነዋሪዎች ነበሩ።”*

በየማኅበራቱ የታቀፉት እና ፖለቲካዊ ንቁ የነበሩት ሕዝቦች ቁጥር ከጠቅላላው የከተማ ሕዝብ አንጻር እንኳን ሲታይ ከ10 በመቶ የማይበልጡ እና በወቅቱ ከነበረው ጠቅላላ የሕዝብ ብዛት አንጻር ከ1 በመቶ የማይበልጡ ቢሆንም አብዮቱን ማስነሳት ችለዋል። አብዮቱ ከተማ እና ኮርፖሬታዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሳይወሰን አገር አቀፍ እንዲሆን በማድረግና ስር ሰድዶ የነበረውን ንጉሣዊውን ስርዓት በማንገጫገጭ ለማስወገድም ችሏል። ይህ ሊሆን የቻለው በተለያዩ ማኅበራት ጥንካሬ ነው እንጂ በተሳታፊዎቹ ቁጥር ብዛት አይደለም ብዬ አምናለሁ። በዝርዝር እንመልከተው፡-

## የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮ)

*ኢሠማኮ የተለያዩ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ለጥቅማቸው ለመቆም ያቋቋሟቸው ማኅበራት አቃፊ ኮንፌዴሬሽን ነበር።*

ኢሠማኮ በ1965፣ 167 የሠራተኞች ማኅበራትን ያቀፈ ሲሆን ከ80,000 በላይ አባላት ነበሩት። ኮንፌዴሬሽኑ በ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት ወቅት ውስጥ የነበረው ሚና ከየትኛውም አካል የጎላ ነበር። ኮንፌዴሬሽኑ በመጀመሪያ የሠራተኞቹን ጥቅም ያስጠብቃሉ ያላቸውን (የደሞዝ ጭማሪ፣ የሠራተኞች የመደራጀት መብቶች) እና ሌሎችም (5 ያክል) ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ይዘት ያላቸውን - ብዙ ምንጮች እንደሚሉት 16 (አንዳርጋቸው ጥሩነህ 17 ነው ይላሉ) ጥያቄዎች አነሳ። መንግሥት ይህንን ጥያቄያቸውን ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ ጠቅላላ አድማ ለጥር 30/1965 እንደሚጠራም አስጠነቀቀ። የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን ከአድማው ቀነ ቀጠሮ አንድ ቀን ቀድመው ጥያቄዎቹ ከሦስት እስከ ስድስት ወር በሚደርስ ጊዜ መልስ እንደሚያገኙ ብቻ ተናገሩ። በማግስቱ (የካቲት 1/1965 /ማርች 8/) ግን እስከ መቶ ሺሕ የሚጠጉ ሰዎች የሥራ ገበታቸው ላይ ባለመገኘት የሥራ ማቆም አድማ አደረጉ። የታሪክ ጸሐፊዎች በዕለቱ ፀጥ-ረጭ የማለቱን ገጠመኝ የሚያስታውሱት በተለይ አዲስ አበባ ‹‹ሸባ ሆነች /በእንብርክኳ ሄደች/›› በማለት ነው።

በወቅቱ ኮንፌዴሬሽኑ የገጠመው ችግር አብዛኛዎቹ ሠራተኞች በአድማው ከሦስት ቀን በላይ መሳተፍ አለመቻላቸው ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት አብዛኛዎቹ ሠራተኞች ኑሯቸው ከእጅ ወደአፍ ስለሆነና ሥራችንን አጥተነው እንቀራለን የሚል ፍራቻ ስለነበረባቸው ነበር። ነገር ግን ለጥያቄዎቻቸው በሙሉ መልስ የሚሰጥ ስምምነት የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው እንዲፈርሙ ማስገደድ አላቃታቸውም። እንዲያም ሆኖ የአድማው ትልቅ ግብ ተደርጎ እስከዛሬም የሚቆጠረው እንቅስቃሴው ሌሎች በርካታ አድማዎችን እና መንግሥትን ለለውጥ የሚያስገድዱ እበያዎችን ማበረታቱ ነው።

## የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር (ኢመማ)

ኢመማ ከ60 ዓመት በላይ ያስቆጠረ አንጋፋ ማኅበር ነው። ይሁን እንጂ እንደንጉሡ ዘመን ማብቂያ ሰሞን አቅሙ-ትልቅ ማኅበር ሆኖ አያውቅም። በ1965፣ 18,000 ያህል አባላት ነበሩት። ማኅበሩ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ቢያንስ ለስድስት ዓመታት ያክል በደሞዝ ጭማሪ እና የደሞዝ ስኬል ጉዳይ ሲነታረክ ከርሟል። አንዳርጋቸው ጥሩነህ እንደጻፉት የመምህራን ማኅበሩ የካቲት 11/1966 ታክሲዎች የነዳጅ ጭማሪን ተከትሎ በጠሩት አድማ ላይ ተደምሮ የትምህርቱን ሥርዓት በዝምታ ሊያውለው ወሰነ። ማኅበሩ ጥያቄዎቹን ከመምህራን (የደሞዝ እና የሴክተሩ ክለሳም) በላይ እንዲሆን፤ የሰላማዊ ሰልፍ መብት እንዲከበር፣ የደሞዝ ወለል እንዲበጅ፣ ለፋብሪካ ሠራተኞች የደሞዝ ጭማሪ እንዲደረግ፣ ለኢንዱስትሪ ሠራተኞች የጡረታ መብት እንዲከበር፣ ሠራተኞን የማባረሪያው ሕግ እንዲስተካከል እና ሌሎችንም ጥያቄዎችን አነገበ።

የመምህራን ማኅበሩ የደሞዝ ስኬት ይሻሻል ጥያቄውን ከአብዮቱ 6 ዓመት ቀድሞ ያነሳ ቢሆንም መልስ ማግኘት ባለመቻሉ ትግሉን አጠናክሮ፣ የመምህራንን ብቻ ሳይሆን የሌሎችም ሠራተኞች መብቶችን የሚያስከብሩ እና ሌሎችም ፖለቲካዊ ጥያቄዎችን አንግቦ ተጠናክሮ በመንቀሳቀስ የሌሎቹን ማኅበራት ዓይን ለመግለጥ መቻሉ እንደስኬት ይቆጠርለታል።

## የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ማኅበር (USUAA)

የኢትዮጵያ ዩንቨርስቲዎች ማኅበር (ከቀኃሥ - ዩንቨርስቲ በተጨማሪ የሌሎች ሁለት ራስ ገዝ አካባቢዎች ዩንቨርስቲዎችን የሚጨምር ሲሆን) የነበረው አቅም ግን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማኅበር ያነሰ ነበር። ሆኖም የተማሪዎች ሚና ጉልህ ነው በሚል እስከዛሬም ‹‹የተማሪዎች እንቅስቃሴ›› ውጤት ሆኖ የሚታወሰው የ1966ቱ አብዮት በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ማኅበር (ESUNA) እና የኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ማኅበር በአውሮፓ (ESUE) የታገዘ ነበር።

የዩንቨርስቲ ተማሪዎች እንቅስቃሴ እስካሁንም ድረስ በተቃዋሚ እና ገዢው ወገን ያሉትን አንጋፋ ፖለቲከኞች ያነሳሳ እና ለአብዮቱ ምልከታዎችን ለግሶታል። አንጋፋዎቹ የ‹‹መሬት ላራሹ›› እና የብሔሮች እኩልነት ጥያቄ ቦታ የተሰጣቸው ያኔ - በተማሪዎቹ አማካይነት ነው። USUAA (በ1966 መባቻ ላይ የታገደባቸውን) '*ስትራግል*' የተሰኘ ጋዜጣ በማሳተም የብሔሮች መብት እስከመገንጠል ድረስ የመዝለቅ ጥያቄዎችን ሳይቀር አንስቷል። መኢሶን፣ ኢሕአፓንና ሕወሓትን የመሰሉ ለተከታዮቹ ረዘም ላሉ ዓመታት ተጽዕኖ ፈጣሪ ፓርቲዎችም የተፈጠሩትም ከተማሪዎች እንቅስቃሴ ነው።

በተማሪዎቹ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ጉልህ ሚና ኖሮት ነገር ግን ብዙም ያልተወራለት ‹‹Crocodiles Society›› (የአዞዎቹ ማኅበረሰብ) የሚባለው ነው። ይህ ቡድን የዩንቨርስቲውን እንቅስቃሴ ያጋግሉ የነበሩትን ‹‹ዜና እና አስተያየቶች›› የታተሙበትን በራሪ ወረቀቶች የማዘጋጀት/የማሰራጨት ሚና የነበረው ሲሆን ‹‹መሬት ላራሹ›› የሚለው አጀንዳም የፈለቀው ከዚያ እንደሆነ የባሕሩ ዘውዴ Documenting the Ethiopian Student Movement: An Exercise in Oral History ይጠቃቅሳል።

የተማሪዎች ኅብረት ለአብዮቱ መፋፋም የሐሳብ መዋጮ፣ እና የፓርቲ መመስረት የመጨረሻው ውጤት ቢሆንም የትምህርት ክፍለጊዜዎችን ክፍል ባለመግባት እና የተቃውሞ ሰልፍ በማስነሳትም ጭምር የወቅቱ ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ ተግተው ነበር።

ይሁን እንጂ የተማሪዎቹ እንቅስቃሴም ፈተና ነበረበት። የወቅቱ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ኅብረት ፕሬዚደንት ጥላሁን ግዛው ባልታወቁ ሰዎች (በዝግታ በምትነዳ መኪና ውስጥ በተተኮሰ ጥይት) ተገድሏል። ጆን

ያንግ Peasants Revolution of Ethiopia በተባለ መጽሐፋቸው ጥላሁን ‹‹ከገንጣዮች እንቅስቃሴ ጋር ትተባበራለህ›› በሚል ዩንቨርስቲውን ለቅቆ እንዲወጣ ማስጠንቀቂያ እንደደረሰው ገልጾ ነበር ሲሉ ጽፈዋል፡፡

ከነዚህ በተጨማሪም የ5 ሣንቲም የነዳጅ ዋጋ ጭማሪን ተከትሎ የተጠራው የታክሲ ማቆም አድማም ለአብዮቱ መጧጧፍ እና ለንጉሡ ስርዐት የኢኮኖሚ ፈተና ለመሆን በቅቷል፡፡

## ትላንት ይማረኝ?

ደርግ ሁሉንም ማኅበራት በራሱ መልክ ለማዋቀር ሞክሮ ነበር፡፡ የነጋዴዎች፣ የከተሜዎች፣ የገበሬዎች... እየተባለ ማኅበር በማኅበር አገሪቱን አጥለቀለቃት፡፡ አንዳርጋቸው ከላይ በጠቀስነው ጥናታዊ ጽሑፋቸው "ከሞላጎደል ሁሉም ዜጋ አንዱ፣ ወይም ሌላኛው ወይም ከአንድ በላይ የሆነ ማኅበር/ራት ውስጥ መታቀፉ የማይቀር ነበር፡፡ ዕድሜዋ ከ18 እስከ 30 የሚደርሳት ሴት ለምሳሌ የገበሬች ወይም የከተሜዎች ማኅበር (እንደምትኖርበት ቦታ ሁኔታ) እና የወጣት አብዮተኞች ማኅበር አባል ትሆናለች፡፡ እንዲሁም፣ የነጋዴዎች፣ የነርሶች፣ የዶክተሮች ብሎም የፓርቲ አባልም ልትሆን ትችላለች፤" በማለት የደርግን ዘመን ማኅበር የረከሰበት ቢሆንም ሁሉም የመንግሥታዊ ስርዐቱን ከማስፈፀም በላይ ፋይዳ እንዳልነበራቸው አመላክተዋል፡፡

በኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥት ደግሞ የተለየ አጨዋወት እናገኛለን፡፡ ኢሕአዴግ በጥቅሉ በመደራጀት (communalism) ያምናል፤ ሆኖም እያንዳንዱን ማኅበር የመቆጣጠር ኃላፊነቱን ግን ካድሬዎቹ እንዲወስዱት ይፈልጋል - እስካሁን ባለው ሁኔታ ተሳክቶለታልም፡፡

የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ማኅበር በ1993 የገጠመው የነጻነት ማጣት ችግር እና የዩንቨርስቲው ቀውስ እስከዛሬ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ በወቅቱ የዩንቨርስቲ ተማሪዎቹ 4 ጥያቄዎችን በማንሳት ያመጹ ቢሆንም ከወቅቷ ሚኒስቴር ያገኙት የመጨረሻው መልስ ‹‹ካልፈለጋችሁ ግቢውን ጥላችሁ ውጡ›› የሚል ነው፡፡ ተማሪዎቹ በእምቢተኝነት አድማቸውን በመቀጠላቸው ደግሞ በአድማ በታኞች ብዙዎች ሲጎዱ ለሞት የተዳረጉም እንዳሉ በወቅቱ የኢትዮጵያ ሰብኣዊ መብቶች ጉባኤ ዝርዝር መግለጫ ማውጣቱ ይታወሳል፡፡ የዩንቨርስቲው ማኅበር በኢሕአዴግ ዘመን ‹ሕሊና› የተሰኘ ጋዜጣ ሦስት ጊዜ ያህል ብቻ ያሳተመ እና ያሰራጨ ቢሆንም ከዚያ በኋላ ታግዷል፡፡ አሁን ሁሉም ሊባል በሚችል ሁኔታ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ማኅበራት ፕሬዚደንቶች በውስጠ ታዋቂነት ካድሬዎች ናቸው፡፡

የመምህራን ማኅበሩን የነጻነቱ ዘመኑ በ1999 ከማብቃቱ በፊት ፕሬዚደንቱ የነበሩት ታዬ ወልደሰማያት ታስረው ሲፈቱ ከአገር ተሰደዋል፡፡ የግጭቱ መንስኤ ነው የሚባለው መንግሥት የሚያምነውን ማኅበር አዲሱ ኢመማ በማለት ለመፍጠር መሞከሩ ነው፡፡ ጉዳዩ ፍርድቤት የደረሰ ቢሆንም መንግሥት ግን ዕውቅናውን ለአዲሱ ሰጥቶ የቀድሞውን አፈራርሶታል፡፡ የመምህራን ማኅበሩ የውድቀት ምልክት ነው ብዬ እዚህ ልፈርድበት የሚያስደፍረኝ በ2004 የመምህራን ደሞዝ ጭማሪ ጥያቄ ለዲፕሎማ ምሩቅ 31 ብር፣ ለዲግሪ ምሩቅ ደግሞ 73 ብር እንዲሆን ሲወሰን ማኅበሩ - ውሳኔውን ማድነቁን በማጣቀስ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ማኅበራት የቆሙለትን አካል ጥቅም በማስጠበቅ ፈንታ የመንግሥትን ፊት እያዩ ማዳነቅ ወይም ማራከስ ሲይዙ ፋይዳቸው ዋጋ ያጣል፡፡

በሌላ በኩል በሕግ ባይከለከልም ሌላ የመምኅራን ማኅበር ለማቋቋም እንደቀድሞው ምቹ የፖለቲካ ሁኔታ እንደሌላ የሚናገሩም አሉ፡፡ The Status of Governance, Academic Freedom, and Teaching Personnel in Ethiopian Higher Education Institutions በሚል በFSS ርዕስ በተደረገ ጥናት ላይ ነጻ የመምህራን ማኅበር ለማቋቋም ማሰብ በጅማ ዩንቨርስቲ መምህራን ‹‹*unattainable luxury*›› ተብሎ ሲገለጽ የባሕር ዳር ዩንቨርስቲ ተወያዮች ደግሞ ‹‹*You never think of forming teachers' association since the political environment is complex and ambiguous*›› በማለት የመምህራን ማኅበር ማቋቋምን እንደተአምር ገልፀውታል፡፡ ይህንኑ በሚያጠናክር መልኩ ያለፈውን ከመፍረሱ በፊት እና አዲሱ እየተቋቋመ ሳለ የነበራቸውን አቋም ሲተቹ፣ አሰፋ ፍስሐ የተባሉ ጸሐፊ Ethiopia's Experiment in Accommodating Diversity: 20 Years' Balance Sheet ባሉት መጣጥፋቸው ላይ ‹‹ሁለት የመምህራን ማኅበራት አሉ፤ አንዱ ገዢውን ፓርቲ ሌላኛው ተቃዋሚዎችን ይደግፋሉ›› በማለት ከፖለቲካ አጀንዳ የፀዱ (ነጻ) እንዳልሆኑ መስክረዋል፡፡

አዲስ አበባ የወጣቶች ማኅበር አላት፤ የወጣቶቹ ማኅበር ከኢሕአዴግ ደጋፊዎች ወጣቶች ሊግ የሚለይበት አንዳችም ባሕሪ የለውም፤ የቀድሞ የወጣቶች ማኅበሩ ፕሬዚደንት የነበሩት አቶ ታጠቅ አሁን ሁነኛ ሹመት

በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የአሁኖቹም ‹‹ወጣትነታቸው›› ሲያልፍበት ይሾማሉ፡፡ ማኅበራቱ የመንግሥትን ሥርዐት መደገፋቸው እንደጥፋት ላይቆጠር ይችላል፤ ሆኖም በመንግሥታዊ ሥርዐቱ ውስጥ የሚወክሏቸውን የኅብረተሰብ አካላት ጥቅም በሕጉ ውስጥ በአግባቡ ካላስጠበቁ ቅቡልነት ያሳጣቸዋል፡፡ አሁን እየሆነ ያለውም ይኸው ነው፡፡

የሴቶች ማኅበርም አለ፣ ከኢሕአዴግ ደጋፊ የሴቶች ሊግ የሚለይበት የለም፤ በጥቅሉ ሁሉም ማኅበር (የንግዶቹን ጥቃቅን እና አነስተኛ ማኅበራት ጨምሮ) በኢሕአዴግ እና በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ክበብ ውስጥ የተቀነበቡ እና አሻግረው ማየት እንዳይችሉ ተደርገው የተሠሩ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሌሎቹንም በገለልተኛ ወገኖች የሚመሠረቱ ማኅበራት ካድሬዎች በግራም በቀኝም ብለው የፕሬዚደንትነቱን ስፍራ ይቆናጠጡ እና የመንግሥትን ሕልም ማስፈፀሚያ ያደርጉታል፡፡ በካድሬዎች የማይመሩትም የባለሙያዎች ማኅበራት ሳይቀሩ ኢሕአዴግን ላለማስቀየም ወይም ለማኅበሩ ሕልውና ሲሉ እውነትን ለመናገር ከመቆጠብ ጀምሮ የሠሩትን ጥናት ውጤት ለሕዝብ ይፋ ሳያደርጉ የመደርደሪያ ማሞቂያ አድርጎ እስከማቆየት ድረስ ይዘልቃሉ፡፡ በጥቅሉ አሁንም ማኅበራት አሉ፤ ማኅበራቱ ግን እንኳን የሥርዐት መሻሻልና ለውጥ ሊጠይቁ ቀርቶ ቢሳሳትም ባይሳሳት መንግሥትን ከመደገፍ የተለየ ተግባር የላቸውም - የኔ መደምደሚያ ነው፡፡

366